ኢትዮጵያ ከአንድ ትውልድ በኋላ

የኢትዮጵያን ኤኮኖሚክስ አሶሴሽን ባዘጋጀው

“ርዕይ 2020” የውይይት መድረክ የቀረቡ ጽሑፎችና

አስተያየቶች

(ከ25ተኛ - 36ተኛው ‹‹ርዕይ 2020›› መድረክ የቀረቡ)

ህዳር 2002

ዋና አዘጋጅ

ጌትነት አለሙ

አዘጋጅ

ደምረው ጌታቸው

ኤዲቶሪያል ቦርድ

ጌትነት አለሙ

አለማየሁ ስዩም

አለሙ መኮንን

እዮብ ተስፋዬ

ገዛኸኝ አየለ

ኣሳቅ ዲዋን

ዲዛይን

ራሄል ይልማ

እና

ሃናን ተፈራ

© መብቱ ለኢትዮጵያን ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

ስለመፅሐፉም ሆነ ስለማህበሩ ጥያቄ ወይም መረጃ የምትሹ አድራሻችን የሚከተለው ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር
ፖ.ሣ.ቁ. 34282
ስልክ፤ 251-1-645 3200
ፋክስ፤ 251-1-645 3020
ኢ-ሜይል፤ eea@ethionet.et
ድህረ-ገጽ፤ www.eeaecon.org

ISBN 978-99944-54-11-2

ማውጫ

መግቢያ..... vi

አርብቶ አደር እና ልማት በኢትዮጵያ.....1

ሰሎሞን ደስታ

በአቶ ሰለሞን ደስታ ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት.....18

አያሌው ገብሬ

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ሚና.....27

ተመስገን አክሊሉ

መንገድና ልማት በኢትዮጵያ.....57

በቀለ ንጉሴ

በአቶ ተመስገን አክሊሉ ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት.....77

ዓቢይ ጽጌ.....77

በአቶ በቀለ ንጉሤ ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት.....92

አሕመድ ሳላህ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና ልማት በ2020.....97

ሥርግው ገላው

በአቶ ሥርግው ገላው ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት.....131

በላይ መኮንን.....131

በአቶ ሥርግው ገላው ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት.....144

በኩረትጉሃን አለም አታላይ

እስልምና እና ልማት በኢትዮጵያ.....149

መሐመድ አሕመድ ሸሪፍ

እስልምና እና ልማት በኢትዮጵያ **አስተያየት**.....159

አህመድ ሁሴን

እስልምና እና ልማት በኢትዮጵያ **አስተያየት**.....166

መሀመድ ሳላህ

የሲቪል ማህበራት ለኢትዮጵያ ዕድገት የሚኖራቸዉ አስተዋጽኦ.....171

ካሳሁን ብርሃኑ

በዶ/ር ካሳሁን ብርሃኑ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት.....185
ያቦወርቅ ኃይሌ
በዶ/ር ካሳሁን ብርሃኑ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት.....188
ፈለቀ ታደለ
የኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች የማሳካት ዕድል.....193
ጌታቸው አደም
በአቶ ጌታቸው አደም ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት.....234
ያቦወርቅ ሃይሌ.....234
በአቶ ጌታቸው አደም ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት.....238
ደግነት አበባው
ሙስና እና ልማት በኢትዮጵያ.....245
አሊ ሱሌይማን
በኮሚሽነር አሊ ሱሌይማን **ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት**.....258
መድህኔ ታደሰ
በኮሚሽነር አሊ ሱሌይማን **ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት**.....262
አማረ አስገዶም
የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) **ምንነት፤ የኢትዮጵያ የአባልነት እንቅስቃሴና የወደፊት** የልማት ተስፋ.....267
ሀብታሙ ታደሰ
የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት (EPAs): **የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁኔታ**.....291
አሚን አብደላ
በአቶ ሀብታሙ አበራ እና አቶ አሚን አብደላ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት.....306
ማሞ እስመለዓለም ምህረቱ
ሰላም እና ልማት በኢትዮጵያ ዛሬና ነገ.....311
መድህኔ ታደሰ
በረዳት ኘሮፌሰር መድህኔ ታደሰ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት 319
ካሣሁን ብርሃኑ

በረዳት ኘሮፌሰር መድህኔ ታደሰ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት322
ዘውድነህ በየነ ኃይሌ
የአየር ንብረት ለውጥና የካርቦን ንግድ በኢትዮጵያ.....329
ደስአለኝ መስፍን
የአየር ንብረት ለውጥና የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ተጽእኖዎችን የመቋቋምና የማለማመጃ እርምጃዎች በኢትዮጵያ.....341
አበበ ታደገ
በአቶ አበበ ታደገ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት.....357
አባቡ አናጌ
የሀገር መከላከያና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በኢትዮጵያ.....361
ገብረዊድቃን ገብረተንሣይ
በሌ/ጀ ገ/ዊድቃን ገ/ተንሣይ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት...387
መስፍን በነጋ
በሌ/ጀ ገ/ዊድቃን ገ/ተንሣይ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት...392
ያዕቆብ አርሳኖ

መግቢያ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ኢትዮጵያ ካለችበት የድህነት አረንቋ ወጥታ በእድገት እንድትራመድ እና ዜጎች በረጅም ጊዜ እይታ ውስጥ ስለአገራቸው የጋራ ርዕይ ጨብጠው የበኩላቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ "ርዕይ 2020" የሚል መድረክ በማዘጋጀት ተከታታይ ውይይት አካሂዷል።

የ "ርዕይ 2020" የውይይት መድረክን ለማዘጋጀት የተለያዩ መነሻ ምክንያቶች ቢኖሩት አንደኛው መጪውን ዘመን ጥርት ባለ እይታ የማየት ችሎታን ለማዳበር ነው። በተለይም በተመረጡ የውይይት ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ "ኢትዮጵያ ከ25 ዓመት በኃላ አሁን ባለው ሁኔታ ብትቀጥል የት ትደርሳለች? አገራችን ከ25 ዓመት በኃላ የት ደርሳ፤ ምን ሆና ልናያት እንፈልጋለን ? ይህንን ምኞት እውን ለማድረግ ከዛሬ ጀምሮ ምን መደረግ አለበት?" በሚሉ ጭብጦች ላይ የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ያለመ ነው። ከዚህም ሌላ በነዚህና ከነዚህ ጋር ተዛማጅ ለሆኑ ጭብጦች የመፍትሔ ሃሳቦችና የተግባር መርሐ ግብሮች መመንጨት ያለባቸው የችግሩ ሰለባ ከሆነው ሕዝብ መሆን እንዳለበት ተሰምሮበታል። ለችግሮቻችን መፍቻ ተጠያቂው መንግሥት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ግለሰብ ሕይወቱን የመለወጥ ኃላፊነት የራሱ መሆኑን ተገንዝቦ አስፈላጊውን የዜግነት ግዴታ እንዲወጣ ማድረጉ ለፍትሃዊ ልማትና እድገት አማራጭ የሌለው መሆኑን በመረዳት ሕዝቡንም ለዚህ ጊዜ የማይሰጥ ጉዳይ ማንቀሳቀስና ማነቃቃት ተገቢ ሆኖ መገኘቱ ነው የ "ርዕይ 2020" የውይይት መድረክ የተዘጋጀው።

አቀራረቡ በ"ርዕይ 2020" የውይይት መድረክ ላይ በተለያየ ሙያና የሥራ መስክ ከፍተኛ እውቀትና ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውን በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ፅሁፍ እንዲያዘጋጁና ለመድረኩ ታዳሚዎች እንዲያቀርቡ ተደርጓል።

በተጨማሪም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ከፍተኛ እውቀትና ልምድ ያላቸው ሰዎች ተመርጠው ፅሁፉ አስቀድሞ ተሰጥቷቸው ትችት እንዲያዘጋጁና ለታዳሚዎች እንዲያቀርቡ ተደርጓል። በውይይት የተስተናገዱ ሃሳቦች

በአዳራሽ ብቻ ተወስነው እንዳይቀሩ እና መላው ሕዝብ እንዲወያይበት ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ እንዲመቻች ጥረት ተደርጓል።

ከላይ እንደተገለጠው ወይይቶቹ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ 36 የ "ርዕይ 2020" የውይይት መድረኮች አቅራቢዎችና በተጋባዥ እንግዶች የጎላ ተሳትፎ እጅግ በተሳካ ሁኔታ ተዘጋጅቷል። ውይይቱ በአዳራሽ ተወስኖ እንዳይቀር "ልሳነ ኢኮኖሚክስ" በተባለው የማኅበራችን ወርሃዊ መፅሔት ላይ ታትሞ እንዲሰራጭ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ "ልሳነ ኢኮኖሚክስ" ሕትመቶችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ በፅሁፍ መልክ ማሳተሙ ለተጠቃሚዎች የተለየ ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ ስለታመነ በ1996 ዓ.ም የመጀመሪያው መፅሐፍ 12 በ "ርዕይ 2020" የውይይት ሃሳቦችን ይዞ እንዲታተም ተደርጓል። ሁለተኛው መፅሐፍ ደግሞ በ1999 ዓ.ም 12 የ "ርዕይ 2020" የውይይት ሃሳቦችን ይዞ እንዲታተም ተደርጓል። ይህ መፅሐፍ 3ተኛውና ተከታይ መፅሐፍ ሲሆን ከ25ተኛው እስከ 36ተኛው በ "ርዕይ 2020" መድረክ ላይ የቀረቡትን የውይይት ሃሳቦች የያዘ ነው።

በመጨረሻ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ በተካተቱ 12 የውይይት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በአቅራቢነት እና ሃሳብ በመስጠት የተሳተፉትን እንዲሁም በውይይቱ ወቅት አስተያየትና ጥያቄዎችን በማቅረብ የተሳተፉ የ"ርዕይ 2020" ታዳሚዎችን በማህበራችን ስም ለማመስገን እወዳለሁ። ይህ የመፅሐፍ ይበልጥ ተነባቢ እንደሚሆንና የያዛቸው የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች በሕብረሰቡ መካከል በቂ ግንዛቤ እንደሚፈጥር ያለኝን እምነት እገልፃለሁ።

መልካም ንባብ

ደምረው ጌታቸው
የኢትዮጵያን ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ጽ/ቤት ኃላፊ

አርብቶ አደር እና ልማት በኢትዮጵያ[1]

ሰሎሞን ደሰታ[2]

1. መግቢያ

በዚህ ታላቅ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ስብሰባ ላይ ጥናታዊ የመወያያ ጽሑፍ እንዳቀርብ በመጋበዜ ከፍ ያለ ክብርና ደስታ ይሰማኛል። በዚሁ አጋጣሚ ዶክተር አሰፋ አድማሴ ባልደረባዬን ጌታቸው ገብሩን አግኝቶ «አርብቶ አደር እና ልማት በኢትዮጵያ፤ ርእይ 2020» በሚል ርእስ ጥናት ለማቅረብ እንዳስብ መልእክት ስለላከብኝ ከፍ ያለ ምስጋናየን አቀርባለሁ። በከፍተኛ ፍጥነት እየተለወጠ በሚሄድ፣ አንዳንድ ጊዜም ባልታሰበ አቅጣጫ ተጉዞ ካልታሰበ ውጤት ጋር በሚያገናኝ አሁን ባለንበት ዓለም ስለወደፊቱ መናገር ከባድ ሊሆን ይችላል ብዬ ሳመነታ፣ የቻልኩትን ያህል እንድሞክርና ጥናቱን ማዘጋጀት እንድጀምር ያበረታታኝ ዶ/ር ጌታቸው ነው። እንድጀምረውና ጥናቱን እንዳዘጋጅ ያደፋፈረኝን ዶክተር ጌታቸውን ማመስገን እፈልጋለሁ፤ ለጥናቱ ይዘትና ጥራትም ዋጋው ሊተመን የማይችል አስተዋጽኦ አድርጓልና።

በዛሬው ስብሰባ ላይ የንግግሬ ዋና ርእስ ስለሆነው፣ የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ስላሉበትና በ2020 ላይ ሊገኙ ስለሚችሉበት ሁኔታ ከመናገሬ በፊት ስለ አርብቶ አደር ምንነት፣ በሀገሪቱ ውስጥ በምን ያህል መጠን እንደሚገኝ፣ ለብሔራዊ ኢኮኖሚውም ዕድገት ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳለው በመናገር እጀምራለሁ። አስከትዬም ከዚህ ቀደም ስለነበሩትና አሁንም በመከናወን ላይ ስላሉት የፓስቶራል ልማት ሥራዎችና በነዚህ የልማት ሥራዎች ውጤት ላይ ተጽእኖ ስላደረጉት ፖሊሲዎች አጠቃላይ ገፅታ ያሉኝን ሐሳቦች እሰነዝራለሁ።

2. አርብቶ አደር ለኢኮኖሚ ዕድገት ያለው ረብ (ሚና)

አርብቶ አደር በብዛት በረሃማና ከፊል በረሃማ የሆነውን የዓለምን አንድ አራተኛ የመሬት ክፍል የያዘ ሲሆን በአሥር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የአርብቶ አደር ቤተሰቦች የሚተዳደሩበት ነው። ከነዚህም ውስጥ በመቶ የሚሆኑት የሚገኙት በአፍሪካ ውስጥ ነው። አርብቶ አደር የራሱ ልዩ ባህርያት ያሉት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና የመሬት አጠቃቀም ስርዓት ነው። በሰው ጉልበት ካልለማና ተፈጥሮ ካበቀለችው የዕፀዋት ዘር

[1] ሰኔ 30 ቀን 1998 .ዓ.ም የተካሄደ የርዕይ 2020 የውይይት መድረክ፡፡

[2] ዶክተር ሰሎሞን ደስታ የመጀመሪያ (የላይንስ ባችለር) ዲግሪያቸውን እ.አ.አ. በ1981 ዓ.ም. ከአለማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን እ.አ.አ. በ1987 ዓ.ም. ከሎንዶኑ የኒቨርሲቲ ዋይ ኮሌጅ፣ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በዩናይትድ ስቴትስ ከዩታ ስቴት ዩኒቨርሲቲ በ1999 አግኝተዋል። ጥናታቸውን የሠሩት "Range Land Resources Economics and Management in Borena" በሚል ርእስ ነው። በዓለም ባንክና በአፍሪካ ልማት ባንክ የሚደገፉ የተለያዩ የአርብቶ አደር ልማት ሮጅክቶችን ተግባራዊ በማድረግ ሥራ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣን ሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ ሠርተዋል። አሁን በዩታ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ጥናት ተባባሪ ባለሙያ በመሆን ይሠራሉ። በአርብቶ አደሮች የምርት ሥርዓት ላይ በተናጠልም፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆንም ብዙ ጥናታዊ ጽሑፎችን ደርሰዋል።

እየተመገቡ ከሚረቡ የቤት እንስሳት ምግብና ገቢያቸውን የሚያገኙ ሰዎች ኑሯቸውን የሚመሩበት ሁኔታና ሥልት አርብቶ አደር ይባላል (Sandford, 1983)። በአርብቶ አደር ስርዓት ውስጥ የእንስሳት ሀብት ምርት የሰዎች የኑሮ መሠረትም ዋስትናም ነው።
አርብቶ አደር በተለያዩ ሀገሮች ለሚገኙ ሀገሮች ብሔራዊ ገቢ በማስገኘትና የሥራ እድል በመክፈት፣ በእርሻ ምርቶች እና የሕዝቦችን የምግብ ፍላጎት በማሟላት ረገድ ትንሽ የማይባል አስተዋጽኦ ያደርጋል። ለመላው የዓለም ሕዝብ ምግብነት ከሚውለው የሥጋ ምርት ውስጥ 10 ከመቶውን የሚያቀርቡት እነዚሁ አርብቶ አደሮች ናቸው (Roger Blench, 2001)።

በኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች በጥቅሉ ከሀገሪቱ አጠቃላይ የመሬት ስፋት ሁለት ሦስተኛውን ያህል ሲይዙ፣ ከ12 - 15 በመቶ (ወይም ከ10 - 12 ሚሊዮን) የሚሆነው የሀገሪቱ ሕዝብ የሚኖሩባቸውና እና ከፍተኛ ቁጥር ላለው የእንስሳት ሀብት የሚረባባቸው ናቸው። በተለምዶ የግጦሽ መሬት በመባል የሚታወቁት እነዚህ ስፍራዎች በረሀማና ከፊል በረሀማ በሆኑ የሀገሪቱ ምሥራቅ፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ምእራብና ደቡብ ክፍሎች የሚገኙ ናቸው። በኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰቦች አባላት በአርብቶ አደርነት ይተዳደራሉ። በሕዝብና በእንስሳት ብዛታቸውና በክልላቸው ስፋት የታወቁት በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ሶማሌ፣ በሰሜን ምሥራቅ አፋር እና በደቡብ ቦረና ናቸው። ከነዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርነት የሚኖሩ፣ እንደ ሀመርና ገለብ፣ አርቦሬ፣ ዳሰነች፣ ወዘተ... የመሳሰሉ ብሔረሰቦች አሉ። አርብቶ አደሮች በትግራይ፣ በቤኒሻንጉልና በጋምቤላም ይገኛሉ። በሀገሪቱ ከሚገኙት አርብቶ አደሮች ስብጥር፣ በሶማሌ 59 በመቶ፣ በአፋር 29 በመቶ፣ በቦረና 10 በመቶ እና በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል እና ትግራይ ክልሎች 8 በመቶ ነው። በሀገሪቱ ከሚገኘው አጠቃላይ የእንስሳት ቁጥር 40 ከመቶ የሚሆኑት የቀንድ ከብቶች፣ 75 ከመቶ የሚሆኑት ፍየሎች፣ 25 ከመቶ የሚሆኑት በጎች፣ 20 ከመቶ የሚሆኑት የጋማ ከብቶች እና መቶ በመቶ ግመሎች የሚገኙት በአርብቶ አደሮች ዘንድ ነው (Coppock 1994)።

በኢትዮጵያ የሚገኙ አርብቶ አደሮች የእንስሳቱን ወተት በመጠጣትና ሥጋ በመብላት፣ እንዲሁም ከእነሱ በሚገኙት ውጤቶች እህሎችን፣ ሌሎች ነገሮችንና አገልግሎቶችን በመለወጥ (በመሸመት) ኑሯቸውን ይመራሉ። ሀገሪቱ በየአመቱ በህጋዊ መንገድ ወደ ውጪ ከምትልካቸው የቁም ከብቶችና የእንስሳት ውጤቶች ውስጥ ከ90 ከመቶ በላይ የሚሆኑት በዋናነት የሚገኙት ከቆላማው ክፍል የከብቶች፣ የበጎችና የፍየሎች እርባታ ነው። በተጨማሪም በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮች ያወጣሉ ተብለው የሚገመቱ ከብቶች ድንበር አቋርጠው ለዓለም አቀፍ ገበያ ይቀርባሉ፤ ይህ በይፋ በሚታወቁት ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ውስጥ አይካተትም (Coppock 1994)። ከዚህም በላይ በደጋማው የኢትዮጵያ አካባቢዎች ለጭነት ከሚያገለግሉ እንስሳት 20 በመቶ የሚሆኑት የሚገኙት ከአርብቶ አደሮቹ ክልሎች ነው (Coppock 1994)።

በኢትዮጵያ የሚገኙት የአርብቶ አደር አካባቢዎች ከፍተኛ የእንስሳት ሞት የሚያስከትል ተደጋጋሚ ድርቅ የሚያጠቃቸው ሲሆን፣ ይህም ብዙ ጊዜ አርብቶ አደርነትን ለአደጋ የሚያጋልጥ፣ በህዝቡም ላይ ረሀብና ሞት የሚያስከትል ይሆናል። ለምሳሌ፤ በ1973/74 የአርብቶ አደር ክልሎችን በተለይ ደግሞ የአፋርን ክልል ያጠቃው ድርቅ 72 ከመቶ የሚሆኑትን ከብቶች፣ 45 ከመቶ የሚሆኑትን በጎች፣ 34 ከመቶ የሚሆኑትን ፍየሎች እና 37 ከመቶ የሚሆኑትን ግመሎች ገድሏል። በ1983-5 እና 1990-2 በተከሰቱት ድርቆች በደቡብ ኢትዮጵያ የሚኖሩ የቦረና አርብቶ አደሮች ከ50 እስከ 60 ከመቶ የሚደርስ የእንስሳት ሀብታቸውን አጥተዋል (Desta et al. 2002, Coppock 1994)። የ1984-85 የቦረና ድርቅ 90 በመቶ የሚሆኑ ጥጆቻቸውን ገድሎባቸዋል (Cossins and Upton, 1988)። በቅርቡ በ2005/6 አፋርን፣ ቦረናንና ሶማሌን የመታው ድርቅ በእንስሳት ሀብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ ነበር። በአርብቶ አደር አካባቢዎች በብዛት የሚከሰቱ የሰውና የእንስሳት በሽታዎች ወረርሽኝ፣ ግጭትና የጸጥታ ችግሮች፣ እንዲሁም ሌሎች ውስጣዊ የሆኑ ጉዳዮች፣ ለምሳሌ፤ የሕዝብ ብዛት መጨመርና የግጦሽ መሬት ከከብት ርባታ ጋር ላልተያያዙ የኢንቬስትመንት ሥራዎች እንዲለቀቅ መደረጉ ከድርቅ ጋር ተጨማምረው የአርብቶ አደሮችን የኑሮ መሰረትና መረጋጋት፣ እንዲሁም ህልውናቸውን ስጋት ላይ የጣሉ አሁንም ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱና በቀላሉ ለመቆጣጠር ያልተቻሉ ችግሮች ናቸው። የኢትዮጵያ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ለድርቅ አደጋ የተጋለጡና ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያለባቸው ናቸው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ተገልለው ከሚኖሩት ሕዝቦች ከፍተኛውን ደራጃ የያዙት አርብቶ-አደሮች ናቸው። ሌላውን ትተን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ብቻ ስናሰላ እንኳን ትምህርትንና ጤናን የመሳሰሉትን ሕዝባዊ አገልግሎቶች በቀላሉ የማያገኙት እነሱ ናቸው፤ እንደ መንገድ፣ ስልክ፣ ገበያ፣ የመሳሰሉ የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙባቸው አካባቢዎች ናቸው። ረሀብና የምግብ እጥረት የተስፋፉባቸው፤ በብሔራዊ የፖለቲካ ሂደቱም ውስጥ ዝቅተኛ ውክልና ያላቸው ናቸው። የሚኖሩባቸው አካባቢዎች ተፈጥሮአዊ ይዞታ ለከብት እርባታና በሱው ላይ ለተመሠረተ ኑሮ የሚስማማ በመሆኑ በበረሀማውና በከፊል በረሀማው የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚኖሩትን አርብቶ አደሮች ኑሮ ለማሻሻልና ለሀገሪቱ እድገትም ሲባል አርብቶ አደርነትን በሀገሪቱ አጠቃላይ ብሔራዊ የልማት እቅድ ውስጥ ማካተት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ብዛት የያዙትንና በሀገሪቱ ሰፊ ቦታ ውስጥ የሚኖሩትን አርብቶ አደሮች ሳያሳትፉ በኢትዮጵያ ዘላቂና ሁሉን አቀፍ እድገት ማምጣት ጨርሶ የማይታሰብ ነው።

3. የከብት ሀብት ልማት አጠቃላይ ገፅታ በኢትዮጵያ

በመጪዎቹ አሥርተ ዓመታት የአርብቶ አደር ይዞታና ልማት በኢትዮጵያ ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ ጥርት ያለ አስተያየት ለመስጠት ጥቂት ቀደም ብለው የተከናወኑትና አሁንም በመከናወን ላይ ያሉት የአርብቶ አደር የልማት ሥራዎችና ከነሱ ጋር የተዛመዱ ፖሊሲዎች ምን ያህሉ የተሳካላቸው፣ ምንስ ያህሉ ያልሆነላቸው መሆናቸውን መመልከት በጣም አስፈላጊ ነው። የወደፊቱ የኢትዮጵያ የፓስቶራሊዝም ልማት፣ በከፊል ቀደም ብለው በተከናወኑትና አሁን እየተከናወኑ ባሉት ሥራዎች ጥንካሬ ላይ፤ በከፊል ደግሞ በስርዓቱ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችሉት የተለያዩ የልማቱን ዘርፎችና የልማቱን አቅጣጫ

በሚወስኑት በዛሬዎቹና በወደፊቶቹ ፖሊሲዎች ላይ የተመሠረተ ነው። ስለዚህ አርብቶ አደሮቹ የተነሱበት ደረጃና የሚከተሉት የልማት አቅጣጫ በመጪዎቹ ከ15-20 በሚደርሱት ዓመታት ውስጥ የሚደርሱበትን ደረጃ የሚወስኑ ናቸው። የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ አስተዳደር፣ ጸጥታና የተፈጥሮ አደጋዎችን የመሳሰሉት ውጫዊ ነገሮች የልማቱ እንቅስቃሴ በሚያስገኛቸው ውጤቶች ላይ የራሳቸው አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

ከበፊቶቹና አሁን እየተከናወኑ ካሉት ዋና ዋና የአርብቶ አደር ኢንቬስትመንቶች (ሁሉም ባይሆኑ) አብዛኞቹ የተጀመሩትና የገንዘብ ወጪያቸው የተሸፈነው የዓለም ባንክን በመሳሰሉ ዘርፈ ብዙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የአሜሪካ የልማትና ተራድኦ ድርጅትን (USAID) በመሳሰሉ በሁለት ወገኖች መካከል በተደረገ ውል መሠረት የሚንቀሳቀሱ (bilateral) ድርጅቶች ነው። በብዙዎቹ ኢንቨስትመንቶች ውስጥ እነዚህ ድርጅቶች 80 ከመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆነውን ወጪ በመሸፈናቸው አበዳሪዎቹ ወይም ረጂዎቹ በእነዚህ ፕሮጀክቶች ዲዛይን እና በአተገባበራቸውም ላይ የበላይነትን ይዘው አድራጊ ፈጣሪ ለመሆን የሚያስችል ዕቅምና ተሰሚነት አላቸው። በተጨማሪም ፕሮጀክቶቹ የሚጓዙበት አቅጣጫ፣ የሚያመርቷቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ምን ዐይነት መሆን እንደሚገባቸው በሚወሰንበት ጊዜም ጫና ያደርጉ ነበር።

በኢትዮጵያ አርብቶ አደሩ ያለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑ ቢታወቅም፣ እስከ 1960ዎቹ አጋማሽ ድረስ ለአርብቶ አደር አካባቢዎችና ለአርብቶ አደሮች የተሰጠው የልማት ትኩረት በጣም አነስተኛ ነበር። በ1950ዎቹ ማለቂያና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ የአሜሪካ የልማትና ተራድኦ ድርጅት (USAID) ከንጉሠ ነገሥቱ አስተዳደር ጋር በመተባበር በቦረና አካባቢ ለውኃ ሀብት ልማትና ለእንስሳት ገበያ ማእከሎች መገንቢያ የሚሆነውን ወጪ ሸፍኗል (Zere 1987)። የሆነ ሆኖ የኢትዮጵያ መንግሥት የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ለማልማት በሰፊው እንቅስቃሴ የጀመረው **የእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድ** ከተመሠረተበት ከ1964 በኋላ ነው።

የእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድ

የእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በእንስሳት ሀብት ዘርፍ ጠቀም ያለ ገቢ ለማግኘት የሚያስችለውን የልማት ስትራቴጂ ለማሳደግ የተቋቋመ ነበር። ቦርዱ በኢትየጵያ የአርብቶ አደር ልማት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በ1960ዎቹና በ1970ዎቹ በእንስሳት ሀብትና ሥጋ ቦርድ የተቀረጹትና የተጀመሩት የልማት ፕሮጀክቶችና በአተገባበራቸው ላይ የተደረጉት ጥናቶች እስከ 1980ዎቹ የመጨረሻ ዓመታት ለነበሩት የአርብቶ አደር ልማት ሥራዎችና ውጤቶቻቸው አስተዋጽኦ አድርገዋል። የእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድ የተጠቀመበት የልማት ሞዴል ዓላማዎቹ በእንስሳትና በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያተኮሩ፣ የአተገባበር መንገዳቸው ደግሞ በቴክኖሎጂ የሚመራ ነበር። በቦረና የሚገኘውንና ለመጀመሪያ ጊዜ በአሜሪካ የልማትና ተራድኦ ድርጅት (USAID) የገንዘብ ወጪ የተከናወነው የአሬሮ የግጦሽ መሬት የሙከራ ፕሮጀክት (ARPP) የቀረጻውና ተግባራዊነቱንም ሲከታተል

የነበረው ይኸው የእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድ ነበር። በገበያ ላይ የሚያተኩረው ሁለተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት (SLDP) የተጀመረው በእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድ ነበር። የእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድ ለብዙ ጥናቶች የሚያስፈልገውን የገንዘብ ወጪ ያቀርብ ነበር። እነዚህ ጥናቶች በጎላ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ለተለያዩ ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ ለመጠየቅ የጠቀሙ የልማት ፕሮጀክቶችን ዕቅዶች ለማዘጋጀት አገልግለዋል። እስከ 1980ዎቹ መጨረሻ የነበረው ሦስተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት የነዚህ ጥናቶች ውጤት ነበር። ባለፉት ሁለትና ሦስት አሠርታት በአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ውስጥ የተሳተፉት ቀደምት ባለሙያዎች የእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድን የልማት ሞዴል እንዲያጠናክሩ በሚያደርግ ሁኔታ በእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድ በራሱ ወይም በቦርዱ ፕሮጀክቶች ሥልጠና የተሰጣቸው ነበሩ።

በ1980ዎቹ መጨረሻ በቦረና ሲከናወን የነበረው የደቡብ የግጦሽ መሬት ፕሮጀክት፣ በ1990ዎቹ በክልል 5 በሚኖሩት ሶማሌዎች ዘንድ ሲከናወን የነበረው የደቡብ ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክት እና በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አስተባባሪነት በዓለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ እየተከናወነ ያለው የአርብቶ አደር ማኅበረሰብ ልማት ፕሮጀክት፣ (PCDP) በሚከናወኑባቸው ቦታዎች ነባራዊ ሁኔታ፣ በአቀራረጻቸውና ተግባራዊ በሚሆኑባቸው መንገዶች የእንስሳት ሀብትና የሥጋ ቦርድ ፕሮጀክቶች ከተኪያሄዱባቸው ሁኔታ ከፍ ያለ የአቅጣጫ ለውጥ የታየባቸው ነበሩ። በፕሮጀክቶቹ ቀረጻና አተገባበር ላይ አርብቶ አደሮቹንና ተቋሞቻቸውን የማሳተፍ ሙከራዎች ተደርገዋል። ከዚህ በታች የየልማት ፕሮጀክቶቹ አጫጭር መግለጫዎች ቀርበዋል።

የአሬሮ የግጦሽ መሬት የሙከራ ፕሮጀክት

የአሬሮ የግጦሽ መሬት የሙከራ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ሰው ያልሰፈረበት ወይም የማይታረስ መሬት በመንግሥት ባለስልጣናት ዘንድ ባለቤት የሌለውና የመንግሥት ሀብት ተደርጎ በሚቆጠርበት በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የተጀመረና በተግባር ላይ የዋለ ነበር። የአሬሮ የግጦሽ መሬት የሙከራ ፕሮጀክት የቆየው ከ1965 እስከ 1975 ድረስ ነው (Zere 1987)። በቦረና ማኅበረሰቦች ውስጥ በያቤሎ ከተማ አካባቢ እና በአርሲ በአበርኖሳ ከተማ አካባቢ ይከናወናል ተብሎ የታሰበ ነበር። ፕሮጀክቱ የአርብቶ አደሩን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና ለገበያ የሚቀርቡትን እንስሳት ብዛት ለማሳደግ የታቀደ ቢሆንም አርብቶ አደሮቹ በከፍተኛ ጥርጣሬ ነበር ያዩት። አርብቶ አደሮቹ፣ በጊዜው በነበረው ሕግ መሠረት መሬታችንን መንግሥት ይቀማናል ብለው ፈርተው ነበር። የፕሮጀክቱ ዓላማ በያቤሎ አካባቢ በ2000 ካሬ ኪሎሜትር ቦታ ላይ የተለያዩ የተከለሉ የግጦሽ ቦታዎችንና የውሃ ማጠጫዎችን በማዘጋጀት በዙር (በተራ) በየግጦሽ ቦታዎቹ በማጋጥ የእንስሳት ሀብትን ምርታማነት ማሻሻል ነበር። ነገር ግን ከልማዳዊው የቦረና የንብረት ባለቤትነት መብት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ በግዴታ ተግባራዊ ማድረግ የማይቻል ነበር (Zere 1987)። በአንዳንድ ቦታዎች በፕሮጀክቱ የተገነቡ ትልልቅ የውሃ ማጠጫዎች ብዙ አርብቶ አደሮች በአካባቢው እንዲሰፍሩ በመሳባቸው የተነሳ መሬቱ አለመጠን ተግጦ በአንድ ወቅት ሣር የሞላበት የግጦሽ መሬት ተራቁቶ ዛፎች ብቻ ያሉበት ሆኗል (Coppock 1994, Desta 1996)። የአበርኖሳ ንኡስ ፕሮጀክት በንኡስ

ፕሮጀክቱ መሪዎችና በአካባቢው አምራቾች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት የተነሳ ከመጀመሩ በፊት አካባቢውን ለቆ እንዲሄድ ተገዷል።

ሁለተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት

ሁለተኛው የእንስሳት ሀብት ፕሮጀክት በ1973 ተጀምሮ እስከ 1981 ድረስ ቀጥሏል። ፕሮጀክቱ የተጀመረው በንጉሡ ዘመን ሲሆን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሆነው በደርግ ዘመን ነበር። ፕሮጀክቱ በሀገሪቱ የተቀናጀ የገበያና የእንስሳት ሀብት ማጓጓዣ (መንገድ) ስርዓትን መዘርጋት ዓላማው አድርጎ በመነሳት ለአምራቾቹ የተሻለ የገበያ እድል በመክፈት የእንስሳት ሀብት የገበያ አቅርቦትን ያሳድጋል ተብሎ ይጠበቅ ነበር (Zere 1987)። የእንስሳት ሀብት ማጓጓዣ መንገዶችና የገበያ ቦታዎች ተገንብተው ነበር፤ ነገር ግን አብዛኞቹ በሚያሳዝን ሁኔታ በ1977-8 በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል በተነሣው ጦርነት ወደሙ (Coppock 1994, Desta 1996)። ጦርነቱን ተከትሎ የተፈጠረው አለመረጋጋት በምሥራቅና በደቡብ የግጦሽ መሬቶች ላይ ይከናወን የነበረውን የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴ አደናቀፈው። ይህ ፕሮጀክት በ1981 ሲጠናቀቅ ጥቂት ገበያዎች ብቻ ነበሩ አገልግሎት የሚሰጡት። የእንስሳት ሀብት የማጓጓዣ መንገዶች ጨርሶ አገልግሎት አልሰጡም። የዚህ ፕሮጀክት ዋናው ድክመት ከአርብቶ አደሮቹና ከነጋዴዎቹ ጋር ምክክር አለመደረጉና ትኩረቱን የአርብቶ አደሮችን ኑሮ በማሻሻል ላይ ከማድረግ ይልቅ ከእንስሳት ሀብት ገቢ በማግኘት ላይ ማድረጉ ነበር። ለሁለተኛው የእንስሳት ሀብት ፕሮጀክት የሚውለውን ወጪ ይችል የነበረው የዓለም ባንክ ነበር።

ሦስተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት

ሦስተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት (TLDP)፣ ወይም አንዳንዶች ይጠሩት እንደነበረው፣ የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክት (RDP) የተቀረጸው ካለፉት ፕሮጀክቶች በተገኙት ልምዶችና በኢትዮጵያ ዋና ዋና የአርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ በተደረጉ የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥናቶች ላይ በመመሥረት ነበር። ሦስተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት (1975-1984) በረጅም ጊዜ የኢትዮጵያ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ታሪክ ውስጥ እንደ አንድ ትልቅ እርምጃ የታየ የመጀመሪያው መጠነ ሰፊ የአርብቶ አደርልማት ተግባር ነው። የዚህ ፕሮጀክት ጥናት የተካሄደው በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ሲሆን፣ በተግባር የዋለው በደርግ ዘመን ነው። ፕሮጀክቱ ሲከናወን የወጣው ወጪና ከእንስሳት ሀብት ኢንዱስትሪው ትርፍ የማግኘቱ አላማ በደርግ ዘመን ከነበረው ማርክሳዊ ፖሊሲ ጋር እንዲጣጣም ተደርጓል።

የፕሮጀክቱ ዓላማ በሥሩ ባሉት ሦስት ንኡሳን ፕሮጀክቶች ሦስት ሰፋፊ የሆኑ አካባቢዎችን ማልማትና መልሶ ማቋቋም ነበር። እነዚህ ሦስት ንኡሳን ፕሮጀክቶችና የተዘረጉባቸው ቦታዎችም፣ በደቡብ በቦረናና በጉጂ ዞኖችና በክልል 5 በሊበን ዞን የደቡብ የግጦሽ መሬት ልማት ክፍል (SORDU)፣ በሰሜን ምሥራቅ በአፋር ክልልና በትግራይ የጠረፍ ወረዳዎች የሰሜን ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ልማት ክፍል (NORDU)

እና በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ በሶማሌ ክልል የጂጂጋ የግጦሽ መሬት ልማት ክፍል (JIRDU) የሚባሉት ነበሩ። የፕሮጀክቱ ዓላማም በነዚህ ሦስት ንኡሳን ፕሮጀክቶች 203 ሺህ ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለውን አካባቢ ማልማት ነበር።

ሦስተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት ብዙ ከብቶች የማርባትን ልማዳዊ ወይም ነባር ስርዓት እንደገና በማዋቀር የእንስሳት ሀብት ምርታማነትን ማሳደግ፣ የገበያ አቅርቦትን መጨመር፣ የአርብቶ አደሩን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ከፍ ማድረግን ዓላማው ያደረገ ሰፊ እንቅስቃሴ ነበር። እዚህ ግብ ላይ ለመድረስ የታሰበው በእንስሳት ህክምናና በእንስሳት ሀብት የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን በመስጠት፣ የውሃና የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችን በማስፋፋት፣ ለገጠሩ ሕዝብ ስልጠና በመስጠት፣ በእንስሳት ሀብት ዘርፍ ውስጥ ኃላፊነት ያላቸውን ተቋማት አቅም በመገንባትና ተገቢ የሆኑ ጥናቶችን በማከናወን ነበር (RDP 1975)። በድርቁ ሳቢያ በአርብቶ አደር ስርዓቱ ላይ የተከሰቱ ጫናዎችን እንዲያስወግዱ ታስበው የተዘጋጁ የፕሮጀክቱ ሌሎች መርሐ ግብሮች ነበሩ። እነዚህም መርሐ ግብሮች ውሃ የማዳረስ መርሐ ግብርን፣ የከብት እርባታ ልማት መርሐ ግብርን፣ የከብት አድላቢዎች መርሐ ግብርንና የማርኬቲንግ መርሐ ግብሮችን ያካትታሉ (Zere 1987, World Bank 1991)። የከብት እርባታ ማሳው እቅድና የከብት ማድለብ መርሐ ግብሮች ዓላማ በድርቅ ከማለቃቸው በፊት ከብቶቹን ከግጦሽ መሬቱ ማንሳት ነበር። የከብት ማድለብ መርሐ ግብር ዓላማ የገበያ አቅርቦቱን በማፋጠን የእንስሳት ክምችት እንዳይኖር በማድረግ ሊከተል የሚችለውን የእንስሳት ሞት መቀነስ ነው። በአጠቃላይ የሦስተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት የረጅም ጊዜ ዓላማ ከብት አርቢዎች የከብቶቻቸውን ቁጥር ከግጦሽ መሬታቸው መጠንና አቅም ጋር ለማመጣጠን የሚያስችላቸውን አጠቃላይ የግጦሽ መሬት አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት የግጦሽ መሬትን ምርትና ምርታማነት እና የእንስሳት ሀብትን ማሳደግ ነው።

የሦስተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት እንቅስቃሴም በእርስ በርስ ግጭቶችና ከሶማሊያ ጋር በነበረው ጦርነት ተደናቀፈ። የፕሮጀክቱን ተግባራዊነት ያደናቀፉ ሌሎች ነገሮች በኢትዮጵያ ከካፒታሊስት ኢኮኖሚ ወደ ኮሚኒስት እዝ ኢኮኖሚ የተደረገውንም ለውጥ ይጨምራሉ (World Bank 1991)። በልማት ተግባሩ የተሰማሩት ወገኖች ስለአርብቶ አደሩና ስለአካባቢው ባሕርያት ያላቸው ዕውቀት አነስተኛ በመሆኑ የተነሣ፣ የአርብቶ አደሩን ባህላዊ ልምዶች ለመቀየር በፕሮጀክቱ የተደረገው ሙከራ የሦስተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት ከገጠሙት ችግሮች ዋነኛው ነበር። በመጨረሻም ፕሮጀክቱ የመልሶ ማዋቀርና የማሻሻል ግቦቹ ላይ መድረስ አልቻለም። የመሬት አጠቃቀም እቅድና የተሻሻለ የግጦሽ መሬት አያያዝ እቅዶች ጨርሶ በተግባር ላይ አልዋሉም። ነገር ግን በእንስሳት ሕክምና አገልግሎት በመስጠትና መሠረተ ልማት (የውሃ ልማት፣ መንገድ፣ ወዘተ...) በመገንባት ረገድ ጥሩ መሻሻል ታይቷል (World Bank 1991)። የሦስተኛውን የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት ወጪ የቻሉት የዓለም ባንክና የአፍሪካ ልማት ባንክ ነበሩ።

ከዚህ በላይ የተወያየንባቸው ሦስቱም ፕሮጀክቶች ሩቅ ያለሙና ማኅበረ-ባህላዊ ስርዓቱን በመለወጥ ምርትን ወደማፋጠን ያዘነበሉ ነበሩ (World Bank 1991, Desta 1996)። በአፍሪካ በ1970ዎቹና

በ1980ዎቹ እንደተጀመሩት ሌሎች ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች እነዚህም በሰዎች ኑሮ ላይ ያስከተሉት መሻሻል በጣም አነስተኛ ነበር። የዚህ ምክንያቱም አኪያሄዱ ከላይ ወደታች በመሆኑ የተነሣ፣ የከፊል በረሃማና የበረሃማ አካባቢ የአርብቶ አደር ስርዓት ግንዛቤ ማነስ፣ የባህላዊ ተቋማትን አቅም ዝቅ አድርጎ መመልከትና የአካባቢያዊ እውቀት አጠቃቀም ችግሮች ናቸው። የእነዚህ ፕሮጀክቶች ትኩረታቸው የአርብቶ አደሮችን ኑሮ ማሻሻል ሳይሆን የእንስሳት ሀብትን ወይም የተፈጥሮ ሀብትን ማልማት ነበር። ፕሮጀክቶቹ ለከተሜው ሸማችና ለውጪ ገበያዎች የሚቀርብ ሥጋ በርካሽ የሚያመርቱ የምዕራባውያንን የእንስሳት እርባታዎች ሞዴል የሚከተሉና በነሱው ሥልት የሚመሩ ነበሩ።

የደቡብ የግጦሽ መሬት የሙከራ ፕሮጀክት

በ1988 ተግባራዊ መሆን የጀመረው አራተኛውና ወጪውን የአለም ባንክ የቻለው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት (FLDP) በደጋማው የሀገሪቱ ክፍል የእንስሳት ሀብቶች ላይ ያተኮረ ነበር። በደቡብ በቦረና ማኅበረሰብ ውስጥ ሲከናውን የነበረው የደቡብ የግጦሽ መሬት የሙከራ ፕሮጀክት የአራተኛው የእንስሳት ሀብት ፕሮጀክት አካል ነበር (FLDP 1987)። ፕሮጀክቱም በአምስት ዓመታት ውስጥ ሊከናወን የታቀደ ነበር። ከዚህ ቀደም እንደነበሩት ፕሮጀክቶች ሁሉ፣ የሙከራ ፕሮጀክቱም ዋና ዓላማ የአርብቶ አደሮቹን የምግብ ዋስትና ማሻሻል ነበር። ነገር ግን ይህ ፕሮጀክት ከቀደሙት ሦስት ፕሮጀክቶች በአቀራረቡና በፓስቶራል ልማት ፍልስፍናው የተለየ ነበረ። የሙከራ ፕሮጀክቱ መመሪያ የሆኑ ሦስት ቁልፍ ነጥቦች **ዘላቂነት፣ ሕዝባዊ ተሳትፎ** እና **የተጠቃሚዎቹ ወጪ መጋራት** ነበሩ። የባህላዊ ተቋማትና የአካባቢያዊ እውቀት አጠቃቀም በአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማትን ለማስተዋወቅ መሰረታዊ ነገሮች ተደርገው የተቆጠሩበት ፕሮጀክት ነበር። የሙከራ ፕሮጀክቱ የያዘው ዓላማ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማዳዊውን የልማት ዘዴና ሥልት በመጠቀም ለውጦችን ማስተዋወቅ ነበር። ፕሮጀክቱ በጎብረት ሥራ ማኅበራት ላይ የተመሰረተ፣ አሳታፊ የሆኑ መንገዶችን መከተል በአርብቶ አደር ልማት ውስጥ ውጤታማና ዘላቂ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገ ተግባራዊ ሙከራ ነበር። ይህ ሙከራ ውጤታማ ከሆነ፣ እነዚህን አዳዲስ አቀራረቦች በውስጡ የያዘ መጠነ ሰፊ የሆነ ፕሮጀክት በደቡብ የግጦሽ መሬት ላይ ለማከናወን የሙከራ ፕሮጀክቱን በማስረጃነት ለመጠቀም ታስቦ ነበር። የሙከራ ፕሮጀክቱ ተግባራዊነትም ከደርግ መውደቅ በኋላ በነበረው የፖለቲካ ሽግግር ወቅት በአካባቢው በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት ክፉኛ ተደናቅፎ ሙሉ በሙሉ ተቋርጧል። ነገር ግን ፕሮጀክቱ በልማቱ ውስጥ የተሳተፉ ሰዎች አስተሳሰብና አመለካከታ ቸውን እንዲለውጡ አድርጓል። በሙከራ ፕሮጀክቱ ሀሳቦች ዋና ተጠቃሚ የሆነው የደቡብ ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ፕሮጀክት (SERP) ነው።

የደቡብ ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክት

በ1990 የተጀመረው የደቡብ ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክት ሶማሌዎች በሚኖሩበት 245 ሺህ ካሬ ኪሎ ሜትር ቦታ ላይ የተዘረጋ ሲሆን፣ ለፕሮጀክቱ የሚውለውንም ወጪ የቻለው የአፍሪካ የልማት

ባንክ ነበር። የደቡብ ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክት ዓላማ የእንስሳት ሀብት ምርታማነትን በማሳደግና የተፈጥሮ ሀብት ዘላቂ ሆኖ እንዲቆይ በማድረግ የአርብቶ አደሩን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ከፍ ማድረግ ነበር (SERP 1989)። ከዚህ በተጨማሪ ልክ እንደ ደቡቡ የግጦሽ መሬት ልማት ክፍል (SORDU) የሙከራ ፕሮጀክት፣ የአርብቶ አደር ማኅበራትን ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋቋም የማኅበራዊ አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ ለመስጠትና ማኅበረሰቦቹ በተለይ በድርቅ ወቅት ራሳቸውን የመቻል አቅማቸውን ለማሳደግ ያስችላል ተብሎ ተስፋ የተደረገበት ነበር። የደቡብ ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክት ከቀድሞ ፕሮጀክቶች ብዙ ልምድ የቀሰመና ያለፉትን ስህተቶች ላለመድገም ጥረት አድርጓል። ተጨማሪ ጊዜውን ሁለት ጊዜ ካራዘመ በኋላ ግን ተቋርጧል። የደቡብ ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክት በታቀደለት ጊዜ እንዳይከናወን የአካባቢው የጸጥታ ችግርና ከደርግ መውደቅ በኋላ አዲስ አስተዳደር ለማዋቀር የፈጀው ረጅም ጊዜ እንቅፋቶች ነበሩ። የደቡብ ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክት በመሠረተ ልማት እድገትና በእንስሳት ሕክምና አገልግሎት ረገድ የተሳኩ ውጤቶችን አሳይቷል። በተጨማሪም፣ አርብቶ አደር ሕዝቡን የማሳተፍ እና ከታች ወደላይ የተዋቀረ የአርብቶ አደር ልማት ሥልትን በመጀመርም ጥሩ ውጤቶችን አስመዝግቧል። በአብዛኛው የፕሮጀክቶቹን የመሠረተ ልማት፣ የእንስሳት ሕክምናና የመኖ ልማት መርሐ ግብሮችን ተግባራዊ ለማድረግ ሕዝብን ማእከል ያደረገ አቀራረብን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ትምህርት የተቀሰመበት ነበር። ፕሮጀክቱን በመቅረጽና ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የሚመለከታቸውን ክፍሎች ሁሉ የማሳተፍ ተጨባጭ ሙከራ ተደርጓል። የደቡብ ምሥራቅ የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክት ያስገኘው አጠቃላይ ውጤት ገና ወደፊት የሚታይ ነው።

የአርብቶ አደር ማኅበረሰብ ልማት ፕሮጀክት

ከ2003 ጀምሮ ለ5 ዓመታት ወጪውን የዓለም ባንክና ዓለምአቀፍ የእርሻ ልማት ተቋም የቻሉለት የአርብቶ አደር ማኅበረሰብ ልማት ፕሮጀክት፣ በ15 ዓመቱ ፕሮጀክት ታሪክ ውስጥ ካሉት ሦስት ደረጃዎች የመጀመሪያው ተደርጎ የሚቆጠር ነው። የፕሮጀክቱ ዓላማ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች (ደብብሕ) ክልሎች የሚኖሩ አርብቶ አደሮችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ነው። ፕሮጀክቱ የተቀረጸው አርብቶ አደሮች፣ እንዲሁም የወረዳና የክልል መንግሥታት የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ልማት በተሻለ ሁኔታ ለመምራት የሚያስችላቸውን አቅም ለማጎልበትና አርብቶ አደሮቹን የልማቱ ባለቤት እንዲሆኑ በሚያስችል መንገድ ነው። የአርብቶ አደር ማኅበረሰብ ልማት ፕሮጀክት፣ በተግባር የሚውልበት መንገድ የተቀረጸው አሳታፊ፣ በማኅበረሰቡ የሚመራና የኑሮ ደረጃን በማሻሻል ላይ ያተኮረ እንዲሆን ተደርጎ ነው። ይህም በኢትዮጵያ መንግሥታት ለአያሌ አመታት ሲያገለግል ከነበረው፣ የሥልጣን ተዋረድን ተከትሎ ከላይ ወደታች በትእዛዝ ከሚመራበት አቀራረብ የተለየ ነው። ፕሮጀክቱ በተሳካ ሁኔታ አርብቶ አደርነትን የሚደግፍ፣ ልማትን በተሳካ ሁኔታ ለማስተዋወቅ የሚያስችል ትክክለኛ

ፖሊሲ እንዲያወጣና ተቋማዊ አሰራር እንዲፈጥር ያግዘዋል ተብሎ ይጠበቃል። ከዚህ በተጨማሪም የአርብቶ አደር ማኅበረሰብ ልማት ፕሮጀክት የአርብቶ አደሮችን የመሬት አጠቃቀም መብትን፣ አሰፋፈርን፣ የእንስሳት ሀብት ንግድና ማርኬቲንግን እና የሕዝባዊ አገልግሎቶችን አቅርቦትን ጨምሮ ሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ለማጠናከርም ይበጃል (PCDP Project document)። የአርብቶ አደር ማኅበረሰብ ልማት ፕሮጀክትን እንቅስቃሴ የሚያስተባብረውም የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ነው። የልማት ንብረቶችና የፕሮጀክቶቹ ሥራዎች የሚመሩባቸውን ወረዳዎች በቴክኒክ፣ በፋይናንስ፣ በአቅርቦትና በሌሎች ነገሮችም የሚያስተባብሩ ክልላዊ የማስተባበሪያ ቢሮዎችም አሉ።

የአርብቶ አደር ማኅበረሰብ ልማት ፕሮጀክት በታቀደው መሠረት ተግባራዊ መሆን አለመሆኑና በፕሮጀክት ሰነዱ ውስጥ የተጠቀሱት ነገሮች መከናወን አለመከናወናቸው ወደፊት የሚታይ ነገር ነው። ከዚህ ውጪ የአርብቶ አደር ማኅበረሰብ ልማት ፕሮጀክትን የተዋጣለት ፕሮጀክት የሚያደርጉት ነገሮች ሁሉ በእቅድ ንድፉ ውስጥ ተካተዋል። ፕሮጀክቱ በዓላማው ላይ መሠረታዊ የአቅጣጫ ለውጥ አድርጓል። ይህ ለውጥም ከዚህ በፊት ይታወቅ ከነበረው በእንስሳት ሀብት ላይ ያተኮረ፣ ከላይ ወደታች ይወርድ ከነበረው የልማት አቀራረብ በሕዝቡ ኑሮ ላይ ወደ አተኮረና ከታች ወደ ላይ ወደ ሆነ አሳታፊ የልማት አቀራረብ ተቀይሯል። ፕሮጀክቱ የረጅም ጊዜ ፕሮጀክት ሲሆን የንብረት አጠቃቀሙም እንደ የተጨባጭ ሁኔታው የሚመራ ነው።

በመንግሥት የተያዙ ሌሎች የቅርብ ጊዜ የአርብቶ አደር ምርምር ልማት እንቅስቃሴዎች

የአርብቶ አደር ልማት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ የብሔራዊ ልማት እቅድ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት እንደአንድ ክፍል የተካተተበት ጊዜ ጨርሶ አልነበረም። የአርብቶ አደሩን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል የልማት እቅዶችን ማውጣትና መተግበር የሚያስችል ስልጣን ያለው ራሱን የቻለ ቋሚ መንግሥታዊ አካል አልነበረም። በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የአርብቶ አደር ልማት ክፍል፣ በፌዴራል የግብርና ሚኒስቴር ሥር የአርብቶ አደር ኤክስቴንሽን ክፍል፣ አርብቶ አደርነት ዋናው የምርት ሥርዓቱ አካል በሆነባቸው ክልሎች (እንደ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ አፋርና ደብብሕ) የአርብቶ አደር ልማት ጽሕፈት ቤቶች እንዲኖሩ ለማድረግ በቅርቡ የተከናወነው ሥራ በተገቢው አቅጣጫ የተደረገ አዎንታዊ እንቅስቃሴ ነው። እነዚህ ጽሕፈት ቤቶች አሁን የአርብቶ አደር ልማት እንቅስቃሴዎችን በመደበኛነት በማቀድና በመተግበር ሥራዎች ላይ በንቃት እየተሳተፉ ነው።

የምርምርና የትምህርት ተቋማት የአርብቶ አደር ጉዳዮችን በምርምርና በትምህርት መርሐ ግብሮቻቸው ውስጥ የማካተት ፍላጎታቸው እየጨመረ መጥቷል። አለማያ ዩኒቨርሲቲ የአርብቶ አደር ጥናት ተቋም የማቋቋም እቅድ አለው፤ የኢትዮጵያ የእርሻ ምርምር ድርጅት በሥሩ የበረሃማ አካባቢና የአርብቶ አደር ምርምር መምሪያ አለው። ወጪያቸውን የዓለም ባንክ የሚችልላቸው በአርብቶ አደር ምርምርና ልማት ላይ የሚያተኩሩ ትልልቅ የምርምር ማእከላት ግንባታ በኦሮሚያ፣ በአፋር፣ በሶማሌ እና በሌሎች ክልሎች

ተከናውኗል። የገዋኔ የሙያ ማሰልጠኛ ማእከል በአርብቶ አደር አካባቢዎች ውስጥ መሥራት የሚችሉ የልማት ሠራተኞችን ለማሰልጠን ተቋቁሟል። እስካሁን ብዙም ተግባራዊ ባይሆንም፣ በፌዴራል የትምህርት ሚኒስቴር ሥር ለአርብቶ አደሮች ተስማሚ የሆነ በምሳሌነት የሚያገለግል የትምህርት ሥርዓት (ሞዴል) የመቅረጽና በተግባር ላይ የማዋል ኃላፊነት ያለው የአርብቶ አደር ትምህርት ግብረ ኀይል አለ። እነዚህ ሁሉ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማትን ሊያፋጥኑ የሚችሉ አዎንታዊ እርምጃዎች ናቸው።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የአርብቶ አደር ልማት

ብዙ ዓለም አቀፍና አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያዶች) ለብዙ አሠርታት በአርብቶ አደር አካባቢዎች ሲሠሩ ነበር። ሁሉም ባይሆኑ ብዙዎቹ መያዶች መጀመሪያ ወደ አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጡት በድርቅ ምክንያት የአደጋ ጊዜ እርዳታ ለመስጠት ነው። እነዚህ ድርጅቶች በ1980ዎቹ፣ በ1990ዎቹና በቅርቡም በተከሰቱ ድርቆች የብዙዎችን ሕይወት በማዳን ውጤታማ ሥራ ሠርተዋል። ከጊዜ በኋላ ግን የልማት ሥራዎችን ከእርዳታ ሥራ ጋር ለማቀናጀት ሞክረዋል። መያዶቹ የውሃ ልማት፣ የእንስሳት መድኃኒቶችን፣ ወዘተ... የመሳሰሉትን አቅርቦቶች የሚያከናውኑ አነስተኛ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ማድረጋቸው እየጨመረ መጥቷል። ነገር ግን ቀዳሚ ትኩረታቸው የአደጋ ጊዜ እርዳታ መስጠት ስለነበር በአርብቶ አደሮች ኑሮ ላይ ያመጡት አጠቃላይ ለውጥ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም።

የመንግሥት ፖሊሲዎችና የአርብቶ አደር ልማት

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አርብቶ አደሮች የአርብቶ አደር ስልተ-ምርቱና የፓስቶራል የኑሮ መንገዳቸው ለምዕተ ዓመታት ባሕርያቸውን እንደያዙ ያቆዩባቸው ባህላዊ ተቋማትና ድርጅቶች አሏቸው። እነዚህ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ እና ፖለቲካዊ ተቋማት የንብረት ባለቤትነትና አመራርን፣ የግጭቶች አፈታትን፣ የሀብት መጋራትንና ክፍፍልን፣ እና የአስተዳደር ተግባራትን ሲያቃልሉ ኖረዋል። የሶማሌው «ሄራ»፣ የቦረናውና የጉጂው «ገዳ» እና የአፋሩ «ሜዳ» እና «አዳ» የመሳሰሉት እነዚህ ማኅበረሰቦች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሕይወታቸውን ለብዙ ምዕተ ዓመታት የተመሰረቱባቸውና የመሩባቸው የአርብቶ አደር ተቋማት ነበሩ። ነገር ግን የሕዝብ ብዛት መጨመርና የግጦሽ መሬት እያነሰ መሄድ፣ በተመናመኑ የልማትና የሕይወት ንብረቶች ላይ የሚደረገው ሽኩቻ መጨመርና የመሳሰሉት ውስጣዊ ችግሮች፤ ባህላዊ ተቋማትን እየዋጡ የሄዱ የመንግሥትና የዘመናዊ ስልጣኔ መስፋፋት፣ የአርብቶ አደር የምርት ሥርዓቱን አገልግሎት የሚያዳክሙ ተገቢ ያልሆኑ የመንግሥት ፖሊሲዎችና የመሳሰሉት ውጫዊ ችግሮች የእነዚህን ባህላዊ ተቋማት ህልውናና አገልግሎት የተፈታተኑና ለአደጋ ያጋለጡ፣ እንዲሁም በጊዜ ብዛት የመሪዎቻቸውን ስልጣን ያዳከሙ ናቸው።

የኢትዮጵያ መንግሥታት ፖሊሲዎች ከፓስቶራሊዝም፣ ከአርብቶ አደሮች እና ከባህላዊ ተቋሞቻቸው ጋር የሚጻረሩ ነበሩ። በአንዳንድ ቦታዎች ባህላዊ ተቋማትንና ማኅበራትን ለመተካት መንግሥታት የወሰዷቸው የኀይል እርምጃዎች ያስገኟቸው ውጤቶች በቋፍ ያለውን በረሀማና ከፊል በረሀማ ሥርዓተ ምህዳር

በትክክል ለመያዝ የሚያስችለውን ተገቢ የሆነውን አካባቢያዊ እውቀት ማጥፋት ሆነ። ያለፉት ሁለት መንግሥታትና አሁን ያለው መንግሥት የነደፏቸውን፣ ከአርብቶ አደርነትና ከፓስቶራል ልማት ጋር የተዛመዱ ፖሊሲዎች ከዚህ በታች በአጭሩ እንቃኛለን።

የንጉሠ ነገሥቱና የደርግ ዘመናት እና የአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲዎቻቸው

በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሰው ያልሰፈረበት ቦታ ባለቤት አልባ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠር ነበር። ዛሬ የምናውቃቸው ብዙዎቹ የመንግሥት እርሻዎችና ብሔራዊ ፓርኮች በአፋር፣ በከረዩ፣ በሐመር፣ በገለብ፣ ወዘተ... የሚገኙ የአርብቶ አደር ማኅበረሰቦችን በኃይል በማስለቀቅ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ የተቋቋሙ ናቸው። በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ባለቤት አልባ የሚባለውን መሬት ከአርብቶ አደሮቹ እየወሰዱ «አልሚዎች» ለሚባሉ ግለሰቦች ለገበያ የሚቀርቡ ሰብሎችን እንዲያመርቱበት መስጠት የፖሊሲው አንድ አካል ነበር። ይህ አርብቶ አደሮችን በኅይል በማስለቀቅ የአርብቶ አደሮቹን መሬት ፓስቶራል ላልሆኑ ኢንቨስትመንቶች ማዋል የአርብቶ አደሮቹን የኑሮ ደረጃ (አኗኗር) በጣም እንዲወድቅ አድርጎታል። ይህ ሁሉ የተደረገው የአርብቶ አደር አካባቢዎችንና አርብቶ አደሮችን ኋላ ቀር ከሆነውና ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ ከሚኖሩት ኑሮ የተሻለ ነው ወደሚባለው አንድ ቦታ ረግተው አምራች ወደሚሆኑበት ኑሮ ለማሳደግ በሚል ሽፋን ነው። እርምጃው የአርብቶ አደሮችን ሰብአዊነት ከቁብ ያገባ አልነበረም። የልማት ፖሊሲው በተፈጥሮና በእንስሳት ሀብቶች ላይ ብቻ እንጂ የአርብቶ አደሩን ኑሮ በማሻሻል ላይ ትኩረት ያደረገ አልነበረም። በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የተጀመሩት የፓስቶራል ልማት ፕሮጀክቶች (ከላይ የተጠቀሰውን ይመለከቷል) በግልጽ እንደሚያንጸባርቁት የመንግሥቱ ፖሊሲ ያተኩር የነበረው በእንስሳትና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ እንጂ ኑሯቸው በእነዚህ ሀብቶች ላይ በተመሠረተው በአርብቶ አደሮች ላይ አልነበረም።

የንጉሠ ነገሥቱና የደርግ መንግሥታት በአርብቶ አደር ልማት ውስጥ ሰዎቹን አለማካተታቸውና በእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነት ላይ ማተኮራቸው የጋራ ባህርያቸው ነበር። በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ የደርግ ዘመን ፖሊሲ በጣም መጥፎ ነበር። የገጠርን መሬት የመንግሥት ያደረገው የ1975ቱ አዋጅ አርብቶ አደሩ በመሬቱ የመጠቀም መብት ብቻ እንዲኖረው (የንብረቱ ባለቤት መሆኑን አስቀርቶ) በማድረጉ ሶሻሊስቱ መንግሥት የአርብቶ አደሩን መሬትና የውሀ ሀብት ከፓስቶራል ኑሮ ወይም ደኅንነት ጋር ላልተያያዘ ኢንቬስትመንት መስጠት የሚያስችለውን ስልጣን አስጨበጠው። ሰፋፊ የመንግሥት እርሻዎች ተገነቡ፤ የቀደሙትም በአርብቶ አደሩ ሀብት ላይ ተስፋፉ። በጣም ጥሩዎቹ የግጦሽ መሬቶች ለብሔራዊ ፓርክ፣ ለመንግሥት ደን፣ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ላሉ የእርባታ እርሻዎች ተከለሉ። አርብቶ አደሩ እነዚህን ቦታዎች ለግጦሽ እንዳይጠቀምባቸው ተከለከለ። ታላላቅ የሆኑ የሰፈራ መርሐ ግብሮች በአርብቶ አደሩ ቦታዎች ላይ ተከናወኑ። ሶሻሊስታዊው መንግሥት ከዚህም አልፎ ኮታ በማውጣት የአርብቶ አደር ማኅበራት እያንዳንዳቸው የተወሰኑ እንስሳትን በየተወሰነው ጊዜ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ለሚንቀሳቀሱ የእንስሳት ሀብት ድርጅቶች በመንግሥት ተመን እንዲሸጡ በማስገደዱም

በገበያው ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ተቆጣጠረው። ይህም ለከተሜው ሸማች የሚያስፈልገውን ለማቅረብና ለውጪ ገበያ በመላክ የውጪ ምንዛሪ ለማግኘት ሲባል የተደረገ ነው። ሦስተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት የመንግሥትን ከብት እርባታ፣ ሰፈራ፣ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ለሆነው ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል የኮታ ሥርዓት፣ ወዘተ... የሚያካትተውን የመንግሥት ፖሊሲ በተወሰነ ደረጃ ለማጠናከር ያገለገለ ነበር።

በንጉሠ ነገሥቱና በደርግ ዘመን የነበሩት የአርብቶ አደር ልማት ፕሮጀክቶች በሙሉ ተግባራዊ የሆኑት የእንስሳት ሀብት ልማትን ከአርብቶ አደር ልማት ጋር አንድ አይነት አድርገው በሚቆጥሩ ፖሊሲዎች ሥር ነበር። ፕሮጀክቶቹ በተወሰነ ደረጃ አርብቶ አደርነት ጎላ ቀር የሆነ የምርት ሥርዓት ስለሆነ ዘመናዊ መሆንና እንደገና መዋቀር የሚገባው ነው የሚለውን የመንግሥታቱን እምነት የሚያንጸባርቁ ነበሩ። ወደኋላም ቢሆን፣ እነዚህ ፕሮጀክቶች ይህን ባህላዊ የምርት ሥርዓት መልሶ ለማዋቀር ያደረጉት ሙከራ ሙሉ በሙሉ ሳይሳካ ቀርቷል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) በፓስቶራል የምርት ሥርዓት ሥር ያሉት አካባቢዎች የራሳቸው የሆነ ልዩ ችግር ያለባቸው አካባቢዎች በመሆናቸው ለሁኔታው ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን የሚሹ ናቸው ብሎ ያስባል። በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚከናወኑ ልማቶችን የሚያስተባብር ክፍል በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሥር አቋቁመ። በሀገሪቱ ያሉትን የአርብቶ አደር ልማት እንቅስቃሴዎችን የሚከታተል የአርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም በተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ እንዲቋቋም ተደረገ። አርብቶ አደርነት ዋና የምርት ሥርዓት በሆነባቸው ክልሎች ውስጥ የአርብቶ አደር ልማትን በኃላፊነት የሚመሩ የክልል ቢሮዎችም ተቋቁሙ። ከቀደሙት ሁለት መንግሥታት በተለየ ሁኔታ ይህ መንግሥት የአርብቶ አደር ልማትን በብሔራዊ የልማት እቅዱ ውስጥ ለማካተት ሞክሯል (ከ2000-2004 እና ከ2005-2009 ድረስ ያሉ የአምስት ዓመት የልማት እቅዶች)።

የግልጽነት ችግር ቢኖርበትም፣ መንግሥት በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚከናወኑ የልማት ተግባራትን ለመምራት ብሔራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ አውጥቷል። የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ማልማትና የአርብቶ አደሮችን ኑሮ ለማሻሻል የሚያስችል የልማት አቅጣጫ የማሳየትን አስፈላጊነት በማሰብ ረጅም ጉዞ ተጉዟል። ከቀደሙት መንግሥታት ከነበረው ሁኔታ በመለወጥ፣ የፓስቶራል ልማት አስተሳሰብ የተለየ አቅጣጫ ይዟል። በእንስሳት ሀብት ላይ ከማተኮር ይልቅ በድሆቹ አርብቶ አደሮችና በድህነት ቅነሳ ላይ በጣም በማተኮሩም ከቀደሙት መንግሥታት ይለያል። ነገር ግን፣ አሁንም ቢሆን መንግሥት አርብቶ አደሮቹ በኑሯቸው ላይ ለውጥ በሚያመጣው የፖሊሲ ማውጣት ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ለማድረግ የበለጠ መሥራት ያስፈልገዋል።

የ1994 ሕገ መንግሥት ለአርብቶ አደሮቹ ነጻውን መሬት ለግጦሽ የመጠቀምና እራሳቸው ፈልገው ካልሆነ በስተቀር ከሚኖሩበት አካባቢ ያለመፈናቀል መብት አጎናጽፏቸዋል። በተጨማሪም፣ ሕገ መንግሥቱ አርብቶ አደሮቹ በህይወታቸው ላይ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ተገቢ ዋጋ ለምርቶቻቸው እንዲያገኙ አስችሏቸዋል። እነዚህ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የሚገኙ አንቀጾች መንግሥት በተለይ የአርብቶ አደሩን ጥቅም አስመልክቶ ያለውን አቋም የሚያንጸባርቁ ናቸው። በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ የልማት ፖሊሲው መንግሥት የአርብቶ አደሮቹን የምግብ ዋስትና ለማሻሻል በፓስቶራሊዝም ላይ ኢንቬስት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል። በፓስቶራል ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ ባህላዊው የአርብቶ አደሮች እውቀት አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል። ነገር ግን በረጅም ጊዜ ፖሊሲው አርብቶ አደሮችን በመስኖ ልማት በአንድ አካባቢ ረግተው እንዲኖሩ ማድረግን ያበረታታል፤ ይህ በጣም አከራካሪና በተወሰነ መልኩም ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር ነው። አርብቶ አደሮቹን በአንድ ቦታ ረግተው የሚኖሩ በማድረጉ ላይ ያለው የረጅም ጊዜ ፖሊሲ የሚኖረውን አንድምታና ተገቢነት በግልጽ ለማየት በፖሊሲ አውጪዎች፣ በልማት ሰራተኞች (አሳታፊዎች)፣ በተመራማሪዎችና አርብቶ አደርነትን በሚያበረታቱ (በሚደግፉ) ቡድኖች፣ በአርብቶ አደር ማኅበረሰቦች መካከል ተጨማሪና ግልጽ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ነው። መንግሥት ምንም በማያወዛግብ ሁኔታ አርብቶ አደርነት የሕይወት ዘይቤ በሆነባቸው አካባቢዎች ውጤታማ የሆነ የሕይወት መምሪያ ሥልት መሆኑን መቀበልና መንቀሳቀስ አለበት፤ ዝናባማ አካባቢዎች ለሰብል አምራቾች ተስማሚ እንደሆኑ ሁሉ ማለት ነው።

4. አርብቶ አደርነት ዛሬ ምን ይመስላል?

በኢትየጵያ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ሰፊ የልማት ተግባራት ሲከናወኑ ግማሽ ምዕተ ዓመት ሊሆን ነው። ነገር ግን መልስ የሚሻ ትልቅ ጥያቄ አሁንም መልስ አላገኘም፤ እነዚህ የልማት ሥራዎች በአርብቶ አደሩ ሕዝብ ሕይወት ላይ ዘላቂና አዎንታዊ ለውጥ አምጥተዋልን? ዛሬ ዛሬ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች እንኳን የልማት ሥራቸው ያስገኘው ለውጥ መኖር አለመኖሩን እየጠየቁ ነው። ለምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ በጥሩ ሁኔታ የተከናወነውና የብዙ ሰዎች የኑሮ መሠረት የነበረው የአርብቶ አደር ሥርዓት እየዋዠቀ ያለና የአርብቶ አደሮች ዘላቂ የኑሮ መሠረት ሆኖ መቀጠሉ እያጠራጠረ መምጣቱን ብዙ ጥናቶች ይፋ እያደረጉ ነው። በአርብቶ አደር አካባቢዎች በአሁኑ ጊዜ አለመረጋጋቱ እየተባባሰ፣ የምግብ ዋስትና እጥረት እየጨመረ፣ ገቢ እየቀነሰ፣ ድህነት እየጨመረ፣ ማኅበራዊ ምግባሮችን መከተል እየቀነሰና አካባቢ እየተራቆተ የሚሄድባቸው መሆናቸው መለያቸው እየሆነ ነው። ለምሳሌ፤ ሰሎሞን ደስታና ሌሎች በ2002 ላይ ዋና ዋናዎቹ የአርብቶ አደር ምርታማነት ጠቋሚዎች የፓስቶራል ደህንነቱ እየቀነሰ መሆኑን እንደሚያመለክቱ በቦረና አካባቢ አረጋግጠዋል። ከሁሉም በላይ በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ ያለው የእንስሳት ሀብትና የሕዝቡ ተመጣጣኝነት (ሬሺዮ) ነው። የእንስሳት ሀብቱ በየወቅቱ በድርቅ በመመታትና በመኖ እጥረት የተነሳ ሲዋዥቅ የሕዝብ ብዛቱ ግን እየጨመረ ነው የሄደው። ከዚህ በተጨማሪ ሀብት ባላቸውና በሌላቸው መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ሄዷል። ሀብት በጥቂት አባወራዎች እጅ ሲከማች (ከዚህ ቀደም የነበራቸውን ያህል ሀብት የላቸውም) ከዚህ በፊት ከነበሩበት ድህነት በባሰ

ድህነት ውስጥ ያሉት ድሀ አባወራዎች ቁጥር ግን እየጨመረ ነው። ባህላዊ የሀብት ክፍፍል መንገዶች፣ የመከባበርና እርስ በርስ የመረዳዳት ስሜቶች በቦረና አርብቶ አደሮች ዘንድ እየቀነሱ መጥተዋል። በቦረና በአገር ሽማግሌዎች የሚመራው ማኅበረ-ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ሊጠፋ በአደጋ ላይ ነው ያለው። ሁኔታው በሌሎችም የሀገሪቱ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ተመሳሳይ ናቸው (Desta et al 2004)። ይህ ማለት ግን ባለፉት ዘመናት በፓስቶራል ልማት ላይ የተደረጉት ኢንቨስትመንቶች ባክነው ቀርተዋል ማለት አይደለም። የመንግሥት ፕሮጀክቶችና መያዶች መሠረተ ልማቶችን በመዘርጋትና ተላላፊ የእንስሳት በሽታዎችን በመቆጣጠር ረገድ ስኬታማ ነበሩ። በተጨማሪም የአርብቶ አደሩን ንቃት በማሳደግና የራሳቸውን የልማት ጉዳዮች ራሳቸው እንዲቆጣጠሯቸው የሚያስችላቸውን አቅም በመገንባት ይህ ነው የሚባል አስተዋጽኦ አድርገዋል። ነገር ግን መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድህነትን በማስወገድና በምግብ ራስን መቻልን በማሳደግ ረገድ ያደረጉት አስተዋጽኦ የሚታይ አይደለም።

አንድ ነገር ግን በወቅቱ የሚያበረታታ ነው። የብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ፖሊሲዎች፣ አርብቶ አደሮች ራሳቸው የልማት ፍላጎታቸውን የመምራት /የመቆጣጠር/ አቅማቸው፣ መንግሥታዊ ተቋማትና መያዶች በአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ላይ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ መጨመር በኢትዮጵያ የፓስቶራል ልማትን ውጤታማነት ለማጠናከር በጣም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ። መንግሥታዊም መንግሥታዊ ያልሆኑም የልማት ሥራ የሚሠሩ ድርጅቶች በጊዜ ብዛት በአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማትን በማስተዋወቅ በነበረው አስተሳሰብና እንቅስቃሴ ላይ ያሳዩት ለውጥ የሚያበረታታና አዎንታዊ አቅጣጫን የተከተለ ነው። ከላይ ወደ ታች ከሚወርደውና በእንስሳት ሀብት ላይ ከሚያተኩረው መንገድ ከታች ወደላይ፣ አሳታፊና በአርብቶ አደሮች ኑሮ ላይ ወዳተኮረው መንገድ ለውጥ ተደርጓል። ይህም ለውጥ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ዘላቂ ልማት ለማስገኘት ብዙ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል ነው።

5. አርብቶ አደር እና ልማት በኢትዮጵያ በ2020

ስለምርት ሥርዓትና በሥርዓቱ ስለሚተዳደሩ ሰዎች የወደፊት ሁኔታ መናገር ቀላል አይደለም። የተለያዩ ግምቶች በመሰንዘር እንዲህ ቢሆን እያልኩ መናገር አልፈልግም። ከዚህ ይልቅ አርብቶ አደሮች ለብዙ አሥርታት ያለፉባቸውን፣ አሁን የሆኑትን እንዲሆኑ ያደረጓቸውን የልማት ሂደቶች እና በአርብቶ አደሮች የኑሮ ሁኔታ ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የመንግሥት ፖሊሲዎችንና ሌሎች መሰል ነገሮችን መመርምር መርጫለሁ። በአርብቶ አደር ልማት ላይ ለረጅም ጊዜ የተከማቸና ከፍ ያለ ጥቅም የሚሰጥ ልምድና እውቀት አለን። አርብቶ አደሮች በሰፈሩባቸው በረሃማና ከፊል በረሃማ ዝቅተኛ ቦታዎች የሚገኘው የተፈጥሮ ሀብት በትክክል ከተያዘና ተመጣጣኝ የሆነ ሕዝብና የእንስሳት ሀብት ከያዘ ለሰዎች ጥሩ የኑሮ መሠረት ሊሆን ይችላል። የአርብቶ አደር ማኅበረሰቦች የራሳቸውን ጉዳይ የመምራት ንቃታቸውና አቅማቸው እያደገ ነው። አርብቶ አደሮች ሀብታቸውንና የገቢ ምንጮቻቸውን በማብዛት ከፍ ያለ ሀብት ለማግኘት እየሞከሩ ነው። አርብቶ አደሮች ባህላዊ ተቋሞቻቸውን የሚደግፉ፣ ለምሳሌ፤ እንደ ኦሮሚያ የአርብቶ አደር ሽማግሌዎች ጉባኤ ያሉ ተቋማትን እየመሠረቱ ነው። ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ አርብቶ አደርነትን የሚያበረታቱ ተቋማት እየተፈጠሩ ሲሆን፣ ተቋማቱ የአርብቶ አደሮችን ጥቅም ለማስጠበቅ ድምጻቸውን እያሰሙ ነው። አሁን ያለው መንግሥት በአርብቶ አደሮች ላይ ያለው ፖሊሲ

በአጠቃላይ ሲታይ አዎንታዊ ነው። የአርብቶ አደሮችን ፍላጎት ለማሟላት ፖሊሲዎችን በመቅረጽና ተቋማትን በማቋቋም ረገድ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል። በ2020 የዓለም የሥጋ ፍጆታ ይጨምራል (Delgado 1999)። ከሰው ሰራሽ ማድለቢያ ነጻ በሆነ መንገድ የተመረተ የሥጋ ፍጆታ መጨመርም ለአነስተኛ የእንስሳት ሀብት አምራቾች ጠቃሚ ይሆናል። ነገር ግን በአርብቶ አደር አካባቢዎች ያለ የጸጥታ ችግርና የልማት ሥራዎችን የሚያጓትት አስተዳደር፣ እንዲሁም የኤች አይ ቪ ኤድስ መስፋፋትና በአምራቹ ኃይል ላይ የሚያደርሰው ተጽእኖ በልማት ለውጦቹ አቅጣጫና መጠን ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ነው።

ርእይ

በኢትዮጵያ ውስጥ በ2020 ዓ.ም. የአርብቶ አደር ልማት ምን ሊመስል እንደሚችል አስተያየቴን ትክክለኛውን ሁኔታ ሊያመለክት ይችላል በሚል ግምት ለመስጠት ያህል ደፈር ልበል።

መንግሥት እርሻ የኑሮ መሠረት እናም የአኗኗር ዘይቤ መሆኑን የሚያምነውን ያህል አርብቶ አደርነትም አንደ አንዱ የኑሮ መሠረት እና የአኗኗር ዘይቤ መሆኑን ተቀብሎ ተጨባጭ እርምጃ ይራመዳል፤ የፖሊሲ ውሳኔዎቹም ሥርዓቱ የበለጠ ምርታማና ውጤታማ እንዲሆን የሚያደርጉትን ድጋፎች እስካሁን ከነበረው ሁኔታ በበለጠ የሚያካትቱ ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ።

የባህላዊው የአርብቶ አደሮች የአመራር አካላት የአርብቶ አደሮቹን ሀሳብ በግልጽ ለማሰማትና ጥቅማቸውንም ለማስጠበቅ በድፍረት እንዲሚገቱ የሚያስችላቸውን የፖለቲካ ውክልና ለማሳደግ ከራሳቸው ነባር የኑሮ ብሂል ውጪ ካሉ ኃይላት ጋር ተቀናጅቶ ለመሥራት በራቸውን የበለጠ ክፍት ያደርጋሉ ብዬ አምናለሁ።

በተጨማሪም የተለያዩ ነገሮችን የማምረትና የመሸጥ ደረጃቸውን በማስፋት፣ ከለመዱት የአርብቶ አደር ኑሮ ውጭ በሆኑ የኢንቬስትመንት ተግባራት የሚሰማሩ አርብቶ አደሮች ይኖራሉ፣ ቁጥራቸውም ይጨምራል ብዬ አምናለሁ። (ይህ ግን በልማት ሂደቱ ውስጥ በያዙት ቦታና በየአካባቢያ ቸው በተለያዩ ነገሮች ላይ ለመሳተፍ በሚኖሯቸው እድሎች መጠን ሊለያይ እንደሚችል ሳንረሳ ነው።) በተለይ ሀብታም የሆኑ ብዙ አርብቶ አደሮች በከተሞች ኢንቬስትመንት ውስጥ በመግባት ከፍተኛ የተጣራ ትርፍ ያገኛሉ። ይህም ሆኖ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የእንስሳት ሀብት ዋናው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንደሆነ ይቀጥላል።

በአርብቶ አደር አካባቢዎች እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ መንገድና መገናኛ ባሉ ሕዝባዊ አገልግሎቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ መሻሻል ይኖራል ብዬ አምናለሁ። ከአርብቶ አደር አካባቢዎች የወጡና የትውልድ አካባቢያቸውን የልማት እንቅስቃሴ የሚመሩ፣ እንዲሁም ፓስቶራሊዝም የኑሮ ዘይቤ መሆኑን ለማሳወቅ የሚቀሰቅሱ/ግፊት የሚያደርጉ ብዙ የተማሩ (በባችለር፣ በማስተርስ፣ በዶክትሬት፣ ወዘተ... ደረጃ) እና በንግድ ሙያ የተሰማሩ ሰዎች ይኖራሉ። እነዚህ ሰዎች ውጤታማና ከፍ ያለ ትርፍ በሚያስገኙ፣ አርብቶ

አደር ያልሆኑ ኢንቨስትመንቶችን ጨምሮ በተለያዩ መስኮች ውስጥ የፓስቶራል ኢኮኖሚው መግባቱን ለማጠናከር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ይሆናሉ።

በአርብቶ አደር አካባቢዎች ውስጥ ያሉ ከተሞች አድገው የሁሉንም የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት የሚያፋጥኑ ጠቃሚ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ። በገጠሩ የአርብቶ አደር አካባቢና እያደጉ ባሉት ትንንሽ ከተሞች መካከል ጠንካራ የኢኮኖሚ ቁርኝት ይኖራል።

በ2020 አርብቶ አደሮች ከእንስሳት ሀብት አብዮትና ከዓለም አቀፍ ተፈጥሮአዊ ምርቶች ገበያ ተጠቃሚ ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ፤ ይህም በአካባቢው ልማትን ያፋጥናል።

አርብቶ አደሮች የአጎራባች ሀገሮችን ድንበር አቋርጠው እንዲንቀሳቀሱ ይፈቀዳል፤ በዚህም በተሻለ ሁኔታ የግጦሽ መሬትንና ገበያን ለማግኘት፣ እውቀትንና ክሂሎችን ከአንዱ ወደሌላው ለማሸጋገርም እድል ያገኛሉ ብዬ አምናለሁ።

የአርብቶ አደር ሥርዓቱ በኑሮ ላይ የሚደርስ መቃወስን ለመቋቋምና በኑሮ ላይ የሚደርስ ጥፋትን ከወዲሁ ለመከላከል የሚያስችል መልሶ የማንሰራራት ዓቅም የሚያገኝበት ደረጃ ላይ ይደርሳል፤ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ የሚኖረው አስተዋጽኦም በከፍተኛ መጠን ያድጋል ብዬ አምናለሁ።

እስካሁን የተባለውን ለማጠቃለል፣ በ2020 በኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች የኑሮ ደረጃ ላይ ከፍ ያለ ለውጥ ይታያል። የተፈጥሮ ሀብት ከመጥፋት ተጠብቆ፣ ቁሳዊ ካፒታል (ወረት) በጣም ዳብሮ፣ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ወረትም አድጎ፣ የሰው ኃይልና አዳዲስ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስፈልገው በራስ የመተማመን ብቃት ተሻሽሎ የሚገኝበትን የፓስቶራል ሥርዓት እናያለን። ለአርብቶ አደሮቹ የተሻለ የኑሮ ደረጃ የሚያስገኝ፣ በይዘቱም በመልኩም የተፈራረቀና የተሰባጠረ የፓስቶራል ሥርዓት እናያለን። ነገር ግን፣ ወሳኙ ነገር የቴክኒካዊ ግብአት ብቻ አይደለም፤ ለልማት አስፈላጊ የሆኑትን ሰላምንና መረጋጋትን ሳይናወጡ መጠበቅ፣ ለልማት የግድ አስፈላጊ የሆነው መልካም አስተዳደር፣ ፓስቶራሊዝምና አርብቶ አደሮች የተሻለ የኑሮ ይዞታ እንዲኖራቸው ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑት የፖለቲካው በጎ ፈቃድና እሱንም መሠረት ያደረጉ ተገቢ ውሳኔዎች ያስፈልጋሉ።

ዋቢ መረጃ

Blench, R. 2001. 'You can't go home again' Pastoralism in the new millennium. 2001. Institutional Research Fellow, Overseas Development Institute, London, UK.

Coppock, D. L. 1994. The Borana Plateau of Southern Ethiopia: Synthesis of Pastoral Research, Development, and Change, 1980-1991. System Study No. 5. International Livestock Center for Africa, Addis Ababa, Ethiopia.

Cossins, N. J. and M. Upton. 1988a. Options for improvement of the Borana pastoral system. Agric. Systems 27:251-278.

Delgado, C., M. Rossegrant, H. Steinfeld., and S. Ehui. 1999. Livestock to 2020. The Next Food Revolution. IFPRI 2020 Brief 61.

Desta, S. 1996. Past and present pastoral development in Ethiopia. p. 26-28. *In:* S. Edwards and T. Mesfin (eds). Proceedings of the conference on pastoralism in Ethiopia, 4-6 February 1993, Addis Ababa.

Desta, S., and Coppock, D. L. (2002) "Cattle Population Dynamics in the Southern Ethiopian Rangelands, 1980-97." *Journal of Range Management* 55: 439-451.

_____ (2004) "Pastoralism under pressure: Tracking system change in southern Ethiopia." *Human Ecology* 32(4): 465-486.

Devereux, S. 2006. Vulnerable Livelihoods in Somali Region, Ethiopia. Research Report 57. Institute of Development Studies at University of Sussex Brighton, UK.

FLDP (Fourth Livestock Development Project). 1987. Staff appraisal report (implementation volume). Eastern and Southern Africa Projects Department, Northern Agricultural Division, the International Bank for Reconstruction and Development.

Kebebew, F. and D. Tsegaye. 2001. Traditional Coping Strategies of Afar and Borana Pastoralists in Response to Drought. Report No. 17. Drylands Cooerdinations Group. Mekelle University, Gry Synnevag, Noragric.

RDP (Rangeland Development Project). 1975. Appraisal Report Rangeland Development Projects, Ethiopia, credit 603-Et.

Sandford, S. 1983. Management of pastoral development in the third world. John Willey and Sons, New York, USA/Overseas Development Institute, London.

SERP (South East Rangelands Project). 1989. Appraisal report South East Rangelands Project, Ethiopia, Eth/PAAL/89/01. ADF, Abidjan, Cote d'Ivoire.

World Bank. 1991. Ethiopians Rangelands Development Project: Project Completion Report. World Bank, Washington D. C.

Zere, G. H. and B. E. Norton. 1987. Range/Livestock development in East Africa with particular reference to Ethiopia. Post Doctoral paper, Department of Range Science, College of Natural Resources, Utah State University, Logan Utah, USA.

በአቶ ሰለሞን ደስታ ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

አያሌው ገብሬ[1]

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር 'አርብቶ አደሩና ልማት በኢትዮጵያ፤ ርዕይ 2020' በሚል ርዕስ በዶ/ር ሰለሞን ደስታ በተዘጋጀው ጥናታዊ ጽሁፍ አስተያየት አቅራቢ እንድሆን ስለጋበዘኝ በቅድሚያ ላመሰግን እወዳለሁ።

የቀረበው ጽሁፍ በአምስት ተያያዥነት ባላቸው ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን እኔም የማቀርበው አስተያየት በዋናነት ይህንኑ ቅደም ተከተል የያዘ ይሆንና እንደአስፈላጊነቱ ግን ከአንዱ ክፍል ወደሌላው ክፍል ወጣ ገባ ሊሉ የሚችሉ ሃሳቦችም ይኖሩኛል። እነዚህ የቀረቡት አምስት ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው። መግቢያና መንደርደሪያ፣ የአርብቶ አደር ልማት ተሞክሮ በኢትዮጵያ፣ (አጠቃላይ ዳሰሳ)፣ በአርብቶ አደሩ ልማት ላይ ያነጣጠሩ የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች እንዲሁም እነሱን ተከትለው የመጡ ለውጦች ወይም ውጤቶች፣ የአርብቶ አደሩ የኑሮ ፈርጅ (Pastoralism) አሁን የሚገኝበት ሁኔታ፣ በመጨረሻም አርብቶ አደሩና ልማቱ በ2020 ምን ምን ገጽታዎች ይኖራቸዋል (አጠቃላይ ትንበያና ዕይታ) ናቸው።

በመጀመሪያዎቹ ገጾች ላይ በቀረበው መንደርደሪያና መግቢያ ላይ የጽሁፉ አቅራቢ የአርብቶ አደሩ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ፈርጅ (Pastoral livelihood) ምን ምን ገጽታዎች እንዳሉት፣ የራሱ የዚህ የኑሮ ፈርጅ ትርጓሜውን (Definition) የዚህ የኑሮ ዘርፍ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሰረቶች ምን እንደሆኑ በኢትዮጵያ የአርብቶ አደሮች ብዛትና መልከዓ ምድራዊ ሥርጭት፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የአርብቶ አደሮች የኑሮ መሰረት የሆኑት የእንስሳት ብዛት ግምት ቀርቧል። በተጨማሪም ይህ የአገራችን አንዱ ኤኮኖሚያዊ ንዑስ ክፍል (Pastoral sub-sector) ለአጠቃላይ የአገር ልማት ያደረገው አስተዋጽኦና ያለው ዕምቅ ጠቀሜታ (Potential) እስከአሁን ከአደረገው ማለትም ከውጭ ንግድ ገቢ፣ ለክልላዊና አካባቢያዊ የገበያ ፍላጎቶች መሟላት፣ እንዲሁም የእርሻውን ክፍል ኢኮኖሚ ከማገዝ አንፂር ያደረገው አስተዋጽኦ ተጠቅሷል። በመጨረሻም በዚህ ክፍል የተነሳው ጉዳይ ይህ ንዑስ ክፍለ ኢኮኖሚ ከላይ ያበረከታቸው ጠቀሜታዎች እንዳሉ ሆነው የሚገባውን ያህል የልማት ፖሊሲ ትኩረት የተነፈገው መሆኑና ቢያንስ ባለፉት 50 እና 60 ዓመታት በኢትዮጵያ ወደሥልጣን የመጡ ተከታታይ መንግስታት ልማቱንና ዕድገቱን ረስተውት ዝቅተኛ ግምት የሰጡት (Marginalized) የሆነ እንደነበር ተወስቷል።

[1]ዶ/ር አያሌው ገብሬ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሶሲዮሎጂ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በሶሻል አንትሮፖሎጂ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንዲሁም የዶክትሬት (Ph.D.) ዲግሪያቸውን ከኔዘርላንድ ISS አግኝተዋል።። ዶ/ር አያሌው ገብሬ በከረዩ አርብቶ አደሮች ላይ "Pastoral Transformation" የሚል የምርምር ጽሑፍ ያበረከቱ ሲሆን፣ የተለያዩ የምርምር ጽሑፎችን በመጻሕፍትና በሌሎች የህትመት ውጤቶች ላይ ያቀረቡ ናቸው።።

በዚህም ምክንያት የአርብቶ አደር አካባቢዎች በልማት ወደኋላ የቀሩ፣ ማህበራዊ ተቋማት (ትምህርት፣ ጤና፣ መሠረተ ልማት፣ (መንገድ፣ ስልክ፣ ገበያ፣) የሌሉባቸው እንደሆኑና፣ በተጨማሪም እነዚህ አካባቢዎች ያሉባቸው መልከዓ ምድራዊና ኤኮሎጂያዊ ገጽታዎች ታክለውባቸው የአርብቶ አደር አካባቢዎች በአብዛኛው ለድርቅና ርሃብ የተጋለጡ መሆናቸው፣ የምግብ ዕጥረትም አንዱና ዋነኛ ችግር መሆኑ፣ ይህም ችግር የአርብቶ አደር አካባቢዎች ራሳቸውንና በውስጣቸው የሚገኙትን ማህበረሰቦች የሚደግፉ (Viable) የመሆን አቅማቸውን ያደከሙና አሁንም የሚፈታተኗቸው መሆኑ ተብራርቷል።

በእኔ እምነት በእዚህ ክፍል ውስጥ የተብራሩት ሃሳቦች በአብዛኛው በመረጃ የተደገፉና የተለያዩ ጥናቶችም ያረጋገጧቸው በመሆኑ ከሞላ ጎደል የምንስማማባቸው ናቸው። ሆኖም ግን እዚህ ላይ ጥቂት ጽንሰ ሃሳባዊ ይዘት ያላቸው አመለካከቶችን ላነሳ እወዳለሁ።

በመጀመሪያ አርብቶ አደር (Pastoralism) የሚለው ስያሜ ለዚህ የኑሮ ፈርጅ (Livelihood system) ሙሉ በሙሉ ገላጭ አይደለም። አርብቶ አደር የሚባለው የዚህን የኑሮ ዘይቤ አንዱን ገጽታ ብቻ የሚያሳይ ነው። ይህም ማለት በዚህ የኑሮ መስክ የተሰማሩ ማህበረሰቦች ህዝቦች የእንስሳት እርባታን ዋና መሰረታቸው ያደረጉና ከአመታዊ ገበያቸው እጅግ ላቅ ያለውን ከእንስሳትና ከእንስሳት ተዋጽኦ የሚያገኙ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው። እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦዎችም ከዚህ አልፎ ለእለት ተዕለት የምግብ ፍጆታቸው ዋና መሰረቶችም ናቸው። በተጨማሪም እንስሳት በተለይም ከብቶች በባህላዊና ዕምነታዊ ስርዓታቸውም ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ አሏቸው። በዋናነት ግን ይህ አርብቶ አደር የሚለው ሥያሜ የሚጠቁመው ሌላው ተጨማሪ ሃሳብ በዚህ የኑሮ ዘርፍ የተሰማሩ ህዝቦች እንስሶቻቸውን የሚያረቡት በጋራ በሚጠቀሙበት የተፈጥሮ ግጦች መሬት እንጅ በተጣሩና (Fenced) በዘመናዊ መልክ በሚተዳደሩ ራንች (Ranch) መሰል መስኮች ወይም እንስሳቶቻቸውን በተወሰኑ አካባቢዎች ከልለው የእርሻ ውጤቶች በመመገብ አይደለም። ይህ ከሆነ ደግሞ የዚህ የኑሮ ፈርጅ ዋና መሰረቱ አርብቶ አደሮች ለእንስሳታቸው ሲባልና የተፈጥሮ ሃብትንም (ግጦሽና ውሃን) በአግባቡ ለመጠቀም ከቦታ ቦታ መንቀሳቀሳቸውን የግድ ይላል። ይህ ተንቀሳቃሽነት የአብዛኞቹ አርብቶ አደሮች (የኢትዮጵያንም) ጨምሮ ዋና ስልታቸው ነው። ለዚህም ነው (Pastoralism) ከማለት ይልቅ በእንደኛ ሃገር ባለ ሁኔታ (Nomadic Pastoralism) ወይም (Migratory Pastoralism) የሚባለው። ይህም እንዳለ ሲተረጉም ተንቀሳቃሽ አርብቶ አደር ማለት ነው። ስለዚህ እንደ ጽንሰ ሃሳብና ሥያሜ ይህ ነጥብ ሊተኮርበት ይገባል።

ሁለተኛውና ዋናው ጽንሰ ሃሳቢው አስተያየት በተለይ አርብቶ አደሮችን በተመለከተ የሚወጡ የልማት ፓሊሲዎችና ጥረቶች አትኩሮት ሊሰጡት የሚገባው ጉዳይ ነው። የዚህም ጉዳይ አንደኛው ገጽታ አርብቶ አደሮች ምንም እንኳን ዋናው የኑሮ መሠረታቸው እንስሶቻቸው ቢሆኑም በተለይ በአሁኑ ግዜ በከብቶችና በከብቶች ተዋጽኦ ላይ ብቻ ተመርኩዞ የሚኖር አንድም የአርብቶ አደር ማህበረሰብ የለም። እንዲያውም ብዙ አርብቶ አደሮች በኢትዮጵያም ጭምር ከእንስሳት እርባታው ጎን ለጎን እንደ አካባቢያቸው ሁኔታ ገቢዎቻቸውን ሊደጉሙላቸው በሚችል የተለያዩ የገቢ ምንጭ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋል በእርሻ (የዝናብና መስኖ)፣ በንግድ (ህጋዊና ህገወጥ (ኮንትሮባንድ)፣ በዕደ ጥበብ፣ ደንና የደን ውጤቶችን

በማምረት (ሙጫ፣ ዕጣን የመሳሰሉትን) ጨውና የማዕድን ውጤቶችን በማምረትና በመሸጥ፣ እንዲሁም በእርሻ፣ በፋብሪካ፣ በጥበቃ፣ በውትድርና በቅርብና በርቀት ተቀጥረው በመስራት (Wage labour) ገንዘብን ለዘመድና ቤተሰብ በመላክ ይሰማራሉ። ስለዚህ ስለአርብቶ አደሩ ስናስብ በእነዚህ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች እነዚህን ሁሉ የተለያዩ የገቢ ምንጭ አማራጮች እንደየሁኔታውና አስፈላጊነቱ ከእንስሳት ርባታው ጎን ለጎን ለመጠቀም የተዘጋጁና እየተጠቀሙበትም ያሉ መሆኑን ጭምር ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊቀረብ የሚገባውና በአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጅዎችም ውስጥ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚያስፈልገው ጉዳይ የአርብቶ አደሮች የአኗኗር ዘይቤ (Livelihood system) የጋራ የሆኑ ባህሪያት ቢኖሩትም አንድ ወጥና ተመሳሳይ አለመሆኑ ነው። አርብቶ አደርነት (Pastoralism) የተለያዩ ገጽታዎችን በተለያዩ አካባቢዎች ሊላበስ እንደሚችልና ሰዎችም በተለያየ መልክና መጠን ሊሰማሩበት የሚችል መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። የነዚህ የተለያዩ ገጽታዎች መንስኤዎች ብዙ ናቸው። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል የኑሮ ፈርጁ የሚካሄድበት አካባቢያዊና ኢኮሎጂያዊ ሁኔታ፣ ለኑሮ አስፈላጊ የሆነ የተፈጥሮ ሃብቶች ብዛት፣ ጥራትና ሥርጭት፣ የኑሮ ፈርጁ ከሌሎች የኑሮ ፈርጆች ጋር ያለው ትስስርና ግንኙነት፣ ማህበራዊና ባሕላዊ ሁኔታዎቹ፣ ነዋሪዎቹ የሚያራቧቸው የእንስሳት አይነቶችና ሥብጥራቸው፣ እንስሶችን በአግባቡ ለማራባት የሚደረገው የሰዎችና የከብቶች እንቅስቃሴ መጠን፣ ርቀት፣ የግዜ ብዛትና የሚከተለው ሥራዕት፣ ከአካባቢና ማዕከላዊ መንግስታት ጋር ያለው ታሪካዊ ቁርኝት፣ እንዲሁም ከገባያና ከገበያ ተቋማት ጋር ያለው የትስስር መጠን ሊጠቀሱ ይችላሉ። ስለዚህ ስለ አርብቶ አደር አካባቢዎችና ህዝቦች ልማት ሲታሰብ የእያንዳንዱ አርብቶ አደር አካባቢና ህዝብ ልዩ ሁኔታዎች ታሳቢ ተደርገው የልማት ትኩረቱና አቅጣጫውም በዞን ወይም በአካባቢ ያነጣጠረ መሆን እንዳለበትና ለሁሉም አካባቢዎች የሚሆን ሁሉንም አንድ አድርጎ የሚወስድ መሆን እንዳሌለበት ነው።

በጽሁፍ ሁለተኛና ሶስተኛ ክፍሎች የቀረቡት ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆኑ ይዞታቸውም በአርብቶ አደር አካባቢዎች የተካሔዱት የልማት ፕሮግራሞች ምን ይዘት እንደነበራቸውና፣ የእነዚህ ፕሮግራሞች ውጤት ምን ይመስላል የሚለውን መዳሰስና ተሞክሮዎችን ማሳየት ነው። በዚህ ዳሰሳ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠውና (ሊሰጠውም ይገባ ስለነበር) ደካማ ጎኖቹና ለውጤታማነቱ አናሳ መሆን ምክንያቶቹ የተብራሩበት በአገራችን ከ1960 ዎች (እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር) አጋማሽ ጀምሮ እስከ 1990 መጀመሪያ ድረስ የዘለቀው የእንስሳትና የግጦሽ መሬት ልማት ፕሮጀክቶች (Livestock and rangeland development) ነበሩ። እነዚህም የመጀመሪያው፣ ሁለተኛው፣ ሶስተኛው እና አራተኛው የከብት ሃብት ልማት ፕሮጀክት ሥር የተዋቀሩ በሶማሊያ፣ በአፋርና በቦረና የተካሄዱ የግጦሽ መሬት ልማት ንዑስ ፕሮጀክቶች ናቸው። የእነዚህ የልማት ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ትኩረት በተለይም በንጉስ ዘመን የመጨረሻ 10 ዓመታት የነበረው፣ የአርብቶ አደሩን ንዑስ የኢኮኖሚ ዘርፍ ከአገሪቱ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ጋር እንዲተሳሰር ለማድረግና የከበት ንግድን ከፍተኛ ገበያዊና ንግዳዊ መልክ (Commercialization of livestock production) በመስጠት አርብቶ አደሮች ምርታቸውን በማሳደግና ከብቶቻቸውን በስፋት ለገበያ በማቅረብ ከዚህ ዘርፍ የሚገኘውን የውጭ የከብት ገበያ ንግድ ገቢን ማሳደግ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው የሚባሉ ቴክኒካዊ ግብዐቶች ለምሳሌ፣ የውሃ ማልማት፣ የከብቶች ጤናና

ሕክምና አገልግሎት፣ የግጦሽ መሬት ልማትና አስተዳደር፣ የእንስሳት መንገዶች፣ ማቆያ ቦታዎች፣ ገበያዎች፣ የዕርድ ቦታዎች ወዘተ... በማስፋፋት ነበር።

ሆኖም ግን በቀረበው ጽሁፍ መሠረት የእነዚህ ኘሮጀክቶች ውጤቶች አመርቂ አልነበረም። እንዲውም ከአስገኛቸው ጠቀሜታዎች ይልቅ ያስከተሏቸው ጥፋቶች አመዝነው የታዩበት ሁኔታ ነበር የነበረው። ይህም ማለት እነዚህ ኘሮጀክቶች በእንስሳት ጤና አጠባበቅና እንስሳትን ለገበያ ለማቅረብ የሚያግዙ የእንፍራስትራቸር አገልግሎቶች በማቅረብ ረገድ መጠነኛ ስኬት የታየባቸው ቢሆኑም ባብዛኛው ያልተሳኩ ነበሩ። ለዚህም ውድቀት በዋናነት የሚጠቀሱት ምክንያቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ የሚባሉትን አርብቶ አደሮችና በእንስሳት ንግድ ሥራ የተሰማሩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ያላማከሩና ተሳታፊ ያላደረጉ መሆናቸው፣ አርብቶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን የኑሮ ፈርጅ ማሻሻልና ማሳደግን ሳይሆን እንስሳትንና የእንስሳት ንግድ ማስፋፋትን ማዕከል አድርገው የተቀረፁ መሆናቸው፣ የአርብቶ አደሮችን የቆዩ የእንስሳት ሃብትና የተፈጥሮ እንክብካቤ ዕውቀትና ግንዛቤዎችን ባሕላዊ ተቋማትን ግምት ውስጥ በማስገባት በእነሱም ለመጠቀም የተዘጋጁ አለመሆናቸው፣ በተጨማሪም አዘገጃጀታቸውና አፈጻጸማቸው ከላይ ወደታች እንጅ ከታች ወደላይ ያልነበር በመሆኑና የተንዛዙ በመሆናቸው ነበር። በተጨማሪዋ በውጭም በውስጥም ምክንያቶች የተከሰቱ ግጭቶችና የፀጥታ ችግሮች ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተደራራቢነት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ተብራርቷል።

እነዚህ ኘሮጀክቶች በተመሳሳይ መልኩ በደርግ ግዜ የቀጠሉ ቢሆንም አላማና አፈፃፀማቸው ግን የአገሪቱ አጠቃላይ የልማት ፖሊሲዎች በዕዝ ወደሚመራ ሥርዓት በመቀየራቸው ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወደቁ። በተግባር ያልተሳካ ቢሆንም የደርግ መንግስትም አርብቶ አደሮችን በማስፈርና በቋሚ ቦታዎች ላይ እንዲወሰኑ (Sedentarize) በማድረግ ግዙፍ የከብት ሃብት ልማት ኘሮጀክቶች መስፋፋትን አላማ አድርጎ ነበር።

በእርግጥም ከላይ የተዘረዘሩትን ምክንያቶች ለእነዚህ ሁሉ ኘሮጀክቶች ውድቀት በምክንያትነት መጠቀሳቸው አግባብነት አለው። በእኔ ግምት ምክንያቶቹ በአብዛኛው ትክክል ናቸው። በጎ ጎናቸውና ተሞክሯቸው በዚያው መጠን ትኩረት ያልተሰጠው ቢሆንም። ስለዚህም የአርብቶ አደሩን የአኗኗር ዘይቤ (Livelihood) ለመለወጥ ታቅደው የተፈጸሙ ኘሮጀክቶች የተሳካ ውጤት አላመጡም። እንዲያውም የአርብቶ አደሩን የተፈጥሮ ሃብት መሰረት ለማስፋት በሚል ታሳቢነት የተፈፀሙ የውኃ አጠቃቀም ኘሮጀክቶች ለእነዚህ አካባቢዎች የተፈጥሮ መራቆት ምክንያት ሆነው ተገኙ። የእንስሳት ንግድን ለማስፋት የተወጠኑትም ዕቅዶች በአርብቶ አደሮች መካከል ያልተመጣጠነና ከፍተኛ የሃብት መበላለጥ በመፍጠር ችግሩን አባባሱት።

በዚህ ምክንያት በአርብቶ አደር አካባቢዎች ያለው ዋናው ችግር የእነዚህ ቀደም ሲል የተሞከሩ የልማት ኘሮጀክቶች ቴክኒካዊ ውድቀት (Technical failure) ሳይሆን የአርብቶ አደር አካባቢዎችና የአርብቶ አደር ጉዳዮች በመንግስታት የዕድገት አጀንዳዎች ውስጥ ትኩረት አለማግኘታቸው ነው። በዕርግጥ በዚህ ጽሁፍ አቅራቢዎች እንደተገለፀው በተለይ ከ1991 በአገራችን የመንግስት ለውጥ ከተካሄደ በኋላ አርብቶ

አደሩን በተመለከተ አበረታችና ተሰፋ ሰጭ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው። ከነዚህም መካከል አርብቶ አደሮች በሚኖሩባቸው ቦታዎች አካባቢ መሬትን ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የመጠቀም ነፃ መብትና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው ህገመንግስታዊ ዋስትና ማግኘቱ፣ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ዕቅድ የአጠቃላይ የአገር ልማት ዕቅድ አካል እንዲሆን መደረጉ (ለምሳሌ፤ ከ2000 - 2004 ከ 2005 - 2009 በታቀዱ የአምስት አመት ዕቅዶች አካል መሆኑ)፣ ይህንንም ለማስፈፀም በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ጽ/ቤት ሥር የሚሰራ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ክፍል መቋቋሙና በግብርና ሚኒስቴር ሥርም የፖሰቶራል ኤክስቴንሽን ዩኒት መመስረቱ በተዋረድም አርብቶ አደሮች ይኖሩባቸዋል በሚባሉ ክልልሎች ተመሳሳይ ተቋማት እንዲኖሩ መደረጉ፣ በአገሪቱ የገጠር ልማትና ግብርና ጋር በተያያዘ ትምህርትና ሥልጠና በሚሰጡ ተቋማት ውስጥ አርብቶ አደሩን በተመለከተ የሚከናወኑ ጥናትና ምርምሮች መበረታታቸው የሚጠቀሱ ሲሆን በተጨማሪም በፌደራል ፖርላማ ውስጥ ለአርብቶ አደሮች መብትና ጥቅም፣ ዕድገት የሚከራከር የአርብቶ አደሮች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ እንዲኖር መደረጉ እንደ አንድ እምርታ ይቆጠራል።

ከዚህ ጋር ተያይዞም በመንግስት ተዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ያለው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ኘሮጀክት (Pastoral Community Development Project) በየአምስት አመታት ለሶስት አምስት አመታት የተዘጋጀው ዕቅድ ሌላው የሚጠቀስ ነው። ይህ ዕቅድ በተለይ አርብቶ አደሮች በስፋት ይኖሩባቸዋል በሚባሉበት በአፋር፣ በሱማሌ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ህዝቦች ክልል ላይ ያተኮረ ሆኖ ከአለፉት ኘሮጀክቶች ልምድ በመውሰድ የአርብቶ አደሩን ኑሮ ማሻሻልን ማዕከል አድርጉ ድህነትን ለመቀነስና ለድሃ አርብቶ አደሮች ትኩረት በመስጠት የምግብ ዋስትናን ለማሻሻል አፈፃፀሙንም አሳታፊ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የአርብቶ አደሮችንም የቆዩ ተሞክሮዎችና ግንዛቤዎች እንዲሁም አካባቢ በቀል ዕውቀቶች አስፈላጊ መሆናቸውን ዕቅዱ እንደሚቀበል ተገልጿል።

ዕቅድ ግን ስለአርብቶ አደሩ የኑሮ ዘርፍ አመራረትና አወቃቀር በቂ ዝርዝር አለመስጠቱ ምናልባትም ስለዘርፉ የዕውቀት ክፍተት መኖሩን የሚጠቁም ሊሆን እንደሚችል ሲገመት፣ በተጨማሪም የተለያዩ አርብቶ አደር አካባቢዎችን ልዩ ባህሪያት (Socio-economic system) ግምት ውስጥ ሳያስገባ ተመሳሳይ ችግርና ተመሳሳይ መፍትሄ የሚሹ አድርጎ የሚወሰድ መሆኑ ሌላው ችግር ነው። ለዚህም በረጅም ጊዜ ግቡ አርብቶ አደሮች በአንድ አካባቢ ሰፍረው (Sedentarize) የመስኖ እርሻን መሰረት ያደረገ አኗኗር እንዲከተሉ ማድረግን ለሁሉም የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች እንደመፍትሄ ማቅረቡ ተጠቃሽ ነው። ስለዚህ ይህ እቅድ ወደ ዝርዝር የአፈፃፀም ፖኬጆች ከመተርጎሙ በፊት በቂ ምክክርና ውይይት ከሚመለከታቸው አካላትና የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ጋር ማድረግን ይጠይቃል። እቅዱ ተግባራዊ የሚሆንባቸው የአርብቶ አደር ወረዳዎች ለኑሮ አስቸጋሪ ከመሆናቸው አንፃርም እቅዱን በተግባር ለመተግበር ለሚሰማራው የሰለጠነ የሰው ኃይል ምቹ የሥራ ሁኔታ መፍጠርም ራሱን የቻለ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

በጽሁፉ ክፍል አራት ላይ የተነሳው ነጥብ አርብቶ አደርነት አሁን ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለው ነው። በአቅራቢው እምነት ለዘመናት ያለ ብዙ ችግር ሲራመድ የቆየውና በአኗኗር ዘይቤው ለተሰማሩት ነዋሪዎችም የኑሮ መሰረታቸው ሆነ የቆየው አርብቶ አደርነት አሁን ከፍተኛ ችግር (Crisis) ላይ ወድቋል። ድህነት፣ የምግብ ዋስትና አለመኖር፣ የነፍስ ወከፍ ቤተሰብ አመታዊ ገቢ ከግዜ ወደ ግዜ ማሽቆልቆል፣ የአካባቢ መራቆት የአርብቶ አደር አካባቢዎች መለያ ምልክት ሆነዋል። ይህም ብቻ ሳይሆን በከብት ሃብት ብዛታቸውና ጥራታቸው በሚታወቁ አርብቶ አደር አካባቢዎች ሳይቀር የነፍስ ወከፍ የከብት ሃብት መጠን ተመናምኗል። የህዝብ ብዛት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል፣ በተለያዩ መልኩ ለመተጋገዝ፣ ለመረዳዳት፣ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት የሚያስችሉ ባህላዊ ተቋሚትን እየተዳከሙ መጥተው የሚሰጡትም አገልግሎት እንዲሁ እናሳ ሆኗል። በሌላ በኩልም የአኗኗር ዘርፉ ያለበትን ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ተስፋ ሰጭ ሁኔታዎች እንዳሉ ተጠቅሷል። አርብቶ አደሮችና የአርብቶ አደር አካባቢዎች በልማት ፖሊሲ አውጭዎችና አስፈፃሚዎች ለዘመናት የተረሱ በመሆናቸወ ምክንያት አሁን ባሉበት ሁኔታ አስገዳጅነት አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ትኩረት እንዳገኙ የሚጠቁም ሁኔታዎች መፈጠራቸው፣ በመንግስትም የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት እንደ አንድ የልማት አጀንዳ መወሰዱ፣ እንዲሁም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በአርብቶ አደር ልማት ለማሳተፍ ተነሳሽነት ማሳየታቸው እንደ በጉ ሁኔታ ተጠቅሷል።

በእርግጥም የኢትዮጵያ አርብቶ አደር አካባቢዎችና ማህበረሰቦች በአስቸጋሪ ሁኔታ (Crisis) ላይ ይገኛሉ። ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ የመጣ ድህነትም ዋንኛ መለያቸው ሆኗል። ለዚህም ሶስት ምክንያቶችን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል።

1. በአብዛኛው አርብቶ አደሮች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች በተፈጥሮ ሃብት መጠንና ሥርጭታቸው ዝቅተኛና ደሃ ሊባሉ የሚችሉ አካባቢዎች (Resource - poor environment) ናቸው። በእነዚህ አካባቢዎች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ የተፈጥሮ ሃብት መጠንና የአርብቶ አደሮችም ምርታማነት ከዝናብ መጠንና ሥርጭት ጋር የተቆራኘ ነው። ዝናብ ሲያንስ ወይም ሲጠፋ የከብቶች መሞትንና የምግብ ዋስትና ማሽቆልቆልን ያስከትላል። ዝናብ በበቂ ሲኖር የአርብቶ አደር አካባቢዎች በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።
2. በተሳሳቱና ተጨባጭ ሁኔታውን ባላገናዘቡ የአርብቶ አደሩን ችግሮችና ፍላጎቶች ግምት ውስጥ ባላስገቡ የልማት ዕቅዶችና ተፈፃሚነታቸው ምክንያት አሁን ያለበትን አስቸጋሪ መከራ እንዲቀበሉ መደረጋቸው፣ በእነዚህ ፖሊሲዎች ምክንያት የኑሮ መሰረታቸው የሆነው መሬት እንዲያጡ መደረጉና ከግዜ ወደግዜ መጠኑ በማነሱ ከዚህ ጋር ተያይዞ የመጣው የተፈጥሮ ሃብት መራቆት፣ እንዲሁም በተግባር የዋሉ የእንስሳት ሃብት ልማትና የግጦች መሬት አስተዳደር ስልቶች ቴክኒካዊ ውድቀትና ያስከተሉት ጣጣ፣
3. በአኗኗራቸው ዘይቤ ምክንያት ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል ተቆርጠው የቀሩና ምንም አይነት ተደማጭነት የሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች (Politically marginalized) መሆናቸው፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ እራሳቸው መንግስታቶቹ ቀርጸው በተግባር ያዋሉት የልማት ዕቅድ ፋይዳ ያላመጣ መሆኑን ሲያውቁ በቦታው ምንም ነገር ሳይተኩ እንዳሻቸው ይሁኑ በሚል በመንግስት በኩል ችላ

የተባሉ መሆናቸውና እንዲያም ሲል ፍላጉቱ ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲያግዟቸው እጣ ፈንታቸው ለእነሱ የተተወ መሆናቸው ነው።

በመጨረሻም በቀረበው ጽሁፍ ማለቂያ ላይ የተነሳው ጉዳይ የአርብቶ አደር አኗኗር ዘይቤ (Pastoral livelihood system) በ2020 ምን መልክ ይኖረዋል የሚል ትንበያና እይታ ነው። በዚህ ረገድ እንዳቅራቢው ዕምነት በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚገኘው ለእንስሳት እርባታ የሚፈለገው የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ ከተያዘና ሊሸከመው የሚችለውን የሰውና የእንስሳት መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት ጥቅም ላይ ከዋል ለአርብቶ አደሮች አስተማማኝ (viable) የኑሮ መሰረት ሆኖ ሊቀጥል ይችላል። በዚህ ላይ የመንግስት በጉ አመለካከትና የአርብቶ አደሮችም ከግዜ ወደግዜ በድርጅትና በአቅም እየጎለበቱ፣ እያደጉ መሄድ ለዚህ ለተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ተጨማሪ እገዛ ያደርጋል። በዚህ ሂደትም መንግስተ የዚህን የኑሮ ዘርፍ አስፈላጊነትና ለብዙ ሰዎች የኑሮዋቸው አማራጭ የኤኮኖሚ ዘርፍ ሆኖ ሊቀጥል እንደሚችል እየተረዳና እየተቀበለው ይመጣል። በዘርፉ የተሰማሩ ሰዎችንም በዘለቄታዉ ሊጠቅም እንዲችል የሚያስፈልገውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ እንዲሁም የፖሊሲ ድጋፉን ይቀጥላል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በየአካባቢው የሚኖሩ አርብቶ አደሮች እንደሚኖሩበት አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ከአርብቶ አደርነት ጎን ለጎን ተጓዳኝ የኑሮ መስኮች፣ ኢኮኖሚያዊ አማራጭ የሥራና የገቢ ማግኛ መስኮች (Livelihood and economic diversification) የሚገቡበት ሁኔታ ተፈጥራል። በተለይም በአንዊራዊ ሃብታም የሚባሉት የእነዚህ ማህበረሰቦች አባላት ይህን እንደአማራጭ ይጠቀሙበታል። በዚህ ሂደትም በክልላዊና ፌደራል መንግስታት ድጋፍ በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች የሚሰጡ የማህበራዊ ተቋማት (ትምህርት፣ ጤና፣ መንገድ፣ መገናኛ ዘዴዎች) እየተስፋፉ ይመጣሉ። አዲሱ የአርብቶ አደር ትውልድም በትምህርትና ሥልጠና የተሻለ ደረጃ ላይ የደረሰ ይሆንና የአርብቶ አደሮችን የኑሮ ዘርፍ በተሻለና በዘርፉ የተሰማሩትን ሰዎች በቅጡ ሊያግዙ የሚችል እንዲሆን በሚደረጉ ሂደት ላይ ንቁ ተሳታፊ ይሆናል።

ይህ በሚሆንበት ግዜም ቀደም ሲል የነበሩት የአርብቶ አደር አካባቢዎችና የግብርና አካባቢዎች፣ በአርብቶ አደር የገጠር አካባቢዎችና ከተማዎች መካከል የሚኖረው የመደጋገፍ ግንኙነት ይጎለብታል። በዚህም በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚገኙ ምርቶች አካባቢያዊ ገበያ ብቻ ሳይሆን ከብሄራዊና አለማቀፋዊ ገበያዎች ጋር የሚተዋወቁበት ሁኔታ ይመቻቻል። ከአጉራባች አገሮች አርብቶ አደር አካባቢዎች ጋርም የተፈጥሮ ሃብትን በጋራ መጠቀም፣ የጋራ ገበያ፣ እንዲሁም የአመራረትና የአሠራር ዕውቀትና ልምዶችን የመካፈልና የመጋራት ሁኔታ ይፈጠራል።

እዚህ ላይ ላነሳቸው የምፈልገው ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ። አንደኛው አርብቶ አደሮች ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ በቂ የግጦሽ መሬት ከአጎራባች አርብቶ አደሮች ወይም ድንበር ዘለው ጎረቤት አገር ካሉ አርብቶ አደሮች ጋር የተፈጥሮ ሃብት በጋራ የመጠቀም ሁኔታ አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል። ይህ ከቦታ ቦታ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ አርብቶ አደሮችን ለአስተዳደርና ለቁጥጥር የሚያመቹ፣ ለታክስ ሥርዐት ተገዥ ያልሆኑ፣ ማህበራዊ አገልግሎትም ለማቅረብም እንደዚሁ አስቸጋሪ ናቸው ተብሎ ይታመናል። በዚህም

ምክንያት ነው አንድ አካባቢ መስፈርና ተረጋግተው መሬት ይዘው (sedantarized) መሆን አለባቸው የሚባለው። ይህን ጉዳይ አቅራቢዎቹ በእይታ መልክ እንዴት ያዩታል።

ሌላው ጉዳይ በተለይ ከተፈጥሮ ሃብት መመናመንና ከግዜ ወደግዜ እያነሰ መምጣት ጋር ተያይዞ በአንድ አርብቶ አደር ማህበረሰብና በሌላ አርብቶ አደር ማህበረሰብ፣ በአንድ አርብቶ አደር ማህበረሰብ በሚገኙ ጉሳዎች መካከል፣ በአርብቶ አደር ማህበረሰብና በግብርና በሚተዳደሩ ማህበረሰቦች፣ ከዚያም አልፎ ከአጉራባች አገር ማህበረሰቦች ጋር የሚካሔዱ ግጭቶችና እነዚህም በልማት ላይ የሚያስከትሉት አሉታዊ ሁኔታ ምን መልክ ይይዛል። በዚህ ላይ እይታው ምንድን ነው?

ከላይ በእይታ (Vision) መልክ የቀረቡትን ጉዳዬች ከሞላ ጎደል የምንቀበላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በተጨማሪ ግን ትኩረት ሊቸራቸው የሚያስፈልጉ የሚከተሉትን ነጥቦችን ለማንሳት እወዳለሁ።

አንደኛ የአርብቶ አደሩ የአኗኗርና የአመራረት ዘይቤ ከሌላው በተሻለ ያለው ንጽጽራዊ ጠቀሜታ (Comparative advantage) በጣም የተበታተነና በአንፂራዊም ደሃ ሊባል ከሚችል የተፈጥሮ ሃብት ነዋሪዎቹ ለህይወታቸው የማያስፈልጋቸውን ገቢ እያገኙ እንዲጠቀሙ ማስቻሉ ነው። እንደብዙዎቻችን እምነት እነዚህ አርብቶ አደሮች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች ከዚህ የአኗኗርና የአመራረት ዘዴ ወጭ የሚጠቀምባቸው አጥተው፣ ባክነው ሊቀሩ የሚችሉ ወይም ቢጠቀሙባቸውም በከፍተኛ ወጭና ተያይዘው ከሚመጡ አካባቢያዊ ቀውሶች ጭምር ጋር ነው የሚሆነው። አርብቶ አደሮች ግን እነዚህን አካባቢዎች ያለምንም ችግር ነው ባይባልም የኑሮ መሰረታቸው አድርገው ለረጅም አመታት ተጠቅመውባቸዋል። ለወደፊትም እነዚህን አካባቢዎች አስተማማኝ (Sustainable or viable) በሆነ መልኩ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ ወይ? የሚለው ጉዳይ ግን አጠያያቂ ነው።
የአርብቶ አደር አካባቢዎች ምርታማነት የሚጨምረውና የሚቀንሰው በአካባቢው ከአለው የዝናብ ሁኔታ ጋር ቢሆንም እነዚህ አካባቢዎች በብቃት ሊሸከሙትና ሊያስተናግዱት የሚችሉት የሰውና የእንስሳት ብዛት ግን ውሱን ነው። የአርብቶ አደሮች የኑሮ ዘይቤ (Livelihood) የተሻለ ውጤታማና ነዋሪዎቹን በአግባቡ ሊደግፍ የሚችለው የህዝብ ብዛት አነስተኛ ወይመ መካከለኛ ብቻ ሲሆን ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ምንም እንኳ ከግብርና አካባቢዎች አንፂር ሲታይ የአርብቶ አደር አካባቢዎች በህዝብ መጨናነቅ አንስተኛ ቢሆንም ሁሉም የሚስማማበት ባለፉት 25 ዓመታት በአርብቶ አደር አካባቢዎች የህዝብ ቁጥር በእጥፍ አድጓል። ወደፊትም ከዚህ በላቀ መልኩ ይጨምራል። በእዚህ ላይ ለአርብቶ አደሮች አስተማማኝ የመሬት ይዞታና አጠቃቀም መብት በሌለበት ሁኔታና ከግዜ ወደግዜም መሬታቸው እያነሰ ሲመጣ ይኽ የሕዝብ መጨናነቅ እየባሰ ይመጣል። መጥቶዋልም። ስለዚህ ጥንታዊውና ለረጅም ዘመናት በተግባር የተፈታነው የአኗኗር ዘይቤያቸው አጣብቂኝ ውስጥ ወድቋል - እያደገ በመጣው በህዝብ ቁጥር መጨመርና ይህን ሊደግፍ የሚችለው የተፈጥሮ ሃብት መሰረት ከግዜ ወደግዜ እያነሰ በመምጣቱ። በዚህ መሠረት በአሁኑ ግዜ ብዙዎቹ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ሊደግፉት ከሚችሉት በላይ ህዝብ ተሸክመዋል። ወይም በቅርቡ እዚያ ደረጃ ይደርሳሉ።

ለዚህም የተሻሻለ የፀጥታ ሁኔታ፣ የህክምና አገልግሎት መቅረብ፣ እንዲሁም ረሃብና ድርቅን ለመቋቋም የሚሰጡ የምግብ ርዳታዎች አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ስለዚህ ለወደፊት ያለው አማራጭ ከአርብቶ አደርነት ውጭ ሰዎች አማራጭ የኑሮ መሰረት እንዲያገኙ (Alternative livelihoods) ሊመቻችላቸው ይገባል። የመጭዎቹም 20 ና 30 ዓመታት ፈታኝ ጉዳይም ይኸው ነው። ምክንያቱም አማራጮቹም እራሳቸው ውስጥ ናቸውና።

ዋናው መቀበል ያለብን ሃቅ ግን አርብቶ አደሩ አሁን ያለበትን ችግር በአመዛኙ ለመፍታት ቀላል ሊባል የሚችል መፍትሄ አለመኖሩን ነው። ከረጅም ግዜ አኳያ በመንግስት በኩል የቀረበው ሃሳብ አርብቶ አደሮች በአንድ አካባቢ ተረጋግተውና ሰፍረው እንዲኖሩና በተለይም የመስኖ እርሻን መሰረት ያደረገ የኑሮ ስልት እንዲከተሉ ነው። በዚህ ረገድ የተሳካ ውጤት ያመጡና አርብቶ አደሮችንና «ዘመናዊ ነዋሪዎች» ያደረጉ አገሮች ልምድ የለም፣ ወይም ውስን ነው። አርብቶ አደሮችን በአንድ አካባቢ አስፍሮ (Sedantarize) የኑሮ ዘይቤያቸውን ሙሉ ለሙሉ የመቀየር ሂደት ከአቅምና ከተግባር አንፂር አስቸጋሪና ውድም ሲሆን ለብዙዎች እንደኛ ያሉ ታዳጊ አገሮች በቀላሉ የሚችሉትም አይደለም። ስለዚህ ይህ አማራጭ በይበልጥ ሲጠናና ሌሎች አማራጮች ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክፍሎች ሁሉ ሲመክሩባቸው ተሻሽሎ ሊቀርብ ይችላል።

ስለዚህ ሁላችንም እንደምንጋራው የአርብቶ አደር አካባቢዎች የተጋረጡባቸው ችግሮች ፈታኝና አስቸጋሪ ናቸው። ያም ሆኖ ግን አሁንም ቢሆን በኢትዮጵያ በሚገኙ ቆላማና በረሃማ አካባቢዎች ለሚኖሩ ብዙ ህዝቦች አርብቶ አደርነት አንዱና ዋና የኑሮ መሰረታቸው ሆኖ ይቀጥላል። በተደራጀና በተባበረ ሥልትና ጥረት ይህን የኑሮ ዘይቤ የገጠሙትን ችግሮች ለመቅረፍ በመንግስት፣ ጉዳዩ በሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በራሳቸው በህዝቦች ጭምር ችግሮቻቸውን በልማት አጀንዳነት አስይዞ ያልተቋረጠ ጥረት ማካሔድን ይጠይቃል። በመጨረሻ ግን የአርብቶ አደር አካባቢዎች ራሳቸው የገጠሟቸውን ችግሮች ለመለወጥና እጣ ፈንታቸውን ለመወሰን ሙሉ ኃላፊነቱን መውሰድ ይኖርባቸዋል።

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ሚና[1]

ተመስገን አክሊሉ[2]

1. መግቢያ

ይህ ፅሁፍ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ኃላፊነት ስለ ሀገራችን የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲዳስስ በማሰብ የቀረበ ነዉ። በዚህ መሰረት ፅሁፉ በአምስት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን የመጀመሪያዉ ክፍል መግቢያ፣ ሲሆን ሁለተኛዉ ክፍል ደግሞ ስለ ትራንስፖርት አጠቃላይ ፅንሰ ሃሳብ ላይ ያተኩራል። ምዕራፍ ሶስትና አራት ስለ ሀገራችን የዘመናዊ ትራንስፖርት ዕድገትና ነባራዊ ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ። የመጨረሻዉ ምዕራፍ ለወደፊቱ በሚኖረዉ ርዕይና ትንበያ ላይ የሚያነጣጥር ይሆናል።

2. የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ፅንሰ ሀሳብ

2.1 የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነቶች ክፍፍል /Transport Modes Classification/

እስከአሁን በታየው የሰው ልጅ የቴክኖሎጂ እድገት ታሪክ ውስጥ አምስት አይነት የትራንስፖርት ዘርፎች /Transport Modes/ ይተዋል፡፡ እነዚህም የመንገድ ትራንስፖርት፣ የውሃ ትራንስፖርት፣ የባቡር ትራንስፖርት፣ የአየር ትራንስፖርት እና የቱቦና ተያያዥ መስመሮች /Continuous Flow System/ ናቸው፡፡

የመንገድ ትራንስፖርት በውስጡ በርካታ ክፍሎች ያለዉ ሲሆን የሚጠቀሱት ሞተር አልባና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ተብለው ይመደባሉ፡፡ ሞተር አልባ ከሚባሉት መካከል ደግሞ እግረኛ፣ በእንስሳትና በሰው ኃይል የሚሣቡ እና የሚሽከረከሩ ጋሪዎች፣ ጋሪዎላ /Wheel barrow/ ባለ 2 እና 3 እግር ብስክሌቶች፣ የጭነት እንስሳት /ፈረስ፣ አህያ፣ ግመል፣ በቅሎ፣ ዝሆን ወዘተ.../ እና ሌሎች ተጐታች መሣሪያዎች ናቸው፡፡

ባለሞተር ተሽከርካሪዎች የምንላቸው ደግሞ በጭነት እና በህዝብ ትራንስፖርት ይከፈላሉ፡፡ የጭነት ሲባል ከመለስተኛ ፒክአፕ ተሽከርካሪ ጀምሮ እስከ 500 ኩንታል ድረስ የሚጭኑ የጭነት ተሽከርካሪዎችን

[1] ነሐሴ 5 ቀን 1998 ዓ.ም የተካሄደ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡፡

[2] አቶ ተመስገን አክሊሉ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ ከአስመራ ዩኒቨርስቲ በ1979 ዓ.ም. እንዲሁም ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በክልላዊና አካባቢያዊ ልማት በ1993 ዓ.ም. አግኝተዋል። ከዚህም በላይ በተለያዩ ድርጅቶችና መ/ቤቶች ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ አገልግለዋል። ለመጥቀስ ያህል በአዲስ አበባ ትራንስፖርትና መገናኛ ቢሮ የከተማ ትራንስፖርት ሲስተም መምሪያ ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል። በግል አማካሪነትም የሰሩ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በማስተማር ላይ ይገኛሉ።

/Trucks of lorry/ ያጠቃልላል፡፡ የህዝብ ትራንስፖርት ደግሞ ከሞተር ብስክሌትና የቤት የግል አውቶሞቢል እስከ ከፍተኛው አውቶቡስ /የከተሞች አቋራጭና የከተማ አውቶቡሶች/ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል፡፡ የውሃ ትራንስፖርት በዋነኛነት በሀገር ውስጥ ውሃና በዓለም አቀፍ /ባህር/ ትራንስፖርት ይከፈላል፡፡ የሀገር ውሰጥ ውሃ ትራንስፖርት የሚያካትታቸው የወንዝ፣ ሀይቅ፣ የቦይ /Canals/ እና በትላልቅ ግድቦች /ኩሬዎች/ ላይ የሚደረግ ትራንስፖርት ሲሆን የባህር ትራንስፖርት ደግሞ በሀገራት ባሉ የተለያዩ ወደቦች መካከል በውቅያኖስ/ባህር ላይ ያለውን የጭነትና የህዝብ ምልልስ /ጉዞ/ ያጠቃልላል፡፡

የባቡር ትራንስፖርት በዓለም ላይ በሰው ልጅ አገልግሎት ላይ መዋል የጀመረው ከእንግሊዝ የኢንዱስትሪ አብዮት አካባቢ ከ1810ዎቹና ከ1820ዎቹ በኋላ በመሆኑ የሁለት መቶ ዓመታት ዕድሜ ሊያስቆጥር ተቃርቧል፡፡ የባቡር አገልግሎት በርካታ ዓይነትና ይዘት ያለው ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ በፈረስ ሀይል የሚሣብ የሀዲድ ላይ ባቡርና በመቀጠል በውሃ እንፋሎት የሚሠራ ባቡር ተሠርቶ እንደነበርና ከዚያ የጐዳና ላይ ባቡር /Street Car/ የመጀመሪያዎቹ ባቡር ነበሩ። ከዚያ በኋላ ግን በርካታ የባቡር ዓይነቶች ማለትም መደበኛ የምድር ባቡር፣ የምድር ውስጥ ባቡር /Metro or subway/ ሞኖሬይል /Monorail/፣ ጋይድድ ባስ /Guided Bus/ ትሮሊባስ /Trolley Bus/ ወዘተ… የሚባሉ የባቡር ዓይነቶች ተፈልስፈው ዓለማችንን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ በአጠቃላይ አከፋፈላቸው ቀላል የባቡር አገልግሎት /Light Rail Transit (LRT)/ እና ከፍተኛ ወይም ከባድ የባቡር ትራንዚት /Heavy Rail Transit (HRT) ተብለው ይከፈላሉ፡፡

ሌላውና በዘመናዊነቱ እና የቅርብ ጊዜ ትውልድ ውጤት የሆነው የትራንስፖርት ዓይነት የአየር ትራንስፖርት ነው፡፡ አየር ትራንስፖርት አመጣጡ ከፊኛ /Balloon/ ጋር የተያያዘ ሆኖ ሁለቱ አሜሪካን ወንድማማቾች ያደረጉት ሙከራ ለዛሬው የዓለማችን ቁጥር አንድ ፈጣን የትራንስፖርት አገልግሎት መሠረት ሆኗል፡፡ የአየር ትራንስፖርት በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ በረራ የሚከፈል ሆኖ እንደሌሎቹ በህዝብና በጭነት /Cargo/ አየር ትራንስፖርት ይከፈላል፡፡ በአሁኑ ሰዓት አንድ አብራሪ ብቻ ከሚይዝ አይሮፕላን ጀምሮ እስከ 350 መንገደኞች ይዞ አየርን እየቀዘፈ አድማስን አቋርጦ ዓለምን ማገናኘት የቻለ አይሮፕላን መጠቀም ተችሏል፡፡

በመጨረሻ ላይ አንዱ የትራንስፖርት አይነት የቱቦና ተያያዥ መስመሮች /Continuous Flow System/ የሚባለው ሲሆን ይኸኛው በውስጡ የውሃና የነዳጅ ቱቦ /Water or Petroleum Pipe/ እቃንና መንገደኛን በቋሚ መስመር ላይ የሚያጓጉዝ መሣሪያ /Belt Conveyor/ እና በተለይም በማዕድን ማውጫዎች አካባቢ የምንጠቀምበት አፈር፣ ማዕድን ውሃ በተቀላቀለበት ሁኔታ ከማውጫ ወደ ማጣሪያ ቦታ የሚያጓጉዝ መሣሪያ-ስላሪ ፓይፕ /Slurry Pipe/ የሚባሉት ናቸው፡፡

2.2 ትራንስፖርት ለማህበራዊ-ኢኮኖሚ ዕድገት ያለው አስተዋጽኦ

በሰዉ ልጅ እድገት ታሪክ ዉስጥ ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት የትራንስፖርት ዓይነቶች መካከል የመንገድና የዉሀ ትራንስፖርት ቀዳሚዉን ደረጃ ይይዛሉ። የትራንስፖርት ዘርፍ (Sector) መስፋፋት የሚያስገኛዉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታዉ ከፍተኛ ሆኖ ቢገኝም አንዳንድ ጎጂ ጎኖች ማስከተሉ ግን አልቀረም። እነዚህም የኢነርጂ ሀብት ከፍተኛ ተጠቃሚ (ከ16-35 በመቶ) መሆኑ፣ የአካባቢ የተፈጥሮ ሀብት ብክለት በማስከተል ረገድ ቀዳሚ መሆኑ፣ ከትራፊክ ደህንነት ችግር ጋር በተያያዘ መልኩ በዓለም ላይ ከሚታወቁ ቀዳሚ ገዳይ በሽታዎች እኩል መመደቡ፣ መጨናነቅን በመፍጠር ረገድ ዓለማችንን እያሳሰበ የሚገኝ መሆኑ የሚሉ ናቸዉ።

ትራንስፖርት ለአንድ ሀገር ዕድገት የሚያደርገዉ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነዉ። በዚህ መሰረት ከሀገር ዉስጥ ምርት (GDP) የሚኖረዉ ድርሻ ከሀገር ሀገር የሚለያይ ቢሆንም ከፍተኛ ነው። ለመረጃ የሚከተለውን ሠንጠረዥ ይመልከቱ።

ትራንስፖርት በሀገር ዉስጥና በዓለም አቀፍ ንግድ መስፋፋት ረገድ በገሀድ የማይታይ (invisible trade) ንግድ ዉስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በዚህ ረገድ በብዙ የበለፀጉ ሀገሮች የሚጫወተዉ ሚና የንግድ ሥራ መስፋፋት ዉስጥ 26% ድርሻ እንዳለዉ ተረጋግጧል።

ሠንጠረዥ 1፣ የትራንስፖርት ሴክተር በGDP ዉስጥ ያለዉ ድርሻ

ተ.ቁ No.	ሀገር Country	ከGDP ዉስጥ የትራንስፖርት ድርሻ (%) Share of Transportation in GDP (%)
1	ደቡብ አፍሪካ South Africa	9
2	አልጄሪያ Algeria	8
3	አርጀንቲና Argentina	8
4	ደንማርክ Denmark	9
5	ቤልጅየም Belgium	8
6	ታይላንድ Thailand	6
7	ቱኒዚያ Tunisia	5
8	ታንዛኒያ Tanzania	7
9	ጃፓን Japan	7

10	እንግሊዝ England	8
11	ኢትዮጵያ (የተሰላ) Ethiopia (estimated)	3.43

Source: *The Economist*: The World in Figures, 1978

ትራንስፖርት በኢንቬስትመንት ዉስጥ የሚኖረዉ ድርሻ በበለፀጉትና በታዳጊ ሀገሮች ይለያያል። በበለፀጉት ሀገሮች ዉስጥ አብዛኛዉ መሰረተ ልማት የተሟላ በመሆኑ ኢንቬስት የሚደረገዉ በኦቶሞቲቪ ዕቃዎች ላይ ሲሆን በታዳጊ ሀገሮች ግን በመሰረተ ልማት ግንባታ ላይ ያተኮረ ነዉ። በቋሚ የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ላይ የሚደረገዉ ኢንቬስትመንት ወጪ ድርሻ ከጠቅላላዉ የታዳጊ አገሮች ኢንቬስትመንት ድርሻ ዉስጥ ከ30%- 50% ይይዛል። በበለፀጉ ሀገሮች ግን ይህ ድርሻ ከ15%- 20% ብቻ ነዉ።

የሥራ እድል በመፍጠር በታዳጊ ሀገሮች ካለዉ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተነሳ የሚኖረዉ ድርሻ ከ2%-4% ሲሆን በበለፀጉ ሀገሮች ግን ከ4%-8% ድርሻ አለዉ። ይህ የሥራ ዕድል መፍጠር ለመሰረተ ልማት ግንባታ የሚሰማራዉን የሰዉ ሀይል አያካትትም።

የአንድ ሀገር ህዝብ የኑሮ ደረጃ ሲሻሻል ለትራንስፖርት ያለዉ ፍላጎት (Transport demand) ይጨምራል። በታዳጊ ሀገሮች ያለዉ የነፍስ ወከፍ የጉዞ መጠን በአማካይ በ500 እና በ2,000 ኪ.ሜ. መካከል ሲሆን በበለፀጉት ሀገሮች ከ7,000 ኪ.ሜ. እስከ 10,000 ኪ. ሜ ይሆናል። የአሜሪካኖች ግን ከ17,000- 20,000 ኪ.ሜ. በዓመት እንደሚጓዙ ይታወቃል። ከአሜሪካኖች ቀጥሎ የኖርዌይ፣ ሆላንድ፣ ኒዉዝላንድ፣ የፈረንሳይና እንግሊዝ ዜጎች የቅደም ተከተል ደረጃ ይዘዋል።

ከዜጎች የገቢ ደረጃ መጨመር ጋር ትራንስፖርት ሴክተር ዉስጥ የሚንፀባረቅ ትልቁ ነገር ቢኖር የግል አዉቶሞቢል ባለቤትነት (Motorization) መጨመር ነዉ። በዚህ ረገድ በደረጃ ሰንጠረዥ ስናስቀምጥ በ1980ዎቹ በበለፀጉ ሀገሮች ለ1000 ህዝብ ያለዉ የተሽከርካሪ ብዛት ከ550-600 ደርሷል። በዚህ መሰረት አሜሪካ (USA) ቀዳሚ ሲትሆን በመከተል ፈረንሳይ፣ አዉስትራሊያ፣ አስትሪያና እንግሊዝ ይጠቀሳሉ። ይህ ገፅታ በከተሞች በተመሳሳይ መልኩ ይንፀባረቃል። የህዝቦች የገቢ ደረጃ ከፍ ሲል የህዝብ ትራንስፖርት ከመጠቀም የግል ተሽከርካሪ መጠቀም እያመዘነ ይሄዳል።

በምሳሌነት ብንመለከት በአሜሪካ የመንገድ ትራንስፖርት ድርሻ በህዝብ ማጓጓዝ 92 ከመቶ ሲይዝ በጭነት ማመላለስ ግን 25 ከመቶ ብቻ ድርሻ አለዉ። የባቡር አገልግሎት ደግሞ በህዝብ ማመላለስ ከ1 ከመቶ ያልበለጠ ድርሻ ሲኖረዉ በጭነት ማመላለስ ግን 43 ከመቶ ድርሻ ይዟል። በህንድ የመንገድ ትራንስፖርት ድርሻ 48 እና 35 ከመቶ በጭነትና በህዝብ የማጓጓዝ ድርሻ በቅደም ተከተል ሲይዝ የባቡር ትራንስፖርትን በተመለከተ ደግሞ 50 እና 65 ከመቶ በህዝብና በጭነት ማጓጓዝ ድርሻ በቅደም ተከተል ይዘዋል።

ስናጠቃልለዉ የትራንስፖርት ሚና ለዉጭ ንግድ ሚዛን ለመቆጠብና ምንዛሪ የማስገኘት፣ ለመንግስትና ህዝብ የገቢ ምንጭ ሆኖ ማገልገል፣ የሀገር ሰላም፣ ፖለቲካና ደህንነት ለማረጋጋት፣ ገጠርንና የገጠር ምርቶችን ከከተማ ጋር በማገናኘት፣ የገበያ ቦታዎች እንዲበዙና እንዲገናኙ በማድረግ፣ የጉዞ ሰዓት በማሳጠር (Shortening of travel time)፣ ከፍተኛ የህዝብና የጭነት መጠን በማጓጓዝ፣ ለዓለም ቱሪዝም፣ መዝናኛ፣ ስፖርትና ሰላማዊ ግንኙነት በማስፋፋት እያደረገ ያለዉ አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ነው። አለም የኮሙኒኬሽኑንና የትራንስፖርት ዘርፎችን በመጠቀም አንድ መንደር ሆናለች። አምስቱ የሰዉ ልጅ ያለባቸዉ አህጉሮች በደቂቃና በሰዓታት ልዩነት መገናኘት ችለዋል።

3. የኢትዮጵያ ዘመናዊ የትራንስፖርት ዕድገት አጭር ታሪክ

3.1 ከሚኒልክ ዘመነ መንግሥት እስከ ደርግ ዘመን መጨረሻ

በሀገራችን ስለዘመናዊ ትራንስፖርት ዕድገት ታሪክ ሲነሣ በቀዳሚነት የአፄ ሚኒልክ ዘመነ መንግስት ተጠቃሽ ነዉ፡፡ በአንዳንድ ፀሐፊዎች ዘንድ አፄ ቴዎድሮስ ለሴባስቶፖል መድፍ ለመሣብና ለመጐተት እንዲመች በሰው ሃይል መንገድ ተጠርጐ ተስተካክሎ ስለነበር በዛ ጊዜ ነው የተጀመረው ይላሉ፡፡ ሆኖም ይህ ዋና አላማው ለሲቪል ተግባር ባለመሆኑ እዚሁ ላይ ገታ እናድርገውና ወደ ሚኒልክ ዘመነ መንግሥት እንመለሳለን፡፡

አፄ ምኒሊክ ከኦስትሪያ መንግሥት ጋር በነበራቸው ከፍተኛ ግንኙነት የዘመኑ ቴክኒዎሎጂ ውጤት የሆነውን መሬት የሚዳምጥ /Roller/ ተሽከርካሪ በ1885–1887 እ.ኤ.አ. ወደ ሀገር ውስጥ አስገብተዉ ነበር፡፡ ይህ ዳምጠው ተሽከርካሪው የሚሄድበት መንገድ ግን ሙሉ በሙሉ በወቅቱ በነበሩ የመንግሥቱ ጦርና በህዝቡ ጉልበት ጫካው እየተመነጠረ መንገድ እየተጠረገ እየወጣለት ነበር የሚነዳው፡፡ በዚህ መሠረት የመጀመሪያ ድልድይ በአዋሽ ወንዝ ላይ በ1886/87 እንደተሠራ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ተሽከርካሪው አዲስ አበባ ከደረሰ በኋላ ወደ አዲስ ዓለም 45 ኪ.ሜ በጦሩና በህዝቡ ጉልበት መንገድ እንዳስወጡና ሩሎው ወደ አደስ ዓለም እንደተወሰደ ከዚያም በዚህ መሥመር ላይ ለተወሰነ ጊዜ ሠርቶ ተበላሽቶ ቁሞ እንደቀረ ተገልጿል፡፡ የመጀመሪያዋ አውቶሞቢል ወደ ሀገራችን የገባችው እ.ኤ.አ. በ1907/08 እንደሆነና በማከታተል ግን በርካታ ሞዴል ያላቸው ተሽከርካሪዎች ከእንግሊዝና ከጀርመን እንደገቡ እና በርካታ የጭነት ተሽከርካሪዎች በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ በ1908 እ.ኤ.አ. በበጋ ጊዜ ሲያገለግሉ እንደነበር የተለያዩ ታሪካዊ ምንጮች ጠቅሰዋል፡፡

በወቅቱ በነበረው አስተሳሰብ ሁሉም ያገኘውን ተሽከርካሪ ከመንዳት ባለፈ ስለ ትራፊክ ህግና ደንብ እስከ 1915-17 ባሉት አመታት አካባቢ ምንም የሚመሩበት መመሪያና ህግ አልነበረም፡፡ ቀስ በቀስ ግን የቃል መመሪያና ትእዛዝ ለእግረኞችና ለአሽከርካሪዎች ህግ ወጥቶ እንደነበር ተጠቅሷል፡፡

ምንም እንኳን የጣሊያን ወረራ /1928-33/ የራሱ የሆነ ጉዳት ቢኖረውም ለዘመናዊ ትራንስፖርት ሀገራችን ውስጥ መስፋፋት የራሱ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ የህዝብ ትራንስፖርት በተለይም ታክሲና አውቶቡስ አገልግሎት በጣሊያን የወረራ ዘመን ሀገራችን ውስጥ እንደተጀመረ ተገልጿል፡፡

ታሪክ እንደዘገበዉ ምንም እንካF የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ የሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪ የነበሩት አፄ ሚኒሊክ እንደነበሩ ቢገልፅም ትክክለኛዉንና ህጋዊዉን መንጃ ፈቃድ በመያዝ የመጀመሪያ አሽከርካሪ የነበሩት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ እንደነበሩ እና ይህንን የማሽከርከር ጥበብ ጀርመን አገር ሄደው ተምረዉ እንደመጡ ተዘግቧል።

የመንገድ ትራንስፖርት ህጎች አወጣጥን በተመለከተ በ1934 እና በ1935 ዓ. ም. የወጡ ህጎች የመጀመሪያዎቹ በወረቀት ላይ የሰፈሩ ህጎች ተደርገዉ ይወሰዳሉ። በመንግስት መ/ቤት ደረጃ ግን በ1960 አካባቢ የመንገድ ትራንስፖርት አስተዳደር ጽ/ቤት የሚል እንደነበረና ከዚያ በፊት ግን ብዙዎቹ የትራንስፖርት ስራዎች በቦርድና በትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ርና የአክሲዮን ድርጅቶች ይሠሩ ነበር።

ከመንገድ ትራንስፖርት ዉጪ ሌሎችን የትራንስፖርት ዓይነቶች ብንዳስስ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አስተዳደር ባቡር ሀገራችን ዉስጥ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ 1910ዎቹ አንስቶ አብሮ የመጣ ሲሆን የአየር ትራንስፖርት በተመለከተ ከ1921 ዓ. ም. የመጀመሪያ አይሮፕላን ወደ ሀገራችን መምጣትና መብረር እንደጀመረ ካፕቴን መኮንን በሪ «አቪዬሽን በኢትዮጵያ» መፅሀፋቸዉ ዉስጥ ገልፀዋል። ከዚያ በኋላ በህጋዊ መንገድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1930ዎቹ መጨረሻ (1938 ዓ.ም.) ተቋቁሟል፡፡ የዉኃ ትራንስፖርት፣ የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በ1950ዎቹ መጨረሻና 1960ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ እንደተመሰረተ ሌሎች ከዚህ ጋር ተያያዥ የነበሩ የወደብና የባህር ትራንስፖርት መ/ቤቶች /የባህር ትራንስፖርት ባለስልጣን/ እስከ 1985 ዓ.ም. የውጭዉን የዉሀ ትራንስፖርት በበላይነት ያስተዳድሩ ነበር።

በ1950ና 1960ዎቹ አካባቢ በሀገራችን ትራንስፖርት እድገት ታሪክ ዉስጥ ሰፊ ድርሻ ያለዉ ሥራ የተሰራበት ወቅት ነዉ። በዚህ ወቅት በሀገራችን በርካታ ማህበራትና ኩባኒያዎች የተፈጠሩበት ጊዜና በአንፂሩም የተሻለ አገልግሎት ሰጥቶ ተሳፋሪንና ደንበኞችን ለመሳብ ብዙ ዉድድር የነበረበት ነበር። ከዚህ አንፂር በርካታ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተዋል። ከ1967/68 በኋላ ግን ብዙ ሁኔታዎች የተቀያየሩበትና በተለይም የመንገድ ትራንስፖርት በብዙ መልኩ ተገድቦ በአንድ ጥላ ሥር የወደቀበት ወቅት ነበር፡፡ በርካታ ኩባንያዎች ተወርሰው በጭማድ እና በህዝብ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን ሥር እንዲተዳደሩ ተደረገ፡፡ ሁሉም ነገር በቀጣና /zoning/ እንዲመራ ተደረገ፡፡

በደርግ ዘመን በመንግሥት የግሉ ሴክተር ሚና የተገደበ ነበር፡፡ በዚህ የተነሣ በህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በኩል የነበረው እጥረት ከፍተኛ ነበር፡፡ የመሠረተ ልማት ግንባታና ማስተዳ ደርን ሙሉ በሙሉ የመንግሥት መ/ቤት በሆነዉ አውራ ጐዳና ባለስልጣን ሥር ነበር፡፡ በማዕከላዊነት የትራንስ ፖርት አገልግሎት መስጠቱም ሆነ የመሠረተ ልማት ግንባታ ጥገና እና በአጠቃላይ ማስተዳደርና ቁጥጥር እስከ 1984/85 ድረስ እንደቀጠለ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡

3.2 የትራንስፖርት ገፅታ ከ1984–1997 ዓ.ም.

በበርካታ መንግሥታዊ መ/ቤቶች የማስተካከያ ለውጥ እርምጃ መውሰድ የተጀመረው ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ከ1984 የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ከማዕከላዊነት ወዳልተማከለ አሠራር እንዲወርድ ሲደረግ ሌሎቹ ግን በነበሩበት ሁኔታ እስከ አሁን ድረስ ቀጥለዋል፡፡

በውሃ ትራንስፖርት በኩል በተለይም ሀገራችን ከ1983 ሚያዚያ ወር ጀምሮ የአሰብን ወደብ ካጣች ጊዜ ጀምሮ በውሃ ትራንስፖርት በከፍተኛ ደረጃ ያሽቆለቆሉበት ሁኔታ እንዳለ እንረዳለን፡፡ በሀገር ውስጥ የጣና ዙሪያና የባሮ ትራንስፖርት አገልግሎት በክልሎች ሥር በመሆኑ በአነስተኛ አቅም እንደ አንድ ኦፕሬተር እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

በምድር ባቡር ትራንስፖርት በኩል እንደሚታወቀው ከ1910ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ በሀገራችን አገልግሎቱ ሣይቋረጥ ይሰጥ የነበረበት ሁኔታ ነበር ሆኖም ግን ባለፉት 15 ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ ችግር ውስጥ ወድቆ ይገኛል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ የቆመበት ሁኔታ እንዳለ እንረዳለን፡፡ ለኢትዮጵያና ጅቡቲ አገልግሎቱን በአዲስ መልክ ለመጀመር እና ወደ ግል ሴክተር ለማዛወር ዓለም አቀፍ ጨረታ ወጥቶ ለደቡብ አፍሪካ ኩባንያ ጨረታውን ለመስጠት በሂደት ላይ እንደሚገኝ የሚታወቅ ነዉ፡፡ ድርጅቱ የመንገድ ላይ ፀጥታ ችግር፣ ጐታች ሞተሮች ማርጀትና ኋላ ቀር መሆን፣ በማናጅመንት ጥራትና ብቃት ጉድለትና በሠራተኛው ማህበር የተለያዩ የውስጥ ችግሮች እና የፋይናንስ እጥረት ችግሮች አሉበት፡፡

የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ከ13 ዓመታት ቀደም ሲል ከነበረበት የተሽከርካሪዎች እጥረት በማገገም የተሽከርካሪ ቁጥር በተሻለ ደረጃ ይገኛል፡፡ ከ1984/85 ጀምሮ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፉን ለማሻሻል የተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች የወጡ ሲሆን በተለይም አዳዲስ አውቶቡሶችን እና የጭነት ተሽከርካሪዎችን ለሚያስገቡ ግለሰቦችና ድርጅቶች የማበረታቻ እርምጃዎች የተወሰዱበት ሁኔታ በበጐ ጐኑ የሚጠቀስ ነው፡፡

ከዚህ ሌላ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ለነፃ ገበያ ሲተዉ በኢትዮ-ጅቡቲ መስመር በቋሚነት የሚሰሩ ከፍተኛ የመጫን አቅም ያላቸው የጭነት ተሽከርካሪ ዎች ተፈጥረዋል፡፡ እንደዚሁም በሀገር ውሰጥ ባሉት ክልሎች ከአጭር ርቀት እስከ መካከለኛ ርቀት የሚሰሩ በርካታ መካከለኛ የጭነት ተሽከርካሪዎች ከ30-100 ኩንታል የሚጭኑ ተሽከርካሪዎች በብዛት ሀገር ውስጥ ገብተው ለአገልግሎት በቅተዋል፡፡ በሀገራችን ድርቅ፣ ጦርነት በሚኖሩበት ጊዜ በጅቡቲ አዲስ አበባ መስመር የሚሠሩ ከፍተኛ የጭነት ተሽከርካሪዎች በርካታ ሥራ ሲያገኙ በሀገር ውስጥ ያሉት ደግሞ መካከለኛ የመጫን አቅም ያላቸው የግብርናው ምርት ሲጨምር አገልግሎት አድማሳቸዉ የሚጨምር መሆኑና በተለይም ከሐምሌ ጀምሮ እስከ ጥቅምት ባሉት 4 ወራት ጊዜ ዉስጥ በከፍተኛ ደረጃ የጭነት መጠን ስለሚቀንስ የተሽከርካሪ ባለቤቶች ተሽከርካሪዎቻቸውን እስከማቆም የሚ ደርሱበት ሁኔታ አለ። በጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ውስጥ ጐልቶ የሚታይ ሌላዉ ችግር የጭነት አፈላላጊና አገናኝ ግለሰብ ደላሎች ጫና ከፍተኛ መሆን ነው፡፡ በኩባንያዎችም ሆነ በግለሰቦች ኦፕሬተሮች በኩል የማስተዋወቅ ሥራ ማካሄድ ስላልተለመደ የደላሎች ጫና መረጃ በመሸጥ፣ በሁለቱም ወገን ላይ ዋጋ በመወሰን ከፍተኛ ተጽእኖ እየፈጠሩ ይገኛሉ፡፡

በዚህ ዘርፍ ካሉት ገጽታዎች መካከል ሌላው ነጥብ የአሮጌ ተሽከርካሪዎች በተለይም ከ15-40 ዓመት ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ቁጥር በርካታ መሆን ነው፡፡

በህዝብ ማመላለሻ ዘርፍ አንዱ ልዩ ገጽታና ችግር ከ30 ዓመት በላይ ያገለገሉና በቴክኒክ አቋማቸዉ ብዙ አስተማማኝ ያልሆኑት ከአዳዲስ አውቶቡሶች እኩል ድልድልና ስምሪት ማግኘት መቻላቸው ነው፡፡ በከፍተኛና መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ረገድ አሁንም በማዕከላዊነት ለአዲስና አሮጌ ተሽከርካሪዎች እኩል ስምሪት መሰጠቱ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ችግር ፈጥሮ ይገኛል፡፡ በርካታ አሮጌ ሞዴል ያላቸው አውቶቡሶች በገበያ ውስጥ የሚኖራቸውን ተቀባይነት ላለማጣት የሞተር ለውጥ ሣይደረግ የቦዲ /አካል/ ለውጥ በማድረግ ከዘመናዊዎቹ የካቻማሊና አይሱዙ ተሽከርካሪዎች የቦዲ ቅርጽ በማመሳሰል ህብረተሰቡን ለማታለል የሚደረገው ጥረት በጣም አስገራሚ ክስተት ነው፡፡ ከህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ዘርፍ ባለፉት 15 ዓመታት ካየናቸው ችግሮች መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል፤ የተሣፋሪው ሻንጣና ጓዝ ዋስትና ማጣት፣ የታግ አሰራር መቅረት፣ በመናኸሪያዎች ውስጥና ዙሪያ የደላሎችና አስጫኞች መብዛት፣ ለትንሽና ትልቅ ዕቃ /ሻንጣ/ በርካታ ገንዘብ ተሣፋሪውን ማስከፈል፣ የሚዛን አሠራር በግልጽና ሁሉም እንዲጠቀምበት አለመደረግ፣ በመናኸሪያ ዎች ውስጥ አንድም የመረጃ ምንጭና ሌሎች የአገልግሎት ዓይነቶች ተሟልተው አለመገኘት፣ የአውቶቡሶቹ መስታወቶች፣ መጋረጃ፣ መቀመጫ ወንበርና መተላለፊያዎች ምቹ ንፁህ ሆነው አለመገኘት፣ የአውቶቡስ ውስጥ ለመንገደኞች የሚሰጠው አገልግሎት ማለትም ለምሣሌ ሙዚቃ፣ ማስታወቂያ፣ ስዕሎች ሥርዓትን የተከተለ አለመ ሆን ናቸዉ። ሌላው አውቶቡሶች በከፍተኛ ደረጃ ከማርጀታቸው የተነሣ ከአዲስ አበባ ሣይወጡ መንገድ ላይ እየተበላሹ ሌላ አውቶቡስ ለመተካት የሚደረገው ሩጫ የየእለት ትዕይንት ሆኗል፡፡

4. የኢትዮጵያ ትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ነባራዊ ሁኔታ (አሁን የሚገኝበት ሁኔታ)

4.1 የትራንስፖርት አገልግሎት ሁኔታ

የትራንስፖርት አገልግሎት ሁኔታ በሀገራችን ካሉት የትራንስፖርት ዓይነቶች መካከል መረጃ የምኖራቸዉ የመንገድ፣ የአየር፣ የባቡርና የውሃ ትራንስፖርት ዓይነቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት አብዛኛውን ድርሻ ይዞ የሚገኘው የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ነው፡፡ በዚህ መሰረት «የሀገሪቱ የገቢና የወጪ ዕቃዎች ዝውውር 90%፣ እንዲሁም የመንገደኞች እንቅስቀሴ 95% ያህሉ አገልግሎት የሚገኘው በመንገድ ትራንስፖርት ነው»::

አብዛኛው የከተማ ነዋሪዎች አጭርና መካከለኛ ርቀቶችን የሚሸፍኑት በእግር በመጓዝ ሲሆን በገጠር ግን በእግር በመጓዝና በተወሰነ ደረጃ የእንስሳት ጉልበት በመጠቀም ነዉ። የዘመናዊ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆነው የሀገራችን ህዝብ ብዛት መጠን ከ20% እንደማይበልጥ ተጠቅሷል፡፡ /ፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን መጋቢት 1998/ አጠቃላይ የትራንስፖርት እንቅስቃሴዉን ብንመለከት አሁንም ያለመረጋጋት ወይም የማሽቆልቆል ሁኔታ ይታያል።

በመንግስት መስሪያ ቤቶች ያለዉን የሰዉ ኃይል ሥርጭት ብንመለከት ከመንገድ ጋር የተያያዙ መ/ቤቶች ማለትም ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንና የመንገድ ፈንድ አስተዳደር

መሥሪያ ቤቶች የሰው ኃይል በአጠቃላይ የ46.7% ድርሻ በመንግሥት መ/ቤቶች ቅጥር ደረጃ ይዞ ይገኛል፡፡ ይህ አሀዝ በክልል ትራንስፖርት መ/ቤቶች ያለውን አያካትትም፡፡ ከመንገድ ትራንስፖርት በመቀጠል የአየር ትራንስፖርት የ39.3% ድርሻ ይዟል፡፡ አሁን በሀገሪቷ ውስጥ በትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ የተሻለ እንቅስቃሴ ደረጃ ላይ የሚገኙት እነዚሁ ሁለቱ ንዑስ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ናቸዉ።

4.1.1 የመንገድ ትራንስፖርት ሴክተር ገጽታ

የመንገድ ትራንስፖርትን በሁለት ከፍለን ስናይ በመሠረተ ልማት ግንባታ እና በአገልግሎት አሰጣጥ ይከፈላሉ፡፡ በመሠረተ ልማት አቅርቦት በኩል ያለውን ካየን በሀገራችን ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ የተሻለ እንቅስቃሴ ቢኖርም እስከ 1995 ዓ.ም. በነበረው መረጃ መሠረት በሀገሪቷ ውስጥ በአጠቃላይ 33,876 ኪ.ሜ. መንገድ ብቻ እንደነበረ የፌዴራል ትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ር ዶክመንት ይጠቅሳል። ከዚህ ጠቅላላ መንገድ ርዝመት ውስጥ 13% /ወይም 4362 ኪ.ሜ./ የሚሆነው የአስፋልት መንገድ ሲሆን፣ 36% /12,360 ኪ.ሜ/ የሚሆነው ደግሞ የክረምትና በጋ ጠጠር መንገድ ነዉ። ቀሪዎቹ የገጠር መንገድና ጥርጊያ መንገዶች ሲሆኑ እነዚህም በአጠቃላይ 50% ድርሻ እንዳላቸው ተረጋግጧል፡፡ የሀገራችን መንገድ ዝርጋታ /ልማት/ በ1.7% እድገት በዓመት እንደሚያሣይ መረጃዎቹ ጠቁመዋል፡፡

ከፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን በተገኘው መረጃ መሠረት በየዓመቱ የ10% እድገት በማሣየት በሀገሪቷ የሚገኙ የተሽከርካሪ ቁጥር /ብዛት/ በ1997 ዓ.ም. 166,310 እንደሆኑ ያሣያል፡፡ ባለፉት 12 ዓመታት በተለይም ከ1985–1997 ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ የእድገት የታየበት ወቅት ነው፡፡ ዝርዝር ሁኔታዎች በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 2፤ የተመረመሩና የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች

ዓ.ም Year	የተሽከርካሪዎቹ አገልግሎት ዘርፍ / Motor Transport Services Sector										
	የመንግ. Gov't.	ሕዝባዊ.ድ Civ. Org.	የተ.መ UN	ኮር. ዲ CD	ተራድኦ Aid	ኤ.አድ A.A.T.	ንግድ Business	ታክሲ Taxi	የግል ን. Pr. Bus.	የቤት Dom.	ድምር Total
1985	10267	286	835	248	2208	127	11954	5233	3951	30074	65183
1986	11338	438	745	733	3493	129	12335	4869	4711	30928	69719
1987	13691	311	1154	590	3768	54	21725	6323	2341	35155	85113
1988	14264	348	1323	751	3864	230	25756	6627	4202	36503	93868
1989	14057	517	955	774	3533	064	26161	6530	5323	39111	97124
1990	13960	196	1003	731	3636	200	25553	9969	9765	41194	106207
1991	15786	311	975	786	3561	119	28990	9525	1667	40672	107392
1992	16081	239	1015	819	3794	134	30851	10156	9859	42258	115206
1993	16611	256	1001	815	4280	132	39311	10632	4661	43858	121557
1994	17278	294	954	921	4219	157	304995	12010	11531	47905	130264
1995	17070	261	1056	1060	4052	217	34931	12506	8245	53540	132938
1996	17424	780	1045	672	4393	192	36703	12395	13546	58696	145807
1997	20013	1657	1202	1050	4384	225	50046	14523	14985	58221	166310
Av.Gr.	7.12%	38.01%	5.59%	25.98%	8.31%	29.61%	17.47%	11.91%	31.57%	6.9%	10%

ምንጭ፡ ፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን መጋቢት 1998

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ በዓመት 59,785 አዲስ መንጃ ፈቃዶች የተሰጡ ሲሆን በዓመት በአማካይ በ0.8% እድገት ያሣያል፡፡

ሀገሪቷ ያላት ተሽከርካሪ ብዛት በአፍሪካ ውስጥ ካሉት ሀገሮች አንፃር ሲታይ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ከመሆኑም በላይ የተሽከርካሪዎቹ የመጫን አቅም ስርጭት ሲታይ በጭነትም ሆነ በህዝብ በዝቅተኛ እና መካከለኛ የመጫን አቅም የተወሰኑት ናቸዉ ፡፡

ከምርት አገልግሎት ጋር በቀጥታ ያልተገናኙት የግል አውቶሞቢሎች ከፍተኛውን እጅ ማለትም ከ37% በላይ ድርሻ አላቸው፡፡ በአጠቃላይ የህዝብ ማመላለሻ 70% ሲይዝ የጭነት በአማካይ 30% ድርሻ አለው፡

ወደ ሀገር ውሰጥ ስለሚገቡና አዲስ ስለሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎች

በየዓመቱ አዲስ ስለሚመዘገቡ ተሽከርካሪ ዎችን ብንመለከት ከ1981 ዓ.ም. ጀምሮ ያለዉ መረጃ በተለይም ከ1983 እስከ 1988/89 ድረስ በከፍተኛ ደረጃ የጨመረ ሲሆን ከ1990 እስከ 1993 ድረስ ደግሞ የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቶ ከ1994 ጀምሮ ግን በተከታታይ ከፍተኛ ዕድገት የታየበት ወቅት ነው፡፡

በተገኘዉ መረጃ መሰረት ወደ ሀገራችን እየገቡ ካሉት ተሽከርካሪዎች መካከል ከ3/4 እጅ በላይ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል ከ51% በላይ ድርሻ ያለው አውቶሞቢሎች በአብዛኛው ለግል አገልግሎት የሚውሉ መሆናቸው ደግሞ ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰብ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ተሽከርካሪዎች የሞተራይዜሽን መስፋፋት ምልክት ናቸዉና፡፡ በህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት መስፋፋትን በተመለከተ በአነስተኛ የመጫን አቅም ያላቸው በተለይም ከ6-30 መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎች በብዛት እየገቡ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በጭነት ትራንስፖርት በኩል ደግሞ አብዛኛውን ድርሻ የያዙት ከ70 ኩንታል በታች ያላቸው ተሽከርካሪ ዎች ሲሆኑ በጭነት ሥራ ዘርፍ ከተሠማሩ ዉስጥ 79% ድርሻ አላቸው፡፡ ይህ ማለት ኢኮኖሚያችን በጅምር ላይ የሚገኝ በመሆኑ ይህንንም ፍላጐት ለማሟላት የመጫን አቅማቸው በአብዛ ኛው ከ30-70 የመጫን አቅም ያላቸው ‘‘አይሱዙ’’ ተሽከርካሪዎች ምቹ መሆናቸዉን ያመላክታል። ዝርዝር ሁኔታውን ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ተሽከርካሪዎች እድገት ከ1980 እስከ 1995 ባሉት 16 ዓመታት ውስጥ በአማካይ በዓመት የ38 በመቶ ዕድገት ያሣየ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ1984 በኋላ ያለውን ብቻ ከተመለከትን ደግሞ በአማካይ በዓመት ከ21 በመቶ በላይ እድገት አሳይቷል፡፡

ሠንጠረዥ 3፤ የጭነት ተሽከርካሪዎች /ወደ ሀገር ዉስጥ የገቡ

ዓ.ም. Year	ከ19 ኩ. በታች <19 qts.	ከ20-90 ኩ.ታ.ል 20-90 qts	ከ91 ኩ. በላይ በተሣቢና ያለተሣቢ >91 qts. with & without trailers	የፈሣሽ ተሽከርካሪዎች በተሣቢና ያለተሣቢ Liquid transport vehicles with & without trailers	ድምር Total
1980	-	74	71	86	231
1981	2	33	73	71	79
1982	24	146	17	16	203
1983	199	425	32	7	663
1984	423	716	283	23	1445
1985	217	985	270	32	1504
1986	243	969	621	138	1971
1987	416	1327	1078	184	3005
1988	651	1791	1286	139	3777
1989	308	1205	844	144	2501
1990	254	600	366	39	1259
1991	197	616	476	312	1604
1992	309	941	1379	544	3173
1993	528	2070	2633	91	5322
1994	381	2040	1181	46	3648
1995	316	3277	1608	46	3648
አማካይ አዲስ ተሽከርካሪ በዓመት New AV. Annual import	292	1076	764	131	
ከ84 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው አማካይ ዓመታዊ ዕድገት Av. Ann. Growth rate since 1984	**346**	**1378**	**1002**	**160**	**2886**
መቶኛ ድርሻ ከ84 ጀምሮ ላለው % share since 1984	**12**	**48**	**35**	**5**	**100**

ምንጭ፡ 1. ፌዴራል ትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ር እና የትራንስፖርት ባለሥልጣን፤

2. ከመረጃው በመነሣት የተሰላ ስሌት

የህዝብና የጭነት ምልልስ መጠን

ካለው የሴክተሩ ልዩ ፀባይና በሀገራችን ካለው ኋላቀር የመረጃ አያያዝ የተነሳ የጭነትና የህዝብ ጉዞ ምልልስ መጠን ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን በተለየዩ ምክንያቶች የተለያዩ ድርጅቶ ችና መ/ቤቶች ፌዴራል ትራንስፖርት በዋነኛነት የናሙና መረጃ አሰባሰብ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህን በመጠቀም በትራንስፖ ርት ክፍለ ኢኮኖሚያችን ያለውን እንቅስቃሴ ከዚህ በታች ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

ከዚህ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ባለፉት 13 ዓመታት ከ1985-1997 ባለው ጊዜ ውስጥ በህዝብ ማመላለሻ ዘርፍ ከ10-13% የተሣፋሪ ምልልስ እድገት የታየ ሲሆን በደረቅ ጭነት ደግሞ የ6-7% ዕድገት ታይቷል፡፡ በፈሣሽ ማመላለሻ ረገድ የታየው ለውጥ በዓመት በአማካይ የ5% ዕድገት ነበር፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ግን በጭነትም ሆነ በህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት በተለይም በህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ ዕድገት እየታየ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተናጠል የህዝብ ማመላለሻ እድገትን ስንመለከት በሀገሪቱ ውስጥ በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት በህዝብም ሆነ በጭነት አገልግሎት በመስጠት ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው የሚገኙት በግሉ ሴክተር የሚንቀሣቀሱት ተሽከርካሪዎችና ድርጅቶች ቢሆኑም ካለው መረጃ እጥረት የተነሣ የሴክተሩን ጠቅላላ አገልግሎት መጠን ለማቅረብ አዳጋች ሆኗል፡፡ ነገር ግን የመንግሥታዊ ድርጅቶች እንቅስቃሴና የአገልግሎት መጠን ጠቋሚ መረጃ ሊሰጥ ስለሚችል የእነዚህን መረጃ መዳሰሱ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ መንግሥታዊ የሆኑ የትራንስፖርት ድርጅቶችን ማለትም፣ የህዝብ፣ በአንበሣ የከተማ አውቶቡስና በዋሊያ የከተሞች አገናኝ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅቶች በኩል ያለውን የአገልግሎት ይዘት ጠቅለል አድርገን እንመለከታለን፡፡

ሠንጠረዥ 4፤ በሀገራችን ያለው የጭነትና የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት መጠን /1985-1997 ዓ.ም./

በጀት ዓመት Fiscal year	የህዝብ ማመላለሻ Public Transport		የጭነት ማመላለሻ /የደረቅ/ Goods Transport (Dry)		የፈሣሽ ጭነት Liquid Goods	
	ተሣፋሪ በሺህ Passengers in '000	ተሣፋሪ በኪ.ሜ/በሚሊዮን/ Passengers by kms./in Mns/	ቶን በሺህ Tons in '000s	ቶን ኪ.ሜ በሚሊዮን Tons in kms. In millions	ቶን በሺህ Tons in '000s	ቶን ኪ.ሜ በሚሊዮን Tons in km. in millions
1985	22817.0	2131.0	3095.5	1353.6	625.8	498.2
1986	24633.0	2472.0	2814.2	1002.7	689.1	391.2
1987	42774.0	3184.0	3366.5	1467.9	655.8	629.3
1988	52350.0	4199.0	4060.3	1714.9	846.1	583.9
1989	54296.0	4378.0	5134.3	2070.9	895.1	570.9
1990	56314.0	4908.0	5532.8	2229.9	1030.9	655.5
1991	35180.0	3644.0	4810.6	1529.5	790.3	560.0
1992	43459.0	4062.0	4913.1	1585.7	865.1	577.4
1993	48319.0	4238.0	4890.2	1866.2	885.5	589.5
1994	51440.0	4404.0	5232.5	2090.1	974.1	600.0
1995	64560.0	40844.0	5272.3	2058.5	964.8	614.8
1996	17045.0	4337.0	-	-	-	-
1997	70872.0	6979.0	-	-	-	-

ምንጭ፡ ፌዴራል መንገድ ትራንስፖርት

ሠንጠረዥ 5፤ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመንግሥታዊ ድርጅቶች በኩል የተሰጠ

ዓ.ም. Year	ከተሞችን የሚያገናኝ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት Inter-Urban Public Transport Services		የከተማ ህዝብ ትራንስፖርት Intra-Urban Public Transport Services			
			አዲስ አበባ Addis Ababa		ጅማ Jimma	
	ተሣፋሪ /000 Passengers in '000	ተሣፋሪ ኪ.ሜ በሚሊዮን Passengers by kms./in Mns/	ተሣፋሪ /በሺህ/ Passengers '000s	ርቀት በኪ.ሜ /በሚሊዮን/ Distance in km. In millions	ተሣፋሪ /በሺህ/ Passengers in '000s	ርቀት በኪ.ሜ /በሺህ/ Distance in km. in millions
1984	1904	605	108479	8598	2091	290
1985	2046	578	102816	8743	1674	313
1986	1851	521	98233	8390	1807	355
1987	1798	521	74587	5847	1761	320
1988	1799	510	53890	4646	1384	262
1989	1658	400	100936	8855	1265	306
1990	1578	354	162764	15337	1396	322
1991	1656	475	190394	18387	1312	305
1992	1017	240	208243	19642	1230	311
1993	995	200	200384	18853	1108	250
1994	930	189	186065	18911	1407	232
1995	1129	201	204210	21596	1617	228

ምንጭ፡ ፌዴራል ትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ርና ፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን

ከሠንጠረዡ እንደምንረዳው ከተሞችን በሚያገናኙ የህዝብ አውቶቡስ /Inter urban public transport/ አገልግሎት በኩል ያለው ድርሻ በከፍተኛ ደረጃ እያሽቆለቆለ እንዳለና በከተማ ትራንስፖርት በኩል ደግሞ በተለይም በአዲስ አበባ የተሻለ ተሣፋሪ የማጓጓዝና ርቀት መሸፈን አዝማሚያ ቢታይበትም የእድገት ሁኔታው ግን በተለይም ከ1986–1988 ባሉት 3 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በጣም አሽቆልቁሎ እንደነበር እንረዳለን፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ አገልግሎት ላይ የነበሩት አውቶቡሶች ቁጥር በ1984 ዓ.ም. 145 ብቻ የነበሩ ሲሆን በ1995 ይህ አሀዝ ወደ 343 ከፍ ብሎ እንደነበር እንረዳለን፡፡ በጣም በመዳከምና በማሽቆልቆል ደረጃ ውስጥ ያለው የጂማ ከተማ ህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሲሆን እነዚህ አውቶቡሶች ቁጥራቸው ከ4-6 ባለው መካከል ከፍና ዝቅ የሚሉ ቢሆንም ተሽከርካሪዎቹ ብዙ ዓመት ከማገል ገላቸው የተነሣ በከፍተኛ ደረጃ የአገልግሎት ደረጃቸው ወርዶ ይገኛል፡፡

የመንገድ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች ጥምርታ ነፍስ ወከፍ ድርሻ

ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገሮች አንፃር ሲታይ የሀገራችን የመንገድ ተሽከርካሪዎች በቁጥርም ሆነ ህዝብ ብዛት አንፃር በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለመረዳት ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ማየቱ ይጠቅማል፤

ሠንጠረዥ 6 እንደሚያሳየው ካለው የህዝብ ብዛት አንፃር በሀገራችን ያለው የተሽከርካሪ መጠን በጣም ዝቅተኛ መሆን ብቻ ሣይሆን /በአማካይ ከ80 ከመቶ በላይ ያሉት ተሽከርካሪዎች እድሜያቸው ከ10 እና 15 ዓመት በላይ መሆናቸው ደግሞ ሌላ የተለየ ገጽታ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ጠቀሜታቸው ሁሉን አቀፍ ለሆነ ለሀገሪቷ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ውስን መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፡፡

ሠንጠረዥ 6፡ የነፍስ ወከፍ ተሽከርካሪ ንጽጽር

	አገር Country	ተሽከርካሪ በየ1000 ሰው Vehicles /1000 people	
		ዘመን /እ.ኤ.አ/ (Year G/C)	ብዛት Number
1	ኢትዮጵያ Ethiopia	2003	2.2
2	ታንዛኒያ Tanzania	1997	4.6
3	ማዳጋስካር Madagascar	1997	5.7
4	ጋና Ghana	1997	7.7
5	ካሜሩን Cameroon	1997	12.0
6	ኬኒያ Kenya	1997	13.0
7	ዙምባቡዌ Zimbabwe	1997	32.0
8	ቦትስዋና Botswana	1999	68.0
9	ናሚቢያ Namibia	1997	85.0
10	ደቡብ አፍሪካ South Africa	1999	143.0

ምንጭ፡ ፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ መጋቢት 1998

የሀገራችን የትራንስፖርት አገልግሎትና የትራፊክ ደህንነት

በማንኛውም የምርት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ የደህንነት ጉዳይ ቅድሚያ ትኩረት ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በሀገራችን ካሉት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሴክተሮች መካከል ከፍተኛ የደህንነት /ሴፍቲ/ ችግር ጐልቶ የሚታይበት /የመንገድ/ትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ከሆነ ረጅም ዓመትን አስቆጥሯል፡፡ በተለይም 20 ዓመታት ወዲህ በሀገራችን እየደረሰ ያለው የትራፊክ አደጋ መጠን ካለው የመንገድ ተሽከርካሪዎች ብዛት አንፃር ሲታይ በጣም ከፍተኛ ነዉ፡፡

ከሠንጠረዥ 7 ለማየት እንደሚቻለው የአደጋው ሁኔታ በተለይም ከ1994 ዓ.ም. ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መሆኑንና የሞት አደጋው ከቀላልና ከከባድ የአካል ጉዳት ብዛት ባልተናነሰ በከፍተኛ ደረጃ /ከ12 በመቶ/ እየጨመረ መምጣቱን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት ሀገራችን ከአፍሪካና

ከታዳጊ ሀገሮች የትራፊክ ደህንነት በከፍተኛ ደረጃ ችግር ካለባቸው ሀገሮች ቀዳሚ ሥፍራ ላይ ከተመዘገበች ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ከኢንተርኔት መረብ በተገኘው መረጃ መሠረት ከፍተኛ የትራፊክ አደጋ በማድረስ ምጣኔ /Rate/ ስሌት መሠረት ከማዕከላዊ አፍሪካ ሪፖብሊክ በመቀጠል በአስከፊነቱ ኢትዮጵያ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ተመዝግባለች፡፡

ሠንጠረዥ 7፤ በሀገሪቷ የተከሰቱ የትራፊክ አደጋዎች

	የአደጋው ዓይነት Type of Accident	አደጋው የተከሰተባቸው ዓመታት Year of Accidents								
		1989	1990	1991	1992	1993	1994	1995	1996	1997
1	ቀላል የአካል ጉዳት አደጋ ብዛት /Number of Minor-damage accidents	2080	2444	2173	2120	2134	2196	2365	2705	2731
2	ከባድ የአካል ጉዳት አደጋ ብዛት /Number of serious-damage accidents	1618	1762	1642	1771	1697	1712	1790	2072	2368
3	በንብረት ላይ የደረሰ አደጋ ብዛት / Number of property-damage accidents	6512	7783	6560	6666	6684	7188	8563	10569	10822
4	የሞት አደጋ ብዛት Number of accidents involving death	1314	1313	1283	1274	1261	1659	1888	2111	2176
	ድምር Total	**11524**	**13302**	**11658**	**11831**	**11776**	**12755**	**14606**	**17457**	**16099**
	የሞት ድርሻ በመቶኛ Percentage of Deaths	**11.4**	**9.8**	**11**	**10.8**	**10.9**	**13**	**12.9**	**12.1**	**13.5**

ምንጭ፡ ፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን 1998

በዚህ መሠረት በብዙ መልኩ በሀገራችን ያለው የትራፊክ ደህንነት ችግር በጣም የከፋ መሆኑንና ከጐረቤት ሀገሮች ከእነ ኬኒያ፣ አንፃር ስናነፃፀር ህብረተሰባችን በከፋ ሁኔታ ዉስጥ ይገኛል፡፡ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ላይ የትራፊክ ደህንነት ችግር የሚያስከ ትለው ተጽእኖ በአሀዝ አስደግፎ ለማቅረብ ባይቻለንም እያደረሰ የሚገኘውን ጉዳት ግን ማንም በቀላሉ የሚገነዘበው ጉዳይ ነዉ፡፡

እንደ ምሳሌ ለማሳየት ያህል (ሠንጠረዥ 8) በኬኒያ የሚደርስ የትራፊክ አደጋ የሞት መጠን ለ10,000 ሰዎች 64.3 ሰዎች መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ አሀዝ በሀገራችን እየደረሰ ካለው አደጋ አንጻር ከአንድ ሦስተኛ በታች ነው፡፡ ነገር ግን በትራፊክ አደጋ የተነሣ ኬኒያ በዓመት ከ1.2-2 በመቶ በሀገሪቷ ከሚመረተው የሀገር ውስጥ ምርት /GDP/ የምታጣ መሆኑን ታዉቋል፡፡ የእኛን ጉዳት ከዚህ አንፃር በቀላሉ ማነፃፀር ቢሞክር በቀጥታ ያለውን ጉዳት ብቻ ብንመነዝር ቢያንስ ከ5 በመቶ ያላነሰ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) በየዓመቱ እናጣለን ማለት ነው፡፡

ሠንጠረዥ 8፤ በትራፊክ አደጋ የሚደርስ የሞት መጠን ለ10,000 ተሽከርካሪ ብዛት ንጽጽር

ተ.ቁ No	ከሠሃራ በታች ካሉ አፍሪካ ሀገሮች ስም Names of Sub-Saharan African Countries	የሞት መጠን ባለው የ10000 ተሽከርካሪ ብዛት አንፃር Number of deaths for every 10,000 vehicles
1	ማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ Central African Republic	339.2
2	ኢትዮጵያ Ethiopia	195.1
3	ማላዊ Malawi	193.2
4	ኡጋንዳ Uganda	121.9
5	ጊኒ Guinea	120.9
6	ኬፕ ቨርዴይ Cape Verdé	112.2
7	ታንዛኒያ Tanzania	111.4
9	ጋና Ghana	73.1
10	ናይጄሪያ Nigeria	65.0
11	ኬንያ Kenya	64.3
13	ቦትስዋና Botswana	61.8
14	ደቡብ አፍሪካ South Africa	16.8
16	ቻድ Chad	7.4
17	ማዳጋስካር Madagascar	3.2

ምንጭ፡ ከኢንተርኔት መረብ የተገኘ መረጃ

4.1.2 ውሃ ትራንስፖርት

የውሃ ትራንስፖርታችንን በተመለከተ በተመሣሣይ መልኩ በባህር ትራንስፖርት አገልግሎት ረገድ በዓለም አቀፍ አገልግሎት የጭነት ማጓጓዝ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ከሚገኙ በግዢና በኪራይ ከሚሰሩ ከ13-18 ከሚሆኑ መርከቦቻችን ውጪ በሀገር ውስጥ በጣት የሚቆጠሩ አነስተኛ ጀልባዎች በጣና ሀይቅና በባሮ ወንዝ ላይ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ሀገሪቷ ወደብ አልባ ከሆነችበት ከ1983 ጀምሮ ሀገሪቷ የምትጠቀመው በጐረቤት ሀገሮች ወደቦች ነው፡፡ በተለይም እስከ ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ድረስ አብዛኛው የገቢና ወጪ ጭነት በአሰብ ወደብ በኩል የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን የጅቡቲ ወደብ ከ90% በላይ የገቢና የወጪ ጭነቶቻችን ያስተናግዳል፡፡ ሌሎች አማራጭ ወደቦች የሱዳን ወደብ /port of Sudan/ እና የሀርጌሳ /ሱማሌ ላንድ/ ወደቦች ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በማሪታይምና ትራንዚት አገልግሎት በኩል በርካታ የግል ድርጅቶች መፈጠር ትልቅ ለዉጥ ነዉ፡፡ በጭነት ምልልስ ረገድ ያለውን ሁኔታ ብንመለከት በጠቃላይ ከ1981 እስከ 1992 ባሉት 12 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ለውጥ ሳያሣይ ወይንም የቀነሰበት ሁኔታ ሲታይ ከ1993–1995 ባሉት ጊዚያት ውስጥ ግን በተከታታይ ከፍተኛ ዕድገት የታየበት ወቅት ነበር፡፡

ከጭነት ምልልስ ውስጥ በአማካይ 80% የሚሆነው ወደሀገር ውስጥ የሚገባ ጭነት በማመላ ለስ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ እስከ 1993 ድረስ በነበረው የድርቅ፣ ረሃብና ጦርነት የተነሣ በአብዛኛው ከእነዚህ ጋር የተያያዙ የጭነት ዓይነቶች እና ነዳጅ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ከ1993 በኋላ ግን የልማት ዕቃዎች /Capital goods/ በብዛት ሀገር ውስጥ መግባት የጀመሩበት ሁኔታ እንዳለ ታዉቋል፡፡ እስከ 1995 በነበረው ሁኔታ ሀገራችን ያላት የራሷ የሆነ መርከቦች ብዛት 9 /ዘጠኝ/ ብቻ ሲሆኑ እነዚህ በአጠቃ ላይ በአንድ ጊዜ 101288 DWT ብቻ የመሸከም አቅም ያላቸው ናቸው፡፡

4.1.3 አየር ትራንስፖርት

የአየር ትራንስፖርታችን በተለይም የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆኖ መላ ውን ዓለም እያገናኘን የሚገኘው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካና በዓለም ያለው ድርሻ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ ለአፍሪካ ሀገሮች በከፍተኛ ደረጃ የሚመኩበት አየር መንገድ እንደሆነ በተለያዩ መድረኮች ይገለጻል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሀገር ውስጥ በረራው እንደ ውጪው ስሙ የገነነ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ከቅርብ አመታት ወዲህ በግል የተቋቋሙ የግል አየር አገልግሎት ኦፕሬተሮች ቢኖሩም የአገልግሎት አድማሳቸው አሁንም በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በሀገር ውስጥ ያለው የአየር አገልግሎት ሽፋን አነስተኛ የሆነበት ዋና ዋና ምክንያቶች ከሚባሉት መካከል የአይሮፕላኖቹ ቁጥር ማነስ፣ የህዝቡ የመግዛት አቅም ውስንነትና የአየር ማረፊያ ቦታዎች በአንፃራዊ መልኩ ቅርብ መሆን እንደሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎች ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን በሀገር ውስጥ ያሉን የአየር ማረፊያዎች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደረጃቸው እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ በዋነኛነት የድሬዳዋ፣ ባህርዳር፣ መቀሌ፣ ላሊበላ፣ አክሱም፣ አርባምንጭና ጋምቤላ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአንዳንዶቹ ምሳሌ የጅማ አየር ማረፊያና ሌሎች ተጐሣቁለው እናገኛቸዋለን፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ45 የማረፊያ ጣቢያዎች በውጪው አለም የሚያርፍ ሲሆን በሀገር ውስጥ ግን 34 ማረፊያ ጣቢያዎች ላይ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያዎች ሁለት ሲሆኑ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ናቸው፡፡ ሌሎች ማረፊያዎች ግን ለሀገር ውስጥ በረራ አገልግሎት ብቻ የተወሰኑ ናቸው፡፡ እነዚህም አርባ ምንጭ፣ አሶሳ፣ አክሱም፣ ሀመር ባኮ፣ ባህርዳር፣ ቤካ፣ ደብረማርቆስ፣ ደብረታቦር፣ ደምቢዶሎ፣ ደሴ፣ ጋምቤላ፣ ጐባ፣ ጐዴ፣ ጐንደር፣ ጐሬ፣ ጅጅጋ፣ ጅማ፣ ቀብሪደሀር፣ ላሊበላ፣ መካነሰላም፣ መቀሌ ሚዛን ተፈሪ፣ ነገሌ፣ ሽላቦ፣ ሽሬ እና ቴፒ ወዘተ... ናቸው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው ዘመናዊ የአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት ተርሚናል 11 ግዙፍ ዘመናዊ አይሮፕላኖችን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል ነው፡፡ ይህ ተርሚናል በአንድ ጊዜ ለ1300 መኪኖችን የዘመናዊ ሞተር ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ ቦታ ዘመናዊ ፋሲሊቲዎች ምግብ ቤቶች፣ ባንኮች፣ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች፣ ጉምሩክ፣ ሱቆች አለዉ።

ለግል ሴክተር ተሣትፎን የወጣው አዋጅ እስከ 20 መቀመጫ ያለውና ያለ ገደብ የጭነት አይሮፕላን አገልግሎት ላይ ማዋል እንደሚቻል ቢያስቀምጥም እስከ አሁን 3 ድርጅቶች ብቻ ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የአቢሲኒያ አየር አገልግሎት ብቻ ውጤታማ ሆኖ በአገልግሎት ውስጥ እንዳለ

ይታወቃል፡፡ በጐረቤት አገር ኬንያ ከ400 የሚበልጡ የግል አይሮፕላን ኩባንያዎች በአገልግሎት ላይ ይገኛሉ፡፡

ዓለም አቀፍ በረራም ሆነ በሀገር ውስጥ የበረራ አገልግሎት የመንገደኞች አገልግሎት እድገት ያሳየ ሲሆን በጭነት አገልግሎት ግን የሀገር ውስጥ በረራ በአማካይ የ3% ቅናሽ በየዓመቱ አሳይቷል፡፡ በዓለም አቀፍ በረራ በመንገደኞችም ሆነ በጭነት በአማካይ በየዓመቱ የ6.12% ዕድገት አሳይቷል፡፡

4.1.4 የምድር ባቡር አገልግሎት

የኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር ብቸኛው የምድር ባቡር አገልግሎት ሲሆን በአጠ ቃላይ በ781 ኪ.ሜ. ርዝመት የባቡር ሀዲድ አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ ከዚህ ውስጥ 681 ኪ.ሜ በኢትዮጵያ ክልል ነው፡፡

አገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ በሀገራችን ውስጥ የተደረገውና በጅቡቲ ክልል የተደረገውን የጉዞ ምልልስ ስንመለከት ከዓመት ዓመት የማሽቆልቆል ሁኔታ የታየበት እንደነበር ያሣየናል፡፡

ከ1981 እስከ 1999 ባሉት ጊዚያት በኢትዮ - ጅቡቲ ምድር ባቡር አገልግሎት ያለው የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በዓመት በአማካይ በ7% እየቀነሰ የመጣ ሲሆን በጭነት በኩል ደግሞ በአማካይ በየዓመቱ በአንድ በመቶ እየቀነሰ ይገኛል፡፡

የትራንስፖርት ዓይነቶችን በተመለከተ አሁን ያለንበት ሁኔታ በዚህ መልኩ ከዳሰስን ለመሆኑ ሀገራችን የምትመራበት የትራንስፖርት ፖሊሲ አላት ወይ የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ መልሱ በአጭሩ የላትም! ነው፡፡ ነገር ግን የሁሉም የትራንስፖርት ዓይነት ዘርፎች በተለያዩ አጋጣሚ በርካታ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችን በማውጣት የሚጠቀሙበት ብቻ ነዉ ያለዉ።

4.2 የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ገጽታ

ከ1983 ዓ.ም. የመንግሥት ለውጥ በኋላ በሀገራችን ያለው የመንግሥት መዋቅራዊ አወቃቀር በፌዴራሊዝም ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በአብዛኛው ገጽታው ያልተማከለ አሠራር ጐልቶ ይታይበታል፡፡ ይህም ሲባል በርካታ የመንግሥት ሥራዎች በፌዴራልና በክልል በደረጃ ተከፋፍለው የሚሠሩ ሲሆን ጥቂት የመንግሥት ሥራ ተግባራት እንደ ቴሌኮሙኒኬሽን መብራት ሀይል፣ ፖስታ አገልግሎት፣ የመሣሠሉት በፌዴራል መዋቅር ሥራ የቀሩ ናቸው፡፡

በክልልና በፌዴራል መዋቅር ተከፋፍለው ከሚሰሩ ሴክተሮች መካከል አንዱ የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ነው፡፡ ከትራንስፖርት ክፍል ኢኮኖሚ ደግሞ የመንገድ ትራንስፖርት ሙሉ በሙሉ በፌዴራልና በክልል የተከፈለ ነው፡፡ በሌላ በኩል ዓለም አቀፍ ውሃ ትራንስፖርት በትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ርና በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ሥር ሲሆን የሀገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት ደግሞ በክልል የትራንስፖርት ቢሮዎች /ጽ/ቤቶች/ ሥር ነው፡፡

በመንገድ ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ግንባታ በኩል ያለውን ዘርዘር አድርገን የተመለከትን እንደሆን በፌዴራል ደረጃ ያለው አንድ መ/ቤት ነው፡፡ ይኸውም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ሲሆን የዚህ ባለሥልጣን መ/ቤት ዋነኛ ተግባር ለክልሎች ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ ክልሎችን የሚያቋርጥና የሚያገናኛቸውን ዋና ዋና ጐዳናዎችን መገንባት /ማስገንባት/፣ መቆጣጠርና ጥገና ማድረግ ተግባርን ያካትታል፡፡ በዚህ ረገድ በተለይም ካለፉት አራት እና አምስት ዓመታት ወዲህ እነዚህን ዋና /አውራ/ መንገዶችን ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲገነቡ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም የተከፈቱ አዳዲስ መንገዶች ተገቢው ጥገና ስለማይደረግላቸው በክረምት ጐርፍ እየተሸረሸሩና እየተጐዱ እንደሆነ ወጣ ብንል መታዘብ እንችላለን፡፡ በከተሞች የመንገድ ግንባታ ረገድ በአዲስ አበባ ባለፉት ሦስት አመታት የታየው ለውጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ በከተማችን በርካታ የማስፋፋት፣ ደረጃውን ከፍ ማድረግና አዳዲስ መጋቢና ዋና መንገዶችን በተለያዩ የከተማው ክፍሎች በመገንባት የተሻለ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ከተሞች እየተገነቡ ካሉት መንገዶች ጐልቶ የሚታዩ ችግሮች በርካታ ቢሆኑም በዋነኛነት የህብረተሰቡን ማህበራዊ አኗኗርና የኢኮኖሚ ደረጃ ያገናዘቡ አለመሆናቸው ነው፡፡ ለዋቢነት ያህል በየከተሞቻችን ያሉን የጉዞ ዓይነቶች በአብዛኛው የእግር ጉዞና የሞተር አልባ /ብስክሌት/ እንቅስቃሴ ሆነው እያሉ ለእነዚህ የጉዞ እንቅስቃሴዎች ምቹነት ትኩረት ሳይሠጥ ለተለመደው የሞተር ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ብቻ ትኩረት መሰጠቱ ተጠቃሚው ማይኖረን ከፍተኛ ወጪ ማውጣት መሆኑን እንረዳለን፡፡ የተገነባው የቀለበት መንገድ ከዓለም ስታንዳርድ አንፃር ሲታይ ሊያስኬድ ይችላል፡፡ ወደ አካባቢያችን ዘልቀን ብንመለከት የእግረኛ መሻገሪያዎች በአንድ ኪ.ሜ. መራራቅ ለአረጋውያን፣ ለበሽተኞችና ለህፃናት ከአንደኛው የመንገድ ጐን ወደሌላኛው አቅጣጫ ለመሻገር የግድ ሁለት ኪ.ሜ. መጓዝ ወይም ህጉን ጥሶ አጥር መዝለል፣ አጥሩን ማፍረስ ወዘተ ተግባራት ማከናወን የግድ የሆነበት ሁኔታ እናስተውላለን፡፡ በዚህ ባልተለመደ አቋራጭ /የህዝቡ እርምጃ/ የተነሣ በርካታ ህይወት የትራፊክ አደጋ ሰለባ የሆኑበት ሁኔታ አስተውለናል፡፡ ነገር ግን በሌሎች ከተሞች ያለው ከመሬት አቀማመጣቸው ምቹነት የተነሳ የነዋሪው እንቅስቃሴ በእግርና በብስክ ሌት ሆኖ እያለ ለሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች ምንም ትኩረት ማይሠጥ ለባለ ሞተር ተሽከርካሪ ዎች ብቻ ትኩረት መሰጠቱ ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም... የተባለው ተረት እንድናስታውስ ያደርገናል፡፡

የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አስተዳደር

የመንገድ ትራንስፖርት መዋቅራዊ ገጽታ የተመለከትን እንደሆነ በፌደራል ደረጃ ያሉት መ/ቤቶች ወይም ተቋማት፡ ትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር፣ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ የመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤት፣ የብሔራዊ ትራፊክ ደህንነት ኮሚቴ፣ በፌዴራል ፖሊስ ሥር የትራፊክ ደህንነት መምሪያ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ በዋነኛነት የአገልግሎት አሰጣጡን ለማስተዳደር ፖሊሲና ስትራቴጂ በማዉጣት፣ በመቆጣ ጠርና አስፈላጊውን የፋይናንስ ሀብት በማመቻቸት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

በክልሎች ያለው መዋቅራዊ ገጽታ ደግሞ የየክልሎቹ የትራንስፖርት ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች ወይም በአነስተኛ ደረጃ በመምሪያ ደረጃ ያሉት ብቻ ናቸው፡፡

በፌዴራል ደረጃ ካሉት መንግሥታዊ መ/ቤቶች መካከል የትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ር ዋናው እናት ሚ/ር መ/ቤት ነው፡፡ ይህ ሚ/ር መ/ቤት ከ1983 ወዲህ ለበርካታ ጊዜ የስም መቀየርና መዋቅራዊ ለዉጥ አድግጓል። በተለይ የመሠረተ ልማት ሚ/ር በተባለበት ወቅት ከትራንስፖርት ሁለት ገጽታዎች መካከል የአገልግሎት አስተዳደር ዘርፉ ዝቅ የተደረገና ወደጐን የተተወ ይመስል ነበር፡፡ ለማንኛውም አሁን ሁኔታዎች ቀድሞ ወደ ነበሩበት ሁኔታ ተመልሰው እናያለን፡፡

በፌዴራል የትራንስፖርት ባለሥልጣን በኩል ደግሞ መ/ቤቱ ከደርግ ሥርዓት መጀመሪያዎቹ /1969 ዓ.ም./ ጀምሮ እስከ 1997 ዓ.ም. አካባቢ የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን እየተባለ የሚጠራ ተቆጣጣሪ ፌዴራል መ/ቤት ነው፡፡ በዋነኛነት ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር የተያያዙ የአሽከርካሪ፣ ተሽከርካሪ አገልግሎት፣ አስተዳደርና ቁጥጥር ተግባራትን የሚያከናውን ነው፡፡ ከአንድ ዓመት ወዲህ ደግሞ የባቡር አገልግሎትንና የውሃ ትራንስፖርት አስተዳደራዊ የቁጥጥርና ፈቃድ መስጠት ወዘተ /regulating and licensing/ ሥራዎች በሥሩ በማካተት ስሙን የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን በሚል ስያሜ በአዲስ መልክ ተቋቁሟል፡፡

ይህ ባለሥልጣን መ/ቤት በዋነኛነት እያከናወነ ያለው በዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ደረጃ ያሉትን የመንገድ ትራንስፖርት ነክ ህጐች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ከማውጣት በተጨማሪ የሀገር አቀፍ ስትራቴጂያዊ ጥናቶችና ምርምሮችን መመሪያዎችን እያወጣ ተፈፃሚ እንደሚደረጉ ይከታተላል ይላል። ነገር ግን በበርካታ ጉዳዮች በዝርዝር የአፈጻጸም ሥራዎች ውስጥ /በተራ መደበኛ ሥራዎች/ በመግባት ተወጥሮ የሚገኝበት ሁኔታ እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክልሎች እና በፌደራል መ/ቤቱ መካከል የሥራ ድግግሞሽና በክልሎች የአፈፃፀም ክትትል ሂደት ላይ አለመግባባት ሁኔታዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ለትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ መቀጨጭ በሀገራችን ከትራንስፖርት ፕላኒንግና ማናጅመንት ዙሪያ አንድም ከፍተኛ የትምህርት ፕሮግራም/ ተቋማት አለመኖራቸው ተጠቃሽ ምክንያት ነዉ።

ሌላው ከመዋቅራዊ ገጽታ ሣይነሣ መታለፍ የሌለበት ነጥብ ቢኖር ሀገሪቷ የምትመራበት አጠቃላይ ትራንስፖርት ፖሊሲና ስትራቴጂ /National transport policy and strategy/ አለመኖር ክፍለ ኢኮኖሚውን ለየት ያደርገዋል፡፡ እስከዛሬ አጠቃላይ ፖሊሲና ስትራቴጂ አለመኖሩ «ስለሴክተሩ ያለው ችግር ምንድነው?» የሚል ጥያቄ እንድናነሣ ያደርገናል፡፡

የብሔራዊ የትራፊክ ደህንነት ኮሚቴ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየከፉ ያለውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ሥር ጽ/ቤት ከፍቶ እንቅስቃሴ እያደረገ መገኘቱ ነው፡፡ በዚህ በኩል በሬዲዮና በቴሌቪዥን ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ማቅረብ እየተዘወተረ ሲሆን በተለይም በኤፍ ኤም 97.1 ሐሙስ ጧት በየሣምንቱ የሚቀርበው የትራፊክ ውይይትና ትምህርታዊ መግለጫዎች፣ በፋና ሬዲዮ በዜናና በተለያዩ መልኮች እየቀረበ ያለው ፕሮግራም ጥሩ ጅምሮች መሆናቸውን መጥቀስ ተገቢ

ይሆናል፡፡ በአዲስ አበባና በአንዳንድ ከተሞች ከትራፊክ ፖሊስ መምሪያዎች ጋር በመተባበር የሚደረገው የተማሪ ትራፊክ ፖሊሶች ስልጠናና ለአገልግሎት ማብቃት በስፋት እንዲቀጥል ማድረግ የሚገባው ነዉ።

በየክልሎቹ የትራንስፖርት አገልግሎት አስተዳደርና ቁጥጥር የሚያደርጉ መ/ቤቶች በተለያየ ስም የሚጠሩ ትኩረትና ደረጃ ተሰጥታቸው የሚንቀሣቀሱ ናቸው፡፡ እንደኦሮሚያና ደቡብ ክሌሎች ለትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ የተሰጠዉ ትኩረት በጣም አናሳ ከመሆኑም በላይ የተዛባ ነዉ። ብዙዎቹ በሌሎች ቢሮዎች ሥር ተለጥፈዉ በመምሪያ ወይም በዋና ከፍል ደረጃ ተወስነዉ ይገኛሉ። ይህ ደግሞ ችግሩን ያባብሰዉ እንደሆን እንጂ ችግሩን አይቀርፈዉም። ከዚህ ጋር ተያይዞ የክልላዊነት ስሜት እየከፋ መምጣትና የሰሌዳ አሰጣጥ አለመጣጣም የመረጃ ልዉዉወጥ ባህል አለመዳበር የመንጃ ፈቃድ ያለምንም ቁጥጥር በዞኖች ወረዳዎች እየታደለ መሆኑ የሚጠቀሱ ችገሮች ናቸዉ።

4.3 ትራንስፖርት በከተሞችና በገጠሪቷ ኢትዮጵያ

የሀገራችን 85 በመቶ የሚሆነው ህዝብ በገጠር እንደሚኖር ይታወቃል፡፡ ይህ ደግሞ አንዱ ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃችን መግለጫ ነው፡፡ ይህ የገጠሩ ህብረተሰባችን ደግሞ በግብርና የሚተዳደር ከመሆኑም በላይ አብዛኛው ህብረተሰብ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚኖር ነው፡፡ የዚህ መገለጫው ደግሞ በሀገሪቷ ውስጥ በሚኖር የትራንስፖርት ዝቅተኛ እንቅስቃሴና እድገት ላይ ይንፀባረቃል፡፡ በሀገራችን ያሉት ከተሞች በጣም የቀጨጩና በብዙ መልኩ የእድገት መጠናቸው የማይመጣጠን ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በከተሞቹ መካከልና በገጠር አካባቢዎች መካከል ያለው ግንኙነት የላላ እና የደከመ እንዲሆን አድርጐታል፡፡ የዚህ የደከመ ግንኙነት በሀገራችን በሚኖረው የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ላይ መታየቱ አልቀረም፡፡

አሁን በሚታየው ሁኔታ ስናይ ጥቂት ከተሞች በተለይም አንድ ከተማ /አዲስ አበባ/ ብቻውን እየሠፋ እያበጠ ሌሎች ከተሞች ግን ያልተመጣጠነ ዕድገት ደረጃ ላይ መገኘታቸው አሣሣቢ ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ የአንድ ከተማ ብቻውን ማበጥ /Primate city/ በሀገሪቷ ያለውን ማናቸውንም የሀብት ስርጭትና ስብጥር ተመጣጣኝ እንዳይሆን /unbalanced regional growth/ ሊያደርገው ይችላል፡፡ አሁን ባለው የፌዴራሊዝም አወቃቀር በክልሎች ከተሞች መካከል የሚኖረውን የእድገት መጠን ተመጣጣኝ ያደርገዋል ተብሎ የሚጠበቅ ቢሆንም አሁን ባለንበት ሁኔታ ግን ለመደምደም ያስቸግራል፡፡ ለገጠሩ ህብረተሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መጐልበት የትራንስፖርት መሠረተ ልማት መስፋፋትና የዘመናዊ ትራንስፖርት አገልግሎት ማደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ከከፍተኛና መካከለኛ ከተሞች ወደ አነስተኛና የገጠር አካባቢዎች የሚያገናኙ መጋቢ የገጠር ጥርጊያና፣ የጠጠር መንገዶች በብዛት መሠራት ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ ጐን ለጐን በብዙዎቹ የአፍሪካና የእስያ ሀገሮች እንደ ሚታየው የመካከለኛ ትራንስፖርት አይነቶች /Intermediate transport/ ወይንም ሞተር አልባ የተሸከርካሪ ዓይነቶችና ቴክኖሎጂዎች በሀገሪቷ የገጠር አካባቢዎች መስፋፋት ይገባቸዋል::

የገጠሩ ህብረተሰብ አሁንም ቢሆን ከጋሪዮሽ ዘመን ጀምሮ ሲጠቀምበት የነበረውን አህያ፣ ፈረስ በቅሎና ግመል የመሣሉትንና እግሩን በመጠቀም ብቻ ነው ከገጠር ወደ ከተማ የሚንቀሳ ቀሰዉ። ይህ ደግሞ መሆን ለሚገባው የገጠር-ከተማ ግንኙነትና የምርትና ግብዓት ግብይት መስፋፋት፣ ምርታማነትና የገበያ ቦታዎች መስፋፋት ከፍተኛ እንቅፋት ይሆናል፡፡
አሁን ባለው መጠነኛ እንቅስቃሴ በተወሰኑ ገጠር አካባቢዎች መጋቢ የገጠር መንገዶች በመሠራታቸው በበጋ ጊዜ አነስተኛ የመጫን አቅም ያላቸው አይሱዙ መኪኖች የገበሬው ማሣ በማቋረጥ የገበሬው ደጅ ድረስ በመግባት ትርፍ ምርቶችን ለገበያ ለማቅረብ የሚደረገው እንቅስቃሴ መበረታታት አለበት፡፡

በሀገራችን ያለውን የከተማ ትራንስፖርት ስንዳስስ ደግሞ በጣት ከሚቆጠሩ የክልልና የዞን ዋና ከተሞች፣ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች በስተቀር የሚታይ የከተሜነት እንቅስቃሴ አዝጋሚ ነው፡፡ ብዙዎቹ እነዚህ አነስተኛ ከተሞች ባረጁ የጣራ ቆርቆሮዎችና በደከሙ የእንጨት ግርግዳዎች ችብችብ ብለው ይታያሉ፡፡ በጥቂት ምርታማ ወረዳዎች ግን የተለየ የከተማ መስፋፋትና /Urbanization/ እና የከተሞች እድገት /Urban growth/ ይታያል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ሁኔታ ግን ሁኔታው ለየት ያለና የተወሳሰበ ነው፡፡ አዲስ አበባ የሀገሪቷ ዋና ከተማ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት መቀመጫ እና የአፍሪካና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ኤምባሲዎች መናኸሪያ በመሆኗ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት፣ አገልግሎት አሰጣጥ አቅርቦትና ፍላጐት አለመመጣጠን ጐልቶ ይታያል፡፡ ከአራት ሚሊዮን በላይ ለሆነው የከተማዉ ነዋሪዎች ያሉት የከተማ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነቶች በቁጥር ከ400 በማይበልጡ የአንበሣ አውቶቡሶችና እያገለገሉ ይገኛሉ ከሚባሉ ከ10 ሺህ በማይበልጡ ታክሲዎች /ሚኒባሶች/ ጫንቃ ላይ የወደቀ ሸክም ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ነዋሪ ህዝብ መካከል የግል ተሽከርካሪ ያለው ወደ 50 ሺህ ቢጠጋ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ተደማምረው በከተማችን ያለው የትራንስፖርት ፍላጐትና አቅርቦት በተለይም በጧዋትና ከሰዓት በኋላ ባሉት የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች ከቁጥጥር ውጭ መሆንና የትራፊክ መጨናነቅ አስከፊ ያደርገዋል፡

በገጠርና በከተሞቻችን ያለውን የትራንስፖርት ሁኔታ ያሻሻላል ተብሎ የሚጠበቀው በከተሞች መካከል ያለው የህዝብና የጭነት ትራንስፖርት /Interurban transport/ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ዙሪያ ከሚገኙ ከተሞች በተለይም አዳማ፣ ቢሾፍቱ የመሣሉት ከተሞች መካከል በየደቂቃዎች ልዩነት ከሚደረግ የስምሪት እንቅስቃሴ ባሻገር ከሌሎች የሀገሪቷ መካከለኛና አነስተኛ ከተሞች መካከል ያለው የትራንስፖርት ስምሪት ግንኙነት በአንድ ወይም ሁለት አውቶቡሶች ስምሪት ብቻ የተገደበ ነው፡፡ ይህ አሠራርና የአውቶቡሶቹ ጥራት ብቃት ጉድለት ሥር ነቀል የአሠራር ለውጥ የሚፈልግ ነው፡፡

4.4 በትራንስፖርት ዘርፍ የሚታዩ ጠንካራ ጐኖች

በሀገራችን ያለው የዘመናዊ ትራንስፖርት አገልግሎት መቶ ዓመት ያስቆጠረ ሲሆን ማደግ የሚገባውን አላደገም፡፡ በተለይም ካሉት የትራንስፖርት ዓይነቶች /Modes/ መካከል የምድር ባቡርና የውሃ ትራንስፖርት የኋልዮሽ ጉዞ እየሔዱ ነዉ። የምድር ባቡር ደግሞ የባሰውኑ እስከ መዘጋት ደርሷል።

በመሻሻልና ዕድገት በማሣየት ረገድ በአየር ትራንስፖርታችን የተገኘው ለውጥ ሁሌም ልንኮራበት የሚገባን የትራንስፖርት ዘርፍ ነው፡፡ ይህ ዘርፍ በሀገራችን ከተቋቋመ የ60 ዓመት ዕድሜ ብቻ ቢኖረውም አሁን ያለበት ደረጃ በአፍሪካና በዓለም ደረጃ የሚያኮራ ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ የእድገት ሁኔታው ደግሞ የሚዋዥቅ ሣይሆን ሁሌ በተከታታይ የዕድገት አዘማሚያ የሚያሣይ /Sustainable growth/ መሆኑ ነው፡፡ በአየር ትራንስፖርት ዘርፍ ከሚታዩ ጠንካራ ጐኖች መካከል፤

1. የዘመኑ ቴክኒዎሎጂ ውጤት የሆኑትን አይሮፕላኖችና መሣሪያ ዎች የመጠቀም ደረጃው ከፍተኛነት፡
2. የጥገና ባህሉ፣ እውቀቱና አቅሙ ለአፍሪካና ለመካከለኛ ምሥራቅ አገሮች አርዓያ መሆን፡፡
3. የሀገሪቷ ሕዝቦች አየር መንገዱን አንደ አምባሳደር የመመልከት ገጽታ /Good Company Image/ መፍጠር መቻሉ፣
4. የሠለጠነ የሰው ሃይል በማፍራት ረገድ ያደረገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆን፡
5. ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ መሆኑ፣ ጠንካራ ተፎካካሪ መሆን መቻሉ ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል መፍጠሩ፣ ኢትዮጵያን ከአፍሪካና ከዓለም ማገናኘት መቻሉ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ መንገደኞችና የጭነት አገልግሎት በተከታታይ የእድገት አቅጣጫ መስጠት መቻሉ፣ ወደ ውጭ መላክ ለሚገባቸው እንደ አበባና ወርቅ ወዘተ የሀገር ምርቶችና የውጭ ምንዛሪ ለሚያስገኙ ከፍተኛ እገዛ ማድረጉ፣ የኢትዮጵያን ቱሪዝም፣ ባህል፣ ስፖርት፣ አርት በማስተዋወቅ በኩል የተጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆን፣ እና በአገልግሎት መስጠት ሂደት ውስጥ የጉዞ ላይ ደህንነት /traffic safety/ አስተማማኝ መሆኑ ተጠቃሽ ጠንካራ ጐኖቹ ናቸው፡፡

ከአየር መንገዳችን ወጣ ብለን የአቪዬሽን ባለሥልጣንና የኤርፖርቶች አስተዳደርን በጣምራ ስንመለከት በሀገራችን ለተከሰተው የአየር መንገድ ድርጅት እድገትና መሻሻል በአቪዬሽን ባለሥልጣን በኩል የተከናወኑ የፖሊሲ፣ ስትራቴጂያዊ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣት፣ መተግበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለውና መሠረት እንደሆነ መረዳት አያስችግርም፡፡ የኢትዮጵያ አቪዬሽን አስተዳደር ከሚታይባቸው ጠንካራ ጐኖች መካከል፤

ሀ. አየር መንገድና አቪዬሽን በሀገራችንም ሆነ በዓለም ላይ የቅርብ ዘመን ቴክኒዎሎጂ ውጤት በመሆኑ ይህንን ቴክኖሎጂና እውቀት ለሀገራችን እንዲጠቅም በማድረግ ረገድ ያደረገው ተከታታይ ጥረት ከፍተኛ ነው፡፡

ለ. የሀገሪቷ አየር ክልል አስተማማኝ እንዲሆን የሚያደርገው የትራፊክ ማኔጅመንት ጥረት ከፍተኛነት፣

ሐ. ከዓለም ሀገራት በተለይም የዓለም ሀያል ሀገር ከሆነችው አሜሪካና ሌሎች የአውሮፓ ጠንካራ ሀገሮች፣ ጀርመን፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ ጣሊያን ሀገሮች ጋር ጠንካራ ግንኙነትና ስምምነት በመፍጠር ለአየር መንገዳችን ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት መቻሉ፣

መ. የግል ሴክተር በአየር አገልግሎት ኦፕሬተርነት እንዲሠማሩ የሚደረግ ጥረት መኖር፣

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች አስተዳደር ከተቋቋመ የሦስትና አራት ዓመት ዕድሜ ባይበልጠውም ከአቪዬሽን ባለሥልጣን የተረከባቸውን በሀገራችን ያሉትን ኤርፖርቶችን በማስተዳደር በመንገንባት በማስፋፋት ረገድ የሚያደርገው ጥረት አበራታች ነው፡፡ በተለይም የአዲስ አበባ ቦሌ አለም

አቀፍ ኤርፖርት ሀገራችን ያኮራ በሠለጠኑ ሀገሮች ያለውን ቴክኒዎሎጂና ልምድ ሀገራችን እንድንጠቀም መደረጉ በጠንካራ ጐን ከሚነሱት ነጥቦች አንዱ ነው፡፡

የመንገድ ትራንስፖርት በሀገራችን ሁሉም ነገር ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ለህብረተሰቡ በቅርብ በመገኘት የህዝብና የጭነት ማመላለስ አገልግሎት በመስጠት ከዚህ ዘርፍ የተሻለ ሥራ እያከናወነ የሚገኝ የትራንስፖርት ዘርፍ የለም፡፡ በዚህ መሠረት በጠንካራ ጐኖችመካከል

1. በሀገር ውስጥ ህዝብና ጭነት በማጓጓዝ ከፍተኛውን /ከ90-95%/ ድርሻ በላይ ይዞ መገኘት፣
2. የአዳዲስ መንገዶች ግንባታና የነባሮች ደረጃ ማስፋፋት፣ ማሣደግ ጥረት ከፍተኛ መሆን፣
3. ዘርፉ ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል መክፈት መቻሉ፡፡
4. አምራችንና ገዢን በማገናኘት ረገድ ያለው ድርሻ ከፍተኛነት
5. የዘመኑ የቴክኒዎሎጂ ውጤት የሆኑትን የጭነትና የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የመጠቀም ደረጃችን መሻሻል
6. ካለው የፌዴራል ሥርዓት አንፃር የመዋቅር ወደታች የማውረድ ተነሣሽነት መኖር

በዉኃ ትራንስፖርት በኩል በባህር ትንስፖርት ያሉን መርከቦች /ከ10 የማይበልጡ/ እና በኪራይ የምሰሩ ጥቂት መርከቦችን ጨምሮ ወደ ሀገራችን የሚገቡና የሚወጡ ጭነቶችን በማመላለስ ረገድ የሚደረገዉ ጥረት ሳይጠቀስ መታለፍ የለበትም፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአሁኑ ሰዓት የሎጂስቲክ ሥራዎችን በመሥራት ላይ የሚገኙ የጭነት አቅራቢዎች፣ አሠናጆችና አስተላላፊዎች የጉምሩክ ክሊራንስ ኤጀንቶች በሀገራችን እየበዙና እየተጠናከሩ መገኘት በበጐ ጐኑ የሚታይ ነው፡፡

4.5 በትራንስፖርት ዘርፍ የሚታዩ ደካማ ጐኖች

እንደ እኛ ባሉ ደሀ ሀገሮች የማንኛውም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በውስጡ በሚፈጠሩ እና ከወጭ በሚኖር ጫናዎች የተነሣ በርካታ መሠናክሎች ችግሮችና እንቅፋቶች አለባቸው፡፡ ችግሮቻችን ሥር ነቀል የአሠራር /system/ መዋቅር ለውጥ ከመፈለግ ጀምሮ በአነስተኛ ማስተካከያ እርምጃ ብቻ ሊስተካከሉ የሚችሉ መሆናቸው ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ደሀ ሀገሮች ከፍተኛ የአቅም ውስንነትና የተቃና የማኔጅመንት እርምጃ እንደሚገል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት ወደ ሀገራችን የትራንስፖርት ሴክተር ደካማ ጐኖች ስንመለስ ከፍለ ኢኮኖሚው በተለይም በመንገድ ትራንስፖርት፣ በምድር ባቡር እና ውሃ ትራንስፖርት ከፍተኛ ደካማ ጐኖች ታይተዋል፡፡

1. የአገሪቷ የትራንስፖርት ፖሊሲና ስትራቴጂ /Transport Policy and Strategy/ አለመኖር፤
2. የእሣት አደጋ ማጥፋት አሠራር፣ /Fire fighting/ ህጐች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣት፣ መልመድ፤
3. በመንገድ ትራንስፖርት ያለው የትራፊክ ደህንነት ችግር፤
4. በየክልሎቻችን መንጃ ፈቃድ ያለገደብና ቁጥጥር መቸብቸብ፤
5. ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች የምርት እድሜ ገደብ አለመኖር፤
6. በትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ዘርፎችና መ/ቤቶች መካከል ስትራቴጂያዊ አካሄድ አለመኖር፤

7. የተፈጥሮ አካባቢያችን ሀብቶች ለጉዳት የማጋለጥ እርምጃ በስፋት መኖር፤
8. የምድር ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አድማስ እየከሰመ የመገኘት ሁኔታ፤
9. ለሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች ሚዛኑን የጠበቀ አመለካከትና ግንዛቤ አለመኖር፤
10. የተሽከርካሪዎች ስርጭት ተመጣ ጣኝ አለመሆንና በጥቂት ከተሞች የትራፊክ መጨናነቅ እየከፋ መምጣት፤
11. በአንፃራዊ መልኩ የትራንስፖርት አገልግሎት ወጪ ክፍያ /Transport unit cost per passenger/freight tone/ ከፍተኛ መሆን፡- ከጥቂት ዘመናዊ የጭነት ኩባንያዎች በስተቀር ብዙዎቹ የሀገራችን የተሽከርካሪ ኦፕሬተሮች/ ባለቤቶች/ ወጪያቸውን አለማወቅ፤
12. በህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ዘርፍ ለአዲስና አሮጌ አውቶቡሶች የስምሪት ድልድል የአሠራር ችግር፤
13. በከተሞች የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በስፋት እንዲስፋፉ ጥረቶች አለመደረግ
14. ለገጠር ትራንስፖርት ትኩረት አለመስጠት፤
15. የወደብ ባለቤት የሆኑት ሀገራት ጫና ለመቋቋም የሚደረግ ስትራቴጂያዊ አካሄድ ዉስንነት።

4.6 በትራንስፖርት ዘርፍ ለሚታዩ ችግሮችና መሠናክሎች የመፍትሄ ሃሣቦች

1. የትራንስፖርት ዓይነቶች /Transport modes/ የሚመሩበት አጠቃላይ የትራንስፖርት ፖሊሲና ስትራቴጂ በጋራ እና በተናጠል ሊኖር ይገባል፤ ፖሊሲውን ማውጣት ብቻ ሣይሆን በተግባርም ማሣየት ይገባል፡፡
2. በክፍለ ኢኮኖሚው ለውጥ ለማምጣት ሥር ነቀል የሆነ የአሠራርና አስተሳሰብ ማምጣት ነው፡፡ ለዘመናዊ የትራንስፖርት ማኔጅመንትና ፕላኒንግ ትኩረት መስጠት
3. በፌዴራልና በክልሎች ትራንስፖርት መ/ቤቶችና በትራንስፖርት ዓይነቶች መካከል ቅንጅት ማጠናከር፤
4. በትራፊክ ደህንነት ችግሮች በመቅረፍ ረገድ በዋነኛነት ፈፃሚውና አስፈፃማው አካል የአመለካከት ለውጥ ማምጣት፤ የቴክኒዎሎጂ ተጠቃሚ መሆን፤ የመንጃ ፈቃድ አሰራር መቀየር ህጎችን ማሻሻል፤ ትምህርታዊ ቅስቀሳዉን ማስፋፋት
5. ለምድር ባቡርና የህዝብ ማመላለሽ ትኩረት መስጠት
6. መንግሥት፤ ህዝብ፤ የግሉ ሴክተር ሙሉ በሙሉ ለአካባቢያችን የተፈጥሮ ጥበቃ ትኩረት መስጠት፤ የዘመኑ የብክለት መቀነሻ መሣሪያዎች መግጠም
7. በሀገር ውስጥ ያሉ የውሃ አካላት /ትላልቅ ወንዞቻችንና ሀይቆቻችንን በአግባቡ መጠቀም
8. ለክልል ትራንስፖርት መ/ቤቶች የተሰጠው ዝቅተኛ አመለካከት መቀየር
9. ለህዝብ ትራንስፖርትና ሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች/ ገጠር/ለከተማ/ ትኩረት መስጠት፡
10. ስለትራንስፖርት የወጪ አያያዝ ግንዛቤ ለኦፕሬተሮች ማስፋት
11. የተመጣጠነ የክልሎችና አካባቢ ዕድገት /Balanced regional growth/ አሠራር መከተል
12. በክልሎችና በፌደራል መ/ ቤቶች መካከል የተዋጣለትና ግልፅ አሰራር መፈጠር
13. ሀገራችን ወደብ አልባ እንደመሆኗ መጠን ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚደረገዉ ስምምነት ስትራቴጂያዊና የሀገራችንን ጥቅም ለዘለቄታዉ እንዳይጎዳ ጥንቃቄ መደረግ

5. በመጪው 2020 የሚኖር የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ገጽታ ትንበያ

5.1 አጠቃላይ

በዚህ ተለዋዋጭ ምድር አሁን የሚታይ ጥሩም ነገር ወይም መጥፎ ተግባር ነገ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመተንበይ የተለየ ተፈጥሯዊ ችሎታ ካልታከለበት በእርግጠኝነት መናገር ይቸግራል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው በዚህ ምድር ለመኖር በዋነኛነት ራዕይ ያለው ሆኖ በተስፋና በመስራት መሆር ይኖርበታል፡፡ የሁኔታዎች መለዋወጥ ከታለመው አቅጣጫ በተለየ መልኩ ሲሻሻሉ ወይም ሲበላሹ ታይተዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖማያችን ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ለማየት የሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ገጽታ በከፍተኛ ደረጃ ወሣኝነት አለው፡፡ ምክንያቱም ትራንስፖርት ከማንኛውም ክፍለ ኢኮኖሚ በሰፋ መልኩ የሌሎች ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች እድገት ይወስኑታል፡፡

ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት /እንቅስቃሴ/ ሲኖር የትራንስፖርት እድገት በከፍተኛ ፍጥነት ይጨምራል፡፡ ምክንያቱም አንዱ ላንዱ ዘርፍ የሚያደርገው አስተዋኦ /backward and forward linkage/ ይጨምራል፡፡ በአንፃሩም የትራንስ ፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ማደግ ለኢኮኖሚው ያለው አስተዋጽኦ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል፡፡ ለዚህ ጥሩ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚቻል ቢሆንም ለአሜሪካ /USA/ ኢኮኖሚ ማደግ አንዱና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው በትራንስፖርት በተለይም በመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ ከጀን ኤፍ ኬኔዲ ፖሊሲና አመለካከት በኋላ በተለየ መልኩ መጨመር አስተዋጽኦ እንዳደረገ በርካታ ፀሐፊዎች ዘግበዋል፡፡ የአጠቃላይ ኢኮኖሚውና የትራንስ ፖርት ክፍለ ኢኮኖሚው ዘርፍ መደጋገፍ አንዱ ላንዱ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ለውጥና እድገት በታሰበው ሁኔታ ሊታይ ይችላል፡፡

5.2 ርዕይ በ2020

ቀና አእምሮ /positive attitude or optimistic/ ሆኖ አንድን ነገር ማሰብ ለግለሰቡም ሆነ በሌላው አእምሮ ውስጥ ተስፋን ይጭራል፣ ተስፋ ደግሞ ወደ ምኞች እስካልተቀየረ ድረስ ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል፡፡ «በዚህ መሠረት በሀገራችን ያለው የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ የተሟላ መሠረተ ልማት ተዘርግቶ ደህንነቱ የተረጋገጠ ዜጐች በአራቱም አቅጣጫ ተዘዋውረው /maximized mobility/የዘመኑ ቴክኒዎሎጂ ውጤት ተጠቃሚ በመሆን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብሎም ፖለቲካዊ እድገት አጋር ምሰሶ የሆነ ከሀገራችን አልፎ ለምሥራቅ አፍሪካ ጐረቤት ሀገሮች ትልቁ የትራንስፖርት መረብ ምንጭ ሆኖ መገኘት ነው፡፡

5.2.1 አሁን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ሂደቱ እንደተለመደው ከቀጠለ በ2020 ኢትዮጵያ ምን ዓይነት የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ሊኖራት ይችላል?

በሀገራችን በአጠቃላይ ማለት ይቻላል ትላንት የለመድነውን ነገር፣ አስተሳሰብና አሠራር መልቀቅ ይከብደናል፡፡ በተቻለ መጠን ወደ ባህል ልንቀይረው እንፈልጋለን፡፡ ይህ አስተሳሰባችን ደግሞ በብዙ መልኩ ወደኋላ አስቀርቶናል፡፡ ይህንን ሃሣብ እንዳነሣ ያደረገኝ በትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚው

የሚታየው የግል ኦፕሬተሮችም ሆኑ የመንግሥት መ/ቤቶች አንድን አሠራር ለአርባና አምሣ ዓመታት ይዘን መጓዛችን ነው፡፡ አንድ ጥሩ ምሣሌ ላቅርብ በ1960 /1961 የወጡ የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ህጐች እስከዛሬ ድረስ እየተጠቀ ምንበት እንገኛለን፡፡ ነገር ግን ባለፉት 38 ዓመታት ውስጥ ሦስት በጣም የተለያዩ መንግሥታትን አይተናል:: ሌላ ተጨማሪ ምሣሌ ለማቅረብ በሀገራችን ያለው የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት አሰጣጥ የድልድል፣ ስምሪት አሰጣጥ፣ ወዘተ አሠራሮች ከ45 ዓመት በኋላም ለውጥ አይታይበትም፡፡ ለ30 እና 40 ዓመታት ያገለገሉ አውቶቡሶች ምክንያቱ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ የተለያዩ ጉድለቶች እየታየባቸው /አገልግሎታቸው አስተማማኝ ሳይሆን/ በስምሪትና ድልድል ውስጥ ገብተው ዛሬም አዲስ በሚሊዮን ብሮች ተገዝተው የዘመኑ ቴክኒዎሎጂ ውጤት ከሆኑ ተሽከርካሪዎች እኩል ህብረተሰቡን እንዲያስተናግዱ ይደረጋሉ፡፡

ዛሬ የግብርና ምርትም ሆነ የኢንዱስትሪው በአቧራ፣ ጭቃ ዝናብ የተጨማለቀ /የተበላሸ/ ምርት እንዲቀርብለት አይፈለግም፡፡ ነገር ግን በአገልግሎት ሰጭውና በአስፈፃሚው የመንግሥት መ/ቤቶች አካባቢ ከፍተኛ ጉድለት ይታያል፡፡ አዳዲስ ሃሣብ የሚያቀርብ ሠራተኛ ወይም ግለሰብ ሌላ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ ችግሩ አሁንም በስፋት አለ፡፡ ከዚህ መሠረት ሃሣብ በመነሣት የተወሰኑ አንኳር ትንበያ ዎችን ላስቀምጥ፡-

1. ሀገሪቷ የምትመራበት የትራንስ ፖርት ፖሊሲና ስትራቴጁ ሣይኖራት በዚሁ መልኩ ከቀጠለች አሁን በአለማችን ላይ እያየን ካለነው የግሎባላይዜሽን ተጽእኖ ሥር ወድቀን የዓለም ጭራ ሆነን እንቀራለን፡፡ አሠራራችንንና አስተሳሰባችንን ሳንቀይር ከቀጠልን የሚከሰተውን የገበያ ውድድር መቋቋም ስለሚያቅተን ተሽመድ ምደን የመውደቅ እጣ ፈንታ ብቻ ይጠብቀናል፡፡
2. በትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ በጎረቤት ሀገሮች የምንጠቀም ባቸዉ ወደቦች አስተማማኝና ዋስትና ያለዉ ሳይሆን ሊቀጥል ይችላል
3. በመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ያለው ኋላቀር አሠራር /በተለይም በግል ኦፕሬተሮች፣ በክልል ቢሮዎች፣ /እንዲሁም በፌዴራል መ/ቤቶች/ ሳይሻሻል፣ የአስተሳሰብ ለውጥ ሳይመጣ አሁን ባለበት ሁኔታ የበለፀጉ ሀገሮች አሮጌ ተሽከርካሪዎች ማራገፊያ ሆነን ከመቅረት በተጨማሪ ከፍተኛ የትራፊክ ደህንነት ችግር ያለበት ጊዜ እንደሚሆን ከፍተኛ ስጋት አለ፡፡ ነገር ግን በመሠረተ ልማት ግንባታና በኢንፎስት መንት በኩል ያለው ሁኔታ አሁንም ከቀጠለ የተሻለ የመንገድ ኔትወርክ ያለባት ሀገር ሆና ትታየኛለች፡፡ በሌላ መልኩ ለአካባቢያችን ተፈጥሮአዊ ሀብቶች ትኩረት አለመስጠት በዚህ መልኩ ከቀጠለ በተበከለ አየር የታፈነች አዲስ አበባን ማየት እንደሚሆን ከፍተኛ ስጋት አለ፡፡
4. ከመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ውጭ አንድም የምድርና የውሃ ትራንስፖርት አማራጭ የሌለባት በተለይም ፈጣን የባቡር አገልግሎ ቶች፣ የመንገደኛና መዝናኛ ጀልባዎች በሀገራችን ለማየት በመናፈቅ ብቻ ታሪክ አውርተን የምንቀርበት ሁኔታ ይታያል፡፡
5. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከብዙ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ አሁን ያለውን ስም፣ ዝናና ተግባር ይዞ ከቀጠለ የኢትዮጵያ አምባሳደር ብቻ ሣይሆን የአፍሪካና የመላ ጥቁር ህዝቦች አምባሣደርና መለያ ምልክት ሆኖ ሊቀጥል ይችላል፡፡
6. በመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ያለው የትራፊክ ደህንነት ችግር እየከፋ በመሄድ ሁኔታዎች ተባብሰው ወደ ከፋ ደረጃ ይደረስና ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት አንድ የአውሮፓ ታዋቂ ጋዜጣ በአምዱ ላይ /Do not drive in Ethiopia!!/ የሚለው አባባል እውን የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል፡፡

5.2.2 አሁን ያለውን አስከፊ ሁኔታ ለመለወጥ እርምጃዎች እየተወሰዱ ከሄዱ፡-

መልካም ጥረት መልካም ውጤት የሚያስገኝበት ደረጃና አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም በቅን ልቦና በፀዳ አእምሮ ከተንቀሣቀሰ ሀገራችን በማንኛውም ዘርፍ የተሻለች ሆና ማየት የማንችልበት ምንም ምክንያት የለም፡፡

በዚህ መሠረት፡-

1. **የትራንስፖርት ሴክተር በመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶ አገር አቀፍ እና ክልል አቀፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ወጥተው ወደ ተግባርዊ አፈፃፀም ከተገባ በብዙ መልኩ የተስተካከለች ሀገር፣ ሴክተሩ ለሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ የሆነ ከትራፊክ አደጋ የፀዳች፣ ከአካባቢ ብክለት የዳነች ሀገር ማየት ይቻላል፡፡**
2. **አለም የሚጠቀምበትን የትራንስፖርት ማኔጅመንትና ፕላን ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኙ የመንግሥት መዋቅራዊ አካላት፣ የትራንስፖርት ኦፕሬተሮች መብት፣ ግዴታቸውና፣ ተጠያቂነታቸውን አውቀው የሚሰሩበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡**
3. **ከተሞቻችን በዘመናዊው የመሬት ፕላን አጠቃቀም በመጠቀም የከተማ ትራንስፖርት ማኔጅመንትና ፕላኒንግ ሥራ ላይ ማዋል ከቻሉ የከተማ ነዋሪዎች አስተማማኝ የሆነ የከተማ ህዝብ ትራንስፖርት /በዓይነትና በብዛት የተሻለ/ አገልግሎት ሊቀርብ ይችላል፡፡ እግረኞችም ሆነ ብስክሌት ተጠቃሚዎች ለትራፊክ አደጋ የመጋለጥ ስጋታቸው ይቀንሣል፣ ብሎም ይጠፋል፡፡**
4. **በተሽከርካሪ የተነሣ እየተከሰተ ያለው የአካባቢ ብክለት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እየታገዘ ህግ ወጥቶለት በተግባር መተርጉም ከተቻለ ሰው፣ አየር፣ ውሃ፣ አፈር፣ ዕጽዋትና እንስሳት ከማንኛውም የትራንስፖርት ብክለት የፀዳና ንፁህ አየር መተንፈስ የሚቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡**
5. **የዘመናዊ ትራንስፖርት ማኔጅመንት አሠራርና ፅንሰ ሃሣብ በህብረተሰባችንና ኦፕሬተሮች ውስጥ ማስረጽ ከተቻለ በኦፕሬሽን ወጪ ከፍተኛነት የሚደርስብን ጉዳት /በደል/ ይቀንስልናል፡፡**
6. **ለክልሎች እኩል /የተመጣጠነ/ ትኩረት ወጥቶ የመሠረተ ልማት ግንባታና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ከተደረገ በሀገራችን ያሉ ወደ 85 የሚጠጉ ብሔር ብሔረሰቦች የኢትዮጵያዊነት ስሜት አዳብረው ሀገር በጋራ እንድትለማ ማድረግ ይቻላል፡፡**
7. **ለባህር ትራንስፖርት ልዩ ትኩረት ከተደረገና አስተማማኝ የምንጠ ቀምበት ወደብ እንዲፈጠር ከተደረገና በምድር ባቡር በኩል እስከ ዛሬ ያለው አመለካከት ከተቀየረና ለሀገራችን በሚጠቅም መልኩ ከተስተካከለ በአንድ መስመር ብቻ ከመወሰን ቢያንስ ከ3-5 መስመሮች ሊኖረን ይችላል፡፡**
8. **ለሞተር አልባና የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስፋፋት ትኩረት ከተሰጠና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ከቻልን ድሆች የተሻለ አጋጣሚ የሚፈጠርላቸው በመሆኑ ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ተቋዳሽ ይሆናሉ፡፡**
9. **ለገጠር ትራንስፖርት ትኩረት ከተሰጠዉ የግብርና ኢኮኖሚያችን ጥገኛ መሆኑ ቀርቶ አጋዥና ደጋፊ ሴክተር ይሆናል።**

መንገድና ልማት በኢትዮጵያ*

በቀለ ንጉሴ[1]

1. መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የመንገድ አውታር ይዘታ፣ በብዛትም ሆነ በጥራቱ ረገድ ሲመዘን፣ እጅግ የከፋ የብቃት ጉድለት እንዳለበት የሚያጠያይቅ አይደለም።

የመንገድ ትራንስፖርት ዋናው የማመላለሻ ዘርፍ ሲሆን፣ በከተሞች መካከል ከሚጓጓዘው ሕዝብና ከሚንቀሳቀሰው ጭነት 95% ያህሉን ድርሻ የያዘ ነው። ይህም ሆኖ ከኢትዮጵያ የመሬት ስፋትና ሕዝብ ብዛት ጋር ሲነፃፀር ያለው የመንገድ አውታር በጣም አነስተኛ ነው።

በ2005 ዓ.ም. በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የነበረው መንገድ ጠቅላላ ርዝመት 37018 ኪ.ሜ. ሲሆን፣ 70% የሚሆነው ሕዝብ መንገድ ለማግኘት ለስድስት ሰዓታት ያህል መጓዝ ይገደዳል። ይህም በገጠር አካባቢዎች የኢኮኖሚውን ልማት እያደናቀፈ ነው። በኢትዮጵያ ተለይቶ የሚታወቀው የመንገድ መረብ ያለበት አጠቃላይ ሁኔታ አስከፊ ነው። በአሁኑ ወቅት በደህና ሁኔታ ላይ የሚገኘው የመንገድ አውታር 39% የሚሆነው ብቻ ነው።

አንድ ሰው በሰዓት 80 ኪ.ሜ. ሳያቋርጥ እየነዳ ቢጓዝ በኢትዮጵያ ያሉትን መንገዶች አውታር በሙሉ ለመጓዝ 20 ቀን ይፈጅበታል። በዚሁ ሁኔታ ይኸው ሰው በአሜሪካ መንገዶች ላይ ተጉዞ ያለውን አውታር ለማጠናቀቅ 470 ሳምንታት (3290 ቀናት) ያህል ይፈጅበታል።

በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የመንገድ መሠረተ ልማትን ማሻሻል በሚከተሉት መንገዶች የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን ያግዛል።

- **የመንገድ ትራንስፖርት የምርት ንብረቶችና ገበያዎች ወደሚገኙባቸው ሥፍራዎች በቀላሉ ለመድረስ ይረዳል።**
- **ገበያን ያስፋፋል፤ የንግድ ልውውጥን በቀለጠፈ ሁኔታ ለማከናወን ይረዳል።**

[1] አቶ በቀለ ንጉሴ BA. ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በ1979 ያገኙ ሲሆን፣ MSc ዲግሪያቸውን ደግሞ በትራንስፖርት ኢንጂነሪንግ በ1992 ከኒዘርላድ አግኝተዋል። አቶ በቀለ ንጉሴ በተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎች ላይም ተሳትፈዋል። የሥራ መስክን በተመለከተ በኢትዮጵያ መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያገለገሉ ሲሆን፣ በአሁኑ ሰዓት የፕላንና ፕሮግራም መምሪያ ኃላፊ ናቸው። በተጨማሪም በትራንስፖርት ዙሪያ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎችን ያቀረቡ ሲሆን በተለይ የአሥር ዓመት የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ፕሮግራም ጥናት ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ አድርገዋል።

***** **ተለይቶ ካልተጠቀሰ በቀር በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሰው ዓመተ ምህረት ሁሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነው።**

- ብቃት ያለው የመንገድ ትራንስ ፖርት አገልግሎት የሀገር ውስጥ ምርቶች ዋጋ እንዲቀንስ ያደርጋል፣ በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ገበያዎች ውስጥ ውድድር እንዲኖር ያደርጋል።

የመንገድ መረብ መስፋፋት የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን በማስፋት፣ የኢኮኖሚያዊ ሃብትን በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል የሀገሪቱን በአደጋ የመጎዳት መጠን ለመቀነስ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ



በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የሚከናወነው በ1998 ዓ.ም. የተጀመረው የመንገድ ሴክተር ልማት ፕሮግራም አካል የሆነው በመንደር ደረጃ የተደረገው የጉዞና ትራንስፖርት ጥናት ግኝት በ1998 ተጀምሯል። የዚህ ጥናት ግኝት የመንደሮችን የጉዞና የትራንስፖርት ችግሮችን ለመረዳት አገልግሏል።

ችግሮቹ ተለይተው መታወቃቸውም በገጠር አካባቢዎች ለሚታዩ የትራንስ ፖርት ችግሮች የሚበጅ ተግባራዊ መፍትሔ ምን እንደሚመስል ለማሳየት የገጠር የመሠረተ ልማት ፓይለት ፕሮጀክትን ለመቅረጽ አገልግሏል።

ይህን ለማግኘት ጥናቱ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ ሦስት ወረዳዎች ላይ ተካሂዷል። እነዚህ ሦስት ወረዳዎች በደቡብ ማእከላዊ ደጋማ ክፍል የሚገኘው የባኮ ወረዳ፣ በመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኘው ወረዳ፣ በሰሜን ደጋማ ክፍል የሚገኘው **ተኹልደሬ** ወረዳዎች ናቸው።

የጥናቱ ግኝቶች ማጠቃለያ


የአካባቢ ትራንስፖርት

የአካባቢ ትራንስፖርት፣ ማለትም፣ ለቤት ውስጥ የሚያስፈልገውን ማገዶ መሰብሰብን፣ ውሃ መቅዳትን፣ ወዘተ... የሚያካትት ነው። ጥናቱ በተካሄደባቸው ወረዳዎች ውስጥ እነዚህን ተግባሮች ለማከናወን የሚደረጉትን ጉዞዎች 73%፣ ለጉዞዎቹ የሚፈጀውን ጊዜ 61%፣ ለመጓጓዝ የሚወጣውን ጉልበት 93% ያህሉን ይሸፍናል።

በሦስቱ ወረዳዎች እንዲህ ያለው ጉዞ የሚደረግባቸው ሁለት ዋነኛ ተግባሮች ውሃ መቅዳትና ማገዶ መሰብሰብ ሲሆኑ፣ እነዚህ ተጣምረው፣ በዚያው በቀዬው የሚደረገውን ጉዞ፣ ለመጓጓዝ የሚወጣውን ጊዜና የሚፈሰውን ጉልበት ጨምሮ በድምሩ ከ89% በላይ የሚሆነውን ድርሻ ይይዛሉ። በእያንዳንዱ ቤተሰብ

ውስጥ 1058 ሰዓታት ያህል የሚፈጁ ከ792 እስከ 1735 የሚደርሱ የውስጥ ለውስጥ የእግር ጉዞዎች ይደረጋሉ።

በአካባቢው ውሃ፣ ማገዶና ሌሎች ነገሮችን የማጓጓዝ ኃላፊነት በአብዛኛው የሴቶች ነው። ይህንም የሚያከናውኑት፣ አልፎ አልፎ አህያ ከሚጠቀሙት ነዋሪዎች በስተቀር፣ እስከ 25 ኪ.ግ. የሚደርስ ሸክም በጀርባቸው በመሸከም ነው። በአካባቢው ውስጥ የሚደረገው ጉዞ ከ20 - 25% የሚሆነውን የአዋቂ ሴቶች የሥራ ጊዜ የሚወስድ ሲሆን፣ ከ80% በላይ የሚሆነው የማጓጓዝ ተግባራቸውን የሚይዝ ነው። ወንዶችና አህዮች በሴቶች የሚከናወነውን የአካባቢ ትራንስፖርት የሚያግዙትና ሴቶቹን ተክተው የሚሠሩት ወቅትን እየጠበቀ የሚከሰት የውሃ እጥረት ችግር ባለበት ወረዳ ወረዳ ብቻ ነው፡፡ (**በመንደር ደረጃ የተካሄደ የጉዞና የትራንስፖርት ጥናት ግኝቶች - የቤተሰብ የትራንስፖርት ሁኔታ** (ቻርት ይመልከቱ)።



የግብርና ትራንስፖርት

የግብርና ትራንስፖርት በአብዛኛው ጥቂት ጉዞዎች የሚደረጉበት ነው። በተኹልደሬ 87፣ በባኮ ከ200 በላይ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት ከመስክ ወደቤት የሚደረጉ የአጭር ርቀት ጉዞዎች ናቸው። እነዚህም ጉዞዎች በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ለጉዞ ከሚወ ጣው ጊዜ ጥቂቱን የሚይዙ፣ በአመት 285 ሰዓታት ብቻ የሚፈጁ ናቸው።

የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት፣ ወደ ተቋማትና ወደሌሎች ቦታዎች የሚደረጉ ጉዞዎች

እንዲህ ያሉት የጉዞ ዓይነቶች፣ አንድ ቤተሰብ ማኅበራዊ አገልግሎት ለማግኘትና ማኅበራዊ ግዳጆቹን ለማሟላት ያለውን ፍላጎት የሚያንፀባርቁ ናቸው። እነዚህ ጉዞዎች በአብዛኛው ሸክም የሌለባቸውና ረጃጅም ርቀት የሚያስጉዙ ናቸው። ከእነዚህ ጉዞዎች ውስጥ አብዛኞቹ ብዙ ጊዜ በእግር የሚከናወኑና ከነዋሪዎቹ ቀበሌዎች ውጪ የሚደረጉ ሲሆኑ፣ ከወረዳው ውጪ ወዳለ ቦታ የሚደረጉት ደግሞ በሕዝብ መጓጓዣ መኪኖች የሚደረጉ ናቸው። ማኅበራዊ አገልግሎት ለማግኘት የሚደረጉ ጉዞዎች በዓመት በአማካይ 389 ሰዓታት ይፈጃሉ። ጥናቱ በተካሄደባቸው ቦታዎች ይህ ዓይነቱ ጉዞ በሚፈጀው የጊዜ መጠን ሁለተኛ ሲሆን፣ በዓመት ለዚህ ጉዞ የሚወጣው ወጪ ከዓመታዊ ገቢያቸው ከ8% በታች ነው። ይህ ዓይነቱ ጉዞ፣ ለምሳሌ በዚምባብዌ በዓመት ከሚደረገው ተመሳሳይ ጉዞ ካለው የ10% ድርሻ ጋር ተመሳሳይ ነው። (*በኢትዮጵያ በመንደር ደረጃ የሚኪያጄድ ጉዞና ትራንስፖርት*፣ ሴፕቴምበር 1999)።

ይህ ማስረጃና ሁኔታ በመላ ሀገሪቷ ያለውን የመንገድ ሴክተሩን ችግር ለመቅረፍ የተቀናጀ ስልታዊ የመፍትሔ እርምጃ እንደሚያስፈልግ የሚያመለክት ነው።

2. የመንገድ ሴክተር ልማት ፕሮግራም

መንግሥት የመንገድ ሴክተሩ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ልማት የሚጫወተውን ወሳኝ ሚና በመገንዘብ የመንገድ ሴክተር ልማት ፕሮግራም (RSDP) ጀምሯል። ይህም የመንገድ አውታሮቹን መሻሻልና መስፋፋት ለማፋጠን የሚከናወን ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ ቁልፍ የሆኑ ለመንገድ ሥራ የተቀየሱ ኢንቨስትመንቶችንና ዋና ዋና የፖሊሲና የተቋማት ለውጦችን አተገባበር ለማቀናጀት የሚቻልበትን ሁሉን አቀፍ ዘዴ የሚጠቁም ነው።

የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (RSDP) በአስር ዓመታት ውስጥ (1997 - 2007) እንዲከናወን የታቀደ ሲሆን፣ የመንገዶች ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (RSDP) **«1»** እና የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (RSDP) **«2»** ተብለው በሚጠሩ በሁለት ደረጃዎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (RSDP) በጁን 2002 ተጠናቅቋል። አሁን እየተከናወነ ያለው የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (RSDP) **«2»** በ2002 የተጀመረ ሲሆን፣ የሚጠናቀቀው በ2007 ነው።

የአለም ባንክ፣ የአውሮፓ ኅብረት፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ የአረብ ባንክ ለአፍሪካ የኢኮኖሚ ልማት (BADEA)፣ የነዳጅ አምራች ሀገሮች ድርጅት ፈንድ (OPEC Fund) እና የኢትዮጵያን መንግሥት ጨምሮ፣ የጃፓን፣ የጀርመን፣ የዩናይትድ ኪንግደም፣ የአየርላንድና የስዊድን መንግሥታትና ሌሎች ረጂዎች ፕሮግራሙ በተግባር እንዲውል አስፈላጊውን የገንዘብ ድጋፍ እየሰጡ ናቸው። ሁለተኛው የመንገድ ግንባታ ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ሲጀመር የሳውዲ የልማት ፈንድ ለፕሮግራሙ የገንዘብ ድጋፍ ከሚያደርጉት ጋር ተቀላቅሏል።

የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዓላማዎች

ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ልማት መርሐ ግብር ዘላቂነት ዋና እንቅፋት የሆኑትን የመንገድ አውታሮች መጠገንና ማስፋፋት፤

- የመንገድ አውታሮቹን አያያዝና አስተዳደር ማሻሻል
- የሀገር ውስጥ የግንባታ ኢንዱስትሪን አቅም ማሳደግ
- በአጠቃላይ ለድህነት ቅነሳው አስተዋጽኦ ማድረግ

የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ግቦች

የመንገድ ይዞታን የሚመለከተው ግብ በ1997 ዓ. ም. 18% የነበረውን የመንገዶች ጥሩ ይዞታ በ2007 ዓ.ም. ወደ 45% ማሳደግና በተጨማሪም በጥናት በተመረጡ ቦታዎች በየአንድ ሺህ ካሬ ኪ.ሜ. 36 ኪ.ሜ. አዲስ መንገድ (በዝቅተኛ ደረጃ ያሉ መንገዶችንም ጨምሮ) መገንባትና በአብዛኛው መረብ ላይ መደበኛ ጥገና ማካሄድ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የመንገድ አውታሮቹን መጠን በሚመ ለከት በ2007 በየአንድ ሺህ ሰው 0.50 ኪ.ሜ. መንገድ ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል።

የመንገድ ግንባታ ዘርፍ የልማት ፕሮግራም እንቅስቃሴ አሁን ያለበት ደረጃ

በሴፕቴምበር 1997 ዓ.ም. መጀመሩ በይፋ የተገለጸው የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም በሥራ ላይ መዋል ከጀመረ 8 ዓመት ሆኖታል። ይህ ፕሮግራም በመጥፎ ሁኔታ ላይ በሚገኘው የመንገድ መረብ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት፣ ኢኮኖሚውን ለመደገፍና የመጓጓዣ አገልግሎት ሥርዓቱን ለማሻሻል ሲባል የቢሮ ሥራዎችን (የሲቪል ሥራዎችን)፣ የአቅም ግንባታን፣ የፖሊሲ ጉዳዮችንና ሌሎች ነገሮችንም በውስጡ አካትቷል።

በመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ውስጥ መካተት የሚገባቸ ውን ዕቅዶች በደረጃ ለመምረጥ የሚያስፈልገው መሥፈርት ፕሮግራሙ በተዘጋጀበት ወቅት በግልጽ ተለይቶ በመቀመጡ የፕሮግራሙ ተግባራዊነት በትክክል መሥፈርቱን የተከተለ ነው። የገንዘብ ወጪያቸው በመንግሥትና በተራድኦ ድርጅቶች የሚሸፈኑና በመሥፈርቱ የተመረጡ ዕቅዶች የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ እየተከናወኑ ነው። የብዙ አውራ መንገዶችን ደረጃ የማሳደግ/ መልሶ የመገንባት ተግባሮች ሲከናወኑ ነበር፤ አሁንም እየተከናወኑ ነው። ከሀገሪቱ ግብርና-መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣሙና ለልማቱ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ አካባቢዎችን ለማገናኘትም አዳዲስ አገናኝ መንገዶች ተገንብተዋል።

እስከ ጁን 2005 ድረስ ባሉት የስምንት ዓመታት ጊዜ ውስጥ 14536 ኪ.ሜ. ርዝመት ያላቸው መንገዶች ተሠርተዋል፤ ደረጃቸው አድጓል/የመልሶ ግንባታና እድሳት ሥራ ተካሂዶባቸዋል። ከነዚህም ውስጥ 6848 ኪ.ሜ. የሚሆኑት የፌዴራል መንገዶች ሲሆኑ 7687 ኪ.ሜ. የሚሆኑት ደግሞ አዲስ የተሠሩ የክልል

መንገዶች ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ የሁሉም ዐይነት መንገዶች ጥገና ተካሂዷል፤ ለጥገና የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና የብረት ድልድዮች ተገዝተዋል።

ለብዙ ፕሮጀክቶች የሚያገለግሉ የተቋማት አቅም ግንባታ፣ በፖሊሲ የተደገፉ ዕቅዶችና ዝርዝር ዲዛይኖች/ የዲዛይን ማሟገማዎች፣ የተግባራዊነት ፍተሻ እና የEIA ጥናቶች ተከናውነዋል። በነዚህ ዓመታት ለሚከናወኑት ዕቅዶች ተይዞ የነበረው በጀት ብር 15.1 ቢሊዮን (1.776 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር) ሲሆን፣ በሥራ ላይ የዋለው ደግሞ ብር 15.0 ቢሊዮን (1.741 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር) ነው። ይህም ከታቀደው ውስጥ 99% የሚሆነውን ያካተተ ነው። (ዝርዝሩን በሠንጠረዥ 1 ይመልከቱ)።

ሠንጠረዥ 1፡ የተከናወኑ ሥራዎችና የገንዘብ ወጪያቸው

	የተከናወኑ (በኪ.ሜ.)	አማካይ ዓ.ም.	ክንውን በመቶኛ	ወጪ (በሚሊዮን ብር)	አማካይ የዓመት ወጪ	ክንውን በመቶኛ
የፌዴራል መንገዶች	**6848**		**102.5**	**12190.4**		**107.8**
የአውራ መንገዶች መልሶ ግንባታ	1590	199	83.8	4664.7	583.1	109.3
የአውራና የአገናኝ መንገዶች ደረጃ ማሳደግ	1505	188	97.7	3389.8	423.7	113.8
የአዳዲስ አገናኝ መንገዶች ግንባታ	1136	142	114.6	1467.3	183.4	104.4
የፌዴራል መንገዶች ከባድ ጥገና	2617	327	124.1	789.6	98.7	102.4
የእለት ተእለት ጥገና				1121.8	140.2	110.7
ሌሎች (ተቋማዊ እገዛዎችን ጨምሮ)				757.2	94.7	86.8
የክልል መንገዶች	**7687**		**122.8**	**2606.5**	**325.8**	**68.6**
ግንባታ፣ ጥገናና ሌሎች	7687	961	122.8	2606.5	325.8	68.6
የማኅበረሰብ?? መንገዶች				**24.9**	**5.0**	**19.1**
አዳዲስ ተግባራት				24.9	5.0	19.1
የከተማ መንገዶች				**173.1**	**21.6**	**362.9**
የእለት ተእለት ጥገና				173.1	21.6	362.9
ድምር	**14536**		**112.3**	**14,995.0**	**1,874.4**	**99.4**

ባለፉት ስምንት ዓመታት ውስጥ የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የገንዘብ ወጪ፣ ወጪውን ከሸፈኑት አካላት አንፂር ሲታይ፣ ከ50% በላይ የሚሆነው ገንዘብ የተገኘው ከሀገር ውስጥ ምንጮች (ከኢትዮጵያ መንግሥትና ከመንገድ ፈንድ) ሲሆን፣ ቀሪው (46%) ደግሞ ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የተገኘ ነው። በተናጠል ሲታይ የኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛውን ወጪ (40%) ሲሸፍን፣ በመከተል አለም አቀፍ የልማት ድርጅት (IDA) (25%)፣ የመንገድ ፈንድ (14%)፣ የአውሮፓ ኅብረት (9%) እና ሌሎች አበዳሪ መንግስታትና ድርጅቶች 12% (የጃፓን፣ እንግሊዝ ጀርመን፣ አየርላንድ መንግስታት እና የአፍሪካ ልማት ባንክ ወዘተ... የሚሆነውን ይሸፍናሉ።


3. መንገድ ኢንቨስትመንቱ ውጤት

ስለትራፊክ እንቅስቃሴ

የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም በ1997 ዓ.ም. በተግባር ላይ መዋል ሲጀምር የመንገድ አውታሮቹ ይዞታ መጥፎ ሆኖ በመገኘቱ፣ የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ በጣም አነስተኛ ነበር። የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ተግባራዊ ሲሆን የተወሰኑ መንገዶች ይዞታቸው በመሻሻሉ የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ በከፍተኛ መጠን ጨምሯል። በአውራ መንገዶች የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ

ጥናት ተካሂዶ እንቅስቃሴው በፍጥነት እየጨመረ መሄዱን አሳይቷል። ከመንገዶቹ ልማት ጋር የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴም ጨምሯል። በሁሉም መንገዶች ላይ የሚደረገው የማሻሻል ሥራ ገና ያልተጠናቀቀ ቢሆንም የእንቅስቃሴው አማካይ ዓመታዊ እድገት መጠን 8.4 ሆኗል።

በቻርቱ እንደተመለከተው በመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ወቅት (1997 - 2005) የታየውን የሕዝብ ብዛት፣ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርትና የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ እድገት ያሳያል። የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ብዙ ጊዜ ከሕዝብ ብዛትና ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት እድገት በልጦ ይታያል። ባለፉት 8 ዓመታት የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ በአማካይ በዓመት 8% ሲጨምር የሕዝብ ብዛት እድገቱ 3%፣ የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት እድገቱ ደግሞ ወደ 5% ተጠግቷል።




ስለ መንገድ ሥራ መስፋፋትና ስለ ጥራት

የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ሲጀመር አጠቃላይ በሀገሪቱ የሚገኘው የመንገድ አውታር 26550 ኪ.ሜ. ገደማ የነበረ ሲሆን፣ በየ1000 ሰው 0.46 ኪ.ሜ. እና በእያንዳንዱ ኪ.ሜ. ካሬ 24.4 ኪ.ሜ. ነበር። በመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም በተካሄደበት የስምንት ዓመታት ጊዜ ውስጥ አዳዲስ የጋረጋንቲ መንገዶችና የክልል መንገዶች በመሠራታቸው በ2005 አጠቃላይ የመንገድ አውታሩ ርዝመት ወደ 37018 ኪ.ሜ. አድጓል። ሀገሪቱ ባላት 1.1 ሚሊዮን ስኳር ኪ.ሜ. ካሬ ስፋትና 37018 ኪ.ሜ. የመንገድ አውታር አሁን ያለው የመንገድ መጠን በየ1000ው ኪ.ሜ. ካሬ 33.6 ኪ.ሜ. ሲሆን፣ በየ1000ው ሰው ደግሞ 0.51 ኪ.ሜ. ሆኗል። ይህም በመንገድ ስፋት 9.5 ኪ.ሜ. የጨመረ ሲሆን በሕዝብ ብዛት ደግሞ 0.05 ኪ.ሜ. እንደጨመረ ያሳያል። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የመንገድ አውታር ከ1951 - 1973 ድረስ ባሉት ዓመታት በአማካይ በ2.05%፣ ከ1974 - 1991 ድረስ ባሉት ዓመታት ደግሞ 6.2% እና ከ1992 - 2005 ባሉት ዓመታት 8.1% ጨምሯል።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የሀገሪቱ የመንገድ አውታሮች መሻሻል የመንገድ አውታሩን ይዞታ ቀስ በቀስ እየለወጠው ነው። በመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የመጀመሪያው ዓመት ላይ 52% የሚሆነው

የመንገድ አውታር በመጥፎ ይዞታ ላይ ይገኝ የነበረ ሲሆን፣ 22% የሚሆነው ብቻ በጥሩ ይዞታ ላይ ይገኝ ነበር። በተከታታይ እየተከናወኑ ባሉት የፕሮግራሙ የመልሶ ግንባታ፣ የደረጃ ማሳደግና የጥገና ተግባራት ምክንያት በጥሩ ይዞታ ላይ የሚገኘው የመንገድ አውታር ወደ 65% ከፍ ሲል፣ በአንፃሩ ደግሞ በመጥፎ ይዞታ ላይ የሚገኘው ወደ 35% ዝቅ በሏል።

በቀረበው ቻርት ላይ እንደሚታየው፣ ከ1990ዎቹ ወዲህ የመንገድ አውታሩ እያደገ፣ በመጥፎ ይዞታ ላይ የሚገኘው አውታር ደግሞ እየቀነሰ መጥቷል። ይህም የሚያሳየው መንገድ ባልነበረባቸው ቦታዎች አዳዲስ መንገዶች ከመገንባታቸው በተጨማሪ፣ በመልሶ ግንባታና በጥገና ላይ የሚወጣው ወጪ አውታሩን በማሻሻል ረገድ የማይናቅ ሚና መጫወቱን ነው።



ሌሎች የመንገድ ቅርበት ጠቋሚዎች፤ መንገድ በቀላሉ ሊገኝ የሚችልበትን ሁኔታ ለመለካት በዚህ ጥናት ላይ የተጠቀምነው ራንደም የመንገድ አውታር መጠን ሞዴል[1] የሚባለውን ነው። ራንደም የመንገድ አውታር የሚባለው በአንድ ቦታ በዘፈቀደ ተሰባጥረው የተሠሩ በጣም ረጃጅምና ቀጥ ያሉ መንገዶችን ያካተተ አውታር ነው። አንድ ራንደም የመንገድ አውታር በአቅራቢያው ከሚገኘው መንገድ ያለው አማካይ ርቀት ሲሰላ፣ ቀመሩ የሚከተለውን ይመስላል፤

$$\text{አማካይ ርቀት (m)} = \frac{\text{የቦታ ስፋት}}{\text{የመንገድ ርዝመት}} \times \frac{1}{2}$$

ለራንደም የመንገድ አውታር የአካባቢው ስፋት ከአውታሩ ከተወሰነ ርቀት (d) በላይ ሲገኝ፣ ምጥጥኑ (Proportion):


$$e^{-d/m}$$


እዚህ ላይ m ከመንገዱ አውታር ያለውን አማካይ ርቀት ያመለክታል።

ከመንገድ አውታሩ በአማካይ ያለውን ርቀት በበጋም በክረምት ከሚያገለግል መንገድ ከ5 ኪ.ሜ. በላይ ከሚርቁ ቦታዎች ጋር በማመጣጠን ለመንገዱ ያለው ቅርበት ሲለካ የመንገድ አውታሩ በመስፋፋቱ ትልቅ ግምት የሚሰጠው እድገት እንዳለ ማየት ይቻላል።

በሀገሪቱ ያሉ ቦታዎች ከመንገድ ያላቸው አማካይ ርቀት በ1997 ዓ.ም. 21 ኪ.ሜ. የነበረ ሲሆን፣ በ2005 ወደ 16 ኪ.ሜ. ቀንሷል፤ ይህም የሆነው አዳዲስ መንገዶች በመገንባታቸው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ በበጋም በክረምትም ከሚያገለግል መንገድ ከ 5 ኪ. ሜ. በላይ የሚርቁ ቦታዎች መጠን በ1997 ዓ.ም. 79% የነበረ ሲሆን፣ በ2005 ወደ 73% ቀንሷል።

ከዚህ በላይ የታየው ቅርበት ውጤት GIS environment በሚጠቀሙ ካርታዎች ላይ ነጂ ቀጠናዎችን ባለው የመንገድ አውታር ላይ በመፍጠር ተፈትኖ የተደረሰበት ነው። እንደዚሁ ነጂ ቀጣናዎች በተለያዩ ርቀቶች ላይ እንዲኖሩ ተደርገዋል (ለምሳሌ 5፣ 10 እና 20 ኪ.ሜ.)። በዚህ ትንተና መሠረት፣ አሁን ባለው የመንገድ አውታር ላይ በተጠቀሱት ርቀቶች ክልል ውስጥ ምን ያህል አካባቢዎች እንደሚገኙ ለመገመት ይቻላል። (የቀረቡትን ካርታዎች ይመልከቱ።)





ከካርታው የተገኘው ውጤት ከሀገሪቱ አጠቃላይ ስፋት 27% ያህል የሀገሪቱ ክልል ከመንገድ አውታር ከ5 ኪ. ሜ ባልበለጠ ርቀት ላይ የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጣል (ይህም የቀረበውን ወጤት ትክክለኛነት ያሳያል)።

በተመረጡ ከሰሀራ በታች በሚገኙ ሀገራት ውስጥ (ሠንጠረዥ 2) በበጋና በክረምት ከሚያገለግሉ መንገዶች ከ2 ኪ.ሜ. ባነሰ ርቀት ላይ የሚገኘውን ሕዝብ ብዛት በመቶኛ የማያነፃፅር ነው። ኢትዮጵያ በስፋት ትልቅ ሀገር እንደመሆኗ በበጋም በክረምትም ከሚያገለግሉ መንገዶች ከ2 ኪ.ሜ. ባነሰ ርቀት ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ መጠን በጣም አነስተኛ ነው።

ሠንጠረዥ 2፡ ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገሮች ለመንገድ ያለው የቦታዎች ቅርበት ንጽጽር

Benin ቤኒን	32%
Burkina Faso ቡርኪና ፋሶ	19%
Burundi ቡሩንዲ	19%
Cameron ካሜሩን	20%
Chad ቻድ	25%
Ethiopia ኢትዮጵያ	**12%**
Ghana ጋና	44%
Kenya ኬኒያ	44%
Madagascar ማዳጋስካር	67%
Malawi ማላዊ	38%
Mali ማሊ	51%
Niger ኒጀር	52%
Nigeria (eight states) ናይጀሪያ (8 ግዛቶች)	47%

Tanzania ታንዛኒያ	38%
Zambia ዛምቢያ	51%

የመንገድ ጥራት በትራንስፖርት ታሪፍ ላይ ያለው ጫና

የመንገድ ትራንስፖርት ክፍያ መጠን በሀገሪቱ ውስጥ ካሉት መንገዶች የጥራት ሁኔታ ጋር በጣም የተቆራኘ ነው። የአንድ መንገድ ይዞታ ከተበላሸ ወዲያውኑ የትራንስፖርት ታሪፉ አንድ ቶን/ በኪ.ሜ. እጥፍ ወይም ሦስት እጥፍ ይጨምራል። የመንገዱ ይዞታው ሲበላሽ ታሪፉ እንደሚጨምረው ሁሉ፣ ይዞታው ከተሻሻለ ደግሞ ለአንድ ቶን በኪ.ሜ. የሚከፈለው የትራንስፖርት ታሪፍ በአስገራሚ ሁኔታ ወዲያው ይቀንሳል።

በሠንጠረዥ 3 ውስጥ እንደሚታየው፣ የትራንስፖርት ዋጋ ካልተጠገኑት (መልሶ ግንባት ካልተካሄደባቸው) መንገዶች የበለጠ በተሻሻሉት መንገዶች ላይ ቀንሷል። በተሰባበሩት መንገዶች ላይ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ዋጋ በቅርቡ መልሶ ግንባታ ከተደረገላቸው መንገዶች በእጥፍ ይበልጣል። እንደዚሁ የአዲስ አበባ ጂቡቲ መስመርን ከኡጋንዳና ከሩዋንዳ (ሁለቱም ሀገራት የሞምባሳ ወደብን የሚጠቀሙ ናቸው) ብናወዳድር ከሞምባሳ ወደ ካምፓላ ለሚደረግ ትራንስፖርት የሚከፈለው ለአንድ ቶን በኪሎ ሜትር 0.080 የአሜሪካ ዶላር፣ ከሞምባሳ ወደ ኪጋሊ የሚደረገው ደግሞ ለአንድ ቶን በኪሎ ሜትር 0.098 ነው። ከጂቡቲ ወደ አዲስ አበባ ለአንድ ቶን በኪ.ሜ የሚከፈለው ግን 0.049 የአሜሪካ ዶላር ነው። ከዚህ በመነሳትም፣ በኢትዮ-ጅቡቲ መስመር ላይ የሚከፈለው ዋጋ ጥሩ ነው ማለት ነው። በኢትዮጵያ የመንገዶች መልሶ ግንባታ ጥረት የገቢና ወጪ ምርቶች በሚመላለሱበት መስመር (መንገድ) ላይ ማተኮሩ ከፍተኛ መሻሻል ያስገኘ ሲሆን፣ ይህም በተለይ በዚህ መስመር ያለውን የማጓጓዣ ዋጋና ጉዞው የሚፈጀውን ጊዜ ቀንሶታል።

ሠንጠረዥ 3፡ የሀገር ውስጥ የትራንስፖርት ዋጋ ከጂቡቲ ወደብ

Route መንገድ	Road Condition የመንገዱ ይዞታ	Cost per ton km (in $) ዋጋ ለአንድ ቶን በኪ.ሜ. (በአሜሪካ ዶላር)	% change in cost from rehab. Road የመልሶ ግንባታ ከተካሄደባቸው መንገዶች የከፍያው ልዩነት በ%
ጂቡቲ - መቀሌ	Partly improved	0.076	+55%
ጂቡቲ - ወረታ	Partly improved	0.073	+49%
ጂቡቲ - ሻሸመኔ	Rehabilitated	0.049	---
ጂቡቲ - አዲስ አበባ	Rehabilitated	0.049	---
ጂቡቲ - ኮምቦልቻ	Partly improved	0.061	+25%

ጂቡቲ - ሽኒሌ	Rough road	0.094	+92%

በሠንጠረዥ 3 ውስጥ እንደሚታየው፣ የትራንስፖርት ዋጋ ካልተጠገኑት (መልሶ ግንባት ካልተካሄደባቸው) መንገዶች የበለጠ በተሻሻሉት መንገዶች ላይ ቀንሷል። በተሰባበሩት መንገዶች ላይ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ዋጋ በቅርቡ መልሶ ግንባታ ከተደረገላቸው መንገዶች በእጥፍ ይበልጣል። እንደዚሁ የአዲስ አበባ ጂቡቲ መስመርን ከኡጋንዳና ከሩዋንዳ (ሁለቱም ሀገራት የሞምባሳ ወደብን የሚጠቀሙ ናቸው) ብናወዳድር ከሞምባሳ ወደ ካምፓላ ለሚደረግ ትራንስፖርት የሚከፈለው ለአንድ ቶን በኪሎ ሜትር 0.080 የአሜሪካ ዶላር፣ ከሞምባሳ ወደ ኪጋሊ የሚደረገው ደግሞ ለአንድ ቶን በኪሎ ሜትር 0.098 ነው። ከጂቡቲ ወደ አዲስ አበባ ለአንድ ቶን በኪ.ሜ የሚከፈለው ግን 0.049 የአሜሪካ ዶላር ነው። ከዚህ በመነሳትም፣ በኢትዮ-ጅቡቲ መስመር ላይ የሚከፈለው ዋጋ ጥሩ ነው ማለት ነው። በኢትዮጵያ የመንገዶች መልሶ ግንባታ ጥረት የገቢና ወጪ ምርቶች በሚመላለሱበት መስመር (መንገድ) ላይ ማተኮሩ ከፍተኛ መሻሻል ያስገኘ ሲሆን፣ ይህም በተለይ በዚህ መስመር ያለውን የማጓጓዣ ዋጋና ጉዞው የሚፈጀውን ጊዜ ቀንሶታል።

በሀገሪቱ ውስጥ ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ከተደረጉት የተለያዩ ጥናቶች በተሰበ ሰቡት መረጃዎች ላይ በመመስረት የመንገድ ይዞታ በእንሰሳት መጓጓዣዎች ላይም የሚፈጥረው ለውጥ ተመርምሯል (ተተንትኗል)። የትንተናው ውጤቶች እንደሚያሳዩት የመንገዱ መሻሻል ሰዎችና እንስሳት በቀላሉና በፍጥነት እንዲራመዱ ያስችላቸዋል።

በብልሽት ትንተና ቀመር መሠረት የተደረገው የትራንስፖርት ታሪፍ ትን ተና እንደሚያለክተው፣ አውራ መንገዶች የቆረቆሱ ሲሆኑ እቃዎችን በእንስሳት ማጓጓዙ በተሸከርካሪ ከማጓጓዝ ይልቅ ርካሽ ሆኖ ተገኝቷል። ነገር ግን በተሰባበረ መንገድ ላይም ረዥም ርቀት በእንሰሳት ከመጓዝ ይልቅ በተሽከርከሪ መጓዝ ርካሽ ነው። አውራ ጐዳናዎች በጥሩ ሁኔታ ላይ ከሆኑ ዕቃዎችን በጭነት መኪናዎች ማጓጓዝ ለረዥም ጉዞ ብቻ ሳይሆን ለአጭርም ጉዞ ርካሽ ነው።

ለ50 ኪሎ ሜትር ጉዞ አንድ ሰው የሚከተሉት የጭነት መጓጓዣ ዋጋዎች ሊገጥሙ እንደሚችሉ ማሰብ አለበት፡-

ሀ. ዋና ጉዳና፡- በኩንታል ብር 8.55

ለ. የተጎሳቆለ መንገድ፡- በኩንታል ብር 19.35


ሐ. በእንስሳት፡- በኩንታል ብር 35.15


በአውራ ጉዳናዎች እና በተጎሳቆሉ መንገዶች መካከል ያለውን የትራንስ ፖርት ታሪፍ ልዩነት ስንመለከት፣ በተጎሳቆሉት መንገዶች ላይ የሚከፈለው በተሻሻሉት አውራ ጉዳናዎች ላይ የሚከፈለውን ላይ አራት እጥፍ ሆኖ እናገኘዋለን።

የትራንስፖርት ዋጋ፣ የማዳበሪያ አጠቃቀምና የሚያስከትላቸው ውጤቶች

ከፍተኛ የትራንስፖርት ዋጋ ማዳበሪያ ለገበሬዎች በሚሸጥበት ዋጋ ላይ ለውጥ ያስከትላል፤ ይህ ደግሞ በተራው በማዳበሪያ መጠቀም መቻልን ያዳክማል፤ በማዳበሪያ አለመጠቀም ደግሞ ምርትን ይቀንሳል። በኢትዮጵያ የማዳበሪያ ስርጭት ጥናት እንደሚያሳየው፣ ደቡብና ሰሜን ወሎ በሀገሪቱ ውስጥ ማዳበሪያን በዝቅተኛ ደረጃ የሚጠቀሙ ናቸው። በሁለቱም አካባቢዎች የማዳበሪያ ዋጋ ከሌሎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ከፍተኛ መሆኑ ተመዝግቧል። የዚህ ምክንያቱ በከፊል የትራንስፖርት ዋጋ ከፍተኛ መሆን ነው።

በማዳበሪያ መጠቀም ምርትን እንደሚ ጨምር ግልፅ ነው፤ በምርት መጠንንና ማዳበሪያን በመጠቀም መካከል ያለው ግንኙነት ቀጥተኛና ተካካቢ ነው። የመንገድ አውታር ባደገባቸው አካባቢዎች የማዳበሪያ ዋጋ ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ገበሬዎች በማዳበሪያ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙ በማስረጃ ማረጋገጥ ይቻላል።





አዳዲስ መንገዶች በምርታማነት መጠን ረገድ የሚያመጡት ለውጥ

በአጠቃላይ ሲታይ፣ በገጠር አካባቢዎች የትራንስፖርት አገልግሎት አይኖርም፤ ምክንያቱም በነዚህ አካባቢዎች ያሉት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ አገናኝ መንገዶች በመሆናቸውና የመንገዶች መበላሸት የመጓጓዣ ዋጋውን ስለሚያሳድገው ነው። ስለዚህ ጥርጊያ መንገዶችን ወደ ኰረኮንች መንገድነት ማሳደግ በገጠር አካባቢዎች በግብርናና በማኅበራዊ ልማት ላይ በጣም ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል። ገበሬዎች ቤተሰቦቻቸውን ለመመገብና ወደ ገበያ አውጥተውም ለመሸጥ የሚበቃ ምርት ማምረት ያስፈ ልጋቸዋል። ስለዚህ የመንገዶች መኖር ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የሚያሰፈልጋቸውን ማዳበሪያና ዘር ወደ አካባቢያቸው ለማጓጓዝ ያስችላቸዋል። እንዲሁም የመንገዶች መኖር ገበሬዎች ምርታቸውን ለገበያ ለማቅረብ ያስችላቸዋል።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው፣ በመጀሪያው የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ወቅት በጪዳ ሶዶ መስመር የተገነባው ከፍተኛ ደረጃ ያለው ገረጋንቲ መንገድ ነው። ይህ መንገድ ከመሠራቱ በፊት ጥርጊያ መንገድ የነበረ ቢሆንም፣ የአካባቢው ኮረብታማነት፣ አንሸራታ ችነትና ተራራማነት አቧራው በተሸከርካ ሪዎች ላይ ከሚያደረሰው ችግር ጋር ተደማምሮ በነዚህ ጠቀሜታ ባላቸው ዋና ዋና አካባቢዎች የትራንስፖርት አገልግለት አልነበረም። ነገር ግን ከፍተኛ ደረጃ ያለው የጪዳ - ሶዶ ገረጋንቲ መንገድ ከተሠራ በኋላ ግን በነዚህ አካባቢዎች ለሚኖሩት የገጠር ሰዎች የትራንስፖርት አገልግሎት መሰጠት ተጀምሯል። መንገዱ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ከአንድ አመት ከመንፈቅ በኋላ በአፍሪካ ልማት ባንክ በ2000 ዓ.ም. የድኅረ ግንባታ ጥናት ተካሂዶ ነበር። ይህ ጥናት የመንገዱ መሠራት የብዙ ዐይነት የእህል ዘሮች የምርት መጠን ከ100% በላይ እንዲጨምር አድርጓል (ሠንጠረዥ 4ን ይመልከቱ)።

ሠንጠረዥ 4፡ የምርት መጠን ንፅፅር (ኩንታል በሄክታር)

Crop Type የእህል ዐይነት	Before road construction መንገዱ ከመሠራቱ በፊት የነበረው ሥራ	With the project (Assumed) በፕሮጀክቱ ጊዜ [illegible]	Actual መንገዱ ከተሠራ በኋላ በእውን የተመረተው
Teff ጤፍ	5	12	12
Maize በቆሎ	15	30	60
Wheat ስንዴ	7	14	24

የመንገድ ዘርፉ በአስቸኳይ ጊዜ የእርዳታ ምግብ ሥርጭት ላይ ያለው ተፅዕኖ

> መንገድ ካለን፣ የማኅበረ ሰብዕ ማእከላትን፣ የሥራ እድልን፣ የፖስታ አገልግሎትን፣ ውሃና ስልክን ጨምሮ፣ የቀረውን ነገር ሁሉ ማግኘት እንችላለን።
>
> አንዲት የሊትል ቤይ፣

በኢትዮጵያ ውስጥ፣ በተለይ በድርቅ ጊዜያት በችግር ላይ ያሉትን ለመርዳት በአደጋ መከላከልና ዝግጅት ኮሚሽን የሚከናወን ሁሉን አቀፍ የምግብ ሥርጭት ሥርዓት አለ።

ነገር ግን፣ የዕርዳታ ማከፋፈያ ማዕከሎቹ የሚሠሩት ዓመቱን ሙሉ ሳያቋርጡ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ መንገዶች ባሉባቸው አካባቢዎች ነው። መንገዶች በሌሉባቸው አካባቢዎች ያሉ ሰዎች በእግር መጓዝ አለባቸው (አንዳንዴም በወር አራት ቀን ያህል)።

ደካማና አረጋውያን ሰዎች ብዙ ጊዜ ድርሻቸውን ተቀብለው ለሚያመጡላቸው የጉልበት ዋጋ መክፈል ይኖርባቸዋል። የተሻለ የመንገዶች አውታር መኖር የእርዳታ ማከፋፈያ ጣቢያዎችን በተረጅዎቹ አካባቢ ለመትከል ያስችላል።

4. በመንገድ ግንባታ ዘርፉ ረገድ ሊከናወኑ የታሰቡ የወደፊት እቅዶች

የመንገድ ሴክተሩ ርእይና ተልእኮ የሚከተሉት ናቸው።

ርእይ፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ርእይ ኢትዮጵያውያን በቂና ከፍተኛ ጥራት ያለውን የመንገዶች አውታር ማግኘታቸውን ማረጋገጥና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙትን የልማት አቅም ያላቸውን አካባቢዎች በመንገድ ማገናኘት ነው።

ተልእኮ፡ ለሀገሪቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ድጋፍ የሚሰጥ አስተማማኝ፣ ምቹ፣ እና በቂ የመንገድ መሰረተ ልማት መዘርጋትና የመንገድ ተጠቃሚ ዎችን ፍላጎቶች በሚከተለው መንገድ ማሟላት ነው፤

- የመንገዶችን ይዞታ ማሻሻልና
- የመንገዶቹን አውታር ማስፋፋት

እስከዛሬ ለመንገድ ልማት ፕሮግራም አማካይነት ለመንገድ ሥራ የዋለው ኢንቨስት መንት በመንገድ አውታሩ መጠንና ጥራት ላይ ትንሽ የማይባል መሻሻልን አምጥቷል። ይህም ሆኖ ግን፣ በመንገድ ችግር ምክንያት ሌሎች የልማት ፕሮግራ ሞችን የተሳኩ የማድረጉ ጥረት አዳጋች እንደሆነ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ብዙ ጊዜም መገናኛ መንገድ ባለመኖሩ የገጠሩን ድሃ ህዝብ ለማዳረስ አለመቻሉን የሚጠቁሙ ግልፅ ምልክቶች አሉ። ስለዚህ በሀገር አቀፍ ደረጃ አስተማማኝ የመንገድ ግንኙነት ለማስገኘት አሁን የተያዘውን እንቅስቃሴ ማሳደግ አስፈላጊ ነው።

ሀገሪቱ የሚያስፈልጋትንና ሊደረስበት የሚችለውን የመንገዶች አውታር መጠን ለይቶ ለማወቅ፣ አካባቢዎቹ ምን ያህል በመንገድ እንደተሳሰሩ ከግምት ውስጥ በማስገባት እና/ወይም የመንገዶቹ የአውታር ስርዓት እንዴት እንደተዋቀረ በመተንተን የተለያዩ ዘዴዎችን ወይም ሞዴሎችን መጠቀም ይቻላል።

በተለያየ የትንተና ዘዴዎች የሚያሳዩት በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2020 ተመጣ ጣኝ ትስስር ይፈጥራል በማለት ሊሠራ የታቀደው አጠቃላይ የመንገድ መጠን 167115 ኪ.ሜ. ነው (ይህ የማኅበረሰብ መንገድን ይጨምራል)። የኢትዮጵያ የመንገድ ዘርፍ በኢትዮጵያ በ2020 ዓ.ም. ሊኖረው የሚገባው ርእይ (ወይም ግብ) 170000 ኪ.ሜ. መንገድ እንዲኖር ማድረግ መሆን አለበት። (ሠንጠረዥ 5)

ሠንጠረዥ 5፡- አሁን ያለውና ወደፊት መኖር ያለበት የኢትዮጵያ የመንገድ መረብ ገፅታ

	አሁን ያለንበት ሁኔታ (2005)					በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2020 ይሆናል ተብሎ የተገመተው				
	Vertices (v) መገናኛ ነጥቦች (ጉምብራዎች) (V)	Edges (e) የመገናኛ ጠርዞች	Beta Index (e/v) β መጠቁም	Maximum Possible Edges 3(v-2) ከፍተኛ የመገናኛ ጠርዞች	Gamma Index (e/3(v-2)) γ መጠቁም	Vertices (v) መገናኛ ነጥቦች (ጉምብራዎች) (V)	Edges (e) የመገናኛ ጠርዞች	Beta Index (e/v) β መጠቁም	Maximum Possible Edges 3(v-2) ከፍተኛ የመገናኛ ጠርዞች	Gamma Index (e/3(v-2)) γ መጠቁም
Ethiopia ኢትዮጵያ	1039	971	0.93	3111	0.31	1463	3498	2.39	4384	0.80

የተገመተው የመንገድ አውታር መጠን , 167115 ኪ.ሜ. ነው።

5. ርእይ 2020

በ2005 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥት ድህነትን ለማጥፋትና ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማምጣት (ከ2006 - 2010 የሚዘልቅ) የአምስት ዓመት የልማት መርሐ ግብር ለማውጣት ወስኗል። ይህም ከመንገድ ዘርፉ ልማት ፕሮግራም ጋር የሚጣ ጣም ነው። የመንገድ ዘርፉ መንግሥት በገጠር አካባቢዎች ድህንነትን ለመቀነስ ያስችላሉ ብሎ ከመረጣቸው ቁልፍ ሴክተሮች አንዱ ሲሆን፣ ለዚህ ዘርፍ የሚመደበው ገንዘብ በየጊዜው እየጨመረ ነው። በዚህ ረገድ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ጥረት ለማሳደግና ከሚሊኒየሙ የልማት ግቦች ላይ ለመድረስ የሚያስ ችል ተግባራዊ ማእቀፍ አዘጋጅቷል። ለኢትዮጵያ የበጀት ዓመት 2020 ዓ.ም. የታለመው ርእይ ከነዚህ እቅዶች ጋር አብሮ የሚሄድ ሲሆን መጠኑም እየጨመረ ይሄዳል። ይህም ማለት አሁን ያለው የመንገድ ልማት አኪያሄድ ደረጃውን የጠበቀ 75000 ኪ.ሜ. መንገድ ያስገኛል ማለት ነው። ልዩነቱ ዝቅተኛ ደረጃ ባላቸው መንገዶች የሚታገዝ ሲሆን፣ የእነዚህ መንገዶች ዕቅድም እስከ 2010 ድረስ እንኳን በጣም ከፍተኛ ነው።

ድህነትን ለማጥፋት የታቀደው የፈጣንና ዘላቂ ልማት ስትራቴጂ (PASDE) ለመንገድ 43.2 ቢሊዮን ብር (4.9 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር) ለማውጣት የታቀደ ሲሆን፣ በመንግሥትም ጸድቋል። ከአጠቃላዩ ወጪ ለፌዴራል መንገዶች 31.5 ቢሊዮን ብር (3.6 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር)፤ ለክልል፣ ለማኅበረሰብና ለከተማ መንገዶች ደግሞ 11.7 ቢሊዮን ብር (1.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር) ሊወጣ ይችላል ተብሎ

ይገመታል። እስከ 2015 የታቀደው ወጪ 52.0 ቢሊዮን ብር (5.9 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር) ይደርሳል ተብሎ ይገመታል።


የሚከተሉት ከ5 ዓመት በኋላ (ድህነትን ለማጥፋት ፈጣንና የዘላቂ ልማት ስትራቴጂ)፣ ከ10 ዓመት በኋላ (የሚልኒየሙ የልማት ግቦች) እና ከ23 ዓመት በኋላ (የ2028 ዓ.ም.) ሊደረስባቸው የታቀዱ ግቦችን የሚያሳዩ ጠቋሚዎች ናቸው (ሠንጠረዥ 7ትን)።

ለ2028 በተለይ የታለመው የግንባታ ሒላማ የሚከተለወን ያካትታል፤

- በበጋም በክረምትም ከሚያገለግሉ መንገዶች ከ5 ኪሜ በላይ ርቀው የሚገኙ ሰዎች የሰፈሩባቸውን ቦታዎች መጠነ ስፋት አሁን ካለው 73% በ2028 መጨረሻ ወደ 50 ከመቶ መቀነስ።
- በበጋም በክረምትም ከሚያገለግሉ መንገዶች ያለውን አማካይ ርቀት አሁን ካለው 16 ኪ.ሜ. በ2028 መጨረሻ ወደ 7 ኪ.ሜ. መቀነስ።
- አጠቃላይ የመንገድ አውታሩን ርዝመት (የማህበረሰብ መንገዶችን ሳይጨምር) አሁን ካለው 37018 ኪ.ሜ. በ2028 መጨረሻ ወደ 80.000 ኪ.ሜ. ማሳደግ።
- አሁን በየ1000ው ኪ.ሜ. ካሬ ያለውን የ33.6 ኪ.ሜ እና በየ1000ው ሰው ያለውን የ0.51 ኪ.ሜ. የመንገድ መጠነ ርዝመት፣ በ2028 በየ1000ው ኪ.ሜ. ካሬ ወደ 73 ኪ.ሜ. እና በየ1000ው ሰው ወደ 0.62 ኪ.ሜ. ማሳደግ (የማህበረሰብ መንገዶች ሳይጨምር ነው)።
- በጥሩ ይዞታ ላይ የሚገኙ ሁሉንም አይነት መንገዶች አሁን ካለው 39% በ2028 መጨረሻ ወደ 75% ማሳደግ።

ሠንጠረዥ 7፡ የኢትዮጵያ ፊስካል ዓመት 2020 ግቦች


Policy Objective የፖሊሲ	Indicator ጠቋሚዎች	2005 (Base Year) 2005 (መነሻ ዓመት)	2010 (PASDEP) 2010 (ድህነትን ለማጥፋት	2015 (MDGs) 2015 (የሚሊኒየም	Vision 2020 (E.F.Y.) ርእይ 2020 (የኢ.ትዮጵያ
Expand overall road network አጠቃላይ የመንገዶች	Road network (km)-excluding community roads የመንገድ አውታር በኪ.ሜ. (የማኅበረሰብ መንገድን ሳይጨምር)	37,018	48,000	65,000	**80,000**
	Road network (km)-including community roads የመንገድ መረብ በኪ.ሜ. (የማኅበረሰብ መንገድን ጨምሮ)		133,000	140,000	**170,000**
Improve accessibility የአካባቢዎችንተስስር ማሻሻል	% of land area further than 5km from all-weather roads በበጋም በክረምትም ከሚያገለግሉ መንገዶች ከ5 ኪ.ሜ. በላይ የሚርቁ ቦታዎች በመቶኛ	73	65	56	**50**
	Average distance to all-weather roads (km) በበጋም በክረምትም ከሚያገለግሉ መንገዶች ያለው አማካይ ርቀት	16.0	12.0	8.7	**7.0**
	Time taken to an all weather road (hrs.) በበጋም በክረምትም እሚያገለግሉ መንገዶች ላይ ለመድረስ የሚፈጀው ጊዜ በሰዓት	5.3	4.0	2.9	**2.4**
Improve density የመንገዶችን ዴንሲቲ መጨመር	km per 1000 sq.km (excluding community roads) በ1000 ስኳር ኪ.ሜ. የሚገኝ መንገድ (የማኅበረሰብ መንገዶችን አይጨምርም)	33.6	43.7	59.1	**72.7**
	km per 1000 population (excluding community roads) ለ1000 ሰዎች ያለው የመንገድ ርዝመት (የማኅበረሰብ መንገዶችን አይጨምርም)	0.51	0.58	0.70	**0.62**
	km per 1000 sq.km (including community roads) በ1000 ስኳር ኪ.ሜ. የሚገኝ መንገድ (የማኅበረሰብ መንገዶችን ጨምሮ)		120.9	127.3	**154.5**
	km per 1000 population (including community roads) ለ1000 ሰዎች ያለው የመንገድ ርዝመት (የማኅበረሰብ መንገዶችን ጨምሮ)		1.61	1.50	**1.32**
Improve condition የመንገዶችን ይዞታ መሻሻል	Increase the rate of roads in good condition (%) በጥሩ ይዞታ ላይ የሚገኙ መንገዶችን መጨመር (በመቶኛ)	39	65	68	**75**




በዚህም በደረጃ ተለይተው የተመደቡ መንገዶች አውታር በ2028 ዓ.ም. ከሁለት እጥፍ በላይ ይጨምራል ተብሎ ይገመታል። ለምሳሌ የመንገዶች አውታሩ ዕድገት ባለፉት 54 ዓመታት (ይህም ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ምስረታ ወዲህ) ውስጥ በየዓመቱ ያሳየውን አማካይ ዕድገት ብንመለከት 686 ኪ.ሜ ያህል መንገድ (ሁሉንም ዐይነት ደረጃ ማለት ነው) ተጨምሮ መሠራቱን ማወቅ እንችላለን። በአንፂሩ ግን የ2028 ዓ.ም. ግብ ላይ ለመድረስ በየዓመቱ 1870 ኪ.ሜ. መንገድ ለመሥራት/ ለመጨመር ታቅዷል (ርእይ 2020)። የማኅበረሰብ መንገዶች ተለይተው በተፈረጁ የመንገዶች አውታር ዝርዝር ውስጥ ባለመጨመራቸው በዚህ ትንተና ውስጥ አልተካተቱም።

የተተነበየው የትስስር መጠን የተገመ ተው የGISን ሥሌት በመጠቀም ነው። ከዚህ በታች የሚታየው ካርታ በኢትዮጵያ የበ2020 የበጀት ዓመት ሊኖር የሚችለውን የመንገዶች ቅርበት መጠንን ያሳያል፤ ይህም ማለት፣ መንገዶቹ አሁን ያሉትን ከተሞች እርስ በርሳቸው የሚገናኙ ይሆናሉ ብሎ በማሰብ ነው። ይህ ግምት አሁን ካለው የከተሞች መቀራረብ መጠን ከፍተኛ መሻሻል ይኖራል የሚል ነው (50% የሚሆኑት ከተሞች ከመንገድ በ5 ኪ.ሜ. ርቀት ውስጥ የሚገኙ ናቸው)። አሁን ያለው ግን የሀገሪቱ 60፣ 70፣ 77፣ 82 እና 97 ከመቶ ያህሉ ቦታዎች ከመንገድ በ10፣ 20፣ 30፣ 40፣ 50 እና 60 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸው የሚገኙ ናቸው ተብሎ ይገመታል።

ከዚህም በላይ ግን፣ ኢትዮጵያ የሚኖሯት መንገዶች ጥራት በማንኛውም መስፈርት ቢለካ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ይሆናል። (የኢትዮጵያን ካርታዎች ይመልከቱ)


Road network in 2020
N
Roads
Ethiopia
150 75 0 150 Kilometers


Accessibility scenario in 2020
Distances in km
0 - 5
5 - 10
10 - 15
15 - 20
> 20
N
200 100 0 200 Kilometers

ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

እንደዚህ ባለ በከፍተኛ ደረጃና ስፋት ዕቅድ ሲቀየስ፣ ብዙ ጊዜ አሳሳቢ ሆኖ የሚነሣው ጥያቄ፣ በመዋቅር ችግርና በተቋማት የመተግበር አቅም ማነስ የተነሳ የመንገድ ልማት ዘርፉ ይህን ያህል ከፍተኛ መጠን ያለውን የመንግስት ሀብት በታለመው ተግባር ላይ ሊያውለው ይችላል ወይ የሚለው ነው (ይህም ሲባል፣ ለተግባሩ ማኪያሄጃ የሚያስፈልገው ገንዘብ በሙሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይገኛል ብለን በማሰብ ነው)።

ሙያ ነክ ቴክኒካዊና የሥራ አመራር ችግሮች

የመንገድ ልማት በሚከናወንበት ወቅት የባለሙያዎች መኖር ቁልፍ የልማቱ አካል ነው። የሰለጠነ የሰው ኃይል መኖር አገልግሎቶችን ለመስጠት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው (በቂ መንገድ መሥራት አገልግሎቶችን የመስጠት አንዱ አካል ነውና)። ስለዚህ ዘርፉ ከፍተኛ መጠን ያለውን ሀብት በውል ለመጠቀም ይችል ዘንድ የአቅም ግንባታ ጥረት ማድረግ አለበት።

ተቋማዊ ችግሮች

ከፍተኛ መጠን ያለውን ሀብት የተሳኩ የመንገድ ልማት ሥራዎችን ለማኪያሄድ እንዲችል ለማድረግ የሚያበቁ አስተማማኝ ስትራቴጂዎችን፣ ፓሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችን ለመቅረፅ ተጨማሪ ተቋማዊ አቅም አስፈላጊ ነው። የተሳካለትን ልማት ለማከናወን የዘርፉን አቅም ከሚወስኑት ተቋማዊ ተግባሮች ውስጥ የግንባታ ንብረቶችንና ኃላፊነቶችን ያልተማከሉ ማድረግና የተጠያቂነትን ሥርዓት የመለየት ዘዴ መቀየስ ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።

በሌላ አቅጣጫ የዘርፉን የገበያ ድባብ ወይም ሁኔታ ማሻሻል አንዱ ሊከናወን የሚገባው ጉዳይ ነው። ዓለም አቀፍ የሆነውን የግንባታ ስራ ዘርፍ ገበያ ስንመለከት፣ በቅርቡ ሳያቋርጥ እየጨመረ ባለው የነዳጅ ዋጋ ምክንያት የባህረ ሰላጤው አካባቢ ከፍተኛውን ድርሻ እየያዘ ነው። ይህም በተራው የግንባታ ስራውን ወጪ ያዋዥቀዋል። ከዚህ አንጻር ሲታይም ሥራውን የሚሠሩ ተቋራጮች እጥረትና የግንባታ ወጪ በከፍተኛ መጠን መጨመሩ ለኢትዮጵያ ዋና ችግር ሊሆንባት ይችላል።

ስለዚህ የርዕይ 2020 እቅድ በጣም አስፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይልና ተቋማዊ ችግሮችን የሚያካትት ስልትን በመጠቀም እነዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀመጡ እቅዶችን መቀየስ ይኖርበታል።

በአቶ ተመስገን አክሊሉ ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ዓቢይ ጽጌ[1]

መግቢያ

አቶ ተመስገን አክሊሉ «በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ የትራንስፖርት ክፍለ-ኢኮኖሚ ሚና» በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጽሑፍ የትራንስፖርትን፤

- ጽንፀ - ሃሳብ
- ታሪካዊ አመጣጥ
- ዓለም አቀፋዊ፣ አሕጉራዊና ሃገራዊ ሁኔታ በመዳሰስና ችግሮችን በመለየት የመፍትሔ ሃሳብና የወደፊት ርዕይ አስቀምጧል።

ጽሑፉ ሰፊና ትምህርት ሰጪ እንዲሁም ፖሊሲ በማውጣት፣ በማስፈጸምና በሌላ ደረጃ የሚመለከታቸው ሁሉ ጠቃሚ ሃሳብ ሊያገኙበት የሚችሉ መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ።

አጠቃላይ አስተያየት

በቅድሚያ አቀራረቡን በሚመለከት የሚከተሉትን ሃሳቦች ማቅረብ እፈልጋለሁ።

ምዕራፍ 2፦ ላይ «የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገትና የአንድ ሀገር ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ፅንሰ ሀሳብ» የሚለው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትንም የሚመለከት ርዕስ ሆኖ ሳለ በንዑስ ምዕራፎቹ የተጠቀሱት የትራንስፖርት ምንነትና የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎቹ ስለሆኑ ለዚህ የሚስማማ ርዕስ ቢመረጥ ይሻላል።

ምዕራፍ 3፦ «የታዳጊ አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገትና የትራንስፖርት ሴክተር ልምድ» በሚል የቀረበው አንድ ገጽ ከሩብ ጽሑፍ ባብዛኛው የትራንስፖርትን ጠቃሚነት (ምዕራፍ 2 የቀረበውን ዓይነት) ለማሳመን የቀረበ እንጂ ርዕሱ እንደሚያመለክተው የታዳጊ አገሮችን የኢኮኖሚ ዕድገትና የትራንስፖርት ሁኔታ

[1] አቶ ዓቢይ ጽጌ BSc. ዲግሪያቸውን በኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ በጊዜው ከኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የወሰዱ ሲሆን MSc. ዲግሪያቸውን ደግሞ በቴክኖሎጂ ኢኮኖሚክስ ከእንግሊዝ ስተርሊንግ ዩኒቨርሲቲ ወስደዋል፡፡ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን በኢንጅነርነትና በአሠልጣኝነት ያገለገሉ ሲሆን፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ አገልግለዋል፡፡ ለመጥቀስ ያህል የትራንስፖርትና ኮሙዩኒኬሽን ዲፓርትመንት ኃላፊ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኢኮኖሚ አማካሪነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

የሚገልፅ ባለመሆኑ ይህንን በሚያንፀባርቅ መልኩ ቢፂፍ ወይም ራሱን ችሎ ለአንድ ምዕራፍ በሚመጥን መልኩ ሰፋ ብሎ ቢቀርብ የሚሻል ይመስለኛል።

ምዕራፍ 4፡- «የኢትዮጵያ ዘመናዊ የትራንስፖርት ሴክተር ልምድ» በሚል ርዕስ ሥር «ከሚኒልክ ዘመነ መንግሥት እስከ ደርግ ዘመን መጨረሻ» ቀጥሎ ደግሞ «የደርግ ዘመን ታሪክ» የሚለው (የጽሑፍ ግድፈት ይመስለኛል) በአንድ ርዕስ ሥር ቢጠቃለል። የደርግ ዘመን ታሪክ በሚል በተጠቀሱት ዓመታት የተደረጉ የፖሊሲ ለውጦችና የተከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎች ቢጠቀሱ ሚዛናዊ ይሆናል።

«የትራንስፖርት ዕድገት ከ1984-1997 ዓ.ም» በሚል ርዕስ የቀረበው ደግሞ ዕድገት ብቻ ሳይሆን ወደታች መሄድንም፣ ችግርንም የሚያመላክት ስለሆነ «የትራንስፖርት ክፍለ-ኢኮኖሚ፡- ከ1984-1997» በሚል ርዕስ ቢቀርብ፣ ይዘቱም በያንዳንዱ የትራንስፖርት ዓይነት በፖሊሲ፣ በአደረጃጀት በአገልግ ሎት አሰጣጥ ከአሃዛዊ ማስረጃ ጋር በ13 ዓመታት የተደረገውን የመጠንና የጥራት ለውጥ በሚያሳይ መልኩ ቢገለፅ ለአንባቢ የተሻለ ግንዛቤ ይሰጣል የሚል እምነት አለኝ። አሁን በቀረበው መልኩ የትራንስፖርትን የ13 ዓመት ሰፊ የሥራ እንቅስቃሴና ሁኔታ የሚዳስስ ሳይሆን በተወሰኑና ችግር በሚታይ ባቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ ያነጣጠረ ነው።

በመሆኑም ምዕራፍ 5 ውስጥ የተመለከቱት ሠንጠረዦች እስከ 1997 የነበረውን የትራንስፖርት ሁኔታ የሚያሳዩ አሃዞች ስለሆኑ ከነትንታኔዎ ቻቸው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ምዕራፍ 4 «የትራንስፖርት ክፍለ-ኢኮኖሚ፡- ከ1984 - 1997» ውስጥ መካተት እንዳለባቸው ይታየኛል።

ምዕራፍ 6፡- በዚህ ምዕራፍ የትራንሰፖርት ክፍለ ኢኮኖሚን ትንበያ ለማቅረብ የታሰበ ቢሆንም በውስጡ የቀረበው የትራንስፖርትን ምንነትና ጠቀሜታ አንዲሁም ያለፉት ዓመታትን ሁኔታ እንደገና የሚተነትን ስለሆነ ጽንሰ ሃሳብና ታሪካዊ ሁኔታ የሚገልጹትን ሃሰቦች ወደ ምዕራፍ 2፣ 3፣ 4 እና 5 በመውሰድ ድግግሞሽን ለማስቀረት ከማስቻሉም በተጨማሪ ሃሳቦችን ለማስተሳሰር ያስችላል።

ዝርዝር አስተያየት

ትራንስፖርትና ልማት

በጽሑፉ የትራንስፖርትን ሚና ለመግለፅ በሚከተለው ሁኔታ ተቀምጧል። «ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ሲኖር የትራንስፖርት ዕድገት በከፍተኛ ፍጥነት ይጨምራል በአንፂኑም የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ማደግ ለኢኮኖሚው ያለው አስተዋጽኦ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል። ትራንስፖርትና የሰው ልጅ ሳይነጣጣሉ ለብዙ ሺህ ዓመታት ስለመኖራቸው ብዙ የሚከራከር አይኖርም፣ ትራንስፖርት ማለት ደግሞ ለአንድ ዓላማ ሲባል ሰውና ዕቃ ከአንድ ቦታ ተነስቶ ወደ ሌላ ቦታ መንቀሳቀስ ማለት ነው።» በማለት አቶ ተመስገን አክሊሉ የዩናይትድ ስቴትስን የመንገድ ግንባታ ፕሮግራም ለኢኮኖሚ ዕድገት ያደረገውን

አስተዋጽዖም በማስረጃነት በመጥቀስ አቅርበዋል። በሌሎችም አገሮች ትራንስፖርት ከኢኮኖሚና ማሕበራዊ እንቅስቃሴ ጋር ያለውን ግንኙነት አመልክተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም አቶ ተመስገን አክሊሉ በጽሁፋቸው «ማነው የሚቀድመው ትራንስፖርት ወይስ የኢኮኖሚ ልማት (ዶሮው ወይስ እንቁላሉ?)» ብለው ጠይቀዋል?

የጽሁፉ ዋና ዓላማ ትራንስፖርት ከልማት ጋር ያለውን ግንኙነት አጉልቶ ለማውጣት ስለሆነ በዚህ ረገድ የተደረጉ ጥናቶችን በመጥቀስ ዘርዘር ያለ መግለጫ ማቅረብ ይቻላል።
ለምሳሌ ማነው የሚቀድመው፡ ትራንስፖርት ወይስ ልማት? የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት ከተፈጥሮ ሳይንስም (Natural Science) ሆነ ከሕብረተሰብ ታሪክ በመነሳት ብዙ መወያየት ይቻላል። በተፈጥሮ ሳይንስ በኩል እንቅስቃሴ (motion) በአቶሞች ውስጥም ሆነ ከዚያም ገዘፍ ባሉ አካላት ውስጥ የሰው ልጅ ከመከሰቱ በፊትም የነበረና አሁንም ያለ መሆኑን እንገነዘባለን። ከሕበረተሰብ ታሪክ አኳያ ደግሞ፣ አያሌ ዘመናት ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንመለከት ጥንታዊው ሰው የሚመገበውን መሰብሰብና መጓጓዝ አብረው የነበሩ ክስተቶች ናቸው። ትንሽ የእግር ጉዞ ትንሽ ምግብ፣ ትንሽ ምግብ ተመልሳ ተጨማሪ የጉዞ ኃይል እየወለደች፣ ከብዙ ሺህ ዓመታት በኋላ ባለ ሞተር ትራንስፖርት ተፈጠረ። ባለፉት ጥቂት ምዕተ ዓመታት ደግሞ ዘመናዊ ትራንስፖርትና ሌሎች የልማት ዘርፎች እርስ በርሳቸው እየተመጋገቡ ዛሬ የምናውቀውን የዓለም ብልፅግናና የላቀ የትራንስፖርት ሥርዓት አምጥተዋል።

ትራንስፖርት ወይም መጓጓዝ በሰዎች መካከል ርቀት በመኖሩ የተከሰተ ፍላጐት ነው። ሰዎች ሁሉ በአንድ ቦታ ተሰባስበው ስለማይኖሩ፣ የግብርና የኢንዱስትሪና የማዕድን ውጤቶች በሚመነጩበትና ተጠቃሚው በሚገኝበት መካከል ርቀት ስላለ ከአንድ መነሻ ቦታ ወደ ሌላ መድረሻ ቦታ ሰውና ዕቃ መጓጓዙ የግድ ይሆናል። በመሆኑም ሰዎች ለሥራ፣ ለትምህርትና ለመዝናናት ከጥቂት ኪሎሚትር ጀምሮ በብዙ ሺህ ኪሎሜትር የሚቆጠር ርቀት ይጓዛሉ። የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና የማዕድን ውጤቶችም ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይጓጓዛሉ።

የትራንስፖርት አገልግሎት ለኢኮኖሚና ማሕበራዊ ልማትና እንቅስቃሴ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ያለ ትራንስፖርት አገልግሎት ከራስ ፍጆታ በላይ የሚመረት ምርት ራቅ ላለ ገበያ ማቅረብ አይቻልም፣ የውጭ ንግድ አይታሰብም፣ የኢንዱስትሪ ጥሪ ዕቃ ማቅረብም ሆነ ምርቱን ለተጠቃሚ ማድረስ አይቻልም። ሰዎችም ከሚኖሩበት ቦታ ርቀው መሄድ ይሳናቸዋል። ባጠቃላይ ያለትራንስፖርት ሕይወት ዛሬ እንደምናውቀው አይኖርም።

ትራንስፖርት ከልማት ኢንቬስትመንት ውስጥ ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆን (20-30 በመቶ) ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው ሲሆን፣ በብሄራዊ ገቢ ውስጥም ትራንስፖርት 5-9 በመቶ ድርሻ አለው። ዝቅተኛው ድርሻ የታዳጊ አገሮች ነው።

የትራንስፖርት አገልግሎት በራሱ የፍጆታ ሸቀጥ ቢሆንም ባብዛኛው ጊዜን በመቆጠብ ፍጥነት በመጨመር ምርታማነትን ይጨምራል። ትራንስፖርት ለኢኮኖሚ እድገት የሚያደርገውን አሰተዋጽዖ ለማወቅ ብዙ ጥናቶች ተደርገዋል። አንዳንዶች ጥናቶች በተወሰኑ ዓመታት ለትራንስፖርት የተደረገውን ወጪ በተመሳሳይ ጊዜ የተገኘውን ሃገራዊ ምርት በማነጻጸር ትራንስፖርትና የኢኮኖሚ ዕድገት ጠንካራ ግንኙነት እንዳላቸው አሳይተዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ጥናቶች በእርግጥ በትራንስፖርት ላይ የሚደረገው ኢንቨስትመንት የኢኮኖሚ እድገት የሚያመጣ ወይም የኢኮኖሚ እድገት ራሱ የትራንስፖርት እድገት ለማምጣቱ ሙሉ በሙሉ ለማረጋገጥ እንዳልተቻለ ይገልጻሉ።

የተሻሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት ለአንድ ክፍለ ኢኮኖሚ (ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ ወዘተ...) ወይም ለአንድ መንደር ወይም ለአንድ ቤተሰብ የሚያደርገው አወንታዊ አስተዋጽዖ በብዙ ጥናቶች ተደገፈ ነው። ትራንስፖርት ወይም መጓጓዝ ሲታሰብ በአነስተኛ ወጪ፣ በአጭር ጊዜና ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ የትራንስፖርት ወይም የመጓጓዣ ዘዴ ይታሰባል። ለዚህም በየብስ ላይ የሚሸከረከር መኪናና ባቡር፣ በውሃ ላይ የሚንሳፈፍ መርከብ፣ እንዲሁም በአየር ውስጥ የሚበር አውሮፕላን የተሰኘ የትራንስፖርት መሣሪያ ከተፈጠረ ዘመናት አልፈዋል። ለመኪናው መንገድና ለባቡሩ ሐዲድ ስለሚያስፈልግ የመሠረተ ልማት ግንባታ ይካሔዳል። በአንፂሩ መርከብና አውሮፕላን በተፈጥሮ የሚገኘውን ውሃና አየር ይጠቀማሉ። ለመርከብ መጠጊያ ለአወሮፕላን ማረፊያና መንደርደሪያ መሥራት ግን ያስፈልጋል።

የትራንስፖርት መሣሪያዎችን፣ መለዋወ ጫዎችን፣ የኃይል መስጫዎችን ለሚያመርት አገር በተለይ ትራንስፖርት ከአገልግሎት መስጫነቱ በተጨማሪ የማዕድንና ኤነርጂ፣ የኢንዱስትሪ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የግብርናና የመሳሰሉት ክፍላተ ኢኮኖሚ ልማቶችም ማለት ነው። ዛሬ በዓለማችን የበለፀጉ አገሮች ከሚለዩባቸው ባሕርያት መካከል አውሮፕላን፣ ተሽከርካሪ፣ ባቡር፣ መርከብ የመሳሰሉትን የትራንስፖርት መሣሪያዎችና የእነኚህ መሣሪያዎች ማንቀሳቀሻ የኃይል ምንጭ በማምረት ለዜጐቻቸውና ለሌሎች አገሮች የሚሸጡ መሆናቸው አንዱ ነው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የትራንስ ፖርት መሣሪያዎች የሚያመርት ሀገር ከብረታ ብረትና ልዩ ልዩ ማዕድናት ማውጣት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የብረታ ብረትና የልዩ ልዩ ኬሚካል ኢንዱስትሪ ልማት ያለው ሀገር ማለት ነው።

የትራንስፖርትና የኢኮኖሚ ዕድገትን ተደጋጋፊነት ለማሳየት ከሀገር ውስጥም ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል። ቀደም ሲል እንደተገለፀው 78 ሚሊዮን ያህል ሕዝብ በ 1.1 ሚሊዮን ኪሎሜትር ካሬ ስፋት ባለበት ኢትዮጵያ ከ36000 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ መንገድ ይገኛል። ይህ የሚያሳየው አብዛኛው ሕዝብ ከመንገድ ርቆ እንደሚኖር ነው።

በ1997 መንገድ ለማግኘት የገጠሩ ሕዝብ በአማካይ 5 ሰዓት ያህል መጓዝ ነበረበት። በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ የግብርና ምርታማነት ዝቅተኛ ለመሆኑ ከሚጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ ለገበሬው የግብርና ግብዓቶች ለማድረስ የተመረተውን ምርትም ወደ ገበያ ለማውጣት በቂ ትራንስፖርት አለመኖሩ ነው።

ኢትዮጵያ በርካታ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስሕቦች እያሏት ለምን በቂ ጉብኝ እንደሌሏት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ የትራንስ ፖርት ኢንፍራስትራክቸርና አገልግሎቱ ዝቅተኛ መሆኑ ነው። በአንዳንድ የኢትዮጵያ አካባቢ ትርፍ ምርት እያለ ሌላ ቦታ ለምን ሕዝብ ድርቅ ባስከተለው ረሃብ ያልቃል ሲባል አሁንም አንዱ ምክንያት በቂ ትራንስፖርት ስለሌለ ነው።

የኢትዮጵያ የትራንስፖርት ክፍለ-ኢኮኖሚ ሁኔታ

የመንገድ ትራንስፖርት

በአቶ ተመስገን አክሊሉ ጽሁፍ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶታል። መሆንም አለበት። ምክንያቱም አቶ ተመስገን እንደጠቀሱት በሀገር ውስጥ በዘመናዊ ትራንስፖርት ከሚጓጓዘው ጭነት ውስጥ በመጠን ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው በመንገደኛ በኩል ደግሞ ከ95 በመቶ በላይ የሚንቀሳቀሰው በመንገድ ትራንስፖርት ነው።
ምንም እንኳን በአቶ ተመስገን አክሊሉ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሱት አሃዞች እስከ 1995 የነበሩ የትራንስፖርት አገልግሎት ቢሆኑም በሌሎች የመንግሥት ሰነዶች አንደተመለከቱት በ1997 መጨረሻ በሃገሪቱ የነበሩት መንገዶች ርዝመት 36000 ኪሎሜትር የደረሰ ሲሆን ከሃገሪቱ የቆዳ ስፋት ጋር ሲነፃፀር በ1000 ኪሎ ሜትር ካሬ ውስጥ 33 ኪሎሜትር መንገድ ነበር። ከህዝብ ብዛት ጋር ሲነፃፀር በዚሁ ዓመት ለአንድ ሚሊዮን ሕዝብ 490 ኪሎሜትር መንገድ ነበር። የቆየ መረጃ ነው እንጂ፤ በዓለም ባንክ የተዘጋጀ መረጃ እንደሚያሳየው እ.ኤ.አ በ1988 የኢትዮጵያ መንገድ ርዝመት ከሕዝብ ብዛት ጋር ሲነፃፀር ለአንድ ሚሊዮን ሕዝብ 84 ኪሎ ሜትር መንገድ የነበረ ሲሆን በዚያው ዓመት ኬንያ፣ ኡጋንዳና ሕንድ እንደ ቅደም ተከተላቸው 278 ኪሎ ሜትር፣ 190 እና 893 ኪሎሜትር መንገድ ነበራቸው። የቅርብ ጊዜ አሃዞች ሲታዩም ለምሳሌ፤ የኢትዮጵያና የኬንያ ሲነፃፀር የእድገቱ ፍጥነት የኬንያ እንደሚበልጥ ያሳያል። ከጥቂት ዓመታት በፊት ለአንድ ሚሊዮን ሕዝብ ኢትዮጵያ 432 ኪሎ ሜትር መንገድ ሲኖራት ኬንያ 1890 ኪሎሜትር ሕንድ ደግሞ 3072 ኪሎሜትር መንገድ ነበራቸው።

አሁን በመንግስት የታቀደው ልማት ተግባራዊ ከሆነ ደግሞ በ2002 ዓ.ም በኢትዮጵያ 54 ኪሎሜትር መንገድ በ1000 ኪሎ ሜትር ካሬ የቆዳ ስፋት ውስጥ ይኖራል። ከሕዝብ ብዛት ጋር ሲነፃፀር ደግሞ በ2002 ዓ.ም ለአንድ ሚሊዮን ሕዝብ 720 ኪሎ ሜትር መንገድ ይኖራል ማለት ነው።

ይህ አሃዝ ከአገራችን የቆየ አዝጋሚ የልማት ሒደት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ቢመስልም መጠኑ ከ20 ዓመት በፊት ሕንድ ከነበራት (893 ኪሎሜትር መንገድ ለአንድ ሚሊዮን ሕዝብ) በታች መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

የምድር ባቡር ትራንስፖርት

አቶ ተመስገን ካቀረቡት መረጃ እንደ ሚታየው የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ድርጅት የሚሰጠው አገልግሎት በ1990 እና በ1995 መካከል ብቻ በዓመት ያጓጓዘው የመንገደኛ ብዛት ከ714 ሺህ ወደ 288 ሺህ ዝቅ ብሏል። በዚሁ ጊዜ ያጓጓዘውን ጭነት በሚመለከት ከ202 ሺህ ቶን ወደ 162 ሺህ ቶን ዝቅ ብሏል።

በእርግጥም እነዚህ አሃዞች ድርጅቱ ችግር ያለበት መሆኑን ያመለክታሉ። የችግሩን አይነትና መንስዔ ትንሽ ዘርዘር አድርጐ ማሳየት ለአንባቢ የተሻለ ስዕል ይሰጣል ብዬ እገምታለሁ። ይህ ድርጅት በመቶ ዓመት ዕድሜው ውስጥ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚችል የማሻሻያ ሥራ ያልተሠራለት ድርጅት ነው። ከችግሮቹ መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

- የመስመሩ ዲዛይን ጊዜ በአለፈበት ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ መሆኑ፣
- ሐዲዱ ያረጀና በቂ ጥገና የማይደረግለት መሆኑ
- የመንገደኛም ሆነ የጭነት ባቡሮች ያረጁ መሆናቸው
- በየጊዜው ጠንካራ ማኔጅሜንት ያለማግኘቱ
- መስመሩ ለሴኩሪት ችግር የተጋለጠ መሆኑ
- ማሻሻያዎችን ለማድረግ የሚያስ ፈልገው ገንዘብ አለመገኘቱ

እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ አገልግሎቱን ለማሻሻል ባለፉት ሃያ ዓመታት ብቻ ከውጭ ድጋፍ የማፈላለግና የማኔጅ መንት ለውጥ ለማድረግ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ከረዥም ጊዜ ጥናት በኋላ በቅርቡ የሚያስፈልገውን የማሻሻያ ሥራ በመሥራት አገልግሎትን አስተማማኝ ለማድረግ የድርጅቱን ማኔጅመንት ለውጭ ኩባንያ በኮንትራት ለ25 ዓመታት ለመስጠት ስምምነት ተፈርሟል። ጨረታውን አሸንፎ ስምምነቱን የፈረመው የደቡብ አፍሪካ ኩባንያ በቅድሚያ አዳዲስ ባቡሮችን በመግዛትና በሐዲዱ ላይ ማሻሻያዎችን በማድረግ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በዓመት የሚጓጓዘውን ጭነት ወደ 1.5 ሚሊዮን ቶን ከፍ ለማድረግ ቃል ገብቷል። ይህ ቃል እውን ከሆነ ለባቡር ድርጅቱ ከፍተኛ ዕድገት ነው። ቀደም ሲል ከተጠቀሰው በ1995 ከተጓጓዘው 162 ሺህ ጭነት ጋር ሲነፃፀር 926 በመቶ ያህል መሻሻል ይሆናል።

የውሃ ትራንስፖርት

ሃገሪቱ ለዓለም አቀፍ ንግዷ የውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት የምትሰጥበት በጐረቤት አገር ወደቦች፣ በራሷ 9 መርከቦችና ከ 4 - 9 የሚደርሱ የኪራይ መርከቦች የምትጠቀም መሆኑና በሀገር ውስጥ ደግሞ በጣና እና በአርባ ምንጭ ሀይቆች እንዲሁም በባሮ ወንዝ ላይ መጠነኛ አገልግሎት የሚሰጡ አነስተኛ ጀልባዎች መኖራቸው በአቶ አክሊሉ ጽሁፍ ተጠቅሷል።

በእርግጥም የዓለም አቀፍ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት በሚመለከት የመንግሥት ድርጅት በሆነው የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት የሚሰጠው አገልግሎት ከሃገሪቱ የውጭ ንግድ አንፃር ሲታይ የማይናቅ መሆኑን ማየት ይቻላል። በንግድ መርከብ ወደ አገር ውስጥ የገባው ጭነት በ1990 ከነበረው 226297 ቶን በ 1995 ወደ 665549 ቶን ከፍ ብሏል።

በአቶ ተመስገን አክሊሉ ጽሑፍ ባይጠቀሱም ስለ ኢትዮጵያ ንግድ መርከብ እና ስለሃገሪቱ የውሃ ትራንስፖርት የሚከተሉትን ተጨማሪ ነጥቦች ማንሳት ያስፈልጋል።

- በ1995 ኢትዮጵያ የንግድ መርከብ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልከው ጭነት ውስጥ እጅግ ዝቅተኛ የሆነ (0.63 በመቶ) ድርሻ የነበረው ሲሆን ወደ አገር ውስጥ ከሚገባው ጭነት ደግሞ 13 በመቶ ድርሻ ነበረው።
- ለአገር ውስጥ አገልግሎት ሰጪዎች መንግሥት በሚሰጠው ቅድሚያ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የሚጫኑ ጭነቶች ለኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት ቅድሚያ እንዲሰጡ የሚያደርግ መመሪያ በመኖሩ ደርጅቱ በተወሰነ ደረጃ ከውድድር ከለላ አለው ማለት ነው።

አየር ትራንስፖርት

በአቶ ተመስገን አክሊሉ ጽሑፍ እንደተገለፀው በአየር ትራንስፖርት ዘርፍ በመሠረተ ልማት ግንባታና ዘመናዊ አውሮፕላኖችን ገዝቶ አገልግ ሎት በመስጠት ረገድ በሃገሪቱ ጐልተው የሚታዩ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል።

በኤርፖርት ግንባታ በኩል ከጥቂት ዓመታት በፊት የተጠናቀቀው የአዲስ አበባ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳና የመንገደኞች ማስተናገጃ ተርሚናል ጥናቱ፣ ዲዛይኑ፣ ገንዘብ ማፈላለጊያው መጨረሻም የግንባታ ሥራው ከ20 ዓመታት በላይ ፈጅቷል፣ ከፍተኛ ወጪም ጠይቋል። በመሆኑም ከአገር ውስጥ አቅም በተጨማሪ ከፍተኛ የውጭ ብድርና ዕርዳታ ታክሎበታል። ይህ ፕሮጀክት በቅርብ ዓመታት ከተጠናቀቁት ከፍተኛ የኢንቬስትመንት ወጪ ከጠየቁት የልማት ሥራዎች መካከል ነው።
በኢትዮጵያ አየር መንገድ በኩል የሚሰጠው የዓለም አቀፍ ትራንስፖርት አገልግሎት በጥሩ ምሳሌነት ከሚጠቀሱት መካከል ነው።

የአገልግሎቱን መጠን በሚመለከት በ1990 ከደረሰበት 607 ሺህ የዓለም አቀፍ የመንገደኛ ብዛት በ1995 ወደ 846 ሺህ መንገደኛ ወይም በ39 በመቶ ከፍ ብሏል። ይህ ዕድገት ከፍተኛ ውድድር ባለበት ሁኔታ የተገኘ በመሆኑ የሚያኮራ ነው። በአንፂሩ በአገር ውስጥ መንገደኛና ጭነት በማጓጓዝ የሚያሰጠው አገልግሎት የማይናቅ ቢሆንም ዕድገቱ ጐልቶ የሚታይ አይደለም።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በጽሑፉ እንደተመለከተው በእርግጥም ጥሩ አገልግሎት በመስጠት በሀገር ውስጥ ተመልካቾች ብቻ ሳይሆን በውጭ አገር ዜጐችና ድርጅቶችም ተመስክሮለታል።
ይሁንና አየር መንገዱ በዓለም አቀፍ ውድድር ውስጥ ስለሚንቀሳቀስ መንግሥት ከሌሎቹ የአገር ውስጥ ትራንስፖርት ዘርፎች በተለየ መንገድ ድጋፍ ሲሰጠው ቆይቷል። በዚህ ረገድ አየር መንገድ አውሮፕላኖችን በውጭ ብድር ሲገዛ ዋስትና በመስጠት፣ በውጭ ምንዛሪ የሚያገኘውን ገቢ ለአገልግሎቱ ማስፋፊያ እንዲጠቀምበት በመፍቀድ፣ ሠራተኞቹ (በተለይ አብራሪዎቹ) በኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሚባል የደመወዝ ደረጃ እንዲኖራቸው በመፍቀድ የሚደርገው እገዛ ሊጠቀስ ይገባል። ለመንግሥት ሠራተኞችና ኃላፊዎች የውጭ ጉዞ የቲኬት ግዥ ቅድሚያ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ

መሰጠቱም የማይናቅ ድጋፍ ነው። እነዚህ ድጋፎች እና ማበረታቻዎች ለድርጅቱ ምርታማነት ያደረጉትን አስተዋጽዖም አብሮ ማየት ያስፈልጋል።

አንድ ድርጅት አሠራሩ የሚገኝበትን ከባባዊ ሁኔታ መተንተን ወይም ዘርዘር አድርጐ ማየት የሚያስፈልግበት ምክንያት ውስጣዊ ጥንካሬውና ደካማ ጐኑን እንዲሁም ስጋት ሊያስከትሉ የሚችሉና መልካም አጋጣሚዎችን ለይቶ በማወቅ ለወደፊት እንቅስቃሴው የሚበጁ ስትራቴጂዎችን ለመቀየስ እንዲረዳ መሆኑ የሚታወቅ ነው። በሌላ በኩል የአንድ ድርጅት ውጤታማ ተሞክሮ ለሌሎች ድርጅቶችም ትምህርት ሰጪ ስለሚሆን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስኬት በሌሎች ድርጅቶችም የሚደገምበትን ሁኔታ ለማየት ያስችላል።

ትራንስፖርት በከተሞችና በገጠሪቷ ኢትዮጵያ

አቶ ተመስገን አክሊሉ ባቀረቡት ጽሑፍ የገጠሪቱ ኢትዮጵያና የከተሞች የትራንስ ፖርት ሁኔታ በአንድ ክፍል ተጠቃልሎ ቀርቧል።

እንደሚታወቀው የገጠሩ ሕዝብ የትራንስፖርት ፍላጐትና አቅርቦቱም ከከተማው በብዙ መልኩ ስለሚለያይ እያንዳንዱ ራሱን ችሎ ሰፋ ያለ ትንታኔ ያስፈልገዋል።

በኢትዮጵያ ከተማ ሲባል 2000 ህዝብና ከዚያ በላይ ሕዝብ የሰፈረባቸውን ከ800 የማያነሱ የገጠር ከተሞች የሚያካትት ቢሆንም የከተማ ትራንስፖርትን በተመለከተ ከአዲስ አበባ ሌላ ከ15 የማይበልጡ ከተሞችን ማለትም ታክሲና አውቶቡስ የመሳሰሉ ባለሞተር ትራንስፖርት መጠቀም የሚችል ሕዝብ የሰፈረባቸውን ይመለከታል። በዙዎቹ ደግሞ ከቢስክ?ሌት ጀምሮ በእንስሳት የሚሳቡ ሞተር አልባ የትራንስፖርት አገልግሎት ማስተናገድ የሚችሉ ናቸው።

የአዲስ አበባን ከተማ በተመለከተ ከሌሎች ከተሞችም በተለየ ሁኔታ ማየት ያስፈልጋል። የአዲስ አበባ ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ ከ3 ሚሊዮን በላይ መሆኑ፣ በያመቱ ከ4 በመቶ የማያንስ ዕድገት መኖሩ እንዲሁም ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ እንቅስቃሴ ያለበት መሆኑ የተለየ ያደርገዋል። በመሆኑም የተለያዩ ዘመናዊ የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ይጠይቃል።

ትንሽ ዘግየት ያለ ጥናት እንደሚያሳየው ከአዲስ አበባ ሕዝብ መካከል ከ 70 በመቶ የሚበልጠው የከተማ ውስጥ ጉዞ በእግር አማካኝነት የሚደረግ ነው። ይህን አሃዝ ወደ 40 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ወይም የዘመናዊ ትራንስፖርት ተጠቃሚውን በአምስት ዓመት ወደ 60 በመቶ ከፍ ለማድረግ ቢታሰብ ያለው የትራንስፖርት አቅርቦት በእጥፍ መጨመር ይኖርበታል ማለት ነው። በዚህ መሠረት በአምስት ዓመት ውስጥ የከተማ አውቶቢስ ቁጥር 800 የታክሲ ቁጥር ደግሞ ወደ 20,000 ከፍ ማለት ይኖርበታል።

ይህ ሁኔታ ከቀጠለ በ2020 ዓ.ም. ተጨማሪውን የሕዝብ ብዛት ለማስተናገድ የአውቶቢሱ ቁጥር ከ2500 በላይ የታክሲው ቁጥር ደግሞ ወደ ስድሳ ሺህ መድረስ ይኖርበታል።

ከዚህ እንደሚታየው 10 ተሳፋሪ የሚሸከሙ ታክሲዎችና 60 ሰው ያህል የሚይዙ አውቶቡሶች በማብዛት በከፍተኛ ፍጥነት የሚያድገውን የአዲስ አበባ ሕዝብ የትራንስፖርት ፍላጐት በአውቶቡስና በታክሲ ለማርካት መሞከር ከወጪ ቁጠባ፣ ከትራፊክ ደህንነትና ከአካባቢ ብክለት ቅነሳ አኳያ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።

በ2020 ዓ.ም. የሚኖረው የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ፍላጐት ከታክሲና ከአውቶቡስ በተጨማሪ ከአምስት ያላነሱ ከተማዋን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የሚያቋርጡ የባቡር መስመሮች ተዘርግተው አገልግሎት ሊሰጡ ይገባቸዋል የሚል እምነት አለኝ። በነገራችን ላይ በውጭ ኮንሳልታንቶች በ1970ዎቹ የተካሔደ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ 7 ያህል የባቡር መስመር ሊዘረጋባቸው የሚችሉ አቅጣጫዎች በመለየት አቅርቦ ነበር። ከዚያ ወዲህ ሩብ ምዕት ዓመታት ያለፉ ቢሆንም በልዩ ልዩ ምክንያት ሃሳቡ በተግባር አልተተረጎመም።

የገጠሩን ሕዝብ የጭነትና የመንገደኛ ትራንስፖርት ፍላጐት ለማርካት የዘመናዊ ትራንስፖርት መሠረተ ልማትና የተሽከርካሪ አቅርቦት በሚቀጥለው 14 ዓመታት የሚሠራው የልማት ሥራ አሁን በመንግሥት በታቀደው የእድገት መጠን ይቀጥላል ቢባል በ2020 ዓም 136000 ኪሎሜትር መንገድ ይኖራል። በወቅቱ ይኖራል ተብሎ ከሚገመተው 120 ሚሊዮን ያህል ሕዝብ አንፂር ሲታይ ለአንድ ሚሊዮን ሰው 1133 ኪሎ ሜትር መንገድ ይኖራል ማለት ነው። ይህም በአሁኑ ጊዜ ደህና የመንገድ ኔትዎርክ አላቸው ከሚባሉት አንዳንድ የአፍሪካ አገሮች ልንደርስ እንደምንችል ይጠቁማል። ይሁንና የገጠሩ ሕዝብ የመንገድ ፍላጎት ይሟላል ማለት ግን አይደለም።

ወደ ዘመናዊ መሸጋገሪያ የትራንስፖርት ዘዴ (Intermediate Means of Transport)

የገጠሪቱን ኢትዮጵያ የትራንስፖርት ሁኔታ ወደ ዘመናዊ ደረጃ (ማለትም በቂ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች በተሰተካከለ መሠረተ ልማት ላይ አገልግሎት የሚሰጡበት) ለማሸጋገር ብዙ አሥርተ ዓመታት እንደሚያስፈልግ ግልፅ ነው። ዘመናዊ የትራንስፖርት ሥርዓት የሰፈነበት ኢትዮጵያ እውን እስኪሆን የጥንቱን የመጓጓዣ ዘዴ ማለትም የእግር ጉዞ፣ የራስና የጀርባ ሸክም እንዲሁም የእንስሳት ጭነት በጉልበት ቆጣቢ ዘዴ በመጠቀም የሽግግር ጊዜ የትራንስፖርት ሥርዓት ጐን ለጐን ማስፋፋት ያስፈልጋል።
ብዙ ጥናቶች እንደሚያሳዩት 75 በመቶ የሚሆኑት እርሻዎች ክረምት ከበጋ ከሚያስኬድ መንገድ 5 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀው ይገኛሉ። ይህ ብቻ አይደለም በነዚህ መንገዶች ላይም የሚጓዙ የሕዝብና የጭነት ተሽከርካ ሪዎች የሚሰጡት አገልግሎት በቂ ካለመሆኑም ሌላ ለአብዛኛው ገበሬና ቤተሰቡ የአገልግሎቱ ዋጋ ከአቅሙ በላይ ነው።

ባለፉት 20 ዓመታት ብቻ የተጠኑ ጥናቶችን እንኳን በማየት የገጠሩ ሕዝብ ምርታማነቱን ለማሳደግ እንቅፋት ከሆኑበት ምክንያቶች አንዱ ጭነቱን የሚያጓጉዘው በጥንቱ የትራንስፖርት ዘዴ ሲጠቀም መቆየቱ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ለምሳሌ ያህል፣ ከ20 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ «የምግብና የሥርዓተ ምግብ ስትራቴጂ» በሚለው ሰነድ ውስጥ የገጠር ትራንስፖርትን አገልግሎት አስመልክቶ የሚከተለው መከናወን እንደሚያስፈልገው ተገልጾ ነበር።

- ለመንገድ ግንባታ ከሚደረገው ጥረት ጐን ለጐን ለእንስሳትና በእንስሳት ለሚሳቡ ጋሪዎች መተላለፊያ የሚያገለግሉ መንገዶች (Trails) በገጠሩ ኢትዮጵያ እንዲስፋፉ ማድረግ፤
- በያካባቢው የሚገኙ የዕደ ጥበባት ባለሙያዎችን ብቃት ከፍ በማድረግ የተሻሻሉ ጋሪዎችና ተዛማጅ መሣሪያዎች እንዲመረቱ ማበረታታት፤
- ለጋሪዎች ምርትና ጥገና የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችንና መለዋወጫዎችን አቅርቦት ማሻሻል።

ከዚያም በኋላ በየጊዜው በተደረጉ ጥናቶች የገጠር ትራንስፖርት አገልግሎት መሻሻል እንዳለበት ከመጠቆሙ በላይ ጥናቶችም በተለያዩ አካላት ሲካሄዱ ቀጥለው ረቂቅ ስትራቴጅዎችም ሲነደፉ ቆይተው በቅርቡ «የኢትዮጵያ የገጠር ጉዞና ትራንስፖርት ፕሮግራም» (Ethiopian Rural Travel and Transport Program) የተሰኘ መርሐግብር በለጋሾች ድጋፍ ተዘርግቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው። በዚህም መሠረት የወረዳ ትራንስፖርት ልማት ዕቅዶች ተዘጋጅተው በተወሰኑ ወረዳዎች (በ 1996 - 8 ብቻ) ወደ ተግባር ተሸጋግረዋል። ይህ ፕሮግራም በሚገባ ተግባራዊ ከተደረገ ለገጠሩ ሕዝብ የትራንስፖርት ፍላጎት ማስተናገጃ ጥሩ እርምጃ መሆኑ አያጠራጥርም።

የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ገጽታ

በጽሁፉ ውስጥ «በኢትዮጵያ ያለው የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ገጽታ ነባራዊ ሁኔታ» በሚል ርዕስ በትራንስፖርት መሠረት ልማት ግንባታና አገልግሎት መስጠት ተግባር ላይ የተሰማሩ የፌዴራልና የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና አካላት ተጠቅሰዋል።

ሰፊ ቦታ ተሰጥቷቸው የተዳሰሱት የመንግሥት ሕግ አስፈፃሚና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ሲሆኑ የግል የትራንስፖርት ድርጅቶች በሚገባ ከለመዳሰሳቸውም ሌላ አንዳንዶቹ ስለመኖራቸውም አልተገለፀም። ለምሳሌ፤ ያህል የጭነት ማመላለሻ ድርጅትም ሆነ የሕዝብ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን ይባሉ የነበሩት የመንግሥት ድርጅቶች በአዋጅ ሲፈርሱ ወደ ግል በተዛወሩት ተሽከርካሪዎች «ሴፍቲ ኔት» በተሰኘ ፕሮግራም ሠራተኞች ተደራጅተው እንዲያስተዳድሯቸው ከተቋቋሙት የትራንስፖርት ድርጅቶች በተጨማሪ በግል ባለሀብቶች የተቋቋሙት የትራንስፖርት ድርጅቶች ቢጠቀሱና ችግራቸውና አገልግሎታቸው ቢዳሰስ ለሚጠቆመው መፍትሔ ሊረዳ ይችላል።

በሌላ በኩል በክልል መስተዳድር የሚገኙ የትራንስፖርት መ/ቤቶች የስልጣን ደረጃቸው ከበፊቱ ዝቅ ያለ መሆኑና ለአገልግሎቱም የተሰጠውም ግምት አብሮ የወረደ እንደሆነ በጽሁፉ ተገልጸዋል።

በመንግሥት የሥልጣን መሰላል (Government Hierarchy) የአንድ የመንግሥት መ/ቤት (ለምሳሌ፤ ትራንስፖርትን እንዲከታተል ሃላፊነት የተሰጠው መ/ቤት) በሚኒስቴር ደረጃ ወይም በባለሥልጣን ወይም

በቢሮ ደረጃ ሲቋቋም መንግሥት ለመ/ቤቱ የሰጠው ግምት በዚያው መጠን ከፍና ዝቅ ያለ ሊሆን ይችላል። መ/ቤቱ በሚኒስቴር ደረጃም ተቋቋመ ወይም በቢሮ ደረጃ በፖሊሲ ደረጃም ሆነ በአስፈፃሚዎች ደረጃ ቁርጠኝነቱ ካለ በየትኛውም ደረጃ ቢዋቀር የሚፈለገውን ውጤት ማግኘት ይቻላል። የዓለም ባንክ ከጥቂት ዓመታት በፊት ባወጣው ጥናታዊ ጽሑፍ የጋና እና የቡርኪና ፋሶ የመንገድ ሴክተር ሁኔታ ተነፃፅሮ ቀርቦ ነበር። በወቅቱ ጋና የመንገዶችና የአውራ ጐዳናዎች ሚኒስቴር ነበራት። ቡርኪና ፋሶ በአንፃሩ የመንገድ ጉዳይን የሚከታተለው የመሠረተ ልማት፣ የቤቶችና የከተማ ልማት ሚኒስቴር የተሰኘ ብዙ ኃላፊነቶችን ያካተተ መ/ቤት ነበር። በሁለቱም አገሮች መንግሥታቱ ለመንገድ ግንባታና ጥገና የሰጡት ግምትና ያሳዩት ቁርጠኝነት ብዙም የተለያየ ስላልነበረ ሁለቱም አገሮች ተመሳሳይ ውጤት አስመዝግበዋል።

የመንገድ ፈንድን (Road Fund) አስመልክቶ የተደረገው ንፅፅርም በአንድ በኩል ጋና በነዳጅ ላይ የተጣለ ከፍተኛ ቀረጥና ከሌላም ምንጭ የተገኘ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ የመንገድ ፈንድ ሲኖራት ቡርኪና ፋሶ በአንፃሩ ለመንገድ ብቻ የተቋቋመ ፈንድ አልነበራትም።

ይሁንና ንፅፅሩ በተካሔደባቸው አመታት ቡርኪና ፋሶ ውጤታማ የሆነ የመንገድ ሥራና ጥገና ፕሮግራም ሲኖራት በአንፃሩ ጋና ብዙዎች መንገዶቿ በአሳሳቢ ደረጃ ላይ ነበሩ።

የመፍትሔ ሃሳቦች

1. የትራንስፖርት ፖሊሲና ስትራ ቴጂን አስፈላጊነት አስመልክተው የጽሑፉ አቅራቢ የገለፁትን እኔም እስማማበታለሁ። የተጠና፣ የተመከ ረበት ፖሊሲና ስትራቴጂ ካለ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ይታወቃሉ፣ በቅድሚያ ካልታወ ቁም በዕውቀት ላይ የተመሠረተ መገመቻ ዘዴ ይበጅላቸዋል፣ አማራጭ መፍትሔዎች ይታወቃሉ፣ የተመረጠው መንገድ ውጤት ካለመጣም ወዴትና በየትኛው አቅጣጫ መሄድ እንደሚቻል ለመምረጥ አዳጋች አይሆንም። በአንፃሩ ፖሊሲና ስትራቴጂ የሌለው ተቋምም ሆነ ሀገር የድንገተኛ አደጋ መከላከል (ፀሃፊው እሳት ማጥፋት ብለውታል) ሥራ እንደሚሠራ ሊቆጠር ይችላል።
2. የትራፊክ ደህንነት ችግሮችን አቀራረፍ በሚመለከት የጽሑፉ አቅራቢ የትራፊክ ደንብ አስከባሪዎችንና አሽከርካሪዎችን በሚመለከት ሰፊ የግንዛቤ ጉድለትና ቸልተኝነት እንደሚታይ የገለፁት በእጅጉ ሊያሳስበን ይገባል። ሁላችሁም እንደምታውቁት በደብረ- ዘይት መንገድ ብቻ የሚደርሰው የመኪና አደጋ ከመብዛቱም ሌላ አሰቃቂም ነው። የግንዛቤው ጉድለት በቂ የትምህርትና የሥልጠና ሥራ በመሥራት የሚቀረፍ ሲሆን የቸልተኝነቱ ጉዳይ ደግሞ ከማስተማር ባሻገር አግባብ ያለው የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ዘርግቶ ጥብቅ የሕግ ማስከበርና የዳኝነት ሥራ መሥራት ይጠይቃል።
3. የባቡር ትራንስፖርት ካለው ከፍተኛ የመጫን አቅምና በሌሎች ምክንያቶች ሊስፋፋ እንደሚገባው ፀሐፊው የጠቀሱት አግባብ ቢሆንም ለባቡር ሐዲድ መዘርጊያ የሚያስፈ ልገውን ከፍተኛ ወጪ ግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ለማገናዘብ ያህል በ1970ዎቹ መጨረሻ በውጭ ኩባንያዎች የተጠና ጥናት ከአዲስ አበባ አሰብ የባቡር መስመር ለመዘርጋት 1.2 ቢሊዩን የአሜሪካ

ዶላር እንደሚያስፈልግ ጠቁሟል። ባለፉት 20 ዓመታት የታየውን የዋጋ ንረት ግምት ውስጥ በማስገባት ቢሰላ የሐዲዱ ግንባታ ዛሬ ከ3 ቢሊዩን የአሜሪካ ዶላር (ወይም ከ26 ቢሊዮን ብር) በላይ እንደሚሆን መገመት ይቻላል።

የኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ (ለምሳሌ የ1994) የካፒታል ወጪ እንደሚያሳየው ለሁሉም የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፎች በድምሩ 4.8 ቢሊዮን ብር የካፒታል ወጪ ተደርጓል። ከዚህም ምንያህል የኢንቬስትሜንት ፋይናንስ አቅም ውሱንነት መኖሩን መገመት ይቻላል። ከዚህ ውስጥ በፌዴራልና በክልል መንግሥታት ለሚሠሩ መንገዶች (አዲስ ግንባታ፣ ማሻሻያና ጥገናን ጨምሮ) 1.7 ቢሊዩን ብር ወጪ ተደርጓል። ለኤርፖርት ሥራና ተዛማጅ መሣሪያዎች ግዥ ደግሞ 400 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ወጪ ተደርጓል። ከዚህ እንደሚታየው የመንገድ ሥራ ብቻውን ከመንግ ስት ጠቅላላ የልማት ወጪ ከ 35 በመቶ በላይ ድርሻ እንደሚወሰድ ግልፅ ነው። ይሁንና ከፍተኛ ጭነት የሚያመነጩ የልማት ቦታዎችን የሚያገናኙ የባቡር መስመሮች መዘርጋት አንዳለባቸው የሚያጠ ያይቅ አይሆንም።

4. ያረጁ ተሽከርካሪዎችን ወደ አገር ውስጥ እንደገቡ የሚያበረታታውን አሠራር በማሰቀረት ረገድ ፀሐፊው ያነሱት ጉዳይ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ያረጁ ተሽከርካሪዎች አካባቢን ከመበከል በተጨማሪ፣ ነዳጅ በማባከንና ከፍተኛ የጥገና ወጪ በመጠየቅ የታወቁ ናቸው። በጽሑፉ «ያረጁ ተሽከርካሪዎች ያለገደብ የሚገቡበት ሁኔታ መቆም አለበት» በሚል የጉዳዩ አሳሳቢነት ተጠቅሷል። የነኚህ ተሽከርካሪዎች ወደ አገር ውስጥ መግባት የሚገታበት ሁኔታ ደግሞ አብሮ ቢቀርብ ጽሑፉን የተሟላ ሊያደርገው እንደሚችል እገምታለሁ። ለማንም ተመልካች ወዲያው የሚታሰበው የመግቻ ዘዴ ከተወሰነ ዕድሜ በላይ ያላቸው ተሽከርካሪዎች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ በሕግ መደንገግ ነው። ሌላው ደግሞ በአዲስና በአገለገሉ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚጣለውን ቀረጥና ታክስ በሚገባ መርምሮ ወጪ ቆጣቢና አካባቢ የማይበክሉ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች እንዲገቡ የሚበረታቱበትን መንገድ መፈለግ ይኖርብናል።

5. ስለወደብ አልባነትና ስለመፍትሔው አቶ ተመስገን «ከጐረቤት አገሮች ጋር የሚደረገው ስምምነት ስትራተጂያዊና የሀገራችንን ጥቅም ለዘለቄታው እንዳይጐዳ ጥንቃቄ መደረግ አለበት» በሚል ያቀረቡት <u>ጥንቃቄ የተሞላበት አስተያየት ነው</u> ለማለት እደፍራለሁ። ወደብ አልባ አገር ወደብ ካለው አገር ጋር ስምምነት ሲያደርግ ጥቅሙን ለማስከበር ቢሞክርም ይህ ብቻ ግን ወሳኝ አይደለም። ዋናው ቁም ነገር እንደማንኛውም ንግድ የአንድ ብቸኛ አቅራቢ ደንበኛ አለመሆን ነው። የአንድ አገር ብቻ ወደብ ከመጠቀም የጐረቤት አገሮችን ወደቦች ሁሉ እያማረጡ (እያወዳደሩ) መጠቀም ነው የተሻለ ስትራተጅ የሚሆነው።

6. ፀሐፊው የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ገጽታ ትንበያ በሚለው ርዕስ ሥር በመጀመሪያው አረፍተነገር ውስጥ «. . . ነገ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመተንበይ የተለየ ተፈጥሯዊ ችሎታ ካልታከለበት በእርግጠኝነት መናጋር ይቸግራል» በሚል የሰው ልጅ የትንበያ ችሎታ ውሱን መሆኑን ያስታውሱናል። በአማርኛ «ትንቢት» ብሎም «መተንበይ» የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ Prophesy እና Forecasting ለተሰኙት ቃላት በትርጉምነት የሚውል በመሆኑ ስለወደፊቱ ሁኔታ አስተያየት በሚጠየቅበት ጊዜ «ስለወደፊቱ ትንቢት ለመናገር ወይም ወደፊት የሚሆነውን በእርግጠኝነት ለመናገር

ያስቸግራል» ይላሉ። ትንቢት ተናጋሪዎች የወደፊቱን ሁኔታ በትክክል ይናገራሉ የሚለውን ከእምነት የመነጨ አስተሳሰብ ለጊዜው በመተው የሰው ልጆች በረዢሙ የህይወት ልምዳቸውና ሳይንሳዊ ምርምራቸው ያገኙትን የወደፊት ሁኔታ የመገመቻ ዘዴ (Forecasting Techniques) በመጠቀም መገመት ይሻላል።

በትራንስፖርት ዘርፍ የወደፊቱን አቅጣጫ ለመተንበይ (Forecasting)፣ ፍላጐቱ በብዛኛው ከሌሎች ክፍላተ ኢኮኖሚ የሚመነጭ (Derived Demand) እንደመሆኑ፣

- የኢኮኖሚውን አጠቃላይ ዕድገት
- የሕዝብ ቁጥር ዕድገትና አሰፋፈር
- የግብርና
- የማዕድን
- የኢንዱስትሪ
- የቱሪዝም
- የቴክኖሎጂ ለውጥ

የመሳሰሉት የትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጐትና አቅርቦት ፈጣሪና ወሳኝ ሁኔታዎች ማገናዘብ ያስፈልጋል። እነዚህንና ሌሎችን ተዛማጅ ሁኔታዎች በማገናዘብ የሚሰጥ ግምት ወይም ትንበያ ስህተት ነው ሊባል አይገባውም።

አስፈላጊው እርምጃ ከተወሰደ ወደፊት የሚኖረው የትራንስፖርት ሁኔታ

1. «በትራንስፖርት ሴክተር ፖሊሲ ዎችና ስትራቴጂዎች ወጥተው ወደ ተግባራዊ አፈፃፀም ከተገባ በብዙ መልኩ የተስተካከለች ሀገር . . . ከትራፊክ አደጋ የፀዳች ከአካባቢ ብክለት የዳነች ሀገር ማየት ይቻላል» የሚለው አጠቃላይ እውነትነት ስላለው እስማማ በታለሁ። ይሁን እንጂ በየትኞቹ የትራንስፖርት ዘርፎች በየትኛው ደረጃ ፖሊሲዎቹ በአስቸኳይ መውጣት እንዳለባቸው ቢጠቀስ ለፖሊሲ አውጭዎች ጥሩ ጥቆማ ይሆናል።
2. «አለም የሚጠቀምበትን የትራንስ ፖርት ማኔጅመንትና ፕላኒንግ ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ . . .» በሚል የሚጀምረው አንቀጽ በርዕይነት እንዲገባ ከሆነ የተፈለገው «በዘመናዊ የትራንስ ፖርት ማኔጅመንትና ፕላኒንግ በቂ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ፕላነሮች ያሉበት የትራንስፖርት ተቋም ማየት እመኛለሁ» በሚል መልክ ቢቀረጽ የተሻለ ይመስለኛል
3. «ከተሞቻችን በዘመናዊ የመሬት አጠቃቀም ፕላን በመጠቀም የከተማ ትራንስፖርት ማኔጅመንትና ፕላኒንግ ሥራ ላይ ማዋል ከቻሉ አስተማማኝ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት ሊቀርብ ይችላል። . ለትራፊክ አደጋ የመጋለጥ ስጋታቸው ይቀንሳል፣ ብሎም ይጠፋል።» ይህ ርዕይ ዋናው ነጥቡ <u>አስተማማኝ አገልግሎት</u> ሊቀርብ ይችላል የሚለው ከሆነ አሃዛዊ መግለጫ ወይም ሊለካ የሚችል መመዘኛ ሊኖረው ይገባል። የትራፊክ ደህንነትን የሚመለከት ከሆነ አሁን ካለበት 195 የሞት አደጋ ከ10,000 ተሽከርካሪ ውስጥ ወደ 60 የሞት አደጋ (ማለትም አሁን ኬንያ በደረሰችበት) ዝቅ ይላል ቢባል ተጨባጭ መሻሻል ያሳያል።

4. በተሽከርካሪ የተነሳ የሚከሰተውን የአካባቢ ብክለት በተመለከተ በቴክኖሎጂ ምርጫና አግባብ ያለው ሕግ አውጥቶ በሥራ ላይ በማዋል ይሻሻላል የተባለውም ትክክል ነው። ከዚህ አልፎ ደግሞ በነዚህ እርምጃዎች የሚቀንሰው የብክለት መጠን ቢጠቀስ የተሟላ ይሆናል። በሃገሪቱ ከልዩ ልዩ የስራ እንቅስቃሴዎች በመመንጨት ወደ አየር የሚገባው የካርቦን ዳይ ኦክሳይድ መጠን እ.ኤ.አ በ1980 1.8 ሚሊዮን ቶን የነበረ ሲሆን በ1996 ወደ 3.4 ሚሊዮን ቶን ከፍ ብሎ ነበር። የሃገሪቱ የኢነርጅ አጠቃቀም ዝቅተኛ በመሆኑ ይህ አሃዝ ይህን ያህል የሚያሳስብ ባይሆንም የነላ ችግር ካለባቸው አገሮች በመማር ከወዲሁ መጠንቀቅ አይከፋም።
5. «የዘመናዊ ትራንስፖርት ማኔጅመንት አሠራርና ፅንሰ ሃሣብ በሕብረተሰባችንና ኦፐሬተሮች ውስጥ ማስረፅ ከተቻለ በኦፐሬሽን ወጪ ከፍተኛነት የሚደርስብን ጉዳት ይቀንስልናል» በሚል የቀረበውን በሚመለከት፡- ይህ ሃሳብ ብዙ ፍሬ ነገሮችን አጠቃልሎ የያዘ ነው።

   የዘመናዊ ትራንስፖርት ማኔጅመንት አሠራርና ፅንሰ ሃሳብ፡-
   - በትራንስፖርት አገልግሎት በቂ ውድድር መኖር አለመኖርን
   - የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የተቋ ቋመው የመንግሥት አካል በቂ ሥልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም አቅም ያለው መሆኑን አለመሆኑን
   - ተገልጋዩና የሚመለከተው ሁሉ በውሳኔ አሰጣጡ ተሳታፊ መሆን አለመሆኑ
   - አገልግሎት ለመስጠት የተቋ ቋሙ የመንግሥት ድርጅቶች ከባለ ሥልጣናት አላስፈላጊ ጣልቃገብነት ነፃ መሆን አለመ ሆናቸው

   እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ያካትታል። ለምሳሌ፤ ፀሐፊው በጽሑፋቸው እንደጠቀሱት በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ውድድርን የሚያዛባ አሠራር አለ። ይኸውም ያረጁ አውቶቡሶችንና አዳዲሶቹን በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሥምሪት የመስጠት አሠራር ነው። ይህ አሠራር አስተማማኝ ደህንነት ያላቸውንና ወጪ የሚቀንሱትን አዳዲስ አውቶቡሶች ለመጠቀም አገልግሎት አቅራቢዎችን የሚያበረታታ እንዳልሆነ ግልፅ ነው።

   ስለዚህ የውድድር አሠራር በሚያስፈልግበት ቦታ ውድድርን የሚያበረታታ ፖሊሲ በማውጣት፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ተጠቃሚዎች ለአገልግሎቱ ተመጣጣኝ ክፍያ ለመክፈል የሚያስችላቸው የድጐማ አሠራር እንዲዘረጋ በማድረግ፣ አካባቢ በመንከባከብ፣ በገጠሩ የተመጣጠነ መሠረተ ልማትና አገልግሎት እንዲኖር በማድረግ ረገድ የመንግሥት ፖሊሲ አውጭዎች አስፈፃሚዎች፣ ሕግ አስከባሪዎችና የዳኝነት አካላት ሃላፊነት እንዳለባቸው በግልፅ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

6. ለክልሎች የተመጣጠነ መሠረተ ልማትና አገልግሎት ስለማስፈለጉ፣ ለሞተር አልባና ለገጠር ትራንስፖርት ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ እኔም ከፀሐፊው ጋር እስማማለሁ። እዚህ ላይ ሊነሱ የሚችሉ የክልሎች ድርሻ እንዴት ይመጣጠን?፣ ለሞተር አልባና ለገጠር ትራንስፖርት ትኩረት መስጠት እንዴት ይገለፃል? የሚሉና የመሳሰሉት ናቸው። በዚህ ዙሪያ ለሚነሱት ጥያቄዎች ፍትሃዊ ምላሽ ለማስገኘት የሚረዳው የሚመለከታቸው ሁሉ ያሉበት የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት ሲኖር

ነው። በሃገር፣ በክልል እና በሌሎችም የተደራጁ የህብረተሰብ ደረጃዎች ውይይት እየተደረገ በሚደረስበት ውሳኔ መሠረት ተግባ ራዊ የሚደረግ ሥልት ውጤታማ የመሆኑ እድል ሰፊ ነው።

7. ምንም እንኳን ኢንዱስትሪን የሚመለከት ቢሆንም የተሽከርካሪ (የትራንስፖርት መሣሪያ) ምርትን በሚመለከት አዚህ ላይ አንድ ነገር ማንሳት ያስፈልጋል። በአገራችን የትራንስፖርት መሣሪያ ለማምረት የተደረጉ ጥረቶች ሲጠቀሱ አምቼ የተሰኘው የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ድርጅትና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥር በተደራጀ የምርት ክፍል የተገጣጠሙ «እሸት» የሚል ስያሜ የነበራቸው የመድሃኒት መርጫ አነስተኛ አውሮፕላኖች ሊታወሱ ይችላሉ። በዚህ ረገድ ከተደረጉ ጥረቶች መካከል በአምቼ የሚገጣጠሙ ተሽከርካሪዎች አብዛኛው አካላቸው በሌላ አገር ተፈብርኮ የሚመጣ በመሆኑ የሀገር ውስጥ ተጨማሪ እሴት (Value added) ዝትተኛ (ከ 20 በመቶ በታች) መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ከተሽከርካሪው እሴት ውስጥ ቢያንስ 60 በመቶ የሀገር ውስጥ ምርት እንዲሆን ስትራቴጂ ተቀይሶ ነበር። ይህ እንግዲህ በ1970ዎቹ የነበረ ዕቅድ ነው። ዛሬ ከሩብ ምዕት ዓመታት በኋላ በሀገር ውስጥ በሚገጣጠሙ ተሽከርካሪ ዎች ውስጥ የሀገር ውስጥ የእሴት ድርሻ ምን እንደሆነ መረጃዎችን ሰብስቦ ማየት ያስፈልጋል። ለማጠቃለል ያህል በሚቀጥሉት 14 ዓመታት ተሽከርካሪዎችን በማምረትም ሆነ በመገጣጠም ጎላ ያለ እንቅስቃሴ ከግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ይጠበቃል።

በነገራችን ላይ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በቅርብ ጊዜ የኢትዮ-ጅቡቲን ምድር ባቡር ድርጅት የ25 ዓመት የማኔጅሜንት ኮንትራት ጨረታ ያሸነፈው የደቡብ አፍሪካ ኩባንያ በሚቀጥሉት አምስት አመታት በሚያደ ርገው ማሻሻያ በዓመት የሚጓጓዘውን ጭነት ወደ 1.5 ሚሊዮን ቶን ለማድረስ ቃል ገብቷል ።

በውሃ ትራንስፖርት ዘርፍም የዓለም አቀፉን አገልግሎት ከማስፋፋት ጀምሮ የሃገር ውስጥ ውሃዎችን በስፋት ለትራንስፖርት አገልግሎት ማዋል ያስፈልጋል።

ስለዚህ በትራንስፖርት ክፍለ-ኢኮኖሚ ውስጥ ያሉትን ንዑስ ክፍላተ-ኢኮኖሚ (Transport Modes) የሚመለከት የ2020 ርዕይ መቅረፅ ተገቢ ይሆናል። በርዕዩ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ፍሬ ነገሮች የሚከተሉትን ሊይዙ ይችላሉ።

- የዳበረ የትራንስፖርት ኔትዎርክ
- የተመጣጠነ የትራንስፖርት ንዑሳን ክፍሎች (Balanced Transport Mode)
- አስተማማኝ ደህንነት ያለው
- ፈጣን
- ወጪ ቆጣቢ
- ለተፈጥሮ ሃብት ደህንነት ልዩ ግምት የሚሰጥ

የትራንስፖርት ሥርዓት ሰፍኖ ማየት እንመኛለን።

የአቶ ተመስገን አክሊሉን የ2020 ርዕይ በሚመለከት፡-

አቶ ተመስገን ለ2020 የሚከተለውን ርዕይ አሰቀምጠዋል።

«በሀገራችን ያለው የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ በተለይም የመንገድ ትራንስ ፖርት ዘርፍ የተሟላ መሠረተ ልማት ተዘርግቶ ደህንነቱ የተረጋገጠ ዜጐችም በአራቱም አቅጣጫ ተዘዋውረው የዘመኑ ቴክኖሎጂ ውጤት ተጠቃሚ በመሆን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብሎም ፖለቲካዊ እድገት አጋር ምሰሶ የሆነ ከሀገራችን አልፎ ለምሥራቅ አፍሪካ ጐረቤት ሀገሮች ትልቁ የትራንስፖርት መረብ ምንጭ ሆኖ መገኘት ነው»

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የአቶ ተመስገን ርዕይ ለባቡር፣ ለውሃና ለአየር ትራንስፖርት ብዙ ግምት የሚሰጥ አይመስልም። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ወደፊት በተለይ የባቡር ትራንስፖርት ከፍ ያለ ግምት ሊሰጠው ይገባል። ከፍተኛ ጭነት በሚነሳባቸውና በሚራ ገፍባቸው ቦታዎች መካከል አሁን ያለውን የኢትዮጵያና የጂቡቲ ምድር ባቡር በማሻሻልና ሌሎችንም አዳዲስ መስመሮች በመዘርጋት የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ማስፋፋት ያስፈልጋል። ሲሚንቶ፣ ጨውና ሌሎች የማዕድን ውጤቶች እንዲሁም ማዳበሪያ፣ እህልና ተመሳሳይ ግዙፍ ጭነቶች ለባቡር ትራንስፖርት ፍላጎት ዋና ምንጭ ናቸው።
በነገራችን ላይ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በቅርብ ጊዜ የኢትዮ-ጅቡቲን ምድር ባቡር ድርጅት የ25 ዓመት የማኔጅሜንት ኮንትራት ጨረታ ያሸነፈው የደቡብ አፍሪካ ኩባንያ በሚቀጥሉት አምስት አመታት በሚያደ ርገው ማሻሻያ በዓመት የሚጓጓዘውን ጭነት ወደ 1.5 ሚሊዮን ቶን ለማድረስ ቃል ገብቷል ።

በውሃ ትራንስፖርት ዘርፍም የዓለም አቀፉን አገልግሎት ከማስፋፋት ጀምሮ የሃገር ውስጥ ውሃዎችን በስፋት ለትራንስፖርት አገልግሎት ማዋል ያስፈልጋል።

ስለዚህ በትራንስፖርት ክፍለ-ኢኮኖሚ ውስጥ ያሉትን ንዑስ ክፍላተ-ኢኮኖሚ (Transport Modes) የሚመለከት የ2020 ርዕይ መቅረፅ ተገቢ ይሆናል። በርዕዩ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ፍሬ ነገሮች የሚከተሉትን ሊይዙ ይችላሉ።

- የዳበረ የትራንስፖርት ኔትዎርክ
- የተመጣጠነ የትራንስፖርት ንዑሳን ክፍሎች (Balanced Transport Mode)
- አስተማማኝ ደህንነት ያለው
- ፈጣን
- ወጪ ቆጣቢ
- ለተፈጥሮ ሃብት ደህንነት ልዩ ግምት የሚሰጥ

የትራንስፖርት ሥርዓት ሰፍኖ ማየት እንመኛለን።

በአቶ በቀለ ንጉሴ ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

አሕመድ ሳላህ[1]

በቅድሚያ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር በአገራችን የልማት ጉዞ ላይ ሁነኛ ስፍራ ባለው የመንገድ ልማት ዙሪያ እንዲህ ዓይነት የመወያያ መድረክ በማዘጋጀቱና እኔም በዚህ መድረክ በሚቀርበው ጽሑፍ ላይ ለውይይት የሚረዱ ሐሣቦችን እንዳቀርብ ዕድል በማግኘቴ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

አቶ በቀለ ንጉሴ «መንገድና ልማት በኢትዮጵያ» በሚል ጽሑፍ የመንገድ ልማት (አዳዲስ ግንባታዎች፣ የማሻሻያና የመልሶ ግንባታ ሥራዎች፣ የመንገድ ጥገና) በአገሪቱ አጠቃላይ ልማት ላይ ምን ያህል አወንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ዘርዘር ባለ መንገድ ገልፀውልናል። ጽሑፋቸው በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ላይ ያተኰረ ነው። ይህም ከ1990 በፊት የነበረው የመንገድ ሁኔታ፣ የመንገድ ልማት ኘሮግራም ከተጀመረ ከ1990 ወዲህ ያለው ሁኔታና የወደፊቱ የመንገድ ልማት ዕቅዶች በሚል ተከፋፍሎ ሊታይ ይችላል።

1. ከ1990 በፊት የነበረው የመንገድ ሁኔታ

አቶ በቀለ በጽሑፋቸው እስከዚህ ዘመን ድረስ በአገሪቱ የነበረው የመንገድ ሽፋን 26,550 ኪ.ሜ. ብቻ መሆኑን፣ ይህም ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት ጋር ሲወዳደር እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን፣ ከዚህም ውስጥ 52% የሚሆነው መንገድ በጣም የተበላሸ እንደነበር ገልፀውልናል። ከጽሑፉ እንደ ምንረዳው የገጠሩ ሕዝብ የመጓጓዣ ችግር እንዳልተፈታ፣ ይልቁንም ወደ ክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ በአማካይ ከ5 ኪ.ሜ. በላይ ርቆ የሚኘው የአገሪቱ ክፍል 79% እንደነበረ ጠቁመዋል። ወደ ክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ በአማይ 21 ኪ.ሜ. በእግር ወይም በእንሰሳት ጀርባ መጓዝ እንደሚጠይቅ ተገልጿል። ይህ የሚያመ ለክተው ብዙዎቹ የወረዳ ከተሞች እንኳን የመንገድ ትራንስፖርት ተጠቃሚ ያልነበሩ መሆናቸውን ነው። በምርት ሥራ ላይ ቢውል የተሻለ ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ያስመዘግብ የነበረው የአርሶ አደሩ የሥራ ጊዜ በመንገድና በትራንስፖርት አቅርቦት ችግር ምክንያት በጉዞ ላይ የሚያሳልፈው ጊዜ እንዲበዛ አድርጐታል። ለምሳሌ ጽሑፉ በማጣቀሻነት ባቀረበው የሦስት ወረዳዎች የዳሰሳ ጥናት በአንድ ዓመት ውስጥ አንድ ቤተሰብ ውሃ ለመቅዳትና ማገዶ ለመሰብሰብ 1058 ሰዓቶች፣ ወደ እርሻ ቦታ የሚደረግ ጉዞ 285 ሰዓቶች፣ እንዲሁም ለማህበራዊ አገልግሎቶች የሚደረግ ጉዞ 389 ሰዓቶች እንደሚወ ስድበት

[1] አቶ አህመድ ሳላህ BSc. በሲቪል ኢንጅነሪንግ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም MSc. በመንገድ ምህንድስና ከኔዘርላንድ አገር አግኝተዋል፡፡ በሥራ መስክ በመንገድ ትራንሰፖርት ዘርፍ የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው ሲሆን በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከ1979 – 1980 ዓ.ም በፕሮጀክት መሀንዲስነት፤ በፕሮጀክት ኃላፊነትና በፕላንና ፕሮግራም መምሪያ የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ኃላፊ ሆነው ሰርተዋል፡፡ በመቀጠልም በአማራ ክልል በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የኮንትራት አስተዳደር ኃላፊ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን የገጠር መንገዶች ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሰርተዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር ናቸው፡፡

ተገልጿል። እነዚህ ችግሮች ከአገሪቱ የመሬት አቀማመጥ አስቸጋሪነት ጋር ተዳምረው ከእስከአሁኑ ሥራ በተሻለ/በበለጠ ደረጃ ማቀድና መፈፀምን የሚያመለክቱና በ1990 ለተጀመረው የመንገድ ልማት የ10 ዓመት ኘሮግራም በመነሻነት መቅረባቸው ተገቢ ይመስለኛል።

2. የመንገድ ልማት ኘሮግራም ከተጀመረ ከ1990 ወዲህ ያለው ሁኔታ

ይህ ኘሮግራም ሲጠናቀቅ የመንገድ ጥግግት በ1000 ካሬ ኪሎ ሜትር (km^2) እና በ1000 ሕዝብ እንደቅደም ተከተላቸው 36 እና 0.5 እንዲደርሱ እንደሚጠበቅ ጽሑፉ ያስረዳል። ኘሮግራሙ ከተጀመረ እስከ ስምንተኛው ዓመት ድረስ ያለውን ልዩነት አቶ በቀለ ሲገልፁ የመንገድ አውታሩ ከ26,500 ኪ.ሜ. ወደ 37,018 ኪ.ሜ ማደጉን፣ የመንገድ ጥግግት በ1000 ካሬ ኪሎ ሜትር ከ24.14 ወደ 33.6 ኪ.ሜ፣ በ1000 ሕዝብ ደግሞ ከ0.46 ወደ 0.51 ኪ.ሜ. መድረሱን ያመላክታሉ። በተጨማሪም ከክረምት ከበጋ መንገድ የነበረው አማካኝ ርቀት ከ21 ኪ.ሜ ወደ 16 ኪ.ሜ ዝቅ ማለቱንና በአማካይ ከአቅራቢያው መንገድ ከ5 ኪ.ሜ በላይ ርቆ የሚገኘው የአገሪቱ ክፍል ከ79% ወደ 73% መውረዱ ተጠቁሟል። የዚህ ኘሮግራም ጠቀሜታ ጐልቶ የሚታየው አዳዲስ መንገዶችን በማስፋፋት/መገንባት ላይ ብቻ ባለመወሰኑ ነው። የፌዴራል የመንገድ ኤጀንሲው ለደረጃ የማሳደግ (gravel to a asphalt; surface treated to asphalt concrete)፣ መንገድ የማሻሻል ሥራ (improvement)፣ የመልሶ መገንባት (rehabilitation) እና የጥገና ሥራዎች (routine and periodic maintenance) ትኩረት የተሰጠ ሲሆን፣ የክልል መንገድ ኤጀንሲዎች ደግሞ አዳዲስ መንገዶችን በመሥራትና የመንገድ አውታሩን በማስፋፋት (expansion)፣ በመልሶ ግንባታና በጥገና ሥራዎች ላይ አተኩረው ቆይተዋል። በተለይ የነበሩ መንገዶችን መጠገን፣ ማሻሻልና መልሶ መገንባት ላይ መተኰሩ በመንገዶቹ ላይ የፈሰሰው ኢንቨስትመንት ዋጋ እንዲያገኝ አድርጐታል።

በመንገዶች መስፋፋትና መሻሻል ምክንያት በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ መንገዶች ከ18% ወደ 39% ከፍ ማለቱን፣ የመንገድ ትራፊክ ፍሰት በ8.1% ዕድገት ማሳየቱን፣ የጭነት ማጓጓዣ ታሪፍ እየቀነሰ መምጣቱን፣ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ወደ ገጠሩ በተሻለ መንገድ ማቅረብ መቻሉንና በዚህም ምክኒያት ለምርት መጨመር ተጨማሪ ምክኒያት መሆኑን፣ የዕለት ደራሽ እርዳታ ለማቅረብ አመቺ ሁኔታ እንደሚፈጥር በጽሑፉ ተብራርቷል።

አቶ በቀለ ይህን ጽሑፍ ለማቅረብ ብዙ እንዳነበቡና በሥራቸው አጋጣሚም ያገኛEቸውን መረጃዎች ሁሉ በተገቢው መንገድ እንደተጠቀሙበት ለመረዳት ችያለሁ። የመንገድ ልማት ኘሮግራምን በመፈፀም ረገድ ያገጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችን (challenges) አለመግለጻቸው ግን የተገኘው ውጤት ሁሉ በቀላሉ እንደተገኘ ያስቆጥረዋል። ከእነዚህ ችግሮች ዋና ዋናዎቹን እንመልከት።

G. በሥራው ላይ የተሳተፉ የአገር ውስጥ አማካሪዎችና ሥራ ተቋራጮች አቅም ዝቅተኛ ስለነበር በሥራ አፈጻጸሙ ላይ በዚያው መጠን ችግሮች ተከስተዋል። ደረጃ በደረጃ አቅማቸውን ለማሳደግ የተወሰዱ እርምጃዎች ቢኖሩም፣ አሁንም ሁለቱ ወገኖች ተጨማሪ የአቅም ግንባታ ሥራ ሊሠራልን ይገባል ባይ

ናቸው፡ እነዚህ ወገኖች በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በርካታ ሥራ እንዲሠሩ እንደሚጠበቅ በ"PASDEP" የመንገድ ዕቅድ ላይ ተመልክቷል። ስለዚህም ይህንን ችግር በጥሞና ማየትና መፍትሄ መፈለግ ተገቢ ይመስለኛል።

K. የውጪ ተቋራጮች በበቂ መጠን አለመገኘት በመንገድ ልማት ኘሮግራሙ የመጨረሻ ዓመታት በገሃድ እየታየ መጥቷል። በአገር ውስጥ ተቋራጮች የማይሸፈኑ ትላልቅ ሥራዎች በርካታ የመሆናቸውን ያህል የውጪ ተቋራጮች አገልግሎት አስፈላጊነት አያጠራጥርም። የውጪ ተቋራጮቹ በመንገድ ሥራ ላይ ለመሳተፍ/ ለመወዳደር ፍላጐታቸው የመቀነሱ ምክኒያት በውል ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ነው።

N. በዲዛይን ግምገማና በኮንትራት አስተዳደር (በተለይም በ"claim settlement") የመንገድ ኤጀንሲዎች ራሳቸውን ማጠናከር ይኖርባቸዋል። በእነዚህ ሁለት ክፍተቶች ምክኒያት የሚወጣው ተጨማሪ ወጪ ከፍተኛ መሆኑ በቂ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።

መ. በጽሑፉ እንደተመለከተው በመንገድ ልማት ኘሮግራም ስምንት ዓመታት በጠቅላላው 15.1 ቢሊዮን ብር ለማውጣት ታቅዶ 15.0 ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል። ነገር ግን በክልል መንግሥታት የተሠራው ፊዚካል ሥራ ከዕቅድ በላይ 22.8% እንደሆነ ቢመለከትም፣ የወጣው ወጪ ግን የዕቅዱን 68.6% ብቻ መሆኑ የወጪ መቆጠብን የሚያመለክት አይመስለኝም። ልዩነቱ የ1.2 ቢሊዬን ብር ነው። ለመንገድ የሚመደበው በጀት ከፍላጐቱ ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ በመሆኑ በተመደበው በጀት ሥራውን ለማጠናቀቅ ሲባል ለጥራቱ መሟላት አስፈላጊ የሆኑ አንዳንድ ሥራዎች ሊታለፉ ይችላሉ። ይህም በዕቅድ ወቅት የፌዴራልና የክልል ኤጀንሲዎች በጋራ ያለመሥራታቸው፣ በዚህም ምክኒያት የክልል መንግሥታት በመንገድ ልማት በጀት አመዳደብ ላይ ተመሳሳይ ግንዛቤ ካለመያዛቸው የመነጨ ሊሆን ይችላል። በዕቅድ ዝግጅት ወቅት እያንዳንዱ ክልል ለኘሮግራሙ መሳካት በቂ በጀት መመደብ እንዲችል መግባባት ላይ ቢደረስ ደረጃቸውን የጠበቁ መንገዶች እንዲኖረን ያግዛል። በተለይ ደግሞ የክልል መንገድ ኤጀንሲዎች የራስ ኃይላቸውን ጥገና ላይ በማሰማራት የኮንስትራክሽን ሥራውን በተቋራጮች የሚያሠሩበት ሁኔታ ማመቻቸት ለሥራው ጥራት መጠበቅ ወሳኝነት አለው።

W. በመንገድ ልማቱ ኘሮግራም ስምንት ዓመታት ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው እጅግ ጠቃሚ ሥራ ተሠርቷል። የወደፊት የልማት ሥራው ላይ ከፍተኛ ጫና የሚፈጥር የዋጋ ንረት የታየውም በዚሁ ወቅት ነው። ዋጋ ሊያንሩ የሚችሉ አገራዊና ዓለምአቀፋዊ ክስተቶች አልነበሩም አይባልም። ነገር ግን የተፈጠረው የዋጋ ንረት እመርታ ከሚዘጋጁ የምሕንድስና ግምቶች እየራቀ መምጣት የገበያውን ጤናማነት የሚያሳይ አይመስልም። ብዙ አልመን በትንሹ እንዳንቀር የችግሩን መንስኤ ማጥናት ተገቢ ይመስለኛል። ምናልባትም የተወዳዳሪዎች ማነስ የፈጠረው ችግር እንዳይሆን።

3. የወደፊቱ ዕቅድ

አቶ በቀለ ወደፊት የሚኖረውን የመንገድ ልማት ሥራ በተመለከተ ሦስት ዕቅዶችን አቅርበዋል። የመጀመሪያው የ'PASDEP' ዕቅድ ሲሆን አጠቃላይ የመንገድ አውታሩ አሁን ካለበት 37,018 ኪ.ሜ. በመነሳት 11,000 ኪ.ሜ. ያህል በመሥራት 48,000 ኪ.ሜ. ማድረስ ነው። ሁለተኛው የሚሊየነሙን የልማት ግብ (MDGs) መሠረት ያደረገና በተከታዩ አምስት ዓመት 17,000 ኪ.ሜ በመሥራት የመንገድ

አውታሩን 65,000 ኪ.ሜ. ማድረስ ነው። ሦስተኛው ደግሞ በመጨረሻዎቹ አምስት ዓመታት 10,000 ኪ.ሜ. በመሥራት የአገሪቱን የመንገድ ኔትወርክ 75,000 ኪ.ሜ. የሚያደርሰው ነው።

በየዓመቱ በአማካይ 2530 ኪ.ሜ. መንገድ በመሥራት እ.ኤ.ኤ. በ2020 ዓ.ም. 75,000 ኪ.ሜ. የሸፈነ የመንገድ አውታር ሲኖረን፤

G. በአማካይ ከመንገድ ከ5 ኪ.ሜ. በላይ ርቆ የሚገኘው የአገሪቱ ክፍል አሁን ካለበት 73% ወደ 52% ዝቅ እንደሚል፣
K. የመንገድ ጥግግቱ 68 ኪ.ሜ. በ1000 ካሬ ኪ.ሜ. እና 0.76 ኪ.ሜ. በ1000 ሕዝብ እንደሚደርስና
N. በጥሩ ሁኔታ የሚገኙ መንገዶች ከ39% ወደ 72% እንደሚያድጉ አቶ በቀለ በጽሑፋቸው አመላክተዋል።

በየወረዳው በሚገኝ ማህበረሰብ የተጀመረው የዝቅተኛ ደረጃ መንገዶች ግንባታ ተጨምሮ በጠቅላላው 139,100 ኪ.ሜ. መንገድ እንዲኖር ይጠበቃል።

እንደ ኢትዮጵያ ላለች ሰፊ አገር፣ ግን ደግሞ በመንገድ ልማት በኩል ከሰሐራ በታች ከሚገኙ አገሮች እንኳ በማንኛውም መለኪያ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለምትገኝ አገር፣ በ"PASDEP" ማጠናቀቂያ ዘመን 48,000 ኪ.ሜ.፣ እ.ኤ.አ. በ2020 ደግሞ 75,000 ኪ.ሜ. ደረጃውን የጠበቀ መንገድ እንዲኖር ማቀድና ማሰብ የሚበዛብን አይሆንም። ነገር ግን በፋይናንስ፣ በሰው ኃይል፣ በመሣሪያ፣ በግሉ ሴክተር ተሳትፎ (የአገር ውስና የውጪ) እና በመሳሰሉት አካባቢዎች ሊያጋጥም የሚችለውን ፈተና ካሁኑ ጠንቅቆ መረዳትና መፍትሔ ማፈላለግ አስቀድሞ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል።

አመሰግናለሁ!

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና ልማት በ2020[1]

ሥርገው ገላው[2]

1. መግቢያ

"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማት ድርሻ በ2020" በሚል ርእስ የማቀርበው ይህ ወረቀት ለ2020 ለተያዘው የልማት እቅድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ድርሻ ምን ሊሆን ይችላል? በሚለው ርእስ ዙሪያ አስቤበት ለውይይት የሚያግዙ የመንደርደሪያ ሃሳቦችን እንዳቀርብና በተጋባዥ እንግዶች ውይይት ዳብረው ወደ ጎብረተሰቡ እንዲደርሱ ለማድረግ እንደሆነ ይሰማኛል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለ2020 ልማት ሊኖራት ይገባል የምለውን ድርሻ ከማንሳቴ በፊት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን የተሠሩትንና እየተሠሩ ያሉትን ዋና ዋና ተግባራት በመዳሰስና መጠነኛ ትረካ በማቅረብ በ2020 የልማት እቅድ ልትጫወት ይገባታል የምለውን ሃሳብ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያው ምእት ዓመት ከተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ናት። የሐዋ 8÷26 ኢትጵያዊው ጃንደረባ ኢየሩሳሌምን ለመሳለም ሂዶ በፊልጶስ መጠመቁን ይተርክልናል። የሮም የተባለ የላቲን ቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ እንድርያስ፣ ሶቅራጥስ የተባለ ታሪክ ጸሐፊና ዮሐንስ አፈወርቅ ቅ. ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን እንደሰበኩ ጽፈዋል።

በ330 ዓ.ም አካባቢ ኢትዮጵያ ጵጵስናን መቀበሉዋን ታሪካዊ መረጃዎች አሉን። የፓትርያርክ አትናቴዎስ፣ የቄሳር ቁንስጣ የጢሮሱ ካህንና ታሪክ ጸሐፊ የሩፊኖስ ዘገባ ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍትን በራሷ ቋንቋ ተርጉማ የተቀበለች መሆኗ ከሁሉም ልዩ ያደርጋታል። በዚህም ትርጉም ሥራ በሃይማኖት ስደት ምክንያት በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከሶርያ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት 9 ቅዱሳን በመባል የሚታወቁት መነኰሳት አስተዋጽኦ ይጠቀሳል። መነኰሳቱ ከትርጉም ሥራ በተጨማሪ በአክሱም አካባቢ ገዳማትን በማስፋፋት ተግተው መሥራታቸው ይታወቃል። ጥንታዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ መነኮሳት እጅግ ዝነኛ በሆነው ትህርምቱ (ጾምና ጸሎት) ከመታወቁም በላይ ለሃይማኖታዊ ሥነ ጥበብና ኪነ ጥበብ እንዲሁም ለትምህርት

[1] ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ.ም የተካሄደ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡፡

[2] አቶ ሥርገው ገላው በቤተክህነት የሚሰጡ ትምህርቶችን የተከታተሉ ሲሆን በዝዋይ ካህናት ማሰልጠኛ ተቋም የ4 ዓመት ትምህርት ተከታትለው ተመርቀዋል። በውጪ አገርም በጀርመን በመለኮት ትምህርት የማስትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። አቶ ሥርገው ገላው በቤተክህነት ውስጥ ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመምህርነትና ተመራማሪነት በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

ያደረገው አስተዋጽኦም ከፍተኛ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዚሁ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከትርጉም ሥራ አልፋ የራሷ የሆነ ሥነ ጽሑፍ (ማኅሌትና ቅኔ) ባለቤት ለመሆን በመብቃቷ ክርስትና በኢትዮጵያ ከማበብ አልፎ ፍሬ ማፍራት የጀመረበት ጊዜ ነበር። ሆኖም በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የአረቦች መስፋፋት የኢትዮጵያን ክርስትና አደጋ ላይ ጣለው።

ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ወደ ቅድስት ሀገርና ወደ ግብፅ እንዳይሄዱ መንገድ ከመዝጋት አልፎ ከውጭው ዓለም ጋር የነበራቸውን ግንኙነት እንዲቋረጥ አደረገ። ይህንን ተከትሎ 10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዮዲት (ጉዲት) በተባለች ሴት መሪነት የተነሳው የቤተ እስራኤሎች ንቅናቄ ክርስቲያኑን የአክሱምን መንግሥት ለመገልበጥ በቃ። በዚህ ምክንያት መቀመጫው አክሱም የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ሥልጣኑን ለቆ ወደ ደቡብ እንዲያፈገፍግ ተገደደ። ወደ ደቡብ ማፈግፈጉ ግን የደቡቡ ኢትዮጵያ ክፍል ክርስትናን እንዲቀበል ምክንያት ሆኗል።

ከዮዲት በኋላ የአክሱም መንግሥት በዛጔ ሥርወ መንግሥት ተተካ። ዛጔዎች አገዎች ናቸው። እንዴት ክርስቲያን እንደሆኑ ባናውቅም ወደ ቤተ መንግሥት የገቡት ግን ክርስቲያን ሆነው ነው። በዘመነ ዛጔ ለቤተ ክርስቲያን የተሠሩን ተግባራት የሚያትቱ ብዙ መረጃዎች ባይኖሩም በላስታ አካባቢ የተሠሩት ድንቅ አብያተ ክርስቲያናት የነገሥታቱን ድካምና ጥረት አጉልተው ያሳያሉ። ቅዱስ ሀርቤ (ገብረ ማርያም) የተባለው ንጉሥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ ነፂ ሆና ራስዋን እንድትችል ለማድረግ ጥረት ቢያደርግም በግብፅ ፓትርያርክ ዘንድ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ድካሙ ፍሬ ሳያፈራ ቀርቷል።

የአረቦች መነሣት ለዛጔ መንግሥትም አልበጀውም። በአረቦች መጠናከር ምክንያት የዛጔ መንግሥት እየተዳከመ ሲሄድ የአክሱም ነገሥታት ዘር ነኝ የሚለው ይኩኖ አምላክ መንግሥቱን ወረሰ። በትውፊት እንደተላለፈልን ሸምጋዮቹ አባ ኢየሱስ ሞዐና አባ ተክለ ሃይማኖት ሲሆኑ በዚሁ ጊዜ አዲሱ ሥርወ መንግሥት ለቤተ ክህነት ሚሶ መንግሥት ለአባ ተክለ ሃይማኖት እጨጌነትና ለአባ ኢየሱስ ሞዐ ዐቃቤ ሰዓትነት ለመስጠት መስማማቱ ይተረካል።

በዚሁ ዘመን የቤተ ተክለ ሃይማኖት መሥራች የሆኑት አቡነ ተክለ ሃይማኖት 33 ያህሉ መነኮሳትን አሰልጥነው በምድረ ሸዋ በስብከተ ወንጌል አሰማርተዋል።

በዚሁ በሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት ዘመን የቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፎች በመስፋፋታቸው ዘመኑ ሁለተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን (ወርቃማው የሥነ ጽሑፍ ዘመን) በመባል ይታወቃል። በዐፄ ዐምደ ጽዮን (1297-1327) ዘመን የስንክሳር፣ ኪዳን፣ እና ግንዘት የመሳሰሉት መጻሕፍት ከአረብኛ ወደ ግዕዝ ተተርጕመዋል። ክብረ ነገሥት የተደረሰውም በዚሁ ዘመን ነው።

በዐምደ ጽዮን ዘመን ያዕቆብ የተባለ ግብፂዊው ጳጳስ በመላ ኢትዮጵያ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት ተግቶ ሰርቷል።

12 መነኰሳት ንቡራነ እድ ብሎ በመሾም በሸዋና ደቡብ ኢትዮጵያ ሲያስማራ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን ሌሎች መነኰሳት ከዋክፍት በሚል መጠሪያ ወደ ሰሜን አትዮጵያ ልኳቸዋል።

ከአባ ያዕቆብ በኋላ የመጣው ሰላማ መተርጉም (1340-80) የተሰኘው ጳጳስ ከስብከተ ወንጌል ይልቅ ለቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ትኩረት ሰጥቶ ነበር። በዚህም መሠረት ሐዲስ ኪዳንን ከአረብኛ ጋር አስተያይቶ ወደ ግዕዝ የመለሰ ሲሆን በተጨማሪ እንደ ግብረ ሕማማት፣ ገድለ አባ ከረዙን፣ ገድለ አዝቂር፣ ድርሳነ ገላውዴዎስ፣ ፊልክስዩስ፣ ገድለ ይስሐቅ፣ ገድለ ዮስጦስ፣ ገድለ ኖብ፣ ለሀ ማርያም፣ ድርሳነ ያዕቆብ ዘኢየሩሳሌም፣ ድርሳነ ያዕቆብ ዘስሩግ እና መጽሐፈ ግንዘት በአባ ሰላማ ዘመን ተተርጉመዋል።

ከዐፄ ዐምደ ጽዮን ቀጥሎ ዐበይት የሃይማኖት ሥራዎች የተከናወኑት በዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን ነው። አፄ ዘርአ ያዕቆብ በሰሜን ኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ትምህርት ቤት ስላደገ ጥልቅ የሆነ የሃይማኖት እውቀት ነበረው። ስለሆነም ወደ ስልጣን ከወጣበት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ለማምጣት ጥረት አድርጓል። ከሁሉም በላይ አምልኮ ባዕድን ለማስወገድ የጣረ ሲሆን በተጨማሪም ደቂቀ እስጢፋ የተባሉትን ቡድኖች ከተከተሉት አዲስ ትምህርት በሰላማዊ መንገድ ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት አድርጎ ጥረቱ ባለማፍራቱ የጎይል እርምጃ ወስዶ ትምህርታቸው እንዲገታ አድርጓል። ዐፄ ዘርአ ያዕቆብ የጎይል እርምጃ የወሰደው ደቂቀ እስጢፋ ላይ ብቻ ሳይሆን አምልኮ ባዕድ በሚከተሉ ጭምር ነበር። ይህም ልጆቹንም ይጨምራል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሁለት ሰንበትና የአንድ ሰንበት ባህል ክርክር በስምምነት ለመፈጸም ችሏል። ይህም የሆነው እሱ እራሱ በሰሜን አካባቢ ያደገ በመሆኑ ጳጳሳቱን በማሳመን የሁለት ሰንበት ባህልን እንዲቀበሉ በማድረግ ነው። ዐፄ ዘርአ ያዕቆብ በአንድ ጊዜ ሦስት ጳጳሳትን ለማስመጣት የቻለ ንጉሠ ነገሥት ነው። በ1433 ዓ.ም. ፍሎረንስ ላይ በተደረገው የዓለም ክርስቲያኖች ስብሰባ ላይ መልዕክተኞቹ በመገኘታቸው ስሙ በውጭው ዓለም ገኖ ነበር። ዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ራሱም በቀጥታ በሥነ ጽሑፍ ሥራ ላይ ተሰማርቶ መጽሐፈ ብርሃንንና መጽሐፈ ምዕላድን ደርሷል። በዘመኑ እንደ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ያሉ ምሁራን ተነስተው በርከት ያለ ሥነ ጽሑፎችን ለቤተ ክርስቲያን አበርክ ተዋል። በሰሎሞናውያን ዘመን እጅግ ድንቅ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት በወርቅና እንቁ ተገንብተው ነበር። ሆኖም እነዚህና ሌሎችም ብርቅና ድንቅ የሆኑና ሥፍር ቁጥር የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት በዘመነ ግራኝ ወድመው ባታል።

ዐፄ ገላውዴዮስ በግራኝ ወረራ የወደሙትን አብያተ ክርስቲያናት መልሶ ለማቋቋምና ተገደው ወደ እስልምና የገቡትን ክርስቲያኖች ወደ ክርስትና ለመመለስ ተግቶ ሠርቷል። ሆኖም የክርስቲያኑና የሙስሊሙ ግጭት ጋብ ሲል በምትኩ የኦርቶዶክስና የካቶሊክ ግጭት ተተካ። እንደ በርሙዲዝ ያሉ ራስ ወዳድ ሚስዮናውያን ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና አልፎ ተርፎም ለፖርቱጋል መንግሥት ተቆርቋሪ በመምሰል ኢትዮዮያ ለተደረገላት የጦር ድጋፍ ሉአላዊነቱዋንና እምነቱዋን እንድትከፍል በመጠየቃቸው ግጭቱ ተከሰተ። ጥያቄያቸው በገላውዴዎስ ዘንድ ተቀባይነት ባይኖረውም እንደገና በአፄ ሱስንዮስ ዘመን

አገርሽቶ በአገሪቱ ላይ ታላቅ እልቂትን አስከትሏል። በዚሁ ወቅት ሚስዮናውያን ሕዝቡን በአማርኛ ቋንቋ መስበክ ስለጀመሩ ኦርቶዶክሳ ውያንም ከነሱ በመማር የአማርኛ አንድምታ ጀመሩ። የአንድምታ ትርጉም ሁለት አላማዎች ነበሩት። አንደኛ በግዕዝ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ተንትኖ ለአማርኛ ተናጋሪው ማስረዳት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ፀረ-ሚስዮናውያን የሆነ ትምህርት ማስረጽ ነበር።

በጐንደር ዘመነ መንግስት የአንድምታ፣ የድጓና የቅኔ ትምህርት ተስፋፋ። አብያተ ክርስቲያናት ተገነቡ። ስዕሎች ተሳሉ። መጻሕፍት ባይደረሱም ተባዙ። ነገር ግን በካቶሊክ ምስዮናውያን እና በኦርቶዶክስ መምህራን መካከል የተደረ ገውን ክርክር ተከትሎ ሁለት ልደትና ሶስት ልደት በሚል ባህል ቤተ ክርስቲያን መታመስ ጀመረች። መሳፍንቱም እንደ ካህናቱ በመከፋፈል አገሪቱን በጦርነት አመሷት። በዚህ የሃይማኖት ግጭት ተወጥሮ ተይዞ የነበረው የጎንደሩ ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት ቀስ በቀስ እየደከመ ሂዶ ሥልጣኑን በመሳፍንት ለመነጠቅ በቃ።

በዘመነ መሳፍንት ዋናውን ሚና የተጫወቱት የየጁ መሳፍንት ናቸው። የየጁ መሳፍንት ሥረ መሠረታቸው እስልምና ቢሆንም ሥልጣን ሲይዙ ግን ክርስቲያን ሆነው ነው። በየጁ መሳፍንት ዘመን ለቤተ ክርስቲያን ተደረገ የሚባል የጎላ ታሪክ ባይኖርም ተቀዋሚዎቻቸው እንደጠረጠሩት በቤተ ክርስቲያን የወሰዱት ግልጽ የሆነ ፀረ ቤተ ክርስቲያን አቋም አልነበረም።

የዐፄ ቴዎድሮስ መነሣት በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ለረጅም ጊዜ ጸንቶ የቆየውን ግኑኝነት አሻከረ። በመጀመሪያ አፄ ቴዎድሮስ የሁለት ልደት ባህልን በይፋ አውጀው ከዚህ ውጭ የሆነ ሁሉ ቅጣት እንደሚያገኘው አስጠነቀቁ። በካህናት ዘንድ የበለጠ መጠላትን ያተረፈላቸው ግን የካህናት ቁጥር እንዲወሰን መደንገጋቸው ነበር። በአፄ ቴዎድሮስ ውሳኔ መሠረት ለአንድ ቤተ መቅደስ ከአምስት የበለጠ ካህናትን መመደብ አስፈላጊ አልነበረም።

ሌላው ዐፄ ቴዎድሮስን ከካህናቱ ጋር ያጋጫቸው በዘመኑ የሰሞን መሬት ይባል ከነበረው ርስት ቀንሰው የተወሰነውን ለሠራዊቱ መተዳደሪያ መደንገጋቸው ነው። ይህ ድንጋጌ ላይ ላዩን ሲታይ በአቡነ ተክለሃይማኖትና በይኩኖ አምላክ መካከል የተደረገውን ቃል ኪዳናዊ ስምምነት ያፈረሰ በመምሰሉ በካህናቱ ዘንድ እንደ ክህደት ተቆጥሯል። ይሁንና ስሙ ተረፋቸው እንጅ ካህናቱ የሰሞን መሬት ተጠቃሚዎች አልነበሩም። በመሬቱ የሚጠቀመው የቄስ ልጅ ነኝ የሚለው ባላባቱ ሲሆን ካህናቱ ግን የሚተዳደሩት እንደተራው ገበሬ እያረሱ ነበር። ከዚህ አንፃር ሲታይ የቤተ ክህነት ሲሦ መሬት የሚባለው የተጋነነ ብቻ ሣይሆን ተረት ነበር።

ዐፄ ዮሐንስ ሦስት ነገሥታትን የማንገሥ እቅድ ስለነበራቸው በአንድ ጊዜ አራት ጳጳሳትን በማስመጣት ከአፄ ዘርአ ያዕቆብ ቀጥሎ ሁለተኛው ንጉሠ ነገሥት ናቸው። የሁለት ልደትና ሶስት ልደት ባህል አሥመልክቶ ቦሩሜዳ ላይ ያደረጉት ጉባኤ በዘመናቸው ካደረጉ ዋቸው ሃይማኖታዊ እንቅስቃ ሴዎች አንዱ ነው። አፄ ዮሐንስ ለኦርቶዶክስ እምነት በተለይም ለሁለት ልደት ባህል ያላቸው ቀናኢነት

እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ተቃራኒ የሆነው የኦርቶዶክስ ባህልና በሌሎችም እምነቶች ላይ የወሰዷቸው የጎይል እርምጃዎች ተገቢ አልነበሩም።

በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ የስብከተ ወንጌል እድል አምልጧታል። የምኒሊክን ሀገር የማቅናት ፖሊሲ ተከትላ የወንጌል ተልእኮዋን መወጣት ስትችል የኢትዮጵያ ካህናት ባለትዳርና እንደማንኛውም ዜጋ በእርሻ የሚተዳደሩ በመሆኑ ይመስላል አብረው አልተንቀሳ ቀሱም። መሳፍንቱና የጦር አበጋዞቹ ናዛዥ ካህናት ቢኖራቸውም ካህናቱ የመቀደስና የማቁረብ ልምድ እንጅ የስብከተ ወንጌል ልምድ ስላልነበራቸው በተጠቀሰው ዘመን ስብከተ ወንጌል አልተስፋፋም። በተለይም በደቡብና ደቡብ ምዕራብ አትዮጵያ የወንጌል ልማት መድረስ ሲችል ከፍ ሲል በተጠቀሱትና በሌሎች ምክንያቶች ለመስፋፋት አልቻለም። በወቅቱ በጉዳዩ ታስቦበት ቢሆን ኑሮ አገር ማቅናቱ ብሔራዊ አንድነት እንዳመጣ ሁሉ ስብከተ ወንጌሉ ይህንኑ ብሔራዊ አንድነት የበለጠ ያጠናክረው ነበር።

ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ገና ራስ ተፈሪ እየተባሉ ከመላ አትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን በቤተ መንግሥ ታቸው አሰባስበው ቅዱሳት መጻሕፍትን በአንድምታና በነጠላ አስተርጉመው አሳተሙ። ምንም እንኳን ቀደም ሲል የተተረጐመ የመጽሐፍ ቅዱስ እትም ቢኖርም ይህ የዐፄ ኀይለ ሥላሴ ትርጉም በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሊቃውንትን ያሳተፈ በመሆኑ ቀደም ሲል ከነበረው የተሻለ ነበር። ይህ ትርጉም ቤተ ክርስቲያኗ ከ1,500 ዓመታት በላይ ስትገለገልበት ከኖረችው ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተደረገ አፈሴላዊ ሽግግር ነበር። ቢሆንም አብዛኞቹ ካህናትና አማንያን በደስታ አልተቀበ ሉትም ነበር። አንዳንዱ ትርጉሙ ስህተት አለው በማለት ሲሆን ሌላው ከሃይማኖታዊው ቋንቋ ወደ ዓለማዊ ቋንቋ የተደረገውን ሽግግር እንደ ክህደት በመቁጠር ነበር። ሌላው ደግሞ የውጭ ሃይማኖቶች ተጽዕኖና ኑፋቄ ይኖረዋል ብሎ በመስጋት ነበር። በዚህም ምክንያት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስን ካለመስፋፋቱም በላይ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እንደ መናፍቅ ያስቆጥር ነበር። ይሁን እንጂ ሥራው ታላቅና ንጉሡንም የሚያስመሰግን መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

ዐፄ ኀይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን የበላይነት ነፂ ማውጣታቸው ሌላው ተጠቃሽ ጉዳይ ነው። የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያውያንን ሰብኣዊ እኩልነት በመፂረር ለሁለት ሺ ዓመታት ለኢትዮጵያውያን ጽጽስና መከልከሏ ወንጌል ሳይሆን ወንጀል ነው። ስለዚህ ንጉሡ ዘመን ረድቷቸው እስከ እርሳቸው ዘመን ድረስ ያልተሳካውን ይህን ተግባር በማከናወናቸው እድለኛ ናቸው። በሌላ በኩል ግን ሽግግሩ የተካሔደው በቂ ዝግጅት ተደርጐ እንዳልሆነ ይታየኛል። በመጀመሪያ ከተመረጡት አትዮጵያውያን ጳጳሳት ውስጥ አንዳንዶቹ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባህላዊ ትምህርት ጥልቅ እውቀት ያላቸው ቢሆንም ምንም ዐይነት የውጭ ቋንቋና ዓለም አቀፋዊ እይታ የነበራቸው አልነበሩም። ይህም ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ጉዳት ይመስለኛል።

ሁለተኛው ጉዳት ጳጳሳቱ ይመረጡ የነበሩት ለንጉሡ ካላቸው ተአማኒነት አንፂር መሆኑ ነበር። ይህም ቤተ ክርስቲያኗ ከመንግሥት ነፂ እንዳትሆን ያደርጋል። አፄ ኀይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ

ክርስቲያንን ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ነፂ አወጡ እየተባሉ ቢሞካሹም ይህችው ቤተ- ክርስቲያን ምን ያህል በመንግሥት አገዛዝ ስር እንደወደቀች የምናየው ፓትሪያርኮች ሲሾሙ ከሚፈፅሙት ሕገ መንግስታዊ ቃለ መሀላ ነበር።

በዘመነ አፄ ጎይለ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያኗ ወንጌልን የማስፋፋት ታላቅ እድል አጋጥሟት አልተጠቀመችበትም። በዓለም ያሉ ጥቁሮች ሁሉ በነጮች ከመገለላቸው የተነሳ ራሣቸውን ከነጮች ባህልና ሃይማኖት የማግለል እንቅስቃሴ ነበራቸው። እንቅስቃሴውም» "ኢትዮጵያዊነት" የሚል ስያሜ ነበረው። ይህን እንቅስቃሴ ካነገቡት ውስጥ አንዳንዶቹ በየአካባቢ ያቸው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ተመኝተዋል፣ ጠይቀዋል፤ መስርተዋልም። ለምሳሌ፤ በ1884 ዓ.ም በደቡብ አፍሪቃ አንድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተመስርቶ በ1905 ዓ.ም ቁጥራቸው ወደ 15 ከፍ ብሎ ነበር። ብዙ የአፍሪቃ መሪዎችና ሕዝቦች የአትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምህራን እንድትልክላቸው ጠይቀው ምንም አይነት ዝግጅት ስላልነበር ጥያቄያቸውን ማስተናገድ አልተቻለም። ይህም የዝግጅት አለመኖር እስካሁን ደረስ የቀጠለ ይመስለኛል። ሆኖም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በመላው ዓለም ለተበተኑ ምእመናኖቿ እያደረገችው ያለው ሐዋርያዊ አገልግሎት መልካም ጅምር ይመስለኛል። ለተከታዮቿ ከምትሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ የኢትዮጵያ መልእክተኛ ሆና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሃይማኖትና ባህል ለማስተዋወቅ ይረዳል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትና የመላው አፍሪቃ አብያተ ክርስቲያናት ኮንፈረንስ መስራች አባል ናት። በቅርብ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያኗ የተሰጡት መግለጫዎች እንደሚያመለክቱት 40.000.000 ያህል ተከታዮች፣ 500.000 ያህል ካህናት፣ 40.000 አብያተ ክርስቲያናትና 2.000.000 የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣት አባላት እንዳሏት ያሳያል። ቤተ ክርስቲያኗ በምእመናን ብዛት በኦርቶዶክስ ዓለም ከራሽያ ቀጥላ ሁለተኛዋ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን ከኢኬልቄዶናውያን አብያተ ክርስቲያናት አንጻር ስትታይ የመጀመሪያዋ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ናት። በካህናት ብዛት በዓለም ተወዳዳሪ የሌላት ስትሆን በመላ ሀገሪቱ ከዳር እስከ ዳር፣ ከገጠር እስከ ከተማ ተንሰራፍታ ትገኛለች።

3. ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ እያደገረች ያለው የልማት እንቅስቃሴ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ የትምህርት ዋና ማዕከል ሆና እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ዘልቃለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያንን በነጻ በማገልገልና በነጻ በማስተማር መላ ሕይወታቸውን አሳልፈዋል። ቀን በትምህርት፣ ሌሊት በጸሎት ሀገራቸው ንና ፈጣሪያቸውን አገልግለው በታላቅ ቅድስና አልፈዋል። ያሉት የሥነ ጽሑፍ፣ የሥነ ስዕል፣ የሥነ ጥበብ፣ የሙዚቃ፣ የቅኔ፣ የሕግና የባህል መድኃኒቶችም ሳይቀሩ የእነሱ የትምህርት እንቅስቃሴ ውጤቶች ናቸው።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድሆችን የመንከባከብና የመርዳት የቆየ ባህል አላት። በቅዱስ መጽሐፍ ምፅዋት ከመስዋዕት ይበልጣል ተብሎ ተጽፏል። አንዳንድ የሀገራችን ትምህርት ቤቶች "ብራብ አበላችሁኝ፣ ብጠማ አጠጣችሁኝ፣ ብታረዝ አለበሳችሁኝ.." የሚሉትን የወንጌል ቃላት ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ይሏቸዋል። ክርስቶስ ለፍርድ ሲመጣ የሚቀርቡ ጥያቄች መሆናቸውም በቅዱስ ወንጌል ተገልጧል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህ ቃለ ወንጌል በምእመናኑ ልብ በጥልቅ እንዲሰርጽ ስለ አደረገችና የምጽዋትም ዋጋ በብዙ ገድላትና ድርሳናት ጎልቶ ስለተሰበከ ምጽዋት በጠቅላላ የኢትዮጵያውያን ትልቁ ባህላችን ሆኗል። በመሆኑም ዱሮም ሆነ ዛሬ የጎበረተሰብአችን ማኅበራዊ ዋስትና ይሄው ባህላችን ነው። የድሮውም ሆነ የዛሬው የባህል ትምህርት ቤት ተማሪ የተማረው ቤተ ክርስቲያን በዘረጋቸውና በሺ በሚቆጠሩ ዓመታት በዘለቀው በዚሁ ጽኑ ባህል እንጅ በመንግሥት እገዛ ወይም የወጭ መጋራት ሥርዓት አይደለም። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ለተራቡት ቀለብ፣ ለታረዙት ልብስ፣ ለሕሙማን ሆስፒታል፣ ለአረጋውያን መጦሪያና ለእጓለ ማውታ ማደጊያ የሆነ ማኅበራዊ ዋስትና ዘርግታ ሕዝብን ለዘመናት አገልግላለች።

ሆኖም ይህ ባህል በዘመናዊና ችግርን ለዘለቄታ በሚፈታ መልኩ ቢደራጅ የበለጠ ፍሬያማ ሊሆን እንደሚችል በመረዳት ምስጋና ይግባቸውና የቀደ ሙት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽንን አቋቁመዋል። ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን እና ቤተ ክርስቲያናትና ገዳማት በርካታ የልማት እንቅስቃሴዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ። የእነዚህ አካላት የልማት እንቅስቃሴ ከዚህ በታች ቀርቧል። -

3.1 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የልማት እንቅስቃሴ

3.1.1 ከእ.ኤ.አ 1972 - 1984

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በ1964 ዓ. ም. በነጋሪት ጋዜጣ የሕግ ክፍል ማስታቂያ ቁጥር 415/1964 የተቋቋመ ሲሆን አላማውም፣

1. ወጣቶችን ተፈላጊ በሆኑ የሙያ ትምህርቶች እንዲሰለጥኑ ማበረታታትና መርዳት፣
2. ነዳያንን መርዳት፣
3. በጠቅላላው ለትምህርት፣ ለኢኮሚና ለማህበራዊ ልማት በሚደረገው ብሔራዊ ጥረት ተካፋይ መሆንና መርዳት ነበር<።

ከፍ ብሎ የተጠቀሱት አላማዎች በዘመናዊ አሠራር ከመለወጣቸው በቀር ከነባሩ የቤተ ክርስቲያኗ ተግባራት የተለዩ አልነበሩም። ስለሆነም የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ከተመሠረበት ከ1964 ዓ. ም. ጀምሮ ካህናትን በማሰልጠንና ነዳያንን በመርዳት በጠቅላላውም በትምህርትና ኢኮኖሚ እንዲሁም ማኅበራዊ ልማት ሲንቀሳቀስ ከቆየ በኋላ በ1966 ዓ.ም በተከሰተው ድርቅና ቸነፈር ምክንያት የኮሚሽኑ

ሃላፊነት እየሰፋ ሂዶ በድርቅና በጦርነት የተጎዱትንና የተፈናቀሉትን ሲረዳና መልሶ ሲያቋቁም ቆይቷል። በዚሁ መሠረት በገጠር ልማት የደን ልማት፣ የአፈርና የውሃ ጥበቃ፤ የመስኖ ልማት፣ የግብርና ሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችንና የግብርና ግብአቶችን ማለትም ምርጥ ዘርና የእርሻ መሳሪያ (በሬም ጭምር) ገዝቶ ለገበሬዎች በማስረከብ ሲሠራ ቆይቷል። የጤና ኬላ፣ ክሊኒክ፣ ጤና ጣቢያና የከብት ህክምና ማዕከል ከነሙሉ ድርጅቱ ሠርቶ ያስረክባል። ከዚህም ሌላ የገጠሩ ነዋሪ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት እንዲያገኝ የጥልቅ ውሃ ቁፋሮ እስከ 200 ሜትርና በሰው ጉልበት የሚቆፈሩ ጥልቀታቸው ከ8-12 ሜትር የሆኑ ጉድጓዶችን የመቆፈር፣ ምንጮችን የማጎልበትና የመንከባከብ ሥራ ያካሄዳል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የገጠሩ ነዋሪዎች በሽንት ቤት እንዲጠቀሙ የማስተማርና ሽንት ቤት ሠርቶ የማስረከብ ሥራ ሲያካሂድ ቆይቷል። በተያያዘም ለልምድ አዋላጆች የጤና ትምህርት ይሰጣል። ከዚህም ሌላ ለገዳማትና ለአድባራት የሚሰጡ ጥቃቅን አገልግሎቶች አሉ። እነዚህም አነስተኛና ጥቃቅን ኘሮጀክቶች ውሀ ማውጣት፣ ወፍጮ ቤት፣ ዘይት መጭመቂያ፣ ዳቦ መጋገሪያ፣ ከብት ማርባት፣ የተቃጠሉ አብያተክርስቲያን ማሠራት፣ አልባሳትን መተካት፣ የምግብ አልግሎት፣ ስንዴ ዘይት፣ ብርድ ልብስ የመሳሰሉትን... ማቅረብ ናቸው። ትምህርትን በተመለከተ 1ኛ ደረጃና አማራጭ ት/ቤቶችን ሠርቶ ለመንግሥት ያስረክባል።

ከዚህም ሌላ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ መምሪያ የተባለ ክፍል አለ። ይህ መምሪያ የሚያስተናግዳቸው ስደተኞች ከተለያዩ ሀገሮች ማለትም ከሱዳን፣ ከሶማሊያ፣ ከዛየር፣ ከኤርትራና እንዲሁም ከየመን የመጡ ናቸው። መምሪያው ለስደተኞቹ የተለያዩ እራስን በማስቻል ላይ የተመሠረቱ ስልጠና ዎችን ይሰጣል። እነዚህም ስልጠናዎች የቀርቅሀ፣ የልብስ ስፌት፣ የሳሙና... ማምረት ስልጠናዎች ናቸው። በተጨማሪም ለስደተኞች የጤና፣ የትምህርት፣ የመኖሪያና የምክር አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል።

3.1.2 እ.ኤ.አ. ከ1985 - 2004

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የአገልግሎት አድማሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ ሂዶ ኤ.አ. ከ1985-2004 ዓ.ም ባሉት ዓመታት፤ 1. የምግብ ዋስትናን፣ 2. ጾታንና ልማትን፣ 3. ስደተኞችንና ከስደት ተመላሾችን፣ እና 4. የኤች አይ ቪ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠርን የሚያመለክቱ የእስተራቴጂ ፕላን አውጥቶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። በዚሁ መሠረት በምግብ ዋስትና ሥር፡-

1. ቤተ ክርስቲያናዊ ፕሮግራም፣
2. ሰብአዊ እርዳታ፣
3. መልሶ መቋቋምና
3. የገቢ ምንጭን ማሳደግ

የተባሉ ፕሮግራሞችን አካሂዶአል። የእነዚህን አፈጻጸም፤

የሥልጠና ፕሮግራሞች

በቤተ ክርስቲያናዊ ፕሮግራም ሥር በቀጥታ ለቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሚሰጠው ስልጠናና ርዳታ ተጠቅሷል። ኮሚሽኑ የገቢ ምንጭ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚያደርገው እንቀስቃሴ በአንድ በኩል ቀጣይነት ያለው ሰብአዊ ልማት ፕሮግራም ግቡን እንዲመታ በሌላ በኩል ብቁ የቤተ ክርስቲያን አመራር የሚሰጡ ካህናትን ለማፍራት በአካባቢ ጥበቃ፣ በእርሻ ልማት፣ በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር እንዲሁም ድህነትን ስለማስወገድና ስለ ልማት ባለፉት ዓመታት 12,000 ለሚሆኑ ገዳማዊያንና የአካባቢ ኗዋሪዎች፣ ከ15.000 በላይ ለሚሆኑ ወጣቶችና የወጣቶች መሪዎች እንዲሁም በ7 የካህናት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች ለ10,000 ካህናትን ስልጠና ሰጥቷል። በተጨማሪም ለገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ትናንሽ የመስኖ ልማቶች፣ የውሃ አቅርቦት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት፣ የእንስሳት ልማትና አሳ ማርባት የመሳሰሉትን ልማቶች ማቋቋሙ ተመልክቷል።

የሰብአዊ እርዳታ ፕሮግራም

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት እህል፣ ዘይትና ሌሎች ምግቦችን በማቅረብ የሰብአዊ እርዳታና መልሶ ማቋቋም ተግባር አከናውኗል። በዚሁ መሠረት በተለይም በድርቅና በሀገር ውስጥ ጦርነት ለተጎዱት በትግራይ እና በአማራ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሰሜንና ደቡብ ጐንደር፣ በምስራቅ ጐጃም፣ በሰሜን ሸዋና ዋግ ህምራ ዞኖችና በሌሎችም ክልሎች 23,000.000 (ሃያ ሶስት ሚሊየን) ዜጐችን ህይወት ታድጓል። በዚህ ወቅት 5.000.000 (አምስት ሚሊየን) ኩንታል እህል ያከፋፈለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 3.3 ሚሊዮን ኩንታል ለአማራ ክልል 0.76 ኩንታል ለትግራይ እና ቀሪውን ለሌሎች ክልሎች አከፋፍሏል።

መልሶ ማቋቋም

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በወንበራ፣በወላይታ፣ በእንደርታ፣ በፎገራ፣ በጅንካ፣ በላስታ፣ በዋግ ህምራና በአዳማ አካባቢዎች የመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም አካሂዶአል። በዚሁ መሰረት 20,400 ኩንታል የእህል ዘር 55,000 የተለያዩ የእርሻ መሳሪያዎች 6,900 ያህል የእርሻ በሬዎች አከፋፍሏል። ኮሚሽኑ ከዚህም ሌላ 2,825 ኩንታል ዘር፣ 743 ኩንታል ማዳበሪያ፣ 889 የእርሻ በሬዎች፣ 192 የእርሻ ፈረስ፣ 8,334 የእርሻ መሳሪያ 1,470 የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች፣ 266 በጎችና ፍየሎች፣ 180 የተሻሻሉ የንብ ቀፎዎች፣ 5 የቀንበር አህያዎች በአደጋ ለተጋለጡ ገበሬዎች ያከፋፈለ ሲሆን በተጨመሪም 15 መጋዘኖችን ሠርቶ አስረክቧል። በተጨማሪም ጎብረተሰቡን በማሰልጠን፣ አካባቢውን መልሶ በማልማት፣ ለስደተኞችና ከስደት ተመላሾች መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማለትም የምክር አገልግሎት፣ ህክምና፣ የገጠርና ከተማ ቤሰብን የማገናኘት፣ የ1ኛ 2ኛ ደረጃ እንዲሁም የሙያ ትምህርት አገልግሎቶችን በመስጠትና ስደተኞችንና ከስደት ተመላሾችን በማቋቋም ሲንቀሳቀስ ቆይቷል።

ኮሚሺኑ 21 ዘላቂነት ያላቸው የገቢ ማስገኛና የውሃ ልማት ፕሮግራሞችን ያካሄደ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 13 በአማራ፣ 4 በትግራይ፣ 2 በደቡብ ሕዝቦችና 2 በኦሮምያ ይገኛሉ። የኤች አይ ቪ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠርን በ23 የተለያዩ አህጉረ ስብከቶች የሚያካሂድ ሲሆን ከ1994-2004 ባሉት ዓመታት ላካሄዳቸው የተለያዩ ፕሮጀክቶች 200 ሚሊየን ብር ወጭ ማድረጉ ታውቋል።

ስደተኞችና ከስደት ተመላሾች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በ35 ዓመታት የስደተኞችን የመርዳት ታሪኩ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎችና ከአፍሪቃ በተለይም ከሱማሌና ሱዳን የመጡትን ስደተኞች ተቀብሎ ረድቷል።። በዚሁ መሠረት 22,600 ስደተኞችንና ከስደት ተመላሾችን የረዳ ሲሆን ከእርዳታዎችም ውስጥ የምግብ፣ የልብስ፣ የመጠለያ፣ የትምህርት፣ የህክምናና የምክር አገልግለት ይጠቀሳሉ። ከዚህም በተጨማሪ ለስደተኞች የገቢ ማስገኛ ስልጠናዎችን ይሰጣል።

የቤተሰብን የገቢ ምንጭን ማሳደግ

ለዚህ ዘርፍ፤ 1. የእርሻ ልማትና ኤክስቴንሽን፣ 2. የአካባቢ ጥበቃ፣ እና 3. የማኅበራዊ አገልግሎት እርዳታ የተባሉ ንኡሳን ፕሮግራሞች አሉት።

የእርሻ ልማትና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

በእርሻ ልማት ሥር የተለያዩ የዛፍ፣ የአበባ፣ የፍራፍሬና አትክልት፣ የአዝርእትና ቡቃያ ዝርያዎችን በማስተዋወቅ በማሰራጨት ፕሮግራሙን ተግባራዊ ያደርጋል።

አካባቢ ጥበቃ

በአካባቢ ጥበቃ ሥር የአፈርና ውሃ ጥበቃ፣ የደን ጥበቃ፣ ችግኝ ጣቢያና ችግኝ የማፍላት ፕሮግራምና የእጸዋት ዘር ጥበቃ የአቅም ግንባታ የመሳሰሉት ተግባራት ያከናውናል። ኮሚሽኑ አካባቢን መልሶ ለማልማት እቅድ ይዞ የሚንቀሳቀስ እንደ መሆኑ የዛፍ ዘርን በማባዛትና ለጎብረተሰቡ በማከፋፈል ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። በዚሁ መሠረት በአቋቋማቸው 64 የችግኝ ጣቢያዎች ውስጥ 137,000,000 የተለያዩ የችግኝ ተክሎችን በማፍላት ለተጠቃሚዎች አቅርቧል። 141 የግል የችግኝ ማፍያ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ እገዛ አድርጓል። ከዚህም ሌላ ከ7,400 ሄክታር በላይ የሸፈነና በተጨማሪም አፈርና ውሀን ለመጠበቅ 7.986 ኪሎ ሚትር የሸፈነ የእርከን ስራ የአከናወነ ሲሆን በተጨማሪም 61.400 m^3 ቦዮችንና 244.000 m^3 ግድቦችን ሠርቷል። ከ58.000 በላይ የአፈርና የውሀ ጥበቃ መሳሪዎችን ለተጠቃሚዎች አከፋፍሏል።

ኮሚሽኑ በሚቀሳቀስባቸው አካባቢዎች ድርቅን መቋቋም የሚችሉ ምርቶችንና እንዲሁም አትክልትና የፍራፍሬ ምርቶችን ለገበሪዎች ያቀረበ ሲሆን በተለይም 2,600,000 የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኞችን በደጋና ቆላ ለሚገኙ ገበሬዎች አቅርቧል። ከዚህም ሌላ ኮሚሽኑ ለ771 ገበሬዎች የግል አትክልትና ፍራፍሬያቸውን እንዲ ያመርቱ እገዛ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ 216 ኪሎግራም የአትክልትና ፍራፍሬ ዘሮችንና እንዲሁም 250 ኩንታል የድንች ዘር አከፋፍሏል።

ማኅበራዊ አገልግሎት

በማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፍ ሥር 1. ውሃ፣ 2. ጤናና 3. ትምህርት 4. የገጠር መንገድና 5. ገቢ ፈጠራ... ያሉ ፕሮግራሞች ይታቀፋሉ።

የውሃ አቅርቦት፡- ጥልቅና በጣም ጥልቅ ያልሆኑ የውሃ ጉድጓዶችን፣ በሰው እጅ የሚዘወሩ የውሃ አቅርቦቶችን፣ የምንጭ ጥበቃና ማጎልበት ሥራዎችንና የባህላዊና የተሻሻሉ መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ እንዲሁም የስነ ጤና ትምህርት ይጠቃልላሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ጥልቀታቸው እስከ 180 ሚትር የሆኑ 22 ጥልቅ የውሀ ጉድጓዶችን፣ ጥልቀታቸው እስከ 60 ሜትር የሆኑ 39 መለስተኛ የውሀ ጉድጓዶችንና ከዚህም ሌላ መካከለኛ ጥልቀት ያላቸው 413 ጉድጓዶችንና 40 ትናንሽ ምንጮችን እንዲሁም በእጅ የሚዘወሩ 340 ጉድጓዶችን ቆፍሮ ለተጠቃሚዎች ያስረከበ ሲሆን በተጨማሪም ለ4 ከተሞች የተሟላ የውሀ አገልግሎት አቅርቧል ።

ጤና፡- በጤና አቅርቦት ሥር የጤና ኬላ፣ ክሊኒክና የጤና ጣቢያ ግንባታ፣ የመድኃኒትና የመድኃኒት መሳያና መገልገያዎች አቅርቦትና ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ትምህርት... ይጠቀሳሉ። በዚሁ ፕሮግራም መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በተለይ በጠረፍ ለሚገኘው ኅብረተ ሰብ የጤና አገልግሎት እገዛ ያደርጋል። በዚሁ መሠረት 13 የጤና ኬላዎችን 8 ክሊኒኮችንና 1 የጤና ጣበያ ሠርቶ ለተለያዩ አካባቢዎች ያስረከበ ሲሆን 3.577 የባህልና 778 ቬንትሌትድ የሆኑ መፀዳጃ ቤቶችንና 1.213 የቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓዶችን አሠርቷል። በተጨማሪም መድኀኒቶችና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን አቅርቧል።

ትምህርት፡- በትምህርት ፕሮግራም ሥር የትምህርት ቤቶች ግንባታ፣ የ1ኛ ደረጃ ት/ ቤቶችን በመገንባትና የ1ኛ ደረጃ ት/ ቤቶችን ወደ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማሳደግ፣ የመደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደት የሚያግዙ አስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን በማቅረብ፣ ኅበረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት እንዲጠይቅ በማሰተማርና በማደራጀት፣ በትምህርት ቤቶች አማካኝነት በወጣቶች ክበባትና በካህናት ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ ያለውን ግንዛቤና ንቃት በማዳበርና የሥነ ጾታ ትምህርት በመስጠት ይተገበራል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በብዙ ሺ ለሚቆጠሩ ዜጎች የትምህርት እድልን

ያመቻቸ ሲሆን በዚሁ መሠረት 2 ትምህርት፣ 15 መደበኛ ትምህርት ቤቶችና 42 መደበኛ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶችን ከነሙሉ ድርጅታቸው ሰርቶ ለተጠቃሚው ኅብረተ ሰብ አስረክቧል።

የገጠር መንገድ ሥራ፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የገጠር መንገድ 488 ኪሎ ሜትር የገጠር መንገድና 8 ትላልቅ ድልድዮችን ሰርቶ አስረክቧል።

የገቢ ማስገኛ ፈጠራ፡? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የሴቶችን የሥራ ጫና ለመቀነስ በማቀድ 63 ወፍጮዎችና አንድ የዘይት መጭመቂያ እንዲሁም 1 የስጋጃ መስሪያ አቋቁሟል ።

አቅም ግንባታ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን አማካኝነት 20.000.000 በሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ስለ ኤች አይቪ ኤድስ ትምህርትና ንቃተህሊና አግኝተዋል ተብሎ ይታመናል። ከዚህም ሌላ 51 ሙያተኞችን ለአካባቢ ጥበቃ 201 ለእርሻ ልማት 7 በትምህርት ዘርፍ ሰልጥነዋል። ከ1.000.000 የሚበልጡ አባላት በአዝመራ ምርት በአፈርና ውሀ ጥበቃ በእርሻና ደን ጥበቃ በእንስሳት ልማት በአትክልትና ፍራፍሬ በንብ እርባታ በመስኖ ልማትና ውሀ አቅርቦር ስልጠናዎችን ወስደዋል።

የኤች አይ ቪ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ከ1988 ዓ.ም. ጀምሮ በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም ዙሪያ ሲሠራ ቆይቷል። ኢትዮጵያ በኤች አይ ቪ ኤድስ ከተጠቁ ሀገሮች ውስጥ በመጀመሪያው ረድፍ ትገኛለች። እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም በተደረገው ግምገማ መሠረት ኢትዮጵያ 2.5 ሚሊየን ያህሉ ሰዎች በኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ የተያዙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 10% የኤድስ በሽታ ተጠቂዎች እንደሆኑ ተጠቅሷል። በአሁኑ ጊዜ ኤች አይ ቪ ኤድስ የጤና ችግር ብቻ ሳይሆን ዋና የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ችግር ነው። ይህንኑ ችግር በመገንዘብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ክፍል ከፍቶ ኤች አይ ቪ ኤድስ የመከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም በማካሄድ ላይ ይገኛል። ከሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ውስጥ ከጋብቻ በፊት የመታቀብና ከጋብቻም በኋላ የመታመን ግንዛቤን ማዳበር፣ መንፈሳዊ የምክር አገልግሎት መስጠት፣ ባይረሱ በደማቸው ላሉና በበሽታው ለተጠቁ እርዳታ ማድረግ፣ ለዕንለ ማውታኖችና ለአደጋ ለተጋለጡ ሕጻናት እንክብካቤ ማድረግና የቅድመ ጋብቻ ምርመራንን ማበረታት... ናቸው።

3.1.3 የእ.ኤአ. 2005 - 2009 እቅድ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን እ. ኤ አ. 1991 ዓ. ም. የጸደቀውን የመንግሥት የገጠር ልማት ፖሊሲ በመከተል ከ2005-2009 የሚቆይ ሰባት ዋና ዋና ግቦችን ያቀፈ የስትራቴጂ ፕላን አውጥቶና ከእርዳታና መልሶ ማቋቋም ወደ ዘላቂ ልማት ፕሮግራም ተሸጋግሮ ቀጥሎ የተመለከቱትን ልማቶች በማካሄድ ላይ ይገኛል።

1. የምግብ ዋስትናን በቀጣይነት ለማረጋገጥ በሚደረገው ትግል መካፈል፣
2 መሃይምነትን መዋጋት፣
3 ኤች አይ ቪ ኤድስንና ተዛማች በሽታዎችን መዋጋት፣
4 ለዖታ እኩልነት በሚደረገው ትግል የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ፣
5 በሰላም ግንባታና ግጭት ማስወገድ እንቅቃሴ የራሱን ድርሻ መወጣት፣
6 የኮሚሽኑንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ገጻማትንና ሰበካዎችን አቅም ማጎልበት፣
7. ሰብዓዊ መብቶችን ማስተማር ናቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ራእይ እያንዳንዱ ማኅበረ ሰብ ጥሩ ሕይወት እንዲኖረው መጣር ሲሆን፤ ተልዕኮው በድርቅ፣ በግጭት፣ በዖታ አድሎአዊነት፣ በኤች አይ ቪ ኤድስ ወዘተረፈ.. የተጐዱ ማኅበረሰቦች በተቀናጀና ዘላቂ ልማት ማንቀሳቀስና ራስን ማስቻል ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በዓመት 45,000,000 ብር የሚያወጡ 39 ፕሮጀክቶችን ቀርዖ በተለይም በአማራ፣ በኦሮምያ፣ በሶማሌ፣ በጋምቤላና በሌሎችም ክልሎች በመንቀሳቀስ ላይ ሲገኝ በፕሮጀክቱም 2.5 ሚሊዮን ሕዝብ ይጠቀማል ተብሎ ይገመታል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሌላ የሕጻናትና ቤተሰብ ጉዳይ የተባለ ሌላ ድርጅት አላት። ይህ ድርጅት በ1966 ዓ.ም. በሀገራችን በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን 20, 000 ያህል ሕጻናትን ማሳደጉና በአሁኑ ጊዜም 7,000 ያህል ሕጻናትን በመርዳት ላይ ይገኛል። ወደፊትም ወደ ኮሚኒቲ ሥራ ለመሸጋገር እቅድ አውጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

3.2 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን እየተካሄደ ያለ የልማት እንቅስቃሴ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር እየተካሄዱ ካሉት የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ አንዱ በማኅበረ ቅዱሳን እየተካሄደ ያለ የልማት እንቅስቃሴ ነው።

ማኅበረ ቅዱሳን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች ያቋቋሙት መንፈሳዊ ማኅበር ነው። በዚያን ጊዜ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ይማሩ የነበሩ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች

ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ከነበራቸው ፅኑዕ ፍላጎት የተነሳ በየግቢው፣ በሰንበት ትምህርት ቤቶችና በተለያዩ ቅዱሳን ስም በጽዋ ማኅበራት በ1977 ዓ.ም ራሳቸውን ማሰባሰብ ጀመሩ። ይህ እንቅስቃሴያቸው በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና ካህናት ማሠልጠኛ በሰለጠኑ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ተጠናክሮ በ1983 ዓ.ም ከየከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በብላቴ ዘመቻ በተገናኙ የቤተክርሰቲያን ልጆች አማካይነት በሀገሪቱ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ተስፋፋ።

ማኅበሩ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር ሆኖ በየሀገረ ስብከቱም ሃያ ዘጠኝ ንኡሳን ማዕከላት፣ አምስት ጊዜያዊ ንኡሳን ማዕከላት፣ ሁለት ግንኙነት ጣቢያዎችና አንድ መቶ ሠላሳ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት /ግቢ ጉባዔያት/ በሀገር ውስጥ ሲኖሩት ከሀገር ውጭ አራት ንኡሳን ማዕከላትና ግንኙነት ጣቢያዎች አሉት። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓት እና ትውፊት በየአጥቢያ ሰንበት ትምህርት ቤቶቻቸው እንዲማሩ በማድረግ በአባቶች ቡራኬ አስመርቋል።

ከዚህም በተጨማሪ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ ትምህርት ለማስተማር በካሴት በቪዲዮ፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔት፣ በመዝሙራት እንዲሁም፣ በፖስት ካርዶች በመላ ሀገሪቱ በማሠራጨትና ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል። ማኅበሩ መንፈሳዊ አገልግሎቱን የሚከታተልባ ቸውና የሚፈጽምባቸው 16 የተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎች ሲኖሩት ከ16ቱ ውስጥ እኔ ከተነሳሁበት አርእስት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በተለይ «የቅዱሳት መካናት ልማትና ተራድኦ» የተባለው ክፍል ነው። ክፍሉ ምእመናንን በማስተባበርና በማደራጀት የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ሲገኝ ዋና ዋና አላማዎችም ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው።

ሀ. የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ቅዱሳት፣ መካናት ራሳቸውን ችለው ለማኅበረሰቡ እድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል፣

ለ. ገዳማትና አድባራት እንዲሁም በውስጣቸው የሚገኙ ንዋያተ ቅድሳት መጻሕፍትና የተለያዩ ቅርሶች ባሉበት ይዘታ ተጠብቀው እንዲቆዩ ማስቻል፣

ሐ. የገዳማትና አድባራት ጊዜያዊና አጣዳፊ ችግሮችን /ጧፍ፣ እጣን፣ ዘቢብ፣ ልብሰ ተክህኖ፣ ንዋያተ ቅድሳት ወዘተ.../ አቅም በፈቀደ መጠን መርዳት፣

መ. የአብነት ትምህርት /የቤተ ክርስቲያን ትምህርት/ ትውፊታዊ ሥርዓቱን ጠብቆና ተጠናክሮ እንዲቀጥል መርዳት፣

ሠ. አጽራረ ቤተክርስቲያን በሚበዙባቸው ቦታዎች ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የንዋያተ ቅድሳት፣ የመምህራን እና የካህናትን የደሞዝ ድጎማ በማድረግ ምዕመናን እምነትና ሥርዓታቸውን አጠናክረው እንዲይዙ ማድረግ የሚሉ ናቸው፡

ክፍሉ የተለያዩ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር የሚገኙ የሰንበት ት/ቤቶችን፣ የፅዋ ማኅበራትን፣ የሠራተኛ ጉባዔያትን እና የግል በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር በጊዜያዊ እርዳታና በዘላቂነት ቅዱሳት

መካናቱን በልማት እራሳቸውን እንዲችሉና ለአካባቢው ኅብረተሰብ አርአያ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ ይገኛል። እነዚህን አገልግሎቶች ለመፈጸምም፡-

- ከአህጉረ ስብከቶች ጋር በመነጋገር የገዳማቱን፣ የአድባራቱንና የአብነት ትምህርት ቤቶችን ችግሮች ያጠናል፣ ዘላቂ መፍትሔ የሚያስገኙ ቋሚ የልማት ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል።
- ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚሆን የቁሳቁስ፣ የገንዘብና የሙያ ድጋፍ ከበጎ አድራጊ ምዕመናን እና አባላት አሰባስቦ ተገማባራዊ ያደርጋል።
- በሀገር ውስጥ እና በውጭ አገር የሚገኙ በጎ አድራጊ ምዕመናንን፣ የሠራተኛ ጉባዔያትን፣ ፅዋ ማኅበራትንና ሰንበት ት/ቤቶችን በማስተባበር ለተጎዱ ገዳማት፣ አድባራትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ጊዜያዊ ዕርዳታና ለአብነት መምህራን ድጎማ ያደረጋል።

በዚሁ መሠረት በየዓመቱ ሁለት መቶ ለሚሆኑ ቅዱሳት መካናት የመባ፣ የንዋየ ቅድሳትና ሠላሳ ለሚሆኑ ቅዱሳት መካናት ደግሞ የልብስ ተክህኖ ድጋፍ ያደርጋል።

ከዚህም በተጨማሪ ሊቀውንትንና ካህናትን በማፍራት የሚታወቁ የአብነት ትምህርት ቤቶች ይዞታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ በዓመት እስከ 70, ዐዐዐ ብር የሚደርስ የአብነት መምህራን በጀት ይዞ ለያንዳንዳቸው በወር ከ150-350 ብር የሚደርስ ደጎማ ያደርጋል።

ቅዱሳት መካናት ቀደም ሲል ይተዳደሩበት የነበረው መሬት በመንግስት ይዞታ ሥር እንዲሆን በመደረጉ/በመውረሱ አብዛኛቹ ገዳማት እና አድባራት ለዕለት ጉርስ የሚሆን ገቢ እንኳን በማጣታቸው የገዳማቱ ማኅበረ-ሰብ ለረሀብና ለዕርዛት ከመጋለጣቸውም በላይ ገዳማቱን ለቀው በመሰደድ ላይ ይገኛሉ። ማኅበረቅዱሳን ይህንን ችግር በመረዳትና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በማጥናት እንዲሁም በጎ አድራጊችን በማስተባበርና ድጋፋቸውን በተቀናጀ መልኩ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት እያንዳንዳቸው በአማካይ ከ 20,000 – 300,000 ብር የሚፈጁ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን እያጠና በመተግበር ላይ ይገኛል። ተግባራዊ ከሆኑት ፕሮጀክቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ አነስተኛ የመስኖ ልማት፣ የንብ እርባታ፣ ከብት እርባታ፣ የመጠጥ ውሀ እና ጥበበ እድ ናቸው። በዚህም መሠረት ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ አስራ ሰባት የሚሆኑ ፕሮጀክቶች ሙሉ በሙሉ ተጠናቀው ርክክብ የተፈጸመና አግልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን አስራ አራት የሚሆኑ ፕሮጀክቶች ደግሞ በመተግበር ላይ ናቸው።

3.3 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትረያርክ ጠ/ጽ/ቤት የተካሄደ ያለ የልማት እንቅስቃሴ.

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር እየተካሄዱ ካሉት የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ አንዱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓተረያርክ

ጠ/ጽ/ቤት ሥር እየተካሄዱ ያሉት የግንባታ እንቅስቃሴዎች ይጠቀሳሉ። ከእነዚህም ግንባታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው፤

1. የመንበረ ፓትረያርኩ ሕንጻ
2. የመንበረ ፓትረያርክ ጠ/ጽ/ቤት መ/ቤት
3. የመንበረ ፓትረያርኩ ሙዝየም
4. ጎፋ ቅዱስ ገብርኤል የሚገኘው የብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፊሎስ መታሰቢያ ሙዝየም
5. የመንበረ ፀሐይ እንጦጦ ማርያም ሙዝየም፣
6 የብጹዕ አቡነ ጴጥሮስ መታሰቢያ ሐውልት እድሳት፣
7. በመንበረ ፓትረያርክ ጠ/ጽ/ቤት መ/ቤት የሚገኘው የሜሮን ማዘጋጃ ቤት... ናቸው።

ከፍ ብሎ የተጠቀሰት ሥራቸው ተጠናቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን ቀጥሎ የተመለከቱት ግንባታዎች ሥራ ደግሞ በሂደት ላይ ይገኛል። እነሱም፡-

1. የ6 ፓትረያርኮች (እንግዶች) መቀበያ ሕንጻ፣
2. የ60 ሊቃነ ጳጳሳት መኖሪያ ባለ 3 ፎቅ ሕንጻ፣
3. የቅዱስ ፓትረያርኩና የ20 ሊቃነ ጳጳሳት ማረፊያ ሕንጻ (ደብረ ሊባኖስ)፣
4. 25 ሚሊየን ብር ይፈጃል ተብሎ የተገመተ የዩኒቨርስቲ ሕንፂ (ቅ. ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሊጅ)፣
5. የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት ቤት ሕንፂ፣
6. 5 ሚሊየን ብር ይፈጃል ተብሎ የተገመተ የቁልቢ ትምህርት ቤት ሕንጻ፣
7. ለገቢ ማስገኛ የታቀደ ባለ 10 ፎቅ ሕንጻ፣
8. የብጹዕ አቡነ ሚካኤል መታሰቢያ ሐውልት (ጎሬ ከተማ).... ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከፍ ሲል የተገለጹት ግንባታዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትረያርክ ጠ/ጽ/ቤት እየጠከናወኑ ያሉት ሲሆኑ በየሀገረ ስብከቶቹም ተመሳሳ ግንባታዎች እንዳሉ ተጠቁሟል። በተለይም የነባር አብያተ ክርስቲያናት እድሳት አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ግንባታ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። ለምሳሌ በ1999 ዓ.ም. 127 ነባር አብያተ ክርስቲያናት እየታደሱ ሲሆን በዚሁ ዓመት 27 አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ተገንብተዋል።

ከዚህም ሌላ የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት የተለያዩ ግንባታዎቸን እንደሚያካሂዱ የሚታወቅ ሲሆን ሕንጻዎችም 1. ለትምህርተ ቤት፣ 2. ለጤና ጣቢያ፣ 3. ለሁለገብ አገልግሎት (ለገቢ ማስገኛ) የሚያገለግሉ ናቸው። እዚህ ላይ የደብረ ጎይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን፣ የማኅደረ ስብሐት ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን፣ የምስካየ ኀዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን፣ የአዲሱ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፣ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን፣ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን የቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን፣ የቦሌ በልቡላ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን፣ የሰአሊተ ማርያም ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ይጠቀሳሉ። አብያተ ክርስቲያናቱ በትምህርት (ለምሳሌ፤ ምስካየ ኀዙናን መድኃኔ ዓለም፣ ደብረ ጎይል ቅዱስ ራጉኤል፣ የማኅደረ ስብሐት ልደታ

ማርያም፣ የአዲሱ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፣ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል...) በትምህርት ኅብረተሰቡን በማገልገል ላይ ሲገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በተለያዩ አንስተኛ ልማቶች ማለትም ቡሎኬትና ብረታ ብረት ዳቦ ቤት..... ከፍተው እንደሚያካሂዱ ታውቋል።

በአጠቃላይ በምዕራፍ 3 ለመጥቀስ እንደተሞከረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለምግብ ዋስትና፣ ጾታና ልማት፣ ሠራተኞችና ከስደት ተመላሾች፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ፣ በእርሻ ልማትና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ፣ በትምህርትና ጤና፣ የገጠር መንገድ ግንባታ፣ ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያት ያጡ ሕጻናትን ለማሳደግ ወዘተ... በስፋት እየተንቀሳቀሰች ሲሆን ቤተክርስቲያኗ ካላት አደረጃጀትና የሕዝብ ተቀባይነት አንጻር ከዚህ የተሻለ የልማት ተሳትፎ ሊደረግ እንደሚችል ይታመናል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የ2020 ልማት ግቡን ይመታ ዘንድ የጀመረችውን የሰላም እንቅስቃሴ አጠናክራ መቀጠል ይጠበቅባታል።

ኢትዮጵያውያን ቀድሞውንም ደጎችና ሰላማውያን እንደሆኑ ሆሜር ጽፏል። ኢትዮጵያውያን ሰላማዊውን የክርስትና ሃይማኖትም ሆነ እስልምናን በሰላም ተቀብለውታል። ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በሰላም ነው። ክርስቶስ ሲወለድ የሰማይ መላእክት የሰላም መዝሙር ዘመሩ። ለምድር በጐ ፈቃድ ለሰው ልጆች ሰላምን ሰበኩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ስለ ሰላም ያለመታከት ትጸልያለች። በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ ያለመሰልቸት እየደጋገመ "ተንሥኡ ለጸሎት" ባለ ቁጥር ቄሱም ያለመሰልቸት "ሰላም ለኵልክሙ" በማለት ያስተጋባል። ምእመናኑም "ምስለ መንፈስከ" በማለት ሰላማዊ መልስ ይሰጣሉ። በመስተብቁዕ "በእንተ ሰላም" ተሠርቷል። ማኅሌት ምንግዜም በሰላም መዝሙር ይደመደማል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰላም ከመጸለይ በተጨማሪም ስለ ሰላም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳለባት በማመን በቀረጸችው የልማት ፕሮገራም የሰላም አጀንዳ ቀርጻ መንቀሳቀሷ ያስመሰግናታል። ሰላም በቤተ ሰብ፣ ሰላም በማኅበረሰብ፣ ሰላም በብሔር፣ ብሔረሰቦችና በሃይማኖች መካከል መካከል ሊሰፍን ልማት ሊቀላጠፍ ይችላል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብ፣ በብሔርና ብሔረሰቦች መካከል የተዘረጋች ተቋም እንደመሆኗ በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብ፣ በብሔርና ብሔረ ሰቦች ውስጥ በሰላም፣ ስለ ሰላም ብትሠራ ውጤታማ ትሆናለች የሚል እምነት አለኝ። ስለዚህ በተቀረጸው የልማት ፕሮግራም መሠረት በርትታ ልንሠራ ይገባል የሚል እምነት አለኝ።

ለሰላም መኖር አስፈላጊ ከሆኑት ውስጥ አንዱና ዋናው የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትሕ ርትዕ መኖር ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቤተሰብ፣ በማኅበረ-ሰብ፣ በብሔርና

ብሔረ ሰቦችና ብሎም በዓለም ፍትሓዊ የሆነ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲኖር አጥብቃ ልትሰብክና ልታስተምር ይገባል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መቻቻልን፣ ይቅርታን፣ እርቅና ፍቅርን አጠናክራ ማስተማር ይጠበቅባታል።

ለልማት ሰላም መሠረት እንደሆነ ሁሉ ለሰላምም ከማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እኩልነት (ፍትሕ) በተጨማሪ መቻቻል፣ ይቅርታ፣ እርቅና ፍቅር ያስፈልጋል። ፍቅር ይቅርታና እርቅ የክርስቲያንነት መለኪያዎች ናቸው። እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ሰዎች ሁሉ ደቀ መዛሙርቶቼ መሆናችሁን በዚህ ያውቃሉ ይላል ጌታ። ስለ ይቅርታም የበደሉንን ይቅር እንድንል በደላችንን ይቅር በለን በማለት ይቅር ለመባል ይቅር ማለት፣ ለመማር መማር እንደሚያስፈልግ ጌታ አስተምሯል። በየቀኑም እንተገብረው ዘንድ በየቀኑ እንድንጸልየው ታዝዟል። መቻቻል፣ ይቅርታ፣ እርቅና ፍቅር በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብና በሃይማኖቶች.. መካከል ያለ ማቋረጥ ሊተገበር ይገባል። ለዚህ ነባሮቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖት ተቋማት ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖት ለ1400 ዓመታት ያህል ተቻችለው ኖረዋል። በዚህም ባህላቸው ለዓለም መልካም ምሳሌ ተብለው ይጠቀሳሉ። ይህም ከሌሎች ሀገሮች ታሪክ ጋር በማነፃፀር እንጅ በማጋነን ወይም ለይስሙላ ብቻ የሚነገር አይደለም። በመካከለኛው ምስራቅ፣ በእስያ፣ በሰሜን አፍሪካና በአውሮፓ የነበረውን ታሪክ ስናስታውስ መካከለኛው ምስራቅ ማለትም ፍልስጥኤም፣ ሶርያ፣ ሌባኖስ ዮርዳኖስና በሰሜን አፍሪካም እንዲሁ ግብፅ፣ ሊብያ፣ ቱኒዝያ፣ ሱዳንና ሌሎችም ሀገሮች ክርስቲያኖች ነበሩ። በአውሮፖም ቱርክ የክርስቲያን ሀገር ነበር። እንዲሁም በእስፔን ሙስሊሞች ነበሩ። ይሁን እንጂ ሁሉም እንደ ኢትዮጵያ ተቻችለው እስከ አለንበት ጊዜ ድረስ አልዘለቁም። አንዱ ሌላውን አጥፍቶ ነው ሕይወት ቀጥሎ የምናገኘው። ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ሁኔታው ከዚህ የተለየ ነው። ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ መንግሥት የተለያዩ ሃይማኖቶች ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ አብረው ሊኖሩ እንደሚችሉ ለመጀመሪያ ጊዜ አምኖ የተቀበለ ብቻ ሳይሆን በዚህ የማያምኑትንና የነቢዩ መሐመድን ተከታዮች እያሳደዱ እስከ ኢትዮጵያ የመጡትን ቁሪቶች አሳፍሮ የመለሰ መንግሥት ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያኖቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት (ከአንዲት የታሪክ አጋጣሚ በቀር) ሙስሊሞቹ ክርስትናን እንዲቀበሉ ያስገደዱበት ጊዜ በታሪክ አይታወቅም። እርግጥ አልፎ አልፎ ግጭቶች ነበሩ። ይህ ግን የአካባቢ ገዢዎችና ባላባቶች ግብር ሲከለክሉ ወይም አደጋ ጥለው ክርስቲያኑን ማኅበረ ሰብ ሲያጠቁ እንጅ ክርስቲያኑ መንግሥት የክርስትናን ሃይማኖት ካልተቀበላችሁ ብሎ ያስገደደበት (ከአንድ የታሪክ አጋጣሚ በቀር) ሌላ አጋጣሚ አላገኘሁም። የሁለቱን ነባር ሃይማኖቶች መቻቻል አስመልክቶ መጠቀስ ያለበት ሌላ ነገር አንድ የኦርቶዶክስ ሰባኪ ወደ ሙስሊም ቤት ሄዶ ወይም በመንገድ አቁሞ መጽሐፍ ቅዱስ ልስበክ ወይም አንድ የሙስሊም ሰባኪም ወደ ክርስቲያን ቤት ሄዶ ወይም ክርስቲያኑን በመንገድ አቁሞ ቁርአን ልስበክ ወይም ልቅራ ሲል አይገኝም። ከዚህም በላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰባክያን እስልምናን አጣጥለው ሲሰብኩና ሲጽፉ አይስተዋልም። ይህም ለጤናማ ግንኙነታቸው ምሳሌ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል። ወደ ፊትም በዚሁ ቢቀጥል ለልማታችን አወንታዊ የሆነ ትርጉም ይኖረዋል።

በተመሳሳይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትናና በሌሎች የክርስትና እምነት ተከታዮች መካከልም ተመሳሳይ ግንኙነት ቢኖር ለልማታችን ጠቃሚ ይሆናል። ኢትዮጵያ በርካታ ችግሮች ያሉባት ሀገር ናት። በርካታ ብሔር ብሔረሰቦችን ያቀፈችና በቆዳ ስፋትም ስትታይ ታላቅ ሀገር ናት። ምንም እንኳን የረጅም ጊዜ የጋራ ታሪክ ቢኖረንም ካለው መልክአ ምድራዊ አቀማመጧና ጎላ ቀር መገናኛ የተነሳ አንድ ዐይነት ቋንቋ፣ አንድ ዐይነት ሃይማኖትና አንድ ዐይነት ባህል የለንም። ይህ በአንድ በኩል ውበት ነው ቢባልም ችግር ያለው መሆኑም አይካድም፤ ልዩነታችን በዚያው ልክ የሠፋ ነውና። ይህን ልዩነታችን የበለጠ እንዲሰፋ አንዳንድ ኃይሎች ተግተው እንዳይሠሩ ነቅተን ልንጠባበቅ ይገባል።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በጥቁር ዓለም ለረጅም ጊዜ የቆየ ነፂ መንግሥት፣ ነፂ ባህልና ነፂ ሃይማኖት ያላት ጠንካራ ሀገር ሆና እሰከ እኛው ዘመን ድረስ ዘልቃለች። ይህም ለብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ምሳሌና መኩሪያ እንድትሆን ስላደረጋት ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያዊነት የሚለውን የጥቁር ሕዝብ እንቅስቃሴም አነሳስቷል። በዚህ የጥቁር ሕዝቦች እንቅስቃሴ ደስ የማይሰኙ ኃይሎች መኖራቸው ደግሞ ግልጽ ነው። እነዚህ ኃይሎች "ኢትዮጵያዊነት" የተሰኘውን እንቅስቃሴ ምክንያት የሆነችውን ሀገራችንን በቋንቋ፣ በባህልና በሃይማኖት ስትከፋፈል ማየት ደስ ይላቸዋል። ይህም የማኅበረሰቡ አንድነት እንዲላላና እንዲፈራርስ ተግተው ሊሠሩ ይችላሉ። ከእነዚህም መሳሪያዎች አንዱ ሃይማኖት ነው።

በንጉሡ ጊዜ የውጭ ሚሲዮናውያን ክርስቲያን ወደ አልሆኑት የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሂደው ወንጌልን እንዲሰብኩ ተፈቅዶላቸው ነበር። ሆኖም በዚህ ፋንታ በፅናት የሠሩት ከእነሱ በፊት በሺ የሚቆጠር እድሜ በነበራት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሰባክያንና አማንያን ይህንን እንደ ወረራ በመቁጠር በተደጋጋሚ ቅሬታቸውን ሲገልጹ ይሰማሉ። እውነትነትም አለው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስሟም እንደሚያመለክተው ትክክለኛ የክርስትና እምነት ያላት መሆኑ እየታወቀ የራሳቸውንን ባህልና ልማድ ለመገንባት ሲሉ ብቻ የእሷን እምነትና ባህል እንዲሁም ማኅበራዊ ግኙኝነት ለማፈራረስ ሌት ተቀን ተግቶ መሥራት በጎ ነገር አይደለም። እነዚህ ጎይሎች ቀደም ሲል በአውሮፓና በአሜሪካ በሰፊው ተንቀሳቅሰው እንደ ነበር ይታወቃል። ይህ እንቅስቃሴያቸው በሀገራቸው እየከሸፈ ሲመጣ ወደ ሀገራችን በገፍ በመግባት የኅብረተሰባችንን ማኅበራዊ ግኙኙነት ሲጎዱት ይስተዋላሉ። የኅብረተሰቡ ማህበራዊ ግንኙነት መላላት ደግሞ ጠንካራ ያልሆነችና የደከመች ሀገርን ይፈጥራል። ይህም በወደፊቱ ልማታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ስለዚህ ሁለቱም ወገኖች በችግሩ ዙሪያ ውይይት አድርገውና መፍትሄ ፈልገው እልባት ቢሰጡት ለ2020 ለተያዘው እቅዳችን መልካም ውጤት የሚያስገኝ ይመስለኛል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ለሥራ ማንቀሳቀስ አለባት።

ለልማት መሠረቱ ሥራ ነው። ልማትና እድገት የሚመጣው በሥራ ነው። ድህነትን ለማስወገድ መሥራት ያስፈልጋል። ስለዚህ የሃይማኖት ተቋማት ሥራን ማበረታታትና ራሳቸውም ትጉህ ሠራተኞች ሊሆኑ

ያስፈልጋል። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ትዕዝዝ «በወዝህ ላብ ብላ» የሚል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም«አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ» በማለት የሥራን ክቡርነት አጽንኦት ሰጥቶ ተናግሯል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «የማይሠራ አይብላ» በማለት ይህንኑ መሠረታዊ ሃሳብ አጠናክሮታል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ለሥራ ጥሩ አብነት ናቸው። እየቀደሱ ያርሳሉ። እያረሱ ይቀድሳሉ። በአንድ ግዜ ማለቴ አይደለም። በእርሻ ሥራ እየተዳደሩ ቤተ ክርስቲያንን በነፂ ያገለግላሉ ለማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እለታቱን በበዓላት ሞልታቸዋለች የሚል ስሞታ ይሰማል። እንደተባለውም በዓመት ውስጥ ያሉት የሥራ ቀናት ቢቆጠሩ የዓመቱ ግማሽ ቀናት እንኳን አይሆኑም። ሆኖም ሁሉም በዓላት ቀኖናዊ አለመሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። አብዛኞቹ የሀገራችን በዓላት የተደነገጉት በዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው። በዓላቱን ለማብዛት ምክንያት ተብሎ የሚጠቀሰው በዘመናቸው አምልኮ ባዕድ በዝቶ ስለ ነበር ምእመናኑን ለማስተማር ሲባል የተወሰኑ የመሰብሰቢያ ቀናት ለማግኘት የተደረገ ነው የሚል ነው። ውሳኔው መጽሐፈ ምሥጢር በተባለው መጽሐፍ እንደሚከተለው ተላልፎልናል።

ግበሩ በዓላቲሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል በክልኤ ሠላሳ ወሠለስተ ዕለተ በከመ ወሀብናክሙ ቀዳሚ እስመ አልቦ ዘይከብር እምኔሃ እምታሕተ እግዚአብሔር። ወበዓለ ሚካኤልሂ አመ 0ወ2 ለለወርኁ፣ ወበዓለ ገብርኤልሂ አመ 0ወ9 ለታኅሣሥ፣ ወአመ ፷ወ2 ምስለ ደቅስዮስ፣ ወአመ ፷ወ6 ለሰኔ ቅዳሴ ቤቱ። ወግበሩ በዓለ ሩፋኤል አመ ሠሉሱ ለጳጉሜን፣ አመ አሚሩ ለመስከረም ራጉኤል፣ አመ ሰሙኑ ለኅዳር አፍኒን፣ አመ ሠሉሱ ለታኅሳስ ፋኑኤል፣ አመ፷ወ7 ለጥር ሱርያል፣ አመ 5 ለሐምሌ ሳቁኤል፣ አመ ፷ወ2 ዑራኤል። እሉ እሙንቱ ሊቃነ መላእክት ወአክብሩ በዓሎሙ።

ትርጉም

በመጀመሪያ እንዳስተላለፍንላችሁ በሁለት ወገን ድንግል የሆነች የእመቤታችን ማርያምን ሠላሳ ሦስት ቀኖች አክብሩ፤ ከእግዚአብሔር በታች እንደሷ የሚከብር የለምና። የሚካኤልም በዓል (ወር በገባ) በየ12 ቀኑ፣ የገብርኤልንም በዓል በታኅሳስ 19 ቀንና ከደቅስዮስም ጋር (በዚሁ ወር) በ22 ቀን፣ እንዲሁም በሰኔ 26 ቀን ቅዳሴ ቤቱን፣ (አክብሩ) የሩፋኤልን በዓል ጳጉሜ 3 ቀን፣ የራጉኤልን በዓል መስከረም 1 ቀን፣ የአፍኒን በዓል ኅዳር 8፣ የፋኑኤልን በዓል ታኅሳስ 3 ቀን፣ የሱርያልን በዓል ጥር 26 ቀን፣ የሳቁኤልን በዓል ሐምሌ 5፣ የዑራኤልን (በዚሁ ወር) በ22 ቀን አክብሩ።

በዚህ ውሳኔ መሠረት፣ ለእመቤታችን 33 በዓላት፣ ለቅዱስ ሚካኤል 12 ቀናት፣ ለቅዱስ ገብርኤል 3 ቀናት፣ ለቅዱስ ሩፋኤል 2፣ ለሌሎቹ ሊቃነ መላእክት 5 በድምሩ 56 ቀናት ተወስነዋል።

ከዚህም ሌላ ቅዳሜን በዓል እንዲሆን ያስወሰኑ አፄ ዘርአ ያዕቆብ ናቸው። በስም ቀዳሚት ሰንበት ተብላ ትታወቃለች። በሌሎቹ ክርስቲያኖች ዘንድ አትከበርም። ለነገሩ በሀገራችንም እስከ ዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን አትከበርም ነበር። ቅዳሜ በመጀመሪያ መከበር የጀመረችው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ጀምሮ ነው። የዘህ አሳብ ዋና አመንጭና ደጋፊ የደብረ ቢዘኑ አቡነ ኤውስጣቴዎስ ነበሩ። በዓሉ በክርስትናው ዓለም ያልተለመደ መሆኑን በመሀል ሀገር ሊቃውንትና በጳጳሳቱም ቢነገራቸው አቡነ ኤውስጣቴዎስ አልተቀበሉትም። በዚህ ምክንያት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ከተቀናቃኞቻቸው ጋር ወደ ግብጽ ቤተ ክርስቲያን ተላኩ። ሆኖም እዚያም አልቀናቸውም። በዚህም ምክንያት ወደ ሀገር ቤት በመመለስ ፋንታ ወደ አርመን አምርተው እረፍታቸው በዚያ ሆኗል። ከአቡነ ኤውስጣቴዎስ በኋላም ውዝግቡ አልበረደም። ይህንኑ ምክንያት በማድረግ የሰሜን ሀገር መነኮሳት ከመሀል ሀገር ክርስቲያኖች ጋር አንድነት አይኖረንም ብለው ስለ አከረሩ ያለው አማራጭ የቅዳሜን ሰንበትነት ተቀብሎ አንድነቱን ማምጣት ነበር። ስለዚህ ውሳኔው ከሃይማኖት ይልቅ ፖለቲካዊ ነበር ለማለት ይቻላል። በዐፄ ዘርአ ያዕቆብ የተወሰኑት በዓላት ብቻ ከቅዳሜ ጋር ወደ 109 መሆናቸው ነው። ከተጠቀሱት ውጭ፤ -

ዐበይት በዓላት	9
በዓለ እግዚአብሔር	12
መድኃኔ ዓለም	12
የሐዋርያት በዓላት	12
የቅዱስ ጊዮርጊስ	3
የአቡነ ተክለ ሃይማኖት	
የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ	

በድምሩ ወደ 50 ይሆናሉ። ከዚህ ጋር እሁድ ሲጨመር 100 ገደማ ይሆናሉ። ስለዚህ በዓላቶቻችን በድምሩ 210 ያህል ይሆናሉ። እንግዲህ በዓመት ውስጥ የሚኖሩን የሥራ ቀናት 150 ገደማ ከሆኑ ነው።

ይህም ደግሞ የወር በዓላትን ሳናስገባ ነው። በብዙ ሰበካዎች የየደብሩ ጽላት በየወሩ እንደሚከበር ማስታወስ ያስፈልጋል። እነዚህ ሲጨመሩ ከዚህም በላይ ሊሄድ ነው። ይህ ጸሐፊ ብዙዎቹ በዓላት (ቅዳሜንም ጨምሮ) ታስበው ቢውሉ ይደግፋል። እርግጥ ምእመናን ለበዓላት ስሱ እንደሆኑ ሳይረሳ።

እራሳቸውን ከማንም በላይ ጻድቃን አድርገው ይቆጥሩ የነበሩት ፈሪሳውያን በጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ይሰነዝሯቸው ከነበሩት ክሶች አንዱና ዋናው ከነደቀ መዘሙርቱ ሰንበትን አያከብርም የሚል የበዓል ወንጀል ነበር። እሱ በሰንበት ድውያንን ፈውሷል። ደቀ መዛሙርቱ እሸት ቆርጠው በልተዋል (ማቴ.12፣7) የሚል ነው። እሱ ግን ዳዊት በረሃብ ጊዜ ሊበላው የማይገባውን መስዋእት መብላቱንና ከእሱም ጋር ለነበሩት መስጠቱን፣ ካህናትም በቤተ መቅደስ ሰንበትን እንደሚያረክሱና ጎጢአትም እንዳይሆንባቸው መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሶ ራሱንና ደቀ መዛሙርቱን ተከላክሏል። በማያያዝም ሰንበት ስለ ሰው እንጅ ሰው ስለ ሰንበት አለመፈጠሩን ግልጽ አድርጓል (ማቴ.12፣7)።

ወደ ሀገራችን ስንመጣ ዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ዕለታቱን በበዓል የሞሉበት ምክንያት አምልኮ ባዕድን ከሀገሪቱ ለማስወገድ ለተያዘው እቅድ የማስተማሪያ ዕለታት ለማግኘት እንደ ነበር ተወስቷል። ከዚያም ሌላ በዚያን ጊዜ በሀገራችን የምግብ ጥያቄ አልነበረ ይሆናል። ዛሬ ግን ዋናው ጥያቄያችንና ችግራችን ሆኗል። ረሃብ ደግሞ ምን እንደሚያደርግ ከዳዊትና ከሐዋርያት ታሪክ ተምረናል። በአንጻሩ በሀገራችን ዛሬ አምልኮ ባዕድ ተወግዷል። አለ ከተባለም ይህን ለሚያደርጉት ግለሰቦች በተጠቀሱት በዓላት የሃይማኖት ትምህርት ሲሰጥ አናይም። በተለይም ተጨማሪ የሥራ ቀናት በሚያስፈልጉት በገጠሩ አካባቢ።

ለመደህየታችን ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አንዱ እያንዳንዱ ሰው በቂ ሥራ አለመሥራቱ እንደሆነ ይታመናል። አንዳንዱ ሥራ በማጣት ሌላው ደግሞ በበዓላት ብዛት በቂ ሥራ አይሠራም። በአንጻሩ በሥራ ቀናትም የሚሠራ ሥራ የለንም የሚሉ ምእመናን እንዳሉ አውቃለሁ። በተለይ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ለአብዛኛወቅ ቤተ ሰብእ 3 ጥማድ ብቻ ስለሆነ ባሉት የስራ ቀናትም የምንሠራው የለንም የሚል ድምጽ ይደመጣል። ሠራተኛ እያለ ሥራ መጥፋቱ ሊታሰብበት የሚገባ ቢሆንም የበዓላት ብዛት የሚያሳስባቸው ግን ሥራ ያላቸው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። እየተነጋገርን ያለነውም ሥራ እያላቸው በበዓል ስም መሥራት ላልቻሉት ነው። ሥራ ለሌላቸው ግን ሁሉም ቀናት በዓሎች ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ አንድ ኢንቬስተር አማኝ ነው እንበል። የቤተ ክርስቲያንን ሕግጋት መጠበቅ ይፈልጋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገሩን ማልማትና ወገኑን መርዳት ይሻል። እንዴት ነው የሚሆነው? ወዛደሩም ተመሳሳይ ችግር ያጋጥመዋል። አማኝ ነው። ግን ሳይሳቀቅ ሠርቶ መኖርና መጽደቅም ይፈልጋል። የኢትዮጵያ ካህንም አርሶ አደር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እሱ አስቀድሞ በዓል አክብሮ ምእመናንን ማስከበር ይኖርበታል። ግን ደግሞ ካህኑ ብዙውን ጊዜ (በሥራ ቀንም እንኳ) በቤተ ክርሳቲያን አገልግሎት የሥራ ጊዜውን ያሳልፋል። ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መልስ የቀሩት ቀናት በዓላት ሊሆኑበት ነው። ስለዚህ ከማንም በላይ ተጎጂ ነው የሚሆነው። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኞቹ የሀገራችን በዓላት የተደነገጉት በአጼ ዘርአ ያዕቆብ እንጅ በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በሲኖዶስ ወይም በዓለም አቀፋዊ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን አይደለም።

በሌላ በኩል ደግሞ በቅዱሳንና በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የተደነገጉት በዓላት ሁሉም እየተከበሩ እንዳልሆነ እናውቃለን። ስለዚህ አብዛኞቹ በዓላት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሲኖዶሳዊም ስላልሆኑ በሲኖዶስ ተጠንተው አንዳንዶቹ ታስበው እንዲውሉ ቢደነግግ መልካም ነው እላለሁ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቁጠባን ልታስተምር ይገባል።

ልማትን ለማምጣት አንዱ መንገድ ቁጠባ እንደሆነ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይመክራሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ነገ ለራሷ ታስባለችና ለነገ አታስቡ። የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ። አይዘሩም፣ አያጭዱም፣ በጎተራ አይከቱም የሚለው ጎይለ ቃል በጎብረተ ሰባችን በተዛባ መልኩ ሰርፁዋል። ክርስቶስ ይህንን ያለው የእግዚአብሔርን ከሀሊነት ለመግለጽ እንጅ እንደ ወፎች አትዝሩ፣ በጎተራም አትክተቱ፣ ለነገም አታትርፉ ለማለት አይደለም። ያ ቢሆን "በወዝህ ላብ ብላ" የሚለው መለኮታዊ ትእዛዝ አላስፈላጊ ነበር። ሆኖም

ምእመኑ በዚህ መንፈስ ስላልተረዳው ቁጠባ በባህላችን ንፉግነትና ሰፍሳፋነት የሚል ትርጉም አለው። ስለሆነም የኢኮኖሚስቶች የቁጠባ ምክር በሀገራችን ሊሰርፅ አልቻለም። የኢኮኖሚስቶች የቁጠባ ምክር ከኢኮኖሚስቶች ይልቅ በሃይማኖት አባቶች በኩል ቢቀርብ በጎበረተሰባችን ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት ይኖረዋል። ጎበረተሰቡን ለጋስ ያደረጉት የሃይማኖት አባቶች ናቸው። ለጋስ ማድረግ ከቻሉ ቆጣቢ ማድረግም አይሳናቸውም። ምእመናን እንዳይቆጥቡና ብሎም እንዲደኸዩ ከሚያደርጉት ልማዶች ውስጥ አንዱ ጎዘንንና ደስታን ተከትሎ የሚመጣ ወጭ ነው።

በተፈጥሮ ሞትን ሕማም ይቀድመዋል። ሟች በሕማም ላይ በሚሆንበት ጊዜ ቤተሰቦቹ ታማሚውን በሐኪም ቤትና በፀበል በማስታመም ቅርሳቸውን ያራግፋሉ። የጉልበት አቋማቸውም በማስታመም ይሟጠጣል። ሕመምተኛው ካረፈ በኋላ ቤተሰቦች አግባብ የሆነ የቀብር ሥነ ሥርዓት አስፈጽመው ማረፍና መደበኛ ሕይወታቸውን መቀጠል ሲገባቸው ልማዱ ይህንን እንዲያደርጉ አይገፋፋቸውም። በመጀ መሪያ ምንም የሚሰጠው ጥቅም ባይኖርም በቀብሩ ላይ ዘመድ ወዳጅ ብቻ ሳይሆን የዘመድ ወዳጅ ዘመድ ወዳጅ ሁሉ ተገኝቶ ያስተዛዝናል። ይህም የያንዳንዱን ማኅበረሰብ የግልና የመንግስትንም ሥራ በእጅጉ ይጎዳል። የመንግሥት ሥራም እያንዳንዱን ማኅበረሰብ ይነካል። የሠራተኛው ቀብር መሄድ ባለጉዳዩ እንዲጉላላ ምክንያት ይሆናልና። ከቀብሩም በኋላ ፍራሽ ተነጥፎ ጎዘኑ ለ40 ቀናት ሊቀጥል ይችላል። ይህ ሁሉ በቤተ ሰቡ፣ በማኅበረ ሰቡና በአጠቃላይ በአገሪቱ ላይ ቀላል የማይባል የሀብትና ጉልበት ብክነት ያመጣል። ከዚህም አልፎ ለግልስቱ፣ ለሰባቱ፣ ለአስራ ሁለቱ፣ ለሠላሳው፣ ለአርባው፣ ለሰማንያው፣ ለመንፈቁ፣ ለዓመታቱ፣ ለሐውልቱ ወይም ለመቃብር ቤት ምረቃው ለተዝካሩ የሚወጣው ወጪ ያለ የሌለ የሚችንና የቤተሰብን ቅርስ የሚያሟጥጥ ነው። በዚህም ሰበብ የሙት ልጆች፣ አረጋውያን ተጧሪዎችና በአጠቃላይ የሟች ቤተሰቦች ያለመተዳደሪያ ይቀራሉ። ይህ ልማድ የሚከናወነው በቤተ ክርስቲያን ስም ቢሆንም እውነቱ ግን በጎበረተሰቡ ባለው ከማን አንሼ መንፈስ ተገፋፍቶ የሚፈጸም መሆኑ ይታወቃል። ከባለቤት በላይ፣ ከልጅ በላይ፣ ከወላጅ፣ በላይ ወይም ለነፍሱ ያልሆነ ... እየተባለ ያለ የሌለው ጥሪት እንዲሟጠጥ ከጎበረተሰቡ ግፊት ይደረጋል። ይህንን ግፊት የሚያደርጉት ደግሞ ያልተማሩና የባህል እስረኞች የሆኑ ሰዎች ናቸው። ግፊቱንም መቋቋም የማይችሉት እንዲሁ ያልተማሩ ሰዎች ናቸው። የሃይማኖት አባቶች እነዚህን ሰዎች እማእሰረ ባህል እግዚአብሐየር ይፍታ ሊሏቸው ይገባል። ምክንያቱም ግለሰቦቹ ይህንን የሚያደርጉት ሃይማኖታዊ ግዴታ እየመሰላቸው ነውና። በደስታም በኩል ያለው ብክነት ከዚሁ ያልተናነሰ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ችግር ተጠቂዎች ምእመናን ብቻ ሳይሆኑ ራሳቸው ካህናትም ጭምር ናቸው። እነሱም እንደቀሪው ጎበረተሰብ ቤተሰብ አላቸው። ባለቤት. ልጅ፣ ወላጅ አላቸው። ጎዘንና ደስታ ይፈራረቅባቸዋል። ስለዚህም ከፍ ሲል የተጠቀሱት ባህሎች በእነሱም ተፈጻሚ ይሆናሉ። ጉዳቱም ይልቁንም ለሃይማኖት አባቶች ድርብ ድርብርብ ነው። በመጀመሪያ እንደ ጎበረተሰቡ ይጎዳሉ። ቀጥሎ በተቋም ደረጃ ጉዳት ያገኛቸዋል። በሀገር ደረጃም እንዲሁ። ራሱ የምእመናን ጉዳት ለአባቶች ከባድ ጎዘን ነው።

ስለዚህ የሃይማኖት አባቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቅጥ እያጣ የመጣውን የደስታም ሆነ የኀዘን ብክነት ሊዋጉት ይገባል። ኋላ ቀር የሆነውንና ከጊዜ ወደ ጊዜ ቅጥ እያጣ በመጣው ከንቱ ልማድ ተገደው ያለ የሌለ ቅርሳቸውን አሟጠው አንዳንዱም ተበድረው ከአቅማቸው በላይ እየደገሱ መጋበዝ ጎጅ ባህል መሆኑን ለምእመናን ሊነገሯችና ሊገስጹዋቸውም ይገባል። ካህናት ልማዱ ምዕመናንን ለድህነት እየዳረገ እንደሆነ ሊረዱትና ሊዋጉት ይገባል። የምእመናን ድህነት የቤተ ክርስቲያናን ድህነት ነው። ደሀ አባላት ያሳት ቤተ ክርስቲያን ደሀ ናት።

በሌላ በኩል የኀብረተሰባችን መሪር የሞት ባህል የራሱን ሚና ይጫወታል። ምእመናን ቤተ ሰብ በሞት በሚለያቸው ጊዜ በጽኑ ኀዘን ስለሚዋጡ ያለ የሌለ ጥሪታቸውን አማጠው ለመጽናናት ይሞክራሉ። መጽናናት የሚችሉት ግን በትምህርት ነው። በክርስቲያን ትምህርት ትንሣኤ ሙታን ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢር አንዱ ነው። ስለዚህ የሃይማኖት አባቶች ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ ለምእመኖቻቸው ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን በማስተማር ኀዘናቸውን ሊቀርፉላቸው ይገባል።

ይህን የምለው የሃይማኖት አባቶች ከማንም በላይ ለኀብረተሰቡ ቅርብ ስለ ሆኑ ነው። በኀብረተሰቡ ደስታና ኀዘን ሲደርስ አስቀድመው ይጠራሉ፤ አቀድመው ይደርሳሉ፤ ምክር ይሰጣሉ። ምክራቸውም ተቀባይነት አለው። ልጅ ሲወለድ ፀበል እንዲረጩና ክርስትና እንዲያነሱ፣ ምርቃት ሲኖር በበዓሉ ላይ ተገኝተው ቡራኬ እንዲሰጡ፣ ጋብቻ ሲፈፀም ቀለበቱን እንዲባርኩ ወይም ተክሊል እንዲያደርሱ ካልሆነም ደግሞ በሰርጉ ሥነ ስርዓት ላይ ተገኝተው ጋብቻውን የአብርሃምና የሣራ ጋብቻ እንዲያደርገው አቡነ ዘበሰማያት እንዲያሳርጉ፣ ማኅበር እንዲባርኩ... መጋበዛቸው የተለመደ ነውና።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀሳፊውን ኤድስ የመዋጋት ዘመቻዋን አጠናክራ ልትቀጥል ይገባል።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታምሜ ነበር ጠይቃችሁኛል የሚለው ቃለ ወንጌል ከስድስቱ ቃላተ ወንጌል አንዱ እንደሆነ ታስተምራለች። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ከሁሉም በላይ የሕሙማንን ጭንቀት አዳምጧል። እውሮች አይተዋል። ደንቆሮዎች ሰምተዋል። ዲዳዎች ተናግረዋል። ለምጻሞች ነጽተዋል። ኅባጦች ቀንተዋል። አጋንንት ወጥተዋል። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የጌታዋን ፈለግ ተከትላ ማየት፣ መስማትና መናገር የተሳናቸውን፣ ለምጻሞችን፣ ኅባጦችንና አጋንንት ያደሩባቸውን ስትፈውስ መኖሯ የሚታወቅ ነው። ዛሬም በዘመነ ሳይንስ ወደ ሆስፒታል ከሚሄዱት ሕሙማን ይልቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱት እንደሚበልጡ በየቀኑ ይስተዋላል።

ቤተ ክርስቲያኗ ሕሙማንን በጸበልና ጸሎት ከመርዳት አልፋ በአሁኑ ጊዜ እንደ ሰደድ እሳት ሀገሪቱን እያዳረሳት ላለው የኤች አይ ቪ ኤድስ ጽሕፈት ቤት ከፍታ እየተንቀሳቀሰች መሆኗ ያስመሰግናታል። በሽታው እስከ አሁን በሰፊው እያጠቃ የነበረው ከተሞችን ነበር። በቅርብ ጊዜ ደግሞ በሽታው ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ እየሰረገና ሥር እየሰደደ እንደሆነ እየሰማን ነው። ለዚህ የሰደድ በሽታ በአፋጣኝ መስፋፋት

ምክንያት ከሆኑት ውስጥ ዋናዎቹ የንቃተ ኅሊና ችግርና ሥር የሰደደ ድህነት መሆኑ ይተወቃል። ከዚህ አንጻር የገጠሩ ሕዝብ ንቃተ ኅለና ከከተሜው ንቃተ ኅሊና ዝቅ ያለ ስለሆነ ድህነቱም ከከተሜው ድህነት የላቀ ስለሆነ አደጋው የከፋ ይሆናል።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊት እንደመሆኗ ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ የሚለውን ኢትዮጵያዊ ምሳሌያዊ አነጋገር ጠንቅቃ ታውቀዋለች። ቤተ ክርስቲያኗ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የተዘረጋ መዋቅር ያላት ከመሆኑም በላይ በገጠሩ ኅብረተሰብ ዘንድ ያላት ተደማጭነት ከፍ ያለ ነው። ስለዚህ ይህንን መዋቅሯንና ተደማጭነቷን ተጠቅማ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በሽታውን ልትቀድመውና ልትገታው ይገባል። በመጀመሪያ እሷ ራሷ ፍቅር አሳይታ ምእመናን ለበሽታው ተጠቂዎችም ፍቅርና እንክብካቤ እንዲያደርጉላቸው ልታስተምር ይገባል። ልቅ የግብረ ሥጋ ግኑኝነትና ሕገ ወጥ ጋብቻን መዋጋት ልትወስደው ከሚገባት እርምጃ ውስጥ አንዱና ዋናው ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጋብቻ ላይ የበለጠ መሥራት ይጠበቅባታል፡

ጋብቻ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የከበረ ነው። በሁለት ዖታዎች መካከል በእኩልነት የተመሠረተ የኮንትራት ውል ከመሆን አልፎ ሁለቱን ተጋቢዎች አንድ የሚያደርግ ምሥጢር ነው። ፈሪሳውያን ወደ ክርስቶስ ቀርበው «ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን» ብለው ቢጠይቁት ጌታም መልሶ «ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው። ስለዚህም ሰው እናትና አባቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ» ብሎ መለሰላቸው። እነሱም «እንኪያስ ሙሴ የፍቺን ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈቷት ስለምን አዘዘ?» ቢሉት «ሙሴስ ስለልባችሁ ጥንካሬ ሚስታችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንደዚህ አይደለም» ብሎ መለሰላቸው። ይህ ቃለ ወንጌል ክርስቲያናዊ ጋብቻ በሆነ ባልሆነው ምክንያት በቀላሉ የሚፈርስ አለመሆኑን ያሳያል። ሆኖም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ምሥጢረ ተክሊል በምእመናን ልብ በጥልቅ ለማስረጽ የቻለች አይመስልም። ጭራሽ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን መሆኑ የሚታወቅ አይመስለኝም። ምእመኖቿ በሆነ ባልሆነው ምክንያት ፍች ሲፈጽሙ ይታያሉ። ይህ ልማድ በየትኛዎችም ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት የሌለ ነው። ብዙ ሰዎች ይህ ልማድ የመጣው ከግራኝ ወረራ ወዲህ ነው ብለው ይናገራሉ። ሌላ ታሪካዊ ምክንያት ያለው ይመስለኛል።

በታሪክ እንደምናውቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ርእሶች ነገሥታቱ ነበሩ። ነገሥታቱ ደግሞ ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ሕግ አይጠብቁም ነበር። ለምሳሌ የእኛ ሀገር ነገሥታቱ የቀኝና የግራ እመቤት የሚሏቸውን ሁለት ሚስቶች በአንድ ጊዜ የማግባት ልማድ ነበራቸው። ይህም ልማድ ወደ ኅብረተ ሰቡ ወርዶ ለማስተዳደር አቅም ያለውና የሌለውም ሁሉ ሳይቀር ሁለትና ከዚያም በላይ ሚስት የማግባት ልማድ ዳበረ። ምሳሌዎቻቸውም የብሉይ ኪዳን ነገሥታት ነበሩ። ይህም ጋብቻ እንደ ቀላል ነገር እንዲቆጠርና በቀላሉ እንዲፈርስ በር የከፈተ ይመስለኛል። ቤተ ክርስቲያን ይህንን መጥፎ የጋብቻ ልማድ ለመዋጋት በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያደረገቸው እንቅስቃሴ ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል። በዚህ በኩል ከፍተኛ እንቅስቃሴ? ማድረጉ በታሪክ የተጠቀሰለት በዘመነ ዐምደ ጽዮን

መጥቶ የነበረው አቡነ ያዕቆብ የተባለ ጳጳስ ነው። አቡነ ያዕቆብ 12 መነኰሳት ንቡራነ እድ ብሎ በመሾም በሸዋና ደቡብ ኢትዮጵያ በማሰማራትና ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን ሌሎች መነኰሳት "ከዋክፍት: በሚል መጠሪያ ወደ ሰሜን አትዮጵያ በመላክ ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ተግቶ ሰርቷል። ከዚህ ስብከተ ወንጌልን የማስፋፋት ተልዕኮው በተጨማሪ ልዩ ልዩ ሞራላዊ ድክመቶችን ለማረም በሰፊው ተንቀሳቅሷል። ይህ እንቅስቃሴው ግን ከንጉሠ ነገሥቱ ከዐምደ ጽዮን ጋር አጋጨው። ንጉሠ ነገሥቱ እንጀራ እናቱን አግብቶ ስለነበር ጳጳሱ ከዚህ አድራጐቱ እንዲታቀብ አስጠነቀቀው። ንጉሠ ነገሥቱም ስላልተመለሰ ጳጳሱ ቁርባን ከለከለው። ሃሳቡን ብዙዎቹ መነኰሳት ተጋርተውታል። ሆኖም ዐምደ ጽዮን የሚመለስ አልሆነም። መነኰሳቱን ገርፎ ካጋዛቸው በኋላ ጳጳሱን ወደ ሀገሩ (ግብጽ) መለሰው።

ከዚያ ወዲህ እንደ አቡነ ያእቆብ ያለ ጠንካራ ጳጳስ ባለመነሣቱ ባህሉ ሳይታረም እስከ ዘመናችን ደረሰ። ይሁንና የጋብቻ መፍረስ ለቤተሰብአዊ መናጋትና መበታተን ምክንያት ከመሆን አልፎ በአሁኑ ጊዜ ሀገሪቱን እንደ ሰደድ እሳት እያዳረሳት ላለው የኤድስ በሽታ ዋና መንስኤ ሆኖ ታላቅ ጥፋት እያሰከተለ ይገኛል። ይህም ለልማታችን ታላቅ እንቅፋት ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጋብቻን ምሥጢርነት በማስተማር ይህን ኢክርስቲያናዊ የሆነ የጋብቻ ልማድ ልትዋጋውና ከሥር መሠረቱ ልታስተካክለው ይገባል። የጋብቻ ባህል መስተካከል ለቤተሰብና ማኅበረ ሰብ እንዲሁም ሀገር ግንባታና ልማት መሠረት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። ዘመቻው ጋብቻን በቀላሉ የማፍረስ ልምድ ባዳበረው በገጠሩ አካባቢ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ልማት የበለጠ ጠንክራ ልትንቀሳቀስ ይገባል።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ብራብ አበላችሁኝ፤ ብጠማ አጠጣችሁኝ፤ ብታረዝ አለበሳችሁኝ ያለውን ቃለ ወንጌል ለመፈጸም ስታደርገው የኖረችውና አሁንም በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን አማካኝነት እያደረገች ያለውን ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ከፍ ሲል ተመልክተናል። ሆኖም ኮሚሽኑ ከአመሠራረት ታሪኩም ሆነ ከእስትራቴጂ ፕላኑ አንጻር እንዲሁም አፈጻጸሙን ስናጤነው በአብዛኛው እየተንቀሳቀሰ ያለው በቁሳዊ ልማት ዙሪያ ነው። ዘእንበለ ሥጋ ኢትቀውም ነፍስ ተብሏልና ቤተ ክርስቲያን በቁሳዊ ልማት ዙሪያ እያደረገች ያለው እንቅስቃሴ ያስመሰግናታል። ግን ደግሞ የነፍስ ረሃብ፣ የነፍስ ጥማትና የነፍስ ርዛት ከሥጋ ረሃብና ጥማት ያላነሰ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። የተራበና የተጠማ ደግሞ ወዶም ሆነ በግድ ቅልውጥ መሄዱ አይቀርም። በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ አንጣቦ ያለው ትልቁ አደጋም ይሄው ነው። የምእመናን ፍልሰትና ስደት። በአሁኑ ጊዜ በየቀኑ ከቤተ ክርስቲያኗ ወደ ተለያዩ የእምነት ተቋማት እየፈለሰ ያለው አማኝ ቁጥር አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን አስደንጋጭም ነው። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ አስደንጋጭ አደጋ ቅድሚያ ሰጥታ መንቀሳቀስ ይገባታል። ምእመናን ፈልሰው ከማለቃቸው በፊት የነደላቸውን ልታሚላላቸው የተራቡትንና የተጠሙትን ቃለ እግዚአብሔር ልታቀርብላቸው ይገባል። ቤተ ክርስቲያኗ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ መምሪያ የተባለ ክፍል አቋቁማ ከተለያዩ የአፍሪቃ ሀገሮች ማለትም ከሱዳን፣ ከሶማሊያ፣ ከዛየር፣ ከኤርትራና እንዲሁም ከየመን የመጡ ስደተኞችን መርዳቷን ተመልክተናል። ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ግን የራሷን ስደተኞችና ከስደት ተመላሾች የሚያቋቁም መምሪያ ያስፈልጋታል። በወንጌል "መቅድመ

ጎሱ መንግሥቶ ወጽድቆ ወዝ ኩሉ ይትዌሰከክሙ"። (አስቀድማችሁ መንግሥቱንና ጽድቁን ሻቱ። የቀረውም ሁሉ ይጨመርላችኋል) ተብሎ ተጽፏል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ከሥጋዊው ስደት ይልቅ ለመንፈሳዊው ስደት ከቁሳዊው ልማት ይልቅ ለመንፈሳዊው ልማት ቅድሚያ ሰጥታ ልትንቀሳቀስ ይገባል። ይህንን ካላደረገች ለጴጥሮስ "ዕቀብአ አባግእየ ዕቀብአ መሐስእየ" (በጎቼን ጠብቅ፤ ጠቦቶቼን ጠብቅ) ተብሎ የተሰጠውን አደራ አለመወጣት ይሆናል። በጎችንና ጠቦቶችን ለአውሬ አስረክቦ የተመለሰ እረኛ ዋጋው ምን እንደሚሆን ለማንም ግልጽ ይመስለኛል።

እንደ ኢትዮጵያ ላለ ደሀ ሀገር የቁሳዊ ልማት አንገብጋቢነት የማያጠያይቅ ቢሆንም በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን ከቁሳዊው ልማት የበለጠ ለመንፈሳዊው ልማት ትኩረት ልትሠጥ ይገባል። መንፈሳዊ ልማት ቁሳዊ ልማትን ያመጣል። በመሆኑም ከቁሳዊው ልማት ጎን ለጎን የወንጌል ልማት ሰትራቴጂ ቀርጻ መንቀሳቀስ ይገባታል። በአንድ በኩል የወንጌልን ልማት እየሰበከች በአንጻሩም የልማት ወንጌልን ተግታ ማስፋፋት ይገባታል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የ2020 መንፈሳዊና ቁሳዊ ልማት ግቡን እንዲመታ የካህናት ስልጠናን ቁልፍ ተግባር አድርጋ መንቀሳቀስ አለባት።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የ2020 መንፈሳዊና ቁሳዊ ልማት ግቡን ይመታ ዘንድ ዛሬውኑ ቀሚሷን ሰብሰብ፣ ቀበቶዋን ጠበቅ አድርጋ ልንቀሳቀስ ይገባል። ለዚህም መፍትሄውና ቁልፉ የካህናት ትምህርት፣ የካህናት ልማትና የካህናት አቅም ግንባታ ነው።

አብዛኞቻችን እንደምናውቀው የካህናቶቻችን ሥልጠና ዜማ ማለትም ጾመ ድጓ፣ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ፣ መዋስዕት፣ አቋቋም፣ ቅኔ፣ ቅዳሴና የመሳሰሉት ናቸው። የተጠቀሱት ትምህርቶች ጠቀሜታ ለቅዳሴና ለስብሐተ እግዚአብሔር ነው። ትምህርቶቹ ሀገር በቀል ስለሆኑ የሚያኮሩንና ለምእመናኖቻችንም ጆሮ የማይጠገቡ ናቸው። ይሁን እንጅ ለቅዳሴና ለስብሐተ እግዚአብሔር አገልግሎት ተብለው ከቅዱሳት መጻሕፍት ተውጣጥተው የተቀነባበሩ በመሆናቸው ሌላው ቀርቶ ከዋናው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንኳን ብዙም አያስተዋውቁም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በቀጥታ የሚያስተዋውቀው ትምህርት ትርጓሜ መጻሕፈት የተባለው የትምህርት ዐይነት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በዚህ ሙያ የሰለጠኑ ብዙ ካህናት የሉንም። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህም ሥልጠናዎቹ ከ15-20 ዓመታትና ከዚያም በላይ የሚጠይቁ ናቸው። ይህ ሁሉ ጊዜ ተወስዶ ከመዘመርና መቀደስ ውጭ ሌላ ክሂሎቶችን ለምሳሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና የስብከት ክሂሎትን ወይም የቤተ ክርስቲያን ታሪክን ወይንም ዘመናዊ ትምህርትን አያካትቱም። ካህኑ 15 እና 20 ዓመታትን በባህል ትምህርት ስለሚያሳልፍ ዘመናዊ ትምህርት ለመቀጠል ጊዜ አይበቃውም። ይህም ባለመሆኑ (ሥልጠናው ሀገር በቀል ብቻ በመሆኑ) ለዘመናዊ ትምህርትና ለዓለም አቀፍ እይታ እንዲሁም ለሳይንሳዊ አስተሳሰብ ባዕድ ያደርገዋል። በልማድና በሃይማኖት፣ በባህልና በሃይማኖት፣ በሳይንስና በሃይማኖት ያሉትን ግኑኝነቶችና ልዩነቶች ለመረዳት ያዳግተዋል። ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ተሞክሮ ለመማር እድሉ አይኖረውም። የማያዉቁት ሀገር አይናፍቅም እንዲሉ የተሻለ መንፈሳዊና ቁሳዊ ልማት አይመኝም። ለዚህ ሁለት ዐይነት መፍትሄዎችን መጠቆም እወዳለሁ። አንደኛው መፍትሄ ጊዜአዊ ነው።

ይህም ላሉት ካህናት ተከታታይና ቀጣይነት ያለው ስልጠና መስጠት ሲሆን ይህም በርቀት ትምህርት ሳይቀር ሊታገዝ ይገባል። ሁለተኛው መፍትሄ ወጣት ካህናትን በዘመናዊ መልክ ማሰልጠን ነው። ኮሚሽኑ ባለፉት 35 ዓመታት በዚህ ዙሪያ ትኩረት ሰጥቶ ተንቀሳቅሶ ቢሆን ኑሮ ፕሮጀክቱ አገር አቀፍ፣ ውጤቱም ፍሬያማ ይሆን ነበር። አበው ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራም እንዲሉ ለወደፊቱ መንፈሳዊና ሥጋዊ ልማታችን እንዲሳካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወጣት ካህናትን ማሰልጠኑን በሠፊው ልታስብበት ይገባል።

የወደፊቱ ካህን ለዘመናዊ ትምህርትና ስልታዊ ለሆኑ ሌሎች የትምህርተ መለኮት ሥልጠናዎች በቂ ጊዜ እንዲኖረው የባህል ትምህርቱን በአጭር ጊዜ ለማጠቃለል የሚያስችል አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ባህላዊውንና ስልታዊ የሆኑ ሌሎች የትምህርተ መለኮት ሥልጠናዎችን የወሰደ ካህን በአንድ በኩል ለባህል ትምህርቱ እንግዳ አይሆንም። የባህል ትምህርቱ ተቆርቋሪ በሆኑት የኢትዮጵየ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዘንድ ከበሬታና ተቀባይነት ይኖረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ስልታዊ የሆነውን የትምህርተ መለኮት ሥልጠና ስለሚወስድ ዓለም አቀፋዊ እይታና ሳይንሳዊና ሃይማኖታዊ አመለካከት ይኖረዋል፤ ከዘመናዊው ትውልድ ጋር በቀላሉ ይግባባል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የ2020 ልማትን ስታስብ ከሁሉም በላይ የካህናትን ሥልጠና አጽንኦት ሰጥታ መንቀሳቀስ ይኖርባታል።

እርግጥ ነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከ1930ዎቹ ጀምሮ የተለያዩ ማሰልጠኛዎችን ለማቋቋም ያደረገችው ሙከራ ይታወሳል። እዚህ ላይ የቀድሞው ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት፣ የቀድሞው ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ የቀድሞው ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ቤትና የቀድሞው የዝዋይ ካህናት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች ይጠቀሳሉ (ከ1961-1966 የነበረው)። ሆኖም ማሰልጠኛዎቹ በአብዛኛው ውጤታማ አልነበሩም። በመጀመሪያ ማሰልጠኛዎቹ በመምህራንና በቆሳቁስ የተሟሉ አልነበሩም። እኛ በሰለጠንበት ጊዜ የነበሩት ፓትረያርክ ሊጎበኙን በመጡበት ጊዜ ብቁ መምህራንና የትምህርት መሳሪያ የሌለን መሆኑን ስናመለክታቸው የሰጡን መልስ "እናንተ ራሳችሁ ሊቃውንት ናችሁ። እዚህ ያሰባሰብናችሁ እርስ በርሳችሁ እንድትሳሳሉ ነው" የሚል እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ከውጭ ሀገር ስልጠናየ በኋላ አባባሉ ጉድለት እንደነበረው ተረድቻለሁ። ምንም ያህል ሥልጠና አይሰጥም ነበር ለማለት እችላለሁ።

በተመሳሳይ በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗ ሁለት ኮሌጆችና እንድ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አሏት። ይሄውም 1. የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ ትግራይ መቀሌ የሚገኘው የመንፈሳዊ ኮሌጅና የሰዋስው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ናቸው። ሆኖም ማሰልጠኛዎቹ ምን ያህል በሰው ጎይልና በቆሳቁስ እንደተሟሉ በቂ መረጃ ባይኖረኝም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ ኮለጆችንና ማሰልጠኛዎችን ስትከፍት ከሁሉ አስቀድሞ ብቁ መምህራንን ማዘጋጀትና የትምህርት መሳሪያዎችንም ማሟላት እንዳለባት ማሳሰብ እወዳለሁ። ያ ሳይሆን ቀርቶ የባህል ተማሪዎቿን በባህል መምህራን ብታሰለጥን ግን ያው የባህል ትምህርት ቤት እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊው ችግር ካህናትን በተገቢው ደረጃ ለማሰልጠን አለመቻል ሲሆን ሁለተኛው ችግር የሰለጠኑትንም ቢሆን ለመቅጠር አለመቻል ነበር። ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች ውሰጥ በተነጻጻሪነት የተሻለ ሥልጠና ያገኙ የነበሩት የቀድሞው ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች ሲሆኑ ነገር ግን ተመራቂዎቹ ቤተ ክህነት የመቀጠር እድል አልነበራቸውም። በተነጻጻሪ ከሁሉም ማሰልጠኛዎች የታሻለ የመቀጠር እድል የነበራቸው የቀድሞው የዝዋይ ካህናት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲሆኑ ለዚህም ዋናው ምክንያት የት/ቤቱ መሥራች ፓትረያርኩ ራሳቸው መሆናቸውና የት/ቤቱ መዋቅርም ሰልጣኞቹ ሌላ የቅጥር እድል እንዳይኖራቸው የሚያስር ስለ ነበር ነው።

በዚያን ጊዜ የድሮዎቹ ሠልጣኞች ቤተ ክህነት እንዳይቀጠሩ ዋና እንቅፋት የነበረው የድሮው ቤተክህነት ቢሮክራሲ ነበር። የድሮውን ቤተ ክህነት ቢሮክራሲ ያንቀሳቅሱ የነበሩት ግለሰቦች ምንም አይነት የባህል ትምህርትም ሆነ ሥልጠና የሌላቸው በዘመድ አዝማድ በተላላኪነትና በጸሐፊነት ተቀጥረውአድገው ቢሮክራሲውን ያሽከረክሩ የነበሩ ግለሰቦች ነበሩ። እነዚህ ግለሰቦች የባህል ትምህርት ምሁራኑንም ሆነ ሰልጣኞቹን ቦታችንን ይወስዳሉ፣ ያፈናቅሉናል፣ በስልጣናችንና በእንጀራችን ይመጡብናል በሚል ሥጋት ቤተ ክህነት እንዳይቀጠሩ ከፍተኛ ትግል ያደርጉ ነበር። ወደ አባቶች እየገቡ ምሀራኑን ትዕቢተኛ ነው። ለአባታችን አይታዘዝም... ሰልጣኞችን ደግሞ ፀረ ማርያም ነው። መናፍቅ ነው። ለእሱ የሚሆን በጀት ቤተ ክርስቲያኗ የላትም.... በማለት በቀላሉ ማሳመን ይችሉ ነበር። አልፎ አልፎ አስገዳጅ ምክንያት ተፈጥሮ ከተቀጠሩም በተቻለ መጠን በዝቅተኛ ደመወዝ እንዲቀጠሩ፣ ስብከተ ወንጌል ወደ አልደረሰበት ይሂዱ በሚል ማሳሳቻ ወደ ጠረፍ እንዲወረወሩ በማድረግና ቀጥሎም እርስ በርስ በመደዋወልና በመላላክ ከቦታ ቦታ እንደኳስ በማጓን አበሳጭተው ሥራቸውን እንዲተውና ቤቱን እንዲጠሉ በማድረግ ተግተው ሠርተዋል። ጥረታቸውም ተሳክቶላቸው እነሱ እስከ መጨረሻ ዘመናቸው ሲቀጥሉ ምሁራኑንና ሠልጣኞችን ባክነው ቀርተዋል። በእኔ እምነት ለቤተ ክርስቲያኗ ወደ ፊት አለመራመድ ምክንያት ከሆኑት ውሰጥ ይህ ዋናው ይመስለኛል።

በቂ መረጃ ባይኖረኝም በአሁኑ ጊዜ ያለው የቤተ ክህነት መስተዳድር ይህንን ለውጦታል የሚል ተስፋ አለኝ። ይህን በተጨባጭ ለመናገር በጠቅላይ ቤተ ክህነት፣ በየሀገረ ስብከቶችና በታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት በተለይም በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ተራድኦ ኮሚሽን ሥር ካሉት ሠራተኞች መካከል ምን ያህሉ ካህናት፣ ምን ያህሉ ባህላዊው የቤተ ክህነት ትምህርት ያላቸው፣ ምን ያህሉ በከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት የሰለጠኑና አልፎ ተርፎም ምን ያህሉ ኦርቶዶክሳውያን መሆናቸውን ማጥናት ያስፈልጋል። ይህ ተለውጦ ከሆነ ቤተ ክርስቲያኗ ለ2020 ልማት ዝግጁ ናት ማለት ነው።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የአመለካከት ለውጥ ልታደርግ ይገባል።

እዚህ ላይ የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናትና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት የተለያየ አመለካከት ያላቸው መሆኑን መጥቀስ ያስፈልጋል። ዘርዘር አድርገን እንመልከተው።

ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ጥንታዊው የግሪክ ፍልስፍናና ሳይንስ ከፍተኛ ደረጃ በደረሱበት ዘመን ነበር። ጥንታውያን የግሪክ ፈላስፎች እውነትን ፍለጋና የሰውን ልጅ ዘላቂ ሕይወት ፈር ለማስያዝ ሌት ከቀን በሚደክሙበት በዚያን ዘመን በጆሮአችን የሰማነውን፣ በዐይናችም ያየነውንና በእጃችንንም የዳሰስነውን እውነት እንነግራችኋለን (1 ዮሐ.1፣1) የሚል አዲስ ትምህርት የያዙ ሃጆች ከምሥራቅ ሀገር ወደ ግሪክ ብቅ አሉ። ትምህርቱም የናዝሬቱ ኢየሱስ ከተቀበረ ከሦስት ቀናት በኋላ ከመቃብር መነሳቱን፣ በግልጽ እያዩት ወደ ሰማይ ማረጉንና በእሱም አማካኝነት እውነት መገለጹን የሚሰብክ ነበር። ለብዙ ዘመናት እውነትን ፍለጋ ሲባዝኑ የኖሩ ግሪኮች እንደተለመደው አዲስ ዜና ለመስማት ሲጓጉ ክርስትናና ፍልስፍና ግሪክ ውስጥ ተፋጠጡ። ይህንን ተከትሎ ፈላስፎች ክርስቲያን መሆን ሲጀምሩ በአንጻሩ ክርስቲያ ኖችም መፈላሰፍ ያዙ። ከዚህ በተቃራኒ የክርስትናንና ፍልስፍናን ማምታታት (በእነሱ አስተሳሰብ) የተቃወሙ ክርስቲያኖች ተነስተው ኢሩሳሌም ከአቴን ጋር፣ ጨለማስ ከብርሃን ጋር ምን ግኙኝነት አለው በሚል መፈክር ክርስትንና ፍልስፍናን መቀላቀል እንዲቀር ታገሉ። በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን እራሷን ከግሪክ ፍልስፍና ሳይንስ እንድታርቅ ተወሰነ። ሁሉንም እውነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ለማግኘት ታሰበ። የፍልስፍና መጻሕፍት ተቃጠሉ። ፍልስፍና የሚያነቡ ክርስቲያኖች በመናፍቅነት ተወገዙ።

የፍልስፍናው ክርክር በዚህ እልባት ሲያገኝ ቤተ ክርስቲያን በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም መታመስ ጀመረች። በዚሁ ሳቢያ በተለይም በ451 ዓ.ም. የተከሰተው የነገረ መለኮት ትምህርት ልዩነት ቤተ ክርስቲያንን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሁለት ከፈላት። በምሥራቅና በምዕራብ ተከፈለች። የምሥራቁን ክፍል የሚወክሉት ግብጽ፣ ኢትዮጵያ፣ ሶርያ፣ህንድ፣ አርመን ኢየሩሳሌም ሲሆኑ የአውሮፓና የቀሩት የሰሜን አፍሪቃ ሀገሮች የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ተባሉ። የግሪክና መሰሎቿም ትምህርተ መለኮት ከምዕራባውያኑ ጋር ሆነ።

ልዩነቱ ከነገረ መለኮት ትምህርት በተጨማሪ ፖለቲካዊ ገጽታም ነበረው። ከኢትዮጵያና ህንድ በቀር ሌሎቹ ሀገሮች የቢዛንታይን (ግሪክ) መንግሥት ግዛቶች ነበሩ። ስለሆነም የተጠቀሱት ቅኝ ግዛት ሀገሮች የነገረ መለኮት ትምህርቱን አስታከው ፖለቲካዊ ነጻነት ለማግኘት ታገሉ። በአንጻሩ የቢዛንታይን መንግሥት የራሱን ትምህርተ መለኮትና ግዛት በተጠቀሱት ሀገሮች በጎይል ለመጫን የጎይል ርምጃ በመውሰዱ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ምእመናን፣ ካህናትና ጳጳሳት ተሰዉ። ግጭቱም ከ451 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቀጠለ። በዚሁ ክፍተት እስልምና ተነሳ። ለ300 ዓመታት ያህል የዘለቀው ጦርነት የዘገነናቸው ምሥራቃውን እስልምናን ከክርስቲያን ወንድሞቻቸው (ወይም ጠላቶቻቸው) የሚታደግ ቤዛ አድርገው ስለተመለከቱት የተሳሳተ ድጋፍ ሰጡ። እስልምናም ይህንኑ አጋጣሚ ተጠቅሞ በአጭር ጊዜ ግብጽን፣ ሶርያንና ኢየረሳሌምን እንዲሁም ሌሎችን የሰሜን አፍሪካ ክርስቲያኖች ተቆጣጠረ። ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉ የተጠቀሱት ሀገሮች ከቢዛንታይን መንግሥት ነፂ ሲወጡ

በእስልምና መዳፍ ሥር ወደቁ። ቀደም ሲል ከእስልምና መሪዎች የተገባላቸው ሃይማኖትን በነጻ የመለማመድ ተስፋ ቀርቶ በልዩ ልዩ ተጽእኖ እስልምናን እንዲቀበሉ ተገደዱ። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ያሏቸው አማኞች ቁጥር በእጅጉ ተመናምኗል።

ቤተ ክርስቲያን በምሥራቅና ምዕራብ ከተከፈለች በኋላ በሚቀጥሉት 1500 ዓመታት ሁሉም (አብያተ ክርስቲያናት) የየራሳቸውን አቅጣጫ ይዘው ተጓዙ። የአመለካከታቸው ልዩነት በዚያው ልክ እየሰፋ ሄደ። ለምሳሌ የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ቀደም ሲል የፍልስፍና ትምህርት ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን እንዲወጣ በጋራ የተወሰነውን ወደ ጎን በመተው ፍልስፍና ዋና የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዲሆን ደነገጉ። ቀሳውስቶቻቸውም ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ፍልስፍናን አነበቡ። የሚገርመው ብዙዎቹ ንጹሓን ፈላስፎች ሆነው ሳለ በፍልስፍናቸው ቅዱስ እስከ መባል መድረሳቸው ለፍልስፍና የተሰጠውን ክብደት በግልጽ ያሳል። ስለዚህም ፍልስፍና በምዕራባውያን ቀሳውስት ተጠምቆ ክርስቲያን ሆነ። ክርስትናም ቀስ በቀስ ማተቡን ቆርጦ የአሕዛብ ፍልስፍና ሆነ። አላማው ፍልስፍናን የክርስትና መሳሪያ ለማድረግ ነበር። አበው የሰማዩን በመጽሐፍ፣ የምድሩን በአፍ እንዲሉ ምዕራባውያን የሰማዩን በመጽሐፍ ቅዱስ፣ የምድሩን በመጽሐፈ አፍላጦን ወሶቅራጥስ ለመመርመር ተጉ። ይህም ሁለት ዐይና እንዲሆኑ ረዳቸው።

የምዕራብ ካሕናት ከፍልስፍና ትምህርት በተጨማሪ ከመስቀል ጦርነት ብዙ ስለተማሩ ከዓለማዊ አመለካከት አንጻር የእውቀት አድማሳቸው እየሰፋ ሄደ። ስለሆነም ያለፈውን ታሪካቸውንና ባህላቸውን እየመረመሩና እየዳሰሱ ያለመሰልቸት ተሐድሶ ስለአደረጉ (ቤተ ክርስቲያናቸውን በጊዜው ማደራጀት) ከቀን ወደ ቀን ከዓመት ወደ ዓመት እያደጉ ሄዱ። ኮሌጆችንና ዩኒቨርስቲዎችን በመክፈት የሀገራቸው የትምህርት ማዕከሎችና ቁንጮች ለመሆን በቁ። ከዚህም ጋር የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ለቁሳዊ ልማት ትኩረት ይሰጡ ነበር። የዚያን ጊዜው ምዕራብ ጥሮ ግሮ የሚኖርበት እንጅ እንደ ምሥራቁ ክፍል ፀሐይ እየሞቁ የሚኖርበት አካባቢ አልነበረም። ይህም አስገዳጅ ሁኔታ አብያተ ክርስቲያናቱ በልማት ሥራ እንዲተጉ ገፋፋቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የታሪክ ሂደት ከምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት የታሪክ ሂደት የተለየ ነው። ምሥራቃውያን ከሁሉ አስቀድሞ ለአበው ትምህርትና ውሳኔ ታማኞች ናቸው። በመሆኑም ቀደም ሲል ፍልስፍናና ዓለማዊ አስተሳሰብ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን እንዲወጣ በተወሰነው ድንጋጌ ፀንተው ቀጥለዋል። ስለዚህም የምዕራባውያን ዝንባሌ ፍልስፍና፣ የምሥቃውያን ዝንባሌ ብሕትውና፣ የምዕራባውያን ዝንባሌ ስብከት፣ የምሥራቃውያን ዝንባሌ ማኅሌት፣ የምዕራባውያን ዝንባሌ ልማት የምሥቃውያን ዝንባሌ ጾም፣ ጸሎትና ብቃት እየሆነ ሄደ። ስለዚህ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የሚደነቁት ከቁሳዊ ልማታቸው ይልቅ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማለትም ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ቅዳሴ ማኅሌት... ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትመደበው ከምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ነው። ኢትዮጵያ በመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በሥነ ልቡናና በደምም የምትዛመደው

ከምሥራቃውያን ጋር ነው። ከዚህም ሌላ ከቢዛንታይን መንግሥት ጦርነት እየሸሹ በሃይማኖትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ወደምትመስላቸው ሀገራችን የጎረፉት የሶርያና ግብጽ መነኮሳት ገዳማትን በመመሥረትና ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተርጎም የሕዝባችንን ሥነ ልቡና በመልካቸው በመቅረጻቸው የካሕናቶቻች ንና የሕዝባችን አስተሳሰብ ወደ ጥልቅ መንፈሳዊነት አዘነበለ። የግእዝ ሥነ ጽሑፎቻችን ሁሉ ይህንን እውነት አጉልተው ያሳያሉ። ለምሳሌ አንድ የቅዱስ ያሬድን መዝሙር እንጥቀስ። "አጎውየ ጎድግዎ ወመንንዎ ለዝንቱ ዓለም። ዓለሙኒ ጎላፊ፣ ንብረቱኒ ጎላፊ፣ እስመ ኩሉ ጎላፊ ውእቱ።" (ወንድሞቼ ይህንን ዓለም ተውት። ናቁትም። ዓለሙም፣ ንብረቱም፣ ሁሉም ጎላፊ ነውና።) ሁላችንም (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያደግን ደቀ መዛሙርት) ይህንን የቅዱስ ያሬድ መዝሙር እያዜምን ነው ያደግነው። ድምጽ ያለንም የሌለንም። ቅዱስ ያሬድ ይህንን መዝሙር ከመጽሐፍ ቅዱስ መጥቀሱ ቢታወቅም በዜማ ይልቁንም በአራራ ዜማ በማቀናበሩ ትምህርቱ የበለጠ እንዲሰርጽና አይረሳም እንዲሆን አድርጎታል። ይህንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል በመከተል ኢትዮጵያውያን ባሕታውያን አይደለም የተመጣጠነ ምግብ ቀርቶ እህልና ውሃ ሳይቀር ትተው በሥርና ቅጠላቅጠል ዘመናቸውን ገፍተዋል። በዘመነ ሐዋርያት እንኳን የማይታወቅ የተለየ ባህል ነበር። በመሆኑም ይህ ገድላቸው በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ምሳሌ የሌለውና የብቃት ደረጃውም ከፍተኛ እንደ ነበር እናውቃለን። በአንጻሩ ሀገራችን የተቃኘቸው ከእነዚሁ ባሕታውያንና ገዳማት ሕይወት በመሆኑ ለቁሳዊ ልማትና እድገት የነበረው አመለካከት ዝቅተኛ እንደነበር ግልጽ ነው። እርግጥ በዚያን ዘመን የሕዝቡ ቁጥር አንስተኛ፣ ሀገሪቱ የነበራትም የደን ሀብት ከፍተኛ፣ የአየር ንብረቱ ጤነኛ ስለነበር ለዓለማዊ ሀብትና ንብረት መጨነቅ አላስፈለገም ይሆናል። አሁን ግን የሕዝብ ቁጥር መጨመርንና የአየር ፀባይ መለዋወጥን ተከትሎ የድህነቱ መጠን እያደገ መጥቷል። ከማደግ አልፎ ጉዳዩ በሕይወት የመኖርና አለመኖር ጥያቄ እየሆነ መጥቷል። ይህም የልማትን አስገዳጅነት በግልጽ የሚያሳይ ነው።

በሌላ በኩል ልማት ካልመጣ የኢኮኖሚ ጥገኝነት ይመጣል። የኢኮኖሚ ጥገኝነትም የሃይማኖት ጥገኝነትን ያስከትላል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሓይማኖት ነጻነቷን ለማረጋገጥ ስትል ለኢኮኖሚ ነጻነትም ተግታ መሥራት ይኖርባታል። ለዚህም የአመለካከት ለውጥ ማድረግ ያስፈልጋል። መደረግ ያለበትን የአመለካከት ለውጥም ቀጥሎ ለመዳሰስ ይሞከራል።

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከምስራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ናት። በመሆኑም ፍልስፍናና ሳይንስ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን እንዲወጡ በአበው የተወሰነውን መሠረት በማድረግ እስከ አሁን ከፍልስፍናና ሳይንስ ራሷን አግልላ ቆይታለች። ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ይህን አመለካከታቸውን አስተካክለዋል። ሳይንስን ማወቅ ሌላ ሳይሆን ተፈጥሮን ሕግ መረዳት ነው። የተፈጥሮን ሕግ በጥንቃቄ መረዳትና በዚሁ መኖርም ቃለ እግዚአብሔርን አውቆ በውስጡ የመኖርን ያህል ጠቃሚ ነው። ስለዚህ ካህናቶቻችን ስለሳይንስና ፍልስፍና እንዲሁም ስለቁሳዊ ልማት ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል።

ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን፣ በሕፃናት አስተዳደግና በማኅበረ ቅዱሳን አማካኝነት የተለያዩ የልማት ሥራዎችን እያንቀሳቀሰች እንደሆነ ከፍ ሲል ተመልክተናል። ከተጠቀሱት ክፍሎች ውጭ በሰበካ ጉባኤ በትምህርት ዘርፍና በቅርስ ጥበቃ.. አማካኝነት ሌሎች የልማት ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ይታወቃል። ሆኖም ከቤተ ክርስቲያኗ ከዚህ በላይ ይጠበቃል፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ የትምህርት ዋና ማዕከል ሆና እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ማገልገሏ ቀደም ሲል ተገልጹዋል። ዐፄ ሚኒሊክ ከመቶ ዓመት በፊት የምኒስትሮች ምክር ቤት ሲያቋቁሙ የትምህርት ሚንስነርነቱ ቦታ ሰው አልተመደበበትም ነበር። ይህም የሆነው በወቅቱ በተነሚሪ ንቁ የበሩት ግብጻዊው አቡነ ማቴዎስ የትምህርት ሚኒስነርነቱ ለቤተ ክህነት ይገባል በማለታቸው እንደ ነበር ይተረካል። የዳግማዊ ምኒሊክ ት/ቤት ሲከፈትም የመጀመሪያዎቹ አስተማሪዎች ከግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የመጡ መምህራን ነበሩ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለዘመኑ ትምህርት እንግዳ ስለነበረች የታሰበው አልሆነም። የሚገርመው ላለፈው ምዕት ኣመት ከዘመኑ ትምህርት ራስዋን እንዳገለለች መቀጠሏ ነው። ይህም በጅጉ ጐድቷታል። ሌሎቹ ሚሲዮናውያን ተከታዮቻቸውን በዘመናዊ ትምህርት ሲያሰለጥኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ያለ ሥልጠና ቀሩ። ውጤቱም ምን እንደሆነ ግልጽ ነው። ቤተ ክርስቲያኗ በአዲስ አበባ አንዳንድ ጥቂት ዘመናዊ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች እንዳሏት ቢታወቅም ካላት የትምህርት ታሪክ አንጻር ሲታይ አበረታች አይደለም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በነበራት ተሰሚነት ከመንግሥት ጋር ተባብራ በትምህርት መስክ ተሰልፋ ቢሆን ኑሮ የሀገራችን የትምህርት ሽፋን ከአሁኑ በብዙ እጥፍ የበለጠ ይሆን እንደነበር መገመት ይቻላል። አሁንም ቤተ ክርስቲያን ሰዎቿን እያሰለጠነች በመዋዕለ ሕጻናትና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሰፊው ልትሳተፍ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ልትሳተፍበት የሚገባ የልማት መስክ ከሁሉም በላይ ትምህርት ነው።

ሌላው መረሳት የሌለበት የአብነት ትምህርት ቤት ጉዳይ ነው። እንደ ትርጓሜ መጻሕፍት፣ ቁም ዜማ፣ ቅዳሴ፣ቅኔ፣ አቋቋምና ዝማሬ መዋስዕት ያሉ ት/ ቤቶች በተለምዶ የአብነት ትምህርት ቤቶች በመባል ይታወቃሉ። ምንም እንኳን እንደ ተርጓሜ መጻሕፍት ያሉ ትምህርት ቤቶች እየከሰሙ መምጣተቸው ግልጽ ቢሆን ዛሬም በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ የቁም ዜማ፣ የቅዳሴ፣የቅኔ፣ የአቋቋምና የዝማሬ መዋስዕት ተማሪዎች መኖራቸው ይታወቃል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ከአኗኗር ስልታቸውም ሆነ ከስርዓተ ትምህርቱ አንጻር ሲታዩ ከሺህ ዓመት በፊት በነበሩበት ይዞታ ነው ያሉት። በእውነቱ አረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ያሳዝናሉ። ስለዚህ የአኗኗር ስልቱም ሆነ ሥርዓተ ትምህርቱን ለመለወጥ ሙከራ ቢደረግ መልካም ነው። ለልማታችን አጋዥ ነው።

የገዳማቱ ጉዳይም እንዲሁ አሳሳቢ ነው። የመሬት አዋጅ ብዙ ገዳማትን ያለ ምንም ይዞታ አስቀርቷቸዋል። በመሆኑም የሚያርሱት መሬት በማጣት አረጋውያንንና እጓለ ማውታዎችን የመንከባከብ ባህል የነበራቸው ብዙ ገዳማት ተፈተዋል። አያያዙ ከታወቀበት ገዳማት ለልማት ምቹ ነበሩ። ስልጠና

ካገኙና ልማት ከተቋቋመላቸው ከራሳቸው አልፈው ሌሎችንም የመርዳት ባህላቸውን ሊያድሱ ይችላሉ። ከዚህም በላይ ገዳማት የስልጠና ማዕከላትና የቤተ ክርሰርስቲያን መሪዎች መመልመያ ማእከል ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉና ይታሰብበት እላለሁ።

የአብነት ትምህርት ቤቶችንና ገዳማትን በመርዳት በኩል ማኅበረ ቅዱሳን እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ አርኪ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ማኅበሩ ለዚሁ አላማ በመደበው 1000000 የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ቅዱሳት መካናት ራሳቸውን ችለው ለማኅበረሰቡ እድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል፣ በውስጣቸው የሚገኙ ንዋያተ ቅድሳት መጻሕፍትና የተለያዩ ቅርሶች ባሉበት ይዞታ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግናየአብነት ትምህርት ቤቶችም ትውፊታዊ ሥርዓታቸውንን ጠብቀውና ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በመርዳት ላይ እንደሆነ ተረድቻለሁ። እንቅስቀሴውም መንፈሳዊ ጥበብና ብልሃትን የተሞላ በመሆኑ ረክቻለሁ።

ቤተ ክርስቲያን ልታስብበት የሚገባ ሌላ ዐቢይ ጉዳይ የቅርስ ጉዳይ ነው። ምስጋና ይገውባቸውና የቀደሙት አባቶቻችንና ነገሥታት የተውልን የቅርስ ሀብት የማንነታችን መገለጫዎችና መኩሪያዎቻችን ሆነዋል። አብዛኞቹ ቅርሶች ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች ናቸው። የጥንት አባቶቻችን ጠንካሮችና ችግርም የማይፈታቸው ስለነበሩ ከወረራና ዘረፋ የተረፉተን በርካታ ቅርሶች ጠብቀውና ተንከባክበው አስተላልፈውልናል። ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ብዙ በአያያዝና በመሳሰሉት ችግሮች ቅርሶች እንደ ቀላል ነገር በመጎሳቆልና በመጥፋትም ላይ ናቸው። በተለይም ይህንን በተመለከተ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ጋር እጅና ጓንት ሆነው ሊሠሩ ይገባል።

ለልማት ግብ መምታት ዋናው ነገር ለልማት ምቹ የሆነ አስተዳደር መዘርጋትና የሰለጠነ የሰው ኀይል ማዘጋጀት ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሁሉ በፊት ለልማት ምቹ የሆነ አስተዳደር መዘርጋት ይጠበቅባታል። ለዚህ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን የሰለጠነ የሰው ኀይል ያስፈልጋታል። የሰለጠነ የሰው ኃይልን ጥቅም ከማኅበረ ቅዱሳን እንቅስቃሴ ልብ ይሏል። ሁሉም ካህናት እንደ ማኅበረ ቅዱሳ ትምህርት ቢኖራቸው ኑሮ ይሄኔ የት በደረሰን ነበር።

የሰለጠነ የሰው ኀይል ችግርን ለመቅረፍ ቤተ ክርስቲያኗ 23 የካህናት ማሰልጠናዎች፣ አንድ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት (ሰዋስወ ብርሃን ቅ. ጳውሎስ) ሁለት ኮሌጆች (ቅድስት ሥላሴና መቀሌ ያለው መንፈሳዊ ኮሌጅ) ከፍታ እየንቀሳቀሰች እንደሆነ ተገልጾአል። ይህ መልካም ጅምር ነው ቢሆንም 40.000.000 ያህል ምእመናን፣ 500.000 ካህናት፣ 2.000.000 የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣት አባላትና 44 አህጉረ ስብከት፣ 511 ወረዳ ቤተ ክህነትና 40000 አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ላሏት ቤተ ክርስቲያኗ ከተጠቀሱት ማሰልጠኛዎችና ኮሌጆች የሚወጡ ምሩቃን በቂ አይደሉም። በእኔ እምነት ለእያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና የወሰደ ካህን ያስፈልጋል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኗ የማሰልጠኛዎቿን ቁጥር በብዙ እጥፍ ማሳደግና የጥራት ደረጃቸውንም መጠበቅ አለባት። ሰልጣኖችን በተገቢው ቦታ ማዋልም ቀጣዩ ሥራዋ መሆን ይገባዋል። የ2020 ልማት ግቡን ይመታ ዘንድ ካሕናቶቻችን፡-

1. ባህላዊውንና ዘመናዊውን እውቀት ያስተባበሩ፣
2. በእምነታቸው የተመሰከረላቸው፣
3. በጎብረተሰቡ ዘንድ ከበሬታና ተቀባይነት ያላቸውና ሕዝብን መምራት የሚችሉ፣
4. በአዲሱና በአሮጌው ትውልድ መካከል ድልድዮች ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ፣
5. የራሳቸውንና የሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት እምነት ጠንቅቀው የሚረዱ፣
6. በሃይማኖትና በልማድ፣ በሃይማኖትና በባህል መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት ማበጠር የሚችሉ፣
7. ሃይማኖትንና ሳይንስን (አእምሮአዊ እውቀትን) የሚያገናዝቡ፣
8 . ዓለምአቀፋዊ እይታ ያላቸው፣
9. ለሕዝብ መንፈሳዊና ቁሳዊ ልማት የሚጨነቁ፣
10. ቤተ ክርስቲያንን የማደራጀትና የተደራጀውንም መምራተ የሚችሉና
11. በዓለም አቀፍ ደረጃ ቤተ ክርስቲያኗን ሊወክሉ የሚችሉ... መሆን ይኖርባቸዋል።

ይሁንና ባለኝ መረጃ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ባለፈው ያከናወነው ተግባርና አሁንም ያጸደቀው እስትራቴጂ ፕላን ይህንን ታሳቢ ያደረገ አይደለም። ለምሳሌ የኮሚሽኑን ሠራተኞችና ካህናትን ለማሰልጠን እንዲሁም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትንና ሰበካዎችን ለመርዳት በጠቅላላወው ለ5 ዓመት የያዘው በጀት 9.5 ሚሊየን ብር ሲሆን ይህም ከጠቅላላው 346 ሚሊየን ብር ጋር ሲተያይ 2.8% ብቻ ነው። ከዚህ ውስጥ ግማሹ እንኳ ለካህናት ሥልጠና ይውላል ተብሎ ቢታሰብና ኮሚሽኑ አሉኝ ለሚላቸው 5000000 ካህናት ቢካፈል ለአንድ ካህን በዓመት አንድ ብር እንኳ አይደርሰውም። ይህም ለካህናት ስልጠና ትኩረት አለመሰጠቱን በግልጽ ያሳያል። ቤተ ክርስቲያን ለ2020 ልማት አስተዋጽኦ ማድረግ እንድትችል ከሁሉ አስቀድሞ ራሷን ልታለማና የካህናቶቿን አቅም ልታጎለብት ይገባል። ከመንግሥትን የአቅም ግንባታ ፕሮግራም በመማር በየቀኑ በትምህርት እየተገነቡ ላሉ ወጣቶች መምህራንና አባቶች ሊሆኑ የሚችሉና ከወደፊቱ የኢትዮጵያ ራእይ ጋር ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ ካህናትን ከወዲሁ ልታዘጋጅ ይገባል። በዚህ በኩል የመንግሥት እገዛም የሚያስፈልግ ይመስለኛል።

እንደሚታወቀው መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን እየሠሩ ያሉት በዚያው በአንዱ ሰው ላይ ነው። ስለዚህ ሃይማኖቶች አቅማቸውን አጎልብተው መንፈሳዊና ቁሳዊ አገልግሎታቸውን በተገቢው ደረጃ እንዲወጡና ለብሔራዊ ልማት ሊያደርጉ የሚገባቸውን አስተዋጽኦ እንዲያጠናክሩ መንግሥት ሊያበረታታቸውና ሊደግፋቸው ይገባል። እንዳለፈውም ሁሉ ጤናማና ለሀገር ተቆርቋሪ ትውልድ እንዲያፈሩ መርዳት ይገባዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአንድ በኩል ብቃትና ጥራት ያለው፣ በእሳት የተፈተነ ወርቅ የሆነና የሚያኮራ ትምህርተ መለኮት ያላት ሲሆን በአንጻሩ ሲውርዱ ሲዋረዱ የመጡና ሥር የሰደዱ ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዱ ልማዶችም መኖራቸውም ይታወቃል። ይህ መታረም አለበት። ከካህናቶቻችን የሚስተዋለው ችግር ሃይማኖትንና ባህልን፣ ሃይማኖትንና ልማድን ለይቶ ለመረዳት አለመቻል ነው። በመሆኑም ባህሉ፣ ልማዱ... ይሻሻል ሲባል ጉዳዩን ባለመረዳት ብዙዎቹ ቅሬታ ይሰማቸዋል። እንደ

ኑፋቄም ይቆጥሩታል። ይሁንና ሥርዓትን፣ ባህልንና ልማድን ማሻሻል ኑፋቄ አይደለም። ኑፋቄ የሚሆነው ሃይማኖትን (ቀኖና ቤተ ክርስቲንን) ማሻሻል ወይም መለወጥ ነው። ቀኖና ቤተ ክርስቲንን ማሻሻል አይቻልም። የሚሻሻልበትም ምክንያት የለም። አንዳችም ችግር የለበትምና።

ቤተ ክርስቲያን ከወረሰቻቸውና መሻሻል ካለባቸው ልማዶች ውስጥ አንዱ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ያልተከተለ የሚመተ ክህነት አሰጣጥ ነው። ለምሳሌ አንድ ደቀ መዝሙር ዳዊት አስተካክሎ ከደገመ ሙሉ ዲያቆን የመሆን ባህላዊ መብት አለው። ይህ በአንድ በኩል የክህነትን ሙያ ዝቅ የሚያደርግ ሲሆን በሌላ በከል ቤተ ክርስቲያኗ ልታስተዳድራቸው በማትችል ካህናት እንድትጥለቀለቅ አድርጓታል። ከዚህም ሌላ ያልሰለጠነ ካህን ለመንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ልማት አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ አይታሰብም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኗ ይህን ሥር የሰደደ ችግር ለመፍታት ማሰብና መንቀሳቀስ አለባት።

ከዚህም ጋር ቤተ ክርስቲያኗ ሚዛናዊ የሆነ የበጀት ምደባ ብታደርግ ጠቃሚ ነው። ሚዛናዊ የሆነ የበጀት ምደባ አለመኖርም የተመጣጠነ የካህናት ምደባ እንዳይኖር ያደርጋልና። ለምሳሌ፤ በከተማ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን 200ና ከዚያም በላይ ካህናት ሲኖሩት በገጠር አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምንም ካህን ላይኖር ይችላል። ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት ምንም አይነት የበጀት ምደባ ባለመደረጉም የገጠሩ ካህናት ያለ ማቋረጥ ወደ ከተሞች ሲፈልሱ ይስተዋላል። ይህም በአንድ በኩል በከተሞች የተትረፈረፉ ካህናት እንዲኖሩ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ያለ አገልጋይ እንዲቀሩ ምክንያት ሆኗል። በተጨማሪም በከተሞች የሥራ አጡ ቁጥር እንዲጨምር አስተዋጽኦ አድርጓል። ለዚህ ሁለት ዐይነት መፍትሄዎች መጠቆም ይቻላል። አንደኛው መፍትሄ ልማት ኮሚሽን የልማት ተቋማትን ከፍቶ ከተትረፈረፉት ካህናት ውስጥ አንዳንዶቹን በልማት ሥራ እንዲሰማሩ ቢያደርግ ለሀገር ልማት አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ ከልማቱ ከሚገኘውም ገቢ የልማቱ ሠራተኞችና ቤተ ክርስቲያኒቱ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ። ቤተ ክርስቲያንም የሰበካ ጉባኤውንም በጀት ለስብከተ ወንጌልና ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት መርጃ ለማዋል ትችላለች። ከዚህም ሌላ እንደ ልማዳዊ ጋብቻ፣ በዓላት ተዝካር.. ባሉ ባህሎች ላይ ለውጥ ቢደረግ ነፋቄ አይደለም። ከዚህም ጋር እንደ ተዝካርና ተደራራቢ በዓላት ቢሻሻሉ ጥቅም እንጅ ጉዳት የለውም። ለዚህ ሁሉ የክርስቶስን አርአያነትና የጳውሎስን ምሳሌነት ተከትለው ባህልና ልማድን የሚዋጉ፣ በእውነት ስለ እውነት ለትክክለኛ ኦርቶዶክሳዊነትና ለልማት የሚቆሙ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ያስፈልጋሉ። ቤተ ክርስቲያኗ እስከ 2020 እነዚህን የሰለጠኑ ካህናትን በጥራትና በብዛት ለማፍራት ብትንቀሳቀስ ከ2020 ቀጥሎ ባሉት ዓመታት ብሩህ ተስፋ ይኖራታል። በቤተ ክርስቲያኗ በኩል ለጊዜው የተያዘው እቅድ ግን ከ2005-2009 እንደሆነ ቀደም ሲል ከቀረበው ዘገባ ተመልክቷል።

በአቶ ሥርግው ገላው ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

በላይ መኮንን[1]

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በ2020 ልታደርገው የሚገባት ልማት» በሚል ርዕስ በአቶ ሥርግው ገላው በተዘጋጀው ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ አስተያየት አቅራቢ እንድሆን ስለጋበዘኝ ከልብ አመሰግናለሁ። በዚህም የተሰማኝን ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ።

አስተያየት አቀራረቤ ሙሉ በሙሉ ከይሉንታ የጸዳ ነው ባልልም ይጠቅማሉ የምላቸውን ሃሳቦች በግልጽነት ለማቅረብ እሞክራለሁ። ይህን ስል ብዙ ሰዎች እንደሚሉት በሃይማኖትና በፖለቲካ ጉዳዮች ዙሪያ የሚቀርቡ አስተያየቶች የራሳችንን ስሜት እያዳመጥን እንድንናገር፣ ወይም በራሳችን ላይ የቅድመ ምርመራ ሥራ እየሰራን እንድንጽፍ የማድረግ ኃይል ያላቸው በመሆኑ ነው። ይህን ማለት በራሱ ግልጽነት ይመስለኛል። ጽሑፉ የሚያነሳቸው ርእሰ ጉዳዮችና እነሱም የያዙዋቸው ጭብጦች ሰፋ ያሉ በመሆናቸው አስተያየቴ ትንሽ ሰፋ ሳይል አልቀረም።

ወደ ጥንተ ነገሩ ልመለስና፣ እላይ እንደገለጽኩት የቀረበው ጽሑፍ በውስጡ ብዙ ርእሰ ጉዳዮችን የሚያነሳ ቢሆንም ወጥነት ባለው አጻጻፍ የቀረበ ነው። እኔ ግን አስተያየቶቼን ሳቀርብ ነጥቦችን እንዳልስታቸው ስለሰጋሁ ጽሑፉን በተለያዩ ክፍሎች አስፈላጊ ሆኖ ሳገኘውም በንዑሳን ክፍሎች ከፍሎ ለማየት ሞክሬያለሁ። የአከፋፈል ስልቱም የዋናውን ጽሑፍ ቅደም ተከተል የጠበቀ ሲሆን፣ ክፍሎቹም የሚከተሉት ናቸው።

(1) የቤተ ክርስቲያኒቱ አመሰራረት፣ (2) ሀገሪቱና ሃይማኖቱ የነበራቸው ትስስር፣ (3) **የልማትና ክርስታናዊ ተራድኦ** ኮሚሽን፣ (4) የጋብቻ ሥርዓት በኢ.ኦ.ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፣ (5) መቻቻል፣ ይቅርታ እርቅና ሰላም የክርስቲያንነት መለኪያዎች ስለመሆናቸው፣ (6) የሥራ ክቡርነት፣ (7) የሥራ ቀናት በበዓላት ስለመሞላታቸው፣ (8) ልማት ለማምጣት ቁጠባ አንዱ መንገድ ስለመሆኑ፣ (9) የጽሑፉ ማጠቃለያ፣ (10) የቤተ ክርስቲያኒቱ ሁለንተናዊ ውለታ የሚሉት ናቸው ።

[1] ሊቀ ጎሩያን በላይ መኮንን በቤተክህነት ትምህርት ለ19 ዓመታት ያህል ተምረው በድጓና በዝማሬ መዋሥዕት መምህርነት ተመርቀዋል፡፡ ዘመናዊ ትምህርት፤ በማኔጅመንት ዲፕሎማ ያላቸው ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ የተከታታይ ትምህርት ክፍል በዲግሪ ፕሮግራም ለመመረቂያ ጽOፍ እየተዘጋጁ ነው። በአሁኑ ወቅትም በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሥር ባለው ብሔራዊ አፈር ምርምር ማዕከል የሰው ሀብትና የንብረት ሥራ አመራር መምሪያ ኃላፊ ናቸው።

ጽሁፍ አቅራቢው በመግቢያቸው ላይ ያነሱዋቸው ነጥቦች የቤተክርስቲያኒቱን አመሠራረትና ሀገርና ሃይማኖት ያላቸውን ትስስር በተመለከተ ነው። እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች አጠር አድርጌ ለማየት እሞክራለሁ።

1. የቤተክርስቲያኒቱ አመሠራረት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአፍሪቃ ቀደምት ከሚባሉት አብያተክርቲያናት አንዷ መሆኗን የሚጠራጠር የለም። እንዲያውም ፀሐፊው ከቀደምትነቷ ጋር በማያያዝ ሐዋርያው ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን እንደሰበከ በጽሑፍ ያረጋገጡ የቤተክርስቲያን አባቶችን እና ታሪክ ጸሐፊዎችን በመጥቀስ አቅርበዋል።

ይሁን እንጅ እንደኔ ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ ቀደም ብሎ «ኩሽ» ይባል የነበረውን ቃል ስለወረሰና ኩሽ ወይም የኩሽ ምድር የሚለው ደግሞ በሰሜንና ምሥራቅ አፍሪቃ ሰፊ ግዛትን የሚሸፍን እንደነበረ አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌን ጨምሮ አንዳንድ ምሁራን ስለሚያምኑ ጉዳዩ አከራካሪ ሊሆን ይችላል። ሊቀ ጎሩያን በላይ መኮንን በቤተክህነት ትምህርት ለ19 ዓመታት ያህል ተምረው በድጓና በዝማሬ መዋሥዕት መምህርነት ተመርቀዋል፡፡ ዘመናዊ ትምህርት፤ በማኔጅመንት ዲኘሎማ ያላቸው ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ የተከታታይ ትምህርት ክፍል በዲግሪ ፕሮግራም ለመመረቂያ ጽሑፍ እየተዘጋጁ ነው። በአሁኑ ወቅትም በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሥር ባለው ብሔራዊ አፈር ምርምር ማዕከል የሰው ሀብትና የንብረት ሥራ አመራር መምሪያ ኃላፊ ናቸው።

ያም ሆኖ ጽሑፉ ለጥናት መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ጸሐፍት ሥራዎችን ስለጠቆመ ጥናትና ምርምር ለሚያካሄዱ የስነሰብእ፣ መልክዐምድር ወይም የሥነመለኮት ተመራማሪዎች ትልቅ ዋጋ እንደሚኖረው አልጠራጠርም።

2. ኢትዮጵያና የኦርቶዶክስ እምነት

ሃይማኖት ለሀገር ሉዓላዊነት ያበረከተው አስተዋጽኦ፣ በጥንቱ የኢትዮጵያ ሰው ዘንድ ሃይማኖትና ሀገር ያንድ ሣንቲም ገጽታዎች መሆናቸው፤ መንግሥት ሰማያት የሚወረስ ነፂ ሀገር ሲኖር መሆኑና ከዚህ አስተምህሮ ጋር ተያይዞ ለሀገር ፍቅር የሚከፈለው መሥዋዕት ነት እጅግ የላቀ መሆኑ ተንፀባርቋል። ይህን ሀቅ እንዳለ እንቀበለውና በዚህ ሀሳብ ዙሪያ በትንሹ ላነሳው የምፈልገው ተጨማሪ ነጥብ አለኝ።

- ይህ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ በህብረተሰቡ ላይ ያሳደረው በጐ ተፅእኖ በየክፍለ ዘመኑ የተነሱ ወራሪዎችን ማለትም እንደቱርክ፣ ግብጽ፣ ኢጣሊያ ወዘተ. የመሳሰሉትን ለማንበርከክና የዚች ሀገር ሉዓላዊነት ተጠብቆ ከነአኩሪ ባህሏና ታሪኳ ወደ 3ኛው ሚሊኒየም እንድትዘልቅ አስችሏታል።

- ይህ የሀገር ፍቅር ሰሜት በጥንታዊው ኢትዮጵያዊ ደም ውስጥ ብቻ ፈልቶ አልበረደም። ይህን ትውልድም ደመ ሞቃት አድርጐታል። ምክንያቱም እያገባደድ ነው ካለነው ምእተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ወዲህ የተካሄዱብንን ሁለት የውጭ ወረራዎች ለማክሸፍ ይህ ትውልድ የፈፀመው አኩሪ ገድል ሲታሰብ የአባቶቹና የእናቶቹ የደም ውርስ መሆኑን አንጠራጠርምና ነው።

3. በኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን፣

በ1964 ዓ.ም የተቋቋመው ኮሚሽን በመጀመሪያ ሲቋቋም 3 ዓላማዎች እንደነበሩት ተጠቅሶዋል። ከቤተ ክርስቲያኒቱ አካባቢ ወጣ ብሎ ለሀገርና ለወገን ሰፊ ድጋፍ እያደረገ ያለውን ይህን ኮሚሽን ያቋቋሙ የቀደሙት የቤተክርስቲያን አባቶች ተመስግነዋል። ተገቢ ነው። ኮሚሽኑ ከተቋቋመባቸው ሦስት ዓላማዎች የመጀመሪያው «ወጣቶችን ተፈላጊ በሆኑ የሙያ ትምህርቶች እንዲሰለጥኑ መርዳትና ማበረታታት» የሚል ነው። ይህ ዓላማ ትልቅ ጉዳይ ነው። አሁንም ቢሆን ቤተክርስቲያኒቱ መያዝ ያለባት ወጣቱን ትውልድ ነው። ምክንያቱም በማይፈለጉ ነገሮች የመጠመድ እድሉ ሰፊ ስለሆነ ወጣቱን ትውልድ ለመያዝ ብዙ መሠራት አለበት። የቤተክርስቲያኒቱ የትምህርት አሰጣጥም እንዲስበው ያስፈልጋ። ከዚህም ሌላ አስተማሪዎቹ ጥሩ ምሳሌ መሆን መቻል አለባቸው። አለበለዚያ ዝም ብለህ ተከተለኝ ቢሉት ትውልዱ አፈንጋጭ ስለሆነ በጂ አይልም።

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ደረጃ በደረጃ የሥራ ዘርፉን እያሰፋና የልማት መርሐግብሮቹን እያሻሻለ እንደመጣ ተገልጿል። በዚህም መሠረት፣

- o በ1976 ዓ.ም በተከሰተው ድርቅ ምክንያት የእርዳታና የመልሶ ማቋቋም ሥራ ውስጥ መግባቱ፣
- o ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ የመንግስትን የልማት ፖሊሲ በመከተል ወደ ዘላቂ የልማት ፕሮግራም መሸጋገሩና በዚህም ስር ሰባት የልማት መርሐግብሮች እንዳሉት ተጠቅሰዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ኮሚሽኑ በሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቅ ተሳትፎ እያደረገ መሆኑን ነው።

ሦስቱ ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች፣

3.1 የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ መምሪያ

ይህ መምሪያ ከተለያዩ አፍሪካ ሀገሮችና ከየመን ለመጡ ስደተኞች ሁለንተናዊ የሆነ የማቋቋምና የመርዳት ብሎም ራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ሥራ እየሠራ እንደሆነ ተገልጿል። ከዚህም ሌላ ኮሚሽኑ ከ2005-2009 እ.አ.አ. ሰባት ዋና ዋና ግቦችን ያቀፈ እስትራቴጂክ ፕላን አውጥቶና ብር 45 ሚሊዮን የሚያወጡ ፕሮጀክቶችን ቀርፆ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑ በጽሑፉ የቀረበ ሲሆን፣ ሰባቱ ፕሮጀክቶችም ከነበጀታቸው በሰንጠረዥ ቀርበዋል። ሁሉም ከድህነት እንድንወጣና የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት

የሚያግዙ ናቸው። እንደእኔ በዚህ እቅድ ውስጥ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በ35 ዓመታት ዕድሜው ካከናወናቸው ተግባራት ቁልፍ የሚባሉት ፕሮጀክቶች የዕቅድ ክንውን አፈፃፀማቸው በዚህ ወረቀት ቢካተት የወደፊት ርእዩን ለማሳካት ያለውን አቅም ያሳይ ነበር ብዬ እገምታለሁ።

ከዚህም ሌላ በእቅዱ ውስጥ እንደ ማይምነት ሁሉ የሥነ ምግባር ትምህርት መካተት ነበረበት የሚል ሀሳብ አለኝ። ተጨባጭ ሁኔታዎች እንደሚያሳዩን ባሁኑ ወቅት ምእመናን ብቻ አይደሉም ካህናትም የሥነምግባርትምህርት ያስፈልጋቸዋል። "ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ፣ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።" ይላል ሐዋርያው ያዕቆብ። ከዚህ ጥቅስ አንጻር እምነቱን በሥራና በመልካም ሥነምግባር የሚገልጹ ካህናትና ምእመናን እንዲበዙ ጥረት መደረግ አለበት። በስብከታቸውና ትምህርታቸው ብቻ ሳይሆን በመልካም ሥራቸው ጭምር የትውልዱን ልብ የሚይዙ አስተማሪዎች ያስፈልጋሉ የሚል እምነት አለኝ። የሥነ ምግባር ትምህርቱ የሚጠቅምም ለዚህ ነው።

3.2 የሕጻናትና ቤተሰብ ድርጅት

በ1966 ዓ.ም. የተከሰተውን ድርቅ ተከትሎ የተቋቋመው የሕጻናትና ቤተሰብ ድርጅት 20 ዐዐዐ ሕፃናትን አሳድጐ ለቁም ነገር ማብቃቱ የሚያኮራ ተግባር ነው። ነገር ግን እንደሐይማኖት ተቋም ቤተክርስቲያኒቱ እነዚህ ወጣቶች ከጉያዋ እንዳይወጡ አድርጋለች ወይ? ወይስ አሳድጋ ነው የለቀቃቻቸው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል።

3.3 የሰላም ግንባታና የግጭት ማስወገድ ፕሮግራም

በኢት.ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን ሰላም የሁሉም ነገር ማዕከል ነው። ማህሌቱ ስብሐተ ነግሁ፣ መዝሙሩ፣ ቅዳሴው፣ ስብከቱና ትምህርቱ ለሁሉም ነገር ማሰሪያው ሰላም ነው። ሰላ ይሰበካል፤ ሰላም ይዘመራል፤ ሰላም ይጸለያል፤ መልካም ነገር ነው። ይህ ሁሉ ፍጹም እንዲሆን ደግሞ እንደእምነቱ ሁሉ ሰላም በሥራ መገለጽ ይኖርበታል። ደጀ ሰላሙ እንደ ስሙ የሰላም ቦታ መሆን አለበት። ምክንያቱም ሰላም ፍቅር ነው። ፍቅር ደግሞ እግዚአብሔር ነው። ለሀገራችን ዕድገት ዋናው እንቅፋት የሰላም እጦት ነው። ጦርነት ነው። ብዙዎች እንደሚሉት የሀገራችን ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው። ጦርነት ደግሞ ያችኑ ያለችውን ጥሪት ያሟጥጣል። አምራች ሀይል የሚበላውን ትውልድ ይበላል። በታሪክና በስልጣኔ ግንባር-ቀደም የሆነችው ኢትዮጵያ በድህነትም ቀዳሚውን ስፍራ ልትይዝ ከቻለችባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ይሄው ነው። ጦርነት ነው። ስለዚህ አይደለችም የኢትዮጵያ ኦ/ተ.ቤተ ክርስቲያን ሁሉም የሃይማኖት ተቋማት ስለ ሰላም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ማሰማት አለባቸው። ይህ ከሆነ ደግሞ የበለጸገች ኢትዮጵን ለማየት ያለን ርእይ እውን ይሆናል።

4. ጋብቻ በኢትዮጵያ ኦ/ተ ቤተ ክርስቲያን

"አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት" የሚለውን፣ ወይም ሁለቱን ተጋቢዎች አንድ የሚያደርግ ምስጢር ቤተ ክርስቲያኒቱ በምእመናን ልብ ማስረጽ አለመቻሏና የዚህም ችግር ታሪካዊ ምክንቶች በጽሑፉ ተገልጸዋል። በኦሪት ዘፀዓት ምዕራፍ 20÷7-18 የምናገኛቸውና ለሙሴ የተሰጡት አስርቱ ትእዛዛት ለብሉይ ኪዳንም ሆነ ለሐዲስ ኪዳን አማንያን ቁልፍ የሕይወት መመሪዎች ናቸው። ከአሥርቱ ቃላት ውስጥ ጋብቻ አንድ ለአንድ መወሰን እንዳለበት የሚያስተምረን ኃይለቃል «አታመንዝር» የሚለው ነው። የኢትዮጵያኦ/ተ.ቤተ ክርስቲያን ይህን ኃይለቃል በምእመናን ልቡና ውስጥ ማስረጽ እንዳልቻለች ጽሑፉ ይጠቁማል። በኔ አስተያየት ግን ይህ ብቻ አይደለም። «አትግደል፣ አትስረቅ፣ በባልንጀራህ ላይ በሀሰት አትመስክር።» ወዘተ... የሚሉት ክርስቲያናዊ መርሆዎች በሕዝቡ ልብ ውስጥ አልሰረጹም። ክርስቲያን ነው። ግን ይሰርቃል፤ ይዋሻል፤ ይገድላል። ግድያ፣ ስርቆት፣ ዝሙት፣ የሐሰት ምስክርነት፣ ምቀኝነት፣ የሰው ገንዘብ መመኘትና የመሳሰሉት ደግሞ ሕገ እግዚአብሔርን ከመጣስ አልፈው ማህበራዊ ጠንቆችና የልማት እንቅፋቶች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በ2020 ልታሳካው የያዘችውን በጐ ራዕይ ከግብ ለማድረስ እነዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ ጥረት ማድረግ ይኖርባታል።

ነገሥታቱ የቤተክርስቲያን ርእሶች እንደነበሩ እና ከነገሥታቱም አንዳንዶቹ ሕገ ቤተክርስቲያንን አለመጠበቃቸው መጥፎ የጋብቻ ልማድ ሥር እንዲሰድ አስተዋጽኦ በማድረጋቸው ይህ መጥፎና ክርስቲያናዊ ያልሆነ የጋብቻ ባህል ሳይታረም እስከዘመናችን መዝለቁና ይህን ባህል ለማረምም እንቅስቃሴ አለመታየቱ ለትዳር መፍረስና ለቤተሰብአዊ ህይወት መናጋት ምክንያት ከመሆን አልፎ ለኤድስ በሽታ መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑ ተዘክሯል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኒቱ ባሁኑ ወቅት "አንድ ወንድ ላንድ ሴት" በሚለው መርሕ ላይ ተመሥርታ እየሰጠችው ያለውን ትምህርት አጠናክራ ልትገፋበት ይገባል።

5. መቻቻል፣ ይቅርታ፣ እርቅና ሰላም የክርስቲያንነት መለኪያዎች ስለመሆናቸው፣

ኢትዮጵያ መቻቻል፣ እርቅና ሰላምን ገንዘቡዋ አድርጋ የኖረች ሀገር ስለመሆንዋ ክርስቲያኑና ሙስሊሙ ህብረተሰብ ለ1400 ዓመታት ያህል ተከባብሮና ተቻችሎ መኖሩ አንድ ተጨባጭ ማስረጃ ሆኖ የቀረበ ሲሆን፣ የሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች በሰላም አብሮ የመኖር ታሪክም ለሌላው ዓለም በመልካም ምሳሌነት የሚጠቀስ መሆኑ አጽንኦት ተሰጥቶበታል። ከዚህ በጐና ድንቅ ተመክሮ በመነሳት በኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያንና በሌሎች የክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል የሠመረ ግንኙነት ቢፈጠር ለሕዝባችን አንድነትና ለልማታችን እድገት ምን ያህል የላቀ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ጸሐፊው አስምረውበታል።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩና የተለያየ ባህል ያላቸው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖራቸው መለያ ውበታችን መሆኑ ቢታወቅም፣ ልዩነቶች እንደሚኖሩም ተጠቅሷል። አንዳንድ ኃይሎች ይህ ልዩነታችን እንዲሰፋና ትንንሽ ነገሮችን በማራገብ ተግተው ሊሠሩ እንደሚችሉም ተብራርቷል። ስለዚህ ይህን ስጋት ለማስወገድ ሁሉም የሃይማኖት ተቋማት ተግተው መሥራት ይኖርባቸዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ነፂ መንግሥትና ነፂ ባህል ያላት ሀገር፣ የሁለቱ ዋና ዋና የእምነት ተከታዮች ተቻችለው የኖሩባት ሀገር ሆና እስከዘመናችን ድረስ መዝለቋና ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ "ኢትዮጵያዊነት" ለሚለው የጥቁር ሕዝቦች እንቅስቃሴ መንስኤ መሆኗ ያስከፋቸው ወገኖች ሀገራችን በቋንቋ፣ በባህልና በሃይማኖት ስትከፋፈልና የማህበረሰቦች አንድነት ሲላላ ማየት ይሻሉ። ለዚህ ደግሞ ዋናው መሣሪያ ሃይማኖት ነው። ማህበራዊ ግንኙነታችን መላላቱ ደካማ ሀገርን ይፈጥራል። በልማታችን ላይም አሉታዊ ተፅዕኖን ያሳድራል። የሚለውም በሁሉም ዘንድ ትኩረት ሊያገኝ የሚገባው አስተሳሰብ ነው። እንደኔ በሃይማኖት ተቋማት መከከል አንዱ የሌላውን ህፀፅ መፈለግና የትምህርት ርእሱ ማድረግ ቢቆምና ሁሉም የየራሱን ነገረ ሃይማኖት ተከትሎ ነጻዋን ወንጌለ መንግሥት ቢሰብክ መቻቻሉ ይመጣል። «የኔ እምነት ከሌላው ይሻላልና እኔን ተከተል።» የሚለው አካሄድ ሕዝቡን አላዋቂ ከማድረግ አልፎ ጥላቻ እንዲለመልም ያደርጋል። ከመከባበርና ከሰላም እንጅ ከጥላቻና ከመለያየት ጽድቅ አይገኝም። ስለዚህ መከባበርና መፈቃቀር ለሁሉም የሃይማኖት ተቋማት ይሁን እላለሁ።

6. የሥራ ክቡርነት

የመጀመሪያው አምላካዊ ትእዛዝ "ብላዕ በጎፈ ገጽከ - ላብህን ጠርገህ ብላ" የሚል በመሆኑ ሁሉም የሃይማኖት ተቋማት ሥራን ማበረታታትና ተግተው ማስተማር አለባቸው የሚለው ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ነው። ባሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ኦ/ተ. ቤተ ክርስቲያን ጎልተው የሚታዩ የልማት ጅምሮች አሉ።

ለምሳሌ በአ/ አበባ ከተማ ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ ታላላቅ ሕንፂዎችን እየገነቡ ት/ቤቶችን በመክፈት የተማረ ዜጋን ለመፍጠር የሚደረገውን ሀገራዊ ጥረት በጉልህ እያገዙ ነው። በሌላም በኩል ሕንፂዎቹ እየተከራዩ ከፍተኛ የልማት ሥራ እየተሠራባቸው ይገኛል። ይህ መቼም በጣም የሚያበረታታ የልማት እንቅስቃሴ ነው። ከዚህ በተጓዳኝ የሚተኮርበት ጉዳይ አለ። በአ/አበባ ከተማ ከመቶ የማያንሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ እገምታለሁ። በያንዳንዱ ቤተመቅደስ ደግሞ በአማካይ 150 ካህናት አሉ ብለን ብንገምት ከ15,000 የማያንሱ ካህናት አሉ ማለት ነው። እነዚህ ካህናት መደበኛ ሥራቸው የተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት ቢሆንም በትርፍ ጊዜያቸው ብዙ ሊያመርቱ የሚችሉበት ሁኔታ አለ። በገጠር ያለው ካህን ገበሬ እንደሆነ ሁሉ በከተማ ያለው ካህንም ላብ-አደር ቢሆን ለውጥ ሊመጣ ይችላል። በየቤተክርስቲያኑ አነስተኛ የጐጆ ኢንዱስትሪዎችና የጥበበ እድ ማምረቻዎችና ማከፋፈያዎች መስፋፋት አለባቸው። መነኰሳቱና ካህናቱ (የቢሮ ሠራተኞችን ሳይጨምር) ረጅም ሐር ቀሚስ ብቻ ሳይሆን ቱታ መልበስም ቢለምዱ መልካም ይመስለኛል።

ይህ ከሆነ ከሰው የማይጠብቁ ካህናትና የበለጸገች ቤተክርስቲያንን መፍጠር ይቻላል። ሀገርም ታድጋለች። ርእዩም ግቡን ይመታል። ይህን ማድረግ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አዲስ ነገር አይደለም። ለምሳሌ፤

እንደ ደብረሊባኖስ፣ ዝቋላ፣ ዋልድባ፣ ማህበረሥላሴ፣ ዳጋ፣ መንዳባ፣ ክብራን ወዘተ... ባሉት ገዳማት የሚኖሩ መንፈሳዊያን አባቶች የጠዋት ጸሎታቸውን ካደረሱ በኋላ ባጭር ታጥቀው፣ ዶማና አካፋቸውን ይዘው እስከ ተሲያት ድረስ ሲያርሱና ሲቆፍሩ፣ ድንጋይ ሲፈነቅሉ፣ አትክልት ሲያለሙ፣ ሰብል ሲያመርቱ እንደሚውሉ፤ ወይም ሸማ እየሸመኑና ምንጣፍ፣ ጥላና ሌላም ሌላም የጥበበእድ ሥራዎችን እየሠሩ እንደ መጽሐፉ ቃል በወዛቸው ጠብታ የዓመት ልብሳቸውንና የዕለት ጉርሳቸውን እንደሚያገኙ መዘንጋት የለበትም።

7. የኢትዮጵያ ኦ/ተ. ቤተ.ክርስቲያን የሥራ ቀናትን በበዓላት ሞልታቸዋለች ስለሚለው ስሞታ

የአቶ ሥርግው ጥናታዊ ጽሑፍ አንድ የምሥጢር በር የከፈተ ይመስለኛል። የበዓላት አከባበርን በተመለከተ እስካሁን ያለው ግንዛቤ መጽሐፍ ቅዱሳዊና በሲኖዶስ የተወሰነ ጉዳይ መሆኑን ብዙዎች እንደሚያምኑት አልጠራጠርም። ቀዳሚት ሰንበትን በተመለከተ ዛሬም በሕይወት ሥጋ ያሉት ታላቁ ሊቅ መ/ነኔት ገብረሥላሴ «ወበዕለተ ሰንበት ኢታጽርኡ ተገብሮ ከመ አይሁድ። በመጀመሪያዋ የሰንበት ቀን እንደ አይሁድ ሥራ ፈታችሁ አትዋሉ። የሚለውን ከፍትሐ ነገሥት ጠቅሰው ሲያስተምሩ አውቃለሁ። በሌላ ወገን ሰንበትነቷን አክረውና አጠንክረው፣ በመ/ቅዱስ ጥቅስም አዳብረው የሚያስተምሩ ሊቃውንት ነበሩ አሁንም ይኖራሉ። የቀዳሚት ሰንበት አከባበር ግጭትን ለመፍታት ተብሎ ከሃይማኖት ይልቅ ፖለቲካዊ ይዘት በነበረው ውሳኔ መጀመሩ ለብዙዎች እንደ አንድ ታሪካዊ የጥናት ግኝት የሚቆጠር ይመስለኛል። በሌላ በኩል የ33ቱን የእመቤታችን በዓላት አከባበር የሚነግረን መቅድመ ተአምር «ዝንቱ መጽሐፈ ሥርዓት ዘወጽአ እመንበረ ማርቆስ ሐዋርያ እመካነ ማልቃ ዘምስር ዘአንበሩ መምህራን አበው ሊቃነጳጳሳት... » ይህ የሥርዓትና የሕግ መጽሐፍ ከሐዋርያው ማርቆስ ወንበር/እስክንድርያ/ የተገኘ፣ የግብጽ ክፍል ከሆነች ማልቅ ከምትባል ቦታ አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳት ያቆዩት...» የሚል መግቢያ ስለተጻፈበት በአፄ ዘርዐያዕቆብ የተደነገገ ነው ተብሎ ለኢትዮጵያ ኦ/ ቤተ ክርስቲያን ካህን ቢነገረው ጆሮውን አያምንም። አፄ ዘርዐያዕቆብ ዕለታቱን በበዓላት የሞሉበት ምክንያት አምልኮ ባዕድን ከሀገሪቱ ለማስወገድና የትምህርት ቀናትን ለማብዛት እንደሆነ በጽሑፉ ተጠቅሷል። ይህ አንድ አሳማኝ ነጥብ ነው። በኔ አስተያየት ሌላም ምክንያቶችን መጥቀስ ይችላል። በዚያ ዘመን ሃይማኖት አንድ ሀገራዊ ጉዳይ ስለሆነ ከሥራ ቀናት ይልቅ የትምህርት ቀናት ቢበዙ አያስገርምም። ከዚህም ሌላ የበዓላት ብዛት በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ላይኖር ይችላል። መሬቱ እንደዛሬው አልተራቆተም ወይም አልተጣበበም። ትንሽ መሬት አርሶ ብዙ ምርት ማግኘት ይቻላል። መሳሩ ከጫካ ይቆረጣል። የላሞቹ ግት ሳያልቡት ይፈሳል። እና ይህ ጸጋና በረከት በነበረበት ዘመን የዕረፍት ቀን እንዲበዛ ቢደረግ የሚያስደንቅ አይሆንም። ለምሳሌ፤ ዛሬ በበለፀጉ ሀገሮች የሚኖረው ህብረተሰብ ትንሽ ሠርቶ ብዙ ያገኛል። ጊዜውንም በመዝናናትና በሀገር ጉብኝት ያሳልፋል። ከኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ግን ባለንበት ዘመን ጥቂት ሠርቶ የሚታረፍበት ሳይሆን፣ በብዙ ድካም ጥቂት ምርት ወይም ውጤት የሚገኝበት ስለሆነ የበዓላት አከባበራችን በሃይማኖቱ አባቶች ሊጤንበትና ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባ ይመስለኛል።

እዚህ ላይ አንድ አባባል/ተረት ትዝ አለኝ። አንድ የጐጃም አዛውንት የሮሃን አብያተመቅደስ ለመሳለም ወደ ቅዱስ ላሊበላ ሲሄዱ ጋይንት አካባቢ ጉና ሚካኤል የሚባል ቦታ ላይ መሸባቸው ይባላል። የእንግዳ አቀባበል ባህልን ላወረሱን አባቶች ምስጋና ይግባቸውና ማደሪያው አላሳሰባቸውም። ግን በአካባቢው ቤት ያጣሉ። አንድ ሰው አግኝተው ሲጠይቁት «ቁልቁለቷን ወረድ ይበሉ» ይላቸዋል። አዛውንቱ በደከመ ጉልበታቸው የገደሉን ቁልቁለት እንደምንም ወርደው ካንድ ገበሬ ቤት «የግዜር እንግዳ» ይላሉ። ከዚያም ጥሩ መስተንግዶ ተደርጐላቸው ሲጫዎቱ «ካልጠፋ ቦታ ምነው ከዚህ ገደል ውስጥ ትኖራላችሁ?» ብለው ባለቤቱን ሲጠይቁት፣ «የናት አባቶቻችን ባድማ ስለሆነ ነው» ሲል ይመልሳል። በዚህ ጊዜ አዛውንቱ ትንሽ አሰቡና «ዛዲያ እናት አባት ገደል ከቶ ቢሞት ልጅ እንዴት አይወጣም?» አሉ ይባላል። በጊዜው ለነሱ ተስማሚ ሆኖ አባቶቻችን ያቆዩት ባህል ዛሬ ትውልዱን የሚጐዳ ከሆነ መሻሻል አለበት ለማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያኒቱ በግብጽ ቤተክርስቲያን ስር በምትተዳደርበት በአፄ ዘርያዐቆብና በዚያ ዘመን በነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሀገራችን ውስጥ የተወሰነው ድንጋጌ ዛሬ የተሟላ ቅዱስ ሲኖዶስና መንበረ ፓትርያርክ ያላት ቤተ-ክርስቲያናችን ድንጋጌውን የማታሻሽልበት ምክንያት የለም የሚል እምነት አለኝ። ጽሑፍ አቅራቢው በዚህ ክፍል ማጠቃለያ ላይ ያቀረቡት መፍትሔ «አብዛኞቹ በዓላት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሲኖዶሳዊ ስላልሆኑ በሲኖዶስ ተጠንተው አንዳንዶቹ ታስበው እንዲውሉ ቢደነገግ መልካም ነው» ይላሉ። እንደኔ ማጠቃለያው ትንሽ ላላ ያለ ይመስለኛል። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሆነው ሕብረተሰብ /በተለይ አርሶ አደሩ/ እነ አጼ ዘርዐያቆብ የደነገጉአቸውን በዓላት ብቻ አይደለም እያከበረ ያለ። ለአንድ ጻድቅ ወይም ሰማዕት የምናከብረው በዓል ልደቱ ወይም የዕረፍት ቀኑ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፤ የጻድቁ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዓመታዊ ክብረ በዓል መጋቢት 5 ቀን ሲሆን፣ ይህም በውሣኔ የተደነገገና ሊከበር የሚገባው ነው። ህብረተሰቡ ግን «የአቡየ በዓል» እያለ በየወሩ አምስት ቀንን ያከብራል። ከእመቤታችን በአላት ብንወስድ ልደታ ለማርያም ግንቦት 1 ቀን፣ በዓታለማርያም ታህሣስ 3 ቀን በዘወሀባ ኪዳነ ምሕረት የካቲት 16 እና ነሀሴ 16 እንዲከበሩ ተደንግጓል። ክርስቲያኑ አርሶ አደር ግን (ከተሜው ትቶታል ብዬ ነው) እነዚህንና ሌሎችንም በዓላት በአመት አንድ ጊዜ ሳይሆን በየወሩ ያከብራቸዋል። ይህንም ወዶና ለምዶ የሚፈጽመው ሳይሆን በባህለ-ሃይማኖቱ ተገዶ ነው። በዓላቱን ባያከብር አዝመራውና ሰብሉ በበረዶና በትል እንደሚጠፋ፣ ዐባርና ቸነፈር እንደሚወርድበት፣ በረከት እንደማያገኝ አንዳንድ የማስፈራሪያ ትምህርት የሚሰጡ ካህናት እንዳሉ ግልጽ ነው። ስለዚህ ይህን ለዘመናት በህብረተሰቡ አስተሳሰብ ሰርጾ የቆየውን የተንዛዛ የበዓላት አከባበር ደረጃ በደረጃ ለማሻሻል ጥረት ቢደረግ የቤተክርስቲያኒቱ ተከታዮች ከጠባቂነት ተላቀው ራሳቸውን፣ ቤተክርስቲናቸውን፣ ብሎም ሀገራቸውን እንዲያበለጽጉ ለማድርግ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። ቤተክርስቲያኒቱ የያዘችው የልማት ርእይም የታለመለትን ግብ እንዲመታ አስተዋጽኦው ከፍተኛ ይሆናል።

8. ልማትን ለማምጣት ቁጠባ አንዱ መንገድ ስለመሆኑ

የቁጠባ ምክር ከኢኮኖሚስቶች ይልቅ በሃይማኖት አባቶች ቢቀርብ በህብረተሰቡ ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት እንደሚኖረው ጸሐፊው ከገለጹ በኋላ ኅብረተሰቡን ለጋስ ያደረጉት የሃይማኖት አባቶች ናቸው። ለጋስ ማድረግ ከቻሉ ቆጣቢ ማድረግም አይሳናቸውም ይላሉ ፀሐፊው። እንደእኔ ይህ አስተሳሰብ በጣም ትልቅ አባባል ነው። ቅኔያዊ አገላለጽም ይመስለኛል። በሌላ በኩል በዚህ ስለቁጠባ በሚያወሳው ክፍል ውስጥ ያለ የሌለ የሚች ቤተሰብን ቅርስ በማሚጠጥ የሙት ልጆችንና አረጋውያን ተጧሪዎችን ያለመተዳደሪያ የሚያስቀረው ልማድ የሚከናወን በቤተ ክርስቲያን ስም ቢሆንም ህብረተሰቡ ባለው ከማን አንሼ መንፈስ ተገፋፍቶ የሚፈጽመው መሆኑ ተሰምሮበታል። ይህም አባባል ህብረተሰቡን ተጠያቂ ስለሚያደርግ ከላይኛው ሀሳብ ጋር ይጣረሳል። ለዚህ ጉልህ ችግር መፍትሄው አንድና አንድ ነው። ቤተክርስቲያኒቱ ከ33 ዓመታት በፊት ያጸደቀችውና እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያዎችን ያደረገችበት አንድ ወጥ መመሪያ አላት። ምእመናን ከቤተክርስቲያን ወይም ከካህናት ለሚያገኙት መንፈሳዊ አገልግሎት መክፈል ያለባቸው ዋጋ ምን እንደሆነ በግልጽና በማያሻማ መልኩ ተቀምጧል። ቃለ ዓዋዲው በተለይ በገጠሯ ቤተክርስቲያን በተግባር ላይ ውልኟ ወይ? ተብሎ ቢጠየቅ አፍን ሞልቶ መልስ የሚሰጥ ሰው ያለ አይመስለኝም። በሌላ መልኩ ቃለዓዋዲው ተግባራዊ እንዳይሆን እንቅፋት የሆኑ ምእመናን ናቸው? ተብሎ ቢጠየቅ ደግሞ አዎ? የሚል አንደበት አይኖርም። ስለዚህ ይህን የድህነት ምንጭ ናቸው ከሚባሉት ልማዶቻችን አንዱ የሆነውን የሙታን መታሰቢያ ድግስ ለማስቀረት ወይም በሩን ለመዝጋት በምእመናኑ እጅ ቁልፍ እንዳለ ብናስብም ዋናው ቁልፍ /Master key/ የሚባለው ግን በካህናት እጅ ነው እላለሁ። ለተንዛዛ የሙታን መታሰቢያም ሆነ ለሰርግ ከሚወጣው ወጪ አንጻር የችግሩ ተጠቂዎች ምእመናን ብቻ ሳይሆኑ ካህናትም ጭምር ናቸው የሚለው አሻሚነት የሌለው ትክክለኛ አባባል ነው።

በሌላ በኩል በዘመናችን የምእመናን ብዛት እድገት እያሳየ በመጣ ቁጥር አብያተ ክርስቲያናትም የዚያኑ ያህል እየተስፋፉ ነው። መስፋፋት ብቻ አይደለም ውብና ድንቅ የሆኑ ሕንጻዎች በከተማዎችና በገጠሩ አካባቢም ሳይቀር እየተገነቡ ይገኛሉ። እነዚህ ህንጻዎች ለዛሬው ትውልድ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጫ ለነገው ትውልድ ቅርሶች ስለሆኑ በዚህ የማይደሰት አማኝ አይኖርም። ግን የአንዳንዶቹ ግንባታ የህዝቡን አቅም የዳሰሰ ጥናት ሳይካሄድበት እየተጀመረ አማኙን ይፈታተናል። ምንም ጥሪት/ገንዘብ/ ሳይያዝ ግንባታው ይጀመርና ብዙም ሳይነቀሳቀስ ሥራው ይቆማል። ከዚያም በኋላ በገበያው ፣ በየመንገዱ ልመና ይጀምራል። ይህ እንግዲህ ለምእመኑ ትልቅ ፈተና ነው። በአምስት ዓመት ያልቃል ተብሎ የተገመተው ግንባታ እስከ አስር ዓመት ሊዘልቅ ይችላል። ይህን ችግር ለመቅረፍ የምጠቁመው መፍትሄ አለኝ። በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሥር የምህንድስናና ህንጻ ጥገና መምሪያ ሊኖር ይገባል። / አሁን ይኑር አይኑር አላውቅም/። ቢቻል በየአህጉረ ስብከቶች መዋቅሩ ቢዘረጋ መልካም ነው። ይህ መዋቅር ከተዘረጋ አንድ ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ ሲታሰብ የሚሠራው ሕንጻ የህዝቡን አቅም የሚመጥንና ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ በባለሙያዎች ተጠንቶና ፕላኑ ተዘጋጅቶለት፣ የግንባታ ፈቃድ እየተሰጠና ክትትል እየተደረገበት ቢሠራ ችግሩ ይቃለላል የሚል ግምት አለኝ። የምህንድስናና ሕንጻ ጥገና መምሪያ/ክፍል በየሀገረ ስብከቱ በተዋረድ እንዲኖር ቢደረግ ለግንባታው ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ የሆኑ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በእድሳት ስም የነበራቸውን የታሪክ አሻራና ቅርስነታቸውን እንዳያጡ በማድረግም ትልቅ አስተዋጽኦ

ይኖረዋል። መዋቅሩ ካለ ማጠናከር ነው። ይህም ለልማታዊ እቅዱ ስኬታማነት የማይናቅ ሚና ይኖረዋል የሚል ግምት አለኝ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ብዙ የሚጠቀሱ አባባሎች አጋጥመውኛል። «የምእመናን ድህነት የቤተክርስቲያን ድህነት ነው። ደሀ አባላት ያላት ቤተ ክርስቲያን ደሀ ናት «ድንቅ አባባል ነው። ይህን አባባል በሌላ አገላለጽ ማጠናከር ይቻላል። ህብረተሰቡን ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች የድህነት ቀንበር ተጭኖታል። ድህነት ያጠቃው ሰው ሞራል የለውም። ሞራል የሌለው ሰው ደግሞ ሃይማኖት ሊኖረው አይችልም። ወይም ችግርን በሥራ ማሸነፍ ያልቻለ ሰው አይደለም ሌላውን ሰው፣ አይደለም ሃይማኖቱን፣ አይደለም ቤተክርስቲያንን ራሱንም አይወድም። ምክንያቱም በችግር ምክንያት አንገታቸውን ወደ ገመድ የሚያስገቡ ብዙዎች ናቸውና።

የማይቀር እዳ መሆኑ እየታወቀ ሰው በሞተ ቁጥር ሞትን በመሪር ኀዘን የማስተናገድ ባህላችን የራሱ የሆነ ተጽእኖ እንዳለው ተጠቁሞ ጥሪታቸውን በማሟጠጥ ለመጽናናት የሚሞክሩትን ሁሉ ለማህበረሰቡ የቅርብ ደራሽ የሆኑት ካህናት ከፍተኛ የማጽናናት ሥራ መሥራት እንዳለባቸው የተቀመጠው ነጥብ ተቀባይነት ያለው ነው። ከዚህ በማያያዝ ጸሐፊው ባህል ለእድገት መሠረት መሆኑን አውስተው ለባህላችን መሠረቱ ሃይማኖት ነው ይላሉ። እዚህ ላይ ግን በዚህ ሀሳብ ለመስማማት እቸገራለሁ። እርግጥ በባህልና በሃይማኖት መካከል ትስስር እንዳለ ማንም አይጠራጠርም። ግን በእኔ እይታና አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ሃይማኖቱ ለባህል መሠረት ነው ብሎ መናገር የሚቻል አይመስለኝም። ይህ ቢሆንማ ከላይ የዘረዘርናቸውን ችግሮች ማንሳት አልነበረብንም። ባህሉ በሃይማኖት ላይ ቢመሠረት ኖሮ አሥርቱ ትእዛዛት ተሽረው እርስ በእርስ መገዳደል ባልነበር። አንዱ የሌላውን ገንዘብ መስረቅ፣ የጓደኛውን ሚስት መመኘትና የመሳሰለው ሁሉ ባልነበረም ነበር። ያነሳናቸው ችግሮች ሁሉ የሚያመለክቱን መጀመሪያ ባህሉ በሃይማኖት ላይ ተመሥርቶ በዘመናት ሂደት በሰዎች አስተሳሰብ /አእምሮ/ ውስጥ ብዙ ቦታ እንደወረሰ ነው። በሌላ በኩል ከጥንቱ የባዕድ አምልኮ የተወረሱ ባህሎችም አሁን ድረስ እንዳሉ መዘንጋት የለበትም።

9. የጽሑፉ ማጠቃለያ

በጽሑፉ ማጠቃለያ ቁልፍ የሆኑ መፍትሔዎች ተቀምጠዋል። ባለንበት ክፍለ ዘመን በተለይ በክርስትናው ዓለም መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ተቋማት መሆናቸውና ሕዝቦችን በእኩልነት ለማስተዳደር የተወከለ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንደማይገባ በየሀገራቱ ሕግጋተ መንግሥታት ላይ ሰፍረዋል። ጸሀፊው ከዚህ በመነሳት ይመስለኛል መንግስት የሃይማኖት ጉዳይ አያገባኝም ብሎ የሃይማኖት ተቋማትን ችላ እንዳይላቸው እያሳሰቡ ያሉ። ችላ ማለቱ አደጋ እንደሚኖረውም ባሳሰቡበት አገላለጻቸውም፣ ሃይማኖቶች ችላ በመባላቸው የሚመጣው ዕድገት አክራሪነት መሆኑን አስምረውበታል።

የሃይማኖት ተቋማት አቅማቸውን ማጎልበት እንዳለባቸውም መክረዋል - ፀሐፊው። የእምነት ተቋማቱ አቅማቸውን ካልገነቡ የአባላቱ ከአንዱ ወደሌላው እምነት የመግባት ጉዳይ ማህበራዊ ግንኙነትን ከማላላት አልፎ ወደ ቅራኔ እንደሚወስድም አስጠንቅቀዋል። እነዚህ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉበት ዋናው ዓቢይ

መፍትሔ የካህናቱን አቅም ማጎልበት ነው ይላል ጽሑፉ። በእኔ በኩል ተጨማሪ አስተያየት አለኝ። ስለቤተክርስቲያኒቱ ታሪክ መግቢያው አካባቢ በቀረበው ዘገባ 500.000 ካህናት እንዳሏትና ይህም ከአለም ብቸኛዋ እንደሚያደርጋት ተገልጿል። እዚህ ላይ የጥራትም ጉዳይ መነሳት ይኖርበታል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የቀሳውስትና የዲያቆናት ሚመት በጅምላ የሚሰጥ እየሆነ እንደመጣ፣ ህዝብን ማስተማር ቀርቶ ሕሊናቸውን መምከር የማይችሉ ቀሳውስትና ዲያቆናትም እንዳሉ ከብዙዎች የሚሰጥ አስተያየት ነው። ሚመተክህነትን በተመለከተ ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ በጻፈው መልዕክት የተቀመጠው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሚመተ ቅስና እና ዲቁና የሚያበቁ መስፈርቶችን ቅዱስ ሲኖዶሱ ቢያዘጋጅ መልካም ነው እላለሁ። ይህ ከሆነ ጸሐፊው እንዳሉት ለባህላዊው ትምህርት አዲስ ስርዓተ ትምህርት በመቅረጽ፣ በማስተማርና ተከታታይ ሥልጠናዎችን በመስጠት ብቃትና ሃይማኖታዊ ሥነምግባር ያላቸውን ካህናት በቀላሉ ማብዛት ይቻላል።

ካለፉት ሦስትና አራት አስርታት ዓመታት ጀምሮ ወይም ቀደም ብሎ ቤተክርስቲያናችን ጠብቃ ያቆየቻቸው ታሪካዊ ቅርሶቻችን እየተዘረፉ ለባዕዳን መበልጸጊያ ሲሆኑ፣ እኛ ግን የማንነታችን መገለጫ የሆኑ ቅርሶቻችንን በማጣታችን የታሪክ ክስረት እየደረሰብን ነው። በዚህም ሥነምግባር የጎደላቸው የአንዳንድ ካህናት እጅ እንዳለበት ህብረተሰቡ ያምናል። ስለዚህ ጥራት ያላቸው፣ የሠለጠኑና መስፈርቱን የሚያሟሉ ካህናት እንዲተኩ ማድረግ እነዚህንና መሰል ችግሮችን ይቀርፋል። ለልማቱም አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

10. የቤተክርስቲያኒቱ ሁለንተናዊ ውለታ

የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ባለውለታ መሆኗን በማጠቃላያው ማንሳት አስፈላጊ መሰለኝ። ጸሐፍ አቅራቢው አቶ ሥርግው በመግቢያው አካባቢ ይህን ጉዳይ ጠቅለል ባለ መልኩ አንስተውታል። የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ለትምህርት ዋና ማዕከል ሆና ማገልገሏ ለሀገሪቱ ሥልጣኔ መሠረት የሆኑ ሃይማኖታዊ ሥነ ጥበቦች፣ ተግባረእድ፣ ሥነ ስዕልና ስነ ጽሑፍ፣ የሙዚቃ፣ የቅኔ፣ የሕግና የባህል መድኃኒቶችም ሳይቀሩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት እንቅስቃሴ ውጤቶች መሆናቸው በጽሑፉ ቀርቧል። እነዚህን ዓበይት ታሪካዊ የቤተክርስቲያን እሴቶች ትንሽ ዘርዘር አድርጌ ለማቅረብ እወዳለሁ።

የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሲባል ብዙዎች ነገረ ሃይማኖት ወይም ቅዳሴ ብቻ መስሎ ይሰማቸው ይሆናል። የቤተክርስቲያን ትምህርት ሁለንተናዊ እውቀትን የሚያስጨብጥ ነው። መሠረቱ ነገረ መለኮት ቢሆንም የሰው ልጅን አመጣጥ፣ የዓለምን ተፈጥሮ፣ የሥነ ተፈጥሮን መስተጋብር፣ ታሪክን፣ የሂሳብ ስሌትን፣ ሙዚቃን፣ ጥበበ እድን፣ የዘመናት ቀመርን፣ ሥነ ምግባርን የባህል መድኃኒት ቅመማን፣ ቋንቋን፣ ቅኔን፣ ሥነ ጽሑፍን፣ ኪነ ሕንፃን ወዘተ... ያካትታል። የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ከ4ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ይህን ነው ለሕብረተሰቡ እያስተማረች እስከ ዘመናችን የዘለቀች።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ዛሬ በ21ኛው ምእተ ዓመት አይደለም ከአፍሪካ፣ ከአለም ለየት ብላ የምትታይባቸው ብዙ ሀገራዊ እሴቶች አሏት። ከነዚህም ሥነ ሙዚቃ አንዱ ነው።

ሀ. ዜማ፣ በ6ኛው ምእተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በአክሱም ከተማ የተወለደው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ የደረሳቸው የመንፈሳዊ ሙዚቃ /ዜማ/ ድርሰቶች አሁን ድረስ ዓለምን የሚያስደምሙ ናቸው። በሀገሪቱ ለባህላዊ ሙዚቃ ዕድገትም ከፍተኛ አስተዋጽ እንዳላቸው ማንም አይጠራጠርም። ዛሬ በሀገራችን እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራሱ ሆነ የሙዚቃ ቃና እንዳለው ሁሉ፣ ወይም በአንድ ብሔረሰብ የተለያዩ የሙዚቃ ስልቶች እንዳሉ ሁሉ የቅዱስ ያሬድ ዜማም በተለያዩ ዘመናት፣ በተለያዩ ማህበረሰቦች ስያሜ እየተሰጠው ሲዘምር ኖሯል። ለምሳሌ፤ የአጫብርና የወንጨር ዜማ በጎጃም፣ የተጉለት ዜማ በሸዋና በወሎ፣ ቆሜና የቤተልሔም ዜማ በጎንደር ይጠቀሳሉ።

ለ. ቅኔ፣ አንዳንድ የቀደሙ ሊቃውንት በሰምና ወርቅ ፣ በህብረ ቃል፣ በውስጠ ወይራ ወዘተ. የሚነገር ቅኔ የኢትዮጵያ ብቸኛ ሀብት ነው የሚል አመለካከት ነበራቸው። ይህን አባባል ለሥነ ጸሑፍ አጥኝዎች እንተወውና የቅኔ አባት ቅዱስ ያሬድ መሆኑ ሳይዘነጋ የግእዝ ቅኔ በኢትዮጵያ ትልቅ ቦታ እንዳለው መዘንጋት የለበትም። ለዘመናችን የስነ ግጥም እድገትም መሠረቱ የግእዝ ቅኔ ነውና።

ሐ. ሥነ ስዕል፣ ሀገራችን የሥልጣኔ ምንጭ መሆኗን ዓለም እንዲያውቅ ዛሬ አፍ አውጥተው የሚናገሩልን በድንጋይ ላይ፣ በየመጻሕፍቱ፣ በቤተ ክርስቲያን ግድግዳዎች ወዘተ. ላይ በረቀቀ የአሳሳል ዘይቤና የቀለም ቅብ በኢትዮጵያዊ ደም ግባት የተሳሉት ስእሎቻችን ናቸው። ከሰአልያኑ የጥንቶቹን ታሪክ መዝግቦ ባይቆየንም ከቅርቦቹ አለቃ ሉቃስ፣ አለቃ መዝሙረ ዳዊት፣ ነጋድራስ አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ፣ ሰአሊ አገኘሁ እንግዳና ዛሬ በሕይወት ያሉት ሰአሊ መንግሥቱ ቸርነትን መጥቀስ እችላለሁ። እነዚህና ቀደምቶቹ ሰአልያን በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተኮትኩተው ያደጉ ናቸው።

መ. ኪነ ሕንጻ፤ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ጎንደር የኢትዮጵያውያን አሻራዎች እንደሆኑ ይታመናል። አንድ ሰው አዲስ ነገር ለመፍጠርና አቅድ ለመሥራት ቢያንስ ማንበብና መጻፍ አለበት። ከላይ የጠቀስኳቸውን ታሪካዊ ሥራዎች ለመገንባት ሲታሰብ ንድፍ ያወጡና ያማከሩ በቤተክህነት ት/ቤት የተማሩ ሰዎች መሆናቸውን አንጠራጠርም። አስኳላ ትምህርት ያኔ የለምና። ከዚህ በላይ ያነሳኋቸው የኢትዮጵያን ጥንታዊ ገጽታ ለዓለም ያስተዋውቃሉ ያልኳቸውን ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውለታ በዚህ ብቻ አይገደብም። ቅርስን ጠብቆ በማቆየት በኩልም ትልቅ ባለውለታ ናት። ቤተ ክርስቲያኒቱ ራሷም ቅርስ መሆኗ አያጠያይቅም።

ሠ. **ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ**

- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የግእዝ ቋንቋን የሥራ ቋንቋዋ አድርጋ ማለትም፣ ለትምህርት፣ ለቅዳሴ፣ ለቅኔ ማመሳጠሪያነት እንዲውል በማድረግ እስካሁን ጠብቃ ማቆየቷ ለትውልዱ ትልቅ ባለውለታ ናት።
- የቤተክርስቲያኒቱ የነገረ መስኮት፣ የሥርዓትና የምስጋና መጻሕፍት ባብዛኛው ከእብራይስጥና ከአረብኛ የተተረጎሙ መሆናቸው ቢታወቅም ገድላትና ድርሳናት፣ መልክአ መልኮች ወዘተ... የኢትዮጵያውን ሥራዎች ናቸው። እነዚህ ሥራዎች ደግሞ ለዘመናችን የፈጠራ ድርሰቶች ማለት ለልቦለዱ፣ ለግጥሙ፣ ለድራማው፣ ለቲያትሩና ለፊልሙ መሠረቶች መሆናቸው የታመነ ነው። በተጠቀሱት ሙያዎች የመጀመሪያና ፈር ቀዳጅ ከሚባሉትም ውስጥ አብዛኞቹ ማለት ይቻላል ስማቸውን መጥቀስ ቢያስፈልግ አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ፣ ዮፍታሔ ንጉሴ፣ ተመስገን ገብሬ፣ መንግስቱ ለማ፣ አቤ ጉበኛ፣ ሓዲስ ዓለማየሁና ሌሎችም በነ "የኔታ ጉባዔ ቤት" አትሮንስ ዘርግተው የተማሩ ናቸው።

ረ. የባህል መድኃኒት ቅመማ፣ የባህል መድኃኒት ከጥንቆላ ተለይቶ መታየት አለበት። ጥንቆላ መናፍስትን መጥራትና ሰውን የሚጎዳ ሰይጣናዊ ሥራ መሥራት ነው። በራሱም አምልኮ ባዕድ ነው። እርግጥ ይህን ዕኩይ ተግባር የሚፈፅመው ተራውና ያልተማረው ሰው አይደለም። በቤተክህነት ት/ቤት የተማረው ወይም ሊቅ የሚባለው ሰው ነው። ይህ ደግሞ ሊያስገርመን አይችልም። ምክንያቱም ዛሬ በሥለጠነው ዘመን፣ በሥለጠነው ዓለም በዘመኑ ትምህርት ሳይንሳዊ ዕውቀት ካገኙት ምሁራን መካከል የሰውን ዘር የሚያጠፋ የኒኩሊየር ቦምብና ባዮሎጂካል መሣሪያ ለማምረት ሌት ተቀን ተግተው የሚሠሩ «አዋቂዎች» አሉና።

የባህል መድኃኒት ግን በአብዛኛው ከዕፀዋትና ከሌሎች ተፈጥሮአዊ ነገሮች የሚቀመም መድኃኒት ነው። ዛሬ ብዙ ገንዘብ እያወጣን የምንገዛው ክኒን፣ ፈሳሽ መድኃኒትና ጠብታ፣ ወይም የሕመም መፈወሻና ማስታገሻ የምንለው ሁሉ በፋብሪካ ተዘጋጅቶ መቅረቡ ካልሆነ በስተቀር ከላይ ከጠቀስኳቸው ነገሮች የሚዘጋጅ መሆኑ ከማንም የተሠወረ አይደለም። **የኢትዮጵያ ኦ/ተ.ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በነበራቸው እውቀት ባህላዊ መድኃኒቶችን በማጥናትና በመቀመም ለዘመናት ህብረተሰቡን ሲያክሙ ኖረዋል።**

ሰ. ሥነመንግሥት፤ ሀገራቱን ለዘመናት ከመሩት ነገሥታት አብዛኛዎቹ በቤተክርስቲያን ትምህርት ከፍተኛ ዕውቀት የነበራቸው ናቸው። ከዚህም ሌላ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ፍትሐ ነገሥት የተባለውን የመንፈሳዊና የሥጋዊ አስተዳደር ሕግ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ቋንቋ በመተርጐም ዓለም-0ቀፍ ይዘት ያላቸው ብሔራዊ ሕጐች እስከተዘጋጁበት 1940ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ድረስ ሀገሪቱ እንድትመራበት አድርገዋል። በዚህም ቤተክርስቲያኒቱ ለሥነ መንግሥትና ለሥነ ሕግ ማደግና መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክታለች ማለት ነው። በሌላም በኩል በፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓቱ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ የነበራቸው የቤተ ክህነት ምሁራን ናቸዉ።

ከፍልስፍና አንፃር፣ ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ዘርዐያዕቆብ አክሱማዊ ፍልስፍናውን ይዞት አልተወለደም። ከቤተ ክህነት ት/ቤት ባገኘው ዕውቀት ላይ ተመሥርቶ ባደረገው ምርምር እንጅ።

ቀ. አማካሪነትና ጀግንነት፣ የቤተክርስቲያኒቱ ሊቃውንት ለነገሥታቱና በየተዋረዱ ለነበሩ የአስተዳደር ስዎች የቅርብ አማካሪዎችም ነበሩ። የውጪ ወራሪ ኃይል ሲመጣም ወረቀት አቅራቢው በግልጽ

እንዳስቀመጡት «ነፂ ሀገር ከሌለች ነፂ ሃይማኖት አይኖርም» እያሉ ሕዝቡን በመቀስቀስ አዋግተዋል። እነሱም ተዋግተዋል። ለዚህም የቅርብ ጊዜውን ታሪክ መጥቀስ ይቻላል። ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በአዲስ አበባ፣ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በጎሬ የከፈሉት መሥዋዕትነት ለጀግኖች አባቶቻችን ከፍተኛ የሞራል ስንቅ ሆናቸው ዘመናዊ መሳሪያ ታጥቆ የመጣውን የኢጣሊያ ወራሪ ጦር በአምስት ዓመታት ውስጥ ጠራርገው ሊያስወጡት ችለዋል። ሌላም የሚጠቀሱ አርበኛ አሉ። የየካ ሚካኤል አስተዳዳሪ የነበሩት አለቃ መርሻ ወ/ማርያም ወራሪውን የኢጣሊያ መንግሥት በይፋ ይቃወሙ ስለነበረ አስገዳጅ ወታደሮች ወደ መኖሪያቸው መጥተው ሊወስዷቸው ሲሉ «ወግድልኝ ድጓ ወግድልኝ ቅኔ፤ ጀግኖች ከዋሉበት መዋሌ ነው እኔ» በማለት ሶስቱን ብሉቅባሽ በሽጉጥ ካንበረከኩት በኋላ ለሀገራቸው መሥዋዕት መሆናቸው ይነገራል።

እንግዲህ እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ሲታሰቡ የኢትዮጵያ ኦ/ተ.ቤተ ክርስቲያንን ለሕዝቡ ትልቅ ባለውለታ ያደርጋታል። ጽሑፍ አቅራቢው ከዚህ በመነሳት ይመስለኛል ቤተ ክርስቲያኒቱ ቸል እንዳትባል አንጽንኦት ሰጥተው ለማስገንዘብ የፈለጉ። እኔም በበኩሌ ቤተክርስቲያኒቱ የሕዝቡን የልብ ትርታ እያዳመጠችና መሻሻል ላለባቸው ነገሮች ትኩረት እየሰጠች ልታሳካቸው ያቀደቻቸውን ሀገራዊ የልማት ሥራዎች ከግብ እንድታደርስ መንግሥትም ሆነ ህብረተሰቡ ከጎኗ ሊሰለፍ ይገባል በማለት አስተያየቴን አጠናቅቃለሁ።

አመሰግናለሁ!

በአቶ ሥርግው ገላው ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

በኩረትጉሃን አለም አታላይ[1]

ጸሐፊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ያበረከተችውን የረዥም ዘመን ታሪካዊ ሥራ በሙሉ ማቅረብ ባይቻልም የተወሰኑትን አጉልተው በማሳየታቸው ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበርም ይህንን የመሰለ ትልቅ ሀገራዊ የውይይት አጀንዳ አዘጋጅቶ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ዜጎች እንዲነጋገሩበት በማደረጉ ሊመሰገን ይገባል፡፡

በመጀመሪያ የጽሁፉን ይዘትና መልዕክት በመቀጠልም በጽሁፉ ውስጥ ያልተካተቱ አንዳንድ ነገሮችን በመጨመር አስተያየቴን እቀጥላለሁ፡፡

ጽሁፉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ከመጀመሪያው መቶ ዓመት ጀምሮ እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በትምህርት፣ በሥነ ጽሁፍ፣ በሥነ ጥበብ፣ በተግባረ እድ፣ በሥዕል፣ በቅርጻ ቅርጽ፣ በሕግ፣ በቅኔ፣ በዝማሬና በመሳሰሉት ሁሉ የሥልጣኔ መሠረት የጣለች፤ እንደ ትምህርት ማዕከል በመሆንም የሕዝቡን ሞራልና ሥነ ምግባር በትምህርት ገንብታ ጥንታዊው ኢትዮጵያዊ ለሀገሩና ለሐይማኖቱ እኩል እንዲያስብና ፍቅር እንዲኖረው ያደረገች መሆኗን ያስረዳል፡፡

ቤተ ክርስቲያኗ ከ40 ሚሊዮን በላይ ምዕመናን ከአምስት መቶ ሺ በላይ ካህናት ያሏት በሀገሪቱ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ተንሰራፍታ የምትገኝ ትልቅ ተቋም ስትሆን የዓለምና የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤቶች መሥራች አባል እንደሆነችም ጽሁፉ ያመለክታል፡፡

ልማት ኮሚሽንና የሕጻናት ማሳደጊያ ማዕከል በሚባሉ ሁለት ድርጅቶቿ አማካይነት ከውጪ በሚገኝ ዕርዳታ ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ መገኘቷም በዘገባው ተካቷል፡፡

ስለ ሠላም የምትጸልይና የምታስተምር በተለይም ከእስልምና እምነት ጋር ለሌሎች አርአያነት ያለው ተከባብሮና ተቻችሎ የመኖር ባሕል ያዳበረች የተጣላን የምታስታርቅና ለተቸገረ ምፅዋት መስጠትን የምትሰብክ የማይሠራ አይብላ እያለች ስንፍናን የምታወግዝ ተቋም መሆኗ በጥናቱ ተዘግቧል፡፡
ቤተክርስቲያኗ በአሳለፈችው የረዥም ጊዜ ታሪክ ለሀገሪቱ ያበረከተቸውን አገልግሎት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቢሆንም፣ በበዓል ቀን መብዛት ምክንያት የሀገሪቱን እድገት ማፋጠንና የሕዝቡን ኑሮ መለወጥ

[1] በኩረትጉሃን አለም አታላይ በአሁኑ ጊዜ በቤተክህነት ቅርሳቅርስ መምሪያ ምክትል ኃላፊ ሲሆኑ ከዚህ በፊት በተለያዩ ቦታዎች በኃላፊነት አገልግለዋል። በኩረትጉሃን አለም አታላይ በቤተክህነት ትምህርት ረዥም ጊዜ ያሳለፉ ሲሆን በዘመናዊው ትምህርት የሁለተኛ ደረጃን አጠናቀዋል።

አለመቻሉን እንዲሁም ቅጥ እያጣ ያመጣውን የሐዘንም ሆነ የደስታ አፈጻጸም ሥርዓት መልክ ማስያዝ እንደሚ ያስፈልግ ጥናቱ ጠቁሞ ይህች ጥንታዊትና ብሔራዊት ቤተክርስቲያን ካህናትን እያሰለጠነች ሕዝቡን እንዲያስተምሩ በማድረግ ጎታችና ኋላቀር ልማዶችን በማስወገድ የ2020ን የልማት ራዕይ ተግባራዊነት ልታግዝ እንደሚገባት በማሳሰብ የጽሁፉ መልዕክት ተጠቃሏል፡፡

የጽሁፉ ርዕስ ተግባራዊነት ያተኮረው በውጪ እርዳታ የሚንቀሳቀሱት የቤተ ክርስቲያኗ የልማት ድርጅቶች (ልማት ኮሚሽንና ሕጻናት ማሳደጊያ) የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች በተመለከተ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በጽሁፉ ውስጥ ያልተካተቱ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ስለምትገኝ ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም ጎላጎላ ያሉትን ብቻ መጨመር እፈልጋለሁ፡፡

1. ቤተ ክርስቲያኗ መንፈሳዊና ማህበራዊ አገልግሎት የምትፈጽምባቸው በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሥር 44 አህጉረ ስብከት፣ 511 የወረዳ ቤተ ክህነት፣ 40000 የአጥቢያ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤቶች፣ 40 ሚሊዮን ምዕመናን አሏት፡፡
1. ሁለት ኮሌጆች፣ 23 የካህናት ማሠልጠኛዎች፣ ከአጸደ ህጻናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ በርካታ መደበኛ ት/ቤት ከፍታ ታስተምራለች፣ ታሰለጥናለች፡፡
2. በ44ቱ አህጉረ ስብከት ሥር የልማት ክፍል በመክፈት በካህናትና ምዕመናን የገንዘብ፣ የጉልበትና የዕውቀት ድጋፍ በግብርናው፣ በጎጆ ኢንዱስትሪውና በጤናው ዘርፍ አያሌ የራስ ገዝ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ትገኛለች፡፡
3. በየሰበካ ጉባኤው ጽ/ቤት ሥር የሰንበት ት/ቤተ በመክፈተ ከ2 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ወጣቶችን አደራጅታ ታስተምራለች፡፡
4. በየሰበካው ጽ/ቤት በተለያየ ምክንያት ችግር ለደረሰባቸው ዜጎች ልዩ ልዩ የእርዳታ አገልግሎት ትሰጣለች፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ቤተክርስቲያኗ ከጥንት ጀምሮ በሀገሪቱ ሁለንተናዊ የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበራትን የጎላ ተሳትፎ አሁንም ቀጥላለች የሚያሰኙ እውነታዎች ቢኖሩም ለልማት ግንባታውና ለድህነት ቅነሳው የበለጠ አስተዋጽኦ ስለሚጠበቅባት እቅዶችን በንድፍና የሥልጠና ፕሮግራሞችን በመዘርጋት የአፈጻጸም ሥልት ቀይሳ ሰፊ ሥራ ለመሥራት ጥረት እያደረገች ነው፡፡

የቤተክርስቲያኗ የሥራ እንቅስቃሴ በጥቅል ሲታይ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ሆኖ ሳለ ቤተክርስቲያኗ በበዓላትና ኋላ ቀር በሆኑ ልማዶች ምክንያት በልማቱ ሥራ ላይ አሉታዊ ጫና እንደምትፈጥር የሚናገሩ ሰዎች ስለአሉ አንዳንድ ነገሮችን ማንሳት እፈልጋለሁ፡፡

በዓል፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያ የበዓላት አከባበር ሥርዐት በቀኖናዋ ውስጥ ለይታ አስቀምጣለች፡፡ በአቆጣጠር ድግግሞሽ ብዙ ናቸው እየተባለ ይነገራል እንጂ ቤተ ክርስቲያኗ ይምታከብራቸው አበይት በዓላት በዓመት ውስጥ 35 ቀናት ብቻ ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው ገበሬው 365 ቀናት በሬ ጠምዶ አያርስም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በነዚህ 35 የበዓል ቀናት በሬ ጠምዶ አይረስ አንጂ እጅ እግሩን አጣምሮ ይቀመጣል ማለት አይደለም፡፡ በበዓል ቀን መንፈሳዊና ማሕበራዊ

አገልግሎት ይፈፅማል ያስፈፅማል፣ የታመመ ይጠይቃል፣ የተጣላ ያስታርቃል፣ ዘመድ ይጠይቃል፣ ወደ ገበያ ሄዶ የሚፈልገውን ይሸጣል፣ ይገዛል፣ ቤት ይሠራል፣ አጥር ያጥራል፣ እህል ይሰበስባል፣ ይከምራል፣ አውድማ ያዘጋጃል፣ ለከብቶቹ መኖ ያቀርባል፣ ከብቶቹን ይመግባል፣ ይህንና የመሳሰለውን ሥራ ሁሉ የሚሠራው በበዓል ቀን ስለሆነ ለትጉህ ሰው ሥራ የማያሰራ በዓል አለመኖሩን ከዚህ መረዳት ይቻላል፡፡

በመሠረቱ ለድህነታችን ተጠያቂ የሚሆነው በዓል ሳይሆን ጠንካራ የነበረው የአባቶቻችን የሥራ ባህል አሁን በመጥፋቱ ነው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ የቀድሞዎቹ አባቶቻችን ከአሁኑ ትውልድ በተሻለ መልኩ በዓል እያከበሩ ጠንክረው በመሥራታቸው ብቻ ከዓመታዊ ፍጆታቸው አልፎ የተትረፈረፈ ድግስ በመደገስ አላፊ አግዳሚውን ሲመግቡና ለአሥር ዓመት የሚበቃ እህል በንተራ ያከማቹ ነበር፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ከላሊበላ ህንፃ ጀምሮ የሌሎች አድባራትንና ገዳማት ዕጹብ ድንቅ የሚያሰኝ የተራቀቀ የሥራ ውጤትና ጥበብ ስንመለከት የአባቶቻችን የሥራ ባህልና ጥንካሬ ምን ያህል ያደገ እንደነበር እንረዳለን፡፡ ይህ ጠንካራ የነበር የሥራ ባህል በአሁኑ ዘመን በመጠጥ (በስካር)፣ በጫት (በሐሺሽ)፣ በልመና፣ በፊልምና በተለያየ መንገድ ከውጭ ወደ ሀገር ያለገደብ በሚገቡ ርካሽ ባህሎች እየዘቀጠ በመምጣቱ የድህነት ሰለባዎች ሁነን የጥገኝነት ኑሮን በመግፋት ላይ እንገኛለን፡፡

ማህበርና ሰንበቴ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ራሷ የማህበራዊ ኑሮ ትምህርት ቤት ናት ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በጎ አድራጎትና ማህበራዊ የህብረት ሥራ የሚከናወንባት፣ የማህበራዊ አኗኗር ትምህርት የሚሰጥባት ተቋም በመሆኗ ነው፡፡

በዚህም መሠረት ክርስቲያኖች በበዓል ቀን በየቤተክርስቲያናቸው እየተሰበሰቡ ስለ ኑሮአቸውና ስለ አካባቢያቸው በመምከር፣ ስለቤተ ክርስቲያናቸውና ስለ ሀገራቸው በመወያየት፣ በቅዱሳን ስም የተዘጋጀውን ፀበል ጸዲቅ ከድሆች ጋር በአንድነት በመቋደስ ይሳተፋሉ፡፡ በዚህም ማህበራዊ አንድነታቸውንና ፍቅራቸውን አጽንተው ስለሚኖሩ የሚዘጋጀው ፀበል ጸዲቅ ከአቅም በላይ እንዳይሆን ከተደረገ የሚደገፍ አንጂ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

ሀዘንና ለቅሶ፣ የሚወዱት ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ቢሆንም ሀዘንተኞች እንዲጽናኑና እንዲረጋጉ የሚያደርግ መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጣል እንጂ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የመረረ ሀዘንና ለቅሶ አይፈቀድም፡፡ ፊትና ፀጉር እየነጨ፣ ልብስ እየቀደዱ፣ ደረት እየደቁ፣ አስለቃሽ አቁሞ ሙሾ እየደረደሩ ማልቀስ ጎጂ ልማድ በመሆኑ ቤተክርስቲያኗ አወግዛለች፡፡ ሆኖም ይህ አጉል ልማድ የሥራ ጊዜንና ከፍተኛ ወጪን በሚጠይቅ መልኩ ቀጥሎ ስለሚታይ ቤተክርስቲያኗ ቀጣይነት ያለው ሰፊ ትምህርት ልትሰጥበት እንደሚገባ ይታመናል፡፡

ሐውልትና የአበባ ጉንጉን፣ የመቃብር ቦታዎች ደስ በሚያሰኙ አበባዎችና ዕጽዋት አጊጠው፣ በንጽህና ተጠብቀው መታዘ ሲገባቸው የሚች ቤተሰቦች የሚረዱበትን ከፍተኛ ገንዘብ እያወጡ በመቃብር ቦታ ላይ ሐውልትና ለማኅበራዊ አገልግሎት የማይውል ህንጻ በመገንባት የመቃብር ቦታ ከማጣበብ በቀር

ለሚችም ሆነ ለቋሚ የሚሰጠው ጥቅም የለም፤ ቤተክርስቲያን ባላት ሥርዓት መሠረት በመካነ መቃብር ላይ ለሚቾች ጸሎት ታደርጋለች እንጂ በመቃብር ላይ የአበባ ጉንጉን እንዲቀመጥ፣ የሐውልት ምረቃ እያሉ ህዝብን ሰብስቦና ሐውልቱን ግምጃ አልብሶ ፀሎት እንዲደረግ አታዝም፡፡ የተፈቀደም አይደለም፡፡ ይህ የአበባ ጉንጉን የማስቀመጥ እና የሐውልት ሥራ ግንባታ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ያፈነገጠ በመሆኑ ከጎጂ ልማድ ተለይቶ አይታይምና ቤተክርስቲያን በትምህርት ልትከላከለው ይገባል የሚል አመለካከት አለኝ፡፡

ተስካር፣ ተስካር የሚለው ቃል መታሰቢያነትን የሚያመለክት ነው፣ የሙታን መታሰቢያ ዓይነቱና ይዘቱ ብዙ ቢሆንም በቤተ ክርስቲን ውስጥ የሚደረገው የተስካር መታሰቢያ መንፈሳዊ ዓላማ ይዘት አለው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ስለ ሙታን ነፍስ ትፀልያለች፣ ትማልዳለች፣ ወዳጅ ዘመድም በሞቱት ሰዎች ስም እንዲጾሙ እንዲጸልዩ ለችግረኞም ምጽዋት እንዲሰጡ ታሳስባለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቅዱስ መጽሐፍን መሠረት በማድረግ ምዕመናን አስራት ብኩራት እንዲያወጡ ታዛለች፡፡ ይህም ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ቤተክርስቲያን የሚችን ድግስ ደግሰው ትልቅ ግብዣ አዘጋጅተው ተስካር እንዲያወጡ አላለችም፡፡ ከጥንት ጀምሮ ምዕመናን በፈቃዳቸው ሲፈጽሙት የቆየ ልማድ እንጂ ከቤተክርስቲያን ቀኖና ጋር ግንኙነት የለውም ሆኖም ምዕመናን ከሙታን መታሰቢያነት ጋር አያይዘው ስለሚፈጽሙት መንፈሳዊ ይዘት ያለው ይመስላላና በአሁኑ ዘመን ከጊዜም ሆነ ከወጪ አኳያ ሲታይ ጉዳት ያለው ልማድ መሆኑን ገልጾ በማስተማሩ በኩል የቤተክርስቲያኗ ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ መናገር ይቻላል፡፡

ጋብቻ፣ ጋብቻ የቤተሰብና የህብረተሰብ መሠረት በመሆኑ ልዩ ክብር ሊሰጠው የሚገባ ነው፣ ቤተክርስቲያንም የጋብቻ መሠረት የፀና እንዲሆን ለማድረግ ጋብቻው በተክሊልና በቁርባን እንዲፈጸም ታስተምራለች፡፡ ጋብቻ ትልቅ ማኅበራዊ ዓላማ ያለው የሕብረተሰብ መሠረት ስለሆነ ከአቅም ጋር የተመጣጠነ ዝግጅት ለሠርጉ (ለክብረ በዓሉ) መገለጫ አያስፈልግም ባይባልም ከማን አንሼ በሚመስል መልኩ ከአቅም በላይ የሚደረገው የሠርግ ድግስ በቤተክርስቲያን ትምህርት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ስለዚህ ቤተክርስቲያን ህጋዊ ጋብቻ እንዲፈፀም ትመክራለች፣ ታስተምራለች እንጂ አቅምን ያላገናዘበ ድግስ እንዲደገስ አትፈቅድም፡፡

ልመና፣ በአሁኑ ጊዜ ልመናን እንደ መደበኛ ሥራ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ዜጎች ቁጥር ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ይህንን ቅጥ ያጣ የልመና ባህል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አንደምታበረታታ የሚናገሩ ሰዎች መኖራቸው ይሰማል፣ ቤተክርስቲያኗ አሳዳጊ የሌላቸውን ህጻናት፣ ጧሪ የሌላቸው አረጋዊያን፣ መሥራት ለማይችሉ የአካል ጉዳተኞች፣ በድንገተኛ አደጋ ሀብት ንብረታቸውን ለአጡ ወገኖች ምዕመናን ዕርዳታ እንዲያደርጉ ታስተባብራለች፣ ከዚህ ውጭ ግን የመሥራት አቅም ያለው የሰው ልጅ ሁሉ ላቡን አንጠፍጥፎ ሠርቶ መጠቀም እንደሚገባው ነው የምታስተምረው፡፡

ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ያላት የበጀት አቅም ከምታከናውነው መጠነ ሰፊ መንፈሳዊና ማሕበራዊ አገልግሎት አንፃር ሲታይ እጅግ አነስተኛ ቢሆንም የምዕመናን ገንዘብ ጉልበትና ዕውቀት በማስተባበር ፀሐፊው በዕሁፋቸው መጨረሻ ገጽ ከተራ ቁጥር 1-9 ድረስ ያስቀመጧቸውን የሥራ ዘርፎች ሁሉ ከወዲሁ ጀምራ በሰፊው እየተንቀሳቀሰች መሆኗን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች ስለአሉ በመላ ሀገሪቱ ተንቀሳቅሶ መሥራት የሚያስችል ሠላምና መልካም አስተዳደር ከተገኘ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከማህብረሰቡ ጋር ተቀናጅቶ መሥራት ከተቻለ የ2020 የልማት ራዕያችን ግቡን ይመታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

አመሰግናለሁ

እስልምና እና ልማት በኢትዮጵያ[1]

መሐመድ አሕመድ ሸሪፍ[2]

1. መግቢያ

የተሰጠኝ የውይይት ርዕስ "እስልምና እና ልማት በኢትዮጵያ" ሰፊ እንደመሆኑ ስፋቱን በጥልቀት ለማስታረቅ እሞክራለሁ። ርዕይ ምንጊዜም ቁልጭ ብሎ መታየትን ስለሚጠይቅ ድንበሮቹና ክፈፎቹ ግልጽ እንዲሆኑ ይገባል። በመሆኑም ጽሑፌን በአምስት ጠለቅና ምጥን ባሉ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ክፍሎች ለይቼ አቀርባለሁ።

የእስልምናና የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ትውውቅ መንፈስ በዓለም አቀፍ ደረጃ አርያና ተምሳሌት ያተረፈ እንደነበረ ቀጥሎም ከ7ኛው ምዕተ-ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ጀምሮ እስከ 19ኛው ምዕተ-ዓመት መገባደጃ የነበረውና ያሳለፋቸው ግንኙነት፣ ይዘት፣ መስፋፋትና የታሪክ ውጣ-ውረድ ክስተቶች በአጭሩ፤

የሚሊኒየሙ መጨረሻ ምዕተ-ዓመት ፊዩዳላዊና ንጉሣዊ እንዲሁም የወታደራዊ አገዛዝ የፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊና አስተዳደራዊ ሥርዓቶች እና የሙስሊሙ ህብረተሰብ አኗኗርና አጠቃላይ የዜግነት ሁኔታ፤

የ1987 ፌዴራላዊ ህገ መንግሥት የዲሞክራሲ የመልካም አስተዳደርና የልማት ዓላማዎችና መመሪያዎች እና በነዚህ ጉዳዩች ላይ የእስልምና መሠረታዊ መርሆዎች ንፅፅር፤

የሙስሊሙ ህብረተሰብ የልማት ተሳትፎ እድልና ከዚያም አልፎ በተጨባጭ ሊያስገኝ የሚችለው አገር አቀፍ እድገት በአንጊሩም መቋቋም የሚገባቸው አስፈላጊ የSocio-economic መሠረተ-ልማቶች እና፤

በ2020 ለኢትዮጵያ ያለኝ ርዕይ መልዕክትና ዐቢይ ተግባራት ጥቆማ፡ ሲሆኑ ለውይይት የማቀርባቸው ሀሳቦችና ነጥቦች የበለጠ ተጨባጭነት ይኖራቸው ዘንድ ምሥራቅና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ /ማለትም ከታላቁ ስምጥ ሸለቆ በስተምሥራቅ የሚገኘው ቀጠና/ እንደ ናሙና ማቅረብን እመርጣለሁ።

[1] መጋቢት 21 ቀን 1999 ዓ.ም የተካሄደ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡፡

[2] አቶ መሐመድ አህመድ በ1999 ከማንችስተር ዩንቨርሲቲ ከኢንግላንድ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በ1963 ከኘሪስቲን ዩንቨርስቲ ከአሜሪካ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሂሳብና ኬሚስትሪ ዲፖርትመንት ያስተማሩ ሲሆን Mathimatics for school የሚል የመማሪያ መጽሐፍ ከጓደኛቸው ጋር አዘጋጅተዋል። በአዲስ አበባ ባንክ ከ1965-1978 ዓ.ም. የማናጅመንት ቦርድ አባል ሆነው አገልግለዋል። በ Economic Research and Planning Department (ERPD) አማካሪ፣ የዘመቻ መምሪያ ይባል በነበረው መ/ቤት ከ1979- 1981 እ.ኤ.አ የውጭ ኢኮኖሚ ዲፓርትመንት ኃላፊ ነበሩ። የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ሆነውም አገልግለዋል። የሐረር መልሶ ግንባታ ማህበር መሣራችና ኘሬዝዳንት ሆነው አገልግለዋል። ከ1983 ወዲህ የመጀመሪያው የፖርላማ ተመራጭና የበጀት ቋሚ ኮሚቴ ተጠሪ ሆነው አገልግለዋል። በሁለተኛው ፖርላማ የአፈጉባኤው ጽ/ቤት አማካሪ፣ የእንባ ጠባቂና የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እጩ አቅራቢ ኮሚቴ ዋና አማካሪ ሆነው ሰርተዋል። ከ2004 - 2006 የሰብአዊ መብት ኮሚሽን አማካሪ ሆነው ሠርተዋል። በአሁኑ ሰዓት የግል አማካሪ ናቸው።

በዚህ ጽሁፍ ተለይቶ ካልተገለጸ በስተቀር የዘመን አቆጣጠር የተቀመጠው በጎርጎርዮስ ዘመን አቆጣጠር ነው።

2. መጀመሪያ እርምጃ እና ታሪካዊ እድገት

"ወደ ሐበሻ ብትሄዱ ይሻላል ንጉሡ ፍትሕ ያለው ንጉሥ በመሆኑ በእርሱ ዘንድ ማንም ሰው አይበደልም። ሌላውንም አይበድልም። ሀገሪቷም የሐቅ አገር ናት። አላህ ችግሮችን እስከሚያቃልል ድረስ እዚያው ቆዩ" በማለት ነቢዩ ሙሐመድ /ሠ.ዐ.ወ./ በእምነታቸው ምክንያት ከባድ ጥቃት የደረሰባቸውና ከፍተኛ ችግር ላይ የወደቁትን ተከታዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ላኳቸው።

ከተጓጉቹ መኻከል ታላቋ የነቢያችን አሳዳጊና የሐበሻ ተወላጅ ኡሙ-አይመን እንዲሁም 3ኛ ኸሊፋ የሆኑት ዑስማን ኢብን ዐፋን እና ጀዕፈር ኢብን አቢ ጣሊብ ይገኛሉ። ስደቱም የመጀመሪያና የሁለተኛ ስደት ተብሎ ሲታወቅ የስደተኞቹም ጠቅላላ ብዛት 185 የቆዩትም ለ15 ዓመታት /ከ604 እስከ 629/ ነበር።

የሐበሻም ነጋሽ ስደተኞቹን ተቀብሎ በሰላም እምነታቸውን ጠብቀው ሀገራቸው እስከሚመለሱ መጠለያ ሰጣቸው። የአገራቸው ሁኔታ ሲመቻችላቸው እቤታቸው ለመግባት በቁ። ይህ የንጉሡ ሥራ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያው ከሃይማኖትና እምነት ተጽእኖ ጥገኝነት Asylum for refugees against religious persecution የመስጠት አርአያ በመሆን ተመዝግቧል። በአንፂሩም ነቢዩ ሙሐመድ /ሠ.ዐ.ወ./ ለእስልምና ምእመናን ሁሉ ሐበሻ ላይ እስካልደረሱባችሁ ጥቃት አትሰነዝሩባት አትንኳት የሚል መርህ አስተላልፈዋል። በመሆኑም የእስልምናና የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ግንኙነት በፀጋ በመከባበርና በውለታ የታነፀ ነበር። በመርህ ደረጃ ኢትዮጵያ በስደተኛ ተቀባይነትና ጉርብትና አከባሪነት ስትታወቅ በሕዝቦቿ ደረጃ የሁለቱም እምነቶች ተከታዮች ወንድማዊ ፍቅር በተላበሰ የጋራ አኗኗር ፀንተው የቆዩ ክፋውንም ደጉንም ጎን ለጎን ያሳለፉና በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረው አብረው እንደኖሩ የውጭ ጥቃትንም በአንድነት የመከቱ ስለመሆናቸው ረጅሙ ታሪካቸው ይመሰክራል።

በምድረ ሸዋ ጨርጨር/ዝዋይ አካባቢ በ896 የሙስሊም ሱልጣን ግዛት ተመሠረተ። ሱልጣኑ የመጀመሪያው ሚሊንየም አልቆ አሁን እየተገባደደ ያለው ሁለተኛው ሚሊንየም መባቻ ላይ የይፋቱ ዋሊ አስመዕ ጋር የጣምራ መንግሥት /Alliance/ በመፍጠር ግዛታቸው ከኤደን ሰላጤ እስከ አዋሽ/ጨርጨር ተፋሰስ ያለውን አገር አጠቃለለ። በአጠቃላይ በሸዋ የተፈፀመው ይህ ውህደትና የመስፋፋት እንቅስቃሴ በሰሜን ኢትዮጵያ የአገው ሥልጣን /ሥልጣነ ዛግዌ/ መጠናከርና የመስፋፋት ዘመቻዎች ጋር ይዛመዳል። የሱልጣኖቹ ግዛት መስፋፋቱን ቀጥሎ በ1285 የይፋቱ የገናናው ዋሊ አስመዕ ልጅ የሸዋውን ንጉሥ በማሸነፍ ብቸኛ ገዥ ለመሆን በቃ። በ1344 ማለትም ከአጼ አምደጽዮን ሞት በኋላ የሙስሊሙ ሱልጣኔት ከአጼው መንግሥት ጋር ቁርኝቱን ጠብቆ እያለ በሌላ በኩል የራስ ገዝ ሥርዓትን በጥቅሉ በአፍሪቃ ቀንድ የአጼዎቹን ሥልጣን የሚቀናቀን ኃይል አቋቋመ።

በተከታታይ ዓመታት በተካሄዱት የሁለቱ መንግሥታት የሥልጣንና የግዛት ማስፋፋት ትግልና ጦርነት በአመዛኙ የሱልጣኖቹ ኃይል እየተዳከመ በመምጣቱ በ1415 ላይ ሱልጣኑ ግዛቱን የዐዳል ሱልጣኔት ብሎ በመሰየም ወደ ደከር /ከሀረር ከተማ ጥቂት ኪሎሜትሮች ራቅ ያለ/ አዛውሮ ከሸዋ ባሻገር ትጥቁንም ኢኮኖሚውንም ገነባ። በዚህ ጊዜ ሀረር የዐዳል ሱልጣኔት ርዕሰ ከተማ ሆና ይፋትን ተካች። ለዘመናት ይካሄድ የነበረው የሱልጣኖችና የኢማሞች ውስጣዊ የሥልጣን ሽኩቻና ሽምያ ገሃድ ወጥቶ የኢማሞቹ ወገን በማሸነፍ በ1524 ኢማም አሕመድ ኢብራሂም አል-ጋዚ /በግራኝ ቅጽል ስም የሚታወቁ/ የዐደል ሱልጣኔት መሪ ሆነው በትረመንግሥት ጨበጡ።

የኢማሙ ጦር፣ በ1529 ሽምብራ ኩሬን፣
በ1531 ደዋሮና ሸዋን ፣ በ1533 አማራና ላስታን፣ በ1535 መሐልና ደቡብ ሐበሻን እና ባሌ፣ ሀዲያ፣ ሲዳማና ጉራጌን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ትግራይ ላይ ዘምቶ በቆላና ባህር ዳርቻ ሀገር ከሰላ ደረሰ።

ከ1529 እስከ 1543 ኢማም አሕመድ በአጼው ግዛት ላይ ያካሄዷቸው ዘመቻዎች ውጤትን ስንገመግም የሚከተሉትን እንገነዘባለን።

ሀ) ጦርነቱ በቀይ ባህር የአውሮፖ ኃይሎች ወደ Proxy war እየተቀየረ መምጣቱን ፖርቱጋል በአፄው በኩል አትማን ቱርኮች በኢማሙ በኩል እንደነበሩ ይታሰባል።

ለ) ታሪክ የሚያሳየን
- በ4ኛው ምዕተ-ዓመት ክርስትና በአሌክዛንደሪያ አድርጎ በኢትዮጵያ በሰላም ሲመሠረት፣
- የነቢዩ ሙሐመድ ተከታች በስደት በ7ኛው ምዕተ-ዓመት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ክርስትያኑ ንጉሥ ተቀብሎአቸው ከ14 ዓመታት የሰላም ቆይታ በኋላ ወደ አገራቸው ሲመለሱም በበጎ ሲሸኙ እስልምናም በኢትዮጵያ ቀጥሎ በሰላም ሲመሠረት ኃይማኖት ትእምርተ ሰላምና የፍቅር ሆኖ ቆይቶ ነበር። የኋላ ኋላ የነገሥታቱና የሱልጣኖቹ የሥልጣንና የግዛት ማስፋፋት ፍላጎትና ዓላማ ወሳኝ ግብ እየሆነ ሲመጣ ከሰይፍና ጠብመንጃ እኩል /እንዲያውም ሳይበልጥ አልቀረም/ የጦርነት መሣሪያና ማራመጃ ሆኖ ጥቅም ላይ ዋለ። በproxy ጦርነትና በኃይማኖት ስም የተካሄደው ትንቅንቅ የሁለቱንም የሥልጣን መሠረት አዳከመ። ማዕከላዊ መንግሥት አገዛዝ ከኢትዮጵያ ጠፋ። ለሶስተኛ የኃይል አካል ተጋለጠች።

ሐ/ ታላቁ የኦሮሞ ፍልሰት በነዚህ ጊዜያት ማለትም ከ1500 አካባቢ እስከ 1660 ድረስ ተካሄደ።

ጦርነት እንዲሁም የህዝቦች ፍልሰት በታሪክ ዓይን ሲታይ ሶስት ውጤቶች ይኖሩታል።

1. የተሸናፊው ወገን እልቂትና የብሄረሰብ መደምሰስ(extermination) እነ ደዋሮ፣ ሸረካ፣ ደራ፣ ፈጠጋር፣ ሁባት፣ እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ እነ ጋፋት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።
2. አሸናፊውና ተሸናፊው መዋሀድ (assimilation) ጎንደር፣ ወሎ
3. የተለያዩ መደቦች መፈጠር (caste system) ገዥ መደብ፣ ቀጥቃጭ፣ ቡዳ ወዘተ...

በሰሜን ኢትዮጵያ የተበታተኑ ግዛቶችና የጦር አበጋዞች ሲፈጠሩ ከዐደል ክፍላተ ሀገር የሀረሩ ብቻ ሲተርፍ የዘይለዕና የአውሳ ክፍሎች ጠፍተው የሶማሌና የአፋር ብሔሮች ማዕከላት ሆኑ። ነገር ግን ሀረር ከ1647 ወደ ከተማ ደረጃ ብትመነምንም ከአርጎባ፣ ከሶማሌ፣ ከዐፋር እና

- ከምሥራቅ ኦሮሚያ ብሄረሰቦች ጋር የላላ ኮንፌዴሬሽን ፈጥራ፣ የትምህርትና የጥበብ ማዕከል
- ባህር ማዶና ሀገርቤት የንግድ መስመሮች እንብርት
- ለአካባቢ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች በተለይ ሕክምና፣ የጤና ጥበቃና የመድኃኒት አቅራቢ

በመሆን ተገልጋዩቹ በተለይ ገበሬዎች ፣ አርብቶ አደሮች እና ተዘዋዋሪ ነጋዴዎች እስከ አፄ ሚኒሊክ ፍልሚያ ድረስ ለ240 ዓመታት የምሥራቅና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ አስተማሪ መንፈሳዊ መሪ እንዲሁም በውጭ ንግድ መስመሮች እየተጠቀመች በምዕራብ እና ደቡብ ኢትዮደጪ ማጂ፣ ሶዶ፣ ዓሊዩ አምባን፣ ወደ ሰሜን ደግሞ እንደርታን የዘይለዕ ወይም የበርበራ ወይም የታጁራ ወደቦች በኩል ከኤደን፣ ከሙምባይና ከጃቫ ጋር እያገናኘች ቆይታለች። በአጭሩ አጠቃላይ የቀጠናውን ትምህርት፣ ጤና እና የፋይናንስ አገልግሎቶች በማቅረብ፣ በማቀናጀትና በመምራት ይህንን ሰፊ የኢትዮጵያ ክፍል ከውጭው ዓለም በተለይ ከቅርብ መካከለኛና ከሩቅ ምሥራቅ አገሮች አስተዋወቀች። ጥሩ የአለም አቀፍ ባህልና ልምድም አካበተች።

3. የፊዩዳሉና የአምባገነን አገዛዝ ጊዜያት

አገር ውስጥ ከፍተኛ የብሄረሰቦች ፍልሰት፣ በውጭ የአትማን ሥልጣን በቀይ ባህር ተፋሰስ መሸነፉ፣ የሱዊዝ ካናል መከፈቱና የመጀመሪያ ዓለም ጦርነት ማለቁ የፈጠረው ዓለም አቀፍ የኃይል አሰላለፍ ለአውሮፖዊያን የአፍሪቃ "ሻሞ" እና ለቅኝ ገዥዎች የግዛት ሽምያ በር ከፈተ። ኢትዮጵያን በተመለከተ የጣልያን የፈረንሳይና የእንግሊዝ መንግሥታት የቀይ ባህር ዳር አገሮቻችን በሰሜን ከቃሮራ እስከ ደቡብ ሸበሌ/ጁባ ተፋሰስ ድረስ ተነጠቀ። ኢትዮጵያ (land-locked) ባህር አልባ ሆነች። በሌላ በኩል በአፄ |ዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የተጀመረው ኢትዮጵያን የማማከል ስትራ|ጂክ ዓላማ አፄ ምኒልክ በ1889 ሀረር ከገቡበት ጊዜ አንስቶ ባካሄዷቸው ዘመቻዎች የዛሬዋ ታላቂቱ ኢትዮጵያ ተካለለች።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ውጤት የፊዩዳል ብሎም የንጉሣዊ አምባገነን ሥርዓቶችን በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊያሰፍን ቻለ። በሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትንና እድገትን አቀጨጨ፣ አፈነ፤

- "ሲሶ ለቀዳሽ "፣
- " ሲሶ ለነጋሽ" እና
- " ሲሶ ለአራሽ"

ሲባል የቆየው የብዝበዛ መፈክር ተግባራዊ በመደረጉም፡- ከ"እጅ ወደ አፍ" ባሻገር የገበያ አቅርቦት እንዳይኖር፣ ዝቅተኛ የሠራተኛ ውጤታማነት፣ ውሱን የተፈጥሮ ሀብት፣ የሰውና ንብረት የአጠቃቀም ብኩንነት እና ዝቅተኛ የካፒታል ግንባታ በመፍጠር ህዝቦችን ለችግርና ለኋላ ቀርነት ለዘመናት ዳረገ ሰቆቃው

የሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ሆኖ ሳለ የቀዳሽ/ነጋሽ ትብብር በሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ላይ ተደራቢ ጫና ፈጠረ። ይህ የንጉሥ/የሃይማኖት ጣምራ አስተዳደር ለሙስሊሙ የምርቱ ባለቤትነቱን እጅግ አናሳ ከማድረጉም በተጨማሪ የሥራ መስኮቹንም በsubsistence ግብርና፣ በተናቁ የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ቀጥቃጭ፣ አንጥረኛ፣ ሸማኔ፣ ፋቂ፣ ወ.ዘ.ተ. - እና ከፍ ቢል በሸቀጣሸቀጥ ማዞርና በመንደር ንግድ ወሰነለት።

የዚህ ዓይነቱ ሥርዓት የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ አሉታዊ ውጤቶች፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ገጽታዎች እና አስተዳደራዊ በደሎች በእጅጉ በስፋትና በጥልቀት ስለተጻፈ ለኢትዮጵያ ስላተረፈው ድህነት ባለብዙ ፈረጅ ጎላ ቀርነት የዓመታት የህዝቦች አመጽ፣ በሃይማኖት፣ በብሄረሰብ መናቆር ወ.ዘ.ተ. እምብዛም መናገር እንደማያስፈልግ አምናለሁ።

ለሙስሊም ኢትዮጵያኖች በተለይ በናሙና ለመረጥኩት የኢትዮጵያ ክፍል ህዝብ ማለትም፣

- እስከ 16ኛው ዘመን አጋማሽ የዐዳል ሱልጣን ግዛት ሲባል የቆየ፣
- እስከ 1880ዎቹ ሀረርን ያማከለ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ኮንፈዴሬሽን ብለን ልንሰይመው የምንችል በአጼ ምኒልክ ካርታ ሀረርጌ አሩሲ ባሌ የተባለው፣
- በመጨረሻም በአፄ ኃይለሥላሴ የሀረርጌ ጠቅላይ ግዛት /ባሌና አሩሲን በመገንጠል/ ተብሎ ዐፋር፣ ሶማሌ፣ ምሥራቅ ኦሮሚያን፣ ሀረርንና ድሬደዋን ያጠቃለለ የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ያቀፋቸው ኢትዮጵያኖች አመዛኙ - የ20ኛው ክፍለ ዘመን - ፊዩዳላዊ፣ ንጉሣዊ ሥርዓቶች - በእምነታቸው ምክንያት ብቻ በመንግሥት ፖሊሲ የሁለተኛ ደረጃ ዜግነት የተወሰነላቸው ሲሆን፣ በአንፂሩም ጠንካራና የማይታክት አምራች፣ እሴት ፈጣሪ፣ ቆጣቢና ቻይ የሀገር ወገን አድርጓቸዋል። ይህ ባህርይ የእምነታቸው የሥራ፣ የምርትና የአኗኗር መርሆዎች ጋር ተጣምሮ ከዚህ በታች ለመግለጽ እንደምሞክረው ሙስሊሞች ለኢትዮጵያ ልማት ወሳኝ ተሳትፎና አስተዋጽኦ ያለውና የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል ሆነዋል።

እስልምናና ልማት በመርህ ደረጃ እንደሚከተለው ሊተነተን ይችላል። ሰው በምድር የፈጣሪ ወኪል ነው። የውክልናውም የሥራ መዘርዝር የሚያካትታቸው፣

- ሰው ከፈጣሪ የተሰጠውን ሀብትና ፀጋ በአግባቡ ተጠቅሞ መሬትን ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለህብረተሰቡ ጥቅም ከማዋልም ባሻገር ለተከታታይ ትውልዶች የተሻሻለና ያደገ እሴት ማውረስ፣
- ሀብት የመፍጠርና የክፍፍል ሥርዓቶች ፍትሐዊ እንዲሆኑ፣ ሞኖፖሊ፣ አራጣ፣ ገበያን ለመቆጣጠር ያለአግባብ ክምችት፣ ተገቢ ያልሆነ ትርፍ እንዳይኖር፣
- ያልተመጣጠነ እንዲሁም የድህነትን ደረጃ የሚያባብስ የሀብት ክፍፍልና ሥርዓት በተቻለ እንዲጠፋ ማድረግ፣

ሲሆኑ የልማት እንቅስቃሴዎች ሰውን ማዕከል ያደረጉ፣ የተፈጥሮ ንብረትን የሚጠብቁ፣ ውጤት ተኮርና የዘለቄታ ብልጽግናን የሚያረጋግጡ ተደርገው መቀየስና መተግበር እንደሚኖርባቸው በፅኑ ይደነግጋል።

ከነሐሴ 15 ቀን 1987 ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ የዋለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 89 ከሚያስምራቸው የኢኮኖሚ ዓላማዎች "መንግሥት የኢትዮጵያዊያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ እንዳለበት" እንዲሁም "በእድገት ወደኋላ ለቀሩ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መንግሥት ልዩ ድጋፍ እንደሚያደርግ" የሚሉ ሐረጎችን ያካትታል።

የእስልምና የልማት መርሆችና የህገ መንግሥቱ የኢኮኖሚ ዓላማዎች ተወራራሽና ተደጋጋፊ እንደሆኑ ግልጽ ነው። የልማት ማዕከል ሰብአዊ ልማት መሆኑ ግልጽ ሲሆን ለዚህ ልማት እውን መሆንም መልካም አስተዳደርና ፍትሐዊ እኩልነት (equity) በአንድ በኩል የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት በተጨማሪ መሠረታዊ ተፈላጊዎች መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።

ቀደም ሲል የተነሱት ኢ-ዴሞክራሲና ኢ-ፍትሕ ሥርዓቶች ሲያራምዷቸው የቆዩ በደሎችን ይህ ህገ መንግሥት በመገርሰሱ ለሙስሊሙ ህብረተሰብ የእኩል ደረጃ ኢትዮጵያዊነትና የሀገር ባለቤትነት አረጋግጦለታል። በተለይም አንቀጽ 11

(1) *መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።* ''
(2) *መንግሥታዊ ሃይማኖት*
አይኖርም።
(3) *መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖት በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።*
''

ለሚሉት ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ከፍተኛ የመንፈስ እርካታ አበርክቷል።

4. የሙስሊሙ ህብረተሰብ የልማት ተሳትፎ

ቀደም ሲል በጠቀስናቸው ኢ-ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች አስገዳጅ ሥራ ክፍፍል የሙስሊሙ ህብረተሰብ አምራች፣ የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ሠራተኛና የፈጠራ ባለቤት የኢኮኖሚና የንግድ አገልግሎቶች አቅራቢ ሆኖ ከ17ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ እስከ 20ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ቆይቷል። ዓለም አቀፍ የንግድ መስመሮች (trade route) ጋር የረጅም ጊዜ ትውውቅ አዳብሯል። ከደጋው አካባቢ "ደሴትነት መንፈስ" (Insularity) እና የመከበብ ስሜት ይልቅ ኢንተርናሽናል ልምድ (expertise) አካብቷል። እርግጥ በ20ኛው ዘመን የመጀመሪያ መንፈቅ ድረስ ለውጭ ዜጎች የኤክስፖርት ምርቶችን በማቅረብና የኢምፖርት ሽቀጦችን ተቀብሎ አገር ውስጥ በማከፋፈል ተወስኖ ቢቆይም በምሥራቅ ኢትዮጵያ ደረጃ በደረጃ የዐረብና የህንድ ነጋዴዎች ጋር በመሻረክ ወደ መተካቱ ደረሰ። ከዚያም አልፎ በቅርቡ ምሥራቅ ቀጠና የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ሥር ሰደው ለ "ሀገር ቤት" ልማት የማይናቅ አስተዋጽኦ በማድረግ ለቤተሰቦቻቸው የኑሮ ማሻሻል ድጎማ በስፋት አበርክተዋል እያበረከቱም ናቸው።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሥርዓተ መንግሥት ፓርላሜንታዊ ሆኖ የተዋቀረው በፌዴራል መንግሥትና በዘጠኝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ነው። ከዘጠኙ ክልላት መካከል የዐፋር፣ የሶማሌ ፣ የምሥራቅ ኦሮሚያና የሀረሪ ክልሎች እና የድሬዳዋ ካውንስል በቀድሞው ትልቁ የ "ሀረርጌ ጠቅላይ ግዛት" ይካተታሉ። የዚህ ከፍተኛ የምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና

- የሃይማኖት እኩልነት የተረጋገጠበት ሠራተኛ ታታሪ እና አሌ የማይባል የንግድና የኢኮኖሚ ልምድ ያካበተ የሰው ኃይል፤
- በደጋው ክፍሉ ለም እርሻ መሬት ቡና፣ አትክልትና ፍራፍሬ ለኤክስፖርት የሚያመርት፤
- በቆላው ክፍሉ ሰፊ የእንስሳት ሀብት ያለው፤ ከከርሰ ምድሩ ከዳሎል ጀምሮ እስከ መጨረሻ ደቡብ የሶማሌ ክልል የተዘረጋና የተንጣለለ ሀገር የኮንስትራክሽን የኬሚካል እና የፔትሮ-ኬሚካል የኢንዱስትሪ ማዕድናት ያዘለ፤
- ለህንድ ውቅያኖስ ባለው ቅርበት ለደቡብና ምዕራብ ኢትዮጵያ ፈጣን የአጭርና የረጅም የትራንስፖርት መስመሮች ውጤት ተኮር አገልግሎት ለማቅረብ አመቺነቱ፡

እነዚህ እሴቶች ተዳምረው ለኢትዮጵያ ልማት እድገትና ለህዝቧ የተሻሻለ ኑሮ ለማረጋገጥ እምቅ ችሎታ ፀጋና ሀብት አለው።

በሌላ አባባል ቀጠናው የኢትዮጵያ የኬሚካልና የፔትሮ-ኬሚካል ኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽን ጥሬ ዕቃዎች አመንጪና አቅራቢ በተለይ ከቅርብ፣ ከመካከለኛና ከሩቅ ምሥራቅ ጋር ለሚኖረው፣ እያደገ መምጣት ላይ ላለው የንግድ ሸቀጦች ፍሰት የየብስ ትራንስፖርት አውታር የመሆን ብሩህ ተስፋ አለው።

ይህ የምሥራቅ ኢትዮጵያ አጎራባች ክልሎች ቀጠና ከታሪክ የተዛባና ጎላ ቀርነት ያጠቃው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በመውረሱ በህገ መንግሥት የኢኮኖሚ ዓላማዎች እንደተጠቀሰው፤ " በእድገት ወደ ጎላ ለቀሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መንግሥት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል።" አንቀጽ 89 (4) በተጨባጭም እያደረገ ነው። ድጋፎቹም ልዩ ትኩረት እየሰጡ ያሉት፣ "በማህበራዊ ረገድ ለትምህርትና ስልጠና፤ ለጤናና ለመሠረተ ልማት" "በኢኮኖሚ አኳያ ለክልላዊ ልማት የድጎማ አመዳደብ" ላይ ነው።

የእስልምና የልማት መርሆችም ሰውን ማዕከል ላደረገ ሁለንተናዊ እድገት ለፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን ለማረጋገጥና ድህነትን ለመቀነስ እንቅስቃሴዎች ትኩረት ይሰጣሉ። ሥርዓቶችም ተወስነዋል። በተለያዩ ሀገሮች በሚገኙ የሙስሊም ህብረተሰቦች በተግባር ውለው ለልማትና እድገት ሰፊ ድጋፍ አበርክተዋል። ከእስልምና ሃይማኖት አምስቱ አእማድ ሶስተኛው ዘካት የማውጣት ግዴታ ነው። ዘካት የሚሰላው ከዓመት ወደ ዓመት ለሚተላለፍ ከገቢ ጠቅላላ የኑሮ ወጪዎች ተቀንሰው ከቀሪ ትርፍ፣

- 21/2 % ከጥሬ ገንዘብ፣ የንግድ እሴት፣ ወ.ዘ.ተ.
- 5 % ከከርሰ ምድር ከሚገኝ ሀብት
- 10 % የእርሻና የከብት ሀብት

ሲሆን ዓመት ሙሉ የቆየና በህግ የተወሰነ ምድብ መጠን መሠረት ይታሰባል። በነፂ ለድህነት ቅነሳ በማይክሮ ፋይናንስ አማካኝነት ዘካት በማህበረሰብ ደረጃ በትክክል እየተሰላ በየዓመቱ ተሰብስቦ በዕቅድ ለሥራ ፈጠራ ዓላማ ከተሰጠና ከዋለ ምን ያህል የገንዘብ ክምችት እንደሚያስገኝ መገመቱ አያዳግትም።

የምስራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና የሰው ሀብት፣ የተፈጥሮ ሀብትና እምቅ ኃይል ለሀገርና ህዝብ ልማት በተጨባጭ ከተጠቀሙበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው። የመሰረተ ልማት አውታሮች መዘርጋት ይኖርበታል። የሰለጠነና ጤናው የተጠበቀ አምራች የሰው ኃይልና አስተማማኝ የፋይናንስ አቅምም ማፍራት፣ ማረጋገጥና መገንባት የማያጠያይቅ የእድገት ግብኣት ነው። የእስልምና ሃይማኖትም በህግ፣ በማስተማርና ሥርዓቶች በመፍጠርም ለሰው ልጅ የምድራዊና የመንፈሳዊ ደህንነት ወደ ማስገኘት ይመራል።

5. ለልማቱ ምን ማድረግ ይገባል?

የሙስሊሙ ህብረተሰብ በኢኮኖሚው ሙሉ ተሳታፊ ነው። በምድርም የፈጣሪው ተወካይ መሆኑን ያምናል። ግዳጆችንም ለመወጣት በሙሉ ልብና ተሰፋ ይጥራል። ይህም ከሃይማኖቱ የወረሰው ነው። የምሥራቅ ቀጠና ምድር የተፈጥሮ ፀጋና ሀብት ባለቤት ነች። የእርሻ መሬት፣ የእንሰሳት ክምችት፣ ማዕድናትና እምቅ እንፋሎት ኃይል ወ.ዘ.ተ. ለሀገር ውስጥ ፍጆታና ጥቅም እና ለኤክስፖርት የሚበቃ ነው። በአጭሩ እነዚህን ሀብቶች ለመጠቀም በመንግሥት ደረጃና በህዝቡም ዝግጁነቱ አለ። ማህበራዊ ጥረቶችም ባልተቀናጀ መልክ እየተደረጉ ናቸው። መሳካትና ግብ ለመምታት ከሁሉ በላይ ለትምህርትና ስልጠና (Skilled Human Resource)፣ ለሥርዓቶች/ተቋማት ለአመራር ትኩረት መስጠት ያሰፈልጋሉ።

ትምህርትን በተመለከተ፡ ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው "በአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር አካባቢ ያለውን ዝቅተኛ የትምህርት ጥቅል ተሳትፎ፣ ማለትም በአፋር 13% እና በሶማሌ 16% የሆነውን በሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ 60% ለማድረስ የሚስያችል ከሌሎች የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች ግንባታ ጋር ተቀናጅቶ የሚካሄድ የፈጣን ውጤት ጉዞ (fast track) ስትራቴጂክ ዕቅድ ከህብረተሰብ አኗኗር፣ ባሕልና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ጋር ተገናዝቦ" እንደተዘጋጀ ነው። ሆኖም ግን በTertiary ደረጃ አንድ የScience and Technology Institute በኬሚካልና ፔትሮ ኬሚካል ሳይንሶች የሚያተኩርና ለቀጠናው ከፍተኛ ተማሪዎች በሙሉ የSpecialization እና ረሰርች ማዕከል የማቋቋም ሥራ በፍጥነት ቢጀመር ይመረጣል። ቀጠናው ከሳውዲ ዐረቢያና ከገልፍ ኢሚሬት አገሮች የፔትሮ-ኬሚካል ጥናት ተቋሞች ጋር የቅርብ ትስስርና ብሎም ጠለቅ ያለ የመረዳዳት ፕሮግራሞች በቀላሉ ሊመሠርት ይችላል።

ሥርዓትና ተቋማትን በተመለከተ፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን ሉዓላዊነቷ ለዘመናት ተከብሮ ለዛሬው ትውልድ የደረሰው በህዝቦች የተባበረ ትግልና መስዋዕትነት መሆኑን ታሪክ ያረጋግጣል። ባለንበት ታሪካዊ ወቅት የህዝቦቿ አንድነት እየጎለበተ በሚሄድበትና ዘላቂ ሰላም በአስተማማኝ መልኩ ሊረጋገጥ በሚችልበት ዲሞክራሲዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ላይ ስለምንገኝ ብሩህ ተስፋ ያንፀባረቀበት ጊዜ ነው።

ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ታዋቂነትና ክብር ካተረፈችባቸው ታሪካዊ ቅርሶቿ አንዱ በተለያዩ ሃይማኖት ተከታይ መካከል ተጠብቆ የቆየው እርስ በርስ የመከባበርና የመቻቻል ባህል ነው። ይሁን እንጂ በህዝቦች መካከል ተጠብቆ የኖረው መልካም የመከባበርና የመቻቻል ባህል እንደተጠበቀ ሆኖ በሀገሪቱ ላይ የዘመናት የሥልጣን መረባቸውን ዘርግተው የኖሩ የቀድሞ ገዢዎች የአስተዳደር ፈሊጥ የተባለው አኩሪ ባህል እየጎለበተ እንዲሄድ የሚያበረታታ አልነበረም።

እንደዚህ ዛሬ ሀገራችንን ለማኩራት ያበቃው የተለያዩ እምነት ተከታዮች የመቻቻል ባህል ከህዝቡ ከራሱ የመነጨ ፀጋ እንጂ ቀድሞ የነበረ መልካም አስተዳደር ያስገኘው ውጤት አልነበረም። አሁን በምንገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ዴሞክራሲ እየጎለበተ ከሄደና ሀገራችን ለተሟላ መልካም አስተዳደር በዘላቂነት ከታደለች ህዝቦቿ በገዛ ፈቃዳቸው ጠብቀውት ያኖሩት አኩሪው የመከባበርና የመቻቻል ባህላችን በብቃት ሊዳብርና ለምንጊዜም ፀንቶ ሊኖር የሚችልበት ታሪካዊ ዕድል እንደተፈጠረም በሰፊው ይታመናል።

በዚህ ረገድ አበክሮ ሊጠቀስ የሚገባው የሙስሊሙ ህብረተሰብ ሁኔታ ነው። ለዘመናት ተጠብቆ ለኖረው አኩሪ የመከባበርና የመቻቻል ታሪክ ከክርስቲያን ወገኖቹ ጎን የሙስሊሙ ህብረተሰብ ታላቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል። በዘመናችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በማቆጥቆጡ ለታሪካዊ ብሶታቸው ዘላቂና ፍትሃዊ መፍትሄ እንደሚያገኙ በታላቅ ተስፋ ከሚጠብቁ ወገኖች አንዱ ሙስሊሙ ህብረተሰብ መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነው። ለዚሁም ዋነኛው ምክንያት እሰከ ዛሬ ከተመዘገቡት አበረታች ውጤቶች መካከል አንዱ የእምነት ነፃነት እኩልነት በህገ መንግሥቱ የማያሻማ ዕውቅና ማግኘቱ ነው። ከእንግዲህ አሳሳቢ ሊሆን የሚችለው በህገ መንግሥቱ የሰፈሩት መብቶች በተሟላ መልኩ ተፈጻሚ መሆናቸው ብቻ ነው። በዚህም ረገድ ቢሆን መንግሥት አቅምና ሁኔታ የፈቀደውን ያህል ያልተቆጠበ ጥረት ሲያሰደርግ እንደቆየ ሙስሊሙ ህብረተሰብ በሚገባ ይረዳል።

እስከ አሁን እልባት ሳያገኝ የቆየው አንዱ የአፈጻጸም ችግር በክልልና በፌዴራል ደረጃ የተቋቋሙት የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት የማደራጀትንና ማቋቋምን የሚመለከት ነው። ምዕምናኑ በነፃነት የሃይማኖት አስተዳደር ተቋማትን ለማቋቋም እንደሚችሉ ህገ መንግስቱ ያረጋግጣል። ይህ መብት ተፈጻሚ በሚሆንበት ሂደት መንግሥት ተገቢውን አመራር እየሰጠ አግባብ ያላቸው ሥነ-ሥርዓቶች በተሟላ መልኩ እንዲከበሩ ማድረግ ህገ መንግሥታዊ ኃላፊነት መሆኑን ህብረተሰብ ይገነዘባል።

ይሁን እንጂ የታወቀ የህግ ከፍተት በሌለበትና የመንግሥት በጎ ፈቃድ ባልተጓደለበት ሁኔታ ህብረተሰቡን እርካታ የነሳ ሁኔታ መቀጠሉ አግባብነት የለውም፡፡ ስለሆነም ሁኔታው በተቻለ ፍጥነት ተገቢው እርምት እንዲደረግለት አሰፈላጊው ሁኔታ መሟላት ይኖርበታል።

አመራርን በተመለከተ፡ ዘካት፣ የማይክሮ ፋይናንስ ሥርዓት፤ ማህበራዊ የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፣ የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች እና ተቋማትን የማቋቋም የማደራጀትና የመምራት ተግባራትን አቀናጅቶ በሀገር አቀፍ ደረጃ ስኬታማ እንዲሆኑ የማረጋገጥ ሥራ ጠንካራና የተከበረ የበላይ አመራርን ይሻል።

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ የህዝቡ ተወካዮች ምክር ቤት በ1989 ሲያፀድቀው ሙስሊሙ ህብረተሰብ ሁለት ተጎዳኝ ሥራዎችን ጠይቆ ነበር።

ይኸውም፤

ሀ) ፍትሐ-ብሔር እና የቤተሰብ ህግ በተጠናቀሩበት መልክ ፍትሐ - ሸሪዓ (አራቱንም መዝሀቦች የሚያስማማና አማራጮችንም የሚፈታ) እንዲዘጋጅና ለፍርድ ቤቶች በቋሚ መመሪያነት እንዲያገለግል ማድረግ እና

ለ) ለሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኞች፣ ጠበቆች በአጠቃላይ የዚሁ አካል አባላት በዲግሪ እና በከፍተኛ ዲፕሎማ ደረጃ የሰለጠኑና የተካኑ ምሁራንና ብቃት ያላቸው ፕሮፌሽናሎች የሚመረቁበት የዩኒቨርስቲ ኮርሶች እንዲዘጋጁ፣

በተቻለ ፍጥነት አሁን ያለውን አሳዛኝ ክፍተት በቅጡ ማስተካከል ነበር። ዛሬ ከአዋጁ መጽደቅ አሥር ዓመታት በኋላ የፍትሐ -ሸሪዓን የማጠናቀር ሥራ አልተጀመረም፣ የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ ኮርስ ጥያቄም ምን ደረጃ ላይ እንዳለ የተከታተለ የሙስሊም ድርጅት ወይም የበላይ አካል የለም።

6. የ2020 ርዕይ

ብሔራዊ የሚሌኒየም የልማት ግቦች እውን የሚሆኑት መላውን የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ክፍሎች በእኩል ደረጃ ሲያላድጉ ብቻ ነው አሁን በልማት ኋላቀር ክልሎች የሚል ሀረግ ጠፍቶ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች ህዝቦች ፍትሓዊነትን በተላበሰ ድልድል አድገው ይገኛሉ ለማለት የሚያስችል መሠረተ ልማትና ላዕላይ መዋቅር ተደራጅተው ማየቱ የመጀመሪያ ደረጃ ርዕይ ነው።

የሙስሊሙን ህብረተሰብ የሚመራ፣ የእምነት ጉዳዮቻቸውን በአግባቡ ሸሪዓው በሚደነግገው ቀጥተኛ መስመር የሚያስተናግዳቸው፣ በመዋቅር ደረጃ ሦስቱን የሸሪዓ አካላት ማለትም ፈትዋ፤ የዳኝነትና አስተዳደር ያቀናጀ የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች መጅሊስ በቻርተር፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደ ሀገራዊ ተቋም (የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር፣ የአ.አ. ዩኒቨርሲቲ... በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ) እውቅና አግኝቶ ለምዕመናኑ ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሓዊና የመልካም አስተዳደር መርሆችን ያከበሩ አገልግሎቶችን የሚያቀርብና ሁሉን አሳታፊ አመራር የመስጠት ግዴታዎቹን በኃላፊነት ስሜት ለመወጣት የሚችል ሆኖ ማግኘቱ ሁለተኛ ርዕዬ ነው።

እስልምና እና ልማት በኢትዮጵያ **አስተያየት**

አህመድ ሁሴን[1]

1. ልማት ምንድን ነው?

ልማት የማያቋርጥ ሒደት (Process) ሆኖ ቅጽበታዊ እና አዝጋሚ ለውጥን፣ እድገትን እና መሻሻልን ያቀፈ እውነት ነው። (Wikipedia Encyclopedia)

ልማት ከኢኮኖሚ ባሻገር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ እና ሌሎችም ገጽታዎች አሉት።

ልማት በአንድ በተወሰነ ሥነ ምድር ላይ በሠፈሩ ማህበረሰብ ላይ ወይም በሐገሮች ወይም ደግሞ በአንድ ሰው ላይ ሊገለጽ ወይም ሊለካ የሚችል ነው።

ልማት በአብዛኛው በተለይ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ሲያሟላ ተፈላጊ ወይም አዎንታዊ ይሆናል።

- ሰብዓዊ ፍጥሩን ያማከለ ሲሆን
- አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል ያሳተፈ ሲሆን
- ተፈጥሮን (Environment) ለተተኪው ትውልድ በሚያስተላልፍ መልኩ ሲሆን

ልማት ከላይ በተጠቀሱት መመዘኛዎች መሠረት መከናወን ከቻለ ለሠላም፣ ለአንድ ሐገር ፖለቲካዊ መረጋጋት፣ ለሐገር ፍቅር መጎልበት፣ ከጎረቤት ሐገራት ብሎም ከአለም ህብረተሰብ ጋር ተሳስቦ ለመኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ከላይ የተጠቀሡትን ጥቅሞች ለማግኘት ልማት በእቅድ መመራት ይገባዋል። ነገር ግን ከሥራው ጥልቀት፣ ስፋትና ውስብስብነት የተነሳ የእቅድ አወጣጡ ተለዋዋጭ እና በየጊዜው እየታረመ መሔድ የሚችል መሆን ይኖርበታል። የመሳካት እድሉን ያሰፋ የልማት እቅድ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፤

- የተፈጥሮ ሐብት
- የሠው ሐይል
- የህብረተሰብ ተሳትፎ
- የሕዝቦችን ሥነ ልቦና፣ ባህል፣ እና ሐይማኖት

[1] ዶ/ር አህመድ ሁሴን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሂሳብ (Mathimatics) ያገኙ ሲሆን የማስትሬትና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በኮምፒውተር ሳይንስ ከፈረንሳይ አገር አግኝተዋል። ዶ/ር አህመድ ሁሴን ለ8 ዓመታት በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በረዳት ፕሮፌሰርነት ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በግል የማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ ይገኛሉ።

- ሌሎችም።

ለልማት እንቅፋት የሆኑ ሁነቶችንም በሚገባ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይ ወደ ዛሬው ርዕሳችን ስንመጣ ባህል በተለይም ሐይማኖት በተለይም እስልምና ለልማት የሚኖራቸው አዎንታዊና አሉታዊ ተጽኖዎች በመጠኑም ቢሆን መታየት ይኖርባቸዋል።

2. እስልምና እና ልማት

እስልምና ስራና ምርታማነትን የሚያበረታታ በአንዲሩ ደግሞ ሥንፍናን፣ ልመናን፣ ዳተኝነትን፣ ሙስናን ወ.ዘ.ተ. የሚያወግዝ ለመሆኑ አያሌ የቅዱስ ቁርአን አናቅጽትና የመልእክተኛው መሐመድ (SAW) አባባሎችና አኗኗር ምስክሮች ናቸው።

ስለ ሥራ

«እርሱ ምድር ላይ የጠራችሁና እንድታንጿት ያዘዛችሁ አምላክ ነው።» (ሁድ 61)

«ምድር የተፈጠረችው ለሰው ልጆች መጠቀሚያ ነው።»

«ስግደት ሲያልቅ በመሬት ላይ ተሠራጩ፣ የአላህንም ጸጋ ፈልጉ» (62 ፡ 10)

«ሲሳያችሁን ከመሬት ውስጥ ፈልጉ።» (አቡ የዕላ)

ስለ ልመናና ስንፍና

ልመና በእስልምና የተወገዘ ተግባር ነው።

«ከታችኛው እጅ የላይኛው ይሻላል» (ቡኻሪና ሙስሊም)

«አንድ ሰው የልፋቱና የጥረቱ ውጤት ከሆነ ምግብ የበለጠ መልካም ምግብ አልተመገበም» (ቡኻሪ)

ስለ አሠሪና ሠራተኛ

«ሠራተኞችን መበደል ከትልቅ ወንጀሎች አንዱ ነው» (አህመድ) «አንድን ሠራተኛ ከኃላፊው ጋር ያለውን ግንኙነት ያበላሸ ከኛ አይደለም.....» (በይሀቂ)

«ወዝአደሮች ላባቸው ሳይደርቅ የጉልበት ዋጋቸውን ስጡ። » (አቡ የዕላ)
«የቤት ሠራተኞቻችሁ ዕቃ በመሰበራቸው አትምቱአቸው ሰው ውስን እድሜ እንዳለው ሁሉ ዕቃዎችም ውስን እድሜ አላቸው»

(ጠበራኒ)

ስለ እጅ ሙያ፣ ንግድ፣ ግብርና

«ታማኝና እውነተኛ ነጋዴ በመጪው ዓለም ከነቢያት፣ ከእውነተኞች እና ከሰማእታት ጋር ይሆናል» (ቲርሚዚ)
« ሙያ ያለው ድህነት አይነካውም.....»

3. የኢትዮጵያ ሙስሊም እና ልማት

ሙስሊሞች እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲኖሩ/እንዲታዩ ተፈርዶባቸው በነበረው ዘመን («በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሙስሊሞች») ለሙስሊሞቹ የተተወው የስራ መስክ በጣም የተወሰነ ነበር። እነዚህም ግብርና፣ ንግድ እና የእጅ ሙያ ነበሩ። ንግዱም ቢሆን በአብዛኛው የግብርና ምርቶችን ገበያ ላይ ማቅረብና ሽቀጦችን ማከፋፈል እና መቸርቸር ላይ ያተኮረ ነበር። የእጅ ሙያ በተለይ ሽመና እንደ አይነተኛ ምሳሌ ይጠቀሳል።

በነበረው ተጽዕኖ ምክንያት አብዛኛው የሙስሊም ልጅ ዘመናዊ ትምህርት ተምሮ እንደሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድምና እህቶች በመንግስት መሥሪያ ቤቶች፣ በፖሊስ፣ በውትድርና፣ በሚዲያ እና በመሳሰሉት መ/ቤቶች ተቀጥሮ የመሥራት እድሉ በጣም የጠበበ ነበር። እድሉን ያገኙ የጥቂት ሙስሊሞች ታሪክ እንደሚያሳየው የተወሰኑት ሐይማኖታቸውን እንዲቀይሩ ተገደው ነው ስራው የሚሰጣቸው። አለበለዚያም በሚሠሩበት መ/ቤት በጥርጣሬ የሚታዩ በመሆናቸው ለውስጥ እድገትና የደመወዝ ጭማሪ እጅግም የሚታሠቡ አልነበሩም። የዛ ስርአት ተጽዕኖ መላው የኢትዮጵያ ህዝቦችን በአንድ ላይ የጎዳ ቢሆንም በተለይ ሙስሊሞቹ ላይ ይደርስ የነበረው ግፍ ድርብ ድርብርብ ነበር ማለት ይቻላል።

የ1960 ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ በአንድ በኩል የፊውዳላዊ ሥርአቱን የመደብ ትግል ያንጸባርቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በብሔር ብሔረሰቦች መሐከል የነበረውን የባህል እና የቋንቋ ተጽዕኖ የሚያሳይ ነበር። ከእነዚህም በተጨማሪ መለስተኛ በሆነ መልኩም ቢሆን የዜግነት ትርጉም ከሐይማኖቶች እኩልነት ጋር በሚኖረው ቁርኝት የተነሡ ጥያቄዎች ነበሩ።

በእርግጥ የሙስሊም ተማሪዎች ድርሻ በት/ቤቶችና በተለይም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ እጅግ በጣም አናሳ በመሆኑ ድምፂቸው ከሌሎች እኩል ለመሰማት የቁጥር ተጽዕኖ ነበረበት። ይሁንና በቤቱ፣ በንግድ ቤቱ፣ በሱቁ፣ በጫት ቤቱ፣ በማሳው ላይ ሁኖ የአብዮቱን መጋጋል ይታዘብ የነበረው መላው የሙስሊም ሕዝብ ልቡንና ጸሎቱን ለእነሡ ሠጥቶ ነበር። በጊዜው ክስተቱን ከታዘቡ ታላላቅ ወንድሞች መረዳት እንደሚቻለው ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች ለሙስሊሙ መብት መረገጥ እኩል ከሙስሊሙ ጋር በአንድነት መነሳት ታላቅ ስሜትን ይቀሰቅስ የነበረ ክስተት ነበር። ከዛም አልፎ ብዙዎች እንደሚሉት «ኢትዮጵያዊነት» እንደገና የተወለደበት በተለይ ሙስሊሙ ለመጀመሪያ ጊዜ አንደኛ ዜጋ የመሆን ሕልሙን «ሊሳካ ይችል ይሆን?» ያለበት ወቅት ነበር።

የ1966ቱ አይነት አብዮት በአዎንታዊ ጐኑ የሚታዩ ብዙ ክስተቶች የነበሩት ቢሆንም መመሰቃቀሎችን፣ የሰብዓዊና የንብረት ውድመቶችንም አስከትሏል። አዲስ ሥርዓተ ማህበር በተንኮታኮተው አሮጌ ሥርዓተ ማህበር ላይ እንዲበቅልም አስችሏል። ይህ «በሙስሊሙ የልማት ተሳትፎ» ላይ ምን አዎንታዊ/የቀየረው ገጽታ አለ? ሙስሊሞቹስ ይህን አጋጣሚ ተጠቅመውበታል ወይ? ይህ ቀጥሎ የምናየው ይሆናል፡-

ከአብዮቱ በኋላ ምንም እንኳን በጊዜው የነበረው መንግስት ሲከተለው ከነበረው ርዕዮተ አለም አንፃር ብዙ ተጽዕኖዎች በሐይማኖቶች ላይ የነበረ ቢሆንም፤

- መንግሥት ከሐይማኖት /ከማንኛውም/ ተጽእኖ ውጪ የቆመ ተቋም ሆኖ ታውጇEል።
- እስልምና ከክርስትና እኩል እንደ አንድ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሐይማኖት ታውቋል።
- ሙስሊሞች የሐይማኖት ግዴታቸውን በተሻለ ነፃነት ተወጥተዋል፡፡ በዓሎቻቸው በብሔራዊ ደረጃ ተከብረውላቸዋል።
- የመማር እድል አግኝተዋል፡፡
- የስራ እድሎች ቢያንስ በሐይማኖት ምክንያት በሩ የተዘጋባቸው አልነበሩም።
- የተሻለ የሥነ ልቦና ለውጥ አምጥተዋል።
- የፖለቲካ ተሳትፏቸው በተሻለ ጨምሯል።
- በዚህም የተነሳ ይህቺ ሐገር «የእኔም ናት» የሚል መንፈስ መፍጠሩ አይቀሬ ነበር።

የደርግ ሥርዐት ከተገረሠሠም በኋላ ለሕዝበ-ሙስሊሙ አሁንም የተሻለ መብቶችን ያጐናፀፈ ሥርዓት ላይ ነው የደረስነው። በተለይ ደግሞ ገጠርን ማዕከል ያደረጉ ልማቶች፣ ብሔር ብሔረሰብ ተኮር የሆኑ ፖሊሲዎች ከበፊተኛው ስርዓት በጣም በተሻለ ሙስሊሞች በብዛት በሚገኙባቸው አካባቢ ማለትም በቤንሻንጉል፣ ሶማሌ፣ አፋር እና በአንዳንድ ከመሐከል የራቁ የኦሮሚያ ዞኖች በት/ርት በጤና በግብርና Extension በመሰረተ ልማት እና በመሳሰሉት ከፍተኛ ለውጦች ታይተዋል። የዚህ መሠረተ - ሠፊ የለውጥ ሒደት ፍሬው ወደፊት በተሻለ የሚታይ ይሆናል ተብሎ ሊጠበቅ የሚችል ነው።

ይሁንና ሙስሊሙ አገሪቱ ውስጥ ባለው የቁጥር ክብደት (ratio) አንጻር ሲሰላ በተፈጠሩት አጋጣሚዎች የሚገባውን ያህል ተጠቅሟል ወይ የሚል ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይመስለኛል። ይህንን ጥያቄ ለማጠናከር አንዳንድ መረጃዎችን እንውሰድ፡-

- ሙስሊሙ በመንግስት ሥራ ላይ ያለው ተሳትፎ እጅግ በጣም አናሳ ነው በከፍተኛ ትምህርት የሙስሊሙ ተሳትፎ አሁንም ከ10% የዘለለ አይደለም፡፡ በኢኮኖሚው ስናይ ባንክ እና ፋይናንስ ተሳትፎ የለውም ማለት ይቻላል።
- ሆቴል፣ ምግብ ቤት፣ መዝናኛ ማዕከላት አሁንም በጣም ዝቅተኛ ነው።
- ፋብሪካ (Manufacturing) ከ10-15% በላይ አይደለም ኮንስትራክሽን እና በመሳሰሉት ዘርፎች የሙስሊሙ ተሳትፎ እጅግ በጣም አናሳ ነው።
- በፖለቲካው ተሳትፎም ስንመጣ ሙስሊሙ ሌሎች ድምጹን ለማግኘት የሚሯሯጡለት እንጂ የራሱን አጀንዳ አስቀምጦ በንቃት የሚንቀሳቀስ አይደለም።
- በፕሮፌሽናል እና ምሁራዊ ሥራዎች ማለትም፡-
    - በታሪክ

  - በፖለቲካል ሳይንስ
  - በኢኮኖሚክስ
  - በሕክምና
- በምህንድስና እና በመሳሰሉት ዘርፎች የሙስሊሙ ተሳትፎ እጅግ በጣም አናሳ ነው።
- በሚዲያ ላይ የሙስሊሙ አስተሳሰብ ብዙ የተቀየረ አይመስልም። ሚዲያ ለእሡ ባህልና ሐይማኖት እንግዳ የሆነ ሲበዛ ደግሞ ተቃራኒው (hostile) አድርጎ የማሰብ አዝማምያ አሁንም ይታያል። በዚህም የተነሣ ባህሉን ሐይማኖቱን ወይም ባጭሩ ማንነቱን የሚቃረን ነገር በሰማ እና ባየ ቁጥር ለዛ መልስ በመስጠት (reaction) ተወስኖ ቀርቷል።
- በጥበብ አዳራሽ እና በስፖርቱ ሜዳም ቢሆን ተሳትፎው አለ ተብሎ የሚቆጠር አይደለም። በተለይ ጥበቡ የሚመለከተው ጉዳይ አይመስልም።

ለማጠቃለል

- ሙስሊሙ ከአደባባይ ርቋል
- ተከታይ እንጂ ፈር ቀዳጅ አይደለም
- ለሐገሩ ሁለንተናዊ እና የተመዛዘነ ዕድገት/ልማት የቁጥሩ ክብደት (ratio) ያህል አስተዋጽኦ ሊኖረው አልቻለም።

4. ወቃሽ ተወቃሽ

ከላይ በንኡስ ምዕራፍ 3 እንደተብራራው ምንም እንኳን የሙስሊሙ ተሳትፎ በአጠቃላይ ሲታይ ከዛሬ 33 ዓመታት በፊት የተሻለ ቢሆንም የሚጠበቀውን ያህል አለመሆኑ ግን ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። ለዚህ ብዙ ምክንያቶች ሲሰነዘሩ ይሰማል። ከነዚህም ውስጥ፡ -

- በሽብር ስም መላው የሙስሊሙን ህብረተሰብ ቀፍድዶ የመያዝ አለም አቀፍ ደባ በመኖሩ።
- የሴኩራሊዝም መመሪያ/ፍልስፍና በተግባር ከተተረጎመው ይልቅ የሕገ-መንግስቱን ንቅዒት ማስዋቢያ ከመሆን ያላለፈ መሆኑ
- ለምዕተ ዓመታት ወደ ኋላ የተጎተተ ህብረተሰብ የማስተካከያ በተለይም የAffirmative Action ተጠቃሚ በማድረግ የእርምት እርምጃ ባለመወሰዱ
- ሌሎችም

በዚህ ውይይት/Forum ግን እንድናየው የፈለኩት ሙስሊሙ ህብረተሰብ ራሱስ የችግሩ ምንጭ አይደለም ወይ የሚለውን ነው። ሌሎች ላይ ጣት በመቀሰር ሐላፊነትን የተወጣን ሊመስለንና ጊዜያዊ የዐዕምሮ እረፍት ልናገኝበት ይቻለን ይሆናል። ይህ ግን የዘለቄታ መፍትሔ የሚያመጣ አይደለም። አንድ ህብረተሰብ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩበትን ውጫዊ ሐይላት ከመጋፈጡ ጋር ወይም በፊት ራሱንም critically ማየቱ የተሻለ መሆኑ ጥርጥር የለውም።

ከዚህ ጋር ተያይዞ እንደ አንድ መሠረታዊ ችግር የሚታየው ስለዚህ ዓለም የተወሠኑ ሙስሊሞች ያላቸው ምናልባትም የተሳሳተ አመለካከት ነው። ከዚህ አንጻር ታዋቂው ኢትዮጵያዊ ሸህ ሠይድ መሐመድ ሲዲቅ የዛሬ 40 አመት ስለ ሙስሊሙ ችግሮች ከጻፏቸው ላይ ሁለቱን በመውሰድ ለውይይት ለማቅረብ እወዳለሁ።

ይህ ዓለም የመጪው ዓለም መሸጋገርያ ስለዚህም ጊዜያዊ መኖሪያ ተደርጎ መወሰዱ በእስልምና ተቀባይነት ያለው አመለካከት ነው። ነገር ግን አንዳንድ ሙስሊሞች ይህን አመለካከት በተዛባ መልኩ በመለጠጥ፡

1. ምድራዊ አለምንም ሆነ የራስን ሁኔታ መቀየር የሚቻለው በጾም በጸሎት ብቻ መሆኑን አበክረው ይገልፁሉ። እንዲፈጸም ወይም እንዲቀየር ለሚፈልጉት ነገር ሁሉ ለጸሎቱ አብዛኛውን ጊዜና ሐይላቸውን ይሠጡታል። ይህ አመለካከት ተለጥጦ ሲወሰድ ሥራንና ታታሪነትን የሚገል ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ መገለልን እና ስንፍናን ያወርሣል። ይህ ታዋቂው ሸህ ሠይድ መሐመድ ሲዲቅ ሲታገሉት የነበረው አንዱ «ጣአት» ነው። ሸህ ሠይድ የዱአን አስፈላጊነት ከማንም ያላነሠ የተገነዘቡ ሰው መሆናቸው እንዳለ ሁኖ በስራ መታገዙን ግን አበክረው ይገልጹ ነበር።
2. ሌላው ከቀዳ ወልቀደር ጋር የተገናኘ ሲሆን ቀዳ ወልቀደር ማለትም «በአላህ ወይም በተፈጥሮ ህግና ሥርዓት» ማመን ከእስልምና የኢማን መሠረቶች አንዱ ነው። ይሁንና በቁርአንም ሆነ በሐዲስ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ሰበብን («Cause and effect») የሚያስቀር አይደለም። አንዳንድ ሰዎች ለስንፍናቸው እና ለሐላፊነታቸው መዘናጋት ይህን እንደ ምክንያት ያቀርቡታል። ሸህ ሠይድ ይህንን ነገር ሲያብራሩት «ወንጀል የሠራ ሠው በቀደር ሊጠለል አይችልም! የሚገባውን ቅጣት ማግኘት ይገባዋልና።» ሼህ ሠይድ ሰፋ አድርገው ሲያዩት ሙስሊሞች በተሳሳተ የቀደር አመለካከት፡-

    - ለመብታቸው ከመቆርቆር
    - ከሥራ እና ከትምህርት
    - ከሌሎችም አያሌ የማህበራዊ ግልጋሎቶች ራሳቸውን አግልለዋል ይላሉ። እንደውም እንደተ ጥመለመለ አካል (paralyzed body) አይነት ማህበረሰብ ሆነዋል ይላሉ።

ታዋቂው የግብፅ ሸህ አልቃርዳዊ (አል አዝሐር ዩኒቨርሲቲ) «Economic security in islam» በተሰኘ መጽሐፋቸው እስልምና ምናኔን እና Predestinationን እንደሚያወግዝ በጽኑ አስቀምጠዋል። የPredestination አመለካከት ድሃው ህብረተሰብ ከሚገኝበት የድህነት ቀንበር ተፈትልኮ እንዳይወጣ ትልቅ እንቅፋት ሆኖበታል ይላሉ። ትክክለኛ አማኝ ለችግሩ ምንግዜም እና ያለማቋረጥ መፍትሔ የሚያፈላልግ ነው፤ ልክ ለረሃቡ ምግብ ለጥማቱ ውሃ እንደሚያፈላልግ ሁሉ።

ከላይ የተጠቀሱት የተሳሳቱ አመለካከቶች የሚከተሉት አይነት አሉታዊ ተጽእኖ አላቸው፡-

- ሰብዓዊ ፍጡር እንደ የለውጥ ሐይል (Change Agent) የማየት እይታን ያደበዝዛሉ
- በራስ ጥረት ለውጥ ወይም ዕድገት የማምጣት ቁርጠኝነትን ያኮላሻሉ
- ሥራን አጥርቶ እና አሚጦ የመስራት ፍላጎትን ይገድባሉ።
- የሥራ ሥነ-ምግባሮች (Professional ethics) የሚኖራቸውን ዋጋ ያሳጣሉ
- ብቃት ወይም አሸናፊነት የሚመዘኑበትን አንጻራዊ ሚዛን ያዛባሉ
- ሰዎች ከስራቸው ወይም በአጠቃላይ ከኑሯቸው በተያያዘ ሒስ የመሰጣጠት አቅም ያሳጣቸዋል
- ጥናትና ምርምር አላስፈላጊ (Irrelevant) ይሆናሉ
- ሥራዎች ውጤት ላይ ያላተኮሩ እና የደበዘዘ ዓላማ የያዙ ይሆናሉ
- ሰዎች በሐላፊነት እንዳይጠየቁ መደበቂያ/መከለያ ሆነው ያገለግላሉ
- ዕቅድ ወይም ራዕይ በፍጹም ቦታ የላቸውም።

ሰፋ አድርገን ስናያቸው ደግሞ ወደ መምታታት (Confusion)፣ ቀቢጠ-ተስፋነት ብሎም ወደ ሥርዐተ-አልበኝነት (Anarchy) ሊወሰዱ የሚችሉ ይሆናሉ።

5. ምን ሊደረግ ይገባል?

ከላይ የተዘረዘሩት የሙስሊሙ ማህበረሰብ ችግሮች ለእሱ ብቻ የሚተው አይደለም። ይህ የሐገር ችግር ነው ተብሎ እንደሚታመን ጥርጥር የለውም። እንኳን የሐገሪቱን እኩሌታ የያዘ ማህበረሰብ ቀርቶ በጣም አናሳ (minority) ተብለው ለሚቆጠሩ ማህበረሰቦችም ሁለንተናዊ እድገት ማሰብ ወይም መጨነቅ የሐገር ግዴታ ነው። በሌላ ወቅት እና በሌላ አህጉር አንድ ሰው እንዳለው፡-

“አንድ ሐገር በውስጡ ለሚገኙ ለመጨረሻዎቹ Disadvantaged ማህበረሰቦች መብት መቆም ካልቻለ እንደ ሐገር መቀጠል ይሳነዋል፡፡”

ሸህ ሠይድ በጊዜያቸው በየመንግሥት መ/ቤቶች እየሄዱ የሚከተለውን ይሉ ነበር፡-

“ለብቻችሁ ልታድጉ ፈለጋችሁ - እንጎትታችኋለን!”

እንግዲህ መፍትሔው መታሰብ የሚገባው በአንድ ላይ እንጂ በተናጠል መሆን አይገባውም፡፡ ይህንን ማድረግ ከቻልን ርቀቱ በቀላሉ መጥበብ እንኳን ባይችል፣

- መተሳሰቡ ትልቅ ተስፋ ይጭራል
- በመግባባት ላይ የተደላደለ የችግር አፈታት አካሄድ በመሆኑ አላስፈላጊ ጊዜ እና ጉልበት ይቆጥባል።
- ጉዳዮቹ የፖለቲካ መልክ እንዳይኖራቸው ያግዛል ወይም የፖለቲካ ሥልጣንን እንደ ብቸኛ የመፍትሔ ጎዳና የመውሰድ ቁርጠኝነት ይቀንሳል።

ዋቢ

1. **ቅዱስ ቁርዐን**

ከቻልን ርቀቱ በቀላሉ መጥበብ እንኳን ባይችል፡-
መተሳሰቡ ትልቅ ተስፋ ይጭራል የነብዩ መሐመድ ሐዲሶች እንግዲህ መፍትሔው መታሠብ የሚገባው በአንድ ላይ እንጂ በተናጠል መሆን አይገባውም። ይህንን ማድረግ Al-Khardawi «Economic Security in Islam» **ሸህ ሠይድ መሐመድ ሲዲቅ «ለብቻችሁ ልታድጉ ትፈልጋላችሁ - እንጎትታችኃለን!»።**

እስልምና እና ልማት በኢትዮጵያ **አስተያየት**

መሀመድ ሳላህ

"እስልምና እና ልማት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ አቶ መሀመድ አህመድ ሸሪፍ በርዕይ 2020 በሚለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር መድረክ ለመወያያ ባቀረቡት ፅሁፍ ላይ ያለኝን አስተያየት እንዳቀርብ በመጋበዜ አመሰግናለሁ።

የአስተያየቴም ይዘት እንደሚከተለው ይሆናል።

1. መግቢያ

የፅሁፉ አቀራረብ በቁርአን የትንታኔ ስልት ላይ እንዲሆን መጀመሪያው ላይ፣

ሀ. የአትኩሮት ነጥቦችን ያመለክታል። ማለትም Boundary and frame of reference በውል ያስቀምጣል። ቀጥሎም ጭብጦችን በመረጃ ለማስደገፍ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ከጉዳዩ ጋር የተዛመደውን የኢትዮጵያን ታሪክ ይዳስሳል። ያለፈውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን Socio-economic survey አሁን ካለው ሁኔታ ጋር በተለይም ከማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሕጋዊ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ለቀጣዩ የፅሁፍ ጭብጦች መሰረት ይጥላል። በዚህ መሰረት አሁን ያለውን ሁኔታ የወደፊቱን በ2020 መሰረት ራዕዩን ያመለክታል።

2. ዝርዝር ጉዳዮች

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራ|ጂ /Strategic and international/ relation በተለይም ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር በቅርቡ የተቆራኘ መሆኑ አሌ የማይባል ሀቅ ነው። የዚህ ግንኙነት ጠንካራ መሰረቱ ሀይማኖታዊ መሆኑን በግልፅ ያስቀምጣል። ከጣኦት አምላኪ መሪዎች ጥቃት ሸሽቶና በነብዩ መሀመድ (ሰ.አ.ወ) መመሪያ የመጣው ቡድን በኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ጊዜ መቆየት የሁለት ታላላቅ እምነቶች ተከታይ የኢትዮጵያ ህዝብ የመልካም ግንኙነት መሰረት እንደነበረ ፅሁፉ ይገልፃል።

ክርስትና ከመካከለኛው ምስራቅ ተነስቶ ወደ ኢትዮጵያ በአረቦች አማካኝነት መምጣቱን በተመሳሳይነት ኢስላምም በአረቢያ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱን- በሁለቱም እምነቶች ላይ ተመስርተው በተገነቡት የፖለቲካ

[1] አቶ መሐመድ ሳላህ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአካውንቲንግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በተለያዩ ቦታዎች በኃላፊነት ሠርተዋል። በአሁኑ ሰዓት በኑር ሰላም ኮሌጅ ረዳት ዲን ሲሆኑ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በ Accounting and Finance ላይ እየሠሩ ይገኛሉ።

ሀይሎች መሀከል በተካሄደው ትግል እነዚህ ሀይሎች መዳከማቸውንና የማዕከላዊ መንግስት /Central Government/ መዳከምና መውደቅ ምክንያት መሆኑን ይጠቅሳል። /The Great Oromo Migration sociological and political/ ውጤቶችንም ይገልፂል።

- በተለይም የዚህ ሂደት ዋነኛ ውጤት የሆነው የኢትዮጵያ ምስራቃዊ ኢስላማዊ አካባቢ
- የበርካታ ብሄረሰቦች የላላ ኮንፌደሬሽን ፈጥረው፣
- የትምህርትና የጥበብ ማዕከል፣
- የሀገር ውስጥ የባህር ማዶ የንግድ መስመሮች እንብርትነት ለረጅም ጊዜ በአጼው ስርአቶች እስኪፈርስ ድረስ ማገልገሉን እንደዚሁም
- ይህ አካባቢ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ መስመር ብቻ ሳይሆን የአምልኮት፣ የምሁራንና ሃይማኖት ማዕከል እንደነበረ ጽሁፉ ይገልፂል።

ጸሐፉ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ሃብትን መጠቀምና መንከባከብ እንዳለበት እንዲሁም ለአምላኩ ተገዥ በመሆን በምድር ላይ ያሉ ፍጡራንን ሊጠቀምባቸው እንደሚገባ ያብራራል።

3. ልማትን በተመለከተ

ልማት (ዴቬሎፕመንት) የሚለውን ተመጣጣኝ የእንግሊዘኛ ቃል ያለመኖሩን ብዬ ነው የተረዳሁት። በመሆኑም ኢስላማዊው ፍቺው ሰው በአምላኩ የተለገሱትን የተፈጥሮ ሀብቶች ለራሱ ፈላጎቶችና ምቾቶች እርካታ ሊያስገኙ በሚችሉበት ሁኔታ አደራጅቶና ቀይሮ መጠቀምን ያመለክታል። ይህንንም ለማከናወን ጥረት በሚያደርግበት ሂደት ውስጥ የህይወትን ሁኔታ አመቺ ማድረግ እንጂ መለኮታዊ እምነቱን የመለወጥ ግብ የለውም። እምነቱን በቁሳዊ ፍላጎቶች እርካታ መቀየር አያስፈልገውም የሚል ፅንሰ ሀሳብ ነው ልማት።

ሌላኛው ኢስላምና ኢኮኖሚክስ እንዴት ይገናኛሉ የሚል ዘውትር የሚሰማ አስተያየት አለ። ለዚህ አጭር ፅሁፍ አቀራረብ እንዲያመች ኢኮኖሚክስን እንደሚከተለው ተርጉሜዋለሁ። የዚህ ትርጉም መሰረቱ አስተያየት የምሰጥበት ፅሁፍ ነው። ኢኮኖሚክስ እንደ እውቀት ስርዓትነቱ የሚያመለክተው የማምረት፣ የልውውጥና ፍጆታ ሂደቶች የተመሰረቱባቸውን መርሆዎች ነው። የአስተሳሰብ ስርዓት እንደመሆኑ የተጠቀሱት የክንዋኔ ዘርፎችንና እነርሱም የተመሰረቱባቸው መርሆዎች በፅንሰ ሀሳቦችና መመሪያዎች ያመለክታል።

የኢኮኖሚክ ስርዓት ደግሞ የሚያመለክተው የኢኮኖሚውን አደረጃጀትና የዚህም ልዩ መርሆዎችን ነው። ለምሳሌ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ስርዓት፣ የፊውዳል የኢኮኖሚ፣ የቅይጥ ኢኮኖሚ ስርዓት እንደሚባለው ነው።

ኢስላም የማምረት፣ የመለዋወጥ፣ የክፍፍልና የፍጆታ ተግባራት የሚገነቡባቸው መለኮታዊ ወይም ኢስላማዊ መርሆች ፅንሰ ሀሳቦችና ደንቦች ያሉት በመሆኑ ኢስላማዊ የኢኮኖሚ ስርዓት የሚባል

የህብረተሰብ አደረጃጀት ይገኛል። የዚህም የኢኮኖሚ ስርዐት ኢስላማዊ መሰረቶች በፅሁፉ ውስጥ በአጭሩ ተዘርዝረዋል።

በፅሁፉ ውስጥ የፅሁፉ አቅራቢ የጠቀሱት አንዱ ሀሳብ የኢስላማዊው የሱልጣኔቶች ኢኮኖሚያዊ ፋኢዳ እና በፋይናንስ ረገድ ያበረከቱት አስተዋፅኦ ነው። የሱልጣኔቶች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ጉልህ ገፅታው በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ይደረግ የነበረው የገቢና የወጪ ነግድና ከዚህም የተያያዘው የፋይናንስ እንቅስቃሴ ነው።

እንደሚታወቀው በቅርቡ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የፋይናንስ እንቅስቃሴ የተጀመረው በአቢሲኒያ እስቴት ባንክ ስያሜ በተቋቋመው ባንክ ነው። ይህም ባንክ ለረዥም ጊዜ የፋይናንሱ ዘርፍ በመንግስት የፋይናንስ መቆጣጠሪያ መሳሪያነት ሲያገለግል ቆይቷል።
ለዘርፉ ማደግና መስፋፋት ረዳት ሊሆኑ የሚችሉ የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ ሲገድብ የቆየበት ወቅት ነው እስከ 1964 ድረስ። ይህ ወቅት እምብዛም በፋይናንሱ ዘርፍ የጎላ እድገት ያሳየበት ወቅት አልነበረም።

1965 ግን በርካታ የግል ባለሀብቶች በፋይናንሱ ዘርፍ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ያሳዩበት ዓመት ነበር። ይህ ወቅት አብዛኛው የአፍሪካ አገሮች ገና ከቅኝ ግዛት ስርዓት ያልተላቀቁበትና አውሮፓም ከደረሰበት (2ኛው የዓለም ጦርነት ተብሎ ከሚጠራው) ድቀት ገና ያላገገሙበት ወቅት ነበር። 1966 የመጣውና የግል ሀብትን ወደ መንግስት ያዛወረው አብዮት ግን ዘርፉ በእንጭጭነቱ እንዲቀጭ አድርጎታል።

ከ1983 በኋላ የተፈጠረው ሁኔታ ደግሞ የግል ባለሀብቶች በፋይናንሱ ዘርፍ ሰፊ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ የሚረዳ የህግና የፖሊሲ አመቺ ሁኔታ አስገኝቷል። ይህንንም በመጠቀም በርካታ የግል ባለሀብቶች በዘርፉ እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ የዚህ ዘርፍ የወደፊት የእድገት እድል በግል ባለሀብትነትና የዘርፉንም አገልግሎት ለመጠቀም የሚችለውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ በማሳተፍ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ነው።

ይህ ካልሆነ ግን የፋይናንሱ ዘርፍ የእድገት እድሉ የሚቀጭና ያልተመጣጠነ የጂአግራፊ አካባቢዎችን እድገት የሚያስከትል ይሆናል። ይህ ደግሞ ለልማት አመቺ ሁኔታን አያሰገኝም።

መለኮታዊ የእምነት ስርዓቶች ወለድ መብላትን አጥብቀው ይኮንናሉ። በኢስላም ወለድ መብላት ከባድ ከሚባሉት ወንጀሎች ውስጥ የሚቀመጥ በመሆኑ ኢስላምን አውቆ የሚተገብር አማኝ ወለድን መብላት አይደፍርም አይጠጋውም እንዲያውም ይሸሸዋል። የኢትዮጵያን አብዛኛው ክፍል የሚወክለው ሙስሊሙን የማስተናገድ የፋይናንስ ስርዓት አመቺ የእድገት እድል አለው ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር ያዳግታል።

የረዥም ጊዜ ፋይናንስ ዘርፎች ተብለው በሚጠሩት ውስጥ ፋይናንሲንግ፣ ተርም ሎንስ ተብለው የሚታወቁት ከወለድ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ሙስሊሙን ተጠቃሚ አያደርጉም። የአጭር ጊዜ ብድርም እንዲሁ።

ሌላኛው ሙስሊሙ ሊሳተፍበት የሚችለው ዘርፍ ኤኪውቲ ፋይናንሲንግ ነው። ይህ ደግሞ ለእድገቱ የሚያስፈልገው፡- እስቶክ የሚገዛበትና የሚሸጥበት ቦታ ባለመኖሩ እና ዲቪደንድ ሳይጠብቅ በእጁ ያለን አክሲዮን ፈጥኖ ለመሸጥ ቢፈልግ ሁኔታው ስለሌለ የእስቶክ ኤክሰቼንጅ ባይኖርም የእስቶክ መነገጃ ባለመኖሩ።

የፋይናንስ ሬሶርስ ከአንዱ ወደ ሌላኛው በቀላሉ ለመዘዋወር አስቸጋሪ ነውና ይህም በተጠቀሱት ሁኔታዎች ለማደግ ያለው እድል ጠባብ ነው። የኢትዮጵያም ሙስሊም በፋይናንሱ ረገድ ያለው ተሳትፎ ያንኑ ያህል ጠባብ ነው።

በማይክሮ ፋይናንስ እንዲሁም በማይክሮ ክሬዲትም ዘርፍ ከወለድ ጋር በተያያዘ ምክንያት የሙስሊሙ ተሳትፎ አናሳ መሆን የዘርፉን የእድገት እድል የጠበበ ያደርጋል። መፍትሄውም ኢንተረስት ፍሪ /ወለድ የማያስከፍል/ ባንክ እንደሌሎቹ አገሮች ሁሉ ማቋቋም ብቻ ነው።

ሌላኛው ለኢትዮጵያ የፋይናንስ እድገት ከፍተኛ የእድገት አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችለው የዘካት ስርዓት ነው። የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፋኢዳ ከሌሎች አገሮች ዘርፍ ጥናት ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል። እጅግ ከፍተኛ ኢኮኖሚክ ሀብት ለማንቀሳቀስ ስለሚረዳ።

ኢስላም ድህነትን የሚዋጋ ስንፍናን የሚወነጅል እውቀት መገብየትን የግልና የጋራ ሃላፊነት የሚያደርግ ሃይማኖት ነው። የዚህንና የቀጣዩንም አለም ዓላማዎች አስታርቆ ሙስሊሙ ህይወቱን እንዲመራ የሚያግዝ የበዓላት ብዛት የሌለበት እንዲሁም በበዓላት ቀናት ስራ መስራትን የማይከለክል ሀይማኖት ነውና ለእድገት አመቺ ነው።

የሙስሊሙ ዓለም ታሪክ ያስመዘገበው አኩሪ ድሎች አሉት። ደህነትን መቅረፍ ሳይሆን ድህነትን ማጥፋት በሰው ልጅ ታሪክ ያስመሰከረ ኢስላም ብቻ ነው። ለሰርገኛ ጥሎሽ የመስጫ፣ ለእውቀት ፈላጊ መፅሀፍ መግዣ፣ የቤትና የጋማ እንሰሳት ሲያረጁ የመጦሪያ ቦታ ያዘጋጀ፣ የቤት ሰራተኞች በስራ ምክንያት በሚደርስባቸው የእቃ መጥፋትና መሰበር የመተኪያ ገንዘብ የሚያዘጋጅ ኢኮኖሚያዊ ስርዓት የነበረው ነው። አሁንም ይህንን ስርዓት ለመገንባት የሚያስችሉ መርሆዎች ያሉት ነው።

የኢስላማዊው የልማት ፅንሰ ሀሳብ የሰዎችን የችሎታ ልዩነት ተቀብሎ ተግባራዊ የሚያደርግና የሚቀበል ነውና የሰዎችን በሀብት መበላለጥን አይቃወምም። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ያሉበት ስፍራ ጂኦግራፊያዊና ስትራቴጂክ ጠቀሜታ አለው። ይሁን እንጂ ከእድገት ወደ ኋላ የቀሩ አካባቢዎች የሚባሉት ሙስሊሙ የሚኖርባቸው ናቸው። ይህም የታሪክ አጋጣሚ ሳይሆን ከዚህ በፊት ይራመድ የነበረ የጋራ ውጤት ነው /deliberate politically motivated policy result ነው/።

ትምህርትና ስልጠናን በተመለከተ ትምህርት ከእምነት የሞራል እሴቶች ጋር መጋጨት አይኖርበትም። የትምህርት ሥርአቱ የሙስሊሙን ዝቅተኛ ተሳትፎ የሚያሳድግ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ለማልማት የሚያስችል ሊሆን ይገባል። ለዚህም Science & technology ተቋማት መስፋፋት ጠቃሚ ነው።

የ2020 ራዕይ በተመለከተ የውል አላማ የጋራ እንቅስቃሴን ይሻልና የኢትዮጵያ ህዝቦችን የሚጠቅም መሰረተ ልማት መገንባት። የተቋማት ግንባታ የሚሄድና ለእድገት ማነቆዎች መፍትሄ ለማሰገኘት የሚችል የትምህርት ስርዓት መገንባትን የሚጠይቅ መሆን ይገባዋል፡፡

የሲቪል ማህበራት ለኢትዮጵያ ዕድገት የሚኖራቸዉ አስተዋጽኦ[1]

ካሳሁን ብርሃኑ[2]

1. መግቢያ

ይህ ጽሑፍ ከላይ በተጠቀሰዉ ርዕስ የኢትዮጵያ የኤኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ከ1995 ዓ.ም. ጀምሮ "ርዕይ 2020 በኢትዮጵያ" (Vision 2020 Ethiopia) እየተባለ በሚታወቀው ወርሃዊ መድረኩ ላይ ለውይይት የቀረበ ነው ።

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በአጠቃላይና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገሮች የሲቪል ማህበራት (Civil Society Organizations) መፈጠር ለማህበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገት መሠረት መያዝና መስፋፋት በተለያዩ ደረጃዎች አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ይታወቃል ። በኢትዮጵያ ውስጥም የሲቪል ማህበራት አሁን ጽንሰ ሃሣቡን በምንረዳው መልኩ ብቅ ብቅ ማለት ከጀመሩ ወዲህ ምንም እንኳ ዕድገትና ጥንካሬያቸው ውሱን ቢሆንም በተመሣሣይ ሁኔታ ከሞላ ጐደል የራሳቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ በመጣር ላይ ይገኛሉ። ይህንን ስንል፣ ሲቪል ማህበራት ተመሥርተዉ ለማደግና ለመጠናከር በሚያደርጓቸው ጥረቶች የሚያጋጥሟቸውን የዕለት ተዕለትና መዋቅራዊ (structural)፣ ፖሊሲ-ነክ፣ አስተዳደራዊና ፓለቲካዊ ችግሮችና እንዲሁም በልምድና አቅም እጥረት ሳቢያ በራሳቸው በሲቪል ማህበራት ላይ የሚታዩትን ድክመቶች ሳንዘነጋ ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከሲቪል ማህበራት ጋር ግንኙነት ያላቸውን አንዳንድ ነገሮች ማለትም ምንነታቸውን፣ አመሠራረታቸውን፣ የሚለዩዋቸውን ባሕርያት (characteristics)፣ ዓይነታቸውን (types)፣ ሚናቸውን (roles) እና ከመንግሥት ጋር ያላቸውን ግንኙነት አስመልክቶ፣ በአጠቃላይና በአጭሩ ያወሣል። በመቀጠልም ከእነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት ጉዳዮች አንጻር በኢትዮጵያ የሚገኙ የሲቪል ማህበራት ሁኔታ ይዳሰስና በመጨረሻም ከአንድ ትውልድ በኋላ የሲቪል ማህበራት ለኢትዮጵያ ዕድገት የሚያደርጉትና ሊያደርጉ የሚገባቸውን በተመለከተ ፀሀፊው ያለውን ራዕይ ለታዳሚዎችና ለአንባቢያን በማካፈል ያጠቃልላል።

[1] ሚያዝያ 26 ቀን 1999 ዓ.ም የተካሄደ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡፡

[2] ዶ/ር ካሳሁን ብርሃኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት ዲፓርትመንት ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ ደ/ር ካሳሁን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በፖለቲካል ሳይንስ አለም አቀፍ ግንኙነት ከአዲስ አበባ ዩኒቨሪስቲ ያገኙ ሲሆን የማስትሬት የዶክትሬት ዲግሪአቸውን ከሆላንድ አግኝተዋል፡፡ ዶ/ር ካሳሁን የተለያየ የምርምር ሥራዎችን በምግብ ዋስትና በአስተዳደር ነፃነት በግጭትና ግጭት ማስወገድ በፖለቲካ ፓርቲና ሕገመንግስት ዙሪያ አካሂዳዋል፡፡ ዶ/ር ካሳሁን በተለያየ የፖለቲካ ቦታዎች ላይ የሰሩ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሶሻል ሳይንስ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዲፓርትመንት ኃላፊ እንዲሁም በምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የማህበራዊ ሳይንስ ምርምር ኢንስቲትዩት ረዳት ፕሬዚዳንት እና በፎረም ሶሻል ሳይንስ (Forum for Social Studies) በፕሬዝዳንትነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

2. የሲቪል ማህበራት ጽንሰሃሳባዊ እድገት፣ መገለጫዎችና ባህርያት

2.1 ጽንሰ ሃሳብ

የሲቪል ማህበረሰብ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ መታወቅ የጀመረዉ የመካከለኛዉ ዘመን ሥርዓት (middle ages) የተዋቀረባቸዉ ዋና ዋና አስተሳሰባዊና ርእዮተ ዓለማዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መሰረቶች እየተሸረሸሩና ተጽእኖዎቻቸዉ ቀስ በቀስና በየደረጃዉ በአዳዲስ የፍልስፍና አመለካከቶች እየተተከ በሄዱበት በ17ኛዉና በ18ኛዉ ክፍለዘመናት አካባቢ ነዉ። የጉልተኛዉ (feudal) ሥልተምርትና ሥርዓት በዉሥጡ በያዛቸዉ በተለያዩ ተቃርኖዎች የተነሳ በነበረበት ሁኔታ መቀጠል ያለመቻሉና ሥፍራዉን ለተተኪዉ የካፒታሊስት ሥርአት እንዲለቅ መደረጉ ለሲቪል ማህበራት መፈጠር መሰረት እንደጣለ ይታመናል።

በዚህ ሂደት ዉስጥ በርካታ አስተሳሰባዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ለዉጦች በተለይም በፖለቲካ ፍልስፍናዉ መስክ እየጎሉ የመጡ ሲሆን በዚህም ረገድ ስለሕብረተሰብና መንግስት የነበረዉ አመለካከት ቀስ በቀስና በየደረጃዉ እየተቀየረ ሄዷል። ቀደም ሲል መንግስት በመለኮት ፈቃድ የሰዎችን ባህሪ ለመግራትና የሰዉ ልጅ ለመልካም ኑሮና ህይወት እንዲበቃ ለማድረግ የተፈጠረ ተቋም (institution) ነዉ ተብሎ በቤተክህነትና በገዥ መደቦች ሲራመድ የነበረዉ አቋምና ከዚህም ተያይዞ ለመንግስት ፈቃድና ተግባር መገዛት የመለኮትን ፈቃድ እንደመፈፀም ይቆጠራል የሚለዉ አስተሳሰብ[3] የተሳሳተ አዝማሚያ ነዉ የሚል ትችት በተደጋጋሚ ደርሶበታል። በምትኩም መንግስት የተቋቋመዉ ለህዝብ የተረጋጋ ህይወትና ሥርዓት ያለዉ አኗኗር ሲባል በህብረተሰብ ፈቃድና ይሁንታ በማህበራዊ ዉል (social

[3] በእንግሊዝኛዉ " Divine Right School of Thought" ተብሎ የሚታወቀዉ የአስተሳሰባዊና ርዕዮተ አለማዊ ፈርጅ ገዥዎች ስልጣን ላይ የሚወጡት በመለኮታዊ ፈቃድና መቀባት ሆኖ ተግባሮቻቸዉም የሰዉን ልጅ በተፈጥሮ ያልተገራ ባህርይና ጎጅ ዝንባሌዎች መስመር በማስያዝ ሕብረተሰብ ስርዓት ያለዉ የተረጋጋና መልካም ህይወት እንዲኖረዉ ማስቻል ነዉ። በመሆኑም በስልጣን ላይ የሚወጡ ገዥዎችን አመራር መከተልና ድጋፍ መሥጠት ከህብረተሰብ የሚጠበቅ ሆኖ ይህንን ለመጣስ መሞከር የመለኮትን ፈቃድ እንደመተላለፍ የሚያስቆጥር መሆኑን ይሰብካል። የዚህ አመለካከት ዋነኛ አራማጆች በመሆን በመካከለኛዉ ዘመን ገናና የነበረችዉ የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የቅድስና ማእረግ የሰጠቻቸዉ ቶማስ አኩዊናስና አዉግስጢኖስ የተባሉት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ።

contract)[4] በታሰረ አኳኋን የመብትና የግዴታ ባህርያትን ተላብሶ ነዉ የሚለዉ አመለካከት ቀስ በቀስና በየደረጃዉ ተቀባይነትን እያገኘ ለመሄድ በቅቷል።

በምዕራቡ ዓለም የብርሃንና የተሀድሶ ዘመን[5] ተብሎ የሚታወቀዉ የ17ኛዉና የ18ኛዉ ክፍለ ዘመናት ክስተት የሲቪል ማህበረሰብን ፅንሰ ሃሳብ መሰረት ለመጣል ያስቻለ የመጀመሪያ ምዕራፍ (points of entry) ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ለዚህም በፖለቲካ ፍልስፍናና እሳቤ መስክ ሕብረተሰብና መንግስትን የሚመለከቱ አዳዲስ የአስተሳሰብ ዝንባሌዎችና አዝማሚያዎች ብቅ በማለታቸዉና በህብረተሰቡ አእምሮዎች እየሰረፁና ተቀባይነት እያገኙ መምጣታቸዉ እንደ አንድ ምክንያት ይቀርባል። በዚህ ረገድ በየተራና በቅደም ተከተል የምዕራቡን ዓለም አስተሳሰብ (በተለይም መንግስትንና ሕብረተሰብን አስመልክቶ) በመለወጥ አብይና ዐይነተኛ ሚና የተጫወቱ የፖለቲካ ፈላስፋዎችና ሥራዎቻቸዉን መጥቀስና ማስታወስ[6] ተገቢ ይሆናል። ምንም አንኳን የሲቪል ማህረሰብን ጽንሰ ሃሳብ በተመለከተ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ የተወሰኑ ልዩነቶች ቢኖራቸውም፣ እነዚህን ፈላስፎች፣ የሚያስተሳስሯቸው የጋራ አቋሞች ነበራቸው። ከእነዚሁም መካከል መንግስት በሕብረተሰብ ፈቃድና ለህብረተሰብ የጋራ ደህንነት (common good) ሲባል የተመሰረተ ተቋም መሆኑ፣ ሕብረተሰብና ሲቪል ማህበረሰብ ተመሳሳይና ተወራራሽ ጽንሰሃሳባዊ ትርጉም እንደሌላቸዉና፣ ሲቪል ማህበረሰብ መንግስትና ሕብረተሰብን በድልድይነት የሚያገናኝ[7] በፈቃደኛነትና የጋራ ጥቅም ላይ የተማከለ ስብስብ

[4] የማህበራዊ ዉል (social contract) ተብሎ የሚታወቀዉ አስተሳሰባዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ፈርጅ ቀደም ሲል የተጠቀሰዉን የፈቃደ መለኮት (divine Right) አስተሳሰብ ከሞላ ጎደል የሚቃወም ሲሆን የመንግስትና የገዥዎች የሥልጣን መሰረቱ የሕብረተሰብ ፈቃድና ይሁንታ እንጅ ሌላ አይደለም የሚለዉን የአመለካከት አቅጣጫ ያራምዳል። የገዥዎችና የተገዥዎች (የመንግስትና ህብረተሰብ) ግንኙነት ቁርኝትም በማህበራዊ ዉል የታሰረ ሲሆን ይኸዉም መንግስት/ገዥዎች ሕብረተሰቡን ስርዓትያለዉና የጋራ ጠቀሜታን የተላበሰ ህይወት እንዲኖረዉ የመምራትና የማስተባበር ግዴታዎች እንዳሉባቸዉ ያመለክታል። ይህንንም እዉን ለማድረግ ሕብረተሰብ በተፈጥሮ ከተነናፀፋቸዉ የማይገሠሡ መብቶቹ ከፍሎ ለመንግስት በመስጠት መተባበር እንዳለበት የሚጠቁም ነዉ። ይህ አመለካከት መንግሥት በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ይህንን ግዴታዉን ሳይወጣ ቢቀር መለወጥ እንደሚኖርበትና ካስፈለገም በኃይል ወይም በጉልበት ጭምር መወገድ እንደሚገባዉ ይሰብካል።
ለዚህ አመለካከት መሰረት መያዝ አስተዋጽኦ ያደረጉ ክስተቶች ነበሩ። ከነዚህም መካከል በካቶሊክ ቤተክርስቲያን መሪዎችና ምዕመናን መካከል በተለይም በሉተር በተመራዉ የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ ግቢያ የደረሰዉ መቃቃርና መከፋፈል፣ የኢንዱስትሪዉ አብዮት ፈር እየያዘ መምጣትና የአዳዲስ አስተሳሰብ ለዉጦች መሰረት እንዲይዙ የተጫወተዉ ሚና፣ የመካከለኛዉ መደብ (Middle class/ bourgeois) አባላት ተቀባይነት ለማግኘትና ሥልጣን ለመቆጣጠር ያደረጉዋቸዉ እንቅስቃሴዎች በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

[5] ይህ በእንግሊዝኛዉ " The Era of Enlightenment and Renaissance" በመባል ይታወቃል።

[6] ከቀደምቶቹ የሲቪል ማህበረሰብ ጽንሰ ሃሳብ አራማጅ የፖለቲካ ፈላስፋዎች መካከል ቶማስ ሆብስ፣ ጆን ሎክ፣ ሩሶ፣ ሞንቴስኩና፣ ሄግል በዋነኛነት የሚጠቀሱ ሲሆን በሃያኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ አንቶኒዮ ግራምሺና ሌሎች ደግሞ ጽንሰ ሃሳቡን ከቅቡልነት (ሌጂቲሚሲ) በማያያዝ አዳብረውታል። እነዚህ የተለያዩ ሀገሮች ዜግነት ያላቸው ምሁራን በየነበሩበት አከባቢ (እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን) እና ከዚያም ውጭ የጽንሰ ሃሳቡ አቀጣጣዮች በመሆን ለአስተሳሰባዊና ርዕዩተዓለማዊ ለውጦች መሰረት መያዝና በሕብረተሰቡ ውስጥ መስረጽ አስተዋጽኦ በማድረግ የጎላ ሚና ተጫዉተዋል። አንዳንዶቹም በምዕራቡ ዓለም ለተከሰቱት የሶሲዮ ኤኮኖሚና የፖለቲካ አብዮች መንደርደሪያ መሰረቶችን እንደጣሉ ይታመናል ።

[7] ከሲቪል ማህበረሰብ ዋነኛ ባህርዮች አንዱ የሆነዉ በመንግስትና በህብረተሰብ መካከል የአገናኝነት/ የድልድይነት ሚናን በማስመልከት ጆን ሀርበሰን የሚከተለዉን ይላሉ።
"A central feature of civil society is its function in defining and establishing bridges between the guiding norms of the polity and of society. The literature of political philosophy suggests numerous alternatives and, again not necessarily antithetical ways by which this key function may be performed. These included civil society as (a) buffer (b) broker (c) symbol (d) agent (e) regulator (f) integrator (g) representative, and (h) midwife" (Harbeson, 1992 : 31)

መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው (Hobbes 1950, Locke 1967, Rousseau 1987, Migdal 1988, Montesquieu 1949)::

የሲቪል ማህበረሰብን ጽንሰሃሳብ አስመልክቶ በተደረጉት ምልልሶችና የሃሣብ ልዉዉጦች አንድ ጎልቶ የወጣ ጉዳይ በሲቪልና በፖለቲካ ስብስቦች መካከል ያለው ልዩነት ነው። በዚህ አስተሳሰብ መሰረት ሲቪል ማህበረሰብ የሚያካትታቸው ስብስቦች ከፖለቲካ አደረጃጀትና ስልጣን ክልል ውጭ የሚገኙት የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ፣ የመረዳጃና በተመሳሳይ የጋራ ጥቅም ዙሪያ በፈቃደኝነት ተደራጅተው አንጻራዊ ነጻነታቸውን (autonomy) በማስከበር የአባሎቻቸዉን ፍላጎትና ምኞት ለማስፈጸም የሚንቀሳቀሱትንና በጥቅል አነጋገርም መንግስታዊ/ፖለቲካዊ ያልሆኑ ተቋማትን ነው። በአንጻሩም የፖለቲካ ማህበረሰብ (political society) የሚባለው የመንግስትን ስልጣን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የሚቆጣጠሩ ወይም ለምሳሌ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ስልጣን ለመያዝና ለመቆጣጠር የሚጥሩትን የሚያካትት ነው። (Gramsci 1971)። በግራምሺ አመለካከት የሲቪልም ሆነ የፖለቲካ ማህበረሰቦች ሁኔታና ተአማኒነት መታየት ያለበት ካላቸው ተሰሚነትና ቅቡልነት (hegemony and legitimacy) አኳያ ነው። በሌላ አነጋገር ቅቡልነት ስብስቦች በህብረተሰቡም ሆነ በአባሎቻቸው ዘንድ ተአማኒነትና ለሚያራምዱት ዓላማ ከልብ የመነጨ ድጋፍ ሲያገኙ የሚረጋገጥ ጉዳይ ይሆናል። ይህንን የሲቪል ማህበረሰብ ጽንሰሀሳብ አመጣጥና እድገት በተመለከተ የቀረበውን አጭር ዘገባ ከማጠቃለላችን በፊት አንድ መጠቆም ያለበት ጉዳይ አለ። ጽንሰሃሳቡንና በተለይም ተግባራዊነቱን አስመልክቶ በየጊዜው በሚደረጉ ክርክሮችና የሃሳብ ልውውጦች የሚነሳው አብይ ነገር ሲቪል ማህበረሰብ በአስተሳሰብም ሆነ በተግባር ቅርጹንም ሆነ ይዘቱን ያገኘው በምእራቡ ዓለም ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ ስለሆነ ከዚህ ውጭ እንደ አፍሪካ እስያና የሌሎች ክፍላተዓለም ህብረተሰቦች አስተሳሰብና አኗኗር የሚስማማና የሚጠቅም አይደለም የሚለዉ ነዉ። ብዙዎቹ ለዚህ የሚሰጡት ምላሽ፣ ምንም እንኳን ከምእራብ አለም ውጭ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ስብስቦች በብዙ መልኩ ገና በማቆጥቆጥ ላይ እንደሚገኙና በርካታ መሰናክሎችን ማለፍ እንደሚጠበቅባቸው የሚካድ ባይሆንም፣ ለሲቪል ማህበረሰብ መፈጠር መነሻ የሚሆኑ መንግስት፣ ህብረተሰብና፣ የመንግስትና-ሕብረተሰብ ግንኙነትን የመሳሰሉ ነገሮች ከምእራቡ አለም ውጭም ተሟልተው ስለሚገኙ የሲቪል ማህበራት ስብስቦች መፈጠርና እንቅስቃሴ በምዕራቡ ዓለም ብቻ መወሰን አለበት ብሎ መሟገት አያዋጣም በማለት ነው። በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገሮች ያሉት ሲቪል ማህበራት እንደ ምዕራባዊያኖቹ በብዙ መልኩ በበርካታ ምክንያቶች (የግንዛቤና የልምድ እጥረት፣ የመንግስት ተጽእኖዎች፣ የአቅም ውሱንነት ወ.ዘ.ተ) የተነሳ ያልተጠናከሩና እድገታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ የሚያከራክር ባይሆንም በጽንሰ ሃሳብና በተግባር ደረጃ ከምዕራቡ ዓለም ውጭ ሊፈጠሩና ጠቃሚ አስተዋጽኦ ማድረግ አይችሉም ማለት አከራካሪ ይሆናል።

በዚህ ረገድ በአለም ላይ በየጊዜው የሚታዩት በርካታ የሶሲዮ-ኤኮኖሚና የፖለቲካ ለውጦች፣ በህዝቦችና በመንግስታት መካከል በክልላዊ፣ አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ ደረጃዎች እየተስፋፉ የመጡ ግንኙነቶችና የመሳሰሉት ነገሮች ሲቪል

ማህበራት የምዕራቡ ዓለም ክስተቶች በመሆናቸውእንቅስቃሴያቸውና ጠቃሚነታቸውም በዚህ ይወሰናል የሚለዉን አቋም መሠረተቢስ አድርገውታል።

2.2 የሲቪል ማህበራት ምንነት፣ ገላጭ ባህርያትና ሚና

የሲቪል ማህበራትን ትክክለኛ ምንነትና ትርጉም በውል የማሳወቁ ሙከራ በተለያዩ ጊዜያትና መድረኮች እየተነሳና አንዳንዴም ልዩነቶችን እያስከተለ ሄዶ በመጨረሻ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ መደምደሚያ እንደተደረገለት መናገር ይችላል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁንም ቢሆን ሲቪል ማህበራትንና ሕብረተሰብን አንድና ተመሳሳይ አድርጎ የመውሰድ ዝንባሌ ሙሉ ለሙሉ ተወግዷል ለማለት አያስደፍርም።

ይህ አዝማሚያ በተለይም በአፍሪካ የመንግስትና የህብረተሰብ ግንኙነት በሚተነተንበት ጊዜ በሰፊው ይንጸባረቃል (Harbeson 1992፡21)። ይህንን መሰሉንና ሌሎች ጥቃቅን የግንዛቤ ልዩነቶች ለጊዜው ወደጎን ትተን፣ በሲቪል ማህበራት ምንነትና ገላጭ ባህርያት ላይ እጅግ በአብዛኛው ስምምነት በተደረሰበትና በስፋት ተቀባይነት ባገኘው መደምደሚያ ላይ እናተኩር። ይህ መደምደሚያ ሲቪል ማህበራትንና ሕብረተሰብን አንድ አድርጎ የመውሰድን ብዥታ የማጥራት አስፈላጊነት የተለያዩ ምሁራን የሚስማሙበት ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም መሰረት ለሲቪል ማህበራት የተሰጠው ትርጓሜ ዜጎች ከፖለቲካ ስልጣን መለስ ያሉ ዓላማዎቻቸውን ለማራመድ፣ ጥቅማቸውን ለማስከበር በሚፈልጓቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ዙሪያ በፈቃደኝነት የሚፈጥሩት ስብስብ ሲሆን ይህ በመንግስትና በህብረተሰብ መካከል አማካይ ስፍራ ይዞ እንደአገናኝ ድልድይ የሚያገለግል ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ሲቪል ማህበራትና አጠቃላይ ሕብረተሰቡ አንድ አለመሆናቸውን ነው። ምክንያቱም ሕብረተሰብ በአንድ ሀገር አብሮ የሚኖርና የሚሰራ አጠቃላይ ህዝብን የሚገልጽ ሲሆን፣ ሲቪል ማህበራት በህብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ አላማዎችና ፍላጎቶች ዙሪያ የተሰባሰቡ የተወሰኑ የሕብረተሰቡ አባላት የሚፈጥሯቸውና የሚያንቀሳቅሷቸው ተቋማት ናቸው። በእርግጥ የሲቪል ማህበራት አራማጆችና አባላት በዓላማቸው ዙሪያ የሕብረተሰብን ድጋፍና እገዛ ለማግኘት የተለያዩ ጥረቶች ማድረጋቸው አይቀርም። ይህ የሕብረተሰብ ድጋፍን የማግኘት ጥረት መሳካት መቻሉና አለመቻሉ በበርካታ ምክንያቶችና ሁኔታዎች የሚወሰን ስለሆነ ዝርዝር ውስጥ መግባቱ አሁን ከያዝነው ተግባር ወጣ ስለሚል አንገባበትም። ዓላማችን ሲቪል ማህበራትና አጠቃላይ ሕብረተሰብ አንድና ተመሳሳይ አይደሉም የሚለውን ለማጉላት ነው።

በዚህም ተነሳ የአንድ ወይም ከዚያ በላይ ላሉ ሲቪል ማህበራት ሕዝቡ/ ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ አባል ወይም የድጋፍ መሰረት (constituency) አይደለም። የአንድ ሲቪል ማህበር አባላትና የድጋፍ መሰረት የሚሆነው ውሱን የህብረተሰብ ክፍል፣ ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ በመደገፍ በአባልነት የተቀላቀለና የማህበሩን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በንቃት የሚሳተፍ ነዉ። እንዲሁም በስምምነት በተቋቋመ ደንብ መሰረት ግዴታዎቹን የሚወጣና እንደአባልነቱ ሊያገኝ የሚገባውን መብት የሚጠይቅ ነው። ለማጠቃለል ያህል ሲቪል ማህበራት ከፖለቲካዊ/ መንግስታዊ ክልል ውጭ

የሚገኙ የዜጎች ስብሰቦች በቁሳዊ/ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በፍላጎታቸውና በጥቅሞቻቸው አንጻር ተደራጅተው በመንቀሳቀስ አሉታዊ መንግስታዊ ተጽእኖዎችን የሚከላከሉበት ተቋም ነዉ። (Gramsci 1971 :12)

ስለ ሲቪል ማህበራት ምንነት ከላይ የተገለፀውን ካልን በኋላ የሲቪል ማህበራት ገላጭ ባህርያትና ሚና በአጭሩ ምን እንደሚመስሉ እንዘረዝራለን። ሲቪል ማህበራት በመንግስትና በህብረተሰብ መካከል አማካይ ስፍራ በመያዝ ለሁለቱ እንደአገናኝ ድልድይ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው ተገልጾአል። ከመንግስትም ሆነ ከሕብረተሰብ የሚለዩዋቸው ባህርያትን የተላበሱ ናቸው ቢባልም፣ ከሁለቱም ወይም ከአንዳቸዉ ጋር የግድ በተቃርኖ መስመር የተሰለፉ ናቸው ማለት አይደለም። በሌላ በኩልም አንድ ናቸው ማለትም አይደለም። ከመንግስት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት እንደአስፈላጊነቱና እንደሁኔታው የትብብርም የተቃውሞም መልክ ሊይዝ ይችላል። የመላ ህብረተሰብን ጥቅም በጥቅሉ የማይወክሉና የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም በአብዛኛዉ የአባሎቻቸውን ፍላጎት የሚያራምዱ በመሆናቸው እንቅስቃሴዎቻቸው በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚደገፉ ባለመሆኑ በዚህ ሳቢያ ጥቅማችን ይነካል ብለው ከሚገምቱ ክፍሎች አልፎ አልፎም ቢሆን ችግር ሊደርስባቸው ይችላል። ከህብረተሰብ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነትም አሁንም እንደሁኔታው የትብብርም የተቃውሞም መልክ ሊይዝ ይችላል።

የሲቪል ማህበራት ዋና ዋና ገላጭ ባህርያት ተብለው በስፋት የሚታወቁት በፈቃደኝነትና በፍላጎት ከጥቅማቸው አንጻር የአባሎቻቸው መደራጀት፣ ከመንግስትም ሆነ ከህብረተሰብ ተጽእኖ አንጻራዊ ነጻነታቸውን (autonomy) ለመጠበቅ የሚያደርጉት ጥረት፣ እንዲሁም በመንግስትና በህብረተሰብ መካከል እንደ እርከን አገናኝና ድንበር ሆኖ መንቀሳቀስን ያካትታል። ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ሲቪል ማህበራትን እንደአጠቃላይ ህብረተሰብ ስብስቦች አድርጎ መመልከቱ በተለይም እንደአፍሪካ ባሉ በማደግ ላይ በሚገኙ አህጉሮች ጎልቶ መቀጠሉ ጽንሰሃሳቡን በግልጽ ያለመገንዘብን ችግር አስከትሏል።[8]

ቀደም ሲል እደተገለጸው ሲቪል ማህበራት የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን ለማራመድና ለማስከበር በፈቃደኝነት ተሰባስበው መተዳደሪያ ደንቦቻቸውን አዘጋጅተውና የስራ ሃላፊዎችን ሰይመው የሚመሰርቷቸው ተቋማት ናቸው። ሲቪል ማህበራት የሚራመዱአቸው ፍላጎቶች ከአባሎቻቸው ግብና አላማ አንጻር የሚወሰኑ እንደመሆናቸው አይነታቸውም ይለያያል።

ከሞላ ጎደል ተመሣሣይ ዓላማና ግብ ያላቸው ማህበራት ቁርኝት በመፍጠርና አልፎ አልፎ በመዋሃድ የተቀናጀ የጋራ እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉ ብዙ ጊዜ ይስተዋላል። በጥቅሉ የሲቪል ማህበራት ሚና አባሎቻቸው የማቴሪያል፣

[8] ሮበርት ፋተን የተባሉ ፀሐፊ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚከተለዉን ብለዋል ፤

“The forms of state, the nature of civil society, the behavior of citizens and thus the very relationship between state and civil society are not self-contained. The nation state is no longer relatively isolated from the immediate consequence of distant happenings. Social, political and economic linkages between and across long distances and communities have ligatured the world in to a single globalized space” (Fatton 1992 : 23).

የአስተዳደርና የህግ ምክርና እገዛ አገልግሎት እንዲያገኙና ሌሎች ችግሮቻቸውን እንዲቀርፉ መርዳት፣ የመንግስትም ሆነ የሌሎች አሉታዊ ተጽእኖዎች በአባላትም ሆነ በህብረተሰብ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ መከላከል፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ህብረተሰቡና አባላት እውቀትና መረጃ እንዲኖራቸው ማገዝ፣ በባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ አባላትና ደጋፊዎቻቸው በሚያደርጉት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጥረታቸውን ማስተባበርና ማቀናጀት፣ እንዲሁም መንግስትን ከአባላትና ከዜጎች ለማገናኘት የሚረዱ መድረኮችን መፍጠርና ማስፋፋትንና ያካትታል (Dessalegn 2002፡104)። በተጨማሪም ሲቪል ማህበራት በአብዛኛው የሚሰማሩባቸው የስራ መስኮች ሲዘረዘሩ፣ ሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲ፣ ትምህርትና ጤና፣ የተሻሻሉ የአመራረት ዘዴዎች፣ የነፍስ አድን እርዳታ፣ የህግ ምክር አገልግሎት፣ የሴቶችና ወጣት ማህበራትን ማደራጀትና ማጠናከር፣ የብድር አገልግሎት፣ የስነዜጋና ስነምግባር ትምህርቶችና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በሲቪል ማህበራት ደረጃ የሚፈረጁ ስብስቦች እነማን ናቸው የሚለው ሲነሳም በአብዛኛው ስምምነት የተደረሰባቸው፣ የሞያ ማህበራት (trade unions)፣ የባለሞያዎች ማህበራት (professional associations)፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ መንግስታዊ-ያልሆኑ ድርጅቶች (Non-governmental organizations)፣ የህብረት ስራ ማህበራትና፣ የነጻ ፕሬስ ስብስቦች ይጠቀሳሉ። አንዳንዶች የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የንግድ ስብሰቦች፣ እና ባህላዊ ማህበራት በሲቪል ማህበራት ዝርዝር ዉስጥ መካተት እንደሌለባቸው ይናገራሉ (Dessalegn 2002፡104)። በሌላ በኩል፣ በክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት (CRDA) አስተባባሪነት የወጣው መንግስታዊ-ያልሆኑ ድርጅቶች የስነ ምግባር መመሪያ ባህላዊና ልማዳዊ የህብረተሰብ ስብስቦች (community-based organizations) በሲቪል ማህበራት ዝርዝር ውስጥ ሊካተቱ እንደሚችሉ ይገልፂል። በሲቪል ማህበራት ዝርዝር ውስጥ መካተትንና አለመካተትን በተመለከተ እስካሁን ያልተቋጨ በርካታ ክርክሮች አሁንም በመካሄድ ላይ ናቸው።[9] በጉዳዩ ላይ እስካሁን ሙሉ ስምምነት ስላልተገኘ ይህንን አስመልክቶ ቁርጥ ያለ ድምዳሜ ላይ መድረስ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ ጥረቱ መቀጠልና አንድ ማጠቃለያ ማበጀት አስፈላጊ መሆኑ ግን አያከራክርም።

3. የመንግስትና የሲቪል ማህበራት ግንኙነት

ቀደም ሲል ለማመልከት እንደተሞከረውመንግስትና ሲቪል ማህበራት የሚኖራቸው ግንኙነት የተቃርኖ ብቻ ሳይሆን የትብብር መልክም የተላበሰ ነው። ይህ በአብዛኛው የሚወሰነው በአላማዎቻቸውና በእንቅስቃሴዎቻቸው መጣጣም ወይም አለመጣጣም ሆኖ እንደሁኔታዉ ትብብሩ ወይም ፉክክሩ የጎላ ወይም የደበዘዘ እንዲሆን ያደርገዋል። የፖለቲካ ስርአቱ መሰረታዊ ባህርያት የአንድን መንግስት መርህግብሮችና ለየትኛው የህብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም እንደቆመ እንደሚወስኑ ሁሉ የሲቪል ማህበራት መሰረታዊ ተፈጥሮና የሚያራምዱአቸው ግቦችም በተመሳሳይ መልኩ

[9] ጆን ሀበርሰን ይህንን የግንዛቤ ችግር አስመልክተዉ የሚከተለዉን ይላሉ፤
"To the extent that civil society is recognized in contemporary analysis of state-society relations in Africa, it is frequently not differentiated from but treated as synonymous with society at large" (Harbeson, 1992:21)::

ይንጸባረቃሉ። አላማዎቻቸውና የተግባር እንቅስቃሴዎቻቸው ከፖለቲካ ስርአቱ ጋር የሚጣጣሙ ሲቪል ማህበራት በአብዛኛው ከመንግስት ጋር በትብብር የሚሰሩ ሲሆን ከዚህ ውጭ የሚገኙት ከመንግስት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በአብላጫ ወደ ተቃርኖና ፉክክር ያጋድላል። እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን ሲቪል ማህበራት በጅምላ የዴሞክራሲና የህዝብ ጥቅም ጠበቆችና አራማጆች አለመሆናቸውን ነው።[10] የሲቪል ማህበራት ማደግና መበራከት የግድ በመንግስት ላይ ተቃውሞን ማፋፋምም ሆነ የዴሞክራሲን ማበብ አመላካች አይሆንም (Fatton 1992፡30)። ለዴሞክራሲ ማቆጥቆጥና የመንግስትን ጋጠወጥነት ለመግራት ወሳኙ ነገር የሲቪል ማህበራት በደፈናው መበራከት ሳይሆን ዴሞክራሲን መሰረት ለማስያዝ አላማና ግብ አድርገው ተከታዮቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን በመምራት በጥምረት መንቀሳቀሳቸው ነው።

የመንግስትና የሲቪል ማህበራትን ግንኙነት በተመለከተ ማእከላዊውና ወሳኙ ነገር የማህበራት ዋነኛ ባህርይና መገለጫ የሆነውን አንጻራዊ ነጻነት (autonomy) የማስጠበቁ ጉዳይ ነው። መንግስት በአስተዳደራዊ ህግ ሰበብ አስባቦች በሲቪል ማህበራት ላይ ተጽእኖ ለማሳረፍና ከተቻለም የራሱ አጀንዳ አራማጆች እንዲሆኑ ለመመልመል (cooptation) ይሞክራል። ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለአባሎቻቸውና ለህብረተሰቡ ለመስጠት የሚንቀሳቀሱ ማህበራት በየጊዜው ከሚገጥሟቸው ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶች ባሻገር ከመንግስት ጋር ግጭት ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ የተወሰነ ነው። በአንጻሩ እንደሰብአዊ መብት፣ የህግ የበላይነትና የዴሞክራሲ ጉዳዮች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማህበራት በመንግስት በጥርጣሬ እየታዩ ግንኙነታቸው እየሻከረ የሚሄድበት ሁኔታ በብዛት ይስተዋላል (Bratton 1989:429)። አልፎ ተርፎም ከመንግስትና ከፖለቲካ ድርጅቶች ሙሉ ድጋፍና እገዛ እያገኙ በሲቪል ማህበራት ስም የሚንቀሳቀሱ ስብሰቦች እየተበራከቱ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር እየሆነ መጥቷል።

ስለዚህ፣ እነዚህንና መሰል ተቋማትን በተመለከተ የአንጻራዊ ነጻነት ጉዳይ ፈጽሞ ሊነሳ አይችልም። ምክንያቱም ህልውናቸው የተመሰረተው በመንግስት ወይም የፖለቲካ ስልጣን በያዙና ሊይዙ በተዘጋጁ ኃይሎች አነሳሽነት፣ በጎፈቃድና እገዛ ላይ ስለሆነ የራሳቸው ድምጽ አላማና ርዕይ ስለማይኖራቸዉና የሲቪል ማህራት አይነተኛ ባህርይዎችና መገለጫዎች ስለሚጎድሏቸው እነዚህን እንደሲቪል ማህበር መቁጠሩ አዳጋች ይሆናል።

በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገሮች በአጠቃላይ፣ በተለይም ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ አህጉር፣ በምእራቡ አለም ለሲቪል ማህበራት መቋቋም ወሳኝ የሆኑ ዋና ዋና ነገሮች ተሟልተው አለመገኘት በመንግስትና በማህበራት ግንኙነት ላይ የየራሳቸውን ተጽእኖ አሳድረዋል። እንደምእራቡ አለም ለሲቪል ማህበራት ማቆጥቆጥ ወሳኝ ሚና የተጫወቱ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች በአፍሪካም ሆነ በሌሎች ብዙ የሶስተኛ አለም ሀገሮች ጎልተዉ አይታዩም።

[10]በሲቪል ማህበርነት መፈረጅ ያለባቸዉ እነ እገሌ ናቸዉ ብሎ ቁርጥ ያለ መልስ የመስጠትን አስቸጋሪነት አንድ ፀሐፊ እንዲህ ሲሉ ይገልፂሉ፣

"Civil Society is not a sector with well-defined boundaries. It is a notion of a civic system that interacts and overlaps with socio-political and socio-economic systems" (Alan Fower Cited in Sisay Gebre-Egziabher 2002:4).

በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታው በኢንዱስትሪ አብዮት ላይ የተመሰረተ የካፒታሊስት እድገት ያለመኖሩና በዚህም ሳቢያ ሊፈጠሩ የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች (በተለይም የወዝአደርና የከበርቴ መደቦች) እንዲሁም ከዚህ አንጻር መልክ የያዙ ማህበራዊ ግንኙነቶች እውን አለመሆን ጠንካራ የሲቪል ማህበራት እንዳይፈጠሩ ምክንያት ሆነዋል። በፖለቲካ ረገድም እንደምእራቡ አለም፣ የመንግስት ክልል በሆነውና ከዚህ ውጭ ባለው (public versus private) መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ ካለመሆኑም ሌላ በሁለቱ መካከል የጠራ ክፍፍል (separation) አይታይም። በኢኮኖሚው መስክ ደግሞ እንደ አፍሪካ መንግስታትና ህብረተሰቦች ሁሉ የሲቪል ማህበራትም በውጭ እርዳታና ድጎማ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው አይነተኛ መለያቸው ሊሆን የሚገባው አንጻራዊ ነጻነት ፈተና ላይ ይወድቃል። ስለዚህም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ የመንግስትና የሲቪል ማህበራት ግንኙነት ሚዛኑን በመሳት ወደአንድ ወገን ማጋደሉ አይቀሬ ነዉ። (Lewis 2002:577)። እንደ አፍሪካ ባሉ አህጉራት፣ በማህበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የመንግስት ቁጥጥርና ተጽእኖ ጉልህና ወሳኝ በመሆኑ የሲቪል ማህበራት ሕልዉናም ሆነ እንቅስቃሴ እንዲሁም የሚጫወቱት ሚና በአብዛኛዉ የፖለቲካ ሥርአቱን ይሁንታ ማግኘት የግድ ይላል።

4. የሲቪል ማህበራትና ዕድገት (Development)

እድገት ዘርፈ-ብዙ ጽንሰሃሳባዊ እንድምታዎች ያሉት ሲሆን በተለያዩ ፀሃፊዎችና ክፍሎች የተለያየ ትርጉም እንደየሁኔታዉ ይሰጡታል ። ለአንዳንዶቹ፣ እድገት ሲባል ከኤኮኖሚ አንጻር ብቻ የሚታይ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ከየዝንባሌያቸዉና ከሙያ መስካቸዉ አኳያ መታየት ያለበት ይመስላቸዋል። ለዚህም ነዉ እንደ ጽንሰ ሃሳብ፣ እድገት በተለያዩ ክፍሎች የተለያየ ትርጉም የሚሰጠዉ (Goulet 1995:49)። እነዚህ ልዩነቶች እንዳሉ ሆነዉ ዕድገት (development) እንደ ጽንሰ ሃሳብም ሆነ እንደ ተግባር ከአንድ የሕይወትና የአኗኗር ገጽታ አንጻር ብቻ የሚታይ አለመሆኑ ከሞላ ጎደል በሙሉ ስምምነት ላይ እየተደረሰበት ይገኛል። እድገት ሁለንተናዊና ሁሉን-አቀፍ ጉዳዮችን ማለትም ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚዳስስና እነዚህን በማካተት ግንዛቤ የሚወሰድበት ጽንሰ ሃሳብ ነዉ።

በተግባር፣ በቀን ተቀንና በዘለቄታዊ አኗኗር አንፂርም እንደዚሁ ።

በአጭሩ፣ ጽንሰሃሳቡ በአጠቃላይ የሚያመለክተዉ ነገር ከላይ ከዘረዘርናቸዉ ነገሮች አንፂር በአሃዝና በአይነት ሊለኩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ መሻሻልን የሚያመለክትና፣ ይህም ከጥቂት ወደ ብዙ፣ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ፣ እንዲሁም ከተመሰቃቀለ ወደ ተረጋጋ ሁኔታ የመሸጋገር ሂደትን የሚያመለክት ነዉ። መገንዘብ ያለብን በአንድ ወይም ከዚያ በላይ መስኮች በአንድ ሀገር እድገት ተገኝቷል ሲባል እያንዳንዱ ግለሰብ ወይም የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሆነና በአኗኗሩም ሆነ በሰብአናዉ አወንታዊ ለዉጥ ያገኘ ተደርጎ መወሰድ የለበትም (Goldsworthy 1988 ፡508)። ዳሩ ግን አንድ የማይታለፍ ነገር ቢኖር እድገት ሲባል በአብዛኛዉ የህብረተሰብ ክፍል ሕይወትና የአኗኗር ዘይቤ ላይ አወንታዊ ተጽእኖ ሲያሳድርና ደረጃዉ ከፍ ያለ (qualitative) ለዉጥ ሲያስከትል ነዉ።

ይህንን ካልን ዘንድ፣ ሲቪል ማህበራት እድገትን ለማምጣት የሚኖራቸዉ አስተዋጽኦ ምን ይመስላል የሚለዉን በአጭሩ እንዳስሳለን። በአሁኑ ጊዜ፣ ባደጉትም ሆነ በማደግ ላይ በሚገኙ አህጉራትና ሀገሮች ሲቪል ማህበራትን እንደ ልማትና እድገት አጋሮችና ተዋናዮች የመመልከቱ አዝማሚያ እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ይገኛል። በተለይም በታዳጊ ሀገሮች ይህ ዝንባሌ በጉልህ የሚስተዋል ነዉ። ምክንያቱም መንግስታት የልማት አጀንዳዎችን ለመተግበርና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎት ለማሟላት፣ እንዲሁም ችግሮቻቸዉን ለመቅረፍ የሚያስችል ብቃትና አቅም አልፎ አልፎም በጎ ፈቃድ የሌላቸዉ በመሆኑ ነዉ (Munhande 2007 :23)። ስለዚህ ከመንግስት አቅም ዉሱንነት ወይም በጎ ፈቃድ ማጣት የሚመነጩ ክፍተቶችን በመሙላትና ለእድገትና ልማት ጋር የተያያዙ ጊዜያዊና መሰረታዊ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚደረግ ጥረት የሲቪል ማህበራት የጎላ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ምንም እንኳ ልማትን በመምራትና በማስተባበር የመንግስት ሚና አሁንም ወሣኝ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ማበብና ለልማት ሲቪል ማህበራት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ እያደገና የተጠናከረ መምጣቱ አያከራክርም (Sachikonye 2002 :18)። ለዚህም መንስኤ ከላይ ከተነገረዉ የመንግስት አቅም ዉሱንነትና በጎ ፈቃድ የማጣት ዝንባሌ በተጨማሪ በግልጽ የሚታወቁ በርካታ ምክንያቶችን መዘርዘር ይቻላል።[11] የሲቪል ማህበራት መፈጠርና የሚያደርጉት ተግባራዊ እንቅስቃሴ አባሎቻቸዉም ሆነ ሕብረተሰቡ ከመንግስትና ከሌሎች ኃይሎች ተፅእኖና ጥገኝነት ለመላቀቅ የተወሰነ አማራጭና አንጻራዊ ነጻነት እንዲኖራቸዉ ያስችላሉ። በዚህም ልማትና እድገትን የማምጣቱ እድል የሰፋ ይሆናል። ምክንያቱም፣ ይህ ሁኔታ ሰዎች ተነሳሽነት እንዲኖራቸዉና ለጋራ ጥቅም በቁርጠኝነትና በህብረት በርካታ ተግባሮችን እንዲያከናዉኑ አመቺ ሁኔታ ስለሚፈጥርላቸዉ ነዉ (Hyden 1996፡ 92)።

5. የሲቪል ማህበራት ለኢትዮጵያ እድገት ያላቸዉ አስተዋጽኦ

5.1 መግቢያ

በሲቪል ማህበራት ዝርዝር ዉስጥ እነማን መካተት አለባቸዉ በሚለዉ ጥያቄ ዙሪያ አንዳንድ መለስተኛእና ጥቃቅን ልዩነቶች መኖራቸዉ ቀደም ሲል ተጠቁሟል። በኢትዮጵያ ሁኔታ በዝርዝሩ ዉስጥ ይካተታሉ ተብለዉ የሚገመቱት

[11] የሲቪል ማህበራትን ማንነት የመለየት አስፈላጊነትን በተመለከተም ጎርደን ዋይት የሚሉት አላቸዉ።

" we would then need to distinguish between different types of sectors of civil society : for example, between interest groups such as trade unions or professional associations and ' traditional' ascriptive organizations based on kinship; between formal organizations and informal social networks based on patrimonial or clientelistic allegiances; between those institutions with specifically political roles as pressure or advocacy groups and those whose activities remain largely outside the political system; between legal or open associations and secret or illegal organizations…" (Gordon White Cited in Sisay Gebre-Egziabher, 2002:4).

እንደ ነጋዴዎች ምክር ቤት የመሳሰሉት የኤኮኖሚ ስብስቦች፣ ባህላዊ የህዝብ ማህበራት፣ የሞያና የባለሞያዎች ማህበራት (trade unions and professional associations)፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን (NGOs) ጨምሮ የእርዳታና የልማት ድርጅቶች፣ የሴቶችና የወጣቶች ማህበራት፣ የሰብአዊ መብት ድርጅቶችና የመሳሰሉት ናቸዉ[12]። በአጠቃላይ መናገር የሚቻለዉ በሲቪል ማህበራት ዝርዝር ዉስጥ መካተት ያለባቸዉ በራሳቸዉ ተነሳሽነትና ፈቃድ የተደራጁ፣ የአባሎቻቸዉንና የደጋፊዎቻቸዉን ተገቢ (legitimate) ፍላጎትና ጥቅም ለማስከበር የሚንቀሳቀሱና አንፂራዊ ነፂነታቸዉን የሚጠብቁ ናቸዉ። ስለዚህም አንዳንድ ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተቆራኙ የእርዳታና የአካባቢ የልማት ድርጅቶችና ሌሎች ስብስቦችን እንደ ሲቪል ማህበራት መቁጠሩ አጠያያቂ የሚሆንበት ምክንያት ቀደም ሲል ተገልፂDል።

አሁን በምንረዳዉ ትርጓሜዉና በባሕላዊ መልኩ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት መፈጠርና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ሂደት ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ነዉ።

ባህላዊ የወል ስብስቦችና ማህበራት ለተለያዩ የአባሎቻቸዉ አላማዎችና ፍላጎቶች ማስፈፀሚያ እንዲያገለግሉ ሆነዉ በመቋቋም በርካታ ተግባራትን አከናዉነዋል። ለምሳሌ ያህልም በእምነት ላይ የተመረኮዙ ስብስቦች (ማህበር፣ ሰንበቱ .. .. ..)፣ እቁብ፣ ደቦ/ጅጌ/ወንፈል፣ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ተቋማት ምንም እንኳ ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ቢሆንም በአደረጃጀታቸዉም ሆነ በአሰራራቸዉ በአብዛኛዉ መሰረታዊና አይነተኛ ለዉጥ ሳያካሂዱ እነሆ እስከዛሬ የተወሰነ አገልግሎት ለአባሎቻቸዉ እየሰጡ እንደሁኔታዉ በከተማም ሆነ በገጠር ይገኛሉ[13]። በቁጥር በጣም አነስተኛ ከሆኑት በስተቀርም ብዙዎቹ ይህ ነዉ በሚባልና ትርጉም ባለዉ የልማትና የእድገት እንቅስቃሴ በቀጥታና በራሳቸዉ አቅም ተሰማርተዋል ብሎ ለመናገር ያዳግታል። ሆኖም የአባሎቻቸዉን ችግር ከተቋቋሙባቸዉ ዓላማዎች አንፂር ለመቅረፍ ያበረከቷቸዉ አገልግሎቶች በርካታና ጠቃሚ መሆናቸዉን መገንዘብ ይገባል። ከላይ በአጭሩ ከተዘረዘሩት በተጨማሪም በኢትዮጵያ ዉስጥ እንደየአካባቢዉና እንደ ባህላዊ ሁኔታዉ በጣም ብዙ መሰል ስብስቦች መኖራቸዉን እንገነዘባለን። ሆኖም፣ ዝርዝራቸዉንና ቁጥራቸዉን በቀላሉ ማግኘት አስቸጋሪ የሚሆንበት ምክንያት እንደ ዘመናዊ ማህበራት በመንግስት መስሪያ ቤቶች ስለማይመዘገቡና ማንነታቸዉና ተግባራቸዉ በልምድ ብቻ ስለሚታወቅ ነዉ።

[12] ሲቪል ማህበራት አንድወጥ አለመሆናቸዉን ለመገንዘብ የሚከተለዉን መመልከት ይጠቅማል፤

"Civil society is not a uniform and homogenous group of institutions. On the contrary, the institutions of civil society are a myriad of particular interests, which have got an institutional form or an institutional expression. They express conflicts, rivalries, and struggles-or consented action. They may act as integrating or disintegrating elements" (Marcussen 1996:25) ::

[13] የመንግስትን ሁለንተናዊ ወሳኝነት አስመልክቶ የሚከተለዉ ተነግሯል፤

"The state barred other groups from using the political space of the political domain, exceeding the claims of the colonial state in this regard. At any rate, the post-colonial state has come to assume the political space of the public domain can be used at its pleasure and that permission to use it can be revoked on its own sole judgment" (Ekeh, 1994:7) ::

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ተብለዉ የሚጠሩ ማህበራት ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩት በአብዛኛዉ የኢጣሊያ ወረራ ከሀገሪቱ ከተወገደ በኋላ ነዉ። ምንም እንኳ የዘመናዊነት አኗኗር በኢትዮጵያ ብቅ ማለት የጀመረዉ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን መሆኑ ቢታወቅም ከባህላዊ ስብስቦች ለየት ያሉ ማኅበራት ተፈጥረው መንቀሳቀስና መስፋፋት የቻሉት ከ1950ዎቹ አሥርተ ዓመታት ጀምሮ ነው። በዚህ ወቅት በሀገሪቱ ውስጥ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት በሚሲዮናዊያን የሚደገፉ አንዳንድ ድርጅቶች በትምህርት፣ በጤናና በገጠር ልማት ዙርያ ተጠቃሚዎችን አሰባስቦ በማደራጀትና አልፎ አልፎም ቀደም ሲል ከነበሩ ባሕላዊ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ያደረጓቸው ሙከራዎች ነበሩ። በ1950ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት የሠራተኛ ማህበር (የምድር ባቡር ሠራተኞች ማህበር) የተቋቋመ ሲሆን በመቀጠልም የተለያዩ ተመሣሣይ የሠራተኛ ስብስቦች (trade unions) በተለያዩ ጊዜያት ተቋቁመዋል። ከሠራተኛ ማህበራት በተጨማሪም፣ በማህበራዊና በመረዳጃ ጉዳዩች ላይ ያተኮሩ የተወሰኑ ስብስቦች ብቅ ብቅ ያሉ በመሄድ ይህ አዝጋሚ ሂደት እስከ 1966ቱ አብዮት ድረስ ቀጥሎ ነበር። በኢትዮጵያ የዘመናዊ ማህበራትን መፈጠር ጅማሮ ከላይ እንደተጠቀሰው ስናወሣ መዘንጋት የሌለባቸው አንዳንድ ነገሮች መኖራቸውን መጠቆሙ ተገቢ ይሆናል። ይኸውም እነዚህ ማህበራት በቁጥራቸውና በእንቅስቃሴ አድማሶቻቸዉ አነስተኛና ዉሱን መሆናቸውን፣ በርካቶች በከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ የተከማቹ እንደነበሩ፣ የሲቪል ማህበርነት መለያ ማሣረፋቸው ግልጽ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩ ሲቪል ማህበራት በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ከልማትና ዕድገት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ሲያከናውኑ ይታያሉ። ምንም እንኳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማህበራት በተለይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ከእርዳታና ልማት ባሻገር ፖሊሲንና የዜጎች መብትን በተመለከተ አንዳንድ አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ቢገነዘቡም፣ በራሳቸው አቅም ውሱንነትና የመንግሥትን ጥርጣሬና ቁጣ ላለመጫር ከሚያደርጉት ጥንቃቄ የተነሣ እስካሁን በዚህ ረገድ ይህ ነው ተብሎ ሊነገር የሚችል ሥራ አላከናወኑም።

5.3 በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ችግሮች

ሲቪል ማህበራት መርሐግብሮቻቸዉን በተግባር ለመተርጎምና ቀጣይ ህልዉናቸዉን ለማስከበር በሚያደርጉት ጥረት በርካታ ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸዉ ጥናቶች ያመለክታሉ (Dessalegn 2002 :116-117, Kassahun 2002 :127-129)። የእነዚህንም መሰናክሎች መንስኤ በጥቅሉ ዉሥጣዊና ዉጭያዊ(internal and external) ብሎ መፈረጅ ይቻላል። ዉስጣዊ ችግሮች በአብዛኛዉ ከማህበራቱ ከራሳቸዉ ድክመትና የአቅም ዉሱንነት ጋር ተያይዘዉ የሚወሱ ሲሆን፣ ከዚህ ዉጭ ያሉት ደግሞ የሚመነጩት ከአመቺ የመንግስት ፖሊሲና አመለካከት እጦት፣ በህብረተሰቡ ዉስጥ ሰፍነዉ ከቆዩ የአሰራርና የአመለካከት ግድፈቶች እንዲሁም በሐገሪቱ ተንሰራፍቶ ከሚገኘዉ የድህነት ችግርና ደካማ የሶሲዮ-ኤኮኖሚ ሁኔታዎች አንጻር ነዉ።

የማህበራቱ ዋና ዋና ዉስጣዊ ችግሮችን በተመለከተ የሰዉ ኃይል፣ የገንዘብ፣ ለስራዎቻቸዉ ማካሄጃና አስፈላጊ ለሆኑ ሌሎች ጉዳዮች የሚዉሉ ግብአቶች ተሟልተዉ አለመገኘትና በዚህም ሳቢያ የሚከተለዉ የአቅድ መስተጓጎልና በጥገኝነት የመዘፈቅ አደጋ ነዉ ብሎ በአጭሩ ማጠቃለል ይቻላል። ይህ ሁኔታም የአባላትና ደጋፊዎችን አመኔታና

ድጋፍ እንደሚሸረሸርና የማህበራትን አንጻራዊ ነጻነትም እንደሚያላጣ ግልጽ ነዉ። ምክንያቱም፣ ጥገኝነት ለጋሾች የራሳቸዉ አጀንዳና ፍላጎቶች ቀደምት ትኩረት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችሏቸዉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በማህበራት ዉስጥ ጎልቶ የሚታየዉ የማስተባበር፣ የስራ አመራርና የቴክኒክ ክህሎት እጥረት በተመሳሳይ መንገድ መርሃግብሮችን በመንደፍና እቅድ በማዉጣት እንዲሁም በማስፈጸም ረገድ በራስ ያለመተማመንና በሌሎች የመታገዝን አዝማሚያ በማጎልበት በርካታ አሉታዊ ችግሮችን ማስከተሉ አይቀሬ ነዉ።

በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ ሲቪል ማህበራት ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ችግሮች አሏቸዉ። ለምሳሌም፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከሕብረት ስራ ማህበራት በስተቀር አብዛኞቹ የሲቪል ማሕበራት የተከማቹት በአዲስ አበባና በተወሰኑ አንዳንድ ከተሞች መሆኑን፣ የሕልዉናቸዉ ቀጣይነት አስተማማኝ ለመሆኑ የተጨበጠ ዋስትና አለመኖሩን፣ ማህበራቱ ራሳቸዉ በአመራርም ሆነ በሌሎች ደረጃዎች ዴሞክራሲያዊ ባህልንና የአሰራር ዘይቤዎችን በሚገባ በዉስጣቸዉ ያላዋሃዱ መሆናቸዉን፣ በማህበራትና በመንግስት መካከል በጋራ ጉዳዮች ላይ ለመምከርና ሃሰብ ለመለዋወጥ በቂ እድልና መድረክ አለመፈጠሩን፣ እንዲሁም ዓላማቸዉንና ስራቸዉን ለህዝቡ የሚያስተዋዉቁበት በቂ የግንኙነት መስመር ማጣታቸዉን መጥቀስ ይቻላል (Dessalegn 2002 : 118) ::

5. የ2020 ርዕያችን

በኢትዮጵያ ታሪክ የሲቪል ማህበራት እርሾ በባህላዊ እሴትነት መታወቅ ከጀመረ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ቢሆንም የዘመናዊ ማህበራት ብቅ ብቅ ማለት የተጀመረዉ ከጥቂት አስርተ ዓመታት ወዲህ ነዉ። በተደጋጋሚ እንደተገለፀዉ ባህላዊና ዘመናዊ ብለን የፈረጅናቸዉ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሲቪል ማህበራት፣ ጽንሰ ሓሳቡ በትርጓሜም ሆነ በመስፈርትነት ያስቀመጣቸዉን ሁኔታዎች አሟልተዉ የማይገኙና በእድገታቸዉም ሆነ በጥንካሬያቸዉ ብዙ ያልገፉ ናቸዉ። በዚህ የተነሳም ለልማትና እድገት እስካሁን ያደረጉት አስተዋፅኦ፣ እነርሱም ሆኑ አገልግሎት ተቀባይ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንደሚመኙትና እንደሚፈልጉት ሊሆን አልቻለም። ይህ ሲባል ግን ማህበራት በርካታና የተለያዩ ጠቀሜታ ያላቸዉን ተግባሮችን ማከናወናቸዉ ሳይዘነጋ ነዉ።

ባህላዊ ማህበራት ከብዙ ዘመናት በፊት በተለያዩ የሃገሪቱ ማህበረሰቦች ፍላጎትና የጋራ ጥቅም አንጻር የተቋቋሙባቸዉን አላማዎች ይህ ነዉ ሊባል የሚችል ለዉጥ ሳያደርጉባቸዉ አሁንም ድረስ በነባር ተግባሮቻቸዉ ተወስነዉ ይገኛሉ። በመሆኑም ለመሰረታዊና ለዘለቄታዊ የአሰራርም ሆነ የአኗኗር ለዉጥና ለእድገት ያደረጉት አስተዋጽኦ ጥቂት ነዉ። ለዚህ መንስኤ ከሆኑ በርካታ ምክንያቶች መካከል፣ የአብዛኞቹ የሀገራችን የህብረተሰብ ክፍሎች አስተሳሰብ፣ አኗኗርና አሠራር ከቀደምቶቹ አያት ቅድመአያቶቻችን እምብዛም ያልተለየ መሆኑን፣ በተለያዩ የልማትና የእድገት መስኮች ወደፊት ተራምደን አለመገኘታችንን፣ በአስተሳሰብ፣ በአሰራርና በአኗኗር ላይ ዐይነተኛና መሰረታዊ ለዉጦች ባደጉት ሃገሮች ያስከተሉት ነባራዊ ሁኔታዎች (የማህበራዊ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሽግግሮች) በኢትዮጵያ እዉን ያለመሆናቸዉን፣ እንዲሁም በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ ሰዉ ሰራሽ (ግጭቶች፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣

ማህበራዊ ቀዉሶች) እና የተፈጥሮ ችግሮችን መጥቀስ ይቻላል። በዕለት ተዕለት ደራሽና አጣዳፊ ጉዳዮች ላይ መረባረቡ የጊዜዉ የባህላዊ ማህበራትን ጊዜ፣ ጉልበትና እሴት እያሟጠጠ መገኘቱም ሌላዉ ምክንያት ነዉ። በነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች የተነሳም ባህላዊ ማህበራት በአደረጃጀትና በአሰራር አንጻር እንዲሁም ከመጀመሪያዉ ተግባራዊ ሊያደርጓቸዉ የተነሱባቸዉን ዓላማዎች እንዳሉ ይዘዉ ቀጥለዋል። ይህ ሁኔታ እንዲህ እስከቀጠለ ድረስ ባህላዊ ማህበራት ለኢትዮጵያ እድገት ትርጉም ያለዉ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብሎ መጠበቅ አይቻልም።

አሁን ካለንበት በመነሳት በ2020 የኢትዮጵያ ባህላዊ ማህበራት አሰራርና አደረጃጀታቸዉን በመለወጥ የመሰረታዊ ባህርይዎቻቸዉን ገጽታ እንዲሁም ግብና ዓላማዎቻቸዉን ለእድገትና ልማት አመቺ በሆነ መንገድ በማስተካከል ብዙ ሚና ለመጫወት የሚችሉባቸዉ እድሎች አሉ። ምንም እንኳን ፈታኝ ችግሮችና መሰናክሎች በአጭር ጊዜና ሙሉ በሙሉ ይወገዳሉ ማለት ቢያዳግትም፣ የትምህርት በየደረጃዉ መስፋፋት፣ የጤና አጠባበቅ ሁኔታና አደረጃጀት በብዙ መንገድ አንጻራዊ መሻሻል እያሳየ መምጣቱ፣ የህብረተሰብ አባላት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መረጃና ዕዉቀት እያገኙ ግንዛቤያቸዉ በየጊዜዉ እየዳበረ መሄዱ፣ የከተሞች እድገትና ከከተሞች ጋር ያለዉ የገጠሩ ህብረተሰብ ትሥሥርና የጥቅም ግንኙነት በተለያዩ የመገናኛና የመሰረተልማት አዉታሮች እድገት የተነሳ እየጎለበተ በመሄድ ላይ መሆኑ፣ ዘመናዊ የአኗኗርና የተሻሻሉ የአመራረት ዘዴዎች እየተለመዱ መሄዳቸዉ፣ ወዘተ... የባህላዊ ማህበራትን አደረጃጀትና አሰራር በየጊዜዉ እየለወጠ መሄዱ አይቀሬ ነዉ። ምንም እንኳን በርካታ ችግሮች የሚታዩባቸዉ ቢሆንም፣ እየታዩ ያሉት መልካም ጅማሮዎች በኢትዮጵያ እዉን እየሆኑና መሰረት እየጣሉ መሄዳቸዉ የግድ ነዉ። አሁን ያሉ ችግሮች እየተቀረፉና እነዚህ በጎ ጅማሮዎች እስከ 2020 ሥር እየሰደዱና መሰረት እየያዙ ሲሄዱ ባህላዊ ማህበራት ከዉሱን ዓላማዎችና አሁን ከሚታየዉ «ኋላቀር» አደረጃጀታቸዉና የአሰራር ዘይቤያቸዉ በከፊልም ቢሆን ተላቀዉ በመቀናጀትና ጉልበትና እሴቶቻቸዉን በማስተባበር እድገትን ለማምጣት በሚደረገዉ ጥረት የጎላ ደርሻ ይኖራቸዋል ብሎ ተስፋ ማድረግ ይቻላል። በዚህም ረገድ ህብረተሰቡ፣ በተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሌሎች የሲቪል ማህበራት፣ መንግስትና ሌሎች ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያሳስባቸዉ ሁሉ ከወዲሁ ተገቢዉን እገዛ እንዲያደርጉ ማነቃቃት ያስፈልጋል።

ዘመናዊ የሲቪል ማህበራት ብለን የዘረዘርናቸዉና በተለያዩ የስራ መስኮች የተሰማሩ በርካታ ስብስቦችም በየፊናቸዉ በርካታ ጠቃሚ ተግባራትን ያከናወኑና እያከናወኑ የሚገኙ ቢሆኑም ከዉስጣቸዉም ሆነ ከቁጥጥራቸዉ ዉጭ የሚመነጩ ችግሮች እንደሚፈታተኗቸዉ ተገልፂDል። እንደገና በአጭሩ ለማስታወስ አንፃራዊ ነፃነታቸዉን የሚፈታተኑ የገንዘብም ሆነ የተለያዩ የአሰራር ክህሎቶች እጥረትና የአቅም ዉሱንነት፣ ማህበራት የለጋሾችና የሌሎች ጥገኛ እንዲሆኑ በማድረጋቸዉ፣ በመንግስት በኩል በጥርጣሬ መታየታቸዉና በቢሮክራሲያዊ ዉጣ ዉረዶች እንዲንገላቱ መሆኑ፣ የመንግስትን ቁጣና አስተዳደራዊ እርምጃ በመፍራትና የድርጅቶቻቸዉንም ሆነ የሰራተኞቻቸዉ ፍላጎትና ህልዉና ለመጠበቅ በፖሊሲ-ነክ ጉዳዮች ላይ ለመሳተፍ ፈራ ተባ ማለታቸዉ ዋና ዋና የችግሮቻቸዉ መገለጫዎች ናቸዉ።

አሁን ከሚታዩት አንዳንድ አዝማሚያዎችና ጅምሮች በመነሳት በኢትዮጵያ የሚገኙ ዘመናዊ የሲቪል ማህበራት የጋጠሟቸውን ችግሮች ተቋቁመዉና የራሳቸዉን ድክመቶች ፈትሸዉ አሰራራቸዉን በማሻሻል በ2020 ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የማበርከት ሰፊ እድል ይኖራቸዋል። ለዚህም እንደመነሻ፣ ሲቪል ማህበራት በተለይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ፈራ ተባ እያሉም ቢሆን በፖሊሲ-ነክ ጉዳዮች ዙርያ መስራትና መሳተፍ እንደሚገባቸዉ መገንዘባቸዉ፣ የድርጅቶች የስነምግባር መመሪያ መዉጣቱና በመንግስትም ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱ፣ በተወሰነ ደረጃ ቢሆንም መንግስትና ማህበራት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ (ድህነት-ቅነሳ፣ ምግብ ዋስትና፣ ፕሮግራም ግምገማ፣ ጤና፣ የመጠጥ ዉሃ) የጋራ ኮሚቴዎችን በማቋቋምና የምክክር መድረኮችን በመፍጠር እየተገናኙ መሆኑን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ጅምሮች እየተሻሻሉ፣ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ በመሄድ በ2020 ማህበራት ለኢትዮጵያ መሰረታዊና ዘላቂ ዕድገት የበለጠ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉበት የተመቻቸ የፖሊሲና የተግባራዊ እንቅስቃሴ አየር ይሰፍናል ብሎ ተስፋ ማድረግ ይቻላል። ይህ ሁኔታ ግን በራሱ የሚመጣ ሳይሆን በቅድሚያ ማህበራት ራሳቸዉ፣ በመቀጠልም መንግስትና ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዋዋሪ የሚመለከታቸዉና የሚያሳስባቸዉ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ማህበራት የአሰራርና የአደረጃጀት ቅንጅት በመፍጠርና አስተማማኝ የግንኙነት መስመር በመዘርጋት እንዲሁም ከአሁኑ የተሻለ የጋራ መድረክ በማቋቋም ህልዉናቸዉን የሚያስጠብቅ፣ አንጻራዊ ነፃነታቸዉን የሚያከብርና የሚያስከብር፣ ተገቢ እንቅስቃሴያቸዉን የሚያግዝና የሚያበረታታ ፖሊሲ/ሕግ ወጥቶ በስራ ላይ እንዲዉል በመንግስት ላይ አዎንታዊ ጫናና ገንቢ ተጽእኖ በማድረግ በስፋት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል። ይህ፣ እግረመንገዱን ለዲሞክራሲ፣ ለመልካም አስተዳደርና ለህግ የበላይነት የሚደረግ ትግል አካል ሆኖ መታየት ይገባዋል። በስፋት እንደሚታመነዉ፣ ዘርፈ-ብዙ ልማትና እድገትን እዉን ለማድረግ ዴሞክራሲና የህግ የበላይነት ወሳኝ ሚና ስለሚኖራቸዉና ከዚህ ተጠቃሚዎቹም መላዉ ህብረተሰቡና መንግስትም ጭምር በመሆናቸዉ ማህበራት በዚህ ረገድ ለሚያደርጉት ጥረት ተገቢ ትብብርና እገዛ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በዚህ ረገድ የአመለካከትና የዝንባሌ ለዉጥ እንዲታይ ሰፊ የቅስቀሳ (sensitization) ሥራ ከወዲሁ መጀመር አለበት።

የፖለቲካ ስልጣንን የተቆጣጠሩና ወደፊት የሚቆጣጠሩ ኃይሎችም፣ አላስፈላጊ ጥርጣሬዎችን በማስወገድና ከመሰናክልነት ቀለበት በመዉጣት የማህበራት መጠናከር በመንግስትና በግሉ ሴክተር ጥረት ብቻ ሊወገዱ የማይችሉትን ክፍተቶች በመሙላት ሠፊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ እንዲገነዘቡና እንዲተባበሩ ማድረጉ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባ ተግባር ነዉ። ማህበራት፣ በገንዘብ፣ በማቴሪያልና በሰዉ ኃይል ያለባቸዉ ችግርም ለጥገኝነታቸዉና በዚህም ሳቢያ አንፃራዊ ነፃነታቸዉን ለማጣታቸዉ አንዱ ምክንያት በመሆኑ፣ በ2020 የራሳቸዉን አቅም ገንብተዉና በቅድሚያ በራስ የመተማመን ሁኔታቸዉን አጎልብተዉ የሚገኙበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ለዚህ ዓላማ መሳካት እንቅፋት የሆኑ ሕጋዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅፋቶች እንዲወገዱ፣

ማህበራት ጥረታቸዉንና ሰላማዊና ህጋዊ ትግላቸዉን በሕብረተሰቡ እየታገዙ ከወዲሁ ከጀመሩ በ2020 በአብዛኛዉ ራሳቸዉን ችለዉ የሚሰሩበት፣ የሚያድጉበትና የሚጠናከሩበት ሁኔታ ይፈጠራል።

በዶ/ር ካሳሁን ብርሃኑ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ያቦወርቅ ኃይሌ[1]

ይህ ጹሁፍ በርካታ ጠቃሚና አስተማሪ የሆኑ ሀሳቦችን ያቀፈ ነው። ለዚህም አቅራቢው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። ከዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፣

1. **የሲቪል ማህበራት ጽንስ ሀሳብና እድገት ወደ ሥረ መሰረቱ በመዝለቅ የተለያዩ አመለካከቶችን ይዳስሳል።**
2. **የሲቪል ማህበራት አመጣጥ፣ ከመንግሥት (State) ጋር ያላቸውን ግንኙነት በግልጽ ያስቀምጣል።**
3. **በሲቪል ማህበራት ምንነትና ማንነት እንዲሁም ሚናቸው ላይ አወዛጋቢ ሀሳቦች ወይም ሙሉ በሙሉ ስምምነት ላይ አለመድረሱን ያመለክታል።**
4. **በሲቪል ማህበራት ስም የሚንቀሳቀሱ ግን ማህበራቱን የማይወክሉ አካላት እንዳሉ በግልጽ ያሳያል። ይህ የጹሁፉ አንደኛው በጣም ጠንካራ ጐኑ ነው ማለት ይቻላል።**
5. **የሲቪል ማህበራት እንደ ልማትና እድገት አጋሮችና ተዋናዮች የመመልከት አዝማሚያ እየተጠናከረ መምጣቱን ይገልፃል። ትክክል ነው።**
6. **አንፃራዊ ነፃነታቸው ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል ይደግፋልም። ይህም ትክክል ነው በጣም አስፈላጊ ሀሳብና እምነት ነው።**
7. **የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት አመጣጥና ችግሮች ላይ የቀረበው ሀሳብ መልካም ነው ውይይት ቢደረግበት ጥሩ ነው።**
8. **ለ2020 ትልማችን /የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ዕድገት/ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይቀበላል። ጠንካራና ግልጽ የሆነ እንዲሁም ትልቅ ተስፋ እንዳለው ይገለፃል በዚህም አቅራቢው ሊመሰገኑ የገባቸዋል።**
9. **ሚናቸውን በትክክል ለመወጣት ብዙ ጥረቶች መደረግ እንዳለበት ያምናል። እውነት ነው።**
10. **የቋንቋ ጥራቱም የሚደነቅ ነው።**

በጹሁፉ ላይ በርካታ ጠቃሚና አንባበያንን ሊያሰተምሩ የሚችሉ ሀሳቦች እንዳሉ ሁሉ አንዳንድ ክፍተቶችም ይታያሉ። እነዚህ ክፍተቶች ቢሸፈኑ ጹሁፉን የበለጠ ጠንካራ ከማድረጋቸውም በላይ

[1] አቶ ያቦወርቅ ኃይሌ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በአለም አቀፍ ቢዝነስ ማኔጅመንት አግኝተዋል። አቶ ያቦወርቅ ኃይሌ በበርካታ ቦታዎች በኃላፊነት ደረጃ ያገለገሉ ሲሆን ለመጥቀስ ያህል፦ በAction-Aid Ethiopia እና ዩጋንዳ ውስጥ በኘሮግራም ዳይሬክተርነት እንደዚሁም ኘሮኘራይድ የሚባለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት መስራችና ሥራ አስኪያጅነት አገልግለዋል። በአሁኑ ሰዓት በACORD ውስጥ በኘሮግራም ዳይሬክተርነት እየሠሩ ይገኛሉ።

የአስተሳሰብ ጥራትን (Conceptual clarity) ያመጣሉ የሚል ሀሳብ አለኝ። ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፣

1. ጹሁፉ የሲቪል ማህበረሰብ መፈጠር የጀመረው በ17ኛው ክፍለ ዘመን መሆኑን ያመለክታል። ይህ ሀሳብ የዘመናዊ ወይም የዚህ ዓይነት የአደረጃጀት መልክ እየያዘ መምጣት የጀመረው በሚል ሀሳብ ቢተካ የሚሻል ይመስለኛል። ምክንያቱም የሲቪል ማህበረሰብ አመጣጥ ከState ጋር የተያየዘ መሆኑን ከተቀበልን State ባለበት ሁሉ የሲቪል ማህበረሰብ አለ ማለት ይቻላልና። ለምሳሌ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ *እረኛ ምን አለ" የሚለውን ሀሳብ በዘመኑ የነበረውን የሲቪል ማህበረሰብ ምንነት ያሳያል።
2. የሲቪል ማህበረሰብ ምሁራን ሲጠቀሱ የነ ሄግልና በዛሬ ዘመን ያሉ አስተሳሰቦች ቢታከልበት ጥሩ ነው። በተለይ ሲቪል ማህበረሰብ እንደ Third Sector የሚቀርበው አስተሳሰብ መታከል አለበት ይህ (Conceptual clarity) ለማምጣት ያግዛል።
3. የሲቪል ማህበረሰብ ሚናና ከመንግሥት ጋር ያለው ግንኙነት ላይ የቀረበው ሀሳብ መስተካከል አለበት ይመስለኛል። ሲቪል ማህበረሰብ እንደ አገናኝ ድልድይ ሳይሆኑ ራሱ የቻለ በህብረተሰብ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚጥር አካል መሆኑን በግልጽ ማሳየት ያስፈልጋል። እንዲያውም የሲቪል ማህበረሰብ እየተጠናከረ የመጣው State fail በማድረጉ መሆኑን መግለጽ ተገቢ ነው። Division of power Check and balance መጥፋቱ ሲቪል ማህበረሰብ እያጠናከረው እንደመጣና መጠናከርም እንዳለበት መታየት አለበት። ድንበር ዘለል የኢኮኖሚ ተቋማት Transnational Conglomerates መፍጠር የህብረሰብን ችግር እያበዛ መምጣት ይህም የሲቪል ማህበረሰብን ያጠናከረ ጉዳይ መሆኑን በጹሁፍ መካተት አለበት። በዚህም ተግባራቸው ከመንግሥትና ከደንበር ዘለል የኢኮኖሚ ተቋማት ጋር የትብብርና የተቃርኖም ግንኙነቶች ሊኖረው እንደሚችል አጉልቶ ማሳየት ይገባል። በተጨማሪም በመንግስት በጐ ፈቃድ የሚፈጠሩና የሚጠፉ ሳይሆን ከማህበረሰብ የሚመነጩ የማህበረሰብ ችግር ውጤቶች መሆናቸው መሰመር አለበት።
4. በጽንስ ሀሳብ ደረጃ መቅረብ ያለበት የሲቪል ማህበረሰብ አጠቃላይ ገጽታ እንጅ በእያንዳንዱ ሲቪል ማህበረሰብ ባህርያት ላይ የተመረኮዘ ሀሳብ ማቅረብ ደንን በዛፍ መግለጽ ያህል ነው። ዝግባ እንደዝግባነቱ ያለው ባህርይ እንደደን አባልነቱ ያለው ሚና የተለያየ ስለሆነ ጹሁፍ እንደሲቪል ማህበረሰብ አባልነቱ ባለው ሚና ላይ ትኩረት ቢሰጥ ይመረጣል። አንድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት

ያባላቱን ጥቅም ማስጠበቅ ዓላማው ቢሆንም እንደሲቪል ማህበረሰብ ግን በአጠቃላይ የህብረተሰብ ጥቅም እንደሚያስጠብቅ ጐልቶ ቢታይ ይመረጣል።

5. ስለ 2020 ራዕይ፣ ስለ አጠቃላይ ዕድገት ያቀረበው ሀሳብ የበለጠ ቢዳብር፣ ለኢትዮጵያ አሁን ካለችበት ሁኔታ ዕድገት ማለት ምን እንደሆነ የበለጠ ቢብራራ ይመረጣል። የአመለካከት አንድነት ያዳብራል። ዛሬ እኮ እድገት በሚለው ቃል አንድነት አለ እንጅ በእድገት ምንነት ላይ አንድ ወጥ አመለካከት ገና አልዳበረም። የፖለቲካ ዕድገት ስንል የፖሊሲ Consensus የተደረሰበት፣ የፖለቲካ ሀሳቦች መቻቻል የሰፈነበት፣ ስልጣን በምርጫ የሚሸጋገርበት፣ ስልጣን የለቀቀው ቡድን ካገር የማይሰደድበት፣ በአገሩ በሰላም የሚኖርበት፣ የፖለቲካ ልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱባት፣ በሀገሪቱ በሚገኙ የዲሞክራሲ ባህሎች የጐለበቱበት አገር መሆኑን መግለጽ ያስፈልጋል።

   እንዲሁም የኢኮኖሚ ዕድገት ሲባል ምን እንደሆነ መግለጽ አለበት። የኢኮኖሚ ዕድገት ብልጽግና የሰፈነበት ድህነት የሌለበት የህብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ በዘላቂነት የተሻሻለበት የእርሻው ዘርፍ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚ ያለው አስተዋጽኦ የቀነሰበት ከእጅ ወደ አፍ የአኮኖሚ (Subsistence economy) የተላቀቀበት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ግንባር ዋነኛ የኢኮኖሚ አሰተዋጽኦ የሚያደርግበት መሆኑን ቢዘረዘር ጥሩ ነው። የቴክኖሎጂ ዕድገትም ቢታከልበት፣ የባህላዊ (Traditional) የአመራረት ዘይቤ በዘመናዊ የአመራረት ዘይቤ ሲተካ መሆኑን ቢገለጽ፤ የባህል ለውጥ ሲባል የአሰተሳሰብና የአመለካከት ዕድገት ሲባልም ምን እንደሆነ ቢገለጽ ይበጃል እላለሁ።

6. የሲቪል ማህበረሰብ ያለው ሚናና በተጨባጭ እያደረገ ያለውም አስተዋፅኦ በዚህ አንፃር መቃኘት አለበት።

7. ዛሬ የሲቪል ማህበረሰብ የፖለቲካ ዕድገት ለማምጣት ብዙ ጥረት እያደረገ ነው። የፖለቲካ መሪዎችን ሳይቀር የሲቪክስ ትምህርት ይሰጣል። በየጣቢያው የሰብአዊ መብት ምንነትን እያሰተማረ ነው። በየእርከኑ ለሚገኙት የመንግስት ሹማምንት፣ ለሕዝብ ተመራጮች ትምህርት ይሰጣሉ። በሬድዮ ሳይቀር መልካም አስተዳደር ምን እንደሆነ ድህነትን ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት ያለው አስተዋፅኦ ምን እንደሆነ እያሰራጨ፤ ምሁራንና የመንግስት ባለስልጣኖችም እያወያዩ ነው። የሚያሳዝነው ግን ይህንን ሰራችሁ ተብሎ የሚንገላቱ ብዙ መሆናቸው ነው።

8. የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ቀንና ሌሊት ደፋ ቀና እያለ ነው። የብድርና ቁጠባ ፕሮግራሞቻቸው፣ የአነስተኛ ንግድ ክህሎት ማዳበራቸው፣ የአነስተኛ ሥራ ፈጠራቸው፣ ገንቢ የሆነ የፖሊሲ አስተያየት መስጠታቸው እንደ ምሳሌ ይጠቀሱ። የአርሶ አደሩና የአርብቶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻል የሚያደርጉትም አስተዋጽኦ ይገለጽ።

9. ቴክኖሎጅም ለማሳደግ በአነስተኛ የመስኖ ልማት ግንባታ፣ የባህላዊ የአመራረት ዘይቤ በማሳደግ ላይ መሆናቸውም ይታከል።

10. በሀገሪቱ ውስጥ የዖታ እኩልነት ለማስፈን የስነ ጾታ ትምህርት በመስጠት ሴቶችና ልጃገረዶች በማንኛውም የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ላይ በእኩልነትና በንቃት እንዲሳተፉ እያደረጉ መሆናቸው ይገለፅ። የባህላዊ ለውጥ ለማምጣት ግርዛትን ያለ እድሜ ጋብቻን ጠለፋን ሴት ልጅን በማስተማር ተግባር እየተንቀሳቀሱ ነው።

11. በጤና፣ በትምህርት፣ በንጹህ ውሃ አቅርቦት ላይ ያልተሳተፈ የሲቪል ማህበረሰብ የለም ማለት ይቻላል። በተለይም የእምነት ተቋማት እንደካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በትምህርት ላይ ያበረከቱትና በማበርከት ላይ ያሉ አስተዋፅኦ ትውልድ የማይረሳው ነው።
12. HIV/AIDSን በመከላከልና በማስቆም ፈር ቀዳጅ ሚና የተጫወተው የሲቪል ማህበረሰብ ነው እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉትን በጹሁፍ ላይ ቢካተቱ ጥሩ ነው እላለሁ።

በዶ/ር ካሳሁን ብርሃኑ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ፈለቀ ታደለ[1]

የተከበራችሁ እንግዶች፣ የመድረኩ ታዳሚዎች፣ ክቡራትና ክቡራን፤

በቅድሚያ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ከላይ በተጠቀሰው ርዕስ ዙሪያ ይህንን የዛሬውን መድረክ በማዘጋጀቱ ያለኝን አድናቆት እየገለጽኩ፣ እኔም አስተያየት እንድሰጥ በመጋበዜ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ።

ዶ/ር ካሳሁን በሰከነ አንደበታቸውና በሰላ ቋንቋቸው የሲቪል ማህበራት ፅንሰ ሀሳብና ታሪካዊ አመጣጥ፣ የሲቪል ማህበራት መለያና መገለጫ ባህሪዎች፣ በልማት ሥራ ውስጥ የሲቪል ማህበራት ያላቸው ሚና እና የሲቪል ማህበራትን በተመለከተ ያላቸውን ራዕይ አስመልክተው የሰጡትን ትንተና በመስኩ ላይ ድባብ እንድንጥል የሚያደርግ ነው።

ለጥናታቸው ያለኝን አድናቆት በድጋሚ እየገለፅኩ፣ አስተያየቴን አንኳር በሆኑ ጭብጦች ላይ በማተኮር የበለጠ ትኩረት ይሻሉ ባልኳቸው ጉዳዮች ዙሪያ እሰጣለሁ። እነሱም ሀ/ የፅንሰ ሀሳብ ትንታኔና ዘይቤአቸው ለ/ የሲቪል ማህበራት ሚና ሐ/ የሲቪል ማህበራት ችግሮችና መ/ የወደፊት ራዕይ ማጠናከሪያዎች በሚል በአራት ንዑስ ክፍሎች በመዘርዘር አቀርባለሁ።

(ሀ) የፅንሰ ሀሳብ ትንታኔና ዘይቤአቸው

ዶ/ር ካሳሁን በጥናታቸው ከዛሬ 3 እና 4 ክፍለ ዘመናት በፊት የነበሩትን የፖለቲካ ፍልስፍናዎችንና የዘመናዊ የአስተሳሰብ ዘይቤዎችን በመቃኘት ሲቪል ማህበራት ዜጎች በፈቃደኝነት የሚፈጥሩትና አንፂራዊ ተቋማዊ ነፂነታቸውን ጠብቀው በመንግስትና በህብረተሰብ መካከል እንደአገናኝ ድልድይ የሚያገለግሉ ስብስቦች እንደሆኑና አሁንም ይህንኑ ተግባር የሚያከናውኑ መሆናቸውን ገልፀዋል። አያይዘውም ሲቪል ማህበራትና ህብረተሰብ አንድና ተመሳሳይ አለመሆናቸውን፣ ስብስቡም እስከአሁን ስምምነት ላይ ያልተደረሰባቸው ነገር ግን በርካታ ተቋማትን ጨምሮ እንደሚያቅፍ አስገንዝበዋል።

እነዚህ ከላይ የተገለፁት ትርጓሜዎችና ፅንሰ ሀሳቦች መኖራቸውን የተረጋገጠና የሀሳብ ልዩነታችን የጎላ ባይሆንም ትንታኔአቸው በፖለቲካው ፍልስፍና ዙሪያ ላይ ያጠነጠነ በመሆኑ የገበያውን /የግሉ ኢኮኖሚ/

[1] አቶ ፈለቀ ታደለ የካናዳ ሕፃናት አድን ድርጅት የኢትዮጵያ ፕሮግራም ተጠሪና የምስራቅ አፍሪካ ፕሮግራም አስተባባሪ በመሆን እያገለገሉ ነው፡፤ በዓለም አቀፍ የልማት አስተዳደር ዘርፍ በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጪ ላለፉት 19 ዓመታት በከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት ላይ ተሰማርተው አስተዋፅኦ ያደረጉና በመስኩ በርካታ ልምድ ያካበቱ ናቸው።

ገፅታ አደብዝዞት አልፏል። በበርካታ ባለሙያዎች ዘንድ እንደሚገለፀው አንድ ህብረተሰብ የሶስት አካላት - ማለትም መንግስት /ፖለቲካ/፣ ሲቪል ማህበራት (ትርፍ አምራች ያልሆነ) እና ገበያ (የግሉ ኢኮኖሚ) ክፋይ ሲሆን፤ ሲቪል ማህበራትም በዜጎች (ግለሰቦች) እና በሁለቱ አካላት ማለትም በመንግስትና በገበያ መካከል እንደ ድልድይ ሆነው የሚያገለግሉ ስብስቦች ናቸው።

እንደሚታወቀው በምዕራቡ ወይም የ«ነፂ» ኢኮኖሚ ስርዓት በሚያራምዱ አገሮች ውስጥ የገበያው (የግሉ ክፍል) ሴክተር ለሲቪል ማህበራት ማደግ ከፍተኛ የገንዘብ ምንጭ ሲሆን፣ የመንግስት/የፖለቲካ ክፍሉም (ሴክተሩም) ይህ አስተዋፅኦ የተመቻቸ እንዲሆን የህግና የገቢ ግብር ስርዓት ማሻሻያ ሥርዓት በማዘጋጀት እገዛ ያደርግለታል። ይህም በሶስቱ የህብረተሰብ አካላት መካከል ያለውን ተደጋጋፊነትና የዜጎችን መብት መከበርን ያጠናክራል። ስለሆነም በመልማት ላይ ለሚገኙ እንደ ኢትዮጵያ አይነት አገሮችም ትልቅ ሚና የሚኖረው ነውና የሲቪል ማህበራት እድገትና የሚኖራቸው ሚና መገለጫ የተቀሩት ሁለቱ የህብረተሰብ አካላት እድገትና ግንኙነት መሆኑን መገነዘብ ያስፈልጋል።

ሌላው ስለ ሲቪል ማህበራት ታሪካዊ አመጣጥና እድገት ሲጠቅሱ ዶ/ር ካሳሁን በምዕራቡና በተቀረው በተለይም በታዳጊ አገሮች ያሉት ነባራዊ ሁኔታዎች የተለያዩ በመሆኑ ለሲቪል ማህበራት መስፋፋትና ማደግ የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉና አንዳንድ ባለሙያዎች አልፈው ተርፈውም በታዳጊው በተለይም በአፍሪካ አገሮች ለሲቪል ማህበረሰብ መፈጠር መነሻ የሚሆኑ የመንግስትና የኢኮኖሚ ስርዓቶች ተሟልተው የሚገኙ ባለመሆኑ የሲቪል ማህበራት ከጅምሩ አሉ ለማለት እንደማይደፍሩና ይህ ሰጣ-ገባ እስከአሁንም አከራካሪ ሆኖ መቆየቱን ገልፀዋል። ይሁን እንጂ በትንታኔአቸው አፍሪካና የተቀረውም የታዳጊ አገሮች በምዕራቡ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ መገለጫ በነበሩት የቅኝ አገዛዝ፣ የወታደራዊ ወረራና የእርዳታ ስርዓትን ተገን በማድረግ አገር በቀል የሆኑ የሲቪል ማህበራትን በመጫን፣ «ጎላ ቀር» ናቸው በሚል በማጥላላትና በማስወገድ በራሳቸው ተቋማት ለመለወጥ ያደረጉት ተፅዕኖ በቀላሉ መታየት እንደሌለበትና በአንፂሩም እነዚህ አገራዊ /ባህላዊ/ የሲቪል ማህበራት ይህንን ሁሉ ተፅእኖ በመቋቋም ከዘመን-ዘመን ተሻግረው ዛሬም ህብረተሰባቸውን ማገልገላቸው አድናቆት ሊቸራቸው እንደሚገባ ነው።

በተጨማሪም እንደ ኢንዱስትሪ አብዮቱና የብርሃንና የተሀድሶ ዘመናት ሁሉ ዛሬ በምንገኝበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ድንበር የለሽ፣ ወጥ-ዓለማዊነት (ግሎባላይዜሽን) ድንበር የለሽ የሆኑና ድንበር ሳይገድባቸው የዓለም ዜጎች ዓለማችንን ያስጨንቃታል ባሉበት እንደ ከባቢ አየር መለወጥ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ፣ የድህነት ቅነሳ ጥሪ፣ የዓለም የኢኮኖሚ ስርዓት መዛባትና ሌሎችም ጉዳዮች ዙሪያ በመሰብሰብ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እናስተውላለን።

ይህም የሲቪል ማህበራትን መነሻ ፅንሰ ሀሳብ እንደገና እንድንቃኝና እንድንፈትሽ የሚያደርግ ነው። ስለሆነም ዶ/ር ካሳሁን ትኩረት ሰጥተው አልፈውት ቢሆን ኖሮ መልካም ነበር።

ለ/ የሲቪል ማህበራት ሚና ዶ/ር ካሳሁን በፅሁፋቸው የሲቪል ማህበራትን በኢትዮጵያ ሚና ተፈራራቂ ከነበሩት የፖለቲካ ስርዓቶች ጋር በማነፃፀር ያላቸውን ሀሳብ አንፀባርቀዋል። አያይዘውም ባህላዊ

የሲቪል ማህበራት ድርጅታዊ ተቋማቸውና ተልዕኮአቸው በአብዛኛው ያልተለወጠ በመሆኑ አገራዊ በሆኑ የልማት ሥራዎች ላይ አስተዋጽኦአቸው አነስተኛ መሆኑን ጠቁመዋል፤

እዚህ ላይ ያለን የሀሳብ ልዩነት እነዚህ የባህል ተቋማት «ኋላቀር» ሆነው ሳይለወጡ የቀሩ ሳይሆን በመለወጥ ላይ ያሉ ተቋማት መሆናቸውንና እንደውም በተከታታይ በአገራችን ሰፍነው የነበሩ የፖለቲካ ስርዓቶች የራሳቸውን አገዛዝ ለማስረፅ ሲሉ እነዚህ ተቋማት ላይ ጫና ማድረሳቸውና ከልማት መስመር ውጪም እንዲሆኑ ማድረጋቸው ተቋቁመው መቆየታቸው ትኩረት የሚስብ ነው። እንዲሁም ይህንን ሁሉ ተቋማዊ ጫናና የፖለቲካ አገዛዝ ሥርዓት ተቋቁመው ዛሬም ሰፊውን ሕዝብ በተለይም የአነስተኛ ኑሮ ነዋሪ የሆነውን ዜጋ በስፋት ማገልገላቸው ጥንካሬአቸውን የሚያሳይ መሆኑን ነው። ድጋፍም ከተደረገላቸው በአገር ልማት ላይ ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ ነው።

ለአብነት ያህል የዕቁብ ተቋማትን ብንወስድ ከሥራ የተፈናቀለን፣ ከዘመቻ የተመለሰን፣ ከገጠር የፈለሰን፣ ከንግድ የከሰረንና፣ አዲስ ተለማማጅ ሥራ ፈጣሪን እንደ አቅሙና ችሎታው በማቋቋም፣ የገንዘብ/ካፒታል ምንጭ በመሆን፣ የመተማመን ሥርዓትን በማስፈን ምናልባትም ባንኮቻችን እያደረጉ ካሉት አስተዋፅኦ በማይተናነስ ሽፋን ከፍተኛ አገራዊ አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው።

በኢትዮጵያ የአነስተኛ የገንዘብ ቁጠባና የህብረት ሥራ ማህበራትም በከተማ በተለይም በተቀጣሪነት የሚያገለግለው የሠራተኛ ክፍል በማሰባሰብ የሚያደርጉት የቁጠባ ባህል ማስፋፋትና የገንዘብ ምንጭ እንቅስቃሴ የሚደነቅ ነው።

የበርካታ መንደር አቀፍ ግጭቶች የሚፈቱትና በየአካባቢው ዜጎች በሰላም ገብተው እንዲወጡ የሚደረገው የዚሁ የባህላዊ ተቋማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በመኖሩ እንጂ በአብዛኛው በዘመናዊ ፖሊስና ሰራዊት በማሰማራት ለመሆኑ የበለጠ ትኩረት ለወደፊትም ሊቸራቸው ይገባል።

2ኛ. በአዲስ መልክ እየተለመደ እያበረታታ የመጣው የሲቪል ማህበራት ሚና ደግሞ የዓለም ዓቀፍ የንግድ ሥርዓትን ጭቆና ለመቋቋም የሚደረጉት ጥረት ሲሆን በቅርቡ እንደምናስታውሰው የኢትዮጵያ የቡና አምራቾች ህብረት፣ ከኦክስፋም ዓለም ዓቀፍ ድርጅት ጋር የንግድ ምልክት መብት ባለቤትነት ጥያቄ ዘመቻ መጀመሩ የሚያበረታታና አዲስ የተሳትፎ ዘርፍን የሚያንፀባርቅ ነው። ከዚህ በፊትም ሌሎች ዓለም ዓቀፍ የንግድ ተቋማትን በተመለከተ ተመሳሳይ ርምጃ ተወስዷል። ይህ ለአገር ኢኮኖሚና ልማት ከፍተኛ ጥቅም መስጠቱ የማይታበል ነው።

3ኛ. የአገር ውስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተቋማት (ግድፈታቸው ዶ/ር ካሳሁን እንዳሉት ተጠብቆ) ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር በመሆኑ በአገራችን የልማት ሥራ ላይ የውጪ ርዳታን በመሳብ መንግስት ባልደረሰባቸው ወይም የመንግስት አቅም ግንባታ ክፍተት በሚታይባቸው ቦታዎችና ጉዳዮች ላይ የልማት እንቅስቃሴ ማድረጋቸው ግልጽ ነው። የእነዚህ የሥራ ውጤት ውስብስብ የሆኑ በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎችን ሁለንታዊ ችግሮች የሚቀርፍ ሥራዎችን ማከናወኑ በመሆኑ በአህዝ አስልቶ ማስቀመጥ ቢያስቸግርም አንድ በሲ.አር.ዲ.ኤ አማካይነት ተካሂዶ የቀረበ ጥናት እንደሚያመለክተው እ.ኤ.አ በ1997-2001 የ5 ዓመታት ጊዜ ውስጥ እነዚህ ተቋማት

ከ3.6 ቢሊዮን ብር በላይ ለልማት ሥራ በአብዛኛው ከውጪ ምንጮች ፈሰስ ያደረጉ ሲሆን 23.2 ሚሊዮን የሚሆን የህብረተሰባችን ክፍልን የጤናና ውሀ (51%)ና፣ የምግብ ዋስትና (17%) የመሠረታዊ ልማት (15%) የትምህርት (11%) ተጠቃሚ አድርጓል።

ከዚህ በተጨማሪም የሲቪል ማህበራት የፖለቲካ ሥርዓቱ «በጋበዛቸው» የፖሊሲ ውይይት መድረኮች ላይ በመሳተፍ የየበኩላቸው አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ለምሳሌም፤ የኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ መሻሻል፣ የኤች አይ ቪ ኤድስ አገር አቀፍ መመሪያ መውጣት፣ የድህነት ቅነሳ ስልት መተለምን መጥቀስ ይበቃል።

እስከአሁን የዘረዘርኳቸው ዶ/ር ካሳሁን አቅርበዋቸው ነገር ግን ትኩረት የበለጠ ሊሰጣቸውና ጎልተው ሊወጡ ይገባል ባልኳቸው የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት የልማት ሚና ላይ ነው። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ዋና ዋና ችግሮቻቸው ላይ አተኩራለሁ። ዶ/ር ካሣሁን እንዳሉት እነዚህ የሲቪል ማህበራት ማንነትን በጋራ ከመግለፅ አንስቶ የውስጥ ባህሪያቸውንና የሥራ እንቅስቃሴያቸውን በተመለከተ ችግሮቻቸውን በሚገባ አብራርተዋል። የወደፊት ራዕያችን በጎና የተሻለ ሆኖ ማየት ከሆነ ደግሞ እነዚን ችግሮች በሚገባ ማወቅና መፍታት ያስፈልጋል። ስለሆነም የሚከተሉትን በሁለት ዘርፍ በመክፈል አቀርባቸዋለሁ፡

1. <u>ውስጣዊ ችግሮች</u> - ሲቪል ማህበሮቻችን በተለይም የተወሰኑ የአገር ውስጥ መያድ የአመራር ጥንካሬ ማነስና የአመራር ሽግግር ባህል «መሆን» መሆን ይታያል። ይህ ደግሞ የተወሰኑ ተቋማት የሲቪል ማህበራት መሠረታዊ መገለጫ የሆኑትን የአባላት የነቃና የጠነከረ ተሳትፎና የአመራር አባላት ግልፅነትና የስልጣን ሽግግር እንዳይኖራቸው ያደርጓቸዋል። ይህ በሌሎቹ የንግዱና የፖለቲካ ዘርፎች ውስጥ መፀባረቁ ተመሳሳይነት ቢኖረውም በራሱ አሉታዊና የሲቪል ማህበራትን እድገት የሚፃረር ነው።

2. <u>ውጫዊ ችግሮች</u> - አንዱ ውጫዊ-ውስጣዊ የምላቸው የሲቪል ማህበራት ሥነ-ምግባር ኮድ ተዘጋጅቶ የቀረበ ቢሆንም በተገቢ ሁኔታ ተግባራዊ አለመሆኑ፣ የአመዘጋገብና የአደረጃጀታቸውን ሁኔታ በመንግስት በኩል አገሪቱን በሚጠቅም አኳያ በህግ አቃፊነት እስከአሁን አለመውጣቱ የሚያሳስብ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የዓለም ዓቀፍ አጀንዳዎች እንዲፈፀሙ ተጋላጭ መሆንና እንቅስቃሴዎቹ በውጪ እርዳታ እገዛ ላይ ጥገኛ መሆን ለመስኩ አለመዳበር የራሱን አስተዋፅኦ አድረጓል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊጠቀስ የሚገባው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ታዳጊም ቢሆኑ ከዕለታዊ ምፅዋት አልፎ በስልታዊና ሥርዓት በጠበቀ የዕርዳታና የልማት ሥራዎች ላይ አለመሳተፍና የግንኙነት ድልድዩ ክፍተት መታየት ነው።

በመጨረሻም ዶ/ር ካሳሁን ያሏቸውን ራዕይ የምጋራ ሲሆን የሚከተሉትን ማጠናከሪያ አስተያየቴን በማቅረብ ጽሑፌን እደመድማለሁ።

በ2020 ስንደርስ የምናገኛቸው የሲቪል ማህበራት፣ ከፖለቲካ/መንግስት/ና ከገበያው /ግል/ ሴክተሩ ጋር በአንድ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ፣ በመከባበር በባለቤትነት ተቀምጠው የጋራ አገራዊ ራዕይና የልማት ስልት የሚቀይሱበትን መድረክ ማየት ነው። ለዚህ ራዕይ መሳካትም፡-

1. አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍላችን የሚስማማበትና ተፈፃሚ የሚሆን የህግ መመሪያና ድጋፍ ከመንግስት ወጥቶ ተግባራዊ መሆን ይገባዋል።

2. የግሉ ንግድ ክፍል ከትርፍና ከግብር ክፍያ ግዴታው ጋር በተጣጣመ መልኩ ለሲቪል ማህበራትና ትርፍ ለማያመነጩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መጎልበት የሚያደርግበትን ሥርዓት ማመቻቸትና ማስፈፀም ይገባል።

3. ባህላዊና ነባራዊ የሲቪል ማህበራት ህብረተሰቡን በማገዝና በማስተባበር በኩል የሚኖራቸው ሚና የበለጠ እውቅና አግኝቶ አዳዲስ ከሚፈጠሩት ድርጅቶች ጋር በጋራ ወይም በተጓዳኝ ልማታዊ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ተቋማዊና የማቴሪያል ድጋፍ ሊደረግላቸው ያስፈልጋል።

4. የአገር ውስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጠንካራ አባላትን የሚያፈሩበትንና ተገቢ የአመራር ሽግግር የሚያደርጉበትን መንገድ በመፍጠርና በማመቻቸት ከፕሮጀክት እድሜ አልፈው፣ ከአንድ ትውልድ በላይ የሚያገለግሉ ድርጅቶች እንዲሆኑ የበኩላቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባል።

5. ከዚህም በላይ የአገር ውስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) «በተጋበዙባቸው» ብቻ ሳይሆን «በሚፈጥሯቸው» የፖሊሲ መድረክ ላይ ጭብጥን ምርኩዝ አድርገው የፖሊሲ አወጣጥና አፈፃፀም ላይ ጥራትና ብቃት ያለው እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ይጠበቃል።

በመጨረሻም በ2020 በጋራ የበለፀገች ለዜጎቿ ሁሉ በእኩል የምትመች ኢትዮጵያን ለማየት ያብቃን!

አመሰግናለሁ።

የኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች የማሳካት ዕድል[1]

ጌታቸው አደም[2]

1. ምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ታሪካዊ አመጣጥና ምንነት፣

1.1 የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ታሪካዊ አመጣጥ

ድህነት በተለያየ ፈርጁ የዓለም ህብረተሰብ የሥጋት ምንጭ ከሆነ በርካታ ዓመታትን አስቆጥሯል። አንዱና ዋነኛው የልማት አጀንዳም ሆኗል። የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች እ.አ.አ በ1990ዎቹ በተለያዩ ጊዜና ወቅት በተባበሩት መንግሥታት አስተባባሪነት የተካሄዱ የተለያዩ አገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች የተገኙ ግንዛቤዎች ነፀብራቅ ናቸው። እነዚህ ግንዛቤዎች የመንግሥታት ተወካዮችን ብቻ የሚወክሉ ሳይሆኑ፣ በተለያየ ደረጃ የሲቭክ ማህበረሰቦችንና የግሉን ዘርፍ ተወካዮች አመለካከትና ሀሳቦችን ጭምር ያስተናገዱ ነበሩ። በመጨረሻም ከእነዚህ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች የተገኘው አጠቃላይ ግንዛቤ የልማት ችግሮች ዘርፈ ብዙ (Multi-dimensional) መሆናቸውንና ልማት ደግሞ የመጨረሻ ግቡ የሰዎች ደህንነት መሆን እንደሚገባውና የሰው ሀብት ልማትን (Human Development) ማረጋገጥ ያልቻለ የኢኮኖሚ ልማት የመጨረሻ ግቡን ያልመታ መሆኑን ነው።

የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (Millennium Development Goals -MDGs) የበለፀጉ አገሮች የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) አካል የሆነው የልማት ድጋፍ ኮሚቴ (Development Assistance Committee) አማካይነት እ.አ.አ በ1996 በተቀረጹት የዓለም አቀፋዊ የልማት ግቦች (International Development Goals-IDGs) ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

የዓለም አቀፋዊ የልማት ግቦች የጊዜ አድማስ 25 ዓመት ሆኖ የመነሻ ጊዜው እ.አ.አ. 1990 ሲሆን የመድረሻ ጊዜው ደግሞ እ.አ.አ. 2015 ነው።

የዓለም አቀፍ የልማት ግቦችን የመቅረጽ ዓላበጊዜው የበለፀጉ አገሮች የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) አባል የሆኑ 23 የበለፀጉ የአውሮፓ አገሮች ከድሃ አገሮች ጋር በሚኖራቸው የልማት ትብብር ግንኙነት በ21ኛው ፍለ ዘመን በእነዚህ አገሮች የሚኖሩ ህዝቦችን ህይወት ለማሻሻል ታስቦ ነበር።

[1] ግንቦት 17 ቀን 1999 ዓ.ም የተካሄደ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡ ፡

[2] አቶ ጌታቸው አደም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በስታትስቲክስ፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በእንግሊዝ ሀገር በኢኮኖሚክስ አግኝተዋል። አቶ ጌታቸው አደም በገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተለያየ የኃላፊነት ቦታዎች ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት የልማት ዕቅድና ጥናት መምሪያ ኃላፊ ናቸው።

ሆኖም እነዚህ ዓለም አቀፋዊ የልማት ግቦች የለጋሾች (Donor Community) ዓዕምሮዊ ውጤት በመሆናቸው (Being the Brain-child of Developed Nations) ምክንያት በታዳጊው ዓለም በሚገኙ አገሮች የመንግሥታት ተወካዮችም ሆነ በስቪክ ማህበረሰቡ በኩል በሙሉ ልብ ተቀባይነት አላገኙም ነበር። ለዚህም ይመስላል እ.አ.አ በ2000 የተሻለች ዓለም ለሁሉም፤ የዓለም አቀፋዊ የልማት ግቦችን ለመድረሰ የተደረገው ግስጋሴ (A Better World for All: Progress to Wards the International Development Goals) በሚል የተዘጋጀው ሪፖርት ከሁሉም አቅጣጫ ሰፊ ትችትና ተቃውሞ ገጥሞት የነበረው። የትችቱ መነሻ ከሪፖርቱ ላይ ለተመለከተው የሶሻልና የኢኮኖሚ ግስጋሴ መጓተት የበለፀጉ አገሮችና ዓለም አቀፍ የፋይናንስና የልማት ተቋማት ታዳጊ አገሮችን ተጠያቂ ማድረጋቸውና ራሳቸውን ከደሙ ንፁህ ለማድረግ መሞከራቸው ነው።

ከዚህም በላይ ደግሞ እነዚህ ግቦች የበለፀጉ አገሮች ወይም ለጋሾች የአዕምሮ ውጤት መሆናቸውና ገና ከጥንስሱ በታዳጊ አገሮች ወገን በእነዚህ ግቦች ላይ ሙሉ መግባባት ያለመድረሱ ነው። የበለፀጉ አገሮች የዕርዳታ አሰጣጥ ስርዓት ከተቀባይ አገሮች ፍላጐትና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አለመጣጣም፣ የየአገሮችን የልማት ፍላጐት ቅደም ተከተል ያላገናዘበ መሆኑንና የበለፀጉ አገሮች ታዳጊ አገሮች በሚከተሉት የልማት ፖሊሲ አቅጣጫ ላይ ተፅዕኖ ማድረጋቸው ... ወዘተ ለልማቱ መጓተት የሚያደርገው ተፅዕኖ ከግንዛቤ ውስጥ ያለመግባቱ የትችቶቹ ማጠንጠኛዎች ነበሩ።

ይህ አጋጣሚ የዓለም አቀፋዊ የልማት ግቦች (International Development Goals – IDGs) አጀንዳ ወደ ምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (Millennium Development Goals – MDGs) አጀንዳ እንዲሸጋገር መንገድ ከፍቷል። ይህ ሁኔታ ግን በግቦቹ መሠረታዊ ይዘት ላይ እምብዛም ለውጥ አላመጣም። ለምሳሌ፤ ቀድሞ በዓለም አቀፋዊ የልማት ግቦች ውስጥ ከተካተቱት ውስጥ ከአንዱ በስተቀር ቀሪዎቹ አሁን ባሉት 8 የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (Goals) ውስጥ ተካተዋል። ይህም ሆኖ ግን የሁሉንም ይሁንታ አግኝተው እ.አ.አ በሴፕቴምበር 2000 የ189 አገሮች መሪዎች ሊተገብሯቸው በፊርማቸው አረጋግጠዋል። እነዚህ ግቦች ዓለም በአንድ ድምፅ በድሀ አገሮች የሚኖሩ ህዝቦችን ህይወት በሁለንተናዊ መልኩ ለማሻሻል በጋራ ቃል መግባታቸውን ያረጋገጡባቸው እውነተኛ የልማት ግቦች ተደርገው ተወስደዋል።

ከዚህ አንፃር እነዚህን የማህበራዊና የልማት ችግሮች ማስወገድ ቅድሚያ ኃላፊነቱ የየአገሮቹ መሪዎች ቢሆንም የበለፀጉ አገሮችም ዓለም አቀፍ ደህንነትን ከማረጋገጥ አኳያ የበኩላቸውን መወጣት እንዲችሉ ተጨባጭ ግዴታዎችን ለማስቀመጥ አንድ ግብ (Goal 8) የተቀመጠ ቢሆንም ይህ ግብ እንደሌሎቹ ሰባት ግቦች አኃዛዊ የግብ አመልካች የሌለው ከመሆኑም በላይ የአመልካች ግቦች መፈፀሚያን ለማረጋገጥ የሚያስችል የተወሰነ የጊዜ ገደብን ያስቀመጠ አልነበረም። በሂደት ግን በተለይም እ.አ.አ ከ2002 የሞንተሬ (ሜክሲኮ) ኮንፍረስ እና ተከታታይ መድረኮች የበለፀጉ አገሮች የገቡትን ዓለም አቀፋዊ የልማት አጋርነት ቃል እንዲወጡ የሚያስችሉ አኃዛዊ የግብ አመልካቶች (Indicaters) ተቀምጠዋል።

ይህም የበለፀጉ አገሮች በጋራ የጠቅላላ የብሔራዊ ምርታቸውን 0.7 በመቶ ለድሃ አገሮች በዕርዳታ መልክ ለመስጠት የገቡት ቃል ነው። ሆኖም (Goal 8) መቀመጡ በራሱ የበለፀጉ አገሮች ዓለም አቀፋዊ የልማት

አጋርነት (Solidarity) የሚሊኒየሙ የመሪዎች ውሣኔ (Decleration) መሠረታዊ መርህ ተደርጐ ተወስዷል።

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው እ.አ.አ በማርች 2002 በሞንተሬ ሜክሲኮ ላይ የተካሄደው ፋይናንስ ለልማት (Financing for Development) የተሰኘው ዓለም አቀፍ ጉባኤ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከማሳካት አንፂር ለሚሊኒየሙ ውሳኔ (Millennium Declaration) የዓለም መሪዎች ያላቸውን የፀና አቋም ለሁለተኛ ጊዜ ያረጋገጡበት ነበር። በዚህ ጉባኤ ላይ የበለፀጉ አገሮችና የታዳጊ አገሮች ዓለም አቀፋዊ አጋርነት ወደ አዲስ ደረጃ የተሸጋገረበትና በሁለቱም መካከል የሚኖረው አጋርነት በጋራ ኃላፊነት ላይ የተመሠረተ አንዲሆን መግባባት ላይ የተደረሰበት ነበር።

ይህም ማለት ታዳጊ አገሮች በአገር ውስጥ የልማት የፋይናንስ ማስፈጸሚያ የገቢ ምንጮችን የማስፋፋት (Domestic Resource Mobilization) አቅማቸውን በማጎልበት ረገድ ጥረት የማድረግን፣ መልካም አስተዳደርን የማስፈን፣ የሕዝባቸውን የሶሻልና የኢኮኖሚ ልማት ችግሮች ለማስወገድ የሚያስችላቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የመቅረጽ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ነው። በበለፀጉ አገሮች በኩል ደግሞ ለታዳጊ አገሮች አመች የሆኑ ደጋፊ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን መፍጠርና የታዳጊ አገሮችን ልማት ለማፋጠን የሚያስችል የፋይናንስ ድጋፍን ማሳደግ ናቸው። ደጋፊ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን መፍጠር ሲባል ከታዳጊ አገሮች ጋር የሚደረጉ የንግድ እንቅስቃሴዎችን መደገፍንና የገበያ ሁኔታን ማመቻቸትን የሚያካትቱ ድጋፎች ናቸው። እ.አ.አ በሴፕቴምበር 2002 ጆሃንስበርግ ደቡብ አፍሪካ የተካሄደው በታዳጊ አገሮች ቀጣይ ልማት (Sustainable Development) በማምጣት ላይ የመከረው የመሪዎች ስብስብ በሞንተሬ በሁለቱም ወገን ለተወሰደው አቋም ድጋፉን ሰጥቷል።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዓለምአቀፋዊ ጥረቶች የምዕተ ዓመቱን ግቦች በአገር ደረጃ ወደተግባር ከማሸጋገር አኳያ መሠረት የጣሉ ናቸው።

1.2 የምዕተ ዓመቱ ግቦችና የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂዎች

የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች እና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። ቀደም ብሎ እንደተመለከተው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የዓለም አቀፋዊው የልማት ግቦች ቀጣይ ሆነው እ.አ.አ. በሴፕቴምበር 200ዐ የዓለም መሪዎች በአዲስ መንፈስ ለዓለም ሕዝቦች ሁለንተናዊ ደህንነት ያላቸውን ቁርጠኝነት ያደሱበት ነው። የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች በአዲስ መንፈስ የተጀመሩት የዓለም አቀፋዊው የልማት ግቦች ከተፀነሱበት እ.አ.አ. ከ1990 በኋላ 10 ዓመት አስቆጥሮ ነው። የምዕተ ዓመቱ ግቦች የጊዜ አድማስ 15 ዓመት ሲሆን የዓለም አቀፉ የልማት ግቦች የጊዜ አድማስ 25 ዓመት እንደነበር ልብ ይሏል።

ከጊዜ ቅደም ተከተል አንፂር የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ከዓለም አቀፉ የልማት ግቦች መፀነስ በኋላ የመጡ ሲሆኑ ከምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ጋር በአንድ በተወሰነ የጊዜ አድማስ ውስጥ የተፀነሱ ናቸው። የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች የጊዜ አድማስ እንደየአገሮች ተጨባጭ ሁኔታ ከ3 እስከ 5 ዓመት የሚወሰን

በመሆኑ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማዳረሻ ምዕራፎች ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው።

የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች (Poverty Reduction Strategies) እ.አ.አ. በ1980ዎቹ እና በ1990ዎቹ በዓለም ባንክ እና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አስተባባሪነት በታዳጊ አገሮች የተተገበሩ የመዋቅራዊ ለውጥ ማሻሻያ እርምጃዎች (Structural Adjustment Programs) አፈጻጸም ሂደት ከታዩ ውጤቶች የተወሰዱ ግንዛቤዎችና ተሞክሮዎች ነፀብራቅ ናቸው። እነዚህን ዓለም አቀፍ የፋይናንስና የልማት ተቋማትን (World Bank and IMF) ክፉኛ የሚተቹ አካላት እንደሚሉት ከሆነ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች እነዚህ ተቋማት ለ50 ዓመታት ያህል በድሀ አገሮች ላይ እንዲተገበሩ ሲያበረታቷቸው የነበሩ የፖሊሲ አቅጣጫዎችንም የማያዋጡ የነበሩ መሆናቸውን የተናዘዙበት አጋጣሚ ነው ይላሉ። በዚህ ዘመን በዓለም ባንክ በኩል ይንፀባረቅ የነበረው እምነት አጠቃላይ ዕድገት እስካለ ድረስ የዕድገት ትሩፋት ቀስ በቀስ በመንጠባጠብ (Trickle down) ወደ ድሀው የሕብረተሰብ ክፍል ይደርሳል የሚል ነበር።

በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) በኩል የነበረው እምነት ደግሞ የአጠቃላይ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ማስፈን ከሁሉ በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው የኢኮኖሚ አመራርና አስተዳደር ተግባር አድርጐ የሚወሰድ ስለነበር ድሀ አገሮች ዕድገትን ለማፋጠን ከሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫ አንፃር መፈናፈኛ የሚያሳጣ ስለነበር ዕድገትን በከፍተኛ ደረጃ የገደበ ነበር የሚል ነው። በመሆኑም ሁለቱም ተቋማት ይከተሉት የነበረው የፖሊሲ አቅጣጫ በታዳጊ አገሮች ውድቀትን ያስከተለ መሆኑ በሰፊው ተተችቷል። ለምሳሌ በአሜሪካ ኮንግረስ የሁለቱን ተቋማት ሚና ለመመርመር የተቋቋመውና በታዋቂው የምጣኔ ሀብት ምሁር በፕሮፌሰር አላን ሜልዘር የተመራው ልዩ የአማካሪ ኮሚሽን እ.አ.አ. በማርች 2000 ባቀረበው ሪፖርት ሁለቱን አካላት ክፉኛ ኮንኗል። በሪፖርቱ እንደተመለከተው እነዚህ ተቋማት ያደርጉ በነበረው ግፊት ሳቢያ በታዳጊ አገሮች የተሳሳቱ ፖሊሲዎችና እርምጃዎች በመወሰዳቸው ድህነት በከፍተኛ ደረጃ መባባሱንና የአገሮች የልማት ደረጃም በከፍተኛ ደረጃ ማሽቆልቆሉን አመልክቷል። ለምሳሌ ባለፉት 50 ዓመታት በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ (Least Developed Countries) ውስጥ ተፈርጀው ከነበሩ አገሮች ውስጥ ወደ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ (Middle Income Countries) የተሸጋገረችው አፍሪካዊት አገር ቦትስዋና ብቻ ነበረች። የዚህች አገር እርምጃም ቢሆን የራሱ ምክንያት ያለው ነው።

በመሆኑም አዲስና የተለየ አግባብ (New Approach) መቀየሱ የግድ ነበር። አዲሱ አግባብም ዕድገትና ልማትን ማፋጠን እንደተጠበቀ ሆኖ የዕድገትና የልማት እንቅስቃሴ ሰብአዊ ፍላጐትን በማሟላት ድህነትን ማስወገድ ላይ ቀጥተኛ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል የሚል ነው። ይህም ማለት በድህነት ላይ የሚደረገው ርብርብ ዙሪያ ገጠም መሆን ይኖርበታል ነው። ዕድገትን ከማፋጠን ባሻገር በትምህርት፣ በጤና፣ በንፁሕ ውሃ አቅርቦት፣ በመሠረተ ልማት (መንገድ) አቅርቦት ወዘተ... ላይ በማተኮር የድህነት መንስዔዎችን ከሥሩ መዋጋት ያስፈልጋል የሚል መርህን ያዘለ ነው።

ሁለቱ እህትማማች ዓለም አቀፍ የፋይናንስና የልማት ተቋማት የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂን ሃሳብ ሲያራምዱ ዋነኛዎቹ ማሳመኛዎቻቸው (Justification) ከዚህ በላይ የተመለከቱት ሲሆኑ ሌላው ተያያዥ የሆነውና በዚህ ረገድ ሳይጠቀስ የማይታለፈውና ከድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ፅንሰ ሃሳብ ጋር የተያያዘው ከፍተኛ

የዕዳ ጫና ያለባቸው አገሮች የዕዳ ማቃለያ ፕሮግራም (Heavily Indebted Poor Countries Initiative) **የተሰኘው ነው። ሁሉን አቀፍ የሆነ የዕዳ ማቃለያ ፕሮግራም ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ የሆነው እ.አ.አ. በ**1996 **በዋሽንግተን በተካሄደው የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ ላይ ነበር።**

በቀጣይ እ.አ.አ. በሴፕቴምበር 1999 **በተካሄደው ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ ላይ ደግሞ የዓለም ባንክ እና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ዝቅተኛ ወለድ ያለው የልማት ብድር** (Concessional Loan) **ተጠቃሚ ለመሆን በታዳጊ አገሮች በራሳቸው ባለቤትነት የሚዘጋጁ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች እንደማዕቀፍ እንዲያገለግሉ ሆኖ ከዕዳ ማቃለያ የሚገኘው ፋይናንስ አመዳደብና አጠቃቀም በእነዚህ ስትራቴጂዎች ማዕቀፍ እንዲመራ መግባባት ላይ ተደረሰ። እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ፅንሰ ሃሳቦችን አመጣጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዴት እንደነበር የሚጠቁሙ ናቸው።**

ይህንኑ መሠረት በማድረግ ቀደም ብሎ የተጠናከረ የመዋቅራዊ ለውጥ ማስፈጸሚያ (Enhanced Structural Adjustment Facility) **ተብሎ ይታወቅ የነበረው የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የፋይናንስ ድጋፍ መሣሪያ የድህነት ቅነሳና የዕድገት ማስፈጸሚያ** (Poverty Reduction and Growth Facility - PRGF) **በሚል ተተካ። በዓለም ባንክ በኩልም እንደዚሁ በታዳጊ አገሮች የሚተገብራቸው ፕሮግራሞች የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂን መንፈስ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲቃኙ በማድረግ የመካከለኛ ዘመን ዕይታ** (Three Years Time Frame) **ያላቸው ፕሮግራሞችን ያቀፉ አገራዊ የድጋፍ ስትራቴጂዎች** (Country Assistance Strategy) **በመቅረፅ የመተግበር እንቅስቃሴ ተጀመረ።**

በመሆኑም የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂም ዝቅተኛ ወለድና ረጅም የመክፈያ ጊዜ ያላቸው የልማት ብድሮችን ተጠቃሚ ለመሆን እንደ ቅድመ ሁኔታ ማሚያ (Necessary Condition) **ተደርገው ተወሰዱ። ከዚህም በተጨማሪ ለተከታታይ የዕዳ ማቃለያና ዕዳ ስረዛም ቅድመ ሁኔታ ተደርገው ተወሰዱ። የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች በዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በአንድ ወገን እና በሌላ ወገን በድሃ አገሮች መካከል ለሚኖረው የልማት ትብብር ግንኙነት እንደ ማዕቀፍ ተደርገው ከመወሰዳቸውም በላይ በስተኋላ ከለጋሽ አገሮችም ጋር ለሚደረጉ የትብብር ግንኙነቶች ጭምር ማዕቀፍ ተደርገው በመወሰዳቸው በመጨረሻ በአጠቃላይ በለጋሾችና በድሃ አገሮች መካከል የትብብር ማዕቀፍ ተደርገው ተወስደዋል።**

የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች እንደየአገሮች ሁኔታ የሚለያዩ ቢሆንም የሚከተሉት የጋራ መገለጫዎች አሏቸው። እነሱም የዝግጅት ሂደታቸው አሳታፊ መሆኑን ማረጋገጥ (Participatory)**፣ የአገሮች ባለቤትነትን ማረጋገጥ** (Country ownership)**፣ አገራዊ የፖሊሲ ማዕቀፍ የመኖር አስፈላጊነትና ከአገሮች ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ጋር የመጣጣም አስፈላጊነት፣** (PRSPs should not be stand alone strategies)**፣ ስትራቴጂዎቹ በረጅም የጊዜ አድማስ ውስጥ መተግበር የሚገባቸው ስለመሆኑ (ይህም ማለት በምዕተ ዓመቱ ግቦች ዕይታ ውስጥ መተግበር ይገባቸዋል የሚሉ) ናቸው።**

2. **የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ከአገራዊ የልማት ዕቅዶች ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ጋር ያላቸው ትስስር፣**

የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። ቀደም ቡሎ እንደተመለከተው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የዓለም ዕቀፋዊው የልማት ግቦች ቀጣይ ሆነው እ.አ.አ በሲፕቴምበር 2000 የዓለም መሪዎች በአዲስ መንፈስ ለዓለም ህዝቦች ሁለንተናዊ ደህንነት ያላቸውን ቁርጠኝነት ያደሰበት ነው። የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች በአዲስ መንፈስ የተጀመሩት የዓለም ዕቀፍዊው የልማት ግቦች ከተፀነሱበት እ.ኤ.አ. 1990 በኋላ 10 ዓመት አስቆጥሮ ነው። የምዕተ ዓመቱ ግቦች የጊዜ አድማስ 15 ዓመት ሲሆን የዓለም አቀፋ የልማት ግቦች የጊዜ አደማስ 25 ዓመት እንደነበር ልብ ይሏል።

ከዚህ አንፃር የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂውን ዝግጅት የሚያስተባብረው አካል በጊዜው የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር በመሆኑ እንደጉዳዮቹ አግባብነት ከሚመለከታቸው የዘርፍ አስፈጻሚ አካላት ፕሮግራሞች አኳያ እየታየ በሰነዱ ውስጥ እንዲንፀባረቁ አስፈላጊው ጥረት ተደርጓል። በየደረጃው ከምክክሩ የተገኙ ውጤቶች በየዘርፉ ተለይተው በሪፖርት መልክ እንዲደርስ በመደረጉ የተገኙ ውጤቶችን ጭምቅ ግኝት ራሱን በቻለ ምዕራፍ በመጨረሻ በዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም (Sustainable Development and Poverty Reduction Program - SDPRP) **ሰነዱ ውስጥ እንደ አንድ የመንደርደሪያ ምዕራፍ በየዘርፉ በመከፋፈል ለማቅረብ ተሞክሯል።**

በይዘት ረገድ የመጀመሪያው የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ሰነድ በኢትዮጵያ በመተግበር ላይ በሚገኙ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ላይ የተመሠረተና ከእነዚሁ ጋር የተጣጣመና በእነዚሁ ላይ የቆመ ነው። ለዚህም ነው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነዱ «የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም» (Sustainable Development and Poverty Reduction Program - SDPRP) **ተብሎ የተሰየመው። የኢትዮጵያ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ከስያሜው እንደሚታየው መሠረቱ ሰፊ እና ድሃ ተኮር የሆነ ዕድገትና ልማትን በማፋጠን ድህነት ቅነሳና ብሎም ማስወገድን ማዕከል ያደረገ አገር በቀል ፕሮግራም ነው። ከዚህ አኳያ የመጀመሪያው የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም በአራት ምሰሶዎች ላይ የቆመ ነው። እነዚህም፣**

- **ሀ) የግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ** (Agricultural Development Led Industrialization (ADLI) Strategy)፣
- ለ ያልተማከለ አስተዳደርን ለማስፈንና የታችኛውን የህብረተሰብ ክፍል የማብቃት ፖሊሲና ስትራቴጂ (Decentralization and Empowerment Policy and Strategy)'
- ሐ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት አቅም የማጎልበት ኘሮግራምና ስትራቴጂ (Capacity Building Program for Public and Private Sector)'
- **መ) የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች፣ የፍትሕና የዳኝነት ሥርዓት የማሻሻያ ፕሮግራሞች** (Justice and Civil Service Reform Program)፣

እነዚህ ምሰሶዎች ሁሉን አቀፍ ናቸው። የኢኮኖሚውን ዘርፍ፣ የማህበራዊውን ዘርፍ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ፣ የፖሊቲካውን ዘርፍ የፍትህና የዳኝነት ሥርዓቱን ዘርፍ (የንብረት ባለቤትነትን ጨምሮ) የዜጐችን ግዴታና ተጠያቂነትንና የሕዝብ አገልጋይነት፣ ተቋማዊ ለውጥን፣... ወዘተ ያቀፉ ናቸው። እነዚህ ሁሉ ለዕድገት፣ ለልማትና ለድህነት ቅነሳ የሚኖራቸውን ሚና መገንዘቡ የሚያዳግት አይደለም።

የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሣ (ዘልድቅ) ፕሮግራም ሰነድን የማዘጋጀቱ ሥራ ከ1 ዓመት ያላነሰ ጊዜ (የምክክሩን ሂደት ጨምሮ) የወሰደ ሲሆን በመጨረሻ ከ1995 እስከ 1997 ያለውን ጊዜ የሚሸፍን የሦስት ዓመት የጊዜ አድማስ ያለው የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም (ዘልድቅፕ) ተዘጋጅቶ በነሐሴ 1994 ለዓለም ባንክና ለዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ቀርቦ ተቀባይነት በማግኘቱ ተግባራዊ ሆኗል። ይህ ሰነድ ሁሉን አቀፍ ፕሮግራም ሆኖ የአገሪቱን የሶሺዮ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለመምራት እንደማዕቀፍ ከማገልገሉም በላይ ከልማት አጋሮች ጋር ለሚደረገው የትብብር ግንኙነትም አንዱና ዋናው አገናኝ ድልድይ በመሆን እስከ 1997 በጀት ዓመት መጨረሻ አገልግሏል። አሁን በመተግበር ላይ ያለው የ5 ዓመት የልማት ዕቅድ በዚሁ ቋት የተተካ ነው።

የድህነት ቅነሳን ዓላማ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከግብ ማድረስ እንደማይቻልና ይህ ዓላማ በረጅም ጊዜ ዕይታ ውስጥ መተግበር እንደ? ሚኖርበት ቀደም ብሎ በመንግሥት ግንዛቤ በመወሰዱና በዓለም አቀፍ መድረክም የምዕተ ዓመቱን ግቦች በእያንዳንዱ አገር ደረጃ ተግባራዊ የማድረጉ ጥረት ትኩረት የተሰጠው አጀንዳ ስለነበር በኢትዮጵያም ይህንኑ የሚደግፉ እንቅስቃሴዎች በተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት በኩል በመጀመራቸውና ይኸው ሃሣብ ተቀባይነት በማግኘቱ የመጀመሪያው ተግባር የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለማየት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ ነበር። በዚሁ መሠረት ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ የተቃኘ «የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ፈታኝ ሁኔታዎችና ዕድሎች» የሚል የጥናት ሰነድ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና በተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት (UNDP) ትብብር ተዘጋጅቶ በሐምሌ ወር 1996 ይፋ ሆነ።

በዚህ ጥናት አማካይነት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሙከራ ተደርጓል።

ሀ) የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ለኢትዮጵያ ምንድን ናቸው? በአገሪቱ ከመተግበር ላይ ከሚገኙ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች እንዲሁም በመወሰድ ላይ ካሉ የፖሊሲና የተቋማዊ አወቃቀር ለውጦች ጋር ይጣጣማሉን?

ለ) የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ከዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም የግብ አመልካቾች (targets) ጋር ይጣጣማሉን?

ሐ) በዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙ ትኩረት የተሰጣቸው ዘርፎች ከምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የትኩረት መስኮች ጋር ይጣጣማሉን?

መ) የኢትዮጵያ የመረጃ ምንጭና የመረጃ ፍሰት ሥርዓት የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች የግብ አመልካቾች አፈጻጸም ለመገምገም የሚያበቁ ናቸውን? የግብ አመልካቾቹን ከኢትዮጵያ የመረጃ ሥርዓትና ፍሰት ጋር እንዴት ማጣጣም ይቻላል? (How to customize the targets so that the data requirements of MDGs are accommodated by the existing information infrastructure)?

ሠ) በዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም የተጣሉ የግብ አመልካቾች (targets) የምዕተ ዓመቱን ግቦች ለመድረስ ከሚጠበቀው እንቅስቃሴ አንፂር በቂ ናቸውን?

ረ) በዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ከተጣሉ ግቦች ለመድረስ የተገመተው ፋይናንስ የምዕተ ዓመቱን ግቦች ከመድረስ አንፂር የተቃኘ ነውን?

የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራምን የመሰሉ የመካከለኛ ዘመን ፕሮግራሞች/ስትራቴጂዎች የምዕተ ዓመቱ ግቦች ማዳረሻ ድልድዮች እንደመሆናቸው መጠን በዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም የሚጣሉ ግቦች የምዕተ ዓመቱን ግቦች ከመድረስ አንፂር የተቃኙ እንዲሆን የግድ ይላል። በዚህ ጥናት መሠረት በዘልድቅ ፕሮግራም የተቀመጡ የዘርፍ ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም የሚያስፈልገው ፋይናንስ የኢትዮጵያን የልማት ችግሮች ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ከማፋጠን አንፂር የተቃኘ (MDGs consistent) ያለመሆኑን ለመገንዘብ አስችሏል (MDGs: Challenges and Prospects for Ethiopia, July 2004)::

ይህ ጥናት የምዕተ ዓመቱ ግቦች የትኩረት መስኮችና የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙ የትኩረት መስኮች ከይዘት አኳያ የተጣጣሙና የሚመጋገቡ መሆናቸውንና ሁሉም የድህነት ተኮር ዘርፎች ማለትም ትምህርት፣ ጤና፣ መንገድ፣ የውሃ አቅርቦትና የግል ንፅሕና፣ ግብርናና ገጠር ልማት እንዲሁም ምግብ ዋስትና እያንዳንዳቸው እኩል ሚዛን የሚሰጣቸው እኩል አስፈላጊና ወሳኝ ስለመሆናቸው (All poverty – targeted sectors are equally important for Ethiopia) ግንዛቤ ተወስዷል። ዋናው ጉዳይ ግን ለፕሮግራሞቹ የሚያስፈልገው ፋይናንስ የምዕተ ዓመቱን ግቦች ከመድረስ አንፂር የተቃኘ አለመሆኑን ግንዛቤ በመወሰዱ ከዚህ አንፂር ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ ለፕሮግራሞቹ የሚያስፈልገውን በጀት በማዘጋጀት የረጅም ጊዜ ዕይታ ያለው አገር በቀል የምዕተ ዓመቱ ግቦች አመልካች የኢንቨስትመንት ዕቅድ (Ten-Year Investment Plan) የማዘጋጀት አስፈላጊነት ወቅታዊ ስለመሆኑ ግንዛቤ መወሰዱ ነው።

በዚሁ መሠረት ሁሉንም የድህነት ተኮር ዘርፎችና መድበለ ዘርፎች ያካተተ የምዕተ ዓመቱ የሪሶርስ ፍላጐት የዳሰሳ ጥናት (MDGs Needs Assessment Sectoral Study) ለማካሄድ አስፈላጊው ዝግጅት ከተደረገ በኋላ በሐምሌ 1996 የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የሪሶርስ ፍላጐት የዳሰሳ የጥናት ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ። ይህ ጥናት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስተባባሪነትና በልማት አጋሮች ትብብር (በተለይም በተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት) በመጀመሪያ የየዘርፎች የዳሰሳ ጥናት ከነሐሴ 1996 እስከ ጥቅምት 1997 የተካሄደ ሲሆን የየዘርፉን የዳሰሳ ጥናት የሚያጠቃልልና የሚያቅፍ የ10 ዓመት የኢንቨስትመንት ዕቅድ (MDGs Needs Assessment Synthesis Study Report) ዝግጅት ከታህሣሥ 1997 እስከ ሐምሌ 1997 ተካሂዶ ሪፖርቱ በመጨረሻ መልኩ እንዲወጣ ተደርጓል። በ1997 በጀት ዓመት የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ማጠናቀቂያ ጊዜ ስለነበር በዚህ ቋት የተተካው የ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ ከአመልካች ዕቅዱ ተጨልፎ የወጣ ነው። ከዚህም በተጓዳኝ ዕቅዱን የበለጠ የተሟላ ለማድረግ ከሰኔ 1997 እስከ መስከረም 1998 በክልል ዋና ከተሞችና በፈዴራል ደረጃ አዲስ አበባ በአፍሪካ የኢኮኖሚክ ኮሚሽን አዳራሽ በመጀመሪያው የዘልድቅ ፕሮግራም አፈጻጸም ማዕቀፍ ላይ ተመስርቶ የተካሄደው ምክክር ጭምቅ ውጤቶች እንደተጨማሪ ግብዓቶች ተወስደው የ5 ዓመቱን የልማት ዕቅድ ሰነድ ለማዳበር ጥቅም ላይ ውለዋል።

በመጨረሻም የ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ /1998 - 2002/ በየደረጃው ውይይት ከተካሄደበት በኋላ በግንቦት 1998 በተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። ይህ እቅድ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፂር የተቃኘው የምዕተ ዓመቱ አመልካች የልማት ዕቅድ /1998 - 2007/

የመጀመሪያው የ5 ዓመት ምዕራፍ ተደርጐ ተወስዷል። የሁለተኛው ምዕራፍ ከ2003 - 2007 ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ይሆናል። ከይዘት አንፂር የ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ የመጀመሪያው የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ኘሮግራም ውስጥ የተመለከቱ ኘሮግራሞች ቀጣይ ሆኖ ከዚህ በፊት ያልታቀፉ ዘርፎችን በተጨማሪ /ቱሪዝም የከተሞች ልማትና ኮንስትራክሽን የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት ስነ ሕዝብና ልማት . . . ወዘተ/ የሚያካትት በመሆኑ ሁሉን አቀፍ አገራዊ የልማት ዕቅድ ተደርጐ ተወስዷል።

የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችና (Goals) **የግብ ስኬት አመልካቾች** (Targets) **እንዲሁም አጋዥ አመልካቾች** (Indicators) **ዝርዝር በዕዝል 1 ተመልክቷል።**

3. የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች፣ የኢትዮጵያ የእስካሁኑ ጉዞና የወደፊቱ አዝማሚያ

3.1 በእስካሁኑ አፈፃፀም የተገኙ ውጤቶች

በዚህ ክፍል በኢትዮጵያ የእስካሁኑን የምዕተ ዓመቱን ጉዞ በ4 ዋና ዋና የፖሊሲ ግቦች በመከፋፈል ለማመልከት እሞክራለሁ። ይህ አቀራረብ አገራዊውን የፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ የተከተለ እንጂ የምዕተ ዓመቱን ግቦች አወቃቀር የተከተለ አይደለም። ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 3.1. እንደተመለከተው በምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦችና በዘርፉ ከተመረጡ አጋዛዊ አመልካች (Indicators) **አንፂር አፈፃፀሙን ለማመልከት ተመኩሯል።** ይህ ግን ሙሉ ስዕሉን የሚሰጥ ባለመሆኑ ሌሎች ተጓዳኝ አመልካቾችን ጭምር በመጥቀስ ለግቦቹ አፈፃፀም የሚኖረውን እንደምታና የወደፊር አዝማሚያ ለመጠቆም እሞክራለሁ። ቀደም ብሎ እንደተመለከተው የምዕተ ዓመቱ ግቦች ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፂር በአጠቃላይ በመንግስት ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ኘሮግራሞች ማዕቀፍ ውስጥ ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ መታየት ስለሚገባቸው የአፈፃፀም ግምገማውም ይህንኑ አገራዊ የፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ የተከተለ መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

በዚሁ መሠረት በዚህ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከመተግበር አንፂር አፈጻጸሙ አገራዊ የልማት ፖሊሲ ማዕቀፉን ባገናዘበ መልኩ በ4 ዋና ዋና ክፍሎች ይቀርባል። እነሱም፡-

ሀ/ ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን መቀነስና ብሎም የማስወገድ ዓላማ/ግብ በተመለከተ፣
ለ) የሰው ሀብት ልማትን (Enhanced Human Development) ዓላማ/ግብን በተመለከተ፣
ሐ) የከባቢያዊ ሁኔታንና የተፈጥሮ ሀብት መሠረትን በመጠበቅ ቀጣይ ዕድገትና ልማትን የማፋጠን ዓላማ/ግብ በተመለከተ፣
መ) የውጭ ኢኮኖሚ ልማት ትብብርን የማጐልበት ዓላማ/ግብ በተመለከተ የሚሉት ናቸው።

በእያንዳንዱ ዓላማዎች ሥር የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች አወቃቀር በተከተለ አኩሀን የኢትዮጵያ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ጋር በተጣጣመ መልኩ የግብ ስኬት **አመልካቾቹ** (Targets) አሃዛዊ **አመልካቾቹ** (Indicators)' ቅደመ ዘልድቅኘ ዘመን የሚገኝበት ደረጃና በዘልድቅኘ የመጨረሻ ዓመት የተደረሰበት የ5 ዓመቱ የልምድ እቅድ ግብ እና የምዓተ ዓመቱ የመጨረሻ ዓመት የተደረሰበት የ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ግብ እና በምዕተ ዓመቱ የመጨረሻ ዓመት የሚደረስበትን የሚያሳየው በዕዝል 2

ተመልክቷል። በሠንጠረዥ 3.1. የተመለከተው ከዚህ ዝርዝር ውስጥ የተመረጡ አመልካቾች ላይ የተመረኮዘ ነው።

ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው የመጀመሪያው የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራምና በዚሁ ቋት የተተካው የ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባው የ10 ዓመት ጠቋሚ የልማት ዕቅድ (Ethiopia's Ten Year MDGs Plan) ማዳረሻ ምዕራፎች ናቸው። ከምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችና የግብ ስኬት አመልካቾች የሚደረገውን ግስጋሴ ለመገምገም ወጥነት ያለው የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቷል። የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች በኢትዮጵያ በመተግበር ረገድ የአፈጻጸም ውጤቶቹ መነሻ ይኸው የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ነው።

ሀ) ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን መቀነስና ብሎም የማስወገድ ዓላማን/ግብን በተመለከተ

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ድሃ አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገትን ወደ ልማትና ድህነት ቅነሳ መተርጐም ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው የሥራ ስምሪትን ደረጃ በደረጃ ከግብርና ውጭ ባሉ ዘርፎች ማስፋፋት መቻል ነው። በዚህ ረገድ እንደ መንደርደሪያ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ማለትም የዕድገት ምንጮችንና እነዚህ ዘርፎች አሁን ያሉበትን የሥራ ስምሪት የማስፋፋት አቅም በአጭሩ ማመልከት ያስፈልጋል።

በመሠረቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የተንሰራፋውን ባለብዙ ፈርጅ ድህነት ለመቋቋም ወሳኙ ጉዳይ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ድሃ ተኮር (pro-poor) የኢኮኖሚ ዕድገት ማስፈን መሆኑ ነው። በተለምዶ
የኢኮኖሚ ዕድገት አመልካች ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) በመሆኑና ይህ አመልካች ደግሞ የገቢ ሥርጭትን (Income Distribution) የማያሣይ በመሆኑ በራሱ በቂ ያለመሆኑ ይታመናል። ምክንያቱም የዕድገቱ አይነትና በዕድገቱ ተጠቃሚ የሆነው ህብረተሰብ እንዲሁም የዕድገቱ ሥርጭት (Distuibution of income) ለድህነት ቅነሳ ከዕድገቱ ከራሱ ባልተናነሰ ከፍተኛ ሚና አላቸውና።

በብዙዎች የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ ታዳጊ አገሮች ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት በተመዘገበባቸው ዓመታት ድህነት ተባብሶ ታይቷል። ለምሳሌ እ.አ.አ ከ1990ዎቹ አጋማሽ ወዲህ እስከ 2005 ባለው ጊዜ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ባስመዘገቡ የነዳጅ ማዕድን አምራች የአፍሪካ አገሮች በአብዛኞቹ ድህነት ተባብሶ ታይቷል (Africa Development Indicators 2006)። ለዚህም ዋናው ምክንያት በእነዚህ ዘርፎች የተሰማራው የሰው ኃይል ውስን በመሆኑና ሥራውም በከፍተኛ ማሽነሪዎች የሚታገዝ በመሆኑ በአገሮቹ ውስጥ የሚገኘውን ሰፊ የሰው ጉልበት በመጠቀም የሥራ ስምሪትን ለማስፋፋት ባለመቻሉ ነው። ይህም የሚያሳያው የኢኮኖሚ ዕድገቱ ድሃ ተኮር (Pro-poor) ያለመሆኑን ነው። የአንድ አገር የሥራ ስምሪት ፖሊሲ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የሰው ጉልበት በሙሉ አቅም መጠቀምና ከዚህም ገቢ መፍጠር የሚያስችል መሆን ስለሚኖርበት ነው።

ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂው (ADLI) የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙ አንዱ ምሰሶ (Pillar) ነው። ይህ ስትራቴጂ በበርካታ አጋጣሚዎች ይተቻል። በሂደት ራሱን እየለወጠ

(evolution) የወሰዳቸው ማስተካከያዎች እንኳን እስከአሁን ግንዛቤ ያገኙ አይመስሉም። **ለምሣሌ** አንዱ የስትራቴጂው ክፍተት የአቅርቦት ጐኑ ላይ በማተኮሩ የገበያ ሥርዓቱን በአግባቡ አለማየቱ ነበር። ከዚህ አንፂር በተወሰነ ደረጃ ገበሬው የምርቱ ተጠቃሚ ያልሆነበት ሁኔታ እንደነበር ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። ምርት ሲጨምርም ምርት ሲወድቅም ገበሬው የተጐዳበት ሁኔታ ታይቷል። አሁን ዳግሞ ስትራቴጂው በአነስተኛ ገበሬ የሚካሄድ የስፔሻላይዜሽንና የኮመርሻላይዜሽን እንቅስቃሴዎችን በማቀፉ ለገበሬዎች ገቢ ማደግና ለአጠቃላይ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ለውጥ መሠረት የሚጥል እንዲሆን በማድረግ ተቃኝቷል። ይህም በ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ ውስጥ ተንፀባርቋል።

በመሰረቱ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ከእጅ ወደ አፍ ሕይወት የሚመሩና ዝቅተኛ የንብረት መሠረት ባለው አነስተኛ ገበሬ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ያላቸው አገሮች ኢንዱስትሪን በፈጣን ሁኔታ ለማስፋፋትና ኢኮኖሚውን ለማሣደግ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በአይነትም ሆነ በጥራት ቀድሞ ማደግና ለኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑትን የምርት ግብዓቶችና የሕብረተሰቡን የምግብ ፍጆታ ማሟላት ይኖርበታል። ከዚህም በላይ የግብርናው ዘርፍ የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ መሠረታዊ ምርቶችም ምንጭ በመሆኑና (90 በመቶ ያህሉ የወጪ ንግድ ገቢ የግብርና ውጤቶች ላይ የተመሰረተ በመሆኑ) ብሎም ልማትን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገው ዋና የሰው ጉልበት (80 በመቶ) የተሰማራበት ዘርፍ ነው። ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ግማሽ ያህሉን (46 በመቶ በ1998) ይሸፍናል። ለዚሁ ነው ስትራቴጂው ግብርናንና ገጠር ልማትን መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ነው የሚባለው።

የግሉ ዘርፍ ለዕድገትና ለሥራ ፈጠራ የጐላ ድርሻ ያለው መሆኑን ሁሉም ያምናል። ግን ብዙ ጊዜ ስለግሉ ዘርፍ ሲነገር አንድ የሚረሣ ወሳኝ ጉዳይ አለ። ይኸውም የግል ዘርፍ ማለት ከመንግሥት ውጭ ባሉ አካላት (ሕጋዊ) የሚመራ ዘመናዊ የሥራ ተቋም (Business Entity) ብቻ ተደርጐ መወሰዱ ነው። እዚህ ላይ ግን በውል ልብ ሊባል የሚገባው አነስተኛው ገበሬ የግሉ ዘርፍ አካል መሆኑንና ዘመናዊው የግል ዘርፍ ይህን አነስተኛ አቅም ያለው ሰፊ የልማት ኃይል ጐትቶ ሊያዋጣው እንደሚገባ ግንዛቤ ያለማግኘቱ ነው። የእነዚህ አካላት መደጋገፍና መስተጋብር ነው የኢኮኖሚ ዕድገትና አጠቃላይ የሶሽዮ ኢኮኖሚ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የወደፊቱን ቀጣይ ልማት ለማፋጠን ይህ ጉዳይ በቂ ግንዛቤ ማግኘት የሚገባው ይመስለኛል።

የዘመናዊ ዕቃ አምራች ዘርፉ (ኢንዱስትሪ) የግብርና ምርቶችን ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በመጠቀም የፍጆታ ሸቀጦችን፣ ለግብዓት የሚውሉ አነስተኛ የግንባታ ዕቃዎችን እና መሣሪያዎችን እንዲሁም የካፒታል ዕቃዎችን ያመርታል። በኢትዮጵያ አሁን ባለበት ደረጃ የኢንዱስትሪ መሠረቱ በጣም ጠባብ ነው። ኢንዱስትሪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ1997 ግምት መሠረት 13 በመቶ ነው። ዘመናዊ የግሉ ዘርፍ ሚና በኢንዱስትሪ ውስጥ ያለው ድርሻ እያደገ ቢመጣም አሁንም ገና መስፋፋት ይኖርበታል። **ለምሳሌ** በመካከለኛና ከፍተኛ ፋብሪካዎች ከሚመነጨው ተጨማሪ እሴት ውስጥ የግሉ ዘርፍ ያለው ድርሻ በ1991 ከነበረበት 21 በመቶ በ1997 ወደ 39 በመቶ አድጓል። በሥራ ስምሪትም እንዲሁ በ1991 ከነበረበት 31 በመቶ በ1997 ወደ 50 በመቶ አድጓል። ይህም ሆኖ ግን በአጠቃላይ የመካከለኛና ከፍተኛ ፋብሪካዎች ለሥራ ስምሪት ያላቸው ድርሻ ከጠቅላላው የሥራ ስምሪት ከ4.0 በመቶ አይበልጥም።

በአጠቃላይ የዘመናዊ ዕቃ አምራች ዘርፍ (Industry) ለሥራ ስምሪት ያለው ድርሻ ከ7 በመቶ አይበልጥም።

የአገልግሎት ዘርፉ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 40 በመቶ የሚደርስ ሲሆን ለሥራ ስምሪት ያለው ድርሻ ከ8 በመቶ አይዘልም። በአጠቃላይ የሥራ ስምሪትን በተመለከተ እ.አ.አ. በ2005 የማዕከላዊ ስታትስቲክስ አገራዊ የሥራ ስምሪት ጥናት መሠረት የሠራተኛው ኃይል በተሰማራበት የኢኮኖሚና የማህበራዊ ዘርፍ አንፂር ሲታይ ለሥራ ስምሪት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ግብርናና ተዛማጅ ዘርፍ (80.2 በመቶ) ሲሆን የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ (5 በመቶ)፣ ጅምላ ንግድና የችርቻሮ ንግድ (5.2 በመቶ)፣ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች (2.5 በመቶ)፣ የሕዝብ አስተዳደር መከላከያና የማህበራዊ ደህንነት (1.2 በመቶ)፣ ትምህርት፣ ጤናና የማህበራዊ አገልግሎቶች (2.6 በመቶ) እና ሌሎች (3.4 በመቶ) ነበር። የሥራ ስምሪት ከተለያዩ ቀጣሪ አካላት አንፂር ሲታይ የመንግሥት ሠራተኞች ከጠቅላላው 2.6 በመቶ፣ በራሳቸው የተሰማሩ (Self employeed) 40.9 በመቶ፣ የቤተሰብ አባላት ሆኑ ቀጥታ ክፍያ የማይከፈላቸው ሠራተኞች 50.3 በመቶ በግል ድርጅት ተቀጥረው የሚሠሩ የ2.9 በመቶ እና ሌሎች 3.3 በመቶ ነበር። በአጠቃላይ በዚህ ጥናት መሠረት በክፍያ የሚሠሩ (Total paid employees) ከጠቅላላ የሠራተኛ ኃይል ውስጥ 8 በመቶ ድርሻ አላቸው።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠንና ግብርናም ለተፈጥሮ ጥገኝነት (በዝናብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ) የተጋለጠ በመሆኑ ዕድገቱ የሚዋዥቅ ነበር። በመሆኑም ቀጣይና ተከታታይነት ያለው ዕድገት ለማስመዝገብ የግብርናውን ዘርፍ ደረጃ በደረጃ ከተፈጥሮ ጥገኝነት የማላቀቁ ተግባር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው። ይህም ውሃን በአግባቡ በመጠቀም ገበሬውን ከዝናብ ጥገኝነት ደረጃ በደረጃ ማላቀቅ መቻል ነው። ለዚህም ነው መስኖን የማስፋፋትና ውሃን የማቆር እንቅስቃሴ በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው።

በአጠቃላይ ያለፉት ሦስት ዓመታት (1996-1998) ሲታይ አማካይ ዕድገቱ ከ10 በመቶ በላይ በመሆኑ የኢኮኖሚው አፈጻጸም ተከታታይነት ያለው ሆኖ ወደ አዲስ የዕድገት ደረጃ መሸጋገሩን የሚጠቁም ነው። ይህ ቀጣይነት እንዲኖረው ማስቻል ዋናው ፈታኝ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ ሁኔታ የምዕተ ዓመቱን ግቦች ለመድረስ የሚያስፈልገው ዝቅተኛው አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት መጣኔ 7 በመቶ ነው።
ስለዕድገት አዝማሚያና የዕድገት ምንጮች ይህን መንደርደሪያ ከሰጠሁ ዘንድ ከድህነት ቅነሣ አኳያ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንሳት እስከአሁን የተመዘገቡ ውጤቶችን ለመጠቆም እሞክራለሁ።

1ኛ/ በኢትዮጵያ እስካሁን የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ድህነትን ከመቀነስ አንፂር ምን አስተዋጽኦ አድርጓል?

2ኛ/ ከዕድገቱ በአንፂራዊ መልኩ ማን ተጠቀመ? ዕድገቱ ድሃ ተኮር (pro-poor) እና መሠረቱ ሰፊ ነበርን?

3ኛ/ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የዕድገትና የድህነት ቅነሳ ቁርኝት ምን መልክ አለው?

የመጀመሪያውን ነጥብ አስመልክቶ በሠንጠረዥ 3.1 እንደተመለከተው በ1988 ለመጀመሪያ ጊዜ በአገሪቱ ታሪክ በተካሄደው አገራዊ የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ የመስክ የናሙና ጥናት መሠረት ከድህነት መስመር በታች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት 45.5 በመቶ የነበረ ሲሆን በ1992 ለሁለተኛ ጊዜ በተካሄደው ተመሳሳይ አገራዊ የመስክ የናሙና ጥናት መሠረት ወደ 44.2 በመቶ ዝቅ ብሎ ነበር። ለሦስተኛ ጊዜ በ1997 በተካሄደው አገራዊ የመስክ የናሙና ጥናት መሠረት ደግሞ ወደ 38.7 በመቶ ወርዷል።

ይህ መጣኔ በገጠርና በከተማ ተለይቶ ሲታይ በገጠር በ1988 47.5 በመቶ የነበረው በ1992 ወደ 45.4 በመቶ በ1997 ወደ 39.3 በመቶ ወርዷል። በከተማ ከድህነት መስመር በታች የሚኖረው ሕዝብ ከጠቅላላው ሕዝብ በ1988 ከነበረበት 33.2 በመቶ በ1992 ወደ 37 በመቶ የጨመረ ሲሆን በ1997 እምብዛም ለውጥ ሳያሳይ 35.1 በመቶ ሆኗል። በአጠቃላይ መረጃዎቹ የሚያሳዩት ከ1988 እስከ 1997 ባለው 10 ዓመት ውስጥ ድህነት በገጠር በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰ ሲሆን (ከ47.5 በመቶ ወደ 39.3 በመቶ) በከተማ ግን የመጨመር አዝማሚያ ማሳየቱን ነው (ከ33 በመቶ ወደ 35 በመቶ)። በሌላ መልኩ ከአንፂራዊ አመልካች (Relative Indicator) በተጨማሪ ከድህነት መስመር በታች የሚገኘውን ሕዝብ ቁጥር (Absolute Number) አዝማሚያ ስንመለከት በ1992 ከነበረበት 28,063,909 በ1997 ወደ 27,523,414 ዝቅ ብሏል። ይህም የ1997 ከ1992 ጋር ሲነፂፀር የ2 በመቶ ቅናሽ ማለት ነው።

በድህነት ጥልቀት አመልካች አንፂር በገጠር በ1988 ከነበረበት 13.4 በመቶ በ1992 ወደ 12.2 በመቶ እንዲሁም በ1997 ወደ 8.5 በመቶ ወርዷል። ይህም ማለት በ1988 ከድህነት ወለል በታች የሚገኝን አንድ ሰው በ1988 ወደ ድህነት መስመሩ ድረስ ለማምጣት የነፍስ ወከፍ የፍጆታ ወጪውን በ13.4 በመቶ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል። በዚሁ መሠረት እንዲሁ በ1992 በ12.2 በመቶ ከፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የሚያሳይ ሲሆን በ1997 ደግሞ በ8.5 በመቶ ከፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያሳያል። ይህም መንግሥት አቅሙ ቢኖረውና ሁሉንም ከድህነት መስመር በታች ያለ የገጠር ሕዝብ ወደ ድህነት መስመሩ ለማስጠጋት የሚያስፈልገውን ጠቅላላ የፋይናንስ መጠን ለመገመት ያስችላል። ይህንኑ ሁኔታ በከተማ ስንመለከት በአንፂራዊ መልኩ የድህነት ጥልቀት ሊቀንስ ያለመቻሉን ነው። በ1988 ከነበረበት 9.9 በመቶ በ1992 ወደ 10.1 በመቶ በ1997 ደግሞ ወደ 8 በመቶ ዝቅ ብሏል። በአማካይ ግን የጐላ ቅናሽ አልታየም። ይህም ማለት በአማካይ ለአንድ ከድህነት መስመር በታች ለሚገኝ ሰው የነፍስ ወከፍ የፍጆታ ወጪ ከድህነት መስመሩ ለማስጠጋት የሚያስፈልገው የፋይናንስ መጠን በነፍስ ወከፍ ከገጠር ይልቅ በከተማ ከፍተኛ መሆኑን ነው።

ሠንጠረዥ 3.1፡ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የእስካሁኑ አፈጻጸምና የወደፊቱ አዝማሚያ

ተ.ቁ	የፖሊሲ ዓላማ/ግብ	አጋዛዊ አመልካች (Indicators)	ቅድመ-ዘልድቅፕ የነበረበት	በዘልድቅፕ የመጨረሻ ዓመት የተደረሰበት (1997)	የ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ግብ (2002)	የምዕተ ዓመቱ ግብ (2007)
I	ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን መቀነስ ብሎም ማስወገድ	1.1 ከድህነት መስመር በታች የሚገኘው ሕዝብ (በመቶኛ)	44.2 (1992)	38.7 (1997)	29	15
		1.2 ከአገራዊው የምግብ የድህነት መስመር በታች የሚኖረው ሕዝብ (በመቶኛ)	42(1992)	38	28	13
		1.3 ከዕድሜያቸው ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ቁመት የላቸው ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት የሚያንሱ ሕፃናት (በመቶኛ)	57(1992)	47	ግብ አልተጣለም	ግብ አልተጣለም
		1.4 ከዕድሜያቸው ጋር የማይመጣጠን ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት የሚያንሱ ህፃናት (በመቶኛ)	45(1992)	37	ግብ አልተጣለም	ግብ አልተጣለም
II	የሰው ሀብት ልማትን ማፋጠን (Enhanced Human Development) 2.1 የትምህርት አገልግሎትን ማስፋፋት	2.1.1 የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ	17.2(1986)	68	81	100.0
		2.1.2 ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ዕድሜያቸው ከ15-24 የሚገኝ (%)	48 (1987)	54.4	ግብ አልተጣለም	ግብ አልተጣለም
		2.1.3 የአንደኛ ደረጃ የጾታዊ ተሳትፎ ልዩነት ጥመርታ	--	0.87	0.97	1.00
	2.2 የጤና አገልግሎት ማሻሻል	2.2.1 የህፃናት ሞት ከ1000 ህፃናት(%)	167 (1993)	140 (1996)	85	46
		2.2.2 የእናቶች ሞት መጣኔ ከ100,000	---	871 (1996)	600	218

ተ.ቁ	የፖሊሲ ዓላማ/ግብ	አጋዛዊ አመልካች (Indicators)	ቅድመ-ዘልድቅፕ የነበረበት	በዘልድቅፕ የመጨረሻ ዓመት የተደረሰበት (1997)	የ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ግብ (2002)	የምዕተ ዓመቱ ግብ (2007)
	2.3 ኤች.አይ.ቪ. ኤድስና ሌሎች ገዳይ በሽታዎችን መዋጋት	2.3.1 አጠቃላይ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭት መጣኔ (%)	7.3 (1993)	4.4 (1997)	4.4	4.4
		2.3.2 ለወባ በተጋለጡ አካባቢዎች 2 አጉበር የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ከጠቅላላው በመቶኛ (%)	---	1	100	100
		2.3.3 የሣንባ ነቀርሣን የመፈወስ ብቃት መጣኔ (%)	--	15	60	ግብ አልተጣለም
	2.4 የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻል	2.4.1 የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በገጠር በ1.5 ኪ.ሜ. ክልል ውስጥ (%)	24 (1993)	35 (1997)	80	100
		2.4.2 የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በከተማ በ0.5 ኪ.ሜ. ክልል ውስጥ (%)	72 (1993)	80 (1997)	93	100
	የአካባቢያዊ ሁኔታንና የተፈጥሮ ሀብት መሠረትን በአግባቡ በመንከባከብ ቀጣይ ዕድገትንና ልማትን ማረጋገጥ	3.1.1 የተፈጥሮ ደን ሽፋን (%)	--	3.6	9.0	ግብ አልተጣለም
	3.1 የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅና መንከባከብ	3.1.1 ደረቅ የኃይል ምንጮችን የሚጠቀመው ሕዝብ ብዛት በመቶኛ (%)	--	99.5	ግብ አልተጣለም	»
	3.2 በከተሞች መሠረታዊ አገልግሎቶችንና መጠለያ ማቅረብ	3.2.1 መጠለያ መሠረታዊ አገልግሎት ማግኘት የቻሉ ቤተሰቦች ሽፋን (%)	---	30	65	»
		3.2.2 የተጐዱና የተጨናነቁ አካባቢዎችን መቀነስ	--	70	35	»

ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን ከመቀነስ ብሎም ማስወገድ ዓላማ አንፂር ሁለተኛው የምዕተ ዓመቱ የግብ ስኬት አመልካች (Target) በረሃብ አለንጋ የሚገረፈውን ሕዝብ ብዛት በግማሽ መቀነስ ነው። ከዚህ አኳያ በሦስጠረኛ 3.1 እንደተመለከተው በኢትዮጵያ ከአገራዊው የምግብ ድህነት መስመር በታች የሚገኘውን ሕዝብ በ1992 ከነበረበት 42 በመቶ በ1997 ወደ 38 በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል። ከዕድሜያቸው ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ቁመት ያላቸውን ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት በ1992 መጨረሻ ከነበረበት 57 በመቶ ወደ 47 በመቶ መቀነስ ተችሏል።

የግብርናው ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ዋነኛ ምንጭ እንደመሆኑ መጠን የተመዘገበው ዕድገት ለድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ ማድረጉን መገንዘብ አያዳግትም። ሆኖም በግብርናውና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ካለው የላላ ቁርኝት አኳያና ወደ ከተማ ከሚደረገው ፍልሰት አንፂር የከተማው ድህነት ጨምሮ መታየቱ የኢንዱስትሪውና የአገልግሎት ዘርፉ አብዛኛውን የሥራ ኃይል ለማቀፍ መሠረቱ ጠባብ መሆኑን ያሳያል። ይህም በቀጣይ የመንግሥትን ልዩ ትኩረት የሚሻ ዋና ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

በገጠር ለተገኘው ውጤት መነሻዎች ምንድን ናቸው? ዕድገቱስ ድሃ ተኮር (pro-poor) ነበር ወይ?

ስፋት ያላቸውና ፈርጀ ብዙ የሆኑ የድህነት ተኮር ፕሮግራሞች በገጠሪቱ ኢትዮጵያ መተግበራቸው አንዱ ሲሆን ከዚህም አንፂር የሚጠቀሰው አንዱ አምራቹን ገበሬ ከዋና ዋና ክረምት ከበጋ መንገዶች ለማገናኘት የሚደረገው ጥረት ነው። ይህም ገበሬው የእርሻ ምርቱን በተሻለ የገበያ ዋጋ መሸጥ ያስችለዋል። ገበያ መር የግብርና ልማት ሥራን ለማስፋፋት የተደረገው የኤክስቴንሽን ፕሮግራም፣ የገጠር መሠረተ ልማቶች መስፋፋት (መንገድ፣ መስኖ ልማት፣ ቴሌኮም፣ የኃይል ምንጭ፣... ወዘተ)፣ የገጠር የአነስተኛ ብድር መስፋፋት፣ የምግብ ዋስትናና በቅርቡ ተጀምረው በመተግበር ላይ ያሉት በምርታማ እንቅስቃሴ ላይ ያተኮሩ የሴፍቲ ኔት ፕሮግራሞች አፈጻጸም በገጠር ለተመዘገበው የድህነት ቅነሳ የሚኖራቸው አስተዋጽኦ የጐላ እንደሚሆን ይገመታል።

በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በሚደረገው የተቀናጀ እንቅስቃሴ ከድህነት መስመር በታች የሚኖረውን ሕዝብ በ1997 መጨረሻ ካለበት 38.7 በመቶ በ2002 መጨረሻ ወደ 29 በመቶ ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን በምዕተ ዓመቱ ማብቂያ ማለትም በ2007 መጨረሻ ደግሞ ወደ 15 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ከምግብ ድህነት መስመር በታች የሚገኘውን ሕዝብም እንደዚሁ በ1997 መጨረሻ ከተደረሰበት 38 በመቶ በልማት ዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ወደ 28 በመቶ እና በ2007 መጨረሻ ደግሞ 13 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

ለ) የሰው ሀብት ልማትን የማፋጠን (Enhanced Human Development) ዓላማ/ግብን በተመለከተ

ይህ ዓለማ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማትን ለማፋጠን ዋነኛ የመሠረት ድንጋይ ነው። ዓለማው ሰፋ ባለ መልኩ ሲታይ ትምህርትን፣ ጤናን፣ የፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ የሚያመለክት ነው። በምዕተ ዓመቱ ግቦች ላይ እንደተመለከተው ይህ ዓላማ ከግብ 2 እስከ ግብ 6 ያሉትን 5 ግቦች የሚያቅፍ ነው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ስለትምህርት ስለጤናና የፆታ እኩልነት ስንናገር ሁሉን አቀፍ እና ዙሪያ መለስ (Holistic) በሆነ መልኩ ነው። ትምህርት ሲባል በሁሉም ደረጃ ያለውን ትምህርት ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ማስፋፋት ማለታችን እንጂ በምዕተ ዓመቱ ግቦች ላይ እንደተመለከተው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ብቻ የሚያተኩር አይደለም። ለሌሎችም የማህበራዊ ዘርፎች አቀራረቡ (Approach) ተመሳሳይ ነው።

ለ.1) ትምህርት

በትምህርት ዘርፍ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ተሳትፎን በማሳደግ ረገድ የሁለተኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት ፕሮግራም (1995-97) ከፍተኛ እመርታ የታየበት ውጤት አስመዝግቧል። በዚሁ መሠረት የ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዛት በ1994 ከነበረበት 8.1 ሚሊዮን በ1997 ወደ 11.4 ሚሊዮን ከፍ ያለ ሲሆን ይህም ጥቅል ተሳትፎውን ከ61.6 በመቶ ወደ 79.8 በመቶ (ሴት 70.9 በመቶ ወንድ 87.3 በመቶ) ሊያሳድገው ችሏል። የ1ኛ ደረጃ (1-8) የሴት ተማሪዎች ንጥር ተሳትፎ አንፂር ሲታይ ንጥር ተሳትፎ በ1994 ከነበረበት 52.2 በመቶ ወደ 68.0 በመቶ አድጓል። እዚህ ላይ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ወደኋላ መለስ ብለን የ1ኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ በ1990ዎች መጀመሪያ ዓመታት ላይ ከ20 በመቶ የማይበልጥ እንደነበር መጠቆም ያሻል። ከዚህ አኳያ ሲታይ ንጥር ተሳትፎ በራሱ በ4 እጥፍ ማደጉን ማየት ይቻላል። የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መስፋፋታቸው (80 በመቶ በገጠር)፣ በሴቶች ትምህርት አስፈላጊነት የሕብረተሰቡ ግንዛቤ እያደገ መምጣት እንዲሁም የመንገድና ሌሎች መሠረተ ልማቶች መስፋፋት ለትምህርት ተሳትፎው ማደግ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይገመታል።

ይህ የተጠቀሰው የተሳትፎ መጣኔ አገራዊ አማካይ በመሆኑ በክልሎች መካከል ያለውን ልዩነት ሊሸፍነው ይችላል። በአዳጊ ክልሎች ሲታይ በተለይ በአፋርና በሶማሌ ክልል የተሳትፎው መጣኔ ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል። ይህንንም ዝቅተኛ የክልሎች የተሳትፎ መጣኔ ለማሻሻል መንግሥት በእነዚህ ሁለት ክልሎችና በሌሎችም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ማለትም በደቡብ ኦሞ፣ ኦሮሚያ፣ ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ የተለያየ ፕሮግራም በመተግበር ላይ ነው። **ለምሳሌ**፤ በአፋር ክልል የተንቀሳቃሽ ትምህርት ሥርዓት ከመደበኛው ጐን ለጐን በመተግበር ላይ ይገኛል።

የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም የማዳረሱ ግብ በኢትዮጵያ ከምዕተ ዓመቱ ግቦች የጊዜ ሰሌዳ ቀድሞ እንደሚደረስበት ይጠበቃል። ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 3.1 እንደተመለከተው የ1ኛ ደረጃ ጥቅል ተሳትፎን የማሟላት ግብ (100 በመቶ) በ5 ዓመቱ ልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት እንደሚደርስ ግብ ተጥሏል። በንጥር ተሳትፎ ከ80 በመቶ በላይ እንደሚደርስ ግብ ተጥሏል። የፆታዊ ልዩነትን ከማጥበብና ብሎም ከማስወገድ አኳያ የ1ኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል የፆታዊ ተሳትፎ ልዩነት መጣኔ በ1994 ከነበረበት 0.45 በ1997 መጨረሻ 0.87 የደረሰ ሲሆን በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን የመጨረሻ ዓመት 0.97 ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

የሁለተኛ ደረጃ (9-10) ትምህርትን በተመለከተ ከተሳትፎ አኳያ እንደ የ1ኛ ደረጃው ሁሉ መሻሻል ታይቷል። በ1994 512,327 የነበረው የሁለተኛ ደረጃ ተሳትፎ በ1997 መጨረሻ ወደ 860,645 አድጓል። በዚሁ መሠረት በ1997 ጥቅል ተሳትፎ 29.2 በመቶ የደረሰ ሲሆን የሴቶች 21.6 የወንዶች 36.6 በመቶ ነው። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት በ1994 መጨረሻ ከነበረበት 455 ወደ 707 አድጓል። በዕቅዱ ዘመን የመጨረሻ ዓመት የሁለተኛ ደረጃ 1ኛ ሳይክል (9-10) ጥቅል ተሳትፎ አሁን ካለበት (1997) 29.2 በመቶ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ 39 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

የመሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን (11-12) በተመለከተ ይህ አሠራር ተግባራዊ መደረግ በጀመረበት በ1994 የተማሪው ቁጥር 79,155 የነበረ ሲሆን በ1997 መጨረሻ 94,660 የደረሰ ሲሆን የመሰናዶ ት/ቤቶች ቁጥርም 371 ደርሷል። የመሰናዶ ትምህርት አጠቃላይ የቅበላ አቅም (ለ11ኛ ክፍል) በ1997 መጨረሻ ከነበረበት 45,671 በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ 212,807 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ይህም የሴቶችን ቅበላ በዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት 42 በመቶ ያደርሰዋል።

የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናን በተመለከተ ይህ ዘርፍ ከ1993 ጀምሮ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በመስፋፋት ላይ ያለ ሲሆን የአሥረኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን ወስደው ወደ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ መግባት የሚያስችል ውጤት ያላገኙትና እንዲሁም በዘርፉ ለመሠልጠን ተሰጥኦና ዝንባሌ ያላቸው ወጣቶች በተለያዩ ሙያዎች ሠልጥነው በራሳቸው ሥራ በመፍጠር ወይም በቅጥር የሚሰማሩበት ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት የሚያስፈልገውን በመካከለኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐት ለማሟላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ይህ የሥልጠና ዘርፍ 10 + 1፣ 10 + 2፣ 10 + 3 በሚል በተለያዩ ደረጃዎች የተዋቀረ ሲሆን ሥልጠናው እስካሁን የሚሰጠው በመንግሥት የማሠልጠኛ ተቋማት በ25 የሙያ መስኮች (trades) እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት በ16 የሙያ መስኮች ላይ ነው። በዚህ ዘርፍ የሥልጠና ተቋማት ብዛት በ1994 ከነበረበት 141 በ1997 ወደ 200 አድጓል። በዚሁ ጊዜ የሠልጣኞች ብዛትም እንደዚሁ ከ38,176 ወደ 105,850 አድጓል። ከዚህ ውስጥ 51 በመቶ የሚሆኑት ሠልጣኞች ሴቶች ነበሩ። በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የዘርፉ (የቴክኒክና ሙያ ትምህርት) የቅበላ አቅም አሁን ካለበት 94,592 በዕቅዱ ዘመን የመጨረሻ ዓመት 312,826 ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

ከፍተኛ ትምህርትን በተመለከተ ዘርፉ ለአገሪቱ ልማት የሚያስፈልገውን በከፍተኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ በመጀመሪያውና በሁለተኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተስፋፋ ያለ ዘርፍ ነው። በዚሁ መሠረት በአገሪቱ ውስጥ 2 ብቻ የነበሩት ዩኒቨርስቲዎች ወደ ስምንት እንዲያድጉ ተደርጓል። የዘርፉ የተማሪ ቅበላ አቅም በ1994 ከነበረበት 18,946 በ1997 መጨረሻ ወደ 36,405 ከፍ ብሏል። በመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚማረው ጠቅላላ የተማሪ ብዛትም በዚሁ ጊዜ ውስጥ ከ87,431 ወደ 172,111 አድጓል። የሴቶች ተሳትፎ 24 በመቶ ደርሷል። ይህ ቁጥር ከፍተኛ ቢመስልም ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት አንፂር ከ0.5 በመቶ ያነሰ ነው። ይህም ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ በእያንዳንዱ 100,000 ሕዝብ ከ500 ያነሰ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ እንደሚኖር ያሳያል። በከፍተኛ ትምህርት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣ ሲሆን በ1996 71 በዲፕሎማ ደረጃ 34 በዲግሪ ደረጃ የሚያሠለጥኑ የግል ዩኒቨርስቲ

ኮሌጃችና ኢንስቲትዩቶች እንደነበሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚሁ ወቅት በእነዚህ የግል ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር 39,125 የነበረ ሲሆን ይህም ከአጠቃላዩ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር 23 በመቶውን ይይዛል።

ለ.2) ጤናና ኤች አይቪ ኤድስ

ጤናን በተመለከተ የተጣሉ የምዕተ ዓመቱ ግቦች የእናቶችንና የሕፃናትን ሞት እንደቅደም ተከተሉ በ2007 በ3/4ኛ እና 2/3ኛ መቀነስ እና ኤች አይ ቪ ኤድስ እና ሌሎች ገዳይ በሽታዎችን (ወባና ሣንባ ነቀርሳ) መዋጋትና እንዳይስፋፉ መቀልበስን የሚመለከቱ ናቸው።

ጤና ለአንድ አገር ዕድገትና ለሕብረተሰቡ ደህንነት መረጋገጥ ቀጥተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። በዚሁ መሠረት የጤና አገልግሎቱን ሽፋን አጠቃቀምና እንዲሁም ጥራቱን ለማሳደግ መንግሥት የረጅም (20 ዓመታት) የጤና ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ነድፎ ሦስተኛውን ምዕራፍ (1998-2002) በመተግበር ላይ ነው። የጤናው ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫ የቅድሚያ መከላከልን መሠረት ያደረገ ሆኖ በከፋ ድህነት ሳቢያ ሊመጡ የሚችሉ እንደ ወባ፣ ሣንባ ነቀርሳ፣ በተደጋጋሚ ሕፃናትን የሚያጠቁ በሽታዎች፣ ኤች አይ ቪ ኤድስንና የአጠቃላይ የእናቶችንና የሕፃናትን የጤና ሁኔታ ማዕከል ያደረገ ስትራቴጂ ተቀርጾ እንቅስቃሴ ተደርጓል።

ከዚህ አንፃር የሚጠቀሰው በመተግበር ላይ የሚገኘው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙ ነው። እስካሁን 3000 ሴት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሠልጥነው መሠረታዊ የሆነ የግልና የአካባቢ ንፅሕና አጠባበቅ፣ ክትባት በመስጠትና ሌሎች መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶችን በቀበሌ ደረጃና ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትም ተስፋፍተዋል። ከዚህ አኳያ ከ1900 በላይ አዲስ የጤና ማዕከላት፣ የጤና ጣቢያዎችና የጤና ኬላዎች ተቋቁመዋል። ይህም ተቋማቱ ከሚገኙበት አካባቢ በ10 ኪ.ሜትር ክልል ርቀት ውስጥ የሚገኘውን ሕብረተሰብ ከ64 በመቶ ወደ 51 በመቶ እንዲቀንስ አድርጓል። እስከ 1997 መጨረሻ ድረስ ከ10,500 በላይ አዲስ ነርሶች፣ ላብራቶሪ ቴክኒሽያን እና የመጀመሪያ ደረጃ ዕርዳታ የሚሰጡ የጤና ባለሙያዎች ሠልጥነዋል።

መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ሽፋን በቅድመ ዘልድቅፕ ዘመን (1993) ከነበረበት 52 በመቶ በ1997 መጨረሻ 70 በመቶ የደረሰ ሲሆን በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት (2002) ሙሉ ሽፋን ለመስጠት (100 በመቶ) ግብ ተጥሏል። የጤና አገልግሎት አጠቃቀም በአሁኑ ጊዜ (1997) መጣኔ 30 በመቶ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዕቅዱ ዘመን የመጨረሻ ዓመት 60 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል። በሠንጠረዥ 3.1 እንደተመለከተው ከ5 ዓመት በታች ያሉ ሕፃናትን ሞት በቅድመ ዘልድቅፕ ዘመን ከነበረበት 167/1000 በ1997 መጨረሻ 140/1000 ማድረስ ተችሏል። በቀጣይም በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት 85/1000 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። የፀረ-ሦስት (DPT3) ክትባት ሽፋን በ1997 70 በመቶ የደረሰ ሲሆን በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ 80 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

የእናቶችን ሞት በመቀነስ ረገድ እንደዚሁ ዘልድቅፕ የመጨረሻ ዓመት ከተደረሰበት 871/100,000 በልማት ዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት 600/100,000 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። በምዕተ ዓመቱ ግቦች የመጨረሻ ዓመት 218/100,000 እንደሚደርስ ያሳያል።

ኤች አይ ቪ ኤድስ ከ1970ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ እየተስፋፋ የመጣና ከፍተኛ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንደምታ ያለው ለፈጣን ዕድገትና ድህነት ቅነሳ ብሎም ማስወገድ የሚደረገውን ጥረት የሚፈታተን አገራዊ ችግር በመሆኑ ችግሩን ለመቅረፍ ብሔራዊ የኤች አይ ቪ ኤድስ ፖሊሲ መውጣቱ፣ የፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ መድኃኒት አጠቃቀምና አቅርቦት ስልት በ1994 መውጣቱ፣ ዘርፈ ብዙ (Multi-sectoral) የኤች አይ ቪ ኤድስ ስትራቴጂካዊ ፕላን በ1997 መውጣቱ የሚጠቀሱ የፖሊሲና የስትራቴጂ እርምጃዎች ናቸው።

ምንም እንኳን የኤች አይ ቪ ኤድስ ሥርጭት በአገራችን ከሌሎች በሽታው በከፍተኛ ደረጃ ካጠቃቸው የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲነፃፀር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በአገሪቱ አጠቃላይ የልማት ጥረት ላይ እያደረገ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። በሠንጠረዥ 3.1 እንደተመለከተው የቫይረሱን ሥርጭት ከመግታት አንፃር በቅድመ ዘልድቅፕ ዘመን ከነበረበት 7.3 በመቶ አገራዊ የሥርጭት መጣኔውን በ1997 መጨረሻ ወደ 4.4 በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል። ይህም በከተማ 12.6 በመቶ በገጠር 2.6 በመቶ ነው።

ለ.3) የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የግል ንፅሕናን በተመለከተ

በምዕተ ዓመቱ ግቦች አወቃቀር (Structure) መሠረት የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የግል ንፅሕና የተመለከቱት በግብ 7 ሥር ነው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ከጤናና ከትምህርት በአጠቃላይም ለሰው ሃብት ልማት ከሚኖረው አስተዋጽኦና ተዛምዶ አኳያ ይታያሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ የዚህ ዘርፍ የእስካሁኑ አፈጻጸምና የወደፊት አዝማሚያም በዚሁ መሠረት ከሰው ሀብት ልማት አኳያ ተዛምዶ ቀርቧል።

መንግሥት የውሃ ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም የረጅም ጊዜ የልማት ስትራቴጀ በመቅረጽ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ከዚህ አንፃር ትኩረት ከተደረገባቸው ተግባራት መካከል አንድ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማስፋፋት ነው። በዚህ ረገድ በሠንጠረዥ 3.1 እንደተመለከተው በገጠሩ አካባቢ የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ1994 ከነበረበት 24 በመቶ በ1997 ወደ 35 በመቶ ዕድገት ያሳየ ሲሆን በከተሞች ደግሞ ከ72 በመቶ ወደ 80 በመቶ ከፍ ብሏል።

ሐ) የከባቢያዊ ሁኔታንና የተፈጥሮ ሀብት መሠረትን በመጠበቅ ቀጣይ ዕድገትና ልማትን የማፋጠን ዓላማን በተመለከተ

በ5 ዓመቱ የልማት ዕድገት ላይ እንደተመለከተው አካባቢው ጉስቁልናን መቀልበስና ድህነትን ማስወገድ እርስ በእርሳቸው የሚደጋገፉ በመሆኑ የኢትዮጵያን የልማት ራዕይ ስኬታማ ለማድረግ የሚቻለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዉና ከባቢያዊ ዘላቂነት ሲጐለብት ነው።

የደን መራቆትና ይህንኑ ተከትሎ የሚመጣው የአፈርና ውሃ ሀብት መራቆት የኢትዮጵያ ዋነኛ የተፈጥሮ ሀብት ችግሮች ናቸው። በዚህ ረገድ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤን በተመለከተ በመጀመሪያው የዘልድቅፕ ዘመን መንግሥት አንድ አብይ አገራዊ ፕሮግራም አከናውኗል። በዚህ ፕሮግራም አማካይነት በፈዴራልና በክልል ደረጃ የአካባቢ ጥበቃ ተቋማት እንዲቋቋሙ መደረጉ፣ አስፈላጊ መመሪያዎች ሕጐችና ደንቦች እንዲወጡ መደረጉ፣ በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ላይ ያተኮሩ ሥልጠናዎችና የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መሰጠቱ የሚጠቀሱ ናቸው።

የደንና የአፈር መራቆትን ለመቋቋምና ለመቀልበስ ከተደረገው ጥረት አኳያ የመሬት መጐሳቆልን ለመመለስና በረሃማነትን ለመከላከል ለድርቅ በተጋለጡ 81 ወረዳዎች ዘላቂነት ያለው የበረሃማ መሬት አያያዝ መርሃ ግብር በመተግበር ላይ ይገኛል። ደንን በሚመለከት የደን አዲት (Forest Accounting) ጥናት በናሙናነት ተካሂዷል። የኢትዮጵያ ጥቅጥቅ የደን ሽፋን 3.6 በመቶ እነደሚሆን ሲገመት በልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት 9 ለመቶ ለማዳረስ ግብ ተጥሏል።

መ) የውጭ የኢኮኖሚ ልማት ትብብርን የማጐልበት ዓላማን በተመለከተ

በኢትዮጵያ የውጭ ፋይናንስን በዕርዳታና በብድር መልክ ማሰባሰብና ለልማት አጋዥ እንዲሆን የሚያስችል እንቅስቃሴ ማድረግ ከተጀመረ ከ50 ዓመታት በላይ ዕድሜ አስቆጥሯል። አገራችን ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የዓለም መንግሥታት ማህበር (League of Nations) እና በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሲቋቋም ድርጅቱን ከመሠረቱት ነፂ አገሮች ውስጥ አንዷ በመሆኗ ከዚህ አንፂርም የዓለማችንን ድሃ አገሮች ለመርዳት በሚል የተለያዩ ዓለም አቀፍ የፋይናንስና የልማት ተቋማት ሲቋቋሙም የመሥራችነት ሚናዋ የጐላ ስለነበረ በመልቲላተራል እና በመንግሥታት ትብብር በኩል ተጠቃሚ ስትሆን ቆይታለች።

በሦስቱም መንግስታት የውጭ ኢኮኖሚ ትብብር ግንኙነት ተቋማዊ ይዘት ነበረው። በአሁኑ ጊዜ የውጭ ፋይናንስ ግኝትን የሚያስተባብረው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሲሆን በሦስቱም ሥርዓቶች በአዋጅ ስልጣን የተሰጣቸው ተቋሞች ይህን ተግባር ሲያስተባብሩ ቆይተዋል። ከ1940ዎቹ አጋማሽ እስከ 1960ዎቹ አጋማሽ የልማት ዕርዳታ በከፍተኛ ደረጃ ያደገበት ዘመን ሲሆን ከ1960ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ የአብዮቱን ፍንዳታ ተከትሎ የደርግ መንግሥት ይከተለው በነበረው ርዕዮተ ዓለምና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሳቢያ የልማት ዕርዳታ በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰበትና በቀጣይ ዓመታት በተወሰነ ደረጃ የመሻሻል አዝማሚያ ቢያሳይም እስከነአካቴውም የቆመበት ጊዜ ነበር። በአብዛኛው በዚህ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ይፈስ የነበረው የውጭ ዕርዳታ ሰብአዊ ዕርዳታ ላይ ያተኮረ ነበር። ይህም እስከ ግንቦት 1983 የደርግ ውድቀት ድረስ ቀጥሎ የሽግግሩ መንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ከግንቦት 1983 በኋላ በተለይም ከ1985 ጀምሮ የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ግጭት እስከተከሰተበት እስከ 1990 ድረስ የውጭ ዕርዳታ በዓይነትም በመጠንም እያደገ

መጥቶ ነበር። ከግጭቱ ጋር ተያይዞ ለኢትዮጵያ ይሰጥ የነበረው የውጭ ዕርዳታ ለሁለት ዓመታት ያህል ቆሟል። ይህም በአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ላይ የፈጠረው ጫና ከፍተኛ ነበር።

ዓለም አቀፋዊ የልማት ትብብርን ከማሳደግ አኳያ 7 የግብ አመልካቾች 16 ያህል አኃዛዊ አመልካቾች ተቀምጠዋል (ዕዝል 1)። ከእነዚህ ውስጥ ከኢትዮጵያ ሁኔታ አንፃር ጠቀሜታ አላቸው ብየ ያመንኩባቸው የታዳጊ አገሮችን የዕዳ ችግር በመሠረታዊ መልኩ መፍታትና የዕዳ ጫናን የመሸከም አቅማቸውን በዘላቂነት እንዲያጐለብቱ ማድረግ የባሕር በር የሌላቸውና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የትንንሽ ደሴት አገሮችን ልዩ ፍላጐት ቀጣይነት ባለው ልማት አማካይነት ማሟላት እና ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታን ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሳደግ የሚሉት ናቸው።

የዕዳ ጫናን ከማቃለል አኳያ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸውን አገሮች ዕዳ ማቃለያ (HIPC Debt Relief) ፕሮግራም አማካይነት ኢትዮጵያ የመሸጋገሪያ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ (Interim PRSP) አዘጋጅታ ለዓለም ባንክና ለዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ቀርቦ በሕዳር 1993 ተቀባይነት በማግኘቱና ይህንኑም ተከትሎ የዋናው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ይፋ ከተደረገ በኋላ በመስከረም 1994 የውሳኔ ነጥብ (Decision point) ላይ መድረስ አስችሏታል። ከዚህ በመቀጠል ዋናውንየድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ማለትም የዘልድቅፕ ፕሮግራሙን በመቅረጽ ትግበራው ከተጀመረና በዚሁ ማዕቀፍ ውስጥ የተቀመጡ ቁልፍ የማሻሻያ እርምጃዎችን (triggers) አሟልታ በመገኘቷ በመጋቢት 1996 የማጠናቀቂያ ከዓለም ባንክ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ከአፍሪካ ልማት ፈንድ እንደቅደም ተከተሉ የ2315፣ የ114 እና የ522 ሚሊዮን ዶላር የዕዳ ሥረዛ በድምሩ የ2951 ሚሊዮን ዶላር የዕዳ ስረዛ ተደርጓል። ይህም በዓለም ባንክ በኩል እ.አ.አ. እስከ 2044፣ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እስከ 2020 በአፍሪካ ልማት ባንክ እስከ 2054 የሚደረግ የመደበኛ ዕዳ ክፍያ ቅናሽን የሚይዝ ነው።

ነጥብ (Completion point) ላይ መድረስ ችላለች። በመጋቢት 1997 በተካሄደው የግሌንኢግልስ ስምንቱ የበለፀጉ አገሮች መሪዎችን የዕዳ ስረዛ ውሳኔን ተከትሎ ኢትዮጵያ የዕዳ ሥረዛው ተጠቃሚ ከሆኑ 18 አገሮች መካከል አንዷ ለመሆን በቅታለች።

በዚሁ መሠረት ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸው አገሮች የዕዳ ማቃለያ ፕሮግራም አማካይነት (HIPC Initiative) ኢትዮጵያ የውሳኔ ነጥብ ስትደርስ የ2174 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የዕዳ ክፍያ ማቃለያ አግኝታለች። ቀጥሎም የፍጻሜ ነጥብ እንደደረሰች 1011.3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የዕዳ ክፍያ ማቃለያ ያገኘች ሲሆን በድምሩ የ3185.5 ሚሊዮን ዶላር የዕዳ ክፍያ ማቃለያ አግኝታለች። ከዚህ አጠቃላይ የዕዳ ክፍያ ማቃለያ ውስጥ የዓለም ባንክ፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ሌሎች ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት 61.3 በመቶውን የሚይዙ ሲሆን የፓሪስ ክለብ መንግሥታት 31.8 በመቶውንና የፓሪስ ክለብ ያልሆኑ 5.0 በመቶውን ይሸፍናሉ። ሌሎችም ቀሪውን ይሸፍናሉ።

ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸው አገሮች የዕዳ ማቃለያ (HIPC) ፕሮግራም አማካየነት የተደረገው ማቃለያ እንደየአበዳሪው በተለያየ መልክና በተለያየ የጊዜ ሰሌዳ የሚፈጸም ሲሆን የዓለም ባንክ የአፍሪካ ልማት

ባንክና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንደየቅደም ተከተሉ እ.አ.አ. እስከ 2019፣ 2021 እና 2009 የሚፈጸም ሆኖ በየጊዜው ከሚደረገው የዕዳ ክፍያ (Debt Service) ነፂ የሚያደርግ ነው። ከሌሎች ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የሚገኘው ደግሞ ከአጠቃላይ የዕዳ ክምችቱ እና በየጊዜው ከሚደረገው መደበኛ የዕዳ ክፍያ ላይ የሚደረግ ቅናሽን (Stock and Flow Reduction) የሚይዝ ነው። ከፓሪስ ክለብ አባል አገሮች የተገኘው የዕዳ ማቃለያ (1014.4 ሚሊዮን ዶላር) ከአጠቃላይ የዕዳ ክምችቱ ላይ የተደረገ የአንድ ጊዜ የዕዳ ቅነሳ ነው።

እ.አ.አ. በ2005 በስኮትላንድ ግሌን ኢግልስ የተካሄደውን የበለፀጉ አገሮች የመሪዎች ስብሰባ ውሳኔ ተከትሎ ለኢትዮጵያ የተደረገውን የዕዳ ስረዛ በተመለከተ በዓለም አቀፍና አህጉራዊ የፋይናንስ ተቋማት በኩል (MDRI) ሌላው የዕዳ ስረዛ የተደረገው በፓሪስ ክለብ አባል አገሮች ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ የዕዳ ክምችቱ (Debt Stock) ላይ በአንድ ጊዜ የተደረገ የዕዳ ስረዛ ነው። በአጠቃላይ ከሁሉም የፓሪስ ክለብ አባል አገሮች የተሰረዘው ዕዳ መጠን 1707.67 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው የሩስያ ፌዴሬሽን (65 በመቶ) ነው። ከሩስያ ፌዴሬሽን ቀጥሎ ጣሊያን 356.6 ሚሊዮን ዶላር (21 በመቶ) በመሰረዝ ሁለተኛ ደረጃን ይዛለች።

ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸው አገሮች የዕዳ ማቃለያ ፕሮግራም (HIPC) አማካይነት በየዓመቱ የሚገኘው ፋይናንስ በዓመታዊ በጀት እየተመደበ ሥራ ላይ ይውላል። በዚሁ መሠረት ይህ ፕሮግራም ከተጀመረበት ከ1994 ጀምሮ የተገኘውና በበጀት እየተመደበ ሥራ ላይ የዋለው ቀጥሎ በሠንጠረዥ 3.2 ቀርቧል።

እ.አ.አ. በዲሴምበር 2006 መጨረሻ የኢትዮጵያ የዕዳ ክምችት 2150 ሚሊዮን ዶላር ነበር። ይህም በ1998 ከተመዘገበው ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ አንፂር ያለው ድርሻ 16.2 በመቶ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ እ.አ.አ. እስከ 2020 ድረስ ባለው ጊዜ ከፍተኛ ተጨማሪ ብድር እስካልወሰደች ድረስ የውጪ ዕዳን በመክፈል አቅሚ (Debt Sustainability) ላይ ተፅዕኖ እንደማያደርግ በቅርቡ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የተካሄደ ጥናት ጠቁሟል። የወጪ ንግድ ማደግ፣ በዝቅተኛ ወለድና ረጅም የመክፈያ ጊዜ ያለው (Grace period) ብድር የምትወስድ መሆኑና የሚገኘው የውጭ ፋይናንስ ዕድገትን ለማፋጠን በማያስችሉ አገራዊ ፕሮግራሞች ላይ እንዲውል የማድረጉ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ከቀጠለ የውጭ የዕዳ ጫና በኢትዮጵያ እምብዛም ችግር እንደማይሆን ይጠበቃል። ይህም ለግል ኢንቨስትመንት መስፋፋት የራሱ በጐ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ሠንጠረዥ 3.2፡ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸው አገሮች የዕዳ ማቃለያ ፕሮግራም አማካይነት በየዓመቱ የተገኘ የዕዳ ክፍያ ማቃለያ በሚሊዮን ብር

አበዳሪ	የተገኘው ቅናሽ በየዓመቱ					
	1994	1995	1996	1997	1998	1999
ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት (Multilaterals)	321.18	534.07	601.54	729.5	915.18	853.43
የፓሪስ ክለብ አባል አገሮች	107.82	59.51	76.36	-	27.11	-

ድምር	429.0	593.58	677.9	729.5	942.29	853.43

* የ1999 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወሩን የሚይዝ ነው።
  ምንጭ፡- ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ኢትዮጵያ የባህር በር ከሌላቸው አገሮች አንዷ ናት። ይህም ለልማት በምታደርገው እንቅስቃሴ ለይ የሚኖረው ተፅዕኖ የጐላ ነው። ከዚህ አንፂር የኢትዮጵያ ምርቶች ከቀረጥ ነፂ እንዲገቡ (AGOA) እና በአውሮፓም እንደዚሁ ሁሉም ሸቀጥ ከመሣሪያ በስተቀር (EBA) ከሚለው የገበያ ዕድል በስተቀር የተለየ ዕድል የለም። የግሉ ዘርፍ የተወዳዳሪነት ብቃት ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ እነዚህን ዕድሎችም ቢሆን ኢትዮጵያ በሙሉ አቅም ልትጠቀምባቸው አልቻለችም።

ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታን በተመለከተ የቅርብ ዓመታትን ፍሰት ስንመለከት ኢትዮጵያ በአማካይ ወደ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚጠጋ ኦፊሴላዊ የውጭ የልማት ዕርዳታ በዓመት እንደምታገኝ ይገመታል። ይህ እንግዲህ በበጀት የሚታየውን ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታን የሚመለከተው ነው። ቢያንስ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ፋይናንስ በመንግሥት በመንግሥታዊ የልማት ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት በኩል ሊገባ ይችላል።

በዚህ ጥናት የምናየው በዓመታዊ በጀት የሚታየውን ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ ነው። በአጠቃላይ ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታን አዝማሚያ ስንመለከት የ1980ዎቹ አማካይ 500 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን የቅርብ ዓመታትን (1990ዎቹን) ስንመለከት በአማካይ ወደ 1 ቢሊዮን ዶላር በመሆኑ ከ1980ዎቹ ጋር ሲነፃፀር በእጥፍ ያህል አድጓል። ይህም ከድህነት ቅነሳ ስትራቴጂውና ከምዕተ ዓመቱ ግቦች ጋር በተያያዘ የተደረገው እንቅስቃሴ ነፀብራቅ ነው።

እዚህ ላይ ከውጭ ፋይናንስ ፍሰት ጋር በተያያዘ የሚጠቀሰው ከ1980ዎቹ ማብቂያ ጀምሮ ከትምህርት፣ ከጤናና ከመንገድ ዘርፍ የልማት ፕሮግራሞች ጋር በተያያዘ የታየው የውጭ ፋይናንስ ግኝት ጭማሪ እና ሌላው ደግሞ የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙ ይፋ እንደተደረገ በ1995 መግቢያ ላይ የታየው ጭማሪ ነው። የ1997 አገራዊ ምርጫን ተከትሎ የታየው የውጭ ፋይናንስ ግኝት ማሽቆልቆል በተቃራኒው የሚጠቀስ ነው። ይህም በልማት እንቅስቃሴው ላይ የራሱን ጫና ፈጥሮ አልፏል።

የውጭ ፋይናንስ ፍሰት አፈጻጸሙን በተመለከተ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 3.3 እንደተመለከተው ጠቅላላ የልማት ፋይናንስ ፍሰት ሰብዓዊ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታን ሳይጨምር በ1994 821 ሚሊዮን ዶላር የነበረ ሲሆን በ1995 676 ሚሊዮን ዶላር በ1996 758 ሚሊዮን ዶላር እና በ1997 818 ሚሊዮን ዶላር ነበር። ለሰብዓዊና ለአስቸኳይ ጊዜ የተሰጠው ዕርዳታ በ1994 118 ሚሊዮን ዶላር የነበረ ሲሆን በ1995 በድርቁ መከሰት ሳቢያ በእጥፍ ያህል ጨምሮ 337 ሚሊዮን ዶላር የደረሰ ሲሆን በ1996 81 ሚሊዮን ዶላር በቀጣዩ ዓመት 83 ሚሊዮን ዶላር ነበር። ከሠንጠረዥ 3.3 ለመረዳት እንደሚቻለው በዘልድቅፕ ሁለት የመጨረሻ ዓመታት የፕሮጀክት ዕርዳታ ከፕሮጀክት ብድር አንፂር እያደገ የመጣበት ጊዜ ነበር። ለዚህም

ዋናው ምክንያት ኢትዮጵያ የከፍተኛ ዕዳ ጫና ማቃለያ ፕሮግራም ተጠቃሚ አገር ስለነበረች የማጠናቀቂያ ጊዜው (Completion point) ላይ እስከምትደርስ ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት በተለይም የዓለም ባንክ ፋይናንስ ወደ ዕርዳታ በመዞሩ ነው። በአጠቃላይ በ4 ዓመት ውስጥ (1994-1997) ወደ አገር ውስጥ የፈሰሰው በበጀት ሥርዓቱ ውስጥ ያለፈው የውጭ ፋይናንስ ግኝት 3.7 ቢሊዮን ዶላር ያህል ነበር።

ሠንጠረዥ 3.3፡ የኢትዮጵያ የቅርብ ዓመታት የውጭ ፋይናንስ ግኝት

በሚሊዮን ዶላር

የዕርዳታው ዓይነት	በጀት ዓመት				
	1994	1995	1996	1997	ድምር
የፕሮጀክት ዕርዳታ	130	139	121	175	565
የፕሮጀክት ብድር	266	216	211	168	861
የበጀት ድጋፍ (ዕርዳታ)	36	54	262	269	621
የበጀት ድጋፍ (ብድር)	250	128	34	90	502
ሌሎች የፋይናንስ ምንጮች (የዕዳ ክፍያ ማቃለያ)	139	138	130	116	523
የአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ ዕርዳታ	118	337	81	83	619
የሕዝብ ብዛት (ሚሊዮን)	66.3	68.2	70.1	72.1	አማካይ 13.4
በነፍስ ወከፍ (አሜሪካን ዶላር)	14.7	14.8	12.0	12.5	
ድምር	939	1012	839	901	3691

ምንጭ፡- ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር

3.2 ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አገሮች አንፂር የምትገኝበት ሁኔታ

እስካሁን የምዕተ ዓመቱን ግቦች ከመድረስ አንፂር የተደረገውን ጉዞ አፈጻጸም በዝርዝር በመጠቆም ለቀረውም ጉዞ ያለውን እንደምታ ለማመላከት ተሞክሮአል። አሁን በዚህ ክፍል የኢትዮጵያን አፈጻጸም በአጠቃላይ ከአፍሪካ አህጉር አፈጻጸም ጋር በማገናዘብ ኢትዮጵያ የት ትገኛለች የሚለውን ጠቅለል ባለ መልኩ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

በዓላማ 1 ሥር እንደተመለከተው ድህነትን በግማሽ ከመቀነስ አኳያ (Goal 1 Target 1) በገጠር ከድህነት መስመር በታች የሚገኘው ሕዝብ ከፍተኛ ቅናሽ አሳይቷል። በከተማ ግን እምብዛም አመርቂ ለውጥ አልታየም። በዚህ ረገድ በአፍሪካ ደረጃ (ከሰሀራ በታች የሚገኙ አፍሪካ አገሮች) ከኢትዮጵያ አማካይ ጋር ሲነፂፀር በተመጣጣኝ ደረጃ ላይ ይገኛል። በዕዝል 3 እንደተመለከተው እ.አ.አ. በ2004 ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ከድህነት ወለል በታች የነበረው ሕዝብ 44 በመቶ ሲሆን በኢትዮጵያ ደግሞ

እ.አ.አ. በ2004/05 38.7 በመቶ ነበር። ይህም ድህነትን በግማሽ ከመቀነስ አኳያ ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ አገሮች አፈጻጸሙ ደካማ መሆኑን ያሳያል። ለዚህም የሚጠቀሰው ምክንያት የገቢ አለመመጣጠን (Income Inequality) እየሰፋ መሄድና ዕድገቱ ድሃ ተኮር (pro-poor) ያለመሆኑ ነው። የተፈጥሮ ክስተቶችና የፖለቲካ ሁኔታም እንዲሁ የራሳቸውን ተፅዕኖ እንዳደረጉ ይታመናል። ሰሜን አፍሪካን ነጥለን ስናይ በመጀመሪያ የድህነት ክስተቱ ውስን ነው (2.4 በመቶ እ.አ.አ. በ2004)። በመሆኑም ግቡን በቀላሉ ለማሟላት እንደሚቻል የተደረጉ ግምገማዎች ያሳያሉ።

ከዓላማ 2 አኳያ የምናየው በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የተመለከቱትን ከግብ 2 እስከ 6 ያሉትን ግቦች ነው። ትምህርትን በተመለከተ በኢትዮጵያ የ1ኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ እ.አ.አ. በ1994 ከነበረበት 17 በመቶ እ.ኤ.አ በ2004/05 68 በመቶ መድረሱ ከ4 እጥፍ በላይ ማደጉን ያሳያል። ከሰሀራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ አገሮች እ.አ.አ. በ1995 ከተደረሰበት 53 በመቶ በ2004 ወደ 64 በመቶ አድጓል። የኢትዮጵያ ከዚህ አንፃር ሲታይ ፈጣን ዕድገት መታየቱን ያስገነዝባል። በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ እንደተመለከተውና ከእስከአሁኑም አዝማሚያ እንደሚታየው ኢትዮጵያ ከምዕተ ዓመቱ የጊዜ ሰሌዳ (እ.አ.አ. 2015) ቀድማ ይህን ግብ እንደምታሟላ ይጠቁማል። የተለያዩ ጥናቶችም ይህንኑ ያጠናክራሉ። የሰሜን አፍሪካ አገሮች ግን ግቡን በቀላሉ ለማሟላት እንደሚችሉ እ.አ.አ. በ2004 የተደረሰበት (94 በመቶ) በራሱ አመላካች ነው።

የጾታ እኩልነትን ከማረጋገጥ አኳያ (Goal 3) ኢትዮጵያ መነሻዋ (Base) ዝቅተኛ ቢሆንም ከአፍሪካም ሆነ ከሰሜን አፍሪካ የተሻለ ለውጥ አስመዝግባለች። የጾታ እኩልነትን ከማረጋገጥ አኳያ ዕድሜያቸው ከ15-24 የሚገኙ ሴቶች ከወንዶች ጋር ያለው ጥመርታ (Ratio) እ.አ.አ. በ1995 ከነበረበት 0.48 እ.አ.አ. በ2004/05 ወደ 0.65 አድጓል። ይኸው መጣኔ በአፍሪካ ከ0.80 ወደ 0.88 አድጓል። በሰሜን አፍሪካ ከ0.73 ወደ 0.91 አድጓል።

የህፃናትን ሞት በተመለከተ (Goal 4) ከ5 ዓመት በታች ያሉ ሕፃናት ሞት በመቀነስ ረገድ በኢትዮጵያ እ.አ.አ. በ2000/01 ከ1000 ሕፃናት 167 እንደሚሞቱ የተመለከተ ሲሆን እ.አ.አ. በ2003/04 ወደ 168 ዝቅ ብሏል። በአፍሪካ ይኸው መጣኔ እ.አ.አ. በ1995 ከነበረበት 185 እ.አ.አ. በ2004 37 ደርሷል። በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ ደረጃ ከዚህ ግብ አንፃር የተደረገው እንቅስቃሴ አዝጋሚ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በአንፃሩ በሰሜን አፍሪካ የችግሩ መጠን አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ ቅነሣ ተመዝግቧል (እ.አ.አ. በ1995 ከነበረበት 88 በ2004 ወደ 37 ወርዷል)።

የእናቶችን ሞት በማሻሻል ረገድ (Goal 5) በሰለጠኑ አዋላጆች የወሊድ አገልግሎት የሚያገኙ እናቶች ሽፋን በኢትዮጵያ እ.አ.አ. በ2003/04 11 በመቶ መድረሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ከተደረሰበት አማካይ (46 በመቶ) አንፃር እጅግ በዝቅተኛ ደረጃ እንደምንገኝ ያሳያል።

አጠቃላይ የኤች አይ ቪ ኤድስን ስርጭት (Prevalence) ከመግታትና ባለበት ከማቆም አንፃር በኢትዮጵያ እ.አ.አ. በ200/01 ከነበረበት 7.3 በመቶ በ2005 ወደ 4.4 በመቶ ወርዷል። ከሰሀራ በታች በሚገኙ

የአፍሪካ አገሮች ግን እ.ኤ.አ. በ2002 ከሚገኝበት 2.7 በመቶ ከእጥፍ በላይ በማደግ 5.8 በመቶ ደርሷል። በሰሜን አፍሪካ ሥርጭቱ ከመነሻው በጣም አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ይህንኑ መጣኔ ባለበት ለማቆየት ተችሏል። ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ከመነሻው አንፂር ሲታይ በእጅጉ አበረታች ውጤት ተመዝግቧል።

ሌላው ከዓላማ 2 አኳያ የሚጠቀሰው የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን ነው። በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ እ.አ.አ. በ200ዐ/01 ከተደረሰበት 24 በመቶ እ.አ.አ. በ2004 ወደ 35 በመቶ ያደገ ሲሆን በምዕተ ዓመቱ የመጨረሻ ዓመት ሙሉ ሽፋን ለመስጠት ግብ ተጥሏል። ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ከሰሀራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ አገሮች አንፂር የምትገኝበት ሁኔታ ተመጣጣኝ ነው (በ1995 ከተደረሰበት 32 በመቶ በ2004 37 በመቶ ደርሷል)። ከሰሜን አፍሪካ አገሮች አንፂር ከግማሽ በታች ትገኛለች።

ከዓላማ 3 አኳያ የተፈጥሮ ሀብት መጐስቆል በተለይም የደን ጭፍጨፋ (Goal 7) ለቀጣይ ዕድገት ከሚኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ አኳያ የደን ልማትን ማስፋፋትና የከባቢያዊ ሁኔታን ሚዛን መጠበቅ አንድ ዓላማ ነው። ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ በተፈጥሮ ጥቅጥቅ ደን የተሸፈነው መሬት ከጠቅላላው እ.አ.አ. በ2005 3.6 በመቶ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከሰሀራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ አገሮች እ.አ.አ. በ1995 ከነበረበት 29 በመቶ ወደ 27 በመቶ ወርዷል። በሰሜን አፍሪካ ከ1.3 በመቶ ወደ 1.5 በመቶ መጠነኛ ዕድገት አሳይቷል። በኢትዮጵያ ከ30 እና 40 ዓመታት በፊት 40 በመቶ የሚደርሰው መሬት በደን ተሸፍኖ እንደነበር ጥናቶች ያመለክታሉ።

ከዓላማ 4 አኳያ የኢኮኖሚ ልማት ትብብርን ከማጐለበት አንፂር ኢትዮጵያ በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የተመለከቱትን ሁሉን አቀፍ ፕሮግራሞቿን ለማስፈጸም የአገር ውስጥ አቅምን በወጭ ፋይናንስ መደገፉ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል። ሆኖም እስከአሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ አበረታች እንቅስቃሴዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ለኢትዮጵያ የሚፈሰው አፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ ከሰሀራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ አገሮች የነፍስ ወከፍ ድርሻ አማካይ ጋር ሲነፃፀር ከግማሽ በታች ነው። እስከአሁን ከኢትዮጵያ አኳያ የተገኘው አበረታች ውጤት በቅርቡ የተገኘው የዕዳ ቅነሣና ስረዛ ነው። (ለዋና ዋና አመልካቾች ዝርዝሩ በዕዝለ 3 ተመልክቷል)።

3.3 በኢትዮጵያ እ.አ.አ. በ2015 የልማት ግቦቹ ይሳካሉን?

3.3.1 ግቦቹን ለማሳካት ያሉ ዕድሎች (Opportunities)

ሀ) ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን የመቀነስ ብሎም የማስወገድ ዓላማን በተመለከተ

በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ እንደተመለከተው ገበያ መር የግብርና ልማትን በማፋጠን ረገድ፣ የአነስተኛውን ገበሬ ምርታማነት ለማሳደግ የሚደረገው ጥረት፣ እነዚህን ፕሮግራሞች ለማገዝ በመንግሥት የሚደረገው መሠረተ ልማትን (መንገድ፣ የመስኖ ልማት የኃይል ምንጭን እና ቴሌኮም) የማስፋፋት እንቅስቃሴ ድህነትን በግማሽ ለመቀነስና ብሎም ለማስወገድ የሚደረገውን ጥረት የሚያግዙ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው።

የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በመካሄድ ላይ ያለው አዲስ መሬትን የማልማት ፕሮግራም፣ በምርታማ እንቅስቃሴ ላይ ያተኮሩ የሴፊቲ ኔት ፕሮግራሞች፣ በፌዴራል መንግሥት በጀት የሚካሄዱ የውሃ ማቆርና አነስተኛ መስኖን የማስፋፋት ፕሮግራሞች ረሃብን ለማስወገድ የሚያስችሉ ዕድሎች ናቸው።

በአጠቃላይ የመሠረተ ልማት አውታር በገጠሪቱ ኢትዮጵያ መስፋፋትና የወደፊት አዝማሚያን በመረጃ አስደግፎ ማየቱ ተገቢ ይሆናል። በዚህ ረገድ የመንገድ ጥግግት (Road Density) በየ100ዐ ካሬ ኪሎ ሜትር በቅድመ-ዘልድቅፕ (1993) ከነበረበት 29 ኪሎ ሜትር በ1997 መጨረሻ ወደ 33.2 ኪ.ሜ. ያደገ ሲሆን በ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት 54.1 ኪ.ሜ. እንደሚደርስ ግብ ተጥሏል። ይህም ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች በአሁኑ ጊዜ የሚገኙበት አማካይ ነው። ክረምት ከበጋ ወደሚያስኬድ የመኪና መንገድ ለመድረስ በአማካይ የሚወስደው ጊዜ (በሰዓት) ቅድመ ዘልድቅፕ (1993) ከነበረበት 7 ሰዓት በ1997 መጨረሻ ወደ 5 ሰዓት ዝቅ ብሏል። በ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት ወደ 3.2 ሰዓት ዝቅ እንደሚል ግብ ተጥሏል።

የሞባይል ተጠቃሚዎች ዴንሲቲ ለ100 ሰው በቅድመ ዘልድቅፕ (1993) ከነበረበት ምንም (0) በ1997 መጨረሻ ዐ.56 ያደገ ሲሆን በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ 8.1 ለሚደርስ ግብ ተጥሏል። የመደበኛ ስልክም እንደዚሁ ከዐ.6 ወደ ዐ.85 ያደገ ሲሆን በ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት 3.38 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። በ5 ኪ.ሜትር ክልል ውስጥ የስልክ አገልግሎት የሚገኘው ሕዝብ ብዛት ቅድመ ዘልድቅፕ ከነበረበት 1 በመቶ በ1997 መጨረሻ ወደ 6 በመቶ ያደገ ሲሆን በ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት ሙሉ ሽፋን ለመስጠት (100 በመቶ) ግብ ተጥሏል። በገጠር የስልክ አገልግሎት የሚያገኙ ቀበሌዎች ብዛት በ1997 መጨረሻ 300ዐ የደረሰ ሲሆን በ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት 1500ዐ (83 በመቶ) ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

የመስኖ ልማትን በተመለከተ ከጠቅላላው 3.2 ሚሊዮን ሄክታር ከሚደርስ በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት እስከ 1997 መጨረሻ 5 በመቶ ብቻ የለማ ሲሆን በ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት 8 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

በከተሞችም እንደዚሁ የሥራ ስምሪትን በማስፋፋት ረገድ በቅርቡ በአዲስ አበባ የተጀመረው የቤቶች ግንባታ፣ የአነስተኛና ጥቃቅን የሥራ ፈጠራ ፕሮግራሞች (የመኪና ማቆሚያ ጥበቃን ጨምሮ) ለሥራ ፈጠራ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ምን አልባት እነዚህ እንቅስቃሴዎች ጥናቱ ሲካሄድ በጅምር ላይ የነበሩ በመሆኑ በቅጡ የተንፀባረቁ አይመስልም። **ለምሳሌ**፤ በ1997 መጨረሻ በአዲስ አበባ መስተዳድር በአነስተኛና ጥቃቅን የሥራ ፈጠራ ብቻ 107283 ያህል ሰዎች ተሰማርተዋል። ሆኖም ጥረቱ ይበልጥ ውጤታማ ይሆን ዘንድ እነዚህ እንቅስቃሴዎች በሁሉም ክልሎች ከተሞች ይስፋፉ። እንቅስቃሴውም ይበልጥ በተቀናጀና ሁሉን አቀፍ በሆነ ማዕቀፍ ይመራል። ከዚህ አኳያ ሥራ አጥነትን በተለይም የወጣቶች ሥራ አጥነትን ለማስወገድ በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ (1998-2002) ዘመን በከተሞች ልማት፣ በኮንስትራክሽንና በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት በወጣቶች ፓኬጅ እና በሴቶች ፓኬጅ አማካይነት ይበልጥ ተጠክሮ እንደሚቀጥል ተመልክቷል።

በአንፂራዊ መልኩ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ የገቢ ሥርጭት አለመመጣጠን አመልካች ካላቸው አገሮች ምድብ ትመደባለች (ከ0.5 በታች የሆኑ አገሮች)። በአጠቃላይ ሲታይ ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን የመቀነስ አቅም (Growth Elasticity of Poverty Reduction) ከሌሎች በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ከሚገኙ አገሮች ይልቅ በኢትዮጵያ የተሻለ ነው። ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን የመቀነስ አቅም (Growth Elasticity of Poverty Reduction) በኢትዮጵያ ከ1 በላይ መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ። ይህም ማለት የነፍስ ወከፍ ገቢን በ1 በመቶ በጨመርን ቁጥር ከድህነት መስመር በታች የሚገኘውን ሕዝብ ቁጥር ከ1 በመቶ በበለጠ መቀነስ እንደሚያስችል የሚያመለክት ነው።

ለ) የሰው ሀብት ልማትን የማፋጠን ዓላማ/ግብን በተመለከተ

በሰው ሀብት ልማት ረገድ ቀደም ብሎ የረጅም ጊዜ ዕይታ ያላቸው ሁሉን አቀፍ የሆኑ የበሰሉ ፕሮግራሞች መኖር ይህንን ዓላማ ለማሟላት ለሚደረገው ጥረት ጥሩ አጋጣሚዎች ናቸው። ከ1990 ጀምሮ በመተግበር ላይ የሚገኙት የትምህርት የጤናና የውሃ ዘርፍ የልማት ፕሮግራሞች (የንፁህ መጠጥ ውሃ) እና ኤች. አይ. ቪ. ኤድስን ለማዋጋት የዘርፈ ብዙ ምላሽ ማጠናከሪያ የ5 ዓመት ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ወጥቶ በመተግበር ላይ መሆኑ በዚህ ዘርፍ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት መልካም አጋጣሚዎች ናቸው።

ትምህርትን በተመለከተ በተለይ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት መቻል ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች መሳካት የሚኖረው አስተዋጽኦ የጎላ መሆኑን ግንዛቤ በመወሰዱ የከፍተኛ ትምህርትን ለማስፋፋት በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ነው።

በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን 13 ተጨማሪ የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎችን ለመገንባት ግብ በመጣሉ የዩኒቨርስቲዎቹ ቁጥር 21 ይደርሳል። በዚሁ መሠረት የከፍተኛ ትምህርት የቅድመ ምረቃ የቅበላ አቅም አሁን ካለበት (1997) 36,405 በዕቅዱ ዘመን የመጨረሻ ዓመት 150,077 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ይህም በዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ከአጠቃላይ የቅበላ አቅም ውስጥ የሴቶችን ድርሻ 39 በመቶ ያደርሰዋል። የከፍተኛ ትምህርት ድህረ ምረቃ ቅበላ አቅምን አሁን ካለበት 3,884 በዕቅዱ ዘመን የመጨረሻ ዓመት 26,000 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ይህም የሴቶችን ድርሻ አሁን ካለበት 24 በመቶ በዕቅድ ዘመኑ የመጨረሻ ዓመት 39 በመቶ ያደርሰዋል።

በአጠቃላይ ሴቶችን በማብቃት ማለትም በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸውን ሚና በማጐልበት ረገድ አንዱ መለኪያ በሕግ አውጪው አካል ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ነው። በዚህ ረገድ በአጠቃላይ በፓርላማ መቀመጫ ያላቸው ሴት ተመራጮች በ1993 ከነበረበት 8 በመቶ በ1997 መጨረሻ ወደ 20 በመቶ አድጓል።

በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ እንደተመለከተው ግብ 4ን እና ግብ 5ን ከማሟላት አኳያ በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙ በአግባቡ መፈጸም የጐላ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይጠበቃል።

ኤች. አይ. ቪ. ኤድስን በተመለከተ በአጠቃላይ በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመንና ከዚያም ባሻገር የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት በማስፈጸም አቅም ግንባታ፣ በማህበራዊ እንቅስቃሴና የሕብረተሰቡን አቅም በማጐልበት፣ ከጤና ፕሮግራሞች ጋር በማቀናጀት አመራርና ኤች አይ ቪ ኤድስን ከሥራ እንቅስቃሴ ጋር በማካተት እንዲሁም አጠቃላይ የማስተባበር ሚናን በማጐልበት ርብርብ እንደሚደረግ በ ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ ተመልክቷል። የኤች.አይ ቪ ኤድስን ስርጭት ከመግታት አንፂር የተወሰዱ እርምጃዎችም ጠቃሚ አስተዋጽአ እንደሚያደርጉ ይታመናል።

በንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ንዑስ ዘርፍ ሁሉን የመሸፈን ፕሮግራም (Universal Access Program) አኳያ እ.አ.አ. በ2010/11 ሙሉ ሽፋን ለመድረስ ግብ በመጣሉ ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን ግብ ከማሟላት በላይ መሄድ እንደምትችል አመላካች ነው።

ሐ) የከባቢያዊ ሁኔታንና የተፈጥሮ ሀብትን መሠረትን በመጠበቅ ቀጣይ ዕድገትና ልማትን የማፋጠን ዓላማን በተመለከተ

የኢትዮጵያ ጥቅጥቅ የተፈጥሮ የደን ሀብት በከፍተኛ ደረጃ ተመናምኖ አሁን 3.6 በመቶ እንደቀረ ይገመታል። በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን ወደ 4.7 ሚሊዮን ሄክታር የሚጠጋ (ከጠቅላላው 5 በመቶ) የተራቆተ መሬት በደን እንደሚሸፈን በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ ተመልክቷል። በዚሁ መሠረት የደን ሽፋን አሁን ካለበት 3.6 በመቶ ወደ 9 በመቶ ከፍ ይላል። ከዚህ አኳያ 2006 ፈርጀ ብዙ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ የዛፍ ዘሮች በአገር ውስጥ በመልቀምና ከውጭ አገር በመግዛት ለሕብረተሰቡ የማድረስ ሥራ እንደሚካሄድ ተመልክቷል። የደን ጥበቃና እንክብካቤም ሕብረተሰቡን ያቀፈና ተጠቃሚ የሚያደርግ እንደሚሆን ተመልክቷል። የዛፍ ዘር አቅርቦትን በዘላቂነት ለማሟላት 5 የዛፍ ዘር ማዕከላት በክልሎች እንደሚቋቋሙ ግብ ተጥሏል። በ1.44 ሚሊዮን ሄክታር የደን መሬት በመቀየስ የደን ሀብቱን ሥርጭትና ሊሰጥ የሚችለውን ጥቅም ለመለየት ቀጣይነት ያለው የማኔጅመንት ፕላንም ለማዘጋጀት በዕቅድ ተይዟል። ከኢትዮጵያ ሚሊኒየም ጋር ተያይዞ ከሚካሄደው ሕዝቡን ለልማት የማንቀሳቀስ «የአንድ ሰው ሁለት ዛፍ በ2000» ዘመቻ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። የደን ፖሊሲ ረቂቅ ሰነድ በሚኒስትሮች ም/ቤት ውይይት ከተካሄደበት በኋላ ለተወካዮት ም/ቤት ቀርቧል። እነዚህ ሁሉ ይህን ዓላማ ለማሳካት መልካም አጋጣሚዎች ናቸው።

በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ እንደተመለከተው የአፈርና ውሃ ጥበቃን በተመለከተ አፈር እንዳይከላ አስፈላጊውን እንክብካቤ በማድረግ የተጐዱ መሬቶችን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ በመጠበቅ እንዲያገግሙና ለልማት እንዲበቁ 693,000 ሄክታር መሬት ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነፂ አድርጐ በመከለል ተመልሰው ለልማት እንዲውሉ ይደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ተዳፋት ባላቸው 10.8 ሚሊዮን ሄክታር የእርሻ መሬቶች ላይ አግባብነት ያላቸው የተለያዩ ሕዳጋዊና ሥነሕይወታዊ የአፈር

ጥበቃ ዘዴዎችን በመጠቀም የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል ጥረት እንደሚደረግ በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ ተመልክቷል።

የከተሞች ልማትን በማፋጠን የተጨናነቁ አካባቢዎችን በመቀነስ ረገድ ባለፉት ዓመታት የተደረገው ጥረት እምብዛም አልነበረም። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ከፍተኛ እንቅስቃሴ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ተደርጓል። በቅርቡ የከተሞች ልማት የፖሊሲ ማዕቀፍ መውጣቱና የከሞች ልማትን የሚመራ በፌዴራል ደረጃ ራሱን የቻለ ተቋም (የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር) መመሥረቱ የሚጠቀሱ ጥረቶች ናቸው። በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ እንደተመለከተው በከተሞች አካባቢ ቆሻሻን አያያዝ ለማሻሻልና ብክለትን ለመቀነስ ነባር የጨርቃ ጨርቅ፣ የቆዳ፣ ኬሚካል፣ የስኳር፣ የሲሚንቶና የመጠጥ ኢንዱስትሪዎች የየራሳቸውን የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት አዘጋጅተው መተግበር ይጀምራሉ። 65 ማዘጋጃ ቤቶች የየራሳቸውን አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ እንደሚነድፉና ትግበራም እንደሚጀምሩ ተመልክቷል።

በከተሞች በተጐዱና በተጨናነቁ ንፅሕናቸው እጅጉን በተጓደለ አካባቢ የሚኖረውን ሕዝብ (Slum Dwellers) ኑሮ በማሻሻል ረገድ ዓላማው በአጠቃላይ የከተሞች ልማት ዓላማ ማዕቀፍ ውስጥ የሚታይ በመሆኑ የማስፈጸሚያ ስልቶቹም ብሔራዊ የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ ተዘዋዋሪ የቤቶች ልማት ፈንድ ማቋቋም፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በቤቶች ልማት ማጐልበት፣ በዝቅተኛ ወጪ የቤቶች ግንባታ የሚከናወንበትን ቴክኖሎጂ ማስፋፋት መሆናቸው በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ ተመልክቷል።

ከዚህ አኳያ በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ በየዓመቱ በመንግሥት በብሔራዊ የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም አማካይነት እስከ 100,000 የመኖሪያ ቤቶች በከፍተኛና በመካከለኛ ከተሞች ለሚገኙ መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው አባወራዎች የመገንባት እንቅስቃሴ ያደርጋል። በሌላ በኩል በግል ቤት ገንቢዎች (Real Estate) 125,000 ቤቶች በዓመት እንደሚገነቡ በዕቅድ በመያዙ በአጠቃላይ በየዓመቱ 225000 መኖሪያ ቤቶች እንደሚገነቡ ግብ ተጥሏል።

በዚሁ በከተሞች በሚደረገው እንቅስቃሴ አማካይነት መጠለያና መሠረታዊ አገልግሎት ማግኘት የሚችለውን አባወራ በ1997 ከሚገኝበት 30 በመቶ በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት 65 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል። እንደዚሁም የተጐዱና የተጨናነቁ ንፅሕናቸው የተጓደለ አካባቢዎችን በመቀነስ ረገድ አሁን ካለበት 70 በመቶ በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት 35 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

መ) የውጭ ኢኮኖሚ ልማት ትብብርን የማጐልበት ዓላማ በተመለከተ

ለጋሽ አጋሮች ለድሃ አገሮች የገቡትን ቃል ተግባራዊ እንዲያደርጉ አሁንም በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ከሚደረገው ጥረት አኳያ የዕዳ ስረዛ ከተደረገላቸው አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት። በድሃ አገሮች በተለይም በአፍሪካ የውጭ ፋይናንስ ግኝትን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ (Scaling up) የሚደረገው ጥረት እንደ ጥሩ አጋጣሚ ሊጠቀስ ይችላል። በተለይ ኢትዮጵያ የዕዳ ስረዛ ተጠቃሚ በመሆኗና በየዓመቱ

ለዕዳ ክፍያ የምታውለውን ሪሶርስ በበጀት በመደልደል ለልማት በማዋል ላይ መሆኗ እንደመልካም ዕድል የሚጠቀሱ ናቸው።

የኢትዮጵያ የፊስካል አስተዳደር በሁሉም አገዛዞች በአንፂራዊ መልኩ መልካም የሚባል አፈጻጸም (Track Record) ያለው ነው። የዚህም ዋነኛው መገለጫ የውጭ ፋይናንስ ግኝት የሚደለደለው የልማት ፕሮግራሞችን ወጪ (Capital Budget) ለማሟላት ሆኖ የመደበኛ ወጪን ሙሉ በሙሉ ከአገር ውስጥ በሚሰበሰብ ገቢ በመሸፈን ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ ነው። እስከ 1987 ድረስ የካፒታል ወጪ ሙሉ በሙሉ በውጭ ፋይናንስ የሚሸፈን ነበር። ከ1987 ጀምሮ ግን ደረጃ በደረጃ የአገር ውስጥ ገቢ መደበኛ ወጪን ሸፍኖ ለካፒታል ወጪም ያለው ድርሻ እያደገ መጥቶ በአሁኑ ጊዜ እስከ 70 በመቶ መሸፈን ተችሏል።

የመንግሥት የወጭ አስተዳደርና የበጀት ድልድል በዋነኛነት ዕድገትን ለማፋጠን ለሚያስችሉ የመሠረተ ልማት ዘርፎች ማለትም ግብርናና ገጠር ልማት እንዲሁም ምግብ ዋስትና፣ መንገድ፣ የመስኖ ልማት፣ የገጠር ኃይል ማስፋፊያ እና የሰው ሀብት ልማት ላይ ማለትም ትምህርት፣ ጤናና ኤች አይ ቪ ኤድስ እና የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የግል ንፅሕና ላይ ያተኮረ ነው። ከዚህ አኳያ ከ1994 እስከ 1998 ባለው ጊዜ ውስጥ ለዕድገትና ሌሎች የድህነት ተኮር ዘርፎች የተመደበው በጀት ከጠቅላላው የመንግሥት በጀት (በአገር አቀፍ ደረጃ) እንደቅደም ተከተሉ ከ43 በመቶ ወደ 63 በመቶ አድጓል። ይህ ደግሞ ዕድገትን በማፋጠን በቀጣይ የአገር ውስጥ ገቢ መሠረትን ለማስፋትና ከውጭ ጥገኝነት ለመላቀቅ ዕድል ይፈጥራል።

3.3.2 ግቦቹን ለማሳካት ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎች (Challenges)

ሀ) ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን የመቀነስ ብሎም የማስወገድ ዓላማን በተመለከተ

ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን ለመቀነስ ብሎም የማስወገድ ዓላማን በማሳካት ረገድ ካሉ ፈታኝ ሁኔታዎች አንዱና ዋነኛው የግብርናውን ዘርፍ ከተፈጥሮ ጥገኝነት ሙሉ በሙሉ ማላቀቅ ያለመቻሉ ነው። ይህም ማለት የገበሬው ምርት በዝናብ አቅርቦትና ሥርጭት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው። ውሃን በመጠቀም ከተፈጥሮ ጥገኝነት ደረጃ በደረጃ ለመላቀቅ የሚደረገው ጥረት ገና በጅምር ላይ የሚገኝ ነው። ሌላው የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ መሠረቱ ግብርና እንደመሆኑ መጠን የግብርና ውጤቶች የሆኑ የወጪ ንግድ ሸቀጦች ዋጋ በዓለም ገበያ ላይ የመዋዠቅ አዝማሚያ ስለሚያሣይ በተለይም የቡና አምራች ገበሬዎች ላይ በቀጥታ ተፅዕኖ ያደርጋል። ለዚህም የኢትዮጵያን የወጪ ንግድ መሠረት ማስፋፋትና ማጐለበት እንዲሁም ምርቶች እሴት እየተጨመረባቸው ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ ማድረግ ወሳኝነት ይኖረዋል። በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ያለው ሕዝብ ሌላው ፈታኝ ሁኔታ ነው።

ድህነት በከተሞች እያሻቀበ መምጣቱ ሌላው ፈታኝ ሁኔታ ነው። በከተሞች የገቢ አለመመጣጠንም እየሰፋ መጥቷል። የገቢ አለመመጣጠን (Income Inequality) አመልካች (Gini Coeficient) በአገር ደረጃ በ1988 ዐ.29 የነበረ ሲሆን በ1992 ዐ.28 በ1997 ደግሞ ዐ.30 ደርሷል። ይኸው በገጠርና በከተማ ተለይቶ ሲታይ በገጠር በ1988 ዐ.27 የነበረ ሲሆን በ1997 ከ1992 ጋር ምንም ለውጥ ሳያሳይ ዐ.26

ነበር። እንዲያውም በ1988 ከነበረበት አንፂር ቅናሽ ማሳየቱን ይጠቁማል። በከተማ ግን በ1988 ከነበረበት 0.34 በ1992 ወደ 0.38 እንዲሁም በ1997 ወደ 0.44 ከፍ ብሏል። ይህም ለድህነት ቅነሳ በሚደረገው ጥረት ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል። የገቢ አለመመጣጠን አመልካች ዝቅተኛው ሊሆን የሚችለው 0 ሲሆን ከፍተኛው 1 ነው።

ቀደም ብሎ ዕድገት ለድህነት ቅነሳ አስፈላጊ ሁኔታ እንጂ በቂ ሁኔታ ያለመሆኑ ተጠቁሟል። ለዚህም ዋናው ምክንያት ዕድገቱ መሠረቱ ሰፊ ካልሆነና ሰፊውን የሥራ ኃይል ያላሳተፈ ከሆነ፣ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የመልማት አቅም ያላገናዘበ ከሆነ (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የገጠርን ሕዝብ፣ ዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ ...ወዘተ) የገቢ ሥርጭቱ ተመጣጣኝ አይሆንም። ይህም የገቢ አለመመጣጠን (Income Inequality) የኢኮኖሚ ዕድገትን በማፋጠን የሚፈልገውን የድህነት ቅነሳ ዓላማ ከማሳካት አኳያ የሚደረገውን ጥረት ያጓትተዋል።

ከዚህ አኳያ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የሥራ ሥምሪትን ለማስፋፋት የሚደረገው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም የዘመናዊው ሽቀጥ አምራች ዘርፍና (ኢንዱስትሪ) እና የአገልግሎት ዘርፍ አብዛኛውን የሥራ ኃይል ለማቀፍ መሠረቱ ጠባብ መሆኑ አንዱ ፈታኝ ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያ መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ (Informal sector) አቅም በመገንባት የገቢ ማመንጨት አቅማቸውን ማጐልበት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው።

ለ) የሰው ሀብት ልማትን የማጐልበት ዓላማን በተመለከተ

ቀደም ብሎ እንደተመለከተው በትምህርት ዘርፍ በተሳትፎ ረገድ በሁሉም ደረጃ ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል። በዘርፉ ዋነኛዎቹ ፈታኝ ሁኔታዎች በሁሉም ደረጃዎች የትምህርትን ጥራት ማሻሻል በክልሎች መካከል ያለውን የትምህርት አገልግሎት ሽፋን ልዩነት ማጥበብ (ፍትሃዊነት)፣ በከተሞችና በገጠር መካከል ያለውን የትምህርት አቅርቦት አለመመጣጠን ማስወገድ፣ የመምህራንና የተማሪዎችን ቁጥር ከተቀመጠው መስፈርት አኳያ ማመጣጠን፣ የመምህራን ስልጠናን በማፋጠን መመደብን የሚጠይቁ ናቸው።

በጤናው ዘርፍ እስከአሁን በተደረገው ጥረት የጤና አገልግሎት ሽፋንን በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል ተችሏል። ሆኖም የተገኘው ውጤት ከመላው ሕዝብ የጤና አገልግሎት ፍላጐት አንፂር የተሟላ አገልግሎት ለማቅረብ ገና ብዙ ይቀራል። በዚህ ረገድ ዘርፉን የገጠሙት ፈታኝ ሁኔታዎች የጤና ባለሙያዎች እጥረት፣ የጤና ዘርፍ ማኔጅመንት ድክመትና የመድሃኒት አቅርቦት አለመሟላት ናቸው። ከኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ቀጥሎ በገዳይነታቸው የሚታወቁት የወባና የሳንባ ነቀርሳ በሽታዎች መስፋፋት በአሁኑ ወቅት እጅግ አሳሳቢ የጤና ችግሮች ናቸው።

የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ በገጠር የሚገኙ መሠረተ ልማቶች (ጥልቅ ጉድጓድ፣ መለስተኛ ጉድጓድ የእጅ ጉድጓድና ምንጭ የማጐልበት ሥራዎች) ቀጣይነት ከማረጋገጥ አንፂር የሕብረተሰቡ የባለቤትነት ስሜት ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑና የውሃውን ዘርፍ በማልማት ረገድ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አናሣ መሆኑ ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።

ሐ) የአካባቢያዊ ሁኔታንና የተፈጥሮ ሀብት መሠረትን በመጠበቅ ቀጣይ ዕድገትንና ልማትን የማፋጠን ዓላማን በተመለከተ

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አስተዳደርን በተመለከተ ኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ስትራቴጂ በመቅረጽ በቀጣይም የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ በ1990 አውጥታለች። ሆኖም በአፈጻጸምና በቅንጅታዊ አሠራር ረገድ እምብዛም የተሳካ እንቅስቃሴ አልተደረገም። ለደን መጨፍጨፍ አንዱ ምክንያት የሆነውን የማገዶ እንጨት በሌሎች አማራጮች በመተካት የደን መራቆትን ለመግታት የተደረገው እንቅስቃሴ እምብዛም ውጤታማ ነበር ማለት አይቻልም። የማገዶ እንጨትን ለኃይል ምንጭ የሚጠቀመው የሕብረተሰብ ክፍል በገጠሪቱ ኢትዮጵያ 99.5 በመቶ ነው። ይህ ለተፈጥሮ ሀብት መራቆት የሚኖረው እንደምታ ግልጽ ነው። የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ሕብረተሰቡን አሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ ካልቻለ ውጤታማ ሊሆን አይችልም። አሁን የወጣው የደን ፖሊሲ ይህን ጉዳይ ያገናዘበ እንደሚሆን ይጠበቃል።

መ) የውጭ ኢኮኖሚ ልማት/ትብብርን በማጐልበት ረገድ

በውጭ ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ረገድ ከእስከአሁኑ ልምድ እንደታየው የውጭ ፋይናንስ ግኝት አገሪቱ በምትከተለው የፖሊሲ ማዕቀፍ መሠረት ከልማት አጋሮቿ ጋር ለመፈጸም ቃል የገባችውን ግዴታዎች ከማሟላት ጋር የተየያዘ አይደለም። በበርካታ አጋጣሚዎች አገሪቱ ግዴታዋን አሟልታ የልማት አጋሮች ግን እጃቸውን የሰበሰቡት ሁኔታ ታይቷል። በ1990 መጨረሻ የኢትዮ-ኤርትራን የድንበር ግጭትና በቅርቡም የግንቦት 1997 ምርጫን ተከትሎ የተከሰተው ሁኔታ የቅርብ ጊዜ ትዝታዎች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ከውጭ ዕርዳታ ጋር ተያይዞ የሚጠቀሰው የዕርዳታው ጥራት (Aid Quality) ነው። ይህም የዕርዳታውን ፍሰት በመካከለኛ የጊዜ አድማስ መተንበይ ያለመቻሉ (Predictability) እና ከዕርዳታው አስተዳደር ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ ችግሮች (transaction cost) ናቸው።

በየዓመቱ የሚካሄዱ የበጀት አፈጻጸም ትንተናዎች እንደሚያሳዩት ዝቅተኛው አፈጻጸም የሚታየው ከውጭ ዕርዳታና ብድር በሚገኘው ፋይናንስ ላይ ነው። እዚህ ላይ የመጣውን ፋይናንስ በመጠቀም ረገድ የአቅም ውሱንነትም መኖሩን መካድ አይቻልም። ይህም የተገኘውን ፋይናንስ ውጤታማ በሆነ ኢንቨስትመንት ላይ ማዋልና የቀጣይ የአገር ውስጥ ገቢ የማፍራት አቅምን ከማጐልበት አንፂር የሚታይ ነው።

ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 3.3 እንደተመለከተው በዘልድቅ ፕሮግራም ዘመን አፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ ከ1980ዎቹ ጋር ሲነፃፀር በእጥፍ የጨመረ ቢሆንም ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ብዛት አንፂር በነፍስ ወከፍ ሲታይ በአማካይ 13 የአሜሪካን ዶላር ነበር። ይህም ከሰሃራ በታች የሚገኙ አገሮች አማካይ የነፍስ ወከፍ የልማት ዕርዳታ ከደረሰበት 26 የአሜሪካን ዶላር አንፂር ሲታይ ዝቅተኛ ነው።

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ የሆነ የ5 ዓመት የልማት ዕቅድ ነድፋ በመተግበር ላይ ትገኛለች። ከዚህ አኳያ ለኢትዮጵያ ዋናውና ወሳኙ ጉዳይ በሙሉ አቅም ዕቅዱን ማስፈጸም መቻል ነው። ዕቅዱን በተሟላ መልኩ ለማስፈጸም የአገር ውስጥ አቅምን ለማሟላት የሚያስችል የውጭ ፋይናንስ ግኝት

ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። ለኢትዮጵያ የሚሰጠው የልማት ዕርዳታ በነፍስ ወከፍ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ አገሮች አማካይ (26 የአሜሪካን ዶላር) እንኳን ቢደርስ በዕቅዱ ውስጥ የተመለከተውን የፋይናንስ ጉድለት (Financing Gap) ሙሉ በሙሉ ከመሸፈን በላይ ይሆናል።

4. ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች በአገር ደረጃ ወደ ተግባር የማሸጋገሩ ጥረት የተጀመረው እ.አ.አ. የሴፕተምበር 2000ን የመሪዎች ጉባኤና ውሣኔ (Millinium Declaration) ተከትሎ በተደረጉ እንቅስቃሴዎችና በዓለም ባንክና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አማካይነት ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸው በአብዛኛው በአፍሪካ የሚገኙ ድሃ አገሮች የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሰነድ ማዘጋጀትና መተግበር ከጀመሩ በኋላ ነው። ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያም የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ወደ ተግባር ማሸጋገር የተጀመረው በ1993 የመሸጋገሪያ ሰነድ (Interim PRSP) በማዘጋጀት በቀጣይም ከ1995 እስከ 1997 ያለውን የሦስት ዓመት ጊዜ የሚሸፍን ሁሉን አቀፍ የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሣ ፕሮግራም ሰነድ አዘጋጅታመተግበር ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ይህም የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች በኢትዮጵያ ለመተግበር የመጀመሪያው እርምጃ ነበር ማለት ያስችላል።

በኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ወደ ተግባር ለማሸጋገር የተደረገው ጥረት መነሻ እነዚህን ዓለም አቀፍ ግቦች ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በመገምገም አገሪቱ ከምትከተለው የፖሊሲና ስትራቴጂ አቅጣጫ ጋር ለማጣጣምና ለማዋሃድ የሚያስችሉ ጥናቶች ከተካሄዱና እነዚህ ግቦች ከኢትዮጵያ አኳያ ምን ማለት እንደሆኑ ግንዛቤ ከተወሰደ በኋላ ነው።

ከዚህ አኳያ የዚህ ጽሁፍ የመነሻ መልዕክት የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ከአገራዊው የልማት ፖሊሲ ስትራቴጂና ፕሮግራም ማዕቀፍ እና አነዚህን ለማስፈጸም በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ዕይታ ውስጥ ከተቀረጹ የልማት ዕቅዶች ጋር የተጣጣሙና የተገናዘቡ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው።

ሌላው ከዚሁ ጋር የተያያዘው ነጥብ በየዘርፉ በተናጠል የተጣሉ ግቦች በሰፊ የዕይታ ማዕቀፍ ውስጥ ሰብአዊ ድህነትን (Human Poverty) ከምድረ ገፅ በማስወገድ ሂደት ወደዚህ የመጨረሻና ሁለንተናዊ ግብ ለመድረስ የሚደረገውን ግስጋሴ ለመለካት እንደ መነሻ (Bench-mark) ልንጠቀምባቸው የሚገቡ እንጂ በራሳቸው እንደ መጨረሻ ግብ መውሰድ አይገባቸውም የሚለው ነው። እነዚህ ግቦች አጠቃላይ የአንድ አገር የልማትና የድህነት ማስወገድ አጀንዳ አካል እንጂ በራሳቸው በተናጠል ተወስደው እንደ መጨረሻ ግብ የሚታዩ ያለመሆናቸውን ነው።

ሦስተኛው ነጥብ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች አዲስ የልማት ሞዴል (New Development Model) ያለመሆናቸውን የመገንዘቡ ጉዳይ ነው። ከዚህ አንፃር እነዚህ ግቦች ድህነትን በሁለንተናዊ መልኩ ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት መግባባት ላይ የተደረሰባቸውን ቁልፍ ዓለም አቀፋዊ የልማት ዓላማዎችን የሚያንፀባርቁናቸው። ሁሉም የምዕተ ዓመቱ ግቦች አስፈላጊነታቸው የማያጠያይቅ ቢሆንም ለእያንዳንዱ ግብ የሚሰጠው ትኩረት እንደ ከእያንዳንዱ አገር የልማት አጀንዳ ቅደም ተከተል ስትራቴጂና ፕሮግራም

አኳያ የሚታይ ነው። ይህም ማለት የአንድ አገር ስኬት ግቦቹን በተናጠል በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከመድረስ አኳያ ብቻ መታየት የለበትም ማለት ነው። ድህነትን መቀነስና ማስወገድ የሂደት ጉዳይ ነውና። ትልቁ ጉዳይ በእያንዳንዱ አገር ደረጃ የሚደረገው እንቅስቃሴ ሥር ነቀልና ሁሉን አቀፍ የሆነ በሰፊ መሠረት ላይ የቆመና የማያዳግም ከመሆኑ ላይ ነው። ግቦቹ ከእያንዳንዱ አገር ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሊደርስባቸው የማይችሉ (ambitious) መስለው ከታዩ ወይም ሆነው ከተገኙ አገሪቱ ካለችበት ሁኔታ አኳያ ጊዜ የማይሰጥ እርምጃ ከወዲሁ መውሰድ የሚጠይቁ መሆናቸውን የሚያስገነዝቡ ተደርገው መወሰድ ይገባቸዋል ማለት ነው።

በኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች የእስከአሁኑ ጉዞ ከየግቦቹ አንፃር በሦስት ምዕራፎች በመከፋፈል ለማሳየት ተሞክሯል። በቅድመ ዘልድቅፕ ዘመን የሚገኝበት መነሻ (Base line)፣ በዘልድቅፕ የመጨረሻ ዓመት የተደረሰበት (1997) እና በ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት ለመድረስ ከተጣለው የግብ ስኬት አመልካች (Target) አኳያ ናቸው። እ.አ.አ. በ2015 የሚደረስበት መጣኔም ሁኔታው እንደፈቀደ ተመልክቷል። ይህ ግን አሁን በመውሰድ ላይ ያሉ ቀጣይ ጉዞውን ለማፋጠን የሚያስችሉ የፖሊሲ ርምጃዎችና ተቋማዊ ለውጦችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሳይሆን የእስካሁኑን አዝማሚያ ከተጣሉ ግቦች አንፃር በማገናዘብ የተሰላ ነው።

ከእስከአሁኑ አዝማሚያ ኢትዮጵያ በቅድመ ዘልድቅፕ ዘመን ትገኝበት ከነበረው ሁኔታ አንፃር በትምህርትና በጤና ዘርፍ የአገልግሎት ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ዕድገት አሳይቷል። ከዓላማዎቹ አንፃር እስከ 1997 መጨረሻ የተደረሰበትን ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች በተለይም ከሰሃራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ አገሮች አኳያ ለማነፃፀር ተሞክሯል። ድህነትን በግማሽ ከመቀነስና ረሃብን ከማስወገድ አኳያ ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ አገሮች በተመጣጣኝ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ተመልክቷል (ዕዝል3)። በተለይ በትምህርት ኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን ግቦች ከጊዜ ሰሌዳው ቀድማ እንደምትደርስ አዝማሚያዎቹ ያመለክታሉ። የእናቶችንና የህፃናትን ሞት ከመቀነስ አንፃር ኢትዮጵያ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝና ከዚህ አኳያ ግቡን ለማሳካት ብዙ መስራት እንደሚጠበቅ ተመልክቷል። ለዚህም በመተግበር ላይ የሚገኘው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የጐላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተመልክቷል።

የኤች. አይ.ቪ. ኤድስን ሥርጭት ከመግታትና በመቀልበስ ረገድ ኢትዮጵያ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንደምትገኝም ተመልክቷል።

የተፈጥሮ ሀብት መሠረትን በመጠበቅ የዕድገትና ልማትን ቀጣይነት ከማረጋገጥ አኳያ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅ ግምገማው ይጠቁማል። የደን ውጤቶችን ለኃይል ምንጭ የሚጠቀመው ሕዝብ 99.5 በመቶ መሆኑና የደን ሽፋኑ በከፍተኛ ደረጃ መመናመን የሕዝብ ብዛት በከፈተኛ ፍጥነት ማደግ በዚህ ረገድ ያለውን ፈታኝ ሁኔታ በውል የሚጠቁም ነው። በዚህ ረገድ በአሁኑ ጊዜ በመንግሥት የተሰጠ ትኩረትና በመደረግ ላይ ያሉ ሰፊ መሠረት ያላቸው እንቅስቃሴዎች እንደ መልካም አጋጣሚ የሚጠቀሱ ናቸው።

በተለያየ መድረክ በሚቀርቡ የጥናት ጽሁፎች እንደሚጠቀሰው የአፍሪካ አህጉር በተለይም ከሰሀራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች እስከአሁን በታየው አዝማሚያ ከሆነ ከግቦቹ ላይ እንደማይደርሱ (off-track) መሆናቸው ተመልክቷል። ይህ እንግዲህ ጉዞው በእስከአሁኑ ፍጥነት (Business as usual) ከተካሄደ ነው። በኢትዮጵያ ግን የእስከአሁኑ ጉዞ በቀጣዩ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማፋጠን ሁኔታዎችን ያመቻቸ ጭምር ይመስለኛል። ከዚህ አንፃር በቀሪዎቹ ስምንት ዓመታት ጉዞውን ማፋጠን ይቻላል።

በአጭርና በመካከለኛ ዘመን ዕይታ የውጭ ፋይናንስ ኢትዮጵያ የተያያዘችውን የልማት ጥረት ከግብ ከማድረስ አኳያ የጐላ ሚና አለው። አሁንም በአማካይ እስከ 30 በመቶ የሚደርሰው የካፒታል ወጪ የሚሸፈነው ከውጭ ፋይናንስ ነው። በዚህ ረገድ በመጀመሪያ ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ ፍሰት አገሪቱ በምታሳየው የሶሻልና የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴና ይህንንም ለማፋጠን በምትወስዳቸው የማሻሻያ እርምጃዎች ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ፣ የውጭ ፋይናንስን ግኝት መተንበይ ያለመቻሉ፣ የውጭ ፋይናንስ ግኝት በመካከለኛ ዘመን ዕይታ ለበጀት ዕቅድ በሚያመች መንገድ ሊፈስ ያለመቻሉና በበጀት የተያዘውም በሚፈለገው ጊዜ ወቅቱን ጠብቆ ሊፈስ ያለመቻሉና አሁንም ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች (SSA) አንፃር የነፍስ ወከፍ የልማት ዕርዳታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ እንደስጋት የሚታዩ ናቸው። የዕዳ ሥረዛና በዕዳ ክፍያ ላይ የተገኘው ቅናሽ የኢትዮጵያን ዕዳ የመሸከም አቅም ለማጐልበት እገዛ አድርጓል። ይህ በዚህ ረገድ በአወንታዊ መልኩ የሚጠቀስ ነው።

እዚህ ላይ ከውጭ የሚገኘውን ፋይናንስ በአግባቡ መጠቀም እንደተጠበቀ ሆኖ የአገር ውስጥ ገቢ የማመንጨት አቅምን በማጐልበት ደረጃ በደረጃ ኢኮኖሚውን ከውጭ ጥገኝነት ማላቀቁ መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ ይኸው በ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ትኩረት ተሰጥቶታል። ሌላው የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጐልበት (social mobilization) ህብረተሰብ አቀፍ የልማት ፕሮግራሞችን መተግበር መቻል ሲሆን ይህም እንደዚሁ በልማት ዕቅዱ ውስጥ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ነው። ለግሉ ዘርፍ ይበልጥ መጐለበት የሚደረጉ ጥረቶችንም ማገዝና ለኢንቨስትመንት አመች ሁኔታዎችን መፈጠርም ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው።

በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የተቃኘው የምዕተ ዓመቱ አመልካች የልማት ዕቅድ (Ethiopia's Ten Years MDGs Plan) የመጀመሪያ ምዕራፍ የሆነው የ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ (PASDEP) ገዥ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች ማለትም ሁሉን አቀፍ የማስፈጸም አቅምን ማጐልበት፣ ዕድገትን ማፋጠን፣ የሴቶችን ሁለንተናዊ አቅም ለልማት አሟጦ መጠቀም፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ከሕዝብ ዕድገት ጋር ማመጣጠን፣ የሰው ሀብትና ልማትን ማፋጠን፣ የመሠረተ ልማትን ማስፋፋት፣ የኢኮኖሚውን ተጋላጭነት መቀነስና የሥራ ሥምሪትን ማስፋፋት በትንሹ (at a minimum) የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የታለሙ ናቸው።

ከዚህ አንፃር የመንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትና የሲቪክ ማህበረሰብ እጅ ለእጅ ተያይዞ በተቀናጀ መልኩ መንቀሳቀስ የተያዘውን የልማት ዕቅድ ግቦችና ከዚያም ባሻገር የሚጠበቀውን ለማሳካት ሊተካ የማይችል ሚና ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ይህ ነው ለልማት አጀንዳው መሳካት የሚደረገውን ጥረት የተሟላ የሚያደርገው።

ዕዝል 1፡ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የግብ አመልካቾች (Targets) እና አጋዛዊ አመልካቾች (Indicators) ዝርዝር መግለጫ

ተ.ቁ	ግቦች (Goals)	የግብ አመልካቾች (Targets)	አጋዛዊ አመልካቾች (Indicators)
1	ከልክ ያለፈ ድህነትንና ረሃብን ማስወገድ	1. እ.ኤ.አ. በ1990 እና በ2015 ባለው ጊዜ ውስጥ የዕለት ገቢ ያቸው ከ1 የአሜሪካን ዶላር በታች የሆነ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ቁጥር በግማሽ መቀነስ	1. ከጠቅላላ ሕዝብ ውስጥ የዕለት ገቢያቸው ከ1 የአሜሪካን ዶላር በታች (PPP) የሆነው ሕዝብ በመቶኛ (%)
			2. የድህነት ጥልቀት መጣኔ (%)
			3. የመጨረሻው ዝቅተኛ 20 በመቶ (%)የፍጆታ መጣኔ ያላቸው ሕዝብ ብዛት
		2. እ.ኤ.አ. ከ1990 እስከ 2015 ባለው ጊዜ ውስጥ በረሃብ አለንጋ የሚገረፉ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በግማሽ መቀነስ	4. ከዕድሜያቸው ጋር የማይመጣጠን ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፂናት በመቶኛ (%)
			5. ከመደበኛው ዝቅተኛ የካሎሪ ፍጆታ በታች የሚገኘው የሕዝብ ብዛት በመቶኛ (%)
2	የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስ	3. እ.ኤ.አ. በ2015 መጨረሻ ሁሉም ዕድሜያቸው ለ1ኛ ደረጃ የደረሰ ሕፂናት (ከ7 እስከ 14 ዓመት) ወንድ ሴት ሳይለይ ለሁሉም አካባቢ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ማጠናቀቅ መቻላቸውን ማረጋገጥ	6. የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ
			7. በ1ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ለጀመሩ ሕፂናት 5ኛ ክፍል መድረስ የቻሉ በመቶኛ (%)
			8. ማንበብና መጻፍ የቻሉ ዕድሜያቸው ከ15-24 የሚገኘው ሕዝብ መጣኔ በመቶኛ (%)
3	የፆታ እኩልነትን ማረጋገጥና ሴቶችን ማብቃት	4. የፆታዊ ተሳትፎ አለመመጣጠንን በ1ኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ቢቻል በ2005 መጨረሻ ማስወገድና ብሎም በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች በ2015 መጨረሻ ማስወገድ	9. የሴቶችና የወንዶች የተሳትፎ መጣኔ በ1ኛ፣ በ2ኛና በ3ኛ ደረጃ
			10. ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ከ15-24 የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር የሚኖረው መጣኔ (%)
			11. ከግብርና ውጪ ባሉ ዘርፎች በደመወዝ የሚተዳደሩ ሴቶች መጣኔ (%)
			12. በሕግ አውጪው አካል ውስጥ ወንበር ያላቸው ሴቶች ድርሻ (%)
4	የሕፂናት ሞት መቀነስ	5. እ.ኤ.አ. ከ1990 እስከ 2015 ባለው ጊዜ ውስጥ ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፂናትን ሞት በ2/3ኛ መቀነስ	13. ከ5 ዓመት በታች ያሉ ሕፂናት ሞት መጣኔ (%)
			14. ከ1 ዓመት በታች ያሉ ሕፂናት ሞት መጣኔ (%)
			15. ዕድሜያቸው ከ1 ዓመት በታች ካሉ ሕፂናት ውስጥ የኩፍኝ ክትባት የሚያገኙት ብዛት በመቶኛ (%)
5	የእናቶችን ሞት መቀነስ	6. እ.ኤ.አ. ከ1990 እስከ 2015 ባለው ጊዜ የእናቶችን ሞት በ3/4ኛ መቀነስ	16. የእናቶች ሞት መጣኔ (ከ100ዐዐዐ እናቶች)
			17. በሠለጠኑ አዋላጆች የወሊድ አገልግሎት የሚያገኙ እናቶች መጣኔ በመቶኛ (%)
6.	ኤች አይ ቪ ኤድስን፣ ወባንና ሌሎች ገዳይ በሽታዎችን መዋጋት	7. የኤች አይ ቪ ኤድስን መስፋፋት እ.ኤ.አ. በ2015 መግታትና ብሎም መቀልበስ መቻል	18. ኤች አይ ቪ ኤድስ የተያዙ ዕድሜያቸው ከ15-24 የሚገኙ እናቶች ብዛት
			19. የወሊድ መከላከያ ከሚጠቀሙት ውስጥ ኮንዶም የሚጠቀሙት መጣኔ(%)
			19ሀ. በኤች አይ ቪ ኤድስ የመያዝ ከፍተኛ አጋጣሚ በነበረበት ሁኔታ ለመጨረሻ ጊዜ ኮንዶም የተጠቀሙ መጣኔ (%)
			19ለ. ጥልቀት ያለው ስለኤች አይ ቪ ኤድስ መስፋፊያ መንገዶች ግንዛቤ ያላቸው ከ15-24 የሚገኙ ሕዝብ በመቶኛ (%)

			20. ትምህርት የሚከታተሉ ወላጆቻቸውን በኤች አይ ቪ ኤድስ ያጡ ሕፃናት ወላጅ ካላቸው ሕፃናት ያላቸው ጥመርታ (ጎ)
		8. የወባንና የሌሎች ገዳይ በሽታዎችን መስፋፋት እ.ኤ.አ. በ2015 መግታትና ብሎም መቀልበስ መቻል	21. በወባ የመያዝና በወባ ምክንያት የመሞት መጣኔ (ጎ)
			22. በወባ በሚጠቁ አካባቢዎች ከሚኖረው ሕዝብ ውስጥ ውጤታማ የመከላከልና የሕክምና አገልግሎት ያገኘው ሕዝብ በመቶኛ (ጎ)
			23. ሰሣንባ ነቀርሳ የመያዝና የመሞት መጣኔ (ጎ)
			24. በምርመራ የተገኘ የሣንባ ነቀርሳ በሽታ ተጠቂዎች እና በተደረገላቸው ውጤታማ ሕክምና መዳን የቻሉ መጣኔ በመቶኛ (ጎ)
7	የነባራዊና ከባቢያዊ ሁኔታን ቀጣይነት ማረጋገጥ	9. የነባራዊና ከባቢያዊ ሁኔታን ቀጣይነት የማረጋገጥን መርህ ከአገራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ጋር መስተጋብር እንዳኖራቸው ማስቻልና የከባቢያዊና የተፈጥሮ ሀብቶችን የመራቆት አዝማሚያ መቀልበስ	25. በደን የተሸፈነው የመሬት መጣኔ በመቶኛ(%)
			26. የሥነ ሕይወትን መራቆት ለመከላከል ሲባል የተጠበቁ አካባቢዎች ከጠቅላላው የቆዳ ስፋት ያለው ድርሻ በመቶኛ(%)
			1. የኃይል አጠቃቀም መጣኔ (ከ1 ኪ.ግ. ዘይት ጋር የሚመጣጠን) ከእያንዳንዱ 1 የአሜሪካን ዶላር ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) አንድ የአሜሪካን ዶላር ሊገዛ በሚችለው መጠን (PPP)
			28. ወደ ከባቢ አየር የሚሰራጨው የካርቦንዳይኦክ ሳይድ መጣኔ በነፍስ ወከፍ እና የከባቢ አየር ንጣፍን የሚያሳሱ ንጥረ ነገሮች መጠን (ODP tons)
			29. ደረቅ የኃይል ምንጮችን (Solid fuels) የሚጠቀመው የሕዝብ ብዛት በመቶኛ (%)
		10. እ.ኤ.አ. በ2015 ቀጣይነት የሌለውና ንፅሕናው ያልተጠበቀ ውሃና የግል ንፅሕናው ባልተሟላ ሁኔታ የሚኖረውን ሕዝብ ብዛት በግማሽ መቀነስ	30. በከተማም ሆነ በገጠር ቀጣይነት ባለውና ንፅሕናው የተጠበቀ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት የሚያገኘው ሕዝብ ብዛት በመቶኛ(%)
			31. በከተማም ሆነ በገጠር የተሟላ የግል ንፅሕና አገልግሎት የሚያገኘው ሕዝብ ብዛት በመቶኛ(%)
		11. እ.ኤ.አ. በ2020 በዓለማችን ንፅሕናቸው በእጅጉ በተጓደለ ከተሞች አካባቢ የሚኖሩ ቢያንስ 100 ሚሊዮን ለሚደርስ ሕዝብ (Slum Dwellers) ትርጉም ያለው መሻሻል ማምጣት መቻል፣	32. የተሻሻለ የመኖሪያ አካባቢና አስተማማኝ የመኖሪያ ቤት ማግኘት የቻሉ የቤተሰብ ኃላፊዎች ብዛት በመቶኛ (%)
8	የኢኮኖሚ ልማት ትብብርን ማጐልበት	12. ነፃ ሕጋዊና ግልፅ የሆነ ልዩነት የማይፈጥር የንግድና የፋይናንስ ሥርዓትን ማስፈን፣	33. የተጣራ ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ አጠቃላዩና ለታዳጊ አገሮች የሚሰጠው ከአውሮጳ የኢኮኖሚ ልማት ትብብር ድርጅት አባል ለጋሽ አገሮች ጠቅላላ ብሔራዊ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ (%)
		13. በዝቅተኛ ልማት ደረጃ የሚገኙትን አገሮች ልዩ ፍላጐት እንደ ወጪ ንግድ ከታሪፍና	34. ከበለፀጉ አገሮች የልማት ትብብር ድርጅት ከአጠቃላይ አባል አገሮች ለጋሾች አፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ ውስጥ በድሃ አገሮች የመሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማዳረስ የሚመደበው ፋይናንስ (%)

		ኮታ ነፂ የማስገባት፣ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸውን ማቃለያ የሚያገኙበት ፕሮግራምና የመንግሥታት ትብብር የዕዳ ስረዛ ዕድልን የሚያሳይ እና የልማት ዕርዳታ ድህነትን ለማስወገድ በገባው ቃል ልግስናውን በበለጠ የመቀጠል ፍላጐት ማሟላት	35. ከማንኛውም ቅድመ ሁኔታ ነፂ የሆነ (Untied) ከበለፀጉ አገሮች የልማት ትብብር አባል አገሮች የሚገኝ ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ በመቶ (%)
			36. ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ የሚወስዱ የባህር በር የሌላቸው አገሮች ከGNLS ያላቸው መጣኔ(%)
			37. ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ የሚወስዱ የታዳጊ ደሴት አገሮች ከGNIS ያላቸው መጣኔ(%)
		14. የባሕር በር የሌላቸው አገሮችና የታዳጊ ደሴት አገሮችን ልዩ ፍላጐት ቀጣይነት ባለው ልማት ማሟላት	38. አጠቃላይ ያደጉ አገሮች ከታዳጊና በዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ ከሚገኙ አገሮች ወደ አገሮቻቸው ከቀረጥ ነፂ እንዲገቡ የሚፈቅዱት መጣኔ (%)
			39. በግብርናና በጥጥ ምርቶች ላይ ያደጉ አገሮች የሚጥሉት አማካይ የታሪፍ መጣኔ(%)
			40. ከበለፀጉ አገሮች የሚሰጠው የግብርናው ዕርዳታ ግምት ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በመቶኛ(%)
			41. የንግድ አቅምን ለማጐልበት በኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ በኩል የሚደረገው የድጋፍ መጣኔ(%)
		15. በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ መፍትሔዎችን በማቅረብ የታዳጊ አገሮችን የዕዳ ችግር መሠረታዊ በሆነ መንገድ በመፍታት ዘላቂ የሆነ ዕዳ የመሸፈን አቅም እንዲያጐለብቱ ማድረግ	42. የውጪኔ ነጥብና የማጠናቀቂያ ነጥብ የደረሱ ከፈተኛ የዕዳ ጫና ማቃለያ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ አገሮች ብዛት ድምር (Cumulative)
			43. ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸው ድሃ አገሮችን ለመርዳት በተቀየሰው የዕዳ ማቃለያ ፕሮግራም ማዕቀፍ ቃል የተገባው የማቃለያ መጠን (በአሜሪካ ደላር)
			44. የዕዳ ክፍያ ከጠቅላላ የወጪ ንግድ ገቢ ያለው ድርሻ (%)
		16. ከታዳጊ አገሮች ጋር በመተባበር ለወጣቱ ቋሚ እና ምርታማ ሥራ ለመፍጠር ስትራቴጂ መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ	45. ዕድሜያቸው ከ15-24 የሆኑ ሥራ አጥ ወጣቶች በፆታና በአጠቃላይ መጣኔ
		17. ከመድኃኒት አምራች ድርጅቶች ጋር በመተባበር ታዳጊ አገሮች አስፈላጊ መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት እንዲችሉ ማድረግ	46. በተመጣጣኝ ዋጋ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶችን በዘላቂነት መግዛት የሚችል የሕዝብ ብዛት መጣኔ (%)
		18. ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር የአዳዲስ ቴክኖሎጂ ግኝቶችን በተለይም	47. የመደበኛ የስልክ መስመርና የሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚዎች ደንሲቲ በ100 ሰዎች
			48. የግል ኮምፒዩተር ተጠቃሚዎች ደንሲቲ በ100 ሰዎችና የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች በ100 ሰዎች

		በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን መስክ ያሉትን ለሁሉም ማዳረስ	

ዕዝል 2፡ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ በተቃኘው የምዕተ ዓመቱ ግቦች መሠረት የእስካሁኑ አፈጻጸምና የወደፊቱ አዝማሚያ

ተ.ቁ.	የፖሊሲ ዓላማ/ግብ	የግብ አመልካች (Target)	አጋዛዊ አመልካች (Indicators)	ቅድመ ዘልድቅፕ የነበረበት ደረጃ	በዘልድቅፕ መጨረሻ ዓመት የነበረበት	የ5ቱ ዓመት የልማት ዕቅድ ግብ	የምዕተ ዓመቱ ግብ (2007)	የግብ አመልካች ውጤቶች ከምዕተ ዓመቱ ግቦች ጋር ያለቸው ተዛምዶ
1	**ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን መቀነስ ብሎም ማስወገድ**	1. **ከድህነት መስመር በታች ያለውን ሕዝብ በግማሽ መቀነስ**	1. **ከአገራዊ የድህነት መስመር በታች የሚገኘው ሕዝብ በመቶኛ** (%)	44.2 (1992)	38.7 (1997)	29	15	**ግብ 1 የግብ አመልካች** 1
			2. **የመጨረሻው ዝቅተኛ** 20 **በመቶ የፍጆታ መጣኔ ያለው ሕዝብ የነፍስ ወከፍ የፍጆታ መጣኔ (በብር)**					**ግብ 1 የግብ አመልካች** 1
			3. **የድህነት ጥልቀት መጣኔ** (%)	11.9 (1992)	8.3			**ግብ 1 የግብ አመልካች** 1
		2. **በረሃብ አለንጋ የሚገረፈውን የሕዝብ ብዛት በግማሽ መቀነስ**	4. **ከአገራዊው የምግብ የድህነት መስመር በታች የሚኖረው ሕዝብ በመቶኛ** (%)	42.0 (1992)	38.0	28.0	13.0	**ግብ 1 የግብ አመልካች** 2
			5. **ከቁመታቸው ጋር የማይመጣጠን ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ዕድሜያቸው ከ**5 **ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት በመቶኛ** (%)	10.0 (1992)	8.0			**ግብ 1 የግብ አመልካች** 2
			6. **ከዕድሜያቸው ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ቁመት ያላቸው ዕድሜያቸው ከ**5 **ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት በመቶኛ** (%)	57.0 (1992)	47.0			**ግብ 1 የግብ አመልካች** 2
			7. **ከዕድሜያቸው ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ሕፃናት በመቶኛ**(%)	45 (1992)	37			**ግብ 1 የግብ አመልካች** 2
2	**የሰው ሀበት ልማትን ማፋጠን** (Enhanced Human Development)							

	2.1. ትምህርትን በስፋትና በጥራት ማስፋፋት	3. በምዕተ ዓመቱ ዘመን ማብቂያ ሁሉም ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ያታና ቦታ ሳይለይ የ1ኛ ደረጃ ትምህርትን ማጠናቀቅ ማስቻል	8. የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ - 1ኛ ሳይክል (1-4) - 2ኛ ሳይክል (5-8)	17.2(1986)	 67.6 33.9	 86.6 63.8	 100.0 100.0	ግብ 2 የግብ አመልካች 3
			9. ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ 5ኛ ክፍል መድረስ የቻሉ መጣኔ (%)		57.4	136.6		
			10. 8ኛ ክፍልን የማጠናቀቅ መጣኔ (%)		34.0	63.0		
			11. ማንበብና መፅፍ የሚችሉ ዕድሜያቸው ከ15-24 የሚገኙ በመቶኛ(%)	48 (1987)	54.4	-	-	ግብ 2 የግብ ስኬት አመልካች 3
	2.2. የያታ እኩልነትን ማረጋገጥ	4. የያታዊ ተሳትፎ አለመመጣጠንን በ1ኛ ደረጃና በ2ኛ ደረጃ ቢቻል በ2005 መጨረሻ ማስወገድና በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ደግሞ በ2015 ማስወገድ	12. የያታዊ ተሳትፎ ልዩነት በ2ኛ ደረጃ	-	65.0	-	-	ግብ 2 የግብ ስኬት አመልካች 3
			13. የያታዊ ተሳትፎ ልዩነት ጥመርታ (%)	0.65				
			- የ1ኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል (%)	-	0.87	0.97	1.00	
			- የ1ኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል (%)	-	0.69	1.00		
			14. በሕግ አውጪው አካል ውስጥ ወንበር ያላቸው ሴቶች ድርሻ (%)	8(1993)	33.0	50.0		
	2.3 የሕፃናትን ሞት መቀነስ	5. እ.ኤ.አ. እስከ 2015 ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናትን ሞት በ2/3ኛ እንዲቀንስ ማስቻል	15. ከ5 ዓመት በታች ያሉ ሕፃናት ሞት መጣኔ (ከ1000 ሕፃናት)	167(1993)	140 (1996)	85		ግብ 4 የግብ አመልካች 5
			16. ከ1 ዓመት በታች ያሉ ጨቅላ ሕፃናት ሞት መጣኔ (%)	-	97 (1996)	45		ግብ 4 የግብ አመልካች 5
			17. ዕድሜያቸው ከ1 ዓመት በታች ከሆኑ ሕፃናት መካከል የኩፍኝ ክትባት ያገኙት መጣኔ (%)	48 (1992)	57 (1996)	-		ግብ 4 የግብ አመልካች 5
	2.4 የእናቶችን ሞት መቀነስ	6. እ.ኤ.አ. እስከ 2015 ባለው ጊዜ የእናቶችን ሞት በ3/4ኛ መቀነስ	18. የእናቶች ሞት መጣኔ (ከ100,000 እናቶች)	-	871 (1996)	600		ግብ 5 የግብ አመልካች 6
			19. በሠለጠኑ አዋላጆች የወሊድ አገልግሎት የሚያገኙ እናቶች መጣኔ በመቶኛ (%)	-	11 (1996)	32		ግብ 5 የግብ አመልካች 6
	2.5 ኤች አይ ቪ ኤድስ መባንና ሌሎች ገዳይ በሽታዎችን	7. የኤች አይ ቪ ኤድስን መስፋፋት እ.ኤ.አ. በ2015 መግታትና ብሎም መቀልበስ	20. ከ15-24 ዕድሜ ክልል በሚገኙ ሴቶች ላይ የቫይረሱ ስርጭት መጣኔ (%)	-	8.6	8.4		ግብ 6 የግብ አመልካች 7
			21. ከ15-24 ዕድሜ ክልል የሚገኙ ኮንዶም	-	-	60		ግብ 6 የግብ አመልካች 7

	መዋጋት		ተጠቅመው ከቋሚ ወዳጆቻቸው ውጭ ግንኙነት ያደረጉ በመቶኛ(%)					
			22. ዕድሜያቸው ከ10-14 የሆኑ በኤድስ ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናት ትምህርት የመከታተል ጥመርታ ወላጅ ካላቸው ጋር ሲነፃፀር በመቶኛ(%)	-	-	80		ግብ 6 የግብ አመልካች 7
			23. አጠቃላይ የኤች አይ ቪ ኤድስ ሥርጭት መጣኔ (%)	7.3 (1993)	4.4 (1997)	4.4		ግብ 6 የግብ አመልካች 7
		8. የወባንና ሌሎች ገዳይ በሽታዎችን መስፋፋት እ.ኤ.አ. በ2015 መግታትና ብሎም መቀልበስ መቻል	24. ለወባ በተጋለጡ አካባቢዎች 2 አጉበር የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ከጠቅላላው በመቶኛ(%)	-	1	100		ግብ 6 የግብ አመልካች 8
			25. የሣንባ ነቀርሳን የመፈወስ መጣኔ(%)	-	15	60		ግብ 6 የግብ አመልካች 8
3	የከባቢያዊ ሁኔታንና የተፈጥሮ ሀብት መሠረትን በአግባቡ በመንከባከብ ቀጣይ ዕድገትና ልማትን ግረጋገጥ	9. የነባራዊና ከባቢያዊ ሁኔታን ቀጣይነት የማረጋገጥን መርህ ከአገራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ጋር መስተጋብር እንዲኖራቸው ማስቻልና	26. የደን ሽፋን በመቶኛ(%)	-	3.6	9.0		ግብ 7 የግብ ስኬት አመልካች 9
	3.1 የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅና መንከባከብ	የከባቢያዊና የተፈጥሮ የሀብት መሠረቶችን የመራቆት አዝማሚያ መቀልበስ መቻል	27. ደረቅ የኃይል ምንጮችን (Solid fuels) የሚጠቀመው የሕዝብ ብዛት ከጠቅላላው በመቶኛ(%)	-	99.5			
	3.2 የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻልና የአካባቢ ንፅሕናን ማስጠበቅ	10. እ.ኤ.አ. በ2015 ቀጣይነት የሌለውና ንፅሕናው ያልተጠበቀ ውሃ የሚጠቀመውንና የግል ንፅሕናው ባልተሟላ ሁኔታ የሚኖረውን ሕዝብ ብዛት በግማሽ መቀነስ	28. የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት (በገጠር) በ1.5 ኪ.ሜ. ክልል ውስጥ በመቶኛ(%)	24 (1993)	35 (1996)	80 (2002)		ግብ 7 የግብ አመልካች 10
			29. የንፁሕ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ0.5 ኪ.ሜ. ክልል ውስጥ በመቶኛ (%)	72 (1993)	80(1996)	93(2002)		ግብ 7 የግብ አመልካች 10
			30. የግል ንፅሕና ሽፋን በገጠር በመቶኛ(%)	-	5.4	-	-	
			31. የግል ንፅሕና ሽፋን በከተማ በመቶኛ(%)	-	22.6	-	-	
	3.3 የመሠረታዊ	11. እ.ኤ.አ. በ2020	32. የመጠለያና መሠረታዊ አገልግሎት ማግኘት	-	30	65		

	አገልግሎቶችንና መጠለያ ማቅረብ	**በዓለማችን እጅጉን በተጐዱና በተጨናነቁ ንፅሕናቸው በተጓደለ ከተሞች አካባቢ የሚኖሩ ቢያንስ 100 ሚሊዮን ለሚደርስ ሕዝብ (Slum Dwellers) ትርጉም ያለው መሻሻል ማምጣት መቻል**	**የቻሉ ቤተሰቦች ሽፋን (%)**					
			33. **የተጐዱና የተጨናነቁ አካባቢዎችን መቀነስ በመቶኛ**(%)	-	70	35		

ዕዝል 3፡ በአፍሪካ የምዕተ ዓመቱ ግቦች የሚገኙበት ሁኔታና የወደፊት አዝማሚያ ንፅፅር

ተራ ቁ.	ግብ/አመልካች	አካባቢ	ጊዜ እ.ኤ.አ. አቆጣጠር		
			1990	2004	2015
1	ግብ 1፡ ከልክ ያለፈ ድህነትንና ረሃብን ማስወገድ፣ አመልካች፡- የዕለት ገቢያቸው ከ1 የአሜሪካን ዶላር በታች የሆነውን ሕዝብ ብዛት በግማሽ መቀነስ	ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች	44.6	44	22
		ሰሜን አፍሪካ	2.2	2.4	1.1
		ኢትዮጵያ	44.2 (1999/2000)	38.7 (2004/05)	19.0
2	ግብ 2፡ የ1ኛ ደረጃን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ፣ አመልካች፡- የ1ኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ	ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች	53.0	64.2	100.0
		ሰሜን አፍሪካ	80.6	94.0	-
		ኢትዮጵያ	17.2 (1994)	68	100.0
3	ግብ 3፡ የፆታ እኩልነትን ማረጋገጥና ሴቶችን ማብቃት፣ አመልካች፡- ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ዕድሜያቸው ከ15-24 የሚገኙ ሴቶች ከወንዶች ጋር ያለው ጥመርታ (%)	ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች	0.8	0.88	1.0
		ሰሜን አፍሪካ	0.73	0.91	1.0
		ኢትዮጵያ	0.48(1995)	0.65(2004/05)	1.0
4	ግብ 4፡ የሕፃናትን ሞት መቀነስ፣ አመልካች፡- ከ5 ዓመት በታች ያሉ ሕፃናትን ሞት መቀነስ (ከ100ዐ ሕፃናት)	ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች	185	168	62
		ሰሜን አፍሪካ	88	37	29
		ኢትዮጵያ	167(2000/01)	140(2004)	47
5	ግብ 5፡ የእናቶችን ሞት መቀነስ /ማሻሻል፣ አመልካች፡- በሠለጠኑ አዋላጆች የወሊድ አገልግሎት የሚያገኙ እናቶች ከመቶኛ(%)	ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች	42	46	100
		ሰሜን አፍሪካ	40	71	100
		ኢትዮጵያ	-	11	80
6	ግብ 6፡ ኤች አይ ቪ ኤድስንና ሌሎች ገዳይ በሽታዎችን መዋጋት፣ አመልካች፡- አጠቃላይ የኤች አይ ቪ ኤድስ ሥርጭት (Prevalence) መግታት፣	ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች	2.7(2002)	5.8(2005)	በሽታው እንዳይስ ፋፋ ባለበት ማቆም
		ሰሜን አፍሪካ	0.1	0.1(2005)	በሽታው እንዳይስ ፋፋ ባለበት ማቆም
		ኢትዮጵያ	7.3(2000/01)	4.4(2005)	በሽታው እንዳይስ ፋፋ ባለበት ማቆም
7	ግብ 7፡ የአካባቢያዊ ሁኔታንና የተፈጥሮ ሀብት መሠረትን በአግባቡ በመንከባከብ ቀጣይ ዕድገትና ልማትን ማረጋገጥ				
	አመልካች፡- በደን የተሸፈነው የመሬት መጠን ከጠቅላላው በመቶኛ (%)	ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች	29.2	26.5	-
		ሰሜን አፍሪካ	1.3	1.5	
		ኢትዮጵያ	-	3.6	9(2009/10)
	አመልካች፡- የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን ያገኘው ሕዝብ በመቶኛ	ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች	32	37	66

	(%)	ሰሜን አፍሪካ	65	77	83
		ኢትዮጵያ	24(2000/01)	35	100
8	ግብ 8፡ ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ ልማት ትብብርን ማሳደግ፣ አመልካች፡- ወደ ታዳጊ አገሮች የሚፈስ አፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ ከጠቅላላው የበለፀጉ አገሮች ጠቅላላ ብሔራዊ ሀብት ያለው ድርሻ(%)	የበለፀጉ አገሮች የኢኮ ኖሚ ልማት ትብብር ድርጅት (OECD)	0.33	0.2	0.7

በአቶ ጌታቸው አደም ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ያቦወርቅ ሃይሌ[1]

ጌታቸው በዚህ አንገብጋቢና ውስብስብ ባለ ጉዳይ ላይ ለውይይት የሚሆን ጽሑፍ አጠር መጠን ባለ መልክ በማቅረባቸው ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

አቶ ጌታቸው በድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ሥራ ላይ ስለምንገናኝ አውቃቸዋለሁ። በዚህ ጉዳይ ላይ በጣም ተጨንቀው ያላቸውን እውቀት ተጠቅመው ጊዜያቸውን ሰውተው ስለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ ስለሚሠሩ አደንቃቸዋለሁ ከፍ ያለ ምስጋናዬንም አቀርብላቸዋለሁ።

ያቀረቡት ጽሑፍ ብዙ ጉዳዮችን ከመዳሰሱም በላይ ብዙ ጠቃሚና አስተማሪ የሆኑ ነጥቦችን ያዘለ ነው። ከነዚህም ውስጥ አንኳር አንኳሮቹን ብጠቅስ።

1. የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ታሪካዊ አመጣጥና ከድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ጋር ያላቸውን ግንኙነት አመልክተዋል።
2. የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (Goals)፣ የግብ አመልካቾች (Targets)፣ አጋዛዊ አመልካቾች (indicators) በዝርዝር አሳይተዋል። ይህ ብዙዎቻችንን ያስተምራል ብዬ እገምታልሁ።
3. በዕዝል 3 ላይ የግቦች መሳካት በንጽጽር መልክ አቅርበዋል። ይህ እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው። ዕድሜ ከሰጠን ለመመሰጋገን ሆነ ለመወቃቀስ ይረዳናል።
4. ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የዓለም አቀፍ ትብብር ታሪክ እንዳላት አመልክተዋል። ትክክል ነው።
5. መንግሥት በልማት ስትራቴጂው ለድህነት ቅነሳ ቅድሚያ መስጠቱን፣ የድህነት ቅነሳና የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማዛመዱንና ማቆራኘቱን ገልፀዋል። እውነትና አስፈላጊ እርምጃ ነው። እንዲያውም ኢትዮጵያ በዚህ በአርአያነት እየተወደሰች ነው።
6. በጽሑፋቸው ውስጥ ብዙ ትክክልና ጠቃሚ የሆኑ አሕዛዊ ማስረጃዎች አበርክተዋል። የትምህርት የጤና ወዘተ... አቅርቦቶች ምን እንደሚመስሉና ምንስ እንደታቀደ በዝርዝር አቅርበዋል። እነዚህ ለመረጃ ፈላጊዎች በጣም ጠቃሚ ናቸው።
7. ግቦችና ታርጌቶች ያሉበት ሁኔታና ወደፊት ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ ያቀረቡት መረጃ አንዳንድ እውነት አለው።

[1] አቶ ያቦወርቅ ኃይሌ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በአለም አቀፍ ቢዝነስ ማኔጅመንት አግኝተዋል። አቶ ያቦወርቅ ኃይሌ በበርካታ ቦታዎች በኃላፊነት ደረጃ ያገለገሉ ሲሆን ለመጥቀስ ያህል፦ በAction-Aid Ethiopia እና ዩጋንዳ ውስጥ በኘሮግራም ዳይሬክተርነት እንደዚሁም ኘሮኘራይድ የሚባለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት መስራችና ሥራ አስኪያጅነት አገልግለዋል። በአሁኑ ሰዓት በ ACORD ውስጥ በኘሮግራም ዳይሬክተርነት እየሠሩ ይገኛሉ።

8. በመሠረተ ልማት አውታሮች መንግሥት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ዘርዝረዋል።
   እውነትን የሚደግፍ ነው።

የአቶ ጌታቸው ጽሑፍ የበለጠ ጠቃሚ ለማድረግ መስተካከል ያለባቸው በርካታ ነጥቦች አሉ። እኔ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ እሞክራለሁ፣ የውይይቱ ተሳታፊዎች ደግሞ ሊያዳብሩት ይገባል።

1. መስተካከል ያለበት ዋነኛና አንገብጋቢ ነጥብ የአመለካከት ጉዳይ ነው። ጽሑፉ የተቃኘው ምንም ችግር የለም፣ ሁሉም ነገር ታቅዶለታል፣ መንግሥት ሁሉንም ነገር ለማሳካት ተዘጋጅቶአል። ስለዚህ አታስቡ፣ አትጨነቁ በሚል መንፈስ ነው። በርግጥ አቅራቢው የመንግሥት ሠራተኛ በመሆናቸው ከዚህ አስተሳሰብ መነሳታቸው አይፈረድባቸውም እኔም በሳቸው ቦታ ብሆን የማደርገው ይህንኑ ነው። ግን የጽሑፉን ተአማኒነት ሙሉ በሙሉ አጥፍቶታል። ጽሑፉ እንደገና በObjective አመለካከት ካልተቃኘ ጠቃሚነቱ እምብዛም ነው እላለሁ።
2. MDGs ውስጣዊው (inherent) ችግሮች እንዳለባቸው መጠቀስ አለበት። በቀን 1 ዶላር የሚለው አጨቃጫቂ ጉዳይ ነው። አንደኛ ደረጃ ከቦታ ቦታ ይለያያል። ድህነት በግማሽ እንቀንሳለን ሲባል የዛሬውን የሕዝብ ብዛት ተወስዶ ነው ወይስ የወደፊቱ /ከ15 ዓመት በኋላ ያለውን/ የድህነት ወለል በኢትዮጵያ ስንት ብር እንደሆነ መግለጽ አለበት።
3. የጽሑፉ ቅኝት መስተካከል ያለበት ሌላው አመለካከት MDGs የሚሳኩ ግቦች አድርጐ መመለከት ነው። ይህ ትክክል አይደለም። ዛሬ ዓለም በሙሉ ባለቤቶቹም ጭምር MDGs በተለይ በ Sub – Sahara አገሮች እንደማይሳኩ በይፋ እየገለጹ ነው። ምክንያቱም /ዋነኛው/ የግብ 8 አለመሳካትና ባለቤት ማግኘት ነው። ሌሎቹም እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮች ጐልተው መውጣት አለባቸው።
4. የ MDGs እና የ PRS ግንኙነትና ትስስር በጽሑፉ እንደቀረበው Logical flow ያለውና ሰላማዊ አይደለም። በሁለቱ መካከል ትልቅ ትልቅ ውጥረት አለ። MDGs የ UN ፕሮግራም ሲሆን PRSP የዓለም ባንክና የ IMF Programm ነው።

   እንዲያውም UNDP እኔ የ PRSP ባለቤት ነኝ እያለ PRS ከ MDGs ጋር እንዲቆራኝለት እየጣረ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ የተሳካለት በኢትዮጵያና በሌሎች ጥቂት አገሮች ነው።

   ሌላው ትልቁ ስጋት እነዚህ ሁለቱም የተዋጣላቸው ፕሮግራሞች አለመሆናቸው እየታየ በመሆኑ ምናልባት በሌላ ፕሮግራም ቢቀየሩ እነዚህ ድሀ ሀገሮች ምን ሊያደርጉ ነው የሚለው። እኔ እንደሚመስለኝ እኛ ኢትዮጵያውያን እነዚህ ፕሮግራሞች የሚጠቅሙን ስለሆነ እንደተጀመረው የሀገራችን የልማት ፕሮግራም አድርጐ መያዙ ይጠቅማል ባይ ነኝ። ቶኒብሌር የአፍሪካ ኮሚሽን እንዳቋቋመው ሁሉ ሌላውም ለምሳሌ ፈረንሳይ ሌላ ፕሮግራም ቢጀምር በጥንቃቄ ማየት አለብን ማለት ነው።
5. መጥቀስ ካለባቸው ሌሎች ዋና ዋና ነጥቦች MDGs ሆነ PRS ገና ወደ ደሀው የህብረተሰብ ክፍል አለመድረሳቸው ነው። ከNew York እና Washington DC ወደ ዋና ዋና ከተሞች ደርሰዋል /በመንግሥት ደረጃ/ በሲቪል ማህበረሰብ አማካኝነት ደግሞ ወደ ክልል ከተሞችና አንዳንድ ወረዳዎች እየደረሱ ነው። ሱሉልታ እና ሰበታ ግን ገና አልደረሱም። Localizing MDGs ምን ያህል ከባድ እንደሆነ እኛ አይተነዋል። ድሀው ራሱ ያልተሳተፈበት የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ሊሳካ እንደማይችል ማሳወቅ ያስፈልጋል።

6. ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን መቀነስ የሚለው ክፍል ብዙ መስተካከል ያለባቸው አስተሳሰቦች አሉ። እንዲያውም ኢትዮጵያውያን በከፍተኛ ደረጃ ውይይት ማድረግ ያለብን ይመስለኛል። እዚህ ላይ በጣም አሳሳቢዎቹ ሁለት ጉዳዮች ናቸው። ግብርና እና የግሉ ዘርፍ ኢኮኖሚ በድህነት ቅነሳ ላይ ያላቸው ሚና።

እኔ ለአለፉት 30 - 35 ዓመታት ለግብርና የምንሰጠው ትኩረት የተሳሳተ ይመስለኛል። 80% የሰው ጕልበት 90 % የውጭ ንግድ ገቢ ስለሚይዝ ትኩረታችን እዚያ ይሁን የሚል ነው። እኔ እንደሚመስለኝ የድህነታችን ዋነኛ ምክንያት ይህ የመስለኛል። ማነው ይህን ዓይነት የኢኮኖሚ ዘርፍ ይዞ ከድህነት የወጣው? ማነው ይህንን ሳይቀይር ያደገው። እኔ አልሰማሁም አላነበብኩምም። እስኪ በዚህ ጽሑፍ በቀረበው አህዛዊ መረጃ እንኳን እንመልከት፤

- Services 8% የሰው ኃይል ይዞ 40% ለ GDP ያበረክታል
- ግብርና 80% የሰው ኃይል ይዞ 46% ለ GDP ያበረክታል
- እንዱስትሪ 6.5% የሰው ኃይል ይዞ 13% ለ GDP ያበረክታል

ታዲያ ለምንድን ነው እኛ ለዘመናት ትኩረት የምንሰጠው ምርታማነት በጣም ዝቅ ያለና እያሽቆለቆለ በሚሄድ ሴክተር ላይ የሚሆነው?

ለግሉ ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት አጥጋቢ አይደለም። ገበሬው የግሉ ዘርፍ አካል መሆን አለመሆን ብዙም የሚያጨቃጭቅ አይመስለኝም። ትልቁ ችግር የግሉ ኢኮኖሚ ካልዳበረ ከድህነት መውጣት እንደማይቻል አበክሮ አለመግለጹ ነው። የግሉ ዘርፍ ያለበትን ችግር ምንም አለመነሳቱ አግባብ አይደለም። በPrivatation በኩል ያለው ሂደት ምን እንደሚመስል በጽሑፉ ውስጥ መካተት አለበት።

7. የኢኮኖሚ ዕድገት ዋነኛ ምክንያት የዝናብ ስርጭት መስተካከል መሆኑን /በአንፃራዊ መልክ/ ማመልከት ያሻል። ድርቅ ቢኖር ኖሮ ሊመዘገብ የሚችለው ዕድገት ምን ሊሆን እንደሚችል መታወቅም መገለጽም አለበት። እዚያው ገጽ ውስጥ ከ1988 /47.5% / እስከ 1997 /37.7%/ ድህነት በ 8.8% እንደቀነሰ ተገልጾአል። ይህ ማለት በ10 ዓመት ውስጥ ድህነት 8.8% ዝቅ ካለ እንዴት አድርጐ ነው በቀሩት 8 ዓመታት በ 41.2% ሊቀንስ የሚችለው? ከተቻለ ጥሩ። ግን እንዴት እንደሚቻል ማሳየት ያስፈልጋል።
8. በትምህርት ላይ የተገኘው ድል ብቻ መጋነን የለበትም። ችግሮቹም ጐን ለጐን መቅረብ አለባቸው። 20 % በታች የ1ኛ ደረጃ ትምህርት የመጨረስ ሁኔታ ባለበት አገር ትኩረት መሰጠት ያለበት ስላለው ችግር ነው። ዛሬ ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው ገና በህፃንነታቸው /በ16 ዓመት/ ከትምህርት ቤት እየወጡ ከሙያውም ከፕሪፓራቶሪውም ሳይሆኑ ቀርተው ጭንቅ ላይ ናቸው። ጽሑፉ እነዚህንና እነዚህ የመሳሰሉትን ችግሮች እንዲት ሊቀርፉ እንደሚችል ቢያቅድ ይመረጣል።
9. ስለውሃ አቅርቦት የሚያብራራው ክፍል ችግሮችን ስለማይዳስስ አንባቢ ማግኘቱ ያጠራጥራል። አዲስ አበባ በምግብና በውሃ ራሺን በወደቀችበት ጊዜ ጥሩ እቅድ ተዘጋጅቶአል ማለቱ ብቻ በቂ አይመስለኝም።
10. ስለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ የቀረበው ጽሑፍ መስተካከል አለበት። እዚህ ላይ ያለው ችግር በጣም ከፍተኛ ነው ብዙዎች ኢትዮጵያ በሙሉ በረሀ እንዳትሆን እየሰጉ ነው። ግብጾች እንኳን ከኢትዮጵያ

የሚመጣ አፈር ደለል ስላስቸገራቸው ስትራተጂአቸውን እየቀየሩ ነው። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በ2000 ዓ.ም. ሁለት ዛፍ ሊተክል ነው ችግሩ ይቃለላል ማለት በቂ አይመስለኝም። ምን ዝግጅት እንደተደረገ ችግኞች መፈላት አለመፈላታቸው፣ መሬት ያለው ሰው መቆጠር አለመቆጠሩን፣ የሕዝቡ ፈቃደኝነት መታወቅ አለመታወቁ፣ እስከ ዛሬ ድረስ በየዓመቱ የሚተኩሉት ዛፎች ዕጣ ፈንታ ምን እንደሆነ ተጠንቶ ትምህርት መወሰድ አለመወሰዱን ማሳወቅ ያስፈልጋል። አስፈላጊ መመሪያዎች ሕጐችና ደንቦች መውጣታቸው ብቻ የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሀብት ችግር ያጠፋል ማለት ያዳግታል።

11. በቁጥር 3.2 ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አገሮች አንፃር የቀረበው ጽሑፍ ዓላማው ግልጽ አይደለም። የሌላ አፍሪካ አገሮች ስላልተሳካላቸው እኛም ባይሳካልን አያስደንቅም ለማለት ከሆነ ትክክል አይመስለኝም። ይልቅስ ጽሑፉ የጋራ ችግሮቻችን ላይ ቢያተኩር ይመረጣል።
12. በመጨረሻ በጣም ያስደነቀኝ ጉዳይ አቶ ጌታቸው ስለአፈጻጸም ጉዳይ በብዛት አለማንሳታቸው ነው። እንደ Challenge እንኳን አርእስት ሰጥተው አለማንሳታቸው ገርሞኛል። እርግጠኛ ነኝ አቶ ጌታቸው መልካም አስተዳደር ከሌለ እነዚህ ዕቅዶች በሙሉ የመደርደሪያ ማዳመቂያ እንደሚሆኑ ያውቃሉ። ስለዚህ በወቅቱ የሚታዩ፣ ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ወይም እነዚህን ዕቅዶች ለማሳካት የሚያስፈልገውን መልካም አስተዳዳር መግለጽ አለባቸው ባይ ነኝ።

በቅርቡ የ Africa Civil Society Forum በቅርቡ አዲስ አበባ ባደረገው ስብሰባ ያቀረባቸውን ወደ 95 /ዘጠና አምስት/ የማጠጉ MDGs ን ለማሳካት የሚያስፈልጉ የመልካም አስተዳዳር recommendations ለአዘጋጆች በመተው የምሰጠውን ሀሳብ አቆማለሁ።

በአቶ ጌታቸው አደም ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ደግነት አበባው[1]

በመጀመሪያ ይህን ትልቅ የሀገር ልማት ጉዳይ ለዚህ መድረክ ለመወያያ ርዕስነት በመምረጡ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ምስጋና አቀርባለሁ። ሁላችንም እንደምናውቀው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ታሪካዊ አመጣጥ፣ የድሃ ሀገራት ተሳትፎ፣ የለጋሽ ሀገሮችና የሌሎች የልማት ተቋማት ትስስርን የተመለከተ ትንታኔ መስጠት በጣም አስቸጋሪና ፈርጀ ብዙ ዕውቀት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ረገድ አቶ ጌታቸው በጽሁፋቸው የተነተኑት እና በዚህ መድረክ ያደረጉት ንግግር ሰፊና አስተማሪ በመሆኑ ያለኝን ምስጋና ላቀርብላቸው እወዳለሁ፡፡

በጽሁፋቸው ውስጥ የምዕተ አመቱን ግቦች በኢትዮጵያ ለማሳካት በየዘርፉ እስከ አሁን በመከናወን ላይ ያሉትንና እና በመሪ የልማት ዕቅድ (PASDEP) ለማከናወን የታሠቡ ድርጊቶችን በስፋት አትተውልናል፡፡ በሁሉም ጉዳዮች ላይ የግል አስተያየቴን መስጠት አሁን ካለን ጊዜ እና ቦታ አንጻር ተስማሚ አይመስለኝም፡፡ ለብዙዎቹም ጉዳዮች ጥልቅ የሆነ ጥናትና ምርምር እስካልተደረገ ድረስ የመጨረሻ ድምዳሜ ላይ መድረስ አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን የዚህ መድረክ ዋና ዓላማ እኔ እንደሚመስለኝ በተነሱ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ድምዳሜ ወይም ትችት መስጠት ሳይሆን ያሉብንን ዘርፈ ብዙ የልማት ችግሮች ማወቅና ለመፍትሄዎቻቸው ደግሞ በተለያየ ዘርፍ ያላሰለሰ ጥረት ለማድረግ እንድንችል የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያነሣሣ ሀሳብ መጫር ይመስለኛል፡፡

በመሆኑም በግሌ ከአቶ ጌታቸው ፅሁፍ ውስጥ በመረጥኳቸው አንዳንድ ጉዳዮች ላይ አስተያየቴን ለመስጠት እወዳለሁ፡፡ የምከተለውም ዘዴ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ዙሪያ በተሰነዘሩት ትንታኔዎች ላይ ማተኮርን ነው፡፡

1. ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን መቀነስ ብሎም ማስወገድ

[1] ዶ/ር ደግነት አበባው በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን በተመራማሪነት እና የ"Poverty and Human Resources Research Division* ኃላፊ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ። ከዚህ በፊት በጅማ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት እንዲሁም የምርምርና ህትመት ዘርፍ ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል። ዶ/ር ደግነት P.hDያቸውን ከጀርመን ሀገር ቦን ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል።

አቶ ጌታቸው በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ጉዳዮችን በስፋት ዘርዝረዋል አንኳር አንኳሮቹን ለመጥቀስ ያህል:-

ሀ. ግብርና ተኮር የልማት ስትራቴጂ

ለ. ግብርናው አሁን ለተመዘገበው ሁለት ዲጂት የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን

ሐ. በግብርናው ዘርፍ ለተገኘው ዕድገትም የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ፣ ሴፍቲኔት ፕሮግራም፣ የግብርናው ዘርፍ ኤክስቴንሽን እና ሌሎችም ተዛማጅ ምክንያቶች ተካተዋል::

በሌላ በኩል ግን በገሀድ የሚታዩት ችግሮች ለምሳሌ:-

1. የግብርና ምርታማነት /ዝቅተኛ የመሬት እና የጉልበት ምርታማነት/ በጣም አናሳ ሆኖ መገኘት፣
2. ከከተማ ወደ ገጠር ያለው የህዝብ ፍሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድ፣ እና
3. በገጠር ድህነት ሲቀንስ በከተማ ግን በከፍተኛ ፍጥነት ድህነት እየተስፋፋ መሄዱን ተናግረዋል።

በፅሁፉ የአንዳንዶቹ ችግሮች መንስኤ ቢጠቀስም የብዙዎቹ ችግሮች መንስዔ ግን በግልፅ አልተጠቀሰም። እኔ ፅሁፉ ቢያካትታቸው ብዬ የምላቸው ጉዳዩች የሚከተሉት ይሆናሉ።

ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው የህዝብ ፍልሰት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍሰት ከድህነት ለማምለጥ (Livelihood Crisis) ነው ወይንስ በሌላ ምክንያት? ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሱት ሰዎች የድህነት ሁኔታ ምን ይመስላል? ድሆች ወደ ከተማ እየገቡ በከተማ የሚገኘውን ያለውንም የድሃ ህብረተሰብ ቁጥር ከጨመሩ ለገጠሩ ክፍለ ኢኮኖሚ የድሃነት ህብረተሰብ ቁጥር መቀነስ አንዱ ምክንያት ይኸው ጉዳይ ሊሆን ነው?

አቶ ጌታቸው በፅሁፋቸው ውስጥ ከገጠር ወደ ከተማ ያለውን የህብረተሰብ ፍልሰት መንግስት እንዴት እንደሚመለከተው ቢዘረዝሩ መልካም ነው። ችግሩንስ በዘላቂነት ለመፍታት ምን የታሰበ ነገር አለ?

2. የትምህርት ዘርፍና የሰው ኃይል ልማት

በአሁኑ ወቅት ድህነትን ለመቀነስ የትምህርት ጠቃሚነት ከፍተኛ ግንዛቤ ያገኘ ጉዳይ ነው። በትምህርት ዘርፍ ኢትዮጵያ በርካታ የልማት ዕንቅስቃሴዎችን እያደረገች ነው። በየደረጃው በሁሉም ቦታ የልጆች የትምህርት ተሣትፎ እያደገ መጥቷል። ይህ ፅሁፉ ላይ እንደተገለፀው አበረታች ተግባር ነው። እስከ አሁን ላለው ስኬት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ለጋሽ ሀገራት እና መንግስት የየራሳቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል። ጠንካራ የሚባሉት የትምህርት ዘርፉ ተግባሮች:-

- የትምህርት ቤቶች ግንባታ በከፍተኛ ፍጥነት መስፋፋቱ፣
- የልጆች የትምህርት ተሳትፎ በተለይም የ1ኛ ደረጃ ትለቅ ዕመርታ ማሣየቱ፣
- የሴት ልጆች የትምህርት ተሣትፎ ማደጉ፣ እና
- ፍትሃዊ የሆነ የትምህርት ስርጭት እያደገ መሄዱ ይገኙበታል።

እነዚህ ከላይ የጠቀስኩአቸው በደንብ ተብራርተዋል። ብዙም አስተያየት የለኝም እድገቱ ይቀጥል ነው የምለው። የእኔ አስተያየት ከትምህርት አሃዛዊ መስፋፋት ጎን ለጎን እየታየ ከመጣው የትምህርት ጥራት (Education Quality) እና ቅልጥፍና (Education Efficiency) ላይ ነው። በፅሁፉ ውስጥ ይህ ጉዳይ ብዙም ትኩረትና ትንታኔ አላገኘም። በብዙ ሃገሮች የትምህርት ጥራት እና ቅልጥፍና ከአሃዛዊ የትምህርት ተሣትፎ ጋር ተነጣጥሎ አይታይም። የትምህርት ዘርፍ ስኬት ዋና መለኪያውም ይህው ጉዳይ ነው። የእኔ ምኞት ብዙ ሰው እየተማረ ብዙውም ትምህርቱን እየጨረሰ በእነዚህም ብዙ ስራ ሲኖር ማየት ነው። ይህን ትስስር መፍጠርና ማጠናከር ዋናው የትኩረት አቅጣጫ መሆን ይገባዋል።

አሁን ያለውን ሁኔታ ስናይ ግን የትምህርት ዘርፉ በዚህ ረገድ ሠፊ ችግሮች አሉበት።
ሀ. የትምህርት ግብዓቶች ጥራት እና ብቃት (Quality of School Inputs) በዚህ ረገድ የመምህራን የትምህርትና ስልጠና ደረጃ መጣኝ መሆን፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች /ለምሣሌ፡ መፅሐፍ፣ የመማሪያ ክፍል፣ የውሃና የሽንት ቤት አቅርቦት፣ የቤተ መፂህፍት መኖር ወዘተ/ ይገኙበታል። በዚህ አኳያ የኢትዮጵያ የትምህርት ዘርፍ አሁንም ቢሆን እጅግ ብዙ ወደ ኃላ የቀረ መሆኑን አንደንድ አሃዛዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ሠንጠረዥ 1፡ በ1ኛ እና በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሠለጠኑ መምህራን ስርጭት በኢትዮጵያ በ1997 ዓ.ም.

(%)

ክልል	1ኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን /1-4/	1ኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን /5-8/	ሁለተኛ ደረጃ /9-12/
ትግራይ	93	52	21
አፋር	83	68	50.9
አማራ	97.6	52	40.3
ኦሮሚያ	97.3	43	30.9
ሶማሊ	91.7	4	32.3
ቤንሻንጉል ጉምዝ	100	70	22.5
ደ.ብ.ብ.ህ	99.4	69	34.2
ጋምቤላ	88.2	85	28.3
ሀረሪ	86	38	45.6
አ.አ	97	84	82.1
	91	80	82.5
አጠቃላይ	**97**	**54.8**	**40.5**

ምንጭ፡ **MOE, Education Statistics Annual Abstracts, 2004/5**

የተማሪ አስተማሪ ጥምረት ደግሞ በ1ኛም ሆነ በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ ሄዷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያለውን አሃዝ ብንመለከት እንኳን በ1987 ዓ.ም. እና በ1997ዓ.ም. መካከል የተማሪ አስተማሪ ጥምረት በመቶ ፐርሰንት /ከ33 ወደ 66/ አሻቅቧል። ሌላው ጉዳይ ደግሞ የተማሪ ክፍል

ጥምረት /Class Size/ ነው። በኢትዮጵያ መስፈርት በአንድ ክፍል ውስጥ መኖር የሚገባው ተማሪ ብዛት በአንደኛ ደረጃ 40 ሲሆን በ2ኛ ደረጃ ደግሞ 50 ነው። ነገር ግን በተግባር የሚታየው ከዚህ ተመን በጣም የራቀ ነው። ለምሣሌ፣ በ1987 ዓ.ም. በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት 48 ሲሆን በ1996 ዓ.ም. ግን ይህ አሃዝ 74 ደርሷል። በሁለተኛ ደረጃም እንደዚሁ የተማሪ አስተማሪ ጥምረት በ1987 ዓ.ም. እና በ1996 ዓ.ም. መካከል የ55 በመቶ /ከ33-51/ ጭማሪ አሳይቷል። የተማሪ ክፍል ጥምረት ደግሞ በ24 በመቶ /63-78/ ከፍ ብሏል።

ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች የሚጠቁሙት ዋና ነገር በ1ኛም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከላይ ለሚማሩ ተማሪዎች ተገቢውን እውቀትና ክህሎት ለማስያዝ ኢትዮጵያ በትምህርት ዘርፍ ያሉበትን ችግሮች ነው። ስለዚህ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ህብረተሰብ ለጋሽ አካሎች መምህራንን በብዛትና በብቃት ለማሰልጠን ቀጣይ የጋራ ርብርብ እንዲያደርጉ ያስፈልጋል። በት/ቤቶች ግንባታም እንደዚሁ አሁን ያለውን የተጨናነቀ የተማሪ ክፍል ጥመርታን እና ቀጣይ የትምህርት ተሣትፎን በማጣጣም አዳዲስ ት/ቤቶች እና ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች በነባር ትምህርት ቤቶች ሊገነቡ ይገባል። በአቶ ጌታቸው ፅሁፍ ላይ የተለያዩ ተስፋ ሰጪ ድርጊቶች በእነዚህ ዙሪያ ተጠቅሰዋል። ነገር ግን በእሳቸው በፅሁፍ ውስጥም ሆነ በኢትዮጵያ የአምስት ዓመት የልማት መሪ ዕቅድ ያልተጠቀሰው የተማሪና ክፍል መጠን (Class Size) ነው። በዚህ ላይ ያላቸውን አስተያየት ቢያካትቱ ጥሩ ነው።

ለ. የትምህርት ስርዓቱ ወጪ ቆጣቢነት እና ቅለጥፍና (School Output indicators) በዚህ ረገድ የአንድ የትምህርት ስርዓትን በመማር ላይ ያሉት ተማሪዎቹ የትምህርት አፈፃፀም (Internal Efficiency/ How measure) እና ትምህርት ጨርሰው በሚወጡት ተማሪዎች የስራ አፈፃፀም (External Efficiency) ማየት ይቻላል። በመጀመሪያው መመዘኛ ሊታዩ የሚገባቸው፡-
1ኛ. የተማሪዎች ክፍል የመድገም መጣኔ (Grade Repetition Rate)
2ኛ. የተማሪዎች ትምህርት አቋርጦ መውጣት መጣኔ (Dropout Rate)
3ኛ. የተማሪዎች የ1ኛ ደረጃ ትምህርት የመጨረስ መጣኔ (Primary Completion Rate) እና የመሣሠሉት ናቸው።

እዚህ ላይ መታወቅ የሚሻው ዋናው ነገር የትምህርት ተሣትፎ አስፈላጊ ቢሆንም ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች በአግባቡ ማሣካት ካልተቻለ የተለያዩ የልማት ዘርፎች ማለትም ለምሣሌ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ማይምነትን ማጥፋት፣ ጤናን ማሻሻል የህዝብ ብዛትን ለመመጠን የአካባቢ ደህንነትን ማረጋገጥ የፆታ ዕኩልነትንና ሴቶችን የማብቃት ግብ እና ሌሎችንም ከትምህርት ዘርፉ ልማት በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚገኙትን አስተዋፅኦዎች አነስተኛና ቀጣይነት የሌላቸው ያደርጋቸዋል።

አቶ ጌታቸው በፅሁፋቸው ውስጥ ኢትዮጵያ በትምህርት ዘርፍ የምርት ዓመቱን የልማት ግብ ከተጣለው የጊዜ ገደብ /ማለትም ከ2015 እ.ኤ.አ/ ቀድማ /2009 እ.ኤ.አ እንደምትደርስ እና ይህም የግቡ ስኬትን እንደሚያሳይ ገልፀውልናል። በእኔ አስተያየት አሁን ያለውን ከፍተኛ የትምህርት የማቋረጥ አዝማሚያ

/14 በመቶ ከአንደኛ ደረጃ እና 22% ከ1ኛ ክፍል/፣ ዝቅተኛ የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቅ መጣኔ 57% የሚሆኑት ብቻ 5ኛ ክፍል የሚያጠናቅቁ መሆኑ እና ብዙዎችም ክፍል የመድገም ሁኔታ እንደሚያጋጥማቸው መታየቱ መቶ በመቶ የንጥር የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ተሣትፎ (Net Primary Enrollment Rate) ማሣካት አስቸጋሪ ነው እላለሁ። ሁኔታዎች እየተሻሻሉ ስለሚሄዱ በርግጥ የንጥር ተሣትፎ መጣኔ አሁን ከለበት የተሻለ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። በእኔ አስተያየት ዋናው ነገር ልጆችን ት/ቤት ማስገባቱ ብቻ ሳይሆን የሚማሩትን ትምህርት ብቃትና ጥራት መከታተል እና እንዲሻሻልም ያላሠለሰ ጥረት ማድረጉ ነው። ንጥር የትምህርት ተሣትፎ (Net Primary Enrollment Rate) በሠለጠኑት አገሮችም አማከይ አሃዝ ከመቶ ፐርሰንት ያነሠ ነው። ነገር ግን በነዚህ ነገሮች ት/ቤት የገቡ ልጆች ሁሉ ትምህርት የማጠናቀቅ ዕድላችው እጅጉን የሠፋ ነው ይህ የሚያመለክተው በኢትዮጵያ ተማሪዎች የ1ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በፍጥነትና በጥራት እንዳይጨርሱ የሚገታቸው መሰናክሎች (constraint) በጥንቃቄ መለየት እና መፍትሄ መሰጠት ቀጣይነት ያለው የትምህርት ልማትን ለማረጋገጥ እና ከሱም የሚገኘውን ዘርፈ ብዙ አስተዋፅኦ ለማግኘት ይረዳል።

የትምህርት ዘርፉን External Efficiency በተመለከተ በየደረጃው ትምህርት የሚጨርሱ ተማሪዎችን በተማሩበት /በሰለጠኑበት ሙያ ዘርፍ ስራ የማግኘት /የመፍጠር አቅም/ዕድል መከታተልና በስራ ላይ ሆነው የሚያዩትን የትምህርት ይዘት (curriculum) ጠንከራና ደከማ ጎን ማወቅ እና ለቀጣይ መሻሻል አስተያየቶችንና የጥናት ውጤቶችንም በትምህርት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ማካተት ይገባል። ብዙ ሰው ተምሮ ብዙ ስራ ከላገኘ እና የተማረውን ሙያ በተግባር ከልተጠቀመበት ለግለሰቡም ሆነ ላስተማረው ቤተሰቡ እና ለሀገር ያለው ኪሣራ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ መንግስት የትምህርት የሙያ ዘርፎችንና የስልጠና ዘዴውን ከገበያ አኳያ ማጣጣም ይኖርበታል።

3. የፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ

በአጠቃላይ ሲታይ ኢትዮጵያ ይህን ግብ ለማሣካት በተለይም ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በተለያዩ ዘርፎች (ለምሳሌ፤ በትምህርት፣ በጤና ፣ በፖለቲካ በስራ ማግኘት ወዘተ..) እያደረገች ትገኛለች። የምዕተ ዓመቱ ዓላማዎች እና አመልካች መሥፈርቶች ጠባብ እና በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉን አቀፍ የሆነ ጥቆማ አይሠጡም። የዚህን ግብ ለመከታተል በምዕተ ዓመቱ የልማት መርህ ላይ የተቀመጡ ዋና ዓላማ የፆታ ልዩነትን በ1ኛ ደረጃ ትምህርትእና በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ሙሉ በሙሉ እ.ኤ.አ በ2005 ማጥፋትና በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ደግሞ ቢዘገይ እ.ኤ.አ በ2015 ማሰወገድ ነው። ከዚህ መርህ አንፂር ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን ዕውነታ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የሚያበረታታ ቢሆንም ግቡን ሙሉ በሙሉ ለማሣካት ግን የሚሣናት መሆኑን ይጠቁማል።

ከ1991 ዓ.ም እስከ 1997 ዓ.ም ባለው ጊዜ በ1ኛ ደረጃ ት/ቤት መጠነኛ የሆነ የፆታ ልዩነት መጥበብ ታይቷል። ነገር በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የነበረው የፆታ ልዩነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ መሄዱን የመንግስትም አሃዛዊ መረጃዎች በግልጽ ያሣያሉ። ለዚህ ሁኔታ ምክንያቶቹና መፍትሄዎቹ በቂ

ትኩረት አልተሠጠውም። በመሪ ዕቅዱም (PASDEP) ላይ ያለው ጠቋሚ አመልካች የለም /በተለይ ስለ 2ኛ ደረጃ/ የ1ኛ ደረጃም ቢሆን የፆ ታ ልዩነትን ለማጥበብ የተጣለ የግብ ዕቅድ የለም።

ሠንጠረዥ 2፡ በ1ኛእና 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ያለው ትምህርት ተሣትፎ የፆታ ልዩነት (Gender Gap) በኢትዮጵያ

ዓ.ም	አንደኛ ደረጃ 1-8	ሁለተኛ ደረጃ 9-10
1991	20.6	
1992	20.2	
1993	20.3	4.0
1994	20.5	6.7
1995	20.8	9.7
1996	18.30	12.3
1997	16.5	14.8

ምንጭ፤ MOE, Annual Education Statistics Annual Abstracts, 2004/05

4. የህፃናት እና የእናቶች ጤንነት

ምንም እንኳን የህፃናትና የእናቶች ጤና ሁኔታ በኢትዮጵያ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ቢገኝም ባለፉት 30 ዓመታት ሀገሪቱ የህፃናት እና የእናቶች ህልፈትን በመዋጋት እና በከፍተኛ ፍጥነት በመቀነስ ተጠቃሽ ከሆኑት አገሮች አንዷ ናት። ለጥሩ ጤና ብዙ ነገሮች (ለምሳሌ፤ የገቢ መጨመር፣ የጤና ተቋማት መበራከት፣ የትምህርት ሽፋን መጨመር፣ የአሰተሳሰብ ለውጥ ማድረግ፣ የሌሎች መሠረታዊ የሆኑ አገልግሎቶች መገኘት) ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ተፅዕኖ እንደሚኖራቸው የሚታወቅ ሀቅ ነው። በህፃናት እና በእናቶች ጤና ላይ የተገኘው መጠነኛ መሻሻል ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የቅርብ ዝምድና ሊኖረው ይችላል። በሌላ መልኩ ደግሞ የህፃናት እና የእናቶች ጤንነት መሻሻል ገቢን እና ድህነትን ለማሰወገድ እንዲሁም የሰው ሃይል ልማትን ከፍ ለማድረግ የጎላ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ሠንጠረዥ 3፡ የህጻናት እና የእናቶች ጤና ሁኔታ

ዓ.ም (እ.ኤ.አ)	ከአንድ አመት በታች ያሉ ህፃናት ህልፈት (ከ1000አዲስ ትውልድ መጠን	ከ5 ዓመት በታች ያሉ ልጆች ህልፈት (ከ1000ልጆች ውስጥ) መጠን	በወሊድ ሣቢያ ለዕለፈተ ህይወት የሚዳረጉ እናቶች መጠን (ከ1000/000)
1990	128	204	1800
2000	117	166	850
2004	97	140	871
የምዕተ ዓመቱ ግብ በ 2015	43	68	450
ከግብ ለመድረስ			

የሚያስፈልግ አመታዊ አፈፃጸም (በ1990እና በ 2015 መካከል)	- 3.4	- 5.4	- 54
የእስከአሁን አፈጻጸም (ከ1990-2004)	-2.2	-4.57	-66
ግብን ለማሟላት ኢትዮጵያ ያላት ዕድል	ምናልባት (Probably)	ምናልባት (Probably)	ይቻላል(Likely)
አስተያየት (ከግቡ ለመድረስ)	የበለጠ (more effort)	የበለጠ (more effort)	

ምንጭ፡- ትንታኔ ከራሴ አሃዛዊ መረጃ **World Bank** እና የአቶ ጌታቸው ፅሁፍ።

5. የውጭ ኢኮኖሚ ልማት/ ትብብርን በተመለከተ

በፅሁፍ ውስጥ በውጭ ልማት ትብብር ረገድ እስከሁን ኢትዮጵያ የምታገኘው የልማት ዕርዳታ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ ሃገሮች አማካይ (26 የአሜሪከን ዶላር) በግማሽ እንደሚያንስ ተጠቅሷል። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ አገር ወደ 26 የአሜሪከን ዶላር ከፍ ቢል ኢትዮጵያ ያቀደቻቸውን የልማት ግቦች ለማሳከት ከበቂ በላይ እንደሚሆን ተጠቁሟል። ነገር ግን ከውጭ ከዕርዳታ ጋር በተያያዘ ዘርፈብዙ ችግሮች እንዳሉ በተለያየ ጊዜ በሌሎች ሀገሮች በተደረጉ ጥናቶች እንረዳለን። በዚህ ፅሁፍ ውስጥም የተነሱት፡-

1. የውጭ ዕርዳታ በመጠቀም ረገድ የአቅም ውስንነት (Absorptive Capacity)
2. የዕርዳታው ጥራት (Aid Quality)
3. ከዕርዳታው አስተዳደር ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ ችግሮች
4. የዕርዳታው ፍሰት በመከከለኛ የጊዜ አድማስ መተንበይ አለመቻሉ እና ሌሎችም አብይት ችግሮች ኢትዮጵያ ላቀደቻቸው የልማት ስራዎች ከፍተኛ አሎታዊ አስተዋጽኦ አላቸው።

አቶ ጌታቸው ዘርፈ ብዙ የሆኑ የልማት ግቦችን ማለትም በ PASDEP እና በ MDGs ኢትዮጵያ እንደምታሟላ ሲተነትኑ ከውጭ ዕርዳታ ፋይናንስ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በተመለከተ ያላቸው ግምት ወይም እሳቤ (Assumption) ምን እንደሆነ ቢያብራሩ ጥሩ ይመስለኛል። ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች ሁኔታ አሁንስ መንግስት ለሚያስበው የልማት እንቅስቃሴ አሉታዊ ገጽታ አይኖራቸውም ወይ?

ስለተሰጠኝ ዕድል አመሰግናለሁ።

ሙስና እና ልማት በኢትዮጵያ[1]

አሊ ሱሌይማን[2]

መግቢያ

ሙስና ልማትን እንደሚጎዳ ወይም እንደሚገታ፣ ሲከፋም የፖለቲካ ስርአቱን ለአደጋና ለመፈራረስ እንደሚያጋልጥ በተለያዩ ምሁራን የተገለጸ ብቻ ሳይሆን በተግባርም የታየ ለመሆኑ የነዛየርና ሴራሊዮን ታሪክ ምስክር ነው። ብዙም ባይሆኑ ሙስና አገልግሎትን በፍጥነት ለማግኘት፣ ስለሆነም እድገትን ለማፋጠን ይረዳል ብለው የሚከራከሩ ጸሀፊዎች አሉ። ይህ ጽሁፍ ሙስና በልማት ላይ ስለሚኖረው ተጽእኖ፣ ባለፉት አምስት አመታት በኢትዮጵያ ሙስናን ለመዋጋት ስለተወሰዱት እርምጃዎችና ስለተከናወኑ ተግባራት፣ እና እነዚህ ባለፉት አምስት አመታት ከተመዘገበው የኢኮኖሚ እድገት አንጻር ሊኖራቸው ስለሚችለው ፋይዳ ለውይይት መንደርደሪያ የሚሆኑ ነጥቦችን ለማንሳት ይሞክራል።

ጽሁፉ በአራት ክፍሎች ተከፍሎ የቀረበ ሲሆን፣ በክፍል አንድ ሙስና እና መገለጫዎቹ በአጠቃላይ ምን እንደሚመስል ለማሳየት የሚሞክር ሲሆን፣ በክፍል ሁለት ሙስና ከልማት አንጻር ያለውን አሉታዊ ፋይዳ ለማሳየት ተሞክሮአል። በሶስተኛው ክፍል ባለፉት አምስት አመታት በኢትዮጵያ ሙስናን ለመዋጋት ስለነበረው እንቅስቃሴና እርምጃ በአንድ በኩል እና በልማቱ አንጻር የተመዘገበውን እድገት በማነጻጸር ሙስናን በመከላከል በተወሰደው እርምጃና በልማቱ መካከል ሊኖር ስለሚችለው ግንኙነት ለውይይት መነሻ የሚሆን ሀሳብ ለማቅረብ ተሞክሯል። በመጨረሻም በክፍል አራት ማጠቃለያና የወደፊት አቅጣጫን በሚመለከት ሀሳብ ቀርቧል።

1. የሙስና ትርጉምና መገለጫዎቹ

ሙስና የእንግሊዝኛውን ኮራፕሽን የሚለውን ቃል እንዲገልጽ የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወረሰ ቃል ነው። የተለያዩ ምሁራን ሙስናን በተለያየ መልኩ ይተረጉማሉ። በተለያዩ አገሮች ህጎችም ሙስና በተለያየ መልኩ ይተረጎማል። ይሁንና ጠቅለል ባለ መልኩና በተለምዶ ሙስና ስልጣንን አለአግባብ በመጠቀም ለግል ጥቅም ከማዋል ጋር ተያይዞ የሚታይ ሲሆን ይህም ጉቦን፣ በስልጣን አለአግባብ መገልገልን፣ ማጭበርበር፣ እምነት ማጉደልን፣ የመንግስት ሀብትና ንብረትን ለግል ጥቅም ማዋልን ይጨምራል።

[1] ነሐሴ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የተካሄደ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡፡

[2] አቶ አሊ ሱሌይማን በሕግ ሙያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እ.ኤ.አ. በ1986 የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡ አቶ አሊ ሱሌይማን በከፍተኛ ፍ/ቤት በዳኝነት፣ እንዲሁም በአማራ ክልል የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት ሆነው አገልግለዋል፡፡ በተጨማሪ በፍትህ ሚኒስቴር በምክትል ሚኒስትርነት ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በፌዴራል ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ አቶ አሊ ሱሌይማን በተለያዩ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ውስጥ በቦርድ አባልነትና በሰብሳቢነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

በ1997 በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 404 (2) ስለሙስና ወንጀል ምንነት የሚከተለው ተደንግጎ እናገኛለን።

«ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በተሰጠው ሀላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ፣ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ ወይም፣ ማንኛውም ሰው ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ ለመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት ቃል የገባ ወይም ያቀረበ ወይም ለማቅረብ የተስማማ እንደሆነ ወይም፣ በአግባቡ ለተፈጸመ ወይም በአግባቡ ወደፊት ለሚፈጸም የመንግስት ስራ የማይገባ ጥቅምን ማንኛውም ሰው የሰጠ ወይም ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ተብሎ እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል።

በወንጀል ህጉ መሰረት የመንግስት ሰራተኛ ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ልማት ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ፣ ተሹሞ፣ ተመድቦ ወይም በህዝብ ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ስራን የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ማለት ነው። (አንቀጽ 402(1) ሙስና በአንድ በኩል በሁለት ወገኖች ማለትም በመንግስት ሰራተኛ ወይም ኃላፊ እና በሌላ በኩል በሌሎች ሰዎች ማለትም የመንግስት ሰራተኛ ባልሆኑ ሰዎች በሚፈጠር መመሳጠር የሚፈጸም ወንጀል ሲሆን በሌላ በኩል የመንግስት ሰራተኛው ብቻውን (በማጭበርበር ወይም እምነት በማጉደል) ወይም ከሌሎች የመንግስት ሰራተኞች ጋር በመመሳጠር የሚፈጸም ወንጀልን የሚያካትት ነው።

ከሙስና ጋር በተያያዘ የሚገኙ ጥቅሞች አይነታቸው በርካታ ናቸው። ከመንግስት ጋር የሚደረጉ ውሎችን፣ የንግድና የስራ ፈቃድን፣ መሬትን፣ ቅጥርን ወዘተ ማግኘት፣ የወንጀል ድርጊቶች ተዳፍነው እንዲቀሩ ማድረግ፣ ለመንግስት የሚከፈሉ ታክሶችና ቀረጦችን ማስቀረት፣ ብድር ማግኘት ወዘተ... ከሚጠቀሱት አንዳንዶቹ ናቸው።

በሌላ በኩል በሙስና ወንጀል ፈጻሚ የመንግስት ሰራተኛ ወይም ባለስልጣን የሚገኘው ጥቅም የገንዘብ ስጦታ፣ የአክስዮን ድርሻ፣ የእዳ መሰረዝ፣ ለልጆች የትምህርት እድል፣ የጤናና የህክምና አገልግሎት፣ የትራንስፖርትና የሆቴል ወጪ መሸፈን ወሲባዊ አቅርቦት ወዘተ... ሊሆኑ ይችላሉ።

ከዚህ በላይ የተመለከተው ትርጉም ስለሙስና አጠቃላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ቢሆንም፣ ሙስናን ለመዋጋት ለሚቀረጸው ስልትና ስትራቴጂ መሰረት እንዲሆን እንዲሁም ሊያደርስ ከሚችለው ጉዳት አንጻር የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት ብዙውን ጊዜ በሚገለጽባቸው አይነት ተከፋፍሎ ይቀርባል። እነሱም አነስተኛ (petty corruption) ከፍተኛ (grand corruption) እና state capture በማለት ተከፋፍለው ይቀርባሉ።

አነስተኛ ሙስና (petty corruption) የሚባለው በመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ በሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች የሚፈጸም ሲሆን በዋነኛነት ከህዝብ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም የሚገኘውም ጥቅምም አነስተኛ

የሆኑ ስጦታዎችን የሚመለከት ነው። ለምሳሌ፤ ሰነዶችን በመደለዝ እና በማጥፋት የሚገኝ አነስተኛ መጠን ያለው ጥቅም፣ በፕሮፎርማ በሚደረጉ ግዢዎች ጋር በተያያዘ ከአቅራቢ ጋር በመመሳጠር የሚገኙ ጥቅሞች ወዘተ... በዚህ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው። አነስተኛ ሙስና የሚገኘው ጥቅም አነስተኛ እንዲሁም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች የሚፈጸም ቢሆንም የሚያደርሰው ጉዳት ግን ቀላል ነው ማለት አይደለም። በአጭሩ እንዲቀጭ ካልተደረገ ህብረተሰቡን በማማረር ህብረተሰቡ በመንግስት ላይ እምነት እንዲያጣ የሚያደርግና ወሳኙን የህብረተሰቡን ተሳትፎ የሚያሳጣ ነው።

ከፍተኛ ሙስና (grand corruption) ስሙ እንደሚያመለክተው ከፍተኛና መጠኑ ሰፊ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚመዘበርበትና የሚዘረፍበት የሙስና ወንጀል አይነት ነው። በአፈጻጸሙም ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና ሀብትና እውቀት ያላቸው ግለሰቦች የሚሳተፉበትና በረቀቀ መልኩ የሚፈጸም ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ከፍተኛ ስልጣን ሀብትና እውቀቱ ያላቸው ሰዎች በረቀቀ ስልት የመፈጸምና ምስጢራዊ የማድረግ አቅሙ ስላላቸው ነው። ከፍተኛ ግዢዎች ለምሳሌ የአውሮፕላን፣ የጦር መሳሪያ የቴክኖሎጂ ግዢ፣ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግንባታዎች፣ ወዘተ...፣ ከፍተኛ ሙስና ለመፈጸም የተጋለጡ ናቸው።

State capture *የሚባለው የተወሰኑ ባለሀብቶችና የመንግስት የፖለቲካ ሀላፊዎች በመቀናጀት የመንግስትን ስልጣን ለግል ጥቅም ለማዋል በሚያስችል መልኩ ህግና ፖሊሲ በማውጣት በህጋዊ መንገድ የህዝብ ሀብትን የሚመዘብሩበት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው የሙስና አይነት የሚፈጸምበት ነው።*

ሙስና እንደማንኛውም አይነት ወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊት ቢሆንም ከሌሎች ወንጀሎች ለየት የሚያደርገውና የመዋጋቱን ስራ የሚያከብደው በወንጀሉ ተበዳይ ነኝ ብሎ የሚቀርብ አለመኖሩ አንዱ ችግር ነው። አንድ ሰው ቢገደል ቢያንስ የሞተው ሰው ሬሳ የወንጀሉ ፍሬ ሆኖ ወንጀሉን ለማፈላለግ መነሻ ይሆናል። ሬሳው ቢደበቅ እንኳን ዘመዶች ስለሚኖሩት ወንጀሉ ለመፈጸሙ መነሻ ምክንያት ሆኖ ወንጀሉን ለመመርመር መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ሌብነትና ዘረፋም ተመሳሳይ ናቸው። የሙስና ወንጀልን በሚመለከት ግን ድርጊቱ የሚፈጸመው በመንግስትና በህዝብ ሀብት ላይ ስለሆነ በዚህ ወንጀል ተሳታፊ የሚሆን እያንዳንዳንዱ ግለሰብ ተጠቃሚ ስለሚሆን የሙስና ወንጀል ሲፈጸም ተበዳይ ነኝ የሚል አለመኖሩ ለሙስና ወንጀል መደበቅ ስለሆነም መስፋፋት እንደአንድ ምክንያት ይቆጠራል።

በሙስና መክበር እንደብልጠት በሚቆጠርበት ጊዜ የሙስና ወንጀልን መመርመርና መክሰስ ወንጀልን እንደመከላከል ሳይሆን ሀብት ባገኘ ሰው ላይ በምቀኝነት እንደመቃወም እየተቆጠረ አንዳንድ ጊዜ በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመከራከርም የሚያሳፍርና የሚያሸማቅቅ መሆኑ በሙስና ላይ የሚደረገውን ትግል እንዲከብድ የሚያደርግ ነው።

ሙስናን እንዲዋጋ ሀላፊነት ያለበትን የመንግስት አካል ሰለባ ለማድረግና ለማጥመድ የሚችልበት እድል የተዘጋ አለመሆኑ ሌላው ሙስናን አደገኛ የሚያደርገው ነው።

2. ሙስና ከልማት አንጻር ያለው ፋይዳ (አንድምታ)

እንደሚታወቀው ሙስና ኢ-ሞራል ነው። በኔ ይሁንብህ፣ እጠብቅልሀለው፣ ብሎ አደራና ቃል ገብቶ ያንን ቃል ማጠፍና በታመነበት አለመገኘት የሚወገዝና የሚያሳፍር ስነምግባር ነው። ስለሆነም ሙስና በራሱ መጥፎ የስነምግባር መገለጫ፣ ሰው ሰውን እንዳያምን በማድረግ ማህበራዊ ግንኙነትን አደጋ ላይ የሚጥል ለማንም የማይበጅ ኢ-ሞራላዊ ድርጊት ነው። በዚህ ምክንያት ሙስና መጠላቱና ሙስናን መዋጋት ተገቢ ነው። ስለሆነም ከጥንት ጀምሮ ሙስና ወንጀል ተብሎ የሚታወቅና የሚወገዝ ነው። የአገራችንን የወንጀል ህግ ታሪክ ከፍትሀ ነገስት ጀምሮ ስንመለከተው ሙስና አስጠያፊና ወንጀል መሆኑን ደንግጎአል (ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል የሚለው ያልተጻፈ ህግ ጎን ለጎን አብሮ ያለ ቢሆንም)።

ይሁንና ሙስና ኢሞራል ብቻ ነው ወይ?

ሙስና መንግስት እንደመንግስት የህግና ስርአት ማስከበር ስራውን እንዳይወጣ የሚያደርግ ነው። ሙስና ቃሉ ቀላል ነው እንጂ ሽብርተኝነት፣ ህገወጥ የጦር መሳሪያ ንግድ ዝውውር የተለያዩ እጾች ዝውውር፣ ህገወጥ የሴቶችና ህጻናት ዝውውር ንግድ፣ ኮንትሮባንድ ወንጀሎች በአጠቃላይ ሁሉም አይነት ወንጀሎች እንዲፈጸሙና የሚዋጋቸው እንዳይኖር መንግስትን የሚያሽመደምድ የከፋ ነገር ነው።

የኢንተርፖል ሴክሬታሪ ጀነራል የነበሩት ሚስተር ሮናልድ ኬኔዝ ኖብል በቼክ ሪፐብሊክ ፕራግ በተደረገው አስረኛው የጸረ ሙስና ጉባኤ ላይ ሙስናን በሴብቴምበር 11 ከደረሰው የሽብርተኝነት አደጋ ጋር በማያያዝ የተናገሩት እዚህ ቢጠቀስ አግባብነት ያለው ነው።

> *'If customs, police and security professionals are corrupt, no expense of high-tech devices will provide our citizens the security they deserve. If corrupt public servants provide false identity documents, terrorists will move more freely throughout the world, and all of us and all of our society will remain threatened. … the most sophisticated security systems, best structures, or trained and dedicated security personnel are useless if they are undermined from the inside by a simple act of corruption. The fact is that the strongest fortress will crumble if built upon sand.*

ይህ ጽሁፍ ሙስና ከልማት አንጻር ካለው ተጽእኖ አንጻር የቀረበ ስለሆነ ሙስና በልማት ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት አንጻር የተቀነጨቡ አንዳንድ ነጥቦችን እንመልከት። በሙስና ምክንያት፤

1. ታክስ ወይም ሌላ ለመንግስት መከፈል ያለበት ክፍያ እንዳይከፈል ሊደረግ ይችላል። ከዚህ አንጻር የታክስና የቀረጥ ሰብሳቢ አካላት ባለስልጣናት ለዚህ የተጋለጡ ናቸው። የታክስ መጠኑን እንዲቀንሱ ወይም ጨርሶውኑ እንዳይከፈል እንዲያደርጉ፣ ከታክስ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች ተደብቀው እንዲቀሩ እንዲያደርጉ ሊጠየቁ ይችላሉ። በህገወጥ መንገድ የሚገቡ የኮንትሮባንድ እቃዎችን እያዩ እንዳላዩ ወይም እንዲተባበሩ ሊደረጉ ይችላሉ።
2. ተገቢውን ማረጋገጫ ሳይኖር ሳይከፈል የሚቀር የባንክ ብድር እንዲሰጥ ሊደረግ ይችላል።
3. ሙስና በተለያየ መልኩ ቢፈጸምም ከግዢ ጋር በተያያዘ እንደሚፈጸመው ሙስና ለሙስና የተመቸ ከፍተኛ ኪሳራም የሚያስከትል የለም ማለት ይቻላል። ምክንያቱም መንግስት በበጀት ከሚይዘው ውስጥ ለሰራተኛው የሚከፈለው ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ሲቀር ቀሪው ወይም የበጀቱን ከፍተኛውን

ክፍል የሚይዘው የሚመደበው ለግዢ በመሆኑ ሙስና ለመፈጸም የሚስብ ነው። በአንድ ግዢ የሚገኝ ጥቅም ወይም ጉቦ ሰራተኛው እድሜ ልኩን የሚያገኘው ደመወዝ ተደምሮም እንኳን የማይደርስበት ይሆናል። ከግዢ ጋር በተያያዘ የተቀመጡ የግዢ ህጎችንና ስርአቶችን በመጣስ ውል የሚደረግ ሲሆን፣ ውል ከተፈረመ በኋላም ተገዝተው ለሚቀርቡ እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሚገባው በላይ የተጻፈበት ደረሰኝ በማቅረብ ክፍያ እንዲፈጸም ይደረጋል፣ የእቃው ወይም አገልግሎቱ ጥራት በውል ከተመለከተው ባነሰ ደረጃ ርካሽ እቃዎችን ወይም ተፈላጊነት የሌላቸውን እቃዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል፣ የውል ማሻሻያ በማድረግ በአዲስ ውል ከፍተኛ ግዢ በከፍተኛ ዋጋ ከውድድር ውጭ ውል ይደረጋል።

እነዚህ የሙስና ድርጊቶች ምን ያስከትላሉ?

G. መንግስት ሊያገኘው የሚገባው ገቢ (በታክስና በቀረጥ) ሳያገኝ ይቀራል። በዚህ ምክንያት የገንዘብ እጥረት ስለሚያጋጥመው መንግስት የህግና ስርአት ማስከበር ስራውን፣ መሰረታዊ አገልግሎት የማቅረብ ስራውን፣ የመሰረተ ልማት የመገንባት ስራውን ሳይሰራ ይቀራል ወይም በከፍተኛ ደረጃ ይደናቀፋል።

K. መንግስት ገንዘብ ሲያጥረው ከፍተኛ ታክስ ህግ በሚያከብረው ታክስ ከፋይ ላይ ይጥልና፣ ታክሱ ከአቅሙ በላይ በመሆኑ ወይ ከስሮ ይወጣል ወይም ወደህገወጥ ስራ ውስጥ ይገባል።

N. ህገወጥነት ህገወጥነትን ስለሚወልድ ህገወጥ ንግድን በማደፋፈር ኪራይ ሰብሳቢነትን በማስፋፋት ነጻ ገበያውን ብሎም ህጋዊ የንግድ ስራውን በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳዋል።

S. በሙስና ምክንያት ከሚቀረው የመንግስት ገቢ ተርፋ የምትሰበሰበው ገንዘብ በግዢ መልክ በሙስና ውስጥ ገብታ ደረጃውን ያልጠበቀ ወይም ለምንም አገልግሎት ሊውል የማይችል እቃ ተገዝቶ ይባክናል፣ አልፎ ተርፎም በጥራት ያልተሰራ መሰረተልማት (ለምሳሌ፤ መንገድ ወይም ድልድል በመፍረሱ ወይም የኤሌክትሪክ ሀይል በመቋረጡ በህዝብ ሀብትና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ይደርሳል)

W. ሊመለስ የማይችል የባንክ ብድር እየጨመረ ሲሄድ አስቀማጩ ገንዘቡን ማግኘት ስለማይችል ባንኮች ሊከስሩ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ጠቅላላ የኢኮኖሚ ስርአቱን የሚያናጋበት ደረጃ ያደርሳል።

ረ. እንዲህ ባለ ስርአት ውስጥ የውስጥም ሆነ የውጭ ልማታዊ ባለሀብት የሚጋበዝበት የሚደፋፈርበት ሁኔታ ስለማይኖር ኢንቨስትመንት አይኖርም። ለአገር ኢኮኖሚ ጥቅም በማይሰጡ ነገር ግን በሙስና ገንዘቡን ለመውሰድ ቀላል በሆኑ የስራ ዘርፎች ላይ ገንዘቡ እንዲፈስ ያደርጋል።

ሰ. በከፍተኛ ሙስና የሚዘረፍ የአገር ሀብት ወደውጭ አገር እየሸሸ የአገር ሀብት ይራቆታል።

በአጭሩ ልማቱን ያቆማል ብቻ ሳይሆን ያለችውን ሀብት ወደመቀራመት ስለሚገባ ድህነት እየከፋ ይሄዳል፣ አልፎ ተርፎም ህግና ስርአትን በመፈታተን ወደ አደገኛ የርስ በርስ ጦርነት ሊያስገባ ይችላል።

ሙስና ምን ጉዳት ያደርሳል? ለሚለው የሚከተሉትን ሁለት ታሪኮች መጥቀስ በቂ ነው።

የናይጄሪያው መሪ የነበሩት ጀነራል ሳኒ አባቺ እና ግብረአበሮቻቸው በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከነዳጅ ኢንዱስትሪ በመመዝበር ወደውጭ አውጥተውታል። በናይጄሪያ የነዳጅ ኢንዱስትሪ ዋና የመንግስት የገቢ

ምንጭ ነው። ከ80 በመቶ ያላነሰ የገቢ መሰረቱ ነው። በዚህ ምክንያት የመሰረተልማት አውታሮች በከፍተኛ ደረጃ ተጎድዋል፣ እራሳቸው የመንግስት የነዳጅ ማጣሪያዎች ከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ ገብተዋል። በ1980፣ 800 ዶላር የነበረው የነፍስ ወከፍ ገቢ ከአስር አመት በኋላ ወደ 300 ዶላር ዝቅ ብሎአል።

ሌላው የሚጠቀሰው የኢንዶኔዢያው ሱሀርቶ ስርአት ነው። የመንግስት ባንኮች ገንዘባቸውን የሱሀርቶና ቤተሰቡ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ በማበደር አወጡት። በዚህ መልኩ የወጣው ገንዘብን በወቅቱ መሰብሰብ ሲገባ ውዝፍ እዳዎችን ሳይሰበስቡ በከፍተኛ ደረጃ አደገ። የውጭ ምንዛሪ ብድርን ለመቆጣጠር የወጡ ህጎችን በመጠምዘዝ በከፍተኛ ብድር ተጥለቀለቁ። በመጨረሻ የገንዘባቸው የመግዛት አቅም በ1997 ሲወድቅ የፋይናንስ ስርአቱም መውደቅ ጀመረ። ይህንን ተከትሎ በደረሰው ኪሳራ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰራተኛ ስራ አጥ በመሆኑ ግማሹን የኢንዶኔዥያን ህዝብ ወደድህነት ከተተው።

3. ሙስናን ለመዋጋት የተወሰዱ እርምጃዎችና የኢኮኖሚ እድገት በኢትዮጵያ ባለፉት አምስት አመታት፣

ከ1996 በፊት በኢትዮጵያ ሙስናን በተመለከተ ያለበትን ሁኔታ ለመገመት አንድ የሙስና ሰርቬይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተካሄደ ሲሆን፣ የዚህ የጥናት ሰነድ ዋናው የመረጃ መሰረት በናሙና ከተመረጡ ቤተሰቦች፣ ከንግዱ ህብረተሰብና ከመንግስት ሰራተኞችና ሃላፊዎች በመጠይቅ የተሰባሰበ መረጃ ሲሆን በሰነዱ ከተመለከቱት ግኝቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

የቤተሰብ ተጠያቂዎች፣

- ሙስና አገሪቱ ካጋጠማት ችግሮች መካከል ከዋናዎቹ አንዱ እንደሆነ ጠቅሰዋል።
- አብዛኛዎቹ የቤተሰብ ተጠያቂዎች ጉምሩክ አገልግሎት በጣም ደካማ አገልግሎት እንደሚሰጥ ገልጸዋል።
- ከጉምሩክ ቀጥሎ በቅደም ተከተል መሬት አሰጣጥ፣ ኪራይ ቤቶች ወይም የቀበሌ አከራይ፣ ዳኞች እና የገቢዎች ስብሰባን የሙስና ችግር እንዳላቸው ጠቅሰዋል።
- ከ30-40 በመቶ መላሾች በፍርድ ቤቶች ላይ ከፍ ያለ ቅሬታ ያላቸው ሲሆን ለቅሬታቸው መነሻ የሆነውን ሲጠቅሱ ጉቦ በቁጥር አንድ ሲቀመጥ ሁለተኛ ደረጃ የሰጡት ረጅም ጊዜ የሚፈጀው የፍርድ ቤት መጉላላት ነው። ስለሆነም ፍርድ ቤት ከመሄድ ሌላ የሙግት መፍቻ መንገዶችን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል።
- ጥቂቶቹ (11 በመቶ) ብቻ ሙስና ሲፈጸም ለማንና እንዴት ሪፖርት እንደሚደረግ እናውቃለን ብለዋል። ይሁንና ከእነዚሁ መካከል አብዛኞቹ ሪፖርት አድራጊዎች በሪፖርቱ ላይ እርምጃ አይወሰድም ብለዋል።
- በጥቅሉ 4.5 የሚሆነው ገቢያቸውን ለጉቦና የማይገባ ጥቅም ለመክፈል እንደሚያውሉ የገለጹ ሲሆን፣ ከገቢያቸው 10 በመቶ ሙስናን ለመዋጋት ለማውጣት ዝግጁነታቸውን ገልጸዋል።

የነጋዴው ህብረተሰብ ተጠያቂዎች፣

- የመንግስት አገልግሎት በጥቅሉ ደካማ እንደሆነ ከሁሉም በላይ በጉምሩክ አገልግሎት ማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነ፣ እንደቴሌ ውሀ እና ኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማግኘት ተጨማሪ ጥቅም ለሰራተኞች መክፈል ግዴታ እንደሆነ ጠቅሰዋል።
- በመጀመሪያ ደረጃ በሙስና የሚጠቀሱት ጉምሩክና እና ግብር ሰብሳቢዎች እንደሆነ ሲጠቅሱ፣ መሬት የሚሰጡ፣ ፖሊስና ፍርድ ቤት በተመሳሳይ ደረጃ እንዳሉ ጠቅሰዋል።
- በሁለተኛ ደረጃ የሙስና ችግር ያለባቸው በማለት ትራፊክ ፖሊስ ፣ መብራት፣ ቴሌና ኪራይ ቤቶችን ጠቅሰዋል።
- በሙስና ምክንያት የባንክ ብድር ማግኘት ከባድ መሆኑን የጠቀሱ ሲሆን በጥቅሉ 6 በመቶ ገቢያቸውን አገልግሎት ለማግኘት ለመንግስት ባለስልጣን እንደሚሰጡ ሙስናን ለመዋጋት እስከ 7 በመቶ ገቢያቸውን ለመክፈል ዝግጁ እንደሆኑ ገልጸዋል።

የመንግስት መስሪያ ቤት ተጠያቂዎች፣

- ከ60 በመቶ የሚበልጡት በክፍያቸውና በጥቅማ ጥቅም የሚረኩ አለመሆናቸውን ሲገልጹ፣ አቅማቸውን ለማሳደግ የሚሰጥ ስልጠና አነስተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ግኝቶች ሙስና ዋነኛ ችግር መሆኑን ያሳየ ሲሆን፣ በሰርቬዩ ከዚህ በመነሳት ምን መደረግ እንዳለበት የመፍትሄ ሀሳቦችን ጠቁሟል።

1. ሙስናን ለመዋጋት ወደተግባር የሚተረጎም ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት፣
2. ተገልጋይ ማወቅ የሚገባውን እንዲያውቅ ማድረግ፣ ቅሬታ የሚሰማበትና የሚወሰንበት ስርአት መዘርጋት፣
3. ህዝቡን በመንግስት ስራ ላይ አስተያየት ለመስጠትና ለመተቸትና ለማረም እንዲችል የሚሳተፍበት ስርአት መዘርጋት፣ ለዚህም የሚዲያውና ሲቪል ሶሳይቲው ተሳትፎን ማሳደግና ማጎልበት፣
4. በሲቪል ሰርቪሱ ፖለቲካውንና ሙያውን በግልጽ የሚለይ አሰራር መዘርጋት፣
5. ብቃት ያለው የመንግስት አገልግሎትለመስጠት፣የመንግስት ሰራተኞች ክፍያ ማሻሻል፣ የመንግስት ሰራተኞችን በእውቀት፣ በክህሎትና በስነምግባር በተከታታይ አቅማቸውን ማሳደግ፣
6. ህዝቡ ማንነቱን ሳይገልጽ ሙስና ስለመፈጸሙ የሚጠቁምበት ስርአት መዘርጋት ወይም ከለላ መስጠት
7. የስነምግባር ጉዳይን የሚከታተል አካል ማቋቋም፣
8. በመጥፎና በጥሩ በተለዩት ተቋማት ዝርዝር ጥናት በማድረግ የችግሩን ምንጮች መለየትና መፍትሄ ማፈላለግ፣
9. ተጠያቂነት ያለው ጠንካራ የዳኝነት ስርአት መፍጠር፣ ወዘተ ተጠቅሰዋል።

ይህ የሙስና ሰርቬይ በተሰራበት ወቅት ጎን ለጎን (ከ1992-1994) የተፈጸመ ታሪካዊ ሁኔታ አለ። በገዢው ፓርቲ ውስጥ የተካሄደውን የተሀድሶ እንቅስቃሴ ተከትሎ ልማትና ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ የህልውና ጥያቄዎች መሆናቸውን በማስመሰከር ፈጣን ልማትን፣ ሰላምን፣ ዴሞክራሲንና መልካም

አስተዳደርን በፍጥነት ለመገንባት ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት እና የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ፖሊሲና ስትራተጂ ተዘጋጅቶ ይፋ ተደርጓል።

የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታ ፖሊሲና ስትራተጂ ተዘጋጅቶ ይፋ ሲሆን ሲቪል ሰርቪሱን የማሻሻልና ተጠያቂ የማድረግ ፕሮግራም ግን ቀደም ብሎ የተጀመረ ነበር።

የሲቪል ሰርቪሱን ሁለንተናዊ ገጽታ በስርአት ማጥናት እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ በህዳር ወር 1987 የአገሪቱን የሲቪል ሰርቪስ አደረጃጀትና አሰራር የሚያጠና ግብረሀይል መቋቋሙ ይታወሳል። ይህ ግብረ ሀይል በወቅቱ የሲቪል ሰርቪሱን ችግር በዘርፍ በዘርፍ በመለየት እንዲሁም በቀጣይነት መወሰድ ያለባቸው ተግባራትን ያካተተ የጥናት ውጤት አቅርቦአል።

በጥናት ውጤቱም የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲካሄድ የሚጠይቅ ሲሆን በዚሁ መሰረት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ተቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ተጀምሮአል። የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አምስት ንኡሳን ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን፣ እነርሱም

1. የስራ አመራር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም
2. የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም
3. የወጪ አስተዳደር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም
4. የሰው ሀይል አስተዳደር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም
5. የስነምግባር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም

ናቸው። (ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመለከተው የሰርቬይ ውጤት በስነምግባር ንኡስ ፕሮግራም ውስጥ ተይዘው ከነበሩ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው።)

በግብረ ሀይሉ በቀረበው የጥናት ውጤት ከስነምግባር ጋር የተያያዙ ተብለው የቀረቡት ችግሮች

1. የተሟላ የሲቪል ሰርቪስ ስነምግባር ደንብ አለመኖሩ፣
2. የበላይ ስራ አመራር የሚያወጣቸው መመሪያዎች መከበራቸው የሚረጋገጥበት ስርአት አለመዘርጋቱ፣
3. ፈጻሚ አካላት የሚያደርጉት ቁጥጥር ደካማ መሆኑ፣
4. የስራ ቁጥጥርና ኦዲት የሚያደርጉ ተቋማት የሰው ሀይል እጥረት ያለባቸው መሆኑ፣
5. ከኦዲትና ከቁጥጥር አካላት የሚቀርቡ ሪፖርቶች አይቶ እርምጃ የመውሰድ ድክመት መኖሩ፣ የሚሉ ነበሩ።

ከዚህ መሰረታዊ ችግር በመነሳትም ስነምግባርን ማእከል ያደረገ የስነምግባር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሙ አንድ አካል ሆኖ እንዲቀረጽ ሆኖአል።

እነዚህ የተቀመጡ አቅጣጫዎችን ተከትሎ ባለፉት አምስት አመታት ምን ተከናውኗል? አንዳንዶቹን ለመጥቀስ፣

- ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች አሰራራቸውን የተገልጋይን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ ለማሻሻል የሪፎርም ጽ/ቤቶች በማቋቋም በመስሪያ ቤታቸው የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ

ፕሮጀክቶች ቀርጸው ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አዲስ የአገልግሎት አሰጣጥ በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለውጦች መታየት ጀምረዋል።

- ተገልጋዮች ቅሬታ የሚያቀርቡበት ስርአትም በየመስሪያ ቤቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው።
- የንግድና ኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ አገልግሎት ላይ በተደረገው ማሻሻያ ተገልጋዮች በቀላሉ አገልግሎት ለማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥራል።
- የወጪ አስተዳደርን ለማሻሻል ታቅደው የነበሩ ፕሮጀክቶች አብዛኛዎቹ ተጠናቀው አስፈላጊው ህግና ደንብ ወጥቶላቸው ተግባራዊ መሆን የጀመሩ ሲሆን፣ ከእነዚህ አንዱ የመንግስት ግዢ ስርአትን የሚደነግገው የግዢ ህግ አንዱና ተጠቃሽ ነው።
- የሰው ሀይል አስተዳደርን በተመለከተ የሲቪል ሰርቪስ ህጉ ተጠንቶ የተሻሻለ ሲሆን፣ ከአራት አመት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ በድጋሚ እንዲሻሻል ተደርጎአል። የሲቪል ሰርቪሱ የደመወዝ ስኬልም ጎን ለጎን እንዲሻሻል ተደርጓል። የመንግስት ሰራተኞችን አቅም ለማሳደግ የተለያዩ ስልጠናዎችም ከቀድሞው በተሻለ ሁኔታ ለመስጠት በርካታ የስልጠና ተቋማት የተቋቋሙ ሲሆን፣ ሰራተኞችም በዚህ የስልጠና ፕሮግራም እንዲሳተፉ ተደርገዋል።
- የስራ መሪዎች በስትራቴጂክ ፕላን ዝግጅት፣ ፐርፎርማንስ ማናጅመንት ስፋት ባለው መልኩ የስልጠና ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።

በስነምግባር ንኡስ ፕሮግራም ለማስፈጸም ስድስት ፕሮጀክቶች የተቀረጹ ሲሆን እነርሱም፣

1. የስነምግባር ደንብ ፕሮጀክት
2. የማእከላዊ አካል ማቋቋሚያ ፕሮጀክት
3. የመገናኛ ብዙሀን አቅም ግንባታ ፕሮጀክት
4. የፖሊስ የአቃቤ ህግና የፍ/ቤቶች አቅም ግንባታ ፕሮጀክት
5. የስነ ምግባር ትምህርት ፕሮጀክት እና
6. የሙስና ሰርቬይ ፕሮጀክት

ነበሩ።

እነዚህን ፕሮጀክቶች በሚመለከት የተወሰኑት ተጠናቀው ወደስራ የተገባ ሲሆን አንዳንዶቹ በሂደት ላይ ናቸው። አንዳንዶቹን ለመጥቀስ፣

1. **የስነዜጋና የስነምግባር ትምህርት በትምህርት ቤት በመደበኛ ትምህርት እንዲሰጥ በካሪኩለም ውስጥ እንዲካተት ተደርጎ ትምህርቱ በመሰጠት ላይ ነው።**
2. የተባበሩት መንግስታት የጸረ ሙስና ኮንቬንሽንና የአፍሪካ ህብረት የጸረ ሙስና ኮንቬንሽን በተወካዮች ምክር ቤት ጸድቀው የአገሪቱ ህግ አካል ሆነዋል።
3. የሙስና ወንጀልን በብቃት ለመዋጋት ይቻል ዘንድ የአለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ባካተተ መልኩ በ1997 በወጣው የወንጀል ህግ ተበታትነው ይገኙ የነበሩ ዋና ዋና የወንጀል ድርጊቶችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ የሙስና ወንጀሎች በዝርዝር እራሱን ችሎ እንዲወጣ የተደረገበት የወንጀል ህግ ወጥቶአል። አዳዲስ የሙና ወንጀሎችም እንዲካተቱ ተደርገዋል። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ፣
   - ምንጩ ያልታወቀ ሀብትና ንብረት ይዞ መገኘት
   - ስጦታ መስጠትና መቀበል

- ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት

ናቸው።

4. የአለምአቀፍ ተሞክሮዎችን መሰረት ባደረገ መልኩ የሙስና ወንጀልን ለመመርመርና ለመክሰስ የሚበጁ የስነስርአትና የማስረጃ ህጎች እንዲወጡ ተደርገው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ናቸው። ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ፣
   - በሙስና የተገኘ ገንዘብን ለመውረስ እንዲቻል ንብረት ስለሚታገድበትና ስለሚወረስበት ሁኔታ፣
   - በሙስና ወንጀል ተባባሪ የሆነን ግብረ አበር ከተከሳሽነት ወደምስክርነት መቀየር ስለሚቻልበት ሁኔታ፣
   - በሙስና ወንጀል የማስረዳት ሸክምን ስለማዛወር፣

   ናቸው። ሙስናን ለመዋጋት በስራ ላይ ከዋሉት አሰራሮች አንዱ በሙስና ወንጀል የተጠረጠረ የዋስትና መብት እንደማይኖረው ይደነግግ የነበረው ድንጋጌ ነው። ይህ ድንጋጌ መንግስት ሙስናን ለመዋጋት ከሚገባው በላይ ሀይለኛ ሆኖአል ተብሎ ትችት የቀረበበት እንደሆነም ይታወቃል። ህጉ ተሻሽሎ በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስትና የመለቀቅ መብት ቢኖረውም አሁንም ቢሆን የሙስና ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው በዋስትና የመለቀቅ መብቱ ከሌላው አይነት የወንጀል ተጠርጣሪ የጠበበ ነው።

በስነምግባር ንኡስ ፕሮግራም ውስጥ ከተያዙት ፕሮጀክቶች አንዱ አንድ ስነምግባርን የሚከታተል ማእከላዊ አካል ማቋቋም ሲሆን የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን የዚህ ፕሮጀክት ውጤት ነው።

ኮሚሽኑ የተቋቋመበት አላማ የሚከተሉት ናቸው።

1. መልካም ስምግባርና የጸረ ሙስና ትምህርቶችን ማስፋፋት
2. የሙስና ወንጀልና ብልሹ አሰራርን መከላከል
3. የሙስና ወንጀልና ብልሹ አሰራርን ማጋለጥ መመርመርና መክሰስ

ከፌዴራሉ በተጨማሪ በአምስት ክልሎች የጸረ ሙስና ኮሚሽኖች ተቋቁመው በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ሲሆን፣ በ267 የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች የስነምግባርና የጸረ ሙስና እንቅስቃሴን የሚያስተባብሩ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተቋቁመው በመስራት ላይ ይገኛሉ።
ሙስናን በሚመለከት ህብረተሰቡ ሁልጊዜም የመነጋገሪያ አጀንዳ እንዲያደርገውና የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ስለሙስናና መልካም ስነምግባር የማስተማርና የማስተዋወቅ ስራ በተለያዩ ሚዲያዎች ላለፉት አምስት አመታት ባለማቋረጥ በመሰጠት ላይ ነው። ከዚህ አንጻር፣

1. ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ጀምሮ ከ100 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለተውጣጡ ኢትዮጵያውያን በፊት ለፊት ትምህርት ስለሙስናና መልካም ስነምግባር ትምህርት ተሰጥቷል።
2. በትምህርት ቤቶች በተማሪዎች በፈቃደኝነት የስነምግባርና ስነዜጋ ክበባት የተቋቋሙ ሲሆን፣ ይህም በየጊዜው እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው።
3. ስለሙስና ጎጂነትና ስለመልካም ስነምግባር የሚያስተምሩ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ብሮሸሮች፣ መጽሄት፣ ፍላየሮች እና ፖስተሮች ተሰራጭተዋል።

4. ኮሚሽኑ በ50 የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ለሙስናና ብልሹ አሰራር በሚያጋልጡ አሰራሮች ላይ ጥናት በማድረግና አሰራሮቹ ስለሚሻሻሉበት ሁኔታ ከመስሪያ ቤቶቹ ጋር ውይይት በማድረግ አሰራሮቹን የሚሻሻሉበትን አቅጣጫ በጋራ በመቀየስ በመስራት ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ የጉምሩክ ባለስልጣን፣ የአገር ውስጥ ገቢ፣ የንግድና የልማት ባንክ፣ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ የመብራት ሀይል ኮርፖሬሽን እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ይገኙበታል።
5. በክልል ያሉትን እንቅስቃሴዎች ሳይጨምር ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ 405 በሚሆኑ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ላይ ክስ መስርቶ 100 በሚሆኑት ላይ ከ8 ወር እስከ 18 አመት የሚደርስ ቅጣት እንዲወሰን ተደርጓል።
6. የሙስና ወንጀልን በመጠቆማቸው በቂም በቀል 40 በሚሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ላይ የተወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃው በኮሚሽኑ እንዲሰረዝ ወይም እንዲታገድ ተደርጓል።

እነዚህ ከዚህ በላይ የቀረቡት መረጃዎች በአጠቃላይ መልካም አስተዳደርን ከማስፈንና ሙስናን ከመዋጋት አንጻር ባለፉት አራት አመታት የተወሰዱትን ጎልተው የሚታወቁትን እርምጃዎች ለውይይት መንደርደሪያ እንዲሆን ተብለው የተጠቀሱ እንጂ መረጃዎቹን በዝርዝር ለማቅረብ አልተሞከረም።

ይሁንና ሙስናን ለመዋጋትና በቁጥጥር ስር ለማዋል ዋናው መሳሪያ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ስርአትን መመስረት ነው። እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት እርምጃዎች በሙስና ሰርቬይ በመፍትሄነት ከቀረቡት የመፍትሄ ሀሳቦች ጋር የሚጣጣሙ እንዲሁም ሙስናን ለመዋጋትና ለመቀነስ ፍቱን መሳሪያዎች ተብለው በአለምአቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ ስትራተጂዎች ናቸው። ስለሆነም ሙስናን ለመዋጋት የተወሰዱት እርምጃዎች የተፈለገውን ውጤት ለማምጣት በሚያስችል ጎዳና ላይ እንደምንገኝ ቢቀመጥ ምክንያታዊ ድምዳሜ ነው።

እነዚህ እርምጃዎች የተወሰዱ ቢሆንም፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስፈልገው ሁሉ ተሰርቷል ወደሚል ድምዳሜም ማምራት የተሳሳተ ይሆናል። እነዚህ እርምጃዎች እየተወሰዱ ቢሆንም፣ በአፈጻጸም ደረጃ ጉድለቶች የሚታይባቸውና መሻሻል የሚገባቸው፣ እስካሁን ጨርሶውኑ ወደተግባር ያልተገባባቸው እቅዶች እንዳሉ መረዳት፣ ከአሁን በኋላ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ረጅምና አድካሚ ጉዞ እንደሚጠብቅ ማስታወስ ተገቢ ነው።

እነዚህ ተቀባይነት ያላቸው እርምጃዎች በእርግጥም ያመጡት ለውጥ ምን ያህል ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት አንዱ መለኪያ መንገድ ህብረተሰቡ ላይ የተፈጠረው የአመለካከት ለውጥ ነው። ህብረተሰቡ ሙስናን በሚመለከት ከዛሬ አምስት አመት በፊት ከነበረው አስተሳሰቡ ተለውጦአል? ለሚለው ጥያቄ ይህንን በሚመለከት ይህ ጽሁፍ እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ የተደረገ ሁለተኛ ሰርቬይ ስሌለለ ይህንን ጥያቄ አሁን መመለስ አይቻልም።

ሌላው መለኪያ የሙስና መጨመር ቢኖር ሊያስከትለው ከሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ አንጻር መገምገም ነው። በዚህ ጽሁፍ ለማመልከት እንደሞከርነው ሙስና እየጨመረ በሚሄድበት ሁኔታ የኢኮኖሚ ልማት ሊኖር እንደማይችል ነው። ከዚህ አንጻር በኢኮኖሚው በኩል ያለውን ለውጥ መመልከት የተወሰኑ ነገሮችን ሊያመላክት ይችላል።

የመጀመሪያው የሙስና ሰርቬይ ከተካሄደ በኋላ የኢኮኖሚ እድገታችንን በሚመለከት መረጃዎች የሚያሳዩት ምንድነው?

ብሄራዊ ባንክ የ1999 አ.ም የመጀመሪያ ስድስት ወር ሪፖርት ባቀረበ ጊዜ የማክሮ ኢኮኖሚው ባለፈው አራት አመታት ያስመዘገበውን እድገት በተመለከተ የሚከተለው ይመስላል።

1996	11.9 በመቶ
1997	10.5 በመቶ
1998	9.6 በመቶ
1999	10.1 በመቶ

የዚህ ተከታታይ እድገት ዋና መሰረት ግብርናው ሲሆን በእድገቱ በዋነኛነት ተጠቃሚ የሆነው በግብርናው ላይ የተሰማራው የሰው ሀይል መሆኑ ሌላው የእድገቱ አዎንታዊ ጎኑ ነው።

ለዚህ እድገት አንዱና ዋናው ምክንያት የተቀመጠው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው።

ይሁንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ ሙስናን ለመዋጋት ባለፉት አራት አመታት የተወሰዱት እርምጃዎች በልማቱ ላይ ያላቸው ፋይዳ ምንድነው? ይህንን በሚመለከት በዳታዎች የተደገፈ ጥናት ማድረግን ይጠይቃል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በንድፈ ሀሳብም ሆነ በተግባር ተደግፈው የሚቀርቡት መረጃዎች የሚያሳዩት ሙስና የኢኮኖሚ እድገትን እንደሚገታና እንደሚያቆም ነው። ከዚህ መንደርደሪያ በመነሳት ኢኮኖሚው በተከታታይ ለአራት አመታት ያመጣው ለውጥ ሲታይ ላለፉት አራት አመታት ሙስናን ለመዋጋት በመንግስት የተወሰዱ እርምጃዎች ውጤታማ ናቸው የሚል ግምት ብናሳድር ተገቢ አይሆንም?

ይሁንና ይህ ግምት ነው። አንዳንድ ወገኖች ጉቦና ሙስና ስራን ስለሆነም ልማትን ለማቀላጠፍ ይረዳል ብለው እንደሚከራከሩ በመግቢያው ላይ ለማንሳት ሞክሬያለሁ። ስለሆነም ያለፈው አራት አመት የኢኮኖሚ እድገትና የሙስና መቀነስ ምክንያታዊ ትስስር የላቸውም ሊባል ይችላል። የመንግስት ሰራተኞች ጉቦ ሊያገኙ እንደሚችሉ ሲያውቁ የስራ ሂደቱን ያሳጥሩታል? የተቀላጠፈ አገልግሎት ይሰጣሉ?

ምናልባት በተወሰነ ደረጃ የተቀላጠፈ አገልግሎት ሊገኝበት ይችል ይሆናል። ይሁንና ጉቦን የለመደ ሰራተኛ ስራውን ከማቀላጠፍ ይልቅ በየደረጃው የሚያገኘውን ህገወጥ ጥቅም መጠን ለማሳደግ መጣሩ አይቀርም። ሌሎችም በየደረጃው የሚገኙ ሰራተኞች አብዛኛዎቹ ድርጊቱ በአጭሩ ካልተገታ የዚህን ሰው አርአያ መከተላቸው አይቀርም። በዚህ ምክንያት በየደረጃው የሚጠየቀው ጉቦና ስጦታ አገልግሎትን የተቀላጠፈ ከማድረግ ይልቅ እንደሚያወሳስበው መገመት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ በጉቦና በስጦታ ላይ የተመሰረተ አመለካከት ያለው የመንግስት ሀላፊ ጥራቱን ያልጠበቀ እቃ እንዲገባ፣ ደረጃውን ያላሟላ ሰው ፈቃድ እንዲያገኝ በማድረግ በአቋራጭ ለሚከብሩ ሁሉ መንገድ የሚከፍት በዚህም ምክንያት ለልማታዊ

ባለሀብቱ ሳይሆን በአቋራጭ ለሚከብረው መንገድ የሚከፍት ነው። ይህም ልማትን የሚያመጣ ሳይሆን ውድቀትን የሚያመጣ ነው።

ስለሆነም ወደፊት በዝርዝር የሚደረጉ ጥናቶች የሚያሳዩን መረጃዎች እንደተጠበቀ ሆኖ የኢኮኖሚ እድገቱ መንግስት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እና ሙስናን ለመቆጣጠር እየወሰደ ያለው እርምጃ ትክክል መሆኑን አንድ አመላካች ነው ቢባል ኢ-ምክንያታዊ አይሆንም።

ይህ ማለት ግን ከዚህ በኋላ ሙስና ሊያሰጋን አይገባም ማለት አይደለም። ኢኮኖሚው እያደገ ሲሄድ ሊበላ የሚችለው ገንዘብ እየጨመረ ሲሄድ ማባበሉና ማጓጓቱ አዳዲስ ሞሳኞችን መፍጠሩ አይቀርም። ሙስና በባህርዩ የሚጠፋ ሳይሆን፣ ከሰው ልጅ አመለካከትና እምነት ጋር የሚሄድ ስትዋጋው የሚቀንስ፣ ስትዘናጋ ደግሞ ተመልሶ የሚያብብና የሚስፋፋ እንጂ የሚሞት ቫይረስ አይደለም። ስለሆነም ሳንዘናጋ ነቅተን ሁልጊዜም ልንጋዋጋው ይገባል።

4. ማጠቃለያና የወደፊት አቅጣጫ

ሙስና የስነምግባር መላሸቅ ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ወንጀሎች የከፋ ማለትም መንግስት ሀላፊነቱን በአግባቡ እንዳይወጣ በማድረግ በተለይም ህግና ስርአት የማስከበር አቅሙን በማሽመድመድ ሌሎች ወንጀሎች እንዲስፋፉ የሚያደርግ ከሁሉም ወንጀሎች የባሰ ከባድ ወንጀል ነው።

ሙስና መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ በማድረግ፣ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለህዝብ እንዳያቀርብ የሚያደርግ፣ ተገልጋይ ፍትሀዊ አገልግሎት ማግኘት እንዳይችል በሚያደርግ፣ በአጠቃላይ የእድገትና ልማት እንቅስቃሴዎችን አንቆ በመያዝ አገርን ወደድህነት የሚመራ ነው።

በኢትዮጵያ ሙስናን ለመዋጋት የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ተቀርጸው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ። እንቅፋትና ችግሮች ቢያጋጥሙም በጥቅሉ ሲታይ መልካም አስተዳደር ለማስፈንና ሙስናን ለመዋጋት የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ለውጦችን በማሳየት ላይ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ላለፉት አራት አመታት በተከታታይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ሲሆን ይህ ፍጥነት በተያዘው ደረጃ እንዲቀጥል ሙስናን እስከአሁን ከነበረው ጥረት በበለጠ ደረጃም መዋጋት ይገባል።

ምን እናድርግ?

ይህ ጽሁፍ በኢኮኖሚስቶች ማህበር በተዘጋጀ መድረክ ላይ የቀረበ በመሆኑ ምን እናድርግ? ለሚለው በተለይም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራት ምን ይጠበቃል በሚለው ላይ ባተኮረ መልኩ ሀሳቤን ላስፍር፣

1. ሙስናን በቁጥጥር ስር ለማዋል የመጀመሪያውና ትልቁ ነገር ሙስና የልማት ጠር መሆኑን መረዳትና የሚበዛው የህብረሰብ ክፍል ይህንን ለመዋጋት የተዘጋጀ መሆን መቻሉ ነው። ህብረተሰቡ ያልደገፈው፣ ያልተዋጋው የጸረ ሙስና እንቅስቃሴ የትም አይደርስም። ከዚህ አንጻር ሲቪል

ማህበረሰቡ ከፍተኛ ሀላፊነት ተሸክሟል። ህዝቡን በማሳወቅና በማስተማር፣ የሙያ ስነምግባር እንዲከበርና እንዲጠበቅ በማድረግ፣ የሙያ ስነምግባርን የሚጥሱትን ባለሙያዎች ሳይፈራና ሳይሸማቀቅ በማጋለጥ፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ያሉ የሙስናና መሰል ድርጊቶችን በማጋለጥና ህብረተሰቡ የነቃ የጸረ ሙስና ታጋይ እንዲሆን በማድረግ ከፍተኛ አቅም አለው።

2. ሙስናን ለመዋጋት ሌላው ትልቁ መሳሪያ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር መዘርጋት ነው። ከዚህ አንጻር መንግስት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ዘርግቶ በመተግበር ላይ ሲሆን፣ ውጤቱም ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት መታየት ጀምሯል። በተለይም ኢንቨስትመንትን በሚመለከት ባለፉት ሶስትና አራት አመታት የታዩት ለውጦች አበረታች ናቸው። ይህ በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚሰራ ቢሆንም የሲቪል ማህበረሰቡ እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴዎችን በመደገፍ በሚታዩ ድክመቶችና ጉድለቶች ላይ በተጠናና ጥቅምና ጉዳቱን ባነጻጸረ መልኩ መተቸትና መምከር፣ በጥናት መደገፍ ይገባዋል።

3. ሙስና የሚፈጽሙትን ያለርህራሄ ማጋለጥና ለፍርድ ማቅረብ ይገባል። በዚህ ጽሁፍ ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው እያንዳንዷ መዘናጋት ሙስና እንደገና እንዲያብብ የምታደርግ ነች። ስለሆነም ሙስና የሚፈጽሙትን ያለርህራሄ መዋጋት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር ሙስና የሚፈጽሙት ሰዎች ከመርማሪ ሊሰወሩ ይችሉ ይሆናል እንጂ ከህብረተሰቡ የሚሰወሩ አይደሉም። ስለሆነም ህብረተሰቡ የሙስና ወንጀል ፈጻሚዎችን ለማጋለጥና ለፍርድ ለማቅረብ የሚደረገውን እንቅስቃሴ እንዲደግፍ፣ መረጃ በመስጠት በመጠቆም እንዲተባበር ለማነሳሳትና ለማደራጀት የሲቪል ማህበረሰቡ የማይተካ ሚና ይጫወታሉ።

ዋቢ ጽሁፎች

1. የተሻሻለው የፌዴራል የስነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97
2. የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርአትና የማስረጃ ህግ ቁጥር 434/9
3. የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ 1997
4. በአቅም ግንባታ ሚኒስትር የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ የስነምግባር ንኡስ ፕሮግራም ጥራዝ (2 ቅጽ)
5. ሲቪል ሰርቪሱን ለማሻሻል የተመረጠው ግብረ ሀይል ያቀረበው ሪፖርት
6. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ (1999) የመጀመሪያው 6 ወራት የስራ እቅድ ክንውን
7. Profile of the FEACC. November,2006.
8. corruption survey in Ethiopia, by Institute of Educational Research Addis Ababa University, December 2001.
9. Corruption and Development: An Impolitic View By Dennis de Tray For the 1818 Society Fall Luncheon November 16, 2006.
10. Daniel Kaufmann, Corruption: The Facts
11. UNITED NATIONS *Office on Drugs and Crime* THE GLOBAL PROGRAMME AGAINST CORRUPTION UN ANTI-CORRUPTION TOOLKIT 3nd Edition, Vienna, September 2004.

12. Garbis Korajian , Good Governance, Transparency and Reform Measures to Enhance Accountability In Ethiopia A Six-Day Course Manual Revised Draft Prepared by July 28, 2003.
13. J. Brian Atwood, corruption: a persistent development challenge, Economic perspectives A USIA electronic Journal, v. 3, no.5, Nov. 1998.

በኮሚሽነር አሊ ሱሌይማን ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

መድህኔ ታደሰ[1]

በኮሚሽነር አሊ ሱሌይማን 'ሙስና እና ልማት በኢትዮጵያ' በሚል ርዕስ የቀረበው ጽሁፍ ብዙ ጠቃሚ ሃሳቦች የያዘና በብዙ አጥኚዎች ያልተዳሰሰ አዲስ ርዕስ ነው። ከዚህ አንፃር በር ከፋችነቱ አያጠራጥርም። ጽሁፉ በመግቢያው ላይ በሚገባ ከዳሰሳቸው ርዕሶች ውስጥ የሙስና ትርጉምና መገለጫዎቹ፣ የሙስና ዓይነቶችና ሙስና ከልማት አንፃር ያለው ፋይዳ (እንድምታ) ይገኙበታል። በአጠቃላይ ሙስና ምን ማለት እንደሆነና በልማት ላይ በተለይም በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ላይ የሚያሳርፈው አሉታዊ ተጽዕኖ ለመዳሰስ ሞክሯል።

ይህ ዳሰሳ ከአጠቃላዩ የዓለም ዓቀፍ ስምምነት (በጉዳዩ ላይ) እምብዛም የማይርቅና አዲስ የሚባል ግኝት ካለመሆኑ ጋር ተዳምሮ የጽሁፍ አቅራቢው ጠንካራና ደካማ ጎን ከመለየት አንፃር እምብዛም አይረዳም። ከዚህ አንፃር በጽሁፉ ላይ ያለኝ አስተያየት የሚያተኩረው ዋናው ርዕስ ጉዳይ በሆነው 'ሙስናና የኢኮኖሚ እድገት በኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት' በሚለው ላይ ይሆናል።

የጽሁፉ አቅራቢ በኢትዮጵያ ያለውን የሙስና ሁኔታ ሲገልጹ ከሙስና ጋር በተያያዘ የሚጠቀሱ የቀድሞ ከፍተኛ ባለስልጣናት መኖራቸውን በመጠቆም እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሚያያዝ ግን ሳያብራሩ ያልፉታል። ቀጠል ያደርጉና ከጥቂት ዓመታት በፊት በተደረገ ጥናት ብዙ ኢትዮጵያውያን የመንግስት አገልግሎት ለማግኘት ጉቦ እንደሚከፍሉ ማስታወቃቸውን ይገልጻሉ። ሁለቱም ማለትም የከፍተኛ ባለስልጣናት ስም መነሳትና ተደረገ የተባለው ጥናት የፈነጠቃቸው ሐቆች ተያያዥነትና ልዩነት ለመዳሰስ አልተሞከረም። ስለዚህ በአንድ በኩል ከፍተኛ የቀድሞ ባለስልጣናት የሚጠቀሱበት በሌላ በኩል ደግሞ ጥቃቅን ጉዳዮች (Petty Corruption) የተንሰራፋበት የሚመስል ግልጽ ያልሆነ የሙስና ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ያመላከተ አቀራረብ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የጽሁፉ አቅራቢ በመግቢያቸው ከዘረዘርዋቸው የሙስና ዓይነቶች ውስጥ የትኛው ዓይነት የኢትዮጵያን ሁኔታ ሊገልጽ እንደሚችል ያመላከቱት ነገር የለም። የኢትዮጵያ ሁኔታ ከየትኛው ደረጃ ጋር ወይም በዚህ ጉዳይ ላይ ከሚጠቀሱት አገሮች በየትኛው ረድፍ እንደምንገኝ ያሉት ነገር የለም። ከዚህ አንፃር በየትኛው ችግር ላይ ርብርብ እንደሚደረግ አይታወቅም።

[1] ረዳት ፕሮፌሰር መድህኔ ታደሰ Center for Policy Research and Dialogu የሚባል ለትርፍ ባልተቋቋመ ተቋም ውስጥ የሰላምና ደህንነት ዲቪዥን (Peace & Security Division) ዳይሬክተር ናቸው። ረዳት ፕሮፌሰር መድህኔ ታደሰ በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ የታሪክ መምህር ሆነው በረዳት ፕሮፌሰርነት አስተምረዋል። በአፋሪካ ቀንድ በግጭትና ደህንነት (Defence, Conflict and Security) ተመራማሪ ናቸው። በርካታ መጽሐፍ አሳትመዋል። የተለያዩ መጣጥፍ (Article) በጆርናል እና በተለያዩ ህትመቶች አውጥተዋል።

ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ፀሃፊው በአገራችን ሙስናን ስርዓት ባለው መልኩ ለመዋጋት ጥረት መጀመሩን ያወሳሉ። ቀጠል አድርገውም የኢትዮጵያ መንግስት ሙስናን ለመዋጋት ያደረገውን ጥረትና የወሰዳቸውን እርምጃዎች ይዘረዝራሉ። የፌዴራል ስነ - ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን መቋቋም የዚህ ውጤት መሆኑና የዓለም ዓቀፍ ተሞክሮዎችን መሰረት ባደረገ መልኩ የሙስና ወንጀልን ለመመርመርና ለመክሰስ የሚበጁ የስነ - ስርዓትና የማስረጃ ህጎች እንዲወጡ ተደርገው ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ።

የጽሁፉ ድክመቶች

- የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታን አልዳሰሰም
- የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ፣ የመንግስት ባህሪ፣ ፖሊሲዎች አስፈፃሚ አካላትና የተፈጠሩት ተቋሞች ሁኔታ አይዘረዝርም
- የሙስና ዓይነትና መጠን በኢትዮጵያ አልተገለፀም። ስለሆነም ችግሩ የሚገኝበት ደረጃ፣ ችግሩን ለመቋቋም መወሰድ ስላለበት እርምጃ ጠንቅቆ ለመረዳት አዳጋች ያደርገዋል።
- ሙስናን ለመዋጋት መንግስት ወሰዳቸው የተባሉት እርምጃዎች ውጤት በሚገባ አልተጠናም። ሙስናን ለመዋጋት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት የሚደግፍ ቢሆንም ከችግሩ ጋር የማይዛመድናያልተመጣጠነ አሰራር ከተዘረጋ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ማብራራት ያስፈልግ ነበር።

እ.ኤ.አ. በ2004 በተደረገው ጥናት በኢትዮጵያ ያለው የሙስና ሁኔታ በጣም የተጋነነና መንግስት የመወሰዳቸው እርምጃዎችም ከችግሩ ጋር እንደማይመጣጠን (over reaction) ውጤቱም የንግድና የኢንቨስትመንት ዝውውሩን እንደጎዳ፣ የውጭና የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ተነሳሽነት እንዳዳከመ (በተለይ business confidence የሚባለውን እንደነካ) እንዲሁም ከህግ የበላይነት አንፃር ጉዳት እንደነበረው ያመለክታል። ይህ በውጭ ዓለም ዓቀፍ ተቋሞች የተደረገው ጥናት ሙስና በኢትዮጵያ ደረጃ በነፃና ትክክለኛ ጥናት ላይ የተመሠረተ መረጃ ሳይኖር የሚደረግ እንቅስቃሴ ብዙ አሉታዊ ጎኖች ሊኖሩት እንደሚችልና ልማትን ማገዝ ሳይሆን ልማትን የሚጎተት ሚና ሊጫወት እንደሚችል የጠቆመ ይመስለኛል።

ሆኖም ግን የሙስና ሁኔታ በአጠቃላይና የትኛው የሙስና ዓይነት (ማለትም Petty Corruption, Grand Corruption n እና State Capture ከሚሉት መካከል) በኢትዮጵያ ውስጥ ተስፋፍቶ እንደሚገኝ ባልተገለፀበት ሁኔታ ሙስና በመዋጋት ረገድ የተገኘው ውጤት ብሎም ይህ ውጤት ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ተያያዥነት እንዳለው መገለጹ በጥናት የተደገፈ ነው ለማለት አያስደፍርም። የአቅራቢው እምነቶችና ድምዳሜዎች እንዳሉ ሆነው አጠቃላይ የሙስና ችግር በአንድ አገር እንዲሁም ከኢኮኖሚ ልማት ጋር ያለው ተያያዥነት ለመዳሰስ አስፈላጊ ከሚባሉ ነገሮች ውስጥ የሚከተሉትን ማየት ይቻላል።

> አጠቃላይ የአገሪቱ ሁኔታ (National Context) የዳሰሳው መነሻ መሆን ይኖርበታል። የአገሪቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ ሳይዳሰስ የሙስና ገጽታና መንግስት የሚወስዳቸው እርምጃዎችን ለመተንተን መሞከር እጅግ አስቸጋሪ ነው።

እንዲሁም የሙስና ሁኔታ ለመዳሰስ ለመነሻነት የሚያገለግል የተወሰነ የቁጥርና የዳታ (Statistic) ኢንፎርሜሽን ማሰባሰብና ይህ በማይገኝበት ሁኔታም በተለያዩ የመረጃ ምንጮች ላይ የተመሠረተ የተወሰነ ግምትና ትንተና ማቅረብ አስፈላጊ ይመስለኛል።

በአንድ አገር ያለው የሙስና ሁኔታ የትኞቹን ዓይነቶች እንደሚያካትት በዝርዝር ባልተገለጸበት ሁኔታ የትኛው ነው ዋነኛው የስጋት ምንጭ ብሎ ለመወሰን አዳጋች ከመሆኑ አንፂር ችግሩን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ማየት ጠቃሚ ነው። የጽሁፉ አቅራቢ ግለሰቦች የመንግስትን አገልግሎት ለመጠቀም ከማሰብ ሙስና ውስጥ እንደሚገቡና የሙስና ጉዳይ ግለሰብ፣ ነጋዴዎችና በመካከለኛ ረድፍ በሚገኙ የመንግስት ባለስልጣናት መካከል የታጠረ እንደሆነ ይጠቁሙና በሌላ በኩል ደግሞ ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተሳሰረ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ድምዳሜውና ትንተናው አብሮ አይሄድም ሙስና በኢትዮጵያ ሁኔታ ከመንግስት ሃብት ምንዘራ (embezzlement) ወይም ስር የሰደዱ የሞኖፖል ጥቅሞች (monopolistic vested interests) ጋር መያያዝና አለመያያዙ ሳይዳሰስ ከአጠቃላይ የአገሪቱ ዕድገት ጋር ማቆራኘት ትንሽ ይከብዳል።

አጠቃላይ የአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታና የመንግስታቱ ባህሪ ሳይዳሰስ ሙስናን ብሎም ሙስና ለመዋጋት የተደረገው ጥረት እንዲሁም ለዚሁ ዓላማ የተፈጠሩ ተቋማትና ስርዓቶች (instruments and mechanisms) በሚገባ መረዳት አዳጋች ይመስለኛል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧልና ሙስና በመዋጋት ረገድ አመርቂ ውጤት ተገኝቷል ብሎ መደምደም ከጥናትና ምርምር ዉጤት ጋር ተያያዥነት ሊኖረው አይችልም።

የኢኮኖሚ ዕድገት መነሻዎች በዝርዝር ሳይታዮ የትኛው የኢኮኖሚ አካል ወሳኝ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ሳይታወቅ ሙስና ከኢንቨስትመንት፣ ከግሉ ሴክተር ዕድገትና ከአጠቃላይ የኢኮኖሚው ድርሻ ጋር ያለው ተያያዥነት በትክክል ሳይጠና ከልማት አንፂር ያለው ፋይዳን በሚመለከት ድምዳሜ ላይ መድረስ አይቻልም።

የትኛውም የሙስና ሁኔታ ከአጠቃላይ የዜጎች ደህንነት በተለይም ከመልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ ጋር ያለው ተያያዥነት በግልጽ መሠመር አለበት። ችግሩ ካለም መዋጋት የሚቻለው መልካም አስተዳደርን በማስፈን፣ የፕሬስ ነፂነትን በማረጋገጥና የቅሬታ ሰሚ ተቋሞች ነፂነትና ጠንካራ እንቅስቃሴ በመፍቀድ ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ሁኔታም ከዚህ የተለየ አይሆንም።

ሙስናን ከመዋጋት አንፂር በመጀመሪያ ደረጃ በሙስና መጠንና ዓይነት ላይ ግልጽ መረጃ፣ በመረጃው ላይ አንድ አገራዊ ስምምነት (consensus) ከዛም ቀጥሎ አደጋውን ለመዋጋት የሚያስችሉ ነፂና ጠንካራ የህግና የዲሞክራሲ ተቋማት መኖራቸው የግድ አስፈላጊ ነው።

ስለዚህ ምን መደረግ አለበት?

በትክክለኛ ጥናት ላይ የተመሠረተ ከተለያዩ ተጽዕኖዎች ነፃ የሆነ አገራዊ መረጃ መኖር አለበት።

የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታና የፖለቲካ ስርዓቱ ባህሪያትና ተቋሞች መነሻ ያደረገ ጥናት ያስፈልጋል።

የሙስና አደጋ በኢትዮጵያ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በተወሰነ አሃዝ የተደገፈ በተለይም ዓይነቱና መጠኑ ምን እንደሚመስል ማወቅ ጠቃሚ ነው።

1. ሙስና ከልማት ጋር ያለው ተያያዥነት ግልጽ ቢሆንም በኢትዮጵያ ደረጃ ከየትኞቹ የልማት አውታሮች ጋር በሰፊው እንደሚቆራኝ መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።
2. ሙስናን ለመዋጋት የተፈጠሩት ተቋሞች ጥንካሬ፣ ነፃነት፣ ተቀባይነት legitimacy እና ተአማኒነት credibility መመዘን ከዚህ አንፃርም ችግሩን ለመዋጋት ያላቸው ብቃትና በሂደቱም የሚኖራቸው ተጽዕኖ መተንተን ይጠይቃል።

ከዚህ አንፃር ሙስናን ለመዋጋት የአደጋው መጠን ጠንቅቆ ከማወቅና ለዚህ ተብሎ የተቋቋሙት ተቋሞች ከመዘርዘር ባሻገር ችግሩን ለመዋጋት መደረግ ያለባቸው ነገሮች አሉ።

1. የዲሞክራሲ ተቋማት ማስፋፋት ነፃ ማህበራትና የጥናት
2. ተቋማት እንዲያብቡ መፍቀድ
3. የህግ የበላይነት ማስፈን
4. የሲቪል ማህበረሰቡ እንቅስቃሴና ዕድገት መርዳት
5. የፖለቲካና የሲቪል መብቶች ማረጋገጥ
6. ነፃ ሚዲያን ማጠናከር
7. የደህንነት ተቋሞች ማሻሻያ ኘሮግራም (Security Sector Reform - SSR) ማካሄድ
8. በተለይ የህግ አካላት አወቃቀርና አሰራር (Justice Reform) ማካሄድ፤
9. የሙስና ችግር ከመልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ ብሎም ከብሄራዊ ደህንነትና የዜጎች ህልውና ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን መገንዘብ

ከዚህ አንፃር ሙስናን ለመዋጋት ኢትዮጵያ ነፃና ጠንካራ የዲሞክራሲ ተቋማት ከመፍጠር ባሻገር የደህንነት ተቋማትን ማሻሻያ ፕሮግራም (Security Sector Governance) ማካሄድና በተለይም የሕግ ተቋማት (Justice reform) ላይ ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ ይጠይቃል።

በኮሚሽነር አሊ ሱሌይማን ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

አማረ አስገዶም[1]

ይህ የምርምር ፅሑፍ (ባሁኑ ጊዜ) አንገብጋቢና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ (የሙስና ጉዳይን የሚፈትሽ) በመሆኑ አቅራቢውን እንኳን ደስ አልዎት ለማለት እፈልጋለሁ። ይህ ፅሁፍ ምንም እንኳ ስለሙስናና ከሙስና ጋር ተዛማጅ የሆኑ ነገሮችን በከፊል የሚፈትሽ ቢሆንም፣ የጥናቱ ዋና ዓላማ ሙስና (ልማትን የሚያበረታታ ሳይሆን) ልማትን የሚገታ መሆኑን በአፅንኦት ለማረጋገጥ ነው። ይህንን ዓላማ ለማሳካትም ፅሁፉ በአራት ዋና ዋና ነጥቦች ተከፋፍሎ ቀርቧል። እነዚህም (1) የሙስና ትርጉምና መገለጫዎች (2) ሙስና ከልማት ጋር ያለው ፋይዳ፣ (3) ሙስናና የኢትዮጵያ ዕድገት፣ እንዲሁም (4) ማጠቃለያና የወደፊት አቅጣጫ ናቸው።

1. የሙስና ትርጉምና መገለጫዎቹ

ምንም እንኳ ሁሉም ሰዎች የሚስማሙበት ትርጉም ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ፀሐፊው ቢገልፁም፣ ቃሉ ከኢትዮጵያ ጥንታዊ ስነፅሁፍ (ግዕዝ) የተወረሰ መሆኑና ከሞላ ጎደል የሙስና መገለጫዎችን (ጉቦን፣ በስልጣን አላግባብ መገልገልን፣ ማጭበርበርን፣ እምነት ማጉደልን፣ የመንግስት ሃብትና ንብረት ለግል ጥቅም ማዋልን) ያካተተ በመሆኑ ቃሉ አግባብነት እንዳለው ፀሐፊው ይቀበላሉ። ይህ ትርጉም በ1997 ዓ.ም. ከወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 404(3) ጋር የሚስማማ መሆኑን የህግ ጥቅስ ባስረጅነት በማቅረብ በቃሉ ላይ ያላቸውን አወንታዊ አቋም ያብራራሉ።

በዚህ ክፍል ውስጥ የሙስና መንስኤዎች፣ የሙስና ሽሪኮች፣ ሙስና የሚፈፀምባቸው የስራ ዘርፎች (መስኮች) እንዲሁም የሙስና ዓይነቶች ባጭር ባጭሩ ተካተዋል። በተጨማሪም ሙስናን ከሌሎች ወንጀሎች ለመለየት በጣም አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል።

ይህ ክፍል ሙሰና ምን ማለት እንደሆነ፣ ከምን እንደሚመነጭ፣ መገለጫዎች እና ባህርያቶቹን ለአንባቢ በቀላሉ ለማስረዳት የቀረበ ስለሆነ፣ በከፊልም ቢሆን ግቡን የመታ ይመስለኛል። በርግጥም ሙስና በልማት ላይ የሚያደርሰውን አፍራሽ ተፅእኖ (የተመራማሪው ዋና ዓላማ) በግልፅ ማመልከት እንዲቻል የሙስናን ምንነት እና ዓይነት መግለፅ በጣም አስፈላጊ ነው።

[1] ዶ/ር አማረ አሰግዶም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ Institute of Educational Research (IER) ውስጥ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ዶ/ር አማረ አሰግዶም የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በዚህ ዓመት ያገኙ ሲሆን በረዳት ኘሮፌሰርነት በዩኒቨርስቲ ውስጥ ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል። ዶ/ር አማረ አሰግዶም ከዚህ በፊት IER በዳይሬክተርነት አገልግለዋል።

እዚህ ላይ ግን ሊነሱ የሚችሉ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። ለምሳሌ፣

(1ኛ) ሙስና በማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ሁሉ ወይስ ስልጣን ባለው የመንግስት ሠራተኛ ብቻ ይፈፀማል? የመንግስት ባለስልጣን ብቻ ከሆነስ ባለስልጣን ማለት ምን ማለት ነው? ማንን ይጨምራል ማንንስ ይቀንሳል?

(2ኛ) በገጽ 2(6ኛ አንቀጽ) እንዲህ ይነበባል "--ሙስና በሁለት ወገኖች ማለትም በአንድ በኩል በመንግስት ሠራተኛ ወይም ሃላፊ፣ በሌላ በኩል በሌሎች ሰዎች (ማለት የመንግስት ሠራተኞች) ሰዎች በመንግስት ስልጣን ላይ የሚፈፀም ወንጀል ነው"። ነገር ግን ሙስና የግድ ሁለት ወገኖችን ማካተት አለበት ወይ? በብቸኝነት የመንግስትን ገንዘብ በማጭበርበር /embazzlement/ ቢፈፀም ሙስና ሊባል አይቻልም ወይ? በተጨማሪ ሙስና በሁለት የመንግስት ሠራተኞች መካከል ሊፈፀም አይችልም ወይ?

(3ኛ) ሙሰናና ባህል ያላቸው ቁርኝት (በገጽ 4 አንቀጽ 2) በትንሹ የተጠቀሰ ቢሆንም፣ በቂ ትኩረት አልተሰጠውም እላለሁ። እዚህ ላይ በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት ግልጽ አልተደረገም። እንዲሁም ሙስና ከአንድ ማህበረሰብ የስነምግባር እሴቶች ጋር ያለው ዝምድና እስከአልተገለፀ ድረስ ሙስና ሊንሰራፋ የቻለበት በስግብግብነት (greed) ምክንያት ይሁን አልያም በፍላጎት አለመሟላት (need) ወይም ደግሞ በሁለቱም መሆኑን ለማወቅ ያስቸግራል።

ባንድ ዓይነት (የማህበራዊ እና ኤኮኖሚያዊ) የዕድገት ደረጃ የሚገኙ ሃገሮችና ማህበረሰቦች የሙስና ሁኔታቸው አንድ አይነት ነው? ወይስ ይለያያል? ሙስና ከማህበረሰብ ፍልስፍና ጋር፣ ያለው (ቀጥታም ሆነ የተዘዋዋሪ) ግንኙነት በዚህ ክፍል ማሳየት አስፈላጊ ይመስለኛል። ለምሳሌ ፣ የሙስና መንስኤ ኤኮኖሚያዊ (ፍላጎት) ወይም ስነልቦናዊ (ስግብግብነት) ወይም ደግሞ ፖለቲካዊ (ወገናዊነት) ሊሆን አይችልም ወይ? ለምሳሌ፤ "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል የሚለው አባባል" (ገጽ 4) ሙስና ከባህል ጋር ያለውን ዝምድና አያሳይም? ይህ አባባል ባሁኑ ጊዜ ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም? የትኛው የህብረተሰብ ክፍል (ተገልጋይ፣ ባለስልጣን፣ የመንግስት ሰራተኛ) ትክክል ነው ብሎ ያምናል? እነማን ደግሞ "ኢሞራል" ነው ይላሉ? የነዚህ ጥያቄዎች መልስ፣ በሙስና ፖሊሲ ቀረፃና መርሃ ግብር ትልቅ እንደምታ የሚኖረው ይመስለኛል።

2. ሙስና ከልማት ጋር ያለው ፋይዳ

ይህ ክፍል ከጥናቱ ዋና ዓላማና ከጥናቱ ጭብጥ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው። በመሆኑም ልማትና ሙስና አሉታዊ ግንኙነታቸውን በማያወላዳ ሁኔታ ተመራማሪው ግልፅ አድርገው አቅርቧል። ሙስና እንዴት አድርጎ የልማት ጠንቅ ሊሆን እንደሚችል፣ እንዲውም ከዚያ አልፎ፣ ጠቅላላ የስርዓት መፈራረስ (የሕግና ስርዓት መጥፋት) ሊያስከትል እንደሚችል ሂደቱን በሙሉ አብራርተው የገለፁ ስለሆነ፣ በሁለቱ ክስተቶች ላይ ያለው ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ግንኙነት ለማጤን ቀላል ነው። ይህን ተሚራሪ ግንኙነት ለማሳመን የጀነራል ሳኒ አባቺና ግብረአበሮቻቸው ወንጀል መጥቀስ በቂ ነው። የተመዘበረን ሃብት ወደ ውጭ ማሸሽ እስካለ ድረስ ሙሰና የልማት ተሚራሪ እንጂ የልማት ቀስቃሽ ሊሆን አይችልም። በተጨማሪም ይህ ጥናት የተለመደውን ያጠናን ዘዴ በመከተል ፈንታ ማለትም በሙስናና በልማት መከካከል የተቃርኖ ግንኙነት አለ የለም በማለት ፈንታ ሙስና ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎች ፈጥሮ፣ ምን እንደሚያስከትል ሂደቱን በትክክል የገለፀ ስለሆነ አቀራረቡ አግባብነት አለው። ፅሑፉን ጥሩ ግንዛቤ እና ሙስናን የመዋጋት ዝንባሌ ሊፈጥር ይችላል የሚል እምነት አለኝ። ነገር ግን ጥናቱ ሙስና በእድገት ላይ ያለው አሉታዊ ገጽታ ከማሳየት ባሻገር አዎንታዊ ጎን አለው ብለው የሚከራከሩትን ወገኖች ጭምር ለመሞገት የቀረበ ይመስላል። ይህ መሳይ እምነት በኢትዮጵያውያን የሚንፀባረቅ ባለመሆኑ የሙጉቱ አስፈላጊነት ብዙም አይታየኝም።

3. ሙስና እና የኤኮኖሚ ዕድገት በኢትዮጵያ

ይህ ክፍል፣ ያለፈውን ክፍል መሠረት በማደረግ የሙስናና የኤኮኖሚ ዕድገት ያላቸውን አፍራሽ ግንኙነት በኢትዮጵያና ለመፈተሽ የቀረበ ይመስለኛል። በዚህም መሠረት ሙስናን ለመዋጋት ብሎ የኢትዮጵያ መንግስት የወሰዳቸው የተለያዩ እርምጃዎችን ይተነትናል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም ያካሄደው አገር አቀፍ የሙስና ቅኝት ተጠቃሽ ነው። እንዲሁም የሠራተኛ የስነምግባር ደንብን ይፋ ማድረግ ሌላው ነው። ከሁሉም በላይ የፀረ-ሙስና ኤጀንሲ ማለትም የስነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን መፈጠር መንግስት በጉዳዩ ላይ ያለውን ቁርጠኝነትን ያመለክታል።

ኮሚሽኑ ከተቋቋመ በኋላ፣ ባወጣው ዓላማ መሠረት የሚከተሉትን ነገሮች ፈፅሙዋል። 1ኛ/ የሙስና የወንጀል ህግን አሰባስበዋል (ገጽ 10) 2ኛ/ የወንጀል ክሶችን በመመስረት በ100 ተከሳሾች ላይ ከ8 ወር እስከ 18 ዓመት በሚደርስ የእስራት ውሳኔ አስፈፅመዋል። እነዚህ ሙስናን ለመዋጋት አስፈላጊ ነገሮች ቢሆኑም በቂ ናቸው ማለት ግን አይቻልም። ፀሓፊውም አላሉም።

እንዲሁም ከ1996 ጀምሮ እስከ 1999 የነበረውን ያገሪቷን ዓመታዊ የዕድገት መጠን የሚያሳይ እስታስቲስክስ ገጽ 11 ቀርቧል። ነገር ግን የአራት ተከታታይ ዓመታት የዕድገት ሁኔታ አሃዞችን ከማስቀመጥ ሌላ ምንም ትንትና አልተደረገባቸውም። እኔ እንደገባኝ ከሆነ፣ በኤኮኖሚው ዘርፍ ዕድገት ካለ፣ በሶሻል ዘርፍም (የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎችች) እድገት መኖሩን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለፅ የተሞከረ ይመስለኛል። ዋናው ጥያቄው ግን በዚህ ወቅት ሙስና ቀንሷል ወይስ ጨምሯል? የሚለውን ጥያቄ አሁንም አለመመለሱ ነው። በርግጥ ይህን ጥያቄ መጠየቅ ቀላል ነው፣ መልሱ ግን ከባድ መሆኑን እነገዘባለሁ።

ነገር ግን የክስ መብዛትና ማነስ ማወቅ በጉዳዩ በቂ ግንዛቤ አይሰጥም። በርግጥም ፀሓፊው እንዳሉት ምርምርና ምርመራ ይህን ጉዳይ ለይቶ ለማወቅ ይጠቅም ነበር። በዚህ ጉዳይ ለምን እንዳልተገፋበት ግን ግልፅ አላደረጉትም። በIER ቅኝት መሠረት በተለያዩ ተቋሞችና ድርጅቶች ጠለቅ ያሉ case studies ካልተደረጉ የሙሰና ዓይነት፣ ባህሪይና መጠን ለማወቅ እንደማይቻል ገልፀን ነበር።

አንዱ ይህ ጥናት ግልፅ ያላደረገው ነገር ቢኖር፣ ከ405 የክስ ጉዳዮች ኮሚሽኑ ምን ተምሯል የሚለውን ጥያቄ ነው። ክሱ በራሱ ግብ አይደለም መሆንም የለበትም። ከያንዳንዱ ጉዳይ ትምህርት የሚፈነጥቅ ብዙ ጠቃሚ መረጃዎች ማግኘትና እነዚሁን በመተንተን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከሰቱ የሙሰና ዓይነቶች፣ መንስኤዎቻቸው እና እንዴት እንደሚፈፀሙ አውቆ ሕዝብን ማስተማር ተገቢ ነበር እላለሁ።

4. ማጠቃለያና የወደፊት አቅጣጫ

ይህ ክፍል ሁለት ንዑስ ክፍሎች አሉት፤ እነሱም ማጠቃለያና ምን እናድርግ? የሚሉ ናቸው።

በመጀመሪያው ክፍል አጠር ባለ ሁኔታ የሙሰናን አደገኛነት ይገልፅና፣ ከልማት ጋር ያለውን መስተጋብር ያብራራል። ያልተሟፈውን አታንብብ አትበሉኝና (ብዙ ሰው ያልተሟፈውን ያነባል) ሙሰናን በመዋጋታችን ምክንያት ዕድገት አምጥተናል የሚል መልዕክት (message not words) አነባለሁ። በህዝብና በዜና ማሰራጫዎች የሚወራው ግን ተቃራኒውን ነው። ለማንኛውም፣ የሙሰናና ልማት ተሟራሪነት በፅንሰ ሓሳብ ደረጃ የማያጠራጥር ቢሆንም፣ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን ግልፅ አይመስለኝም። በውል የሚታወቀው፣ የማክሮ ኤኮኖሚው የአራት ዓመት ተከታታይ ዕድገትና፣ በመንግስት በኩል የታየው የፀረሙሰና እንቅስቃሴ ነው። አሁንም ያልተመለሰው ጥያቄ፣ ሙሰና ቀንሶዋል ወይስ ጨምሯል? የሚለውን ነው። ይህን ጥያቄ ለመመለስ አሠራራቸውን አሻሽለዋል የሚባሉትንና፣ ብልሹ አሠራር አለባቸው የሚባሉትን ሁለት ተቋሞች በማወዳደር ሂደቱን መገንዘብ ይቻል ነበር። የዚህ ፅሑፍ አቀራረብ በጣም ጥቅል ከመሆኑ የተነሳ መሠረታዊ የሆነውን ጥያቄ ለመመለስ አልቻለም።

ምን እናድርግ? የሚለው ንዑስ ክፍል ሶስት መልዕክቶችን ያስተላልፋል። እነዚህም ሀ. የህዝብ ንቃትና ንቁ ተሳትፎ፣ ለ. ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው የመንግስት አሰራር (መልካም አስተዳደር) ሐ. ሙሰናን ያለርህራሄ መዋጋት የሚሉ ናቸው። በኔ እይታ የመጀመሪያ ሁለት መልዕክቶች (መልካም አስተዳደርና የህዝብ ንቁ ተሳትፎ) በዋናው በፅሑፉ በስርዓት ያልተካተቱና ትንታኔ ያልተደረገባቸው ስለሆነ በዚህ ፅሑፍ ውስጥ ማካተቱ አግባብነት ያለው አይመሰለኝም። ሶስተኛው የመፍትሄ አቅጣጫ (ሙሰናን ያለርህራሄ መዋጋት) የሚለውን ግን ባግባቡ በፅሑፍ ውስጥ የተተነተነ ስለሆነ ተገቢነት አለው ባይ ነኝ። ሆኖም ግን ሙሰና እንዴት መዋጋት ይቻላል የሚለው ጥያቄ በተገቢው መንገድ እስካልተመለሰ ድረስ ከመፈክርነት ላያልፍ ይችላል። መልካም አስተዳደርና የህዝብ ተሳትፎ ሙሰናን ለማጋለጥና ለመቆጣጠር በጣም አስፈላጊ ናቸው። ስለሆነም፣ እነሱን መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች ያለኝን አጠቃላይ አመለካከት (reflection) ለመግለፅ እወዳለሁ።

ማጠቃለያ

ከዚህ በፊት እንደገለፅኩት የዚህ ወረቀት ትኩረት የሙስናን አስከፊነትና ከልማት ጋር ያለው "ተቧራሪነት" በአንክሮ ለማሳየት ነው። ስለሆነም ወረቀቱ ጠቅለል ባሉ ጉዳዮችና ፅንሰ ሓሳባዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ጊዜና ቦታ ስለጠፋ ዝርዝር ጉዳዮችን ትኩረት ነፍጓቸዋል። ሙስናን አስመልክተው የተፃፉ ልዩ ልዩ አስተያየቶችና አመለካከቶች በብዙ ስነፅሑፎችና የምርምር ውጤቶች የሚገኙ ስለሆነ፣ ይህ ወረቀት ኢትዮጵያ ላይ ባለው የሙስና ሁኔታ ላይ ብቻ ትኩረት ቢያደርግ የበለጠ እንድምታ ይኖረው ነበር የሚል አመለካከት አለኝ።

የሙስና ቅኝት በ1994 ዓ.ም. እንደተካሄደ ማንም ያውቀዋል። በዚያን ጊዜ የመልካም አስተዳደርን ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና እንዲሁም የህዝብ ተሳትፎ ሁኔታ (በአጠቃላይ መልኩም ቢሆን) ምን እንደሚመስል፣ ተጠንቶ ነበር። ከዚያ በኋላም፣ መንግስት የተለያዩ እርምጃዎች መውሰዱ በዚሁ ወረቀት ተገልፀዋል።
እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ሙስናን ለመቀነስ በመንግስት የተወሰዱ እርምጃዎች ብዙ ቢሆኑም ምን እንድምታ አላቸው የሚለው ነው። እነዚህ አዲስ የተፈጠሩት መዋቅሮችና ቢሮዎች እንዴት እየሰሩ ነው ለምሳሌ፣ መልካም አስተዳደርን አስመልከቶ የመሻሻል ምልክት አለ ወይ? ቅጥርና ዕድገት ችሎታን (merit) መሠረት ያደርጋል? የክፍል ሃላፊዎች ለሚመሩት ሠራተኛ ተጠያቂነት አላቸው ወይስ ተጠያቂነታቸው ለበላይ አካል ብቻ ነው ወይ? ሠራተኛው ስለ አስተዳዳሪዎቹ ምን ይላል? ቢያንስ ይህ ወረቀት ከነዚህ ውስጥ አንዱን ጉዳይ ይዞ በጥልቅ መተንተን ይገባው ነበር።

በየተቋሙ የተቋቋሙት የስነምግባርና ፀረሙስና ቢሮዎች አሁን ምን እየሰሩ ነው? ሙስናን በመከላከል ምን ያህል ውጤት አምጥተዋል? ችግሮችስ ካሉባቸው፣ እነዚህ ችግሮች ከየት ይመነጫሉ? እነሱስ ቢሆን፣ የችግሩ አካል ናቸው ወይስ የመፍትሄው? ከሶስት ዓመት በፊት የሙስና ቅኝትን አስመልክቶ በአንድ ኮንፈረስ ንግግር በማደርግበት ጊዜ "ህጋዊ ሙስና በኢትዮጵያ ምን ይመስላል"? የሚል ጥያቄ ተጠይቄ ነበር።

በወቅቱ መልስ መስጠት ስላልቻልኩ ኮሚሽኑ በቀጣይ እንዲመልሰው አሳስቤ ነበር። ባሁኑ ጊዜ ይህ ጥያቄ ኮሚሽኑ እንዴት ይመልሰዋል?

ባለፈው ሳምንት ይመስለኛል ከንቲባ ብርሃነ ድሬሳ የሚከተለውን ብለው ነበር።
"ለኛ መጓጓጥ የሚሆን ባለ ብር 500,000.00 መኪና ይገዛል፣ ለፅዳት ሠራተኞች ግን የጓንቲ መግዣ የሚሆን ባጀት የለም ይባላል" ይህ አባባል የህጋዊ ሙስና መኖርን አያመላክትም? ባንዳንድ ሰዎች አመለካከት "ሙሰና “necessary evil” ነው"። "የግድ ጉቦ ካልከፈልኩ በስተቀር የባሰ ኪሣራ ይደርስብኛል ይላሉ። ይህ አባባል "አስተዳደሩ ምንም ሊያግዘኝ አይችልም ከሚለው ተስፋ መቁረጥ የመነጨ ይመስለኛል።

ባንድ ወቅት (ከ10 ዓመት በፊት ይመስለኛል) የኢንዱስትሪና ቢዝነስ ተወካዮች በኢቲቪ ቀርበው ስለሙስና ሲወያዩ አንዱ አባል ተነስቶ "ቀልዳችሁን አቁሙ፣ እኔ ጉቦ መስጠቱን እቀጥላለሁ፣ ልጆቼ ጦማቸው እንዲያድሩ አልፈልግም፣ አታታሉን" ብለዋል።

በጣም የሚገርመው፣ ቅኝቱ ስናካሂድ፣ የህብረተሰብና የንግዱ ማህበረሰብ ተወካዮች ሙስና ተጣጥፏል ሲሉ፣ የተቋም ሃላፊዎች (ባለስልጣናት) በድርጅቱ ውስጥ "ሙስና ብሎ ነገር የለም" ብለው ነበር።

እንዲያውም አንድ ስራ አስኪያጅ "ይህ የሚረባ ጥናት አይደለም" በማለት ደብዳቤ እስከመፃፍ ደርሰዋል። ይህ ሁኔታ የሚያሳየን፣ የችግሩ ባለቤት እነማን እንደሆኑ ነው። በመልካም አስተዳደር ዙርያ የሚደረግ ማሻሻያ (reform) ችግሩን በእጥፍ እንደሚቀንሰው ማንም የሚስማማበት ይመስለኛል። ይህ ማለት ግን ጥሩ ጥሩ ፖሊሲዎች መንደፍ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ጥሩ የተቋም መሪዎች መመልመልን ማካተት አለበት። ብቃትን መሠረት ያደረገ አቀጣጠርና ዕድገት (ሹመት) ከሌለ ውጤቱ "ውሀ ቢወቅጡት እምቦጭ" ነው። የኮሚሽኑ ቀጣይ ጥናት በዚህ ዙርያ ብያጠነጥን ተመራጭ ይመስለኛል።

የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) ምንነት፤ የኢትዮጵያ የአባልነት እንቅስቃሴና የወደፊት የልማት ተስፋ[1]

ሀብታሙ ታደሰ[2]

1. መግቢያ

የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO)ን ያህል ዘርፈ ብዙና ውስብስብ ጉዳይ በእንዲህ ዓይነቱ በጊዜ በተገደበ መድረክ በሰፊው ለመዳሰስ የሚቻል አይደለም፡፡ አብዛኛዎቹ የWTO የጓዳ ቋንቋዎች በንግድ ተደራዳሪዎች ካልሆነ በስተቀር በሌላው ህብረተሰብ ዘንድ የሚታወቁ አይደሉም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጽሁፍ ስለዓለም ንግድ ድርጅት ታሪካዊ አመሠራረትና አወቃቀር፤ ስለድርጅቱ ዋና ዋና ተግባራት፤ ስለሚያቅፋቸው ዋና አምዶችና ስምምነቶች፤ ስለ WTO የአባልነት ድርድር ደረጃዎችና ኢትዮጵያ ስለምትገኝበት ሁኔታ፤ ከአባልነት ሊገኙ ስለሚችሉ ጥቅሞችና ፈታኝ ሁኔታዎች፤ ወ.ዘ.ተ... ለውይይትና ቀጣይ ሥራ ሊሆን እንደሚችል እሳቤ በመውሰድ ጥቂት ጉዳዮችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

2. የዓለም ንግድ ድርጅት ታሪካዊ አመሠራረትና አወቃቀር

የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) ቀደም ሲል እ.ኤ.አ ከ1947 ጀምሮ የተቋቋመውንና የታሪፍና የንግድ አጠቃላይ ስምምነት (GATT) በመባል የሚታወቀውን አካል በመተካት እ.ኤ.አ. በ1995 ማረከሽ በተሰኘች የሞሮኮ ከተማ ተመሠረተ፡፡ በእርግጥ የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት እ.ኤ.አ በ1944 ሲመሰረቱ ሌላው ተጀምሮ ዳር ሳይደርስ የቀረው ጉዳይ ንግዱን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚመራ International Trade Organization (ITO) የተሰኘ ተቋም ማቋቋም እንደነበር መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

በዚያን ወቅት ITOን መመስረት ባይቻልም ከብዙ ክርክር በኋላ ሃያ ሶስት በሚሆኑ ሃገሮች መካከል የተፈረመውና ለሃምሳ ዓመታት ያህል የንግድ ድርድር ዋና መድረክ ሆኖ ሲያገለግል የቆየው GATT መፈጠሩ አይዘነጋም፡፡ እ.ኤ.አ ከ1947 እስከ 1994 ድረስ በቆየው GATT ስምንት ያህል የንግድ ድርድር ዙሮች የተካሄዱ ሲሆን እነዚህም ድርድሮች ታሪፍና ታሪፍ ያልሆኑ የንግድ መሰናክሎች

[1] ህዳር 27 ቀን 2000 ዓ.ም የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡፡

[2] አቶ ሀብታሙ ታደሰ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እ.ኤ.አ. በ1985 ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚ ፖሊሲ አናሊስስ ከማካርቲ ዩኒቨርስቲ ዩጋንዳ በማርች 2001 አገኝተዋል። አቶ ሀብታሙ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአለም የንግድ ድርጅት ማስተባበሪያ መምሪያ (WTO Affair Department) ኃላፊ ናቸው። አቶ ሀብታሙ ታደሰ ለተለያዩ ተቋማት በተለያዩ ጊዜ የምክር አገልግሎት ሰጥተዋል።

እንዲቀነሱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ከእነዚህ ስምንት ያህል የንግድ ድርድር ዙሮች ሁሉ በርካታ ጉዳዮች የተፈፀሙበትና በኋላም ለዓለም ንግድ ድርጅት መወለድ ምክንያት የሆነው እ.ኤ.አ ከ1986 እስከ 1994 የቆየው የኡራጓይ ዙር መሆኑም ይታወቃል፡፡

WTO ከተፈጠረ በኋላ የተጀመረውና በአሁኑ ጊዜ የምንገኝበት የንግድ ድርድር ዙር 9ኛው ዙር ሲሆን የዶሃ የንግድ ድርድር (Doha Development Agenda/DDA) በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ስምምነት የተደረሰው እ.ኤ.አ 2001 በኳታር ዋና ከተማ ዶሃ ላይ በተካሄደው 4ኛው የWTO የሚኒስትሮች ጉባዔ ነው፡፡ የዶሃ ዴክላሬሽን በዋናነት የሚታወቀው የልማት ጉዳዮችን የድርድሩ እምብርት ማድረጉ ሲሆን፤ በተለይም በማደግ ላይ ላሉ ሃገሮች የሚደረጉ የተለያዩ አስተያየቶች (S & D) አንቀጾች አስገዳጅ፤ ግልፅና ተግባራዊ ሊሆኑ በሚችል መልኩ እንዲታዩ ወስኗል፡፡ ዴክላሬሽኑ 21 የሚሆኑ የድርድር ርዕሰ ጉዳዮችን ከ50 በላይ በሚደርሱ አንቀጾች ከፋፍሎ አስቀምጧል፡፡ ዴክላሬሽኑ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች የሚደረጉ ድርድሮች የሚጠናቀቁበትን የጊዜ ገደብ አስቀምጦ የነበረ ቢሆንም አብዛኛዎቹ በተቀመጠው መሠረት ሳይጠናቀቁ ቀርተዋል፡፡

የGATT ስምምነት በዋናነት በተፈበረኩ ምርቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን እንደ ግብርና፤ አገልግሎትና የአእምሮአዊ ንብረት ጉዳዮች በኡራጓይ ዙር ድርድር ሲካሄድባቸው ቆይቶ ከWTO መመስረት ጀምሮ የስምምነቱ አካል እንዲሆኑ ተደረገ፡፡

በአሁኑ ወቅት WTO 151 ያህል ሃገሮችን በአባልነት ያቀፈ ሲሆን 95 በመቶ በላይ የሚሆነውን የዓለም ንግድ እንቅስቃሴ የሚሸፍን እንደሆነ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ በተባበሩት መንግስታት መስፈርት መሠረትም ከአባል ሃገራቱ መካከል 25ቱ በኢንዱስትሪ የበለፀጉ፤ 94 ያህሉ በማደግ ላይ ያሉና 32ቱ ደግሞ በልማት ወደኋላ የቀሩ ሃገሮች ናቸው፡፡

በድርጅቱ አወቃቀር መሠረት ከአባል ሃገራት የተውጣጣው የሚኒስትሮች ጉባዔ (Ministerial Conference) ድርጅቱን በበላይነት የሚመራ የመጨረሻው አካል ሲሆን በየሁለት ዓመቱ አንድ ጊዜ በመሰብሰብ ዋና ዋና ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፡፡ WTO ከተመሠረተ ወዲህ 6 ያህል የሚኒስትሮች ጉባዔዎች የተካሄዱ ሲሆን፤ እነርሱም፤ የመጀመሪያው በሲንጋፖር(1996)፤ ሁለተኛው በጄኔቫ(1998)፤ ሶስተኛው በሲያትል(1999)፤ አራተኛው በዶሃ(2001)፤ አምስተኛው በካንኩን(2003)፤ ስድስተኛውና የመጨረሻው በሆንግ ኮንግ(2005) የተካሄዱት ናቸው፡፡

በድርጅቱ ከሚኒስትሮች ጉባዔ ቀጥሎ ስልጣን ያለው አካል አጠቃላይ ምክር ቤት (General Council) ሲሆን የተውጣጣውም አባል ሃገራት በጄኔቫ ከሚመደቧቸው አምባሳደሮች ወይንም ቋሚ መልዕክተኞች ነው፡፡ አጠቃላይ ምክር ቤቱ በየጊዜው በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች የተለያዩ ውሳኔዎችን ይሰጣል፡፡ ም/ቤቱ የአባል ሃገሮችን የንግድ ፖሊሲ ገምጋሚ (Trade Policy Review) እንዲሁም ግጭቶችን የሚፈታ አካል (Dispute Settlement Body) በመሆንም ያገለግላል፡፡ ከዚህ በተዋረድም

ተጠሪነታቸው ለአጠቃላይ ም/ቤቱ የሆኑ የዕቃዎች፤ የአገልግሎቶችና የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ የተሰኙ ሶስት ካውንስሎች ይገኛሉ፡፡

በGATT ታሪክ የተካሄዱት የንግድ ድርድር ዙሮች

ተ.ቁ	ዓመት	ቦታ/ስም	ጉዳዮች	ሃገሮች
1	1947	ጄኔቫ	ታሪፍ	23
2	1949	አንሲ	ታሪፍ	13
3	1951	ቶርኩይ	ታሪፍ	38
4	1956	ጄኔቫ	ታሪፍ	26
5	1960-1961	ጄኔቫ(ዲሎን)	ታሪፍ	26
6	1964-1967	ጄኔቫ(ኬነዲ)	ታሪፍና አንቲ ዳምፒግ	62
7	1973-1979	ጄኔቫ(ቶኪዮ)	ታሪፍና ታሪፍ ያልሆኑ መሰናክሎች፤ ማዕቀፎች	102
8	1986-1994	ጄኔቫ(ኡራጓይ)	ታሪፍታሪፍና ታሪፍ ያልሆኑ መሰናክሎች፤ አገልግሎት፤ አእምሯዊንብረት፤ ግብርና፤ የWTO መመስረት ወ.ዘ.ተ	123

ምንጭ፤ www.wto.org

በተጨማሪም በተለያዩ ስምምነቶች ዙሪያ ማለትም የአካባቢ ጥበቃን፤ የልማት ጉዳዮችን፤ የአባልነት ሂደትን፤ የአካባቢያዊ የንግድ ስምምነቶችን እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚከታተሉ በርካታ የሥራ ክፍሎች፤ ኮሚቴዎችና ልዩ ልዩ የሥራ ቡድኖች ተዋቅረው ይገኛሉ፡፡

የዓለም ንግድ ድርጅት ጽ/ቤት ሴክሬታሪያት መቀመጫ ጄኔቫ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ወደ 630 የሚደርሱ ሠራተኞችን እንደሚያቅፍ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የሴክሬታሪያቱ ዋና ተግባር የሚኒስትሮች ጉባዔንና በስሩ በየደረጃው የተዋቀሩ የተለያዩ አካላትን በቴክኒክ መደገፍ ነው፡፡

3. የድርጅቱ አበይት ተግባራት

የዓለም ንግድ ድርጅት አጠቃላይ ዓላማ ታሪፍና ታሪፍ ያልሆኑ መሰናክሎችን በማስወገድ ንግድ በውድድር ላይ ተመርኩዞ እንዲካሄድ ማስቻል ነው፡፡ የዓለም ንግድ ድርጅት፡-

- በሃገሮች መካከል የሚካሄደውን ዓለም አቀፋዊ የንግድ ህግ ያስተዳድራል፤
- መንግስታት የንግድ ስምምነቶችን የሚደራደሩበት መድረክ ነው፤
- መንግስታት የንግድ አለመግባባቶችን የሚፈቱበት ቦታ ነው፤
- መንግስታት የአባል ሃገሮችን የንግድ ፖሊሲዎች የሚገመግሙበት ሥርዓት ነው፤
- በማደግ ላይ ያሉና በልማት ወደኋላ የቀሩ አባል ሃገሮች ከዓለም አቀፉ የንግድ ሥርዓት ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፤ ለዚህም ስኬታማነት ከሌሎች አለማቀፋዊ ድርጅቶች ጋር በጋራ ይሰራል፡፡

4. የድርጅቱ ዋና ዋና ስምምነቶችና መሠረታዊ መርሆዎች

የዓለም ንግድ ድርጅት ስምምነቶች በርካታ ጉዳዮችን ማለትም ግብርናን፤ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን፤ ባንኮችን፤ ቴሌን፤ የመንግስት ግዢን፤ ደረጃና ጥራትን፤ የምግብ ጤንነትን፤ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃን፤ ወ.ዘ.ተ ያጠቃልላል፡፡ ስምምነቶቹን በሁለት ትላልቅ ምድቦች መክፈል የሚቻል ሲሆን መጠሪያቸውም Multilateral Trade Agreements **እና** Plurilateral Trade Agreements **በመባል ይታወቃሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ስምምነቶች በሁሉም አባል ሃገራት ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ ሲሆኑ፤ በሁለተኛው ምድብ የተመለከቱት ግን ስምምነቱን በፈቃደኝነት በፈረሙ አባላት ብቻ ተፈፃሚ የሚሆኑ ናቸው፡፡**

በMultilateral Trade Agreements **ውስጥ ሶስቱ የዓለም ንግድ ድርጅት ስምምነት ዓምዶች የተጠቃለሉ ሲሆን እነርሱም፤ የዕቃዎች ንግድ ስምምነት** (Multilateral Agreement on Trade in Goods)፤ **የአገልግሎቶች ንግድ አጠቃላይ ስምምነት**(General Agreement on Trade in Services/GATS)፤ **እና ንግድ ነክ የአእምሯዊ ንብረት ስምምነት** (Agreement on Trade Related Aspects of Intellectual Property Rights/TRIPS) **ናቸው፡፡ ከፍ ሲልም ለማመልከት እንደተሞከረው እነዚህን ዋና ዋና ስምምነቶች ማንኛውም የ**WTO **አባል ሃገር እንደ አንድ ማእቀፍ** (Single Undertaking) **የመቀበል ግዴታ አለበት፡፡**

በWTO **አሠራር በእነዚህ ስምምነቶች ሁሉ ተግባራዊ የሚሆኑ የተለያዩ መሠረታዊ መርሆዎች ቢኖሩም ለዚህ ጽሁፍ ሁለቱ ዋና መሠረታዊ መርሆዎች ብቻ ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው መርህ አድሎአዊነትን ማስወገድ**(Trade Without Discrimination) **ሲሆን ይህም አንድ አባል ሃገር መግቢያ በር ላይ ለሌላው የሰጠውን ጥቅም ለሁሉም አባል ሃገራት በተመሣሣይ ሁኔታ ወዲያውኑ የመስጠት** (MFN Treatment) **ግዴታ እና አንድ ዕቃ ወደ አንድ ሃገር ከገባ በኋላ በገበያ ላይ በሃገር ውስጥ ከተመረቱ ተመሣሣይ ዕቃዎች ጋር እኩል የመታየት** (National Treatment) **መብትን ያካትታል፡፡ ሁለተኛው መርህ ደግሞ የንግድ ከባቢያዊ ሁኔታን አስተማማኝ ማድረግ** (Predictability) **የተሰኘው ነው፡፡ ይህም እንደመጀመሪያው ሁሉ ሁለት መገለጫዎች አሉት፤ አስገዳጅ የታሪፍ ጣሪያ ማስቀመጥ** (Binding) **እና ግልፅነት** (Transparency) **የተሰኙ፡፡** Binding **ስንል አባል ሃገራት ለንግድ ሸሪኮቻቸው በዕቃዎች ላይ የሰጧቸው የገበያ ዕድሎች በቀጣይ ድርድር ካልሆነ በስተቀር ታሪፉ እንደማይቀየር ግዴታ መግባት ሲሆን፤** Transparency **ደግሞ አባል ሃገሮች በዓለም አቀፍ ንግድ ላይ የሚከተሏቸውን ፖሊሲዎችና በየጊዜው የሚያወጧቸውን ህጎች ለድርጅቱ ጽ/ቤት በየጊዜው የማሳወቅና መረጃ የመስጠት ግዴታን ይመለከታል፡፡**

በድርጅቱ ስምምነቶች ውስጥ በመልማት ላይ ያሉና በልማት ወደኋላ የቀሩ አባል ሃገሮችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የተለያዩ አፈፃፀሞች (Special and Differential Treatments) **ያገኛሉ፡፡ የተወሰኑትን ለአብነት ለመጥቀስ ያህል፤ የተባሉት ሃገሮች የሚገቧቸው ግዴታዎች የኢኮኖሚ አቅማቸውን መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ፤ በተለይም በልማት ወደኋላ የቀሩ አባል ሃገሮች ስምምነቶችን ለመተግበር ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጣቸው፤ ሃገራቱ አቅማቸውን ለማጎልበት የስልጠናና ሌሎች የቴክኒክ ድጋፎች እንዲያገኙ፤ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል፡፡** ከዚህ ቀጥሎ ስለ ሦስቱ የWTO ዋና ምሰሶዎች ጥቂት እንበል።

4.1 የዕቃዎች ንግድ ስምምነት (Multilateral Agreement on Trade in Goods)

WTO ሲመሰረት የቀድሞው GATT ስምምነት የተሻሻለ ሲሆን ይህም የዕቃዎች ንግድ ስምምነት አብይ ጥላ እንዲሆን ተደረገ። በዚህ አብይ ጥላ ሥርም የተለያዩ ዘርፎችን የሚመለከቱ (ምሳሌ፤ ግብርና፣ ጨርቃጨርቅ) እንዲሁም የተለያዩ ጉዳዮችን የሚዳስሱ (ምሳሌ፤ የሰው፣ የእንስሳትና የዕፅዋት ጤንነት፤ የምርት ደረጃ፤ የድኅማና አጸፋዊ እርምጃ አወሳሰድ፤ ከጉዳት የመከላከያ እርምጃ አወሳሰድ፤የጉምሩክ ቀረጥ አወሳሰን፤ የገቢ ንግድ ፈቃድ አሰጣጥ፤ የመንግስት የንግድ ድርጅቶች አሰራር ወ.ዘ.ተ...) ስምምነቶች በአባሪነት እንዲታቀፉ ተደርጓል።

ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ የበለጠ ትርጉም አላቸው ተብለው የታሰቡ የተወሰኑ ስምምነቶች ምንነት ብቻ በአጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

4.1.1 የግብርና ስምምነት (Agreement on Agriculture/AG)

የግብርናው ዘርፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ድርድር የተደረገበትና ስምምነት የተፈረመው የታሪፍና የንግድ አጠቃላይ ስምምነት (GATT) የኡራጋይ ዙር የንግድ ድርድር ማጠቃለያ ላይ በማራከሽ ነው። ስምምነቱ በሦስት ዋና ዋና አምዶች (Pillars) የተከፋፈለ ሲሆን እነርሱም የገበያ ዕድል (Market Access)፣ የሀገር ውስጥ ድጎማ (Domestic Support) እና የወጪ ንግድ ድጎማ (Export Subsidy) በመባል ይታወቃሉ።

*የገበያ ዕድልን **(Market Access)** በተመለከተ፤*

- በዚህ አምድ ከቀረጥ ሌላ ይወሰዱ የነበሩ ማናቸውም የንግድ መሰናክሎች ወደ ቀረጥ እንዲለወጡ (Tariffication) ወይም እንዲወገዱ፣
- በወቅቱ በሥራ ላይ የነበረው ቀረጥ በሁሉም አባል ሀገራት እንዲቀነስና ገደብ እንዲኖረው፣
- ቀረጥ ያልሆኑ እርምጃዎችን ወደ ቀረጥ የቀየሩና የቀረጥ መጠናቸውንም የቀነሱ ሀገሮችን ካልተጠበቀ ጉዳት ለመከላከል ይችሉ ዘንድ የተለየ የመከላከያ እርምጃ (Special Safeguard Provisions/SSG) መውሰድ እንዲችሉ፣
- የቀረጥ አቀናነስን በተመለከተ በአማካይ የበለጸጉት ሀገሮች በስድስት ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቅ 36 በመቶ፣ በማደግ ላይ ያሉት በ10 ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቅ 24 በመቶ ቅናሽ እንዲያደርጉ ሆኖ ቢያንስ የበለጸጉት ሀገሮች በ15 በመቶ እና በማደግ ላይ ያሉት 10 በመቶ እንዲቀንሱ፣
- በልማት ወደኋላ የቀሩት ሀገሮች ግን ቀረጥ እንዲቀንሱ እንደማይገደዱ፣ በስምምነቱ ተደንግጓል።

*የሀገር ውስጥ ድጎማን **(Domestic Support)** በተመለከተ፤*

- በኡራዓይ የንግድ ድርድር ዙር አጠቃላይ የግብርና ድጎማ (Total Aggregate Measurement of Support) እንዲቀነስ ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን የበለጸጉት ሀገሮች በ6 ዓመት ውስጥ 20 በመቶ፣ በማደግ ላይ ያሉት በ10 ዓመት ውሰጥ 13.3 በመቶ እንዲቀንሱና በልማት ወደኋላ የቀሩት ሀገሮች ግን ምንም ዓይነት ቅናሽ እንዳያደርጉ ስምምነቱ ደንግጓል።
- በዚህ አምድ ለግብርናው የሚሰጡ የድጎማ ዓይነቶች በሦስት ሳጥኖች ማለትም (Green, Blue and Amber Boxes) ተብለው መከፈላቸው፤
- የመጀመሪያው "Green Box" የተባለው ንግድን የማያዛቡ ወይም አነስተኛ ተጽዕኖ ያላቸውን የድጎማ ዓይነቶች የሚይዝ ነው። ሀገሮች የሚሰጧቸውን እንደዚህ ዓይነት ድጋፎች እንዲቀንሱ አይገደዱም።
- የሚፈቀዱት ድጎማዎችም፤
  - ለምርምር፣
  - ለበሽታ መቆጣጠሪያ፣
  - ለሥልጠና፣ ኤክስቴንሽንና ምክር፣
  - ለገበያ ማስፋፊያና መረጃ፣
  - ለመሰረተ ልማት፤
  - በብሄራዊ ህግ የተደነገገ በምግብ እራስን የመቻል ፕሮግራም፣
  - የምግብ እርዳታ፣
  - ለተፈጥሮ አደጋ መከላከያ፣
  - ለመዋቅር ለውጥ ማስተካከያ፣

  የመሳሰሉት ድጋፎች ናቸው።
- ሁለተኛው "**Blue Box**" የተባለው ምርትን ለመቀነስ ሲባል የሚደረግ የቀጥታ ገንዘብ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ግብርናንና የገጠር ልማትን ለማፋጠን በሚል ለገበሬዎች የሚሰጥ የኢንቨስትመንት፣ የምርጥ ዘር የመሳሰሉትን ድጎማዎች የሚመለከት ነው። ድጋፉ ንግድን በማዛባት ረገድ ያለው ሚና አነስተኛ እንደሆነ ይታመናል።
- ሦስተኛው "**Amber Box**" በመባል የሚታወቀው ሲሆን ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ውጭ ያሉትን ድጎማዎች በሙሉ ያካትታል። በዚህ ሥር የሚወድቁ የድጎማ ዓይነቶች ንግድን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያዛቡ በመሆናቸው እንዲቀንሱ ስምምነቱ ያስገድዳል። ሆኖም የበለጸጉ ሃገሮች 5% እና በማደግ ላይ ያሉት 10% ያህሉን የዚህ ዓይነት ድጎማ እንኳ እንዲቀንሱ አይገደዱም። በልማት ወደ ኋላ የቀሩት ሃገሮች ግን የሚሰጧቸውን ድጎማዎች በሙሉ እንዲቀንሱ አይገደዱም።

የወጪ ንግድ ድጎማን ***(Export Subsidy)*** *በተመለከተ፤*

- የወጪ ንግድ ድጎማን በተመለከተ ሀገሮች በሥራ ላይ ያውሉት የነበረውን መጠን ከዓመት ወደ ዓመት እንዲቀንሱ ስምምነት ላይ ተደርሷል።
- የበለጸጉት ሀገሮች የቀጥታ ድጎማ በጀታቸውን በ6 ዓመት ውስጥ 36 በመቶ በዋጋ፤ 21 በመቶ በመጠን፣ በማደግ ላይ ያሉት ሀገሮች ደግሞ በ10 ዓመት ውስጥ በዋጋ 24 በመቶና በመጠን 14 በመቶ እንዲቀንሱ ተስማምተዋል።
- እንዲቀነሱ ስምምነት የተደረሰባቸው የዚህ አምድ ድጎማዎች፡- ለወጪ ንግድ የሚደረግ ቀጥታ የገንዘብ ክፍያ፣ ወደ ውጭ ሀገር ገበያ ለሚገቡ አዳዲስ ምርቶች የሚደረግ ማበረታቻ፣ በሀገር ውስጥ በሥራ ላይ

ካለው ዋጋ በታች ለውጭ ገበያ እንዲውሉ ለማድረግ ከመንግስት ክምችት የሚደረግ ሽያጭ፣ ለወጪ ንግድ የሚደረግ ቀጥታ የገንዘብ ክፍያ፣ የማርኬቲንግ ዋጋን ለመቀነስ ሲባል ለምርት አያያዝ፣ የምርትን ደረጃ ለማሳደግ፣ ለአመራረትና ለዓለም አቀፍ ማጓጓዣ የሚደረግ ክፍያ፣

- በሀገር ውስጥ ካለው የትራንስፖርት ዋጋ በተሻለ ሁኔታ ወደ ውጭ ለሚላኩ ምርቶች በመንግስት የሚቀርብ ማጓጓዣ፣ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

4.1.2. የሰው፣ የእንስሳትና የዕፅዋት ጤንነትን የመጠበቅ ስምምነት (Agreement on Sanitary & Phytosanitary Measures/SPS)

ይህ ስምምነት በ7ኛው የቱክዮ የንግድ ድርድር ዙር ወቅት ስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ ሲሆን፤ ስምምነቱ ከግብርና ጋር የተገናኘ ቢሆንም ከሚሰጠው ከፍተኛ ጠቀሜታ አኳያ ታይቶ እንደገና በኡራጓይ ዙር በተደረገው ድርድር ለብቻው እንዲታይ ስምምነት ላይ ተደርሶ ህግ እንዲወጣለት ተደርጓል።

ስምምነቱ አባል ሀገራት ዓለምአቀፍ ንግድን በማይገታ መልኩ የሰዎችን፣ የእንስሳትንና የእጽዋትን ጤና እንዲሁም አካባቢንና ሀገርን ከጉዳት ለመከላከል የሚያስችሉ የቴክኒክ ሬጉሌሽኖችን በማውጣት የመከላከያ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚችሉ ይደነግጋል። እነዚህ የሚወጡ የቴክኒክ ሬጉሌሽኖች ወይም የመከላከያ እርምጃዎች እንደ ዓለምአቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት (Organization Internationale des Epizotes/OIE)፣ International Plant Protection Convention (IPPC) እና የምግብ አዘገጃጀት ኮሚሽን (Codex Alimentarius Commission) መመሪያዎችንና ደረጃዎችን የተከተሉና ቢያንስ ዝቅተኛ የመከላከል መስፈርቶችን ያሟሉ ቢሆኑ እንደሚመረጥ ተደንግጓል። አንድ አባል ሀገር የሚወስዳቸው እርምጃዎች ዝቅተኛ የመከላከል መስፈርቶችን ያሟሉ ከሆኑ ሌላው ሀገር በእኩልነት ደረጃ እንዲቀበላቸው ስምምነቱ ይገልፃል። በዚህ ስምምነት መሠረት አንድ አባል ሀገር ከበሽታ ነጻ የሆነ አካባቢን/ቀጠናን ለይቶ መከለልና ለሚጠይቀው ሁሉ በማስረጃ አስደግፎ ማሳየት ይችላል። ቀጠናዎቹን አስመልክቶም ሆነ አጠቃላይ ስምምነቱን በማስፈፀም ዙሪያ የተለያዩ መረጃዎችን ለሚጠይቁ የድርጅቱ አባል ሀገራት መረጃ የሚሰጥበት ማዕከል (Enquiry Point) እና በየጊዜው የሚወሰዱት እርምጃዎች ማሳወቂያ የሥራ ክፍል (Notification Authority) መሰየም አስፈላጊዎች መሆናቸውም በስምምነቱ ተመልክቷል።

4.1.3. ቴክኒካዊ የንግድ መሰናክሎች ስምምነት (Agreement on Technical Barriers to Trade/TBT)

አባል ሀገራት ሰውን፣ እንስሳን፣ እጽዋትን፣ አካባቢንና ሀገርን፣ ወ.ዘ.ተ... እንዲሁም አሳሳችና ጥራታቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ሊያደርሱ ከሚችሏቸው የተለያዩ ጉዳቶች ለመከላከል የሚረዱ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚችሉ ስምምነቱ ደንግጓል። የሚወሰዱት እርምጃዎች በሀገሮች መሀል ልዩነት ማድረግ እንደሌለባቸው፣ ለዓለምአቀፍ ንግድ እንቅፋት መፍጠር እንደማይኖርባቸው፣ እርምጃዎች ግልጽና በብሄራዊ ደረጃ በሚታዩም የየሃገሮች ጋዜጣዎች ላይ መውጣት እንዳለባቸው፣ ወዘተ... አባል ሀገራት በድርድሩ ወቅት ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

የሚወጡት የቴክኒክ ሬጉሌሽኖች፣ ደረጃዎችና የኮንፎርሚቲ **ግምገማ** ሂደቶች እንደ ISO ያሉ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች የሚያወጧቸውን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ እንዲሆኑ ስምምነቱ ያበረታታል። አንድ አባል ሀገር የሚወስዳቸው እርምጃዎች ዝቅተኛ የመከላከል መስፈርቶችን ያሟሉ ከሆኑ ሌላው ሀገር በእኩልነት ደረጃ መቀበል እንዳለበት፤ የሚወጡትን የቴክኒክ ሬጉሌሽኖች፣ ደረጃዎችና የኮንፎርሚቲ **ግምገማ** ሂደቶችን የሚያስተባብር የበላይ አካል ማቋቋም፤ የመረጃ ማዕከል (Enquiry Point) እና በሥራ ላይ የዋሉት የቴክኒክ ሬጉሌሽኖች ወይም የተወሰዱት እርምጃዎችን በየጊዜው ማሳወቂያ የሥራ ክፍል (Notification Authority) መሰየም፤ እንደሚያስፈልግ ስምምነቱ ይደነግጋል።

4.1.4. ከጉዳት የመከላከያ እርምጃ አወሳሰድ ስምምነት (Agreement on Safeguard /SG)

የዚህ ስምምነት ዋና ዓላማ አባል ሀገራት ባልጠበቁት ሁኔታ ከፍተኛ መጠን ያለው ምርት ወደ ሀገራቸው ገብቶ በሀገር በቀል ኢንዱስትሪዎች ላይ ጉዳት በሚያደርስበት ወቅት ተገቢ የሆነ የመከላከያ እርምጃ መውሰድ እንዲችሉ ለማድረግ ነው።

አባል ሀገራት የተጠቀሰውን የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸው መረጋገጥ ይኖርበታል። እነርሱም፤

- የገቢ ንግድ በከፍተኛ ደረጃ በመጠንም ሆነ በዋጋ ባልተጠበቀ ሁኔታ መጨመሩ፣
- በሀገር ውስጥ ተመሳሳይ ምርት በሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት (Serious injury) መድረሱ ወይም ጉዳት የማድረስ አዝማሚያ (Threat of serious injury) መኖሩ፣
- የደረሰው ወይም ሊደርስ የሚችለው ጉዳት በተጠቀሰው የገቢ ምርት ምክንያት መሆኑ፣ የሚሉት ናቸው።

ሃገሮች የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ ጉዳቱ ለመድረሱ ወይም ሊደርስ ለመሆኑ በጥናት ማረጋገጥ አለባቸው፤ ሆኖም ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ጊዚያዊ የመከላከያ እርምጃ መውሰድ ይቻላል። የተወሰደው ወይም የሚወሰደው እርምጃ ዋና ዓላማ ጉዳቱን ለማካካስ ብቻ መሆን ይኖርበታል። እርምጃውም ቀረጥ በመጣል ወይም የገቢ ንግዱን መጠን በኮታ በመገደብ መልክ ሊወሰድ ይችላል። የሚወሰደው እርምጃ የሚቆየው ቢበዛ አራት ዓመት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል። ሆኖም በጠቅላላው ከስምንት ዓመት መብለጥ እንደሌለበት ተደንግጓል። አባል ሀገራት ይህን እርምጃ ለመውሰድ ለተጎጂው ሀገር ማካካሻ መስጠት ማለትም በምርቱ ፋንታ በሌላ ምርት ላይ የቀረጥ ቅነሳ ማድረግ አለባቸው።

4.1.5. የጉምሩክ ቀረጥ ትመና (Agreement on Customs Valuation/CVA)

ይህ ስምምነት ለመጀመሪያ ጊዜ ድርድር የተደረገበት እ.ኤ.አ. 1979 ቶኪዮ ላይ በተካሄደው 7ኛው ዙር ነው። ስያሜውም የTokyo Round Valuation Code በመባል ይታወቅ ነበር። በድርድሩም መጨረሻ በልውውጥ ዋጋ (transaction value) ላይ የተመሠረተ ስምምነት ሊፈረም ችሏል። በዚህ ስምምነት የጉምሩክ ዋጋ ትመና የሚካሄደው ወቅታዊ የንግድ ልውውጥ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባትና ለገቢ ምርት በሚከፈለው ወይም ሊከፈል በሚችለው ትክክለኛ ዋጋ (the Price Actually Paid or Payable) ላይ በመመስረት ሲሆን ከ40 በላይ የሚሆኑ ሀገሮች ስምምነቱን ፈርመው እስከ ኡራጓይ ዙር ድረስ ሲሠራበት ቆይቷል።

እ.ኤ.አ. በ1994 የተፈረመው የWTO የጉምሩክ ዋጋ ትመና ስምምነት ከቶኪዮ ዙር ቫሉዌሽን ኮድ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በገቢ ምርት ላይ የሚጣለው ቀረጥ በAd Valorem Duties መሠረት ተሰልቶ የሚከናወን ነው።

የጉምሩክ ዋጋ ትመና (Customs Valuation) በገቢ ምርት ላይ ቀረጥ ለመጣል ሲባል በገቢ ምርቱ ትክክለኛ ዋጋ ላይ Actual Value እና ወይንም በመጠንና ክብደት (volume/weight) ላይ ወይንም በሁለቱም ላይ በመመርኮዝ የሚደረግ የስሌት አሠራር ነው። የልውውጥ ዋጋን (Transaction value) ጨምሮ ስድስት ዓይነት የጉምሩክ ዋጋ ትመና ዘዴዎች በስምምነቱ የተካተቱ ሲሆን በመረጃ አለመኖር ምክንያት በእንዱ ዘዴ ካልተቻለ በሌላው ተከታታይ ዘዴዎች የዋጋ ትመና ማካሄድ እንደሚቻል ስምምነቱ ይገልፃል። እነዚህ ስድስት ዘዴዎች፣ Transaction Value፣ Transaction Value of Identical Goods፣ Transaction Value of Similar Goods፣ Deductive Method፣ Computed Method እና Fall-back Method በመባል የሚታወቁ ናቸው።

የWTO ጉምሩክ የዋጋ ትመና ስምምነት የአስመጪዎችን መብት ለመጠበቅ የሚያስችሉ አንቀጾችን አስቀምጧል። የእነዚህ አንቀጾች ዋና ዓላማ በጉምሩክ አሠራር ውስጥ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን የታለመ ሲሆን በዚሁ መሠረት የአስመጪዎችን ምስጢራዊ መረጃዎችን መጠበቅ፣ በፅሁፍ መረጃ መስጠት፣ ቅሬታቸውን እንዲገልጹ ለማድረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ከጉምሩክ የሚጠበቁ ግዴታዎች ናቸው።

4.2. የአገልግሎት ንግድ አጠቃላይ ስምምነት (GATS)

የGATS ስምምነት ዓላማ አገራት ቀጣይነት በሚኖራቸው የድርድር ዙሮች የአገልግሎት ዘርፎችን ደረጃ በደረጃ ለውጭ አገልግሎት አቅራቢዎች ክፍት እንዲያደርጉ ማበረታታት ነው።

በስምምነቱ ውስጥ በተቻለ መጠን ሁሉም የአገልግሎት ዘርፎች እንዲካተቱ ቢደረግም፣ ለንግድ ወይም ለትርፍ ዓላማና ከሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ለመወዳደር በታለመ መንገድ የማይካሄዱ አገልግሎቶች በስምምነቱ ውስጥ እንዳይታቀፉ ተደርጓል። እነዚህም በአብዛኛው በመንግሥት የሚካሄዱ ሆነው የብሔራዊ ባንክ አገልግሎት፣ የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎትና የመሳሰሉትን የሚያካትቱ ናቸው። ከእነዚህ ውጭ በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሥር የሚወድቀው የአየር ትራፊክ መብት (air traffic rights) የቺካጎ ኮንቬንሽን በመባል በሚታወቀው "International Air Services Transit Agreement" ውስጥ በተዘረዘሩና በአብዛኛው ከብሔራዊ ደህንነት ጋር ከተቆራኙ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ በመሆኑ ለጊዜው ከስምምነቱ እንዲወጣ ተደርጓል።

በዓለም ንግድ ድርጅት አመዳደብ መሠረት የአገልግሎት ንግድ በ12 ዋና ዋና ዘርፎችና ወደ 160 በሚደርሱ ንዑሳን ዘርፎች የተከፋፈለ ሲሆን፣

ዋና ዋና ዘርፎቹም፡-

1. የቢዝነስ አገልግሎት

2. የመገናኛ አገልግሎት
3. የኮንስትራክሽንና መሰል የኢንጅነሪንግ አገልግሎት
4. የማከፋፈል አገልግሎት
5. የትምህርት አገልግሎት
6. የጤናና መሰል ማኅበራዊ አገልግሎት
7. የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ አገልግሎት
8. የፋይናንሽያል አገልግሎት
9. የቱሪዝምና ጉዞ ነክ አገልግሎት
10. የመዝናኛ፣ ባህልና ስፖርት አገልግሎት
11. የትራንስፖርት አገልግሎት
12. ከላይ ከተዘረዘሩት ውጪ ያሉ አገልግሎቶች ናቸው።

ከላይ በተዘረዘሩት 12 ዋና ዘርፎች ውስጥ የተካተቱት 160 የሚደርሱ ንዑሳን የአገልግሎት ዓይነቶችም በአራት ዘዴዎች፡

- ከአንዱ አገር ወደ ሌላው ድንበር እያቋረጡ የሚሰጡ አገልግሎቶች (Cross-border Supply of Services: Mode1) ለምሣሌ፡ ቴሌኮሙኒኬሽንና የፖስታ አገልግሎት፣
- አገልግሎት ፈላጊው ወደ ሌላ አገር በመሄድ የሚያገኛቸው አገልግሎቶች (Consumption Abroad: Mode 2) ለምሳሌ፡ የቱሪዝም አገልግሎት፣
- አገልግሎት አቅራቢው ኩባንያ የአገልግሎት ንግዱን በሌላ አገር ውስጥ ቅርንጫፍ በመክፈት የሚሰጥ አገልግሎት (Commercial Presence: Mode 3) ለምሣሌ፤ የባንክ አገልግሎት፤
- በሌላው አገር በአካል በመገኘት በጊዜያዊ ቆይታ የሚሰጡ አገልግሎቶች (Temporary Movements of Natural Persons: Mode 4) ለምሣሌ፡ የሂሳብና የሕክምና አገልግሎቶች፤ ሊቀርቡ ወይንም ሊሰጡ እንደሚችሉ ስምምነቱ ይገልፃል።

የአገልግሎት ንግድን አስመልክቶ የዓለም ንግድ ድርጅት አባላት ሁለት ዓይነት ግዴታዎች አሉባቸው። እነዚህም፡

- ስምምነቱ በሚያቅፋቸው በሁሉም የአገልግሎት ዓይነቶች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ ግዴታዎች (Unconditional General Obligations) ሲሆኑ፣ ለአንድ አገር የተሰጠ ጥቅም ለሁሉም አባላት ወዲያውኑ መተላለፍ (MFN Treatment)፣ አባል አገራት የአገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ የሚያወጧቸው ደንቦችና መመሪያዎች በግልጽ እንዲታወቁና በተፈለገ ጊዜ መረጃዎች በአግባቡ እንዲገኙ (Transparency)፣ የአገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች አሳማኝ የሆኑና ያለአድልዎ የሚፈፀሙ እንዲሆኑ የሚሉ ግዴታዎች በዚህ ምድብ ውስጥ የሚወድቁ ናቸው።
- አባል አገራቱ ለውጭ አገልግሎት አቅራቢዎች ክፍት ለማድረግ የተስማሙባቸውና አፈጻፀማቸውን አስመልክቶ በዝርዝር ሰንጠረዥ ያስቀመጧቸውን አገልግሎቶች ብቻ የተመለከቱ ግዴታዎች (Conditional General Obligation) ናቸው።

  አባል አገራት ለውጭ አገልግሎት አቅራቢዎች ክፍት ያደረጓቸውንና ቃል የገቡባቸውን አገልግሎቶች ዝርዝር ሠንጠረዥ (Schedule of Commitments) በማዘጋጀት ለድርጅቱ ጽ/ቤት ማቅረብ

ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ ቃል የተገቡ አገልግሎቶች በሁለት ዓይነት መንገድ ተዘርዝረው ይቀመጣሉ። እነርሱም፡-

- በሠንጠረዡ ውሰጥ ለተዘረዘሩት ሁሉም አገልግሎት ዓይነቶች ገደብ የሚሆኑ (Horizontal Commitments)፣ በሠንጠረዥ ውስጥ ለሁሉም አገልግሎት የሚሆኑ ገደቦች የሚሰፍሩባቸው ክፍል መኖር ዋነኛ ምክንያት አገልግሎቶች በሚሰጥባቸው መንገዶች የሚኖረውን የገደብ ዓይነቶች ድግግሞሽ ለማስቀረት ታስቦ የተቀረፀ ክፍል ነው።
- በእያንዳንዱ የአገልግሎት ዓይነት ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ ገደቦች (Sector-specific commitments) ናቸው።

በአራቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች (Modes) የአገልግሎት ዓይነቶች ላይ የተገባውን ቃልና አገልግሎቱን ለማቅረብ የሚጣሉ ገደቦች (limitations) እንዲሁም MFN Exemptions በዝርዝር የሚቀርቡበት ነው። በውጭ አቅራቢዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ሁለት ዓይነት ገደቦች ሊጣሉባቸው ይችላል፡-

- አገልግሎቱ ወይም አገልግሎት አቅራቢው ወደ አገር ውስጥ ገበያ ሲገባ የሚጣልበት ገደብ (Market Access limitations) እና
- ከአገር ውስጥ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር በማነፃፀር የሚጣል ገደብ (National Treatment Limitations)

የመጀመሪያው የገበያ ገደብ በስድስት መንገድ የሚገለፅ ነው። እነርሱም፡-

- የአገልግሎት አቅራቢዎችን ቁጥር መገደብ፣
- የአጠቃላይ የአገልግሎቱን እንቅስቃሴ ዋጋ (Value of Transactions) መገደብ፣
- የአገልግሎቱን መጠን (Output) መገደብ፣
- በአገልግሎቱ ውሰጥ የሚቀጠሩ ሰዎችን ቁጥር መገደብ፣
- አገልግሎቱ ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች ጋር በሽርክና (Joint Venture) ብቻ እንዲሰጥ መገደብ፣
- አገልግሎቱን ለመስጠት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የገንዘብ መጠን መገደብ፣ ናቸው።

በሁለተኛው የገደብ ዓይነቶች ውስጥ ከሚካተቱት ጥቂቶቹን ለመጥቀስ፡-

- የውጭ አገልግሎት አቅራቢዎችን የድጎማና ገንዘብ ድጋፍ አሰጣጥን (Discriminatory subsidies and other financial measures) መገደብ፣
- የአገልግሎቱ አቅራቢዎችን የዜግነት አሰጣጥ (Nationality requirements) መገደብ፣
- ለውጭ አገልግሎት አቅራቢዎች የመኖሪያ ቦታ አሰጣጥ (Residency requirements) መገደብ፣
- የፈቃድ፣ ምዝገባና ብቃት መለኪያ ሰርተፊኬት አሰጣጥ (Licensing, registration and qualifications requirements) መገደብ፣
- የቴክኖሎጂ ሽግግርና ስልጠና አሰጣጥ (Technology transfer/training requirements) መገደብ፣
- የአገር ውስጥ ግብዓቶችን አጠቃቀም (Local content requirements) መገደብ፣

- የአገልግሎት አቅራቢዎችን የንብረትና መሬት ባለቤትነት (Ownership of property/land) መገደብ፣ ወዘተ...

የሚሉና ሌሎችም ገደቦች አባል አገራቱ እንዲያስቀምጡ የአገልግሎት ንግድ ስምምነት ይፈቅዳል።

የአገልግሎት ንግድ ስምምነት አባል አገራት በሚፈልጓቸው አገልግሎት ዓይነቶች ላይ ብቻ ቃል እንዲገቡ፣ በጣም ውሱን ወይም ጥቂት ዘርፎችን (Fewer sectors) ብቻ ለውጭ አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲከፍቱ እንዲሁም የልማት ደረጃቸውን ባገናዘበ መልኩ ጥቂት በሚሆኑ የአገልግሎት እንቅስቃሴዎች (Fewer types of transactions) ብቻ ላይ እንዲወሰኑ አንቀጽ 19 አጽንኦት ይሰጣል።

4.3 ንግድ ነክ የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ስምምነቶች (TRIPS)

TRIPS በዓለም ንግድ ድርጅት ከተካተቱት ሦስት ዋና ዋና ስምምነቶች አንዱ ሲሆን፤ እ.ኤ.አ. ከ1995 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። የTRIPS ስምምነት የተመሠረተው በፓሪስ፣ በርሊን እና ሮም ኮንቬንሽኖች እንዲሁም ዋሽንግተን ትሪይቲ ላይ ነው። በተለይም ፓሪስና በርሊን ኮንቬንሽኖች ውስጥ የነበሩት አንቀጾች ከሞላ ጎደል እንዳሉ በTRIPS ስምምነት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል። የTRIPS ስምምነት ቀደም ብሎ ከነበሩት የተለያዩ ኮንቬንሽኖች ጋር ሲነፃጸር በተሻለ መልኩ ንግድ ነክ የአእምሯዊ ንብረቶችን ማስጠበቅ የቻለ ስምምነት ነው። ምክንያቱም፤

- የንግድ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ሥርዓት በመያዙ፣
- በብሔራዊ ደረጃ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ እንዴት ተግባራዊ መሆን እንደሚችል በስምምነቱ ውስጥ በመገለጹ እና
- አዳዲስ የቴክኖሎጂ ግኝቶች ለምሳሌ፤ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂ ጥበቃን በተመለከተ በስምምነቱ ውስጥ እንዲካተቱ በመደረጉ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ የጥንካሬ ምልክቶች ናቸው።

በTRIPS ስምምነት መሠረት አገሮች በስምምነት ከተቀበሉት የጥበቃ ጊዜ በታች ማድረግ የማይችሉ ሲሆን በስምምነቱ ከተጠቀሱት የጥበቃ ጊዜ በላይ ግን ለፈጠራ ሥራዎች የጥበቃ ጊዜ መስጠት እንደሚችሉ ስምምነቱ ይደነግጋል። የTRIPS ስምምነት የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት። እነርሱም፡-

- የፈጠራ ሰዎች ለደከሙበት የፈጠራ ሥራ ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የፈጠራ ሥራዎች እንዲስፋፉ ለማስቻል፣
- ለፈጠራ ሥራዎች ተገቢውን ጥበቃ በማድረግ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማበረታታት እና
- በዓለም አቀፍ ንግድ ፍሰት ላይ የሚከሰቱትን መሰናክሎች ለመቀነስ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ንግድ ነክ የአእምሯዊ ንብረት ስምምነት የሚይዛቸው ጉዳዮች Copyrights & Related Rights እና Industrial Property በመባል በሁለት አበይት ምድቦች የሚከፈሉ ሲሆን በዝርዝር ሲታዩ የሚከተለውን ይመስላሉ።

(1). ኮፒራይት (Copyright)፡ የTRIPS ስምምነት ከያዛቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ሲሆን የደራሲያንንና የአርቲስቶችን የፈጠራ ውጤት የባለቤትነት መብት የሚያስጠብቅ ነው። በኮፒራይት የሚጠበቁት የፈጠራ

ውጤቶች ሙዚቃ፣ መጽሐፍ፣ ፊልም፣ ኮምፒውተር ሶፍትዌር የመሳሰሉት ናቸው። የኮፒራይት መብት ለፈጠራ ውጤትነት ዕውቅና የሚሰጠው ለሃሳቦች (Ideas) እና አሠራሮች (Procedures) ወዘተ... ሳይሆን የፈጠራው ባለቤት እነዚህን ሃሳቦችና አሠራሮች በተጨባጭ በጽሁፍ፣ በፊልም ወዘተ መልክ ካቀረበ ብቻ ነው። ይህም ማለትም የሚጠበቀው Idea ሳይሆን Expression of Idea መሆኑ በስምምነቱ ውስጥ ተመልክቷል።

በኮፒራይት የባለቤትነት መብት ጥበቃ የሚደረግላቸው የፈጠራ ውጤቶች ያለ ፈጠራ ባለቤቱ ፈቃድ አባዝቶ መሸጥ፣ ውጤቶቹንም በካሴት ወይም በሲዲ ቀድቶ መሸጥ የተከለከለ ነው። ሆኖም የፈጠራ ውጤቶቹ ለምርምር፣ ለትምህርት፣ ለአስተያየት እና ለዘና ዝግጅት ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ የፈጠራ ውጤቶቹን ያለ ፈጠራ ባለቤቱ ፈቃድ መጠቀም እንደሚቻል ስምምነቱ ይደነግጋል። በኮፒራይት መብት ጥበቃ የሚደረግላቸው የፈጠራ ውጤቶች እንደሌሎቹ የTRIPS ጉዳዮች (ለምሳሌ ንግድ ምልክት) በሚመለከተው የመንግሥት አካል ምዝገባ ማካሄድ ሳያስፈልግ የፈጠራ ውጤቱ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ጥበቃ እንደሚደረግለት ስምምነቱ ያዛል። በኮፒራይት የባለቤትነት መብት የፈጠራ ባለቤቱ ህይወቱን ሙሉ የፈጠራው ተጠቃሚ እንዲሆን ከመደንገጉም በላይ ባለመብቱም ከሞተ በኋላ የባለመብቱ ህጋዊ ወራሾች ለ50 ዓመታት ያህል የፈጠራው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በስምምነቱ ተደንግጓል።

(2). ከኮፒራይት ጋር ግንኙነት ያላቸው መብቶች (Related Rights)፡ ሦስት ጉዳዮችን ማለትም የፊልም ትዎናዎችን ወይም ዘፈኖችን፣ የሙዚቃ አቀነባባሪዎችንና የዜና አስተላላፊ ድርጅቶችን መብቶች የሚመለከቱ ናቸው። ከኮፒራይት ጋር ግንኙነት ያላቸው መብቶች ባለቤቶች የጥበቃ መብት ለማግኘት ምንም ዓይነት ምዝገባ ማካሄድ አያስፈልጋቸውም። ተዋናዮች ወይም ዘፋኞች እና የሙዚቃ አቀነባባሪዎች ለ50 ዓመታት እንዲሁም የዜና አስተላላፊ ድርጅቶች ለ20 ዓመታት ጥበቃ እንደሚደረግላቸው በስምምነቱ ውስጥ ተጠቅሷል።

(3). የንግድ ምልክቶች **(Trademarks)**፡ በTRIPS ስምምነት አንቀጽ 15 ሥር በተገለጸው መሠረት የንግድ ምልክት ማለትም ማንኛውም ምልክት ወይም የምልክቶች ጉበር ሆኖ የአንድ ድርጅትን ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ከሌላ ድርጅት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች የመለየት አቅም ያለው ማንኛውም ምልክት መሆኑ ተመልክቷል። የሰው ስሞች፣ ፊደሎች፣ ቁጥሮች የተለያዩ ምስሎች እንዲሁም የተለያዩ የቀለም ቅንብሮች እንደ ንግድ ምልክትነት ሊያገለግሉና ሊመዘገቡ እንደሚችሉ በስምምነቱ ተጠቅሷል።

የንግድ ምልክቶች የአንድን ድርጅት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ከሌላ ድርጅት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች የመለየትና ገበያን የማስፋፋት ተግባራትን ይጫወታሉ። በስምምነቱ መሠረት አንድ የንግድ ምልክት ለ7 ተከታታይ ዓመታት ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን ከ7 ዓመት በኋላም ለምልክቶቹ እድሳት በማድረግ ምልክቶቹን ለሁልጊዜ መጠቀም እንደሚቻል ነው። የንግድ ምልክቶች ተመዝግበው ለ3 ተከታታይ ዓመታት ያለበቂ ምክንያት በሥራ ላይ ካልዋሉ እንደሚሰረዙ ስምምነቱ ይደነግጋል።

(4). በአካባቢ ስሞች የሚጠበቁ የንግድ ምልክቶች **(Geographical Indications)**፡ በTRIPS ስምምነት ከተካተቱት ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። እነዚህ ምልክቶች የአንድን አካባቢ ምርቶች ከሌላ አካባቢ ምርቶች ለመለየት የሚያገለግሉ ናቸው። የንግድ ምልክቶቹ በምልክትነት የሚያገለግሉት በእርሻና እደጥበብ ምርቶች እንዲሁም በምግብ ኢንዱስትሪ ለሚመረቱት ምርቶች ነው።

በአካባቢ ስሞች የሚጠበቁ ምርቶች ከሌላ አካባቢ ካሉት ምርቶች የተለየ ባህሪ፣ ጥራትና በተጠቃሚ ዘንድ የተለየ ተወዳጅነት ወይም ደህና ስም አላቸው ተብለው የሚገመቱ ምርቶች ናቸው። ለምርቶቹ ልዩ መሆን እንደምክንያት የሚጠቀሱት በአካባቢው ያሉት የተፈጥሮ ሁኔታዎች ማለትም የአካባቢው አየርና አፈር እንዲሁም በአካባቢው የሚገኘው የተለየ የአመራረት ዘዴና ልምዶች ናቸው። ለምሳሌ፤ የሸኖን ቅቤ ከሌላ አካባቢ የተለየ ጣዕም እንዲኖረው ያደረገው የአካባቢው አየርና አፈር ሊሆን ይችላል።
በአካባቢ ስምነት የሚጠበቁት የንግድ ምልክቶች የአንድ ሰው ወይም ድርጅት ንብረት አይደሉም። የማንኛውም በአካባቢው የሚገኝና አንድ ዓይነት ምርት የሚያመርት ሰው ወይም ድርጅት የጋራ ንብረት ናቸው። ምልክቶቹን ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ለተመሳሳይ ምርት ሊጠቀምባቸው ይችላል ማለት ነው። ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች ከንግድ ምልክቶች ጋር መሰል ተግባራት አላቸው። በአካባቢ ስምነት የሚጠበቁ የንግድ ምልክቶችን በተመለከተ እስካሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የአመዘጋገብ ሥርዓት ያልወጣላቸው በመሆኑ ጉዳዩ ገና በድርድር ሂደት ላይ ነው። የTRIPS ስምምነት ማንኛውም የWTO አባል አገር በአገሩ ውስጥ በአካባቢ ስሞች ለሚወጡት ምልክቶች ጥበቃ እንዲያደርግ ግዴታ ከመጣሉም በላይ በተለይ ለወይንና አልኮል ምርቶች ከፍተኛ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ያዛል።

(5). ኢንዱስትሪያል ዲዛይኖች፡ የፈጠራ ውጤቶች ሲሆኑ የሚውሉትም አንድን የኢንዱስትሪ ውጤት የሆነውን ምርት ለማስጌጥና ለምርቱም ገበያው በሚፈልገው መልክ ቅርፅ ለመስጠት ነው። ኢንዱስትሪያል ዲዛይኖች አንድን ተመርቶ ለገበያ የሚቀርብ ምርት የተለየ ውበት በመስጠት ምርቱም ከሌሎች ተመሣሣይ ምርቶች ጋር ተወዳድሮ የተሻለ የገበያ ዕድል እንዲያገኝ የማድረግ አቅም አላቸው።

ኢንዱስትሪያል ዲዛይኖች አብዛኛውን ጊዜ በጨርቃጨርቅ፣ በመኪና አምራች ኩባንያዎችና በኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የፈጠራ ውጤቶች ናቸው። ጥበቃ ለማግኘት ዲዛይኖቹ በሚመለከተው የመንግስት አካል መመዝገብ አለባቸው። ዲዛይኖቹም ለምዝገባ ብቁ የሚሆኑት፡-

- አዲስነት (Novelty) ማለትም ዲዛይኖቹ ቀደም ብሎ ለህዝብ አለመቅረባቸው፤
- ኦሪጅናልነት (Originality) ማለትም ቀደም ብሎ ከተሰሩት ሥራዎች ላይ አለመቀዳታቸው፤ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካሟሉ ነው።

ስምምነቱ የፈጠራ ባለቤት የድካሙን ዋጋ እንዲያገኝና ለፈጠራ ሥራው ያወጣውን ወጪ እንዲመልስ፣ በዚህም በመበረታታት ለተጨማሪ የፈጠራ ሥራዎች እንዲዘጋጅ ለማድረግ የፈጠራ ሥራዎቹ ቢያንስ ለ10 ተከታታይ ዓመታት እንዲጠበቁ ያዛል።

(6). ፓተንት **(Patents)**፡ በTRIPS ስምምነት መሠረት ፓተንት ማለት ለአንድ የፈጠራ ውጤት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው። ይህ የምስክር ወረቀት ለፈጠራው ባለቤት፤ የፈጠራው ባለቤት ያልሆኑ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የፈጠራውን ውጤት እንዳይጠቀሙበት የመከልከል መብት የሚሰጥ ነው። መንግሥት ለፈጠራው እውቅና ሲሰጥ የፈጠራው ባለቤት ደግሞ የፈጠራውን ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ ዶክመንት የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት በስምምነቱ ተጠቅሷል። በፓተንት መብት ጥበቃ የሚደረግለት የፈጠራ ውጤት ለአንድ ለተለየ ችግር ቴክኒካዊ የሆነ መፍትሄ የሚሰጥ መሆን አለበት። ፓተንት ለፈጠራ ሥራዎች እውቅና የሚሰጠው በምርትና በምርት ሂደት ለሚቀርቡት የፈጠራ ሥራዎች ነው።የፈጠራ ውጤቱም ለምርት ከሆነ ምርት የማምረት ብቃት ሊኖረው ይገባል። ለፈጠራ ሥራዎች የፓተንት መብት መስጠት፡-

- ለፈጠራ ስራዎች ህጋዊ ጥበቃ በመስጠት የፈጠራ ስራዎች ለሕዝብ ይፋ እንዲሆኑ ይበረታታሉ የፈጠራ ባለቤቶችም ስራዎቻቸውን አይፎብቁም፤
- ለፈጠራ ስራዎች ጥበቃ መደረጉ ትላልቅ ኩባንያዎች ለምርምር ተግባራት በርካታ ገንዘብ እንዲመድቡ ስለሚያግዝ የምርምር ሥራዎች ይበረታታሉ፤
- አማራጭ ቴክኖሎጂ እንዲኖር እድል ይፈጥራል፤

አንድ የፈጠራ ውጤት የጥበቃ ጊዜን ለማግኘት የሚከተሉትን ያሟላል።

- አዲስነት (Newness or Novelty) ማለትም የፈጠራ ውጤቱ ቀደም ብሉ ያሉት የፈጠራ ውጤቶች አካል መሆን አለበት።
- የፈጠራ ሂደቱ ለማንኛውም ተራ ሰው በግልፅ የሚታወቅ መሆን አለበት (Inventive Step or non-obvious)
- ፈጠራው በኢንዱስትሪ ውስጥ ሥራ ላይ መዋል የሚችል መሆን አለበት (Industrial applicability) የሚሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት።

በTRIPS ስምምነት መሠረት የፖተንት መብት ለሁሉም የፈጠራ ስራዎች ሕጋዊ የጥበቃ መብት አይሰጥም። ህጋዊ የጥበቃ መብት ከማይሰጣቸው የፈጠራ ስራዎች መካከል፦

- ለሰው ልጅ ለእንሰሳ እና ለእፀዋት ህይወት አደገኛ የሆነ የፈጠራ ስራዎች
- ለህክምና ዘዴዎች ለምሳሌ diagnostic therapeutic and Surgical methods of human or animal እና
- ከMicro-Organisms በስተቀር ለእፀዋትና ለእንሰሳት በተጨማሪም በስምምነቱ መሠረት መንግስት አጣዳፊ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት /የተፈጥሮ አደጋዎች በወረርሽኝ መልክ የሚነሱ በሽታዎች ወ.ዘ.ተ/ ከፈጠራ ባለቤቱ ፍቃድ ውጭ በCompulsory Licensing የፈጠራ ውጤቱን ራሱ መጠቀም ወይም ለሌላ ኩባንያ መስጠት ይችላል። በTRIPS ስምምነት መሠረት በፖተንት መብት ለሚጠበቁ ግኝቶች ለተከታታ 20 ዓመት ጥበቃ እንዲደረግላቸው ተደንግጓል። የፈጠራ ስራውም ከ20 ዓመት በኋላ የህዝብ ሃብት ይሆናል ማለትም ከ20 ዓመት በኋላ ማንኛውም ሰው ፈጠራውን ያለክልከላ መጠቀም ይችላል ማለት ነው።

(7). Layout Designs of Integrated Circuits: በTRIPS ስምምነት ከሚሸፍኑት ጉዳዮች መካከል አንዱ የኢንተግሬትድ ሰርኪዩትስ ዲዛይኖች ናቸው። የኢንተግሬትድ ሰርኪዩትስ ዲዛይኖች የሰዉ ልጅ የአእምሮ ስራ ውጤቶች ከሆኑት የፈጠራ ስራዎች መካከል የሚመደቡ ናቸው። እነዚህ ዲዛይኖችም ሥራ ላይ የሚውሉት በሰዓት ቴሌቪዥን የልብስ ማጠቢያ ማሽን እና መኪኖች የመሳሰሉት ምርቶች ላይ ነው።

ዲዛይኖቹም Three Dimensional Disposition ያላቸው ሲሆን የፈጠራ ሥራውም በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ዕውቀትና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ ነው። ይህንን የፈጠራ ውጤት መጠበቅ ያስፈለገበት ዋናው መክንያት በሥራው ላይ ያሉትን የ Integrated Circuits Dimensions ለመቀነስና የመሥራት አቅማቸውን ከፍ ለማድረግ (dimensionኑን በመቀነስ ምርቱ የሚይዘውን ቦታ

ለምርቱ መሥሪያ የሚውሉትን ማቴሪያሉችና እና ለምርቱ የሚወጣውን ወጪ ለመቀነስ/ የሚደረገውን የፈጠራ ሂደት ለመደገፍ ነው። በTRIPS ስምምነት መሠረት ለኢንትግሬትድ ሰርኪዩትስ ዲዛይኖች ለ10 ተከታታይ ዓመታት ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

(8). ሚስጥራዊ መረጃዎች (Undisclosed Information)፡ በTRIPS ስምምነት መሠረት ምስጢራዊ መረጃዎች Trade Secrets እና Test Data በሁለት ይከፈላሉ።

- **በTrade Secret የሚሸፈኑት መረጃዎች የምርት ፎርሙላዎች ዲዛይኖች የአንድ ኩባንያ ደንበኞች ስም ዝርዝር የያዘ ሰነድ የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ መረጃዎች ከሚመለከተው የሥራ ክፍል ጥቂት ሠራተኞች በስተቀር ማንም አያውቃቸውም የአንድ ኩባንያ ሚስጥራዊ መረጃዎች ናቸውና።**

- **በTest Data የሚሸፈኑት Pharmaceutical እና Agricultural Chemical Products ናቸው። ስምምነቱ ለሁለቱም ምርቶች ኬሚካሎች ጥበቃ እንዲደረግ የሚያዘው ምርቶቹ አዲስ ኬሚካል ጥቅም ላይ ከዋሉ ብቻ ነው። ምርቶቹንም ከገበያ ላይ ለማዋል የሚመለከተው ኩባንያ ከመንግሥት አካላት ስምምነት ማግኘት አለበት። የመንግስት አካላትም ምርቱን ለገበያ ለማቅረብ ስምምነቱን እንዲገልጽ በሚደረገው የሥራ ሂደት እጁ የሚገቡትን መረጃዎች በሚስጢር መጠበቅ እንዳለበት ስምምነቱ ያዛል።**

ስለሶስቱ የዓለም ንግድ ድርጅት ዓበይት ስምምነቶች ይህንን ያህል ካልን ቀጥሎ ደግሞ ስለ WTO የአባላት ድርድር ሁኔታ እንመልከት ::

5. አባልነትና የአባልነት ድርድር ደረጃዎች

የWTO የአባልነት ሂደት በተለይም በልማት ወደኋላ ለቀሩ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሃገሮች እጅግ የተወሳሰበና የሚጠይቀው ወጪም ከፍተኛ እንደሆነ ይነገራል። የWTO አባል ለመሆን የሚፈልጉ ሃገሮች በኢኮኖሚያቸው ላይ የተለያዩ ለውጦችን የሚያስከትሉ ህጎችን እንዲቀበሉ ከመሻነው ይገደዳሉ። አባል ሃገራት ለአባልነቱ የሚከፍሉት ዋጋ በወደፊቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማታቸው ላይ ትልቅ እንደምታ ሊያሳድር ይችላል።

በመሆኑም ለአባልነት ዝግጅቱና ለድርድር ተሳትፎው ከፍተኛ የሆነ የገንዘብና የሰው ሃብት እንደሚጠይቅ ይታመናል። ይህም ሀበት በተለይ በልማት ወደኋላ የቀሩ ሃገሮችን ስናስብ አቅማቸውን የሚፈታተን ሊሆን ይችላል።

የዓለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን በሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለምሳሌ በተባበሩት መንግስታት፤ በዓለም ባንክ፤ በዓለም የገንዘብ ድርጅት ወ.ዘ.ተ አባል መሆን ጋር ፊጽሞ የተለያየ ነው። የዓለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን የአንድ ወገን (One Sided Affair) ጉዳይ እንደሆነ ይነገርለታል። ይህም ማለት ሁሉንም ከነባር አባላት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በሚገባ የማስተናገዱ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ የሚወድቀው በአመልካች ሃገር ጫንቃ ላይ ስለሚሆን ነው።

በማረካሽ ስምምነት አንቀጽ 12 መሠረት ማንኛውም በራሱ የውጭ ንግድ ግንኙነቶች ላይ ሉዓላዊነት ያለው መንግስት ወይንም ተሪቶሪ በድርድር ወቅት ከአባል ሃገራት ጋር በሚደረስ ስምምነት መሠረት የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ሊሆን እንደሚችል ተደንግጓል። WTOን የመሠረተው የማረካሽ ስምምነት አንቀጽ 12 ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

> *"1. Any State or separate customs territory possessing full autonomy in the conduct of its external commercial relations and of the other matters provided for in this Agreement and the Multilateral Trade Agreements may accede to this Agreement, on terms to be agreed between it and the WTO. Such accession shall apply to this Agreement and the Multilateral Trade Agreements annexed thereto.*
>
> *2. Decisions on accession shall be taken by the Ministerial Conference. The Ministerial Conference shall approve the agreement on the terms of accession by a two-thirds majority of the Members of the WTO.*
>
> *3. Accession to a Plurilateral Trade Agreement shall be governed by the provisions of that Agreement."*

አንድ አመልካች ሃገር ለአባልነት የምትከፍለው ዋጋ ወይንም የምትገባው ግዴታ ድርድሩን እንዲያስተባብር ለሚቋቋመው ለእያንዳንዱ የሥራ ቡድን የተተወ ጉዳይ ነው። ይህም በመሆኑ አንድ ሃገር ለአባልነት የከፈለው/የገባው ግዴታ ከሌላው ሃገር በጣም የተለየ ይሆናል።

የWTO የአባልነት ሂደት አራት ቴክኒካዊ ደረጃዎች ማለፍን የሚጠይቅ ሲሆን፤ ደረጃዎቹ ከዚህ እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርበዋል።

ደረጃ አንድ፡ ጥያቄ ማቅረቢያና የሥራ ቡድን መመሥረቻ፡- ማንኛውም የWTO አባል መሆን የሚፈልግ ሃገር በማረካሽ ስምምነት አንቀጽ 12 መሠረት ተደራድሮ አባል ለመሆን መፈለጉን የሚገልጽ ጥያቄ በጽሑፍ ለዳሬክተር ጄኔራሉ ማቅረብ ይጠበቅበታል። ዳሬክተር ጄኔራሉም ጥያቄውን ተቀብሎ ለቀጣዩ የጄኔራል ካውንስል ስብሰባ ያቀርባል። ጄኔራል ካውንስሉ ጥያቄውን መርምሮ በሙሉ ድምፅ ተቀባይነት ሲያገኝ (WTO ውስጥ ውሳኔ የሚተላለፈው በሁሉም አባል ሃገራት ስምምነት-Consensus መሠረት ነውና) ጉዳዩን የሚከታተል የሥራ ቡድን (Working Party) እንዲቋቋም ያደርጋል።

ደረጃ ሁለት፡ መረጃ ማሰባሰቢያ፡- ይህ ደረጃ አባል ሃገራት ስለ አመልካቿ ሃገር አጠቃላይ ኢኮኖሚ ሁኔታ በዋናነትም ስለ ውጭ ንግድ ሥርዓቱ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚያስችል ነው። ይህንን ደረጃ ለመጀመር አንድ አመልካች ሃገር በቅድሚያ የውጭ ንግድ ሥርዓት መግለጫ ሠነድ (Memorandum on the Foreign Trade Regime/MFTR) እንድታቀርብ ይደረጋል። ሠነዱ የሚዘጋጀው የዓለም ንግድ ድርጅት ሴክሬታሪያት በቃሚነት እንዲያገለግል ባዘጋጀው ፎርማት (Guideline) መሠረት ነው። ሠነዱም በሥራ ቡድኑ ይመረመራል፤ አባል ሃገራት በሠነዱ ላይ ጥያቄያቸውን በጽሑፍ ያቀርባሉ፤አመልካች ሃገር በጽሑፍ ምላሽ ይሰጣል፤ የሥራ ቡድኑ እስከሚረካ ድረስ ሂደቱ ይቀጥላል። በዚህ ደረጃ ላይ ከሚሞራንደሙ በተጨማሪ

ሌሎች ለድርድሩ አጋዥ የሆኑ ሠነዶችም (ACC Documents, Legislative Action Plan, etc) እንደአስፈላጊነቱ በየዘርፉ ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ይደረጋል።

ደረጃ ሦስት፡ ድርድር፡- ስለ አመልካቿ ሃገር አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ መረጃዎች ከተገኙ በኋላ የሥራ ቡድኑ ስብሰባ ይጠራል፤ የሥራ ቡድኑ በስብሰባው በዋናነት ከWTO ስምምነቶች ጋር የማይጣጣሙትን የአመልካች ሃገር የንግድ ሥርዓቶች ይመረምራል። አመልካች ሃገር በዕቃዎችና በአገልግሎት ዘርፎች ልትሰጥ የምትችለውን የገበያ እድል (Initial Offers) እንድታቀርብ በማድረግ የሁለትዮሽ (Bilateral) ድርድር ይካሄዳል:: የሁለትዮሽ ድርድሩ ብዛት በሥራ ቡድኑ ውስጥ በተካተቱ የአመልካች ሃገር ዋና የንግድ ሽሪኮች ብዛት የሚወሰን ነው። አጠቃላይና ሁሉንም የሚመለከቱ በሆኑ ጉዳዮች ላይም የብዙወገን (Multilateral) የንግድ ድርድሩ ጎን ለጎን ይቀጥላል። በመጨረሻም አመልካች ሃገር እና የሥራ ቡድኑ የአባልነት ዋጋውን(Terms and Conditions of Entry) ይወስናሉ። በዚህ ደረጃ ላይ ለየስብሰባው የተዘጋጁትን ቃለ-ጉባኤዎች በማጠናቀርን በማጠቃለል የሥራ ቡድኑ ረቂቅ ሪፖርቱን ያዘጋጃል።

*ደረጃ አራት፡ የአባልነት ፕሮቶኮል፡-*ይህ ደረጃ የአባልነት ሂደቱ መጨረሻ ሲሆን፤ የሥራ ቡድኑ ሪፖርት፤የአባልነት ፕሮቶኮል እንዲሁም አመልካች ሃገር የገባቻቸው ዝርዝር ግዴታዎች (List of Commitments) ተጠቃልሎ ለሚኒስትሮች ጉባዔ ወይንም ለጄኔራል ካውንስሉ ለውሳኔ ይቀርባል። የአባልነት ፕሮቶኮሉ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ከተደገፈ የአመልካች አባልነት እንደሚረጋገጥ በስምምነቱ ቢደነግግም፤ ከእስከ አሁኑ ልምድ ግን ይህ ተግባራዊ ሲሆን አልተስተዋለም። አባልነቱ በጉባዔው ከፀደቀ በኋላ አመልካችም ፕሮቶኮሉን በሃገሯ ፓርላማ እንድታስፀድቅ ተደርጎ የድርጅቱ አባል ትሆናለች።

6. ኢትዮጵያ የምትገኝበት ደረጃ

ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ጥያቄዋን ያቀረበችው እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 2003 ነበር። ጥያቄዋን ከማቅረቧ በፊት ለ6 ዓመታት ያህል በታዛቢነት ስትሳተፍ ቆይታለች። ጥያቄዋ ለጄኔራል ካውንስሉ ቀርቦ በሙሉ ድምፅ ተቀባይነት ያገኘውና የሥራ ቡድን የተቋቋመው እ.ኤ.አ በማርች 2003 ነው። ቀጥሎም በሃገር ውስጥ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ የብሔራዊ እና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተቋቋሙ። የቴክኒክ ኮሚቴውም ለሂደቱ መሠረታዊ የሆነውን ሚሞራንደም እንዲያዘጋጅ ተደረገ። ሠነዱ በየደረጃው እንዲገመገምና እንዲፀድቅ ከተደረገ በኋላ እ.ኤ.አ በዲሴምበር 2006 ለWTO ጽ/ቤት ተልኳል። ሃገሪቱም በአሁኑ ወቅት ከአባል ሃገራት በሚሞራንደሙ ላይ ለቀረቡ ጥያቄዎች ማብራሪያና ምላሾችን በመስጠት ላይ ትገኛለች። ከዚህ ከቀረበው ሁኔታ በአባልነት ሂደቱ፤ ሃገሪቱ በሁለተኛውና የመረጃ ማሰባሰቢያ በሚባለው ደረጃ ላይ የምትገኝ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በድርጅቱ ከሚኒስትሮች ጉባዔ ቀጥሎ ስልጣን ያለው አካል አጠቃላይ ምክር ቤት(General Council) **ሲሆን የተውጣጣውም አባል ሃገራት በጄኔቫ ከሚመደቧቸው አምባሳደሮች ወይንም ቋሚ መልዕክተኞች ነው፡፡ አጠቃላይ ምክር ቤቱ በየጊዜው በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች የተለያዩ ውሳኔዎችን ይሰጣል፡፡ ም/ቤቱ የአባል ሃገሮችን የንግድ ፖሊሲ ገምጋሚ** (Trade Policy Review) **እንዲሁም ግጭቶችን የሚፈታ አካል** (Dispute Settlement Body) **በመሆንም ያገለግላል፡፡ ከዚህ በተዋረድም ተጠሪነታቸው ለአጠቃላይ ም/ቤቱ የሆኑ የዕቃዎች፤ የአገልግሎቶችና የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ የተሰኙ ሶስት ካውንስሎች ይገኛሉ፡፡**

የአባልነት ሂደትን ማጠናቀቅ በጊዜ ገደብ የተወሰነ አይደለም፤ ፍጥነቱም በአብዛኛው በአመልካቹ ሃገር አፈፃፀም ላይ የተመሰረተ ነው። በእርግጥ ሂደቱን በማፋጠንና በማራዘም ተደራዳሪ ሃገሮች ተፅዕኖ የላቸውም ለማለት አይደለም። ለአንዳንዶቹ በጣም ረጅም (ቻይና 15 ዓመት አካባቢ)፤ ለሌሎቹ ደግሞ አጭር ጊዜ (ከርኪስታን 2 ዓመት) እንደወሰደባቸው ተሞክሮዎች ይሳያሉ። በሃገራችን የአባልነት ሂደቱ ይወስዳል ተብሎ በታሳቢነት የተቀመጠው ጊዜ 5 ዓመት ያህል ነው። ይህም ጊዜ ሚሞራንደሙ ለWTO ጽ/ቤት ከተላከበት እ.ኤ.አ 2006 መጨረሻ ጀምሮ የሚቆጠር ቢሆንም፤ የአባልነት ድርድሩ እ.ኤ.አ 2011 መጨረሻ አካባቢ ይገባደዳል ተብሎ ተገምቷል። ሃገሪቱ በሚሞራንደሙ ላይ ከአሜሪካና ካናዳ መንግስታት ወደ 220 የሚደርሱ ጥያቄዎችን እ.ኤ.አ ፌብሩዋሪ 2007 መጨረሻ ላይ የተቀበለች ሲሆን፤ ለጥያቄዎችም ምላሾች ተዘጋጅተው በብሔራዊ ኮሚቴው የፀደቁ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለጽ/ቤቱ የሚላኩ ይሆናል።

ከሃገሪቱ የWTO አባል መሆን ጋር በተያያዘ ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደ ሚሞራንደሙ ያሉ ሠነዶችና በሱ ላይ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልሶች ተዘጋጅተዋል። በሶስቱ የድርጅቱ ዋና ምሰሶዎች ማለትም በዕቃዎች፤ በአገልግሎቶችና በአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ዙሪያ በተለያዩ ዘርፎች የእንደምታ ጥናቶች ተካሂደዋል/በመካሄድም ላይ ናቸው። ረቂቅ የእንደምታ ጥናቶቹም የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በተሣተፉበት በአውደ ጥናት እንዲገመገሙ ተደርጓል። ሃገሪቱ ያወጣቻቸው ከንግድ ጋር የተያያዙ ህጎች ከWTO ስምምነቶች ጋር የተጣጣሙ ስለመሆናቸው የተወሰኑ የህግ ፍተሻ ሥራዎች ተከናውነዋል። በተለይም ለWTO የቴክኒክ ኮሚቴ አባላትና ባለሙያዎች የንግድ ድርድር ክህሎት ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። ድርጅቱን በቅርቡ የተቀላቀሉ የተወሰኑ ሃገራት የአባልነት ሂደት ተሞክሮዎች ባለድርሻዎች በተሳተፉበት እንዲቀርቡ ተደርጓል። ከWTO ህሁ ጀምሮ በስርዓቱ የተለያዩ ስምምነቶች ላይ በርካታ የአቅም ግንባታና የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት (በአብዛኛው በማዕከልና በተወሰኑ ክልሎች ጭምር) ተካሂደዋል/በመካሄድም ላይ ናቸው።

7. ከአባልነት ሊገኙ የሚችሉ ጥቅሞችና ፈታኝ ሁኔታዎች

7.1 ሊገኙ የሚችሉ ጥቅሞች

የWTO አባል መሆን ወደ ግለሰቦች ኪስ ከሚገባ ተጨማሪ ገቢ ጀምሮ ትላልቅ ጦርነቶችን እስከማስወገድ የሚዘልቁ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እደሚያካትት የተለያዩ ጽሑፎች ያስረዳሉ። ጽሑፎቹ እንደሚሉት WTO በህጎች የሚተዳደር የንግድ ሥርዓት በመሆኑ እነዚህ ህጎች ግብይቱን በቀላሉ ይመሩታል። የሥርዓቱ መሠረታዊ መርሆዎች ንግዱ የበለጠ ቀልጣፋና የተሳለጠ እንዲሆን ያበረታታሉ፤ መንግስትን የተለየ ፍላጎት ካላቸው ጥቂት ቡድኖች (Interest Lobby Groups) በንግድ ፖሊሲዎች ላይ ሊንፀባረቅ ከሚችል ተገቢ ያልሆነ ተጽዕኖ ይጠብቃል። በየስምምነቶቹ የተለያዩ የግልጽነት መሥፈርቶች በመቀመጣቸው ሥርዓቱ መልካም አስተዳደርን ያበረታታል፤ የንግድ ያለመግባባቶች ቢነሱ እንኳ ጉዳዮቹ ገንቢ በሆነ መልኩ የሚፈቱበት ሥርዓት ተበጅቷል፤ በመሆኑም ሥርዓቱ በአጠቃላይ ሠላምን ያራምዳል።

የአስተሳሰቡ አራማጆች በተጨማሪም ንግድ ሥርዓት ባለውና ነፃ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ ማድረግ የልውውጥ ወጪን በእጅጉ ይቀንሳል፤ ውድድርን ያበረታታል፤ ውድድር ካለ ደግሞ ተጠቃሚው ብዙ ምርጫ ይኖረዋል፤ በዚህ ሂደት ምርቶችና አገልግሎቶች በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ ይደረጋል፤ ንግድ

ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደዚህ ሲስፋፋ ደግሞ የሥራ መስክ ይከፍታል፣ የኢኮኖሚ እድገትን ያፋጥናል፤ ይህም ውሎ አድሮ በህብረተሰቡ የገቢ መጠን ላይ የሚንፀባረቅ ይሆናል በማለት ይመክራሉ።

ከላይ በጥቅሉ ከቀረቡት ጉዳዮች በመነሳት ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ሲታይ ከንግድ ሥርዓቱ ሊገኙ የሚታሰቡ ጥቅሞች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሀ. ጠንካራ ተቋማዊ አቅም ለመገንባት ያስችላል፣

የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ከመነሻው ሥርዓቱ የሚጠይቃቸውን የተለያዩ መስፈርቶች ማሟላትን የግድ ይላል። እነዚህ መስፈርቶችም በዋናነት ተቋማዊ አቅም መገንባትን የሚመለከቱ ናቸው። ይህም የአቅም ግንባታ ተግባር ዓለማቀፋዊ የንግድ ሥርዓቱ የሚጠይቀውን የሠለጠነ የሰው ሃይል (Trade Lawyers ,Economists, Skilled Negotiators)፤ ጠንካራ ተቋማት (WTO Representative Offices, National Standards, Customs)፤ እንዲሁም የመሠረተ ልማት (Roads, Ports, Telecommunications etc.) ማሟላትን ይጠይቃል። ስለሆነም ድርጅቱ በተለይም በልማት ወደኋላ ለቀሩ የእኛ አይነት ሃገሮች ከሌሎች የልማት አጋሮች ጋር በመሆን የሚሰጣቸው ልዩ ልዩ ድጋፎች ከዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያግዝ ጠንካራ ተቋማዊ አቅም ለመገንባት እድል ይፈጥራል።

ለ. አስተማማኝ የሆነ ገበያ ለማግኘት ይረዳል፣

በድርጅቱ መሠረታዊ መርሆዎች መሠረት አባል ሃገራት የታሪፍ ጣሪያ የመወሰን ግዴታ (Tariff Binding Commitment) እንዲሁም በየጊዜው የሚያወጧቸውን ህጎችና የንግድ አሰራሮች ማሳወቅ ስለሚጠበቅባቸው፤ ይህ ሁኔታ ለአባል ሃገራቱ የወጪ ምርቶችና አገልግሎቶች አስተማማኝና የበለጠ የሚታወቅ ገበያ እንዲኖራቸው ያስችላል። የWTO አባል ሳንሆን አሁን እያገኘናቸው ያሉት የገበያ እድሎች በሰጪዎቹ ሃገሮች ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ እንጂ አስገዳጅ ባለመሆናቸው ነገ ጧት ሊከለከሉ የሚችሉ ናቸው።

ሐ. የውጭ መዋዕለ ንዋይ ለመሳብ ያግዛል፣

የድርጅቱ ስምምነቶችና መሠረታዊ መርሆዎች በየጊዜው እንደተፈለገ የሚለዋወጡ አይደሉም። ይህም ሁኔታ የተረጋጋ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዲኖር ስለሚያስችል ለሃገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ባለሃብቶች ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። ይህም በተለይ ለውጭ መወዕለ ንዋይ (FDI) ፍሰት እንደ ትልቅ ሠርቲፊኬት ይቆጠራል።

መ. ከግልግል ሥርዓቱ ለመጠቀም ያስችላል፣

የዓለም ንግድ ድርጅት ከፈጠራቸው ሥርዓቶች አንዱ ከንግድ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ግጭቶችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለመዳኘት የፈጠረው ሥርዓት መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም የሚከሰቱ ያለመግባባቶች ግልፅና ሥርዓት ባለው ሁኔታ የሚፈቱ ስለሚሆን በአባላት መካከል ቀጣይነት ያለው የንግድ ግንኙነት እንዲኖር ይረዳል።

ሠ. ለተጠቃሚዎች የሚሰጠው የምርጫ እድል ያሰፋል፣

የንግድ ሥርዓቱ ውድድርን ስለሚያበረታታ ህብረተሰቡ በተሻለ ጥራትና ዋጋ አማራጭ ምርቶችና አገልግሎቶች እንዲቀርቡለት ሰፊ እድል ይሰጣል።

ረ. መገለልን (Marginalization) ለማስቀረት ያግዛል፣
የWTO አባል መሆንና አጠቃላይ በዓለም አቀፋዊ የንግድ ሥርዓቱ ተሳታፊ መሆን በሌሎች ዓለም አቀፋዊ የገንዘብ ተቋማትም ሆነ በበለፀጉ ሃገሮች ሊገጥም ከሚችል መገለል እንደሚከላከል ይገመታል።

7.2 ፈታኝ ሁኔታዎች

1. በተለይም በልማት ወደኋላ የቀሩት ሃገሮች የንግድ ፖሊሲዎቻቸውንና ህጎቻቸውን ከድርጅቱ ስምምነቶች ጋር ለማጣጣም የሚያደርጉት ጥረት ምናልባትም አቅማቸውን የሚፈታተንና ከፍተኛ የሆነ ወጪ ሊያስከትል መቻሉ፤

2. በተለይም ከአባልነት በኋላ በሚደረጉ ተከታታይ ድርድሮች ታሪፍ እንዲቀንስ የሚደረግ ስለሚሆን የሃገር ውስጥ ታዳጊ ኢንዱስትሪዎች ጠንካራ ለሆነ የውጭ ውድድር ሊጋለጡ የሚችል መሆኑ፤ በአገልግሎት ዘርፎችም ዘርፎቹን ለውጭ አቅራቢዎች ክፍት ማድረጉ የሃገር ውስጥ ባለሃብቶችን ለከፍተኛ ውድድር የሚያጋልጣቸው እንደሚሆን፤

3. ከአባልነት በኋላም ቢሆን በገቢ ምርቶች ላይ የሚጣለው ታሪፍ በድርድር የሚቀንስ መሆኑ በመንግስት አጠቃላይ የገቢ መጠን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር መቻሉ፤ በተለይም በልማት ወደኋላ በቀሩት ሃገሮች ከታሪፍ የሚሰበሰብ ገቢ መንግስት በታክስ ከሚያገኘው አጠቃላይ ገቢ ትልቁን ድርሻ ስለሚይዝ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ቀላል ያለመሆኑ፤ ወ.ዘ.ተ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓቱ ሊያስገኝ የሚችላቸው ጥቅሞች እንዲሁም ሊከሰቱ የሚችሉ ፈታኝ ሁኔታዎች ጎን ለጎን መኖራቸው አባል ለመሆን የሚወሰደውን እርምጃ አከራካሪ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡ አባል መሆን ያለመሆንን በአማራጭነት እያነሱ በተለያዩ ነጥቦች ዙሪያ መከራከር ይቻልም ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ አሁን በምንገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ የተሻለ ሊሆን የሚችለው የማይቀረውን (አሁንም ቢሆን በውስጡ ያለንበትን) ዓለም መቀላቀልና የሥርዓቱ አካል ሆኖ ጠንክሮ በመስራት በተወዳዳሪነት ለመዝለቅ መጣር ነው፡፡ የመቀላቀሉ ጉዳይ ግን በጥናት ላይ ተመስርቶ ብሄራዊ የድርድር አቋሞች (National Negotiation Positions) በየዘርፉ እየተዘጋጁ፤ አጠቃላይ የሃገርን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ሊኬድበት ይገባል፡፡ ለእንደዚህ ዓይነት ግብዓቶች በተለይም በምርምር ተቋማት አካባቢ ከተሰማሩ ባለሙያዎችና ከእንደዚህ ዓይነት የባለሙያዎች ስብስብ ማህበራት ብዙ ይጠበቃል፡፡ ከዓለም አቀፍ ስርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የመንግሥት አማካሪዎችና ምሁራን በጋራ መሥራት አለባቸው፡፡

8. ማጠቃለያ

በ1940 (እ.ኤ.አ) አንድ ዓለም አቀፍ የንግድ ተቋም ለመመስረት በተደገረው እንቅስቃሴ 23 በሚደርሱ አባላት በ1947 የተፈረመው GATT **ወደ 50 ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ የንግድ ድርድሩን ሲያስተባብር ቆይቶ እ.ኤ.አ በ1995 ለተመሰረተው ለዓለም ንግድ ድርጅት**(WTO) **ስልጣኑን አስረከበ፡፡**

በ GATT *ታሪክ* 8 **ያህል የንግድ ድርድር ዙሮች የተካሄዱ ሲሆን በርካታ ተግባራት የተከናወኑት በመጨረሻውና እ.ኤ.አ. ከ**1986-1994 **ድረስ በቆየው በኡራጓይ ዙር ነው፡፡**

WTO **ከተፈጠረ በኋላ የተጀመረውና በአሁኑ ጊዜ የምንገኝበት የንግድ ድርድር ዙር 9ኛው ዙር ሲሆን የዶሃ የንግድ ድርድር** (Doha Development Agenda/DDA) **በመባል ይታወቃል፡፡ የዶሃ የንግድ ድርድር የልማት አጀንዳን ትልቅ ስፍራ የሰጠው ሲሆን፤ ጉባዔው ያስቀመጣቸው ጉዳዮች አሁንም ገና በድርድር ሂደት ላይ ናቸው፡፡**

ኢትዮጵያ ወደ ዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓቱ በታዛቢነት መሳተፍ የጀመረችው እ.ኤ.አ በ1997 **ሲሆን፤ ተደራድራ አባል መሆን እንዲፈቀድላት ጥያቄዋን ያቀረበችው እ.ኤ.አ በ**2003 *መጀመሪያ* **ላይ ነበር፡፡ ሃገሪቱ ከአባልነት ጋር በተያያዘ በርካታ ተግባራትን ማከናወንና የተለያዩ ደረጃዎችን ማለፍ ይጠበቅባታል፡፡ እስከአሁን** *ለሂደቱ መሠረታዊ የሆነው ሚሞራንደም* **ተዘጋጅቶ ለ**WTO *ጽ/ቤት ተልኳል። በሚሞራንደሙ ላይ ከአሜሪካና ከካናዳ መንግስታት ለቀረቡ የመጀመሪያ ዙር ጥያቄዎች ምላሾች ተዘጋጅተዋል። በተለያዩ ዘርፎች የእንደምታ ጥናቶች ተካሂደዋል።*

የአባልነት ድርድሩን በብቃት ለመወጣት በቀጣይነት በርካታ ጉዳዮች መከናወን እንዳለባቸው ይታወቃል። ለዚህ ሃገራዊ ለሆነ ትልቅ ዓላማም ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል። ዋነኛው ጉዳይ ብሔራዊ ጥቅምን ሊያስጠብቅ የሚችል ሃገራዊ አቋም በየዘርፉ በማዘጋጀት በብቃት መደራደር ነው። ለዚህ ትልቅ ተግባር ዋና ተዋናኞች ኢትዮጵያውያን ምሁራን ናቸው።

9. ርዕይ

የዛሬ 20 ዓመት ማለትም በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2020 ዓ.ም ለሃገሬ የምመኘው፡- ዲሞክራሲ ሰላምና እኩልነት የሰፈነባት ንግድ ኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት የተስፋፋባት በዓለም ተወዳዳሪ የሆነችና መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገሮች ተርታ የተሰለፈች ኢትዮጵያን ማየት ነው።

ዋቢ መረጃዎች

1. The Doha Development Agenda (Doha Declarations) (2001).
2. Doha Work Program (2004): Decision Adopted by the General Council on 1 August 2004,WT/L/579.
3. The Legal Texts (2002): The Results of the Uruguay Round of Multilateral Trade Negotiations.
4. Setting the Trade Policy Agenda: What Roles for Economists? (2005)

5. The Sixth Ministerial Conference, Hong Kong 13-18 December 2005 (WT/MIN (05) DEC.
6. Understanding the WTO (2006)

የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት (EPAs): የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁኔታ

አሚን አብደላ[1]

1. መግቢያ

በአስገራሚ ፍጥነት እያደገ በመጣው የትራንሰፖርትና የመገናኛ ቴክኖሎጂ የተነሳ ዓለማችን ወደ አንድ መንደርነት እየተቀየረች ከመጠች ሰንበትበት ብላለች። ከዚህ ውኽደትና አንዱ ሀገር ከሌላው ጋር ተቆራኝቶ ባለበት ሁኔታ ለብቻ ተነጥሎና በርን ዘግቶ መኖር የማይቻልበት ደረጃ ላይ በመደረሱ ወደ ዓለም ኢኮኖሚ ውህደት መጓዝ የግድ ይላል።

ከዚህ አኳያ ሀገራችን በአሁኑ ወቅት ሶስት የተለያዩ የንግድ ድርድሮችን እያካሄደች ትገኛለች። እነርሱም WTO, የCOMESA FTA & የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት (EPAs) ናቸው። ከእነዚህ መካከል ዋንኛው ከአውሮፓ የንግድ ሽረኮች ጋር ወደ ነፂ የንግድ ቀጠና ምስረታ የሚያመራው የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት (EPAs) ነው።

ላለፉት 3 አሥርት ዓመታት በአውሮፖ ህብረትና በአፍሪካ፣ ካሪቢያንና ፓስፊክ (ACP) ሀገሮች መካከል የነበረው የንግድ ግንኙነት በሁለትዮሽ የሚመራ የተለያዩ ስምምነቶች ነበሩ። ስምምነቶቹም የተቀረፁበት ዋነኛው ዓላማ የACP ሀገሮች በአውሮፓ ህብረት ገበያ ውስጥ የተሻለ ዕድል እንዲያገኙ ታስቦ ነበር። ስምምነቶቹም እ.ኤ.አ ከ1975 እስከ 200ዐ የሎሜ እና ከ200ዐ እስከ ጃንዋሪ 2008 የኮቶኑ ናቸው።

በሎሜው ስምምነት የACP ሀገሮች ምርቶች በአውሮፖ ህብረት ገበያ ውስጥ አቻ ለአቻ ባልሆነ (Non-reciprocal) መልኩና የተሻለ ዕድል ተሠጥቶአቸው ገበያ ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል። የACP ሀገሮች የፋብሪካ ምርቶች ከቀረጥና ከኮታ ነፂ ሙሉ ለሙሉ የሚገቡ ሲሆን የእርሻ ምርቶች ግን ከአውሮፖ ህብረት የጋራ የእርሻ ፖሊሲ አኳያ እየታዩ እንዲገቡ ይደረጋል።

የዚህች አጭር ፅሑፍ ዓላማ በአውሮፓ ህብረት እና ACP ሀገሮች መካከል እየተደረገ ያለውን ወደ ነጻ የንግድ ቀጠና የሚያመራውን የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት (EPAs) ድርድር አጠቃላይ ሁኔታና የሀገራችንን የመፈረም ሁኔታ በመዳሰስ ለውይይት ማቅረብ ነው።

[1] አቶ አሚን አብደላ በ1987 የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ በ1993 የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ ፖሊሲ አናሊስስ ከ አ.አ. ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል። ከነሐሴ 1987 እስከ መስከረም 1999 ዓ.ም. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና በብሔራዊ ባንክ ያገለገሉ ሲሆን ከጥቅምት 1999 ጀምሮ በ EEA/EEPRI የንግድና ኢንዱስትሪ ቡድን ውስጥ ተመራማሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

2. የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት ታሪካዊ አመጣጥና ከWTO ጋር መጣጣም

ታሪካዊ አመጣጥ

የአፍሪካ፣ ካሪቢያንና ፓስፊክ ሀገሮች ከአውሮፓ ህብረት ጋር የኢኮኖሚ ግንኙነት በ1957 የሮማ ስምምነት መሠረት ተመሠረተ። የግንኙነቱ መነሻ የACP ሀገሮችን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማትና ዕድገትን የማገዝ መርህ ይዞ ነበር። ይህም የACP ሀገሮች ከአውሮፓ ህብረት ጋር አቻ ባልሆነ (Non-Reciprocal) **መልኩ መነገድ እንዲችሉና ቅድሚያና የተሻለ የገበያ ዕድል** (Special and Differential Treatment) **አግኝተው ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሳድጉ ማመቻቸት ነበር።**

በዚህም መሰረት ከ ACP **ሀገሮች ወደ አውሮፓ ገበያ ከሚገቡት ምርቶች ውስጥ** 96.5 **በመቶ የሚሆነው ከቀረጥና ከኮታ ነፃ የሚገቡ መሆኑን መረጃዎች ይሳያሉ። የ**1996 **የአውሮፓ አረንጓዴው ሠነድ የ**ACP **ሀገሮች በ**1976 **በአውሮፓ ህብረት ገበያ ውስጥ ከነበራቸው የ**6.7 **በመቶ ድርሻ በ**1994 **ወደ** 2.8 **በመቶ ዝቅ ማለቱን አሳይቶ የሎሜው የንግድ ስምምነት ውጤት በአጠቃላይ ተስፋ አስቆራጭ እንደ ነበር ደምድሞአል።**

የዓለም ባንክ የ2004 *ሪፖርትም* **እንደዚሁ በአደጉና በታዳጊ ሀገሮች መካከል የሚመሠረተው የነፃ ንግድ ቀጠና አቻ ለአቻ** (Reciprocal) **ካልሆነ በስተቀር ታዳጊ ሀገሮች ተጠቃሚ እንደማይሆኑ ያሳያል። ለዚህም የአቻ ለአቻ ያልሆነው ግንኙነትና የሎሜው ስምምነቶች እስከ አሁን ድረስ አጥጋቢ ውጤት እንዳላስገኙ ማስረጃነት ያደርጋሉ።**

የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት

የመጣው በአውሮፓ ህብረት እና በACP **ሀገሮች መካከል የነበረው ቅድሚያና የተሻለ የገበያ ዕድል በመስጠት ላይ የተመሰረተው የንግድ ስምምነት እ.ኤአ በዲሴምበር** 31 **ቀን** 2007 **የሚያበቃ በመሆኑ በምትኩ ከ**WTO *ጋር* **የሚጣጣም አዲስ የንግድ ስምምነት መፈረም የግድ ስለሆነ ነው።**

የተናጠል የንግድ ዕድል (Unilateral trade preference) *መስጠት* **የሚመለከተው የ**WTO **ህግ የ**Enabling **አንቀፅ ነው። ይህ አንቀፅ የተለየ የንግድ ዕድል መስጠት የሚቻለው ሀገሮችን እንደ የልማት ደረጃቸው በመለየት ብቻ ነው ይላል። ይህም ማለት ዕድሉ መስጠት የፈለገ ሀገር ለሁሉም በማደግ ላይ ለሚገኙ በሙሉ ወይንም በልማት ወደኃላ ለቀሩ** (LCDs) **በሙሉ ነው እንጂ ገሮችን በተለያዩ ምክንያቶች ለያይቶ መሆን እንደሌለበት ይገልጻል። የሎሜው ስምምነት ግን ዕድሉን ለ**ACP **ሀገሮች ብቻ ነጥሎ ሲሰጥ ነበር። ይህ ሁኔታ ነው የሎሜውን ስምምነት ከ** WTO **የ**Enabling **አንቀፅ ጋር እንዳይጣጣም ያደረገውና ለውጡን ያስገደደው።**

ከዚህም በተጨማሪ ለውጡን ያስገደደው ነገር ተመሳሳይ ዕድል ከአውሮፓ ህብረት የተነፈጋቸው ሌሎች በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገሮች ከWTO ህግ አንፃር የዕድሉን ህጋዊነት ጥያቄ ውስጥ ስላስገቡት በአውሮፓ ህብረት እና በACP ሀገሮች የተናጠል የንግድ ዕድል የሚያበቃበትን ጊዜ ለማራዘምና ይህንን የሚመለከት የWTO ህግ ተፈፃሚ እንዳይሆን (waiver) መጠየቅ የግድ ስለሆነ ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በ2001 ተጠይቆ የተፈቀደው waiver እስከ ዲሴምበር 31 ቀን 2007 ብቻ ሊራዘም ችሎአል።

ይህ የተሠጠው waiver ማብቂያው መቃረቡ በአውሮፓ ህብረት እና በACP ሀገሮችመካ»ል የሚኖረዉ የንግድ ግንኙነት ከWTO ህግ ጋር እንዲጣጣም ሁለት ግልፅ አማራጮች ብቻ ነበሩት። አንደኛው የአውሮፓ ህብረት የሚሰጠውን ዕድል ከ WTO Enabling አንቀፅ ጋር እንዲጣጣም አድርጐ ለሁሉም በማደግ ላይ ለሚገኙ ወይም ለሁሉም LDCs መስጠት። ይህንን ማድረግ ለACP ሀገሮች ብቻ የተሠጠውን ዕድል የሚሸረሽርና የወጪ ንግዳቸውን ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው። ሁለተኛው የነፃ ቀጠና ስምምነት በአውሮፓ ህብርትና በACP ሀገሮች መካከል መመስረት ነው። ይህንን ሁለተኛውን አማራጭ ነው የአውሮፓ ህብረት ተቀብሎ የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት እንዲፈረም የወሰነው።

2.2 የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነትን ከWTO ጋር መጣጣም የአውሮፓ ህብረት፤ ከ77 የACP ሀገሮች ደግሞ 55ቱ የዓለም አቀፉ የንግድ ድርጅት (WTO) አባል ሀገሮች ናቸው። በመሆኑም የድርጅቱ አባል ሀገሮች የሚፈርሟቸው ማናቸውም የንግድ ስምምነቶች የዓለም አቀፉ የንግድ ድርጅት ህግ ጋር መጣጣም ግድ ይላል።

በዚሁ የአለም አቀፉ የንግድ ድርጅት ህግ መሠረት ልዩ ድጋፍ መስጠት በሀገሮች መካከል መለያየትና መድሎ መኖር የለበትም (Most Favored Nations, MFN treatment) የሚለውን መርህ ሲተላለፍ አቻ ለአቻ ያልሆነ (Non-reciprocity) የንግድ ስምምነት ደግሞ በነፃ ቀጠና የንግድ ስምምነት ውስጥ በWTO የተሠጠውን ልዩ መብት ይጥሳል።

እነዚህን የዓለም አቀፉ የንግድ ድርጅት(WTO) ህግ እየጣሱ መቀጠል የማይቻል በመሆኑ በአውሮፓ ህብርትና በACP ሀገሮች መካከል የነበረውን የንግድ ስምምነት ከWTO ሕግ ጋር እንዲጣጣም አድርጎ መቀየር አስፈልጎአል።

የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነትን ከዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅት ጋር ለማጣጣም በነፃ ቀጠና የንግድ ስምምነት ሥር የ GATT አንቀፅ 24ን ማሟላት ይኖርበታል። ይህ አንቀፅ ግን በራሱ ያለቀለት ባለመሆኑ በዶሃ ዙር (Doha Round) ድርድር ማሻሻያ እየተደረገበት ይገኛል። ይህ አንቀፅ በታዳጊ ሀገሮች መካከል preferential regional agreement እንዲኖር የሚፈቅድ ሲሆን እንዲሻሻል የተፈለገው አንቀፁ አድማሱን አስፍቶ በአደጉና በታዳጊ ሀገሮች መካከል የሚፈጠረውን ነፃ ቀጠናን እንዲያካትት ነው። ከዚህም

በተጨማሪ ለታዳጊ ሀገሮች የተለየ የንግድ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ይጠይቃል። በዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅት ውስጥ ያልተቋጩ የንግድ ድርድሮች ከሚፈለገው በላይ መዘግየታቸው በEPAs በወቅቱ መገባደድ ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ አሳድሯል።

በመሰረቱ በኮቶኑ ስምምነት ላይ የተቀመጠው የዲሴምበር 31 ቀን 2007 ቀነ-ገደብ ታሳቢ አድርጐት የነበረው የነፂ ቀጠናን የንግድ ስምምነት የሚመለከተው የWTO ህግ በዶሃ ዙር (Doha Round) ድርድር EPAs ከመገባደዱ አስቀድሞ ይሻሻላል የሚል ታሳቢ አድርጎ ነው።

ምንም እንኳ የአውሮፓ ህብረት እና ACP ሀገሮች ህጉ መሻሻል እንዳለበት ከስምምነት የደረሱ ቢሆንም የዶሀው ዙር(Doha Round) ድርድር ባለመቋጨቱ የተነሳ ACP ሀገሮች በወቅቱ ባለው ህግ እንዲገዙ አስገድዶአል።

የሁለቱን ወገኖች የንግድ ግንኙነት ከWTO የማጣጣሙ ሥራ በአንድ ጊዜ የሚከናወን ሳይሆን ደረጃ በደረጃ የሚፈፀም በመሆኑ በሁለቱ መካከል በርን የመክፈቱ ሁኔታ በ reciprocity ላይ የተመሰረተ ሆኖ መበላለጥ (**Asymmetry**) ይኖረዋል። ይህም ማለት ለACP ሀገሮች ረዥም የሽግግር ወቅት መስጠት አንደኛው ሲሆን ሌላኛው የታሪፍና ሌሎች ንግድን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ህጎች መነሳት ላይ ከሁለቱ ወገኖች የሚጠበቅባቸው ሁኔታ ነው<።

በመሠረቱ የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት ወደ ነፂ የንግድ ቀጠና ምሥረታ የሚያመራ ጊዜያዊ ስምምነት ነው። በመሆኑም የነፂው ቀጠና ምስረታ አጠቃላይ ዕቅድና ተፈፃሚ የሚያደርገው ተቀባይነት ያለው ረዥም የጊዜ ገደብ እንዲኖረው ያስፈልጋል።

የሽግግር ጊዜን በሚመለከት እንደ GATT አንቀፅ 24 መሠረት ከ10 ዓመት መብለጥ የለበትም። ከዚህ የረዘመ ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ጉዳዩ የተለየ መሆኑ በቂ ማብራሪያ ሲኖረው ብቻ ተቀባይነት እንደሚኖረው ያትታል።

እንደ ACP ሀገሮች አመለካከት የሽግግር ወቅቱ ርዝመት ውሳኔ የታዳጊ ሀገሮችን የንግድ የዕድገትና የፋይናንስ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ታይቶ መሆን ይኖርበታል የሚል ነው። ያም ሆነ ይህ የሽግግር ወቅቱ ከፊርማው ቀን አንስቶ ከ18 ዓመት በታች ያጠረ መሆን የለበትም የሚል አቋም ይንፀባረቃል።

ሌላው መስፈርት የነፂ ቀጠና ስምምነት ላይ በሚደረስበት ጊዜ የታሪፍና ሌሎች ንግድን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ህጎች ከሞላ ጐደል ከሁሉም የሸቀጥ ንግዶች (Substantially all the trade) ላይ መነሳት ይኖርባቸዋል የሚል ነው። እንደ EU አቅዋም 90 በመቶ የሚሆነው የንግድ መጠን በመካከላቸው ነፂ

መሆን ያለበት ቢሆንም መቶኛው በሁለቱ ወገኖች መካከል የተለያየ ጥመርታዎች ይኖሩታል። አውሮፓ መቶ በመቶ በሩን የሚከፍት ከሆነ የACP ሀገሮች ግን 80 በመቶ ብቻ ይጠበቅባቸዋል ምክንያቱም በአማካይ 90 በመቶ ስለሚሆን። ይህ ደግሞ የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት ከዓለም አቀፉ የንግድ ድርጅት ህግ ጋር እንዲጣጣም ያደርገዋል።

3. የድርድር ሂደትና የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ

የACP ሀገሮች ከአውሮፓ ህብረት ጋር የእያንዳንዱ አባል ሀገር ብቻውን መደራደር አስቸጋሪ መሆኑን በመረዳታቸው የተነሳ ጥቅማቸውን ለማስከበር ሲሉ እራሳቸውን በተለያዩ ቡድኖች በማደራጀትና የጋራ አቋም የሚይዙበትን ሥልት በመንደፍ ድርድሩን ለማካሄድ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ። ለዚህም ስኬታማነት እነዚህ የACP ሀገሮች በስድስት ክልላዊ ቡድኖች ተከፍለዋል።

ኢትዮጵያም 16 ሀገሮች በአባልነት የሚገኙበት የESA[2] ማለትም የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ ሀገሮች የተደራዳሪ ቡድን ውስጥ ገብታ ከአውሮፓ ህብርት ጋር በመደራደር ላይ ትገኛለች።
በድርድሩ ደንብ መሰረት ድርድሩ ከመጀመሩ አስቀድሞ እያንዳንዱ ሀገር የNational Development and Trade Policy Forum (NDTPF) ማቋቋም አለበት።

የሚቋቋመውም ፎረም ከመንግሥት ፤ ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚና ከሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች በሚውጣጡ የኮሚቴ አባላት ይሆናል። በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያም ይህንን ብሔራዊ ፎረም እ.ኤ.አ. ጁላይ 22 ቀን 2004 በኦፊሴል አቋቁማለች[3]።

የዚህ ሀገራዊ ፎረም ዋነኛ ተግባር የእያንዳንዱን ሀገር አቋም የሚገልፅ ሠነድ ማዘጋጀት ነው። ይህም አቋም የሚዘጋጀው የNational Study on the Impact and Sustainability of the EPA for Ethiopia ጥናት ግኝት ላይ መሠረት በማድረግ ነው። በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያም የራስዋን ጥናት አካሂዳ በእርሱም ላይ በመመስረት የአቋም ሠነድ አዘጋጅታለች ።

ይህ ከተገባደደ በኃላ የየሀገሮቹ የNDTPF ቡድኖች የየሀገራቸውን አቋም በESA የጋራ መድረክ ላይ በማቅረብ በቀጠናው ደረጃ ድርድር ማካሄድ ነው። በESA ውስጥ በሚደረገው የአባል ሀገሮች ድርድር

[2] የ ESA ሀገሮች ቡሩንዲ፣ ኮሞሮስ፣ ዲ.ሪ.ኮንጎ፣ ጂቡቲ፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ማዳጋስከር፣ ማላዊ፣ ሞሪሸስ፣ ሩዋንዳ፣ ሲሸልሽ፣ ሱዳን፣ ዩጋንዳ፣ ዛምቢያ እና ዝምባቤ ናቸው።

[3] MOTI, 2007. the *National Study on the Impact and Sustainability of the EPA for Ethiopia(Draft final)*

የቀረበው ሰነድ ከዳበረ በኃላ የESA ሀገሮች አንድ የጋራ አቋም በመሆን ከአውሮፓ ህብረት ጋር ለሚኖረው ድርድር መነሻ እንዲሆን ለህብረቱ ይቀርባል። ይህንን ሰነድ መሰረት አድርገው ነው ብራስልስ የሚገኙት የESA አምባሳደሮችና የየሀገሩ የንግድ ሚኒስትሮች ከአውሮፓ ህብረት ጋር ድርድር የሚያካሄዱት።

ድርድሩ በሶስት ደረጃ የሚከናወን ነው። እነርሱም የቅድሚያ ትኩረት ርዕሶችን የመለየት፤ በቅድሚያ ትኩረት ላይ መደራደርና የማጠናቀቅ ናቸው። በቅድሚያ ትኩረት ስር የአውሮፓ ህብረትና የACP ሀገሮች ስድስት ዋና ዋና አርዕስተ ጉዳዩችን ለይተዋል። እነርሱም የገበያ ዕድል፣ እርሻ፣ ዓሣ፣ የልማት ትብብር ፤ የአገልግሎት ንግድና ከንግድ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። በእነዚህ ላይ ላለፉት 4 ዓመታት ድርድር ሲካሄድ ቢቆይም እስከአሁን ሙሉ በሙሉ መቋጫ አላገኘም።

3.1 የግሉ ክ/ኢኮኖሚ/የሲቪል ማህበረሰብ ግንዛቤ፤ ተሳትፎ እና ዝግጅት

የACP ሀገሮች የግሉ ክ/ኢኮኖሚ የEPAs ስምምነት መፈረም የተነሳ ለሚከተለው አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖዎች ግንባር ቀደም ተቋዳሽ በመሆኑ ስለስምምነቱም ሆነ ድርድሩ ይዘት አትኩሮት መስጠት ይጠበቅበታል።

ይሁን እንጂ የሀገራችን የግሉ ክ/ኢኮኖሚ በሰነድ አዘጋጅ ኮሚቴ በአባልነት ደረጃ የተወከለ ቢሆንም የተሳትፎው ደረጃና ጥልቀት ምን ያህል ትርጉም ያለውና ውጤታማ እንደሆነ ግልፅ አይደለም።

የሌሎች ሀገሮችን ልምድ ያየን እንደሆነ የግሉ ክ/ኢኮኖሚ ተሳትፎና ግንዛቤ እጅግ የላቀ ነው። በአንዳንድ አፍሪካ ሀገሮች የግሉን ክ/ኢኮኖሚ የሚወክሉ ቡድኖች ከስምምነቱ ተጠቃሚ ነን ብለው የሚያስቡት ስምምነቱን መንግስታቸው በአፋጣኝ እንዲፈርም በመወትወት ላይ ሲገኙ በአንፃሩ ተጐጂ እንሆናለን ያሉት ወገኖች ደግሞ ስምምነቱ እንዳይፈረም የበኩላቸውን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ኬኒያን የወሰድን እንደሆነ የአበባ ላኪዎች EPAsን በወቅቱ ያለመፈረምን ተከትሎ የሚከሰትባቸውን የንግድ መቋረጥ ወይንም በአውሮፓ ገበያ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ከፍተኛ የታሪፍ ምጣኔ ከግምት በማስገባት መንግሥታቸው ፊርማውን በቀነ-ገደቡ እንዲያኖር እየተሯሯጡ ሲሆን በአንፃሩ በስምምነቱ ምክንያት 65 በመቶ የሚሆነው የአምራች እንዱስትሪዎች ተጐጂ በመሆናቸው የተቃውሞ ድምፂቸውን እያሰሙ ይገኛሉ[4]። እንዲሁም ሌሎች አነስተኛ እና ያልተደራጁ አምራቾችና ድሆች ደካማ ከመሆናቸው የተነሳ ድምፂቸው ሊያሰሙ ባለመቻላቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ድምፅ ሆኗቸው ሲንቀሳቀሱ ይታያል።

[4] Oxfam, a matter of political will: how the European Union can maintain market access for African Caribbean and pacific countries in the absence of economic partnership agreements, briefing note April 2007.

በዚህ ረገድ ሀገራችን ላይ የሚታይ እንቅስቃሴ የለም። ምናልባት ስምምነቱን ለመፈረም የማትገደድ መሆኑን ታስቢ በመውሰድ ይሁን ወይንም ከግንዛቤ ዕጥረት በሀገራችን የሌሎች ሀገሮች መሰል እንቅስንቅንቃሴ በግሉም ሆነ በሲቪል ማህበረሰብ በኩል አይታይም።

ስምምነቱ ከሞላ ጎደል የንግድ እንደመሆኑ ከመፈረሙ በፊት የንግዱ ማህበረሰብ የበኩሉን ተሳትፎና ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅበታል። የተሳትፎውም ደረጃ ከስም የመወከል ያለፈና በግሉ ክ/ኢኮኖሚ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አሉታዊና አወንታዊ ተፅዕኖ በጥናት አስደግፎ ማቅረብ ይጠበቅበታል። ከዚህም አልፎ የጥናቱ ውጤት በሀገራዊ የአቋም ሠነዱ ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ የግሉ ተሳትፎ ተፈላጊ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም።

የሲቪል ማህበረሰቡም ቢሆን ድምፅ የሌላቸውን ተጎጂ የህብረተሰብ ክፍሎችን ወክለው ጉዳዩን በመከታተል አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በአንፃሩ በአውሮፓ ወገን ጥቅማቸውን ለማስከበር ከመቻኮል የተነሳ ስምምነቱ ያለ ACP ሀገሮች የህዝብ ተወካዮች ውሳኔ በጥድፊያ ሊፈረም እንደሚገባ ጊፊት ሲያደርጉ ይታያል፡፡ ለዚህም የአውሮፓ የንግድ ኮሚሽነር ማንዴልሰን በማርች 2007 በሚኒስትሮች የጋራ ኮሚቴ ላይ የተናገሩትን መጥቀስ ይቻላል[5]:: ይህ የህዝብ ተወካዮች ያላሳተፈ ውሳኔ የአውሮፓ ህብረት የዲሞክራሲ መጎልበትና የመንግስት የውሳኔ አሰጣጥ ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን የያዘውን ፖሊሲ የሚፃረር አካሄድ ነው፡፡

4. የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት የመፈረም ጉዳትና ጥቅም

አቻ ለአቻ ያልነበረው ስምምነት የሚበቃበት ቀነ ገደብ ተቃርቦአል። የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት ይፈረማል ወይስ አይፈረምም? አቻ ለአቻ ያልነበረው የንግድ ስምምነት ኢኮኖሚያቸውን ያላሻሻለላቸው የACP ሀገሮች የነፂ የንግድ ስምምነት የት ሊያደርሳቸው ይችላል? ቢፈረም ምን ጥቅምና ጉዳት ባይፈረም ደግሞ ምን ጉዳት ሊያስከትል፤ ምን ጥቅም ይቀርብናል የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተው የተለያዩ ሐሳቦች የተሰጡበት ይገኛሉ።

4.1 ጉዳትና ጥቅም

እንደሚታወቀው በ1980ዎቹ በርካታ የአፍሪካ አገሮች Structural Adjustment Program (SAP) ተብሎ የሚታወቀው የማዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም በዓለም ባንክና በአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF)

[5] Commissioner Mandelson, joint Ministerial Trade Committee, March 2007.

አማካይነት ተግባራዊ ማድረግ ጀምረው ነበር፡፡ ከዚህ ፕሮግራም እርምጃዎች መካከል የንግድ ቁጥጥርን ማላላት በአፍሪካ ዋንኛው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች የተሻለ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ አለመቻላቸው እንዲያውም ተግባራዊ ያደረጉ ሀገሮችን ወደ ድህነት በማምራቱ የተነሳ የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች ቀይሰው በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡

የተባበሩት መንግስታት መረጃም SAPን ተግባራዊ ያደረጉ አገሮች ቀድሞ ከነበሩበት የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ደረጃ አሽቆልቁለው መገኘታቸውን ያሳያል[6]፡፡ በነዚህ አገሮች የድህነት ሁኔታ ከመባባሱ የተነሳ SAP ተግባራዊ መደረጉ ተቋርጦ ሀገሮች የድህነት ቅነሳ እስትራቴጂ ሰነድ አዘጋጅተው ለትግበራ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸው ይታወሳል፡፡ ሀገራችንም በዚሁ ሂደት ውስጥ የምትገኝ ናት:: ይህ ክስተት የቅርብ ጊዜ ትውስታሆኖ ያለ እነዚህን ሀገሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢኮኖሚያቸውን ሙሉ ለሙሉ እንዲከፍቱ ለምን ይዋከባሉ?

ምንም እንኳ የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት የACP ሀገሮችን ከዓለም ኢኮኖሚ ጋር ለማዋሃድ፤ ዘለቄታዊ ልማት ለማምጣትና ድህነትን የማስወገድ ዓላማ ይዞ የተነሳ ቢመስልም የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት ድርድር ይዘት ግን እነዚህን ዓላማዎች የሚያሳኩ መስሎ አይታይም።

በተጨማሪም EU የACP ሀገሮች ከአገልግሎትና ከንግድ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ ድርድር ውስጥ እንዲገቡ ግፊት እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ግፊት የACP ሀገሮች የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማታቸው ላይ እንደምታ አለው፡፡ ይህ ጥረታቸው የሚያሳየው እነዚህ ሀገሮች የሀገሮቻቸውን ዕድገት ለማፋጠን የሚያወጡት ፖሊሲ እንደፈለጋቸው መጋፋት መቻላቸውንና አውሮፓውያን ለሀገራቸው ዕቃዎችና አገልግሎት ላኪዎች እንዴት አዳዲስ ዕድሎችን ለመፍጠር እየጣሩ መሆኑን ነው፡፡

የEBA ዕድል በመኖሩ የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት የሀገሮቹን ከአውሮፓ ህብረት ጋር የሚኖራቸው የንግድ ግንኙነት ወደ አቻ ለአቻነት /Reciprocity/ ከማሸጋገር በስተቀር አዲስ የገበያ ዕድል ሊፈጥርላቸው እንደማይችል ይታወቃል። ምክንያቱም ቀድሞም ቢሆን ከ95 በመቶ በላይ የሚሆነው የACP ሀገሮች ምርቶች የገበያ ዕድል ነበራቸው ችግሩ የማምረትና የማቅረብ እንጂ መች የገበያ ነበረ?

እንደ አብዛኞቹ ምሁራን አዲሱ ACPእና የአውሮፓ ህብረት የነፂ ንግድ ስምምነት ACP ሀገሮች አቅም በእጅጉ እስካልተገባ ድረስ አሁን ባለው ሁኔታ ልማትን ሊያመጣ እንደማይችል ይናገራሉ። ይህም አቅም የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነትን የማቀድና የማስፈፀም ብቻ ሳይሆን የማምረትና የመነገድ አቅምን ያጠቃልላል።

[6] Economic and social council, realization of economic and social cultural rights:2nd progress report 18 july 1991 E/CN.4/sub2/ 1991/17.

EPAs ገበያን የማስፋፋትና ልማትን ለማፋጠን ይረዳል እንድሁም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ይስባል ተብሎ ይገመታል። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ አወንታዊ ገፅታዎች በተለያዩ መሟላት በሚገባቸው ሁኔታዎች የታጠሩ ናቸው።

በEPAs ዙርያ የተደርጉ በርካታ ጥናቶች ከተከተሉት የጥናት ሥልት ደካማነት፣ የመረጃ ዕጦትና ሌሎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉድለቶች ምክንያት የተነሳ ግኝቶቹን አስተማማኝ አድርጎ መውሰድ ያስቸግራል። እነርሱም፡-

1. ጥናቶቹ በንግድ ላይ ብቻ ማተኮራቸው፤
2. በመንግሥት ገቢ መቀነስ ያለውን ቀጥተኛ ተፅዕኖ ላይ ብቻ ማተኮራቸው፤
3. ከተወዳዳሪነት ብቃት፣ ሥራ፣ ዕድል ፈጠራና ከኢኮኖሚ ዕድገት አኳያ በጥልቀት አለመዳሰሳቸውና፤
4. quantitative ሳይሆን qualitative የጥናት ስልትን መሠረት ማድረጋቸው ከሚጠቀሱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የጥናቶቹ ቁልፍ ግኝቶች፡-

1. የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት የንግድ ፈሰትን እንደሚጨምር፤
2. የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት የንግድን ከተፈራራሚዎቹ ወደ ሌላ ሀገር ከማዞር (Trade divertion) ይልቅ ንግድን በመካከላቸው መፍጥር (Trade Creation);
3. የEU የጋራ የእርሻ ፖሊሲ የእርሻ ምርቶቻቸውን ዋጋ ከ50 - 70 በመቶ እንዲቀንስ ከማድረጉ የተነሳ ACP ሀገሮችን ገበሬዎች ወደ ባሰ ድህነት የሚከታቸውና አፍሪካውያን የአውሮፓ ባለፋብሪካዎች የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ሆነው እንዲወሰኑ ማድረጉ፤ የመንግሥትን ገቢ እንደሚቀንስ፤ የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን (UNECA) ስሌት መሠረት ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች ላይ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሚደረገዉ EPAs በዓመት ወደ 1.52 ቢሊዮን ዩሮ የታሪፍ ገቢ እጦት ሊያስከትል እንደሚችል ያሳያል፡፡ ይህ የታሪፍ ገቢ መቀነስ ደግሞ የአፍሪካ መንግስታት የዜጎቻቸውን የመሠረታዊ የማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦትና አስጣጥ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ በማሳደር ከድህነት ለመውጣት የሚያደርጉትን ጥረት ሊያደናቅፍ እንደሚችል፡፡ እንዲሁም
4. የACP ሀገሮች ሸማቾችን ተጠቃሚ፤ ነገር ግን አምራች እንዱስትዎችን ተጐጂ እንደሚያደርግ የሚያሳዩ ናቸው።

በኢትዮጵያም የተደረገው ጥናት ከላይ የተጠቀሱ ጉድለቶችን የሚጋራ ነው። በተጨማሪም የጥናቱን መደምደሚያዎች ለመቀበል የሚስቸግሩ ናቸው። ለመጥቀስ ያህል የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪዎች የእንቨስትመንት ማሽነሪዎችን በነፃ የሚያስገቡ ስለሆነ ከኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት ተጠቃሚ

እንደሚሆኑ ማሳየቱ ጥናቱ የስምምነቱን ጉዳት ከወደፊት (dynamic impact) አንፂር በጥልቀት ያልመረመረ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

4.2 በሁለቱ ተደራዳሪዎች መካከል የሚታዩ ልዩነቶች

ድርድሩ ከተጀመረ ከ4 ዓመት በኃላ እንኳን በአሁኑ ወቅት በሁለቱ ተደራዳሪዎች መካከል የከረረ ልዩነት ይስተዋላል። ይህም ውጥረትንና ተስፋ መቁረጥን በተደራዳሪ ቡድኖች መካከል ፈጥሯል። ዋና ዋና የልዩነት ነጥቦች

- የልማት አስፈላጊነት ላይ ከስምምነት የተደረሰ ቢሆንም ልማት እንዴት የሚል ላይ ፤
- ከታሪፍ ማንሳት ጋር ተያይዞ የሚከተለውን የመንግስት ገቢ ቅነሳ ካሣ ላይ፤
- የሽግግር ወቅት ርዝመትን፤
- የACP ሀገሮችን የኢኮኖሚ መዋቅር ለማስተካከልና የተወዳዳሪነትና የአቅርቦቱን ችግር ለማሻሻል የሚረዳ የዕርዳታ መጠን ፤
- የወሳኝ ምርቶች (Sensitive Products) ዝርዝር ላይ ፤
- የ«ግድ« ነፃ የማድረግ እርምጃ (trade liberalization) ከልማት ግብ ጋር የሚያያዝበት ሁኔታ እና የተመረተበት ሀገር (Rules of Origin) አስመልክቶ፤ የሚጠቀሱ ናቸው።

4.3 የኢትዮጵያና የሌሎች ሀገሮች የመፈረም/ያለመፈረም ሁኔታ

የዓለም ባንክ ለታዳጊ ሀገሮች አውጥቶት የነበረው የSAP ህዝብን ያላማከለ ነው ተብሎ በበርካታ ትችቶች ተሰንዝሮበት ነበር። ይሁን እንጂ ይንን ወደ ጎን በመተው ፕሮግራሙ እንዳለ ተግባራዊ በመደረጉ ሀገሮችን ወደ ባሰ ቀውስ ለማስገባት በቅቷል። አሁንም EPAs ድህ ሀገሮችን ይጎዳል ተብሎ በተለያዩ መረጃዎች የተደገፉ ጥናቶች ቢቀርቡም የአውሮፓ ህብረት ጆሮ ዳባ ልበስ እያለ ይገኛል። ይህም የሚያመለክተው እንደ SAP ሁሉ የEPAs ጉዳት ከጊዜ በኃላ በግልፅ እስከሚታይ ድረስ እየተጠበቀ መሆኑን ነው። አስቀድሞ መጠንቀቅ የተሻለ ሆኖ እያለ ጉዳቱ በግልፅ እስከሚድርስ ድረስ መጠበቁ ትክክል አይደለም።

ከዓለም የተወዳዳርነት መለኪያ የ2005/06 ውጤት ላይ ለማየት እ«ደሚቻለዉ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ የተወዳዳሪነት ጠቋሚ መለኪያ መሰረት »117 ሀገሮች መካ»ል ኢትዮጵያ 116ኛ ላይ ትገኛለች። ይህም የሚያሳየዉ ሀገሪቷ ም« ያህል ዝቅተኛ የተወዳዳሪነት ደረጃ ላይ እ«ደምትገኝ ነዉ[7]። በመሆኑም የሀገሪቷ የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት መፈረም ምንም የገንዘብ ድጋፍ ቢሰጠው በአጭር ጊዜ ውስጥ ብቃቷን አዳብራ ከአውሮፓ ጋር በእኩል ደረጃ ሊያወዳድራት ይችላል የሚል ግምት የለም። ምክንያቱም

[7] World Economic Forum, The Global Competitiveness Report: 2005-2006.

የብዙዎቹ የተወዳዳሪነት ብቃት መለኪያ ጠቋሚዎችን ለማሻሻል ረዥም ጊዜ የሚወስዱ እንደ ትምህርት፤ መሠረተ ልማትና የቴክኖሎጂ ዝግጁነት ናቸው።

ከላይ በተመለከተው የተወዳዳሪነት ጠቋሚ መረጃና ሌሎች የተለያዩ ጥናቶች ውጤት አኳያ ሀገሪቷ አሁን ካለችበት ዝቅተኛ የኢንዱስትሪ ልማትና ዝቅተኛ የምርታማነት እንዲሁም የተወዳዳሪነት ደረጃ ሲታይ EPAsን መፈረሟ ጉዳት ላይ እንደሚጥላት ሳይታለም የተፈታ ነው። በሚሠጣትም አጭር የሽግግር ወቅት ውስጥ የኢኮኖሚ መዋቅሯን አስተካክላ ከአውሮፖ ይቅርና ከሌሎች ተመሳሳይ ታዳጊ ሀገሮች ጋር እኩል የመወዳደር ብቃት ላይ ትደርሳለች ብሎ ማሰብ ያስቸግራል። በመሆኑም ስምምነቱን አለመፈረሙ የተሻለ ይሆናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአውሮፓ ህብረትና እና በESA የንግድ ሚኒስትሮች መካከል እ.ኤ.አ. በኖቬምበር 12 ቀን 2007 ብራስልስ ላይ በተደረገው የጋራ ስብሰባ ላይ የአውሮፓ ህብረት ACP ሀገሮችን የልማት ጥያቄ በመቀበሉ በቀነ-ገደቡ መሠረት ከፊል የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት (light EPAs) በአማራጭነት ቀርቦአል። ይህም ከፊል ስምምነት የሚያካትተው የገበያ ዕድልና የልማት ትብብርን ሲሆን ሌሎች ቀሪ ጉዳዮችን ግን በ2008 ውስጥ ተደራድሮ ለመጨረስ ነው።

ይህንን ከፊል የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት መፈረም የማይፈልጉ ሀገሮችን በተመለከተ LDCs የሆኑት EBA መጠቀም መቀጠል እንደሚችሉ ሲገለፅ Non-LDCs ግን ወደ መደበኛው GSP እንደሚገቡ ያስቀምጣል። ይሁን እንጂ ለLDCs ሆነ ለNon-LDCs የተቀመጠው አማራጭ የሚያስገኘው ጥቅም ከሎሜ/ከኮቶኑ ያነሰ ነው። ይህም በኮቶኑ ስምምነት ላይ ማንም የACP ሀገር ቀድሞ ከሚያገኘው የገበያ ዕድል ያነሰ አይሆንም የሚለውን አንቀጽ የሚፃረር ነው። በዚህም ወቅት ከዚህ ቀደም በድርድሩ ላይ ተነስተው ከስምምነት ላይ ስላልተደረሰባቸው በርካታ ቁልፍ ጉዳይዎች ላይ ምንም የተባለ ነገር የለም።

ኢትዮጵያ ከፊል ስምምነቱን ተቀብላ ለጊዜው እንደማትፈርም ያስታወቀች ስትሆን ሰባት አገሮች አምስቱን የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ (EAC) አባል ሀገሮች ጨምሮ ከፊል የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት (light EPAs) ለመፈረም ተስማምተዋል።

5. የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት አማራጮች

ይህ የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት በቀነ-ገደቡ በስምምነት የማይቋጭ ከሆነ ንግድ ሊስተጓጎል ይችላል የሚል ፍራቻ አለ። ንግድ እዳይስተጓጎል ለማድረግ ምን አማራጮች ይኖራሉ በሚል< ዙርያ የሚከተሉትን አማራጮችን ለመጠቆም ተሞክሯል።

1ኛ/ የሎሜ/ኮቶኑ ስምምነትን ማራዘም

የሎሜ/ኮቶኑ ስምምነትን ማራዘም ለአውሮፓ ህብረት ፈታኝ ነው። ምክንያቱም እስከ አሁን ድረስ በቀነ-ገደቡ ሊፈረም እንደማይችል ተረጋግጦ Waiver **ቀደም ብሎ መጠየቅ ነበረበት። ይህ ግን በወቅቱ አልተፈፀመም። ይህን አማራጭ ሌሎች የ**WTO **አባል ሀገሮች የሚቀበሉት ስላልሆነ አሁን ባለው የአባል ሀገሮች ሁኔታ** Waiver **ቢጠየቅም ማግኘቱ አስቸጋሪ ነው።** Waiver **ጠይቆ ማግኘቱ በራሱ ውስብስብና ረዥም ጊዜ የሚወስድ ነው። ለመጥቀስ ያክል አሜሪካ** AGOA**ን ለማራዘም በ**2001 **ጠይቃ ማራዘሚያው** (Waiver) **እስከ አሁን ድረስ ምላሽ አላገኘም።**

2ኛ/ የGSP **ታሪፍ**

ይህ ታሪፍ ሶስት ደረጃዎች አሉት። እነርሱም EBA**፣** GSP+ **እና መደበኛው** GSP **ናቸው።**

i) EBA (Everything But Arms)

ይህ አማራጭ በእድገት ወደ ኃላ የቀሩ አገሮች (LDCs) EBA**ን መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ ነው። ሆኖም** EBA **ከሎሜ/የኮቶኑ ዕድል ያነሰ በመሆኑ በሀገሮቹ የሚመረጥ አይደለም<። ምክንያቱም በ** EBA **ስር ያለው የ**rules of origin **አሰራርና የመቶኛው ምጣኔ እንደ ሎሜው/ኮቶኑ ለ**ACP **ሀገሮች የሚመች ባለመሆኑ።**

ii) GSP+(Generalized System of Preference plus)

ይህ ዕድል የሚሰጠው የዓለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ፣ የሰራተኛ መብትና ሌሎች ስምምነቶችን ለፈረሙ ታዳጊና ኢኮኖሚያቸው ተጋላጭ ለሆኑ ሀገሮች ነው። ዕድሉ ከሁሉም ዕድሎች የተሻለ ነው። ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ GSP+ **ተጠቃሚ ሀገሮች ዝርዝር ሙሉ በመሆኑ ዕድሉ እንደ አዲስ መታየት የሚጀምረው ከአንድ ዓመት በኃላ ነው። የዕድሉ ተጠቃሚ የሚያደርገውን መስፈርት ያየን እንደሆነ ሁሉም የ**ACP **ሀገሮች ብቁ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው። እዚህ ላይ የሚያስፈልገው የአውሮፓውያን የፖለቲካ ውሳኔ** (EU's Political Will) **ብቻ ነው።**

iii) መደበኛው GSP (the Standard Generalized System of Preference)

ይህ አማራጭ ወደ አውሮፓ በሚገባው ምርት ላይ የሚጣለው የታሪፍ ምጣኔ በአማካይ በ20 **በመቶ ከሌሎች አማራጮች ዝቅ ያለ ነው። መደበኛው** GSP **ከ**WTO **ጋር የሚጣጣም ነው። ይሁንና ይህ የድጋፍ አይነት የ** ACP Non-LDCs **ን ቀድመው በሎሜ/ኮቶኑ ከሚያገኙት ድጋፍም ሆነ ሌሎች የላቲን አሜሪካ ሀገሮች** GSP+**ን ተጠቅመው ምርታቸውን ወደ አውሮፓ ከሚያስገቡ ሀገሮች አንፃር ተጎጂ ያደርጋቸዋል።**

3ኛ/ Light/Phased EPA መፈረም

ሀ) Light EPAs

ይህ አማራጭ አንዳንድ ጉዳይዎች ላይ ስምምነቶች ከተደረሰ ለምሳሌ፤ የገበያ ዕድልንና ልማትን በሚመለከት ብቻ ላይ ስምምነት ከተደረሰ ሌሎቹን ጉዳዮች በሚቀጥሉት ጊዜያት ተደራድሮ ለመጨረስ የሚያስችል ነው።

ለ) Phased EPAs

ይህ አማራጭ እስከ አሁን ድረስ በመካከላቸው ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ በመፈራረም በተቀሩት ላይ ድርድሩን ወደ ፊት ለመቀጠል የሚስችል ነው።

6. የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነትና የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (COMESA) ህልውና

ሀገሮች ለተለያዩ ዓላማዎች የነፃ ገበያ ቀጠና አባልነትን ይቀላቀላሉ። እነርሱም ሰፊ የገበያ ዕድል አግኝቶ ንግዳቸውን ለማስፋፋትና የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ፤ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ወደ ሀገር ውስጥ ለመሳብ፤ ለድንበር ቁጥጥር፤ ትራንዚት፤ የሰው ዝውውርን ለመቆጣጠር፣ የፖለቲካ ዓላማ ለማሳካት እና ገለልተኛ መሆን የሚያስከፍለው ዋጋ እየጨመረ በመሄዱ ናቸው[8]።

በነፃ ገበያ ቀጠናዎች ላይ የተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች አንድን ሀገር ተጠቃሚነት ወይም ተጎጂነት በግልፅ አያሳዩም። በቀጠናው ምክንያት የሀገር ውስጥ ሸማቾች በንግድ ከለላው መነሳት ከሚያገኙት ጥቅምና መንግሥት ከሚያጣው የታሪፍ ቀረጥ ገቢ የትኛው እንደሚያመዝን በግልፅ አይታወቅም። የዓለም ባንክ የSimulation ጥናት ውጤት ከደቡብ-ደቡብ የነፃ የንግድ ቀጠና አባል ሀገሮች የጎላ ጥቅም እንደማያገኙ ያሳያል። ለዚህም በመካከላቸው የሚኖረው የመነገድ ዕድል ጠባብ መሆኑና የምርት አወቃቀራቸውና የተፈጥሮ ሀብታቸው ተመሳሳይ መሆኑ በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

የደቡብ-ደቡብ ቀጠና የሆነው የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (COMESA) በ1981 የተቋቋመና 19 አባል ሀገራት ሲኖሩት ከእነርሱም 13ቱ የነፃ የንግድ ስምምነት (FTA) አባል ናቸው፡፡ በ2008 ደግሞ ሁሉም አባል ሀገራት የነፃ ንግድ ስምምነት(FTA) አካል እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡ ኢትዮጵያም የነፃ የንግድ ስምምነት (FTA) አባል መሆን በሀገሪቷ ላይ የሚኖረውን እንደምታ አስመልክታ ጥናት አካሂዳለች። የጥናቱም ውጤት እንደሚያሳየው ነፃ ሆኖ ይቅርና አሁን ባለው የታሪፍ ከለላ እንኳን ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የአምራች ኢንዱስትሪዎችዋ ውድድሩን መቋቋም እንደማይችሉ ነው[9]።

[8] Agustín Carstens' Making Regional Economic Integration Work' 20th Annual General Meeting and Conference of the Pakistan Society of Development Economists'' January 12, 2005 Islamabad, Pakistan,

[9] Afro Consult and Trading (2002) A Study on COMESA-FTA

የEPAs አንዱ ዓላማ እንደ COMESA ያሉ ክልላዊ የኢኮኖሚ ቀጠናዎችን ማጠናከር ነው፡፡ ከእንደዚህ ዓይነት ቀጠናዎች ጋርም ነው የአውሮፓ ህብረት EPAsን መፈራረም የፈለገው:: ይሁን እንጂ አባል ሀገሮች በCOMESA ሥር አንድ ሆነው ሳይሆን ህጋዊ ሰውነት በሌለው በESA ቡድን ውስጥ ተደራጅተው በመደራደር ላይ ይገኛሉ። አንጎላ፣ ግብፅ፣ ሊቢያ እና ስዋዚላንድ ደግሞ EPAsን እየተደራደሩ አይደሉም፡፡ ናሚቢያ ደግሞ በESA መቋቋም ዋዜማ ላይ ነው COMESAን ለቃ በመውጣት በሌላ ቡድን ውስጥ በመደራደር ላይ የምትገኘው። እንደዚህ ዓይነት ውስብስብ ሁኔታዎች ቀጠናውን ጠብቆና ውህደቱን እያጠናከሩ ለመሄድ አስቸጋሪ ሁኔታን እየፈጠሩ ይገኛሉ። ይህ ደግሞ የCOMESA ህልውናን የሚፈታተንና የክልላዊ የኢኮኖሚ ውህደትን ሂደት ወደ ፊት እንዳይራመድ የሚያደርግ ነው።

EPAs ህጋዊ ሰውነት ባላቸውና ከዚህ ቀደም በተደራጁ ክልላዊ የኢኮኖሚ ቀጠናዎች የሚፈረም ካልሆነ የአውሮፓ ህብረት ለክልላዊ የኢኮኖሚ ቀጠናዎች መጠናከር በሚያደርገው የአቅም ግንባታ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ ይገደዳል። ይህ ደግሞ ሌላ ረዥም ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ የEPAs እንደ COMESA ያሉ ክልላዊ የኢኮኖሚ ቀጠናዎችን የማጠናከር ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ ያደርጋል።

7. ርዕይ 2020

ሀገሪቷ እየተደራደረች ያለችው የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነትም ሆነ ሌሎች የነፂ ንግድ ስምምነቶች ለጊዜው ባትፈርማቸውም ወደፊት በከረረ ውድድር ውስጥ ራስዋን ማግኘቷ የማይቀር ነው። በመሆኑም ከወዲህ< መዘጋጀት ግድ ይላል።

አሁን ያለውን የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታና ሌሎች ሀገሮች የደረሱበትን ደረጃ በንጽጽር ያየን እንደሆነ በሚቀጥሉት 20 ዓመታት ጊዜ ውስጥ እጅግ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ የተወዳዳሪነት አቅም ላይ ይመጣል ብሎ የተጋነነ ርዕይ ማስቀመጥ ጭፍን ብርሀንተኛ (Blind Optimist) ከመሆን ሌላ ትርጉም የለውም። ምክንያቱም ውድድር መነሻን መሰረት ያሚያደርግና ንፅፅራዊ እንደመሆኑ ከዝቅተኛ መነሻ በፍጥነት በምንራመድበት ጊዜ የተቀረው ዓለም ቆሞ አይጠብቀንም። ይሁን እንጂ ብዙም ጨለምተኛ ሳልሆን ሀገሪቷ በሚቀጥሉት 20 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ኢኮኖሚዋ በዓለም ደረጃ አሁን ከሚገኝበት ዝቅተኛ የተወዳዳሪነት ደረጃ ይሻሻላል የሚል ርዕይ አለኝ። በዚህ ጊዜ ውስጥ አምራች እንዱስትሪዎችዋ በዓለም ገበያ ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ ይሆናሉ ባልልም ወሳኝ የፖሊሲ እርምጃዎች የሚወሰዱ ከሆነ የገቢ ዕቃዎችን ውድድር በመቋቋሞ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ የሚል ርዕይ አለኝ።

ይህንን ርዕይ ሳስቀምጥ እስከ 2020 ባሉት በሚቀጥሉት 20 ዓመታት ውስጥ የሚከተሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ የሚል ታሳቢ ወስጄ ነው። እነርሱም፡-

1. **የሀገሪቱ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማብቃት የመልሶ ማዋቀር ሥራ ይከናወናሉ ከአንፃራዊ ተጠቃሚነት** (Comparative advantage) **አንፃር ይቃኛሉ፤**
2. **የሀገሪቷን የንግድ በሮች ለዓለም ገበያ በመክፈት ሂደት ውስጥ የታሪፍ ከለላ የሚፈልጉትን የወሳኝና ስትራቴጂካዊ ምርቶች ላይ ካለው ተጨባጭ ሁኔታና ወደፊት ሊኖር ከሚችለው ዕድል አንፃር ታይቶ በቂ ጊዜና ትኩረት ተሰጥቶት በደንብ ይሰራል፤**
3. **የሀገሪቷን ተወዳዳሪነት በእጅጉ እየገደበ ያለውን የትራንስፖርት መሠረተ ልማትና አገልግሎት እንዲሁም ሌሎች መሰረተ-ልማት ዙሪያ ከፍተኛ ርብርብ ይደረጋል ፤**
4. **ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ ምርት ከማቅረብ አኳያና የቴክኖሎጂ ሽግግር እውን ማድረግ የሚችል የሠለጠነና ብቁ የሰው ኃይል ይኖራል፤**
5. **በቅርብ ጊዜ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ላይ ያሉትን ሀገሮች ልምድ በመቅሰም ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ በስራ መተርጎም፤ እና**
6. **እንደ ማዕቀፍ ሆኖ ሊያገለግል በሚችል ምቹና የውጭውንም ሆነ የሀገር ውስጡን ባለሀብቶች እምነት** (Confidence) **ከፍ የሚያደርግ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ተሻሽሎ ለተግባራዊነቱ ቁርጠኛ አቋም ይያዛል መንግስትም ኢንቨስትመንትን የማበረታታትና የማስተባበር ሥራን ይሠራል።**

ዋቢ መረጃዎች

Agustín Carstens .2005. Making Regional Economic Integration Work At the 20th Annual General Meeting and Conference of the Pakistan Society of Development Economists' January 12, 2005 Islamabad, Pakistan Melaku Geboye Desta.2006. EC-ACP economic partnership agreements and WTO compatibility: an experiment in North –South interregional agreements.

Oxfam. 2007. A matter of Political Will: how the European Union can maintain market access for African Caribbean and pacific countries in the absence of economic partnership agreements, briefing note April 2007

Policy Briefing Paper #2 June 2007;

Economic Partnership Agreements: What Every Parliamentarian needs to know

Report on Negotiations for Economic Partnership Agreement 30 august 2007

San Bilal. 2007. Concluding EPA Negotiations: legal and institutional issues May 10, 2007

The Cotounu Partnership Agreement, 23 JUNE 2000

MOTI . 2004. *National Study on the Impact and Sustainability of the EPA for Ethiopia*, Draft final report.

World Economic Forum. 2005-2006, The Global Competitiveness Report.

በአቶ ሀብታሙ አበራ እና አቶ አሚን አብደላ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ማሞ እሰመለዓለም ምህረቱ[1]

በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር በዚህ ወቅታዊ የፖሊሲ ጉዳይ ላይ የግል አስተያየት እንድሰጥ ስለጋበዘኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

በግሌ ስለ የአለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድርና ስለሚያስከትለው የፖሊሲ ሪፎርም ገዳይ ሳስብ፣ ብዙ ሰዎች አባል በመሆን ስለሚያስከትለው ጥቅምና ጉዳት አስመልክቶ የሚያነሱትን ክርክር ስሰማ እንዲሁም የአባልነት ሂደቱን ውጣ ውረድ ስከታተል፣ የቀድሞው አሜሪካ የኮንግረስ አፈ ጉባኤ ኔውት ጊንግሪች ዳthe tyranny of the presentዴ ሲሉ የተናገሩትን ያስታውሰኛል፡፡ በሌላ አነጋገር ብዙን ጊዜ ብዙዎቻችን በእለታዊ ሁኔታዎች፣ ዛሬ ሃሳባችንና ጊዜያችንን ተሻምተዉ በሚያዙ ፈታኝ ሁኔታዎች በመወጠር በአጭር ጊዜ ባይሆንም በረጅም ጊዜ ሊያሳስቡን በሚገቡ የፖሊሲ እርምጃዎችና አቅጣጫወች ላይ በቂ አጽኦት አለመስጠት ከሞላ ጎደል የተለመደ ነዉ፡፡ ብዙ ጊዜ እንደሚባለውም ዳthe past is organized and has lobbyists, the future never doesዴ የሰው ተፈጥሮ ሆኖ ብዙ ጊዜ ስለ ትላንትና ስለ ዛሬ ሁኔታዎች ብቻ ስናስብ ስለነገው ሁኔታ የማናወሰበት አጋጣሚ አለ፡፡

በእኔ እምነት የአለም ንግድ ድርጅት የሚያስፈጽማቸዉ አለም አቀፍ የንግድ ህጎች ድክመት ያለባቸዉ መሆኑ አሌ የማይባል ሀቅ ነዉ፡፡ የህጎቹ ፍትሃዊነትና በልማት ወደ ኋላ የቀሩ አገሮችን ጥቅም ወሳኝ በሆነ ደረጃ የማስጠበቃቸዉ ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችል ይሆናል፡፡ ይህ ችግር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአለም ንግድ ድርጅት የድርድር ሂደት ኢኮኖሚያችንን በገንቢ ሁኔታ የሚያግዙ ፖሊሲዎችን ለማሰብ፣ ለማዉጣት እና ለማስፈጸም መድረክ (Platform) ይፈጥራል የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡ ይህን ሃሳብ ወደ ኋላ እመለስበታለሁ፡፡

በአቶ ሀብታሙ ታደሰ የዓለም ንግድ ድርጅት ምንነት የኢትዮጵያ የአባልነት እንቅስቃሴና የወደፊት ልማት ተስፋ አስመልክቶ የቀረበው ጽሑፍ የዓለም ንግድ ድርጅት ታሪካዊ አመሰራረትና አወቃቀር፣ የድረጅቱ አብይ ተግባራት፣ የድርጅቱ ዋና ዋና ስምምነቶችና መሠረታዊ መርሆች በስፋት የተብራራ ስለሆነ አልመለስበትም፡፡

[1] አቶ

አቶ ሃብታሙ በጽሑፋቸው እንዳብራሩት የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድር ብዙ የህግ ግዴታዎች እና ሰፊ የፖሊሲ እርምጃዎች የሚያስከትል ሂደት ነው፡፡ ምናልባት ይህ ሂደት የምስራቅ አውሮፓ አገሮች የአውሮፖ ህብረትን ለመቀላቀል ከሚያደርጉት ድርደር ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በብዙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለምሳሌ፤ የወርልድ ባንክ እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባልነት ጥያቄ ውስብስብ የፖለቲካ ችግር ከሌለ በስተቀር አገሮች ሉዐላዊነታቸውን እሳካረጋገጡ ድረስ አገሮች በቀላሉ ሊያሳኩት የሚችል ነገር ነው፡

በአንጻሩ የአለም ንግድ ድርጅት የአባልነት ድርድር የአባልነት ጥያቄ አቀራቢዉ አገር ንግድ ነክ ህጎችንና ፖሊሲዎች የአለም ንግድ ድርጅት ከሚያስተዳድራቸው ስምምነቶች ጋር መጣጣም ግድ ሰለሚልና ከዚህም አልፎ የዕቃና የአገልግሎትን ንግድ አስመልክቶ ተጨማሪ በድርድር የሚወሰን ግዴታዎች ሊያስከትል ስለሚችል የአባልነት ሁኔታውን ረዥምና ውጣ ውረድ የበዛበት ያደርገዋል፡፡

የአባልነት ደርድሩን የሚገዛው የህግ ማዕቀፍ የማራኬሽ ስምምነት አንቀጽ 12 ልል መሆንና አለመብራራት ደግሞ የድርድሩ ሁኔታ ወደ አንድ ወገን ያጋደለ፣ ጥያቄ የመጠየቅ መብትን ለአባል አገሮች በመስጠት ንግድ ነክ ህግና ፖሊሲዎችን አባልነት ጠያቂ አገሮች እንዲያስተካክሉ ግዴታ ይጥላል፡፡

ይህ የአንቀጽ 12 ድንጋጌ አንድ አገር አባል ለመሆን ሊያሟላቸው የሚገባቸውን ነገሮች (Criteria) ሳያስቀምጥ አገሮች በድርድር በሚወስን መንገድ (terms to be agreed) አባል ሊሆን እንደሚችሉ ያስቀምጣል፡፡ ይህም አባል አገሮች አባል ለመሆን በሚፈልጉ አገሮች ላይ ቅጥ ያጣ፣ አግባብ ያልሆነ እንዲሁም አንዳንዴ ኢፍታዊ ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡና ግዴታዎችን እንዲገቡ ለመጠየቅ ገደብ የለሽ እድል (*carte blanche*) ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ግልጽ ያጣ ሂደት የአባልነት ዉይይቱን የአለም ንግድን ህግና ስምምነትን ከመቀበልና ከመፈጸም ጥያቄ (Rule compliance context) ወደ ድርድር ሁኔታ (Negotiation context) ይለውጠዋል፡፡

ይህንን በመረዳት ይመስላል በቅርብ ጊዜ የአለም ንግድ ድርጅት አባሎች በተለይ በልማት ወደ ኋላ የቀሩ አገሮች የሚያደርጉ የአባልነት ድርድር የተቀላጠፈ እንዲሆን የሚረዱ ሃሳቦች ቀርበዉ እንዲጸድቁ የተደረገዉ፡፡

በዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርደር ወቅት ተደራዳሪ አገራት የሚገቡት ግዴታዎችን በሶስት ከፍሎ መመልከት ይችላል፡፡ የመጀመሪያው የአለም ንግድ ድርጅት በሚስተዳድራቸው ህጎችን ስምምነቶችን ለመፈጸም የሚገባ ግዴታ፣ ሁለተኛው በድርድር የሚወሰነዉና የአገልግሎት እና የዕቃዎች ንግድ አስመልክቶ የሚገባ ግዴታ እንዲሁም ሶስተኛው ደግሞ የአለም ንግድ ድርጅት ከሚያስተዳድራቸው ህጎች ውስጥ አስገዳች ያልሆኑ ህጎች (Plurilateral Agreement) እና ሌሎች ተጨማሪ ጉዳዮችን አስመልክቶ ሊገባ የሚችል ግዴታ (Accession Protocol Commitment) ነው፡፡

በእኔ እምነት የዓለም ንግድ አባልነትን ጨምሮ የንግድ ድርድሮች መነሻቸው አገራዊ ጥቅም እና ግባቸው ደግሞ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት ማገዝ መሆን አለበት፡፡ የንግድ ስምምነት ተደራዳሪዎች ድርሻ መንግስት ያወጣቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ግምት ውስጥ በማስገባት እነዚህን ፖሊሲዎችን በተግባር ማስፈጸም ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፖብሊክ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የሚከተለውን ይላል፡፡

ዳበአገራችን ልማትና ዲሞክራሲን ከሌላው አለም ተነጥለን፣ በተራሮቻችን ዙሪያ መሽገን፣ በሮቻችንን ዘግተን ከቶ ልናረጋግጠዉ አንችልም፡፡ በሙሉ ልብ አለም አቀፋዊው ትስስር ውስጥ ከተስፋኝነትና ተመጽዎችነት ተላቀን ወደ አምራችነት፣ በአምራችነት ዙሪያም የስራ ድርሻችንን በቀጣይነት የማሻሻል አላማ ይዘን ከተነሳን ብቻ ነው የአገራዊ ጥቅማችንና ህልውናችን መነሻና መድረሻ የሆኑትን ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ የምንችለው፡፡ ግሎባላይዜሽን የሚፈጥረውን ዕድል በሙሉ አሟጦ በመጠቀም፣ ግሎባላይዜሽን የሚደቀንብንን እንቅፋት በመቀነስ፣ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ውስጥ ንቁ ተዋናይ በመሆን ብቻ ነው፡፡ ጥቅማችንና ድህነታችንን ማረጋገጥ የምንችለው፡፡ ልማትንና ዴሞክራሲን በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ዕውን ማድረግ፣ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲዎችን አንድ መሰረታዊ መነሻ መሆን ያበትም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ዴ ገጽ 17 ስለዚህ በአቶ ሀብታሙ ጽሑፍ የኢትዮጵያ መንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የድርድሩ መነሻ መሆናቸው መጉላት አለበት ባይ ነኝ፡፡ ሌላው በአቶ ሃብታሙ ታደሰ ጽሑፍ ላይ ጉልቶ መውጣት አለበት ብዬ የማስበው ጉዳይ አባልነት ጥቅም አስመልክቶ የተነሳው ነገር ነው፡፡ ይህን ነጥብ አጠንክሮ ማንሳት በጉዳዩ ላይ ለምናደርገዉ ውይይት መነሻ ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡

በእርግጥም አንዳንድ የድርጅቱ ህጎችና ስምምነቶች (ለምሳሌ የአእምሮአዊ ንብረትን አስመልክቶ ያለውን ስምምነት ይጠቅሷል) በማደግ ላይ ካሉ አገሮች ይልቅ ያደጉ አገሮች ጥቅም በይበልጥ የሚያስጠብቁ መሆናቸው ታይቶ፣ ከነጻ ንግድና ኢንቨስትመንት የሚገኙ ጥቅሞች በአገራት መካከል በፍታሀዊ መልኩ አለመዳረሱን ተመልክቶ፣ እንዲሁም ከላይ እንዳየነው የአባልነት ድርድሩን የሚገዙ ህጎች ልልና ኢፍታሃዊ ከሆኑ አባል ለመሆን መደራደሩ አስፈላጊ የሚያደርገው አሳማኝ ምክንያት ሊኖር ይችላል ወይ ብሎ መጠየቅ አግባብ ይመስለኛል፡፡

ውይይት ለመፈንጠቅ ያህል በጽሑፍ አቅራቢዎች ቢጠቀሱም የሚከተሉትን ተጨማሪ ሃሳቦች ባጭሩ ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡

በኔ እምነት መጀመሪያ ግልጽ ሆኖ መውጣት ያለበት ነጥብ ከአለም ንግድ ድርጅት አባልነት የሚገኘው ጥቅም እንደያገሩ የኢኮኖሚ ጥንካሬ ከአገር አገር የሚለያይ መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛዉ ነጥብ ደግሞ አባል መሆን የአንድ አገር ልማት ፖሊሲዎችን ለማሳካት መሣሪያ እንጂ በራሱ ግብ አለመሆኑ ነው፡፡

በአቶ ሀብታሙ እንደተገለጸው የመጀመሪያው የአባልነት ጥቅም የውጭ የገበያ እድልን ለማስፋትና የተረጋገጠ ለማድረግ እድል መስጠቱ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ በቻይና በአንድ ጥናት መሰረት ከአለም ንግድ

ድርጅት አባልነት በኋላ የጨርቃጨርቅና አልባሳት የዉጭ ንግድ በአስር አመታት በ375% ውስጥ አድጓል፡፡ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ይህ ይሆናል ብሎ ለመናገር ያዳግታል፡፡ በተለይም ጽሁፍ አቅራቢዉ በደንብ እንዳብራሩት በአሁኑ ሰዓት አገራችን ከቀረጥ ነጻ የሆና በኮታ ያልተገደበ የተለያየ የገበያ ዕድል ስላላት፣ በአባልነት ምክንያት የሚፈጠር አዲስ የገበያ ዕድል ሊይኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህን የአለም ንግድ ድርጅት ይህን የገበያ ዕድል የተረጋገጠና ዘላቂ፤ አገሮች በተለያየ ምክንያት ሊቀይሩት የሚችሉት እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡ የመጨረሻ ውጤቱ አይታወቅም እንጂ የአሁኑ የዶሃ ዙር የንግድ ድርድር ከቀረጥ እና ከኮታ ነጻ የሆነ የገበያ እድል ያደጉ አገሮችና ሌሎች ዝግጁ የሆኑ በመልማት ላይ ያሉ አገሮች በልማት ወደ ኋላ ለቀሩ አገሮች እንዲሰጡ ማስገደዱ አንዱ አይነተኛዉ ጥቅም ነው፡፡

ሁለተኛው ለኔ በጣም ወሳኝ የአባልነት ምክንያት አድርጌ የምወስደው የድርድሩን ሂደት አስፈላጊ የሆኑ የፖሊሲ እርምጃዎችን ለመወሰድ እንደ መድረክ (Platform) ማገልገሉ ነዉ፡፡ ከአገልግሎት ንግድ ዘርፍ አንስቶ እስከ ግልጽ የንግድ ውድድር ሰርዓት እስከማስፈን የግል ዘርፉን ለማጠንከር የሚረዱ የፖሊሲ እርምጃዎችን ለማሰብና ለመወሰንና ለመፈጸም የድርድር ሂደቱ ሊረዳ ይችላል፡፡ ምናልባት እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ተገቢ ጥያቄ እነዚህን አስፈላጊ ፖሊሲ እርምጃዎች አባል መሆን ሳያስፈልግ መውሰድ አይቻልም ወይ? የሚል ነው፤ ለዚህ መልስ በግል (Unilateral) ከሚወስድ የፖሊሲ እርምጃ ይልቅ በአለም ንግድ ድርጅት አባልነት ሂደት የሚወሰድ የፖሊሲ እርምጃ የበለጠ ተአማኒነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ይህ ሂደት መንግስት ጥበቃ የሚሹ አካላት (Protectionist pressures) የሚደርስበትን ከልክ ያለፈ ጫና ለመከላከል ምክንያት ይፈጥራል፡፡ እነዚህ የፖሊሲ እርምጃዎች ወደ ዓለም አቀፍ ስምምነት ስለሚቀየሩ ዘላቂና በቀላሉ የማይቀየሩ ያደርጋቸዋል፡፡

ይህ በጽሑፍ አቅራቢዉ እንደተገለጸው ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ኢንቨስተሮች ትልቅ የፖሊሲ አቅጣጫ ማረጋገጫ ስለሚሆን ጠንካራ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

ብዙ ጊዜ እንደሚባለው ለአንድ አገር የውጪ ንግድ ዕድገት በሌሎች አገሮች ካሉ የንግድ ክልከላዎች ይልቅ አገር ውስጥ ያሉ ለንግድ አመቺ ያልሆኑ የንግድ ፖሊሲዎችና አሰራሮች የበለጠ ማነቆ ይሆናሉ፡፡

በእኔ እይታ አገሮች በአሁኑ ሰዓት በኢኮኖሚና ንግድ ሁኔታ (Climate) አመቺነት፣ በመንግስት አስተዳደር ተቋማት ጥራት፣ በኢኮኖሚ ነጻነት (economic freedom) እድገት፣ እንዲሁም በፍትህ ስርዓቱ ጥንካሬ በከፍተኛ ሁኔታ ይወዳደራሉ፡፡ የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እነዚህ መስፍርቶች ሁሉ ይንጸባረቁበታል፡፡ ከአለም የንግድ ሰርዓት ውጪ በሆኑ አገር ውስጥ እነዚህ አስፈላጊ ነገሮች አሉ ብሎ ሌሎች አገራትን ለማሳመንና ጠንካራ ኢንቨስትመንትን መሳብ የማይቻል ባይሆንም ፈታኝ ነው፡፡ ሌላው አቶ ሃብታሙ በደንብ ያብራሩት የአባልነት ጥቅም ግጭቶችን ለመፈታት መድረክ ማመቻቸቱና ወደፊት የአለም ንግድ እንቅስቃሴ የሚገዙ ህጎች እና ስምምነቶችን የሚወጡበት መድረኮች ላይ መቀመጫ ማግኘቱ ነው፡፡
ሌላው ጥቅም ልክ ቻይና እና ቬትናም እንዳደረጉት ገጽታን ለመቀየር አንድ መንገድ መሆኑ ነዉ፡፡

በመጨረሻ ላነሳው የምፈልገው እነዚህ ጥቅሞችን ለማግኘት የስርዓቱን ገደቦች (Constraint) መቀበል ግድ ማለቱ ነዉ፡፡ እንደ ሌሎች ነገሮች የአለም ንግድ አባልነት ድርድር ሰጥቶ በመቀበል እና ጥቅሞችን በማቻቻል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በአጭሩ የ ዳzero sum game’’ አይደለም፡፡

አመሰግናለሁ፡፡

ሰላምና ልማት በኢትዮጵያ ዛሬና ነገ[1]

መድህኔ ታደሰ[2]

2. መግቢያ

ይህ ርዕስ የቀረበበት ወቅት አገራዊና አካባቢያዊ ሰላምና የፖለቲካ መረጋጋት ጥያቄ ውስጥ የገባበትና የነገሮች የወደፊት አቅጣጫ በግልጽ ባልታወቁበት ከመሆኑ አንፂር ወቅታዊነቱም ፈታኝነቱም አያጠራጥርም። ከውስጥ ብንጀምር የ1997 ብሔራዊና አገራዊ ምርጫ እንደታሰበው የፖለቲካ መረጋጋትና የዲሞክራሲ ሽግግር ባላመጣበት እንዲሁም የአገሪቱ የቆዩና የቅርብ ጊዜ የፖለቲካ ችግሮችና ግጭቶች የሚፈቱበት አቅጣጫ ያልተጨበጠበት ወቅት ሲሆን የምስራቅ አፍሪቃ ቀንድ አካባቢን ስንመለከት ደግሞ የሶማሊያ ቀውስ ባልበረደበት፣ የሱዳን ውስጣዊ ችግሮች በተባባሱበት፣ በኬንያ አዲስ ድህረ ምርጫ ቀውስ በተንሰራፋበትና የኢትዮጵያና የኤርትራ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ግጭት መቋጫ ባጣበት ወቅት ላይ ነን።

የምዳስሰው ርዕሰ ጉዳይ ሰፊና የተወሳሰበ ከመሆኑ አንፂር ሁሉንም በሚገባ ለመመርመር ባይቻልም የኢትዮጵያና የአካባቢው ሃገሮች ዓበይት መዋቅራዊ ችግሮች በመተንተንና አሁን ለሚገኙበት ሁኔታ ያደረገው አስተዋጽኦ በማብራራት የኢትዮጵያ የሰላምና የልማት ዕድሎች በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ለመጠቆም እሞክራለሁ። በዚህ ላይ ተመስርቶም የአገሪቱና የአካባቢው የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምን ሊመስል እንደሚችል በመጠኑም ቢሆን መተንበይ ቢከብድም የማይቻል አይሆንም የሚል እምነት አለኝ።

አቀራረቤን መልክ ለማስያዝ በሚከተለው አኳኋን ከፋፍየዋለሁ።

1. የኢትዮጵያና የአካባቢው ታሪካዊና መዋቅራዊ ችግሮች
2. የግጭትና የፖለቲካ አለመረጋጋት መንስዔዎች
3. የመፍትሔ አቅጣጫዎች
4. የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታና ልትደርስበት ትችላለች ብዬ የምመኘው ደረጃ

[1] ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ.ም የተካሄደ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡ ፡

[2] ረዳት ፕሮፌሰር መድህኔ ታደሰ Center for Policy Research and Dialogu የሚባል ለትርፍ ባልተቋቋመ ተቋም ውስጥ የሰላምና ደህንነት ዲቪዥን (Peace & Security Division) ዳይሬክተር ናቸው። ረዳት ፕሮፌሰር መድህኔ ታደሰ በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ የታሪክ መምህር ሆነው በረዳት ፕሮፌሰርነት አስተምረዋል። በአፍሪካ ቀንድ በግጭትና ደህንነት (Defence, Conflict and Security) ተመራማሪ ናቸው። በርካታ መጽሐፍ አሳትመዋል። የተለያዩ መጣጥፍ (Article) በጆርናል እና በተለያዩ ህትመቶች አውጥተዋል።

3. መንደርደሪያ

የአፍሪቃ ቀንድ አገሮች የቋንቋ፣ የባህል፣ የታሪክና የተፈጥሮ ሃብት ወዘተ... ትስስር ያላቸውና ሰላሙም ሆነ ልማቱ እንዲሁም የግጭቶች ሁኔታ የተሳሰረ እንዳውም የአንዱን አገር ችግር ከሌላው የማይለይበትና በእጅጉ የተቆራኘበት ሁኔታ ነው። ክፍለ አህጉሩ የአፍሪቃና የመካከለኛው ምስራቅ መገናኛ ከመሆኑ አንፂር የግጭት ስርዓቱና የፖለቲካ አለመረጋጋቱ መልክዓ-ምድራዊ አድማስ የሰፋ መሆኑ አያከራክርም። የምስራቅ አፍሪቃ ቀንድ አገሮች በተለይም ኢትዮጵያ የረዥም ታሪክና ስልጣኔ ባለቤት ቢሆኑም በርስበርስ ጦርነት ሲማስኑ፣ በድህነት ሲሰቃዮና በፀረ-ዲሞክራሲ ስርዓቶች ሲማቅቁ የቆዩ ናቸው። ባጭሩ ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ ርቆባቸው የቆዩ አገራት ያጠቃለለ ክፍለ አህጉር ነው ማለት ይቻላል። ይህ ክፍለ አህጉር በተለያዩ ስልጣኔዎች መፈጠርና መዳከም፣ መወራረስ እንዲሁም በመልክዓ-ምድራዊ ገጽታው የተነሳ ውሱን ሃብት ለመቆጣጠር በየደረጃው ብዙ ግጭቶች የተካሄዱበትና አሁንም ግጭቶቹ ሳይበርዱ የቀጠሉበት ክፍለ አህጉር ነው። በአንድ በኩል በህዝብ ብዛትዋ ቀዳሚነት ያላትና በአካባቢው በማዕከልነት የምትገኝ ኢትዮትያ ከሁሉም የአካባቢው ሃገራት ጋር የምትዋሰንና በዚህ በግጭቶች የተጥለቀለቀና የትርምስ አካባቢ የመረጋጋት ሚና ልትጫወት የምትችል ሆና የተፈጠረች ሃገር ነች።

በሌላ በኩል ከተፈጠረችበትና ከአመሠራረትዋ ጋር የተያያዙ የጠለቁ ችግሮች እንዲሁም ከጎረቤቶችዋ ጋር ካላት የተበላሸ ግንኙነት የተነሳ አገሪቱ የማረጋጋት ሚናዋን እንዳትጫወት ጠፍረው የያዝዋት ሃገር ነች።[3] እነዚህ የኢትዮጵያን የማደግ አቅም ያዳከሙ ችግሮችና ሁኔታዎች በቀላሉ የማይፈቱ በኢትዮጵያና በአፍሪቃ ቀንድ አወቃቀር ላይ የተመሰረቱ ጥልቅና ከባድ ፈተናዎች ከመሆናቸው በላይ ከፖለቲካ ኃይሎች (የውስጥና የውጭ) የማድረግና የመለወጥ ወይም የመፍታት አቅም በላይ ሆነው ይገኛሉ። ሆኖም የበሰለና አቅም ያለው እንዲሁም ጠቃሚ ፖሊሲዎችን የተከተለ የፖለቲካ አመራር ሲገኝ ችግሮቹ ሊፈቱበት የሚችሉበት ሁኔታ ጨርሶ የለም ማለት አይቻልም።

የኢትዮጵያ ዋነኛ ጥንካሬዎችና ድክመቶች የሚመነጩት ካለፈውና በአንፂራዊነት ልዩ ከሆነው ታሪኳ ነው። ይህ ልዩ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፍሪቃ ቀንድ ፖለቲካዊና ማህበራዊ አወቃቀር ጋር ተዳምሮ ለአገሪቱ የዛሬውና የወደፊት የሰላምና የልማት አቅጣጫ ወሳኝነት አለው። የሚቀጥለው ክፍል ይህንን ሁኔታ ለመዳሰስ ይሞክራል።

3. ታሪካዊና መዋቅራዊ ችግሮች

ልዩ ከሚባለው የአገሪቱ ታሪካዊ ዳር ብንጀምር ኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ታሪክ ያላትና ነፂነትዋን ጠብቃ የኖረች ሃገር ብትሆንም የቅኝ አገዛዝ ኢኮኖሚያዊ ክስተቶች ያልተጋራችና በስልጣኔ ያልተራመደች ሆና ቆይታለች። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ አመሰራረት ከውስጥ ኃይሎች መሪነትና ወሳኝነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ከመሆኑ አንፂር ዘመናዊው የመንግስት ስርዓት በመሰረቱትና እንዲሁም በሂደቱ ከተሳተፉት የማህበረሰብና የብሔር ክፍሎች ውጪ ያሉትን ሃይሎች በሚገባ ማስተሳሰር ያልቻለ የፖለቲካ ሂደት

[3] Christopher Clapham, 'An Introduction to the Ethiopian Political System. Unpublished Memo. 2001, Addis Ababa

የፈጠረው የተለየ የማንነት ጥያቄ ውስጥ የገባች ሃገር ነች።[4] በተጨማሪም ነጂነትዋን አስጠብቃ ግን ደግሞ ከውጭው ዓለም ጋር የሚኖራትን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ትስስር አላልታ በቆየች አገር ለረዥም ጊዜ የፊውዳልና ንጉሳዊ አገዛዝ ምናልባትም ከሚገባው በላይ የቆየ የአፄአዊ አገዛዝ የፈጠሯቸው ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ደም ላፈሰሱና ተከታታይ ለሆኑ ጽንፈኛ ለውጦች (አብዬቶች) የተዳረገች አገር ነች።[5] እነዚህ ክስተቶችና ልዩ (በአፍሪቃ ደረጃ) ታሪካዊ ሂደቶች አሁን አገሪቱ ለምትገኝበት የፖለቲካ ቀውስ፣ የማንነት ፉክክር፣ የዲሞክራሲ ሽግግር ምጥ፣ የስርዓተ መንግስት ጥያቄ ውስጥ መግባትና የግጭቶች ውስብስብነት ውስጥ ሳይከታት አልቀረም።

በሌላ በኩል ግን የኢትዮጵያ ችግር የአጠቃላይ የአካባቢው ታሪካዊና መዋቅራዊ ችግሮች አካልና ነፀብራቅ ነው። እነዚህም:-

1. ኋላቀርነትና ድህነት፣
2. በአገራት የተከፋፈለ ግን ደግሞ የተሳሰረ የህዝብ፣ የእምነቶች ግንኙነትና ልዩነት፣
3. የሃብት መመናመንና የአካባቢ መራቆት፣
4. ደካማና ፀረ-ዲሞክራሲ መንግስታት፣
5. በግጭትና በጦርነት የተከማቸ ጠባሳ፣
6. የስትራቴጂዊ ኢኮኖሚ ጥቅሞች ፍክክር፣
7. የተሳሳተ የግጭቶች አፈታትና ኋላቀር የፖለቲካ ባህል፣

ከላይ የተጠቀሱት ታሪካዊ ችግሮች በሙሉ አንድ በአንድ መዳሰስ ባይቻልም ዋና ዋናዎቹን በማንሳት እስከምንገኝበት ወቅት ድረስ ያላቸውን ተጽዕኖ መተንተን ይቻላል። ለምሳሌ ለግብጽ የአባይ ወንዝን የመቆጣጠር እንዲሁም ለኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት ጉዳዮች ባለፉት ምዕተ ዓመታት እንዳዋጉ ሁሉ አሁንም በቀላሉ የሚተው ጥያቄዎች አልሆኑም። ይህ ችግር በእጅጉ ከአካባቢውና በውስጡ ከሚገኙ አገራት አወቃቀር ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በጊዜ ሂደት ሊፈታ ያልቻለና አሁንም ወሳኝ የፖለቲካና ጂኦስትራቴጂ ጥያቄ ከዛም አልፎ የህልውና ጥያቄ ሆኖ ቀጥሏል። እንዳለፉት ምዕተ ዓመታት ሁሉ የድንበር ጉዳይንም ብንወስድ አሁንም አሻሚና አከራካሪ ብሎም የግጭት መንስዔ ሆኖ ቀጥሏል። ድንበሮች አሁንም የህዝብን ልብ ይስባሉ፣ ማንነትን ይፈታተናሉ፣ መንግስታትን ያስጨንቃሉ፣ የታጠቁ ኃይሎችን ያዋጋሉ። በክርስትናና በእስልምና የአገዛዝ ስርዓቶች ለብዙ ምዕተ ዓመታት (ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ) መካከል ሲደረግ የቆየው የሃብት ቁጥጥርና የማንነትና ወታደራዊ የበላይነት ትንቅንቅ መልኩን ከመቀየሩና ዓለምአቀፋዊ ቅርጽ ከመያዙ በስተቀር አሁንም አለ።[6] የነዚህ መሰሉ ግጭቶች ምንጭ ኢትዮጵያ ባትሆንም ወሳኝ የተሳታፊነት ሚና ይዛ ቀጥላለች።

[4] Teshale Tibebu.1995. The Making of Modern Ethiopia, 1896 - 1974. Lawrenceville: Read Sea Press. Erlich Haggai የተባለ ተመራማሪም ተመሳሳይ ትንተና አቅርቧል። ከሌሎች የአፍሪቃ ሃገሮች በተለየ መልክ የኢትዮጵያ ዘመናዊ መንግስት ስርዓት አመሰራረት በውጭ ኃይሎች ሳይሆን ከተወሰነ አካባቢ በበቀሉ የፖለቲካና ወታደራዊ ኃይሎች ላይ ከመመስረቱ አንፂር ብዙ ብሔሮችና ሃይማኖቶች ባሉባት አገር ጽንፈኛ የሆነ የብሔር ጥያቄ እንዲነሳ የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል።

[5] የ1966ቱ ደም አፋሳሽ አብዮትና የ1983ቱ ለውጥና ተከትሎ የመጣው ስር-ነቀል ኢትዮጵያን የማዋቀር ጉዞ የኢትዮጵየ ልዩ ታሪክ ውጤቶች ናቸው። ምናልባትም የአፄው አገዛዝ ራሱን በሂደት ቢያሻሽል ወይም ትንሽ የፖለቲካ ሂደቱን ቢያሰፋው ደርግ አይመጣም ነበር። እንዲሁም ደርግ ያደረገውን ባያደርግና የሆነውን ባይሆን ኖሮ የ1983ቱ ለውጥ ትንሽ የተለየ ይሆን ነበር። ወዘተ...

እነዚህ ግጭቶች በሚያስገርም ሁኔታ ለምዕተ ዓመታት ከመቀጠላቸው ባሻገር አሁንም የኢትዮጵያ ህልውናና የአካባቢው የሰላምና የልማት ሁኔታ እየወሰኑ ይገኛሉ። መንግስታት ቢቀያየሩም ችግሮቹ እምብዛም አልተቀየሩም፣ መዋቅራዊና ጥልቅ ናቸውና። ለዚህም ነው አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ ቀንድ አገሮች መንግስታት ጠንካራና የሚያሰራ የፖለቲካ መፍትሔ አቅጣጫ (Political Formula) ወይም የተሻለ የኢኮኖሚ ህላዊ (Economic Viability) ወይም አስተዳደር የሚያጎናጽፍ ርምጃ መውሰድ ያቃታቸው። አብዛኛዎቹ ገዥ ፓርቲዎች ከላይ የተዘረዘሩት ታሪካዊና መዋቅራዊ ችግሮች የወለዷቸው እናም የችግሮቹ ውጤቶች ቢሆኑም የፈጠርዋቸውን ችግሮች መፍትሔዎች መሆን ግን የተሳናቸው ይመስላሉ።[7] ይህ ችግር በእጅጉ ተንሰራፍቶ ከቆየው ድህነት፣ የመልካም አስተዳደር እጦትና በሚገባ ካልተሳሰሩ የተለያዩ ማንነቶችና እምነቶች፣ እንዲሁም ግጭቶች ራሳቸው ከተውት ጠባሳ ጋር ተዳምሮ የተረጋጉ መንግስታትና የተረጋጋ አካባቢያዊ የግንኙነት ስርዓት እንዲፈጠር አላደረገም። የሱዳን እንደአገር የመቀጠል ፈተና፣ የኤርትራ ነፂ ሃገርነት ጭንቀት፣ የኢትዮጵያ የውስጥ ሰላም እጦትና የዲሞክራሲያዊ ሽግግር ፈተና እና በሶማሊያ የመንግስት መሞት ክስተት የዚሁ ነፀብራቆች ናቸው።

4. የግጭትና የፖለቲካ አለመረጋጋት መንስዔዎች

ከላይ በተጠቀሰው ታሪክና አወቃቀር የተነሳ በአካባቢው የሚገኙ መንግስታት የሁሉንም የሚያስተዳድሩትን ህዝብ ፍላጎትና ቅርጽ የሚወክሉ ሆነው ሊፈጠሩ አልቻሉም። የተለየ አካባቢ ህዝብ ፍላጎትና አመለካከት የሚወክሉ ኃይሎች የሚቆጣጠሯቸው መንግስታት የውስጥና የውጭ ግጭቶች መንስዔ መሆናቸው አልቀረም።

እንዲሁም ከላይ የተዘረዘሩት ዋና ዋና ታሪካዊና መዋቅራዊ የግጭት ክስተቶችና መስመሮች እየተባባሱና ስር እየሰደዱ ጦርነትና ብጥብጥ ከማስከተላቸውም በላይ የተፈጠሩት ግጭቶች በፊናቸው ሌሎች ውስብስብ ሁኔታዎች እየወለዱ ተቀጣጣይ የሰላምና የልማት ችግሮች መፍጠራቸው አልቀረም። ለዚህም ይመስላል ትልቁ የግጭትና የጦርነት ምንጭ (ያለፉት ጦርነቶች ራሳቸው) የሆኑበት ደረጃ ላይ የምንገኘው።[8] ጦርነቶች ልማትን ያሰናክላሉ፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ያወሳስባሉ፣ ህዝብንና መንግስታትን ያዳክማሉ፣ ወታደራዊ አስተሳሰብን ያጠናክራሉ፣ የችግሮች በሃይል የመፍታት ባህልን ያጎለብታሉ፣ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ያጨናግፋሉ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ አንድነትን ይንዳሉ መጨረሻም የግጭት አዙሪትን ያጠናክራሉ። በዚህም የተነሳ በምስራቅ አፍሪቃ ቀንድ በኃይል የተደገፈ ግጭት ራሱ በራሱ የሚራባና (Self-reproducing) ለማጥፋት በጣም የሚያስቸግር ሆኖ የሚገኘው።

አብዛኛዎቹ ግጭቶች የሚፈጠሩት በመንግስት ስልጣንና በሃብት መቆጣጠር Disputes over Power (ሁለቱም በጣም የተቆራኙ በሆኑበት ሁኔታ) ዙሪያ ሲሆን የግጭቶቹ ደረጃ ግን ይለያያል። ማዕከላዊ መንግስትን

[6] Alex DeWaal 2003. Identifying and Preventing Conflicts in the Horn. In conference to Launch an IGAD Strategy for Peace and Security in the Sub-region. Khartoum.

[7] Medhane Tadesse. 2003. Turning Conflicts to Cooperation: Towards and Energy-Led Integration in the Horn of Africa. FES.

[8] Alex DeWaal 2003. Identifying and Preventing Conflicts in the Horn. In conference to Launch an IGAD Strategy for Peace and Security in the Sub-region. Khartoum.

ለመቆጣጠርና በመንግስታት መሃል ከሚደረግ ግጭት በተጨማሪ ከባቢያዊ የህዝብ ግጭቶች የተንሰራፋበት ክፍለ አህጉር ነው። የማዕከላዊ መንግስት ስልጣን መቆጣጠር በምስራቅ አፍሪቃ ቀንድ አገሮች ዘንድ በጣም ወሳኝ የጋለ ፉክክር የሚያስነሳ የህልውና ጉዳይ ከመሆኑ የተነሳ በመንግስት አልባዋ ሶማሊያ እንኳ ገና ለገና ወደፊት የሚፈጠረው መንግስት ለሚፈጥረው ጥቅምና ጉርሻ (rewards of state power) በማሰብ ርስ በርስ መገዳደሉ ቀጥሏል። መንግስትን መቆጣጠር ከሽልማቶች ሁሉ ትልቁ ሽልማት ነው። በመንግስታት መሃል የሚደረጉ ግጭቶች መነሻቸው ብዙ ቢሆኑም በእጅጉ ከዚሁ ጋር ይያያዛል። አከራካሪ ድንበሮችና በአካባቢው የሚገኙ ብሔሮች ከተለያዩ ማዕከላዊ መንግስታት ጋር ያላቸው ያልተስተካከለ ግንኙነት እንዲሁም ማዕከላዊ መንግስታት ከወሰን ክልሎች አንፃር የሚከተሉት ከፋፋይ ወታደራዊ ስትራቴጂ ለአካባቢው አለመረጋጋት አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው። የመንግስታት በጎረቤታቸው ጉዳዮች ጣልቃ የመግባት አዝማሚያ ከዚህ ይመነጫል። ስለሆነም የትኛውም ዓይነት የውስጥ ችግር የአንድ አገር የውስጥ ችግር ሆኖ በጭራሽ ሊቆይ አይችልም።

ባጠቃላይ ሲታይ ግን በምስራቅ አፍሪቃ ሃገሮች በሙሉ ማለት ይቻላል አለመግባባቶችና ግጭቶች ወደ አመጽና ደም መፋሰስ የሚያመሩት ሁለት ነገሮች ሲገናኙ ነው። እነዚህም በአንድ አካባቢ የሚፈጠር ሽኩቻ (local dispute) እና የማዕከላዊ መንግስታት አላግባብ ስልጣን አጠቃቀም (misuse of power of control governments) ናቸው። ስለሆነም የአካባቢ ትናንሽ ግጭቶች አፈታትና የመንግስታት ስልጣን አጠቃቀም በጣም ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው።

ድህነት በተንሰራፋበት፣ ማህበራዊ ግንኙነት (Social Capitalን ጨምሮ) በተዳከመትና በተበጣጠሰበት፣ ኋላቀር የፖለቲካ ባህል በነገሰበትና ሰላማዊ የግጭት አፈታት መንገድ (Civil dispute mechanism) በሌለበት፣ የሃብት መመናመንና ውሱን ሃብት ለመቆጣጠር በሚደረግ እርስ በርስ በማይተማመኑና በሚፎካከሩ ኃይሎች መሃል ግጭትና ፉክክር በተንሰራፋበት፣ የመንግስታት አቅምና ተቀባይነት በተሸረሸረበት ሁኔታ ሰላምና ልማት ማረጋገጥ አይቻልም። ይህ ሁኔታ ከአካባቢያዊ ቀውስና አለመረጋጋት ጋር ተዳምሮ የምስራቅ አፍሪቃ ቀንድ ሁኔታ በእጅጉ አሳሳቢ ከማድረጉም ባሻገር የኢትዮጵያን የአሁኑ እ<ና የወደፊት ዕጣ ፈንታ በእጅጉ የሚወስንበት ደረጃ ላይ እንገኛለን።

5. የመፍትሔ አቅጣጫዎች

የኢትዮጵያ ህልውናና የወደፊት አቅጣጫ የሚወስኑት ሁኔታዎች ስናይ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ከመፍታትና ካለመፍታት ጋር ይገናኛል። መፍትሔዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

ጦርነቶች የፈጠርዋቸውን ድምር ውጤቶችን አንድ በአንድ መቅረፍ። ይህ በተለያየ ወቅት የተከማቸና የተበታተኑ የጦር መሳሪያዎችን ማጽዳት ብቻ ሳይሆን ከሱ ጋር የተቆራኙ አስተሳሰቦችን ማስወገድ ይጠይቃል። ከዚህ አንፃር:-

1ኛ. Demilitarization በተለይም የደህንነትና የፀጥታ አካላት ለውጥና ማሻሻያ ፕሮግራም (Security Sector Reform SSR)) መቀየስና ማስኬድ በእጅጉ ለክፍለ አህጉሩና ለኢትዮጵያ ወሳኝ የሰላምና የልማት መንገድ ይመስለኛል። [9]

[9] Medhane Tadesse. 2007. Overcoming Challenges to Security Sector Reform in the Horn of Africa. CPRD. ISS Monograph Series No. 135.

2ኛ. የሰላማዊና ፖለቲካዊ የግጭት አፈታት ዘዴን መጠቀም ችግሮችን በኃይል የመፍታት አካሄድ ማቆም እንዲሁም የተለያዩ ማህበራዊና ባህላዊ፣ የእምነትና የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እንዲንቀሳቀሱና እንዲጠናከሩ መፈቀድ ብሎም በግጭት አፈታት ላይ የሚኖራቸው ሚና ማጎልበት። የምስራቅ አፍሪቃ ቀንድ የብዙ ሲቪላዊና ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች አቅምና ተሞክሮ ያለው አካባቢ ከመሆኑ አንፃር ግጭቶችን ለመፍታት ከታጠቁና ካልታጠቁ የፖለቲካ ኃይሎችና መንግስታት አካሄድ ውጪ ያሉትን መፈተሽ።

3ኛ. የፖለቲካ ሂደቱ ልዩነቶችን ከማስተናገድ በተጨማሪ ህዝቡን በሚያስተሳስሩ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ። ጠንካራ የሲቪል ማህበረሰብና አገር እንዲሁም ዲሞክራሲ ማስፈን የሚቻለው የህዝቦች አስተሳሰብና ራዕይ ወደ አንድ አቅጣጫ ማለትም ሰላምና ልማት እንዲያተኩር ሲደረግ ነው። ጠንካራ አገርና መንግስት እንዲሁም ተመሳሳይ ራዕይና የተባበረ ጉዞ በሌለበት ሁኔታ ሰላም ልማትና ዲሞክራሲ መፍጠር አይቻልም።

በታሪኩና በወደፊት ህልውናና ጉዞው ላይ የማይስማማ ህዝብ ይዞ ልማትና ዲሞክራሲ አይታሰብም፣ (There is no democracy without the State) State አገር፣ ህዝብና ታሪኩንም ይጨምራል። ይህ ጥያቄ ውስጥ በገባበትና የኢትዮጵያ አገርነትና አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብነት አከራካሪ በሆነበት ሁኔታ ሰላም ዲሞክራሲና ልማት ማስፈን አስቸጋሪ ይሆናል።

4ኛ. የዲሞክራሲ ሂደቱን ማስፋትና የዲሞክራሲ ተቋማትን ማጠናከር። ዲሞክራሲ ሂደት ነው። ሂደት ብቻውን አለ ተቋም ግን የትም አያደርስም። በኢትዮጵያ ሁኔታ ብዙ ነገሮች (ስርዓተ መንግስቱ ባጠቃላይና የመንግስት መዋቅሮች ህግጋትና አካሄዶችን ጨምሮ) ጥያቄ ውስጥ በገቡበት (Contested በሆኑበት) ሁኔታ ጠንካራና በአንፃራዊ መልክ ነፃ ወይም ገለልተኛ ብሔራዊ ተቋማት ሳይመሰረቱ የዲሞክራሲ ሂደቱ ማስፋት፣ ምርጫዎችን በተከታታይ ማካሄድ ጠቃሚ ቢሆንም ጠንካራ የዲሞክራሲ ተቋማት ሳይፈጠሩ የአገሪቱ ዘረፈ ብዙ ግጭቶች ሊፈቱ አይችሉም። ዲሞክራሲን ከማጠናከር አንፃር እና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ብቻ ሳይወሰን ጠንካራ ተቋማት (እንደ ፓርላማ፣ ፍትህ፣ ሚዲያ) መፍጠር አሁን ያሉትን በትጥቅ የተደገፉ ግጭቶች ጭምር ማስተንፈሻና መፍቻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ይህ አካሄድ የሲቪል ማህበራትንና ነፃ ማህበራዊ ተቋማት ከማጠናከር እንዲሁም እንደባህል ችግሮችን በኃይል የመፍታት አቅጣጫ መቀነስ ጋር ተዳምሮ ዋነኛው የአገሪቱ የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በዚህ ላይ ወታደራዊ ቅሪቶችና አስተሳሰቦች ማስወገድና የደህንነት ተቋማትን ማሻሻል፣ በሲቪልና ዲሞክራሲያዊ አመራር ስር እንዲውሉ ማድረግ ተጨምሮበት የኢትዮጵያ የፖለቲካ አለመረጋጋት ችግሮችን ለመፈታት ወሳኝነት ይኖረዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ተዳምሮ

- የህግ የበላይነትን ማስፈን፣
- ነፃና ጠንካራ የኢኮኖሚ ተቋማት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ማበረታታት፤
- ኢትዮጵያ ለአንድ ፓርቲ (አንድ አመለካከት) አገዛዝ ትልቅ መሆንዋን መገንዘብ፤የስልጣን ክፍፍል መርሆና የጥምረት መንግስታት (በየደረጃው) አቅጣጫ መሞከር፣

- ቁጥጥሩን በመቀነስ የገበሬውን ምርታማነት ለማሳደግ መጣር፣
- ክልላዊ ኢኮኖሚያዊ ትስስሮችን መቅረጽ
- ክፍለ አህጉራዊ የኢኮኖሚ ትስስሮችን ማበረታታት
- በኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችና የፖለቲካ አስተሳሰቦች ላይ የተመሠረቱ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ መፈቀድና መረዳት (በሂደት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር እንዲቀንስና ከተቻለም ወደ ሁለት ዓበይት አገራዊ ፓርቲዎች እንዲሰባሰብ መጣር)፤
- ብዘት ካላቸው አካባቢያዊ የብሔር ፖለቲካ ፓርቲዎችና ሚሊሺያዎች ይልቅ ብዛት ያላቸው (እንዲሁም ዘርፈ ብዙ) የሲቪል ማህበረሰብ የጥቅም ቡድኖች እንዲፈጠሩ ማበረታታት ለኢትዮጵያ የወደፊት የፖለቲካ መረጋጋት፣ ሰላምና ልማት ወሳኝነት አላቸው። ይህ አቅጣጫ የኢትዮጲያ የፖለቲካ ሂደትና ሜዳ እንዳይበጣጠስ፣ የፖለቲካ ኃይሎች የማድረግ አቅም እንዳይዳከም፣ ብዛት ያላቸው የተዳከሙና ሰፊ ተቀባይነት የሌላቸው አገሪቱን የማረጋጋት አቅማቸው የመነመነ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና አገራዊ የፖለቲካ አንድነት መፍጠር የማይችሉ ፖለቲካዊ ኃይሎች እንዳይንሰራፉ ይከላከላል።

5ኛ. በእምነት ላይ የተመሰረተ ልዩነቶችን በጥሞና መከታተል፣ ችግሩን በሚያባብሱ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ላይ በጥናት የተመሠረተ የመቻቻልና የዲሞክራሲ መርሆዎችን የተከተለ አቅጣጫ መቀየስ። አካባቢው አንዱ የ'ፀረ-ሽብር' ግንባር ከመሆኑ አንፂር፣ ኢትዮጵያም ባላት ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ብዛትና በሶማልያ በኩል ከመነጨው ስጋት አንፂር የሃይማኖት (በተለይም የዋህቢያ እስልምና) ጉዳይ በቀላሉ የማይታይ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ። ይህ ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተከሰተ ባለው የሃይማኖቶች የኃይል ሚዛን ለውጥና እየጨመረ የመጣው የውጭ ተጽዕኖ[10]፤ የግሎባላይዜሽን ሂደት፣ ከአረቡ ዓለም ጋር (በተለይም ከሳውዲና የገልፍ አገሮች ጋር) ያለው የትስስር ፍጥነት ጋር ተዳምሮ በሃይማኖቶች ትስስር የመቻቻል ሂደት ላይ ትኩረት ማድረጉ ወቅታዊና ጠቃሚ ይመስለኛል።

ሆኖም ከላይ የተዘረዘሩት የመፍትሔ አቅጣጫዎች ሊሳኩ የሚችሉት አጠቃላይ የአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ ችግሮች የሚፈቱበት አቅጣጫ ሲዘረጋ ብቻ ነው። ዋናው የመፍትሔ አቅጣጫ አካባቢያዊ (ክፍለ አህጉራዊ) የፖለቲካና የኢኮኖሚ ትስስር ማጠናከር ቢሆንም ይህን ለማሳካት የሚከተሉት ርምጃዎች መወሰድ የግድ ይላል።

- ተመጣጣኝ የዲሞክራሲ ጉዞ (Parallel Democratisation) በየአገራቱ ማስጀመር፣ ዲሞክራሲን በአገር ውስጥ በማጠናከር በአካባቢው የምሳሌነትና የመሪነት ሚና መጫወት። ከላይ እንደተገለፀው ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ማስፈን የውስጥ ችግሮችን ከመፍታት አልፎ በክፍለ አህጉሩ ሰላምና የኢኮኖሚ ትስስር እንዲፈጠር ይረዳል። የዲሞክራስያዊ ሂደቱን ማስፋትና ለዚሁ የሚያስፈልጉ ተቋማት መፍጠር እንዲሁም የፖለቲካ ትስስሩ የጠነከረ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ እውን እንዲሆን ማድረግ ጠንካራና የደረጀ ህዝብና አገር፣ በቀላሉ የማይደፈር የመከላከያ አቅም እንዲሁም የሞራል የበላይነት ያለው አገር

[10] Erlich Haggai. 2004. The Saudi Factor in Ethiopia. የችግሩን ታሪካዊ መንደርደሪያ መዳሰስ ይሞክራል። Medhane Tadesse. 2005. Religion, Peace and the Future of Ethiopia. Conference on Federalism in Ethiopia. GTZ, Addis Ababa, Ethiopia

ከመፍጠር አልፎ በአካባቢው የመሪነትና የተቀባይነት ሚና የሚኖራት ከዚህ የተነሳም አካባቢውን በማረጋጋት የራስዋን ሰላምና ልማት ማረጋገጥ የምትችል የህዝብዋ ቁጥርና አኩሪ ታሪክዋን የሚመጥን ደረጃ ያላት አገር መፍጠር ይቻላል።

- አገሮቹን ሊያስተሳስሩ በሚችሉ የኢኮኖሚ ዘርፎችና ግንኙነቶች ላይ በሚገባ መስራት። ለምሳሌ፤ ውሃ፣ የኃይል ምንጭና ድንበር ተሻጋሪ የግሪሽ መሬቶች ላይ።[11]
- ክፍለ አህጉራዊ ድርጅቶችን ማጠናከርና እስከታች እንዲዘረጉ ማድረግ። ከመሪዎች ጉባዔ በተጨማሪ የፓርላማ የሲቭል ማህበራትና የሃይማኖት ድርጅቶችን መፍጠር፣
- ክፍለ አህጉራዊ የሃይማኖቶች ጉባዔ መፍጠርና ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር ያለውን ትስስር መፈተሽና መልክ ማስያዝ፣
- በተናጠል እንዲሁም በክፍለ አህጉራዊ ድርጅቱ በኩል ግጭቶችን ለመፍታት መሞከር እንዲሁም ክፍለ አህጉራዊ (የIGAD) የግጭት መፍቻ መዋቅሮችን ማጠናከር።[12]

6. የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ

ከላይ በክፍል 3 ላይ የተጠቆሙት የመፍትሔ አቅጣጫዎችና ፖሊሲዎች ካልተወሰዱ የፈለገ የኢኮኖሚ አቅጣጫ ብትከተልም የወደፊት የኢትዮጵያ ሁኔታ የሚከተለውን ይመስላል።

- ከፖለቲካ ግጭትና ከድህነት አዙሪት ያልተላቀቀች፣
- የፖለቲካ አንድነት የሌለው ህዝብ የሚኖርባት፣
- መንግስታዊ ተቋሞች የተዳከሙባት፣
- የብሔረሰብና የሃይማኖት ግጭቶች የተንሰራፉባት፣
- ለውጭ ተጽዕኖና ከፋፋይ ፖሊሲ የተመቻቸች፣
- እንደሃገር የመበታተን አደጋ የተደቀነባት፣

መበታተኑ የተለያዩ ብሔሮችና ሃይማኖቶች (እስከ አራት የእስልምና ኢሚሮቶች የሚደርስ) ማዕከል ያደረጉ ትናንሽ የፖለቲካና ወታደራዊ ግዛቶች የሚተራመሱባት መልክዓ-ምድር ከመሆንዋ በተጨማሪ እነዚሁ ግዛቶች በአካባቢው ከሚገኙ ግዛቶች ጋር የትርምስ ትስስር በመፍጠር አጠቃላይ ክፍለ አህጉራዊ ቀውስ ውስጥ የሚገባ ህዝብ ያላት አገር ልትሆን ትችላለች።

ከላይ (በክፍል 3) የተዘረዘሩት የመፍትሔ አቅጣጫዎች ከተወሰዱ ግን ኢትዮጵያ በጣም በተሻለ ደረጃ ላይ የምትገኝ አገር ትሆናለች፤ የኔ ፍላጎትና ራዕይም ይሄ ነው። ይኸውም:-

- ኢኮኖሚዋ የበለፀገ፣

[11]Medhane Tadesse. 2003. Turning Conflicts to Cooperation: Towards and Energy-Led Integration in the Horn of Africa. FES.

[12]Intergovernmental Authority for Development (IGAD). Khartoum, 2004 Five year strategy plan

- የዲሞክራሲ ተቋማት የተጠናከሩባት፣
- በፖለቲካ አስተሳሰብና በዓበይት ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የተመሠረቱ ሁለት ትላልቅ የፖለቲካ ፖርቲዎች ለስልጣን የሚፎካከሩባት፣
- የፖለቲካ አንድነትዋ የጠነከረ
- አስተማማኝ የውስጥ ሰላምና የመከላከያ ኃይል ያላት፣
- በኢኮኖሚና በዲሞክራሲ ረገድ በክፍለ አህጉሩ ከፍተኛ ጫና የምታሳድር፣
- ራስዋን አረጋግታ ክፍለ አህጉሩን ወደ ሰላም እንዲሁም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ትስስር የምትመራ አገር እንድትሆን ነው።

በረዳት ኘሮፌሰር መድህኔ ታደሰ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ካሳሁን ብርሃኑ[1]

የአቶ መድህኔ ታደሰ ጽሑፍ በመግቢያው ላይ ኢትዮጵያም ሆነ ሃገሪቱ የምትገኝበት የአፋሪካ ቀንደ አካባቢን ጅኦ-ፖለቲካዊ ሁኔታ በመዳሰስ ይጀምራል። በመቀጠልም ከሰላምና ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በክፍለ አህጉርና በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚታዩ ወቅታዊ ሁኔታዎች በዋቢነት የሚጠቀሱ ታሪካዊና መዋቅራዊ ችግሮችና ያለመረጋጋት መንስኤዎችን በመጠቆም የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያመላክታል። በመጨረሻም ሠላምና ልማትን በማረጋገጥ ረገድ የኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ፋንታና ልትደርስበት ትችላለች የሚለውን የፀሐፊውን ራዕይ በማካፈል ይጠቃለላል።

አቶ መድኃኔ ታደሰ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ግልጽ በሆነና ጠቅለል ባለ መልኩ ኢትዮጵያ ከክፍለ አህጉሩ ሀገራት ጋር በወል የምትጋራቸዉን እሴቶችም ሆነ መዋቅራዊና ታሪካዊ ችግሮችም ሆነ የግጭትና ያለመረጋጋት መንስኤዎች በበቂ ይተነትናል። ይህ አቀራረብ ሀገሪቱ በታሪክም ሆነ በሌሎች የወል ያልሆኑ የኢትዮጵያ ብቻ ተብለዉ ሊወሰዱ የሚችሉ ልዩ መገለጫዎች ሰላምና ልማትን በሚመለከት ያስከተሏቸዉን እንደምታዎች በዝርዝር ቢያቀርብ ኖሮ የጽሑፉ ይዘት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ያለዉን ቀጥተኛ ተዛማጅነት ይበልጥ ያዳብረዉ ነበር። ለምሳሌ፤ የኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ የመንግስትነት ታሪክ የመንግስት ምስረታና ብሄራዊ ነፃነትን የማስከበር ሂደት የኢትዮጵያዊያን የማህበራዊ ሕይወት ገጽታዎች (ባህሎች ኃይማኖቶች ወግና ልማዶች) እንዲሁም እነዚህ ለሰላምና ለልማት ያደረጓቸዉን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አስተዋጽኦዎች ዘርዘር ባለመልኩ ማብራራት የጽሑፉን ርዕሰ ጉዳይ በይበልጥ በአግባቡ ለማስተናገድ አመቺ ይሆን ነበር። ይህንን ስንል እነዚህ ጉዳዮች ፈጽሞ አልተወሱም በሚል ሳይሆን ጠቅለል ብለዉ መቅረባቸዉንና በአብዛኛዉም ከክፍለ አህጉሩ ሀገራት ሁኔታዎች ጋር ተጎዳኝተዉ መነገራቸዉን ለመጠቆም ነዉ። የኢትዩጵያን የሰላምና ልማት ሁኔታ በምንመረምርበት ጊዜ አግባብነት ያላቸውን የሀገሪቱን ታሪካዊና ነባራዊ ሁኔታዎች በቅደም ተከተል ለይቶ ማስቀመጡና እነዚህንም ከውስጣዊና ውጭያዊ ክንውኖችና ሁነቶች ጋር አዛምዶ መመልከቱ የጽሑፉን ይዘት ሊያዳብረው ይችላል ብዬ እገምታለሁ።

[1] ዶ/ር ካሳሁን ብርሃኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት ዲፓርትመንት ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ ደ/ር ካሳሁን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በፖለቲካል ሳይንስ አለም አቀፍ ግንኙነት ከአዲስ አበባ ዩኒቨሪስቲ ያገኙ ሲሆን የማስትሬት የዶክትሬት ዲግሪአቸውን ከሆላንድ አግኝተዋል፡፡ ዶ/ር ካሳሁን የተለያየ የምርምር ሥራዎችን በምግብ ዋስትና በአስተዳደር ነፃነት በግጭትና ግጭት ማስወገድ በፖለቲካ ፓርቲና ሕገመንግስት ዙሪያ አካሂዳዋል፡፡ ዶ/ር ካሳሁን በተለያየ የፖለቲካ ቦታዎች ላይ የሰሩ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሶሻል ሳይንስ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዲፓርትመንት ኃላፊ እንዲሁም በምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የማህበራዊ ሳይንስ ምርምር ኢንስቲትዩት ረዳት ፕሬዚዳንት እና በፎረም ሶሻል ሳይንስ (Forum for Social Studies) በፕሬዝዳንትነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚህም ረገድ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት ይቻላል።

- በኢትዮጵያ የመንግሥት ምሥረታ ሂደት ያስከተላቸው ግጭቶችና መፈናቀሎች እንዲሁም የማንነትና የይገባኛል ጥያቄዎች ያስከተሏቸዉ ዉጤቶች
- የሰላማዊ አብሮ መኖርና የእርስ በእርስ ጦርነቶች ታሪክና እንደምታዎች
- የዘመናዊ አስተዳደር /መንግስት ምሥረታ ሂደቶችና ውጤቶቻቸው
- ለለውጥ የመነሣሣት እንቅስቃሴዎች በሀገሪቱ ሰላምና ልማት ላይ ያሳደሯቸው በጎና አፍራሽ ተጽእኖዎች
- የተፈጥሮአዊና ሠው ሠራሽ አደጋዎች ሚናና አስተዋጽኦ
- የገዥ መደቦችና ሌሎች ተዋናዮች ለሥልጣንና ለበላይነት ያደረጓቸዉ ፉክክሮች ውጤቶች
- የውስጥ አስተዳደር መዛባቶችና ጠንቆቻቸው
- የውጭ ኃይሎች ወረራንና የበላይነት ፍላጐትን ለመመከት የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፂነት ተጋድሎ
- የቀዝቃዛው ጦርነት በኢትዮጵያ ሰላምና ልማት ረገድ የተጫወተው ሚናና ያሳደረው ተጽዕኖ

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ርዕሰ ጉዳዮች ሰላምና ልማትን አስመልክቶ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያስከተሏቸውን እንደምታዎች መመርመሩና እንደ ሁኔታው ገንቢና አፍራሽ ውጤቶቻቸውን ማሳየቱ ለዋናው የጽሑፍ ርዕስ በቂ መንደርደሪያ ሆነው ያገለግላሉ። በመቀጠልም የሰላምና የልማት ዋና ዋና ተዋናዮችና ደጋፊ ኃይሎችን እንደ ባለ ድርሻ (Stake holder) ለይቶ በማውጣት እያንዳንዳቸው በየበኩላቸው ሊያደርጉ የሚችሉትን አስተዋጽኦና ሊጫወቱ የሚገባቸውን ሚና በጽሑፉ ውስጥ መዘርዘር አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ ረገድም መንግሥትን፣ የሲቪል ማህበራትን፣ ባሕላዊ የሕብረተሰብ ስብስቦችን፣ እንዲሁም አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎችን በግንባር ቀደምነት መጥቀስ ይቻላል።

እንደማንኛውም ሀገር ሁሉ በኢትዮጵያችንም ወጣቱን ትውልድ ለሀገር ሰላምና ልማት እንደ ኃይል መቅረጽና ለሀገር ተረካቢነት የማዘጋጀት አስፈላጊነት በጽሑፉ ውስጥ ጐልቶ መውጣት ነበረበት። ተወደደም ተጠላም የሀገሪቱ እጣ ፈንታ የሚወድቀው በወጣቱ ላይ መሆኑ አያጠያይቅም። ወጣቱ ትውልድም ይህንን ድርሻ በብቃትና በአስተማማኝ መልኩ መወጣት የሚችለው በአካል፣ በዝንባሌ፣ በስነ ልቦናና በተግባራዊ ተመክሮ ተዘጋጅቶ ሲገኝ ብቻ ነው። ለዚህም ከወላጆች ጀምሮ ትምህርት ቤቶች ማህበራዊ ተቋማት፣ መንግስትና በአጠቃላይም እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነቱን መውሰድና ለስኬታማነቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴን ማድረግ የማይታለፍ ይሆናል። የኢትዮጵያችን ወጣት ትውልድ በሀገርና ወገን ወዳድነትና በአርበኝነት ከወዲሁ ካልታነፀና ፍትህና ሰላም ወዳድነትን በጊዜው ካልተላበሰ በተለያዩ ምክንያቶችና በጊዜ አጋጣሚዎች በተፈጠሩ ወጥመዶች ተጠልፎ የተለያዩ ጐጅ አዝማምያዎች ሰለባ ከመሆን አያመልጥም። አልፎ አልፎ አሁን እንደሚታየውም የማንነት ባዶነት፣ ለሀገርና ለወገን ታሪክና ስብእና ስሜት-አልባነት እንዲሁም ሁለንተናዊ ደንታ-ቢስነት የወጣቱ ትውልድ መገለጫና ባሕርይ ከመሆን የሚያግዳቸው ነገር አይኖርም። ለዚህም ቀውስ ዋነኛ የታሪክ ተጠያቂዎች የምንሆነው

በአጠቃላይም ሆነ በግል እያንዳንዳችን መሆናችን ታውቆ የአቶ መድኃኔ ታደሰ ጽሑፍ ይህንን የማንቃት ጥሪ የሚያንጸባርቅ ድምፀት ቢኖረው የበለጠ የተሻለ ይሆናል።

እንደ ኢትዮጵያ ባለች ሀገር ሰላምና ልማትን የማረጋገጥ ቀዳሚ ሚናና ኃላፊነት የመንግስት ሆኖ እንደሚቀጥል አጠያያቂ አይሆንም መንግስት መልካም አስተዳደርን የመዘርጋት የሕብረተሰብን የተረጋጋና ሰላማዊ የኑሮ መሰረቶችን የመጣል በሕዝቡ እሳቤ ዉስጥ የሀገር ባለቤትነትና የዜግነት ድርሻ መወጣትን ዝንባሌ የማስረጽ ግንባር ቀደም ሚና የመጫወት ኃላፊነት አለበት። ስለዚህም የአቶ መድኃኔ ጽሑፍ ይህንን ጉዳይ በአጭሩም ቢሆን ቢያካትት ጠቀሜታ ይኖረዋል።

በዚህ ጽሑፍ ዉስጥ የግጭትና የፖለቲካ አለመረጋጋት መንስኤዎች በዝርዝርና ጠቅለል ባለ መልኩ በበቂ ሁኔታ ቀርበዋል። በመፍትሔ አቅጣጫነት በጽሑፉ ዉስጥ የተጠቆሙት ነጥቦችም ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸዉ ናቸዉ። እነዚህን የመፍትሔ ነጥቦች ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ እያንዳንዱ ባለድርሻ (መንግሥት ሲቪል ማህበራትና በአጠቃላይም ሕብረተሰቡ) ሊያደርጓቸዉ የሚገቧቸዉ ነገሮችንና በየበኩላቸዉ ማበርከት የሚኖርባቸዉን አስተዋጽኦ ለይቶ ማዉጣቱ ሰላምና ልማትን በኢትዮጵያ ለማረጋገጥ የእንቅስቃሴ አቅጣጫን አመልካች ይሆናል።

በረዳት ኘሮፌሰር መድህኔ ታደሰ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ዘውድነህ በየነ ታይሌ[1]

1. መግቢያ

ይህች ጽሑፍ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ጥር 16 ቀን 2000 ዓ.ም. በአ/አበባ፣ በሂልተን ሆቴል ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ «ሰላምና ልማት በኢትዮጵያ-ዛሬና ነገ» በሚል ርዕስ በአቶ መድህኔ ታደሰ ለውይይት በቀረበው ፅሁፍ ላይ የተሰጠውን አስተያየት ያካተተች ናት።

2. አስተያየት በረዳት ኘሮፌሰር መድህኔ ታደሰ ፅሑፍ ላይ

የፅሑፍ አቅራቢውን በቅርበት አውቃቸዋለሁ፣ የምርምር ስራዎቻቸውንም አነባለሁ። በንዑስ አህጉራዊ ቀጣናው ዙሪያ የፖለቲካ ዘገባና ምርምር አዘል ፅሁፎች ማቅረብ ከጀመሩ የቆዩ ምሁር ናቸው።

ምሁሩ የተሰጣቸው ርዕስ እጅግ ሠፊና ውስብስብ ሆኖ ሳለ፣ በቀረበው ፅሁፍ ትኩረታቸውን ወደ ምስራቅ አፍሪካ ንፅፅራዊ ሠላምና መረጋጋት ላይ በማተኮር ለየት ያለን የመነጋገሪያ ማዕቀፍ ሠጥተውናል። በሌላ አነጋገር የፅሁፍ አቅራቢው የኢትዮጵያን የሰላምና የልማት የወደፊት እጣ ፋንታ የሚመለከቱበት መነፅር የጎረቤትና የአካባቢው ሀገሮች የሚመሩበትን ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ መዋቅር በታሳቢነት የያዘ ነው።

በተናጠል ያለ የአንድ አገር ብቻ የልማት ትንታኔ በራሱ ምሉዕና ፍፁም ሰለማይሆን፣ ምሁሩ የመረጡት የንዑስ አህጉራዊ የንፅፅር ትንታኔ የኢትዮጵያን የወቅቱን ሁኔታ ጠቅለል ባለ መልኩ ለማቃናትና የወደፊቱን ለመተለም የሚያስችል በመሆኑ፣ የምሁሩ የትንታኔ ስልት ሊወደስ የሚገባው ነው።

ይሁን እንጂ ትንታኔው ያመዘነው በአብዛኛው «በጂኦ-ፖለቲካዊ» ማብራሪያዎች ዙሪያ በመሆኑና፣ የአካባቢውን አንፂራዊ አለመረጋጋት ብቻ በማሳየት የልማት ትንታኔውን አጉልቶ ያላወጣ ነው ቢባል የተጋነነ አስተያየት አይደለም ማለት ይቻላል።

በምሁሩ አስተያየት ኢትዮጵያ ጠንካራ ሆና ብትወጣ ጎረቤቶቿም ለትርምስ እንደማይዳረጉ፣ ዛሬ በኢትዮጵያ የሚታየውም ሰላምና ልማት ነክ ችግር ሁሉ የአካባቢው (የአፍሪካ ቀንድ) ታሪካዊና መዋቅራዊ ችግሮች አካልና ነፀብራቅ እንደሆነ ጠቅሰው፣ በተለይም ኃላቀርነትና ድህነት፣ የሃብት መመናመንና

[1] ዶ/ር

የአካባቢ መራቆት፣ ደካማና ፀረ-ዲሞክራሲ መንግስታት መኖር፣ በግጭትና በጦርነት የተከማቸ ጠባሳ መኖር፣ የስትራቴጂካዊ ኢኮኖሚ ጥቅምና ፉክክር መኖርና፣ የተሳሳተ የግጭቶች አፈታትና ኃላቀርነት የፖለቲካ ባህል ለአለመረጋጋቱና ትርምሱ አበይት ምክንያቶች እንደሆኑ ጠቅሰዋል።

ምሁሩ ያመላከቷቸው የአካባቢው ችግሮች የሉም የማይባሉ በተጨባጭ ማስረጃዎችና Case studies ሊደገፉ የሚችሉ ናቸው። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያን ሰላምና ልማት ፈተናዎች በተናጠል ወስዶ በዝርዝር ለመተንተን አያስችሉም ባይባሉም፣ የሀገሪቷን ችግር በቀላሉ ሊያሳይ ወደሚችል ትንተና የሚያመሩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀመሮችን የሚሰጡ ሆነው አላገኘኋቸውም።

ከዚህ አንፃር በልማት ሳይንስ የተሠማሩ ምሁራንና ፀሀፊዎች እንዲህ ላለ ትንተና ይረዳሉ ብለው ያስቀመጧቸውን የትንተና መርሆች በግርድፍ ለማሳየት የተከበሩ አንባቢዎች በመርሆዎቹ የዛሬይቱ ኢትዮጵያን የሰላምና ልማት ሁኔታ እንዲወያዩባቸው፣ ለነገይቱ ኢትዮጵያ ሰላምና ልማት ማበብና መገኘት ግን ልንቀበላቸው የሚገቡንን የጋራ ነጥቦች በሚቀጥሉት ጥቂት ገፆች ለማውሳት እሞክራለሁ።

ለአፍሪካ አለማደግ ምክንያት በመሆን የፖለቲካ ቀውስን በየሀገሪቱ የፈጠሩ ምክንያቶችን ሲተነተኑ የተለያዩ ምሁራን ለአፍሪካ የአስተዳደር ቅርፆች (ስልቶች) የተለያዩ ስሞችን በመስጠት በተለያዩ የጥናታዊ ፅሑፎች ምዘናን አድርገዋል።

ጥቂቱን ለማስታወስ ያህል፣ Robert Jackson እና Carl Rosberg እ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ ገደማ ለፖለቲካዊ ቀውስ አፍሪካን የዳረጋት አስተዳደራዊ ስርዓት የአንድ መሪ አምባገነንነት (Personal Rule) ነው ይላሉ። ከዚያም በተከታታይ የወጡ ጥናቶች ለቀውስ ስርዓቶቹ ከያዟቸው የተለያዩ መጠሪያዎች "Patrimonialism"፣ "Neo-Patrimonialism", "Prebendalism"፣ Sultanism" ፣ ወ.ዘ.ተ... የሚሉት ይገኙባቸዋል።

በታዋቂው ምሁር ማክስ ዌበር አመለካከት፣ "Patrimomionialism" በአፍሪካ ባህል የወለደው ወይም ሲወርድ ሲዋረድ የተገኘ የአስተዳደር ስልጣን (Traditional Authority) ነው ይለዋል። በዌበር አገላለፅ፣ አንድ የፖለቲካ ስርዓት የከፍተኛ የአመራር አካሉንና የወታደራዊ ኃይሉን የሚመሩ ባለስልጣናት ለሀገሪቱ መሪ የቅርብ ታማኝ ሰዎች ሲሆኑና፣ በስልጣንም ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ ሲደረግ ስርዓቱ "Partimonial" ነው።

እንዲህ ያለው ስርዓት የሚከተሉት ባህርያት እንዳሉት ምሁራኑ ይተነትናሉ።

G) ሹመት የሚሰጠው በችሎታና በበዛ ህዝባዊ ድጋፍ ሳይሆን ለመሪው ባለ ታማኝነት ብቻ ነው።
K) የሚተላለፉ ውሳኔዎች ሁሉ ከግል ስሜት የሚመነጩ፣ የመንግስት ቢሮዎች ደግሞ እንደ ግል ሃብት የኩባንያዎች ወይም እንደ የግል ጥቅም ማስጠበቂያዎች የሚቆጠሩበት ነው። (በWeber አገላለፅ "Prebend" ይባላሉ)
N) ባጠቃላይ በዚህ ዓይነቱ ስርዓት የግል ጥቅምን የዘለለና ህዝባዊ ጥቅምን ለማስከበር የቀደመና ግልፅነት ያለበት አሠራር አልተዘረጋም (የለም)።

ሌሎቹ ምሁራን እነዚህኑ የስርዓቱን የባህርይ ትንታኔዎች ወስደው ይህ አይነቱ አስተዳደር የነገሠበት አፍሪካ በግለሰብ አምባገነንነት (Personal Rule) ስር መወደቋ፣ ላለማደጓ አንድ ዓይነተኛ ምክንያት እንደሆነ ያስረዳሉ። ይህንን ዓይነቱን ስርዓት በሌላ አጠራር የሚሰይሙት ምሁራን ደግሞ የጥቅማጥቅም ተጋሪዎች አስተዳደር ወይም "Clientalism" ይሉታል።

Clientalism በነገሠበት ሀገር ሁሌም ደካማ መንግስት ይኖራል። ምክንያቱም የኢኮኖሚ ስርዓቱ ለበላይ ስልጣኑ በቀረቡ በጥቂቶች ብቻ የሚመራ የኢኮኖሚ ስርዓት በመሆኑ ሀገሪቱ በአንድ ወይም በሁለት ቁልፍ የኢኮኖሚ መሠረቶች ላይ ጥገኛ እንድትሆን ያደርጋታል። ይህንንም የልማት ሳይንሱ ምሁራን "enclave economy" ይሉታል። እንዲህ ያሉ ሀገሮች ወደ ውጭ ኤክስፖርት ተደርገው ወዲያው የውጭ ምንዛሬን ሊያስገኙ የሚችሉ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ለ«ታማኞቻቸው» ብቻ ያለነፃ ፉክክር፣ ወይም ለአሸናፊነት በተመቻቸ ደብዛዛ ፉክክር በቁጥጥር ስር እንዲያውሉት ያደርጋሉ።

እንዲህ ያለን የ«ልማት» አቅጣጫ የመረጡ ሀገሮች፣ በብሔራዊ ደረጃ ለሚያስፈልጓቸው ሌሎች ልማታዊ እንቅስቃሴዎች መደጎሚያ ምንም አማራጭ ስለሌላቸው ለውጭ ዕዳና ብድር የተጋለጡ ናቸው። እንዲህ ባሉ ሀገሮች የተዘረጋው የታክስ ስርዓትም፣ በተለይም የውጭ ምንዛሪን በሚያስገኙ ዘርፎች ላይ የሚኖረው አሠራር አድሎአዊ ከመሆኑም ባሻገር፣ ከጥብቅ እይታና ቁጥጥር ውጭ የሆነን «ያልተገባን ወይም ኢፍትሃዊ የሆነን የገቢ ምንጭ» ("Unearned income" ወይም "Rents") ስርዓት በተለጣፊነት ይዘረጋሉ።

በግርድፍ ከላይ ለማመልከት በተሞከረው መልኩ ቀለል ላለ ተግባራዊ ትንተና የሚረዱ ቁልፎችን ምሁራኑ ከሰጡ በኋላ፣ ጠቅለል ባለ መልኩ ለአፍሪካ አለመረጋጋት ዓይነተኛ ናቸው ያላቸውን ችግሮች ሲተነትኑ የሚከተሉትን ለአብነት ይጠቅሳሉ።

- Enclave Economy ለጥቂቶች የስርዓቱ አራማጆች ብቻ ተከፍቶ የተሰጠ የኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ ጥገኛ የሆነ ስርዓት መኖሩና የውጭ ዕርዳታ ከፍተኛ ጫና የሚሉት በዋነኛነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ምክንያቶች ሲሆኑ የቀሩት እንደየባህልና የኃይማኖት ግጭቶች፣ በዘርና በጎሣ ላይ የተመሠረቱ አለመግባባቶች (Ethnicity Problems) እና ደካማ የአስተዳደር ተቋማት መኖር የሚሉት ተደራቢ ምክንያቶች ናቸው ይላሉ።

በኢኮኖሚክስ የኖቬል ሽልማት ተሸላሚ የሆኑት ምሁር እንዳሉት «ያለዲሞክራሲና ሰብአዊ ነፃነት ሠላምና ልማት ከቶም የማይታሰቡ ጉዳዮች ናቸው» የአፍሪካም መሠረታዊ ችግር ዲሞክራሲን ለመተግበር የሚያስችሉ በግለሰቦች ነፃነት ዙሪያ የሚገኙ ቁልፍ ጉዳዮችን ለመንከባከብና ህዝባዊ ባህል ለማድረግ ቁርጠኝነት አለመታየቱ ነው።

ዲሞክራሲ፣ ልማትና ሰላምን በአግባቡ ለማራመድና ለመከወን ከፍተኛው መሣሪያ ከፍርሀትና ስጋት በነፃ መልኩ መወያየት መቻል ነው። በሌላ አባባል የዲያሎግን ባህል በስፋት በህዝብ ውስጥ ማስረፅ ነው። ይህ ደግሞ መልካም ባህል ሆኖ ሲቀር የአመራር ተቋማትን ለማረቅ፣ በስልጣን በመባለግ የልማትና የሰላም ትግልን የሚያደናቅፉትን በህዝባዊ የውይይት ባህል ቢቻል አሳምኖ ለመመለስና ወደተገቢው አቅጣጫ

ለማስቀየር፣ ካልሆነ ደግሞ ከብሔራዊ ህዝባዊ ማሳፈር (Public shaming) ባሻገር ወደ ግልፅ ተጠያቂነትና ወደ ፈጣን የፍትህ ዙፋን ለማቅረብ ርካሹና ፍቱን መድሀኒት ነው።

ለዚህም ነው በአፍሪካ ነግሦ የምናየው የPersonal Rule ወይም የ Clientalism ስርዓት ለህዝባዊ ውይይትና መቻቻል በተለይም ለዲያሎግ ቦታ የሌለው ነው። ምክንያቱም ዲያሎግ ለከፍተኛ ህዝባዊ ፖለቲካዊና ልማታዊ ተሳትፎ መሠረቱ ስለሆነ ነው።

የህዝባዊ ውይይት ባህል ግልፅ የሆነ የህግ ከለላ እንዲኖረው የህገመንግስታዊና የዘርፋዊ ህጎች መኖርን ይሻል። በመሆኑም አመኔታን ከህዝብ የሚያገኙ የመገናኛ ብዙሃን በስፋት መኖር፣ ምሁራን እምነታቸውንና ፅሑፎቻቸውን ለውይይት የሚያቀርቡባቸው የምርምርና የሲቪክ ማህበረሰባት መድረኮች በብዛት መቋቋማቸው፣ ወቅታዊና በእውነት ላይ የተመሠረቱ የመረጃና የውይይት ማሰራጫ ዘዴዎች ያለምንም ስጋትና ማዕቀብ በህግ በተፈቀደና በተከለለ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲሰራጩ የመረጃ ነፃነት ህግን ማውጣትና መተግበር የግድ ይላል።

ከላይ በግርድፉና በጠባቡ ከተመለከቱት የመመዘኛ ቁልፎች በመነሳት ኢትዮጵያ ዛሬ የምትገኝበትን የሰላምና የልማት ሁኔታ በጥቂቱ ለመመዘን የሚቻል ይመስላል። በመሆኑም በአቶ መድህኔ ታደሰ የተሰጠው ትንተና የኢትዮጵያንና የአካባቢዋን ሠላም መረጋጋት ለመመዘን የሚረዳ በቂ ማዕቀፍን እንደሰጠ ሁሉ የኢትዮጵያን የልማት ሁኔታ ለማየት ደግሞ እስካሁን የተነሱት ተጨማሪ ነጥቦች የመተንተኛ ቁልፎች ክፍተትን በመሙላት ያግዛሉ የሚል እምነት አለኝ።

የኢትዮጵያ ልማት ዘለቄታዊ እንዲሆንና መልክ እንዲይዝ፡-

G. መልካም አስተዳደር ሊነግስ የግድ ይላል፣
K. ተጠያቂነት ያለበት ነፃ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ሊዘረጋ ይገባዋል፣
N. ገደብ ያልተበጀበት፣ ከፍርሃት ነፃ የሆነ የመወያየት ባህል ሊዳብር ይገባዋል፣
S. የድህነት ጉዳይ በአፋጣኝ እንዲወገድ የልማት ስትራቴጂዎች በህዝቡ አእምሮ በባለአደራነት እንዲሠርፅና የዕለት በዕለት የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆኑ የግድ ይላል። ለዚህም ራስን በምግብ የመቻሉ ጥያቄ የቅርብ ግብ ሊሆንና አድሎአዊነት ያለበት የሀብት ክፍፍል መበላለጥን የመግታት አካሄድ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፣
W. ሰፊ የሆነ የስልጠና፣ የምርምርና የአካዳሚ ዕውቀት ስርጭት ቀና ፉክክርን በሚፈጥር መልኩ ያለአድልዖ በግሉም ሆነ በመንግስት የትምህርትና ምርምር ተቋማት ሊካሄድ ይገባዋል፣
ረ. የንግድና የልማት እንቅስቃሴው ብዙ ወጪን የሚጠይቅ እንዳይሆን የመሠረተ ልማት ግንባታና አቅርቦት የመነገጃ ፍሰትን የሚያረጋግጡ ገደብ የለሽ የፈጠራ የኢንተርኔት አገልግሎት የሌሎች የኮሙኒኬሽን ዘርፎች አገልግሎቶች በስፋት እንዲሰጡ፣ ተጠያቂነት ያለበት በግልፅና በፉክክር የሚገኝ የብድር አገልግሎቶች፣ ጎሠኝነት ወዘተ... ሊገታው የማይገባ የሰለጠነ የሰው ኃይልን ያልተገደበ ዝውውር ማረጋገጥ ለነገው የተሻለ የልማት አካሄዳችን ዛሬውኑ መሻሻል የሚደረግባቸው ጉዳዮች ናቸው፣

ሰ. በተናጠል የሚደረግ የልማት ዕድገት ከቶም ስለማይኖር በዓለም አቀፋዊው የኢኮኖሚና መረጃ ትስስር መረብ ውስጥ ለመግባት አስፈላጊ የሆኑ የፖሊሲና የህግ ለውጦችን በጥናት ላይ ተመርኩዞ በማከናወን የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ አራማጆች ክለብ ውስጥ መግባቱም ፋታ የማይሰጠው ጉዳይ ነው።

4. ልዩነታችን ውበታችን፣ ጥንካሬአችንና ለተደጋጋፊ ፈጣን ልማታችን ደግሞ ፅኑ መሠረታችን ነው

ብዙዎቻችን ለልማታችን አለመፍጠን ምክንያቱ፣ ተቋማዊና ህገመንግስታዊ ከለላ በመስጠት ጥርጥርና ስጋት ውስጥ የከተተን ልዩነታችንን ያጎላው ፖለቲካችን ነው እንላለን። ይህ አባባል እውነትን ሊያዝል የሚችለው ልዩነቱን ተቀብሎ፣ በፍቅርና በመቻቻል መንፈስ በጋራ መግባባት በተካለለ አብሮ የመኖር ማዕቀፍ ውስጥ ያለ አድልዖ እንዲሰራ ካልተገደደ ብቻ ነው።

የዓለማችን ተሞክሮ ልዩነትን ባግባቡ ባስተናገደ ስርዓት ውስጥ አንድነት፣ ጥንካሬና ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት እንደተመዘገበ ነው። ይህን በልዩነት ላይ የተመዘገበ የኢኮኖሚ ጥንካሬን ለማሳየት ሲሉ በቅርቡ John Barker የተባሉ ምሁር ባወጡት DVD የተመለከትኩት ዶክመንታሪ ፊልም ዛሬ ኢትዮጵያችን ለምትገኝበት ሁኔታ ጥሩ ምላሽን ያዘለ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ለጆን ባርከር በዕፅዋትና በእንስሳት የታየውን የልዩነት ስብጥር ከማህበረሰባዊው የልዩነት ስብጥር ጋር በማነፃፀር የደረሰባቸው ድምዳሜዎች አሉት። ለባርከር አንድ ወጥ ብቻ የሆነ ዝርያ ብዙነትን ሲያወግዝ፣ ዘርፈ ብዙ ዝርያ ያለበት ደግሞ ልዩነትን አወዳሽ ነው። ምክንያቱም ብዙነት ያለበት ልዩነት ፈጠራን የሚጋብዝ በመሆኑ ሐብትን ለመፍጠር ይቻለዋል። አንድ ወጥ ብቻ የሆነ የዕፅዋት ዝርያ በበሽታ ለመመታት በጣም የተጋለጠ ነው፣ አንድ ወጥ ዝርያ ብቻ መሆኑም ለፈጠራ የማይመች ነው። በመሆኑም ነው አንድ የሆነ ወጥነት (ልዩነት አልባ) በተመሳሳይነት ስለሚከበብ እስከመጥፋት የሚያደርሰው የመቆም (ያለማደግ፣ ያለመለወጥ) ደረጃ ላይ ይወጣል። ለዚህም በተጨባጭ ምሳሌነት ለህዝብ ያቀረቡት ማስረጃ የአየርላንድ ህዝብ አንድ ወጥ ዝርያ የነበረውን የድንች ተክል በብቸኛ ምግብነት በመጠቀም ለረጅም ጊዜ ይኖሩ ነበር። ይህ ሌላ ዝርያ የሌለውን ድንች አንድ በሽታ ስላጠቃው የአየርላንድ ህዝብ ለረሃብ በመጋለጡ ሀገሩን ትቶ ወደ ሰሜን አሜሪካ ለመሰደድ በቃ። በተመሳሳዩ ብዙ ልዩነት ያለባቸውን የድንች ዝርያዎች ይጠቀም የነበረው የላቲን አሜሪካ ህዝብ ባንድ ዘር ላይ የመጣውን የድንች በሽታ የሚቋቋም ተደጋጋፊነት ያለው የሌላ የድንች ዘር በመኖሩ ከአደጋ ሊተርፍ እንደቻለ በስዕላዊ መግለጫቸው አመላክተዋል።

ለዚህም ነው በብዝሀ ህይወት (Bio diversity) ውስጥ ብዙ ዓይነት ልዩ ልዩ ዕፅዋት፣ ውስብስብ የሆነ eco system፣ ግን ጤናማ ዝርያዎች፣ ብዙ ፍሬን የሚያፈሩ ውስብስብ ዝርያዎች ቢሆኑም ግን ዘለቄታዊ የቆይታ ዘመን ያላቸው የሚሆኑት።

ሀብት እንዲፈጠር መረጋጋት (ዘለቄታዊነት) ሊኖር ይገባል፣ የዘለቄታዊነት (sustainability) መኖር ደግሞ የተገማችነት (Predictability) ደረጃን ከፍ ከማድረጉም በላይ ምርታማነትንም ይጨምራል። ለዚህም ነው ልዩነት (Diversity) የተደጋጋፊነት (Mutualism) ምንጭ ነው የሚባለው።

ተደጋጋፊነት (mutualism) የነገሠበት ሥርዓት የዝርያው ከሌላው ጋር ተባብሮ የመስራት ባህል የዳበረበት ነው። ይህ በዕፅዋትና በእንስሳት የታየው ቀመርም በማህበረሰባዊ ተራክቦ ውስጥ የሚታይ ነው። ለምሳሌ ለሲንጋፖር የኢኮኖሚ ዕድገት ትልቁ ሚስጥሩ የአስተዳደር ስርዓቱ ሳይሆን በህዝቦቿ ልዩነት (Diversity) የተገነባው የተደጋጋፊነት ሚስጥር ነው። በሲንጋፖር ቻይኖች፣ ማሌይዞች፣ ህንዶች ወዘተ... በመኖራቸው የባህል ስብጥሩ ያለውን ልዩነት አመልካች ነው። በመሆኑም በሲንጋፖር ብዙ ዘር (ጎሣ)፣ ብዙ ቋንቋ፣ ብዙ ሃይማኖት ይገኛል። ይህን ልዩነት ግን ለጤናማ የመከባበርና የመቻቻል ስርዓት እንዲበለፅግ በመደረጉ ሲንጋፖር በአስገራሚ ሁኔታ ኢኮኖሚያዋ ያደገ ነው፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለአብነት የሚጠቀስ መንግስት መር የሆነን የትምህርት ስርዓትንም (Public Education) የምታራምድ ሀገር ነች።

ለዚህ መሠረቱ ሀሳብንና አመለካከትን በነፂነት የመግለፅ መብት ሲከበር በልዩነቱ ውስጥ የሚያብብ የባህል ስብጥር ሲወደስ፣ በልዩነት ውስጥ በቅን ፉክክር ላይ የተመሠረተ የምሁራን አስተያየት ሲደመጥ፣ በተደጋጋፊነት መርህ (Mutualism) ላይ የተገነባው ህብረተሰብ ልዩነቱን የሃብት ማመንጪያ ታላቅ አጋጣሚ ያደርገዋል። ለዚህም ነው የጆን ባርከን ትንተና ለሲንጋፖር በልማት የመበልፀግ ሚስጥር በህዝቦቿ ያለውን ነባራዊ የልዩነት ስብጥር (diversity) በተደጋጋፊነት ሥርዓት ላይ መገንባቷ ነው የሚለን። ከዚህም በመነሳት ጆን ባርከር የሚከተለውን ድምዳሜ ይሰጠናል፣ ልዩነት ፈጠራን (innovation) ይወልዳል፣ ፈጠራ ለሀብት (Wealth) መገኘት ምንጩ ነው። ውጤታማ ፈጠራ (አዲስ ግኝት) ደግሞ በሃብት ላይ አዲስ ሀብትን ይፈጥራል።

ዛሬ የዓለምን ኢኮኖሚ የተቆጣጠረችው አሜሪካ ለመበልፀግ ምክንያቷ በልዩነት የተሞላው የስደተኛ ሕዝቦቿ ተደጋጋፊነት ነው። የህዝቦቿ ልዩነት የፈጠራን በር በመክፈቱ የሀብት መፈጠርና መከማቸትን በሀገሪቷ ላይ አነገሠ።

ስለዚህም በኢኮኖሚው፣ በተፈጥሮ አካባቢው፣ በባህሉ፣ በቋንቋው፣ በዘር (ጎሣ) ወዘተ ዙሪያ የሚታይ ልዩነት ሀሳብን በነፂነት በመግለፅ ሥርዓት ከታጀበ፣ ልዩነት የሚያስረሳ በነፂነት ላይ በተመሠረተ የመወያየት ባህል እንዲመራ ከተደረገና ግልፅ ተጠያቂነት የተዘረጋበት ያልተማከለ የአስተዳደር ስርዓት እንዲነግስ ከተደረገ ሰላም የሰፈነበትንና ዘለቄታዊ ልማቷን ግቧ ያደረገች ሀገር መመስረት ይችላል።

ማጠቃለያ

እስካሁን ያለፈችበትን የህይወት ውጣ ውረድ ከግምት በማስገባት፣ የተሻለችውን ኢትዮጵያን ነገ ማየት እንድንችል የዛሬው መነፅራችን የሚከተሉትን ነጥቦች በታሳቢነት ቢይዝ መልካም ነው እላለሁ፣

G. ህገመንግስታዊነትን ያከበረ ሥርዓት ለመገንባት ከህገመንግስት በታች መሆን የግድ ይላል። ሁላችንም ከህገመንግስቱ በታች ነን፣ ህጉ ግን እኛ ተስማምተን ያልነው ነው። ለዝርዝር አፈፃፀሙም ተስማምተን በመደበኛ ህግጋት እንተነትነዋለን። በዚህም ተቋማት እንፈጥራለን። በሂደትም ያ አንድ ህገመንግስት የተሟላ የአስተዳደር ቅርፅን ይሰጠናል። ከዚህ አንፃር በሀገራችን የምናየውን ልዩነት ወደተከበረ ተደጋጋፊነት እንዲያመጣልን ያስቀመጥነው ህገመንግስት ከላይ በስፋት የተነተንናቸውን

ጭብጦች በመርህ ደረጃ የሚያፈርስ ሆኖ ባላገኘውም፣ አሊያም እጅጉን በዘገየና ባዘገመ አፈፃፀም፣ ወይም በተበላሸ የአፈፃፀም አስተዳደር ምክንያት ልዩነቱን ባከበረ ቅን ፉክክር ላይ የተመሠረተ የፈጠራም ባህል አልገነባንም። በመሆኑም ዛሬ ልናይ የሚገባንን ሀብት አልፈጠርንም። ይሁን እንጂ ይህን ለመከወን የሚያስችለን የህገመንግስት መሠረት ተጥሏል፣ ቢዘገዩም ጠቀሜታ ያላቸው የመደበኛ ህግጋትና የተቋማት ፈጠራና ግንባታ መሠረት ተጥሏል፣ በሚቀረው ሃሳብንና ልዩነትን በነፃነት መግለፅ ወደሚያስችል ከፍርሀት የነፃን የመወያያት ባህል መገንባቱን አሁኑኑ እንጀምር።

K. የፖለቲካ ፉክክር ጠበኝነት ሊሆን አይገባውም። ጠበኝነት ደግሞ የቂመኛነት የበኩር ልጅ ነውና ለተሸለ ሰላምና ልማት የፖለቲካ ፉክክሮች ሁሉ ልዩነትን ለማስተናገድ ሲባል ፖለቲከኞች በሀሳብ ደረጃ ለህዝብ የሚያቀርቧቸው የአመራር ጥበቦች (Art of Administration) ናቸው። በመሆኑም ለህዝብ ውሳኔ የሚቀርቡ የፖለቲካ ክርክሮች ከቂመኝነትና ከጠበኝነት የሚነፁት ከፍርሃትና ከስጋት ነፃ በሆነ መልኩ በተለያዩ መድረኮች ህዝብ በነፃነት እንዲተችባቸው ሲደረግ ብቻ ነው።

N. ህገመንግስታዊነት የሂደት ውጤት ነው። በተለይም ለፌደራል ሥርዓት የህገመንግስታዊነት ጉዳይ የነላ ስፍራ አለውና ሕዝብን በስፋት የማስተማሩ ስራ የሲቪክ ማህበረሰባቱም የነላ ድርሻ ሊሆን ይገባዋል። በመሆኑም በዲሞክራሲ፣ በሰብዓዊ መብቶች፣ በመልካም አስተዳደር፣ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በማስወገድ፣ በፆታ ነክና በወጣቶች ተሳትፎ ዙሪያ ህዝብን በህገመንግስቱ የከለላና የማዕቀፍ መርህ ውስጥ በስፋት የሚያስተምሩ የሲቪክ ማህበረሰባት እንዲበዙ፣ እንዲጠነክሩና በተፎካካሪነት የተመሠረተን የጥራት አገልግሎት እንዲያበረክቱ መንግስት እገዛን የሚሠጥ፣ የህግ ከለላን የሚያበረክት፣ በፖሊሲም የሚደገፍ ሊሆን ይገባል።

S. ልዩነት በጎላበት ሆኖም ግን ተደጋጋፊነት መርሁ እንዲሆን በፈቀደ የፌደራል ስርዓት ውስጥ ስለምንገኝ የጋራ ራዕያችን በሆኑ ጉዳዮች ላይ አብዛኛውን ጊዜያችንን ካላተኮርን የነገው የተሻለ ሰላማችንና ልማታችን እየራቀን ይሄዳልና የጋራ አጀንዳዎች በስፋት የሚያወያይ፣ ለመፍትሔም የሚሆኑ ምላሾችን የሚፈጥር ማህበረሰብን የመገንባት ዕዳ አለብን።

W. የተረጋጋች ኢትዮጵያን ለትውልድ ማስተላለፍ እንድንችል በእልህ፣ በራስ ወዳድነትና በእኔነት መንፈስ ፓርቲዎችንም ሆነ ሌሎች ማህበረሰባዊ መሰባሰቦችን ከመምራት መታቀቡ በናፍቆት የምንጠብቀው የነገው ሰላምና ልማት እውን እንዲሆን እርግጠኞች ያደርገናል።

ረ. ዓለም እየተጓዘበት ያለው የዕድገት ባቡር እጅጉን ፈጣን ነውና በስራችንና በውሳኔዎቻችን ሁሉ ጊዜና ህዝብ ተኮር እንድንሆን የግድ ይላል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥና የካርቦን ንግድ በኢትዮጵያ[1]

ደስአለኝ መስፍን[2]

1. አጠቃላይ

የአየር ንብረት ለውጥ በተፈጥሮም አለ። የከባቢ አየርም ባዕድ ነገሮችን ተቀብሎ ጉዳት አልባ የማድረግና የመሸከም አቅም አለው። ይህም ከአዳዲስ ክስተቶች ጋር እራሱን አላምዶ ለመቀጠል አስችሎታል። ከባዕድ ነገሮች ለሚከተልበት ጉዳት ቅፅበታዊ ምላሽ የመስጠት አቅም ግን የለውም። ምላሽ ለመስጠት ከሚችልበት ደረጃ እስኪደርስ ጊዜ ይወስዳል። የአሁኑ የአየር ንብረት ለውጥ ግን የተለዬ ነው። የግሪንሃውስ ጋዞች ወይም የበካይ ጋዝ ልቀት ሙሉ በሙሉ ዛሬውኑ ቢቆም እንኳን የዓለም መሞቅ ይቀጥላል። ምክንያቱም አዝጋሚውን ተፈጥሮአዊ የአየር ንብረት የለውጥ ሂደት የሰው ጣልቃ ገብነት አፋጥኖታል። የአየር ንብረት ለውጥ የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ የተጀመረው ደግሞ ችግሩ ከተንሰራፋ በኋላ ነው። ስለዚህ የጥረቱ ውጤትም የሚታየው ከዓመታት በኋላ ይሆናል። ይህ ደግሞ ትውልድ ተሻጋሪ ተፅዕኖ አስከትሏል።

የበለፀጉ አገሮች በተገበሩት የተሳሳተ የልማት አቅጣጫ የከባቢ አየር ተበክሏል። ከመሸከም አቅሙ በላይ በጨመሩበት በካይ ነገርም የከባቢ አየር ጤናማነቱ ተዛብቷል።

ማንም አዳጊ አገር የበለፀጉት ከመበልፀጋቸው በፊት የተከተሉትን ተከትሎ የማደግ ዕድሉ ጠቧል። አዳጊዎች እንደበለፀጉቱ በካይ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር እየለቀቅን መልማት አይቻለንም። ምክንያቱም የከባቢ አየር ሥርዓተ መህዳር በካይ ነገሮችን ተቀብሎ ጉዳት አልባ የማድረግ አቅሙ ከኢንዱስትሪ አብዮት አንስቶ በተቀበለው የበካይ ጋዝ ምክንያት ተናግቷል። ይህ የአቅም ጉድለት ተጨማሪ በካይ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር የሚገባበትን ስፍራ አጥቦታል። ስለዚህ የበለፀጉ አገሮች የፈፀሙትን ታሪካዊ ስህተት የመድገም አዋጪነት ኢምንት ነው።

2. የአየር ንብረት ለውጥን በሚመለከት የተለያዩ ቡድኖች ስጋት

[1] ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የተካሄደ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡፡

[2] አቶ ደሳለኝ መስፍን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሕግ ሙያ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በአካባቢ ጥበቃና ልማት አግኝተዋል። አቶ ደሳለኝ መስፍን በአሁኑ ሰዓት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ም/ዋና ዳይሬክተር ሲሆኑ ኢትዮጵያን ወክለው በተለያዩ አለም አቀፍ ኮሚ|ዎች ውስጥ በሰብሳቢነትና በአባልነት አገልግለዋል በማገልገልም ላይ ይገኛሉ። አቶ ደሳለኝ መስፍን በአካባቢ ጥበቃና ልማት ዙሪያ በርካታ ጹሑፎችን የጻፉና ያቀረቡ ናቸው።

የነዳጅ ዘይት አምራች አገሮች ስጋት ነዳጅ የከባቢ አየር ብክለት የሚያስከትል በካይ ጋዝ ያመነጫል። በጥቅም ላይ መዋሉ ቢከለከል ወይም ደግሞ ነዳጅን የሚተካ ሌላ የሃይል ምንጭ በስራ ላይ ቢውል ያሰጋቸዋል። ምክንያቱም ለእነሱ ነዳጅ የኢኮኖሚያቸው መሰረት ነው።

የበለፀጉ አገራት ስጋት የበካይ ጋዝ የሚያመነጭ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴ እንዳይካሄድ የተከለከለ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም ወደ ንፁህ ልማት መቀየር የሚያስከትለው ወጪ ከፍተኛ ስለሚሆን ስራቸውን የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ኢንዱስትሪዎች ስራቸውን ለሚቋረጥ ሊገደዱ ይችላል።

ከአዳጊ አገሮች የመነጨና ለአሁኑ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚሆን የበካይ ጋዝ መጠን ከቁጥር አይገባም። ይልቁንም በተፈጥሮ ሃብት ላይ በቀጥታ ህይወቱ ለተመሰረተው፣ በቂ የመሰረተ ልማት አውታር ለሌለው፣ ደካማ ማህበራዊና የሰው ካፒታል ላለው ስለዚህም የድሃ አገር ህዝብና አካባቢ በአየር ንብረት ለውጥ ይበልጥ ተጎጂ ነው።

በአየር ንብረት መዋዠቅ የስርዓተ መህድር አቅም ይደክማል። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በተከተለ ድርቅ፣ ጎርፍ እና ሙቀት የውሃ ሃብት፣ ግብርና፣ ደን፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ የሃይል አቅርቦት፣ የሰውና የእንሰሳ ጤና፣ ሌሎች ለህይወትና ለብልፅግና የሚያስፈልጉ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ የአካባቢ ሃብቶች ይጎዳሉ። ስለዚህ አዳጊ አገሮች ባልፈፀምነው ጥፋት መጎዳት የለብንም። በካይ ጋዝ የሚያመነጩቱ ስህተታቸውን ማረም አለባቸው። የሌሎችን በካይ ለመምጠጥ ብለን ደግሞ ድህነትን ለማጥፋትና ለመልማት የምናካሂደውን እንቅስቃሴ መግታት አይጠበቅንም ይላሉ። ከአዳጊ አገሮች መካከል ትናንሽ ደሴቶችን የባህር ከፍታ በመጨመሩ ሊሰምጡ ይችላሉ። እንደ ዓለም ባንክ ግምት የባህር ከፍታ በ 1 ሜትር ቢያድግ 56 ሚሊዮን ህዝብ ለአደጋ ተጋላጭ ይሆናል። ስለዚህ የእነርሱ ጥያቄ የመኖራቸውን ቀጣይነት ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው። የስካንዲኔቪያን አገሮችና አውሮፓውያን ደግሞ የአዳጊ አገሮችንና የትናንሽ ደሴቶችን ስጋት ይጋራሉ። የአየር ንብረት ለውጡ እንዲስተካከልም የማያወላውል አቋም አሏቸው።

የአየር ንብረት ለውጥን በሚመለከት የተካሄደውም ድርድር እነዚህን ቡድኖች ያካተተ ነበር።

5. የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ የማዕቀፍ ኮንቬንሽን

የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ኮንቬንሽን በ1992 ወጥቷል። ይህ ኮንቬንሽን በባህሪይው ማዕቀፋዊ ነው። ከፖሊሲ ሰነድ እምብዛም አይለይም። የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን እንዲቀነስ ከማመቻቸት ያለፈ ይዘት የለውም። በኮንቬንሽኑ ድንጋጌ መሰረት የከባቢ አየርን ደህንነት መጠበቅ የጋራ ጉዳይ ነው። የከባቢ አየር ጤናማ ተስተጋብሮት መዛነፍም የጋራ ችግር ነው። ቀዳሚ ሃላፊነቱም የከባቢ አየር በካይ አገሮች ነው። የአየር ንብረት ለውጥ በድንበር አይከለልም። በሁሉም አገሮች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል። የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር የባህርን ጠለል፣ የበረዶን ክምችትና የዝናብን ወቅት የሚመለከቱ ሁኔታዎች ማናጋቱ ግልፅ ሆኗል። የከባቢ አየር በካይ ልቀት ተቀባይነት እስካለው ደረጃ ዝቅ

ካላለ የውሃ አቅርቦት ይቀንሳል፣ የምግብ እጥረት ይከተላል። የህይወታዊ ሃብቶች ለጥፋት ይዳርጋሉ። የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦችን ስደተኛ ያደርጋል፣ ለህልፈትም ይዳርጋል።

የአየር ንብረት ለውጥን ማቆም ከአቅም በላይ ሆኗል። ስለዚህ ለውጥን መላመድ ለማንም አገርና ሕዝብ አስፈላጊ ነው። በበለፀጉት አገሮች ዘንድ ግን ለውጡን ለመመከት የሚያስችል የተቋም፣ የቴክኖሎጂና የፋይናንስ አቅም ደርጅቷል። አቅሙ የጎደለው ከአዳጊ አገሮች ዘንድ ነው። የሚገነባው ደግሞ ድህነትን በአካባቢ እንክብካቤ ላይ በተመሰረተ ልማት በማጥፋት ነው። ይህ ድህነትን የማጥፋት ጥረት ቁጥሩ እያደገ ያለውን የህዝብ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሆን ይጠበቃል።

በዚህም መሰረት በ2030 ዓ.ም የዓለም ከባቢ አየር ሙቀትን ለማስተካከል ከሚካሄደው ጥረት ጋር የተገናዘበ ልማት በአዳጊ አገሮች ለማካሄድ ከ200 እስከ 210 ቢሊዮን ዶላር መመደብ አለበት። ለአዳጊ አገሮች የአየር ንብረት ለውጥ የመልመጃ አቅም መገንቢያ ከ28 እስከ 67 ቢሊዮን ዶላር ያስፈልጋል። እንደ ኦክስፋም ግምት ከሆነ ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥን ለመላመድ አዳጊ አገሮች 50 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በየዓመቱ መመደብ አለባቸው። ይህን ወጪ የመሸፈኑ ሃላፊነት የበለፀጉት አገሮች ነው።

6. ከአየር ንብረት ለውጥ በአገራችን የሚከተሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች

ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ባንሆንም ለውጡን የሚያስከትሉ በካይ ጋዞችን የሚያመነጩ አገሮች እርምጃ እንዲወስዱ የሞራል ግፊት ማድረግ አገራዊ አቋማችን ስለመሆኑ በኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ ተብራርቷል። ከአየር መዛባት የተከተለ ድርቅ በተደጋጋሚ ጥቃት አድርሶብናል። በዚሁ ምክንያት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ተርበዋል፣ ሞተዋል። ወንዞቻችንም ሆኑ የዕፅዋት ሽፋኖች በዚሁ ችግር ተጠቅተዋል። ወንዞቻችን በመጠን እየቀነሱም ብቻ ሳይሆን የምንጮች መድረቅም ተከስቷል። በአጠቃላዩ በገንዘብ አስልቼ ማሳየት ባልችልም በኢትዮጵያ ላይ የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው።

4.1 በግብርናው መስክ፣

ተደጋጋሚ የወቅት መዛባት፣ የአየር ሙቀት መጨመርና የክስተቱ መራዘም በግብርና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል። የክረምትና የመኸር ወቅት መግቢያና መውጫ ሲቀያየር ምርት ይቀንሳል። ይህንኑ ተከትሎ ድርቅ ይከሰታል። የተከተለን ጉዳት እንደነበር ለመመለስ ወይም ተፅዕኖውን ለማቃለል ደግሞ ሃብት ይጠይቃል። ይህ ደግሞ ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለመንገድ፣ ለውሃ አቅርቦት የመሳሰሉ ተግባራት የተመደበውን ስለሚያስቀንስ የአገር ሃብት ድንገት ለመጣ አደጋ ማስተካከያ ይውላል።

4.2. በኢንዱስትሪው መስክ፣

የአየር ንብረት ለውጥ ለምሳሌ፤ በውሃ ሃብት ላይ በሚያስከትለው ጉዳት የሃይል ማመንጫዎች አቅም ይዳከማል። የኤሌክትሪክ ሃይል የማመንጨት አቅም በመዳከሙ የሚከተለው መናጋት ከዕለት ጉርስ

እጥረት እስከ ድርጅት መዘጋት ይዘልቃል። ውሃን በብዛት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች፤ ለምሳሌ የጨርቃ ጨርቅንና የቆዳ ፋብሪካን የመሰሉት በሰው ጉልበት በስፋት ይጠቀማሉ። በተባሉት ፋብሪካዎች ዘንድ የውሃ እጥረት ከተከሰለ አትራፊነታቸው ይናጋል። ሰራተኛም ይቀንሳል። ይህ ደግሞ ሥራ የመፍጠር ጥረትንና የአገር ውስጥ የገቢን መሰረት ያሳንሳል።

4.3. የበሽታ አምጪ ተህዋሲያን መብዛት፣

የአየር መዛባት ለንዳድ ወይም ለወባ ትንኝ የመፀናወት አቅም ይፈጥራል። ፡ የሙቀት መጨመር ለበሽታ አምጪ ተህዋስያን ምቹ የመራቢያ ሁኔታ ያበጃል። የበሽታ አዛማቾች መፈልፈልም ሆነ ዕድሜ በሙቀትና በወበቅ ላይ የተመሰረተ ነው። ተላላፊ ወረርሽኞች የሚገኑትም ሆነ የሚደክሙት እንደ ወቅቱ ምቹ መሆን ወይም ያለመሆን ነው። ከጎርፍ በሚከተል የውሃ መበከል ህዝብን ለውሃ ወለድ በሽታ ይዳረጋል። በዚህ ክስተት ጤንነቱ የተጎዳ የማምረት አቅሙ ይገደባል። የጤናን ቀውስ ለማከም የሚወጣ ወጪ ደግሞ በግለሰብ፣ በቤተሰበና በአገር ደረጃ ጥሪት የማካበት አቅምን ይጎዳል።

4.4. የግጦሽ መሬት መጎሳቆል፣

ከብት አርቢው ማህበረሰበ ለእንስሳቱ ሳርና ውሃ ለማቅረብ እንዲያስችለው ከአንድ ስፋራ ወደ ሌላ ይዘዋወራል። የዝውውሩ መሰረት ትኩት የሄደው ሥፍራ አገግሞ ይቆየኛል ብሎ ነው። በወቅት መዛባት ምክንያት ያገግማል የተባለው የግጦሽ መሬት ሳያገግም ሲቀር ሰውም እንስሳቱም ከአደጋ ይወድቃሉ። የዚህ ችግር ውጤት በመኖ አቅርቦት አይወሰንም። የእንስሳት ሃብቱን ለጥፋት ያጋልጣል። የእንስሳ የገበያ ዋጋ ይዛነፋል። የዋጋ መዛነፉም ክልል ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል ይችላል። በውስን የተፈጥሮ ሃብት ላይ ሽሚያ ከተፈጠረ ማህበራዊ ቀውስ ሊከተል ይችላል።

4.5 የሰው ጤናና የአደጋ ተጋላጭነት፣

ጎርፍ የውሃ ማስተላለፊያ፣ የቆሻሻ ማስወገጃ ወይም ሌላ የመሰረተ ልማት አውታር ያበላሻል። በጎርፍ የታጠበ ጎጂ ኬሚካልም ሆነ ሌላ በሽታ አምጪ፤ ለምሳሌ፤ ከቆሻሻ ማከማቻ ስፍራ ወይም ማስወገጃ ስፍራ በቀጥታ በዚሁ ገብቶ በህዝብ ጤና ላይ አደጋ ያስከትላል። በድርቅ ወይም በጎርፍ ምክንያት ቤት የፈረሰባቸው መልሰው እስኪቋቋሙ በአንድ መጠለያ ተፋፍገው ይሰፍራሉ። ሰውም፣ እንስሳቱም ሆኑ ሌሎች እንቅስቃሴዎች በውስን የውሃ ምንጭ ሲያተኩሩ የውሃ ምንጩ ለብክለትና ለውሃ ወለድ በሽታ ይጋለጣል። በሌላ በኩል የአንድ ወቅት ተጋላጭነት ሳይስተካከል ሌላ የመጋለጥ አደጋ ሊከተል ይችላል። በዚህ ክስተት ከመጀመሪያው ይልቅ ከሚቀጥለው ተጋላጭነት የሚከተል ጉዳት ይብሳል። በጎርፍ ቤቱ የፈረሰበት ሰው አማራጭ በመጥፋቱ ወይም በአቅም ዕጦት ከዚያው ስፍራ ቤቱን ጠግኖ መኖር ከቀጠለና ተመሳሳይ ጎርፍ ከተከሰተ፤ ተጋላጩ ከመጀመሪያው ይልቅ በቀጣዩ ክስተት የበለጠ ይጎዳል።

4.6. የተፈጥሮ ሃብቶች በጎ ሁኔታ መጎሳቆል፣

በአየር መዛባት በሚከተል ጎርፍና ነፋስ አፈር ይከላል። ለምነቱም ይቆረቁዝና ጠቃሚ አገልግሎት የማበርከት አቅሙ ይደክማል። ይህ ይበልጥ ጉዳይ የሚያስከትለው ለበረሃማነት በተጋለጡ የአገራችን መሬቶች ላይ ነው። በኢትዮጵያ የእነዚህ መሬቶች ስርጭት ሰፊ ነው። በዝናብ ወቅት መዛባት የውሃ እጥረት ይከተላል። የውሃ ውስጥ ህይወታዊ ሃብትም በመጠንና በጥራት ያሽቆለቁላል። ለምሳሌ ውሃ ሲቀንስ የዓሳ ሃብት ከአደጋ ላይ ይወድቃል። ይህ ደግሞ ርካሽ የፕሮቲን ምንጭ የሆነውንና አብላጫው ህዝብ እራሱ አስግሮ ወይም በቀላል ወጪ የሚያገኘውን የምግብ ምንጩን ያሳጣዋል። የአየር ንብረት የበለጠ የሚያጠቃው በቀላሉ የሚጎዳ መሬትን ነው። በዝናብ ወቅት መዛባት ወይም በሙቀት መጨመር በሚከተል ትነት በውሃ አዘል መሬት ላይ የውሃ እጥረት ሊከተል ይችላል። የውሃ አዘል መሬት መጎሳቆል የቤት ክዳን ሳር፣ በበጋ ወቅት የከብት መኖ መገኛ፣ የአዕዋፍ መራቢያ ወይም መቆያ ስፍራን፤ የቱሪስት መስህብን ጭምር ይጎዳል።

የዕፀዋት ሽፋን ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በቀጥታ ይገናኛል። የአየር ንብረት ለውጥ በህይወታዊ ሃብት ላይ የሚያስከትለውን ዓይነት ጉዳት የህይወታዊ ሃብትም ጥፋት የአየር ንብረትን ያዛባል። በአካባቢ አደጋ የእንስሳትና የዕፀዋት መኖሪያ ይጎሳቆላል። በጎርፍና በሙቀት ሰውም ሆነ እንሰሳ ካሉበት ስፍራ ይሰደዳሉ። አንዳንዶቹ ካሉበት ሥፍራ ቢቆዩም ቁጥራቸው ይቀንሳል። በተራራማ ሥፍራ ላይ ያሉት ግን የሚሰደዱበት ተስማሚ ስፍራ ማግኘታቸው አጠራጣሪ ነው።

5. የንፁህ የልማት ዘዴ /Clean Development Mechanism/

የበለፀጉ አገሮች በ2000 የበካይ ልቀታቸውን 1990 ወደ ነበረው የልቀት ልክ ዝቅ እንዲያደርጉ ኮንቬንሽኑ ደነገገ። ይህ ድንጋጌ ውጤት ሊያመጣ አልቻለም። ስለዚህ በኪዮቶ ፕሮቶኮል በግዴታ የሚሰራበት የልቀት ማስቀነሻ ድንጋጌ ወጣ። የኪዮቶ ፕሮቶኮል በ2005 ዓ.ም ፀደቀ። ፕሮቶኮሉ የበለፀጉ አገሮችን ኃላፊነት ይደነግጋል። ታዳጊ አገሮችም የከባቢ አየር በካይ ጋዝ ልቀት የማያመነጭ ልማት እንዲከተሉ ያበረታታል። በዚህም መሰረት ከ2008 እስከ 2012 ባሉት ጊዜያት የበለፀጉ አገሮች 1990 ከነበረው የልቀታቸው ልክ ላይ በአማካይ 5 በመቶ እንዲቀንስ ፕሮቶኮሉ ደንግጓል። ይህንንም ድንጋጌ ለማስፈፀም 3 ዘዴዎች በፕሮቶኮሉ ተካተዋል። እነዚህም የልቀት ንግድ፣ የጋራ ትግበራ እና ንፁህ የልማት ዘዴ እየተባሉ ይጠራሉ። በካይ ኩባንያዎች ልቀታቸውን ባለአስተኛ ወጪ እንዲቀንሱ እነዚህ ዘዴዎች ያግዟቸዋል። የጋራ ትግበራ እና የንፁህ የልማት ዘዴ የሚተገበሩት በቅድሚያ ፕሮጀክት ተዘጋጅቶ ነው። የጋራ ትግበራ የመልከዓ ምድር የተፈፃሚነት ወሰኑ በምስራቅ አውሮፓና በሩሲያ ምድር ነው። የንፁህ የልማት ዘዴ ደግሞ በአዳጊ አገሮች ዘንድ ነው።

5.1 የንፁህ የልማት ዘዴ ተቋማዊ አጠቃላይ ሁኔታ፣

በሰባተኛው የኮንቬንሽኑ አባል አገራት በፀደቀው የማራክሽ አኮርድ የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት ተፈላጊ ሁኔታዎች ተዘርዝረዋል። የፕሮጀክቶቹን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ገለልተኛ አካልም ተሰይሟል። ይህም ዴዚግኔትድ ኦፐሬሺናል ኤንቲቲ እየተባለ ይጠራል። ይህ አካል ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው ፕሮጀክት እንዲፀድቅ የውሳኔ ሃሳቡን በአባል አገራቱ ለተቋቋመው ኤክሲኪዩቲቭ ቦርድ ያቀርባል። በቀረበው ሃሳብ

ላይ ቦርዱ ውሳኔ ይሰጣል። የንፁህ የልማት ዘዴ በገበያ ስርዓት ይመራል። የሰብዓዊ ዕርዳታ አካል አይደለም። በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ውድድር አለበት። ስለዚህ በንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክቶች ዝግጅትና ትግበራ የተለያዩ ስጋቶች አሉ። የተዘጋጀ ፕሮጀክት ሊፀድቅም ላይፀድቅም ይችላል። ለምሳሌ፤ በብሔራዊ ደረጃ ከሚመለከተው አካል በፕሮጀክቱ ትግበራ ላይ ተቃውም የሌለ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ላይሰጥ ይችላል። በመረጃ እጥረት ምክንያት የኤክዚክዩቲቭ ቦርዱ ፕሮጀክቱን ላያፀድቀው ይችላል። ፕሮጀክቱ ሲገመገም ከነአካቴውም ሊወድቅ ይችላል። በክትትልና ግምገማ ወቅት በመጀመሪያ ተሰልቶ የነበረው የካርቦን ክሬዲት መጠን ዝቅ ሊል ይችላል።

5.2 የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት የዝግጅት ሂደት አጠቃላይ ሁኔታ፣

አንድ የበለፀገ አገር ኩባንያ ወይም መንግሥት የበካይ ጋዝ ልቀቱን ለማካካስ በአዳጊ አገር የሚተገበር ፕሮጀክት ከመንግሥት፣ ከግል ወይም ህጋዊ ዕውቅና ካላቸው ማህበረሰቦች ሊገዛ ይስማማል። ይህ ፕሮጀክት ባይኖርና የተለመደው አሰራር ቢቀጥል ሊከተል የሚችለው የከባቢ አየር በካይ ልቀት መጠን ይሰላል። የበለፀገው አገር ኩባንያ ወይም መንግሥት ይህንኑ የልቀት መጠን ይገዛል። ይህም ወደ ከባቢ አየር እንዳይገባ ወይም ደግሞ ከከባቢ አየር ተመጥጦ የተቀነሰ የበካይ ጋዝ መጠን ለገዢው ብክለቱን እንደቀነሰ ተቆጥሮ ይመዘገብለታል። ለምሳሌ አንድ የአሜሪካ ኩባንያ አሜሪካ እንድትቀንስ የሚጠበቅባትን የልቀት መጠን ለማሟላት ይፈልጋል። ይህም ኩባንያ እዚያው በአገሩ እያካሄደ ባለው ፋብሪካ ውስጥ ቴክኖሎጂ ጨምሮ ወይም የአሰራር ዘዴውን አሻሽሎ የሚለቀውን በካይ ለመቀነስ አልተቻለውም።

በኢትዮጵያ ዘንድ ደግሞ ከህይወታዊ ሃብት ነዳጅ የሚያለማ ፋብሪካ እንዲተከል ሃሳብ ቢኖርም በገንዘብ ዕጥረት ምክንያት ተፈፃሚ ሊሆን አልቻለም።

ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ፋብሪካዎች የከባቢ አየር በሚበክል የድንጋይ ከሰል ለመጠቀም ተገደዋል። ፋብሪካው በኢትዮጵያ ቢተከል የድንጋይ ከሰልን መሰረት ያደረገ የኢትዮጵያ ፋብሪካ በንፁህ የሃይል ምንጭ መጠቀም ይችላል። ይህ ሲሆን ከኢትዮጵያ መንጭቶ የከባቢ አየር ብክለትን የሚያባብስ ልቀት ይወገዳል። ይህም የተወገደው መጠን ተሰልቶ ለአሜሪካው ኩባንያ ይሸጥለታል። በገንዘቡም የታቀደው ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ምድር ሊተገበር ይችላል። ለአሜሪካ ደግሞ ይህ አስተዋፅዖ በአገሯ ከሚለቀቀው የበካይ ልቀት መጠን ላይ ይቀነስላታል።

5.3 የፕሮጀክት ዲዛይን ዶክዩመንት ዝግጅት

የፕሮጀክት ዲዛይን ዶክዩመንት በሻጩ መዘጋጀት አለበት። በፕሮጀክቱ ላይ የሻጭ አገር ሕግ በሚፈቅደው መሰረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መካሄድ አለበት። ይህ ሰነድ ማብራራት ከሚጠበቅበት ጉዳዮች አንዱ ፕሮጀክቱ ባይኖርና የተለመደው አሰራር ቢቀጥል የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ምን ይሆን ነበር የሚለውን ነው። በዚህም መልክ ፕሮጀክቱ ያካካሰው የበካይ ጋዝ ልቀት ተሰልቶ ይሸጣል። ከፕሮጀክቱ ትግበራ በፊት የነበረውን ሁኔታ የሚገለፀው እንዲሁም በፀደቀ ፕሮጀክት ላይ ክትትልና

ግምገማ የሚካሄደው የኤክሲክዩቲቭ ቦርድ ባፀደቀው የአሰራር ዘዴ መሰረት ነው። ይህም ቢሆን ሌላ የአሰራር ዘዴ ባለፕሮጀክቱ ማዘጋጀት ይችላል። ተቀባይነት የሚኖረው ግን የተባለው የአሰራር ዘዴ በኤክዝኪዩቲቭ ቦርድ ተገምግሞ ከፀደቀ ነው።

5.4 የተሳታፊ አገሮች ማረጋገጫ

በንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት ተሳትፎ በውዴታ ስለመሆኑ የሻጭና የገዢ አገሮች የሚመለከታቸው አካላት ማረጋገጫ መስጠት አለባቸው። የሻጭ አገር መንግሥት ግን ፕሮጀክቱ የአገሩን የዘላቂ ልማት ዕቅድና ጥረት እንደሚያራምድ የፅሁፍ ማረጋገጫ መስጠት አለበት። ፕሮጀክቱ በኮንሼንሽኑ ድረ ገፅ ላይ ወጥቶ አስተያየት ይሰባሰባል። የፕሮጀክት ሰነዱን ይዘትና በፕሮጀክቱ ይዘት ላይ የተሰጠ የሕዝብ አስተያየት በማገናዘብ አፅዳቂው አካል ውሳኔ ይሰጣል። ፕሮጅክቱ ተቀባይነት ካገኘ በኤክዚኪዩቲቭ ቦርድ ይመዘገባል። የማረጋገጫ የምስክር ወረቀትም ለፕሮጀክቱ ባለቤቶች ይሰጣል። የተቀነሰው የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንም ይፋ ይሆናል።

6. የንፁህ የልማት ዘዴ ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ

በአገራችን ከንፁህ የልማት ዘዴ ሊጠቀሙ የሚችሉ ፋብሪካዎች፣ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ የእርሻ ልማቶች፣ በደህና ሁኔታ ላይ ያሉ ደኖች፣ የተጎሳቆሉ የደን መሬቶች፣ እንክብካቤ የሚሹ ጥብቅ ስፍራዎችና የዕፀዋት ሽፋናቸውን የተገፈፉ ባዶ መሬቶች አሉ። ከሕይወታዊ ሃብት የሃይል ፍላጎትን የሚያሟላ ነዳጅም በአገር ውስጥ ሊመረት ይችላል። ይህም በየወቅቱ ዋጋው የሚጨምረውን በካዩ ነዳጅ የሚያስከትልብንን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ሊያስቀርልን ይችላል። ከከተማ ቆሻሻ የኤሌክትሪክ ሃይልን አመንጭቶ ማከፋፈል ይቻላል። የኬሚካል ማዳበሪያ የፔትሮኬሚካል ውጤት ስለሆነ እንደ ፔትሮሊየሙ ዋጋው ያሻቅባል። በኬሚካሉ ምትክ በተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀም ደግሞ የከባቢ አየር ብክለትን ብቻ ሳይሆን ለአገራችን አርሶ አደር ወጪ ይቀንሳል። በንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት አማካኝነት ይህ አስተዋፅዖ ለካርቦን ንግድ ቢቀርብ ለአገራችን አዲስ የገንዘብ ምንጭ ይሆንልናል። የጂኦተርማልን ጨምሮ የሃይል ፍላጎትን ከንፁህ የሃይል ምንጭ ለሚሟላት የሚያስችል የአነስተኛ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ፣ የፀሃይ እና የንፋስ ሃብቶች አሉን። እነዚህን ሃብቶች ግን ማልማትና የአገራችንን የሃይል ምንጭ ሥብጥር ለማብዛት አልቻልንም። አሁንም የሃይል ፍላጎታችንን በባህላዊ መንገድ እያሟላን ነው። ምክንያቱም እነዚህን ሃብቶች ለማልማት ያለን ጥሪት አነስተኛ ነው።

በሌላ በኩል በኪዮቶ ፕሮቶኮል ድንጋጌ መሰረት የከባቢ አየር በካይን ለመቀነስ ታቅዶ እየተተገበረ ያለው ንፁህ የልማት ዘዴ እነዚህን ሃብቶቻችንን ለማልማት በገንዘብ ምንጭነት ሊያገለግለን ይችላል። የንፁህ የልማት ዘዴ ላይ የተመሰረተ ንግድ እየጎለበተ ነው። እስከ 2012 ድረስ 2 ቢሊዮን ቶን የበካይ ጋዞችን ልቀት ለመቀነስ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች ተመዝግበዋል። ለንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት ማስተግበሪያ በአጠቃላዩ 11 ቢሊዮን ዶላር ተመድቧል።

እስከ አሁን ያሉት የንፁህ ልማት ዘዴ ፕሮጀክቶች በቻይና፣ በሕንድ፣ በብራዚል፣ በኮርያና በሜክሲኮ ተከማችተዋል። እነዚህ አገሮች እስክ 2012 ድረስ ከሚሸጠው 84 በመቶውን ወስደውታል። በዓለም ላይ ለሽያጭ ከቀረቡት ፕሮጀክቶች መካከል 79 በመቶው የቻይና፣ የሕንድ፣ የብራዚል፣ የኮርያና የሜክሲኮ ነው። በአገራችን በኪዮቶ ፕሮቶኮል መሰረት ለሚካሄደው ንግድ የሚውል ሃብት ቢኖርም ተሳትፎአችን ስለዚህም ተጠቃሚነታችን ይህን ያህል አይደለም። እስከአሁን በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ

አንዳንድ ዕንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። ግን መጠናከር አለባቸው። ስለዚህም ይህ የካርቦን ንግድ በአገራችን እንዳይስፋፋ መሰናክል የሆኑ ጉዳዮችን ለማወቅ መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች፣

- ከዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን አንስቶ፤ በሁሉም መስክ ለካርቦን ንግድ የሚውል አገራዊ አቅም የሚያሳይ ስለዚህም የካርቦን ንግድ ኢንቨስትመንትን የሚስብ ዝርዝር መረጃ አመንጭቶ ለንግዱ ተሳታፊዎች እንዴት ማሳወቅ ይቻላል?
- ንፁህ የሃይል ምንጭ ስብጥርን የሚያስፋፋ እንዲሁም በምግብ ራስን ከመቻል ያለፈ የዘላቂ ልማት የማከሄጃ ጥሪት ለማካበትና ቴክኖሎጂ ለማግኘት የሚያስችል የካርቦን ንግድ በአገራችን እንዲሰፍን ምን ማድረግ እንችላለን?
- የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖ መቋቋሚያና የክስተቱን መልመጃ አገራዊ አቅማችንን በሁሉም ደረጃ በካርቦን ንግድ አማካኝነት ለመገንባት የሚያስችል አዲስና ተጨማሪ የገንዘብ ምንጭ ለማግኘት የሚረዱ ፕሮ ጀክቶች ወጪ ለመሸፈን ምን መደረግ አለበት?

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ለሚካሄድ ውይይት በመነሻነት እንዲያግዝ በማሰብ የሚከተሉት ሃሳቦች ቀርበዋል፣

6.1. የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክቶች ማስፋፊያ ህግ በሚመለከት፣

አሁን ያለን የኢንቨስትመንት ህግ አጠቃላይ ነው። ስለዚህ የንፁህ የልማት ዘዴ ኢንቨስትመንትን የሚሰብ ተጨማሪ የሕግ ሥርዓት ያስፈልጋል። ይህ ህግ የተረጋጋና ሊተገበር የሚችል መሆን አለበት። ምክንያቱም የካርቦን ክሬዲቱ በ10 ዓመታት ለሚቆጠር ጊዜ ይቆያል። ስለዚህ በ10 ዓመታት በሚቆጠር ጊዜ ውስጥ ህግ ሊለዋወጥ ይችላል። ይህ ደግሞ በነባር ህግ ላይ ተመስርቶ ለረዥም ጊዜ ለሚቆይ ኢንቨስትመንት አዋጪ አይደለም። ያለ ህግ ደግሞ የኢንቨስትመንት ዋስትና ላይፈጥር ይችላል።

6.2. የካርቦን ንግድ ላይ የተሳትፎ ወሰን በሚመለከት፣

አንዳንድ መሰናክሎች በቀላሉ ሊስተካከሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ማንም ሊረዳው በሚችል መንገድ የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት መገምገሚያና ማፅደቂያ ሥርዓት ማውጣት ቀለል ያለ ነው። በየቱኛው የልቀት መስክ እስከ ምን ደረጃ ድረስ የውጭ ኢንቨስተር ይሳተፍ የሚለውን ዓይነት ጉዳይ ለመወሰን ግን ጊዜ ወስዶ ማሰብ ይጠይቃል። ምክንያቱም ፀድቆ በሥራ ላይ ያለ ህግን ይዘት እንዲሻሻል ወይም እንዲሻር ሊያደርግ ስለሚችል ነው። ለምሳለ፤ የግል ባለሃብት የኤሌክትሪክ ሃይል አመንጭቶና በማከፋፈያ መስፈር አስገብቶ ቢያሰራጭ የሃይል አቅርቦት ይሻሻላል። ይህ የስራ መስክ የግል ሲሆን ግን ድጎማ ይቀራል። ይህ ደግሞ በኤሌክትሪክ ሃይል የመሸጫ ዋጋ እንዲጉር ያደርጋል። የአገር ሕዝብ በኤሌክትሪክ የመጠቀሙ አቅም አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል። ስለዚህም አብላጫው ህዝብ የሃይል ፍላጎቱን በኩበትና በእንጨት ለማሟላት ይገደዳል።

አንዳንድ አገሮች የውጭ ኢንቨስተር ተሳትፎን ይገድባሉ። ህንድ ዕፀዋት የመትከል ፕሮጀክትን ለውጭ ዜጋ አትፈቅድም። አንዳንድ አገሮች ደግሞ ለካርቦን ፕሮጀክቱ መተግበሪያ የሚያስፈልግ ቴክኖሎጂ በአገራቸው ካለ ኢንቨስተሩ ከአገር ውጭ እንዲያመጣ አይፈቅዱም። እነዚህ ተመክሮዎች በጅምላው ጥሩ ወይም መጥፎ አይባሉም። ሁሉም እንደየአገሩሁኔታ ይለያያል። ስለዚህ ከዚህ ዓይነቱ ተመክሮ ለእኛ ለአብነት የሚሆን ምን ጉዳይ ማግኘት እንችላለን?

6.3. የኢንቨስትመንት ወጪ መሸፈኛ ገንዘብ ዕጥረት በሚመለከት፣

አብዛኛውን የካርቦን ክሬዲት የሚገዙት በበለፀገው አገር ያሉ በካይ ኩባንያዎች ናቸው። በበለፀጉ አገሮች የስራ ፈቃድ ያላቸው 22 ኩባንያዎች ከአዳጊ አገሮች ለካርቦን ክሬዲት መግዣ 160 ቢሊዮን ዶላር ድረስ መድበዋል። በቢሊዮን የተመደበው ይህ ገንዘብ የካርቦን ክሬዲት ለመግዛት እንጂ የካርቦን ፕሮጀክትን ለሽያጭ እንዲደርስ የማድረጊያ ወጪ ለመሸፈን አይደለም። የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት የሚያልፍበት እያንዳንዱ ሂደት ደግሞ ወጪ ያስከትላል። የየፕሮጀክቱም ወጪ የተለያዬ ነው። ከ28 000 እስከ 1.2 ቢሊዮን ዶላር ሊደርስ ይችላል።

የፕሮጀክት ማዘጋጃና ፕሮጀክቱን ለሽያጭ ደረጃ ለማድረስ የሚያስፈልግ ወጪ በቅድሚያ መሸፈን አለበት። የካርቦን ክሬዲቱ ወይም የሺያጩ ገንዘብ የሚገኘው ደግሞ በመጨረሻ ነው። ስለዚህ የአገር ውስጥ ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በራሳቸው ወይም ከዓለም ዓቀፍ መሰል የገንዘብ ተቋማት ጋር በመሆን ለፕሮጀክቶች የመድህን የዋስትና ሽፋን ሊሰጡ ይችላሉ። ለኢንቨስትመንት የሚውል ብድር ሊያበድሩ ይችላሉ። ስለዚህም የንግድ አድማሳቸው ስለሚሰፋ እነርሱም ቢሆን ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይህን ማድረጉን እንዲወዱትና የወደዱትንም እንዲፈፅሙት ግን ምን ማድረግ እንችላለን?

6.3. የተሟላ የኢንቨስትመንት አቅም መረጃ አመንጭቶ ማሰራጨት፣

ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ተወዳዳሪ ፕሮጀክቶችን መለየትና ለአልሚው ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ከነፋስ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ገንብቶ፣ የማስተላለፊያ መስመር ዘርግቶ ያመነጨውን የኤሌክትሪክ ሃይል ለመሸጥ የሚችል የፕሮጀክት ባለቤት ከኤሌክትሪክ ሺያጭ እንዲሁም ከካርቦን ክሬደቱ የዳጎሰ ገቢ ያገኛል። አሁን ተገንብቶ ያለ በካይ ፋብሪካን አካባቢያዊ ተቀባይነት ወዳለው አሰራር ለማሸጋገር የሚካሄድ ፕሮጀክት ደግሞ ገቢው አነስተኛ ነው። ምክንያቱም የገቢው ምንጭ የካርቦን ክሬዲት ከሚያስገኘው ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ። እንዲህ ዓይነቱን ጨምሮ፤ በአገራችን ውስጥ የካርቦን ንግድ ኢንቨስትመንት ዕድል ለማሳየት በአሃዝና በምስል የተደገፈ መረጃ ቢኖር አስፈላጊ ነው። ይህን መረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት እየተካሄደ ባለው ጥረት ውስጥ የሲቪል ማህበራት እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ሚና ምን ሊሆን ይችላል?

6.4. የኢኮኖሚያዊ የማበረታቻ እርምጃ በሚመለከት፣

የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክትን ለማስተግበር ወደ አገር የሚገባን ቴክኖሎጂ ከቀረጥ ነፃ ማድረግ ሊታይ የሚገባው አማራጭ ነው። ከካርቦን ክሬዲት ንግድ ላይ ቀረጥ ማስከፈል ኢንቨስትመንት ሊስብ ወይም ሊያርቅ ይችላል። ለምሳሌ የካርቦን ክሬዲት ዋጋ በህግ ይወሰን ወይስ ለገበያ ይተው የሚል ጉዳይ አነጋጋሪና በሁሉም አቅጣጫ መታዬት ያለበት ነው። የበካይ ሃይል ምንጭ ድጎማ ንፁህ የሃይል ምንጭ ልማትንና ስርጭትን ያዳክማል። በሌላ በኩል፤ ለምሳሌ በደቡብ አፍሪቃ አንዳንድ የከተማ አስተዳደሮች የሃይል ማመንጫ ባለቤት ናቸው። ስለዚህ ሃይል አመንጭተው በማከፋፈል ገቢ ያገኛሉ። መስኩን በብቸኝነት ይዘውታል። የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመራቸው ውስጥ በሌላ አካል የመነጨ የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲሰራጭ አይፈቅዱም። ከህይወታዊ ሃብት የመነጨ ነዳጅም በነዳጅ ማደያ ተጨምሮ እንዲሰራጭ የማይፈልጉ የነዳጅ ማደያ ባለቤቶች ይኖራሉ። ስለዚህ የሃይል ማሰራጫ የመሰረተ ልማት አውታሮች የሞኖፖሊ አጠቃቀምን መርምሮ በማሻሻል ጭምር ለካርቦን ንግድ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ እንዴት መፍጠር ይቻላል?

6.5. ግንዛቤ ማስፋፋት

በአንድአንድ አገሮች የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክቶችን መርምሮ የማፅደቅ ሂደት አዝጋሚ ነው። የተለያዩ ባለድርሻዎች ተሳትፎም ይህን ያህል አይደለም። የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት ለልማት የሚያበረክተው አስተዋፅዖን በሚመለከት የባለድርሻዎች ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል። ስለዚህ ለተለያዩ ባለድርሻዎች ሁለት የተለያዩ ነገር ግን ተደጋጋፊ የሆኑ የግንዛቤና የክህሎት ማጎልበቻ ዕርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው። የመጀመሪያው የግንዛቤ ማጎልበቻ ዕርምጃ የንፁህ የልማት ዘዴ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ትርፍ የሚያስገኝ መሆኑን ማስገንዘብ ነው። የሁለተኛው ደግሞ እያንዳንዱ ባለድርሻ ከየድርሻቸው አኳያ የተገናዘበ ክህሎት እንዲኖረው ማስቻል ነው። ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ የግንዛቤና የክህሎት ማጎልበቻ ማኑዋሎችን ማንም ሊረዳው በሚችል ቋንቋ በማዘጋጀት እንዲሁም የግንዘቤና የክህሎት ትምህርቱን ከመስጠት አኳያ የእያንዳንዱ ባለድርሻ ሚና ምን መሆን አለበት?

6.6 የካርቦን ንግድ ኤክፐርቶች ማፍራት በሚመለከት፣

የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት የማዘጋጀት አገራዊ አቅማችን ገና ማደግ አለበት። ስለዚህ በዚህ መስክ የማማከርና ፕሮጀክት የማዘጋጀት እንዲሁም ገለልተኛ የቁጥጥርና ማረጋገጫ በመስጠት የስራ መስክ የሚሰማሩ ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች እና ድርጅቶች መፈጠር አለባቸው። ይህ ሲሆን የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት አዘጋጅቶ ለማስተግበር የሚያስፈልግ አጠቃላይ ወጪ ይቀንሳል። አለባለዚያ ለየፕሮጀክቱ ከውጭ ባለሙያ እየመጣ የሚሰራ ከሆነ የፕሮጀክቱ ማዘጋጃና የማስተግበሪያ ወጪ ከፍ ይላል። በከፍታውም ልክ ወደ አገር የሚመጣ ኢንቨስትመንት ይደክማል።

የመረጃ ምንጭ

A Comparative Analysis (WPS4136, February 2007), at http://econ.worldbank.org/WBSITE/EXTERNAL/EXTDEC/EXRESARCH/O.,Content MDK: 212153 28 ~ Page PK: 641654011piPK:641650261the sitePK: 469382,00,html

CBD Ad HOC Technical Expert Group on Biodiversity and Climate Change (2003) Interlinkages Between Biological Diversity and Climate Change: Advice on the Integration of Biodiversity Considerations into the Implementation of the United Nations Framework Convention on Climate Change and its Kyoto Protocol, CBD Technical Series No.10, Draft Report for Experts and Government Review, CBD Secretariat: Montreal.

Climate Change 2007: Impacts, Adaptation and Vulnerability. Contribution of Working Group II to the Fourth Assessment Report of the Intergovernmental panel on Climate Change, for a discussion of the impacts.

Department for International Development (2002) "Sustainable Livelihoods Guidance Sheets" DFID: London. Internet: http://www.livelihoods.org

Environmental Protection Authority of Ethiopia, Justification Submitted for the Ratification of the Kyoto Protocol.

GTZ, Capacity Development for the CDM, Lessons Learned in Ghana, India, Indonesia, South Africa and Tunisia.

Martin Khor, Development Issues Crucial for Post-2012 Climate Regime (TWN Briefing Paper 40, September 2007) at www.twnside.org.sg

Matthew Stilwell, An Economic Sector Approach to Climate Negotiations, Institute for Governance and Sustainable Development (October 2007)

Oxfam International, Adapting to Climate Change: What's Needed in poor countries and Who should pay (2007), at http://www.oxfam.org/en/policy/briefingpapers/bp104_Climate_Change _0705.

Saphores, J.D. (2003) "Harvesting a Renewable Resource Under Uncertainty" Journal of Economic Dynamics and Control 28: 509-529.

Stockholm Environment Institute (2003) "Community-Scale Adaptation Assessment: Paper presented at first AIACC Regional Workshop and Open Meeting for Africa and Indian Ocean Islands, Hartebeesportdam, Brits, South Africa, 10-13 March 2003.

The Conservation Strategies of Ethiopia, 2 April 1997.

The Environmental Policy of Ethiopia, 2 April 1997.

The Kyoto Protocol to the Convention on Climate Change, Opened for Signature on the 16th of March 1998.

The Nature Conservancy (2001) People Matters: The Nature Conservancy's use of Social Science to Understand and Work within the Human Context of Conservation, The Nature Conservancy: Arlington.

The Right to Development in a Climate Constrained World (September 2007), at http://www.ecoequity.org/docs/The GDRs Framework. pdf.

The United Nations Framework Convention on Climate Change, 9 May 1999.

The World Bank (2003) What International Investors Look For When Investing in Developing Countries, Energy and Mining Sector Board Discussion paper 6 http://iris37.worldbank.org/domodoc/PRD/Other/PRDDContainer.nsf/All+Documents/ 85256D2400 766CC785256FFC00762921/ $File/Investors paper No6.pdf.

UNFCCC (2006) Regional Distribution of Clean Development Mechanism Project Activities, http://cdm.unfcc.in/EB/027/eb27_repan19.pdf.

UNFCCC Secretariat, Report on the Analysis of Existing and Potential Investment and Financial Flows Relevant to the Development of an Effective and Appropriate Response to Climate Change (Dialogue Working Paper 8, 8 August 2007)

ተጨማሪ መረጃ

POTENTIAL FOR INVESTMENT

8.1 Hydropower

The exploited percentage is estimated as 3.3%. Ethiopia will continue short of electric power supply unless new plants are built. Given the time to commission a new plant, the current electricity generation system could soon be viewed as vulnerable. About 10% of the economically feasible potential is deemed to be suitable for small-scale.

8.2 Solar

The average daily solar radiation reaching the ground varies from 5.55 KW/m2 in February and March to 4.55 KW/m2 in July, with a mean of 5.20 KW/M2. The annual variation is small, allowing for a very efficient use of solar energy facilities. (CSE, Vol. 2)

8.3 Wind

Ethiopia has exploitable reserve of 10,000 MW wind energy with an average speed of 3.5–5.5m/s, 6 hours/day. The potential for wind energy is estimated to be some 4.3 million Tcal/year, of which 5% is deemed exploitable. 49.8% of this exploitable potential is located in two regions.

8.4 Natural gas

Natural gas deposits of over 25 billion cubic meters are discovered in one region. Geothermal energy resources totaling 700 MW are available in four areas.

8.5 Biomass

The total energy that can be derived annually from wood, agricultural residues, animal waste and human excreta are estimated to be about 101,656.77 Tcal. Out of which the share of woody biomass is about 79%, followed by animal waste 11 %t, crop residue 8 % and human excreta 2%. The potential of sink in the forestry sector is immense. Last year alone, more than 750 million trees were planted. In one region, a total of 210,832 hectares of land are reforested through natural regeneration and enrichment plantations. (CSE, Vol. 2)

8.6 Bio-fuel/diesel potential

There is considerable potential, without impacting on food security, for the production of bio-fuel from energy crops/trees. The possible annual production of energy from these resources is estimated to be 1, 066 Tcal . The existing Sugar Factories are estimated to produce annually no less than 28 million liters of ethanol from raw molasses. In the coming 5 years the capacity of producing ethanol will be 5 times more than the current production.

8.7 Bagasse

Sugar factories have a potential to utilize sugar cane refuse, commonly known as bagasse to generate heat and power to meet their own energy requirement. They can also produce and supply electricity to interconnected or isolated grids.

8.8 Municipal waste

Per year not lesser than 180.000 tons of refuse is produced in Addis Ababa alone. There is potential to utilize manure from livestock to capture and use methane gas. Studies indicate that about 28,180 Tcal per year can be obtained from human excreta. From the total dung produced annually about 111,284.42 Tcal of energy can be derived.

8.9 Transport

There is a huge potential to substitute fossil fuels with compressed natural gas or with fuels derived from biological resources. There is also potential to introduce electric busses for mass transportation. The transport sector of Ethiopia is eligible to the CDM of the Kyoto Protocol if it involves substituting fossil fuels with hydroelectricity, bio-fuels or compressed natural gas for busses and other vehicles. The measure will also reduce dependence on imported fossil fuel and improve the national balance of payment. Availing facilities to run electric busses, creation of a new gas industry, expansion of hydropower electricity and increased production and processing of bio-fuels will result in the creation of employment. Furthermore, it will address other environmental problems like urban air pollution which is an emerging national concern.

8.10 Organic Agriculture

Crops produced with the use of compost are proved to be better in terms of coping higher temperature and drought. Organic soils hold more carbon than soils farmed with conventional methods. Conversion of farmers to organic production using compost would enable to store carbon in the soil which will be equivalent to taking about many vehicles off the road in Ethiopia

የአየር ንብረት ለውጥና የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ተጽእኖዎችን የመቋቋምና የማለማመጃ እርምጃዎች በኢትዮጵያ[1]

አበበ ታደገ[2]

1. መግቢያ

የምንኖርበትን አካባቢ ጨምሮ፣ የምናከናውናቸው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባሮች ሁሉ በአየር ንብረት ተፈራራቂነት ምክንያት ከፍተኛ ተጽእኖ ይወድቅባቸዋል። ብዙ ሰዎች የአየር ንብረት አንድ ሀገር ካሏት መሠረታዊ የተፈጥሮ ሀብቶች አንደኛው መሆኑን ሲያምኑ፣ ለዚህም ምክንያቱ፣ የአየር ንብረት ሀገሪቱ የምታበቅለውን የዕፀዋት ዓይነት፣ የምታከናውናቸውን የግብርና ተግባሮች፣ ያላትን የውኃ ሀብትና የኃይል ምንጭ መጠንና ዓይነት፣ ወዘተ... የሚወስን መሆኑ ነው።

የአየር ንብረትን በሚመለከት ያሉ መረጃዎችን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ማዋሉ ግብርና ለህልውናቸው መሠረት ለሆነ እንደኢትዮጵያ ላሉ ሀገሮች እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኪያሄደው ግብርና ዋና መጋቢው የዝናም ውኃ በመሆኑ፣ በግብርናው ዘርፍ የሚመረቱት ምርቶች መጠን እና ዐይነት ከፍ - ዝቅ ማለት የዝናሙን መፈራረቅ መሳ ለመሳ ተከትሎ የሚሄድ ነው። በተለይ ደግሞ የዝናሙ መጠን መፈራረቅ እጅግ ከፍተኛ በሆነባቸው አካባቢዎች የሚከናወነው የግብርና ተግባር አስተማማኝ አይደለም።

በአየር ንብረትና በምግብ ማምረት መካከል ያለው የጠበቀ ግንኙነት ደግሞ በብሔራዊ ደረጃ ስላለው የገበያ ሁኔታ በሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያደርጋል። ዝናም ባለመዝነሙ ምክንያት (በተለይ መዝነብ ከሚገባው በታች እጅግ ዝቅ ያለ ሲሆን) የሚከሰተው ድርቅ በእርሻና በከብት ርቢ ረገድ ሊገኝ የሚችለውን ምርት በእጅጉ የመነመነ ያደርገዋል።

አሁን ባለንበት ወቅት፣ ሰዎች በሚያከናውኗቸው የተለያዩ ተግባሮች ምክንያት ወደአካባቢው አየር ውስጥ የሚረጩ እንደካርቦን ያሉ ጋዞች በየቀኑ እየጨመሩና እየታመቁ በመሄዳቸው የዓለማችን ከባቢ አየር እየተለወጠ ለመሄዱ ብዙ መረጃዎች አሉ። በቅርቡ በመንግሥታት መካከል ስለአየር ንብረት መለወጥ የተደረገው ጉባኤ አራተኛው የግምገማ ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ የዓለማችን የአየር ንብረት ሙቀት እየጨመረ መሄዱ በማያዳግም ሁኔታ ተረጋግጧል፤ ይህም ይታወቅ ዘንድ፣ በዓለማችን ላይ በአሁኑ ጊዜ የአየሩም፣ የውቅያኖሶቹም ሙቀት ከፍ እያለ መሄዱ፣ በሁለቱ ዋልታዎች አካባቢ ያለው ግግር በረዶ

[1] ሰኔ 13 ቀን 2000 ዓ.ም የተካሄደ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡፡

[2] አቶ አበበ ታደገ በፊዚክስ ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እ.ኤ.አ. በ1984 እንዲሁም ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በሜትሮሎጂ ከእንግሊዝ ሪዲንግ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል። አቶ አበበ ታደገ በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ በተለያዩ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት የሜትሮሎጂ ምርምርና ጥናት መምሪያ ኃላፊ ናቸው። አቶ አበበ በርካታ የምርምር ጹሑፎችን በጆርናል እና በሌሎች እትሞች ላይ አሳትመዋል።

በሰፊው እየቀለጠ መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት የባህርና የውቅያኖስ የውሀ ወለል ከፍ እያለ መሆኑ ቆም ብሎ ማመንታትን የሚጠይቅ ነገር አይደለም። ቀደም ሲል የጠቀስነው የመንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ሪፖርት እንደዘገበው፣ ቀደም ሲል ወደአየሩ ውስጥ ሲለቀቅ የነበረው፣ አሁንም የሚለቀቀው፣ ወደፊትም መለቀቅ የሚቀጥለው የተለያዩ ጋዞች ክምችት ተጨማሪ የአየር ንብረት ለውጥ እንደሚያመጣ፣ ይህም በዓለማችን ባሉ ሀገሮች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ጉዳት ማስከተሉ አይቀርም ብሎ ደምድሟል።

ይህን ችግር በሚመለከት የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የሰጠው ምላሽ፣ የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ የስምምነት ማዕቀፍ ለመቅረጽ እ. አ. አ. በ1992 በሪዮ ደ ጃኔይሮ ባደረገው የአየር ንብረት መለወጥን ጉዳይ በተነጋገረበት ጉባኤ ተካቷል። የዚህ ጉባኤ የመጨረሻ ግብ «የግሪንሀውስ ጋዞች» በመባል የሚታወቁትን የአየር ብክለት የሚየመጡ ንጥረ ነገሮችን በዓለማችን አካባቢ ያለውን የአየር ንብረትና ሥርዓት አደጋ ላይ እንዳይጥሉ የክምችት መጠናቸውን መቀነስና ወደማይጎዳ ደረጃ ማስተካከል ነው። የኪዮቶ ፕሮቶኮል በመባል የታወቀው የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ፣ ያደጉትና የበለጸጉት ሀገሮች፣ ስምምነቱ በወጣበት እ. አ. አ. በ1990 ወደአየሩ ውስጥ ይረጩ የነበሩትን የግሪንሀውስ ጋዞች መጠን እ. አ. አ. በ2010 በአማካይ በ5.2 በመቶ ያህል እንዲቀንሱ ወስኖ ስምምነቱም እ.አ.አ. በ1997 ጸድቋል።

ይህ የአየር ንብረት መፈራረቅና መለወጥ ለሚያመጣው ጉዳት በተለይ የተጋለጡት በማደግ ላይ ያሉና የልማት ደረጃቸው እጅግ ዝቅ ያለባቸው፣ እንደኢትዮጵያ ያሉት ሀገሮች ናቸው። የዚህም ምክንያቱ፣ እንዲህ እየተፈራረቀና እየተለወጠ ከሚሄደው የአየር ንብረት ጋር ራሳቸውን ለማጣጣም ያላቸው የዝግጅት ዓቅም ዝቅተኛ መሆኑ፣ ያሏቸው ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶችም እንዲህ እየተፈራቀና እየተለወጠ የሚሄደውን የአየር ንብረት ለመቋቋም አለመቻላቸው ነው። ይህ የመቋቋምና ሁኔታዎችን ከለውጡ ጋር የማጣጣም ዓቅም፣ በአንድ ሀገር ውስጥ እንኳን እንደየዘርፉና እንደመልክዐ ምድሩ ሁኔታ፣ እንደጊዜ፣ እንደማኅበራዊ ሥርዐቱ፣ እንደኢኮኖሚውና እንደተፈጥሮአዊ አካባቢው ይዞታ የተለያየ ነው።

አሁን ያለው የአየር ንብረት መፈራረቅ ገና ካሁኑ ኢትዮጵያን ከፍተኛ ፈተና ላይ እየጣላት ነው፡ ባንድ በኩል፣ በምግብ ዋስትና፣ በውኃና በኃይል አቅርቦት፣ እንዲሁም ደግሞ ድህነትን ለመቀነስና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት በምታደርገው ጥረት ላይ አጉል ተጽእኖ እያደረገባት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የተፈጥሮ ሀብቶቿ እንዲመናመኑና የተፈጥሮ አደጋዎች እንዲበዙ ምክንያት ሆኗል። ለምሳሌ፣ እ.አ.አ. በ1972/73፣ ቀጥሎ ደግሞ በ1984፣ እንደገናም ደግሞ አሁን በቅርቡ በ2002/03 የተከሰቱት ድርቆች ከብዙ ኢትዮጵያውያን አእምሮ ያልጠፉ ትኩስ የትናንት ትዝታዎች ናቸው። በ2006ም፣ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች የደረሰው የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ ይህ ነው ተብሎ የማይመጠን ጉዳትንና ጥፋትን በንብረትም በሰዎችም ላይ አድርሷል። እነዚህ ፈተናዎች መላውን ዓለም በሚውጥና የሰውን ዘር ሊደመስስ በሚችል የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ካሁኑም ይበልጥ ሊባባሱ መቻላቸው የሚቀር አይመስልም። ይህንን የመሰለ ዐውድ ውስጥ ሆነን ነገሩን ስንመለከተው፣ ራሳችንን ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር አጣጥመን ለመዝለቅ የሚቻልባቸውን ፖሊሲዎች፣ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎችና ለዘለቄታው የሚበጁ ስትራቴጂዎችን ከወዲሁ አቅዶና ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ለኢትዮጵያ አማራጭ የሌለው ግደታ ነው።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባወጣው ስምምነት መሠረት ሀገሮች ችግሩን ለመቋቋም ሊያስቡባቸው የሚችሉ ሁለት ዐበይት ስትራቴጂዎች አሉ። የመጀመሪያው፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት (አንቀጽ 2) የሰፈረውን ደንብ ለማሟላት በአየሩ ውስጥ ያሉትን በካይ ጋዞች መቀነስ ነው። ሌላው ሊከሰት የሚችል የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ከወዲሁ ተዘጋጅቶ መጠበቅ ነው። የአየር ንብረት ለውጥን አስመልክቶ ጎብረተሰብን ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የአየር ንብረት ሁኔታን በተዋቀረ መንገድ ለመከታተል ትብብር ማድረግ፣ ምርምርና የቴክኖሎጂ ልውውጥ ማድረግ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነቱ ግድ የሚላቸው እርምጃዎች ናቸው። የዚህ ወረቀት ትኩረት አስቀድሞ ተዘጋጅቶ መጠበቅ የሚለው እርምጃ ላይ ነው።

ዝግጅት ማድረግ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቋቋም በጣም አስፈላጊ እርምጃ ነው፤ ምክንያቱም፣ አሁን በአየሩ ውስጥ የሚለቀቁትን በካይ ጋዞች መጠን ለመቀነስ ሲባል የወጡት ስምምነቶች ተግባራዊ ቢሆኑ እንኳን፣ ያለውን የበካይ ጋዞች ክምችት ለመቀነስና የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታት አይቻልም። አስቀድሞ ዝግጁ ሆኖ በመጠበቅ በአየር ንብረት መፈራረቅና መለወጥ ምክንያት እየደረሰ ያለውንና ወደፊትም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ይቻላል። ይህ ግን ያዝ-ለቀቅ የሚደረግ ወይም ብቻ ለብቻ የሚጠመድ ሥራ አይደለም። ይልቁንም በአጠቃላይ የልማት ዕቅዳችን ውስጥ ራሱን ችሎ የሚካተት ጉዳይ ነው፤ ይህ ደግሞ አግባብ ባላቸው ዘርፎች ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግንም ያካትታል።

2. አንዳንድ ጽንሰ ሐሳቦችና ብያኔዎች

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋሙ ጉዳይ ተገቢነት ያላቸው ጽንሰ ሐሳቦችና ብያኔዎች የሚከተሉት ናቸው። እነዚህን ጽንሰ ሐሳቦችና ብያኔዎች የወሰድናቸው የአየር ንብረት ለውጥን ስለመቋቋም ከወጣው የፖሊሲ ማዕቀፍ (እ.እ.አ. 2005) ውስጥ ነው።

የአየር ንብረት፣ የአየር ንብረት መፈራረቅ፣ እና የአየር ንብረት መለወጥ

«የአየር ንብረት» ሲባል፣ በአንድ በተወሰነ አካባቢ፣ ዘለቅ ባለ የጊዜ ክልል ውስጥ የሚከሰቱትን የአየር ባሕርያት አማካይ አጎዛዊ ስሌት የሚያመለክት ሲሆን፣ የአየር ጠባይ ግን በዙሪያችን ያለው አየር ባንድ በተወሰነ የጊዜ ቅጽበት የሚያደርገውን መለዋወጥ ዕለት በዕለት (በየሰዓቱም ሊሆን ይችላል) የምናይበትን ሁኔታ ያመለክታል። የአየር ንብረት መፈራረቅ ስንል፣ የአየሩን ባሕርይ የሚወስኑት ሁኔታዎች፣ ቀዋሚ ከሆነ ይዞታቸውና ደረጃቸው ከፍ-ዝቅ ማለታቸውን ማመልከታችን ነው። የዐየር ንብረት መለወጥ ስንል ግን፣ አንድ የተለየ የአየር ንብረት ባሕርይ ወይም ባሕርዩን የሚወስን ሁኔታ አማካይ የሆነ ደረጃውን ለቅቆ ለረዢም (በዓመታት፣ ምናልባትም በዘመናት ለሚቆጠር) ጊዜ የሚቆይ ለውጥን ማስከተሉን ማመልከታችን ነው። ለውጡ የዕለት ተዕለት የጠባይ መፈራረቅ ሳይሆን የመሠረታዊ ባሕርይ ዐቢይ ለውጥ ነው።

መጋለጥ እና መቋቋም

መጋለጥ የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ለመረዳት የሚከተለውን እንይ፤ አንድ ክስተት፣ ነውጥ ወይም ጭንቅ ያለበት ሁኔታ ውስጥ ሲገባ ከሦስት አንድ ነገር ሊያደርግ ወይም ሊሆን ይችላል። ወይ ሁኔታውን በሆነ ዘዴ ለመከላከል፣ ወይም ጨርሶ ለመወጣት፣ አለዚያም ራሱን ከሁኔታው ጋር አጣጥሞ ችግሩን ለመቋቋም አቅሙ ይኖረዋል (በዚህ ሁኔታ የራሱን ባሕርይ ለውጦ በአዲስ ሥርዓት ይጓዛል፣ ወይም ይህንን ሁሉ ማድረግ ካልቻለ ጨርሶ ይጠፋል፣ ህልውናውን ያጣል)። ይህ ክስተት፣ ሰውን ጨምሮ፣ በተፈጥሮ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ሕያውና ግዑዝ ነገር ሁሉ የሚመለከት ነው።

መቋቋም/መላመድ

በያዝነው ርእሰ ጉዳይ ረገድ መቋቋም ስንል፣ ማናቸውም የተፈጥሮ ወይም ሰብኣዊ ሥርዓቶች በተጨባጭ በሚከሰቱ ወይም ሊደርሱ ይችላሉ በሚባሉ የአየር ንብረት መለወጥ ምክንያቶች ወይም እነሱ ከሚያስከትሏቸው ውጤቶች ጋር ራስን በማጣጣም፣ የደረሰውን ወይም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ዝቅ ለማድረግ፣ ወይም የተገኙ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ከጉዳቱ ለመዳን ከሁኔታው ጋር የሚያደርጉትን ሥምረት ወይም ለውጥ ለማመልከት ነው። ይህ ሂደት፣ የአየር ንብረቱ ይዞታ መለወጥ የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ተገንዝቦ፣ አጋጣሚውን መጠቀሚያ በማድረግ፣ የደረሰውን ወይም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማባበል ወይም ከጉዳቱ ለማምለጥ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች የሚጠናከሩበት፣ የሚዳብሩበትና በተግባር የሚውሉበት ነው። የተለያዩ የመቋቋም ዓይነቶች አሉ፤ ከነዚህ ውስጥ መጪውን ሁኔታ ከወዲሁ ገምቶ ዝግጁ መሆን፣ ግብታዊ ለውጥ፣ እና በዕቅድ የተቀናጀ መቋቋም ሦስቱ ናቸው።

ዝግጁነት፤ ይህ የመቋቋም ሥልት ወይም ዘዴ የአየር ንብረት ለውጥ ውጤቶች ከመከሰታቸው በፊት የሚደረግ ተጠንቅቆ የመቆየት እርምጃ ነው። ባጭሩ ራስን የማዘጋጀት ሥልት ማለት ይቻላል። በአማርኛው ዘዬ «ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ» ልንለው እንችላለን።

ግብታዊ መቋቋም/መላመድ፤
ይህ ሥራዬ ተብሎ ታስቦበት የሚደረግ የመከላከያ ዘዴ አይደለም። ይህን ዓይነቱን የመቋቋም ሥልት የሚቀሰቅሱት በአጠቃላዩ የተፈጥሮ ሥርዓት ውስጥ እና በሰዎች የኑሮ ሥርዓቶች ውስጥ የሚከሰቱ የገበያ ወይም የደኅንነት ለውጦች ናቸው። :

ዕቅድ- ወለድ መቋቋም፤ በአካባቢያችን ያሉት ሁኔታዎች የተለወጡ ወይም ሊለወጡ የዳዳቸው መሆናቸውን፣ ስለዚህም ወደሚፈለገው ሁኔታ ለመመለስ፣ ያንንም ጠብቆ ለማቆየት፣ ወይም ወደዚያ ግብ ለመድረስ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝቦና ይሆነኝ ብሎ ፖሊሲዎችን በመንደፍ ዝግጅት የሚደረግበት ሥልት ነው።

የመከላከል ዓቅምና የማገገምና ችግርን የመወጣት አድማስ

የመከላከል ዓቅም የምንለው አንድ ሥርዓት፣ በአንድ በተወሰነ ወቅት ያለውን ወይም ወደፊት ሊከሰት የሚችል የአየር ንብረት መቀያየርን የመቋቋም አድማሱን ለማስፋት ሲል፣ ጠባዩንና ክንውኑን ከተለወጠው ሁኔታ ጋር ለማጣጣም የሚያስችለውን ባሕርይ ነው። ማገገም የምንለው ደግሞ፣ አንድ ሥርዓት፣ ባሕርዩን ሳይለውጥ በሁኔታው ውስጥ ሊያልፍ የሚችልበትን የለውጥ መጠን የሚያመለክት ሲሆን፣ የመቋቋም አድማስ ደግሞ የአየር ንብረቱ የለውጥ መጠንና የሚያስከትላቸው ውጤቶች አዎንታዊም አሉታዊም ተጽእኖ ሊኖራቸውም የሚችሉ፣ አሉታዊ ሆነውም ግን ለክፉ የማይዳርጉ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ሁኔታው የመቋቋም አድማሱን መጠን ካለፈ ግን የሚደርሰው ጉዳት ወይም ጥፋት ጎብረተሰቡ (ሥርዓቱ) ሊያስታምመው ከሚችል በላይ ይሆንና፣ ያን ጊዜ ጎብረተሰቡ ወይም ሥርዓቱ የተጋለጠ ነው ይባላል።

ሥጋት/አደጋ (ከአየር ንብረት ጋር ሲዛመድ)፤- በተለይ በተጨባጭ ተለይተው የታወቁ አደጋዎች ከተጋለጡት ሥርዓቶች ጋር የሚያደርጉት ተራክቦ ውጤት ነው ማለትም፣ ሥርዓቶቹ (በማኅበራዊ ደረጃ) ስለመጋለጣቸው የሚሰማቸው ስሜት ማለት ነው። *ሥጋት*፣ በቀመር ደረጃ፣ የአንድ ሁነት፣ ሁነቱ ሊደርስ የመቻሉ ጉዳይ እና የሁነቱ ውጤቶች ቅንብር ሆኖ ሊታይ ይችላል --- በሌላ አባባል፣ *ሥጋት*፣ የአየር ንብረት አደጋ ሊከሰት የሚችልበት ሁኔታ አንድ ሥርዓት ሊጋለጥ በሚችልበት መጠንና ደረጃ ሲባዛ የሚያስከትለው ውጤት ነው ማለት ይቻላል።

3. ከአየር ንብረት መለወጥ ጋር የተዛመዱ ክንውኖች በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያወጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት እና የኪዮቶው የስምምነት ደንብ የሚባሉትን ሰነዶች ያጸደቀችው፣ እንደቅደም ተከተላቸው እ.አ.አ. በ1994 እና በ2005 ነው። ስምምነቶቹን ካጸደቁት ሀገሮች አንዷ በመሆኗ መጠን፣ ሀገሪቱ የስምምነቶቹን መርህዎች የማክበር፣ የጣሏቸውን ግዴታዎች የመወጣት ኃላፊነት ያለባትን ያህል ስምምነቶቹ በፈጠሯቸው መልካም አጋጣሚዎች የመጠቀም መብትም አላት።

በዚህ ረገድ በሀገሪቱ ውስጥ በብሔራዊ ደረጃ የተወሰዱ አያሌ እርምጃዎች አሉ።

የአየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲዎች

«የህዋ (የከባቢ አየር) መበከልና የአየር ንብረት ለውጥ» ጉዳይ በ1997 ዓ. ም. በወጣው የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ውስጥ ከተካተቱት ዐሥር የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲዎች ውስጥ አንዱ ነው። የፖሊሲው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

- ሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ የተጋለጠች እንደመሆኗ፣ ያላትን የአየር ንብረት ይዞታና ሁኔታ ለመከታተል የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን መቅረጽ፤

- የአየር ንብረት ለውጥን የመቆጣጠር መርህዎችን በተጨባጭ ማስከበር አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝቦ መቀበል፤ እና
- «ግሪንሀውስ ጋዞች» በመባል የሚታወቁትን (ለምሳሌ ካርቦን) በካይ ንጥረ ነገሮች ወደህዋው የሚለቀቁበትን መጠና ለመቀነስ በውኃ፣ በጂአተርማልና በፀሐይ የኃይል ምንጮች መጠቀምን ማበረታታት።

ከዚህም በተጨማሪ፣ ፖሊሲው፣ የተቋማትን ቅንጅት፣ የሕግ ማዕቀፍን፣ የክትትል፣ የግምገማና ፖሊሲ የማሻሻል ሕጎችን ነድፎ ተግባራዊ የማድረግን ጉዳዮችም ያካትታል። በዚህ ረገድ፣ የሀገሪቱ ብሔራዊ የሜቲሪዮሎጅ ኤጀንሲ፣ ከኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮችን ሲያስተባብር ቆይቷል።

በአየር ንብረት ጉዳዮች ላይ በተደረጉ ድርድሮች ላይ መሳተፍ

- ኢትዮጵያ በብሔራዊ የሜቲሪዮሎጂ ኤጀንሲ ወኪልነት የተመድ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ፈራሚ አባላት በሆኑት ሀገሮች ስብሰባዎች ላይ ተሳትፋለች፤
- የብሔራዊ የሜቲሪዮሎጂ ኤጅንሲ ባለሙያዎች በአየር ንብረት ለውጥ በይነ መንግሥታዊ ስብሰባዎችና የአየር ንብረት ገዳዮች በተነሱባቸው ሌሎችም መድረኮች እየተሳተፉ ነው።

በፕሮጀክቶች ውስጥ መሳተፍ

- በዩናይትድ ስቴትስ ድጋፍ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የተኪያሄደ ሀገራዊ የጥናት ፕሮግራም (እአ.አ. 1994-1996)፤
- በጂኢኤፍ ድጋፍ የአየር ንብረት ለውጥን ተጽዕኖ መከላከልን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከናወኑ ተግባሮችን ለማሳካት የተቀረጸ ፕሮግራም -- ኢትዮጵያ ለተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ያስተላለፈችው የመጀመሪያ ብሔራዊ ዘገባ ዝግጅት (እ.አ.አ. 1999-2001፤
- በጂኢኤፍና በዓለም ባንክ የተቀረጸ አህጉራዊ የአየር ንብረት፣ የውኃ እና የግብርና ፕሮጀክት፤ በአፍሪካ የግብርናና የተፈጥሮ አካባቢ ሥርዓቶች ላይ ያለው ተጽእኖና ከሥርዓቶቹ ጋር ማጣጣም የሚቻልበትን መንገድ መሻት (እ.አ.አ. 2003-2005)፤
- በጂኢኤፍ ድጋፍ የአየር ንብረት ለውጥን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከናወኑ ተግባሮችን ለማሳካት የተቀረጸ ፕሮግራም፣ ሁለተኛው እርከን፤ የሚያስፈልጉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ግምገማ (2005-2006)፤
- የአየር ንብረት ለውጥን ተጽእኖ ለመቋቋም የሚያስችል ብሔራዊ የተግባር ዕቅድ (እ.አ.አ. ጁላይ 2005-ዲሴምበር 2006)፤
- ድርቅንና የአየር ንብረት ለውጥን ተጽእኖ መታገል (2007-2010፣ በመዘጋጀት ላይ ያለ)፤
- የሁለተኛው ብሔራዊ ዘገባ ዝግጅት (2008-2009፤ በዕቅድ የተያዘ)።

የብሔራዊ ዘገባ ዝግጅቶች

- ኢትዮጵያ ለተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ያስተላለፈችው የመጀመሪያ ብሔራዊ ዘገባ ታትሞ እ.አ.አ. በአክቶበር 2001 ተላልፏል፤

- የአየር ንብረት ለውጥን ተጽእኖ ለመቋቋም የሚያስችል ብሔራዊ የተግባር ዕቅድ ዝግጅት እ.አ.አ. በ2007 ተጠናቋል፤
- የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን ለመቀነስ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጓት የቴክኖሎጂ ውጤቶች ግምገማ ዘገባ፤ እ.አ.አ. በ2007 ተጠናቋል።


4. የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ብሔራዊ የተግባር ዕቅድ።

የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ብሔራዊ የተግባር ዕቅዱን የማዘጋጀቱ አስፈላጊነትና ዓላማዎቹ የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ የስምምነት ማዕቀፍ፣ በአንቀጽ 4.9 ላይ በጣም ዝቅ ባለ የልማት ደረጃ ላይ ያሉ ሀገሮችን ልዩ ችግሮችና ያሉባቸውንም የተለዩ ሁኔታዎች ትኩረት ልንሰጣቸው እንደሚገባ ያሳስባል። የስምምነቱ ፈራሚዎች የሆኑት አባል ሀገራት በመደበኛ ጉባኤያቸው ሰባተኛ ዙር ላይ፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ በጣም በዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ ያሉ ሀገሮች፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተዛመዱ አጣዳፊና ፉታ የማይሰጡ ችግሮችን ለመቋቋም ይችሉ ዘንድ ተገቢው ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ሲሉ ውሳኔ አስተላልፈዋል። የብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድ እንዲዘጋጅ መሠረተ ምክንያት የሆኑት፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ የልማት ደረጃቸው በጣም ዝቅተኛ የሆኑት ሀገሮች፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተዛመዱ ችግሮችን ለመቋቋም ያላቸው ዓቅም ዝቅተኛ መሆኑ፣ ስለዚህም፣ አሁን ያሉባቸውንና ወደፊትም ሊገጥሟቸው የሚችሉትን የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸውን ችግሮችና ጉዳቶች ለመቋቋም የሚያስችላቸውን ዓቅም መገንባት እንዲጀምሩ፣ ፈጣንና አስቸኳይ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው መታመኑ ናቸው።


በአሁኑ ወቅት ያለው የአየር ንብረት መፈራረቅና የታዩ አዝማሚያዎች

በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች የታየው የየዓመቱ አማካይ ዝቅተኛ የአየር ሙቀትና የዝናም መፈራረቅ፣ እንዲሁም ሁኔታው የሚጠቁመው አዝማሚያ፣ እንደየቅደም ተከተላቸው፣ ከዚህ በታች ባሉት ግራፍ 1 እና ግራፍ 2 ተዘርዝረዋል። የስሌቱ የጊዜ ክልል እ.አ.አ. ከ1951-2006 ነው። ዓመታዊው አማካይ አነስተኛ የአየር ሙቀት የተገለጸው፣ በ40 ጣቢያዎች የተሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ የሙቀቱ መጠን ከአማካዩ አንጻር በሚያሳያቸው የልዩነት መጠኖች አማካይነት ነው። ግራፍ 1፣ ባለፉት 55 ዓመታት ውስጥ ዓመታዊው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን እየጨመረ የሄደ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል። የሙቀቱ ማደግ መጠን በየዐሥር ዓመቱ 0.37 ዲግሪ ሴንቲግሬድ (ወይም ሴልሸስ) እንደነበረ ግራፉ ያመለክታል። በግራፍ 2 እንደሚታየውም፣ በግራፍ 1 በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥ ሀገሪቱ በድርቅና በዝናም መፈራረቅ ሂደት ውስጥ አልፋለች። የዓመታዊው የዝናም መጠን አዝማሚያ፣ በመላ የሀገሪቱ ክፍሎች በነበረው ሁኔታ አንጻር ሲታይ፣ ከሞላ ጎደል የተመዛዘነ (የማይዋዥቅ) እንደነበረ መረዳት ይቻላል (ግራፍ 2ን ይመልከቱ)።

ግራፍ 1፡ በሀገሪቱ በሞላ የየዓመቱ ዓመታዊ አነስተኛ የአየር ሙቀት ያሳየው መፈራረቅ በሙቀት መጠን ሲለካ።




ግራፍ 2፤ በኢትዮጵየ በሙሉ ዓመታዊው የዝናም መጠንና ሲከተል የነበረው አዝማሚያ በየዓመቱ ያሳየው መፈራረቅ ከመደበኛው የዝናም ልክ አንጻር ባደረገው መዋዠቅ ሲገለጽ።



በኢትዮጵያ በሙሉ የአየር ንብረት ለውጥ የወደፊት አዝማሚያ ግምት


የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ይዞታ የወደፊት አዝማሚያ የተሰላው፣ MAGICC/SCENGEN (Model for the Assessment of Greenhouse-gas Induced Climate Change/(Regional and global Climate SCENario GENerator) **በሚባለው ባለጥምር ቀመር ሶፍትዌር አማካይነት ነው። ስሌቱም የተኪያሄደው ሦስት ዓመተ ምሕረቶችን ማጠንጠኛ ባደረጉ የጊዜ ክልሎች መሠረት ሲሆን፣ እነዚህም** 2030፣ 2050 **እና** 2080 **ዓ. ም. ናቸው። የበይነ መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ባሰላው አማካይ የበካይ ጋዞች ልቀት ገጽታ አንጻር ሲታይ፣ በመላው ኢትዮጵያ የሚኖረው አማካይ የአየር ሙቀት፣ በ**2030 **ከ**0.9 **እስከ** 1.1 **ዲግሪ ሴንቲግሬድ፤ በ**2050 **ከ**1.7 **እስከ** 2.1 **ዲግሪ ሴንቲግሬድ፤ በ**2080 **ደግሞ፣ ከ**2.7 **እስከ** 3.4 **ዲግሪ ሴንቲግሬድ ይሆናል ተብሎ ይገመታል (ሥዕል** 3)። **ይህ ለውጥ ከ**1961 **እስከ** 1990 **ከነበረው መደበኛ የሙቀት መጠን ጋር ሲነጻጸር ነው። እንዲሁም በሀሪቱ በመላ የሚኖረው ዓመታዊ የዝናም መጠን በትንሹ ከፍ ይላል (ሥዕል** 4)።


2030 **2050** **2080**




የአየር ሙቀት ለውጥ (በዲሴ) 2030 የአየር ሙቀት ለውጥ (በዲሴ) 2050 የአየር ሙቀት ለውጥ (በዲሴ)

2030 2050 2080







የዝንም መጠን ለውጥ (በመቶ) 2030 የዝንም መጠን ለውጥ (በመቶ) 2050 የዝንም መጠን ለውጥ (በመቶ) 2080

አሁን ያለው የአየር ንብረት ለውጥ የሚያመጣው ተጽእኖ

በኢትዮጵያ ሁኔታ፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ከተዛመዱ አደጋዎች መካከል፣ ድርቅ፣ የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ ዶፍ፣ ኃይለኛ ንፋስ፣ ውርጭ፣ ከፍተኛ የአየር ሙቀት፣ ወዘተ. ይገኙባቸዋል። ምንም እንኳን የነዚህ አደጋዎች ታሪካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖዎች ሥርዓት ባለው መንገድ ተቀናጅተው በደንብ ያልተመዘገቡ ቢሆንም፣ ዋና ናቸው የሚባሉት ሁለቱ የአደጋ ዓይነቶች፣ ማለትም፣ ድርቅና በጎርፍ መጥለቅለቅ፣ በዚህ ጥናት ውስጥ ይነሣሉ።

ኢትዮጵያ በተለይ ለድርቅ እጅጉን የተጋለጠች ሀገር ናት።

ምናልባትም፣ ድርቅ፣ ሀገሪቱን በየጊዜው በዋነኝት ጥቃት የሚያደርስባት ከአየር ንብረት ጋር የተዛመደ ብቸኛው አደጋ ነው ማለት ይቻላል። ድርቅ በማንኛውም የዓለም ክፍል የሚከሰት አደጋ መሆኑ ቢታወቅም፣ በአጠቃላይ በአፍሪካ፣ በተለይ ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ የሚጠነክረውን ያህል በሌሎች የዓለም ክፍሎች ሲጠነክር አይታይም። ባለፉት አያሌ ዓመታት እየደጋገሙና እያሠለሱ ሲከሰቱ የነበሩት የድርቅ አደጋዎች በሕይወትም፣ በንብረትም ላይ ከፍተኛ ጥፋት ያደረሱ ከመሆናቸው ሌላ፣ ብዙ ሰዎችም የኖሩበትን አካባቢ እየለቀቁ ወደሌሎች አካባቢዎች ለመፍለሳቸው ዐቢይ ምክንያት ሆነዋል።

ኢትዮጵያን በየጊዜው ሲያጠቃት የኖረው፣ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚከሰተው ሌላው አደጋ በጎርፍ መጥለቅለቅ ነው። በሀገሪቱ ውስጥ በሕይወትና በንብረት ላይ ጥፋት ያደረሱ ዐበይት የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋዎች እ.አ.አ. በ1988፣ በ1993፣ በ1994፣ በ1995 እና በ1996፣ እንዲሁም ደግሞ በ2006 ተከስተዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ በአየር ንብረት ለውጥ ለሚከሰቱ አደጋዎች የመጋለጥ ምክንያቶች

ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት መፈራረቅና መለወጥ የተጋለጠች እንድትሆን ያደረጓት ምክንያቶች በአየር ንብረት መፈራረቅና መለወጥ በቀላሉ የሚጠቃው የግብርና ዘርፏ ከዓመት ዓመት ዝናምን ጠብቆ የሚንቀሳቀስ መሆኑ፣ የሀገሪቱ የውኃ ሀብት ክምችት በሚገባው መጠን እንዲለማ አለመደረጉ፣ የጤና ጥበቃ አገልግሎት ደረጃ ዝቅ ያለ መሆኑ፣ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ምጣኔ እያደገ መሄዱ፣ የኢኮኖሚው ዘርፍ የልማት ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑ፣ ሕዝቡ ችግርና አደጋን የመቋቋም ዓቅሙ ዝቅተኛ መሆኑ፣ ለድርቅ በተጋለጡ የሀገሪቱ ክፍሎች ያለው የመሠረተ ልማት አውታር በቂ አለመሆኑ፣ የሀገሪቱ የልማትም ሆነ የአስተዳደር ተቋማት ደካሞች መሆናቸው፣ ሕዝቡ ስላለበት ሁኔታ በቂ ግንዛቤ የሌለው መሆኑ፣ ዋነኞቹ ናቸው።

ባለው መረጃ መሠረት፣ ሀገሪቱ ለነዚህ አደጋዎች የተጋለጠች ስለመሆኗ የተደረገ ግምገማና በብሔራዊው የመቋቋም የተግባር ዕቅድ መሠረት የተደረጉ ወቅታዊ ግምገማዎች እንደሚያመለክቱት፣ ለአየር ንብረት መፈራረቅና መለወጥ ከሁሉም ዘርፎች የበለጠ የተጋለጡት ግብርና፣ የውኃ ሀብት ልማት፣ እና የሰዎች የጤና ጥበቃ አገልግሎት ናቸው። በአኗኗር ልማድና ሥልት አንጻር ሲታይ፣ ከሁሉም ማኅበራዊ ክፍሎች ለጥቃት የበለጠ የተጋለጡት በዝናም ላይ የሚመኩ ባለአነስተኛ የመሬት ይዞታ ባለቤቶች የሆኑ ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች ናቸው። በመልክዐ ምድር አቀማመጥ አንጻር ስንመለከተው ደግሞ፣ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ለድርቅ የበለጠ የተጋለጡት፣ በረሃማ፣ ከፊል በረሃማ እና ዝቅ ያለ የአየር እርጥበት ያለባቸው ናቸው።

የአየር ንብረት መፈራረቅን መወጫ ዘዴዎች

በኢትዮጵያ ውስጥ፣ የአየር ንብረት መፈራረቅንና ጽንፋዊ ለውጦችን ለመወጣት እጥቅም ላይ የሚውሉ ነባርና በዘመናችን የሚሰራባቸው ዘዴዎች፣ የመዝራትንና ዕጸዋት የመትከልን ልማድ መቀየርን፣ ፍጆታን መቀነስን፣ ወፍ-ዘራሽ የዱር ምግቦችን መልቀም፣ ከጎረቤት ጋር ምግብ መለዋወጥንና መበዳደርን፣ አነስተኛ ሸቀጦችን በብዛት ማምረትን፣ ሥራ ፍለጋ በጊዜያዊነት ወይም በቀዋሚነት ወደሌላ አካባቢ መፍለስን፣ እህል ማከማቸትን፣ እንደከብትና እንደእርሻ መሣሪያዎች ያሉትን ወረቶች መሸጥን፣ መሬትን በወለድ አግድ ማሲያዝን፣ ከነጋዴዎች እና ከአራጣ አበዳሪዎች ገንዘብ መበደርን፣ የአደጋ ምልክቶችን አጢኖ መዘጋጀትን፣ የእርዳታ ጥሪ ማድረግን፣ ወዘተ. ያካትታሉ።

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽእኖዎች

የአየር ንብረት መለወጥ በተፈጥሮ አካባቢ፣ በማኅበራዊ ኑሮ እና በኢኮኖሚ ልማት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማድረጉ ምን ጊዜም የሚጠበቅ ነገር ነው። በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የተደረጉ የአየር ንብረት ለውጥን መጠንና አዝማሚያ የሚያመለክቱ አኀዛዊ ግምገማዎች የተወሰኑ ናቸው። ሆኖም ግን፣ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርገውን አሉታዊ ተጽእኖ በሚመለከት፣ ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት ተደርጎ ነበር፤ ምንጮቹም፣ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የማዕቀፍ

ስምምነት የቀረበው የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድ ዘገባ፣ በመንግሥታት መካከል የተደረገው የአየር ንብረት ውይይት ሰነድ፣ እና ሌሎችም ተመሳሳይ ሰነዶች ናቸው። ኢትዮጵያ ለተባበሩት መንግሥታት የማዕቀፍ ስምምነት ያቀረበችው የመጀመሪያው የመቋቋሚያ ዘገባ ሲዘጋጅ፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል በተባሉት ዘርፎች ላይ የተጽእኖና ለአደጋ የመጋለጥ መጠን ግምገማዎች ተደርገው በዘገባው ተካተዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የመቋቋሚያ መንደርደሪያ ሰነድ ከኢትዮጵያ የልማት ግቦች ጋር ያለው ዝምድና

አሁን ባለንበት ወቅት የአየር ንብረት ለውጥን አዎንታዊ ተጽእኖዎች ለመቋቋም የሚደረገውን ጥረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አቅጣጫ ለማሲያዝና ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ብሔራዊ ፖሊሲዎች፣ ዘርፋዊ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና ስትራቴጂዎች አሉ። ከነዚህም ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥን አሉታዊ ተጽእኖ በመቋቋም ረገድ ከፍተኛ ተገቢነት ያላቸው የፖሊሲና የፕሮግራም ሰነዶች፣ ድህነትን ለማጥፋት የተፋጠነና ዘላቂ ልማትን የማኪያሄድ ዕቅድ፣ የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ፣ የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የውኃ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ፖሊሲ፣ የጤና ጥበቃ ዘርፍ ልማት ፖሊሲና ፕሮግራም፣ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ብሔራዊ ፖሊሲ፣ የብዝኀ ሕይወት ጥበቃና ጥናትና ምርምር ብሔራዊ ፖሊሲ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ፣ የሕዝብ ብዛት ፖሊሲ፣ እና ብሔራዊ የግብርና ጥናትና ምርምር ፖሊሲና ስትራቴጂ ናቸው።

ዋና ዋና የሚባሉትን የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም አማራጭ መንገዶች መለየት

በበይነ መንግሥታት የአካባቢ ስምምነት ውስጥ በተካተቱት የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም አማራጮችን ቅኝት፣ በመኪያሄድ ላይ ያሉ ፕሮግራሞችንና የልማት ፕሮጀክቶችን፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ የመቋቋም መንደርደሪያ ዘገባና፣ በብሔራዊ የሜቴሪዮሎጂ ኤጀንሲ የተዘጋጁትን የሁለቱን ብሔራዊና የስምንቱን ክልላዊ የምክክር ዐውደ ጥናቶችን ውጤቶች መሠረት በማድረግ፣ ከዚህ በታች ያሉት የአየር ንብረት ለውጥን አሉታዊ ተጽእኖዎች ለመቋቋም ያስችላሉ ተብለው የተገመቱ 37 አማራጮች የተጠቆሙ ሲሆን፣ እነዚህን እንደአስፈላጊነታቸውና እንደተገቢነታቸው በቅደም ተከተል ለማደራጀትና በደረጃ ለመለየት፣ ከዚያም በሀገሪቱ ብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድ ውስጥ በማካተት ሀገሪቱ ላሉባት የመቋቋም ችግሮች ምላሽ ለመስጠት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ተጨማሪ ሥራ እየተሠራ ነው።

ተቀዳሚ ፕሮጀክቶችን/ተግባሮችን መምረጫ መሥፈርቶች

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ያስችላሉ የሚባሉትን ፕሮጀክቶች ለመዘርጋት የሚያስፈልጉትን ግብአቶች ካሉን ግብአቶች ጋር ለማጣጣም ይቻል ዘንድ፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ፕሮጀክቶች ጨምቆ ለማውጣት የመመዘኛ መሥፈርቶችን መቅረጽ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው። የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ያሉትን አማራጮች እንደአስፈላጊነታቸው የደረጃ ቅደም ተከተል ለማሲያዝ የተጠቀምንባቸው መሥፈርቶች፣ ብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድን ለማዘጋጀት እንዲረዱ ተብለው

በተዘጋጁት ዝርዝር መመሪያዎች ውስጥ በቢጋር መልክ በተካተቱትና በልማት እጅግ ወደኋላ የቀሩ ሀገሮች የባለሙያዎች ቡድን ተብሎ የሚታወቀው አካል ለሀገሮቹ ይበጃሉ ብሎ

ባቀረባቸው አጠቃላይ መሥፈርቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እንዲሁም በብሔራዊና በክልል ደረጃ ከተደረጉ የምክክር ስብሰባዎች የመነጩት መሥፈርቶችም መጠቀሚያ ሆነዋል። ከዚህም በተጨማሪ፣ እነዚህ መሥፈርቶች፣ ከሀገሪቱ ተቀዳሚ ችግሮችና ፍላጎቶች እና የአየር ንብረት ለውጥ አደጋን ከማስወገድ፣ ድህነትን ከመቀነስ፣ የተግባሮችን ተደጋጋፊነት ከማረጋገጥንና ተግባሮችን ከብሔራዊና ከዘርፎች ልማት ዕቅድ ጋር ከማቀናጀት እና ከሌሎችም የበይነ መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ ስምምነቶች ጋር ካላቸው ግንኙነት አንጻር ተመርምረዋል። አማራጮቹን ቅደም ተከተል የማሲያዝ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ የሜትሪዮሎጂ የተቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት መሥፈርቶቹን አጽድቀዋቸዋል። በዚህ መሠረት የሚከተሉት መሥፈርቶች ነጥረው ወጥተዋል፤

- በድህው የኅብረተሰብ ክፍል የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚያመጡት ለውጥ (ድህነትን ለመቀነስ ያላቸው ብቃት)፤
- ከብሔራዊና ከልማት ዘርፍ ዕቅዶች ጋር ያላቸው ተደጋጋፊነት፤
- የአየር ንብረት ለውጥ ሊያደርስ የሚችለውን አደጋ የመከላከል ብቃት (ድሆች ለመከላከል የሚችሏቸው ጥፋቶች)፤
- በበይነ መንግሥታት የአየር ንብረት ስምምነቶች ውስጥ ከተካተቱ የተግባር ዕቅዶች ጋር ያላቸው የቅንጅት መጠን፤
- ወጭን የሚቆጥቡ መሆናቸው።

መሥፈርቶቹ አንድ ጊዜ ከታወቁ በኋላ፣ የሚቀጥለው ተግባር የመሥፈርቶቹን የአስፈላጊነት ደረጃ እያመዛዘኑ ቁጥር በመስጠት በቅደም ተከተል ማደራጀት ነው። ተለይተው የተጠቆሙት መሥፈርቶች በሙሉ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ለሚዘረጉ ፕሮጀክቶች ተገቢ ቢሆኑም፣ የተደረገው ጥናት የአስፈላጊነታቸው ደረጃ የተለያየ ይሆናል የሚል ግምት ይዞ ነው የቀረበው።

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፕሮጀክቶች / ተግባሮች

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያመጣውን ጉዳት ለመከላከል በከፍተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ወይም አስቸኳይ የመቋቋም ፕሮጀክቶችን ለይቶ መጠቆም የኢትዮጵያ ብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድ መድረሻ ግብ ነው። ፕሮጀክቶቹን በደረጃ መድቦ በቅደም ተከተል የማደራጀቱ ዓላማ፣ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽእኖ ወዲያውኑ ለመቋቋም የሚያስችሉትን፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን የመቋቋሚያ ፕሮጅክቶች ለይቶ ለመምረጥ ነው። ይህን ለማድረግ የተጠቀምንበት የትንተና ዘዴ «ባለብዙ እርከን መሥፈርት የትንተና ዘዴ» (ማልቲ-ክራይቴሪያ አናሊሲስ) የሚባለው ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ፣ ላሉት የፕሮጀክት አማራጮች በሙሉ የመመዘኛ ነጥብ በመስጠት፣ ከዚያም ለእያንዳንዱ

መሥፈርት የተሰጠውን የመመዘኛ ነጥብ ከታሰቡት ፕሮጀክቶች አጠቃላይ ሐሳብና ዓላማ ጋር በማጣጣም ነው።

የሀገሪቱን የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተጽዕኖ በአስቸኳይ ለመቋቋም ያስችላሉ የተባሉ 11 ፕሮጀክቶች በአስፈላጊነታቸው ደረጃ በቅደም ተከተል ተለይተው ተዘርዝረዋል (ሰንጠረዥ 1)። እነዚህ ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ ሲታዩ የሚያተኩሩት የሰው ኃይልና የተቋማት ዓቅምን በመገንባት፣ በተፈጥሮ ሀብቶች አያያዝና አጠቃቀም፣ የመስኖ እርሻን በመጠቀምና ውኃ የማቆርን ዘዴ በማሻሻል፣ የአደጋ ምልክቶችን አጢኖ የዝግጁነት ሥልቶችን በመቀየስ እና የሕዝቡን ግብዛቤ ከፍ በማድረግ ላይ ነው።

ሰንጠረዥ 1፤ በባለብዙ እርከን-መሥፈርት የግምገማ ዘዴ መሠረት የደረጃ ቅደም ተከተል የተሰጣቸው ፕሮጀክቶች ዝርዝር

ተ.ቁ.	የፕሮጀክቱ ዓይነት
1	በኢትዮጵያ ውስጥ የድርቅ/የእህል ዋስትና ፕሮግራምን ማስፋፋት
2	ለድርቅና ለጎርፍ መጥለቅለቅ መከላከያ የሚሆኑ የዝግጁነት ሥልቶችን ማጠናከር/ማሻሻል
3	በረሃማ፣ ከፊል በረሃማ በሆኑና እና ከፊል እርጥበት ባለባቸው ደረቅ አካባቢዎች አነስተኛ የመስኖና ውኃ የማቆር ዘዴዎችን መቀየስ
4	አርብቶአደሩ በሚኖርባቸው አካባቢዎች ያሉትን የግጦሽ ሥፍራዎች የንብረትን የአያያዝንና አጠቃቀም ዘዴ ማሻሻል/ማዳበር
5	በተመረጡ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ያሉትን ረግረጋማ ሥፍራዎች ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመጠቀምና ለመጠበቅ የሚያስችሉ በመሠረተ ሕዝብ ተቋማት ላይ የተመሠረቱ የአጠቃቀምና የአያያዝ ሥልቶችን መዘርጋት
6	በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚያስችል የሕዝብ ግንዛቤ ፕሮግራም መዘርጋት
7	በገናሌ-ዳዋ ተፋሰስ ላይ ብዝኀ ተግባር የሆነ ሰፊ የውኃ ሀብት ልማት ፕሮጀክት በመዘርጋት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ
8	በኢትዮጵያ የስምጥ ሸለቆ አካባቢ በመሠረተ ሕዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ የድንጋይ ከሰል (ካርቦን) ኃብትን የማውጣት ፕሮጀክት መዘርጋት
9	የአየር ንብረት ለውጥን ሁኔታ ለማጥናት የሚውል የምርምርና የልማት ማዕከል ማቋቋም
10	በተመረጡ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የወባን ስርጭት በቁጥጥር ሥር ለማዋል የተዘረጋውን ፕሮግራም ማጠናከር
11	በረሃማ፣ ከፊል በረሃማ በሆኑና፣ እና ከፊል እርጥበት ባላቸው ደረቅ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በእርሻ ማሳዎችና በመንደሮች አካባቢ ዛፍ የመትከልንና ሌሎች ዕፀዋትን የማልማት ባህልን ማስፋፋት

የኢትዮጵያን የአየር ንብረት ለውጥ ብሔራዊ የመቋቋሚያ የተግባር ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚገጥሙ ዕንቅፋቶች

ቀደም ሲል እንደተባለው፣ አብዛኛዎቹ ብሔራዊ እርምጃዎች የተግባር ዕቅዶች/ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የአየር ንብረት ለውጥን ለማስተናገድና ለመቋቋም በቅንጅትና በመደጋገፍ እጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ናቸው። ስለዚህም እነዚህን ብሔራዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ማድረጉ፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም አስፈላጊነቱ ከፍ ያለ ነው። ይሁን እንጂ፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም አሁን እየተወሰዱ ካሉት የተለያዩ ብሔራዊ እርምጃዎች የሚገኙትን ጥቅሞች ከፍ ለማድረግ እና እነዚህን አካባቢ ተኮር እርምጃዎችና እንዲሁም ደግሞ የሪዮ-ስምምነት መርህዎችን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል የተቀናጀ ጥረት መደረጉን ለማረጋጥ በሚሞከርበት ጊዜ ሊገጥሙን የሚችሉ አንዳንድ ዕክሎች፣ እንደሚገጥመንም ሁኔታ ልናስተካክል፣ ልንለውጥ የሚገባን ነገሮች ይኖራሉ።

አሁን እየተወሰዱ ባሉት እርምጃዎች መሠረት ከሚደረገው የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ጥረት ሊገኙ የሚችሉት ጥቅሞች እንዳይሟሉ ከሚያነቅፉን ዕክሎች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- በፌዴራልም በክልልም ደረጃ የሚደረጉትን ጥረቶች ለማቀናጀት የሚያስችል በቂ ሥልት አለመኖሩ፤
- በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና በተለያዩት መምሪያዎች መካከል የተለያዩትን ዘርፎች ያካተተ በቂ የግንኙነት መሥመር አለመኖሩ፤
- በፌዴራል ደረጃ የተቋቋሙ የተለያዩ ኮሚቴዎችን የሚያቀናጁ ሥልቶች አለመኖራቸው፤
- በአካባቢ ጥበቃና በልማት ውስጥ የተሰማሩ የፌዴራልና የክልል ዘርፎችን የሚያገናኝ የዳበረ ዝርዝር የግንኙነት መሥመር አለመኖሩ፤
- የዓቅም እጦት፤ ማለትም፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚቻልባቸውን ዘዴዎች ለማጥናት የሚችል የምርምርና ልማት ተቋም አለመኖሩ፤
- በአነስተኛ የሀገሪቱ የአስተዳር አካባቢዎች ለሚኖሩ ማኅበረሰቦች የአካቢ ጥበቃ ጉዳዮችን እንዲያውቁ ለማድረግ የሚያስችል የቀለጠፈ የግንኙነት ፕሮግራም አለመኖሩ፤
- የአጭር ጊዜ የኢኮኖሚ ጥቅሞችን ስናይ በአካባቢያችን ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን የረዥም ጊዜ ተጽዕኖዎችን አለማጤን፤
- የኢኮኖሚ ችግር፤ ማለትም፣ ለአካባቢ ጥበቃ እንዲውል የሚደረገው ገንዘብ የተወሰነ መሆኑ፤
- ስለአካባቢ ጥበቃ በሕዝቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ በደረጃው ዝቅ ያለ መሆኑ፤
- የሕዝቡ የመሠረተ ትምህርት ዕውቀት ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የሀገሪቱ የድህነት ደረጃ ከፍ ያለ መሆኑ፤
- የብሔራዊ የሜቲዮሮሎጂ አገልግሎቶች ኤጀንሲን እና የብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድን ፕሮጀክቶችና/ወይም የተግባር ዕቅዶች ተግባራዊ በሚያደርጉት ወገኖች መካከል መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችል ዓቅም በበቂ አለመኖሩ።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የወጣው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የተግባር ዕቅድ ዝግጅት

የኢትዮጵያን የመቋቋም የተግባር ዕቅድ ለማዘጋጀት እንደመመሪያ ሆኖ ያገለገለው በልማት እጅግ ወደኋላ የቀሩ ሀገሮች የባለሙያዎች ቡድን ያወጣው የመመሪያ ሰነድ ነው።

ተቋማዊ ተሳትፎ

የኢትዮጵያ የመቋቋም ፖሊሲ የተግባር ዕቅድ የተወጠነውና የማስተባበሩ ሥራ የተመራው በብሔራዊ የሜቲዮሮሎጂ አገልግሎት ኤጀንሲ ሲሆን፣ ዝግጅቱን የማስተባበሩን ተግባር በዋናነት ለመምራት፣ ከዚህ በታች ስማቸው ከተዘረዘረው አግባብ ያላቸው ተቋማት የተውጣጡ አባላትን የያዘ አንድ አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ። የአስተባባሪ ኮሚቴው አጠቃላይ ኃላፊነት ለዝግጅቱ ሂደት አጠቃላይ መመሪያዎችን መንደፍና ሥራውን በበላይነት ማቀናበርና መከታተል ነበር። የተወከሉት ተቋማት የሚከተሉት ናቸው፤

- **የውኃ ሀብት ሚኒስቴር**
- **የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር**
- **የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር**
- **የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ**
- **የኢትዮጵያ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ**
- **ብሔራዊ የሜቴሪዮሎጂ አገልግሎት ኤጀንሲ**
- **አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**
- **የብዝኀ ሕይወት ጥበቃና ምርምር ተቋም**
- **የኢትዮጵያ የገጠር የኃይል ምንጭ ማስፋፊያና ልማት ማዕከል**
- **መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመወከል ሲ.አር. ዲ.ኤ.**

የፕሮጀክቱን የዕለት-ተዕለት ክንውኖች ተግባራዊ ለማድረግ፣ የፕሮጀክት አስተባባሪ፣ ምክትል የፕሮጀክት አስተባባሪ፣ ጸሐፊ፣ የሂሳብ ሹም፣ የቴክኒክ ጉዳዮች አስተባባሪ፣ እና መረጃ አጠናቃሪ በአባልነት ያሉበት አንድ የፕሮጀክት አመራር ቡድን በብሔራዊ የሜቴሪዮሎጂ አገልግሎት መሥሪያ ቤት ውስጥ ተመሠረተ። በተጨማሪም የፕሮጀክት አመራሩን ቡድን ለማማከር አንድ አማካሪ ባለሙያ ተቀጥሯል። ለሚዘጋጀው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የመቋቋም ፖሊሲ የተግባር ዕቅድ በግብኣትነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ዘገባዎችን ለማዘጋጀት፣ በሀገሪቱ ያሉት ብሔራዊ ባለሙያዎች በአማካሪነት እንዲሠሩ ተደርጓል።

የመረጃዎች / የኢንፎርሜሽን ቅንጅት

ለብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድ ዝግጅት የሚረዱ ቅድሚያ የሚገባቸውን የመቋቋም አማራጮችን በመንደፉ ተግባር ውስጥ የሚካተቱት በብሔራዊ አማካሪዎች የተኪያሄዱ ግምገማዎች ለአየር ንብረት ለውጥ በመጋለጥ ላይ ያሉትን መረጃዎች ማቀናጀትን፣ በመተባበር ዓቅም ላይ የተደረጉ ግምገማዎችንና ፕሮጀክቶችን ቅደም ተከተል ለማሲያዝ የሚያስችሉ መሥፈርቶችን ያካተቱ ናቸው።

አግባብ ካላቸው ወገኖች (ከባለጉዳዮች) ጋር የተደረጉ ውይይቶች

የኢትዮጵያን ብሔራዊ የመቋቋም ስትራቴጂ የተግባር ዕቅድ የማዘጋጀቱ ሂደት አግባብ ባላቸው ወገኖች (በባለጉዳዮች) ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ነው። ዝግጅቱ የተከናወነው ከተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች ከተውጣጡ ባለሙያዎች በተመሠረተ ቡድን ሲሆን፣ ሥልቱም ቀደም ያሉ ዕቅዶችንና ፕሮጀክቶችን እያጣቀሰ በነሱ ውስጥ የተነሱ ጉዳዮችን እያዳበረ እንዲዘልቅ ሆኖ የተዋቀረ ነው። በዚህም መሠረት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያወጣውን በረሃማነትን የመከላከል ስምምነት መሠረት ያደረጉ ብሔራዊ የተግባር ዕቅዶችን፣ ብሔራዊ የብዝኀ-ሕይወት ጥበቃ ስትራቴጂዎችንና የተግባር ዕቅዶችን፣ የብዝኀ-ሕይወት ስብጥር ስምምነትን፣ ብሔራዊ የዘርፍ ፖሊሲዎችን በድጋፍነት ተጠቅሞባቸዋል።

የብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድን በማዘጋጀቱ ሂደት አስፈላጊ የሆነው የባለጉዳዮች ተሳትፎ በደንብ የተሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የመቋቋሚያ አማራጮችን ቅደም ተከተል አሲዞ ለመምረጡ ተግባር ግብአት የሚሆኑትን መረጃዎች በመሠረተ ሕዝብ ደረጃ ካሉ መረጃ አቀባዮች ለመሰብሰብ እንዲቻል «ሕዝብን ያሳተፈ የዐውደ ጥናት ሥልት» የሚባለው ዘዴ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። በዚህ ረገድ በተለያዩ የዕውቀት መስኮች የሙያ ብቃት ያላቸው 500 ያህል ሰዎች የተሳተፉባቸው ሁለት ብሔራዊ፣ ስምንት ክልላዊ ዐውደ ጥናቶች እንዲኪያሄዱ ተደርጓል። የውይይቶቹ ዓላማ፣ ስለአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች ግንዛቤን መፍጠር እና ለአየር ንብረት ለውጥ በመጋለጥና ይህንንም በመቋቋም አማራጮች፣ ላይ፣ እንዲሁም የመቋቋም ፕሮጀክቶችን የደረጃ ቅደም ተከተል ስለማሲያዝ ሐሳቦችንና አስተያየቶችን ማሰባሰብ ነበር። በዐውደ ጥናቶቹ የተደረጉትን ውይይቶች የሚያሳዩ ሥዕሎች በብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድ ሰነዱ ውስጥ በገጽ 63-65 ተካተዋል።

ሰነዱን የማጽደቅ ሥርዓቶች

የብሔራዊ የመቋቋም የተግባር ዕቅድ ዘገባው፣ እ.አ.አ. ጃንዋሪ 19፣ 2007 በተኪያሄደ ብሔራዊ ዐውደ ጥናት ላይ ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ፣ በዐውደ ጥናቱ ላይ ከተሳታፊዎች የቀረቡ አስተያየቶችንና ሐሳቦችን መሠረት በማድረግና በማካተት ሰነዱ እንዲሻሻል ተደረገ። የሰነዱ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ ሰነዱን እንደገና ከቃኘ በኋላ እንዲጸድቅ ይሁንታውን ሰጠ። በመጨረሻም፣ ሰነዱ በውኃ ሀብት ልማት ሚኒስቴር በይፋ ጸድቆ ተፈረመ።

5. የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋምን ተግባራዊ ለማድረግ የሚገጥሙ ችግሮች

- **የሥልጠና/የሠለጠነ የሰው ኃይል እጦት**
- **የመረጃዎች ዕጦት**
- **ተቋማዊ ችግሮች**
- **የገንዘብ ድጋፍ ማነስ**
- **የሙያዊ/የቴክኒክ ድጋፍ እጦት**

የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋሙ ጉዳይ አድማሱ የሰፋና ውስብስብም ስለሆነ፣ በሁሉም ደረጃ የብዙ ሰዎችን/ተቋማትን የተቀናጀ ጥረት ይጠይቃል።

- የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋሙን ጥረት ከአጠቃላይ የልማት ሂደቱ ጋር ማቆራኘት
- በመሠረታዊ መረጃዎች፣ በሚታመኑ፣ ተለይተው በታወቁ ክልላዊ የአየር ንብረትና የማኅበራዊ-ኢኮኖሚያ ይዞታዎች፣ አስፈላጊ የሆኑ የተጽእኖ ግምገማዎችን ለማኪያሄድ የሚያስፈልጉትን በእጅ ያሉ መሣሪያዎች ሥራ ላይ ለማዋል በሚያስፈልጉ ክሂሎች፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚያስችሉ መፍትሔዎችን ለማፍለቅ በሚያስፈልገው ዓቅም ረገድ ትንሽ የማይባሉ ክፍተቶች አሉ።
- የአየር ንብረት ለውጥን በመረዳትና በአየር ንብረት መፈራረቅና በአየር ንብረት መለወጥ መካከል የሚደረገውን ግልብ ልዩነት በሚመለከት እርግጠኛ ያለመሆን ችግር አለ፤ የአየር ንብረት ለውጥ ስለሚያደርጋቸው ተጽእኖዎችና እነዚህን ተጽእኖዎች ስለመቋቋም በቂ ዕውቀት የሌለ መሆኑ።
- የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚያስፈልገውን ወጭ የአየር ንብረት መፈራረቅን ለመቋቋም ከሚያስፈልገው ወጭ ያለመለየት ችግር
- የአየር ንብረት ለውጥን ምንነት በሚመለከት በፖሊሲና በተለያዩት የውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ላይ በቂ ግንዛቤና ዕውቀት አለመኖሩ
- በዘላቂ ልማት አጠቃላይ ዐውድ ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ዓቅምን የመገንባቱ ጉዳይ (ይህ ደግሞ በሳይንስ፣ በሙያ እና በተቋም ደረጃ ያለውን የዓቅም ግንባታ ያካትታል) ራሱን የቻለ ችግር ነው።

6. በኢትዮጵያ ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋምን በሚመለከት የ2020 ርእያችን

- የአየር ንብረት ለውጥን በሚመለከት ያለን ግንዛቤ በሁሉም ደረጃ ከፍ ይላል፤
- ዋና ዋና የሚባሉት የማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የሚደርሱባቸውን ተጽዕኖዎች/የመጋለጥ አዝማሚያዎች ሁሉም የተረዳቸው ይሆናል (ዕውቀቱ ይጨምራል)፤ ወዲያውም ደግሞ ተለይተው የተጠቆሙት የአየር ንብረትን የመቋቋም አማራጮች ተግባራዊ ይሆናሉ፤
- ሰዎችም ሆኑ ተቋማት የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ዓቅማቸው ከፍ ይላል፤
- ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች ባለቤት ትሆናለች፤
- በብዙ ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የተመደቡ ፖሊሲ ቀራጮች፣ የልማት ዕቅዶቻቸውን ሲነድፉ የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋሙን ጉዳይ ያጤናሉ፤

ሀገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ዕቅዷን ተግባራዊ ለማድረግ በቂ ድጋፍ (የገንዘብ፣ የሙያ፣ የቴክኖሎጂ) ታገኛለች።

በአቶ አበበ ታደገ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

አባቡ ለናሬ[1]

የጥናታዊ ፅሁፉ ጠናካራ ጎኖች፣ አስተያቶች ቢጨመሩ የፅሁፉን ጥራት ይጨምራሉ ብዬ የገመትኳቸው ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፣

ጠንካራ ጎኖች

ከአየር ንብረት ለውጥና የመለማመጃ እርምጃዎች ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ የሚገኙ ቃላቶችን እና ፅንሰ ሀሳቦች ለምሳሌ የአየር ንብረት፣ ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነት፣ ለአየር ንብረት አሉታዊ ተፅእኖዎች መለማመድ ወዘተ ግልፅ በሆነ መልኩ በመተርጎም ጥናታዊ ፅሁፉ መጀመሩ ውይይቱን አሳታፊ ለማድረግ አስተዎፅኦ አድርጓል።

እማካይ የሙቀት እና የዝናብ መጠን በአለም አቀፍና በሀገር ደረጃም የመጨመርና የመቀነስ ሂደቱ ምን እንደሚመስል የሃምሳ አመታት መረጃዎችን ሳይንሳዊና በሞዴሊንግ ዘዴ በመጠቀም የቀረበው ትንታኔ የአየር ንብረት ለውጥ ምን ያህል የአላማችንና የሀገራችንም አሳሳቢ ችግር እየሆነ እንደመጣ የማይናቅ ግንዛቤ ፈጥሯል።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የተዘጋጀውን ብሄራዊ የመለማመጃ የድርጊት መርሀ ግብርን ግኝቶች በመጠቀም በሀገራችን የአየር ንብረት ለውጥ መለዋወጥ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅእኖዎች እና ለአየር ንበረት ለውጥ የተጋላጭነት መንስኤዎች በዝርዝር ቀርበዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ብሄራዊ የመለማመጃ የድርጊት መርሀ ግብሩ የአዘገጃጀት ሂደት፣ሳይንሳዊ የመምረጫ መስፈርት በመጠቀም የተለዩ አስራ አንድ ፕሮጀክቶች ዝርዝር፣ወዘተ በማቅረብ የስብሰባው ታዳሚዎች በዚህ ሀገራዊ ሰነድ ላይ ግንዛቢያቸው እንዲጎለብት ተደርገዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖዎች ከመቋቋም አንፃር ሀገራችን መያዝ ስለሚገባት ርዕይ አስመልክቶ የፅሁፉ አቅራቢ የተወሰኑ ሀሳቦችን ሰንዝረዋል።

በገምጋሚው እይታ ከላይ በአምስት አንቀፆች በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ጥናታዊ ፅሁፉ ጠንካራ ነበር ማለት ይቻላል።

[1] ኡቶ

ለፅሁፉ ጥራት ይጠቅማሉ የተባሉ ሀሳቦች፤

የአየር ንብረት ለውጥን ከመቋቋም አንፃር ሶስት የመለማመጃ አይነቶች በፅሁፉ ውስጥ ተዘርዝረዋል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከተዘረዘሩት ውስጥ የትኛው ለሀገራችን ተስማሚ እንደሆነ ቢገለፅ ጠቃሚነት ይኖረዋል።

እ.ኤ.አ. በ1997 አ.ም የፀደቀው የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ የአየር ንብረት ለውጥን ከመቅዋቅዋም አንፃር ያለው ጠቀሜታ በአጭሩ ተጠቅሷል።

የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ የኪዮቶ ፕሮቶኮል ከመውጣቱ በፊት የወጣ በመሆኑ «Metigation and Adaptation» የመሰሉ ቃላቶች በጥቅም ላይ አልዋሉም። ሆኖም ግን የቃላቶቹ ይዘቶች በሚገባ በፖሊሲው ልዩ ልዩ ክፍሎች ውስጥ ተካተዋል።

በፅሁፉ ውስጥ የተጠቀሰው በፖሊሲው ውስጥ ከተቀመጡት መድብ ለዘርፋዊ ፖሊሲዎች ውሰጥ አንዱ ብቻ ነው። የአየር ብክለትና የአየር ንብረት ለውጥ ሲሆን በዚህም ስር ከተቀመጠው በተጨማሪ የችግሩን ስፋት በይበልጥ አጉልቶ ሊገልፅ ስለሚችል የሚከተለው የፖሊሲ አንቀፅ ቢጨመርበት፣ «ሁኒታውን በሚያካክስ ተመጣጣኝ የእፅዋት ቁስ እሰከተተካ ድረስ ለሀይል ፍጆታ የዋለ የእፅዋት ቁስ ተጨማሪ የአየር ብካላን የማያስከትል መሆኑን መገንዘብ፣ ቋሚ የዕፅዋት ቁስን ለመጨመር የተራቆቱ የደን ቦታዎችን በደን የመሸፈን፣ የእርሻ ድን የማልማት፣ የተሸረሸሩ ቦታዎችን መልሶ እንዲያገግሙ የማድረግ፣ መሬት በእጽዋት እንዲሸፈን የማድረግና በደጋዎች አካባቢ ልቅ ግጦሽን የመቆጣጠር እርምጃዎችን መውሰድ ለዚህም የሚያስፈልገውን ገንዘብ የእፅዋት ቁሱ በቅዋሚነት በመኖሩ ምክነያት የሚያመነጩት የአየር ብከላ ከሚካካስላቸው በኢንዱስትሪ ከበለፀጉ ሀገሮች መሻት በአንቀፅ 3.2 የደንና የዛፍ ሀብት በሚለው የዘርፍ ፖሊሲ ስር በ 9 ንኡስ ዘርፎች የተዘረዘረት ፖሊሲዎች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ለ«Metigation and Adaptation» ጠቃሚነት ያላቸው ናቸው።

ስለሆነም ከፖሊሲው ውስጥ ጠቃሚ አንቀጾችን በትምህርተ ጥቅስ አድርጎ በፅሁፉ ውስጥ ማሰገባቱ አንድም የአካባቢ ፖሊሲ ማእቀፍ ፖሊሲ በመሆኑ ለትግበራው የዘርፍ ወይም የመድብለ ዘርፍ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀትን ስለሚጠይቅ ልናዘጋጅ ለምንፈልገው የአየር ንብረት ፖሊሲ ጥሩ መሰረት ይሆንልናል።

በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያግዙና በብሄራዊ ሜትሮሎጂ አገልግሎት ብቻ የተዘጋጁ ፕሮጀከቶች ተዘርዝረዋል። ሆኖም ግን ሁሉንም መዘርዘር ባያስፈልግም በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እየተተገበሩና ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅአኖዎች መቋቋሚያ ጠቃሚነት ያላቸው እንዳሉ ተጠቅሶ ቢታለፍ።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በአየር ንብረት ለውጥ ለመጋለጥ እንደመንስኤ ከተጠቀሱት ውስጥ የመለማመጃ አቅም አናሳ መሆን ይገኝበታል። ሆኖም ግን ይህ መንስኤ በፅሁፉ ውስጥ የተዘረዘሩት መንስኤዎች ድምር ውጤት እንጂ በራሰ የሚቆም አይመስለኝም። በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የሚከሰትን አሉታዊ ተፅእኖዎች ለመቋቋም የሚረዱ ጥቅል መንገዶች ተቀምጠዋል። ነገር ግን የተጠቀሱትን መንገዶች በእርብቶ አደሩ ወይም በሰብል ምርት አምራቹ አካባቢመሆኑ ቢለይ እና ማን እንደሚተገብራቸው ለምሳሌ ማህበረሰቡ፣ መንግስት ወይም መንግሰታዊ ያልሆኑ ድረጅቶች ቢብራራ ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጥ ይመሰለኛል።

ብሄራዊ የመለማመጃ የድርጊት መርሀ ግብሩ ከኢትዮጵያ የልማት ግቦች ጋር ስላለው ቁርኝት በሚለው ንኡስ ርኡስ ስር ከተዘረዘሩት ፖሊሲዎች በተጨማሪ የደን፣ ኢነርጂ፣ የኢንዱስትሪ፣ የአካባቢ ጥበቃ ህጎች ቢጨመሩበት።

ብሄራዊ የመለማመጃ የድርጊት መርሀ ግብሩን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ መሰናክሎች ተዘርዝረዋል። ስለዚህ ጉዳይ በሚያነሳው ክፍል በሶስተኛው ዕረፍተ ነገር የመሰናክሎቹን ማቃለያ መንገዶች ማየትን አስፈላጊነት ቢያወሳም በፅሁፉ ውስጥ የመሰናክሎች ማቃለያ አልተቀመጠምና ቢቀመጥ።

የብዝሀ ህይወት አለም አቀፍ ስምምነት እና የብዝሀ ህይወት ስልታዊ የድርጊት መርሀ ግብር የተለያዩ ስምምነቶች እንደሚመስሉ ተደርገው ተቀምጠዋል። ፅሁፉን ለሚያነበው ሰው ግልፅ እንዲሆን የድርጊት መርሀ ግብሩ የብዝሀ ህይወት አለም አቀፍ ስምምነት ሀገራዊ የመተግበሪያ ሰነድ መሆኑ ቢጠቀስ።

ብሄራዊ የመለማመጃ የድርጊት መርሀ ግብሩን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ፈተናዎች ቢባል
በዚህ ርእስ ላይ የግንዛቤ ችግሩ በፖሊሲ አውጪዎች አካባቢ ብቻ እንዳለ ነው የተገለፀው። ችግሩ ግን በሁሉም ደረጃ ነውና አባባሉ ቢስተካከል።

የ2020 ርእይ

በዚህ ርእስ ስር እንደ ርእይ የምናስቀምጣቸው ጉዳዮች የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ የብዙ ዘርፎችና የመድብለ ዘርፎችን የሚመለከት መሆኑን ማጤን የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ተጨማሪ ርእዮችን ከማቅረቡ በፊት በቀረቡት ላይ ያለኝን አስተያየት ልስጥ።

የመለማመጃ እርምጃዎችን ለይተን የምንተገብረው ዋና ዋና የማህበራዊና አኮኖሚያዊ ዘርፎች በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅእኖዎች እና ተጋላጭነት ነው ወይንስ የአየር ንብረት ለውጡ በዋና የማህበራዊና የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ወይንስ አንዱ ባንዱ ላይ።

የአየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲና ስልት ማዘጋጀት እንደ ርዕይ ተቀምጥዋል። ይህ የአጭር ጊዜ እቅድ እንጂ ርእይ ሊሆን የሚችል አይመስለኝም።

የአየር ንብረት ለውጥ መለማመጃ ጉዳይን በሀገር ደረጃ በሚዘጋጁ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ውስጥ «mainstream/Integrate with predictable budget« በሚል ቢጠናከር።

ተጨማሪ ርዕዮች

1. ማህበረሰቦች የየአካባቢያቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች የማልማት፣ የመንከባከብ እና ፍትሀዊ የጥቅም ተጋሪ ለመሆንና ብሎም በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የሚከሰትን ተፅእኖ የመቋቋም አቅማችው እንዲጐለብት የሚያስችላቸው ስልጣን ማግኘት፣

2 ከአየር ንብረት ውጭ የሆኑና ነገር ግን በአየር ንብረት መለወጥ ጋር በተያያዘ ለሚከሰቱ አሉታዊ ተፅእኖዎች ተጋላጭነትን የሚያባብሱ ክሰተቶች ተሻሽለው ማየት ለምሳሌ፤ ድህነት፣ የምግብ ዋስትና፣ ማላሪያ፣ ኤች አይ ቪ፣ የአካባቢ ሀብቶች መመናመን ሁኔታ ወዘተ...

3. የመንግስት መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግሉ ዘርፍ ብሄራዊ የመለማመጃ የድርጊት መርሀ ግብሩን ከመተግበር አንፃር በቅንጅት የመስራት ባህላቸው መዳበር፤

4. የአካባቢ ጥበቃ አሀዶች በዋና ዋና የዘርፍ መስሪያቤቶች ተቋቁመው ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ጀምረው ከሌሎች ስራዎቻቸው በተጨማሪ ለብሄራዊ የመለማመጃ የድርገት መርሀግብሩ ትግበራ አስተዋፅኦ ማድረጋቸው፤

5. የንፁህ ልማት ዘይቤ በኪዮቶ ፕሮቶኮል ዘመንና ከዚያም በኋላ በሀገራችን በአግባቡ መተግበር።

የሀገር መከላከያና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በኢትዮጵያ[1]

ጉበረጊድቃን ጉበረተንሣይ[2]

በመጀመሪያ በዚህ መድረክ በሃገር መከላከያና የኢኮኖሚ ዕድገት መካከል ያለውን ዝምድና ጠቅለል ባለ መልኩ ለውይይት መነሻ የሚሆን ሃሳብ እንዳቀርብ ስለጋበዘኝ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበርን ከልብ አመሰግናለሁ።

በዚህ ዛሬ በማቅርበው ጽሁፍ ዋናው ሃሳብ የሃገር መከላከያ ኃይል በአንድ ሃገር ውስጥ ሰላምና የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖር አስተዋጽኦ በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገትን በአዎንታ ይደግፋል በሚለው አስተሳሰብ ላይ ያጠነጠነ ነው። ለአንድ ሃገር አኮኖማያዊ ዕድገት ሰላምና የተረጋጋ ኑሮ እንደቅድመ ሁኔታ የሚቆጠር ጉዳይ ነው። የሃገር መከላከያ ኃይል ደግሞ ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚመጣበትን የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል። ይህንን ግዳጁን ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚጠቀምበት የሃገር ሃብት ውጤታማና ሃብት ቆጣቢ በሆነ አግባብ እንዲጠቀምበት፤ ሰላምን ለማስፈን በሚያስችል የሃገራዊ ደህንነት ፖሊስና ስትራቴጂ መመራትና የሃገራዊ ሃብት አጠቃቀሙ ላይ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ከተደረገ የሃገር መከላከያ ኃይል በሃገራዊ ኢኮኖሚ ላይ ያለው ጫና የሃገሪቱ የደህንነት ሁኔታ የሚጠይቀው ብቻ እንጂ ከዛ በላይ እንዳይሆን ማድረግ ይችላል።

1. መግቢያ

የሃገር መከላከያና የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያላቸውን ዝምድና ለማየት ውይይት በሚካሄድበት ወቅት አሁን ያለው ዓለማዊ የደህንነት ሁኔታ (Global Security Environment) እንደመነሻ መዳሰሱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የእያንዳንዱ ሃገር ሃገራዊ ደህንነት ከዓለማዊው የደህንነት ሁኔታ ጋር የተያያዘና ይህ ዓለማዊ ሁኔታ ከፍተኛ ጫናን ይፈጥርበታል። እያንዳንዱ ሃገር ሊጎቀሳቀስበት የሚችል የሃገራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ የመፈናፈኛው አድማስ በዚሁ በዓለማዊው የደህንነት ሁኔታ ይወሰናል። ከዚህ አንፂር አሁን በምንገኝበት ዓለማዊ የደህንነትና የፖለቲካዊ ስርዓት ውስጥ ሁለት መሠረታዊ ታሳቢ መሆን የሚገባቸው ክስተቶች አሉ።

[1] ነሐሴ 30 ቀን 2000 ዓ.ም ተደረገ የ'ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ' የውይይት መድረክ ንግግር፡፡

[2] ሌተናል ጀነራል ገብረጻድቃን ገብረተንሳይ በጡረታ የተገለሉ ጂነራል ሲሆኑ ከሽግግሩ ዘመን ጀምሮ እስከ እ.ኤ.አ 2001 ዓ.ም. ድረስ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም ሆነው አገልግለዋል። ከዛ በፊት TPLF አባል እና በአብዛኛ በተዋጊነትና በአዋጊነት ደርግ ከሥልጣን ለማውረድ ታግለዋል። ሌ/ጂ ገ/ጻድቃን ገ/ተንሣይ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በInternational Policy and Plicy and Practic ከጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ አግኝትዋል። የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከ Open University በማናጅመንት አግኝተዋል። ሌተናል ጀነራል ገ/ጻድቃን ገ/ተንሳይ የደቡብ ሱዳን መንግስትን፣ የዓለም ባንክንና የተባበሩት መንግስት የልማት ኘሮግራም (UNDP) እና ሌሎች ተቋሞችን የማማከር አገልግሎት ሰጥተዋል። በአሁኑ ሰዓት የ Center for Policy Research ተቋም በዋና ዳይሬክተርነት በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

አንደኛው ዓለማዊው ፖለቲካዊ ስርዓት ባስከተለውና በግሎባላይዜሽን መስፋፋት ምክንያት እየተጠናከረ የመጣው በሃገራት መካከል ያለው የእርስ በርስ መተሳሰር (Interdependence) ነው። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያና በተለይም የቀዝቃዛው ጦርነት በአሜሪካ የበላይነት ከተጠናቀቀ በኋላ በርካታ ዓለም አቀፋዊ ተቋማት የሚመሩባቸው፣ መንግስታትም ተቀብለው ያፀደቋቸው ብዙ ዓለም አቀፋዊ ሕግጋት ወጥተው በስራ ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። እነዚህ ዓለም አቀፋዊ ሕግጋትና ተቋማት የመንግስታትን ባህሪይ መልክ በማስያዝ ለመተንበይ የሚቻል (Predictable) እንዲሆን ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። ከዚህ ጋርም ሰፊ የሆነ የዴሞክራታይዜሽን እንቅስቃሴ፣ የሰብአዊ መብቶች በተሟላ መንገድ መከበር፣ የሃገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሲቪል ማህበረሰብ መጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

ዛሬ ባለንበት ዘመን የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲዊ መብቶችን እንደፈለጉ እየረገጡና ለይምሰልም ቢሆን ምርጫ ሳይካሄድ በስልጣን ላይ መውጣት የማይቻል እየሆነ መጥቷል። ዛሬ ጭቆናም ቢሆን በዴሞክራሲ እየማሉ ነው ማካሄድ የሚቻለው።

ይህ እንግዲህ በአጠቃላይ በዓለም አቀፋዊ ሕግጋትና ተቋማት እየተጠናከረ የመጣው የግሎባላይዜሽን ክስተት የመንግስታት ባህርይ ለመለወጥ ምን ያህል አስተዋፅኦ እንዳደረገ ያመለክታል። ይህ ሁኔታ ዓለማዊውን የደህንነት ሁኔታና ከዚህም በተዛመደ ሁኔታ ሃገራዊውን የደህንነት አስተሳሰብ እንዲለወጥ እያስገደደ ይገኛል።

ሁለተኛው ሁኔታ ደግሞ ምንም እንኳን ቀደም ብሎ የተገለፀው ሁኔታ ቢኖርም፤ ዓለምአቀፋዊ ተቋማቱ ውሳኔያቸውን የሚያስፈጽሙበት አንድ ወጥ የሆነ የዓለምን ፖለቲካዊና ደህንነታዊ ስርዓት መልክ የሚያስይዝ የማስፈፀሚያ አቅም የላቸውም። ስለሆነም አሁንም ቢሆን ዓለማዊው ፖለቲካዊ ስርዓት ከራስ አገዝ ነው። የሃገራት የደህንነት ሁኔታ ሄዶ ሄዶ አደጋ ውስጥ ሲገባ የሚከላከሉት ራሳቸው ናቸው። ከዚህ የዘለለ እንደሆነ ያላቸው ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያስገኘላቸው ግንኙነትና በዚህ ሳቢያ የተወዳጁት ሊረዳቸው የሚችል ኃይል መኖር ነው። ይህ ደግም ሌላው የዓለማዊው የደህንነት ሁኔታ መገለጫው ነው። እነዚህ ሁለቱ ክስተቶች በሃገራት ያለውን የደህንነት ሁኔታ መሠረታዊ በሆነ መንገድ ጫና ይፈጥሩበታል።

የሃገር መከላከያ ኃይል በኢኮኖሚያዊ ዕድገት አዎንታዊ አስተዋፅኦ/ተፅዕኖ የሚኖረው ጦርነት (ከውጭ ጠላት ጋር) ወይም የርስ በርስ ግጭት (በሃገር ውስጥ) እንዳይቀሰቀስ መከላከል ሲችል ነው።

ከዚህ አልፎ በአንድ ሃገር የሚቻለውን ሁሉ ጥረት ከተደረገ በኋላ ጦርነት ወይም ግጭት ከተቀሰቀሰ በተቻለ መጠን ጦርነቱን ወይም ግጭቱን በአጭር ጊዜ በአነስተኛ ሰብአዊና ማቴሪያላዊ ዋጋ በአሸናፊነት መወጣት ያስፈልጋል።

ሃገራት የመከላከያ ኃይልን በከፍተኛ ወጭ የሚገነቡትና ለስራ የሚያሰማሩት ይህ ዝግጅት ሳይደረግ ቀርቶ በኋላ አደጋው ቢከሰት የሚከፈለው ዋጋ ዝግጅቱን በማድረግ ከሚከፈለው ዋጋ በአጠቃላይ ሲታይ ያንሳል ተብሎ ስለማይታመንበት ነው።

የጦርነት ወይም የእርስ በርስ ግጭት ኢኮኖሚያዊና (በገንዘብ ሊተመን የሚችል) ኢኮኖሚያዊ ያልሆነ (በገንዘብ ሊተመን የማይችል) ዋጋው በጣም ከፍተኛ ነው። ጦርነትን ከመቀስቀስ ለመከላከል ሳይቻል ቀርቶ ከተቀሰቀሰና ከዚህ አልፎም ሽንፈት ካጋጠመ ዋጋው በኢኮኖሚያዊ ስሌት ማስላት አይቻልም። ይህ ክስተት ከተከሰተ በሃገራት ላይ የኢኮኖሚ ዕድገት አይኖርም ብቻ ሣይሆን ቀደም ብሎ የተመዘገበው ዕድገት ለዓመታት ወደኋላ ይመለሳል። ለጦርነት መዘጋጀት የሃገርን ሃብት ይበላል። ይህንን መቆጣጠር ከዛም አልፎ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል። ጦርነት እንዳይቀሰቀስ መከላከል ሳይቻል ቀርቶ ሽንፈት ካጋጠመ ግን በተከታታይ ትውልዶች የተገነባውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሠረት ይንዳል። ይህንን መቆጣጠር አይቻልም። አሁን ባለንበት ዓለማዊ የፖለቲካ ስርዓት ደግሞ የጦርነትን አደጋ ለመቀነስ ለጦርነት መዘጋጀት አንዱ መንገድ ነው።

የሃገር መከላከያ ኃይል ግንባታና ስምሪት ተፈላጊውን ውጤት እንዲያስገኝ ከተፈለገ፤ አሁን ያለውን ዓለም አቀፋዊ/አህጉራዊና ሃገራዊ የፖለቲካና የፀጥታ ሁኔታዎችን በአግባቡ የተገነዘበ ከዚህ ሁኔታ የሚመነጩትን የስጋት አቅጣጫዎች በመተንተን ታስቦበት ህዝቡን አሳታፊ በሆነ ሁኔታ የሚነደፍ፤ የሃገርንና የህዝብን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል፤ ካሃገራዊ የደህንነት ፖሊሲ (National Security Policy) መንደፍ፤ ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ስትራቴጅና ስትራቴጅውን ለመተግበር የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ተነድፈው ተግባር ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

የዚህ ጽሁፍ ዋነኛው ትኩረት የሃገር መከላከያ ኃይል ግንባታና ስምሪት ከኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር ያለውን ግንኙነት መዳሰስ ነው። ጽሁፉ በአጠቃላይ የግንኙነቱ ባህርይ ላይ ያተኩራል። በመጨረሻም ከሃገራችን ሁኔታ አንፂር ለውይይት መነሻ እንዲሆኑ በማሰብ መነሳት ይገባቸዋል ብዬ የማምንባቸውን ጥያቄዎች እወረውራለሁ። እስከአሁን ድረስ ያለፈውን ዕድሜዬን ይበልጥኑ ያሳለፍኩት እንደታጋይና ወታደር ነው። ስለሆነም ይህ በሃገር መከላከያና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያለውን ዝምድና የማየው ካለፍኩበት ልምድ በመነሳት ነው። ወደ ዝርዝር የኢኮኖሚ ትንተና ለመግባት ሞያውም የለኝም ይህ ከእኔ የሚጠበቅም አይመስለኝም።

2. የሀገር ደህንነት ጥበቃና የመከላከያ ኃይል

ሃገራትና መንግስታት የሃገር መከላከያ ኃይልን የሚገነቡት ሃገራቸውን ከጥቃት ለመከላከለል ነው። ይህ ማለት ሃገራትና መንግስታት በሰላምና በተረጋጋ ሁኔታ ለመቀጠል እንዲችሉ ከሃገር ውጭ ይሁን ከአገር ውስጥ ሊመጡ የሚችሉ ጥቃቶችን ለመከላከል፤ መንግስታቱ በመረጡት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የዕድገት አቅጣጫ እንዲጓዙ ለማስቻል ነው። የሃገር ደህንነት ጥበቃ (National Security) የአንድ መንግስት መሠረታዊ ተግባራት ከሚባሉት ግዳጆች ዋነኛው ነው። ይህ ማለት ሁሉም ነገር

ከተስተካከለ (Ideally) የአንድን ሃገር ህዝብ በህዝቡ ሰፊና ያልተገደበ ተሳትፎ የመረጠውን ፖለቲካዊ ስርዓት፣ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት አቅጣጫና የማህበራዊ ብልፅግና እንቅስቃሴዎች በውጭ ኃይሎችና ሕገ ወጥ በሆኑ የአገር ውስጥ ኃይሎች ሳይሰናከል እንዲቀጥል የሚያስችል ሁኔታን መፍጠር ማለት ነው። የአንድ አገር ህዝብ በሰላምና በተረጋጋ ሁኔታ የዕለት ተዕለት ኑሮውን እንዲገፋ በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች በአግባቡ በስፋት ያለፍርሃትና መሸማቀቅ እንዲሳተፍ የሚያስችል ሁኔታን መፍጠር ማለት ነው።

የተለመደው አሰራር ሃገራትና መንግስታት የሃገር መከላከያ ኃይልን ተልዕኮና ግዳጅ በሕገ መንግስታቸው በግልፅ ያስቀምጡታል። እንደየሃገራቱ የኋላ ታሪክና ተጨባጭ ሁኔታ ተልዕኮውን የውጭ ኃይል በመከላከል ላይ ብቻ ያጥሩታል ወይም ደግሞ የሃገር ውስጥ አለመረጋጋትና ግጭት ሲኖር የሃገር መከላከያ ኃይልን ተልዕኮ ይጨምሩበታል። ከዚህም አልፈው ሰው ሰራሽ ይሁን ተፈጥሮአዊ አደጋ ሲከሰት እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ሰላም የማስከበር ግዳጅ በመጨመር ተልዕኮውን ሰፋ አድርገው ያስቀምጡታል። ከዚህ ጋር ጎን ለጎን የሃገር ደህንነት የማስጠበቅ ጉዳይ እጅግ መሠረታዊ ከሆኑት የመንግስት ተግባራት አንዱ ተደርጎ ስለሚወሰድና ማንኛውንም የሕብረተሰቡን እንቅስቃሴ (ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ) ስለሚነካ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚወሰድ ውሳኔ በጥንቃቄና በአግባቡ ታስቦበት መወሰድ ስለአለበት በሕገ መንግስቱ ውስጥ መሠረታዊ የሃገር ደህንነት ውሳኔዎችን እንዴትና በማን እንደሚወሰኑ ይቀመጣል። ይህ በሕገ መንግስቱ የሚቀመጠው የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓትና እርከን በአንድ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መኖር ያለበትን የስልጣን ክፍፍል እንዲኖር በማስቻል የCheck and Balance አሰራሩን ይበልጥ ያጠናክራል። የተጠያቂነትንም አሰራር ግልጽ ያደርጋል። ይህ በትክክል ተግባር ላይ ከዋለ የመከላከያ ኃይሉን ህዝባዊ ድጋፍና ሕጋዊነት (Legitimancy) በጽኑ መሠረት እንዲገነባ ከማስቻሉም በላይ በአንድ ሰራዊት ውስጥ መኖር ለሚገባው ለሰራዊቱ ሞራልና ጀግንነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። የአንድ ሰራዊት ሞራልና ጀግንነት ደግሞ በግዳጅ አፈፃፀም ውጤታማነት ላይ ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪም የቁጥጥር ስርዓቱን በማጠናከር አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ የሃገሪቱ ሃብት ይበልጥ ውጤታማና ሃብት ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ እንዲውልና የሃብት መባከንን ለመቆጣጠር ያግዛል።

በአጠቃላይ የሃገር መከላከያ ኃይል ተልዕኮ ከአገር አገር፣ ከመንግስት መንግስት መጠነኛ ለውጦች ቢኖሩትም የውጭ ጥቃትን መከላከል፣ የሃገር ውስጥ አለመረጋጋትና ግጭት ሲኖር፣ በሕገ መንግስቱ በግልፅ በተቀመጠ አግባብ ይህንን የሃገር ውስጥ አለመረጋጋትና ግጭት ለመፍታት ድርሻ እንዲኖረው፣ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋ ሲያጋጥም ይህንን አደጋ ከማስወገድና ጉዳቱን ከመቀነስ አንፂርም ድርሻ እንዲኖረው፣ በዓለም አቀፋዊ ሰላም የማስከበር ተልዕኮም ግዳጅ እንዳለው በብዙ ሃገራትና መንግስታት ዘንድ ተቀባይነት ያለው አሰራር እየሆነ መጥቷል። ከዚህም በተጨማሪ ለግዳጅ አፈፃፀሙ ውጤታማነት ትኩረት የሚሰጠውን ያህል ለአስተዳደሩም (Governance) ከዚሁ ያልተናነሰ ትኩረት ይሰጠዋል። ምክንያቱም የሚገነባው ኃይል በትክክል የሃገርን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚውል መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻለው አስተዳደሩ የተስተካከለ ከሆነ ነው።

የሃገር መከላከያ ኃይል ተልዕኮ ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ እንደተቀመጠው ሲሆን ይህ ኃይል ከኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር ያለውን ዝምድናን ለማየት በመጀመሪያ የሃገር ደህንነት ጥበቃ የሚባለው ፅንሰ ሃሳብ በጊዜ እንዴት እያደገ እንደመጣ አሁን ይህ አስተሳሰብ ምን ይዘት አለው የሚለውን ማየት ይጠቅማል። የሃገር መከላከያ ግንባታና ስምሪት እንዲሁ በነዚ ያለ ምንም የውጭ ተፅዕኖ የሚከናወን ጉዳይ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ሃገራዊ ሁኔታዎች መሠረታዊ ተፅዕኖ እያደረጉበት እነዚህን ተፅዕኖዎች ተቀብሎ ተልኮውን ከሁኔታው ጋር አስተካክሎ በመቀጠል የሚፈፀም ነው። ባለንበት ወቅት በሃገር ደህንነት ጉዳይ ላይ መሠረታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ሃገራዊ ክስተቶች አሉ። በሃገር ደህንነት ጥበቃ በተለይ በሃገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታና ግዳጅ አፈፃፀም ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ምንድነው የሚለውን ማጤን ተገቢ ይሆናል።

የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ አስተሳሰብ በደህንነት ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል። ማንኛውም ሃገር የሃገሩን ደህንነት ለማስጠበቅና በስራው ውጤታማ ለመሆን ከፈለገ አሁን ያለውን ለውጥ በሚገባ የተገነዘበ የሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ይህንን ፖሊሲ ለማስተግበር የሚያስችል ስትራቴጅና ፕሮግራሞችን መንደፍ አለበት። ይህንን ግዳጁን ሲነድፍ ደግሞ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ሃገራዊ ጉዳዮችን በሚገባ መገንዘብና መተንተን ይህ ሁኔታ ለግንባታውና ለግዳጅ አፈፃፀሙ ያለውን እንድምታ መውሰድ ይገባል። ይህ ደግሞ በአንድ በኩል በግዳጅ አፈፀም ውጤታማ በመሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለሃገር ደህንነት በተለይ ደግሞ ለሃገር መከላከያ የሚወጣውን በጀት ሁኔታው ከሚጠይቀው ግዳጅ ጋር የተዛመደ እንዲሆን ለማድረግ ያስችለዋል።

እዚህ ላይ አንድ መነሳት ያለበት ጉዳይ ሃገራት ብሄራዊ ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ ሊጠቀሙበት የሚችሉትና በቁጥጥራቸው ስር ያለ መሣሪያ የሃገር መከላከያ ኃይል ብቻ አለመሆኑ ነው። ጠላቶቻቸውን ለመነጠልና ወዳጆቻቸውን ለማሰባሰብ፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍና በአህጉር ደረጃ ተቀባይነትና ድጋፍ እንዲኖራቸው ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። የጠላቶቻቸውን ዕቅድና አስተሳሰብ ለማወቅና ከወዲሁ ለመከላከል በተጨማሪም የራሳቸውን ሚሰጥር ለመጠበቅ የኢንተለጀንሲ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ጠላቶቻቸውን ለማዳከም ራሳቸውንና ወዳጆቻቸውን ለማጠናከር ይጠቀሙበታል። ከሁሉም በላይ ደግሞ በአገራቸው ውስጥ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ተቀባይነት፣ ሰፊ ህዝባዊ ድጋፍ እናም የተደላደለ የህጋዊነት መሠረት (Legitimacy) እንዲኖራቸውና በሃገር ውስጥ ለእርስ በርስ ግጭት መነሻ የሚሆኑትን ምክንያቶች ለማጥፋት ሰላምና የተረጋጋ ሁኔታ እንዲፈጠር ሰፊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይቻላቸዋል። እነዚህን በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ መሣሪያዎችን አቀናጅተው በመጠቀም ነው የሃገርን ደህንነት ማስጠበቅ የሚቻለው። የሃገር መከላከያ ሰራዊት ከእነዚህ ከተጠቀሱት የመንግስት መሣሪያዎች አንዱ ነው። ግን ደግሞ ሁኔታዎች እየከፉ ሄደው በሌላ መንገድ መፍታት ሳይቻል ሲቀር መንግስታት የሚጠቀሙበት የመጨረሻው መሣሪያቸው ነው። ስለሆነም ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡታል። የሚፈለገውን ወጪ በማውጣት ይገነቡታል። አስፈላጊ መስሎ ሲታያቸው ለግዳጅ ያሰማሩታል። ታድያ ይህ ሚዛኑን ከሳተ ያለመረጋጋት ምንጭም ሊሆን ይችላል።

እንግዲህ የአንድን ሃገር ብሄራዊ ደህንነት የማስጠበቅ ግዳጅ የሃገር መከላከያ ኃይል ግዳጅ ብቻ እንዳልሆነ፤ የሃገር መከላከያ የአንድን ሃገር ሃገራዊ ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ አንዱ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያለ መሣሪያ እንደሆነ ተልዕኮውም ይህንን በወጉ የተገነዘበ ሆኖ መቀረጽ እንዳለበት በሚገባ መጤን ይኖርበታል። ይህ ማለት አንድ ሃገር ለሃገራዊ ደህንነት ጥበቃ የሚመድበው የሃገር ሃብትና አቅም ለሃገር መከላከያ የተመደበው ብቻ አይደለም። ለሌሎች የደህንነት ተቋማትም የሃገር ሃብት ይመደባል። ለሃገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ማህበራዊ ብልጽግና የሚወጣው ሃብትና ሃገራዊ አቅምም የአንድን ሃገር ሃገራዊ ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያም ከፍተኛ ፋይዳ አለው። ይህ ጉዳይ አሁን ሃገራዊ ደህንነትን ከማስጠበቅ አኳያ እየተነሱ ያሉትን አስተሳሰቦች ስናይ ይበልጥ ዘርዘር አድርገን እናየዋለን። ከዚህ አንፂር አሁን በሃገራዊ ደህንነት ጉዳይ ላይ በተለይ ደግሞ በሃገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታና ስምሪት ላይ ያለውን አስተሳሰብ በመቅረጽ ከፍተኛ ተፅዕኖ አላቸው ብዬ የማምንባቸውን ሦስት ጉዳዮች አነሳለሁ። እነሱም፡-

1. በሃገራት ደህንነት ላይ ያለው ግንዛቤ እየተለወጠ መምጣቱ፣
2. የጦርነቶች ባህሪይ እየተለወጠ መምጣቱ፣
3. የግሎባላይዜሽንና ዓለም አቀፋዊ ሕግጋት ተፅዕኖ ናቸው።

እነዚህ ክስተቶች የተያያዙ ናቸው። አንዱ በአንዱ ላይ ተፅዕኖ አላቸው። በዋናነት አንዱ ክስተት ሌላኛውን ክስተት ያጠናክራል።

3. ሀገራዊ ደህንነትና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ

በሃገራዊ ደህንነት ላይ ያለው ግንዛቤ እየተለወጠ መምጣቱ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የአንድን ሃገር ሃገራዊ ደህንነት የማስጠበቅ ተግባር የአንድ መንግስት መሠረታዊና ዋናው ግዳጅ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስታት ይህንን ግዳጅ ሲፈጽሙ የተከተሉትን አካሄድ ረዘም ካለ ታሪካዊ አመጣጡ ጋር ሲታይ አሁን እደረስንበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ለውጥ ተመዝግቧል። በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ማብቂያና በሃያኛው ምዕተ ዓመት የመጀመሪያዎቹ አስርተ ዓመታት ላይ የመንግስታት ዋነኛው ስራ ሰራዊት መገንባትና ጦርነት ማካሄድ ብቻ እስከሚመስል ድረስ ለሃገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታና ስምሪት እጅግ በጣም ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠው ነበር። በዚህ ወቅት አዳዲስ የጦር መሣሪያዎችን ማምረት ለኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ሳይቀር ፈር ቀዳጅ የነበረበት አዳዲስ ቅኝ ግዛቶችን መቆጣጠር የኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ አንድ አካል የነበረበት የሃገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታና ስምሪት ትልቁን የሃገሪቱን የሃብት ድርሻ የሚወስድበት ዘመን ነበር።

ይህ ሁኔታ ሄዶ ሄዶ በአንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች እጅግ ብዙ የሰው ሕይወትና ሃብት በማባከን፣ ዓለማዊውን የፖለቲካ ስርዓት በጦርነት መልክ ማስያዝ እንደማይቻል አረጋገጠ። ከዚህም በመነሳት ሃገራት ደህንነታቸውንና የዓለምን ሰላም ለማረጋገጥ የሚያስችላቸውን፣ ደህንነታቸውን በጋራ የሚጠብቁበት የጋራ ደህንነት /Collective Security/ የአስተሳሰብ መርህ የሚመራውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን መሰረቱ። ከዚህ ጋር ተያይዞም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃያ አካባቢ

የተፈለሰፈው የኑክሊየር የጦር መሣሪያ ከዛን ጊዜ በኋላ የሚደረጉት ጦርነቶች ሁሉንም ወገን አብሮ የሚያጠፋ እንጅ አንድ ግልጽ አሸናፊ ሆኖ የሚወጣበትን ሁኔታ እያጨለመው በመምጣቱ የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን መጣ። በዚህን ወቅት እጅግ በርካታ የፀረ ቅኝ አገዛዝ ጦርነቶች ተካሂደው በተለይ ኤስያና አፍሪካ ራሳቸውን ከቅኝ ግዛት ነፂ ያወጡበት አህጉራዊ ሰላምና ፀጥታ ለማስፈን የሚረዱ አህጉራዊ ድርጅቶችም የተመሠረቱበት ዘመን ሆነ።

በዚህ ታሪካዊ ወቅት በየግዜው የሚዲረጉ መጠነኛ ለውጦች ቢኖሩም መንግስታት የሃገራቸውን ደህንነት ማስጠበቅ ለዚህም ተብሎ ከፍተኛ ወታደራዊ አቅም ለመገንባት ሃገራዊ አቅማቸውና የውጭ ግንኙነታቸው የፈቀደውን ያህል መንቀሳቀስ ዋነኛው ሥራቸው ሆኖ ቆይቷል። ሃገራት በምስራቁና ምዕራቡ ዓለም ተከፋፍለው የሃገራቸው ሃብት የሚፈቀደውን ያህል ራሳቸው እየቻሉ እነሱ ያልቻሉትን ደግሞ ከውጭ ወዳጆቻቸው በእርዳታም በብድርም እያግበሰበሱ ወታደራዊ አቅማቸውን ማጎልበት አንድ ዓይነተኛ ባህሪያቸው ነበር። ከዚህ ጎን ለጎንም የውጭ ወዳጆቻቸው ለሆኑት ልዕለ ኃያላን የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ሆነው ያገለግሉ ነበር።

የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በበለፀጉት ሃገሮች መካከል የኑክሌየር ጦርነት የመቅሰቀስን አደጋ ማስቀረቱ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይ ደግሞ ባልበለፀጉት ሃገሮች መካከልና በውስጣቸው የነበረውን ፍጥጫ ቀንሷል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በየአካባቢው የነበሩት አካባቢያዊ ያልተፈቱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታን ፈጥሯል። ከዚህ ጋርም በነፂ ገበያ ውድድር ላይ የተመሠረተውን የካፒታሊስት ስርዓት በሌላ የዕድገት አቅጣጫ ለመተካት የሚያልም ወይም በነፂ ገበያ ላይ የተመሠረተን የካፒታሊስት ስርዓትን የሚቃወም አንድ ወጥና የተደራጀ ዓለም አቀፋዊ ብሎክ እንዳይኖር አድርጓል። ይህ በመሆኑም በምዕራቡ ዓለምና በምስራቁ ዓለም በመከፋፈል ይፈጠር የነበረውን ውጥረት ከዓለማዊ የደህንነት ሁኔታ እንዲጠፋ አድርጓል።
አሁን ባለንበት ወቅት ማለትም የቅኝ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ በተወገደበት፣ ቀዝቃዛው ጦርነት ባከተመበት፣ ዓለም አቀፋዊ ሕግጋት በተለይ በሰብአዊ መብቶች ላይ ያተኮሩት ሕግጋትና መንግስታት በእነዚህ ሕግጋት ላይ ሰፊ ዓለም አቀፋዊ ትኩረት ባሳረፉበት፣ ድህነትን ማጥፋት ከፍተኛ ትኩረት በሳበበት ሁኔታ፣ በሃገራዊ ደህንነት ግንዛቤ ላይ ያለው አስተሳሰብ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ሰፊ ግፊት እየተደረገበት ነው። ይህ ሁኔታ የጦርነቶች ባህሪይ እየተለወጠ ከመምጣቱ ጋርም በቀጥታ ይዛመዳል። ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በፊት የነበረው የጦርነቶች ባህርይና ከዛ በኋላ ያለው ባህርይ ተለውጧል። በሃገራት መሃከል የሚደረገው ጦርነት የተለመደው የውጭ የፖሊሲያቸው ማስፈፀሚያ የመንግስታት ባህርይ መሆኑ ቀርቶ እንዳልተለመደ ነገር (exception) የሚታይበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። አሁን ያለው ጦርነት/ግጭት ይበልጥኑ በሃገራት በራሳቸው ውስጥ የሚካሄደው ጦርነት/ግጭት ነው። የዚህ ዓይነት ጦርነት/ግጭት መሠረታዊ መነሻዎቹ ደግሞ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ናቸው። እነዚህ ሁኔታዎች ደህንነት (Security) የተባለውን ፅንሰ ሐሳብ ቀደም ብሎ ከነበረው ትርጓሜ በሰፋ መንገድ እንዲታይ አስገድዷል። የHuman Security የሚባለው ፅንሰ ሐሳብ ደግሞ የእነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች ውጤት ሆኖ በዓለም አቀፋዊው የሃገራት ደህንነት ማስጠበቅ አስተሳሰብ ላይ ጎልቶ መታየት ጀምሯል።

ደህንነት ለማን ከምን የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ። በዚህ የደህንነት ክርክር ውስጥ በአንድ በኩል ቀደም ብሎ የነበረው Conventional/ traditional መንግስትን ማዕከል ያደረገው የአንድን መንግስት ራሱን ከውጭ ጥቃት የመከላከል ብቃትን እንደዋነኛ ተልዕኮና መለኪያ አድርጎ የሚወስደው አስተሳሰብ አለ። ይህ መንግስትን ማዕከል (State Centeric) ያደረገው የሃገራዊ ደህንነት አስተሳሰብ ብዙውን ጊዜ ከብሄራዊ ደህንነት (National Security) ተብሎ የሚታወቀው አስተሳሰብ ላይ የሚያጠነጥን ተደርጎ ይወሰዳል። በሌላ በኩል ደግሞ አንድን ሃገር ወይም መንግስትን ከውጭ ጥቃት የመከላከልን ተልዕኮና ብቃት ሳይዊረር ግን ዋነኛውን የትኩረት አቅጣጫ የግለሰቦችን ደህንነት ማዕከል ያደረገው አስተሳሰብ የደህንነቱ አስተሳብ አስኳል እንዲሆን ከመፈለግ የሚመነጭ ሐሳብ (Human Security) ይባላል።

በተለምዶ የሚታወቀውና ቀደም ብሎም የነበረው በዋናነት የብሄራዊ/ሃገራዊ ደህንነት (National Security) እየተባለ የሚታወቀው አስተሳሰብ ዋነኛ መነሻው የአንድን ሃገር ብሄራዊ ጥቅም ተንትኖ በማውጣት ለዚህ መሠረታዊ ብሄራዊ ጥቅም ተፃራሪ የሆኑ ኃይሎችን በመለየት የስጋት አቅጣጫውን ያስቀምጣል። ብዙውን ጊዜም ይህ ትንተና ሃገሪቱን ወይም መንግስትን ከውጭ ከሚመጣ ጥቃት ለመከላከል ታስቦ የሚደረግ ነው። የሃገሪቱን ብሄራዊ ጥቅምና ይህንን የሚፃረሩ ኃይሎችን ታሳቢ በማድረግ የወጣው የስጋት አቅጣጫዎች ትንተና የሚተነትነውና ፖሊሲውን የሚያነጥረው በስልጣን ላይ ያለው ኃይል ነው። ይህ ሂደት በስፋት አሳታፊ በሆነ መንገድ የሚካሄድ ካልሆነና ሰፊ ሃገራዊ መግባባት (Consensus) (በብሄራዊ ጥቅም ትንተና እና በስጋት አቅጣጫዎች ማንጠር ላይ) ካልተደረገበት፣ የሚነደፈው የሃገራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ ፖሊሲ የጊዜውን መንግስት ዕድሜ ማራዘሚያ መሣሪያ ይሆናል። ይህ ክስተት በብዙ ሃገራት በተለይ ደግሞ በኢኮኖሚ ባላደጉት ሃገራት ያለ ጉዳይ ነው።

በቀዝቃዛው ጦርነት ምክንያት ተፈጥሮ የነበረው ዓለም አቀፋዊ የደህንነት ውጥረት ረገብ ማለቱን ታሳቢ ያደረገ በተጨማሪም ባላደጉት አገሮች ያለውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ኋላ ቀርነትና ይህ ለዓለም አቀፋዊ፣አህጉራዊና ሃገራዊ ሰላምና መረጋጋት ያለውን እንድምታ ግምት ውስጥ በማስገባት የተጠነሰሰው በHuman Security ላይ የሚያተኩረው የደህንነት ፅንሰ ሐሳብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊ ተቀባይነትን እያገኘ መጥቷል። የዚህ ፅንሰ ሐሳብ መሠረታዊ መነሻዎች የአንድን ሃገርና ህዝብ ደህንነት ትልቅ አደጋ ውስጥ የሚጥለው የውጭ ወራሪ ኃይል ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ አስተዳደሩ የተዛባ ከሆነ ትልቅ የደህንነት መጓደል እንዳለ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል ከሚል የሚነሳ ነው። "Peace is more than the absence of war, security is generally understood today to be more than the absence of immediate military threat or coercion."[3] ይህ የHuman Security አስተሳሰብ በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ደረጃ ውይይት የተደረገበትና አስተሳሰቡን በመደገፍ አባል ሃገራት ውሳኔ ያስተላለፉበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።[4]

[3] Draft resolution referred to the high level plenary meeting of the General Assembly by the General Assembly at its fifty-ninth session. 2005. World Summit out come. Human Security. p 32.

በርግጥ በዚህ የHuman Security አስተሳሰብ ላይ መጠነኛ የሃሳብ ልዩነቶች ይንፀባረቃሉ። መሠረታዊው የልዩነቶቹ ባህርይ በዚህ የደህንነት አስተሳሰብ ስር ምን ምን ጉዳዮች መካተት ይገባቸዋል? እስምን ድረስ ጉዳዮን በመግፋት ውጤት ማምጣት ይቻላል? በሚለው ላይ ያተኮረ ነው። ከዚህ በዘለለ ግን በመሠረታዊው አስተሳሰብ ላይ ሰፊ መግባባትና ድጋፍ አለ። ከዚህ አንፂር በዚህ የHuman Security አስተሳሰብ ዙሪያ የሚነሱት ሃሳቦች በሁለት የአስተሳሰብ ዘርፎች ይፈረጃሉ። አንዱ ነፂነት ከፍላጎት (Freedom from want) ተብሎ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎት መሟላት ዙሪያ ያሉትን የሰው ልጆች ፍላጎቶች ከተሟሉ፤ መሠረታዊ ጉዳይ ተፈቷል ማለት ነው ከሚል አስተሳሰብ የሚነሳ ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ ነፂነት ከፍርሃት (Freedom from fear) በሚለው አስተሳሰብ ዙሪያ ያጠነጥናል። የዚህ የሁለተኛው የአስተሳሰብ ዘርፍ መነሻው በአንድ በኩል አሁን ካለው የፖለቲካ ተርአየ ማለትም መንግስታት የፖለቲካ ዕድሜያቸውን ለማራዘም የሚጠቀሙበትን የጭቆና ስልቶች በማጤንና ይህ ደግሞ በኢኮኖሚያዊ ዕድገትና በመልካም አስተደደር መስፈን ላይ ያለውን ተፅዕኖ ከመገንዘብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፈጥኖ ለውጥ ሊመዘገብበት ይችላል ከሚል እምነት የሚነሳ ነው። በርግጥም ነፂ ፍላጎቱንና የፈጠራ ችሎታውን የሚጠቀም ሕብረተሰብ በነፂነትና በስፋት እንዲንቀሳቀስ ካልተደረገ፤ ኋላ ቀር በሆኑት ሃገራት ያለው ኢኮኖሚያዊ ችግር የፖለቲካ ስልጣን በጨበጡ ኃይሎች አስተሳሰብና ፍላጎት ብቻ የሚፈታ አይደለም።

እንዲያውም ይህ የሕብረተሰቡን ችግሮች የመፍታት አቅም እጅግ ሊጎዳው ይችላል። ቀደም ብሎ እንደተገለፀውም ለግጭቶችም መነሻ ሊሆን ይችላል። ከዚህ አንፂር የ2005 የHuman Security Report የሚከተለውን ይላል። "The most insidious forms of repression occur where the coercive power of the state is so pervasive that actual physical repression rarely has to be used. What might be called 'rule by fears' is most prevalent in highly authoritarian states"[5]

እንደዚህ ዓይነት ፖለቲካዊ ስርዓት ባለበት ማንኛውም ሃገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማስመዝገብ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል። ስለሆነም ከHuman Security አንፂር በአጭር ጊዜ ፈጣን ለውጥ ሊመዘገብበት የሚችልውና የሰዎችን ዕምቅ ዓቅም ነፂ በማውጣት ለኢኮኖሚያዊ እድገት የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር Freedom from Fear የላቀውን ትኩረት ማግኘት አለበት ተብሎ ይታመናል።

በዚህ አሁን ሰፋ ባለ መልኩ ተቀባይነት እያገኘ ያለው የሃገራዊ ደህንነት አስተሳሰብ የግለሰብንም ይሁን የመንግስትን (State) ደህንነት አጣምሮ በመያዝ ይተረጉማል። ሁለቱ ፅንሰ ሃሳቦች ማለት የ"National Security" አስተሳሰብ እየተባለ የሚታወቀው conventional አስተሳሰቡና አሁን በስፋት ተቀባይነት እያገኘ ያለው የHuman Security አስተሳሰብ በተቃርኖ የሚቆሙ አስተሳሰቦች አይደሉም። እንዲያውም እርስ በርስ የሚተጋገዙ አንዱ ሌላኛውን የሚያጠናክር እንዲሆን ተደርጎ ሊቀረጽና ሊተገበር ይችላል። ከዚህ አንፂር የበለፀጉት ሃገራት (OECD) በማደግ ላይ ከሚገኙት ሃገራት ጋር ከሃገራዊ ደህንነት ስራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ያላቸውን ዝምድና አቅጣጫ ለማስያዝ ይረዳል ብለው ባወጡት Hand Book ላይ የሚከተለውን አስፍረዋል።

[5] Human Security Report 2005. War and Peace in the 21st Century. Oxford University Press. 2005 p7.

"Security is fundamental to people's livelihood, reducing poverty and achieving the Millennium Goals. It relates to personal and state safety, access to social services and political processes. It is a core government responsibility. Necessary for economic and social development and vital for the protections of human rights.[6]

ይህ አስተሳሰብ በአንድ በኩል የደህንነት ጥያቄ መሠረታዊ ከሆነው የሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር በእጅጉ የተቆራኘና ድህነትን ለማጥፋትና የሚሊኒየሙን ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ይገለፂል። ከዚህ ጋር አብሮም ደህንነት ማለት የግለሰቡንም የመንግስትንም ደህንነት በጋራ አጣምሮ የያዘ መሆን እንዳለበት ያመለክታል።

እንግዲህ ጉዳዩ የሚሆነው ይህ በዓለማዊ የሁኔታዎች መለዋወጥ እየሰፋ የመጣውና በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘው አስተሳሰብ የሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን በመቅረጽ ላይ ምን ያህል አስተዋፅኦ አለው ብሎ ማጤን ይሆናል። የHuman Security አስተሳሰብ በሃገራዊ ደህንነት አስተሳሰባችን ውስጥ ትልቅ ግምት ሊሰጠው ይገባል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ በመምጣቱ ብቻ ሳይሆን ግለሰቦችን ያለፍርሃትና መሸማቀቅ ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል በመሆኑ፣ ከኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ አድልዎና የተዛባ አስተዳደር የሚመነጩ ግጭቶችን ከማስወገድ አንፂር ቀላል ያልሆነ አስተዋፅኦ ስለአለው በአጠቃላይ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታም ትልቅ መሠረት ስለሆነ።

2. የግጭቶች ባህርይ እየተለወጠ መምጣቱ

ሌላው ዓብይ ክስተት የጦርነቶችና የግጭቶች ባህርይም እየተለወጠ መምጣቱ ነው። በተለይ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት ወዲህ ዋናው የጦርነቶች/የግጭቶች መከሰቻ መልክ በሃገራት መካከል የሚደረግ ጦርነት ሳይሆን በአንድ ሃገር ውስጥ የሚደረግ የእርስ በርስ ግጭት ሆኗል። አሁን ባለንበት ሁኔታ በሃገራት መካከል የሚደረገው እንደ የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት የመሰለው ክስተት እንደጉድ የሚታይበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ይህ ሁኔታ በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉትን ጦርነቶችና ግጭቶች የሚያጠናው ሲዊድን አገር ያለው የStockholm International Peace Research Institute በየጊዜው እያሳተመ የሚያወጣው እትሙ ላይ የሚከተለውን አስቀምጧል። "State-to-state conflict, at least when both sides act on purely national initiative, has become a rarity" [7]

ከዚህም በመቀጠል ወደ ዝርዝር ጉዳዮች በመግባት የሚከተለውን ያትታል።

> "In the 13 year-post cold war period 1990 - 2002 there were 58 different major armed conflicts in 46 different locations. All but three of the major armed conflcits registered for

[6] Dac Guidelines and reference Series - Security System Reform and Governance Policy Statement.

[7] SIPRI Yearbook 2003. Armaments, Disarmament and International Security. Introduction, p 3 .

1990 - 2002 were internal: that is, the issue concerned control over the government or territory of one state. The three interstate conflicts in the period 1990 - 2002 were Iraq versus Kuwait, India versus Pakistan, and Ethiopia versus Eritrea.[8]

በሃገራት መካከል የሚደረገው ጦርነት እጅግ በጣም እየቀነሰ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን በሃገራት ውስጥ የሚደረገው የእርስ በርስ ጦርነትም እየቀነሰ መጥቷል። ይህ ጉዳይ በአህጉራችን በአፍሪካም የቀነሰ ቢሆንም የእርስ በርስ ግጭቶቹ መብዛትና በዚህ ምክንያት በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ የሚደርሰው ውድመት ግን አሁንም በጣም ከፍተኛ ነው። በዚህ ወደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በተሸጋገርንበት ወቅት ከሰሐራ በታች ያለው አፍሪካ በእርስ በርስ ግጭት ምክንያት የሚጠፋው የሰው ሕይወት በሌላው ዓለም ከሚጠፋው በሙሉ ተደምሮ ይበልጣል።[9]

ስለዚህ የእርስ በርስ ግጭቶች ጉዳይ ለኛ ለአፍሪካዊያን እጅግ አሳሳቢ የሆነ ጉዳይ ነው። ይህ በሃገራት ውስጥ የሚደረገው የእርስ በርስ ግጭት በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ያለው ተፅዕኖ Paul Collier እና Anke Hoffler የተባሉ ተመራማሪዎች በዝርዝር አቅርበውታል።[10] የእርስ በርስ ጦርነቶች የሃገራትን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ምን ያህል ወደኋላ እንደሚመለስ ከዚሁ ጥናት ማየት ይቻላል። በሃገራት ውስጥ የሚደረገው የእርስ በርስ ግጭት መነሻዎቹ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ቢሆኑም በእነPaul Colleir ጥናት የታየው ዋነኛው ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ይመስላል። በአንድ ሃገር የሚኖሩ ህዝቦች ከፍተኛ ጠቀሜታ ላላቸው የሃገር ተፈጥሮአዊ ሃብት ያላቸው የተጠቃሚነት መብት ዋናው ምክንያት ይመስላል። ከዚህም ጋር ለፖለቲካዊ ስልጣንና በሃገራቸው ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው የመወሰን መብትም ለእርስ በርስ ጦርነቶች እንደመነሻ ይሆናሉ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይ ደግሞ በአህጉራችን አፍሪካ ያለው የጦርነቶች ባህርይ እየተለወጠ መምጣት የሚያመለክተው ጉዳይ ቢኖር ዋነኛው የሃገር ደህንነት ትልቅ አደጋ ውስጥ የሚወድቅበት የስጋት አቅጣጫ የውጭ ወራሪ ኃይል ሳይሆን በሃገር ውስጥ የሚከሰተው ችግር መሆኑን ነው። የሃገር ውስጥ የደህንነት አደጋው ደግሞ ከኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች የሚመነጨና በእነዚህ ችግሮች ምክንያት የሚስፋፉ ናቸው። በመሆኑም መንግስታት የሃገራቸውን ደህንነት ለማስጠበቅ ካሉዋቸው መሣሪያዎች ለዚህ ችግር መፍቻ የበለጠ የተመቻቹትን እየመረጡ እነሱን አጠናክረው መጠቀም እንዳለባቸው ያመለክታል። የHuman Security አስተሳሰብ መንግስታት በፖለቲካዊና ማህበረ ኢኮኖሚያዊ መፍትሄዎች (ዲሞክራሲን በማስፋፋት፣ ሰብአዊ መብትን በማክበር፣ የፍትህ ስርዓቱን ከስራ አስፈፃሚው ተፅዕኖ ነፂና የተቀላጠፈ ፍትህ የሚሰጥ እንዲሆን በማድረግ፣ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ተቀላጥፎ በመፍታትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲፋጠን አጋዥ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፤ ማህበራዊ ችግሮችን መፍታት) ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ያመላክታል። በዚህም ውጤት

[8] Ibid. pp109-111

[9] Human Security Report 2005.

[10] "The Challenge of reducing the Global Incidence of Civil Wars". Paul Collier and Anke Hoeffler. Center for the Study of African Economies. Department of Economics. Oxford University. Resized, March 26, 2004.

በማምጣት የበለጠ ደህንነቱ የተረጋገጠና ሰላም የሰፈነበት ሃገር መገንባት እንደሚቻል ይጠቁማል። ይህ አስተሳሰብ የሃገር መከካከያ ሰራዊት ግንባታ አያስፈልግም ማለት ነው የሚለውን ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። የሃገር መከካከያ ሰራዊት ግንባታ ያስፈልጋል። ትንሽ ወረድ ብለን ይህንን በሚመለከት እናነሳለን። የሃገር መከላከያ ኃይል ግንባታ ግን ሚዛኑ አሁን ባለው ሁኔታ ይስተካከላል ማለት ይሆናል።

የሃገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታና ስምሪት አሁን በዓለምአቀፍ ደረጃ እየታየ ካለውና እኛንም በሚመለከተን ከጦርነቶችና ግጭቶች ባህርይ አንፂር እንዴት መታየት አለበት ተብሎ መታሰብ ይኖርበታል። በርግጥ ሁሉም በሃገር ውስጥ የሚቀሰቀስ የእርስ በርስ ጦርነቶች በፖለቲካዊ መንገድ ብቻ ይፈታሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። የተቻለውን ያህል ፖለቲካዊ ጥረት ተደርጎም በዚሁ መንገድ ብቻ የማይፈቱ ችግሮች ይኖራሉ። ስለዚህ መንግስታት የሃገራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ ተቋማት መገንባታቸው አይቀርም። መንግስት የሚገነባቸው የሃገርን ደህንነት የሚያስጠብቁ ተቋሞች (የሃገር መከላከያ ኃይል አንዱ ነው) ግዳጃቸውን እንዴት ይወጡታል፣ ከፖለቲካዊውና ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ጋር እንዴት ተቀናጅተው ውጤታማ ማድረግ ይቻላል የሚለው ሊታሰብብት ይገባል። ይህ አካሄድ በአንድ በኩል የሃገርን ደህንነት ከማስጠበቅ ሰላምና ፀጥታ እንዲሰፍን ከማድረግ አኳያ ውጤታማ እንዲሆን ከማስቻሉም በተጨማሪ ለሃገር መከላከያ ኃይል የሚወጣውን ወጪ እንዲቀንስና ለሌሎች የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፕሮግራሞች እንዲውል ያስችላል።

3. የግሎባላይዜሽንና ዓለም አቀፋዊ ሕግጋት ተፅዕኖ

ግሎባላይዜሽን ማለት በሃገራትና በህዝቦች መካከል በየግዜው ይበልጥ እየሰፋና ጥልቀት እያገኘ ተፅዕኖውም ከፍተኛ እየሆነ የሚሄድ በሁሉም መስኮች ያለውን ግንኙነት ይገልፂል። ይህ ግንኙነት በአንድ ወቅት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚከሰት ሳይሆን ለረጅም ጊዜ የሚቆዩና በየጊዜው ጥልቀትና ስፋት እያገኘ የመጣ በግልፅ የሚታይ ቅጽ (Pattern) ያለው የእርስ በርስ መተሳሰርን ያመለክታል። ይህ በኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና በሃገራዊ ደህንነት ጉዳዮች ላይም የሚታይ ክስተት በየጊዜው ጥልቀትና ስፋት እያገኘ የሚሄድና በዚህም ምክንያት ቀስ በቀስ የመንግስታትን የእርሰ በርስ ግንኙነት ባህርይ መልክና ይዘት እየለወጠ የሚሄድ የዓለማችን የወቅቱ ክስተት ነው። "simply put globalization denotes the expanding scale, growing magnitude speeding up and deepening impact of inter regional flows and patterns of social interactions"[11]

በዚህ ዓለም አቀፋዊ ክስተት ላይ እንደማንኛውም ፖለቲካዊና ማህበራዊ ክስተት ልዮነቶችና ክርክሮች አሉ። ዓለም አቀፋዊውን የፖለቲካዊ እንቅስቃሴና በሃገራት መካከል ያለውን ግንኙነት ከተለያየ ስነ ሃሳባዊ መነሻዎች እየተነሱ የሚተነትኑት ሊቃውንት የግሎባላይዜሽንን ክስተት (phenomena) እንደየመነሻቸው ይተነትኑታል። የሊብራል፣ የሪያሊስትና የኮሚኒስት አስተሳሰብ አቀንቃኞች እንደየስነሐሳባዊ መነሻቸው የግሎባላይዜሽን ምክንያቶች ዋናዎቹ አንቀሳቃሽ ኃይሎችና በውጤቱም ተጠቃሚዎች የትኞቹ እንደሆኑ

[11] David Held & Anthony McGrew. The Global Transformations Reader. An Introduction to the Globalization Debate. 2002. p4

በመግለጽ ላይ የተመሠረተ ልዮነቶች አሉዋቸው። እንደክስተት ዓለማዊ ትስስሩንና ከዚህ የሚመነጩ እንድምታዎች የመኖራቸው ጉዳይ ግን በማንም የሚካድ አይደለም። ግሎባላይዜሽን እንደማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የተወሰኑ ሃገራትንና (የበለፀጉትን) የሕብረተሰብ ክፍሎች ይበልጥ የሚጠቅም ክስተት ነው። ይህ በመሆኑም ግሎባላይዜሽን በፍትሕና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ስርዓት ወደማምጣት ያመራል ማለት እንዳልሆነ እንዳውም በጣም ከፋፋይና ለአዳዲስ ግጭቶች መነሻም ሊሆን እንደሚችል ይገለፂል።

የዚህ የግሎባላይዜሽን አንዱ አካልና መገለጫው አሁን ያለው እጅግ ሰፊ የሆነ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶችና እነዚህ ድርጅቶች (UN, IMF, World Bank, WTO, EU, AU etc...) የተሰማሙባቸውና የሚመሩባቸው ሕግጋት ናቸው።[12] በእነዚህ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶችና ስምምነቶች ምክንያት እያንዳንዱ ሃገር የሚያወጣው ፖሊሲና አቅጣጫ እነዚህን ስምምነቶች ግምት ውስጥ ያሰገባ እንዲሆን ይገደዳል። ግሎባላይዜሽን እና ከዚህ ጋር አብረው እየተጠናከሩ የመጡት ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶችና እነዚህ ድርጅቶች የሚመሩባቸው ሕጎች፣ ይህ ሁኔታ ይበልጥ እንዲጠናከር ከረዳው ሰፊና ቀልጣፋ የመገናኛ መሣሪያዎችና የሲቭል ማህበረሰብ ንቁ ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ የመንግስታት ባህርይ እንዲቀየር እያስገደደ መጥቷል። አሁን የሃገር ሉዓላዊነት የሚባለው አስተሳሰብና አተገባበር በእጅጉ ተለውጧል። የአንድ ሃገር መንግስት ፖለቲካዊ ስልጣን በዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶችና ሕግጋት እየተሸረሸረ መጥቷል። ከዚህ አንፂር በጉዳዩ ላይ ጥናት ያካሄዱ ሊቃውንት ይህንን ሁኔታ በሚከተለው መንገድ ይገልጹታል።

"The paradox and novelty of the globalization of organized violence today is that National Security has become a multilateral affair. For the first time in history, the one thing that did most to give modern nation states to focus and a purpose, and which has always been at the very heart of statehood, can now only be realized effectively if nation states come together and pool resources, technology, power and authority State legitimacy is at issue because with greater regional and global interdependences, states can't deliver fundamental goods and services to their citizens without international cooperation.[13] አሁን ዓለም ከደረሰበት የግሎባላይዜሽን የዕድገት ደረጃ እንደረሃብ እና ከፍተኛ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ይቅርና የአንድ ሃገር ሉዓላዊነት ከውጭ ወራሪ ኃይሎች የመጠበቅ ግዳጅ (ብዙውን ጊዜ የመንግስታት ዋነኛ ስራ ተደርጎ የሚወሰደው) እንኳን አንድ ሃገር ብቻውን የሚወጣው ጉዳይ አይደለም።

ይህ በመሆኑም ባለንበት ወቅት ቀደም ብሎ የነበረው የሉዓላዊነት አስተሳሰብ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሳይሆን የአንድን ሉዓላዊ ሃገር አስተዳደር ከተበላሸም ሌሎች ሃገራት ጣልቃ በመግባት የዜጎችን ሰብአዊ መብቶች ማስከበር እንደሚችሉ ቢያንስ በአስተሳሰብ ደረጃ መግባባት ላይ ተደርሷል። ከዚህ አንፂር Responsibility to Protect (R2P) እየተባለ የሚታወቀው የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ በ2005 ስብሰባው ላይ ያስተላለፈው ውሳኔና የአፍሪካ ሕብረት (Constituive Act) በአፍሪካ መርሃያን መንግስታት የፀደቀው እንደ አብነት ይጠቀሳሉ።

[12] Ibid. p12

[13] Ibid. pp12 - 13

"The right of the Union to intervene in a Member State pursuant to a decision of the Assembly in respect of grave circumstances, namely: war crimes, genocide and crimes against humanity"[14]
ይህ አንዱ ሃገር በሌሎች ሃገሮች ላይ ጥገኛ የመሆን ጉዳይ ደግሞ እንደኛ በመሰሉት በኢኮኖሚ ኋላ ቀር በሆኑት አገሮች ላይ ይበልጥ ይጠናከራል። እኛ ለሃገራችን ይጠቅማል ብለን የምናምንበትን የፖለቲካና የኢኮኖም የዕድገት አቅጣጫ ያለምንም ተፅዕኖ ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም። አሁን በዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያለውን የመንግስታት ባህርይ ባንወደውም የተወሰነ ዋጋ ከፍለን ተቀብለነው መቀጠል ነው የሚቻለው። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ በዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው የመንግስታት ባህርይ መቅረጹ ላይ እንደኛ የመሰሉት ሃገራት ያላቸው ድርሻ እጅግ በጣም አነስተኛ መሆኑ ነው። ምንም እንኳን በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት ያላቸውን ተሰሚነት ከፍ ለማድረግ እየተደራጁ ሁኔታውን ለመጋፈጥ ቢሞክሩም እስከ አሁን ድረስ መሠረታዊ ይዘቱን መቀየር አልቻሉም። ይህንን ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ የሚቀርጹት ኃያላን ሃገራት ናቸው።የግሎባላይዜሽን ክስተት በኢኮኖሚያዊ፣ በዴሞክራታይዜሽንና በሰብአዊ መብቶች መከበር እንቅስቃሴ ላይ ብቻ የታጠረ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። የበለፀጉት ሃገራት ባቋቋሟቸው የፋይናንስና የኢኮኖሚ ተቋሞቻቸውና በግላቸው ከሚፈጥሩት ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ በተጨማሪ በሃገራት ደህንነት፣ ፖሊሲና እንቅስቃሴም ላይ ተመሳሳይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ። በዓለም አቀፋዊው የደህንነት ሁኔታ (Security Environment) በሽብርተኝነት ላይ በአሜሪካ የታወጀው ጦርነት ዓለምን ከማተራመሱ በተጨማሪ በእያንዳንዱ ሃገር የደህንነት ፖሊሲና እንቅስቃሴ ላይ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። ይህ ማለት የአንድን ሃገር ሉዓላዊነት ለማስከበር የሃገሪቱ መንግስትና ህዝቦች በመረጡት የኢኮኖሚና የዕድገት አቅጣጫ ያለምንም የውጭ ተፅዕኖ እንዲቀጥሉ ለመከላከል ተብሎ የሚገነባው የሃገር መከላከያ ሰራዊት ግዳጅ በግሎባላይዜሽን ምክንያት ተሸርሽሯል። የግሎባላይዜሽን ውጤት ይህ ነው።

ስለ ግሎባላይዜሽንና ዓለም አቀፋዊ ሕግጋት ስናነሳ አንድ መነሳት ያለበት ጉዳይ አሁን በስራ ላይ ያሉት ሕግጋትና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት በዋናነት በምዕራቡ ዓለም የተጠነሰሱና ለምዕራቡ ዓለም ጥቅም ማስጠበቅያ የሚውሉ ናቸው። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ በነበራቸው ወታደራዊና ፖለቲካዊ የበላይነትና በተለይ ደግሞ በቀዝቃዛው ጦርነት አሸንፈው መውጣታቸው ይህንን አጠናክሮታል። አሁን በቅርቡ ደግሞ እንደቻይና የመሰሉ ሃገራት በዓለም አቀፍ ግንኙነት ጠንክረው ብቅ እያሉ ይገኛሉ። ሩስያዊያንም በቀዝቃዛው ጦርነት ከደረሰባቸው ሽንፈት አገግመው በኢኮኖሚም በወታደራዊ ኃይላቸውም ጠንክረው መውጣታቸውን በቅርብ ጊዜ በጆርጂያ ላይ በወሰዱት እርምጃና ይህንን ተከትሎ ከምዕራቡ ዓለም ጋር በተፈጠረው ፍጥጫ መንፀባረቅ ጀምሯል። ይህ ለወደፊት በዓለም አቀፋዊ የደህንነት ሁኔታ ምን እንድምታ ይኖረዋል ተብሎ መታሰብ ይኖርበታል። ወደፊት የሚመጣውን ሁሉ መተንበይ አስቸጋሪ ቢሆንም ቀላል ያልሆነ ተፅዕኖ እንደሚኖረው አይካድም። ሆኖም እስከአሁን ድረስ የተደረሰበትን ደረጃ በተለይ ህዝቦች መብቶቻቸውን ለመጠበቅ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ወደኋላ ይመልሰዋል ብሎ ማሰብ አይቻልም።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ መጠነ ሰፊ የሃገራትና የህዝቦች ሁሉን አቀፍ (ኢኮሚያዊ፣ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ፀጥታዊ) ትስስርና ፈጣን ግንኙነት በሃገራትና በህዝቦች ላይ ያለውን አስተሳሰብ ይለውጠዋል። ህዝቦች

[14] African Union Constitutive Act. Principles. Article 4 (h). Durban, South Africa. July 2002

በፖለቲካው በእኩልነት በሰፊ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎና በህዝቦች ፈቃድና ምርጫ ለሚመሰረት መንግስት፣ በኢኮኖሚውም ወደተሻለ የኑሮና የዕድገት ደረጃ ለመድረስ ያላቸውን ፍላጎት ይበልጥ ያጠናክረዋል። ይህ ለዴሞክራሲ፣ ለሰብአዊ መብቶች መከበር፣ ለተሻለ የኑሮ ደረጃና በጠቅላላውም ለነቃ የህዝብ ተሳትፎ የሚደረገው እንቅስቃሴ በግሎባላይዜሽን ይጠናከራል። በተገቢው መንገድ ካልተፈታ ደግሞ ለእርስ በርስ ግጭቶችና ፖለቲካዊ አለመረጋጋት መንስኤ ሊሆን ይችላል። ይህ በሃገራዊ ደህንነት ማስጠበቅ ላይ ያለው እንድምታ ምንድነው ተብሎ መጤን ይገባዋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሃገራት መሃከል የሚደረገው ጦርነት ቁጥር እየቀነሰ ይመጣል ተብሎ ይታመናል። እስከአሁን ያለው ሁኔታ በተለይ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ ያለው ሁኔታ ይህንን ይደግፋል። ስለዚህ በሃገራት መሃከል የሚፈጠርን ጦርነትና ግጭት በሰላማዊና ዴሞክራሲያው መንገድ ለመፍታት ከፍተኛ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ጫና ይኖራል።

በአጠቃላይ ሲታይ የግሎባላይዜሽን ክስተት እያደገ መጥቶ ዛሬ በአንድ ሃገር (በሱዳን ዳርፉር) ላይ በተቀሰቀሰ የእርስ በርስ ግጭት በዓለም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ስልጣን ላይ ያለን የአንድ ሃገር መሪ በጦር ወንጀለኛነት መክሰስ በሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። በአንድ ሃገር (ዚምባቢዌ) በተፈጠረው የአስተዳደር መበላሸትና ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጣሳቸው ሰበብ ሆኖ በተፈጠረው ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ጫና በስልጣን ላይ ያለና ራሱ ባዘጋጀው ምርጫ አሸንፊያለሁ የሚለው የሙጋቤ መንግስት ተገዶ፣ ከተቀዋሚው የፖለቲካዊ ድርጅት ጋር በስልጣን ክፍፍል ላይ እንዲደራደር ተደርጓል። በርግጥ ዓለም አቀፋዊው ስርዓት የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤትንም ጨምሮ የወሰናቸውን ውሳኔዎች ለማስተግበር የሚያስችል አሰራርና ኃይል የለውም። ውሳኔዎቹ ራሳቸው ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለውን ባህርይ በማያሻማ መንገድ ያስቀምጣሉ። እየዋለ እያደረ ደግሞ ቀላል ያልሆነ ዋጋ መከፈሉ አይቀርም። እነዚህ በጣም ከፍተኛ ለውጦች ናቸው። እንደዚህ ዓይነት ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ የአንድን ሃገር ካሉዓላዊነትካ ለማስጠበቅ ተብሎ የሚገነባ ሰራዊትና ግዳጅ ከሁኔታው ጋር እንዲጣጣም ማድረግ የግድ ይላል። ይህ ሲሆን ደግሞ በግዳጅ አፈፃፀም ውጤታማነትና በሃብት ቁጠባ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል።

4. የሀገር መከላከያ ሰራዊት ያስፈልጋል

ከላይ ሲገለጽ ከነበረው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ አንፃር በመነሳት ለመሆኑ የሃገር መከላከያ ሰራዊት መገንባትና ማሰማራት ያስፈልጋል ወይ ተብሎ መጠየቅ ይገባዋል። ይህ ጥያቄ ደግሞ እንዲሁ በአጠቃላይ ያስፈልጋል አያስፈልግም ተብሎ የሚመለስ ሳይሆን እያንዳንዱ አገር ከተጨባጭ ሁኔታው እየተነሳ ሊመልሰው የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል። የሃገር መከላከያ ሰራዊት መገንባት ያስፈልጋል ከተባለም ግዳጁ ምን ይሁን? ይህንን ግዳጅ ለመፈፀም የሚያስፈልገው አቅምና አደረጃጀት ምን ይሁን? ተብሎ መመለስ ይኖርበታል። በሃገራችን ሁኔታ የሃገር መከላከያ ሰራዊት ያስፈልገናል። የሃገር መከላከያ ሰራዊት ያስፈልገናል ብቻ ሳይሆን ይህ ኃይል በግዳጅ አፈፃፀሙ ውጤታማ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። ይህንን ሁኔታ ትንሽ ዘርዘር በማድረግ እናየዋለን።

የሃገር መከላከያ ሰራዊት የሚያስፈልግበት አንዱ ምክንያት (ይህ ለሁሉም ሃገራት እንደምክንያት ሊቀርብ ይችላል) አሁን ያለው ዓለማዊው የፖለቲካ ስርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ ስርዓት (order) ለማስያዝ የሚያስችል አሰራር አለመኖሩ ነው። የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ቢሆን ለአንድ ሃገር ራስን የመከላከል መብት ነው የሚያጎናጽፈው። ከዚህ አልፎ ጥቃት የሚደርስባቸው ሃገራት ለልዕለ ኃያላን ሃገራት ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ካላቸው በእነዚሁ ልዕለ ኃያላን መሪነት የተባበሩት መንግስታት ኃይል የተጠቁትን ሃገራት ለመከላከል ሲሰማራ ተስተውሏል። (Kwait 1991) ከዚህ ውጭ ግን ያለው ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ስርዓት ሃገራት ከቻሉ ራሳቸውን እንዲከላከሉ ነው የሚፈቅደው።

ከላይ ሲገለጹ የነበሩት ግሎባላይዜሽን እንዲስፋፋና እንዲጠናከር እያደረጋቸው ያለው ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ሕግጋት የመንግስታትን ባህርይ ለመተንበይ የሚቻልና (Predictable) ተቀባይነት (credible) ያለው እንዲሆን በማድረግ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ቢኖራቸውም፤ በሃገራት መሃከል ያለው ጦርነት በእጅጉ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም፤ ዓለም አቀፋዊው የፖለቲካ ስርዓት መንግስታት ራሳቸውን በራሳቸው የሚከላከሉበትን ሕግና ስርዓት ከማውጣት የዘለለ ስርዓት (order) ለማስያዝ የሚያስችል ሁኔታ አልፈጠረም። በሪያሊስት የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚያምኑ ሊቃውንት እንደሚሉት ያለንበት ዓለም ፖለቲካዊ ስርዓት ካራስ አገዝና ስርዓት አልባካ (Self Help and anarchic) መሆኑን አላቆመም። ስለዚህ ሃገራት አሁን ተፈጥሮ ካለው አለም አቀፋዊና አህጉራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ራሳቸውን የሚከላከሉበትና ባለው ዓለማዊ ሁኔታ ስር ሆነው በመረጡት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የዕድገት አቅጣጫ እንዲከተሉ፣ ይህንን በመሚረር ጥቃት ሲመጣባቸው ደግሞ ለመከላከል የሚያስችል ኃይል መገንባት ይገባል።

በተለይ ወደሃገራችን ሁኔታ ስንመጣ ደግሞ ሃገራችን በአህጉራችን በጠቅላላ በተለይ ደግሞ በአፍሪካ ቀንድ ያላትን አጠቃላይ ሚዛን (የአካባቢው የሰላምና የፀጥታ ዋነኛ ኃይል መሆን ትችላለች) በማሰብ የሃገር መከላከያ ኃይል ያስፈልጋታል። ይህ ማለት አካባቢውን ለመጠበቅ ኃይል እናደራጅ ማለት አይደለም። ግን በአካባቢው ያለንን ተቀባይነትና ሚዛን ጠብቀን ለመቀጠል ከተቻለም ሚዛኑን ይበልጥ ወደኛ ያጋደለ እንዲሆን ለማድረግና ይህንን ሁኔታ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ለተረጋጋ የአካባቢ ሰላም እንድንጠቀምበት አስበን መስራት ይኖርብናል። ከዚህም አልፎ እኛ ያለንበት ጆግራፊካዊ አቀማመጥ ሁለት ትላልቅ ስልጣኔዎችና ባህሎች በሚገናኙበት አካባቢ ነው። የዓረብ እስልምና ስልጣኔና ባህል በአንድ በኩል የክርስትና ሃይማኖትና ሌሎች አፍሪካዊ ሃይማኖቶች፣ ስልጣኔና ባህል በሌላ በኩል። ይህ ክስተት ለሰላምና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ መነሻ ሊሆን የመቻሉን ያህል በሌላ በኩል ደግሞ ለጦርነትና ከፍተኛ የእርስ በርስ ግጭት መነሻ ሊሆን ይችላል። ይህ ሁኔታ በተገቢው መንገድ መታየት ይኖርበታል። የሃገራችን የኋላ ታሪክ ሲታይም ታሪካችን አያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡባቸውን ጠላቶች የመዋጋትና እነዚህን የመመከት ታሪክ እንደሆነ ማየት ይቻላል። የአካባቢያችን ፖለቲካዊ ሁኔታ በሃገራችን ውስጥ ለሚኖረው ሰላምና መረጋጋትም ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው።

ከዚህ ከአካባቢያችን ሁኔታ ጋር የሚዛመድ ሌላ ሁኔታ ደግም አገራችን እጅግ ከፍተኛ የውሃ ሃብት አላት። የውሃ ሃብት በጣም ተፈላጊ በሆነበት በሳሃራ ደቡባዊ ጫፍ ላይ ሆነን ግን ከኛም አልፎ ጎረቤቶቻችንን

የሚመግብ የውሃ ሃብት አለን። የዚህ ሃብት ተፈላጊነት በጊዜ በኛው በራሳችንም በጎረቤቶቻችንም እየጨመረ ይሄዳል። በሃገራችንና በጎረቤቶቻችን ያለው የህዝብ ብዛት መጨመር፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ግፊት የውሃ ሃብትን ተፈላጊነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር ያደርገዋል። የኛም የኢኮኖሚ ዕድገት አቅጣጫችን ከውሃ ሃብት አጠቃቀም ጋር የተዛመደ ነው። ይህ እንዳይሆን የሚፈልጉ የውጭ ኃይሎች አሉ። እነዚህ የውጭ ኃይሎች በአገር ውስጥ ሊጠቀሙባቸው በሚችሉ ኃይሎችና በራሳቸው ኃይልም ጭምር በሃገራችን ሰላምና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዳይኖር ይጥራሉ። ይህ ለጦርነት ወይም ለእርስ በርስ ግጭት መነሻ ሊሆን ይችላል።

ያለንበት አካባቢ ሰላምና ፀጥታ የናፈቀው ከአህጉራችን አፍሪካም ቢሆን የበለጠው የግጭት ቀጠና እንደሆነ ይነገርለታል። ይህ ሁኔታ ምናልባት ከጆግራፊያዊ አቀማመጣችን ጋር የተዛመደ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን የአፍሪካ ቀንድ የታወቀ የግጭቶች ቀጠና መሆኑ ግልጽ ነው። ከዚህ ጋርም እንደኢሳያስ የመሰለ መሪ ከአቅሙና ሁኔታዎች ከሚፈቅዱለት በላይ የአካባቢው ልዕለ ኃያላን ለመሆን በመንጠራራት በየግዜው አካባቢውን በጦርነት ሲያምስ፣ እንደ ሶማሊያ የመሰለ ለ17 ዓመታት የዘለቀ መንግስት የሌለው ሃገር በመሆኑም ለማንኛውም በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ለመፈፀም ለሚፈልግ ኃይል ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ሃገር፣ እንደ ሱዳን የመሰለ በአህጉራችን በርዝማኔውና በጠፋው የሰው ሕይወት ተወዳዳሪ የሌለው የእርስ በርስ ጦርነት ሲካሄድበት ለዓመታት የዘለቀና የወደፊት ሁኔታውም በእርግጠኝነት መናገር የማይቻል ሃገር፣ የወጪና ገቢ ንግድ እንቅስቃሴያችን እንደ ጅቡቲ በመሰለ ትንሽ አገር በማንኛውም የጎረቤት ሃገር ወይም Multi National Cooporation ፖሊሲዎች በትልቁ ሊቀያየሩ በሚችሉ ሃገር ሙሉ በሙሉ ጥገኛ ሆነን፣ የሃገራችንን ደህንነት ለሌላ ኃይል አሳልፈን በመስጠት መቀመጥ አንችልም። ስለዚህ አሁን ባለው ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ህዝባችን የመረጠውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የዕድገት አቅጣጫን የውጭ ተፅዕኖን ተከላክለን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለን የመከላከያ ኃይል ያስፈልገናል።

ሃገራችን የብዙ ብሄርና ብሄረሰቦች አገር መሆኗ ግልጽ ነው። እነዚህ ህዝቦች በሃገራቸው የፖለቲካ ስልጣን/ክፍፍል፣ የሃብት ክፍፍል፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ለመጠበቅ ዋስትና የሚሰጣቸው የፖለቲካ ስርዓት የተመሠረተ መሆኑን ካላረጋገጡ ለመብታቸው ሲሉ የተለያየ መልክ ያለው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላሉ። ይህ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ወደ የእርስ በርስ ጦርነትም ሊያመራ ይችላል። የሃገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ይህንን ያስታውሰናል። ይህ የእርስ በርስ ግጭት ደግሞ በሃገራችን ላይ ጥቅም አለን በሚሉና የሃገራችን ሰላምና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በማይፈልጉ የውጭ ኃይሎች ሊደገፍ ይችላል።

በአገር ውስጥ የሚቀሰቀሱት የእርስ በርስ ግጭቶች በመሠረቱ ፖለቲካዊ መፍትሄ ማግኘት ያለባቸው ገና ሳይጀምሩም ለመከላከል አስፈላጊውን ፖለቲካዊ መፍትሔ መቀመጥ ያለበት ቢሆንም፣ ሁሉም የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ትክክለኛ የህዝብ ብሶት የያዙ ናቸው ሁሉም በፖለቲካዊ መፍትሄ ይፈታሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም። ይህ ጉዳይ እየባሰ መጥቶ የሃገሪቱንና የመንግስትን ደህንነት አደጋ ውስጥ ከመጣሉ በፊት በወታደራዊ ኃይልም ቢሆን መፍትሄ ማግኘት ይኖርበታል። አንድ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ዴሞክራሲያዊ

ስርዓት መገንባትም፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማስመዝገብም፣ ሰብአዊ መብቶች ማክበርም የሚቻለው በወጉ የተደራጀ በሕግ የሚመራ ስርዓት ያለው አገርና መንግስት ሲኖር ብቻ ነው። ይህ መቼመ ቢሆን መዘንጋት የለበትም።

ቀደም ብሎ ከተገለፀው ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና የአካባቢያችን ሁኔታ አንፂር የሃገር መከላከያ ኃይል መገንባት ያስፈልገናል። ይህ አስፈላጊ የሚሆነው የሃገራችንን ደህንነት በመጠበቅ ሰላሙ አስተማማኝ እንዲሆን በማስቻል ለኢኮኖማያዊ ዕድገትና ማህበራዊ ብልፅግናም አዎንታዊና በሌላ መንገድ ሊተካ የማይችል ጠቀሜታም ስለአለው ነው። ይህንን ካልን በኋላ አንድ መቀመጥ ያለበት ጉዳይ ደግሞ የሃገራችን ኋላ ቀርነትና ድህነት ነው። አገራችን በዘመናዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ስልጣኔ ኃላቀር መሆኗና ከዚህ ጋር ተያይዟም በኢኮኖሚ ድሃ መሆኗ ግልጽ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ በሃገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታና ስምሪት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

በአንድ በኩል ያለንበት አካባቢና የኋላ ታሪካችን ጠንካራ የመከላከያ ኃይል እንድንገነባና የሃገራችንን ደህንነትና የመረጥነው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዕድገት አቅጣጫ ከውጭ ጥቃት የመከላከል አስፈላጊነት ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ ድህነታችንና በቴክኖሎጅ እድገት ኋላ ቀር መሆናችን በምንገነባው የመከላከያ ኃይል ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርጋል። በዚህ ሁኔታ የሚገነባው የመከላከያ ኃይል ጥንካሬው የሚመሰረተው ከፍተኛ የህዝብ አመኔታና ድጋፍ ያለው፣ ሃገሪቱ ያቀረበችለትን ትጥቅና የውጊያ መገልገያ መሣሪያዎች በከፍተኛ ውጤት ለመጠቀም የሚያስችል ወታደራዊ ጥበብ ያለው ኃይል ሆኖ እንዲገነባ በማድረግ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች አሟልተን ማለትም ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍና አሜንታ ያለው፣ ሁኔታዎችን በአግባቡ አገናዝቦ በተነደፈ ፖሊሲና የፖሊሲው ማስፈፀምያ ስትራቴጂ የሚመራ በከፍተኛ ወታደራዊ ጥበብ የታነፀ የመከላከያ ኃይል መገንባት ይገባናል።

4. የሀገር መከላከያ ኃይልና የኢኮኖሚ ዕድገት

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የሃገር መከላከያ ኃይል በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ አወንታዊ አስተዋፅኦ የሚኖረው የተሰጠውን ግዳጅ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መንገድ መፈፀም ሲችል ነው። እንደሚታወቀው የአንድ ሃገር ሰራዊት የመንግስት ፖሊሲ ማስፈፀሚያ መሣሪያ ነው። ጦርነት ደግሞ ሌሎች የፖሊሲ አማራጮች ውጤት ሳያስገኙ ሲቀሩ ወይም በኃይል መታገዝ ሲያስፈልጋቸው ብቻ እንደየመጨረሻ አማራጭ ሆኖ የሚመረጥ ነው። በድምር እነዚህ በመንግስት ስር ያሉት የመንግስት የፖሊሲ መሳሪያዎች ጦርነትን ወይም የእርስ በርስ ግጭትን ለማስወገድ ሲቻላቸው ነው ሰላም ሰፍኖ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚመጣበትን የተመቸ ሁኔታ መፍጠር የሚቻለው።

ከዚህ ውጭ የአንድ ሃገር የሃገር መከላከያ ኃይል ግንባታ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ግኝቶችን እያስገኘና ሰፋፊ የስራ እድል በመፍጠር የጦር መሣሪያዎችንና ሌሎች የውግያ መገልገያችን እያመረተ እየሸጠ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት በቀጥታ አስተዋፅኦ ያደርጋል የሚለው አስተሳሰብ እንደኛ በመሰሉ በኢኮኖሚያዊ

ደረጃቸው ኋላ ቀር የሆኑ አገሮች እንደማይሰራ በጥናት ተረጋግጧል።[15] ከዚህ በተጨማሪም ተዋጊና አምራች ሰራዊት እንፈጥራለን የሚባለው አንዳንዴ ብቅ የሚል አስተሳሰብ፣ የሰራዊቱን ዋነኛ ስራ (በሰላም ጊዜ ለጦርነት የመዘጋጀቱን) ጎድቶ የአካባቢ አዛዥያችን ኪስ ያሳብጥ እንደሆን እንጂ በሃገራዊ ኢኮኖሚያ ዕድገት ላይ ይህ ነው የሚባል አስተዋጽኦ አይኖረውም።

በእርግጥ ለሃገር ደህንነት ማስጠበቂያ በተለይ ለውትድርና እየተባለ በሚወጣው ወጪና በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ላይ ያለው ተዛምዶ አሃዛዊ Quantitative በሆነ መንገድ ሲታይ ለውትድርና የሚወጣው ወጪ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ላይ በተለይ በማህበራዊ ግልጋሎት ማስፋፋት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ታይቷል።[16] ጉዳዩ ግን መጠየቅ ያለበት ጦርነት ወይም የእርስ በርስ ግጭት ቢቀሰቀስና ሽንፈት ቢያጋጥም ኢኮኖሚያዊ እንዲሆን መለካት ይቻላል? በአንፂሩ ደግሞ የተረጋጋና ረጅም ዕድሜ ያለው ሰላም በማስፈን የሃገር መከላከያ ኃይል ድርሻ ለብቻ ለይቶ መለካት ይቻላል። እነዚህ ጉዳዮች በቁጥር ተለይተው ተቀምጠው በመሠረታዊ የሃገር ደህንነት ጉዳይ ውሳኔ ለመስጠት መነሻ ሊሆኑ አይችሉም። አንድ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ግን ለሃገር መከላከያ የሚወጣው ወጪ ለኢኮኖማያዊ ዕድገትና ለማህበራዊ ብልፅግና ከሚወጣው ወጪ እየተጫረተ ነው የሚወስደው። የሃገር መከላከያ ደግሞ በቀጥታ ሃብት የሚያመነጭ አይደለም። ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል እንጂ በላተኛ ነው። ከዚህ ሁኔታ በመነሳት የሃገር መከላከያ ኃይልን ወጪ ለመቀነስ እና ለኢኮኖሚያዊው ዕድገት የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠር እንዴት መመራት አለበት የሚለው ጉዳይ በወጉ ማጤን አስፈላጊ ነው።

የአገር ሰላምና ፀጥታ ማስጠበቅ በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ መከናወን የሚኖርበት በሕብረተሰብ ዘንድ ተፈላጊ የሆነ ጉዳይ (Social good) ነው ብለናል። ይህንን ተግባር ለማከናወን ደግሞ በሃገር ውስጥ ካለው አጠቃላይ ሃብት ለዚህ ስራ የተወሰነው መጠን መመደብና ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ተብሎ ወጪ ማውጣት ይጠይቃል። በማንኛውም ሃገር የሃገርን ደህንነት ለማስጠበቅ በሚመደበው የሃገሪቱ የሃብት መጠን ድርሻና ለኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ልማት ታስቦ በሚመደበው የሃገሪቱ የሃብት መጠን ድርሻ አመዳደብ ላይ ውጥረት መነሳቱ አይቀርም። ይህ ውጥረት እንደኛ በመሰሉት በኢኮኖሚ ዕድገታቸው ወደኋላ በቀሩትና በጦርነት የፈራረሱ ወይም ያልተሰሩ ማህበራዊና ኢኮኖማያዊ የመሠረተ ልማት አውታሮች በርካታ በሆኑባቸው ሃገሮች ከፍተኛ ይሆናል። ይህንን ውጥረት ፈጽሞ ማስወገድ አይቻልም። ግን በአግባቡ የታሰበባቸውና ተተንትነው የተቀመጡ ፖሊሲዎችንና የፖሊሲዎቹ መተግበሪያ ፕሮግራሞችን በማውጣት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ይቻላል።

ማንኛውም ሃገር አሁንና ለወደፊት የሚኖረው የሃብት መጠንና በሁሉም መስክ ሊደርስበት የሚፈለገውን የዕድገት ደረጃ ዕቅድ ይኖረዋል። ይህ በአንድ ወቅት ያለው ተጨባጭና ለወደፊት ሊኖር ይችላል ተብሎ ታሳቢ የሚደረገው የአንድ ሃገር የሃብት መጠን የሃገሪቱን በአጠቃላይና የዜጎቿን የአሁንና የወደፊት ፍላጎቶች ለማርካት እንዲቻል ታስቦ ይሰማራል፤ ይታቀዳል። ከእነዚህ የሃገሪቱ ፍላጎቶች አንፂር ሰላምና

[15] Haile Kibret. Ethiopian Journal of Economics Volume V, Number 2 October 1996. Military expenditures and Economic Performance Lessons from the Ethiopian Economy. page 4

[16] Ibid

ፀጥታ የተረጋጋ የኑሮ ሁኔታ መስፈን አንዱ ነው። ይህንን ሁኔታ ከመፍጠር አንፂር ደግሞ ከፍተኛ ድርሻ ያለው የሃገር መከላከያ ኃይል ነው። ከዚህ ሁኔታ በመነሳት ካለው የተወሰነ የሃገሪቱ ሃብት ምን ያህሉን ለሃገር ደህንነት ማስጠበቂያ ምን ያህሉን ደግሞ የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅና ለማሻሻል ማለትም ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት ምን ያህሉን ለማህበራዊ ብልፅግና መዋል አለበት ብሎ መወሰን አለበት።

እነዚህ ተወዳዳሪ የሆኑ ፍላጎቶች እርሰ በርሳቸው መጓተታቸው አይቀርም። ውጥረቱ በዚህ ምክንያት የሚፈጠር ይሆናል። አንደኛው ክፍል (Sector) በርከት ያለ በጀት ከተመደበለት ሌላኛው መጎዳቱ አይቀርም። የሁሉንም ፍላጎቶች ሁኔታው በሚጠይቀው ደረጀ ማሟላት አይቻልም። በዚህ ምክንያት ነው በአግባቡ የታሰበበትና የተጠና ውሳኔ መወሰን ትልቅ ጠቀሜታ የሚኖረው። ለዚህም ነው ሃገራዊ በጀት ውሳኔ ከስራ አስፈፂሚው ተፅዕኖ ነፂ የሆነና በሃገር መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ውሳኔዎች መወሰን ያለበት የሃገሪቱ ፓርላማ ከዋና ዋናዎቹ ስራዎቹ ውስጥ አንዱ እንዲሆን የሚደረገው።

የአንድን ሃገር ሃገራዊ ደህንነትን ለማስጠበቅ ተብሎ ለሃገር መከላከያ ሰራዊት የሚመደበው በጀት በሦስት ጉዳዮች ላይ በመመሠረት ይወሰናል።

1. በአገሪቱ ውስጥ አሁን ያለውና ለወደፊት ሊገኝ የሚችለው የሃብት መጠንና ዓይነት በአጠቃይ ግምት ውስጥ በማስገባት (ብዙዎቹ ፕሮግራሞች የአንድ ዓመት ፕሮግራሞች ብቻ ስላልሆኑ)፣
2. ለብሄራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ አስፈላጊ የሚሆነውና የአገሪቱ አቅም ሊያቅርብ የሚችለው የሃብት መጠን፣
3. ለሃገር መከላከያ ተብሎ የሚመደበው የሃገሪቱ ሃብት ውጤታማና ሃብት ቆጣቢ በሆነ አጠቃቀም ላይ እንዲመሰረት ታሳቢ በማድረግ ይሆናል።

እነዚህ ሁኔታዎች በሙሉ ደግሞ የሃገርን ደህንነት ለማስጠበቅ ያስችላል ተብሎ በሚወጣው የብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲና ይህንን ፖሊሲ ለማስፈፀም በሚነደፍ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞቹ ላይ ይመሰረታሉ። የሃገር መከላከያ በጀት ስምምነት የተደረሰባቸው ፕሮግራሞችን ለመተግበር የሚፈለገውን የገንዘብና ማቴሪያል አቅርቦት በቁጥር የሚገለጽበት ሰነድ ነው።

ከዚህ ሁኔታ ጋር በማያያዝ Determinants of military expenditure in Sub-Sahara Africa በሚለው ጥናታዊ ጽሑፉ ናድር መሐመድም የሚከተለውን ይላል።

> "The major determinants of military expenditure are therefore (a) political and military situations (security and threat perceptions) (b) overall economic conditions. These factors operate at domestic, regional and global levels.[17]

[17] Nadir A.L. Mohammed. Detrminants of military expenditures in sub Saharan Africa. Ethiopian Journal of Economics. Vol. II, No. 2. October 1993. p 97

እንግዲህ የሃገር ደህንነት ጥበቃ ውጤታማነት መለከያው የአንድን ሃገር የውጭ ይሁን የውስጥ ጠላቶች፣ በወቅቱ በስልጣን ላይ ያለው የጊዜው መንግስት በቁጥጥሩ ስር ያሉትን የፖሊሲ መሣሪያዎች በመጠቀም (ዲፕሎማሲያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ፀጥታዊ) ጦርነት ወይም የእርስ በርስ ግጭት እንዳይቀሰቀስ መከላከል ከቻለ ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከተቀሰቀሰ ደግሞ በአጭር ጊዜ በአነስተኛ ዋጋ በአሸናፊነት ማጠናቀቅ ነው። የሃገር ደህንነት ማስጠበቂያ ፖሊሲው፣ ስትራቴጂዎቹና ዝርዝር ፕሮግራሞቹ ይህንን ውጤት ለማምጣት የሚያስችሉ መሆናቸው በሚገባ መታየት አለባቸው። ለዚህ ነው የሃገር ደህንነት ፖሊሲ ሲወጣ ሰፋ ያለ ውይይት የሃሳብ ልውውጥና ከሰፊ ውይይትና የሃሳብ ልውውጥ በኋላም ሃገራዊ መግባባት (Consensus) ላይ መድረስ ያለበት። የሃገር ደህንነት ማስጠበቂያ ፖሊሲ ሁሉንም የሃገር እንቅስቃሴዎች የሚነካ መሠረታዊ ጉዳይ ነው።

ይህ መሠረታዊ የሆነው የሃገር እንቅስቃሴና ህልውና የሚነካ ጉዳይ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የሃገሪቱ ህዝብ ህይወቱንም ጭምር ለመክፈል የሚያዘጋጅበት ፖሊሲ በዝርዝር አውቆትና አምኖበት ሊቀበለው ይገባል። ከማናቸውም ፖሊሲዎች (የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ) ፖሊሲዎች ይበልጥ እንደሆነ እንጅ በማያንስ መንገድ በሕብረተሰቡ ዘንድ ሰፊ ውይይት ሊካሄድበት፣ ሊነቀፍና ሊወደስ ይገባል። በብዙ ሃገሮች ያለው ልምድ ግን የብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲ በጥቂት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ረቆ ከፍተኛ ሚስጥር ሆኖ የሚጠበቅ ጉዳይ ተደርጎ ይታያል። ሕብረተሰቡ የማይነካው የሚፈራ ታቡ ተደርጎ ይወሰዳል፤ ይህ ትክክል አይደለም። እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ Operational ሚስጥር መኖር የለበትም ማለቴ አይደለም። ወደ ዝርዝር ነገር ሳልገባ በአንድ ወቅት የሃገር መከላከያ ሰራዊት የተሰጠውን ግዳጅ ለመፈፀም እንቅስቃሴ ሲያደርግ እንዴት ይሰማራል ምን ስልቶችን ይጠቀማል ወዘተ ... ህዝብ እንዲወያይበት የሚያስፈልግ ጉዳይ አይደለም። ከዚህ ውጭ ግን መሠረታዊ የሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ይህንን ለማስፈፀም የሚወጡ ፕሮግራሞች ህዝብ እንዲያውቃቸው ብቻ ሳይሆን ሃሣብ እንዲሰጥባቸው፣ እንዲደግፋቸው፣ እንዲቃወማቸው፣ እንዲያጎለብታቸው እንደማንኛውም ፖሊሲ ግልፅ ውይይት የሚደረግባቸው መሆን አለባቸው። በህዝብ ፊት ተቀባይነት የሌለው ሃገራዊ የደህንነት ፖሊሲ ግፋ ቢል ጥሩ ሰነድ ከመሆን አይዘልም። አንዴ ከወጣ በኋላም ደርቆ የሚቀመጥ መሆን የለበትም። በየጊዜው ከወቅቱ ሁኔታ ጋር እየተገናዘበ መፈተሽ፣ መሻሻልና መበልፀግ ይኖርበታል።

ይህ ሳይደረግ ቀርቶ ለሃገር ደህንነት ማስጠበቂያ ተብሎ የሚወጣ ወጪ ግን መሠረታዊ ባህርይው በወቅቱ ስልጣን ላይ ያሉትን ኃይሎች ለመጠበቅ ተብሎ የሚወጣ ወጭ ይሆንና አገሪቱን ከውጭ ጥቃት ይሁን ከእርስ በርስ ጦርነት ላያድናት ይችላል። የአገሪቱንም ሃብት አያድንም። ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ያዳር መሐመድ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ጥናታዊ ጽሁፉ የሚከተለውን ይላል "In developing countires the need for military forces to maintain ruling elites in power and to repress domestic opposition groups is crucial in deciding the level of military effort"[18]16

5. የሀገር መከላከያና የኢኮኖሚ ዕድገት በሃገራችን

[18] Ibid. p 90

በዚህ አጭር ጽሁፍ በሃገራችን ያለውን የሃገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታና የኢኮኖሚ ዕድገት ዝምድና በዝርዝር ማየት ያስችግራል። ከዚህ በተጨማሪም የአጀንዳው አቀራረብና ይዘት በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ እንጅ በዝርዝር የሃገራችን ሁኔታ ግምገማ ውስጥ እንድገባ ያተኮረ አልመሰለኝም። ሆኖም መሠረታዊ ናቸው በምላቸው ሁለት ጉዳዮች ላይ በማተኮር አንዳንድ ነገሮች ማለትና ለቀጣይ ውይይት ጠቃሚ መስለው የሚታዮኝን ጥያቄዎች ማንሳት እወዳለሁ። አንደኛው የሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲ አወጣጡና አፀዳደቁ ሂደት ላይ ያተኩራል። ሁለተኛው የሃገራዊ ደህንነት እንቅስቃሴ የአስተዳደሩን ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቱን በአጠቃላይ governance እየተባለ የሚታወቀውን ይመለከታል። ሁለቱንም በየተራ እንያቸዋለን። በመጀመሪያ አንዳንድ ጠቅለል ያሉ ጉዳዮችን እንደመነሻ ላንሳ።

Year	Millitary Expenditure m. birr	As a % of GDP
1990	1.625	8.5
1991	1.095	5.3
1992	716	2.7
1993	819	2.9
1994	813	2.4
1995	754	2.0
1996	803	1.8
1997	1.512	3.4
1998	3.263	6.7
1999	5.589	10.7
2000	5.075	9.6
2001	3.154	6.1
2002	3.000	5.3
2003	3.000	4.3
2004	3.000	

በሃገራችን ሰላም የመጥፋቱና በቀጣይ ጦርነት ለዘመናት መኖራችን ጋሃድ ነው። ከ1970ዎቹ ወዲህ ያለውን እንኳን ብናይ ሁለት ትላልቅ በሁለት አገሮች መካከል የተደረጉ ጦርነቶች እና ለአስርት ዓመታት ያላቋረጠ የእርስ በርስ ጦርነት አልፈናል። ይህ ሁኔታ ደግሞ በሃገራችን ኢኮኖሚ ላይ የፈጠረው ጫና እጅግ ከባድ ነው።

ከ1990ዎቹ በኋላ በመሃል ከተደረገው የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በስተቀር በየጊዜው እየተጠናከረ የመጣ ተነፃፃሪ ሰላም አለ። ይህ ሁኔታ መንግስት በየጊዜው ከወሰዳቸው ውሳኔዎች ጋር ተዛምዶ በሃገራዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ለውጥ አምጥቷል። ይህንን ሁኔታ መንግስት በየዓመቱ

ለሃገር መከላከያ ሰራዊት ከመደበው በጀት ከጠቅላላ የሃገሪቱ ሃብት አንፂር በንጽጽር ሲታይ ማስተዋል ይቻላል። የሃገር መከላከያ በጀት በየዓመቱ እየቀነሰ መጥቷል። ከዚህ ቅጥ (Pattern) አፈንግጦ የሚታየው በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት የነበረው ሁኔታ ነው። ይህንን ሃሣብ የዓለም ባንክ የኢትዮጵያና ሱዳን ዳይሬክተር የሆኑት ኬን ኦአሺ እንዲህ በማለት ገለፀውታል። "Ethiopia suffered from a war, with GDP contracting by 3.7% in 1997/98"[19] በዚህ ወቅት ለሃገር መከላከያ የተመደበው በጀት ከፍተኛ ለውጥ አሳይቷል። መደረግ የነበረበት ነው ብዬ አምናለሁ።

እ.ኤ.አ. ከ1990 - 2004 ባሉት ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፖሊክ የሃገር መከላከያ በጀት ከሃገሪቱ GPD (Gross demostic product) አንፂር ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።[20]

የዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ማኔጅግ ዳሬክተር የነበሩት ካምደሱስ ይህንን የሃገር መከላከያ በጀት ከሃገሪቱ GPD (Gross demostic product) አንፂር ሲታይ ጣሪያው ከ4.5% መብለጥ የለበትም ሲሉ UNDP ደግሞ ከ4% መብለጥ የለበትም ይላል። በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ የነበሩት ኮፊ አናን ጣሪያው ከ1.5% መብለጥ እንደሌለበት ገልጸው ነበር።

እ.ኤ.አ. ከ1993 - 1996 ድረስ በቀጣይነት እየቀነሰ የመጣው በጀትና በዚህ ወቅት በአፍሪካ ደረጃ ከነበረውና በለጋሽ አገሮችና ዓለም አቀፋዊ የገንዘብ ተቋማት ዘንድ ተቀባይነት ከነበረው የበጀት ጣሪያ በላይ እምብዛም የበለጠ አልነበረም። [19] ይህ በግልጽ የሚታወቀው በጀት በዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ዘንድ በማደግ ላይ ለሚገኙ ሃገራት ያወጣውን ጣሪያ ያልዘለለ ቢሆንም ከተለያዩ አቅጣጫዎች (የሃገራት ስምምነቶች፣ ከተለያዩ ገቢዎች በሚሸፈን ወጪ) የሚወጣው ገንዘብ በተለይ ደግሞ ለጦር መሣሪያና ለውግያ መገልገያ ግዥ የሚወጣው ወጭ በሙሉ ለማወቅ እንደማይቻል ይታወቃል። ሃገሮች ይህንን የሃገር መከላከያ ኃይል የግዥ ስራዎቻቸውን ለመሸፈን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። በአጠቃላይ ሲታይ ግን እኛ ካለንበት ሁኔታ አንፂር የሃገር መከላከያ በጀት በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ ነው ሊባል አይችልም።

1. የፖሊሲው አወጣጥ ሂደት

እኔ እስከማውቀው ድረስ ከዚህ ቀደም የነበሩት የኢትዮጵያ መንግስታት ግልጽ የሆነ የሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲ አልነበራቸውም። ይህ ማለት ያለፉት መንግስታት የሃገራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ መመሪያ ወይም እነሱ የሚመሩበትና የሚመሩበት አቅጣጫ አልነበራቸውም ማለት አይደለም። ግን በግልጽ እንደፖሊሲ ወጥቶ ህዝብ አውቆትና ተቀብሎት የሚሄድ በጽሁፍ የተቀመጠ መመሪያ አልነበረም። እንዳውም በግዜው ተቀባይነት በነበረው አስተሳሰብ መሠረት እንደአንድ መሠረታዊ የሃገር ሚስጥር ተደርጎ የሚታይ እንደሚሆን መገመት ይቻላል። አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በፈረንጆቹ አቆጣጠር በኖቬምበር 2002 ላይ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ግንኙነትና የብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲና

[19] Ken Ohashi Sustaining Growth: Ethiopessimism? The World Bank Group. 2008.

[20] Budeting for the Military Sector in Africa. The processes and Mechanisms of Control. 2006.

ስትራቴጂ አውጥታል።[21] ይህ ሰነድ ወጥቶ ለህዝብ ቀርቧል። ይህ መደረጉ ጥሩ ጅምርና አስራር ነው። በዚህ በወጣው ሰነድ ድህነትን መዋጋት እንደዋነኛ ጠላት ተቀምጧል። እነዚህ ጥሩ መነሻዎች ናቸው ብዬ አምናለሁ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መነሳት ያለባቸው ጥያቄዎች አሉ።

የአንድ ሃገር የሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲ አጠቃላይ የሃገሪቱን መሠረታዊ ጉዳዮች የሚነካ ነው። በተጨማሪም በአንድ ወቅት በምርጫ ወደስልጣን የወጣ መንግስት ያህል ዕድሜ ብቻ እንዲኖረው አይታሰብም። በየጊዜው በህዝብ ፍላጎትና ምርጫ ወደስልጣን የሚመጡትን መንግስታት ከሁኔታው ጋር የተገናዘበ መጠነኛ ማስተካከያ እያደረጉበት እንዲቀጥል ነው የሚታሰበው። ከዚህም አልፎ ሃገሪቱ በከፍተኛ ፈተና ላይ በወደቀችበት ወቅት ህዝቦች በዚህ ፖሊሲ መመሪያነት መሠረት ሁሉንም አቅማቸውን ሕይወታቸውንም ጭምር ከፍለው እንዲተገብሩት ነው የሚታሰበው። እንደዚህ ያለው አንድ ሃገራዊ የደህንነት ፖሊሲ ፀድቆ ወደተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲገባ ከፍተኛ የሃገር ሃብት እየፈሰሰበት ነው ተፈፃሚ የሚሆነው። የዚህ ዓይነት ባህሪይ ያለው ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ትንሽ እንቅስቃሴ ከተደረገ በኋላ እንደገና አቅጣጫ ልቀይር ተብሎ በቀላሉ ወደግራና ቀኝ የምትታጠፍበት ሁኔታ የለም። ብዙ ጊዜ ጉልበትና ገንዘብ የሚፈስባቸው ሃገራዊ ተቋማት ይገነባሉ። እነዚህ የሕብረተሰብና የመንግስት ተቋማት በቀላሉ አይፈርሱም። በአጭሩ የአንድ ወቅትን ሃገራዊ የደህንነት ፖሊሲ ታሳቢ በማድረግ የተገነባን የሃገር የመከላከያ ሰሪዊት ሌላ መንግስት በመጣ ቁጥር እየጠራረገ እያፈረሰ እንደአዲስ መገንባት አስፈላጊ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እያገኘ ባለው የሃገራዊ ደህንነት አስተሳሰብ መሠረት የሚገነባ የሃገራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ ስርዓት (ፖሊሲውም አስፈፃሚ አካላቱም በድምር) ደህንነቱ እንዲጠበቅ ከሚፈለገው የሃገሪቱ ዜጋ ከፍተኛ ትብብርን ይጠይቃል። ከዚህ ውጭ በሌላ መንገድ መፈፀም አይቻልም። አስተማማኝ የሆነ የሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ረቆ የተግባር መመሪያ በመሆን የአገሪቱን የወደፊት አቅጣጫ ግልጽ በማድረግ የሃገሪቱን አጠቃላይ ሰብአዊ ይሁን ማቴሪያላዊ አቅም በመጠቀም (mobilize) ለመፈጽም ከተፈለገ የህዝቡ የነቃና በእምነት የሚደረግ ተሳትፎ የግድ ይላል።[22]

20

እንግዲህ አጠር ባለ መንገድ የተገለፀውን ዓይነት ባህሪ ያለው ፖሊሲ ወጥቶ የተግባር መመሪያ እንዲሆን ቢያንስ በአብዛኛው የሃገሪቱ ህዝብ ተቀባይነት እንዲኖረው የኛ ፖሊሲ ነው እንዲባል ያስፈልጋል። ሕብረተሰቡ በባለቤትነት ሊቀበለው ይገባል። ይህንን የሃገራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ ፖሊሲ በግለሰቦች ወይም በፓርቲ ሊቀሰቀስ (initiate) ይችላል። በመጨረሻ የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ ከተፈለገ ግን ሃገራዊ ተቀባይነት ያለው ፖሊሲ ሆኖ ለሌሎች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች እንደማይናወጥ መሠረት (Bedrock) ሆኖ ማገልገል መቻል አለበት። ይህ እንዲሆን ፖሊሲውን ሕብረተሰቡ በባለቤትነት እንዲቀበለው (own) እንዲያደርገው በሰነዱ ውስጥ ከተካተቱት ሃሳቦች ይበልጥ እንዲሆን እንጂ ባልተናነሰ መንገድ ለሂደቱ ትኩረት መሰጠት አለበት። የፖሊሲውን አጠቃላይ ይዘትና በተለይ ደግሞ ተፈፃሚነት የሚወሰነው የተስተካከለ ሂደት በመከተልና ባለመከተል ነው።

[21] The Federal Democratic Republic of Ethiopia Foreign Affairs and National Security Policy and Strategy. November 2002.

[22] SIPRI Yearbook 2003. Armaments, Disarmament and International Security.

ስለሆነም የፖሊሲ ማውጣት እንቅስቃሴው እጅግ በጣም አሳታፊ እና ግልጽነት የተላበሰ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይ በተለያየ ሞያ ጥልቅ ዕውቀትና ተሞክሮ ያላቸው ሰዎች በተደራጀ መንገድ በፖሊሲ ማመንጨቱና ማጎልበቱ ስራ ላይ በንቃት እንዲሳተፈ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። በተመሳሳይ መልኩ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት፣ የትምህርትና የምርምር ተቋማት የሲቭል ማህብረሰብ በስፋት እንዲሳተፉ የሚያደርግ መሆን አለበት። ይህ በሃገራዊ የደህንነት ፖሊሲው ሳይዳሰስ የሚቀር ጉዳይ እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ ሃገራዊ መግባባት /consensus/ የመፍጠሩ ሂደት ጅምር ይሆናል። በጉዳዩ ላይ እውቀት አላቸው ተብለው የሚታወቁና አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ግለሰቦች ይሁኑ ቡድኖች ፖለቲካዊ አስተሳሰባቸው ምንም ይሁን ምን ያለፍርሃትና መሸማቀቅ በሂደቱ እንዲሳተፉ ማድረግ የፖሊሲውን ተአማኒነትና ሕጋዊነት በማጠናከር ለተፈፃሚነቱ ሰፊ መሠረት ይጥላል። ይህ ደግሞ በጣም ተፈላጊና ጠቃሚ ጉዳይ ነው።

በእንደዚህ ዓይነት መንገድ የመነጨን ፖሊሲ በወጉ በሕግ አውጭው አካል ሰፋ ያለ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ውይይት ተደርጎበት መጽደቅ አለበት። አንዴ ከፀደቀም በኋላ በሕብረተሰቡ እንዲታወቅና የስራ መመሪያ እንዲሆን ሰፊ እንቅስቃሴ መደረግ ይኖርበታል። ይህ በፓርቲ ወይም በመንግስት መዋቅር ብቻ ሳይሆን ከላይ ፖሊሲውን ለማመንጨት በተሳተፉት የሕብረተሰብ ክፍሎችም ተጨምረው በስፋት መካሄድ ይኖርበታል። ከዚህ አንፂር የሃገራችን የሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲ እንዴት ይመዘናል የሚለው ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል።

2. የሀገራዊ ደህንነት እንቅስቃሴ የማስተዳደር ጉዳይ

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የአንድ ሃገር የሃገራዊ ደህንነት ተቋማትና እንቅስቃሴዎች ማስተዳደር፣ በአንድ በኩል ለውጤታማነታቸው በሌላ በኩል ደግሞ የሃገርን ሃብት ከብክነት ለመቆጣጠር፣ ጠቃሚ በመሆኑና ከዚህ በተጨማሪም በሌሎች የሃገሪቱ እንቅስቃሴዎች ላይ ባላቸው ተፅዕኖ ምክንያት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ትኩረት መስጠቱም ተገቢና ትክክል ነው። የሃገራዊ ደህንነት ተቋማትና እንቅስቃሴያቸውን በአግባቡ ማስተዳደር ማለት በተለይ በስትራቴጂካዊ ጉዳዮች ላይ ዴሞክራሲያዊና ግልጽ የሆነ የውሳኔ አሰጣጥ፣ የተጠያቂነትና የቁጥጥር ስርዓት መኖር ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከመሠረቱ ጀምሮ የሃገሪቱ ሕገ መንግስት በሃገራዊ ደህንነት ጉዳይ ላይ የሚወሰኑ ውሳኔዎች የሚወሰኑበት አግባብ (procedure) እና የትኛው የመንግስት አካል በምን ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን እንዳለው በግልጽ በማስቀመጥ ይጀምራል። ከዚህ ቀጥሎም ብዙዎች ሃገሮች እንደሚያደርጉት የሃገር መከላከያ ኃይልን በተመለከተ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቱንና የስልጣን ክፍፍሉን ከሌሎች ውስጣዊ አሰራሩ ጋር በማዛመድ ግልጽ የሚያደርጉበት የሰራዊት ማቋቋሚያ ሕግ (Defence Act) የሚሉትን ያወጣሉ። ይህ በሚገባ ታስቦበትና ተቋሙን ውጤታማ ለማድረግ ታልሞ በሃገሪቱ ህግ አውጪ አካል የሚወጣ ሲሆን በየጊዜው ከሁኔታዎች ጋር እየተዛመደ እያደገ እንዲሄድ ይደረጋል።
ይህንን ተንተርሶ አንድ መነሳት ያለበት ጉዳይ የሃገር መከላከያ ኃይል አስተዳደር (governance) መስተካከል ሦስት መሠረታዊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው።

1. የተስተካከለ አስተዳደር መኖሩ ሰፊ የሕጋዊነት መሠረት እንዲኖር በማስቻል ከዚህ የሚመነጭ ህዝባዊ ድጋፍ እንዲጎናፀፍ ያስችለዋል። ይህ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ለሞራሉም ለጀግንነቱም ብሎም ለውጤታማ ግዳጅ አፈፃፀሙ ምንጭ ነው። በየሄደበት የኛ ሰራዊት ይባላል። በፈቃደኝነት የሚሰጥ ያልተቆጠበ የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት መሠረት ይሆናል። ይህ ሁኔታ በሰራዊት ግዳጅ አፈፃፀም ያለው ጠቀሜታ ግልጽ ይመስለኛል።

2. የተስተካከለ አስተዳደር መኖር የሃገር መከላከያ ኃይሉ በወቅቱ በስልጣን ላይ ያለ መንግስት ከሚፈጥርበት አግባብ የሌለው ተፅዕኖ ተላቆ ረዘም ባሉና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላቸው የሃገር ደህንነት ጉዳዮች ላይ ፕሮፌሽናል በሆነ አግባብ እንዲያስብና እንዲዘጋጅ ያስችለዋል። ይህ ብቃቱ ከፍተኛ እንዲሆን ከማስቻሉም በላይ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም በስልጣን ላይ ያለ መንግስት (regime) መሣሪያ እንዳይሆን፣ የጠቅላላ የሃገሪቱ ደህንነት በሕገ መንግስቱ በተቀመጠለት መመሪያ መሠረት የሚፈጽም ኃይል እንዲሆን የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥርለታል።

3. አሁንም የተስተካከለ አስተዳደር መኖር ሰራዊቱ በግዳጅ አፈፃፀሙ ውጤታማ እንዲሆን በማስቻል ያለው ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም የቁጥጥር ስርዓቱን በማጥበቅ በተለያየ መንገድ የሚፈጠረውን የሃገራዊ ሃብት መባከንን ለመግታት ያስችላል። የሃገራዊ ደህንነት የማስጠበቅ ጉዳይ በአጠቃላይ የሃገር መከላከያ ኃይል ግንባታና ስምሪት ደግሞ በተለይ ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ እንቅስቃሴ ነው። በአንፂሩ የተሳሳተ ፖሊሲ በመከተል የሃገር ሃብት ሊባክን ይችላል። ከዚህ አልፎም ትክክለኛ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተነድፎ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አስራር ባለመስፈኑና በሌሎች ብልሹ አስራሮች የሃገር ሃብት ለታሰበው ግብ ሳይውል ሊባክን ይችላል። ይህ ሁኔታን መቆጣጠር የሚቻለው ወይም የሃገራዊ ሃብት ብክነትን በተቻለ መጠን መቀነስ የሚቻለው፤ የተስተካከለ የአስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባር ላይ ሲውል ነው። እግረ መንገዱን መገለጽ ያለበት ጉዳይ ቁጥጥር ማጥበቅ ማለት የበጀት ምደባን ለመቀነስ መሰራት ማለት ብቻ እንዳልሆነ ነው።

የሃገሪቱ ከፍተኛው የፖሊሲ ውሳኔዎችንና በጀትን የሚወስነው የሕግ አውጭው አካል ስራውን በአግባቡ ከሰራ፣ በስራ አስፈፃሚው አካል ለሃገራዊ ደህንነት ታስቦ የሚመደበው በጀት ፖሊሲውን ለማስፈፀም በቂ አይደለም ብሎ ካመነ፣ ይህንን ማስተካከልም ስራው ነው። በአጠቃላይ ግቡ የሃገሪቱን ደህንነት የሚያስጠብቅ ፖሊሲ መውጣቱን ይህንን ፖሊሲ ለማስፈፀም የሚያስችል ስትራቴጅ መነደፉንና ለዚህም በቂ በጀት መመደቡን መቆጣጠር ነው። ስለዚህ የተስተካከለ አስተዳደር መኖር ውጤታማ የሆነ ዴሞክራሲያዊ የቁጥጥር አግባብ እንዲኖርና ለሃገራዊ ደህንነትም ወሳኝ የሆኑት የሃገሪቱ አካላት ኃላፊነቱን እንዲሸከሙ ያስችላል።

እዚህ ላይ የሚነሳው ጉዳይ የሃገራችን ሕገ መንግስት ሚዛኑን የጠበቀ የቁጥጥር ስርዓት እንዲኖርና በሃገራዊ የደህንነት ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን በተወሰኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ግለሰቦች እንዳይሰበሰብ ምን መፍትሔ አበጅቷል የሚለው ነው። ይህም ማለት ሕገ መንግስቱ በሕግ አውጭውና

በስራ አስፈፃሚው መካከል ያለው በሃገራዊ የደህንነት ጉዳይ ላይ ውሳኔዎችን የመወሰን የስልጣን ክፍፍል እንዴት አስቀምጦታል ተብሎ መጠየቅ ይገባዋል። ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲገባ ደግሞ የሕግ አውጭው አካል በተሰጠው ስልጣን መሠረት ስራውን በብቃት ለመስራት የሚያስችለው ሁኔታ ተመቻችቷል በጉዳዩ ላይ በቂ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች በውስጡ አካቷል ይህ ካልሆነ ደግሞ ውሳኔ ለመወሰን የሚያስችላቸው በቂ ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ ተመቻችቷል? የፖለቲካ ሁኔታው የስራ ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ያስችላቸዋል የገዥው ፓርቲ፣ የስራ አስፈፃሚው አካልና የሕግ አውጪው ዝምድና ምን ይመስላል? በሕገ መንግስቱ የተሰጣቸውን ስልጣንና ኃላፊነት በተገቢው መንገድ ለመተግበር የሚያስችል ሁኔታ ነው ያለው ወይስ መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ? የሚሉትና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች መነሳት ይገባቸዋል።

6. ማጠቃለያ

በሁለት ሺህ ሃያ ምን እመኛለሁ።

ይህ የውይይት መድረክ እኔ እንደገባኝ ለውይይት መነሻ የሚሆን ሃሳብ የምናቀርብ ሰዎች ከዛሬ ሃያ ዓመት በኋላ በምንነጋገርበት ርዕስ ላይ ተመስርተን ራዕያችንን የምንገልጽበት መድረክ ነው። ራዕይ ደግሞ ለእኔ እንደሚገባኝ ያለፍንበት ሁኔታ መነሻ በማድረግ ለቀጣይ እንዲሆን የምንመኘውን ሃሳብ መግለጽ ማለት ነው። ከዚህ አንፂር ከሃያ ዓመት በኋላ በሃገር መከላከያና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያለው ዝምድና እንዲሆን የምመኘው የሚከተለውን ነው።
መቼም እኛ ያለንበት ጂኦግራፊያዊ ቀጠና ወደድንም ጠላንም ጦርነቶችና የእርስ በርስ ግጭቶች ከማንኛውም አካባቢ በበለጠ ሊከሰቱበት የሚችል ቀጠና ነው። ከዚህ በመነሳት ደህንነታችን ነቅተን እንድንጠብቅ የሚያስገድድ ሁኔታ ነው ያለው። በመሆኑም የሃገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታ የደህንነታችን ማስጠበቂያ አንዱ አካል ሆኖ ከጠቅላላው የሃገራችን ሃብት ድርሻውን እየወሰደ መቀጠሉ አይቀርም። ያለው አማራጭ ለዚህ የሚወጣውን ወጭ በየጊዜው Rationalize እያደረጉ ከሌሎቹ የህብረተሰብ ፍላጎቶች ጋር ተጣጥሞና ሚዛኑን ጠብቆ እንዲቀጥል ማስቻል ነው። በዚህ ቀጠና ውስጥ ሆነን በኢኮኖሚ እያደግን፣ ይህ ዕድገታችን ይበልጥ ደህንነታችንን አስተማማኝ እንዲሆን እያደረገ ሰላሙም ይበልጥ እየተረጋገጠ እንዲሄድ ነው የምመኘው።

ሃገራዊ የደህንነት ፖሊሲ ከማውጣት አንፂር የተጀመረው ጅምር ተጠናክሮ ቀጥሎ እንዲጠናቀቅ እመኛለሁ። የሃገራችን ሃገራዊ የደህንነት ፖሊሲ በሰፊ የህዝብ ተሳትፎ በተለይ ደግሞ ከትምህርት ተቋማት፣ የጥናት ተቋማት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በስፋት ተሳትፈውበት የእነሱ ግብአት ፖሊሲውን አጠናክሮ እንዲወጣ። ከሌሎች ሃገሮች ልምድ በመቅሰም አጠቃላይ ህዝቡ የኛ የሚለውና ዋና ዋናዎቹ የማህበረሰቡን እንቅስቃሴ የሚመራ ፖሊሲ እንደሆን እመኛለሁ። ፖሊሲው በህዝብ በባለቤትነት እንዲያዝ (own) እንዲደረግ የፖሊሲ የአወጣጡ ሂደቱ ወሳኝ ስለሆነ ሂደቱ ተስተካክሎ ተፈላጊው ውጤት እንዲገኝ እመኛለሁ።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ በወጣው ፖሊሲና የፖሊሲው ማስፈፀሚያ በሆኑ ስትራቴጅዎችና ፕሮግራሞች መመሪያነት መሰረት የሚገነባ በግዳጅ አፈፃፀሙ ውጤታማ የሆነ በሃገራችን ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና የማይፈጥር ግን ጠላቶቻችን ጦርነት እንዳይቀሰቅሱ መግታት የሚችል፣ ጦርነት ከቀሰቀሱ ደግሞ በአጭር ጊዜ በድል አድራጊነት ግዳጅን የሚፈጽም፣ ከፍተኛ ህዝባዊ ፍቅር፣ ሞራል፣ ጀግንነት፣ ዲስፕሊንና ፕሮፌሽናዊ ብቃት ያለው የሃገር መከላከያ ሰራዊት እንዲኖረን እመኛለሁ። ይህ ተቋም መሠረታዊ ግዳጁ የሃገራቱንና የህዝቦቿን ደህንነት መጠበቅ መሆኑን በሚገባ የተገነዘበ፣ በየጊዜው በዴሞክስራሲያዊ አገባብ እየተፈራረቁ የሚመጡትን መንግስታት ማገልገል የሚችል መንግስታት በተቀያየሩ ቁጥር እየተጠራረገ የማይጣል እንዲሆን እመኛለሁ።

የሃገራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ ተቋሞቻችንና እንቅስቃሴያችን በዴሞክራሲያዊ የቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ የሚተዳደሩ እንዲሆኑ እመኛለሁ። ሰራዊቱ በህዝብ የተመረጡ ሲቭል ባለስልጣናትን ስልጣን የሚያከብር፣ በእነሱ የሚታዘዝ፣ ስራቸውን በተገቢው መንገድ እንዲሰሩና ግዳጃቸውን እንዲወጡ ከሰራዊቱ የሚፈለገውን በሙሉ የሚፈጽም ሆኖ እንዲገነባ እመኛለሁ። ይህንን ለመምራት የሚችል ጠንካራ የሕግ አውጪ እንዲኖረን ለዚህ የተመቻቸ ፖለቲካዊ ሁኔታ እንዲፈጠር እመኛለሁ።

ይህ ሲሆን የሃገር መከላከያ ሰራዊት በማንም ሊተካ የማይችል አዎንታዊ አስተዋፅኦ በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ። ይህ ሂደት የጠቅላላው በሃገሪቱ የሚደረግ የዴሞክራታይዜሽንና የመልካም አስተዳደር ውጤት ሆኖ የሚመጣ፣ ለብቻው ተነጥሎ ሊመጣ የሚችል ጉዳይ እንዳልሆነም በሚገባ እገነዘባለሁ።

Reference

1. African Union Constitutive Act. Principles. Article 4 (h). Durban, South Africa. July 2002.
2. Budeting for the Military Sector in Africa. The processes and Mechanisms of Control. 2006. Edited by Wuyi Omitoogun and Eboe Hutchful
3. Dac Guidelines and reference Series - Security System Reform and Governance Policy Statement.
4. David Held & Anthony McGrew. The Global Transformations Reader. An Introduction to the Globalization Debate. 2002.
5. Draft resolution referred to the high level plenary meeting of the General Assembly by the General Assembly at its fifty-ninth session. 2005. World Summit out come. Human Security.
6. Haile Kibret. Ethiopian Journal of Economics Volume V, Number 2 October 1996. Military expenditures and Economic Performance Lessons from the Ethiopian Economy.
7. Human Security Report 2005. War and Peace in the 21st Century. Oxford University Press. 2005
8. Ken Ohashi. Sustaining Growth: Ethiopessimism? The World Bank Group. 2008.

9. Nadir A.L. Mohammed. Detrmimnants of military expenditures in sub Saharan Africa. Ethiopian Journal of Economics. Vol. II, No. 2. October 1993.
10. Paul Collier and Anke Hoeffler."The Challenge of reducing the Global Incidence of Civil Wars". Center for the Study of African Economies. Depart ment of Economics. Oxford University. Resized, March 26, 2004.
11. SIPRI Yearbook 2003. Armaments, Disarmament and International Security.
12. The Federal Democratic Republic of Ethiopia Foreign Affairs and National Security Policy and Strategy. November 2002.

በሌ/ጂ ገ/ፂድቃን ገ/ተንሣይ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

መስፍን በነጋ[1]

የጽሁፉ ዋነኛ ትኩረት በአንድ በኩል በሃገር መከላከያ ኃይል ግንባታና ስምሪት በሌላ በኩል ደግሞ በኢኮኖሚ ዕድገት መካከል በአጠቃላይ የግንኙት ባህርይን ለመዳሰስ እንደሆነ ተገልጿል።

ጽሁፉ በአምስት ታላላቅ ምዕራፎች ነው የተከፈለው። መግቢያው Global Security Environment ወይንም ዓለማዊ የደህንነት ሁኔታ ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን ከዚህ በመነሳት የጽሁፉን ይዘት መተንተኑ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይገልጻል። ከዚህ አንጻር Globalization እና ይህ ያስከተለው የሃገራት የእርስ በርስ መተሳሰር ቀጥሎም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ ጀምሮ የተፈጠሩት ዓለም ዓቀፋዊ ተቋማትና ያወጧቸው ሕግጋት እንዴት የመንግስታትን ባህርይ ለመለወጥ ብሎም ሃገራዊውን የደህንነት አስተሳሰብ እንዲለወጥ እንዳስገደዱ ይገልጻል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን እነዚህ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ሕግጋታቸውን ማስፈጸሚያ አቅም ስለሚያንሳቸው ሃገራት አሁንም ራሳቸውን ለመከላከል በራሳቸው አቅም ላይ (ስትራቴጂካዊ ወዳጆችንም በመፍጠር) በመተማመን መሆኑን ያሰምሩበታል። በጹሁፉ መሠረት ይህ መሠረታዊ አስተሳሰብ ነው እንግዲህ ሃገራት እንደሁኔታቸውና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው የራሳቸውን የመከላከያ አቅም እንዲገነቡ የሚገፋፋቸው። በዚህ አስተሳሰብ ላይ ነው የመከላከያ ኃይል አስፈላጊነት የሚመሠረተው።

መግቢያው የሚደመድመው በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተገለጸው የሃገር መከላከያና የኢኮኖሚ ግንኙነት ባህርይ በኢኮኖሚ ትንተና ላይ ተመስርቶ እንደማይሆን ነው።

ሁለተኛው ምዕራፍ የሃገር ደህንነት ጥበቃና የመከላከያ ኃይል በሚመለከት ሲሆን እዚህ ውስጥ መንግስታት ወይንም ሃገራት የሃገር መከላከያ ኃይል የሚገነቡበት ምክንያቶች ዝርዝር ባለሁኔታ ተቀምጠዋል። የመከላከያ አደረጃጀትና አስተዳደር እንዴት መሆን እንዳለበት ተገልጿል። ከዕድገት ጋር ያለውንም ዝምድና ለማጥናት "የሃገር ደህንነት" (National Security) የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በታሪክ ሂደት እንዴት እንደመጣ፣ ዓለም አቀፋዊ፣ አሃጉራዊና ሃገራዊ ክስተቶች እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩበትና እነዚህን ተጽዕኖዎች በሚገባ መተንተን በግዳጅ አፈጻጸም ውጤታማ ለመሆን ከማስቻሉም በላይ የመከላከያ በጀት ሁኔታው ከሚጠይቀው ግዳጅ ጋር የተዛመደ እንዲሆን ለማድረግ ያስችላል ተብሏል። በሃገር መከላከያ ሠራዊት ግንባታና ስምሪት ላይ ያለውን አስተሳሰብ በመቅረጽ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ሦስት ዋና ዋና ሁኔታዎችም ተጠቀሰዋል። እነዚህም:-

[1] ኮሞዶር

ሀ. የNational Security ጽንሰ ሃሳብ ላይ በማህበረሰቦች ዘንድ ያለው ግንዛቤ እየተለወጠ መምጣቱ፣

ለ. የጦርነቶች ባህሪይ እየተለወጠ መምጣቱ እና

ሐ. የግሎባላይዜሽንና ዓለም አቀፋዊ ሕግጋት ተፅዕኖ የሚሉት ናቸው።

በሚቀጥለውና ሦስተኛው ምዕራፍ እነዚህን ሁኔታዎች በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል። በተጨማሪ ቀደም ሲል በመግቢያዉ ላይ ስለመከላከያ ኃይል ግንባታ የተቀመጠው ሃሳብ በተለይ በሃገራችን ሁኔታ ላይ በማተኮር ምክንያቶቹ ተዘርዝረዋል።

በአራተኛው ምዕራፍ ላይ ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በመግባት የመከላከያ ኃይል ግንባታ ከኢኮኖሚ አንጻር ስለሚኖረው ጠቀሜታ ስላሉት አመለካከቶች አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል። አንኳር ሃሳቡም መከላከያ ኃይል ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል እንጂ በላተኛ (non-productive) እንደሆነ ነው። ስለዚህ ለዚህ ዋና ዓላማው (ማለትም ለኢኮኖሚዉ ዕድገት የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጥር) ወጪውን ለመቀነስ እንዴት መመራት አለበት የሚለው ጥያቄ ትኩረት መሳብ እንዳለበት ተሰምሮበታል። ስለ መከላከያ በጀት ከሃገር ሃብት ውስጥ ሊኖረው የሚገባ ድርሻ በምን ላይ ተመስርቶ መወሰን እንዳለበትና የሃገር ደህንነት ጥበቃ ውጤታማነት መለኪያ ምን መሆን እንዳለበት ተጠቅሷል።

የመጨረሻው ምዕራፍ በሃገራችን በሃገር መከላከያና በኢኮኖሚ ዕድገት ግንኙነት ባህሪይ ላይ፣ በተለይም የፖሊሲ አወጣጥ ሂደትና በመከላከያ አስተዳደር ወይንም ማኔጅመንት ላይ ያተኮረ ነው። የጽሁፉ ድምዳሜም የፖሊሲ አወጣጥ ሂደቱ የሃገራዊ ደህንነት ተቋማትና አስተዳደር የተስተካከሉ ከሆነ ተቋማቱ ግባቸውን ከመምታት አንጻር ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥና ብክነትን ማስወገድ ይቻላል። ይህ ነው እንግዲህ የመከላከያ ኃይልና የኢኮኖሚ ግንኙነት መሠረታዊ መገለጫ።

የጽሁፉ አጠቃላይ ይዘት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ሊነሱ የሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ታሳቢ መደረጋቸውን አረጋግጧል። በተለይ የሚንጸባረቁት አስተሳሰቦች በጉዳዩ ለረጅም ዓመታት እንደ አንድ ፕራክቲሺነርና ከፍተኛ አመራር አካል ሆነው በሰሩ ሰው የቀረቡ በመሆናቸው ትኩረት ሊሰጡ የሚገባቸው ናቸው። ሆኖም እንደማንኛውም ሰፊና ውስብስብ በሆነ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ጽሁፍ ጥያቄዎችን ይጋብዛል፣ አንዳንዴም በመጠኑም ቢሆን ለየት ያለ የሃሣብ አቀራረብን ይጋብዛል። በዚህ መንፈስ ነው አስተያየቴን የማቀርበው። ሊያጠናክሩ የሚችሉ ሃሣቦች ካሉ ለማከል እሞክራለሁ።

በመጀመሪያ ላነሳው የምፈልገው ነገር በአርዕስቱ ላይ ካየኢኮኖሚ ዕድገትካ ጽንሰ ሃሣብ ላይ ነው። ምክንያቱም ስለኢኮኖሚ ዕድገት ስናወራ የአንድ ሃገር ዓመታዊ የሃብት መጠን መጨመር (increase in gross national product) ማለታችን ነው። ወይንስ በማህበራዊ ዘርፍ በኩል እንደትምህርት፣ ጤና፣ መጠለያ፣ አቅርቦትንና የሃብት ስርጭትንም የሚጨምር ልማት ማለታችን ነው? ይህን ነጥብ የማነሳበት ምክንያት በጽሁፉ ስለ ሃገራዊ ደህንነት ሲጠቀስ Human Security የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ስለሚያነሳና ይህንንም ጽንሰ ሃሳብ ከመከላከያ ኃይል ግንባታ አንጻር የበለጠ ተቀባይነት ያለው ጽንሰ ሃሳብ ሆኖ ስለተወሰደ ነው። እንዲሁም እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ መጠለያ፣ ድህነት ቅነሳ የመሳሰሉት መሠረታዊ

ጉዳዮች ደግሞ በHuman Security ጽንሰ ሃሳብ የሚካተቱ በመሆናቸው ነው። ልማት ባለ ብዙ ፈርጅ ሂደትና ክስተት ነው። የኢኮኖሚ ዕድገትን ከማህበራዊ ልማት (Human Development) ጋር በማቆራኘትና ከHuman Security ጋር በማነጻጸር ሂደት የትንተናውን አድማስ ጥልቀት ሊያዳብር ይችላል ከሚል አንጻር ነው ሃሣቡ የተሰነዘረው።

ሌላው የጽሁፉን ቅርጽ በሚመለከት የምሰጠው አስተያየት የመከላከያና የኢኮኖሚ ዕድገት ከምን አቅጣጫ እንደተገመገመ በሚመለከት ነው። ግሎባላይዜሽንና የዓለም ዓቀፍ ተቋማት ሕግጋት ሃገራዊ ደህንነት አስተሳሰብ ከመለወጥ አንጻር የተሰጣቸው ቀዳሚና ጉልህ ሚና ነው። ጨርሶ ጫና አያደርጉም ባይባልም ማዕከላዊ ስፍራ ይኖራቸዋል የሚለው አስተሳሰብ ግን አከራካሪ ነው። ከፍተኛ ጫና አላቸው የሚለው አስተሳሰብ ትክክል ነው ከተባለ ደግሞ ይህ በሃገር ደህንነትና በሃገር መከላከያ ፖሊሲዎች እንዲሁም የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ይዘት የሚፈጥረውን ጫና መፈተሽ አስፈላጊ ይሆናል። ይህ በበቂ ሁኔታ አልተደረገም።

የግሎባላይዜሽንና ዓለም አቀፋዊ ሕግጋት ተጽዕኖ በሃገር መከላከያ ሠራዊት ግንባታና ስምሪት ያለውን ሃገራዊ አስተሳሰብ ከመቅረጽ አንፂር ከፍተኛ አስዋጽኦ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች አንዱ እንደሆነ በክፍል ሁለትም እንዲሁ ተገልጿል። ሌሎቹ አህጉራዊና ሃገራዊ ክስተቶች ናቸው። በኔ ግምት ውስጣዊና ከባባዊ ሁኔታዎች የበለጠ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል እላለሁ። ከዚህ አንፂር የአፍሪካ ህብረትና የክፍለ አህጉራዊ ድርጅቶች (ማለትም የአፍሪካ ሪጅናል ኢኮኖሚክ ኮሚዩኒቲ) ሚና ለምን እንዳልተጠቀሰ ግልጽ አይደለም። ለምሳሌ በሁሉም አገራት የጸደቀው COMMON AFRICAN DEFENCE AND SECURITY POLICY የጋራ ውጪያዊ ስጋቶችን በጋራ ለመመከት የተመሠረተ ሲሆን እነዚህን ስጋቶች ሲገልጽ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተናጠልም በእያንዳንዱ ሃገር በመላው አህጉር የደህንነት ጥበቃ ጥረቶች ላይ ስጋት የሚጥሉ እንዲሁም በሃገር ውስጥ የሚከሰቱ ስጋቶች ብሎ ያስቀምጣቸዋል። ክፍለ አህጉራዊ ኢኮኖሚክ ድርጅቶችምየጋራ ብልጽግናና የጋራ ደህንነት (Regional Economic Integration) የማራመድ ዓላማ አላቸው።

ይህም ይብዛም ይነስ በየክፍለ አህጉሩ እየተተረጎመ ነው። እነዚህ ድርጅቶች ለአፍሪካ መዋሃድ እንደመሠረት ድንጋይ ነው የሚቆጠሩት የኢኮኖሚ ውህደት እንዲመጣ ስለሚሰሩ፣ በየክፍለ አህጉሩም ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ ስጋት ለመመከት የሚያስችሉ African Standby Brigades በ2010 ተቋቁመው ሥራ እንዲጀምሩ በሂደት ላይ በመሆናቸው ይህ ሁኔታ የዓለም አቀፍ ተቋማትን (ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ምክር ቤትን ሚና) ባይተካም በሂደት ተጨባጭ ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል ይታመናል። ተደጋጋፊነቱ በትይዩ የጋራ ብልጽግናና የጋራ ደህንነት ለማዳበር ስለሚረዳ አፍሪካ ሃገራት በአንድ በኩል የደህንነት ጥበቃ ሽክሙን በመጋራት፣ በሌላ በኩል የኢኮኖሚ ውህደቱን በማጠናከር የጋራ ብልጽግናን በማምጣት በየአንዳንዱ አገር የመከላከያ ግንባታ የሚያስከትለውም ኢኮኖሚያዊ ሸክም በረጅሙ ጊዜ ለማቃለል ይችሉ ይሆናል። ቁምነገሩ አፍሪካ እነዚህን ዓላማ የሚየራመዱ ተቋማት እንዳሏትና ተግባራዊ እንቅስቃሴም እያደረጉ መሆናቸው ነው። ከዚህ በኋላ በጋራም በተናጠልም የፖለቲካ ዓላማ የማዋሃድና በቁርጠኝነት የመጓዝ ጉዳይ ይሆናል። ይህን ሁሉ መጥቀስ

ያስፈለገበት ምክንያት የሃገር መከላከያና የኢኮኖሚ ዕድገት ጥናት በሚከናወንበት ጊዜ በትንተናው ውስጥ እንደአንድ ታሳቢ እንዲወሰድ ለማሳሰብ ነው።

በጽሁፉ ላይ እንደተጠቀሰው ይህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ በሉአላዊነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደርጋል። ምናልባትም በአፍሪካ ውስጥ የጦርነትን ባሕርይ እንደገና ለመለወጥ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። ፍጹም ሉዓላዊነት ዓለም ባለችበት በአሁኑ ዘመን አይታሰብም፣ በታሪክም አልነበረም ይሆናል። አንጻራዊነቱን ግን ለጋራ ደህንነትና ብልጽግና እስከሆነ ድረስ በጸጋ ልንቀበለው የሚገባ ነው።

ጥገኛነትንም አያመለክትም። በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ውህደት ይመጣል ብሎ በአስተማማኝ ለመናገር አይቻል ይሆናል፤ ሆኖም የጋራ ብልጽግናንና የጋራ ደህንነትን በማራመድ ሂደት የእያንዳንዱን ሃገር የስጋት ምንጮችን ብዛትና ከፍተኛነት በመቀነስ በመከላከያ ግንቦታ ላይ ሊደረግ የሚችለውን ወጪ ለማስቀረት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። ትንሽ የዋህነትም አያስመስልብኝ እንጂ በሪጅናል ኢኮኖሚክ ኮሙዩኒቲስ ውስጥ የንግድ ልውውጥ በዳበረ ቁጥር ከአፍሪካ ውጭ የኢንተርናሽናል ንግድ ጥገኝነትን አስከፊነት ሊያለዝበው ይችል ይሆናል። ይህ የግሎባላይዜሽን በአፍሪካ መስፋፋት ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ግን ከመተንበይ በስተቀር በትንተና ላይ የተመሰረተ አስተያየት ለመስጠት አልደፍርም።

ከላይ የተገለጸው አህጉራዊና ክፍለ-አህጉራዊ ሴናርዮ ሙሉ በሙሉ እውን እስኪሆን ድረስ ግን የሃገራችንን ልማትና ደህንነት እራሳችን በአስተማማኝ ዘዴ ማደራጀትና መሥራት የግድ ይላል። ከዚህ በኋላ ይህን በሚመለከት በጽሁፉ ውስጥ ስለቀረቡ ዋና ዋና ሃሳቦች አንዳንድ አስተያየቶችን ለማቅረብ እወዳለሁ።

በሃገራችን የሃገር መከላከያ ሠራዊት የማስፈለጉ ጉዳይ አከራካሪ አይሆንም። በጽሁፉ የተሰጡት ምክንያቶችም አርኪ ናቸው። ሆኖም በአሁን ጊዜ ሁኔታዎች ከታሪክ ድግግሞሽ ብቻ በመነሳት መገምገም ላይበቃ ይችላል። ሃገራዊ ጥቅምና ስጋቶች በሚገመገሙበት ጊዜ ወደፊትም አርቆ ማየት ያስፈልጋል። በተለይ ኢትዮጵያ የባህር ክልል ባይኖራትም ከዚያ አካባቢ የሚሰነዘረውን ጥቃት የመከላከል ተልዕኮ የሌላ ሃገር ኃላፊነት እንደሆነ በመቁጠር ሥጋታችንን እንዳቃለለልን አድርጎ የማየቱ አዝማሚያ (ወታደር እንደመሆኔ መጠን) ስህተት ይመስለኛል። በተቃራኒው ስጋታችንን በከፍተኛ ደረጃ የሚያባብስ መስሎ ነው የሚታየኝ። በመጀመሪያ ደረጃ የቀድሞይቱን ኢትዮጵያ ያዋስን የነበረውን የባህር ክልል ማጣቱ እንደ ወደብ አልባነት ብቻ ተደርጎ መወሰዱ አግባብ አይደለም። ከአጠቃላይ የሃገር ጥቅም አንጻር ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳጣን ግንዛቤ መወሰድ አለበት። ስፋት ባለው የቀይ ባህር ከባቢ በባህር ውስጥና ከባህር በታች ያለውን እምቅ ሃብት አጥተናል። ሁለተኛ ከፍተኛ የገቢና የወጪ ንግዳችን በቀይ ባህር በኩል የሚተላለፍ ሲሆን የዚህን ንግድ እንቅስቃሴ ደህንነት ለመቆጣጠር ምንም ዓይነት ዘዴ የለንም። ማንም የባህር ሽፍታ መርከቦቻችንን ሊያጠቃ ይችላል። የባህር ጠረፍ ጥበቃ አስተማማኝ ባለመሆኑ ሽብርተኞች/ጠላት ሰርጎ በመግባት በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሊሰነዝሩ ይችላሉ። ሃገራት ከዚያ አቅጣጫ በጥምር ኢትዮጵያን ሊያጠቁ ቢሞክሩ የባህር ክልሉን ስለማንቆጣጠር የመከላከል አቅማችንን በጣም ውስን ያደርገዋል፣ በብቃት ለመከላከልም የመከላከያ አቅማችንን በብዛትና በጥራት እጅግ በጣም ከፍ ማድረግ ይኖርብናል። ይህ ስጋት ሊሆንብን እንደሚገባ ያለመገንዘቡ ድክመታችንን ያባብሰዋል። ምክንያቱም በቂ ዝግጅት አይደረግም። ይህ ስጋት ተጨባጭነት የለውም የሚሉ ካሉ ያለፉት ጥቂት ዓመታት የአካባቢው

የወታደራዊና የደህንነት ታሪክ እንዲያጤኑ አደራ እላለሁ። ሌላው የወደብ አልባነቱ ጉዳይ ነው። ይህ ህልውናችንን በሌሎች ሃገሮች በጎ ፈቃድ ላይ እንደመተው የሚቆጠር ሲሆን የወደብ አቅርቦትን እንደንግድ ጥያቄ ብቻ እንጂ እንደ ሃገር ደህንነት አካል አድርጎ አለማየት፣ አንድ ሃገር የወደብ መጠቀም መብት ቢከለክለን ገንዘብ እስካለን በፈለገን ጊዜ የሌላ ሃገር ወደብ መጠቀም አማራጭ እንዳለን፣ የአሰብ ወደብን ኢትዮጵያ ባትጠቀምበት የሚጎዱት ኤርትራውያኖች ብቻ እንደሆኑ አድርጎ የማየቱ ዝንባሌ ከምን ዓይነት የዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ቲዎሪ እንደሚመነጭ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። ግራ የሚያጋባም አቋም ነው።

የዚህ አካባቢ በሃገራችን ደህንነትና ልማት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያደርግ የሚችል ሌላ ሁኔታ አለ። ሃብታም የዓረብ ሃገራት በባብ ኤል መንደብ ባህረ ሰላጤ ላይ የመንንና ጅቡቲን የሚያገኛኝ ድልድይ ለመሥራት ዕቅድ እንዳላቸው በይፋ ተናግረዋል። አቅሙና ፍላጎቱ አላቸው። ዕቅዳቸውን እውን ከማድረጋቸው በፊት ይህ ሁኔታ በአካባቢውና በኢትዮጵያ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የሚኖረውን እንድምታ በተሟላ መልኩ መገምገምና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ከማስከበር አንፃር አማራጭ የብዙ ፈርጅ ፖሊሲዎች ማዘጋጀት ተገቢ ይሆናል። ከወዲሁ ለመናገር የሚቻለው ግን ይህ ዕቅድ ተግባራዊ ከሆነ የአካባቢው ጂኦፖለቲካዊ መሠረት ስለሚናጋ ኢትዮጵያን ለተለያዩ አዳዲስና ውስብስብ የስጋት ምንጮች የሚያጋልጣት እንጂ ደህንነቷን አስተማማኝ ያደርገዋል የሚል እምነት ሊኖር አይችልም። ይህ ስጋት አሳማኝ (Credible) ነው አይደለም የሚለውን አስተያየት ለእያንዳዱ ተሳታፊ እተዋለሁ። ነገርግን ሁኔታው የተቀነባበረ የረጅም ጊዜ የኢንተለጀንስ ጥረት አስፈላጊነትን፣ የሃገር መከላከያ ግንባታ እንደገና የመገምገም አስፈላጊነትን ገሃድ ያደርገዋል።

እንግዲህ ጽሁፉ እንደሚለው የሃገር መከላከያ ግንባታን የምንፈልገው በእርግጥ አስተማማኝ ሰላም እንዲኖር ስለሚያስችል፣ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ማህበራዊ ብልጽግና ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው ነው። ሆኖም ይህን ፍላጎት እንዲሟላ ስንፈልግ የሃገራችንን ጎላቀርነትና ድህነት መርሳት እንደሌለብን ነው የሚያስገነዝበው። ብዙውን ጊዜ በተለምዶ ለልማት አስተማማኝ ሰላምና ደህንነት Security እንደቅድመ ሁኔታ ሆኖ ይቀርባል። ይህ ዓይነት አመለካከት ግን ሃገሪቱ በምትከተለው የደህንነትና የልማት ፖሊሲዎች ከምን ይቅደም (priority) አንጻር የራሱ ሚና እንደሚኖረው ነው። ሁለቱን ሂደቶች ማለትም ደህንነትና ልማት አንዱ አንዱን በሚያጠናክርበት ሁኔታ በትይዩ ማካሄድ አማራጭ የሌለው ስትራቴጂ ሆኖ ሊታይ ይችላል። የሁለቱ እርስ በርስ ተመጋጋቢነት interdependence በመገንዘብ እድገታቸውን ለማረጋገጥ institiutions መፍጠር ይቻላል። ቀደም ሲል የጠቀስኩት ክፍለ አህጉራዊ የልማትና ደህንነት ትብብር (regional cooperation) ተቋማት ውስጥ መሳተፍ እና እነርሱን ማጠናከር አንዱ ዘዴ ሊሆን ይችላል።

በተጨማሪ በጽሁፉ ውስጥ እንደተጠቀሰው የሃገራዊ ፖሊሲ የአወጣጡና የአጸዳደቁ ሂደት እንዲሁም የሃገራዊ ደህንነት አስተዳደር ሂደት ከተስተካከሉ optimum የሆነ የresource allocation ለማድረግና የልማትና የደህንነት መስተጋብርን ለማዳበርና ለማጠናከር ይቻላል። ይህም ፖሊሲ ማውጣትን፣ ከዚያም በፖሊሲው ላይ ተመስርቶ ማቀድና ከዕቅዱ ተነስቶ አግባብ ያለውን ስትራቴጂ መቀየስ፣ ስትራቴጂውን እውን ሊያደርጉ የሚችሉ የመከላከያ ፕሮግራሞችን መምረጥና አስፈላጊው

የፋይናንስ ሆነ ሌላ ሃብት ማቅረብ ያስፈልጋል። ቀጥሎም ጥራትና ብቃት ባለው ሁኔታ ሪሶርሱን ማስተዳደር ተገቢ ይሆናል። የቁጥጥርና አሸርሳይት ስርዓት መዘርጋትና መከታተልም የዚህ ዑደት አካል ነው።

ይህ ሂደት በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል።

1. ሂደቱ በተገቢው መንገድ institutionalized መሆን አለበት። ይህ ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ነው። ቢያንስ ቢያንስ ከመንግስት ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ተቋማት የባህርይ ለውጥ ይጠይቃል።
2. የመልካም አስተዳደር መርሆችንና አሠራሮች ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት።
3. ሰፋ ባለ አመለካከት (wider perspective) ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት።
4. የሃገሪቱ የደህንነት ተቋማት የሃገሪቱን የግዛት አንድነት መጠበቅ ቅድሚያ ሥፍራ ሊሰጡት ይገባል።
5. ልማት ከሌለ ደህንነት ቀጣይነት ሊኖረው እንደማይችል፣ ደህንነት ከሌለ ልማት አስተማማኝ ሊሆን እንደማይችል ግንዛቤ መውሰድና ከዚህ አንጻር ሚዛናዊ አቅጣጫ ይዞ መራመድ ይጠይቃል።
6. የደህንነት አስተዳደር በሚመለከት ሙያዊ ብቃት ያላቸው ፕሮፌሺናሎችና አስተዳዳሪዎች ማሰማራት የግድ ይላል።

በሌ/ጀ ገ/ፂድቃን ገ/ተንሣይ ተዘጋጅቶ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ያዕቆብ አርሳኖ[1]

የጽሑፉ ዋና ትኩረት የሃገር መከላከያ ግንባታና ስምሪት ከኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር ያለውን ግንኙነት መዳሰስ መሆኑ በጽሁፍ አቅራቢ ከመነሻው ተገልፂEል። ጽሁፉ (1) የሃገር ደህንነት ጥበቃና የመከላከያ ኃይል፣ (2) ሃገራዊ ደህንነትና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ፣ (3) የሃገር መከላከያ ኃይልና የኢኮኖሚ እድገት እና (4) የሃገር መከላከያና የኢኮኖሚ ዕድገት በኢትዮጵያ በሚሉ ንዑስ ክፍሎች የቀረበ ሲሆን ሰፋ ያሉ መግቢያና ማጠቃለያ ክፍሎችም አሉት።

ዕድሜያቸውን ይበልጡኑ ያሳለፉት እንደታጋይና ወታደር በመሆኑ የሃገር መከላከያ ኃይልና የኢኮኖሚ እድገትን የሚያዩት በራሳቸው ልምድና አንፂር መሆኑን የጽሁፍ አቅራቢው በግልጽ አስገንዝበዋል። የጽሁፉ እሳቤ የሚያጠነጥነው የሃገር መከላከያ ከውጭ የሚሰነዘርን ጥቃት ሲመክት፣ ያገር ውስጥ ግጭት እንዳይስፋፋ ሲከላከል፣ ጦርነት ወይም ግጭት ከተቀሰቀሰም በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ሰብአዊና ማቴሪያላዊ ጉዳት አሸናፊነት ሲገኝ የመከላከያ ኃይሉ ለሃገር ልማት አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል የሚል ነው።

ከዚህም አልፎ በአግባቡ የተገነባ፣ የተደራጀና ተልዕኮውን የተገነዘበ የሃገር መከላከያ ኃይል የሃገርን ደህንነት የመጠበቅና የኢኮኖሚ ዕድገት በጦርነትና በግጭት እንዳይደናቀፍ የማድረግ ኃላፊነት አለው በማለት የጽሁፉ አቅራቢ ይከራከራሉ። በመቀጠልም ስለሃገር ደህንነት ጥበቃና የመከላከያ ኃይል አስፈላጊነት ፣ ተልዕኮ፣ አደረጃጀት፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራምና አመራር ውጭአዊ ሁኔታዎችን ማለትም አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን ማጤን እንደሚያስፈልግ ንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔ አቅርበዋል።

የጽሁፍ አቅራቢው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ እየተለወጠ መምጣቱን በማስገንዘብ፣ 1) በሃገራዊ ደህንነት ላይ የነበረው ግንዛቤ እየተለወጠ መምጣቱን፣ 2) የግጭቶች ባህርይ እየተቀየር መምጣቱን እና 3) የግሎባላይዜሽን ተጽዕኖ እየተስፋፋና እየተጠናከረ መምጣቱን በስፋት ተንትነው አቅርበዋል። ነገር ግን እየተለወጡ ያሉ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ቢኖሩም ተጽዕኖአቸው ከፍ እያለ የመጣ ቢሆንም ለሃገራችን ለኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት እንደሚያስፈልግ በአጽንኦት ይገልጻሉ። ለዚህም ዋና መከራከሪያቸው 1) የዓለም ፖለቲካ ሥርዓት «ራስ-ገዝና ስርዓት አልባ» መሆኑን ስላላቆመና ዓለም አቀፋዊ ስርዓት ገና

[1] ዶ/ር ያዕቆብ አርሳኖ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ሲሆኑ በማስተማርና በምርምር ሥራ ላይ ይገኛሉ።

ስላልተበጀ፣ 2) ሃገራችን ኢትዮጵያ መርጣ የምትከተለውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርዓት መጠበቅና ብሔራዊ ጥቅምን መንከባከብ አስፈላጊ በመሆኑ 3) ኢትዮጵያ የምትገኝበት ታሪካዊ ሁኔታ፣ ጂዎፖለቲካዊ አቀማመጥና አገሪቱ ያለችበት ቀጠናዊ የደህንነት ስጋት ሁኔታ ስለሚያስገድድ፣ ከዚህም አልፎ ሀገርና መንግስት እንዲኖሩና ተገቢ ስራቸውን እንዲያከናውኑ የመከላከያ ሠራዊት አስፈላጊ መሆኑን በማብራራት ነው።

ሆኖም ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ልማት ባለማደጓ አንፂር ጠንካራ የመከላከያ ኃይል መገንባትና ማሰራት በሃገር ልማት አሉታዊ ተዕጽኖ እንዳያሳድር መፍትሔው 1) የሕዝብ አመኔታና ድጋፍ ያለውን ሠራዊት መገንባትና 2) መከላከያ ኃይሉ ሀገሪቱ የምታቀርበውን ትጥቅና መገልገያ ውጤት በሚያሰገኝ መንገድ መጠቀም መሆኑን አብራርተዋል።

የመከላከያ ኃይል ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያመጣው ፋይዳ ጦርነት እንዳይነሳና የርስ በርስ ግጭት እንዲወገድ በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዳይደናቀፍ ሰላማዊ ሁኔታን መፍጠር መሆኑን በማብራራት፤ ከዚህ ውጭ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ግኝቶችን በማቅረብና ሰፋፊ የስራ ዕድሎችን በመፍጠር ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያደርገው አስተዋጽኦ አቅም የሌለው መሆኑን በማስረዳት «ተዋጊና አምራች ኃይል» በማድረግ የመከላከያ ኃይሉ ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚባለውም ፋይዳ የማይኖረው መሆኑን አስገንዝበዋል።

ይልቁንም የሃገር መከላከያ ኃይል የመንግስት በጀት ተመድቦለት በወጭ የሚስተዳደር በመሆኑ በሃገር ኢኮኖሚ ዕድገት ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌለው በመሆኑም በቁጠባና ለውጤታማነት መሆን እንደሚገባው የጽሁፉ አቅራቢ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያን ሁኔታ በማስመልከት ሲያቀርቡ የሃገር መከላከያ በጀቱ በኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል ለማለት እንደማይቻል አስገንዝበዋል። እ.ኤ.አ. በ2002 መንግስት ያወጣው የውጭ ግንኙነትና የብሔራዊ ደኅንነት ፖሊሲና ስታነጂ መልካም ጅምር መሆኑን አስገንዝበዋል። ሕዝቡ ፖሊሲውን ወዶት፣ ደግፎት፣ ተሳትፎበት ከተቀበለ በጉዳዩ ላይ ሃገራዊ ኮንሰንሱስ እንዲኖር ከተደረገ ለወደፊቱ ትልቅ እርምጃ ሊሆን እንደሚችል ያላቸውን እምነት ገልጸዋል። የጽሑፉ አቀራረብና ዋና ዋና መልዕክቶች ከዚህ በላይ ተጠቅሰዋል።

ከዚህ የሚከተሉት አስተያየቶች ስለጽሑፉ ሊጠቀሱ የሚገቡ ደካማና ጠንካራ ጎኖች ናቸው። በደካማነት አንፂር ሲታይ ጽሑፉ ሙሉ በሙሉ ርዕሱን ተከትሎ የሄደ አይደለም። «ሀገራዊ ደህንነትና ዓለማቀፋዊ ሁኔታ» በሚል ሥር የቀረበው የጽሑፉን ሁለት ሶስተኛውን ስፋት የወሰደ ሲሆን በንድፈ ሐሳባዊ አቀራረብ የተዋጠ ነው። ባንፂ የሃገር መከላከያ ኃይልና የኢኮኖሚ እድገት፣ ማለትም ዋናው የጽሑፉ ነገረ ጉዳይ ብቻ ተገልጿል። አትዮጵያን አስመልክቶ የሃገር መከላከያና የኢኮኖሚ ዕድገት በሚል በቀረበው ውስጥ እ.ኤ.አ ከ1990 - 2002 የነበረው የመከላከያ በጀት ሰንጠረዥ ሙሉ ምሥል በሚሰጥ የቀረበ አይደለም። የሠራዊቱን የብዛትና የዕድገት ሁኔታ ጭምር የሚያሳይ ሆኖ ትንታኔ ቢሰጥበት የተሻለ ይሆን ነበር።

የሃገር የመከላከያና የደኅንነት ፖሊሲ ዲሞክራሲያዊና መላ ሕብረተሰብን ያሳተፈ እንዲሆን ጽሑፍ አቅራቢው አበክረው ያቀረቡት አስተያየት የመከላከያና የደኅንነት ኃይሎች ሊኖራቸው ከሚጠበቀውና ከሚገባው የፕሮፌሽናል ብቃት ደረጃ ፣ አይነትና አደረጃጀት ጋር ተመዛዝኖ ቢተነተን የተሻለ ይሆን ነበር። አንድ የመከላከያ ሠራዊት የፕሮፌሽናል ሥልጠና ደረጃና የማሰልጠኛ ተቋማት ብቃትና ዓይነት ወሳኝና የማይዘለል መሆኑ በጽሑፉ ውስጥ ትኩረት አልተሰጠውም። በኢትዮጵያ የሃገር መከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት በብሔረሰብ ተዋጽኦ ላይ የተመሠረተ ነው ይባላል። ይህ አባባል ዕውነትነት ካለው ብሔረሰባዊ አስተዋጽኦ ለሃገር መከላከያ ኃይልና ለፕሮፌሽናል ብቃቱ ሊኖረው የሚችል ልዩ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ምን ሊሆን እንደሚችል የጽሑፍ አቅራቢው አስተያየት ቢሰጡበት መልካም ይሆን ነበር።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ወቅቶችና የፖለቲካ ሥርዓቶች የመከላከያ ኃይሏን በአፍሪቃና በሌሎች ሥፍራዎች ለጸጥታ አስከባሪነት ስታሰማራ ቆይታለች። ይህ ለሃገር መከላከያ ኃይሏ ፕሮፌሽናል ዕድገት ፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ለኢኮኖሚ ዕድገት ምን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሚና እንዳለው የጽሑፉ አቅራቢ አስተያየት ቢሰጡበት ጠቃሚ ይሆን ነበር።

በጥንካሬ አንፂር ሲታይ ጽሑፉ ወቅታዊ ከመሆኑም በላይ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ብዙ ያልተሠራበት ነው። የሃገር መከላከያና የደኅንነት ጉዳይ «ምስጢር ነው» ስለሚባል እንደዚያም ስለሚታመን መረጃ አግኝቶ ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅቶ ለመድረክ ውይይት ማቅረብ የተለመደ አይደለም። በዚህ ረገድ የጽሑፍ አቀራቢው ያሳዩት ተነሳሽነትና ደፋርነት የሚያስመሰግናቸው ብቻ ሳይሆን ያሳዩት አብነት ለሌሎች ተመራማሪዎች አበረታችና ፈር ቀዳጅ ነው ለማለት ይቻላል።